


Niguss
Digital Library

አስረስ ፡ የኔሰው

# ትቤ ፡ አክሱም

# መኑ ፡ አንተ?

\

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ


በ፳፫ተኛው ዓመተ መንግሥት በ፲፱፻፶፩ ዓመተ ምሕረት ይህ መጽሐፍ ታተመ።

ንግድ ማተሚያ ቤት

ተጻፈ ከአቶ አስረስ የኔሰው።

ይህ መጽሐፍ ያለደራሲው ፈቃድ መልሶ
ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።


NIGUSS
DIGITAL LIBRARY



ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
ዘውእቱ ተፈሪ መኰንን



ግርማዊት እቴጌ መነን አስፋው ሚካኤል



የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ

# ማውጫ

፩ኛ ክፍል ሚያዝያ ..... 7
መቅድም ..... 7
፪ኛ ክፍል ግንቦት ..... 32
፫ኛ ክፍል ሰኔ ..... 70
ምዕራፍ ፩ ..... 70
፬ኛ ክፍል ሐምሌ ..... 103
፭ኛ ክፍል ነሐሴ ..... 129
በኢትዮጵያ የሚገኙ መጻሕፍተ ብሉያት ..... 130
በዓለም ቤተ ክ የሚገኙ መጻሕፍተ ብሉያት ..... 131
፮ኛ ክፍል መስከረም ..... 155
ምዕራፍ ፪ ..... 155
፯ኛ ክፍል ጥቅምት ..... 182
ምዕራፍ ፫ ..... 182
፰ኛ ክፍል ታኅሣሥ ..... 236
ምዕራፍ ፬ ..... 236
፲ኛ ክፍል ጥር ..... 266
፲፩ኛ ክፍል የካቲት ..... 291

## ሀ እኁድ

# ፩ኛ ክፍል ሚያዝያ

## መቅድም

ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያሰብኩበት ምክንያት የሮማ ልዑካን ባጼ ልብነ ድንግል በሺ፭፻፲፯ ዓ.ም በግራኝ ሙሐመድ በተነሣበት ሙሐመድ ከቱርክ እርዳታ አግኝቶ ነፍጥና መድፍ ይዞ ልብነ ድንግል በጦርና በጐራዴ በቀስት ብቻ ስለሆነ የግራኝ ሙሐመድ ጦር ድል እያገሩ ስለሄደ አጼ ልብነ ድንግል ወደ ፖርቲጊዝ መንግሥትና ወደ ሮማው ፓፓ እርዳታ ጠይቀው ስለነበር ምንም እንኳ በቶሎ ባይመጡለት። ለ፲፫ ዓመት በኋላ ፬፻ ወታደሮችና ሹሞች ነፍጥም መድፍም ይዘው ስለመጡ በዚያ ጊዜ አጼ ልብነ ድንግል በጦር ሜዳ ሳሉ በሕመም ምክንያት ስላረፉ ልጃቸው አጼ ገላውዴዎስ በመንግሥቱ ተተክቶ ቆያቸውና በልዑል እግዚአብሔር ቸርነት ግራኝ ሙሐመድ ድል ሆነና በዕረፍት ቦታ በተቀመጡ ጊዜ ፖርቱጊዞች ያገራቸውን ዓላማ አብረው እየሰቀሉ አባ ቤርሙዴዝ የተባለውም የኢትዮጵያ ጳጳስም እኔ እንደሆን ከሮማው ጳጳስ አስፈቅጃለሁና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም በሮም ቤተ ክርስቲያን በታች እንድትሆን ካጼ ልብነ ድንግል ተዋውለን ነበርና አሁንም እንደውለታችን የቤተ ክህነቱን ሹመት ልቀበል ብሎ ቢአመለክት አጼ ገላውዴዎስም እኔ እንደዚህ ያለውን አላውቅም እርዳታ ስላደረጋችሁልን ዋጋችሁን በተቻለኝ እመልሳለሁ። ኢትዮጵያን የወደደ እዚሁ ኢትዮጵያዊን መስሎ ይቆይ ይቀመይጥ። አልቀመጥም ያለ ዋጋውን እየተቀበለ ይሂድ። በሀገሬ ላይ ፪ኛ የውጭ ሰንደቅ ዓላማ ተተክሎ እንዳላይ ብሎ ስለአዘዘው አባ ቡርሙዴዝ ይህን ትእዛዝ አክብሮ ስላልተቀበለ ወደ ከፋ በግዞት ትንሽ ቀን ሰንብቶ ነበር። ከትንሽ ቀን በኋላ መኳንንቱ አማልደውት ወደ ሀገሩ ከሄደ በኋላ በመጽሐፉ ተዘርዝሮ እንደሚገኘው የኢትዮጵያ ሕዝቦች እግዚአብሔርን አክባሪዎችና እንግዳ ተቀባዮች መሆናቸውን ስለ ነገረ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መንፈሳዊ ሥራ ስለ ሚወዱ መንፈሳውይና መስለን የመነኵሴ ልብስ ለብሰን መስቀልና መጽሐፍ ይዘን ሄደን ሕዝቡንና ንጉሡን እየበጠበጥን እርስ በርሱ እየተፋጀ ሕዝቡ ሲቀነስ መንግሥቱም ሲኮስስ ጠብቀን በጦር ኃይል አገሩን አጥፍተን እንገንባና ቅኝ አገፍር አድርገን እንጠቀምበታለን ብለው አስበው በዚህ አኳኋን ካጼ ገላውዴዎስ ዠምረው የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ እነንዳፋጁ ያው ፬፻ ዘመናቸው መሆኑ ነው። በዚህ መካከል የኢትዮጵያን ታሪክ ጻፍን እያሉ በሐሰት የኢትዮጵያን ታሪክ አጥፍተውት በዓለም ባለታሪኮች ዘንድ ስለተዘራ ይህን የሐሰት ባለታሪኮች ላይ እየተቀበሉ እያስፋፉና እየጠቀሱ ለወጣቶቹ እያሳተሙ ሲአቀርቡ እያየሁ ያነን ጽሑፍ ከጥንታውያን መጻሕፍት ለማነጻጸር ስመረምር እነሱ የሚጽፉትን የማላገኘው ስለሆነ የነሱ ሥራ የፖለቲክ ስብከት መሆኑን በጣም ለማረጋገጥ ብዙዎቹን ገዳማት ለመዞር ደርሼ ስመለከት በመካከሉ አባ ጋስፖሪን ገብረ ማርያም የተባሉ መናኔ ዓለም። ለኢትዮጵያ አስበው የኢትዮጵያን ታሪክ ጽፈው ስለ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ፡ሥ፡ የዘውድ በዓለ ንግሥ ንውስ አምኃ ብለው ባቀረቡት የኢትዮጵያ ታሪክ የተባለ መጽሐፍ ብመለከተው ያው ፬፻ ዘመን ዠምረው ያደራጁላት ረቂቅ ሆኖ ስለ አገኘሁት ይህ ረቂቅ ፖለቲክ በብዙ ኢትዮጵያውያን ልብ የብረት ቀለም መስሎ ተቀረጸ። እኔ ደግሞ ከብዙዎቹ ገዳማት ባገኘሁት መሳሪያ ለመ

# ሁ ሰኑይ

ሞረድ አስቤ ነው። ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ የወጣቶችን የልብ አባላዘር የሚሰልብና በፍጹም ሴት የሚአስመስል ነው ፩ደኛ ኢትዮጵያን የግብጽ ተገዥ ነበረች ብለዋል ፪ኛ ኢትዮጵያን ያቀኑና ያሠለጡኑ መንግሥቷን ያጠፉ የደቡብ ዓረቦች ናቸው ፫ኛ ግዕዝን ያመጡ የደቡብ ዓረብ ነገሥታት ናቸው ፬ኛ መጻሕፍተ ብሉያት በሙሉ የተገለበጡ ከጽርዕ ወደ ግዕዝ ነው ፭ኛ አብርሃንና አጽብሐን ሰርዘው ፮ኛውን በትውልድ ዔዛናን በዘመኑ አባ ሰላማ መጡ ብለዋል ፯ኛ ግዕዝን ከአረብ የመጣ ለማስመሰል ከቀኝ እጅ ወደ ግራ እያደረጉ የአሕዛብ ጣዖት ስም እየጻፉ ዔዛና በጣዖት ያመልክ እንደነበረ እያደረጉ ጽፈው በፎቶግራፍ አንስተው ፎቶግራፉን በክልሼ አሥለው ከሐውልት ላይ የተገኘ አስመስለው ጽፈው በጽሑፍ ለማታለያ አግብተውት ይገኛል። ስለዚህ ይህን ለመግለጽ ስል ነው።

ቀዳማሃ ለጥበብ ፈረሃ እግዚአብሔር።

ሰለ ሮማውያን ስብከት ምርመራ።

ሮማውያን ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትን ሐተታ ስንከታተል ባጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ግራኝ ሙሐመድ በተነሣ ጊዜ ግራኝ ሙሐመድ ከቱርኮች ረዳትነት የጦር መሳሪያ መድፍና ጠመንጃ አግኝቶ ያጼ ልብነ ድንግል ሠራዊት በጦርና በጐራዴ ተዋግቶ ድልን ማገኘት ያማይቻል ስለሆነ። በዘመኑ ኃይል ከነበረው ከፖርቱጊዝ መንግሥት አጼ ልብነ ድንግል እርዳታ ጠይቀው ስለ ነበረ መልክተኞችን ቱርኮች ምንገድ እየከለከሉ ስለ አስቸገሩ በዚህ ምክንያት የግራኝ ጦር በርትቶ ከሸዋ ዠምሮ እስከ ትግሬ መሬት

እየሸሹ መከላከል ግድ ሆነባቸው ከሺ፭፻፲፯ ዓ.ም እስከ ሺ፭፻፴፪ ዓ.ም ፲፭ ዘመን ሙሉ ሲከላከሉ ከቆዩ በኋላ በዚያው በጦር ሠፈር እንዳለ በሕማም ምክንያት አረፉና በእሳቸው እግር ታላቁ ልጃቸው ገላውዴዎስ ተተካና ጦርነት ሲዠምር ከፖርቱጊዝ መንግሥት በዶም ክርስቶፍ የሚታዘዙ ፬፻ ፖርቱጋሎች መሳሪያ የያዙ ወዲያው በበሐር ነጋሹ ግዛት ከደረሱለት በኋላ በሐር ነጋሽ ይስሐቅ ለመድፍና ለጠመንጃ ለጥይት ጭነት የሚሆኑ ግመሎችና ለሹማምንቶች የሚሆኑ በቅሎዎች የሚገባውንም በስተግዶ በፍጥነት አቀረቡና ወደዚያው ወደ ደጋው ወጡና ከንግሥቲቱ ከእቴጌ ሰብለ ወንጌልና ከንጉሠ ነገሥቱ ካጼ ገላውዴዎስ ተገናኝተው በእግዚአብሔር ቸርነት ከፖርቱጋልም ረዳትነት ግራኝ ሙሐመድ ሙቶ ጦሩ ከተበታተነ በኋላ ፩ድ ቤርሙዴዝ የተባለ ካቶሊካዊ አስቀድሞ በራሱ ፈቃድ የፖርቱጋልን ዓላማ እየሰቀለና በካቶሊክም ሃይማኖት ስብከቱን እየቀጠለ ከቆየ በኋላ በቀጥታ አጼ ገላውዴዎስን ከአባትህ ጋራ ከኢትዮጵያ እኩሌታው ለፖርቱጋሉ መንግሥት ሊሆን የኢትዮጵያ ቤተ ክህነትም የሮማ ቤተ ክርስቲያን ጥገኛ ልትሆን ተዋውለን ነበርና አሁንም የንኑ ያባትህን ውል እንድትፈጽምልኝ ሲል አመለከተ። አጼ ገላውዴዎስም ይህን ንግግር ከቤርሙዴዝ ከሰማ በኋላ ይህን የምታወራውን ነገር እኔ አላውቅም ስለ ድካማችሁ ዋጋ መክፈል አልቦዘንኩም ለወደፊትም ውለታችሁን በሰፊው እከፍላለሁ እንጅ የማስቀር አይደለሁም እናንተ ግን ከዛሬ ዠምሮ በምድሬ ላይ የውጭ ሰንደቅ ዓላማ መትከልና የካቶሊክም ስብከት እንዳይደረግ ሲል ትእዛዝ የሆነ ቃሉን በተናገረ ጊዜ ቤርሙዴዝ ለንጉሠ ነገሥቱ መልስ መሥጠት ስለዠመረ

## ሂ ሠሉስ

አጼ ገላውዴዎስ ቤርሙዴዝ ከፋ ሂዶ እንዲታሠር ስላዘዘ ሹማምንቱ ወደ ከፋ ወሰዱትና ታስሮ ማለት በግዞት ከቆየ በኋላ አጼ ገላውዴዎስ ተማልዶ እሱም ከከፋ ይመለስ ሌላውም እወዳለሁ የሚል እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ሆኖ ይቀመጥ አልፈቅድም የሚል ሰው ግን ዋጋውን እሰጠዋለሁ እየተቀበለ ይሂድ ብሎ ፪ኛ አዘዘ ከዚህ በኋላ ከቤርሙዴዝ ጋራ ለመሄድ የፈቀዱትን በሚገባ ከግራኝ ሠራዊት ላይ የነበረውን አልማዝና ወርቅ ጌጥ የነበረ ሳይቀር ከግራኝ ጦር ሠራዊት የተማረከውን ወርቅ ሁሉ እየሰጠ ሰደዳቸውና ቤርሙዴዝ ሮማ ከደረሰ በኋላ የኢትዮጵያን ሀብትና ውበት ለሮማውያን በነገረ ጊዜ የቤርሙዴዝን ወሬ የሰሙ ሮማውያን ፍቅር ስለተነደፉ እንደገና ስብሰባ አድርገው ገንዘብ አዋጥተው ለዚህ ፖለቲካ የሚሆን የማኅበር ቤት አቁመው በምን ምክንያት እንዲገቡ ምክር ሲደረግ ቤርሙዴዝ የኢትዮጵያውያንን ታሪክ ሲነግራቸው የኢትዮጵያ ሰዎች መንፈሳውያን ስለሆኑ መጽሐፍና መስቀል የያዘ ሰው የሚአከብሩና የሚቀበሉ መሆናቸውን በጠብ ግን ሞት የማይፈሩ ኃይለኞች መሆናቸውን ስለነጋራቸው እንደዚህ ከሆነማ ከኢትዮጵያ በጣም የተማሩ ሰዎች በገንዘብ እያባበልን አምጥተን የሀገራቸውን ትምህርትና ቋንቋ ካስጠኑን በኋላ የኛ መስቀልና መጽሐፍ እየያዝን ሄደን ወዳጅ እየመሰልን ከቀረብን በኋላ የፖለቲክ ስብከታችንን እንቀጥላለን ተባብለው ምክራቸውን በዚህ ውሳኔ ከጨረሱና ከኢትዮጵያ ሊቃውንቱን እያባበሉ ወስደው ሮማ በቅዱስ እስጢፋኖስ ገዳም ባትካኖ ከቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ማረፊያ አሰናዱ በዚያ ውስጥም የኢትዮጵያ መነኰሳት ፰ መቃብሮች ይገኛሉ። በመቃብሩ ላይም በድንጋይ የተጻፈው ፩ኛ አቦ ተስፋ ጽዮን። ፪ኛ አባ ማርቆስ አገሩ ዳዋሮ ፫ኛ አባ መርቃርዮስ ፬ኛ አባ ጊዮርጊስ ሁለቱ የደብረ ሊባኖስ ናቸው ይባላል ፭ኛ አባ ሃብተ ማርያም ደብረ ጉባዔ በጌምድር ፮ኛ አባ ተክለ ሃይማኖት የዱማ ደብር ፯ተኛ አባ እንጦንዮስ የጣቁሳ ፰ኛ አባ ያዕቆብ ይህ የተደረገ (በሺ፭፻፶፬ዓ.ም ነው እነዚህ ፰ቱን መቃብሮች ያየ ሰው ሁሉ እነዚህ ኢትዮጵያውያኖች በምን ምክንያት እዚህ መጡ ብሎ ለሚጠይቅ ያሰናዱት መልስ የኢትዮጵያን መንግሥት አይሁድ ይዘው በነበረ ጊዜ ሲያስጨንቋቸው እየሸሹ ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ ሮማ እየመጡ የቀሩ ናቸው የሚል ነው። ስብከታቸው ሁሉ እንደዚህ ነው አይሁድ ያሉ የጉዲትን ዘመን ነው። ጉዲት የነበረች በ፲፻፷፭ ዓ.ም በላይ ነው።

በነዚህ ሰዎች መቃብር መታሰቢያ ተጽፎ የሚገኘው ካ፩ሺ፭፻፵ እስከ ሺ፭፻፹፭ ዓ.ም ግርጌ ነው። በመካከሉ የ፪፻ ዘመን ዕድሜ ወሰን እያለበት ይህን አሳብ ለሰው ሲገልጹ ኀፍረትን አለማሰባቸው በጣም ያስገርማል። ከላይ እንደተጻፈው ይህን የፖለቲክ ስብከት ካቋቋሙና ትምህርቱን ካጠኑ በኋላ ሮማውያን ወንጌልና መጽሐፋቸውን መስቀላቸውን ይዘው ለመምጣት ተዘጋጁ። በዚህ ማኅበር የሮማ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ስለ ተስማማበት ለጊዜው መልእክተኞቹን የሚልከው ስሙ ለሮማ ፓፓ ነው። በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የፕሮፓጋንዳ ባልደረቦች ልዑካን ተራ ቁጥር ከዚህ እንደሚከተለው ነው።

፩ኛ ከ፫ኛው ጳውሎስ ፓፓ በፊት አባ ዮሐንስ ቀጥሎ ቤርሙዴዝን በሺ፭፻፵ ዓ.ም ላከ ፪ኛ ፬ኛው ፓፓ ፒዮስ አባ እንድርያስን አባ አቤዶን

## ሃ ረቡዕ

በሺ፭፻፶፭ ዓ.ም ላከ ፫ኛ ፰ኛው ፓፓ ዑርባኖስ አባ አልፎንስን አባ መንዴዝን አባ ሚናስን በሺ፭፻፸፫ ዓ.ም ላከ ፬ኛ በፓፓ ዑርባኖስ አባ አልፎንሱ ተመልሶ እንደገና ባጼ ሱስንዮስ ሌሎች ቄሶች ይዞ መጣ ፭ኛ አባ ጋታኅዘሎስና አባ ክሲያኖስን በጻድቁ ዮሐንስ ዘመን ላከ ፮ኛ ባጼ ኢያሱ ልጅ በኢዮአስ ብዙ ቄሶች መጥተው ሰብከውታል። ከሺ፭፻፶ ዓ.ም ዠምረው ለመምጣት አላቋረጡም በመጡም ቁጥር የስብከት መዠመሪያቸው ወደ ነገሥታቱ ይቀርቡና ወደ

ሮማ መንግሥት የፍቅር የመተዋወቅ ደብዳቤ ብትጽፉ እኛ ወስደን መልሱን እኛ እናመጣለን እያሉ ይሰብኳቸዋል የኢትዮጵያ ነገሥታትም ለጊዜው ከጋሎች ጋራ ጦርነት ስለ ነበራቸው እውነት እየመሰላቸው ደብዳቤ ጽፈው ሲሰጧቸው ፩ዱ ደብዳቤውን ይዞ ወደ ሮማ የውጭ ጉዳይ ፖለቲክ ፈጻሚ ፩ድ የፖለቲክ ደብዳቤ ይዞ እስቲመለስ እዚህ የቀሩት በንጉሡና በመሳፍንቱ መካከል እየገቡ ሲዋጉና ሲጋደሉ ይቆያሉ። ከዚያ የሚመጣውንም የፖለቲክ ደብዳቤ የሮማ መንግሥትና ቤተ ክህነት ስለተስማማበት መሳሪያውን በያይነቱ በቀላል ዋጋ እኛው አምጥተን እናስረክባለን ግን የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት ሃይማኖቱ በካቶሊክ መሆን አለበት ከዚያ በኋላ መሳሪያውን ተቀብሎ የጋላን ሕዝብ ዘሩን አጥፍቶ አገሩን አስከፍቶ እንደ ልቡ ተደስቶ ለመኖር ይችላል እያሉ ሲሰብኩ ይህንም ከነገሥታቱ አልፎ አልፎ ሳይቀበሏቸው እንዳልቀሩ ታሪክ ይነግራል።

ምክንያቱም በዚሁ በመሳሪያ ፍለጋ ነው። የጠላት ነገር ስምተው መሳሪያ እናገኛለን ሲሉ እርስ በርሳቸው እየተፋጁ ኃይላቸው እየቀነሰ ይልቁንስ ለጠላት የተመቹ ሆነው ጋላ እየበረታባቸው ከመሄዱ በተቀር ከሮማውያን እጅ ለጠላት መከላከያ የሚሆን ጠቃሚ መሳሪያ ይገኛል ከንቱ ነው የአንድ አንድዶችም ነገሥታትና ትምህርት ወደ ካህናቱ አለቆች በተሰማ ጊዜ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ ስለሚተዋወክ የኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት የተሳሰረ ስለሆነ አጼ ገላውዴዎስን መክረው ቤርሙዴዝን ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ያደረጉ የኢትዮጵያ ሊቃውንት እነ አባ ዝክሬ እነ አባ ጳውሊ በጣም ተቀይመው በጥብቅ ስለመከሩት ነው። በማነኛውም ንጉሥ የውስጥ አማካሪዎች ሹም ሽር የሚደረገው በካህናቱ አለቆች ስለሆነ ካህናቱ ይህን ነገር እየተከተሉ ስለሚመረመሩ ነገሥታቱ በፈቃዳቸው የሮማን ልዑካን ምክር ተቀብለው ሃይማኖታቸውን ለውጠው መንግሥቱን ይዘው ለመቀመጥ አልቻሉም ፩ኛ አጼ ሚናስ ገና ውስጥ ለውስጥ ዝምረው ሳለ በመካከል በድንገት ስላረፉ በውዝፍ ቀርቷል።

፪ አቤቶ ተዝካሮንና በሐር ነጋሽ ይስሐቅን ያሸፈቱ ቱርክንና አጼ ሚናስን ያዋጉ እነሱ ናቸው አጼ ሠርፀ ድንግልም እንደ አጼ ገላውዴዎስ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ከማድረግ በቀር የጎላ ነገር በታሪኩ አልተገኘም ፫ኛ አጼ ያዕቆብን በጣም ቀርበው ስለ አስተማሩአቸው በቶሎ ብለው ካልጋ አውርደው እናርያ ወስደው አሥረው በዙፋኑ ላይ ካጼ ዘድንግልን አነገሡ ፬ኛ አጼ ዘድንግልንም እንደዚሁ የሮማ ልዑካንን ስብከት ሲቀበሉ ስለታየ የቤተ ክህነቱ ሹማምንቶች ከግብፅ የመጣውን ጳጳስ ካቶሊካዊ የተባለውን ገዝተው ብለው ካቶሊካዊና ኦርቶዶክሳዊ ወገን ለይቶ ጦርነት አደርጉና አጼ ዘድንግል በጦርነት ላይ በክፉ

# ሄ ኅሙስ

ሞት ሙቷል ፭ኛ አጼ ሱስዮስንም እንደዚሁ የሮማ ልዑካን እነ አባ በርሙዴዝ ይህን ከላይ የተጻፈውን የመሳሪያ ጉዳይ አገኛለሁ በማለት በነገሩ ደፍረው ገቡበትና ካቶሊካዊ ስለሆኑ ከመሳሪያው መምጣት አቀድሞ የሮማ ልዑካን የፖለቲክ ሰዎች ስለሆኑ በኢትዮጵያ ገዳማትና አድባራት እኛ አስቀድመን ካልሾምን ካልሻርን መሳሪያውን አናመጣም ስላሉ የሚሲዮኑ መሪ ፔር ፖኤዝ ደግሞ በኋላ ከሮማ ፓትሬያርክ ተብሎ ካ፲፰ ሚሲዮኖች ጋራ የመጣው ሜንዴዝ አልፎንሱ የካቶሊክ ሃይማኖት መሪ ሆኖ ኦርቶዶክሳዊውንን ሁሉ እንደገና ሊያጠምቅ በየገዳማቱም በየአድባራቱም እንዲሾሙ ስለተፈቀደላቸው በአክሡም ጽዮን የነሱን ሰው ሹመው ስለ ሰደዱ አክሱሞች ጽላተ ሙሴን ይዘው ተሰደው ፲፪ ዓመት በስደት ከቆዩ በኋላ አጼ ፋሲል ሲነግሡ ተመልሰዋል በላስታም የላሊበላ ገዳም እንደዚሁ እነሱ ስለገቡበት ካህናቱ ቤተ ክርስቲያኑን ለቀው ሄደው ብዙ ጊዜ ዱር ለብሶ ቆይቶ ከዚያ በኋላ ከላይ ባለው ይቀደሳል እንጅ ወደ ምድር ቤቱ ወደ ውስጥ መግባትን ደፍሮ የሞከረው የለም። በደብረ ሊባኖስም እንደዚሁ እጨጌ እየተባሉ እስከ ፯ት የሚሆኑ ተሾመው ልዩ ልዩ ዓይነት ሃይማኖት ሰብከውታል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሐቲ በነበረችቱ ይህን ያህል መለያየት የፈጠሩባት እነሱ መሆናቸው የሚጠረጠር አይደለም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የመለያየት የጠብ መንፈስ

የዘሩበት እነሱ ናቸው በቤተ ክህነቱና በቤተ መንግሥቱ አንሷቸው በኢትዮጵያ የሚገኙትን የጅ ጥበብ ሠራተኞች ብረት ሠሪውንም ብረት እየሠራና እያደራጀ ኢትዮጵያን ለምን ረዱ በማለት ወዲሁም ጦርና ጐራዴ ጩቤ እየሠራ ለጐበዞቹ እየሰጠ እነሱ በሠሩት ጦርና ጐራዴ ጩቤ ብዙዎቹ ሚሲዮኖች ያለ ኢትዮጵያ መንግሥት ፈቃድ አገር እያቁራረጡ ሲሄዱ በዚሁ መሳሪያ ብዙዎቹ ስላለቁ እንደልባቸው ወዲያና ወዲህ እያሉ ለመስበክ እንዲመቻቸው እኛ በሮማ ሀገሮች ላይ እነዚህን ብረት ሠሪዎች የነበሩ ሰዎች ከአገር ካጠፉን ወዲህ ብዙ ጤና አግኝተናልና እናንተም እነዚህን ብረት የሚቀጠቅጡ ሰዎች ብትፈጁ እንደኛ ጤና ታገኙ ነበር። ፪ኛም እነዚህንም ልብስ ሠሪዎችን ዘራቸውን ከሀገር ማጥፋት ነው። የጅ ሥራ የሚአውቁትን ሁሉ እንደዚሁ አጥፉ እያሉ በየደረሰበት ስብከት ስላበዙ በየቦታው የሚገኙ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከትልቁ እስከ ትንሹ እነዚህን መግደልስ አይሆንልንም ባይሆን ሰፈር እንለይላቸዋለን እያሉ ለብቻችሁ ተቀመጡ ባሏቸው ጊዜ የጅ ስራ አዋቂዎች ሁሉ ከፍ ያለ ኃዘን ስለ ወደቀባቸው። የጅ ሥራ የሚያውቁትም ለሥራ ወደ ነሱ በሄዱ ጊዜ ወይም ሠራተኞቹ ወደነሱ ለ፩ድ ጉዳይ በመጡ ጊዜ የሚሲዮኖችን ነገር ሲአስቡ በልባቸው ከፍ ያለ ፍርሃትና ጥርጥር ስለወደቀባቸው አጋንንት በምክንያቱ እየገቡ ፩ኛውን ታማሚ ፩ኛው አሳማሚ እየሆኑ በሕዝቡ ላይ ተመረዙና እስከ ዛሬም ድረስ ይህ ፖለቲክ ሳይገለጥ እንዲሁ ከወገኖቻችን ጋር እንደተቀያየምን እንገኛለን እነሱ ከሀገራቸው የተነሱ በረቂቅ ፖለቲክ እኛን ከፋፍለውና ለያይተው እኛ ስንደክም የነሱን መንግሥት አምጥተው በኛ ሀገር ላይ እነሱ ጌቶች እኛ የነሱን መንግሥት አምጥተው በኛ ሀገር ላይ የነሱ ባሮች ሽቃላዎች አድርጎ ለመኖር ስለሆነ እነሱ በኛ ላይ የመጠበብ ሥራ ሲሠሩብን ይኖራሉ። እንግዲህ እነዚህ ሥራ አዋቂ ወንድሞቻችን መናቅና እንደዚህ ያለ ስም መቀበል ይገባቸዋል እንበል ይሆንን እነሱ ባይኖሩ ገበሬዎች በምን ያርሱ ነበር። በምንስ ታጭዶ ይገባ ነበር። ሸማኔዎችስ ልብስ

# ሀ ዐርብ

ባይሠሩ ሴቶችስ ጥጥ ባይፈትሉ ገበሬዎችስ ጥጥ ባይዘሩ የመሬታችንንስ ጣዕም በምን እናውቀው ነበር ከሁሉም የበለጠ የኢትዮጵያ ነፃነት በምን ተጠብቆ እስከ ዛሬ ደረሰ የጦርና የጐራዴ የጩቤ አገልግሎቱ አለቀ ለማለት ዛሬም አያስደፍርም ቆዳ ሠራተኛውም ባይኖር የኢትዮጵያ ጀግኖች በጦርነት ጊዜ የሚለብሱት ጋሻ ነበር ያኔ ጋሻ ይለብሱና ጦርም ሆነ ቀስት ሲወረውሩባቸው በጋሻቸው ተቀብለው መልሰው በያዙት ጦር ወይም ቀስት የገደሉ እንደሆነ እንደዚህ ያሉ ጀግኖች በቤተ መንግሥቱ አዳራሽ ሲገኙ ዘራፍ ብሎ ተነሥቶ መፎከር የሚገባቸው ለነዚህ በጋሻ ጦርና ቀስት ዘርፈው ጠላታቸውን ወግተው የመጋደል ልማድ ያላቸው ሰዎች ብቻ ነው እንጅ ለማንም አልነበረም እነሱ ባሉበት ቦታ ዘራፍ ብሎ መናገርና መፎከር የማይገባ መሆኑ የጠበቀ ልማድ እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል። እንግዲህ በቤተ መንግሥቱ የሚከበሩ ጀግኖች ነፃነታቸው መጠበቂያ ለመሆን የበቁት ይህ ጋሻ ሲሆን ይህን ጋሻ የሠራ ሰው እንደምን መናቅ ይገባዋል ይልቁንስ ከፍ ያለ ክብር ይገባው ነበር እንጅ ፫ኛም ብርና ወርቅ የሚሠሩ ሰዎች ለቤተ እግዚአብሔር የሚሆን መስቀሉ ጻሕሉ ጽዋው ጽንሐው እነሱ ባይኖሩ ማን በሠራው ነበር ደግሞ የንጉሠ ነገሥቱ ዘውድ ዝቅ ብሎም ለራሶች የሚሆነውን ራስ ወርቅ የሚሠሩ ሰዎች እንደምን ክብር ይነሳቸው ይህ ከሁሉ ብልጫ ያለው ሆኖ የሚታይ ዘውድ የሚከበር ሲሆን ይህን የሠራው ሰው መከበር ይበዛበት ይሆንን የሮማ ልዑካን ይህን ረቂቅ ፖለቲክ እየፈጠሩ በብልሃታቸው መሆኑን ማስተዋል የተገባ ነው ሽማኔው ልብስ መሥራት ሴቱ መፍተል ወንዱ ጥጥ መዝራት ቢቀር ይህ ሲሆን ጉዳቱ ምን ያህል ነበር

፪ኛ ብረት ሠሪው ከላይ እንደተዘረዘረው ሁሉን ነገር ባያደራጅ ጦርና ጐራዴን ባሠራው ጠላቶቻችንን እንደ ልብ ቢዘዋወሩ ጦርና ጐራዴ ቀስትና ጩቤ በጃችን ሳይኖር ቀርቶ እንደጠመንጃውና እንደ ጥይቱ በነሱ እጅ ሆኖ ቢሆን ዛሬ እኛ ወዴት ላይ ነበርና ፫ኛ ቆዳ ሠራተኛውስ ባይኖር የፈረስና የበቅሎ ዕቃውስ ጋሻውስ የጐራዴ ሰገባውስ ሌሎችም ልዩ ልዩ ሥራዎች ሁሉ በምን በተሠሩ ነበር ከነሱ የምንገዛቸው ሆነው ቢሆን ይህችን ወርቅ ሀገራችንን አስረክበን

አርፈን ነበር ፬ኛ ወርቅና ብር ሠሪዎች ባይኖሩን ስለ ተሠራ ወርቅና ብር በመፍቅዳችን ሁሉ ከነሱ የምንገዛ ሆነን ቢሆን ግምቱን ማሰብ አለብን የሮማ ልዑካን ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ ጥቅሞች ዘግቶ ለማስቀረት አስበው በረቂቅ ፖለቲክ የሕዝቡን ልብና ልብ ከፋፍለው እነሱም ያሰቡት በጭራሽ ሳይሆን የእኛም በጭራሽም ሳይጠፋ እንደሌሎችም ሳይለማ ሳይስፋፋ እስከ ዛሬ እንደፈዘዘ ሲታይ ውስጠ ነገሩን ያላወቀ ሰው የኢትዮጵያ ሰዎች ጥበብ ከሰው ያነሰ እየመሰላቸው ያልሆነ ነገር ሲያወሩ ይሰማል በረቂቅ ፖለቲክ የተዘጋጀውን ቁልፍ የተመለከተ የለም ዛሬ በምንሰማው ሁሉ የጥበብ ጌቶች ፰ ኤል ናቸው እኛም ከነሱ ዘሮች በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ ከሠራተኞቹ ሁሉ አብረው መምጣታቸውን ታሪክ ይነግረናል ሠራተኛ የተባለም የተመረጠ ክብር ያለው መሆኑን ለመረዳት ኦሪት ዘፀዓት ፴፩ ፪ ወናሁ ተሠመይኩ በስመ ባስልኤል ዘውሬ ወልደ ኦር ዘእምነገደ ይሁዳ ፫ ወመላእክዎ መንፈስ ቅዱስ ወጥበበ ወአእምሮ ወእቁም በኩሉ ምግባር ከመ የሐሊ ወይኩን ሊቀ ጸረብት ከመ ይግበር ወርቀ

## ሆ ቀዳም

ውብሩረ ወብርተ ወዘኅብረ ያክንት ወሜላተ ወነተ ዘፍትሎ ወቢሶስ ክዑብ ይላል እነዚህ ሰዎች ለጅ ሥራ ጥበብ ተመርጠው ታዘዙ እነዚህ ሰዎች የታዘዙትን ሥራ ሲሠራ የተገኘው ሰው መከበር እንደሚገባው መሠረቱን ለመርዳት አርቄ የተጠቀሰበትን ማስተዋል አለ እንግዲህ ነገሥታቱን ወደሚሰብኩበት ወደ አጼ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት እንመለስ አጼ ሱስንዮስን ሰብከው ልባቸውን ከጨበጡ በኋላ መቀመጫቸውን በፍሪምና በትግሬ በጎርጎራ ደምቢያ አድርገው በመኳንንቱ ቤት እየገቡ በየከተማውም በየገበያውም ውስጥ የካቶሊክነት ትምርት ስብከታቸውን ማስፋፋት ዠመሩ ሕዝቡን የሚሰብኩበትም ቃል ኦርቶዶክሳዊውን ሃይማኖት እያቃለሉ የሮማን የልዮንን ሃይማኖት እያከበሩ ነው ይህ የሃይማኖት ክርክር አስቀድሞ ባ፬፻፶ ዓ.ም በላይ በልዮንና በዲዮስቆሮስ ተከራካሪነት ተለይቶ የኖረውን እንደገና በኢትዮጵያ ሁለት ባሕርይ እያሉ እየሰብሰኩ ሁለት ባሕርይ ማለትም ክርስቶስ ባምላክነቱ ሙታንን አስነሣ ለምጽ አነጻ ድውይ ፈወሰ ውኃውን ወይን አደረገ በሰውነቱ ግን ተራበ ተጠማ በተሰቀለም ጊዜ ከመጨነቁ የተነሣ አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ ብሎ አለቀሰ ስለዚህ ክርስቶስ ሰውነታዊና አምላካዊ የሆኑ ሁለት የተለያዩ ባሕርያት አሉት እያሉ እነ አባ ፖኤዝ እነ አባ አልፎንስ ከነተከታዮቻቸው የሚሰብኩት ስብከት ተስፋፋ ደግሞ በዚሁ ላይ ቀዳም ሰንበትን እንዳያከብሩ ሕዝቡና ካህናቱ እንደገና በካቶሊካውያኑ እጅ እንዲጠመቁ በተባለ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር በኃዘን ባሕር ስለጠለቀ ሕዝቡም ሲያያዝ የመጣውን ሃይማኖቱን መለወጥ ስለቸገረው ከሕይወቱ ሞቱን ስለመረጠ በሽ የሚቆጠር ሕዝብ በካቶሊካውያን እጅ እንዳለቀ ታሪክ ይነግረናል አጼ ሱስንዮስም ይህን ለማድረግ የደረሱበት ጠላቶቻቸውን የሚአጠቁበት ሀገሩን የሚአለሙበት መንግሥቱን የሚአሰፋበት መሳሪያ የሚገኝ ስለመሰላቸው ነው እንጂ እንደዚህ በረቂቅ ጥበብ መንፈሳውያኑ ያታልሉኛል ብለው ባለመጠርጠር መሆኑ አይካድም።

ሌላው ሕዝብ ይቅርና በጦርነቱ ላይ በግብጻዊ ጳጳስ በአቡነ ስምዖን እግር ኦርቶዶክሳዊው ሁሉ ተሰብስቦ ሲዋጉ የጦር መሪ የነበረ ያጼ ሱስንዮስ ልጅ የመለኮታዊት ባል ራስ ዮልዮስ ነው ይህም ራስ ዮልዮስ በጦርነቱ ሙቷል ራስ ሥዕለ ክርስቶስ ወንድማቸው ፍጹም ካቶሊክ ስለነበር በጎጃም ላይ ቀዳም ሰንበትን ሻሩ እንደ ዓርብና እንደ ረቡዕ እናድርጋት ብሎ ያጼ ሱስዮስን ዓዋጅ አናግሮ ሕዝቡ ከዳር እስከዳር አንቀበልም ብሎ እስከ ፯ቀን ብርቱ ጦርነት ተደርጎ ከቀኝና ከግራው በብዙ የሚቆጠር ሕዝብ አልቋል ታሪኩ እንደሚናገረው ባጼ ሱስዮስ ዘመን ያለቀው ሕዝብ ቁጥሩ ከሚሊዮን በላይ ቢሆን እንጅ ከሚሊዮን በታች ነው ለማለት አይቻልም ከወንድሞምቻቸው በዚሁ ጦርነት እርስ በርሳቸው የተጋደሉ አሉ ይህን ያህል ጉዳት ባጼ ሱስንዮስ ለመድረስ የቻለው አስቀድሞ ሮማ ላይ በተመሠረተው ማኅበር ረቂቅ ፖለቲክ ነው

በግልጽ ጦርነት አንሥተው ቢመጡ ስንኳን ፩ሚሊዮን ሰው ሲአልቅና የሚሊዮን ሩብም ለመግደል ባልቻሉ ነበር እነሱ ግን የመነኩሴ ልብስ ለብሰው ባሕያታውን መስለው መጥተው እንደ መልካሙ መካር መሳሪያ እናስመጣልህ ብለው እያታለሉ ይህን ያህል ደም ለማፍሰስ ከደረሱ በኋላ እንደገና ከወገኖቻቸው በመለያየታቸውና በጽኑ ሕማምም በመያዛቸው ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተመልሰው ልጃቸውን ፋሲለደስን

# ለ እጉድ

አንግሠው በጥብቅ ንሥሐ ገብተው ለማረፍ በቅተዋል እነሱ ግን ይህን የማፋጀት ሰይጣናዊ ሥራ ከታላቅ ጀብዱ ቆጥረውት በታሪካቸው ላይ አጼ ሱስንዮስ ዕረፍቱ በደረሰ ጊዜ በካቶሊክ ካህናት ተናዞ ነው እያሉ ጽፈው ይገኛል። ይልቁንስ ስንኳን በነሱ ሊናዘዙ እንዲያውም በሡሩባቸው ረቂቅ ተንኮል በጣም ስለተናደዱ ለልጃቸው ለፋሲለደስ ቅዱስ ዳዊት ለልጁ ሰሎሞን በቀላሉ እንዳወረሰው አጼ ሱስንዮስም ለልጃቸው ለፋሲለደስ ሐሰተኛና አታላይነታቸውን ገልጸው አንትም እንደኔ የፈለገኸውን መሣሪያ እናመጣልሃለን እያሉ እንዳያታልሉህ ወደ ንጉሣቸውም ደብዳቤ አትጻፍ እነሱንም ከኢትዮጵያ በጭራሽ እንድታስወጣቸው ፪ኛም ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገቡ እንድታደርግ ብለው ከመንግሥቱ ጋር ስለ አወረሱት ፋሲለደስም በነገሡ ጊዜ አባቱ በሕይወት ሳሉ ስለሆነ እነዚህን ሰባኪዎች እንዲወጡ ዓዋጅ ነገረና ከዚያ ጠላቶቻቸው እያባረሩ በዱር በገደል እየገቡ ስላመለጡ ለወደፊትም ካቶሊካውንን ከቤቱ ካገሩ አስገብቶ የተገኘ በአካሉ ይቀጣል የሚል ዓዋጅ ተናግሮ ነበር ከዚህ በኋላ ፋሲል ነገሠ ሃይማኖት ተመለሰ ተብሎ በሺ፮፻፳፫ ዓ.ም ከተነገረ በኋላ ስለ ኦርቶዶክስ ሃይማኖታቸው ተሰደው የነበሩት ሁሉ መነኰሳትና ቀሳውስት በየገዳማቸውና በየደብራቸው ገብተዋል አክሡም ጽዮንም ከተሰደደችበት በ፲፪ ዘመንዋ ተመልሳለች ላሊበላም ገነተ ማርያም ሌሎችም አድባራት ሁሉ በየቦታቸው ተመልሰው እንደ ጥንቱ ሃይማኖታቸውን ይዘው ለመቀመጥ ችለዋል ይህም የሆነ በሺ፮፻፳፱ ዓ.ም ነው። ከዚህም በኋላ ካገር እንዲወጡ ከታወጀም በኋላ አገር ላገር እየተሹለከለኩ መኳንንቱን ከንጉሡ እንዲሸፍት እያደረጉ የተንኮል ሥራቸውን ስለቀጠሉ ባጼ ፋሲል ዘመነ መንግሥት ላይ አቤቶ ዘማርያም የተባለ የተንቤን ገዥ በንጉሡ ላይ ስለሸፈተ የላስታውም መልክዐ ማርያም ጊዜ አገሩ ሲበዘበዝ ከሀገር ውጡ ከተባሉት ሁለት ሰዎች ስማቸውም ፩ኛው ብሩን ፪ኛው ኮርዲያሪ ነው። እነዚህ ነገር እየፈጠሩ ንጉሥንና አቤቶ ዘማርያምን መልክዐ ማርያምን ያሸፈቱና ያዋጉ አቤቶ ዘማርያምን በጦርነቱ ያስገደሉ ተይዘው ወደ ንጉሡ ቀርበው ሞት የተፈረደባቸውና ተደበደቡ ከዚህ በኋላ ሮማ ላይ የቆመው ማኅበር እነሱ የሚሠሩትን ሥራ እየሰማ ከመደሰቱ የተነሣ ገንዘቡን እያከታተለ የሚሠሩትን ሥራ እየሰማ ከመደሰቱ የተነሣ ገንዘቡን እያከታተለ ስለሚልክላቸው እነሱም ያነን እየተቀበሉ በዚያ ገንዘብ ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወሩ ሥራቸውን ከመሥራት አያቋርጡም ፪ኛም በአረንጎ ተገኝተው ግራዝማች ሚካኤል የተባለው ሄዶ ካሉበት ቦታ አስወጥቶ ወደ ስናር በረሃ ለቋቸው ተመልሷል። ፫ኛ እንደዚሁ እየተዘዋወሩ መቀመጥን በሣልሳዊ ዳዊት ዘመን የደብረ ሊባኖስ ካህናቶች ጉዳይ አለንና ጉባዔ ይደረግልን ብለው ለንጉሡ አመልክተው በንጉሡ ፈቃድ የካህናቱ ስብሰባ በሆነ ጊዜ አባ መዝሙረ የተባሉ ተነሥተው ፫ት የፈረንጅ ቄሶች ከበሐር መጥተው በዓይነ እግዚእ ወልቃይት ተቀምጠዋል ያስመጧቸውም አጼ ዮስጦስ ናቸው አጼ ዮስጦስም ወልቃይት ድረስ እየሄዱ የቄሶስችን ቅዳሴ ይሰሙ ነበር አሁን ግን በእግዚአብሔር ፈቃድ አጼ ዮስጦስ ሞቱና እርስዎ ባባትዎ ባጼ ኢያሱ ዙፋን ከተቀመጡ እነዚህ ፈረንጆች ይምጡና ሃይማኖታቸውን ምን እንደሆኑ ይጠየቁልን እሉ አጼ ዳዊትም መልእክተኛ ልከው አስመጧቸውና ከነዚህም ፩ኛው የነምሳ ፪ቱ የሮማ ተወላጅ ፫ቱ የካቶሊክ ሚሲዮን ናቸው ያስመጧቸውም አጼ ዮስጦስ የጦር መሳሪያ

# ሉ ሰኑይ

ለማግኘት ነበር ተብሎ ስለተነገረ እነዚህ ፈረንጆች ቀርበው ቢጠይቁ በኬልቄዶን ጉባዔ እንደተለየው የልዮን ተከታዮች ካቶሊካውያን ነን ብለው ስለተናገሩ በጉባዔው የተገኙ ሊቃውንት በተራ እየተነሡ እነዚህ ፈረንጆች ባጼ ሚናስ ዝምረው በሀገራችን ላይ ተንኮል ለመሥራት ቦዝነው አያውቁም በዚህ ምክንያት በሀገራችን ላይ በየጊዜው የፈሰሰውን ደም ማንም ያውቀዋል በየጊዜው የንጉሥ አዋጅ እየጣሱ እየመጡ የሚያመጡትን መዣሪያ እናመጣለን እያሉ ነገሥታቶቻችንን ሃይማኖት ለማስለወጥ ነውና ባጼ ሱስንዮስ የፈሰሰው ደም ሳይደርቅ አሁን ደግሞ እነዚህ ዓዋጃችንን አፍርሰው አገራችን ገብተው እንደዚህ ያለ ሥራ ሲሠሩ ስለ ተገኙ የሞት ቅጣት ይገባቸዋልና ይሞቱ በቃ እያሉ ስለፈረዱባቸው በሞት ተቀጡ (እነዚህ የተገኙት ከንቱ ተገደሉ እንጅ እነሱ ሥራቸው ስላማረላቸው እየተከታተሉ ለመምጣት አላቋረጡም በየጊዜው እየተከታተሉ መምጣታቸውን የሚገልጽ ከላይ ለተጻፈው ተከታይ (በሺ፲፰፻፵፩ ዓ.ም በመሳፍንት ዘመን ራስ ማርዬ ደጃች ውቤ ደጃች ሰባጋዲስ ፫ቱ በተዋጉበት ዘመን እነ አባ ያዕቆብ በፓፓ ጎርጎርዮስ ዘመን የካቶሊካውያን ትምህርት በኢትዮጵያ ተስፋፍቶ ነበር ተብሎ የተጻፈ የነሱ ጽሑፍ ይነግረናል (እነሱ እንደዚህ ብለው በጻፋቸው የኢትዮጵያን መንግሥት በረቂቅ ተንኮላቸው ከርክረውና ገዝግዘው እንዳደከሙት በመሳፍንት ዘመን እንደልባቸው ስለሆኑ ከአባ ያዕቆብ በኋላ አባ ቢአንኪሪ አባ ዮሐንስ አባ ዮሴፍ በራስ አሊ ጊዜ በፓፓ ጎርጎርዮስ ፲፮ኛ አባ ማስያስን አባ ዮስቶስ አባ ቂሳርዮስ አባ ፌሊክሲዎስ አባ ማስያስ እስከ ፲፱ ዓ. ኢትዮጵያን ዞሩ ይባላል።

(ከዚህ በኋላ በአባ ማስያስ ትእዛዝ አባ ቂሳርርዮስና አባ ያዕቆብ ሀገረ ከፋ ገቡ ይህም የሆነ በነሱ ቁጥር በሺ፲፰፻፶፩ ዓ.ም ይላል (ሀገረ ከፋን እንደ እርስት አድርገው የተመለከቷት ባጼ ገላውዴዎስ አባ ቤርሙዴዝን አስሮ ከፋ ልኮት ስለነበረ ነው) አባ ቂሳርዮስ እዚያው ከፋ ሙቷል አባ ማስያስም በሺ፲፰፻፶፱ ዓ.ም ሀገረ ከፋ ገቡና በዚያ ጊዜ ጠንቋዮቹና ንጉሥ ካሞን እርሳቸውን እንዲአስሄድ ግድ አስደረጉት በአቡነ ማስያስ ፋንታ በከፋ አገር የቀሩ አባ ኃይሉና አባ ዮሐንስ አባ ያዕቆብም ናቸው አባ ሊዎን ደግሞ በጌራ አገር በከፋ መሬት ዳር የነበሩ እርሳቸው በቄሶች ሁሉ ላይ አለቃ ሆኑ አቡነ ፊልኪስዮስ ወደ ከፋ እስቲመጡ ድረስ በሺ፲፰፻፸፯ አባ ሉቃስና አባ ፍሥሐ አባ ባአፍሎ ሲሞቱ ጊዜ በሺ፲፰፻፸፱ አባ ማቲዎስ ወደ ከፋ አገር ተሻገሩ አቡነ ፊሊኪዎስ በሺ፲፰፻፸፯ ወደ እግዚአብሔር በሄዱ በከፋ አገር የቀሩ እስከ ዛሬ ድረስ አባ ፍሥሐና አባ ሉቃስ ናቸው የትግሬው ንጉሥ ራስ አሊ ቢሞት ቴዎድሮስ ካሣ ነገሠ በዚያ ወራት የኢትዮጵያ አቡን አባ ስለማ ነበር። አጼ ቴዎድሮስ ኃይል አገኘ እንጅ ሕዝቡን በግፍ አኖረው) ከላይ እንደተጻፈው በየጊዜው የመንግሥቱን ዓዋጅ እየጣሱ እየገቡ ንጉሡንና መሳፍንቱን በፖለቲክ እያፋጁ ኢትዮጵያ በንጉሠ ነገሥት ሥልጣን ስትተዳደር የኖረቺቱን ለመከፋፈል ባደረሷት ጊዜ እንደልባቸው ለመሆን እንደቻሉ ከላይ የተጻፈውን ታሪካቸው ያስረዳል) አጼ ቴዎድሮስ ሲነግሡ ግን እንደልብ ወዲያና ወዲህ ማለት አለመቻሉ የሚአስረዳ ያጼ ቴዎድሮስን ታሪክ እያኮሰሱ በመዘዋወር መጻፋቸው ይታወቃል) (በሺ፲፰፻፹፰ ዓ.ም ፓፓ ፱ኛ ፒዮስ በሮማ በተቀጡ ጊዜ ፩ኛ አቡነ ማስያስ አቡነ

# ሊ ሠሉስ

ያዕቆብ አባ አትናቴዎስ በሸዋ ገቡ) ንጉሥ ምኒልክ መንግሥቱን በቅርብ እንደያዙ ደስ ብሎት ተቀበላቸው መልካም ትዳርም ሰጣቸው በዚህ ወራት ልቼ ፍቅሬግንብ ደብረ ብርሃን አማን ፈንፈኒ ገላን የካቶሊክ ማኀበር ሆነ በሺ፲፰፻፸፰ ዓ.ም ንጉሡ አጼ ዮሐንስ ብዙ እንግሊዞች በትግሬ ላይ አንግሠውት ነበር የምኒልክን ትልቅነት ፈርቶ ወዳጅና መልካም ምክር እንዳያገን አቡኖችን ካጠገቡ እንዲሄዱ አደረጋቸው ወደ አውሮፓ አራቃቸው ይላል) (እንግዲህ ከላይ ዝምሮ እንደተጻፈው የነሱን ተልኮና አታላይነት የኢትዮጵያ ነገሥታት እየተረዱ ከኢትዮጵያ ውጡ ሲባሉ ፩ኛ ባጼ ገላውዴዎስ

፪ኛ ባጼ ፋሲል ፫ኛ በጻድቁ ዮሐንስ ፬ኛ በሣልሳዊ ዳዊት ፭ኛ ባጼ ቴዎድሮስ ይኸው አጼ ዮሐንስ ከኢትዮጵያ አስወጣን ብለው እነሱ የጻፉት ፮ኛ ጽሑፍ ያስረዳል ስል ከላይ የተዘረዘሩት የልዑካኑ ስምና ይህ ውጡ የሚለው ዓዋጅ ሁሉ ከነሱ ጽሑፍ የተገኘ ነው ለወደፊቱም ለአንባቢው እንዲመቸው የሮማውያኑ ጽሑፍ በምልክት ተጽፎ የሚገኘው ነው (በሺ፰፻፹ አቡነ ማስያስ ቢአረጁ በሮማ አገር ለማረፍ ቀሩ ንጽሕናቸውንም ለማክበር ፲፫ኛው ሌዎን ካርዴናል አደረጋቸው አቡነ ያዕቆብ ያቡነ ማስያስን ወርሰው የጋላን አሕዛብ እረኛ ለመሆን ስም አገኙ ወደ ሸዋ መንገድ ቢአጡ ወደ ሐረርጌ አሕዛብ ዝውር አሉና እዚያች በሺ፰፻፹፩ ዓ.ም ከፋሲካ በፊት ደረሱ ዝውራት የምሥር አገር ዓረብ ይገዛው ነበር። በሺ፰፻፹፬ ዓ.ም እንግሊዝ ከሐረርጌ ላይ የዓረብን ጦር አስነሥቶ የአሚር ሙሐመድን ልጅ አብደላሂ አነገሠው ይህ አሜር ጥቂት ቀን ቆይቶ እንግሊዝን ካዳው አቡነ ያዕቆብንም የምኒልክ ወዳጅ ነው ብሎ እሳቸውን ለመግደል አሰበ ግን የእናቱን እርግማን ፈርቶ ከአገሩ አስወጣቸው እንጅ አልገደላቸውም) (ከላይ እንደተጻፈው አባ ያዕቆብ የተባለው በአባ ማስያስ ተተክቶ ለመምጣት አዳሎችን ስለፈራ ወደ ሐረር መሄዱን ገለጸ አዳሎችንም የፈራበት በሐሰብ በኩል ወደ አንኮ በር ሲመጡ አደሩበት ቦታ ላይ በጨቤ አርደዋቸው ስለነበር ነው።

ሐረርን የምሥር ሀገር ዓረብ ይገዛው ነበር ያለው ግብጽን ይገዛ የነበረው ዓረብ በማለት ፋንታ የግብጽን አገር ዓረብ ማለት ግብጽ ኢትዮጵያን ሐረርንና ምጽዋን ትገዛ የነበረች ለማስመሰል ነው እንጅ ግብጽ ለራስዋ ተገዥ ነበረች እንጅ እስዋ ሙብት አግኝታ ገዥ እንዳልነበረች የተገዥነትዋ ሐውልት ኰብት የሚባል ጥንት ቋንቋዋን ደምስሶ ዓረብኛ ቋንቋውን አንግሦ እስከ ዛሬ በሠረቱ ቋንቋዋ ባለመግባቷ ነው እንግሊዞችና ኢጣልያኖች ተስማምተው እንግሊዞች ወደ ግብጽ ኢጣልያኖች ወደ ኢትዮጵያ ለመከፋፈል በተነሡ ጊዜ ቱርኮች በንግድ ምክንያት እስላሞችን የባርያ ነጋዴዎችን እየተስማሙ ለመንግሥት ፩ድ ጊዜም ሲገብሩ ፩ድ ጊዜም ሲሸፍቱ በመሳፍንት ዘመንም ሁሉም ስለተለያየ እንዲሁ ቆይቶ ነበር እንግሊዝና ኢጣልያ ሲነጋገሩ እንግሊዝ ወደ ግብጽ ሲዞር ቱርኮች ይዘውት የነበረውን ሁሉ ኢጣልያኖች ለመያዝ አሳብ ስለነበራቸው እነ አባ ማስያስ ምጽዋንና ዓሰብን አጼ ምኒልክን እያታለሉ እጅ ካደረጉና ከሮማ የጦር ሠራዊት አስመጥተው ካሰፈሩ በኋላ ወይም ገና እንደአሰቡ ሳሉ አባ ያዕቆብ ወደ ሐረር አሕዛብ ለማስተማር ዝውር ብለው ሐረር ገቡና አብዱላሂም ሊገድላቸው ነበር አስወጣቸው

# ላ ረቡዕ

ያለው የከፋው ባላባትም እንደዚሁ አስወጣን ብለው ጽፈዋል) አብዱላሂምም ውጡ ብሎ ለመግደል አሰበ ያለው እንደምፅዋዕ ሁሉ ቱርኮች ሲለቁ የኢጣልያን ጦር ለማስመጣት አሳብ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ፩ድ ነገር አገኝቶት ይሆናል ብሎ መገመት ሩቅ ጉዳይ አይደለም ወደ ሐረርም አባ ያዕቆብ ሄዶ የሚለው አባ ያዕቆብ እውነት የሐረርን ሕዝብ ለማጽደቅ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስበው ከእግዚአብሔር ዋጋዬን አገኛለሁ ብለው አይደለም ሐረርም የወረዱት የኢጣሊያ ጦር የሚገባትን ዘዴና ፖለቲክ እስቲአሰናዱ ድረስ ከቆዩ በኋላ ያጠኑትን ፖለቲክ ወደ ሮማ ልከው አስፈላጊውን ሁሉ ለማስታወቅ ነው ዋጋ የሚሠጣቸውም የሮማው ንጉሥ ነው በጃቸው የያዙትም መስቀልና መጽሐፍ ማታለያና የሚአሞኙበት ነው እንጅ እውነት የክርስቶስ ሰው ከሆኑ እግዚአብሔር በከፈላቸው አገር የሚኖሩትን ሕዝቦች ፈጅተህ መንግሥት ታሰፋለህ ብሎ ለግፈኛ መሪ መሆን የገተባ ሥራ መስሏቸው አይደለም ወይም ሮማን ስንት ጊዜ ጠላት እየገባ ሥቃይ እንዲያሳያት ታሪኩን አልተመለከቱትም ይሆናልና በሐረር በኩል የተዘረጋው አሳባቸው ስለ ሁለት ነገር ተቋረጠ ፩ኛ አብዱላሂም ስለ አባረራቸው ፪ኛ አጼ ምኒልክ በሺ፰፻፹፱ ዓ.ም ሐረርን ስለ መያዛቸው አሳባቸው ከንቱ ሆኖ ቀረ አጼ ምኒልክ ሐረርን በያዙም ጊዜ ይህነኑ የውሥጥ ተንኰላቸውን ባለመዘንጋታቸው ከልዑል ራስ መኰንን ጋራ የተስማሙ እየመሰሉ ፖለቲካቸውን ያላቋረጡ አለመሆናቸውን የኢትዮጵያ ነፃነት በተመለሰ ጊዜ የተዝረከረከው የታሪክ ጽሑፍ ገልጾለታል ይህ የሮማውያን ፖለቲክ በሜዳ ላይ ተጎልቶ ለመገኘት የቻለውን ፴፻ ዘመን

ሙሉ ሰው እንዳያየው ተሸፍኖ ኖሮ ፀሐይ ስላማረው የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት ግርማዊ ቀ.ኃ.ሥ ወደ አውሮፓ ወደ ዓለም መንግሥታት በሄዱ ጊዜ ማን አለብኝ በማለት የተከተተው ሁሉ ገሃድ ስለ ወጣና በየሥፍራው እንደተዘረጋ መዝኖ ሠሪውን ንጉሥ ነገሥት ፴፱ ዘመን ሲተበተብ የኖረውን ፖለቲክ በታትኖት አስደናቂ በሆነ ድል ሳይታሰብ በታላቅ ግርማ በደረሰ ጊዜ የፖለቲክ መጻሕፍቶች ተገልጠው ተገኙና ይኸው ውስጠ ሥራቸው ለመገለጥ ተቻለ (በሺ፰፻፹፯ ዓ.ም ሐረርጌን ራስ መኰንን ሲገዛው አቡነ ያዕቆብ ሐረርጌ ተመልሰው እዚያው ሲታገሱ ዝም ሲሉ በቀስታ በምድር ላይ ሲራመዱ እንደዚህም የእግዚአብሔርን ማሳ አሰፉ በእርሳቸውም ወዝ በእስላም አሸዋ ውስጥ የእግዚአብሔርን ዘር እንደ ድንቅ አበቀሉ) ይላል (የእግዚአብሔርን ማሳ አሰፉ ይላል እርሳቸው የሄዱ የሮማን መንግሥት ለማስፋት ፖለቲካ ለማስኬድ ነው። የእግዚአብሔርን ሐዋርያነት እየሰጠ ይጽፍላቸዋል) በሺ፰፻፹፱ በ፮ ነሐሴ አቡነ ማስያስ ንጹሕ ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር መለሱ። የሥራቸውን ሁሉ ዋጋ በረከት ሊሰጣቸው አምላክ ጠራቸው። አቡነ ማስያስ የረገጡት መሬት ሁሉ ቡራኬ አገኘ እርሳቸው ሐዋርያትን መስለው መሬትን ሁሉ በእግራቸው ዞሩ የጠፉትን የአምላክ በጎች ለመፈለግ ከነርሱ በኋላ ለመሮጥ ወደ ጌታም ለመግባት የእርሳቸው ትምህርት ከሌላው አገር ሁሉ በከፋ አገር በረከተ) ከላይ የተጻፈውን ሁሉ አላዋቂዎችን ለመስበኪያ ነው እንጅ እውነት አይደለም። የረገጡት መሬት ሁሉ ቡራኬ አገኘ የተባለውን እውነት እንበለው ይሆንን እርሳቸው የረገጧት ኢትዮጵያ የደም ጎርፍ የወረደባት አብያተ ክርስቲያናት እንዲቃጠሉ። ስንት ሊቃውንቶች እንዲታረዱ የሆነው ሮማ ላይ በቆመው የፖለቲክ ማኅበር እርዳታ

# ሌ ጎሙስ

አይደለምን? (አቡነ ማስያስ ሕዝቡን እየሰበኩ የሚአቀርቡት ሀብት ሁሉ ከማን የተገኘው ይሆን ሐዋርያትን መስለው መሬትን ሁሉ በግንባራቸው ዞሩ ይላል) በዘመናቸው መኪና አውሮፕላን አልነበረም ስለዚህ በጊዜው ይገኝ በነበረው በቅሎና ፈረስ በግመልም እርግጥ ይጓዙ ነበር መቼም ውሽት አይቸግርምና ያነን ሁሉ በረሃ ያነን ጓዝ ተሸክመው ተጓዙ ለማለት ይታሰብ ይሆንን በዚያ ጊዜ ለመስበኪያ ይዘውት ይመጡ የነበረው ሀብት ብሩ ይቆይና ለየመኳንንቱ የሚሰጠው ብረት ና ጥይት ዓረቄውና ሽጉጡ ካባው ቀሚሱ ልዩ ልዩ ዕቃዎችን ሁሉ ተሸክመው በእግራቸው መጡ ማለት ይሆንን እንደ ሐዋርያት የተባለውን ጽሑፍ ተመልካች ሲገምተው ሐዋርያት ወደ ነገሥታቱ ሲሄዱ የጦር መሳሪያ እየያዙ ነበር ይሆንን። ወይስ ብር እየተሸከሙ ይሄዱ ነበር ማለት እውነት ይሆንን ሐዋርያት ከነገሥታት ዘንድ ሄደው የጦር መሳሪያ እናምጣላቸው ይሉ ነበር ይሆንን።

ሐዋርያት ብር የሚሸከሙ ከሆኑ ቅዱስ ጴጥሮስን ፩ድ እግረ ሽባ ገንዘብ ቢለምነው ወርቅና ብር ወደኔ አይገኝም የሚገኘውን በጌታዩ ስም እግርህ ይዘርጋልህ ተነሣና ሂድ ብሎ እንደፈውስ ግብረ ሐዋርያት ፫ ፮ መመልከት ነው የሐዋርያትን ሥራና የነ አባ ማስያስን ሥራ ምን አገናኘውና የሐዋርያት ሥራ የሰውን ሕይወት ለመጠበቅ ነው። የሮማ ልዑካን ሥራ የሰውን ሕይወት እንደሚጠፋ ዘዴ መፈለግ ነው የሐዋርያት ሥራ ከዚህ ዓለም ወጥመድ የሚአመመልጥበትን ጾምን ጸሎትን እንዲይዝ እንዲያጠብቅ ነው ይህም ጌታ ማቴዎስ ፭ ፯ ለጽድቅ ብለው የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው እነሱ በመንግሥተ ሰማያት ይጠግባሉና ያለውን ተመልክተው ነው የሮማ ልዑካን ግን በዓርብና በረቡዕ የእንቁላል ቁርስ እያቀረቡ ጾም አይረባም አይጠቅምም እያሉ የሚሰብኩ አይደሉም የሮማውያን ስብከት ሮማ ላይ የቆመውን የማኅበር ገንዘብ እያመጡ የመባልዕልትን ነገር እያደራጁ ጾም የለመዱትን ሰዎች ሁሉ ጾም የማይረባ አይጠቅምም እያሉ በምግብ ብዛት ሰለሚሰብኩ ይህን ስብከት በማቴዎስ ፬ ፭ ሊፈትነውም መጣ አለውም የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ እነዚህ ድንጋዮች ዳቦ ይሁህልህ ቢለው ቁ ፬ ጌታም መለሰለት ከእግዚአብሔር አፍ በወጣው ቃል እንጅ ሰው በእንጀራ በዳቦም ብቻ እንዳይድን ተጽፏል ብሎ መለሰለት መብልና ዳቦ ማቅረብ የማን ሥራ ነው። ይህ ምስጢር ማንን ይመለከታል።

ከላይ አባ ማስያስ ከእግዚአብሔር ዋጋቸውን ሊቀበሉ ተጠሩ ማለት እርግጠኛ ነገር ተጽፏል እርግጥ ነው በቅድመ እግዚአብሔር በምድር የተሠራውን ዋጋ መቀበል የማይጠረጠር መሆኑን አምናለሁ ከላይ ከእግዚአብሔር አፍ የወጣው ነው እንጅ ሰውን የሚአድን መብል ሰውን አያድንም ያለው ጌታችን ያዘዘውን ቃል የፈጸመ ይድናል ማለቱ ነው። ማቴዎስ ፭ ፲፱ ስለዚህ ካ፲ቱ ትእዛዛት ፩ዷቱን ያሻረ እንዲሁም ያስተማረ በመንግሥተ ሰማያት ታናሽ ይባላል ያለውን ካለማስተዋል ነው እንጂ ይህን ያስተዋለ ሰው ቢኖር ፲ቱ ቃላትን አጥብቆ ያልያዘ ሰው ወንጌላዊ ነኝ እያለ ሰውን ማታለል ከንቱ ነው በዚሁ ማቴ፭ ፲፰ አማን እብለክሙ እስከ የኃልፍ በሰማይ ወምድር የውጣ እንተ አሐቲ ቅርጸታ ኢትኃልፍ እምኦሪት የውጣ ያለው ፲ቱ ቃላትን ማለቱ ነው በአብራይስጥ ፊደል ቁጥር የ አሥረኛ ቁጥር ስለሆነ

# ል ዓርብ

ነው እንግዲህ ወንጌላዊ ነኝ ለሚል መደበኛ ሥራው ፲ቱ ቃላትን መያዝና መፈጸም ስለሆነ ማቴ ፲፱ ወአመስ ትፈቅድ ትባእ ውስተ ሕይወት ዕቀብ ትእዛዛተ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባትን ብትወድ ፲ቱ ቃላትን ጠብቅ ፲ ቃላትንም በዝርዝር ፲፯ ፩ ኢትቀትል ነፍሰ ፪ ከሌላ ሴት ዝሙት አትሥራ ፫ኛ የሰው ገንዘብ አትሥረቅ ፬ኛ አባት እናትህን አክብር ፭ኛ አፍቅር ቢጸከ ፮ኛ ወይቤሎ ወሬዛ ዘንተ ኩሎ ዓተብኩ ጎልማሳውም ፮ቱን እንደቆጠረለት ሁሉንም ከልጅነቴ ጅምሬ የፈጸምኩ ነኝ ቢለው ፳፩ ኢየሱስም ፍጹም ለመሆን ትፈቅድ እንደሆነ ሂድና ገንዘብክን ሽጠህ ለነደያን መጽውት ቢለው ጎልማሳውም ገንዘብ ብዙ ስለነበረ አዘነ ይላል የሐዋርያት ተከታይ ለመሆን ብዙ ስለነበረ አዘነ ይላል የሐዋርያት ተከታይ ለመፈጸም ብዙ ችግር አለበት ይህ ጎልማሳ እንኳ ፲ቱ ቃላትን በቃሉ የፈጸመ ሲሆን ከገንዘብ መለየቱ እንደቸገረው በቁ ፳፬ የተጻፈውን ማየት ነው።

ዕቀብ ትእዛዝ ባለው መሠረት ከላይ የተጻፉትን ቃሎች እና ኢትቅትልን የሮማ ልዑካን እናውቃታለን ለማለት የሚቻላቸው ይሆንን ፲ቱ ቃላትን የሚአውቁ ከሆኑ ወሰን ከማያገናኛቸው አገር መልካም ሆና አየን ብለው በፊት ለፊት ጦርነት እንኳን ሳይሆን በረቂቅ ተንኮል መንፈሳውያን መስለው የመነኵሴ ልብስ ለብሰው ቅንነት ያላቸው ሰዎች በዳቦና በስኳር እያባበሉ ሃይማኖታቸውንና አገራቸውን ማስካድ ይህ የሐዋርያተ ሥራ ለመባል የተገባ ነው እንበል ይሆንን ይህን የነሱን ስለ ዓለም ሃይማኖት የእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክ በተባለው ከማርቲን ፍላድ መጽሐፍ በሺ፰፻፺፫ ዓ.ም በታተመው በ፫፻፹፯ ገጽ የሮም ወገንም ወደ አበሻ ሲመጡ ባጼ ገላውዴዎስና በሱስንዮስ ዘመን ጦርን አስነሱ በግፍ ስለ ማይጠቅምም ነገር በምሥር ጳጳስ ፋንታ የሮምን ጳጳስ ሲያደርጉ የፋሲካውንም ጊዜ ሲለወጡ የቅዳሜንም ማክበር ሲአጠፉ እንዲህ ያለውንም ዝምብሎ ነገር ሲያደርጉ ሰውንም በሰው ነገር ማስተማር ሲፈልጉ በእግዚአብሔር ቃልም አይደለም ስለዚህም ሥራቸው አልተባረከም ከእግዚአብሔር አልነበረምና አልጸናም ብለው ጽፈዋል።

ይህም ጽሑፍ እርግጠኛውን ጻፉ እንጂ ለአድልዎ ቢሆን ከኛ ለነሱ ነበር የሚቀርቡ እኔ በጣም የምደነቀውና የምገረመው ፬፻ ዘመን በሙሉ ታሪካቸው እየተገለጸ ከሀገር ውጡ እየተባሉ ከሄዱ በኋላ የማታለያ ዕቃቸውን እየያዙ እየመጡ ቤተ ክርስቲያን እየሠሩ በወንጌላውያን ስም በመጠራታቸው ነው የሚገርመኝ ማቴ ፲፭ ፱ የሰውን ትምህርትና ሥራት እያስተማሩ በከንቱ እንገዛልሃለን ይሉኛል ያለውን እንደዚህ መሠረት የሌለውን ሰው ሠራሹንና ጊዜ ያበቀለውን የሚከተሉትን ነው ቁ ፴፫ ሰማያዊ አባቴ ያልተከላት ተክል ሁሉ ትነቀላለች ብሎ በቃሉ የተናገረ እንደዚህ ያለውን በሰው አገር ሄዶ ከእናንተ ሃይማትኖት የኛ ሃይማኖት ይበልጣል እያለ እየሰበከ ከምዕመናኑም በላይ ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን ወደ መሠረተ ሃይማኖታቸውም እንዳይመለሱ በፅኑዕ መሐላ እያስማሉ የሃገሩን ሃይማኖት ማስካድ ጥቅሙ ምን ይሆን ሮማ ላይ በሺ፰፻፺ ዓ.ም የቆመው ማኅበር ያወጣው ገንዘብ ሁሉ ከንቱ ሆኖ ከመቅረቱ በቀር ምንም ተስፋ እንደለለው ማስረጃውን የፈለገ የዱቼ ሙሶሊኒንና የግርማዊ ቀዳማዊ

## ሎ ቀዳም

ኃ. ሥ. ታሪክ ይመልከት በሺ፰፻፹፰ ዓ.ም ልበ ቅኑ በአምላኩ የሚታመነው ግርማዊ ዳማዊ ምኒልክ ዓድዋ ላይ እንደ ከብት ተነድቶ የመጣውን ነጭ በምሕረት አስተላልፈው በሮማ ሰዎች አንደበት ተመርቀው ነበር እንደዚህም መደረጉ ልዑል እግዚአብሔርን በመተማመን ብቻ ነው አሁንም ኢትዮጵያ ኃይሏና መመኪያዋ እግዚአብሔር ነው ከኢትዮጵያ እጋፋለሁ የሚል ከእግዚአብሔር እጋፋለሁ የሚል ነው። ይህም ጽሑፌ መሠረት የሌለው እንዳይመስል የኢትዮጵያ ኃይልና ጉልበት እግዚአብሔር ለመሆኑ ቅዱስ ዳዊት በመዝሙር ኢትዮጵያ ታበጽሕ እዳዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ብሎ ትንቢት ገና ባ፩ሺ ፬፻፵፯ ዓመተ ዓለም ትንቢት ተናግሮላታል የዳዊትን ትንቢት ለሚጋፋ መልስ የለኝም (ደግሞ ስለ አቡነ ያዕቆብ በሺ፰፻፺፱ ዓ.ም መስከረም ፩ ቀን አቡነ ያዕቆብ ወደ እግዚአብሔር ይህችን ዓለም ተዋት ይህችን መሬት ካቡነ ማስያስ ጋር እንዲሠሩ በሰማይም በርሳቸው ጋር ለማረፍ ሂዱ ተብሎ ያባ ያዕቆብ ገድል ተጽፏል) በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈጸመውን ግፍ ሁሉ ልዑል እግዚአብሔር አይመለከትም ማለት ነው ይህ ስብከት ለጋሎች ብቻ በጋልኛ ቢነገር ጋሎች ይህን ስብከት ቢቀበሉ የተገባቸው ነው። በክርስቲያን አገር ተወልደው ባ፺ ቀናቸው ክርስትና ተነስተው በተማሪ ቤት ካደጉ በኋላ እንደገና በገንዘብ እየተባበሉ ሃይማኖታቸውን የሚለውጡ ሰዎች መልካም አደረጉ ለመባል የሚአስደፍር አይደለም ፩ድ እናት ከወለደቻቸው ልጆች ውስጥ አንዱ ከእናቱ ጀመኛ ጋራ ወዳጅ ሲሆን በበዓልም አብሮ ሲውል የወንድማማቾች መለያየት ለእናት ሀገር ዋና ጉዳት ስለሆነ ነው። ምክንያቱም ወገንና ወገን ሲለያይ የሀገርና መንግሥት እንደምትጠፋ ማስረጃ ማቴዎስ ፲፪ ፳፭ መንግሥትም ሀገርም ቤትም ቢሆን በየራሱ የሚለያይ አይቆምም አለ ፳፮ እንደዚህስ ሰይጣን ሰይጣንን ካወጣው የሰይጣን መንግሥቱ እንደምን ትቆማለች አለና የሰይጣን ኅብረት ኅብረት እንዳላቸው ሰይጣኑ ሰይጣኑ አያስወጣውም ብሎ መለሰላቸው የመተባበር ነገር በአጋንንትም እንኳ መኖሩን ማስተዋል አለ። ይህም የሰይጣናት መንግሥት በእግዚአብሔር ስም የሚፈርስ መሆኑን መገንዘብ ነው በሮማ ልዑካን ረቂቅ ተንኮል የኢትዮጵያ ኃይል እየደከመ በሄደ ጊዜ ቱርክ ግብጽን በመያዙ ጉልበት ስለተሰማው የግብጽን ወታደር እየሰበሰበ መንግሥቱን ወግቶ በጭራሽ እጅ ለማድረግ ብዙ ጊዜ መሞከሩን ታሪክ ይነግረናል ይህንንም ከማድረጉ አስቀድሞ ኢጣልያኖች በኢትዮጵያ ላይ እንደሚሠሩት ስብከት ዓረቦችም ነጋዴ እየመሰሉ እየገቡ የስልምና ሃይማኖት እያስተማሩ ውስጥ ለውስጥ ብዙውን አገር ያረብን ፊደልና የቱርክን ዓላማ እያሳዩ አስለምደውት ስለ ነበር። በዚያ ጊዜ ያረብ ትምህርት ተቀብለው የነበሩ አገሮች ፩ኛ ምጽዋ ፪ኛ ሐሰብ ፫ኛ በርበራ ፬ኛ መቅደሾ ፭ኛ ሐረር ፮ኛ ከረን ናቸው እነዚህን ሁሉ ዓረቦች ሰው እየሸጡ ከተማውን አስፋፍተው ስለተቀመጡ ሃይማኖታቸውን ለውጠው የቀሩ አሉ የእስላም ጦርነት የተነሱባቸው ጊዜዎች በግራኝ ሙሐመድ ፩ኛ ፪ኛ በኑር አህመድ ፫ኛ በዘመነ መሳፍንት በራስ አሊ ጊዜ በቱርክ ጦርነት አድርጎ አጼ ቴዎድሮስ በልጅነታቸው ልጅ ካሣ ሲባሉ ታላቅ ጀብዱ ያገኙበት ፬ኛ ባጼ ዮሐንስ በሺ፰፻፷፮ ዓ.ም እስከ ትግሬ መሐል ጉንዲ ጉንዲ ድረስ ብዙ የጦር ሠራዊት አስከትቶ መጥቶ አጼ ዮሐንስ አፈር አስግጠው እንደመለሱት ፭ኛ በሺ፰፻፷፰ ዓ.ም ጉራዕ ከሚባል ቦታ ላይ እንደዚሁ ከተቀመጠበት ምሽግ ውስጥ ዓመድ አድርገውት

## ሐ እኁድ

ያመለጠው እየበረረ ምጽዋዕ ገብቷል እንደዚህ ሆኖ እያፈረ ከተመለሰ በኋላ በመካከሉ ሱዳን ተነሥቶ የቱርኩን ሠራዊት መዘዋወሪያ ከለከለውና በፖለቲኩ እንግሊዞች ስለ አሉበት እንግሊዞች እንደገና ከቱርኮች ተስማምተው በሱዳን አገር የተከበቡትን በቱርክ የሚመሩትን ግብጻውያን የሚሄዱበት ምንገድና ሰው አድርገው አጼ ዮሐንስ ምንገድ ሰጥተው ስለ አስተላለፉ ሱዳኖች አጼ ዮሐንስን የሚጠሉበት ቂም ተዠመረ ቱርክም በግብጽ ላይ ሱዳንንና ኢትዮጵያን ጨምሬ እይዛለሁ ሲል በመካከል ገንዘብንና ጉልበትን ስለጨረሰ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋራ ተመሳጥሮ ግብጽን ለእንግሊዝ

መ ሊለቅ ተዋውሎ የራሱን ጠብ ለሱዳን አጋብቶ ሲሄድ ከላይ በተቆጠሩት ከተሞች የነበሩትን ወታደሮቹን ሲያነሳ ውስጠ ነገሩን እርስ በርሳቸው ስለሚተዋወቁ ሐረርን ብቻ አጼ ምኒልክ በቶሎ ይዘው ሲያስቀሩ የቀሩትን እንግሊዞችና ኢጣልያኖች ተከፋፍለዋቸዋል አጼ ዮሐንስ ከቱርኮች በተስማሙበት ስምምነቱን ከሱዳኖች ጋር አድርገውት ወደ ሱዳኖች የዞረውን የጦርነት ኃይል በዠመሩት በኢጣልያኖች በኩል አድርገውት ቢሆን ኢትዮጵያን ይህን ያህል ጉዳት ባላገኛትም ነበር እርሳቸውን ከሱዳን ያጣላ የውጭ ወዳጅ ለራሱ ጥቅም የሆነውን አሳብ በመቀበል ነው አሁንም ይህን እንቅፋት ማሳብ የተገባ ነው። አጼ ዮሐንስ የእንግሊዞችን ምክር ባይሰሙ አጼ ምኒልክ የኢጣልያኖችን ስብከት ባይከተሉ ኢትዮጵያ እንደዚህ አትሆንም ነበር። ያጼ ዮሐንስና ያጼ ቴዎድሮስ የፖለቲክ አመራር ፩ ሆኖ ከቆየ በኋላ በመጨረሻው ተለያየ ፩ድ ሆኖ የታየበትም አጼ ቴዎድሮስ በነገሡ ጊዜ ኢትዮጵያን ፩ ለማድረግ ሲፈልጉ አስቀድሞ የሕዝቡ ሃይማኖት ፩ድ እንዲሆን ከአባ ሰለማ ሃይማኖት የወጣውን እቀጣዋለሁ የሚል አዋጅ ባስነገሩ ጊዜ በአካለ ጉዛይና በምጥዋ የካቶሊክን ሚሲዮን የሚመራው ጃስኮቢ ጃውስቲኖ ዲ. ዶኮቢስ የሚሉት የኢጣልያ ተወላጅ ሚሲዮናዊ ነበር ከሱም ጋር በካቶሊክ ሃይማኖት የተስማሙት አባ ገብረ ሚካኤል አጼ ቴዎድሮስ ሃይማኖቴን ይዘህ ካልመጣህ ካገሬ ከነሰውህ እንድትወጣ ካሉ በኋላ በዚሁ ሥራ የተገኙ ሰዎች ቅጣት ሳይገኛቸው እንዳልቀረ ታሪክ ይነግረናል። ያባ ገብረ ሚካኤል ታሪክ አጼ ቴዎድሮስ የሮማ ወርቅ አታሎህ እንደሆነ እኔ አብልጬ ልሰጥህ ወደ ጥንት ሃይማኖትህ ተመለስ ቢሉት አልመለስም ስላለ እሥራት ፈርደውበት እንደታሠረ ስለሞተ የሞተ በ፲፰፻፶፪ በፈረቀኑውና በሽ፱፻፲፱ ዓ.ም ፲፩ኛው የሮማ ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳት የሃይማኖት ጀግና ለሆኑት ኢትዮጵያዊ አባ ገብረ ሚካኤል በቅዱስ ጴጥሮስ መላው ዓለም ብፁዕ እያለ እንዲያከብራቸው አዘዙ ክብሩም በጣም ከፍ ባለነው የሚል ጽሑፍ ከነሥዕሉ ይገኛል ይህን ረቂቅ ስብከት መመልከት ነው።

አጼ ቴዎድሮስን በዚህ ምክንያት ካቶሊካዊት ውሥጥ ለውሥጥ እየሰበኩ ሕዝቡን እያሸፈቱ አበሳጭተው እስከ ሞት የደረሱ ሚሲዮኖች መሆናቸውን በሙያ መቁጠሪያ መጽሐፋቸው ይገኛል ቱርኮችና የሮማ ሚሲዮኖች ውስጠ ሥራቸው ፩ድ ስለ ነበር በቴዎድሮስ ፩ድ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ ብቅ ለማለት አልቻሉም። የሮማ ልዑካን በሌሎችም ነገሥታትና መሳፍንት እየገቡ ማጋደል እንደ ተለመደው የሚሠሩትን ለመግለጽ የደጃች ንጉሤና ያባ ያዕቆብ ታሪክ በኋላ በሰፊው ይመጣል አጼ ዮሐንስም እንደዚሁ የኢትዮጵያ ፩ድነት እንዲጸና በሃይማኖት ሕዝቡን ፩ድ አደርጋለሁ

# ሑ ሰኑይ

ብለው እንደተነሱ ሕዝቤ በሃይማኖት እርስ በርሱ ሲለያይ በማነኛውም ነገር የተከፈለ ይሆናልና ብለው ሚሲዮናውያንንም ከኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን አሰብስበው ከሸዋም አባ ማስያስን ከነተከታዮቻቸው አስመጥተው ፩ድነት አድርገው ምን ልታደርጉ ወደ ኢትዮጵያ መጣችሁ ብለው ቢጠይቋቸው ሚሲዮናውያኑ ወንጌል ልንሰብክ አሉ አጼ ዮሐንስም ወንጌል ፩ድ ነው እግዚአብሔርም ፩ድ ነው። እኔም ሕዝቤን ለመስበክ የሚበቁ ጳጳሳት አሉኝ ለማን ትሰብካላችሁ አሏቸው እነሱም ይሁዲዎችንና እስላሞችን እናስተምራለን ብለው ቢመልሱ ወደ ኢትዮጵያ ስትመጡ ኢየሩሳሌምን የአይሁድን ነገር ግብጽንና ሊብያን የእስላሙን አገር እንደምን ዘላችሁ ወዲህ መጣችሁ አሁንም እኔ ለሀገሬ ሕዝብ የጅ ሥራና ጥበብ የሚአስተምሩ ሰዎች እቀበላለሁ እንጅ እናንተን አልፈልግምና አገሬን ልቀቁልኝ ብለው ገሚሶቹን በመተማ ገሚሶቹን በምጽዋ ሰደዷቸው እንደዚሁ ይሁዲዎችንና እስላሞችን በግድ ክርሥትና ተነሡ እያሉ እንደ ያዙ ከዚሁ ውስጥ ወደ ውጭ እየሸሸ እየሄደ አጼ ዮሐንስን የሚጎዳ ጠላት ፈላጊ ለመሆን የተነሳው በዚህ ምክንያት ነበር ከላይ ተጽፎ እንደሚገኘው ከኢትዮጵያ ውጡ የተባለበት መዝገብ ቁጥሩ ቢበዛም እነሱ እየተዘዋወሩ ሥራቸውን ከመሥራት አቋርጠው አያውቁም ከዚህ በኋላ ባጼ ቴዎድሮስና በደጃች ንጉሤ ይሠሩት እንደነበረው ባጼ ዮሐንስና ባጼ ምኒልክ ለመሥራት ወደ አንኮበር ቆላ ተቀምጠው ባጼ ምኒልክና ባጼ ዮሐንስ መካከል የነገር ተንኮል

የሚፈጠርበትን ዘዴ በማደራጀት እንቁላል እየተመገቡ ይቀመጡ ዠመሩና ያጼ ምኒልክን ልብ ለመያዝና ካጼ ዮሐንስ የተለየ መሆኑን ለመረዳት ያሰናዱ ዠመር አጼ ምኒልክም ወደር ሮማ መንግሥት የሙተዋወቅያ ደብዳቤ እንዲጽፉ ያስቸግሯቸው ጀመር። ምክንያቱም ወደ ሮማው ንጉሥ ደብዳቤ የጻፉ እንደሆን የሮማው ንጉሥ ቁጥር የሌለው መሳሪያ ይስጥዎና በዚያ መሳሪያ ጠላትዎን ድል አድርገው ኢትዮጵያን በያዙ ጊዜ ሁለታችሁ ወዳጆች ትሆኑና በፍቅር የንግድ ውል ተዋውላችሁ በሰላም ለመኖር ትችላላችሁ እያሉ ነበር እንደዚሁ እያሉ ያጼ ምኒልክን ልብ ከያዙ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት እግራቸውን የሚአቆሙበት መሬት ለማግኘት ጁሱፒ ሳፒቶ የሚባለው አላዛሪስ ሚሲዮናዊ የወደብ በር ለመግዛት ኢብራሂም ሐሰን መሐመድ ከሚባለው ከአሰብና ከራሄታ ሡልጣኖች ጋር ተነጋገረ። እነዚህም ሡልጣኖች በዚህች በቁራጭ ቦታ ገብቶ ወደፊት የሚሠራውን ባለማወቅ ፈቃዳቸው መሆኑን ገለጹለት ሚሲዮናዊውም በፍጥነት ወደ ኢጣልያ ከተማ ሄዶ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ በመርከብ ሸቀጥ እያመላለሰ ከሚአስነግደው ሩባቲኖ ከሚባለው ማኅበር ፕሬዝዳንት ጋር ተነጋግሮ ነገሩንም የኢጣልያን መንግሥት ስለሚደግፍ ማኅበሩን ደስ ስለ አሰኘ ፰ሺ ፩፻ ብር ሰጥተው ያንኑ ሚሲዮናዊ ወደ አሰብ መልሰው ላኩትና እንደ ደረሰ ከሡልጣኖች ጋር ተገኝቶ የግዥውን ጉዳይ ተነጋግሮ ከጨረሰ በኋላ ፯ ኪሎ ሜትር ከባሕሩ ዳር ያለውን መሬት በ፰ሺህ ፩፻ ብር መግዛቱን ለሩባቲኖ በመርከብ ዕቃ እያመላለሰ በሚነግደው በማኅበሩ ስም ተፈራረመና ወዲያው ሡልጣኖቹ ገንዘቡን ተቀብለው በማግሥቱ ስለ ደስታው ፳፩ ጊዜ መድፍ ተኰሱና የኢጣልያን ባንዲራ ተከሉ ይላል ከዚህ በኋላ ፲ ዓመት ያህል በማኅበሩ እጅ ከቆዩ በኋላ የኢጣልያ መንግሥት ለማኅበሩ ፩፻፲፮ ሺህ ሊሬ ከፍሎ በጭራሽ ከማኅበሩ ወስዶ የጦር ሠራዊቱን ከኢጣልያ መንግሥት እያመጣ አስፈረበት ከዚህ በኋላ በዚያ በኩል የነበሩትን ደሴቶች ሁሉ እያሰፋ ለመያዝ ቻለ እነዚህ የሮማ ልዑካን መንፈሳውያን ነን እያሉ

## ሐ. ሠሉስ

መጽሐፍና መስቀል እየያዙ በአንኮበር ቆላ ሕዝቡን እያታለሉ ውስጡን እንደዚህ ያለ ሥራ ይሰራሉ ካጼ ዮሐንስ ፊት ከሸሹ በኋላ በአንኮበር ካጼ ምኒልክ ጋር ያደረጉትን ሥራ ሁሉ ከኢጣልያኖች መጽሐፍ የተገኘውን ግልባጭ ከዚህ የሚከተለው ነው። ኢጣልያኖች ወደ ኢትዮጵያ ስለ መግባት በአባ ማስያስ ስብከት እንደ አውሮፓ ቁጥር በሺ፰፻፶፪ ዓ.ም ዠምሮ የካሹር ኮንት ካሚሎ ካፄ ዮሐንስና ካ፩ድ ፩ድ የኢትዮጵያ መኳንንቶችም ስለ ንግድና መርከብ ማስኬድ ጥኑ ውል ተዋውለው ነበር ደግሞ በሺ፰፻፸፰ ዓ.ም ቤኔክዴቶስ ካይሮሌ የሚባል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከጀኖባ በሚባል አገር ተቀምጦ ትልቅ የመንግሥት ጉዳይ ይዞ የንግድ ቤተ ኅብረት ለማስፋፋት ተሾሞ ዠሮውን ጣል አድርጎ ወደ ማአንቀሳቀስ ውል እየላከ ያንጊዜ የሰላም ችሎት በጁ ነበር። ካጼ ምኒልክ በልዑካን አስተዋሽነት በመዠመሪያ ከንጉሥ ምኒልክ ወደ ኢጣልያ የተላከ ደብዳቤ።" አጼ ዮሐንስ በመቤታችን ረዳትነት የመላው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኑ። ግን ወደ አሰብ መግባትን ትጠብቅ ስለነበረች እንደ አውሮፓ ቁጥር በሺ፰፻፸፰ የኢጣልያ ሰንደቅ ዓላማ በዚያው ስፍራ ተተክላ በባሕር ደሴት ሰላይን ሊከለክል ግዛታቸውንም ሊጠብቅ ተቻለው ነገር ግን ያንኑ ሥፍራ ለመያዝ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ ተብሎ የተጻፈ መጽሐፍ ፍርድ እንዳለ የመንግሥት አሳብ መጀመሪያ ምን መሆኑ ከዚያ ዓመት እስከ ዛሬ ድረስ ምንም በግልጥ አይታወቅም ነገር ግን የመንግሥት ፩ኛ አሳብ አለመደባለቅና አለ ፩ድ መከላከያ ምሥጢር ስለተመረመረ በሰላም እየጠበቀና እየታመነ ሄዶ በዚያች ሥፍራ ብቻ የኢጣሊያ ጥቅም እንዲገኝ የተደረገ ይመስላችኋልን ያች ትንሽ ዋሻ ባረመኔ ሕዝብ የተከለለች ከለምለሚቱ ኢትዮጵያ የተለየች ብዙ ተራራና በሚአስፈራ ምድር የተከበበች ግዛቷም ለሕዝብም ደስ የሚአሰኝ ልታበቅል የማይቻላት ምድር ናት ግን የኢጣልያ ወታደር እግር በዚያው ኮሎንያ ዳር ወደ ኢትዮጵያ ምድር መውሰጃ ሆነች ያን ጊዜ ከየኔታ ሰር ሜኔታ ከፍለቶ ፖሪዞ የሚባሉ ደግሞ ሥራቸው በዚያው አገር ምክንያት የሆነ ነገር ለመመርመር ቁርጥ የሆነ ውል ለመዋዋል ችሎትዋ ለማስፋፋትና ማየት የነበረ። አሳብ አለ ፩ድ ፩ድ ንግድ ሌላ ጥቅም እንደሌላት ታስታውቅ ነበር የኢጣልያ ነጋዴዎች ግን መጀመሪያ በዚያ

መንገድ ውጭ ለመድረስ ገና እርግጡ አይታወቅም ነበር በዚህ ውል ብዙ ፍሬና እርባታ እንዲገኝ አስቦ አቡነ ማስያስን አድርጎ ካጼ ዮሐንስ ተረድቶ ከኢጣልያ መንግሥት ፩ድ ፩ድ የንግድ ሥራ ለመዋዋልና ስማቸውን ለመፈረም ጠየቋቸው ግን ያገሩ ዳኛ አዳኝ ንጉሠ ነገሥቱ ስለ አላመናቸው ፈርማዬን አልሰጥም አልዋቸው ማለት ከብዙ ዓመታት የቆንጆ ኢትዮጵያ ብዙዎቹ ጠላቶቿ በርስዋ ቀንተው እርስዋን የሚጎዳ መሣሪያ እያበዙ ስለሄዱ ከኢጣልያኖች የንግድ ሥራ ለመዋዋል ከኢጣልያ የሚመጣ ፍሬ ይቅርብኝ ብለው እምቢ አሉ ከዚህ በኋላ ኢጣልያኖች ተስፋ ቆርጠው ማንንም ማመንና ከሁሉ መደባለቅ ይቅርብኝ አሉ።

ግን ስለ ኢጣልያ መንግሥት ኮሎንያ ግዛት ፩ድ ጊዜ ተሰጥቶናልና ስለሀገር ሁልጊዜ የልጆች ደም ማፍሰስና ብዙ ልቅሶ ማድረግ ይገባል ስለምን በዚህ ነገር የሚአንቀሳቅስ ብርሃኗ ይገለጥላታል እያሉ

# ሓ ረቡዕ

ይችህን ትንሽ ዋሻ አሰብን ይጠብቁ ነበረ ንጉሥ ምኒልክ ካጼ ዮሐንስ ሸሽገው በሸዋ ሆነው ከኢጣልያ መንግሥት የተዋዋሉት ውል የሸዋ የከፋ የጋላ ሁሉ ምኒልክ ፩ኛ በልዑል የሸዋ መንግሥትና የኢጣልያ መንግሥት መካከል የማይነቀል ዘለዓለማዊ ሰላምና ፍቅር ይሆናል ፪ኛ ከኢጣልያና ከሸዋ መንግሥት ታምኖ የተላከ ከ፪ቱ ተዋዋዮች ደብተር የተጻፈ ኮንስል ፪ቱ መንግሥታት በተዋዋሉበት ውል ሁሉ

ሊያስማማቸው ይችላል። እሱም በየቀረበበት ሥፍራ ኮንስል ተብሎ ይጠራል ስለ ንግድ ዋንነት ወደ ሁለቱ አገሮች መጥተው በየተቀመጡበት ቦታ ነጋድራስ ወይም ኮንስል ተብሎ ይጠራል።

በሕዝብና በመኳንንት ደግሞ እንደ አገር ሥርዓት ሊከበሩ ይገባቸዋል ከርሳቸው ጋርም የሚኖሩ ሰዎችዎ ፩ድ ኃጢአት ቢያደርጉ እንዳገር ሥርዓት ልማድ ይቀጣሉ ፫ኛ የሸዋና የኢጣልያ ሰዎች ሁለታቸው በትክክል በነፃነት ወደ ሸዋና ወደ ኢጣልያ አገር ሊመላለሱ ይችላሉ በምድርም ሆነ በባሕር ለመንግሥት የሚጠቅም የንግድ ሥራ ስለ ሠሩ በሆነው ነገር ሁሉ በእነሱ መንግሥት ሥልጣን ይጠበቃሉ

፬ኛ የሸዋ ሰው ወደ ኢጣልያ የኢጣልያ ሰው ወደ ሸዋ በነፃነት እየተመላለሱ ትክክል እንደባላገሮች በሥርዓት እንዲከበሩ በሁለታቸው አገርም የንግድና የአትክልት ሥራ ሊሠሩ የጥበብ ሁሉ ትምርት ሊማሩ ሕግ አይከለክላቸውም ፭ኛ በሸዋ አገር ሌላ ሃይማኖት እንዲያስተምሩ ክልክል ነበረና አሁን ሁለቱ አገሮች ያለመፍራት ነፃነት የሃይማኖት እውነተኛ ትምርት እንዲአስተምሩ በትልቁ መንግሥት ሥልጣን በግልጥ ተፈቅደዋል ፮ኛ ፩ የኢጣልያ ሰው በሸዋ አገር ቢሞት አገር ገዥው እንደ ኢጣልያ ኮንስል ሐሳብና ፈቃድ ገንዘቡን ሁሉ በጥንቃቄና በፍጥነት ቶሎ ብሎ ይጠብቃል የዚያን ሰው ገንዘብ ከኢጣልያ መንግሥት ታውቆና ታምኖ የተላከ ሰው ሊወስነው ይችላል ፯ኛ እስካሁን ድረስ ኢጣልያ ወደ ሸዋ ለመመላለስ ችግር እንደሆነ የታወቀ ነውና አሁን በዚሁ ውል ንጉሥ ምኒልክ ከኢጣልያ ወደ ሸዋ ባገር ውስጥ ልንመላለስ ፈቅደውልን ማለት እየተማማነ የንግድ ሥራ እንሠራለን ለዚሁ ኅብረት የንግድ ግንኙነት የሚሆኑ መሣሪያና የነጋዴዎች ደሞዝ የሚአስብ በገበያም ዋና የሚሆን ነጋድራስ ኢጣልያ ይሆናል ፰ኛ የኢጣልያ ነጋዴዎች በሸዋ በር ሲገቡና ሲወጡ በአሰብም እንኳ ምንም አይከፍሉም ፱ኛ ሁለቱ ወገኖች በተዋዋሉበት ነገር ሁልጊዜ በንግድ የሚመጣላቸው ጥቅም እንደምንና ስንት እንደሆነ የሳቸውስ ስንት ገንዘብ እንዳለ ያውቃሉ የሸዋ ንጉሥ የነበራቸውን ጥቅም የኢጣልያም ንጉሥ የአሰብ በራቸውን ጥቅም ገልጠው እንዲአስታውቁ ማለት ነው። ደግሞ የኢጣልያ መንግሥት ኮሎኒያና የባሕሩ አገር ሁሉ ሰው እንዳይጎዳ በጥንቃቄ ይጠብቃሉ የሸዋ ንጉሥ ነጋዴዎቹን እስከ ባሕር ዳርቻ እየላከ ኪራያቸውንም እየሰጠ ያገሩን ዋና ምንገድ በመሳሪያ ይጠብቃል ፲ኛ ከዚህ በኋላ የሸዋ መንግሥት ኢጣልያኖች በሸዋ መካከል ከ፩ዱ መንደር ወደ ፩ዱ መንደር ሲመላለሱ ሳሉ ከባላገሮቹ ፩ድ ሰው እንዳይጎዳቸው

ይጠብቃል። በድንገት የተጎዳም እንደሆነ በሚገባ ሥርዓት ነገራቸውን መርምሮ ያድናቸዋል። እርሱም እስከ ሐውሳ ሡልጣን ሙሐመድ አንፋሪ የሚጎርፍ ያለ ወንዝ ያጼ ምኒልክ ውል ያለበት ሁሉ ሊከለክል በዚሁም ነገር ፩ድ ፩ድ ያመት ጥቅም ለመያዝ ወይም

## ሔ ኀሙስ

ለኑርዋቸው ፩ድ ግልጥ ሥራት አድርጎ በደንከሎችና በሱማሌ ያለ መሐከለኛ ምንገድ እየጠበቀ የሁለቱ አገር ዋስ ሆኖ የደኅነታቸውን ሊአረጋግጥ እሽ አለ ፲፩ኛ የኢጣልያ መንግሥት የሸዋ ሰዎች ወደ አሰብ በመጡ ጊዜ ለማረፊያና ሁልጊዜም የሚቀመጡበት ቤት ለመሥሪያ ፩ድ ቦታ ይሰጣቸዋል ፲፪ኛ የሸዋ መንግሥትና በኢጣልያኖች መካከል ገብቶ በነገራቸው ሊፈርድ ምንም አይችልም። የኢጣልያኖች ነገር ሁልጊዜ በኮንስላቸው ወይም በተከታዩ ይፈረዳል ሲፈረድ ሳለ ግን አገረ ገዥ በፍርድ ተቀምጦ ነገሩን እየጠበቀ ይፈርዳል። በኢጣልያኖችና በእንግዶች ሰዎች መካከል የተገኘ ነገር ደግሞ እዚያው ያለ ኮንሲል በሸዋ አገር ይፈርደዋል የእንግዶች ኮንስል ቢኖር ግን በኮንሲሉ ይፈረዳል ኮንሲል የሌለው ግን በኢጣልያ ኮንሲል ይፈረዳል

፲፫ኛ የሸዋ መንግሥት በኢጣልያ መንግሥት የተሾመ የአሰብ ገዥ ተፈቅዶ ወደ አውሮፓ መንግሥት ለመተዋወቅና ፩ድ ፩ድ ዕቃ ለመግዛት ደብዳቤ ሊጽፍ በፈለገ ጊዜ መጀመሪያ በአሰብ ላይ ለተሾመው የኢጣልያ ኮንሲል አታውቆ ይጽፋል። ስለምን በላይ እንደተደረገ ከሸዋ መንግሥት የተላከ ደብዳቤ በመንግሥታት ሁሉ የታመነ ይሆናል። ማለት በኢጣልያ ኮንስል ተመሥርቶ በሥልጣኑና በፈቃዱ እንዲስማማ ነው። የሸዋ ባላገሮችም ትክክል እንደ ንጉሣቸው ፩ድ ነገር ወደ አውሮፓ ሊሰዱ በፈለጉ ጊዜ መጀመሪያ የኢጣልያ ኮንስልን ጠይቀው በሥልጣኑና በጥግነቱ ማስመጣትና መስደድ ይችላሉ። በሄዱበትም አገር በኢጣልያ ሥልጣን ይጠበቃሉ ፲፬ኛ ሁለቱ አገሮች በንግድ እየተመላለሱ በመልእክት እየተስማሙ ለሀገር ልማትና ፍቅር ያረባሉ። ከዚያ በኋላም ከ፪ቱ ፩ኛዬቱ የበለጠ ፩ድ ፩ድ የጥቅም ዕቃ ፩ኛዬቱ ትሰጣለች ወይም የተከለከለ መሣሪያ ዓይነትና እሱንም የመሰለ የንግድና ሌላም የሚጠቅም ክቡር ዕቃ ያለችግርና አሳብ ከ፩ዱ አገር ወደ ፩ድ አገር መተላለፍ ይችላሉ ፲፭ኛ የኢጣልያና የሸዋ መንግሥት የሚአመጣቸው ፩ድ ፩ድ ነገር የተገኙ እንደሆነ ወንድሞቻቸው ነጋዴዎች ሊገላገሉ የማይቻል እንደሆነ ነገራቸው በሥርዓት ወደ መሐከለኛው ዳኛ ትቀርባለች እሱም ፪ቱን ያስቃርታቸዋል ወይም ፪ቱን ሥልጣን ወዳለው ዳኛ ገብተው በዚሁ በ፪ቱ በታወቀና በታመነው መሐከለኛው ዳኛ ገብተው በዚሁ በ፪ቱ በታወቀና በታመነው መሐከለኛ ዳኛ በፈረደው ይቆማል ፲፮ኛ ያሁኑ ውል በኢጣልያ ቋንቋና በሐበሻ ቋንቋ ተጽፎ ይኖራል ፪ቱም ሰነድ በ፪ቱ ቤተ መንግሥት ይቀመጣል። የሁለቱ ነገር ሹማምንት ይህንኑ ሰነድ ይዘው በሆነው ነገር አቤቱታ በፍጹም እየተስማሙ በትክክል ነገሩን በሰላም ማቆም ይችላል ፲፯ኛ ይኸው ውል ከተጻፈበት ከ፲ ዓመት በኋላ ከ፪ቱ መንግሥት ፩ዱ ለማሳደስ በፈለገ ጊዜ ከ፩ ዓ፡ አስቀድሞ የፈለገውን ነገር ገልጦ ላ፩ኛው ያስታውቃል ዓመቱም በተጨረሰ ጊዜ ፪ቱ መንግሥታት ነገሩን መርምረው ሊያድሱ ይችላሉ ፲፰ኛ ይህ ውል አሁን በዚህ አገር። ሁሉ ታውቋልና እንደ ተቻለው በቶሎ ወደ ሮማ ይታወቃል ጥር ፲፬ ፲፰፻፸፫ በኢትዮጵያ ቁጥር የልዑል ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ ፊርማ በአንኮበር ተፈርሞ መጣ ስለ እርግጥነቱም ወደ ሮማ በቶሎ እንልካለን እንደ አውሮፓ ቁ ፳፩ ማጅዮ ፲፰፻፹፫ ዓ.ም ከልዑል የኢጣልያ መንግሥት የተላከ ጴጥሮስ አኖሊ በአኮበር ፊርማው ፈርሞ ሰጠ አጼ ዮሐንስ ደግሞ ፲፰፻፹፬ ዓ.ም በፈረንጅ ነው። ሥልጣናቸው እስከ ባሕረ ኤርትራ ዳርቻ ዘርግታ ስለነበረች ከሙሴ ኪዋት የባቡር አለቃ በምጽዋ ላይ በእንግሊዝ

# ሕ ዐርብ

ግርማዊት ንግሥትና በኢትዮጵያ ስም በኤድቶ አገር ያለድንቁርናና ድኅነት ወደ ትልቅ ልማትና ሥልጣኔ ለመውጣት በንግድ ተስማምተው እንዲኖሩ ጥኑ ውል ተዋዋሉ ይልቅ የምጥዋ ከተማ ከቱርክ ቀርታ ልትታዘዝ ነበር ኢጣልያኖች ወደ ምጽዋዕ መግባት የእንግሊዝ ኮንሲል ከኢጣልያ ተስማምቶ ምጥዋን ለመያዝ ፍሬና ጥቅም ያለው ምክር ሰጣቸው ንጉሥ ምኒልክም በሸዋ ሆኖ በሚአስደንቅ ምልክቱ ምጽዋን ለመያዝ ነገሩንና ምክንያቱን እየገለጡ ስለሚሰጧቸው በነዚሁ በ፪ቱ ሰዎች ምክር ምጥዋ ባ፳ የካቲት ፲፰፻፹፭ ዓ.ም ባውሮፓ አቆጣጠር ከኢጣሊያ ሥልጣን ተያዘች። በኮነነሉ ሰላታ የሚታዘዙ ፩ሺ ወታደሮች ከኢጣልያ ወደ ምጥዋ በመርከብ ተጭነው የመጀመርያ መምጣታቸው ሆነ በቱርክ ኮንስል አጠገብ የኢጣልያ ባንዲራ ተተከለች። የኢጣልያ መንግሥት በኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ ገብቶ ግዛት ለመያዝ እጅግ ምኞት ነበረው የንጉሠ ነገሥት አማካሪዎች ግን የኢጣልያ አሳብ በቶሎ አወቁና ጃንሆይ ይህች ብቻ አይደለችም የምትያዘው ኢትዮጵያን ሁሉ ለመያዝ ይሰናዳሉ እያሉ ያስቸኩላቸው ነበር በዚህ ጊዜ ራስ አሉላ ወደ ቱርክ ኮንስል ጸሐፊ ማርኮፖኡሉበዬ ለሚባል የጻፉት ደብዳቤ ክቡር ሆይ ስለምን እናንተ ኢጣልያኖችን ከምጥዋ አታባርሯቸውም በኮዲፏ አሳብ እንደሆነ በሐበሻና በምጥዋ መካከል ባለ መንገድ እኔ አደፈርሰው ነበር ስለምን እሳቸው በዚህ ስፍራ ላይ ይጠብቁናል። እናንተስ ስለምን ለነሱ ፈቃድ ሰጣችኋቸው። ይህ አገር ዋና የሌለበት ምድር ነውና በርሱ ላይ ሊቀጡ ይችላሉ ብላችሁ ይመላችኋልን ያች ሥፍራ የኢትዮጵያ ግዛት እንደሆነች ኢጣሊያኖች በዚች ሥፍራ ሊቀመጡ ፈቃዳችን እንዳልሆነ በንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ስም ሆኘ አስታውቅሃለሁና ወደ ሀገራቸው ይመለሱ ራስ አሉላ የሐማሴን ገዥ ፩ ነሐሴ ፲፰፻፹፯ ዓ.ም በፈረቁ ነገር ግን በንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ዘንድ ታውቅ ስለነበረ ዠኔራል ፖዓሊን እንደ አሳቡ ጥሎ ለመውጣት አልተቻለውም ነበርና እስከ ጊዜው ሠሐጢን ዊንዓ በሚባል አገር ሰፍሮ ነበር እንግሊዝ ከኢጣልያ ተማክሮ አጼ ዮሐንስን ለማታለል ተልኮ መጣ አጼ ዮሐንስ ግን ከኢትዮጵያ ምድር ምንም ፍርፋሪ ለባዕድ እንዳይሰጥ ቁርጥ የሆነ ፈቃድ ነበረው ስለእናቱ ኢትዮጵያም ሊሠዋላት የተሰናዳ ነበርና የእንግሊዝ መልእክተኛ ምንም የፖለቲክ መግቢያ ሳያገኝ ቀረ ኢጣልያኖችም በምጥዋ በኩል እየተለማመጡ መቆየት እንጅ ወደ ላይ ለማለፍ በጥኑ ተከለከሉ ነገር ግን ዠኔራል ማርዛኖ በምጥዋ ሆኖ ወደ አጼ ዮሐንስ መልእክቱን እየጻፈ ማመላለስ ጀመረ ደብዳቤ ማመላለሱም ወደ ደጋው ኢትዮጵያ ሊወጣ ተስፋ አልነበረውም አሳቡ ይችኑ ምጥዋን ብቻ ለመያዝ ነበር። ስለምን ያንጊዜ ዠኔራል ማርዛኖ ከነወታደሮቹ የሚቀመጥበት ሥፍራ አጥቶ ነበር ግን ከኢጣልያ መንግሥት የተላከ ኮንት አንቶሊኒ በሸዋ ሆኖ ብዙ የፖለቲክ ሥራ ይሠራ ነበር። ከዚህ በኋላ አሜራልዮ ከዮሚ የሚባል ፷፻ ወታደሮች ይዞ ወደ ምጥዋ መጣና በምጥዋ የሚቀመጡትን ሕዝብ በዓረብ ቋንቋ እያናገረ ዓዋጁን ለፈለፈላቸው። ወደ ሠሐጢና ወደ አረፋይሌ ወደ ተደዓሊ ሊጠብቁ ከኢጣልያ የመጡ ወታደሮች ድምር ፲፪ ነጮች ነበሩ ከምጥዋ እስከ ሠሐጢ ፳፯ ኪሎ ሜትር ነው ከአረፋይሌ እስከ ምጽዋም ፳፯ ኪሎ ሜትር ነው ማጀር ቦረቲ ከ፪ት ኩባንያ ነጮችና ከ፫፻ የተጠራቀሙ ሰዎች ጋር ሠሐጢን ይጠብቅ

# ሖ ቀዳም

ነበር ኮሌኔል ዶክተርስ ቶፎሪስ ደግሞ ካ፫፻ ጀግኖች ወታደሮች ጋር ተደአሊን ይጠብቅ ነበር የቀሩትም ከነጄነራላቸው አረፋይሌንና ምጥዋን ይጠብቁ ነበር ንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ የተደረገውን ሁሉ ከሰሙ በኋላ ፩ድ የኢጣልያ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይገባ እነዚህን ጄኔራሎች እንዳይቀበሏቸው አዋጃቸውን በግልጥ እየለፈለፈ ኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ በጥኑ ከለከሉ እምቢ የሚሉ እንደሆነ ግን ራስ አሉላ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ሆኖ ከምእንኩሎ ከሁምብሌ ከአረፋይሌ ከሠሐጢ ጨርሰው ሊአባርሯቸው ተወሰነ ያጼ ዮሐንስ መልእክት ይድረስ ለጄኔራል ጆን እናንተ ባለፈው ዓመት ያለፈቃድ በዊዓ ላይ ሰፍራችሁ ነበር ዘንድሮም ለማረድ እስከ ሠሐጢ መጣችሁ

ሲሉ እሰማለሁ አሳባችሁስ እንደ ምን ነው ይህ መሬት አገሬ ይመለኛል እናንተ ግን እንደ እንጀራ ልትውጥዋት ትፈልጋላችሁ እንደ መልእክታችሁስ ሰላም ልታደርጉ የመጣችሁ ትመስላላችሁ ነገር ግን እርድ ማረድ የምን ምልክት ነው እንደኔ አሳብ የጦርነት ነው እናንተም በዚሁ ሥፍራ ተቀምጣችሁ ብዙ መድፍና ጦር መሳሪያ የሚዋጉም ወታደሮች ትሰበስባላችሁ እንጅ ሌላ አሳብ እንደሌላችሁ አውቃለሁና የሰው ክብር ደም በምድር ላይ ማፍሰስ አይገባምና ይልቅ ወደ አገራችሁ እንድትመለሱ እለምናለሁ የኢትዮጵያ ን ነ ዮሐንስ ጥር ፲፪ ፲፰፻፹፯ ዓ.ም በፈረ ቁ መልስ ጄኔራል ጃነ ግን በዊዓ ወታደሮች ሕዝብን ሊጠብቁ ሽፍታውን ሊከለክሉ በዚያውም ስፍራ ሊቀመጡ ሽፍታውን ሊከልክሉ በዚያው ስፍራ ሊቀመጡ ፈቃዴ ነው። የኢጣልያ መንግሥት በሥርዓት ለመሄድ ሰው ማክበር ልማዱ ነው እርሱም በሌሎች ዘንድ በሥርዓት እንዲከበር ይፈልጋል እናንተ እስካሁን የኢጣልያን ትልቁን ሥልጣን አለማወቃችሁም አሁንም እንደፈቀዳችሁ ወዳገሬ ልመለስ የመንግሥቴ ፈቃድ አይደለምና አይቻለኝም ብሎ ወደ ራስ አሉላ መለሰ ጥር ፲፰ ቀን ፲፰፻፹፯ ዓ.ም ከዚህም በኋላ ራስ አሉላ ፳ሺ ወታደሮች ይዘው ጥር ፳፫ ፲፰፻፹፯ ዐ.ም በፈረ ቁ ገሥግሠው ሠሐጢ ገቡና በዚህ እርድ ውስጥ የነበሩ የኢጣልያን ወታደሮች ከበብዋቸው በ፳፯ኛው ቀን ኮነኔሎ ዶክሪስቶፎሪስ የሚባለው ፭፻ ወታደሮች ይዞ ወንድሞቹን ሊረዳ ከተደዓሊ ወደ ሠሐጢ ሲመጣ ራስ አሉላ በሰላይ ስምተው ነበርና ከመንገድ ወታደሮቻቸውን አስደብቀው ጠብቀዋቸው ወደ ሠሐጢ ሳይደርሱ ከመንገድ ላይ ተቀብለው በተዳዓሊ ወንዝ ላይ ፭፻ ወታደሮች ካ፳ ሰዎች በተቀር ሁሉንም ስለ ፈጅዋቸውና ይህ ወሬ ወደ ኢጣልያ አገር ተሰማና የሚያሳዝን ሆነ። ከሰው ሁሉ እንደ ሐበሻ ካውሬም ሁሉ እንደ አንበሳ ጨካኝ ፍጥረት አላየንም እያሉ ኢጣልያኖች በብዙ ልቅሶ ላይ ሆኑ የውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ሮባልንቴ ግን የተዳዓሊ እዳውን ለመክፈል የሚሆን የጦር መሣሪያ ሲአሰናዳ አስቀድሞ ወደ ኮንት አንቶኖሊ እንዲህ ብሎ ጻፈለት የኢጣልያ ልጆች ክቡር ደማቸው በኢትዮጵያ ምድር ከፈሰሰ አሳባችን ሁልጊዜ ኢትዮጵያን በጃችን ለመያዝ ነውና የበለጠው ነገር ማኅበራችን በኢትዮጵያ ገብታ የፖለቲክ ሥራ መሥራት ነው ይህች መልእክት የምታመጣልን ፍሬ መጀመሪያ ንጉሥ ምኒልክ ከነመሣሪያዎቹ ሁሉ እኛን ተከትሎ ካጼ ዮሐንስ መጣላቱ ነው ፪ኛ የበለጠ ነገር እርስዎ በዚያው ስፍራ ሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገና የሚደረገውን ነገር ሁሉ ለመንግሥታችን ማስታወቅ ነው አሁን በክቡርነትዎ በየጊዜው የተሠሩትን ነገሮች ሁሉ ገልጠው

# መ እኁድ

በቶሎ እንዲጽፉልኝ እለምነዎታለሁ ደግሞ ፩ድ ዋና ነገር ንጉሥ ምኒልክ ከኛ ጋራ አብሮ በእንግድነታችን ጊዜ ከንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ለመዋጋት የተሰናዳ መሆኑን ይጠይቁት ፫ኛ ከኛ ጋር ሆኖ ከተዋጋ በኋላ የሚመጣውን ጥቅምና ፍሬ የሚፈልገው እንደምን እንደሆነ ይጠይቁት ፬ኛ እኛ አጼ ዮሐንስን በግድ አስለቅቀን በኋላ በሰሜን ወገን ሁሉ ለንጉሥ ምኒልክ ትልቅ ሥልጣን ለመሥጠትና ፩ድ ፩ድ የጐደለ ነገር ለማገዝ እንችላለን አጼ ዮሐንስ እምቢ ያሉ እንደሆነ እሱ እኛን ተከትሎ በኛ ሥልጣን እንዲጠበቅ ያስታውቁት ይህን ሁሉ ነገር አስረግጠው ምላሹን እንዲጽፉልኝ እጠብቅዎታለሁ ሮበላንቴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መጋቢት ፲፩ ቀን ፲፰፻፹፯ በፈረ ቁ የሮማ ንጉሥ ወደ አጼ ምኒልክ ደብዳቤ ሲልክ ባገርና በእግዚአብሔር ፈቃድ የነገሠው ዑምቤርቶ ፩ኛ የኢጣልያ ንጉሥ ወደ ቻይ ወዳጄ ዳግማዊ ምኒልክ የሸዋ የከፋ የጋላ አገር ሁሉ ንጉሥ ጤና ይስጥልኝ ባ፬ ጳጉሜ ፲፰፻፸፫ ዓ.ም የጻፉት ደብዳቤ ደረሰኝ ልዑል ግርማዊ ያመለከተኝን ነገርም ማለት የኔ አሽከር ኮንትአንቶሎኒ እንዳሳሰበዎ ለጥቂት ጊዜ ከርስዎ ጋር መቆየቱ እጅግ ደስ አለኝ ይህ የማይነቀል ዘለዓለማዊ ፍቅራችን ሁልጊዜ እንደገና እየበዛ እየተቃጠለ እንዲሄድ ተስፋ አለኝ በእንግድነታችን እየተረዳነ እንደ እውቀታችን እየተጠያየቅነ ሁላችንም ምኞታችንን አግኝተን በሰላምና በደስታ እንድንኖር ተስፋ አለኝ ቀድሞ ከማርከዘ እንቲኖራ ብዙ እምነትና ወዳጅነት እንደነበረዎ አሁንም ከኮንት አንቶሎኒ ፍቅርም ከልዑል ግርማዎ የተላኩትን መልክተኞችዎን የኢጣልያ ሰዎች በትልቅ ክብርና በብዙ ወዳጅነት ተቀበሏቸው ወደኔም ግቢ በመጡ ጊዜ ከነሱ አብልጬ በማይረሳ ወዳጅነትና ትልቅ አጀብ ልቀበላቸው ነኝ ነገር ግን ዘንድሮ

የተደረገው ነገር እጅግ ያሳዝናል። ስለምን ያ ጄኔራል በዚያ ሥፍራ ሥልጣኔና ሰላም ለማስፋፋት የተላከ ነበር። አሁን ግን አሳቤ ቀጥሎ ለመሄድ ነውና ኮንት አንቶሎኒ እንደ ብዙ እምነትዎና ወዳጅነትዎ የምናደርገውን ነገር ሁሉ ይነግረዎታል የጻፍልንዎን ነገር ሁሉ እሙን ሰው ካልሆነ በቀር ለ፩ ሰው እንዳይነግሩ እምነትዎን እንዲያስረግጡ አደራዎን ስለምን ምሥጢር የተሰበረ እንደሆን በሰው ሁሉ ዘንድ ትገለጣለችና በሰው ልብ ያልነበረ ሐሳብ ማለት በሰው ላይ የሚሆን ጉዳት አሥነስታ ታመጣለች በክርስቲያን ሰውን ወዲያና ወዲህ እያመላለሰ የሚአጣላ ሰው በደሉ እጅግ ከፍ ያለ እንደሆነ የታወቀ ነው። (ይህ ሰውን የሚአጣላ ነገር አመላላሽ በኢጣልያ ዘንድ ክፉ መሆኑ አይታወቅም በኢትዮጵይውያን እርግጥ ክፉ እንደሆነ ክፉነቱ የታወቀ ነው) ስለ ወታደሮች ጥፋት ብዙ አያሳዝንም እነሱስ ፊታቸውን ሳይመልሱ ባሰለፋቸው ስለ አልጋቸው የተፈጁ ናቸው ነገር ግን ዘንድሮ በዓለም ሁሉ ጥር ፳፮ ቀን በምጥዋ የተጻፈብን ነገር ለኢጣልያ መንግሥት አእምሮ እንደሌለው ሆነ (አሁንስ አእምሮ ካለውማ የመንኩሴ ሰባኪ አታላይ እየላከ ራሱ አታላይ ሆኖ ወገንና ወገን የሚአጣላ በሰይጣን ረዳትነት ጉልበታም የሚመስል አሁንስ ምን አእምሮ አለው) አእምሮ እንደሌለው ልጅ አስመስሎ የሚአስነቅፈን በመሆኑ ብቻ አዝናለሁ ግን ከዚያ በኋላ ያች ሥፍራ የኢጣልያ ደም የፈሰሰባት ናትና የኢጣልያ እርስት እንድትሆን እርግጥ ነው አልሰጥም የሚል ሰው ቢገኝ ደግሞ በኢጣልያ ያለ ሰው ሁሉ እስቲ

## ሙ ሰኑይ

አልቅ ድረስ እንዲዋጋላት እርግጥ ነው ልዑል ሆይ በዚህ አገር የሚመጣ ጦርነት ይህን ያህል ይመስላል ብዬ ልገልጥልዎ አይቻለኝም ነገር ግን ለጦርነት የተሰናዱና የተባረኩ ወታደሮችዎን ይዘው ይጠብቁ ከዚያ በኩል ያሉ እንግዶች ወታደሮችዎን በጨካኝ ከዳተኛ እጅ መሥዋዕት እንዳይቀርቡ ይጠበቁልኝ። ወዳጅነታችን በኔና በርስዎ እየተጠበቀች እንድትሄድ ብዙ ተስፋ አለኝ ለመግንሥትዎ ዕድሜ እረጅምና ሰላም ይሁን። ወዳጅዎ የኢጣልያ መንግሥት ን ፩ኛ ዑምበርቶ መጋቢት ፲፩ ቀን ፲፰፻፹፯ ዓ.ም በፈረ ቁ ተማ ሮ። ከ፡ ልዑል ዳግማዊ ምኒልክ የሸዋ የከፋ የጋላ ንጉሥና የኢጣልያ መንግሥት መላክተኛ ኮንት አንቶሎኒ የተዋዋሉት ውል ፩ኛ በሸዋና በኢጣልያ መንግሥት መካከል በመኳንንቶቻቸውና በሕዝባቸው መካከል ፩ድነትና ወዳጅነት እንዳለ በሥራት ይገለጣል እነዚሁ ሁለቱ አገሮች ፩ድነት ወዳጅነት ስላደረጉ የሚአስደንቅ ነው። (እዚህ እንደ ቀልድ የመሰለ ነገር ፪ቱ አገሮች ወዳጅነት ስለሚአደርጉ ያስደንቃል ተብሎ የተጻፈው አሁንም እርግጥ ያስደንቃል የሚያስደንቅ ነው)። ሥልጡንነታቸውና ጥግነታቸው በቶሎ ይታወቃል ይገለጣል ፪ኛ የኢትዮጵያ መንግሥት ለኢጣልያን መንግሥት በእንግድነታቸው በሚአስጨንቋቸው የጦር መሳሪያ እንዲረዷቸው ሥልጣናቸውንም ከፍ የሚያደርግ ሌላ ክቡር ዕቃ በየተቻላቸው እንዲአግዛቸው እሽ አሉ (ይህች እሽ አሉ የምትባ አማርኛ ሐተታዋ ብዙ ዓምድይፈጃል) ፫ኛ የኢጣልያ መንግሥት ከንጉሥ ምኒልክ ድርሻ ግዛት አልፎ እንዳይነካባቸው ግልጥ የሆነ ውል አደረጉ (እዚህ ላይ ኢጣልያኖች አጼ ምኒልክን በቀድሞ ግዛታቸው ብቻ ወስነዋቸዋል ስለዚህ በግልጥ አሉት) ፬ኛ የኢጣልያ መንግሥት ለንጉሥ ምኒልክ በሚመጣ ነገር ተስማምቶ ፰ሺ ረሚንጎት የሚባል ብረት በአሰብ በነበረው ቆንሲል አድርጎ ሰደደላቸው ፭ኛ የሸዋ ንጉሥ ይህንኑ ብረት ይዞ ለኢጣልያኖች ጥኑ ውል ተዋዋሉ ባዲሱ ከተማ አዲስ አበባ ጥቅምት ፲ ቀን ፲፰፻፹ ዓ.ም ላይ በኢት ቁ ከላይ ስለ ተጻፉ ውሎች ሐተታ ሰው ምንም አታላይ ቢገጥመው በክፉ ጐዳና ቢሄድ የተበደለ ደጋፊው እግዚአብሔር ሥራውን የሚፈታ አይደለም የኢጣልያኖችንና ያጼ ምኒልክን አሳብ መመልከትና ማስተዋል ለወደፊትም ትምርት ይሆናል ሰው ታሪክን መመልከቱ ያለፈ ነገር መሆኑን በመዘንጋት አይደለም ለወደፊቱም ይህን የመሰለ ነገር ባጋጠመው ጊዜ ነገሩን ያጠናው ይሆንና ሳይደነግጥ አስፈላጊውን ለመሥራት የሚረዳው መሆኑን በመገንዘብ ነው እንጅ በከንቱ አይደለምና ስለዚህ ያለፈም ቢሆን የሁለቱን ልብ አስተያየት ገምቶ ላንባቢ መስጠት የሚከፋ አይደለምና ከዚህ አስከትዬ የምጽፈው የኢጣልያኖች አሳብ ከላይ እንደተጻፈው በሃይማኖት ስብከት መንግሥቱንና ቤተ ክህነቱን

እንወርሳለን ብለው ሮማ ላይ ባቋቋሙት ማኅበር እየተረዱ ካጼ ገላውዴዎስ መንግሥት ጀምረው እስከ አጼ ዮሐንስ በየጊዜው ለመድከም ስለ አልቦዘኑ አጼ ዮሐንስ የእናንተ ስብከት አልፈልግምና ከሀገሬ ውጡ ብለው ካሰናበቷቸው በኋላ በአሰብ በር መጥተው አጼ ምኒልክን ተጠግተው በተለመደው መሳሪያቸው አጼ ምኒልክን ከወዳጃቸው ካጼ ዮሐንስ ልብ አካፋፈሉና ወደ ሮማ መንግሥት ደብዳቤ አስተዋውቀው ሐሰት በተመላበት ደብዳቤ

## ሚ ሠሉስ

ልባቸውን ማርከው ንጉሠ ነገሥቱ እያሉ በረቂቅ ፖለቲክ አገር ሰጥተው እስከ መፈረም ካደረሱዋቸው በኋላ ደግሞ ከንጉሠ ነገሥቱ እንዲዋጉ ፲፫ ብረት እስከ መስጠት ደርሰው ማታለያ ማቅረባቸው ተጽፎ ይታያል ያጼ ምኒልክ አሳብ አሰብን በር ብቻ ሰጥተው በዚህ እንደተወሰነው ውል የንግድ ሥራቸውን እያስፋፉ ለመቆየት ሲሉ ነበር። ይኸውም ያጼ ምኒልክ ባለተስፋነት አስቀድሞ በየገዳማቱ የታወቀ ከመሆኑም በላይ ካጼ ቴዎድሮስ አምልጠው በመጡ ጊዜ ከሸዋ ሰዎች በስተቀር የጐጃም የቤጌምድር የትግሬ የላስታ የየጁ የወሎ ሰዎች ሁሉ ተከትለዋቸው የመጡ በከንቱ አይደለምና ይህ ዋና ማስረጃ ነው። ስለዚህ አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያ ባለተስፋ መሆናቸውን የኢጣልያ ሚሲዮኖችም ያውቃሉ ግን ቢያውቁም አሳባቸው ባጭር ለማስቀረት ነበር። ያጼ ምኒልክ አሳብ መሳሪያ ስጡኝ ለማለት ወደ ሮማው ንጉሥ ለመጻጻፍ የደረሱበት መላ ኢትዮጵያን በያዙ ጊዜ ለመጠበቂያ እንዲሆናቸው ነው እንጅ በኢትዮጵያ ላይ ኢጣልያ ነግሦ እርሳቸው በውሥጥ ሆነው ለመኖር አሳብ ነበራቸው ብሎ የሚገምት ሰው ቢኖር ሰው ነው ተብሎ መልስ አይሰጠውም የኢጣልያኖች አሳብ ንጉሥ ምኒልክንና ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን በመሳሪያ እያባበልን ልብ ለልብ ከተራራቁ ከትግሬዎችም ባላባቶች ከየሀገሩም ከቤጌምርም ከማነኛውም ካጣላን በኋላ እንግሊዞች ባጼ ቴዎድሮስ እንዳደረጉት ሁሉ ብዙ ጦር አሰናድተው በድንገት አጼ ዮሐንስን ካስገደሉ በኋላ ኢትዮጵያን ጠቅልለው በያዙ ጊዜ ለንጉሥ ምኒልክ ቀድሞ ይዞት የነበረውን አገር በኛ ውስጥ ሆኖ ይገዛል በማለት ነበር ኢጣልያኖች አስቀድመው ያሰቡት ያጼ ዮሐንስ ስፍራ መያዝ ነበረ እንጅ ሌላ አላሰቡም ነበር) ምናልባት። ማንኛውም ሰው ቢነግሥ በተለመደው የፖለቲካቸው እርስ በርሱ አጣልተን ሲደክም እኛ እንገባለን በማለት ነበር በምጽዋ ምድር ላይ ጦሩን ያሰፈረ በመካከሉ እግዚአብሔር ባሰበው የደርቡሾችን ነገር ባልተሰበ አስነስቶ አጼ ዮሐንስን መተማ አውርዶ አስቀረ በመካከሉ ኢጣልያኖች ኢትዮጵያን እንያዝ እንዳይሉ በዚያ ጊዜ በጣም አልተሰናዱም ነበርና ወዲያውም ካጼ ዮሐንስ እናራርቃለን ሲሉ በቂ መሣሪያ ላጼ ምኒልክ ሰጥተዋቸው ስለ ነበረ ለጊዜው በጦር ኃይል አጼ ምኒልክን እንደማይችሉ ስለተረዱ ነው መቼውንም ቢሆን ኢጣልያኖች ውስጥ ለውስጥ ሳያበጁ በገሐድ ጦርነት ለመግጠም ስለማይችሉ አርፈው ያንኑ ውስጥ ለውሥጥ ሥራቸውን ቀጠሉ። አጼ ምኒልክም ከእግዚአብሔር የታዘዘላቸውን መንግሥታቸውን ያዙ አጼ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ባጼ ዮሐንስ ቀምበር ገብተው ተጠመዱ። (ወደ መሠረቱ እንመለስ ንጉሥ ምኒልክና ኮንት አንቶኖሊ በዚህ ውል ተፈራረሙ ከዚህ በኋላ ኢጣልያኖች ካጼ ዮሐንስ ሊዋጉ ተሰናዱና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሠሐጢንና አረፋይሌን ዊዓንን የኢጣልያ ልጆች ያለቁበትን ምድር ለመያዝ ስፍር ቁጥር የሌለው የጦር መሳሪያ ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ተበድሮ ባ፩ድ ጊዜ በጄኔራል ማርዛኖ የሚታዘዝ ፲፯ሽ ወታደሮች ላከ ያንጊዜ በኢጣልያ አገርና በአውሮፓ ሁሉ በተደአሊ የፈሰሰውን ደም ለመክፈል ሰው ሁሉ ተነሥቶ ነበር ዛሬ ኢጣልያኖች ድል ያልነሱ እንደሆነ ለአውሮፓ ሁሉ ጥቃት ነው እያሉ በአደን የነበረ የእንግሊዝ ቆንሲል ተናገረ አጼ ዮሐንስም ይህንን ሁሉ ከሰሙ በኋላ ሠራዊታቸውን ይሰብስቡ ዠመር ነገር ግን በኢጣልያ ጦርነት እንዳይሸነፉ የተመኩ ነበሩና በኢጣልያኖች ምንም ፍርሃትና ድንጋጤ

# ማ ረቡዕ

አልነበራቸውም ሳሊምቦኒ የሚባል ባጄ ዮሐንስ ወኅኒ ቤት የነበረ ኢጣልያ ከወህኒ ቤት ከወጣ በኋላ አጼ ዮሐንስ የሚአደርጉትን ነገር ሁሉ ሰላይ ሆኖ ወደ ኢጣልያ ሚኒስቴር የሚከተለውን መልእክት ጻፉለት ለክቡር ሚኒስቴር ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሚዋጉ የኢጣልያ ልጆች እንደተሰናዱ ሰምቻለሁና በሀበሻ ጦርነት ፪ኛ ፰ሽ ወይ ፲፰ሽ የሚአህሉ ወታደሮች ብቻ ሊወጋቸው ምንም እንዳይቻላቸው እርግጥ ነው አሁን ፴ሽ ወይም ፵ ሽ የሚአህሉ ጀግኖች ወታደሮች ሰብስበው እንዲአቆዩአችሁ እወቁ ስለምን አጼ ዮሐንስ ተዋግተው አገራቸውን የሚአድኑ ወታደሮች ሰብስበው የሚጠብቁ መሆናቸውን እወቁ አሁን አጼ ዮሐንስ ጦራቸውን ይዘው እስከ ባሕር ዳርቻ እስከ ቦታችን ቢገሠግሡ በፊታቸው ቆሞ የሚከልክላቸው ጦር ወዴት በተገኘ ነበር ግን እርሳቸው ይህን ስለ አላሰቡ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይገባዋል ያጼ ዮሐንስ አሳብ ስለ ወታደሮቻቸው ጤንነትና ምግብ ማለት አሁን በየሥፍራው ለወታደሮቻቸው የሚበቃ ውኃ እንዳይገኝ እያሰቡ ዝናም እስኪዘንም ድረስ በየቀኑ ሠራዊታቸውን እያበዙና እየሰበሰቡ ቆይተዋል የሐበሻ ሰው ደግሞ ጠንካራ እንደሆነ ስለምን እነሱ በረኃብና በጥም እስከ ፫ ሳምንት ጉልበታቸው ምንም የድካም ነገር አይሰማቸውም ደግሞ በመድፍና በመትረየስ ልባቸው አይደፈርስባቸውም እነሱ ያንጊዜውን በቀኝና በግራ በፊትና በኋላ እንደ እሳት ቃጠሎ እንደ ወፍ እየበረሩ የጠላታቸውን ሰልፍ ከብብ አድርገው ያለ ሥራት ነገራቸውን ባጭር ጊዜ የሚቆርጡ ሰዎች ናቸው ዋናው የክፉ ነገራቸው እንዳረመኔ አር እያሉ በሚአስደነግጥ ጕራዴአቸው የሰው አንገት ለመቁረጥ ልማዳቸው ነው ስለዚህ አጼ ዮሐንስ ያገራቸውን ጠንካራነትና ጨካኝነት ያውቃሉና ምንም በዚህ ጦርነት ፍርሃት ድንጋጤ እንደሌለባቸው እገልጥልዎታለሁ ሳሊምቦኒ ሚያዝያ ፯ ፲፰፻፹፫ ዓ.ም በፈረ ቁ (ሮማ ላይ የተመሠረተው የሚሲዮን ማኅበር ይኸውና ያፈራውን ፍሬ ያሳያል ይህ ሳሊምቦኒ የተባለው ኢጣልያ የኢጣልያን ሚሲዮኖች ከሀገሬ ውጡ ብለው እንዳይሰብኩ ካሰናበቷቸው በኋላ እንደገና ተመልሶ ሲስብኩ ስለተገኘ ታስሮ ወህኒ ቤት ከሰነበተ በኋላ እግዚአብሔርን ፈሪ በመሆናቸው ፈተው ቢለቁት ይህን የተንኮል ደብዳቤ ጽፎ በእስላም እጅ ወደ ምጽዋ ልኮ እሱ እንደ ልማዱ እየተዘዋወረ ስብከቱን ቀጠለ ባጄ ዮሐንስ አጠገብ የነበረው ሳሊምቦኒ በንጉሥ ምኒልክ አጠገብ የነበረው ኮንት አንቶሎኒ እነዚህ ብቻ የሠሩት ሥራ አይዘነጋም ነበር ለጤንነት አስፈላጊው የሰው አገር ሰው ያለ ብርቱ ጉዳይ ባይመጣ እንጅ ሌላ ነገር ባላስፈለገም ነበር አለማስፈለጉም የነዚህ ሰዎች ሥራ ብቻ መምህር ነው የሮማ የወንጌል ልዑካን እንደዚህ ጦር ሲያጋጥሙ ይገኛሉ።) ዮሐንስ መኳንንቶችና ወታደሮች ጃን ሆይ ሁላችን ወደ ምጥዋ ሄደን ኢጣልያንን ወግተን ከእናት ኢትዮጵያ ምድር ልናስለቅቀው ይታያልና እያሉ ጩኸትና ፉከራ እየጨመሩ ስለ አስቸኮሏቸው በኢትዮጵያ ልጅጆች እጅግ ደስ አላቸውና ልጆቼ ሆይ እኔም ስለ እናቴ ኢትዮጵያ ሕይወቴን ልሰዋላት ፈቃዴ ነውና እኔም ራሴ ከናንተ ጋራ እሄዳለሁ ሚያዝያ ፫ ቀን ፲፰፻፹፫ ዓ.ም በፈረ ቁ በኢት ፲፰፻፹ ዓ.ም ከያገሩ መኳንንቱንና ወታደሩን ሰብስበው ወደ ጦርነቱ በምጥዋ ምንገድ አቅንተው ሲገሠግሱ ጥኑ ዓዋጅ አሳለፉ ያጼ ዮሐንስ የፊተኛው ጦር ኢጣልያኖች ወዳሉበት

# ሜ ኅሙስ

ሥፍራ ደረሱ። አጼ ዮሐንስም ከሠራዊታቸው ጋራ ወደ ጊንዳ የሚባል ቦታ በደረሱ ጊዜ የኢጣልያ ጄኔራልም ጠላቶቹን ለማሳየት መብረቅ የሚመስል ትልቅ ብርሃን ኤሌክትሪክ ለቀቁባቸው። ወታደሮቹ ከምጥዋ ወደ አሥመራ መንቀሳቀስ ሲሆን ማለት አፄ ዮሐንስን ፊታቸውን ወደ ደርቡሽ ሲመልሱ ነው ደበብ ካጼ ዮሐንስ ከድቶ አገማዳ ከሚባል አገር ከምጥዋ አጠገብ ተቀምጦ ሳለ ለጄኔራል ማርዛኖ እኔ ካጼ ዮሐንስ ከድቻለሁ ለእናንተ አሽከር እንድሆን እፈልጋለሁና የጦር መሳሪያ እንድትሰጡኝ እለምናለሁ። ብሎ ጻፈና ከጄኔራል ፪ሽ የሚአህል የገንዘብና የጦር መሳሪያ እንድትሰጡኝ እለምናለሁ። ብሎ ጻፈና ከጄኔራል ፪ሽ የሚአህል ገንዘብና የጦር መሳሪያ ወስዶ ነበር ማለት ከኢጣልያ

ተስማምቶ የሐበሻን ሰው ሊዋጋ ተዋውሎ ስለነበረ። ኢጣልያኖች ደበብን ፪ሽ የሚአህሉ ወታደሮች ይዘህ ወደ ጄኔራል ግባ ስለምን እኛ ከሀበሻ ልንዋጋ ወደ ሰገነይቲና አሥመራ እንወጣለን ያልገባህ እንደሆነ አንተን ከዚህ እናበርሃለን የሚል መልክተኞች ካሉበት ደበብም ከወታደሮቹ መከሮ አገራችንን አሳልፎ ከመስጠት በርስዋ ላይ ብንሞት ደማችንን ብናፈስ ይሻለናል ብለው እምቢ አሉ በሰገነይቲም ወታደሮቹን ሰብስቦ ከኢጣልያኖች ሊዋጋ ተሰናዳ ኢጣሊያኖችም ደበብ እንደ ከዳቸው አወቁና ካፒታኖ ኮርናኪያ የሚባል ከ፮፻ ወታደሮች ጋር ደበብን ለማስለቀቅ ወደ ሰገነይቲ ሄዱ ደበብም ይኸው ካፒታኖ የሚመጣበትን መንገድ ሳይል ልኮ ጠየቀና ወታደሮቹን ከሰገነይቲ አውጥቶ ይኸው ባሰጋራው በሚመጣበት ጫካ ቦታ ሰዎቹን አሰልፎ በዛፉ ውስጥ ሆኖ በጠበቀው ካፒታናም ወታደሩን ይዞ ወደ ሰገነይቲ በፍጥነት ሊገባ ሲገሠግሥ ባለማወቅ ደቡብ ወዳለበት ደረሰ። የደበብም ወታደሮች አር እያሉ በመካከላቸው ገብተው በጥይትና በጐራዴ ፈጁዋቸው ካፒቻና ኮርናኪያ ተንታፖሊ ፈረጀኒ በረሮ የሚገሉትን ፪፻ የሚአክሉ ወታደሮች ባ፩ሰዓት ፈጃቸው የቀሩትንም አባረራቸው። ድልም አደረጓቸው ይህች ቀን ለኢጣልያኖች ልክ እንደ ተደአሊ ሆነችባቸው አፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ንጉሥ ምኒልክ ከኢጣልያን ተላከ ኮንት ፔትሮ አንቶኖሊ ስለ ወዳጅነትና ስለ ንግድ በውጫሌ የተዋዋሉት ውል ፩ኛ በኢትዮጵያ መንግሥትና በኢጣልያ መንግሥት መካከል በመኳንቶቻቸውና በሕዝባቸውም በሥርዓታቸውም እምነት ተጠግተው ለሚኖሩ ሕዝብ ለዘለዓለም የማይነቀል ሰላምና ፍቅር ይሁን ፪ኛ ከ፪ቱ መንግሥታት ታምኖ የተላከ የኢትዮጵያ ሰውም ሆነ የኢጣልያ ሰው በየተዋዋሉበት ውል ሁሉ ፪ቱ መንግሥታት በዚሁ ኮንስል ተብሎ ይጠራል። እንደ አውሮፓ ነገሥታ ልማድ ተከልክሎ የነበረው ዕቃ ሁሉ እርባታ ያገኛል ፫ኛ የሆነ ሆኖ የሁለቱ ወንድሞች ተዋዋዮች የዳርቻ ሕንፃ በትክክል ያለመሳሳት በመሐከለኛ መሬቱን ሊያነጹ ይችላሉ። ፪ቱ የኢትዮጵያ ፪ የኢጣልያ ሰዎች ከየመንግሥታቸው ተልከው ለዚህ ለትልቁ ነገር ግዛት ዳርቻ ሕንፃውን እያዩ በማይጠፋ ምልክት እያመለከቱ ነገሩን ጨርሰው ወደ መንግሥታቸው ለማቅረብ ይችላሉ። ሕንፃው የሚከተል ነው። የኢትዮጵያንና የኢጣልያን ዳርቻ የሚአመለክት የደጋ ምድር ሕንፃ ካረፋይሌ ተነሥቶ እስከ ኃላይ ለሰገነይቲ አሥመራ የኢጣልያ ግዛት ይሆናል። (ለ) ከቦጎስ ወገን ያለ ዳርቻ ካሥመራ ተነሥቶ አዲነፋስና አዲዮሐንስ የኢጣልያ ግዛት ይሆናል (ሐ) ከአዲ ዮሐንስ እስከ ኢትዮጵያና የኢጣልያ ዳርቻ ነው ፬ኛ የወታደር ሥራ ሊሠሩ የማይቻላቸው የደብረ ቢዘን ግዛት ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ሆኖ ይቀራል።

## ም ዐርብ

፭ኛ ከኢትዮጵያ ግዛት ስለ ንግድ ወደ ምጥዋ የሚመጡ ነጋዴዎች የበር ዓሥራት እንደ ዕቃው ሚዛን ከ፰ ይከፋላሉ ፮ኛ የኢትዮጵያ መንግሥት ለጦርነት የሚሆን መሳሪያ ጠመንጃና ጥይት በምጥዋ እንደፈቀዱ ሊወስዱ ሊአልፉ ተፈቅዷል ነገር ግን እንደ ፍትሐ ነገሥት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አስቀድሞ የሚአስፈገው የጦር መሳሪያ የማን ዓይነትና ስንት እንደሆነ ከኢጣልያ መንግሥት ፈቃድ ለመጠየቅ ይገባዋል (እዚህ ላይ ያጼ ምኒልክ ሰዎች ከፍ ያለ ስንፍና አሳይተዋል ከኢጣልያ መንግሥት ፈቃድ መጠየቅ ይገባዋል ማለት ትርጋሜውን ባለመጠበቃቸው ነው) ይህንንኑም ጥይትና ጠመጃ ጭነው የሚወስዱ ነጋዴዎች እስከ ኢትዮጵያ ግዛት ዳርቻ በኢጣልያ ወታደሮች ተጠበቀው በነፃነት ወዲያና ወዲህ እየተመላለሱ የንግድ ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ ይህ ሥራ ለመንግሥትና ለሕዝብ ብዙ ጥቅም ነው። ነገር ግን የኢትዮጵያ ወታደሮች ጠበንጃ ይዘው ከግዛታቸው አልፈው ወደ ኢጣልያ ግዛት እንዳይመጡ ክልክል ነው።

፯ኛ የኢትዮጵያ ሰው ወደ ኢጣልያ አገር የኢጣልያም ሰው ወደ ኢትዮጵያ አገር በሆነው ነገር ሁሉ ገንዘባቸውን ሊሸጡ ሊለውጡ ሊሰዱ ሊአከራይም ሊአስቀምጡም ይችላሉ ፱ኛ በ፪ቱ አገሮች ያሉትን ሕዝብ እውነተኛ ሃይማኖት በግልጥ ለማስተማር በሙሉ ሥልጣን ተፈቅዷል (እዚህም ላይ ያጼ ምኒልክ ሰዎች ስላስተዋሉም እውነተኛ ሃይማኖት በግልጥ ሊያስተምሩ በሙሉ ሥልጣን ተፈቅዷል ማለቱን ላስተዋለው ታሪኩ ረቂቅ ነው። እውነተኛ ሃይማኖት

ሊያስተምሩ የተባለው ከነሱ በፊት የነበረው ሃይማኖት የውሸት ወይም የጨዋታ ሆኖ ማለት ነው በግልጥ እንዲያስተምሩ ተፈቅዷል ማለቱን ከዚያ በፊት በሥውር ማስተማራቸውን (ሲገልጽ ነው ለመሆኑ አገርን ከተካፈሉ በኋላ ከወዲህኛው ውሥጥ ገብተን እናስተምር ሲሉ መስማማት ምን ያመጣው ነበር ፲ኛ የኢጣልያ ሰው ከኢትዮጵያ ሰው ጋር ቢጣላ ነገራቸው በምጥዋ አገር በኢጣልያ ባለሥልጣን ነገሩ ይጨረሳል። በኢጣልያኖችና በኢትዮጵያ መካከል የሚአጣላቸው ነገር ቢገኝ በኢጣልያ ሥልጣን ወይም በኢትዮጵያ መንግሥት በተላከው ሹም በምጥዋ ይፈረዳል። ፲፩ኛ የኢጣልያ ሰው በኢትዮጵያ ግዛት የኢትዮጵያ ሰው በኢጣልያ ግዛት ውስጥ ቢሞት አገረ ገዥው እንደ መንግሥት ሥራት ገንዘቡን ሁሉ በቶሎ ጠብቆ ወደ አገሩ መንግሥት ይልካል። ፲፪ኛ በማነኛውም ምክንያት ፩ድ የኢጣልያ ሰው የተበደለና የተገፋ እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት በቶሎ ለኢጣልያ መንግሥት ያስታውቅና ነገሩ በምጥዋ በኢጣልያ ሥልጣን ይፈረዳል። (እነዚህም ላይ ከፍ ያለ አለማስተዋል ተደርጓል በማነኛውም ምክንያት የኢጣልያ ሰው የተበደለ እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት በቶሎ ለኢጣልያ መንግስት ያስታውቅና ነገሩም በምጥዋው በኢጣልያ ሹም ይለቅ ማለት ድርብ ግፍ ነበር

የኢትዮጵያው መንግሥት ዳኝነቱን በማጣቱ ላይ በፍጥነት አቤቱታ አቅርበ መባሉ ነው።) እንደዚሁም የኢትዮጵያ ሰው በኢጣልያ ሰው ቢበደልና ቢገፋ በኢትዮጵያ መንግሥት ሥልጣን ይፈረዳል (ይህም ለማደናገሪያ የተሠራ ነው) ፲፫ኛ ከኢትዮጵያ መንግሥት ሸፍተው ወደ ፩ኛው መንግሥት የመጡ ሰዎች በ፪ቱም

# ሞ ቀዳም

መንግሥት ቅጣት እንዲያገኘው አስቀድሞ በየግዛታቸው ያስታውቋቸው ይህን ሰምተው የሚከዱ ቢገኙ ታስረው ወደ መንግሥታቸው ተመልሰው ሊቀጡ ናቸው ፲፬ኛ የባሮች ነገር መዠመሪያ የክርስቶስን ተጻይ እንዳንሆን የኢትዮጵያ ንጉሥ እንደተቻላቸው በግዛታቸው ውስጥ ምንም ፩ድ ሰው ስንኳ ባሪያ እንዳይሸጥና እንዳይለወጥ እንዳይገዛም ያረመኔ ሥራ እንዳይሠራ ሕዝባቸውን በግድ ይከለክላሉ (እዚህም ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት ሙብት ውሥጥ ለመግባት የሚመች ፖለቲክ ስላገኙ መንፈሳዊ መስሎ ለመታየት የተሠራ ነው እንጅ ለኢትዮጵያ መንግሥት ከእግዚአብሔር እንዳይጣላ ታስቦ የተጻፈ አይደለም)

፲፯ኛ ይህንኑ አዲስ ውል ከ፪ቱ መንግሥት ፩ዱ ባንድ ምክንያት ላሳድስ ቢል ከተፈራረሙ ካ፩ድ ዓመት በኋላ እንደገና ለማደስ ይችላል ነገር ግን ፩ዓመት ሲቀረው አስቀድሞ ላ፩ኛው መንግሥት ማስታወቅ አለበት ተስማማተው እስቲያድሱ ድረስ የፊተኛው ውል ይረጋል ማለት ዳርቻና የሌላም ጠንካራ ነገር ካልሆነ በቀር እንደ ቀድሞ ውል ይቆያል (ይህም ከዳርቻና ከሌላም ጠንካራ ነገር በቀር እንደቀድሞው ይቆያል ማለት አስቀድሞ ስለ ወሰን ማፍረስ ነገር ማመልከቱ ነው ፲፯ኛ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ከሌሎቹ መንግሥታት ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት በኢጣልያ መንግሥት አማካይነት ሊሠሩ ይቻላቸዋል (ይህም ፖለቲክ ምንም ከላይም እንደዚሁ አጼ ምኒልክና የኢጣልያ ሰዎች በፔትሮሊ የተዋዋሉት ባ፲፫ኛ አንቀጽ ከመጨረሻው ላይ እሽ አለ የሚል ንግግር አለ ይህ እሽ አለ የሚሉ አማርኛ አለቦታው ገብቶ የሚረቅ ነው እሽ አለ ተብሎ የተጽፈው እሽ አለወደደ ማለትን አድርገው ነው ይህን ሁሉ የሚሠሩት እነዚህ መንፈሳውያኑ ልዑካን ናቸው ፲፰ኛው የኢትዮጵያ ንጉሥ በኢትዮጵያ ላይ በ፫ኛ ክፍል እንደሚለው ባላገሮቹን በታወቀ ሕግ አንድነት ሊያስተዳድሯቸው እሽ አሉ (ይኸውና ይህ እሽ አለ የሚሉ አማርኛ አሁንም መጣ ባላገሮቹን በታወቀ ሕግ ፩ነት ሊአስተዳድሯቸው እሽ አሉ ይላል ይህ ፖለቲክ ምን እንደሆነ አንባቢ ይመርምረው።) በኢትዮጵያ የንግድና የጥበብ እውቀት ሁሉ ነገር በቀና አሳብ በኢጣልያ ብቻ እንዲሆን ተወሰነ (ይህንንም ማስተዋል ነው) ፲፱ኛ ይህ ውል በኢጣልያና በአማርኛ ተጽፎ ፪ቱ ደብተር በ፪ቱ መንግሥታት ቤት ሆኖ አገረ ገዥዎች በሆነው ነገር ሁሉ እየተስማሙና እየተማመኑ በሰላም ይኖራሉ ፳ኛ ይህኑ ውል ሁሉ በኢትዮጵያና

በኢጣልያ በግልጥ ይታወቃል ሚያዝያ ፳፫ ፲፰፻፹፩ ዓ.ም በኢት ቁ በ፪ ማድዮ ፲፰፻፹፱ ዓ.ም በፈረ ቁ የኢትዮጵያ መንግሥትና የኢጣልያ መንግሥት የተላከ ኮንት ፔትሮ አንቶሊኒ ይህንን ውል በውጫሌ ተፈራረሙ ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ን ነ ዮሐንስ መተማ ከቀሩ በኋላ በቶሎ ግቡ ብለው የጐጃምን ገዥ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትን የወሎን ገዥ ራስ ሚካኤልን ፪ቱን የትግሬና የጐጃም የሸዋ አቡኖች አስገቡአቸውና ንጉሣችን መጡ ብለው እጅ ነሥተው ተቀመጡ ግንቦት ፲ ቀን ፲፰፻፹፩ ዓ.ም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ተባሉ አጼ ምኒልክም ከጥንት ጀምረው ከኢጣልያ መንግሥት የተዋዋሉትን ውል ለመግለጽ ደጃዝማች መኰንን የሐረር ገዥ ከኮንት አንቶኖሊ ጋር ወደ ሮማ እንዲሄዱ አዘዙ ደጃዝማች መኰንንና ኮንት አንቶኖሊ በ፳፰ ነሐሴ በ፲፰፻፹፱ በፈረ ቁ ወደ ሮማ ገቡ የኢጣልያ መንግሥትም ደጃዝማች መኰንን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፭ኛ መልእክተኛ

# ሠ እጉድ

ስለሆኑ በብዙ ክብርና ትልቅ አጀብ ተቀብሏቸው ደጃዝማች መኰንንም በግራዝማች ዮሴፍ ንጉሡን በፈረንሳዊ ቋንቋ እያነጋገሩ የሚከተለውን ቃል ተናገሩ ልዑል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በልዑል ግርማዎ ፊት ቆሜ የሚቀጥል ፍቅራቸውን ለማቅረብ አዘውኛልና የርሳቸውን ሰላምታ አቀርብልዎታለሁ አሁን ንጉሤ የኢትዮጵያ ሁሉ አባት ነውና ስለዚህ ከመንግሥትዎ የበለጠ ነገር ለመጠየቅ የወዳጅነትና የንግድ ሥራ የተዋዋልነውንም ጽኑ ለማድረግ መጣሁ። በኢትዮጵያና ባጠገቡ ያሉ ሕዝብ የኢጣልያ ግዛት ሰላምና ፍቅር እስኪሆን ድረስ ልዑል ግርማዎ ለመንግሥቴ ትልቅ ጥግታ እንዲሆነው በመንግሥቱ ስም ሆኘ እለምነዎታለሁ ስለምን የኔ ንጉሥ የሚፈልገው ለጥቅማችን የሚሆን ንግድ ማስፋፋትና ማመላለስ ነው እንጂ ሌላ ነገር እንደሌለው በሆነው ነገር ሁሉ የኢጣልያ ጠላቶች የኛም ጠላቶች እንደሌለው በሆነው ነገር ሁሉ የኢጣልያ ጠላቶች የኛም ጠላቶች እንደሆኑ ልዑል ግርማዎ አረጋግጥልዎታለሁ ይህ ሁሉ ሲሆን ሳለ ደጃዝማች መኰንን በኢጣልያ አገር ተቀምጠው የኢጣልያ መላክተኛ ኮንት ሳሊምቦኒ (ይህ ሳሊምቦኒ ባጼ ዮሐንስ ከተማ ተይዞ ወህኒ ገብቶ ከሰነበተ በኋላ ፈተውት ሲቆይ ያጼ ዮሐንስን ጦር ድርጅትና የጦርኑን ብዛት የወታደሩን ጀግንነት ጽፎ የላከ ነው) ሳሊምቦኒ ካጼ ምኒልክ የፖለቲክ ሥራ ይሠራ ነበር ዶክቶር ቸሬዛ ነሩዚኒ በሐረር ተቀምጦ የፖለቲክ ሥራ ይሠራ ነበር ዶክቶር ሌዎታዳን በስተማረፊያ ተቀምጦ የፖለቲካ ሥራ ይሠራ ነበር ዤኔራል ባልዴሲራ በኢትዮጵያ ደጋ ምድር ማለት በአሥመራ ከከረን በአከለ ኩዛይ በሠራዬ በሐማሴን በ፫ አገሮች ከነሠራዊቱ ተቀምጦ ነበር። የውጫሌንም ውል በገዛ እጁ አፍርሶ እስከ መረብና ሙና በለሳ ዳርቻ ምድር አድርጎ በዚያ ላይ ገዥ ሆኖ ተቀመጠ ይህንም አገር የያዘ ደጃዝማች መኰንን በኢጣልያ አገር ሳሉ ከሰኔ ፪ ዠምሮ እስከ ነሐሴ ፫ ፲፰፻፹፱ ዓ.ም በፈረ ቁ በዚያ ጊዜ እነዚሁ ኢጣልያኖች የፖለቲክ ሥራ እየሠሩ ላጼ ምኒልክ ይነግሩ ነበር ማለት ራስ መንገሻ ራስ አሉላን የሐማሴን ገዥ አጋዥ አድርጎ ያጼ ዮሐንስን አልጋ ይዞ ካጼ ምኒልክ ሊዋጋ ይሰናዳል እያሉ ስላጣሏቸው። (ከላይ በተጻፈው ውል በ፱ኛው ክፍል ላይ እውነተኛ ሃይማኖት እንዲያስተምሩ በግልጥ ተፈቅዷል ያለው ይህውና እየተስፋፉ እየተገለጠ ሲሄዱ ይታያል ይኸውና ካጼ ምኒልክ የተዋዋሉትን ውል እያፈረሱ አገራቸውን በሥርቆት ይወስዳሉ የተሠረቀውን አይተው ጦርነት እንዳይነሱ አስቀድመው ባቆሙት ማኅበራዊ ፖለቲክ ምቹ ጊዜ አጋጠማቸውና ከላይ እንደተጻፈው በተለመደው ፖለቲካቸው ራስ መንገሻ ዮሐንስ ራስ አሉላን የሐማሴን ገዥ አድርጎ ያጼ ዮሐንስን አልጋ ይዞ ካጼ ምኒልክ ለመዋጋት ይሰናዳል እያሉ የተለመደ ሰይጣናዊ ፖለቲካቸውን ሲዘሩት ልክ መንፈሳዊ ሙት የሚአነሱ ቅዱሳን እየመሰሉ ሳይታዩ እንዳልቀሩ አስረጅ ወደፊት ይመጣል) አጼ ምኒልክ እነዚህን ፪ቱን ራሶች ለመቃወምና ነገሩንም ለመመርመር ከሰሜን ወገን ራስ መንገሻ ወዳሉበት ቦታ ወደ ትግሬ ሊሄዱ ራስ ሥዩምን አዘዙዋቸው። ሥዩምም ትግሬ ደረሱና ራስ መንገሻን ጠየቋቸው ራስ መንገሻም አጼ ምኒልክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እንደሆኑ አውቃለሁ ከናገሬ ከመላው ትግሬ ጋር እጅነሳሁ እታዘዛለሁ ብለው ያጼ ምኒልክ ታማኝ ሆነው ተገኙ

(በዚህ ጊዜ እነዚያ መንፈሳውያኑ ምንም ባይጠረጠሩ ለጊዜው ትንሽ መታወቃቸው መገለጽ በተዥመረ ጊዜ ይህነኑ ነገር እውነት ለማድረግ ሥራቸውን ሲቀጥሉ ወደ

# ሠ ሰኑይ

ፊት ይታያሉ።) አጼ ምኒልክ በጥር ወር ባ፲፰፻፹ ዓ.ም በፈረ ቁ ወደ ትግሬ አገር ድረስ ደቡብ እመጣለሁ ብለው ስላስታወቁ እሳቸው እስቲመጡድ ረስ ራስ መንገሻ የትግሬ አገር ሁሉ ገዥ ሆኑ ያንጊዜ ብልዲስራ የሐማሴን ገጽ ተከታይ የነበረ ጄኔራል አሪሮ ራስ መንገሻንና ራስ አሉላን ንቆ በሰሜን ወገን ወደ ዓድዋ ይገሠግሥ ጀመር። ጄኔራል አሪሮም ራስ ስብሐትን ትቶ ወደ ዓድዋ ሄዶ እርድ ለማረድ ከኢጣልያ መ ትእዛዝ መጥቶለት ነበረ ኢጣልያኖች የውጫሌ ፫ኛውን ክፍል ውል አፍርሰው እስከ ዓድዋ መምጣታቸውን ከኢትዮጵያ መንግሥት ጠብ ለማንሳት እንደሆነ ታወቀላቸው አጼ ምኒልክም ከሸዋ ወደ ትግሬ አገር መጡና ሐውዜን ሰፍረው በምሥራቅ ወገን ያለውን ትግሬ የራስ ስብሐት የነበረውን አጋሜን ሁሉ ለራስ ሥዩም ሰጧቸው በምሥራቅና በሰሜን ያለውን ትግሬ ፩ዱን ለራስ መንገሻ ሰጡአቸው ዓድዋና በ፪ቱ ራሶች መካከል ያለውን ትግሬ ፩ኛውን ክፍል ዓድዋ ላይ ተቀምጠው የኢጣልያ ዳርቻ ሊጠብቁ ለመኳንቶቻቸው ከሰጡ በኋላ ኮንት አንቶኖሊ ከራስ ስብሐት ጋር ወደ ሐውዜን አጼ ምኒልክ ወደ ሰፈሩበት መጡ አጼ ምኒልክ ግን በመልካም አልተቀበሏቸውም በኢጣልያና ባጼ ምኒልክ የነበረ በ፫ኛውና ባ፲፯ኛው ውል በውጫሌ የተዋዋሉትን ተካካዱና ተጣልተው ወደ ሸዋ ተመለሱ (ከላይ እንደተመለከተው በኮንት አንቶኖሊና ባጼ ምኒልክ መካከል የተዘራው ፍቅር ታመመና ችግር ሆነ።) የናፖሊ ፕስተኛ አጼ ምኒልክ የውጫሌን ውል ከደው ወደጀርመንና ወደ ፈረንሳይ መንግሥት ወደ ዛንዚባር ሡልጣን መልክት ጽፈው የብረትና የሌላም ነገር እንዳለ ልከዋል እያለ ወደ ኢጣልያ መንግሥት ላከ (ይህንን ወሬ ማነው ወደ ኢጣልያ የላከ እነዚያው እውነተኛ ሃይማኖት እንዲያስተምሩ የተፈቀደላቸው አይደሉምን ካጼ ምኒልክ ጋር ውጫሌ ላይ ተዋዋሉ በ፱ነኛው ክፍል ላይ እነዚህ የሮማ ማኅበር ልዑካን እውነተኛ ሃይማኖት የሚአስተምሩ በግልጽ ሲሰብኩ ተፈቅዶላቸዋል የተባሉ ለዚህ ሥራ መሆኑን የማይገነዘብ ሰው አለ ይሆንን) የኢጣልያ መንግሥትም ይህን ነገር አወቀና ለጄኔራል ባልዴስራ የበለሳን ዳርቻ እንዳይለቅ ይልቁም በኢጣልያ ሥልጣን ጠንክሮ እንዲገዛ ጻፈለት በኢጣልያ መንግሥትና ባጼ ምኒልክ መካከል የተደረገ ጠብ ኮንት አንቶኖሊ አጼ ምኒልክን ተከትሎ ወደ ሸዋ ገባና ካጼ ምኒልክ እየተነጋገረ ስለ ዳርቻ ነገርም ብዙ ምክንያት እያመጣ አሰናከላቸው። እርሳቸውም እስቲውጣና ከመኳንንቶቹ ጋር መክሬ አስታውቅሃለሁ ብለው ከመኳንንቶቻቸው ጋር መከሩ ትልቁም ትንሹም የሸዋ መኳንንት ባ፩ ቃል ሆነው እንደውጫሌው ውል የቆመ እንደሆነ እሽ አለዚያ ግን አካለ ጉዛይና ሠራዬ ለኢጣልያ ግዛት ሊሆን አንሰጥም በጦርነት ካልሆነ በቀር አልዋቸው። አጼ ምኒልክ ግን ከኢጣልያ መጣላት ፈሩና ኢጣልያኖች እንዳሏቸው በመረብና በበለሳ ሙና ዳርቻ ምድር ሊሰጥዋቸው ፈለጉ ነገር ግን የሸዋ መኳንንት በኅብረት ጠንክረው ባ፩ ቃል ሆነው አካለ ጉዛይንና ሠራዬን ለኢጣልያ አሳልፈን ከመሥጠት ደማችንን ማፍሰስ ይቀርበናል። ይልቅስ በውጫሌ ውል ይቁም ብለው ቁርጥ የሆነ ቃል ከተናገሩ በኋላ አጼ ምኒልክ እጅግ ፈሩና ከመኳንንቶቻቸው ተሸሽገው ከኮንት አንቶኖሊ ጋር በእልፍኝ ሆነው እስከ በለሳሙና እስከ መረብ ዳርቻ

## ሣ ሠሉስ

# ፪ኛ ክፍል ግንቦት

የምጥዋ ገዥ ሊገዛው እሽ በለው (ይኸውና እዚህ ላይ እሽ ብለው ማለት በሥፍራው ወደው በማለቱ ተገልጾ ተገኘ) ተዋውለው የካቲት ፳፫ ፲፫፻፩ ዓ.ም በፈረ ቁ ተፈራረሙ የኢትዮጵያ መኳንንት ግን አከለ ጉዛይና ሠራዬ የኢትዮጵያ ግዛት ነው ያለዚያ ያጼ ምኒልክ ውል ውላችን አይደለም እያሉ በየአደባባዩ ያለቅሱ ነበሩ ነገር ግን አጼ ምኒልክ መኳንንቶቻቸው በዚህ ውል ነገር እጅግ አዝነው ባይዋቸው ጊዜ ከጥቂት ቀን በኋላ በውጫሌ የተዋዋልነው ውል ለመንግሥቴ ጉዳት እንዳለበት አውቃለሁና በወዳጅነት እንደገና ልናድሰው እፈልጋለሁ ብለው ኢጣልያ መንሥት ጻፉ በዚህ ባ፲፯ኛው ውል ለኢትዮጵያ ጉዳት እንዳገኛት ያስታወቁ ፩ኛ የጀርመን መንግሥት ፪ኛ የእንግሊዝ መ ናቸው። ስለምን እነዚህ ፪ቱ መንግሥታት ይህንን ነገር ከሰሙ በኋላ አስቀድመው ወደ አጼ ምኒልክ ጽፈው ነበሩ እንደዚህ ሲሉ እርስዎ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ሊጠሩ አይችሉም ስለምን የኢጣልያ ተከታይ ተወራጅ ንጉሥ እንዲሆኑ በውጫሌ የተዋዋሉት ውል ፊርማዎ ይመሰክርብዎታል እንግዲህ ከኛ ጋር ሊጻጻፉና ሊዋዋሉ አይችሉምና እንዳይችሉ እናስታውቅዎታለን ግን ፪ኛ ደብዳቤ ወይም ፩ ነገር ሊጽፉልን በፈለጉ ጊዜ መጀመሪያ ወደ ኢጣልያ መንግሥት ጽፈው ከዚያ በኋላ የኢጣልያ መንግሥት በሥልጣኑ እንደሆነ ያስቡ ያለዚያስ ያለመሪዋ ያለ ኢጣልያ መ ፩ ነገር ወደ አውሮፓ ሊጻጻፉና ሊዋዋሉ አይችሉም ብየ እገልጽልዎታለሁ (እስከዚህ ድረስ በማታለል የሚሠሩት ሥራ ሁሉ በጣም አስደናቂ ነው። እንዋዋል ብለው በንግድ አስመለው በቃል ጽሑፍ ማታለያ ቃል ፈጥረው ነፃነቷ ተከብሮ ፬ሽ ፫፻ ዘመን የቆየችቱን አገር አፈር የሚአስግጡ ጀግኖች ያሉበትን የሌሉ አስመስለው በቃል አታላይነት ያስፈረሙትን የውሸት ሥራ ከቁም ነገር አግብተውት ባውሮፓ ለሚገኙ ነገሥታት ሁሉ ኢትዮጵያ የኛ ጥገኛ ሆነች እያሉ ማስታወቃቸው ምናልባት እውነቱ በተገለጸ ጊዜ ቅሌት ያመጣብናል ብለው ሳይገምቱ መቅረታቸው ባ፲፰፻፹፰ ዓ.ም የተደረገውን የጦር ታሪክ ዓይናቸው እስቲያይ ድረስ ጉልበታቸውን ልክ ሳያውቁት ከመቅረታቸው የተነሳ በኢትዮጵያ ላይ ሰው ያለ ሳይመስላቸው ስለቀረ ነው በሐሰት ስብከት የጀግኖችን አገር ለመንጠቅ የታሰበው ሁሉ ከንቱ ሆኖ ከመቅረቱ በላይ ትርፍ እንደማይሰጥ ይህ ቃል የታሪክ ዓምድ ይዞ በዓለም ላይ ይቀመጥ) የመቀመጡም የሐሰት ሐውልትነቱን ይዞ ነው።

አጼ ምኒልክም እንደገና በልባቸው ያልነበረ ሐሳብ አሰቡና የውጫሌ ፫ና ፲፯ኛ ውል አፈርሳለሁ አሉ። ኢጣልያኖችም ይህን ነገር ከሰሙ በኋላ በፖለቲክ ሥራ ሳይወስዱ ይህንን ውል ብቻ ለማደስ እሽ ብለው ካጼ ምኒልክ ጋር ተስማምተው ልዑል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ከኢጣልያ መ የተላኩ ጴጥሮስ አንቶኖሊ በፊት የነበረው ፫ኛውና ፲፯ኛውን አፍርሰው ውል እንደገና የተዋዋሉት ፪ኛው ውል ከአድባሮ ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ቀንቶ የሚአመለክት ሕንጻጽ ከአድባሮ ወደ ድባርዋ የሚአስኬድ ምንገድ ከድባርዋ ጅምሮ እስከ አድባሮ መሀከል በሰሜን ወገን ያሉ አገሮች የኢትዮጵያ ግዛት ይሆናል ከድባሮዋ ዠምሮ በቶከቲ በአዲኩቡሎ በድንጋራ በኩርባይራ ቀንቶ እስከ ጉራዕ የሚአስኬድ ምንገድ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ዳርቻ ይሆናል እነዚሁም ቴክቲ ዱባይታ የሚባሉ

## ሣ ረቡዕ

አገሮች አድ ግራ ዱርባይራ የሚባሉ አገሮች የኢጣልያ ግዛት ይሆናሉ ትኩል ጉራዕ የሚባሉ አገሮች የኢትዮጵያ ግዛት ይሆናሉ ከጎዲ ጉልጉል ጀምሮ ያሉ እናይቶ ማዕረባ ሰገነይቲ ሄቦ የሚባሉ አገሮች የኢጣልያ ግዛት ይሆናሉ። በሰሜን ወገን ያሉ አገሮችም ከድግሳ ዠምሮ የኢትዮጵያ ግዛት ይሆናሉ። ከሄቦ ተነሥቶ በድግሳ አጠገብ አልፎ እስከ

ሀላይ የሚደርስ ምንገድ የኢጣልያና የኢትዮጵያ ግዛት ዳርቻ ይሆናሉ በዚያው ምንገድ በሰሜን ወገን ያሉ አገሮች የኢትዮጵያ ግዛት መሆኑ ነው በደቡብ ወገን ያሉ አገሮችም የኢጣልያ ግዛት መሆናቸው ነው ከሀላይ ተነሥቶ በሸንፋይ አድርጎ እስከ ማህዮ የሚአስኬድ ምንገድ ደግሞ የኢትዮጵያና የኢጣልያ ግዛት ዳርቻ ይሆናል ከማዮ ተነሥቶ በደግዓ አድ ዘግራ አልፎ እስከ ጥንገብ ማለት አረፋይሌ አጠገብ ከአረፋይሌ እስከ ዋንግቦ ያለውን መንገድ ነው በሰሜን ወገን ያሉ አገሮች የኢትዮጵያ ግዛት ናቸው በደቡብ ወገን ያሉ አገሮች የኢጣልያ ግዛት መሆናቸው ነው በገላጣ ሜዳ የሚያስሄድ ምንገድ ደግሞ የዳርቻ መሐከለኛ ይሆናል። ከአድባሮ ዠምሮ ወደ ምሥራቅና ምዕራብ ቀንቶ የሚያመለክት ሕንጻጽ ከግራ ወደ መረብ የሚወርድ ትልቅ ኸረት መሐከለኛ ዳርቻ ይሆናል በዚሁ ሕንጻጽ በሰሜን በኩል ያሉ አገሮች ሁሉ የኢትዮጵያ ግዛት ይሆናሉ በደቡብ ወገን ያሉት ደግሞ የኢጣልያ መሆናቸው ነው። በጋራስሐ እስከ መረብ የሚያመለክት ሕንጻጽ የሚጎርፍ ያለ ወንዝ እስከ ተከዚ እስከ ተካንድዋ እስከ በሪ ድረስ ያለ ወንዝ የኢጣልያ ግዛት ዳርቻ ይሆናል ማለት በዚሁ ሕንጻጽ በሰሜን በኩል ያሉ አገሮች የኢትዮጵያ ግዛት ነው በደቡብ ወገንም ያሉ አገሮች የኢጣልያ ግዛት መሆኑ ነው። ልዑል የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አጼ ምኒልክና ከኢጣልያ መ ታምኖ የተላከ ኮንት አንቶኖሊ በዚህ ውል ተስማምተው አዲስ አበባ የካቲት ፯ ፲፰፻፹፩ በፊረ ቁ ተፈራረሙ በውጫሌ የተዋዋሉትን አ፲፯ኛውን ውል አጼ ምኒልክ ለማደስ እንደ ፈለጉት ኢጣልያኖች እምቢ አሉ አጼ ምኒልክም እኔ በዚህ ነገር ከኢጣልያ ልዋጋ አልፈልግም ነገር ግን ከእናንተ ጋር እንደ ቀድሞ ፩ድነት ፍቅር የለኝም ብለው መለሱላቸው። ኢጣልያኖችም ካጼ ምኒልክ ተጣሉ። (ካጼ ዮሐንስ አጣልተው ልብ ለልብ አስተዛዝነው በኋላ ተንኮላቸውን ገለጹ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖትንም የሚአጣሉበት ነገር ቢያጡ ወደ ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ያስገዛኸውን ብረትና ጥይት እንድታስወስድ የሚል ደብዳቤ ከምጽዋ ወደ ጐጃም በመሐል ትግሬ ውስጥ ሂድ ብለው ደብዳቤውንም በግልጽ በእንጨት ሰክቶ ይዞ ሲሄድ ይህን ደብዳቤ ያጼ ዮሐንስ የልፍኝ አሽከር ከምንገድ አግኝቶ ቢአነበው እንደዚሁ ከኢጣልያ ሹም ወደ ጐጃም የተላከ የመሣሪያም ነገር ያለበት ስላ ሆነ ወደ አጼ ዮሐንስ አቀረበውና ቢጠይቅ የተላከበትንና የሚሄድበትን ከነገራቸው በኋላ ባጼ ዮሐንስና በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት መካከል ቂም መግባት የተዠመረ ከዚህ በኋላ ነው ምክንያቱም የጦር መሥሪያ እኔን ስጠኝ በማለት ፋንታ ከጠላቶቹ ተዋውሎ ብረት መፈለጉ እኔን እንደ ንጉሥ ምኒልክ ክዳት መፈልጉ ነው በማለት ነው ከዚያ በኋላ ያጼ ዮሐንስ ልብ እንዳዘነ ሁለቱም ንጉሦች አብረዋቸው ሳይሄዱ ብቻቸውን ወደ መተማ ወርደው እዚያው ስለቀሩ ለጠላት በጣም የተመቼ የተከፈተ በር ስላገኘ ከተወሰነው ቦታ አልፎ አገር መያዝ ምቹ ሆነ አጼ ዮሐንስ እስቲሞቱ ያጼ ምኒልክ ዋና አሳቢ ወዳጅ ነበር አጼ ዮሐንስ ሞተው በኢትዮጵያ አጼ ምኒልክ ከተተኩ


## ሤ ጎሙስ

በኋላ ደግሞ አጼ ምኒልክ እንደ አጼ ዮሐንስ ተጠሉና የአጼ ዮሐንስ ልጅ ራስ መንገሻ ለወዳጅነት መታጨት ተዠመረ ማለት ማባበልና መሣሪያ እንስጥህ ማለት ነው ይህ ሁሉ ድካም መንፈሳዊ ሰባኪ መስለው ውስጥ ለውስጥ እየሄዱ ንጉሥን ከመሳፍንቱ ከሠራዊቱ ጋር እያለያዩና እያፋጁ ምድሪቱ ባዶ ስትሆን እነሱ ዋና ሆነው ለመያዝ ነው) ኢጣልያኖች ካጼ ምኒልክ ከተጣሉ በኋላ በፖለቲክ ከራስ መንገሻ ጋር ሊፈቃቀሩ ዠመሩ ራስ መንገሻ ዮሐንስም ካጼ ምኒልክ ተሸሽገው ወደ ኢጣልያ መንግሥት የጻፉት ደብዳቤ ይላል እውነት መሆኑን አምላክ ያውቃል በንጉሥ ተክለ ሃይማኖት እንደተሠራው የፖለቲክ ጽሑፍ በራስ መንገሻ ዮሐንስም ካጼ ምኒልክ ለማጣላት ወደ አጼ የጻፉት ደብዳቤ በእግዚአብሔር ቸርነት ባገር ፈቃድ የነገሡ ፩ኛ ዑምቤርቶ የኢጣልያ ንጉሥ እኔ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይሁን ደና ነኝ ባለፈው መልእክታችሁ ፩ድ ነገር ከኔ ብትፈልጉ ምጽዋ ወዳለው የኔ ሹምና ጸሐፊ አመልክቱ ብላችሁ ጽፋችሁልኛል ልዑል ሆይ እኔ ከናንተ ፍቅር ለማድረግ ነው እንጅ ሌላ ነገር የምፈልገው የለኝም ፍቅራችንም ዘለዓለማዊ እንድትሆን በልቤ ያለ ቅን ሐሳቤን በዚህ ደብዳቤ እልገልጥልዎታለሁ። ነገር ግን እኔ የምፈልገው ፍቅራችን ለጊዜው ብቻ ሳይሆን ለትውልድ ትውልዳችን እንድትሆን ነው። እንደ አሳቤ ሊሆንልኝም ተስፋ አለኝ። ሐምሌ ፳ ፲፰፻፹፫ ዓ.ም በኢትዮ.ቁ

ራስ መንገሻ ዮ) ከላይ እንደተጻፈው ካጼ ምኒልክ ጥል በተዠመረ ጊዜ ወደ ራስ መንገሻ እየሄዱ ያነኑ ልማዳቸውን ፖለቲክ እያመሰሉ እያወሩ ከራስ መንገሻ ዮ ወደ ኢጣልያ ሁምቤርቶ ደብዳቤ እንዲጽፉ አድርገው ወደ ኢጣልያ ንጉሥ ደግሞ እንደዚሁ ብለህ ጻፍ እያሉ ስለሚቦለትኩ ከላይ የተጻፈው ደብዳቤ እንደሚገልጸው ባለፈው መልእክታችሁ ፩ድ ነገር ከኔ ብትፈልጉ ምጽዋ ካለው ሹሜ ብታመለክቱ ትችላላችሁ ይላል ማለቱ ራስ መንገሻ ዮሐንስ ሐምሌ ፳ ፲፰፻፹፫ ዓ.ም የጻፉት መልስ ማስመሰል መሆኑን ያስረዳል።

በዚሁም ደግሞ መልሱ ፫ኛው ደብዳቤ ራስ መንገሻ የንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ልጅ ጤና ይስጥልኝ የጻፉልኝ ደብዳቤ ደረሰኝ እጅግም ደስ አለኝ እኔም ደግሞ ከእናንተ ጋር ወዳጅነት ለማድረግ ብዙ ምኞት አለኝ በትግሬና በኢትዮጵያ ሁሉ ዳግማዊ ምኒልክ የእናንተ ንጉሠ ነገሥት ብዙ ተስፋ አለኝ ነገር ግን የኔና የናንተ ሃሳብ ይስማማ እንደሆነ ለመመርመርና ለማስጌጥ የኔ እሙን አሽከር ዶክቶር ነሩዚን ከወዳጅሁ ዶክቶር ዲማርቲኖ ከእናንተ ሊዋዋሉ እሰድላችኋለሁ በሁሉም ነገር እንደ አሳቤ ልትስማሙ ተስፋ አለኝ የበለጠ ነገር ግን ከጄኔራል ጋንዲልፊ የምጥዋ ገዥ ጋር ፩ድ ትልቅ ጉባዔ አድርጋችሁ እንድትዋዋሉ ፍቅራችንም ለሁላችሁም የሚጠቅም ውል ተስማምታችሁ እንድትዋዋሉ ፍቅራችንም በሁላችን ተጠብቃ ረጅም ዘመን እንድትኖር እግዜርን እለምናለሁ ተጻፈ በኢጣልያ ቡ መ ፲፰ መስከረም ፲፰፻፸፩ በፈረ ቁ ፲፰፻፹፬ በኢት ቁ ፩ኛ ዑበርቶ።)

(ይኸውና ከላይ እንደተመለከተው እሙን አሽከሬ ዶክቶር ነሩዚኒ ከወዳጃችሁ ከዶክቶር ዲማርቲኖ ጋር ከእናንተ ሊዋዋሉ እሰዳቸዋለሁ። ይላል ይህ ዲማርቲኖ ከራስ መንገሻ ዮሐንስ ዘንድ ዋና ሰባኪ የነበረው ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ዘወትር የሚሠሩትን ሥራ ሁሉ ማስተዋል አስፈላጊ ነው። ማለት አሁንም የነሱ ልጆች




ይህ ሥዕል ደጃዝማች ባሕታን ያሳያል

# ፦ ዐርብ

ያባቶቻቸውን ሥራ እንደማይተው ማስተዋል አለ።) ራስ መንገሻና ጄኔራል ጋንደልፊ በመረብ ወንዝ የተዋዋሉት ውል ይላል ጄኔራል ጋንደልፊ ራስ መንገሻ የሚጠላ ጠላቴ ነው ራስ መንገሻን የሚወድ ወዳጄ ነው። ራስ መንገሻን እወዳለሁና አከብራለሁ ራስ መንገሻን የሚአሳዝን ነገር ምንም ትንሽ እንኳ እንዳላደረግም እምላለሁ። አለ። ራስ መንገሻም ኢጣልያን የሚጠላ ጠላቴ ነው። ኢጣልያን የሚወድ ወዳጄ ነው። ኢጣልያን መንግሥት እወዳለሁ አከብራለሁ። የኢጣልያ መንግሥት የሚያሳዝን ነገር ትንሽ እንኳ አላደርግም እምላለሁ አሉና ሁለቱም እጃቸውን በወንጌልና በመስቀል ላይ አስቀምጠው ተማማሉ ይላል ይህንን ጽሑፍ እንመነው ይሆንን ይህ የፖለቲክ ካጼ ምኒልክ ለማጣላት የተፈጠረ መሆኑን ወደፊት መረጃው ይመጣል።

(ይህን ነገር ወስደው እነዚሁ ላጼ ምኒልክ ሠፈር አወሩትና አጼ ምኒልክም ይህን በሸዋ ሳሉ ሰሙና በጣም አዘኑ አጼ ምኒልክ በኢጣልያኖች ብዙ ኃዘን ነበራቸው ዶክቶር ትራንቤሼን ከሸዋ ወደ ኢጣልያ እንዲሄድ አደረጉት ትራንቤሼን ኢጣልያ አገር ከደረሰ በኋላ አጼ ምኒልክ ጄኔራል ጋንደልፊ ትግሬ አገር መረብ ላይ ያደረጉትን ጉባዔ አውቃለሁ የሚል የኃዘን ደብዳቤ ጽፈው ወደ ኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ሰደዱለት ይኸውም ዶክቶር ትራቢሺ።

፪ኛ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመለስ አመለከቱት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሩዲኒ ግን የውጫሌ ፲፯ኛን ውልና የዳርቻ ግዛት እንደገና ሊዋዋሉ አጼ ምኒልክም ከትግሬ መኳንንትና ከጀነራል ጋንደልፊ ጋር የሚመጣላቸውን ለመመርመር በዚያው ዓመት በነሐሴ ወር ዶክቶር ቴራንቢሼን መልሰው ወደ ሸዋ ላኩት ዶክቶር ትራንቤሼንም በሚኒስተር ተልኮ ወደ ሸዋ መጣና ፪ ሚሊዮን ጥይት እጅ መንሻ አቅርቦ አጼ ምኒልክን በፖለቲክ ሊያስናዳላቸው ፈለገ አጼ ምኒልክም ተንኮሉን አወቁና በቶሎ እየሳቁ እንዲህ አሉት። መጀመሪያ ነገር ኢጣልያኖች እኔን ከድታችሁ ከትግሬዎች የተዋዋላችሁትን ሰምቻለሁ ፪ኛም አዲስ አበባ ላይ የካቲት ፺ ፲፰፻፹፩ ዓ.ም በፈረ ቁ ኮንት አንቶኖሊ ጋር የተዋዋልነውን የዳርቻ ውል አልፋችሁ እስከ መረብና ሙና በለሳ ትገዛለችሁ ፫ኛ ፲፯ኛውን ውል በፖለቲክ ልታስተካክሉኝ እንጂ በልባችሁ ቅን ሐሳብ እንዳላመጣችሁ አውቃለሁ። ግድ የለህም ብለው መለሱለት አጼ ምኒልክን እንዲህ አድርጎ ያጠነከራቸው ነገር እንዲህ ነው። የጀርመን ንጉሥ ጉሌልሞ ጊዮም በኢጣልያ መካከል አድርጎ ደብዳቤውን ስለ ጻፈላቸው ነው። ቀጥሎም የኢጣልያ ፖለቲክ ጉዳታቸው እንደሆነ ስለ አስተማራቸው። (ይህም በቀጥታ ጀርመን አገር ልከውት የነበረውን ደብዳቤ ኢጣልያኖች ኢትዮጵያ የኛ ጥገኛ ሆናለች ብለው ለአውሮፓ ነገሥታት ካስታወቁ በኋላ የጀርመን መንግሥት በኢጣልያ በኩል ስለላከላቸው ምሥጢራቸውን ኢጣልያኖች ስላወቁባቸው ተናደዱ ማለት ነው። ) ይልቁንም በአደን የነበረ የጀርመን ኮንስል ላጼ ምኒልክ ደብዳቤ ያለ ኢጣልያ እጅ በተቀር በቀጥታው ካጼ ምኒልክ እንዳይቀበል ስለከለከለው። ያውሥትሪያ ንጉሥ ያጼ ምኒልክን ደብዳቤ ያለ ኢጣልያ እጅ በተቀር በቀጥታ እንዳይቀበሏቸው ውሳኔ ስለ ወሰነ ነው። የሩሲያ ንጉሥም እኔ እስካሁን ያጼ ምኒልክን ደብዳቤ አልተቀበልሁም ከእንግዲህም ቢልኩ አልቀበልም። ብሎ ውሳኔ ስለወሰነባቸው የፈረንሳዊም



በግርማዊ አጼ ዮሐንስ የጎማሴን ገዥ የነበረው ኢጣልያኖችን የወንድ በር ያሳያቸው ራስ አሉላ።

ያሉላ ፈረስ የረገጣቸው
እስካሁን ድረስ አለ ቁስላቸው
ያሉላ ፈረስ ተስቦ ወርዶ
ያነን ነጭ ገብስ አረገው ነዶ።

# ሦ ቀዳም

መንግሥት ከዚህ ቀደምም ካጼ ምኒልክ ፩ድ ደብዳቤ ተቀብያለሁ። ነገር ግን ምላሽ እንዳልመልስላቸው ወሰኛለሁ አለ። እንደዚሁም የአውሮፓ ነገሥታት ሁሉ በጋዜጣ ስለገለጡላቸው ባጼ ምኒልክ እና በኢጣልያ መንግሥት ጠብ ሆነ ከዚያም በኋላ አጼ ምኒልክ በምሥጢር አድርገው የኢጣልያ ሰው ፩ድ ስንኳ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይቀመጥ በውስጧ እንዳይገኝ ለመኳንንቶቻቸው አመለከቷቸው ምልክቱም ራስ አሉላ ለኢጣልያኖች እጅግ ጠላት እንደመሆናቸው በዚያ ጊዜ በዓድዋ ላይ የሚቀመጡትን ኢጣልያኖች በስንት ነገር ያስጨንቋቸው እንደነበር አጼ ምኒልክም በ፲፫፻፺፪ ዓ.ም በፈረ ቁ ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩትን ኢጣልያኖች ኮንስሎች አባረሯቸውና በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ንብረታቸውን ይሰበስቡ ጀመር ራስ መንገሻ የኢጣልያኖችን ክፋትና ተንኰል አውቀ ካጼ ምኒልክ ተስማምቶ ኢጣልያኖችን ሊወጋ ተሰናዳ ደጃዝማች ባሕታም የአካለ ጉዛይ ገዥ ከኢጣልያ ከድቶ ወደ ኢትዮጵያ መንግሥት መጥቶ ኢጣልያኖችን ከመላው ሐማሴን ለአርራቸው ተዋዋሉ የሚል ተወራ (ተዋዋሉ ሲል ውሉ ከራስ መንገሻ ነው ግን ደጃች ባሕታ ሃይማኖታቸው ካቶሊካዊ ሆነው ስለነበር ራስ መንገሻ ዮሐንስ በጥብቅ ያምኑአቸው አይመልም ምክንያቱም ወደ ፊት ይገለጣል) ደጃች ባሕታና የኢጣልያኖች በሐማሴን ላይ የተደረገ ጦርነት ደጃች ባሕታ በፊት የራስ አርአያ ልጅ በሰገነይቲ ተዋግተው ልጅ አምባዬን ገድለው ካገራቸው ከሰገነይቲ ሸሽተው በአገመዳና በምጥዋ መካከል በሐባብ አገር እየተለማመጡ ይኖሩ ነበር። አጼ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ ግን ወደ ኢጣልያ ገዥ አድርገው ሹመዋቸው ፭ ዓመት ገዙና ግን ደጃች ባሕታ የኢጣልያኖችን ክፋት መርምረው ካወቁና ከተረዱት በኋላ ተራስ መንገሻ ተስማሙና ጭራሽ ከሐማሴን ነቅሎ ለማባረር ተማከሩ ኢጣልያኖችም ደጃች ባሕታ እንደ ከዳቸው አወቁና ወዮልን ደበብ ደህና ነው ስንል በኢጣልያ መንግሥት አማኝ ነኝ ብሎ በገዛ መሣሪያችን ብዙ ጐዳን አሁንም ደግሞ ደጃች ባሕታ አከለ ጉዛይን ይዞ በገዛ መሣሪያችን ሊጐዳን አስቧል ብለው ለማሰር ፈልጉና ወሰኑ። ግን ጄኔራል ባራቲሪ ወደ ትንንቲ ሳጎነይቲ የሚከተለውን ጻፈለት ክቡር ሳጎይነቲ ባሕታ ሓጐስ እጅግ ጨካኝ ሰው ነውና እንዳትረታ ሰው አይተህ ችላ እንዳትለው አደራህን ስለምን እሱ ፩ድ ነገር ዓይቶ ታግሶ ለማሳለፍ የማይችል ሰው ነውና አሁንም ደግሞ በትግሬና በሸዋ ትልቅ ድብልቅልቅ ከዳት ሆኗል ባሕታ ይህንኑ ነገር ሰምቶ ነው ምናልባት የኢትዮጵያ መንግሥት ኢጣልያኖችን ድል ነሥቶ ሐማሴንን የያዙ እንደሆነ ኋላ የኔው ይብሰኛል ብሎ ተጠራርጥሮ በኋላ የሚሆነውን ስፍራ ለማሰናዳት ብሎ ነው አሁንም ከራስ መንገሻ ጋር የተስማማሙ ይመስለኛል። እኔ ግን የደጃች ባሕታ ጦር እንዳያስፈራኝ አስረግጥሃለሁ የእግዜር ሠራዊት ካንተ ጋር ይሁን ጄኔራል ባራቲየሪ ታኅሣሥ ፩ ቀን ፲፰፻፺፬ ዓ.ም በፈረ ቁ በዚያ ጊዜ ልጅ ኢያሱ ግራዝማች ማርዬ ዑስማን ናይብ ባላምባራስ ክፍሌ ልጅ ሐጎስ ከንቲባ አማን ባሻይ ባርያይ የሚባሉ መኳንንቶችና ሌሎችም መኳንንቶች (ከላይ የተጻፉትን ሁሉ እንደ ነበር አጼ ምኒልክም መቆጣታቸውም ምጽዋ በተሰማ ጊዜ ኢጣልያኖችን የቀን ብርድ ይዝዋቸው እንደነበረ ከላይ ጄኔራል ባራቲየሪ የጻፈውን መመልከት ነው በደጃች ባሕታ ኃይል ብቻ ምን ያህል

# ረ እኁድ

ጭንቀት እንዳገኛቸው ማሰብ ነው እንደዚህ የሚሸበረውን ሁሉ እየመለሰ የሚጸናው የወንጌል ሰባኪ እየተባሉ በየሀገሩ የተዘራው ፖለቲክ ሠራተኛ በየሀገሩ ውስጥ የሚገኘውን ውሥጣዊ ሥራቸውን በየቀኑ እየዘረዘረ ስለሚጽፍላቸው ነው ጓዟቸውን ይዘው ሊሸሹ ከተነሱ በኋላ እንደገና ገንዘብ እየገዙ እርስ በርሳቸው እያዋጉ ዘራችንን እየቀነሱ መኖር ዋናው ደጋፊ የሮማው ማኅበር የላካቸው ልዑካን መሆናቸውን ማሰብና ማስትዋል ይገባናል።)

አጼ ምኒልክና የኢጣልያ መንግሥት የተዋዋሉት ውል ፈርሷል ራስ መንገሻም ካጼ ምኒልክ ተስማምተዋል ዘንድሮ ፩ ነገር ሳይደረግ አይቀርም የሚል ወሬ ከሰሙ በኋላ ልባቸው ተጠራጥሮ ነበር ማለት ኢጣልያኖች ሊከዱ አስበው ነበር ደጃች ባሕታ ግን ሃይማኖታቸው ካቶሊክ ስለነበረ በሰገነይቲ አጠገብ አክሩር ከሚባል መንደር ከፈረንሳይ ላዛሪስቶች በማኅበር ሁልጊዜ እየተመለሱ ነገራቸውን ከነሱ ጋር ይመካከሩ ነበርና ነገራቸውን በቶሎ ቆረጡ ማለት እነዚያ ላዛሪስቶች ከኮንስላቸው ጋር የኢትዮጵያን መንግሥት በተቻላቸው ነገር ሁሉ ለመርዳት ተሰናድተው ነበር ራስ መንገሻ ራስ አሉላ ደጃች ባሕታ ከላዛሪስቶች ጋር የኢትዮጵያን መንግሥት በተቻላቸው ነገር ሁሉ ለመርዳት ተሰናድተው ነበረ ራስ መንገሻ ራስ አሉላ ደጃች ባሕታ ከላዛሪስቶችና ምጥዋ ከነበረው የፈረንሳይ ኮንስል ብዙ የጦር መሣሪያ ሊአስመጣላቸው ተስማምተው ነበርና ኢጣልያኖች በዚያ ጊዜ እጅግ ፈርተው ነበር። ደጃች ባሕታ ከነወንድማቸ ከግራዝማች ሰንጋል ከ፩ መኰንን ጋራ ታኅሣሥ ፲፬ ፲፰፻፹፯ ዓ.ም በፈረ ቁ ወደ ጄኔራል ሳጐነይቲ ቤት ሄዱና ተቀምጠው ቡን እየጠጡ ሲጫወቱ ሳጐነይቲ የቡና ኩባያ በጁ እንደያዘ ተከታዩ የነበረ ትንቲ ያረቂ ኩባያ በጁ ይዞ ሳለ ሲጫወቱ ደጃች ባሕታና አዝማች ሰንጋል ባ፩ድ ምልክት ተጣቀሱና ያን ጊዜ በሀገራቸው ቅናት የነበራቸው ጀግኖች ልጆች ነበሩና ፎክረው ተነሥተው ሁለቱን ነጮች አንገት አንገታቸውን እየያዙ ከመሬት ጥለው በዱላና በቡጢ ያቀልጧቸው ጀመር ያን ጊዜ ሳጐነይቲ እንዲህ አለ። ባሕታ ሐጐስ መጀመሪያ ከዳተኛ ሰው በእግዜር ዘንድ የተጠላ እንደሆነ ተምረሃልና እግዚአብሔርን ፍራ ፪ኛ የኢጣልያ መንግሥት ሥልጣኑና ብዛቱ እንደምን እንደሆነ አስብ ማለት አሁን እኛን ልትሰቅሉንም ልትገድሉንም ትችላላችሁ በኋላ ግን እስከ ዘር ዘርህ ታልቃለህ ጉዳት እንዳያገኝህ አስተውል እኛን ደግሞ እንደምን ብታደርጉን የኢጣልያ መ ምንም የሚነካው እንደሌለ እርግጥ ነው ይልቅስ አሁን ብትለቁን ይሻላችኋል ያለዚያ ግን ረዳቶቻችንና ደማችንን የሚከፍሉ ጀግኖች የኢጣልያ ልጆች እንዳሉ ሃይማኖት ነውና በልቤ አምናለሁ ላንተ የሚረዱህና ደምህን የሚያወጣልህ ከመላው ኢትዮጵያ አታገኝም ሃይማኖት ነውና አምናለሁ። ስለዚህ ተው ልቀቀኝ ይሻልሃል እያለ ተናገራቸው። ደጃች ባሕታም ሆዱን በጉልበታቸው ረግጠው አንተ ድመት ዓይን ዝንጀሮ ጠጉር ነጭ ቂጥ ፯ ወንዝ ተሻግሮ የመጣ የበኃር አህያ። ከኢጣልያ መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት መብለጡን አታውቅምን ከኢጣልያ ልጆች የኢትዮጵያ ልጆች በእጥፍ እንደሚበልጡ አታውቅምን ለኔም የሚረዱኝ መላው ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ እስካሁን አላውቅህምን አንተ አህያ እያሉ በእጃቸው በብረት አሥረው ወደ ኢትዮጵያ ግዛት እንዲያሻግሯቸው ለወታደሮች ሰጧቸውና ቶሎ

# ሩ ሰኑይ

ብለው በዚያ የነበሩትን የኢጣልያ አሽከሮች ነጩን ጥቁሩን እጅ እጃቸውን ይዘው አሥሯቸውና ወዲያውም ስልኩን ሁሉ በጣጥሰው የኢጣልያኖችን ቤትና ዕርድ ሁሉ በጃቸው ያዙ። የአካለ ጉዛይን ሰው ሁሉ ግባ ብለው ዓዋጅ ነገሩ ሁሉንም ከተት ብሎ ወደ ሰገነይቲ ገባ ጠመንጃ የያዘው ብቻ ፩ሽ ፰፻ ወታደር ነበር ማጆር ቶዞሌ ይህን ነገር በቶሎ ሰማና ሠራዊቱን ሰብስቦ ይዞ በዚያ ወር አሥራ ሰባት ማዕረባ ወደ ሚባል ሰገነይቲ አጠገብ መጣ ደጃች ባሕታም ግን ራስ መንገሻ ስለቀሩባቸው እኔ ብቻዬን ከዚህ ቆይቼ መዋጋት አይቻለኝምና ወደ ሐላይ ሄጀ በሐላይ ያለን የኢጣልያን ብረትና ዕቃ ወስጄ ወደ ራስ መንገሻ እሄዳለሁ ብለው ሰገነይቲን ለቀው ወደ ወደ ሐላይ ሄዱ በፊት እንደ ተናገርን ሃይማኖታቸው ካቶሊክ የነበረ አብረው ያማከሯቸው የነፍስ አባታቸው አባ ክፍለ የሚባሉ የትግሬ ልጅ የላዛሪስት ማኅበር ፩ነ ወደሐላይ ሄዱና ከዚያ የነበሩ የትግሬ ልጅ አባ ተክለ አይማኖት ከላዛሪስት ማኅበር ከላዛሪስት ማኅበር ነበሩ ሁሉም በኢትዮጵያ ሀገራቸው ቅናት የተቃጠሉ ነበሩና ከደጃች ባሕታ ይመክሩ ነበሩ። በሐላይም የነበረ ካፒታኖ እጅግ ፈርቶ ነበርና እየተማመጠ ያታልላቸው ጀመረ እሽ እንዳላችሁኝ አደርጋለሁ ዕቃውንም ጠመጃውንም ውሰዱ የሚቀበሉኝ ሰዎችን ላኩ አላቸው። እነሱም ዕቃውንም ቆጥረው የሚቀበሉ ሰዎች ላኩለት ያው ካፒታኖ ግን ከማጆር ቶዞሊ መልክተኛ ደርሶለት ኑሮ እነዚያ ሰዎች ከቤቱ ሲገቡ ይዞ አሥራቸው ደጃች ባሕታ የሰደዳቸው ሰዎች እንደ ተያዙ

ሰሙና ሠራዊታቸውን ተነሥ ውጋ ተኩስ የሚል ቃል አሰሙ ሠራዊታቸው ተኩስ ሲዠምር ማጆር ቶዞሊ ከሰገነይቲ ገሥግሶ ፲፰ኛው ቀን በዚሁ ወር ተሰልፎ ሐላይ ላይ ደርሶ ደጃች ባሕታ ግን ገና ከዕለቱ ቄሶች ጋር ሲማከሩ ሳሉ የማጆር ቶዞሊ ወታደሮች ቀደም ብለው ገብተው ይተኩሱ ጀመር ደጃች ባሕታ በድንገት ስለሆነባቸው ፮ ሰዓት እንኳ ሊቃወሟቸው አልቻሉም ቢሆንም ጥቂት ተታኮሱና ከኢጣልያኖች ፲፩ ገደሉላቸው ፳፪ አቈሰሉላቸውና ከዚያ ወዲያ የደጃች ባሕታም ወታደሮች ተሻገሩና ተበታተኑ ደጃች ባሕታም ከጀግኖች ወታደሮቻቸው ጋር በሐላይ መንደር ፊታቸውን ሳይመልሱ ስለ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ተሠውተው በ፫ት ጥይት ተወግተው ከዘመዳቸው ከባሻይ ምስጉን ጋር ታኅሣሥ ፲፰ ፲፰፻፺፬ ዓ.ም በፈረ ቁ አረፉ (መተባበር ኖሮ ቢሆን ከራስ መንገሻና ከራስ ላሉላ ፩ኛቸው አንኳ ደርሰው ቢሆን ስንኳን ተከታትሎ ለመግደል ይቅርና ግራና ቀኝ ለማስተላለፍ እንኳ ያቅተው እንደነበረ ከላይ ወደ ትንንቲ ሳጐነይቲ ጄኔራል ባራቲሪ የጻፈው ደብዳቤ ያስረዳል ሆኖም ወንድ ልጅ ያባቱን ጠላት ሳይዘነጋ ልኩን ካሳየው በኋላ ቢሞትም ሞት ለጀግኖች የሕይወት ሐውልት ስለሆነ ደጃች ባሕታ ሐጎስ በኢጣልያኖች ልብ ላይ የኢትዮጵያን ጀግኖች የማያስተማምን ሐውልት ትቶላቸው ሄዶዋል። ግን ኢጣልያኖች ልብ የላቸውም እንጅ ልብአቸው ቢሆን ደበብንና ባሕታ ሐጐስን ከአዩ በኋላ ለኢትዮጵያ ጀግኖች አምነው የጦር መሳሪያ መስጠት ባልተገኘባቸውም ነበር) ደጃች ባሕታ ከሞቱ በኋላ አባ ተክለ ሃይማኖትንና አባ ክፍለ ማርያምን ኢጣልያኖች እጅግ አስጨንቀዋቸው ማለት በኢጣልያኖችና በላዛሪስቶች መካከል ጠብ ነበረና ሊደበድቧቸው ፈልገው ነበር በኋላም ላዛሪስቶችን ከኤርትራ አስለቅቀዋቸው አባ ተክለ ሃይማኖትን ምስክር አግኝተው ተዋቸው። አባ ክፍለ ማርያምን ግን በጽኑ ማሠሪያ አሥረው

## ሪ ሠሉስ

ሕይወቱን በሥር ቤት ይጨርስ ብለው ፈረዱባቸውና በአሰብ ወህኒ ቤት ታሥረው ሲኖሩ ፩ቀን መርዝ አጠጥተው ጣሏቸው አባ ሚካኤል የሚባሉ የካርበነራ አገር ሰው በቶሎ ወደ አሥመራ አመጧቸውና በዋስድባ በሚባል መንደር በዘመዶቻቸው መሀከል አረፉ (ይኸውና የሮማ ልዑካን የኢትዮጵያን ሰዎች ሃይማኖት እስክደን በዚያውም በኩል አገራቸውንም ይከዳሉ። እየመሰላቸው የማኅበሩን ገንዘብ እየተሸከሙ እየመጡ ይህን ያህል ሰበከን እያሉ እየመዘገቡ ወደ ሮማ እየላኩ የኔሮማንን ዘሮች እጅግ ደስ ያሰኛሉ።የሮማ ሰዎችም እውነት እየመሰላቸው እንደገና ገንዘባቸውን እያወጡ ይልካሉ ተታላዮች ናቸው እንጅ ገንዘባቸውን በከንቱ ያለምስጋና ማደል በድንጋይ ላይ የተዘራ ዘር ፍሬ እንደማይሰጥ የነሱ ስብከትም ምስሌው እንደዚሁ ነው። ሐሰት ነው የሚል ቢኖር ከላይ የተጻፉትን በካቶሊክ ሃይማኖት ገብተናል ብለው የነበሩትን ያባ ክፍለ ማርያምንና ያባ ተክለ ሃይማኖትን ታሪክ ያስተውል) ራስ መንገሻና ኢጣልያኖች በኰዓቲክ ላይ ያደረጉትን ጦርነት ራስ መንገሻ ዮሐንስ ከንጉሠ ነገሥት ምኒልክ ተስማምተው ከሹም አጋሜ ተስፋይ አብረው ሆነው በሹመዘር ዳርቻ አድርገው ከኢጣልያኖች ሊዋጉ ወስነው ነበር። ከደርቡሽ እዋጋለሁ እያሉ የኢጣልያኖች ወዳጅ እየመሰሉ ሠራዊታቸውን በእንትጦ ሰበሰቡ ነገር ግን ራስ መንገሻ ወደ ሹም አጋሜ ደብዳቤ ጻፉ ኢጣልያኖች ስለምን አገራችን መጥተው ሊገዙን ይፈልጋሉ። እኛ ግን በሐር ተሻግረን ልንገዛቸው አንችልም ስለዚህ በመጡበት ባሕር ወደ አገራቸው ሊመለሱ ይገባቸዋል የሚል ቃል ጽፈው ነበርና ይህ ወሬ ወደ ኢጣልያኖች ተሰማባቸውና ኢጣልያኖችም በዚህ ነገር አዘኑና ይሁን ግድ የለም። እያሉ ውሥጥ ውሥጡን ነገራቸውን ያበጁ ዠመር በራስ መንገሻ አደባባይ ነጭ እባብ ሲነክስ መዳኒቱ አይገኝለትም ጥቁር እባብ ሲነክስ መዳኒቱ በቶሎ ይገኛል እያሉ ልጃገሮዶቹ ይዘፍኑ ነበር ይባላል

ደጃች ባሕታ ከሞቱ በኋላ የሐማሴን ዤኔራል ለራስ መንገሻ የሚከተለውን ጻፈላቸው። “ክቡር ራስ መንገሻ ሆይ እኔ ነገሩን ሁሉ ትቸዋለሁና በእንትጮ ያሉትን ሠራዊቶችዎን ይበታትኗቸው በመካከላችንም ሰላም እንዲአደርጉ ይልቅ በፊት እንደተዋዋልነው ራስ ሐጎስ ወደ ትምራት ሄደው ሽፍታውን ደርቡሽ እንዲወጉ ስለ ደጃች ባሕታም እግዜር

ያጥናችሁ ጀኔራል ባራትሪ" ራስ መንገሻ ሳይመልሱላቸው ቀሩ (ከላይ የተጻፈው ራስ መንገሻ ዮሐንስ ስራቸው ሁሉ በጣም የረቀቀ ስለመሆኑ የጠላት ጸሐፊው እያረጋገጠው ይመጣል ማለት በውሥጣቸው የተዘሩ ሰባኪዎች ካፋቸው የሚወጣውን ሁሉ እየለቀሙ ቢአስቸግራቸው ከደርቡሽ ጋር ጦርነት አደርጋለሁ ብለው በእንትጮ ላይ ጦር ስለ አጠራቀሙ ኢጣልያኖች ስለሚያምኗቸው ያልተቸገረ መስሎ ጄኔራል ባራትሪ ይጽፍላቸዋል) በዓድዋ የነበረውን ትንንቲ ሙላዚንን ደጃች ባሕታ ሳጐነቴንን እንዳደረጉት ሰዎች ወደ ዓድዋ ልከውት ነበረ። ትንንቲ ሙላዝን ግን አስቀድሞ ዓድዋን ለቆ ወደ ኢጣልያ ግዛት ተሻግሮ ነበር ያንጊዜ ራስ መንገሻ ያጼ ዮሐንስ ልጅ ኃይለኛ መሆናቸው በሕዝብ ሁሉና በኤዲል ዘንድ ታውቀው ነበርና ደርቡሾች ስለ ተነሱባቸው ኢጣልያኖች ጦራቸውን አስከትተው ወደ ከሰላ ሄዱ ደርቡሾችንና ራስ መንገሻ ዮሐንስን ዋና ሆኖ ሊወጋ የተሾመ ጀኔራል ባራቲሪ ነበር እሱም ሠራዊቱን ሰብስቦ አሁን በትግሬና በከሰላ

# ራ ረቡዕ

በኩል በተነሳብን ጦርነት ደኅንነት የለምና መዘንጋት ብዙ አደጋ ይጥልብናል አትዘንጉ አይሰልቻሁ ጠንክሩ እያለ ያነቃቃቸው ነበር። ራስ መንገሻም የኢጣልያ ሠራዊት ወደ ከሰላ እስቲሄድ ድረስ በአካለ ጉዛይ ኢጣልያኖችን ከድቶ የሚመጣላቸውን ሰው እየተቀበሉ ከወሰኑ ላይ ሆነው አካለ ጉዛይን ለመያዝ ይጠብቁ ነበር ኢጣልያኖችም ራስ መንገሻ ኃሳቡን ደብቆ ብዙ ተስፋ ሰጥቶን አሁን በመጨረሻ ያላሰብነውን ብዙ ጉዳት ሊያመጣብን አስቧል እያሉ እጅግ ተጨንቀው ነበሩ። ሐጐስ ተፈሪ የአሳውርታን ጕሶች ይዘው መንገሻን ከድተው ለኢጣልያኖች አደሩ ይህ ክኅደት በማን አማካይነት ተሠራ ይሆን አገራቸውንም ሊወጉ ተነሱ ለጦርነትም የታዘዘው ወታደር ከመንደፈራ ሰፍሮ ነበርና አበጋዝ ጄኔራል ባራቲሪ ነገሩን ሁሉ በፍጥነት አከናውኖ የመንደፈራውንም እርድ የሚጠብቅ ብዙ ሠራዊት አስቀምጦ መረብንም የሚጠብቁ ከተቴ ወታደር ልኮ የሚአበራታታቸውንም ምክር ሰጥቶ ትእዛዝ አስተላልፎላቸው የመንደፈራንም ዕርድ በኰዶፎላሲ በኩል በስተምዕራብ ተራራ ነው። ኩዶ ፈላሲም ጥንት የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት የሚአርፍበት ከዓድዋ ወደ ምጥዋ አቋርጦ የሚአስኬድ ምንገድ በመካከሉ ይሄዳል ዓዲወግሪ አሥመራን ለመጠበቅ መልካም እርድ ናት ዓዲወግሪን የሚጠብቁ እርዶች የኃይላይና የማይ መፋልሶ ናቸው። ጄኔራል ባራቲሪ ራስ መንገሻን በፖለቲካ ለሰለል ወደ ዓድዋ ሊሄድ ወሰነ።


ራስ መንገሻ ግን እኔ ወደ አድዋ እመጣለሁና ደም ከመፍሰስ ብንታረቅ ይሻላል በፊት የተስማማውን መሐላ እናቆማለን ብሎ አስቀድሞ ጻፈላቸው ታኅሣሥ ፳፮ ፲፰፻፺፩ ዓ.ም በፈረ ቁ ወደ ዓድዋ ሊሄድ ሠራዊቱን በአካለ ጉዛይ ሰብስቦ ሳለ ማታውን ሕዝብ እንዳይነሳበት እንዲህ ብሎ ሰበላቸው እኛ አሁን ወደ ዓድዋ የምንሄደው ከሀበሾች ጋር ጦርነት ለማድረግ አይደለም ግን በፊት ከራስ መንገሻ ከትግሬ መኳንንት ጋራ በመረብ ወንዝ የተማማልነውን መሐላ ለማደስና ከሁለታችን የካደ እንዳለ ነገሩን ለመመርመርና ለመጠየቅ ነው የምንሄደው" እያለ በግልጥ ተናገረ ጄኔራል ባራቲሪ በዚሁ ወርበ፳፰ ቀን ወደ ዓድዋ ገባና ሠራዊቱም በድሮው ከተማ በምሥራቅና በምዕራብ መካከል ስፈረ ካህናቱና ሕዝቡም እንዳገሩ ልማድ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው መስቀላቸውንም ይዘው እንኳን ደህና ገቡ እያሉ ብዙ ሆነው ተቀበሉት ጀነራል ባራቲሪ ደግሞ የኢትዮጵያ ወዳጅ መስሎ በፖለቲካ እንደ ኢትዮጵያ መኳንንት መስቀል ስሞ እውነተኛ ሰው መስሎ ነበር አሳባቸው ግን ራስ ሐጎስ ወዳሉበት ከተማ ወደ ገንደብታ ለመሄድ ነበር ገና ከነሠራዊቱ ዓድዋ ላይ ሳለ የራስ መንገሻ ጀግኖች ወታደሮች እየተቃጠሉ ወደ ዓድዋ ገብተው የጄኔራልን ሠራዊት አስጨንቀው ነበር ጄኔራልም በፈረስ ተቀምጦ ወታደሮቹን አሰልፎ ዝም ብሎ ነበር ግን ያገሩ ገዥ እጨጌ ቲዎፍሎስና ነገሩን ያላወቁ ባላገሮች ቄሶች በ፩ድነት ሆነው ባራቲሪን ከበው አዳኑት ስለምን ባራቲሪ የመጣሁት ከራስ መንገሻ የተማማልነውን መሐላ ለማጽናትና ለመጠየቅ ነበር እንጂ ለጦርነት አልመጣሁም ፈቃዳችሁም ካልሆነ ዝም ብዬ ወደ ግዛቴ እመለሳለሁ

አሁን ግን እንዳይገድሉኝ ለምናችሁ አድኑኝ ስላለ ምንም ሳይነካ የአክሡምና የዓድዋ ካህናት ሰላይንቱን ስለ አላወቁ ባራቲሪን አራቁና ራስ መንገሻን ሰላም ያድርጉለት ብለው ብዙ ጣሩለት ነገር ግን ራስ መንገሻ

# ሬ ጎሙስ

አይሆንም ይልቅስ ወደ መጣበት ይመለስ አሏቸውና ባራቲሪም ነገሩን አይቶ ፩ ነገር ለማድረግ እንዳይቻለው አወቀና እሽ ብሎ በጥር ፪ ቀን ወደ ዓዲግራት ተመለሰ በዚያ ጊዜ ፩ ትልቅ ሥልጣን የነበረው ፈረንሳዊ ባለጋዜጣ ዲባት የሚባል። ኢጣልያኖች ወደ ምኒልክ ሥልጣን ገብተው ራስ መንገሻን ቀምተው ትግሬን ሁሉ ሊገዙና የኢትዮጵያ ምድር ሊወስዱ ወደ ዓድዋ ሄደዋል ብሎ ወሬውን ለዓለም ሁሉ ዘርግቶ ነበር የፈረንሳዊ መን ካጼ ምኒልክ ጋር ምስጢር ስለነበረው በኋላ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ አስቀድሞ አስታውቆ ነበርና የፈረንሳዊ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እስኙለር የሚባል የፈረንሳዊ መንግሥት የኢትዮጵያን መንግሥት በነገራቸው ሁሉ ሊተጋገዙና ፩ድነት እንዲያደርጉ የትግሬ አገርም እኛን እንደተጠጋች እናውቃለንና ኢጣልያኖች ሊቀሟት አንወድም ይኸውም ግፍ እንደሆነ እርግጥ ነው ኢትዮጵያም እኛን ተጠግታለች ብሎ ተናገረ ዲባትም ይህነን እንደሰማ ቶሎ ብሎ ለሁሉም በየሀገራቸው አስታወቃቸው። ጄኔራል ባራቲሪ ከማጆር ኬዳልጎ ተማከሩና ማጆር ኬዳልጎ ፯ ኩባንያና የሰራዬን ከተቴ ይዞ በሐዲስ እጅ ወደ ኮዓቲት ወገን ሊሄድ ተወሰነና ጥር ፫ በፈረ ቁ ተነሳ ከማጆር ኬዳልኮ ሠራዊት የሚበልጥ በዓዲቡግሪ ዕርድ ውስጥ ተሰብስቦ ነበር የራስ መንገሻ ሠራዊት ግን ጄኔራል ባራቲሪ ከዓድዋ እየተለማመጠ ወታደሮቹን ይዞ ወደ አዲውግሪ መመለሱ እንደገና ሊወጋቸው አልመሰላቸውም ነበር። ሕዝብ ሁሉ ባ፩ድነት ሆኖ መንግሥታችንንና እኛን ለሚጠሉ ሰዎች ቅድስት አገራችንን ሊገዙ ለባዕድ ሰዎች እግዚአብሔር አሳልፎ አይሰጣቸውም ኢትዮጵያ እግዚአብሔር የባረካት ሀገር ናትና አሳልፎ ለአረመኔ ንጉሥ አይሰጣትም ቢሰጣትም ለርሱ ንቀትና ልግጫ ይሆንበታል እያሉ በከተማ ሁሉ ይዘፍኑ ነበር ራስ መንገሻም እነዚሁ ጠላቶቻቸው እንደገና ተመልሰው ሊወጓቸው እንዳሰቡ አያውቁም ነበር። የራስ መንገሻም አሽከሮች ከዚያ አስቀድሞ በነጭች ድል ሆነው አያውቁም ነበርና ኢጣልያኖች እንኳን ቢወጉም ድል እንሆናለን ብለን አንፈራም እያሉ በፊታቸው ይፎክሩላቸው ነበር። እርሳቸውም

የአሽከሮቻቸውን ፉከራ እየሰሙ ኢጣልያኖችን ከኢትዮጵያ ደጋ አባረው እንደ ጥንቱ እስከ ባሕር ዳርቻ በጃቸው ይዘው ንጉሥ ሊባሉ አሳብ ነበራቸውና ይስቁ ነበር። ከዚህ በኋላ ወታደሮቻቸውን ሰብስበው አሁን ኢጣልያኖችን ልናስለቅቅ እናደርጋለንና በርትታችሁ ጥር ፲፪ ቀን ድረስ አከለ ጉዛይን ሁሉ ልትይዙ ተስፋ አለኝ ብለው አዋጅ አስለፈለፉ የአካለ ጉዛይን አውራጃ ሁሉ በባሕርዩ የታረደ እርድ ነው ስለዚህ ራስ መንገሻ ኰዓቲት ብዙ የሚያስቸግር በአቀብና በቁልቁለት ነውና ቶሎ ብለው ቀድመው በዚያ ቦታ ሆነው ጠላቶቻቸውን ለመውጋት ወታደሮቻቸውን አስታወቁ የባራቲሪ ሠራዊት ደግሞ ቶሎ ብለው ቀድመው የኰዓቲትን ተራሮች ይዘው ጠላቶቻቸውን ለመውጋት ተሰናድተው ነበር። ስለምን ኢጣልያኖች ዘወትር ደማቸው በትግሬዎች እጅ እየፈሰሰ ይሄዱ ነበርና በዚያች ቀን ግን ድል አድርገው የደማቸውን ዋጋ ሊያገኙ እልልታ ሊሆንላቸው ብዙ ተስፋ ነበራቸው ግን አጼ ምኒልክ ራስ መንገሻን ለማገዝ እንዳይመጡ ብለው ይፈሩ ነበር ጄኔራል ባራቲሪ ራስ መንገሻ ካጼ ምኒልክ ሳይስማሙ አልቀረምና ተጠንቀቁ ብቻ ወደ ሚኒስትሩ አስቀድሞ በስልክ አታውቆ ነበር። ራስ መንገሻ እንኳ ይዘን ብናስረው ኋላ እኛን የሚቃወሙ ሳይከተሉ አይቀሩም እያለ



ራስ መንገሻ ዮሐንስ ወደ ኮዓቲት ሲዘምቱ

## ር ዐርብ

ጽፎ ነበር ሁሉም አስቀድሞ ራስ መንገሻ ካጼ ምኒልክ ጋራ በእንጦጦ ከተማ በኛ ላይ የተማከሩት ምክር አለ። የኢጣልያን መንግሥት ከኤርትራ አስለቅቀው ራስ መንገሻን አንግሠው እስከ ምጥዋ ሊገዙ እንደተስማሙ ሰምቻለሁ።

ይህን ወሬ ከማን አገኘው? ከነዚያው የመነኮሴ ልብስ ከለበሱት አይደለም ይሆንን? (ይህን ነገር የሆነ ራስ መንገሻ ሊነግሥ ስለለመናቸው ነው አጼ ምኒልክም እንደምን አድርጌ አነግሥሀለሁ የሚያነግሥ ቦታ የለህም አጼ ዮሐንስ ይገዙት የነበረውን እስከ ምጥዋ ዳርቻ ብትይዝ አነግሥህ ነበር። አለዚያ ግን ትግሬን ሁሉ ጨርሰህ ካያዝህ ላነግሥህ አይቻልም ስላሉት ራስ መንገሻ እስከ ምጥዋ ትግሬን ሁሉ ለመንገሥ ከኢጣልያኖች ጋራ ሊዋጋ አስቦ ይፈልጋል እያለ ባራቲሪ ገና አስቀድሞ ያወራ ነበር። በዚያ ጊዜ ራስ መንገሻ ብዙ ጦርና መሳሪያ ስለ ነበራቸው በጐልበታቸው እጅግ ይኰሩ ነበር። የኢጣልያ ሠራዊት በቅናፍና ሆነው በለሳን ሲያጠቁ ሳሉ የራስ መንገሻ ሠራዊት የቅናፍናን ምንገድ ትተው ወደ ኮዓቲት አቅንተው ይገሠግሣሉ ማለትን ሰሙና በማጆር ኬዶልጎ የሚታዘዙ የኢጣልያ ሠራዊት የቅንፍን ዕርድ ትተው ወደ (አልባ ጥር ፲፩ ቀን ሊገሠግሡ ጀመሩ ደግሞ የቀሩት የኢጣልያ ሠራዊት ከዓዲወግሪና ከሰገነይቲ ወደ ኰዓቲት ሊሰበቡ ተያያዙ ሁሉም ባ፩ድ ስፍራ ተሰብስበው መከሩና ማጆር ቶዞሊ ሠራዊቱን ይዞ ፊታውራሪ ሆኖ ሲገባ ማጆር ኬልዳጎ ሠራዊቱን ይዞ በደጀን ሊገባ ሳሊመርየ የሠራየን ከተቴ ይዞ ግሮሶ መድፈኞችን ይዞ ካማጆር ኬዳልጎ ጋር በደጅን ሊገቡ ትንንቲ ሙላዚኒ ሠራዊቱን ይዞ በግራ ሊገቡ ተወሰነ። ፪ት ትልልቆች በጦሎኒ ጦር በነጋው ባ፬ት ሰዓት ተነሥተው ሊዋጉ ወደ ኰዓቲት ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ተደብቀው ነበሩ እነዚሁ ሠራዊት የሚያነዱትን እሳት በመሀከላቸው ያለ ተራራ አግዶት ነበርና ጢሱ አይታይም ነበረ ማጆር ኬዳልጎ በትንንቲ ከራበሪ የሚታዘዙትን ሠራዊት ልኮ በሰሜንና በምሥራቅ ወገን ባለው ተራራ ተቀምጠው ከእምብር አስንዲ አንስቶ ወደ ኰዓንቲት የሚያደርሰውን መንገድና በዚያው ያለውን ውሃ ይጠብቁ የነበሩትን በዚያች ሌሊት ከ፪ቱ ሠራዊት ፩ድ ስንኳ ጠበንጃ ሳይተኮስ አደረ የኢጣልያ ሰላዮች ራስ መንገሻ ነገ ወደ ኰዓቲት እይዛለሁ ብሎ ያለሀሳብ ዝም ብሎ ተኝቷል አሏቸው ራስ መንገሻም ኢጣልያ የኛን ሠራዊት አላወቀም እንጅ ነገ ጧት የሱን ሠራዊት የሚዋጉ የኛን ጀግኖች እናቀርብለታለን እናስተላልፍለታለን ይሉ ነበር። ምንም ቢቃረቡ በዚያ ሌሊት

የኢጣልያና የራስ መንገሻ ሠራዊት ሊዋጉ አልቻሉም ስለምን ያቦታ ጫካና ተራራ ነውና ወታደሮች ሌሊት ግሥጋሴ የማይመቻቸው ስለ ሆነ ነው ግን የኢጣልያ ወታደሮች በዚያ ዓመት ደጃች ባሕታንና ድርቡሾችንም ሸረው ነበርና ነኝአ እያሉ እየዘፈኑ እየተሠራሰሩ አደሩ የራስ መንገሻ ወታደሮችም ያነን ጫካና አቀብ ቁልቁለት ቦታ ስንቃቸውንና የሚዋጉበትን መሳሪያ ይዘው እንደተሸከሙ ሹልክልክ እያሉ ቶዞሊ ሳይሰማቸው ያነን ቦታ ጨርሰው ያዙት ሰልፋቸውም ብዙ አይታወቁም ነበር። የደጃች ባሕታ ወንድም አዝማች ሰንጋልና ፊታውራሪ ተስፋዬ የእኅታቸው ባል ባላምባራስ መንገሻ ደጀን ተሰልፈው ነበሩ። የኢጣልያ ሠራዊት ጥር ፲፫ በፈረ

## ሮ ቀደም

ቁ በ፱ ሰዓት ተነሥተው እስከ ፲ ሰዓት ከሩብ በየሰልፋቸው ጨርሰው ተሰለፉ የመድፈኞችም አለቃ ታኮዲኮለ ከራስ መንገሻ ፩ሽ ፱፻ ሜትር ባ፲፪ት ሰዓት ጧት ወደ ራስ መንገሻ ድንኳን አቅንቶ ይተኩስ ጀመር። የራስ መንገሻም ወታደሮች ባላገሮች ስለሆኑ በዚሁ በጫካ ቦታ እየተሹለከለኩ በፍጥነት በቀኝና በግራ በፊትና በኋላ እየጮሁ እንደ አንበጣ ወረሯቸውና ከኢጣልያ ወታደሮች ተደባልቀው አንገት አንገቱን እየያዙ በሚያስደነግጥ የጭካኔ ሥራ በጐራዴ እየጐመዱ ጣሉት። ባ፩ ሰዓት ከቀኝ ተሰልፈው የነበሩ የኢጣልያ ወታደሮች አለቁና የራስ መንገሻ ወታደሮች አለቁና የራስ መንገሻ ወታደሮች ደጀኑን ሰንጥቀው ሊከቡት ይዞሩ ነበሩ። ግን የኢጣልያ መድፈኞች አዩና ከነሱ ፩ሽ ፰፻ ኪሎ

ሜትር ርቀው መድፍ ለቀቁባቸውና ተመለሱ የኢጣልያ ሠራዊት ብዙ ተገፍተው ነበሩና እስከ ፫ ሰዓት አጅግ ተሰብረው ቆዩ ከ፫ ሰዓት በኋላ ግን የራስ መንገሻ ሰው ሊቀዘቅዝ ጀመረና ኢጣልያኖች ጥቂት ዕረፍት አገኙ ባ፭ኛው ሰአት ትንንቲ ሳጐንይቲና ትንንቲ ካስተላኒ ሰርጃንት በሮንቶዲያ ሰንደቅ ዓላማቸውን ይዘው ነበሩ ወታደሮች አለቁና የሰገነይቲ ሠራዊት ሊሸሹ ጀመሩ። ይህን ጊዜ ጀኔራል አሪሞንዲ በቶሊ ከደቡብ ወገን ከሰልፉ ተነሥቶ ሠራዊቱን ወደ ነሱ ገሠገሠና አቆማቸው የኢጣልያ ሠራዊት ጥቂት እንኳ ቢሆን ብረት ስለነበራቸው የራስ መንገሻ ወታደሮች ብዙዎች እንኳ ቢሆን ወግተዋቸው ሊአልፉ አልቻሉም ግን የተዋጋው ሰው ብዙ ነበረና ካቤሊሪ ቢርድያ የሚባል ሐኪም በመቃብር ግምብ ተጠግቶ መልእክተኞቹን እየላከ በቤተ ክርስቲያንና በዋርከው ተጠጋግተው የነበሩትን ቁስለኞች እያስጐተተ አምጥቶ ያከማቸው ነበር ራስ መንገሻም በሰሜን ወገን ሆነው ነጋሪታቸውን እያስመቱ በለው ይሉ ነበርና ድል አደረጉ ዋሉና አደሩ ጥር ፲፩ ቀን ከጀኔራል ጋር ሲታኮሱ ዋሉ በኰዓቲትና በንዴውጌ መኸከል ባለው ቦታ እንደፊተኛው ቀን እጅለጅ ተያይዘው ተፋጁ። ግን በዚያ ቀን ኢጣልያኖች ኢትዮጵያዎችን በመድፍ ገደሏቸው ምንም ብዙ ቢጐዱ የኢትዮጵያ ልጆች ፈጽመው እስቲያልቁ ጠንክረው ስለተዋጉ ኢጣልያኖች ተስፋ ቆርጠው ነበር። ግን ራስ መንገሻ ዮሐንስ ባ፲፩ኛው ቀን ሌሊት ላ፲፫ኛው ቀን አጥቢያ ኰዓቲት ትተው ወደ ሰነዓፌ ሊሸሹ ጀመሩ ፩ድ የኢጣልያ ወታደር ተማርኮ የነበረ በዚያ ሌሊት አምልጦና ወደ ኢጣልያ ሠራዊት ሰፈር ገባና ራስ መንገሻ እንግዲህ ከኢጣልያኖች ጋራ መዋጋት የማልችል ነኝ ብሎ ወደ ሰንዓፌ መሸሻቸውን አወራ ጀኔራል አሪሞንዲ ጡርምባ አስነፍቶ ራስ መንገሻ ወደ ሰነዓፌ ሸሽተዋልና እየሮጥህ ተከተለኝ ብሎ ሠራዊቱን አዞ የኢጣሊያን ሠራዊት ገሠገሠና አምባ ታሪኳ የራስ መንገሻ ሠራዊት በሡነዓፌ ሜዳ ሲበሉና ሲጠጡ አየ ከአምባ ታሪኳ እስከ ሰንዓፌ ሜዳ ርዝመቱ ፪ሺ ፬፻ ሜትር ነውና የኢጣልያ መድፈኞች መድፋቸውን ጠምደው ወደ ራስ መንገሻ አነጣጥረው በድንገት ለቀቁባቸው። ለጊዜው የራስ መንገሻ ሠራዊት ከሜዳው ወደ ጥግ ቦታ ሲዛወሩ የኢጣልያ ወታደሮች በቶሎ ደርሰው ከድንኳን ውስጥ ነጋሪቶችና ከብቶችም አግኝተው ወደ ጀኔራል ፊት ቀርበው ትንሽ ጊዜ ዘገዩና ወደዚያው በግሥጋሤ

ተመልሰዋል። ከዚያ ግን በኢጣልያኖች ሰፈር ደጃች ባሕታን ገደልን ራስ መንገሻ ኰዓቲት ላይ ድል አድርገን አባረርን እያሉ ከዓድዋ እስከ አዲግራት ከዓዲግራት እስከ መቀሌ ከመቀሌም እስከ አምባላጌ ድረስ ለመምጣት

# ሰ እሁድ

ቻሉ። ብቻ ፩ድ ነገር በራስ መንገሻ ድንኳን ውስጥ ባገልግል የተገኘ ደብዳቤ እነዚህም ደብዳቤዎች አጼ ምኒልክ ከራስ መንገሻ ራስ መንገሻ ከደጃች ባሕታ የተስማሙበት ነበረ ማለት ደጃች ባሕታ በራስ መንገሻ አጋዥነት። ራስ መንገሻ ባጼ ምኒልክ አጋዥነት ከኢጣልያኖች ለመዋጋት ነበር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን ቀረና ሁሉም ሳይገናኙ እንደዚህ ሆነ። ፪ኛው አጼ ምኒልክ ከጦርነቱ በፊት ለራስ መንገሻ እንደዚህ ሆነ። ፪ኛው አጼ ምኒልክ ከጦርነቱ በፊት ለራስ መንገሻ የጻፉቸው ራስ መንገሻ የንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ልጅ አስቀድሞ ኢጣልያኖችና ደርቡሾች እየተዋጉ ሰምቸ ነበር። አሁን ደግሞ በጽኑ ተያይዘዋል የሚል ጻፍሕልኝ የወትሮቹን ነውን የጻፍሕልኝ ወይስ ፪ኛውን ነው የዚህን እርግጡን እንድትጽፍልኝ። እኔ ግን ነገሬን ሁሉን ሁሉ ደብዳቤ ገልጬ ልጽፍልህ አይቻልምና ቁርጥ የሆነውን ነገር ሁሉ እንዲነግርህ በጅሮንድ ሃብቱን እሰድልሃለሁ። የቀረውንም እነግርሃለሁ ነገር ግን ኢጣልያኖችና ደርቡሾች ሊዋጉ ተሰናድተዋል ያልከኝን ይህም ነገራቸው እስቲያልቅ ድረስ ባልጋህ ተቀምጠህ ጠብቃቸው እንጂ ወደኔ እንዳትመጣ ዳግማዊ ምኒልክ መጋቢት ፪ ቀን መልእክት ራስ መንገሻ ያጼ ዮሐንስ ልጅ የድርቡሾችን ነገር ሁሉ ስለጻፍሕልኝ እጅግ አመሰግንሃለሁ አሳቤንም ሁሉ እንዲነግርህ በጅሮንድ ገብረ ሥላሴን እሰድልሃለሁ አጼ ምኒልክ ሚያዝያ ፲፰ ፫ኛ መልክት ራስ መንገሻ ያጼ ዮሐንስ ልጅ የጻፍሕልኝ ደብዳቤ ደረሰኝ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ዝናም ሳይዘንም ወዳገር በመምጣትህ በጣም ደስ አለኝ ነገር ግን በሰገነይቲ አምባ ሆነህ ስለጻፍክልኝ ነገር ለመሰናዳቱ እጅግ ተቸግሬአለሁ።


ጠላቶችህም ሁልጊዜ ወደኔ እየመጡ ይከሱሃል ነገር ግን አፍረው ቀሩ እንደተባባልነው ቀጥለህ እንድትሄድ እግዚአብሔር ካንተ ጋር ይሁን አጼ ምኒልክ ነሐሴ ፳፩ ፬ኛ ራስ መንገሻ ያጼ ዮሐንስ ልጅ የአከለ ጉዛይ ሕዝብ እንደተባባልነው ሳጐነይቲን አስረው ስልኩንም በጥሰውታል እኔም ደግሞ ከነደጃች ተድላ አባይ ጋር እሱን ለመርዳት እንነሳለን አንተም ወደ ተባባልነው ሥፍራ እንድንገናኝ በቶሎ እንድትነሣ ጊዜ ክቡር ነውና ፩ ቀንም ብታጠፉ እንደ ብዙ ቀን መሆኑን እወቅ ሹም አጋሜ ተስፉይ ወደ ራስ መንገሻ የጻፉት። ታኅሣሥ ፲፯ ቀን ራስ መንገሻ ያጼ ዮሐንስ ልጅ የኢጣልያ ጀኔራል በሠራዬ መሐከል አድርጎ ወደ ዓድዋ እንዲያልፍ አስታውቀውናል እደ ተባባልነው እኛ ተሰብስበን ልናመጣ አስበናል ጊዜው አሁን ይሻለናል ጊዜ ማጥፋት ከንቱ ነው። ስለዚህ ባ፩ድነት መክረን እኛ ከኋለኛው እናንተ ከፊቱ እንድንወጋው ክቡር ሆይ በዓድዋማ የገባ እንደሆነ ዙፋናችን በጁ ሆነ ማለት ነው አሁንም ላገራችን እንድንሠዋ ፈቃዳችን ገልጠን እናቀርባለን የሠራዬ የአረዛ መኳንንቶች ታኅሣሥ ፴ ቀን የራስ መንገሻ ሠራዊት ባለብረት ፲፬ ሺ ጦር የያዘው ፱ሺ ነበረ። ራስ መንገሻ በኰዓቲት ተዋጉና በ፪ ቀን ፩ሺ ወታደር ፳ መኳንንት ሞቱባቸው የመኳንንቱ ስም ደጃዝማች ተድላ ዓይባ ደጃች በየነ የራስ መንገሻ ዘመድ ደጃች ካሣ የራስ አሉላ ዘመድ ቀኛዝማች ፩ አርጋቸው ናቸው። የቆሰሉ ዙም አጋሜ ተስፉይ ከ፪፻ ወታደሮች ነበሩ በዚያ ጊዜ (አገሩን) ከዳተኛ ሐጐስ ተፈሪ የሰባጋዴስ ዘር ሹም አጋሜ ተስፋዬ ፪፻ ወታደሮች ይዞ ወደ ኢጣልያ ገብቶ ነበርና የአጋሜን ገዥነት ተሹሞ በአዲግራት ተቀምጦ ነበረ እስከ ጊዜው ይሾም እንጅ አገሩን

## ሱ ሰኑይ

የከዳ ሰው ኢጣልያኖችም በጣም አያምኑትምና እሱን የሚጠይቁ ፩ ትኒንቲና ፪፻ ወታደሮች በአዲግራት አስቀምጠውበት ነበር። የራስ መንገሻ ወታደሮች ግን ተምቤንና ወደ ዋዠራት ወደ ሽሬ ተበታትነው ነበሩ ከዚህ በኋላ ጀኔራል ባራቲሪ በማዠር ጋሊያኖ የሚታዘዙ ፬፻ የሚአክሉ ወታደሮች በሰነዓፌ ላይ

አስቀመጠ ሐጐስ ተፈሪንና እሱን የሚጠይቁ ትኒንትን በአዲግራት አስቀመጠ በጥር ፳፩ በፈረ ቁ በአከለ ጉዛይ አድርጎ አሥመራ ገባ የኰዓቲትን የሰንዓፌን ድል የያዘ ቴሌግራም የኢጣልያ ወታደሮች በኰዓቲትና በሰነዓፌ የሐበሻ ጨካኝ ወታደሮችን ድል ማድረጋቸው ከኢጣልያ አገር ላይ አዲስ ደስታና ትልቅ ሥልጣን ሆነ በትጋት መሥራትህ ደስ ብሎኛልና በልቤ አመሰግናለሁ ለመኳንንቶችም ለወታደሮችም ከነሱ ፫ እጥፍ የሚበልጡትን ጠላቶቻቸውን ያለ ፍርሃት ያለድንጋጼ ፫ ቀን ሙሉ ተዋግተው ድል ማድረጋቸውን እጅግ ደስ የሚአሰኝ ነውና የልቤንም ምስጋና አቅርብልኝ እንግዲህ ላንተና ላንተ የሚታዘዙ ወታደሮች በኤርትራ እያላችሁ ያች ከሎኒያችን ልትከብና ሌላ ድንገኛ ነገር ያገኛል ብዬ አልፈራም ሮማ ላይ ፩ኛው ዑምቤርቶ የኢጣልያ ንጉሥ ጥር ፲፰ ፲፰፻፹፯ ዓ.ም በፈረ ቁ ፪ኛ ቴሌግራም ሐበሻን ድል በማድረግህ ካንተና ከኢጣልያ ጋራ እጅግ ደስ ብሎኛል ደግሞ ወታደሮችን ብቻ አመስግኜ ዝም አልልም። ነገር ግን ዳግማዊ ጋሪባልዴ የሆነ ካፒታኖ ችኮዳከላ ከጥቂት ወታደሮች ጋራ ኃይለኞች ጠላቶቹን ድል ስላደረገ ምስጋና ይድረስለት ዛሬ የትግሬ አገር በር የተከፈተልን ምንም እንኳ ፈጽመን ባንይዛት ቀኖናችን ናት ሮማ ላይ ሚኒስቴር ክርስፔ ጥር ፲፰ ቀን በፈረ ቁ ጀኔራል ባራቲሪ ከጥቂት ቀን በኋላ የኰዓቲትንና የሰነዓፌን ሙያ በንጉሥ ሙያ ዘንድ ተቈጠረለትና ትኒንቲ ጀኔራል ተብሎ ተሾመ። ትኒንቲ ጀኔራል ባራቲሪ በ፳፫ ጥር ከአሥመራ ወደ ምጽዋ ወረደ ዠኔራል አሪሞንዲጎም ከብዙ መኳንንቶች ጋራ ከምጥዋ ወደ ሕጡብለ መጥቶ ሕዝቡን ሁሉ አሰልፎ በብዙ አጀብና በብዙ ክብር ተቀብለው በሐጡብላ የነበሩ ሕዝብ በሜዳው ተሰልፈው ወንዶችና ሴቶች ልጃገረዶችም እያጨበጨቡ በብዙ ዕልልታ ተቀብለውለት ወታደሮችም በሥርዓት ተሰልፈው ከራስ መንገሻ በትልቅ ክብርና በብዙ በብዙ ደስታ ተቀበሉት ጀኔራልም ባራቲሪም በክሰላና በኰዓቲት በሰነዓፌ ድል ስላገኘ ወርቅ መዳልያና ሐር ልብስ ለብሶ በፈረስ ተቀምጦ እየተፈነነና እየኮራ ወደ ምጥዋ ገባ እንደደረሰም አቅንቶ ወደ ቤ ክ ሄዶ በቤተ ክርስ በሚገባ ተሸልሞ ነበር። ሽልማቱም

ሕዝብን የሚያንቀሳቅስ ነበረ። ማለት ዘውድ በታቦት ላይ በቀኙም መስቀል በግራም ሰንደቅ ዓላማ ነበር በመስቀሉና በሰንደቅ ዓላማውም የኮዓቲትንና የሰነዓፌ ድል ተጽፎበት ነበር። በዚያም የነበሩ ካህን አባ ሚካኤል የካራቦናራ አገር የካፒችኒ ማኅበር ያን ጊዜ ቅዳሴ ቀደሱና እግዜርን አመሰገኑ ከቅዳሴም በኋላ አባ ሚካኤል ጋራ ቲንንቲ ጀኔራል ባራቲሪና ሕዝቡ በጉልበታቸው ተደፍተው ንሴብሖ ለእግዚአብሔር እያሉ በዜማ አመሰገኑ በዚያችም ቤተ ክርስቲያን መታሰቢያ የሚሆን ከኢጣልያ አገር ዕብነ በረድ አምጥተው የታቦት መንበር ሠሩላት በኰዓቲት የነበሩ ትኒንቲ ጀኔራል ባራቲሪ ሠራዊት ፫ሺ ፱፻ ፴፬ ነበሩ ከዚያ ከዚያ የሞቱ ፯ ነጮች ያገር መኳንንት ፪፻፺ ወታደሮች ናቸው። ያን ጊዜ ኢጣልያኖች ለሠራዊቱ



ልዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ መንግሥት ፡ ጠቅላይ ፡ የጦር ፡ ሚኒስቴር ፡ ወደ ፡ አድዋ ፡ ሲዘምቱ ።

# ሲ ሠሉስ

ገንዘብ ፳፱ ሺ የኢጣልያ ፍራንክ ነው። በ፳ ጥቅምት ፲፰፻፹፭ የግብጽ አቡን ኢትዮጵያ ጉዳት ይህን ተብሎ ልናስበው አይቻልም ነገሩ ለውስጥ በፖለቲካ የሆነ ነው ካ፲፰፻፹፰ ዓ.ም ጀምረው እስከ ፲፰፻፹፱ ዓ.ም ላዛሪስቶች ሉማኝ ከሚባል ኮንስላቸው ጋራ ሆነው ከንጉሡ ነገሥቱና ከራስ አሉላ እየተስማሙ ስለ ኢትዮጵያ ጥቅም እጅግ ይጥሩ ነበር። የላዛሪስቶች ማኅበር ከአባ ያዕቆብ ዠምረው እስካሁን ኢትዮጵያን ለመጉዳት ምንም አላሰቡም ነበር እነሆ የፈረንሳዊ ኮንስል የሚባል የላዛሪስቶች ማኅበር እየረዱት በኢትዮያ ዝም ብላ ተቀምጣ ያን ጊዜ የፈረንሳዊ ሚኒስተር የተሟገቱትን ሙግት በፖለቲክ ስለሆነ ገልጠን ልንጽፈው አንችልም ነገር ግን የላዛሪስቶችን ማኅበር ከኢትዮጵያ ግዛት በስተቀር በኤርትራ ውስጥ እንዳይቀመጡ ተከለከሉ የዚያን ጊዜ ደግሞ ፕሮቴስታንት የሪፐብሊክ ማኅበር

ሰላይ ሆነው ከእንግሊዝ ንጉሥ ተልከው በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀምጠው ከኢጣልያ እየተስማሙ የፖለቲክ ሥራ እየሠሩ የጐዱአትን ጉዳት ይህ ብለን ልናስበው አንችልም ነገሩ ፖለቲክ ስለሆነ ተሠውሯል ኢትዮጵያ ግን ከሊቃውንቶቿ ከልጆቿ አቡንነት ፩ድ እንኳ የሚመራት ስላጣች ሁል ጊዜ በባስደን ሰባክን ተጐድታ ትኖራለች የኢጣልያ ጀኔራል እንደገና ወደ ትግሬ አገር ተመልሶ ራስ መንገሻ ወዳሉበት እንደገና ትግሬ አገር ተመልሶ ራስ መንገሻ ወዳሉበት መጥቶ ሊወጋቸው በ፩ በጥቅምት ሠራዊቱን ይሰበስብ ጀመረ በዚያ ጊዜ ወሬው በመላ ኢትዮጵያ ተወራና አጼ ምኒልክ ከፈረንሳዊና ከሩሲያ መንግሥት ተስማምተው በጦር መሳሪያ አመጡና ኢጣልያኖችን ሊወጉ ተሰናድተዋል። የጀኔራል ባራቲሪ ሠራዊት ጥቅምት ቀን ወደ አዲጋራት ገባ። ራስ መንገሻም የኢጣልያ ሠራዊት አዲጋራት ገብቷል ቀጥሎም ወደ መቀሌ ይገሠግሣል ማለትን ሰሙና ጃንሆይ ሠራዊት እስኪደርስልኝ ወደ ወሎ ልጠጋ አሉና ከመቀሌ ወደ ህንጣሎ ሄዱ የኢጣልያ ሠራዊት በቶሎ ወደ መቀሌ መጣና መንገሻን ከተማ ይዞ በቶሎ እርድ ያርድ ጀመር ቀጥሎም ራስ መንገሻ በህንጣሎ አምጣ አሉ ማለት ሰማና ማጆር ቶዞሊ ሠራዊቱን በማይታወቅ መንገድ ዙሮ የህንጣሎን አምባ ከበባት ራስ መንገሻ ግን በሰላይ ሰምተው ኑሮ አስቀድመው ከዚህ ወጥተው ደብረ አላ ገብተው ነበሩ። ቶዞሊም ከተማውን ባዶዋን አገኛት አመሊዮ የሚባል የኢጣልያ ሰውን ይዞ እስከ ደብረ አላ ተከታተላቸውና የራስ መንገሻ መኳንንቶች መክረው ሽየዎች እስቲመጡ እኛ ደብረ አላን አንለቅም እርስዎ ይልቅ ወደ ራስ ወሌ ይሂዱ እኛ ከዚህ እንጠባበቃለን ብለው ቀርተው ሳሉ አመሊዮ ገሥግሶ መጣና ገጠማቸው እነሱም እስከ ጊዜው ጠንክረው ተዋግተው ነበር ግን ጊዜው አልፈቀደላቸውምን ድል ሆኑ በደብረ አላ ከአመሊዮ ጋራ የተዋጉ መኳንንቶች ተስፋይ ህንጣሎ አጋሜ ፪፻፶ ወታደሮች ወልደ ማርያም ፮፻ ወታደሮች ቀኛዝማች ኃይለ ማርያማ ወምበርታ ፪፻ ወታደሮች ቀኛዝማች አብርሃ ፶ ወታደሮች ደጃች ረዳ አባ ጉብራ የራስ አራያ ልጅ ፶ ወታደሮች ድምር ፩ሺ ወታደሮች ይዘው በዚያ ቀን ከኢጣልያ ወታደሮች የሞቱ ፲፩ የቆሰሉ ፴ ነበሩ። በዚያ ጊዜ የራስ ወሌና የራስ ሚካኤል ሠራዊት በወራይይሉ ተሰብስበው ራስ መኰንን ከሐረርጌ እስቲመጡ ይጠብቁ ነበር። ራስ መኰንን ከሐረርጌ መስከረም ፳፺ ቀን ተነሥተው ሲጓዙ የጦር ጠቅላይነቱን ተሹመው ከ፺ሺ

# ሳ ረቡዕ

ሠራዊት ጋር ከጃንሆይ ፊት ፊት እየተጓዙ በኅዳር ወር በአሸንጌና በቦሩ ሜዳ ሰፈሩ ጃንሆይም ራስ መኰንን እየተከተሉ ከ፴ሽ ወታደር ጋር ይጓዙ ነበርና ራስ መኰንን በዓለም መንግሥታት ሁሉ መካከል የቆመውን ድሮ እንተርናሽናል የሚባለውን ሕግና ደምብ አዋቂ ነበሩና በሳቸው እጅ ተይዘው የነበሩትን የውጭ አገር ዜጎች ለጃንሆይ ነግረው በክቡር እንዲያዙ አደረጉ። ያንጊዜም በሐረርጌ የነበሩ የኢጣልያ ዜጎች መንግሥታቸው ለኢትዮጵያ መንግሥት ጥሉን ካስታወቁ በኋላ ምንም ቢያዙ ክፉ ነገርና ችግር ሳያገኛቸው በደህና ይኖሩ ነበር። ኋላም በዓለም ሁሉና

በአውሮፓ እንደሚነገረው የሚሸኝ ሰው ሰጥተው በደህና አገራቸው አስወጧቸው ራስ መኰንን በዲፕሎማቲክና ትምህርት ስመ ጥሩ ታላቅ የሸዋ አርበኛ ነበሩ አጤ ምኒልክም በእውቀትም በጀግንነትም እንዲበልጡ አውቀው ይልቁንም በሥራቸው ሁሉ የታመነ የሠራዊታቸው ሁሉ ጠቅላይ የጦር አበጋዝ ሆኑ በሐበሻ ይቅርና በነጮችም ዘንድ ቢሆን እጅግ የተመሰገኑ ናቸው። ኢጣልያኖች የአፍሪካ መጽሐፍ በሚል ታሪካቸው ባ፩፻፵፰ ገጽ እንዲህ ይላቸዋል። ራስ መኰንን በማናቸውም ቢሆን ነገር የማይሠወራቸው ባለረቂቅ አእምሮ ናቸው የራስ መኰንን ስር የመንግሥት ደም የዞረበት ነበር። አጤ ምኒልክ እንኳ ቢሞቱ ከመኳንንቶቻቸው ሁሉ ለመንግሥት የተገቡ እሳቸው ነበሩ። ስለምን ራስ መኰንን የእግዜር ሰው ነበሩ መጠጥ አይወዱ ንጽሕናንም ይጠብቁ ነበር። ራስ መኰንን

ሥልጣን አለኝ ብለው በሕዝብ ላይ ተቆጥተው አያውቁም ነበር ራስ መኰንን ሁልጊዜ ከመኳንንቶች በላይ ካጼ ምኒልክ በታች ነበሩ ፩ድም ቀን የትዕቢት ምልክት አሳይተው አያውቁም እያሉ በራስ መኰንን ይደነቃሉ። እውነት ነው ለጌታቸው በታመነ አገልግሎት እየረዱ በአላጌና በመቀሌ በዓድዋ ዘመቻ ጊዜ በዓለም መንግሥታት የቆመውን ደምብና ሕግ እንደሚአዘው የሞተውን እያስቀበሩ የቆሰለውን እያስታመሙ ምርኮኛውም በከበሬታ ይይዙ ነበር እያሉ ያመሰግኗቸዋል። ራስ መኰንን አላጌ አምባ ላይ ሰፍሮ የነበረውን የማጆር ቶዘሊ ጭፍራ ጦርነት ሳይደርግ በእርቅ እንዲለቅ ብለው መክረው ነበር። ሳይሆንላቸው ቀረ ግን ለማጆር ቶዘሊ እንዲህ ብለው ጻፉለት ክቡር ማጆር ቶዘሊ ለጦርነት መጥቻለሁ ለውጊያውም የመጣውን ሠራዊት ወደ ኋላ ለመመለስ አይቻለኝም ግን ከበራቱሪ ጋራ ያለኝ ወዳጅነት መሀከለኛ ስለሆነ ለማስታረቅ አሳስቦኝ ነበር ስለዚህ ብየ ወደ ጀኔራል ብራቲሪን ለጻፍኩት ሁሉ ምላሽ ሳይመጣልኝ ስለቀረ ወደ ፊት መግፋት ግድ ሆኖብኛል ማለት ንጉሠ ነገሥቱም አሸንጌን አልፈው ወደዚህ ቀርበዋል። ከዚህ ሆኘ ልቆያቸው ብጽፍ የማይሆን ነው። የጦር ጠቅላይ ራስ መኰንን ታኅሣሥ ፫ ቀን ፲፰፻፹፰ ዓ.ም የቶዘሊ መልስ እጅግ የከበሩ የጦር ጠቅላይ ራስ መኰንን የባራቲሪን ምላሽ ይጠብቁኛል በታኅሣሥ ፪ ቀን ለተጻፈለት ደብዳቤ በዚሁ ወር ፬ ቀን ምላሽ ሰጥቶ መምጣት ጦርነት ለመፈለግ ነው። ወደፊት እገፋለሁ ስላሉ ወደፊት መምጣት ጦርነት ለመፈለግ ነው። ጦርነትም የሚያመጣውን ጉዳት ማንም ሰው ቢሆን ይህ ነው። ብሎ ለማወቅ አይችልም። ሰው ግን ይህን አደርጋለሁ ብሎ ለመነሳት ይቻላል። ፍጻሜው ግን በግዜር እጅ እንደሆነ ያስቡት በመቅደላና በሠሐጢ በመተማም ላይ የ፪ቱን ንጉሠ ነገሥት ነገር ምን እንደሆነ እንደ ተጻፈ ይወቁት ፫ኛውን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሰሎሞን አልጋ



ልዑል ራስ መኰንን አምባ አላጌ ላይ የኢጣልያን አዝማች ጀነራል ቶዜሊን ድል አድርገው እንደገደሉ

# ሴ ኃሙስ

ላይ ዘውድ እንዲጭን ቢአግዝ አሁን የዛሬ ፺ ዓመት ያደረጉትን እርዳታ ሁሉ ለማጥፋት ይቻላቸዋል ማጆር ቶዞሊ በታኅሣሥ ፬ እንዲህ ያለ ምላሽ ሲልክላቸው ራስ መኰንን ገሥግሠው መጥተው ቶዞሊን ለመውጋት በታኅሣሥ ፯ ቀን ሠራዊታቸውን ይዘው ወደ አላጌ አምባ ወጡ። ሰልፋቸውም የራስ መኰንንና የራስ ሚካኤል ጦር በመካከል የራስ ወሌ ጦር በግራ የራስ መንገሻና የራስ አሉላ ጦር በቀኝ ተሰልፈው ባ፲፪ ሰዓት ገቡ። የራስ ወሌ ጦር ባ፩ ሰዓት ጀመረና የራስ ስብሐትን የኤልያስን የካኖቤቴን ጦር ኦር እያለ ገባና ፈጅቶ ድል አደረገ የራስ መኰንንና የራስ ሚካእልም ጦር መሐል ለመሐል ሰንጥቆ ገብቶ በጐራዴ እንደ ብርንዶ ሥጋ ጨፈጨፈው ትንንቲ ሞሪንና ባራል የሚባሉትን ሹማምንቶች ጐማመዳቸው ወታደሮቻቸውንም ፈጅተው ድል አደረጓቸው። ግን ፋቲካኖቲ አቤል ከራስ ወሌ ሸሽቶ ወደ መድፈኞች ገብቶ ስለነበረ በአምባ ሆነው እስከ ፬ ሰዓት ተታኰሱ ከዚህ በኋላ የራስ መንገሻና የራስ አሉላ ሠራዊት በቀኝ ገብቶ በቶጎራ ምንገድ ዞሮ ከበባቸውና ካአምባ ወረደ። ያንጊዜ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሥጋ እንዳየ አሞራ ኦር እያሉ ያሰሟቸው ነበር ያንጊዜ የኢትዮጵያ ወታደሮች ሥጋ እንዳየ አሞራ ኦር እያሉ ያሰሟቸው ነበር ያንጊዜ ሼየዎች ለነፍሳቸው ምንም ሳይፈሩ ወደ መድፈኞች እንደሮጡ እንደ እሳት ቃጠሎ ነበሩ። የቶዞሊ ሰዎች ተስፋ ቆርጠው በ፯ ሰዓት ሩብ ጉዳይ በዝሳራ ምንገድ አቅንተው ሊሸሹ ጀመር የኢትዮጵያ ወታደሮችም መሸሻቸውን ባዩ ጊዜ እየተከታተሉ ይፈጅዋቸው ጀመር የሚሸሸበት ቁልቁለት ርዝመቱ ፬፻ ሜትር ነበር ምንገዱም እጅግ ጠባብ ነበርና ከብቱ ፩ድ ላይ ተደባልቆ ተጨንቆ ስለ የራስ መንገሻ የራስ አሉላ ሠራዊት የራስ መኰንንም ሠራዊት ፩ድ ጊዜ እህል እንዳየ አንበጣ ሰፈረባቸውና አጠፋው። የተረፉትም የኢጣልያ ወታደሮች የሸየዎችን ፉከራና ሽለላ እየሰሙ ስለ ተጨነቁ ከብቶቻቸውን ይዘው ከነጠመንጃቸው ገደል እየገቡ አለቁ። ያን ቀን በመጣው ጦርነት የባሰባቸው በትንቲ

እስከለ የሚታዘዙ ሱዳኖች ናቸው ከአላጌ ጦርነት እንደምንም ሸሽቶ ያመለጠ ሁሉ ባ፲ ሰዓት መቀሌ ደረሱ ፳ የሚያህሉ ነጮች ምንገዱ ጠፍቶባቸው ወደ አዲግራት ገቡ ፫ኛ ፍሻሌው ከማጆር ቶዞሊ በሬሳዎ ዙሪያ አእምሮአቸው ተለውጦ ቁመው ተገኙ ትንንቲጋቢን በራስ አሉላ ዘንድ ተማርኮ ተገኘ የቆሰሉና የካኖባቲ የነበሩት ሠራዊት ፩ሺ ፩፻ ነበሩ። ከ፭ ሰዎች በተቀር የቀረው አለቀ ባ፲፭ኛ ቦጠሎኒም ፩ሺ ሰው አለቀ ከማጆር ቶዞሊም ፲፻፶፲ ሰው አለቀ ቶዞሊና ሐኪም ጅያኮፒቱሊቱሎችም ነጮች ሙተው ተገኙ። የሞቱት ሰዎች ድምር ፪ሺ ፱፻፶፪ ነው ከመቀሌ የነበሩ ኢጣልያኖች ፩ ማጆር ከነሠራዊቱ በእርድ ውስጥ ሆኖ ጠላቶቹን ሊከላከል ይቆይ ብለው ያለዚያ እያባረሩ እስከ ምጥዋ ያባረሩናል ብለው ታኅሣሥ ፳ ቀን ከመቀሌ ተነሥተው ወደ አዲጋራት ሄዱ። የአጋሜ ሰው ሁሉ የአሪምንዲን ሠራዊት እየተከተለ ይፈጃቸው ነበር። ከኢትዮጵያ ወገን የሞቱ ምድር ፪ሺ ሰዎች ናቸው። ግን ከሸየዎች ወገን ብዙ አልቆ ስለነበርና ሸየዎች ስለወንድሞቻቸው እያለቀሱ ቢያስቸግሩ ራስ መኰንን በሕዝቡ መካከል ቁመው ሞትና ኃዘን አይደለም ደስታችንና ክብራችን ነውና ይልቅ ፎክሩ ዝፈኑ እንጅ አታልቅሱ ብለው ከለከሏቸውና በኋላ ጀግኖች የሆኑት ሁሉ ወደ ራስ መኰንን ድንኳን እየሄዱ እጅ እየነሱ የሠራዊቱን ሙያ እየቆጠሩ ይፎክሩ ዠመር። በዚያ በድንኳን ውስጥ ተማርከው

# ስ ዓርብ

የነበሩ ነጮች በዚህ ፉከራ አዝነው በጣም ልባቸው ቆስሎ ነበር ማለት እነሱ ድል ሆነው ተማርከው ስለተፎከረባቸው ነው። የባሰ ንዴታቸው ደግሞ ከነሱ ተማርኮ የነበረ ፪ መድፍና ፯ ጭነት ብረት ደግሞ ብዙ የተሰበረ ነበርና በፊታቸው አቅርበው ፈትሹ የተሰበረውን አብጁ ቢሏቸው ነው። ራስ መኰንን በድንኳናቸው ተማርኮ የነበረውን ትንንቲን ባርቲ። የሚባል ኢጣልያ ጥራ ብለው አስጠርተው ጉዱን ለማየት አንተ ይህን የተሰበረ ብረት እንድታበጀው

ቢሉት ወዲያው መልሶ በድፍረት ቃል እምቢ አላቸው። ራስ መኰንንም በዚህ ሰው ንግግር እጅግ ተደነቁ ራስ መኰንን ቶዞናን ከዚያ አብረው የሞቱትን ባልንጀሮቹን ሁሉ እንደሚገባ አስገንዘው በታላቅ አጀብ ሰልፍ አድርገው አስቀበሯቸው። ደግሞ ቁስለኞችንና ምርኮኞችን በክብር ይዘው አስቀመጧቸው።

ይህም ነገር በኢጣልያና በመላው ዓለም አውሮፓ ተሰማና ኢትዮጵያ የክርስቲያን አገር መሆንዋ ኢትርናሺዎናል የሚአዘውን ደምብና ሕግጋት መጠበቋ ተመሠከረላት የመንግሥትም ኃይል በዓለም ታወቀ (ታሪክን ሰሪው ራሱ ባለቤቱ ነው ጸሐፊው ግን ባለጋራውና ጠላቱ ነው። ይህም እስመ ስምዖን ጻር እሙን ውእቱ እንዳለው ይህ የልዑል ራስ መኰንን ታሪክ በጣም የሚአስደንቅ በእግዚአብሔርም ዘንድ የማይነቀፍ ፈሪሃ እግዚአብሔር የጠበቀ እንደማር የጣፈጠ ታሪክ ሲገኝ ያስደንቃል። ይህ እንደወርቅ ጠርቶ ይገኛል። ታሪክ እንደዚህ ታሪክ ሲሆን ነው። ከዚህ በኋላ መኰንን ከአላጌ ተነሥተው ወደ መቀሌ ተጓዙና እንደደረሱ የኢጣልያ ጦር ዕዳ ኢየሱስ ከሚባል ቦታ በጣም መሽጎና ደርጅቶ አገኙት መዠመሪያ በዕርቅ ምንገድ ዕርዱን እንዲለቅ ተከራከሩት እምቢ ቢል ጦርነት ገጠሙት ብዙ ጀግኖች ምሽጉን እናፈርሳለን ብለው ሲጣጣሩ ከዚያ አለቁ ኋላ ግን መኳንንቱ ሁሉ መክሮ ምሽጉን ማፍረስ ባልቸገረንም ነበር ግን እሱ መውጣቱ ላይቀር ዙሪያውን ከበን ውኃና እንጨት ልንከለክለው ይቻላል አሉና መከሩ ሁሉንም ከበው ያዙት እውነትም እንዳሉት እሱ ራሱ እንታረቅ ብሎ ላከባቸው ራስ መኰንንም የሁለቱ አገር ክርስቲያን ደም በከንቱ በረኃብ ከሚያልቅ ጦርነትም ፪ኛ ላያደርግ የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ለቆ እንዲሄድ በዚህ ውል ከጀኔራል ባራቲሪ ካስማማህኝና ካስታረቅህኝ እሽ ምን ከፋ ጥንቱንስ ቢሆን አገራችን እንቀማችሁ አላችሁን እንጅ እኛ አገራችሁ መጥተን ካገራችሁ እንውሰድ አላልንም። አሁንም

ይህን ውል ካደረግን እንለቅሃለን አሉት እሱም በዚህ ውል ምሎ በጥር ፳፩ ፲፰፻፹፰ ዓ.ም በፈረ ቁ ዕርዱን ለቆ ሄደ ጃንሆይም ቁም ነገር እንዳይሠራ አወቀው ከነወታደሩና ከነመሳሪያው ልቀቁት አሉ። ማጆር ጋሊያኖ ከሰዎቹ ጋር ሲገናኝ እንደማስማማትና እንደማስታረቅ ምኒልክ የያዘውና ያስከተለው ሁሉ ዱላ የያዘ ወታደርና አህያ አጋሰስ ብቻ ነውብሎ ነገሩን እንደገና አጠንክረው ጀኔራል ባራቲሪም ከዋናው ሁዊቱ ጋራ ወደ እንተጨው መጥቶ ሠፈረ ጃንሆይ ግን አሳባቸው ሁሉ ዕርቅ ነበርና ምንም ሠራዊታቸው ቢበዛ ኃይልና ብርታትም ቢሰማቸው የክርስቲያን ደም በከንቱ እንዳይፈስ ብለው ፴ ቀን ሙሉ ሳያቋርጡ ዕርቅ እንዲደረግ አጥብቀው ዱቼልራ ባራቲሪን ቢጠይቁ እሱ ግን በኩራትና በንቀት ዕርቅን እምቢ ብሎ ቀረና በኋላም



አባ መቻል ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ።



የግቢው ፡ መድፎች ፡ ሰልፍ ።



ግርማዊ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒሊክ በአድዋ ጦርነት ላይ




እቴጌ ጣይቱ ብጡል

# ሶ ቀዳም

ምኒልክ ዱላና ጩቤ ይዞ መጥቷል እኔ ግን መድፍና መትረየስ የያዙ አርበኞችን ይዤ እቀጥላለሁ ሳላሸንፈውም አልቀር እያለ የትምክህት ቃል ተናገረ በመካከሉም የደረረደሩትን ሳይጨርስ በሌሊት ገሥግሶ አደጋ ሊጥልባቸው መክሮ ሳለ ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጎስ ተፈሪ ያከለ ጉዛይን ባላገር ሁሉ ሰብስበው ከኢጣልያ ከድተው በስተኋላ የነበረውን ነጭ ወታደርን ፈጅተው የስልኩን ሽቦ በጥሰው ከንቺሊጎኖ ቸጨኖ የሚባሉ ነጮች ማርከው ነጋሪቱ የተባለውን ፈረንጅ ከ፪ ወታደር ጋር ገድለው ወደ አጼ ምኒልክ ገቡ።

ከላይም የዚህ ሥራ ነገር ተመልክቶ ይገኛል አሁንም በነ ደበብ በነባሕታ ሐጐስ የሚያስታውሱ ደጃች ስብሐትና ደጃች ሐጐስ ተፈሪ ቀን ሲጠብቁ ቆይተው ሲሞላላቸው እንደዚህ ያለ ሥራ ሠርተው በገዛ መሳሪያው አፈር አስግጠውት ወደ አገራቸው ሲመለሱ እያየ ለኢትዮጵያዊ አምኖ መሳሪያ መሥጠት እንደ መታወር ያለ ነው። ምን ሲዋልለት ሲሸለም ቢውል ኢትዮጵያዊ አገሩን ክብሩን ይረሳል ማለት ከንቱ ነው።


የዓድዋ ጦርነት ጃንሆይ አጼ ምኒልክ በርቅ ምንገድ ብዙ ደከሙና ሳይሆን ቀረ እንዲያውም ፊት መጥተው አደጋ ሊጥሉባቸው እንደ መከሩ ሰሙና የካቲት ፳፫ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም በኢትዮጵያ ቁ ዓድዋ ላይ ገሥግሠው ኢጣልያኖችን ጦርነት ገጠሙ የኢጣልያ ጀኔራል ዳርቦሜዳ በቀኝ ጀኔራል አሮበርቶን በግራ ጀኔራል አሪሞዲ በመሐል ጀኔራል ጋሊና በደጀን ጀኔራል ላምበርቱ ጀኔራል ብርጋዲዩር ሌሎችም ጀኔራሎችም ሆነው በጎቤርር ባራቲሪ ጋር ተሰልፈው ነበር የጃንሆይ ሠራዊት ፹ሺ ነበር ፶ሺ የሚያህሉ የሸዋ ወታደሮች የኢጣልያኖችንና ሰልፍ ባዩ ጊዜ ሮጠው ከብብ አድርገው በጕራዴ አንገት አንገቱን እያሉ በጨቤ ሆድ ሆዱን እየተበተቡ ፈጅዋቸው። ያን ጊዜ የኢጣልያ ሠራዊት በዕዳ ማርያም ሸዊን በአባ ገሪማ ሜዳ ያለራስ አይታይም ነበር። ያጼ ምኒልክ ሠራዊት ጥይት እንደ በረዶ ይወርድ ነበር ነገር ግን በዚያ ቀን የኢትዮጵያ ሠራዊትና የኢጣልያ ሠራዊት ተደባልቆ ነበር ሌላውም የማን እንደሆነ አይተዋወቅም ነበር። የኢትዮጵያ ጀግኖች ፯ ሰዓት ሲሆን ፈጽመው ኢጣልያኖችን ድል አደረጉ የተረፉ ኢጣልያኖች ሲሸሹ የሸዋ ጋላ በፈረስ እየተከታተለ ፬፻ ሜትር እየራቀ የደከመውን እየማረከ የሮጠውን እየገደለ በጕራዴ ይፈጀው ነበር። በመጨረሻም በመቀሌ ምሎ የነበረውን ማጆር ጋሊያኖን ማርከው እልል ለኢትዮጵያ እያሉ ያጠቁ ነበር። ነገር ግን ከአበሻ ከድተው ወደ ኢጣልያ ሆነው አጼ ምኒልክን የወጉ ብዙ የትግሬ ልጆች ተማርከው ነበርና እነዚህ አገራቸውን የካዱ ለዓለም ዝክር እንዲሆን ግራ እግራቸውንና እጃቸውን እየቀረጣችሁ ልቀቋቸው ብለው ዓዋጅ ነገሩና እየተቆረጡ ወደቁ ማዦር ጋሊያኖም

ምሎ የካደ ነውና ይሰቀል በቃ ተፈርዶበት ተሰቀለ የቀሩት ኢጣልያኖች ፪፻ ነጮች ተማርከው ወደ ሸዋ ተመለሱ ግንቦት ፲፬ ቀን አጼ ምኒልክ የማረኩትን ዕቃና መሣሪያ አሲዘው ወደ አዲስ አበባ ከዓድዋ ተነሱና። በታላቅ ክብርና በደስታ በብዙ ዕልልታ አዲስ አበባ ገቡ። (ከዚህ በኋላ የኢጣልያ ጉራ ሁሉ በረደ

# ቀ እኁድ

ልክ ገባ። አጼ ምኒልክም ከዓድዋ የተመለሱበት የሮማው ፓፓ የእግዚአብሔርን ስም እየጠሩ የጠበቀ የምልጃ ደብዳቤ ልከውባቸው ወደፊት ስለ ሚሆነው ጉዳይ ነገሩ እስቲወሰን ሠራዊቱ የሚጎዳባቸው ስለሆነ እምቢ ካሉም እመለሳለሁ በማለት ነው)። የሮማው ፓፓ መልክት የሮማው ፓፓ ፲፫ኛ ልዩን በኢጣልያ አገር ያሉት የምርኮኞቹ ቤተ ሰቦቹ እያለቀሱ ስለአስቸገሩአቸውና ለራሳቸውም ወገኖቻቸው በመሆናቸው ምርኮኞቹ በነፃ እንዲለቁ ሲሉ ሊቀ ጳጳሳትንና ክርስቲያንነት የተደገፈ የልመና ደብዳቤ አሲዘው ሞንሲዘው ሞንሲኛር ማካሪዮን ወደ አጼ ምኒልክ ላኩ። ከደብዳቤውም ይበልጥ ለኃያሉ የኢትዮጵያ ንጉሡ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ሰላም ለእርስዎ ይሁን ክርስቶስያዊ በሆነው

ልብዎ የምመክርዎን አመዛዝነው የልግሥና ሥራ እንዲአደርጉ እለምንዎታለሁ። የዚህ ዘመቻ ድል በእጅዎ ብዙ የኢጣልያ ምርኮኞች አሳልፎ ሰጥቶዎታል። የነዚህ የኢጣልያኖች መማረክ በዚህ አገር ያሉትን በሽ የሚቆጠሩትን የእናቶቻቸውንና የሚስቶቻቸውን ልብ ኃዘንና ጭንቀት ከማበርከት በቀር ምንም ያህል ግርማዊነትዎን ኃይልና ዝና ሊያስፋፋ አይችልም። እኛም ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበልነው አደራ እንደ ልጃችን ያህል እንወዳቸዋለንና እነዚህ ምርኮኞች በቶሎ በነጻ እንዲለቀቁልን በቅድስት ሥላሴና በድንግል ማርያም ወይም በዓለም ካለው ከሚወዱት ስም እለምንዎታለሁ ኃያሉ ንጉሠ ነገሥት ሆይ ይህንም የምለምንዎትን እንደ ክፉ ሰው እምቢ ማለትዎ በመንግሥታት ፊት የተገለጸ አይሁን ይህችን የተከበረች ደብዳቤዬን ለምስክር እታሪክዎ ያግቧት በዚህም በሚያደርጉት የቸርነት ሥራ እርኅሩኅና የሁሉ አባት እግዚአብሔር ይከሥዎታል ከዚህ በተቀር በብዙ በሚቆጠሩ ሰዎች ሊያመሰግኑዎ ድምፃቸውን ያነሳሉ ከነዚህም መጀመሪያዎቹ እኛ ነን። ይህ የልመና ቃል እንዲፈጸም በተስፋ ከመጠባበቅ ጋር ልዑል እግዚአብሔርን በንጉሠ ነገሥቱና በቤተ ሰቦቹ ላይ በረከቱን እንዲያወርድ እንጸልያለን ሮማ በቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክ ግንቦት ፲፩ ፲፰፻፺፯ ዓ.ም በፈረ ቁ ልዮን ፖፖ ፲፫ኛ። (በሮማ ፖፖ አማካይነት ሰላም ይሁን ተብሎ ኢጣልያኖች የኢትዮጵያን ወሰን ላይ ነኩ ተወስኖ ይሁን ተብሎ ኢጣልያኖች የኢትዮጵያን ወሰን ላይ ነኩ ተወስኖ ካ፲፰፻፹፰ እስከ ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ድረስ ፵፱ ዘመን ሙሉ ከቆየ በኋላ የኢትዮጵያን ማጥፊያ ሲያሰናዳ ኖሮ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በየሀገሩም የሚልካቸውን ሰባክያንና ኮንስሎችን በሚአሠራው ፖለቲክ የኢትዮጵያን ውስጥ ለውስጥ እየከፋፈለ በሀገሩም ላይ ለኢትዮጵያ ማጥቂያ የሚሆን መሣሪያ እያሰናዳ ከቆየ በኋላ ጦርነት የሚአነሳበት ምክንያት እየፈለገ ነገር ቢሞክር ኢትዮጵያ በትዕግሥት እየተቀበለች ዘወትር ስለምትሸኘው ያነኑ ያሰበውን ነገር ለመግለጽ ጊዜ ሲሞላለት መግለጡ ግድ ሆነ በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያን ሊጐድዋት የቻሉ በቸልታ በር የገቡ ፪ት ነገሮች ናቸው። ፩ኛ የሮማ ልዑካን ከገቡ ዝምሮ በየጊዜው የሚደረገውን በንጉሠ ነገሥቱና በመሳፍንቱ በመኳንንቱ በቤተ ክርስቲያን በየገዳማቱ በየአድባራቱ የተሠራውን ጠብ ይህም የሃይማኖት ቁጥር የበዛው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠብና ክርክር የበረከተው ከመቼ ዝምሮ እንደሆነ አሁን ለአንባቢዎች የማቀርበው ፩ድ ቁርጠኛ ቃል አለ ይህም እንደዚህ ነው። በየተቻላችሁ እንድትመረምሩ እነሱ ከማምጣታቸው በፊት በተጻፈው ጽሑፍ ስለ ሃይማኖት መለያየት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምታገኙ እንደሆነ በቤተ ክህነት



የኢትዮጵያ ሰማዕት ብፁዕ ዳግማዊ ጴጥሮስ ማለት የኔሮን ልጆች የታላቁን ጴጥሮስ ልጅ ጴጥሮስን እንደገደሉ በግፍ።



ይህም ፡ ከሰባኪያዎቹ ፩ዱ፡ ነው፡ይሆን ፡ እየመሰለ፡የኢትዮጵያን፡ሕዝብ ፡ ያመነመነ፡ ይሆንነው ።
አንባቢ ፡ ሆይ ፡ ያባ ፡ ማሳያ ፡ ምዕል ፡ መልክ ፡ ተሰወጠ ፡ ብለህ ፡ እትደነቅ ፡ ይልቁንስ ፡
ይህን ፡ የባሕታዊ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡ በውምጡ ፡ የኢጣሊያ ፡ መንግሥት ፡ የዋና ፡ ተዋጊ ፡
ትጥቅ ፡ ያለው ፡ መሆኑን ፡ ዕወቅ ።

# ቁ ሰኑይ

ጠብና ክርክር ቂምና በቀል በቤተ መንግሥቱም እንደዚህ ውስጥ ውስጡን እየሰበኩ ሰውና ሰውን ለያይተውት ፩ድ ምክንያት ሲአገኝ ወደ ኢጣልያ መግባት ሃይማኖቱንም መለወጥ ይህ ሁሉ ነገር አስቀድሞ ያልነበረ መሆኑን እንድትገነዘቡ ነው። ይህ ከላይ ያመጣሁት ከ፪ቱ ፩ኛው ያልኩት አስቀድሞ በረቂቅ የተወረወረው ጦር አባ በርሙዴዝ የተባለው ሮማዊ ባጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ዝምሮ ማኅበር አቋቁሞ አስተላልፎላቸው የሄደው የመርዝ ተክል ነው። ፪ኛው ባጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ኢትዮጵያ በሃይማኖት ፩ድ እንድትሆን አስበው በተነሱ ጊዜ እስላሙንም ክርስቲያንነት የጠላ አገሬን ይልቀቅ በሀገሬ ላይ ልዩ አስተማሪ አይፍቅድም ብለው በቆራጥነት በተነሱ ጊዜ አባ ማስያስ ከነተከታዮቻቸው እስላሞችን ድጋፍ በማድረግና ደግሞ ባንድ ጎን ወደ አጼ ምኒልክ በሥውር ገብተው የማታለያ ስብከታቸውን ባቀረቡ ጊዜ ይህን የጠላት ስብከት ባለማወቅና በመታለል በተቀበሏቸው ጊዜ አባ ማስያስ ይህን ከተደገፉ በኋላ የኢጣልያን ጦር ምጽዋ ላይ አስቀመጡ። ይህ ምጥዋ ላይ የተተከለው የመርዝ ተክል አፍርቶ ባዩ ጊዜ ብዙ ኢትዮጵያውያን ረኃባቸውን መታገሥ ያልቻሉ ሁሉ ያነን እየበሉ ብዙዎች አልቀዋል ያባ ማስያስ መታሰቢያ ምጿ ላይ በሮማ መንግሥት ስም የተተከለው ተክል ከበርሙዴዝ ተክል ጋራ እየተባበሩ ሁለቱ ነገሮች ኢትዮጵያን ለመደምደሰስ በየጊዜው እየተነሱ አሉ ከላይ ሁለት ነገሮች አሉ ያልኩት እነዝህን ማለቴ ነው። የአባ በርሙዴዝ ተክል የአባ ማስያስ ተክል ጀኔራል ፖዞሊን ነው። ጄኔራል ፖዞሊን ሳይገባ እነ አባ ማስያስ ያባ ማስያስ ተክል እነ አንቶኖሊ ናቸው። በነሱ መሪነት አስቀድሞ የጦሩ አለቃ ጄኔራል ፕዞሊን ሳይመጣ በሸ፳፻፸፬ ዓ.ም በፈረ ቁ በኢት በሸ፳፻፸፩ ዓ.ም አጼ ዮሐንስ እያሉ ስለ አሰብ በር ካጼ ምኒልክ ፲፰ ክፍል ውል የተዋዋሉ እነ አባ ምስያስ ከነከታዮቻቸው ሆነው ነው የሮማው መንግሥት ያገር ግዛት ሚኒስቴር የላከው የጦር አለቃ ጄኔራል ፖዞሊን ምጽዋ የገባው በሸ፳፻፸፰ ዓ.ም በኢት ቁ ነው የሮማ ልዑካን እኛን ለማታለል መንፈሳውያን ነን እያሉ በጃቸው መስቀልና መጽሐፍ እየጨበጡ በሆዳቸው ውስጥ ግን የሕዝብ መፍጃ መርዝ እየያዙ እየመጡ እስከ ዛሬ እንደዚሁ እንደሠሩብን አሉ። እንግዲህ ያባ ቤርሙዴዝ ተከታዮች መንፈሳውያን ከሆኑ ካጼ ምኒልክ ጋራ በተዋዋሉት ባ፲፰ቱ ክፍሎች የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ ማስተዋል የተገባ ነው። እነዚህን ፲፰ እርስቶች ሁሉ ለተመለከታቸው ሰው ካ፩ኛው ክፍል በተቀር የቀሩት ስለ መንግሥት አስተዳደር ነው የሚናገሩት ፩ኛው ክፍል የሚለው እንደዚህ ነው። በሸዋ አገር ሃይማኖት ሌላ ሃይማኖት እንዳያስተምር ክልክል ነበርና አሁን ሁለቱ አገሮች ያለመፍራት በነፃነት የሃይማኖት እውነተኛነት ትምህርት እንዲማሩ በትልቁ መንግሥት ሥልጣን ተፈቅዷል ይላል። ይህንን ውል የተዋዋለ ለሮማ መንግሥት የላከውን ያገር ግዛት እንደራሴ ነበር። እንዳይባል በኢትዮጵያ ላይ ባጼ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት የኢጣልያ መንግሥት ቆንስል አልነበረም ምክንያቱም በዚያ ዘመን የሮማ መንግሥት የተለያየ ስለነበረ ነው ስንኳን ቆንስል ሰባኪ ነን የሚሉትንም ተከልክለዋል። መከልከላቸውንም በዚሁ ባ፩ኛው ክፍል ሌላ ሃይማኖት ማስተማር ክልክል ስለነበረ ይላል እሽ ይሁን የነአባ ማስያስ ሰዎች አይደሉም የሮማ መንግሥት ያገር

# ቂ ሠሉስ

ግዛት ሚኒስቴር ሠራተኛ ነው። የተባለም እንደሆነ በዚያው በተባለው ቦታ አስፈላጊውን ጉዳይ ይፈጽማል እንጅ ከማያገባው ቦታ ሸዋ ድረስ መጥቶ እውነተኛ ሃይማኖት ላስተምር ውል ይግባልኝ ማለትን ምን አመጣ ብለን ብንመረምር ማን ይከለክለናል መንፈሳዊ ሰባኪ ነን በሚሉትም ወገን ያልተገባ ነገር የመንግሥት ሥራ የሆነ በ፲፯ ክፍሎች ይገኛሉ በሥጋዊ ወገን ደግሞ ፩ኛው ክፍል የሃይማኖት ስብከት

ይላል። ከላይ እነዚህን ፪ቱን ልዩ የሆኑ ነገሮች መርምረን ማስማማት ግድ አለብን ማስማማት ማለት ሰዎች ከሁለት አለቆች የተላኩልን መስለው ቢገኙም ሥጋዊና መንፈሳዊ በሮማ ላይ የተለየ ሲሆን በኛ አገር የተስማሙ መሆናቸውን ማስተዋል ለኢትዮጵያ ልጆች ይገባቸዋል ይህም መስማማት ማኅበር ማለት ነው። እኔ የምደክመው የሮማ ልዑካን ሥራችን መንፈሳዊ ነው እያሉ ወገኖቻችንን ሲአታልሉ ስለሚኖሩ እነዚህ የሮማ ልዑካን የመንፈሳውያን ልብስ ለብሰው የሚሠሩት ሥራ የጦር ፕሮፓጋርድ መሆኑን ሥራቸውን ሁሉ እየተከተልኩ መርምሬ ለወገኖቼ ለመግለጽ ነው። ከላይ እንደተጻፈው ይህ ማኅበር የቆመበትን ሐተታ አመልክቻለሁ ይህ ምጽዋ ላይ በሸ፲፻፹፫ ዓ.ም በፈአ ቀ የገባው የጦር አለቃ በነዚህ በማኅበሩ ስብከት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ አለ ራስ አሉላ የዶክሪቶፎሪስን ፫፻ ወታደሮች በተደዓሌ ላይ በጨረሷቸው ጊዜ የሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሮቤላቴን ካጼ ምኒልክ ጋራ ሆነው። አጼ ምኒልክን ይሰብክ ወደ ነበረው ወደ ኮንት አንቶኖሊ የጻፈው ደብዳቤ ያስረዳል ከላይም ተጽፎ ይገኛል አሁንም ልጽፈው ፈቀድሁ። ወንድሞቼ ሆይ በጥብቅ ተመልከቱት የኢጣልያ ልጆች ክቡር ደማቸው በኢትዮጵያ ምድር ከፈሰሰ አሳባችን ሁልጊዜ ኢትዮጵያን በእጃችን ለመያዝ ነውና የበለጠው ነገር ማኅበራችን በኢትዮጵያ ገብታ የፖለቲክ ሥራ መሥራት ነው። ይህች መልእክት የምታመጣልን ፍሬ መጀመሪያ ከንጉሥ ምኒልክ ከነመሣሪያዎቹ ሁሉ እኛን ተከትሎ ካጼ ዮሐንስ መጣላቱ ነው ፪ኛ የበለጠ ነገር እርስዎ በዚያው ሥፍራ ሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገና የሚደረግ ነገር ሁሉ ለመንግሥታችን ማስታወቅ ነው አሁን በክቡርነትዎ በዚሁ የተሠሩትን ነገሮች ሁሉ ገልጠው በቶሎ እንዲጽፉልን እለምንዎታለሁ ደግሞ ፩ድ ዋና ነገር ንጉሥ ምኒልክ ከኛ ጋራ አብሮ በእንግድነታችን ጊዜ ከንጉሠ ነገሥት ዮሐንስ ለመዋጋት የተሰናዳ መሆኑን ይጠይቁት ፫ኛ ከኛ ጋራ ከተዋጋ በኋላ የሚመጣውን ጥቅምና ፍሬ የሚፈልገውን እንደምን እንደሆነ ይጠይቁት ፬ኛ እኛ አጼ ዮሐንስን በግድ አስለቅቀን በሰሜን ወገን ሁሉ ለንጉሥ ምኒልክ ትልቅ ሥልጣን ለመሥራትና ፩ድ ፩ድ ነገር ለማገዝ እንችላለን አጼ ዮሐንስ እምቢ ያሉ እንደሆን እሱ እኛን ተከትሎ በኛ ሥልጣን እንዲጠበቅ ያስታውቁት። ይህን ሁሉ ነገር አስረግጠው ምላሽን እንዲጽፉልኝ እጠብቅዎታለሁ። ሮቤላንቴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ፲፩ መጋቢት ፲፰፻፹፯ ዓ.ም በፈረ ቁ (ይኸውና ከላይ የተጻፈውን ሁሉ ማስተዋል የተገባ ስለሆነ የሮማ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የጻፈውን መረጃ አስተውሉ የጻፋቸው ፫ አርእስቶች ናቸው ከነዚሁ ፩ኛው ስለማኅበሩ የጻፈው ነው ምን አለ አሳባችን ሁልጊዜ ኢትዮጵያን በእጃችን ለመያዝ ነውና የበለጠው ነገር ማኅበራችን በኢትዮጵያ ገብታ የፖለቲክ ሥራ መሥራት ነው። ካለም በኋላ ይህች መልእክታችን የምታመጣልን ፍሬ

## ቃ ረቡዕ

መጀመሪያ ንጉሥ ምኒልክ ከነመሣሪያዎቹ እኛን ተከትሎ ካጼ ዮሐንስ በመጣላቱ ነው አለ። እንግድህ ይህን ነገር ስትመለከቱ ይህች ማኅበር የተባለች ሥራ የሮማ የጦር ፕሮፓጋንድ ሥራ አይደለም ለማለት እንደምን ይቻላል ይህንስ አስተውሎ ካየ በኋላ እንደምን ያለ አእምሮ ነው። እነሱ ከውስጥ የሕዝቡን ልብ በፖለቲክ እየማረኩ ከጨረሱት በኋላ ማለት ውስጥ ለውሥጥ እየለያዩ እያበጁ ይሰጡታል ከኋላ የሮማ መንግሥት በየጊዜው ብልጫ ያለውን መሣሪያ እያመጣ ሕዝባችንን ጨረሰው። በዚህ ምክንያት ያለቁትን ወገኖቻችንን ማስታወስ ስለሚገባን ፩ኛ ባጼ ሚናስ በነሱ ምክንያት በተነሳው ፪ኛ በበሐር ነጋሽ ይስሐቅ ምክንያት በሐር ነጋሽ ወደ ቱርክ ቆንስል ተጠግቶ በተደረገው ጦርነት ከግራ ቀኙ ውስጥ በግምት ፪ት ሺ ሰዎች ፫ኛ ባጼ ዘድንልግ። አጼ ዘድንግልን ካቶሊክ ሆኑ ተብለው እንደ አጼ ያዕቆብ ተይዘው እንዲታሠሩ ቢታሰብ አልያዝም በማለት ጦርነት ተነሣና ከግራ ቀኝ የሞቱ ሰዎች ፩ሽ ፲፻ በሐር ነጋሽ

ይስሐቅ ኢትዮጵያ በግራኝ ጦርነት ጊዜ በጣም አድርጎ ያገለገለው ሙቷል አጼ ዘድንግልም የንጉሠ ነገሥቱ ዘር እንዳልሆነ ሆኖ ሙቷል እነዚህ የ፪ቱ ሰዎች ሞት ብቻ ጉዳቱ ምን ያህል ነው ፬ኛ ባጼ ሱስንዮስ በጐጃም በትግሬ በበጌምድር በላስታ በሰቆጣ በሸዋ ያለቀው ሕዝብ በቀላሉ ከ፺ሽ በታች አይደለም ሲደረግ ባ፩ ቀን ወይም ባ፩ ዓመት

ተደረገ በማለት አይደለም በካቶሊክ ሃይማኖት ከገባ በኋላ ፲፪ ዘመኖች ሁሉ በያመቱ በየወሩ በየሥፍራው የተደረገውን ፩ድ ታሪክ ላይ የሚገኘውን ያለቁለትን ካህናት ቁጥር ለይተው እስከ ፲፪ ሽ ደርሰዋል እኔ ግን አመዛዝኜ በቀላል ግምት ፵ሺ አልኩት ፫ኛ ከዚህ ወዲህም በየጊዜው በሚያስነሱት ጦርነት ይቀጥላል ባጼ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የተቢኑን አቤቶ ዘማርያምን የላስታውን መልክን ማርያምን አሸፍተው የ፪ቱም አጼ ፋሲል ጦርነት አድርገዋል። ከ፪ቱ ሰዎች ከግራ ቀኙ ፩፫፻ ሰው ካጼ ሚናስ እስከ አጼ ፋሲል በሮማ ልዑካን ረቂቅ ተንኮል ያለቁ ኢትዮጵያውያን ቁጥር በቀላል ግምት ከተጻፈው ድምር ፶፫ሽ ፪፻ ነው የዚህን ያህል ሕዝብ ደም ያስፈሰሱ በመንፈሳዊ ቦታ ቆምን እያሉ የመንፈሳዊ ልብስ ለብሰው መስቀልና መጽሐፍ እየያዙ ይልቁንም የመንፈሳዊ አባት ነን ሲሉ ይገኛል። ከላይ የተጻፉት ፶፫ሽ ፪፻ ሰዎች ደም በቀላል ይሆንን ይህም በቀላል ግምት ነው እንጅ በእውነት እነሱ ከመጡ ወዲህ በረቂቅ ፖለቲክ ያለቁት ሁሉ በ፶፫ሽ ፪፻ ነፍስ ብቻ መወሰኑን ማን አወቀ።

ከ፲፰፻፸፰ ዓ.ም  እስከ ሽ፰፻፹፰ ዓ.ም የተደረገው ጦርነቶች

፩ኛ ራስ አሉላ ተደዓሊ ላይ።

፪ኛ ደጃች ደበብ ሰገነይቲ ላይ።

፫ኛ ደጃች ባሕታ ሐጐስ።

፬ኛ ራስ መንገሻ ዮሐንስ በኰዓቲት ላይ።

፭ኛ የራስ መንገሻ ዮሐንስ ሰዎች።

፮ኛ ልዑል ራስ መኰንን ያጼ ምኒልክ የጦር ሚኒስቴር አምባላጌ ላይ።

፯ኛ ራስ ስብሐትና ደጃች ሐጐስ ተፈሪ።

፰ኛ የዓድዋ ጦርነት በነዚህ ጦርነቶች ሁሉ የሚአልቀው ከቀኝም ከግራም እየሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። በነዚህ ሁሉ ጦርነቶች ያለቁ ወገኖቻችን በግምት ከ፬ሽ የሚአንሱ አይደሉም ከላይ

## ቁ ኃሙስ

ከጻፍናቸው ሰዎች ጋራ ሲደመር ፩፻፶፫ሽ ከ፪፻ ይሆናል። የነዚህ የወገኖቻችን ደም እንደዚህ እንደ ውኃ ፍሶ ሲቀር የጠላቶቻችንም ልብ የሚቀን ስለዚህ ነው። እነሱ ከሩቅ አገር ድረስ መጥተው የሰው አገር በኃይል ካልቀማን ብለው ሲጋደሉ የሞቱትን ወንድሞቻቸውን ደም ለመቀበል ፴ ዘመን ሙሉ አስበውና አደራጅተው ጠላቶቻችን የመጡበትን ምክንያት ወደ ሥር ገብተን መርምረን ጽፈን ለመጭው ትውልድ አለማስቀመጣችን ፪ኛም ከላይ በተዘረዘሩ ቦታዎች ላይ በጦርነት ለሞቱ ወገኖቻችን መታሰቢያ ሐውልት አለማቆማችን። ከዚህም ሁሉ በልጦ የሚታይ ለዚህ ሁሉ ነገር የሞተ መሪ ሆነው የመጡብን የነዚህን የሮማ ልዑካን ሲያያዝ መጥቶ የቆየንን የሀገራችንን ሃይማኖት እየካድን የነሱን ሃይማኖት እየተከተልን

የመንፈሳዊ አባት አድርገን ስንጓዝ እንገኛለ ምንገዶች ሁለት ናቸው። ፩ኛው ወደቀኝ ፪ኛው ወደ ግራ ቤተ ክርስቲያናችንም ሁለት ሆኑ። ቀኝ ማለት የትኛይቱ ናት ግራ ማለትስ የትኛይቱ ናት ከግራ ያለችቱ በሰው ደም ታጥባለች ይህች ሰው እየፈለገች በሰው ጭዳ የተቋቋመችቱ ቤተ ክርስቲያን በግራ በኩል አይደለችም የሚል ልቡና ያለው ሰው ይኖር ይሆንን። ይህችን በሰው ደም ላይ የታነጸች ቤተ ክርስቲያን ያልኩትን የሚቃወሙ ሰዎች ነገሩ ያልገባቸው አይታጡምና ነገሩን በጣም እንዳስረዳቸው አልታከትም ማለት እነሱ በቅን ልቦናቸው መስቀልና መጽሐፍ መያዛቸውን

የመጽሐፍ አነባበባቸውን ስላዩ የእውነተኛ ሃይማኖት ገተኘ የሚሉ ወሬ ስለ ሰሙ በእውነት ፈጣሪያአቸውን ለመለመን ወደ ሮማ ልዑካን ቤተ ጸሎት እየሄዱ ልመናቸውን ወደ ፈጣሪያቸው ሲአቀርቡ ስለማያቸው በጣም አዝናለሁ። ስለዚህ ለወገኖች መረጃ እንዳያንሳቸው መረጃውን በሰፊው አመጣለሁ ማለት የሮማ ልዑካን ሥራ መንፈሳዊ ብቻ ነው እንጅ ሥጋዊነት የለውም በዚህ አገር እያስገደድን ባላባቱን እየገደልን ሕዝቡን ባርያ አድርገን እንገዛለን እያለ በተነሣው ሥራ ውስጥ የሉም ለሚሉ ሰዎች መረጃዎችን አመጣለሁ። ፩ኛ በመዠመሪያ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን አጥፍተው የነሱን ቤተ ክርስቲያን ለማቆም በመጀመሪያ አጼ ሚናስናን ፪ኛ ያዕቆብን ፫ኛ አጼ ሱስንዮስን ከሃይማኖታችሁ ሃይማኖታችን ይበልጣል። ከጥምቀታችሁ ጥምቀታችን ከቤተ ክርስቲያናችሁ ቤተ ክርስቲያናችን። ከመጽሐፋችሁ መጽሐፋችን ይበልጣል የጦር መሳሪያ እናመጣላችኋለን እያሉ እንደገና እያጠመቁ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እያራቁ ለመሥራታቸው ሐሰት ለሚል የሚቀርብለት መረጃ በኢጣልያ የተጻፈውን አስተውሎ ማንበብ አለበት። በዚህ ምክንያት የፈሰሰውን ደም ከኔ ካአላዋቂው አንደበት በተሻለው በዋና ሊቅ የተጻፈውን አይቶ እንደኔ ለመረዳት ይችላል። ስለ ምክሬ ለወገኖቼ በትሕትና አስረዳለሁ። ፪ኛ መረጃ ከላይ እንደተጻፈው አጼ ዮሐንስ ሳይሞቱ ፲፰፻፸፫ ዓ.ም በተዋዋሉት በ፫ኛ ክፍል በ፲፰፻፹፩ ዓ.ም በውጫሌ ላይ በተዋዋሉት በ፱ነኛ ክፍል በነዚሁ በ፪ቱ አገሮች ያሉትን ሕዝብ እውነተኛ ሃይማኖት በግልጥ ለማስተማር በሙሉ ሥልጣን ፈቅዷል ይላል። የሚዋዋሉም በሁለቱም ጊዜ ያለው አንቶኖሊ መሆኑ የሚካድ አይደለም። አንቶኖሊ ከማኅበረ ልዑካን ቁጥር የነበረው ሰባኪ አልነበረም የሚል ቢኖር ከላይ የተጻፈውን የሮማውን የውጭ ጉዳይ

# ቅ ዓርብ

ሚኒስቴር የጻፈውን ደብዳቤ ይመልከት። እስቲ እውነት ከሆነ ከሮማ ፓፓ የተላከ ፩ድ ደብዳቤ ደግሞ ከነዚህ ከሮማ ልዑካን ወደ ሮማው ፓፓ የተላከ ደብዳቤ ምንም አይገኝም ግን ስለ ፩ድ ጽሑፍ ነገር ያውም የኛን ለማኮሰስና ወደ ኋላ ለማስቀረት የነሱን ለማክበርና ቀዳሚ ለማድረግ የሮማውን ፓፓ ፲፩ኛ ፒዮስን ሲያወሳ ፩ድ ቦታ ላይ ይገኛል ቢገኝም ቅሉ የሮማው ጳጳስ ኢትዮጵያ በተወረረች ጊዜ የሮማው ፓፓ ጦርነቱን ባርኮ ወደ ኢትዮጵያ መስደዱን ዓለምም ያውቀዋል የታሪክ መጽሐፍቶች በየጊዜው የተቀበሉትን እንደያዙ ይገኛሉ ከላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎቻቸውን ሁሉ ሳንመለከት በቸልታ ዝም ብለን እነሱ በመሩን እየተከተልን ስንጓዝ ፵ ዘመን ሙሉ እየተዘዋወሩ መርምረው ካዩ በኋላ ያነኑ ቀድሞ ባጼ ዮሐንስ ያሰቡትን ባጼ ምኒልክ የዠመሩትን የተንኮል አሳብ አስበውና አደላድለው የኢትዮጵያን ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ለመደምሰስ የኢትዮጵያን ታሪክ ለማርከስ የሕዝቡን ደም ለማፍሰስ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ተነሳች ያነኑ የግፍ የተጀመረውን ሥራቸውን ቀጠሉና የኢትዮጵያን ጀግኖች በጦር መሳሪያ እንደማይችሉ ያውቃሉና ከመድፍ ከታንክ ከመትረየስ በላይ ከአውሮፕላን ተኩስ ወይም ቦምብ ከዚህ ሁሉ በላይ በዓለም ላይ ክልክል በሆነ በመርዝና ጢስ በጦር ሜዳ ያልቆሙትን በሀገር ቤት ያሉትን ከብቶችንና ሰዎችንና ሰዎችን አሸብራ በሰሜንና በደቡብ በኩል ያስነሳቸውን ጦር በየከተማዎች ለጊዜው

የኢትዮጵያን ንጉሠ ነገሥትም እውነተኛው ሕግ አዋቂ የጀግናው የራስ መኰንን ልጅ በመሆናቸው ሕግን እስከ ፍጻሜው ለማየት ወደ ዓለም ማኅበር አቤቱታ ወደ አውሮፓ ተሻገሩ ጀግኖቻቸውም በየጫካቸው መሠማራት ጀመሩ። ጠላት በዚህ ጊዜ ከተማ ገብቶ ካየ በኋላ እውነት ኢትዮጵያን በጭራሽ ድል አድርጌ የያዝኩ መሠለውና የወደቀውን ዕቃ ሁሉ መለቃቀም ጀመረና የከተማውን ዕቃ ካጠራ በኋላ ወንዶች ወዳሉበት ስፍራ እያቋረጠ ለመሄድ በዠመረ ጊዜ የኢትዮጵያ ጀግኖች እንደ ንብ እየንደፉ ይጥሉት ዠመር ኢትዮጵያን ድል አድርጌ ያዝኩ ብሎ ለዓለም መንግሥታት አስታውቆ የነበረው እንደገና ሬሳውን በአውሮፕላን እየጫነ ወደ ሮማ ያግዝ ጀመር በዚህ ጊዜ መውጫውም ቸገረው መሄጃውም ቸገረው በሁለት ወገን ዘሎ ሲገባ የመውጫውን ነገር አላሰበም ነበር። የኢትዮጵያ ጀግኖች ከዱር እስከ

ዱር መሳሪያቸውን ይዘው በተነሱ ጊዜ። ደግሞ በበኩላቸው የሮማ ልዑካን በተለመደው የፖለቲክ መሳሪያቸው ያዙት የሕዝቡን ልብ በጽሑፍ እያደረጉ የስብከት መዓት ያወረዱበት ጀመር በዚህ ጊዜ ከጋላውም አካፈለና እስላሙም የነሱን ስብከት ይሰማ ጀመር እንደዚህም ጀግኖች እየተከላከሉ በቀኝም ቢሄድ በግራ ሬሳ ሳይዝ የማይመለስ ሲሆን እያዩት ኢትዮጵያ የቆመች እንደሆን የሚሉ አሳብ አልነበራቸውም እንዲያውም አዲስ ዓለም እንደተከፈተ ተቆጥሮ የሮማ ቤተ መንግሥት ሠራተኞች ለብቻ የቤተ ክህነቱም በዚህ ነገር ስለተደሰተ ለብቻው የሞሶሎኒም ለብቻው ሁሉም ለየራሳቸው መከፋፈል ጀምረው ነበር ባዶ መሬትና ቤት በማግኘታቸው ተደስተው ስለነበር በከተማ ከተገኙ መኳንንቶች እያሡሩ በሥውር ቦታ መግደል ጀመሩ በዚህ ጊዜ ጭራሽ በከተማ ገብቶ የነበረው ሁሉ ወደ ጫካ ገባ። በጫካ የገባውን ሁሉ እየተከታተልን እንገድላለን ሲሉ (የኢትዮጵያ አርበኞች በሐርና ገደል ዛፍና ዱር የማያግዳቸው እንደ አሞራ እዚያ ማዶ የጥይት

# ቆ ቀደም

ተኩስ አሰምተው ዞረው ከኋላ ካለው ገድለው ስለሚሄዱ እነሱን ማግኘት ሳይቻል ጊዜ ባቀረቡ የሚገኙትን ሴቶችና ሽማግሌዎችን አብያተ ክርስቲያናቱን ማቃጠል ሆነ። በዚያ ጊዜ የሮማ ልዑካን ከጦር ሠራዊት ጋራ ተባብረው በየክፍሉ ሀገሩ ላይ ቤተ ክርስቲያን አቆምን አሉና ስብከታቸውን ቀጠሉ። የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት በሽ የሚቆጠሩ ተቃጠሉ በዚህ ጊዜ የሮማ ልዑካን የደስታቸው ብዛት ወሰን አልነበረውም። ያ፳ቱን ዘመኖች ታሪክ በሰፊው የታሪክ መዝገብ ሰጥተው ይቆይና የሮማ ልዑካን ታሪክ እየመረመርን በሮማ ልዑካን መሪነት ካ፲፱፻፳፯ ዓ.ም ዠምሮ እስከ ፲፱፻፴፩ ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ የወረደው የደም ሚዛኑ በምን እንደሚገመት የዓለምን ተመልካች ከማስደነቁም በላይ የልዑል እግዚአብሔር ፍርድ አስተካካይነት እየተመለከተ እግዚአብሔርን ያላመሰገነ ያላከበረ ከዓለም ውስጥ ፩ ሰው አይገኝም ብል አያሳፍረኝም የልዑል እግዚአብሔር ታሪክ በስደት አገር የነበረውን በሰላምና በደስታ በክብር መልሶ በክብር ማስቀመጥ። አሳዳጅ ሆኖ በሀገሩ ላይ የነበረውን በገዛ ሀገሩ ላይ ሽፍታ አሳሥቶ አስገድሎ ሬሳውን ወደ ጉድፍ መጣያ እንዲወድቅ ማድረግ ሁለቱ ሰዎች ፩ኛ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፪ኛው ዱቸ ሞሶለኒ ነው። የ፪ቱን አገሮች ነገር በነዚህ በ፪ቱ ሰዎች አይቶ መረዳት ቀላል ነገር ነው ይሆንን ከላይ በተጻፈው ካ፲፱፻፳፯ እስከ ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ፮ ዓመት ሙሉ የፈሰሰውን ደም ያለቀውን ጦር

፩ኛ በኢትዮጵያ ሰሜንና ደቡብ በየቀለቡና በማደሪያው ከዘመተው የሞቱ

፪ኛ ጠላት አዲስ አበባ በገባ ጊዜ ዓረቦችና ዓርመኖች ግሪኮች ተዘርፈናል በማለታቸው ምክንያቱ የሞቱ

፫ኛ የካቲት ሚካኤል ዕለት በአካፋ በዱላ በእሳት ያለቁ የሞቱ

፬ኛ በአርበኝነት በየጊዜው በጠላት እጅ የሞቱ

፭ኛ በደህንነት አገር ቤት ላይ ሳሉ ሳይስቡት በጠላት እጅ የሞቱ

፮ኛ ወደ ስደት ሲሄዱ በችግር ምክንያት በየመንገዱ የሞቱ

፯ኛ በፈርማቶሪ አመልካችነት በየቀኑ የሞቱ

፰ኛ ጠላት ከኢትዮጵያ ሊወጣ ሲል በተደረገው ጦርነት የሞቱ

፱ነኛ ከጠላት ወገን ሆነው ከተዋጉ ኢትዮጵያውያን የሞቱ

ከጠላት ወገን የነበሩትንም መቁጠር የግድ አስፈላጊ ነው ማለት እነዚህ ጠላቶቻችን ባይመጡ እነዚህ ሰዎች ለባዕድ ተቀጥረው እናት ሀገራቸውን ወግተው በምድርም በሰማይም የሞቱ ባልሆኑ ነበር። ከላይ ሲያያዝ በመጣው ባ፩፻፵፫ሺ ፪፻ ላይ ፻፶ሽ ሲደመር ፫፻፫ሺ ፪፻ ማለት በ፮ቱ ዓመቶች ውስጥ ያለቁት ምሶሎኒ ባነሳው ጦርነት በየቀኑ በሚደረገው የግፍ ሥራ ያላግባብ የሞቱበት በሆለታ ተማሪ ቤት የነበሩ ወጣቶች ሞት የኢትዮጵያን አንዣት እንደ እሳት ያሳረረው ለትውልድ የማይረሳ የበቀል ጥራት ነው የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ እነዚህ ከላይ ቀላል ግምት የሰጠናቸው ሰዎች ደም በምን ምክንያት የፈሰሰ ይመስላችኋል። የኢትዮጵያን ክቡር ለመሠረዝ በመጣው ጠላት መሆኑን አትረዱትም ይሆንን። ለኢትዮጵያ ወጣቶቻችን የማስታወሳችሁ ሁለት ነገሮች አሉ። ፩ኛው ከልብ

# በ እኅድ

ሆናችሁ መርምራችሁ ልትረዱት የምትችሉ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ውስጥ የነበሩትን አገሮችንና ወሰኑን ላይቶ ማወቅ አለባቸው። ፪ኛው የሰንደቅ ዓላማችሁ ተቃዋሚ ዝቅ ለማድረግ የሚፈልገው ጠላታችሁ ማን እንደሆነ አስተውላችሁ ተመለከቱና እዩት። ካላወቃችሁ ካላስተዋላችሁት ውስጥ ለውስጥ እየሄደ የሚሠራውን ለማየት እንደማትችሉ የሚካድ አይደለና የወገኖቻችሁን ደም ልባችሁ ዘወትር ያስብ እንጅ እንዳይዘነጋ የጠበቀ ዓላማ ነው። ለኢትዮጵያ ወጣቶች ይህን ከፍ ያለ አሳቤን ለመግለጽ ያሰብኩት በደገኛው መሪአችን በግርማዊ ቀ ኃ ሥ ትጋት በተገኘው አእምሮ ማስተዋል በመታመን ይህም በተማራችሁት ትምህርት የነፃነትን ነገር በብዙ ቦታ ነው። ፩ነት መኖሩ የሚታመነው ከጠላት ወገን የሚገኘውን ጥቅም ሳይፈልግ ያ፩ድ አገር ሕዝብ ያ፩ድ እናት ልጆች ጠላቶቻቸውን ሲጠሉ ፩ድ ላይ ሆነው ወዳጃቸውንም ሲወዱ ፩ድ ላይ ሲሆን መተባበር ማለት ይህ ነው። እንጅ ፩ዱ ከጠላት ልዩ ጥቅም አገኘሁ እያለ ወገኑን የተለየ ነገር በጐን ልዩ ሥራ እየሠራ ከጠላት እየተመሣጠረ የሚሠራ በእግዚአብሔርም ዘንድም የተጠላ ለመሆኑ መረጃ ሮሜ ፲ ፲፯ ፲፯ ወንድሞች ሆይ የሚያጠራጥር ትምህርት ከሚያመጡ ትለዩ ዘንድ ለዚሁም ድጋፍ ማቴዎስ ፯ ፲፭ ፲፯ ፲፪ ፲፰ ፲፱ ፳ ፳፩ ፳፪ ፳፫። እኔ ይህን ጽሑፍ ለማዘጋጀት ስነሳ ዋናው ዓላማዬ የሮማ ልዑካን ተብለው ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሕዝቡን ካጼ ሚናስ ዘመነ መንግሥት ጀምረው በክርስቶስ ስም እንሰብካለን እያሉ ኢትዮጵያን በፖለቲክ እያመነምኑ መንፈሳዊ መስለው የሚኖሩትን ሰዎች ረቂቅ ፖለቲኮቻቸውን በነሱ ስብከት ውስጥ በማነኛውም ምክንያት አለመድረሴን ማስረጃዬ ይህ ጽሑፌ ነው። ወደ ኢትዮጵያ የተላኩት ልዑካን ሁሉ ለክርስቶስ ብለው የሐዋርያትን ሕግና ሥራ ተከትለው ሠሩ የሚለኝ እንዳለ ግን መልሱን ለጊዜው በቀላሉ ከዚህ አስከትየ የምጽፈው ነው። ፩ኛ ሐዋርያት ለስብከት በሄዱ ጊዜ ወደ ንጉሡ ቀርበው ባለጋራህን

የምታጠቃበት የጦር መሣሪያ የሚሠራልህ እናመጣልሃለን እያሉ ሰብከው ሰብከው እንደነበረ የሚያስረዳ ጽሑፍ የሚገኝ ይሆንን። ፪ኛ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁትን ሁለተኛ አጠምቃለሁ እያሉ መስበክ መረጃው በሮማው መጽሐፍ ይኖር ይሆንን ይሆን። ከቤተ ክርስቲያናችሁ ቤተ ክርስቲያናችን ትበልጣለች ከኢትዮጵያውያን ሃያማኖት የኛ ይበልጣልና ወደኛ ሃይማኖት ግቡ እያሉ በገንዘብ እያባበሉ ወገንና ወገኑን እያለያዩ የሰው ደም ማፋሰስ ይህን የመሰለ ሥራ ሐዋርያት ሠሩ ለማለት መረጃ ይገኛል ይሆንን ይልቁንስ ይህን የመሠለውን ሥራ እንዳይሠራ አስቀድመው በመንፈስ ቅዱስ ስላወቁት እንደዚህ ያለው እንዳይሠራ በማለት እንድንጠነቀቅ አዘውናል እሱም ከዚህ እንደሚከተለው ነው። ፩ኛ ቆሮንቶስ ፫ ፫ እመሰ ትትቃንዑ ወትትጋእዙ አኮኑ ዘሥጋ ወደም አንትሙ ያለውን ማስተዋል ነው። ፪ኛ ዑቁ እመቦ እምውስቴክሙ እለ ይብሉ አነ ዘጳውሎስ። ወካልእ ይብል አነ ዘአጵሎስ አኮኑ እሙንቱ አጵሎስም ጳውሎስም ሰዎች ናቸው ስለምን አንተ የገሌ ነህ እኔ የገሌ ነኝ ትባባላችሁ ከውስጣችሁ እንደዚህ የሚል ቢኖር ቁ ፳ ምንትኑ

# ቡ ሰኑይ

ጳውሎስ ወምንትኑ አጵሎስ ወበላዕሌሆሙ አመንክሙ ወለለ ፩ዱ በከመ ወሀበ እግዚአብሔር ጳውሎስ ምንድን ነው እግዚአብሔር ለየ፩ እንደሰጠው አምናችኋልን ፮ አነ ተከልኩ ወጳውሎስ ሳቀየ ወእግዚአብሔር አልሐቀ እኔ ተከልኩ አጵሎስ ውኃ አጠጣ እግዚአብሔር አልኃቀ አሳደገ። ፯ ዘሂ ተከለ ወዘሂ ሰቀየ ፩ዱ እሙንቱ ወኵሎሙ ዓስቦሙ ይኔሥኡ በአምጣነ ጻማሆሙ። ተከለም ውውሃ ያጠጣም እነዚህ ፩ድ ናቸው ሁሉም የድካማቸውን ዋጋ ይቀበላሉና ልብ ላለውና ላላስተዋለው ይህ ከላይ የተጻፈው በበቃ ነገር ግን ላንባቢ ሰነፍ እንዳልመስልህ ማስረጃዎችን አመጣለሁ አበዛለሁ። ፪ኛ አሁንም ቆሮንቶስ ፬ እስመ ኢኮነ መንግሥተ እግዚአብሔር በነገር ዘእንበለ በኃይል። ይህም የእግዚአብሔር መንግሥት በጠብ በክርክር አይደለምና በኃይል ያለው በጉልበት ማለቱ አይደለም ኃይል ሲል መንፈስ ቅዱስ ማለቱ ነው እንጅ ኃይል ሲል መንፈስ ቅዱስን ማለቱ መሆኑን ለማወቅ ሉቃአስ ፳፬ ፵፱ ወናሁ አነ እፌኑ ተስፋሁ ለአቡየ ላዕሌክሙ ወአንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምአርያም እነሆ እኔ ያባቴን ተስፋ ወደላያችሁ እልካለሁና እናንተስ መንፈስ ቅዱስን እስትቀበሉ በኢየሩሳሌም ቆዩ ያለው እስከ ትለብሱ ኃይለ እምዓርያም። ኃይለ ተለብሱ ያለው መንፈስ ቅዱስን እስክትቀበሉ ማለቱን ማስተዋል ነው። ፫ኛ ቄላሰይስ ፰ ዑቁ ኢይሂጡክሙ በጥበበ ነገር ዘይዬውሁ ለከንቱ በሥርዓተ ትምህርተ ሰብዕ ለሥሒተ ዝንቱ ዓለም ወአኮ በሕገ ክርስቶስ ዑቁ ልብ በሉ እያለ ያውጃል ረቂቅ በሆነ በጥበብ አለ ፖለቲክ እንዳይነጥቃችሁ ዘይዬውሁ አታለው ከንቱ በሆነ በሕግና ትምህርት ስለዚህ ዓለም ለማሳት በማታለል በረቂቅ ፖለቲክ እንዳያጠቋችሁ ልብ ብላችሁ ጠብቁ። ከንቱ በሆነ በሰው ሥርዓተ ሕግ በክርስቶስ ሕግ አይደለምና ዑቁ ልብ በሉ አለ። ፬ኛ እብ ፲ ፮ መሥዋዕተ ዘእንተ ኃጢአት ኢሠመርከ ይህም በእግዚአብሔር በከፈላቸው ሀገራቸው ላይ የሚኖሩትን ሕዝቦች ከሩቅ አገር ድረስ ጦር አምጥቶ እነዚያን አስገድሎ በነዚያ ሥፍራ ላይ ቤተ ክርስቲያን ሠርቼ ለፈጣሪዬ መሥዋዕት አቀርባለሁ ማለት ከንቱ መሆኑን ለማስረዳት አገር ትቶ መጥቶ በሌላ ሰው ርስት ላይ ቤት ክርስቲያን ሠርቶ ለክርስቶስ ሥራ ሠራ ሁለት ማለት ሐሰት ነው። አስቀድሞ የክርስቶስ ቃል ይህ ነው በተረፈ እንደዚህ ያለው መሥዋዕት ለክርስቶስ አይደለም። ፭ኛ ዕብራውያን ፲፫ ፱ ኢታምጽኡ ካልዕ ነኪረ ትምህርተ እስመ ይሄይስ ጸጋሁ ያስተፍስህ ልበክሙ ወአኮ በመባልዕልት ዘኢይበቊያሙ ለእለ እንሶሰው ቦቱ ሌላ ልዩ ትምህርትን አታምጡ ልባችሁን ደስ የሚያናሰኝ ስጦታው ያሰኛችኋልና ወአኮ በመባልዕት በዳቦና በዕንቁላል በዓርብ በረቡዕ እያበሉ ማለቱ ነው እንደሚያታልሏቸው ሲናገር ሲመላለሱበት በማይጠቅማቸው መብል አለ። ፮ኛ መልእክተ ያዕቆብ ፩ ፳፪ ኩኑ ገባ ርያኒሃ ለሕግ ወአኮ ለአጽምዖ ባሕቲቱ። ለመሥራትም ሁኑ እንጅ ለመስማት ብቻ አይደለም። በዚህ ፪ ፲ ወዘሰ ይገብሮ ለኵሉ ሕግ ወይስሕት በአሐቲ ኮነ መንብሰ ይህም ፱ኑን ፈጽሞ ካ፲ቱ ቃላት ፩ዲቱ ቤስት ኮነ መንብሰ በደለኛ ሆነ ስንኳንስ ፱ኙን ሁለቱ እንኳ ተይዘው አይገኙም ብቻ በሰው ሥርት ላይ ቤተ ክር ሠርተን ለክርስቶስ መሥዋዕት እናቀርባለን ሲባል በግብዞች ዘንድ እውነት ይመስላል። ቁ ፲፩ እስመ ዘይቤ ኢትሑር ኀበ ብዕሲት ብዕሲ ይቤ

# ቢ ሠሉስ

ኢትቅትል ነፍስ። ወእመሰ ኢትሐውር ኀበ ብእሲት ብዕሲ ወባሕቱ ትቀትል ነፍሰ ኮንከ ውዱዓ እምሕግ የሰው ሚስት አትንካ ብሎ ነበርና የሰው ነፍስም አትግደል ብሎ ነበርና ወደ ሰው ሚስት ባትሄድም ግን ነፍስን ብትገድል ከሕግ ውጭ ሆንክ በዚሁ ቁ ፲፰ አለ እመቦ ዘይቤለከ አንተ ሃይማኖት ብከ ወአነ ምግባር ብየ አርእየኒኬ ሃይማኖትከ ዘእንበለ ምግባርከ ወአነሰ አርእየከ እምነ ምግባርየ ሃይማኖትየ

እንዲህ እንደዚህ እያሰናዳ ያመጣዋል እኔ ምግባር አለኝ አንተ እንጅ ሃይማኖት አለህን እስቲ ሃይማኖትህን አሳየኝ ምግባር ሳይጨርስ ማለቱ ነው። እኔ ግን ምግባሬን ከነሃይማኖቴ ሳይሃለሁ ፲፱ ወአንተሰ ተአምን ከመ ውእቱ እግዚአብሔር ሠናየ ትገብር አጋንንትኒ የአምኑ ወይደነግጹ አንተስ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ ታውቃለህ አለና አንተስ መልካም አደረግህ ኢጋንንትም ያምኑታል ያውቁታል ይደነግጣሉ ማለት አጋንንት እግዚአብሔርን ቢአውቁትም ሕግን ያስፈርሳሉ እንጅ ሕግን አያውቁም ስለዚህ ሕግን የማያውቁትን ምግባር አጥፊዎች ያውቁታል ብሎ የዘብብት ቃል አንተሰ ትገብር አለው። የሮማ ልዑካን የሚሠሩበትን አያውቁትም አስቀድሞ ፲ቱ ቃላት ኦሪትን መጠበቅ ይገባቸው ነበር። ስንኳን ይህን ያህል ከሚሊዮን በላይ የሚቆጠር ሕዝብ ደም የፈሰሰበትን ይቅርና አክአብ እንኳ ፩ድ ናቡቴን በማስገደሉ ያነን ያህል መከራ ተቀበለ አክአብ የሚስቱን የኤልዛቤልን ምክር ሰምቶ ናቡቴን ገድሎ ቦታውንም ወሰደ እሱንም ገድሎ ቢቀመጥ ግፍ የማይወደው እግዚአብሔር በአክአብና በኤልዛቤል ላይ ያደረገውን ለማወቅ ነገሥት ቀዳሚ ፳፩ እስከ መጨረሻው እይ አክአብ የኤልዛቤልን ቃል ሰምቶ ናቡቴን አስገድሎ ቦታውን እንደወረሰ የሮማ ልዑካንም የጦር መጋጠሚያ ደብዳቤ እያመላለሱ ስለቆዩ የሮማ ነገሥታት በግፍ ይህን ያህል ደም ለማፍሰስ ደረሱ ብዙዎች ሰባኪዎች አይሁኑ የበለጠ ይህን እንደምናገኝ ታውቃላችሁና አለ ፲፫ ወእመሰ ተቃንአ መሪር ወካህድ ብከሙ ውስተ ልብክሙ ኢትትመክሑ ወኢትህሰውዎ ለጽድቅ ፲፭ ወኢኮነት ዛቲ ጥበብ እንተ እምእላእሉ ትወርድ አላ እንተ ምድር እንተ እምነፍስ አጋንንት ፲፮ እስመ ኀበ ሀሎ ተቃንኦ ህየ ሀሎ ህውክ ወካህድ እኩሉ እክየ ምግባር መ ያዕቆብ ፬ ፲፩ ኢትትሐመዩ በበይናቲክሙ አኃዊነ እስመ ሐመዮ ለካልው ወዘይግዕዞ ለካልው ለካልው ሐመዮ ለሕገ እግዚአብሔር ወይግዕዝ ሕገ እግዚአብሔር ወእመሰ ሕጎ ትግዕዝ ኢኮንከ ገባሬ ሕግ አላ ኮንከ ግንዚሃ ፯ኛ መል ዮሐንስ ፬ ፱ ፪ ፬ ወዘሰይብል አእምሮ ወኢየአቅብ ትእዛዞ ሐሳዊ ውእቱ ወአልቦ ጽድቀ እግዚአብሔር ላስሌሁ። ፭ ወዘሰ የአቅብ ቃሎ አማን ፍቅር እግረአብ ፍጹም ውእቱ ላእሌሁ ወበዝንቱ ነአምኖ ከመ ቦቱ ሀለውነ ፱ወዘሰ ይብል ውስተ ብርሃን ሀሎኩ ወይጸልእ ቢጾ ሐሳዊ ውእቱ ወውስተ ጽልመት ሀሎ እስከ ይእዜ። ብርሃን የሚለው ጌታችንን ነው። ጽልመት የሚለው የዲያቢሎስን መሆኑ መረዳት ሐሰተኛ ፖለቲከኛ ነው እንጅ ወንድሙን የሚጠላስ በዲያቢሎስ ዘንድ ነው። እስከ ዛሬም እዚያ አለ ብሎ ተናገረ። ፲ ወዘ ያፈቅር ቢጾ ውስተ ብርሃን ወአልቦ ዕቅፍት በኀቤሁ ወንድሙን የሚወድ ግን በክርስቶስ ዘንድ አለ የዲያብሎስ እንቅፋትም አያገኘውም አለ። ፲፩ ወዘሰ ይጽልዕ ቢጾ ውስተ ጽልመት ውስተ የሐውር ወኢየአምር ኀበ የሐውር እስመ ጽልመት ዓፆሮ

# ባ ረቡዕ

ዓዕይንቲሁ ወንድሙን የሚጠላ የሚሄደው ወደ ጨለማ ዲያቢሎስ ነው። የሚሄድበትንም ምንገድ ምግባር አያውቀውም ምነው ቢሊ ዲያቢሎስ አእምሮውን አይኑን አጥፍቶበታልና አለ ከላይ ፯ አርስቶች አድርጌ የሐዋርያትን ቃል ልንሠራባቸው የጻፉልንን እንደመጠኑ እየገለጥኩ መረጃዎችን ጽፈአለሁ። ይህም ጽሑፍ የሚታየው ዓይኑ ያለበት ሰው ካልተገኘ ከንቱ ሆኖ መቅረቱ ማለት ስለሆነ ድንገት ዓይን ያለው ቢገኝ እነዚህ አያንሱም ደግሞም በዘሁ ተከትሎ መጽሐፍ እያስተዋለ ቢመለከት ውስጠ መሠረቱን ጠልቆ ለማወቅ ይችላል ለነዚህ ለጻፍኋቸው የሙሴ መጽሐፍ ነው። ጠልቆ ከጻፋቸው ካ፭ቱ መጻሕፍተ ብሉያት ፩ኛ ኦሪት ዘዳግም ስለ ሕግ የተጻፈው ኦሪት ዘዳግም ሕግ የተጻፈ ነው። ክርስቲያን ነኝ የሚል ሁሉ በዳግም ሕግ የተጻፈውን መጠበቅ አለበት ስለዚህ ኦሪት ዘዳግም ፲፱ ፲ ኢይትካዓው ደም ንጹሕ ውስተ ምድርከ እንተ ወሀበከ አምላክከ መክፈልተከ ወኢየሐሉ ውስቴትከ ቀታሌ ነፍስ ያንተ ፋንታ አድርጎ በሠጠህ ምድር

ላይ ንጹሕ ደም አይፍሰስ ነፍስ ገዳይም በሀገርም ላይ አታስቀምጥ አለ። ፲፬ ወኢትትኃለፍ ደወለ ቢጽከ ዘሠርዑ አበዊከ በውስተ ርስት ዘተዋረሰከ ይህ ጽሑፍ እኛ ልንመክርበት የተጻፈ ነበር። የባልንጀሃን ወሰን እንዳትደፍር ብሎ

አዞን ነበር። ይህን ቃል ይዘን እንገኛለን ይሆንን አባቶችህ አቆይተውህ ከወርሰከው ርሥት ምድርህ የወንድምህን ድንበር ወሰን አትለፍ አለ። እንደዜህ ማለቱ እንዳንጋደል እንዳንጣላ ብሎ ነበር። የሰማይና የምድር ጌታ ከሰጠህ ክፍል አትለፍ ብሎ ያዘዘውን ቃል ለሮማ ልዑካን የሠረዘላቸው ማነው አምላክ ለማለት የምንችል ገዥአችን ልንለው የሚገባን ትእዛዙን ስንጠብቅ ነው እንጅ ትእዛዙን ስንጠብቅ ነው እንጅ ትእዛዙን እየጣስን አምላካችን ብንለው እውነት አይደለም ለዚህም ማስረጃ ማርቆስ ፯ ወይቤሎሙ መደልዋን ሠናየ ተነበየ ኢሳይያስ ላዕሌክሙ በከመ ጽሑፍ ዝንቱ ሕዝብ በከናፍሪሆሙ ያከብሩኒ ወበልቦሙ ነዋኃ ይርኅቁ እምኔየ እነዚህ ሕዝቦች ባአፋቸው ይጠሩኛል በልባቸው ሕግን አያስቀምጡም ኢሳይያስ ትንቢቱን በመልካም ተናግሯል ብሎ በሚገባ ተናገረ ይላል። ቁ ፯ ወከንቶ ያመልኩኒ ወይሜሕሩ ትእዛዝ ሰብዕ ለኔ እንገዛልሃለን የሚሉ በውሸት ነው። እነሱስ የሚአስተምሩ ጌቶች ያዘዙአቸውን ነው እንጅ ፰ ወየኃድጉ ትእዛዙ እግዚአብሔር ወየዓቅቡ ትእዛዛተ ሰብዕ ጥምቀታት ኩሳኩሳተ ወጸሕታተ ወጽዋዓተ ወባጅ የአንተ ትእዛዝ አይጠብቁም ኩሳኩስት ዝንጉጉሮች አለ ፩ድ ዓይነት አለመሆኑን ሲአመክት ነው በጸሕል በጽዋዕ አኳኋን ሁሉ የተለያየ መሆኑን ይህን በመሰለው ለየራሱ መሆኑን ያመለክታል ሰብዕቱዕኑ ትዕልው ትእዛዛተ እግዚአብሔር ከመ ትዕቀቡ ትእዛዘ ሰብዕ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ፲ቱን ቃላት ትወነጀሉ ዘንድ ቀና ነገር ነውን ይህም የእናንተን ትእዛዝ ሕግ ለመጠበቅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መወንጀል መልካም ቀና ነውን ብሎ ተናገረ። ስለዚህ ማነኛውም ጉዳይ ከእግዚአብሔር ሕግ የወጣው ሥራ ሁሉ ከንቱ ሐሰት ነው ስንኳንስ በግልጽ የእግዚአብሔርን ሕግ ትተው በሰፊው ችላ ብለን በሌላ መንገድ ስንጓዝ ይህን የተጻፈልንን ሁሉ ረስተን ወይም ችላ ብለን ትተነው ፩ዲት ቀለም ተሳስታን እንዳትቀር እንኳ ሲያስታውስ ሉቃ ፲፮ ፲፯ ወባሕቱ ይቀልል ሰማይ ወምድር እምትደቅ አሐቲ ቃል

## ቤ ኃሙስ

## ፫ኛ ክፍል ሰኔ

## ምዕራፍ ፩

እምኦሪት አስጠንቅቆን ነበር ይህም ከኦሪት ፩ ቃል ከምትነጥብ ሰማይና ምድር ማለፋቸው ይቀላል ብሎ የተናገረውን ማስተዋል የተገባ ነው። ከላይ የተጻፈው የሮማ መንግሥት የጦር ፕሮፓጋንዶች ካህናት እየመሰሉ መስቀልና መጽሐፍ እየያዙ እየመጡ ሕዝቡንና መንግሥቱን እያለያዩ ስለሚሠሩ ከሮማ መንግሥት በፕሮፓጋንድ በኩል ዋጋ ተቀባይ ናቸው እንጅ የቤተ ክህነት ሰዎች አለመሆናቸውን ለወገኖች ለመግለጽ ነው የሮማው ፕሮፓጋንድ ባልደርቦች ለመሆናቸው ከላይም የሮማው መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሮባላንቴ ለዋናው ሰባኪ የጻፈው ደብዳቤ ያስረዳል። አጼ ምኒልክን ያታላይነታቸው ብዛት ሮባላንቴ ለአንቶሎኖ ሲጽፍ አጼ ምኒልክን አንተ እያለ አንቶሎኒን እርስዎ እያለ ጽፎ ይገኛል። አባ ማስያስም ይህን የሮማን መንግሥት ፖለቲክ ጽሑፍ ሲአመላልሱ በነበረ ጊዜ ከሮማ መንግሥት ባጼ ምኒልክ ፊት ኒሻን ተልኮላቸው ስላተገለጸ ለማንሳት አፈር ብለው እንደነበረ ካቶ ተክለ መ/ጻድቅ የተጻፈ ታሪክ ይነገራል። የነሱን ሥራ ፩ድ ባ፩ድ እየዘረዘርኩ አቀርባለሁ። እኔ የምለው ለመሆኑ የሮማ ልዑካን ነን ብለው ለመስበክ መጣን የሚሉበት ምክንያት ፩ኛ ከእናንተ ሃይማኖት የኛ ይበልጣል ማለት ፪ኛ ከናንተ ጥቅምት የኛ ይበልጣል ፫ኛ ከናንተ ቁርባን የኛ ቁርባን ይበልጣል ማለት ምክንያቱ ከምን የመጣ እንደሆነ ለመረዳት ወደ ምርመራ እገባለሁ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሮማ ቤተ ክርስቲያን ብልጫና ቅድሚያ መሆንዋን የሚአስረዳ ነገር ይገኛል ይሆንን ምክንያቱ ምን ይሆን በቅድሚያ እንደሆነ ከሮማ

ቤተ ክርስቲያን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወደ ኋላ የቀረች አይደለችም ይልቁንም ቅድሚያው ለኢትዮጵያ ነው። የኢትዮጵያ ሃይማኖት የቆመው ገና ከልደት ክርስቶስ በፊት ፩ሺ ዘመን ቅድሚያ ያላት ናት ይህም በቀዳማዊ ምኒልክ ጊዜ ጽላተ ሙሴና መጻሕፍተ ኦሪት ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተመልሰው መምጣታቸው ነው ከጽላተ ሙሴ ጋርም ካህናተ ኦሪት አብረው መጥተዋል ይህ ታሪክ የሚካድ አይደለም በኢትዮጵያ የሚገኙ መጽሐፍተ ብሉያት አስቀድሞ ከልደተ ክርስቶስ በፊት በየጊዜው ከእብራይስጥ እየተገለበጡ የመጡ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃ ይገኛል። ማስረጃውን አሁን ለመዘርዘር ወደ ጐን ያቆያል ማለት አሁን የምፈልገው የሮማ ልዑካንን ሥራ ለመግለጽ ስለ ሆነ ነው። የኢትዮጵያን ታሪክ እስከ ዛሬ ያለውን ማንም ቢደክም ለማግኘት የሚችል የለም ስል ሥጋት የለብኝም ማለት ምስክሮች ቅድሳን መጽሐፍ ስለሆነ ነው።

ስለ ኢትዮጵያ መሠረት ፩ኛ የኢትዮጵያ ነፃነት ተካም ዝምሮ እስከ ዛሬ ሰይደመሰስ ክብሩ ሳይረክስ ፬ሺ ፹፻፵ ዘመን ስለ መቆየቱ ነው። ፩ድ ፩ድ ሰዎች የኢትዮጵያን መንግሥት እየተቋረጠ እንደመጣ እያስመሰሉ ሲጽፉ ይገኛሉ ይህንም አጻጻፍ ከጠላት ምንጭ ያመጡትን እንደሆነ መረጃው ለወደፊት ይመጣል ማስመያሰቸውም ፩ኛ ከ፹፻፵፪ ዓ.ም ላይ ፩ ሴት ጉዲት ወይም ዮዲት የምትባል ሴት ከመልኳ ማማርና ውበት የተነሳ የሚሰበሰቡትን ሕገ ወጦች ይዛ ስለሸፈተችና መንግሥቱን ስላወከች ምክንያት የሆኑ ሁለት ነገሮች ይነግራሉ ፩ኛው በዚህ ዝመነ ረሃብና በሽታ ነበረ ፪ኛው አንበሳ ውድም ንጉሥ ገና ሕፃን ልጅ ስለ ነበረ ነው ይላሉ። ለጊዜው ይህች ሴት ሕግ ወጦችንና ወስላቶችን ሰብስባ ተነሥታ ብዙዎችን ሐውልቶች

# ብ ዓርብ

ማፍረስዋ እረሃብና አጽብሐ ያሰሩትን የአክሡም ቤተ ክርስቲያን መቃጣሏ እርግጥ ነው። ግን አንበሳ ውድም እያደር እየቆሰለ ስለ ጐለመሰና እየተዘዋወረ እየተዋጋ በኋላ እሱ በጦርነት አሏዋን ገድሎ መንግሥቱን እሱ ራሱ ይዞ በዙፋን ተቀምጦ የአክሡም ጽዮንንም አሠርቶ በ፳ ዘመኑ እንዳረፈ ታሪክ ይነግረናል። ይህች ሴት ሕገ ወጦችን ይዛ የአክሡምን ከተማ ዘረፈች ብለው መጻፍ ትተው ጐዲት ፵ ዘመን ነገሠች እያሉ ሲያወሩ። ሲጽፉ ይገኛሉ ነገሠች እያሉ ያወራሉ የአነጋገሥዋ ሥነ ሥርዓት እንደምን ነበር ብሎ ቢጠይቋቸው እንደ ምን ነበር ብለው ይመልሳሉ ይሆን ፪ኛ መራ ተክለ ሃይማኖት ያጼ ድነዓድን ልጅ መሶብ ወርቅን ያለፈቃድ አግብቶ መንግሥትን ስለ ያዘ እነላሊበላ የመሶብ ወርቅ ልጆች ናቸው። መንግሥቱ ከመንግሥቱ ዘር ሳይወጣ ሌላ ባዕድ እያስመሰሉ ሲጽፉ ይታያሉ። ፫ኛ ባጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት በሸ፲፻፲፮ ዓ.ም ግራኝ መሐመድ የተነሣ ጊዜ ለግራኝ ሙሐመድ ቱርኮች የጦር መሣሪያ ነፍጥ ሰጥተውት ስለነበር እነሱ በጦርና በጐራዴ እነዚህ በሩቅ እየሆኑ በነፍጥና በመድፍ ስለ አጠቋቸው አጼ ልብነ ድንግል መሸሽ ግድ ስለሆነበት ከሸዋ ተነሥቶ ወደ ትግሬ እየሄደ በየጊዜው ጦርነት እንዳደረገ ታሪክ ይነግረናን አጼ ልብነ ድንግል ፲፰ ዓ.ም እስከ ፴፪ ዓ.ም ድረስ ሲከላከል ከቆየ በኋላ እሱ በበሽታ ባረፈ ጊዜ ልጁ ገላውዴዎስ በመንግሥቱ ተተክቶ ሲከላከል ጠላቱን ግራኝ መሐመድን ገድሎ መንግሥቱን ጠቅልሎ መያዙን ታሪክ ይነግረናል ፬ኛ ባ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ኢጣልያ ግፍ በወረረች ጊዜ ብልሁ አርቆ ተመልካቹ ንጉሡ ነገሥት ወደ አውሮፕላን ስለ ተሻገሩ ጠላት በባዶ ከተማ የወደቁ ዕቃዎች እየለቃቀመ ወደ ዓለም ነገሥታት ኢትዮጵያን ድል አድርጌ ያዝኩ ብሎ ቴሌግራም ካስተላለፈ በኋላ የኢትዮጵያ ጀግኖች በየሸንተረሩ ገብተው እንደ ንብ እየነደፉ ሲጥሉት ጊዜ ሬሳውን እየጫነ ወደሀገሩ ሲአግዝ የዓለም ነገሥታት ሁሉ ይገረሙ ዝምር በየሥፍራው ምሽግ ሠርተው ከተቀመጡበት የኢትዮጵያ

አርበኞች በጥይት እየነደፉት ሲቸግረው በረቃ ለበረቃ ሲንከራተት ከዚያ ሲመለስ እንደ ከብት ከተካበ ድንጋይ ውስጥ እየታጎረ ከዚያውም ከበረቱ እየገቡ በጐራዴ እየጐመዱ አሳሩን አስጨርሰው እስከ ፭ ዓመት ሲከላከሉ ሰንደቅ ዓላማቸውን እንደያዙ ከንጉሥ ነገሥታቸው ለመገናኘት ችለዋል በከተማውም የሚቀመጡ ብዙውን ሕዝብ

በመለማመጥ ገንዘብ በመስጠት ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለኢጣልያ ነኝ ይል የነበረው ሁሉ የንጉሡ ነገሥቱን መመለስ እርግጠኛውን ባገኝ ጊዜ በገዛ መሳሪያው እያንገበገበ ያጣድፈው ጀመር ኢጣልያ ልብ የለውም እንጅ ከዚያ በኋላ በኢትዮጵያ ፩ድ ቀን ማደር አይገባውም ነበር ኢትዮጵያ ታውካ የቆየችባቸው ጉዳዮች እነዚህ ፪ቱ ነገሮች ብቻ ናቸው። እንጅ ሌላ ነገር የለም እነዚህም ፫ቱ በክርክር ፩ኛው በዘር ምክንያት የሴቲቱ ልጆች ሲገዙ ከቆዩ በኋላ ወደ ወንዶቹ ልጆች ዘር ተመለሰ ሌላ አይደለም በሴት ልጅ በኩል መንግግሥት አይወርስም እንዳይባል ይኸውና ዛሬ ባለንበት ዘመነ መንግሥት በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ይታያል ኢጣልያ ፭ ዓ ሙሉ በየበረኃቸው ሲንከራተት ቆይቶ ሄዶ እንጅ ምንም ያደረገው ነገር ነፃነት እንደሌለው ሕዝብ አገዛዝ ፩ ቀን ፩ድ አገር ላይም አላሳየም ከመለማመጥ በተቀር ስለዚህ የኢትዮጵያ ነፃነት ፬ሺ ፬፻፵ ዘመን

## ቦ ቀዳም

የኖረ ነው ማለቴ ስለዚህ ነው። ኢጣልያ እውነት ገሥግሣ አዲስ አበባ እንደመግባቷ ሙሉ ሀብት አግኝታ ቢሆን ወደዚያው ከኢጣልያ ቋንቋ በተቀር በኢትዮጵያ ቋንቋ እንዳትጽፉ ብሎ ማወጅ ታሪክ ያለባቸውንም ቦታዎች በሰፊው መቆፈር አልቻለም ምክንያቱም ይህን የመሰለው ሥራ የሠራ እንደሆነ በከተማ ውሥጥ ያለው በውጭ ካሉት አርበኞች ጋራ እየወጡ የተደባለቁ እንደሆነ ኢጣልያ በጭራሽ የወታደሮቿ ዘር ጠፍቶ እንደ ሚቀር የጦር ባለሥልጣኖች ስላወቁ በፍጹም ነፃነቱን እንዳጣ ሕዝብ ያለ አገዛዝ ለማቆም አልተቻላትም ይህም የሆነ በአበኞቿ ኃይል ነው። በከተማው ውስጥ የኢጣልያ ባንዲራ ተተክላ ብትታይ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ደግሞ በውጭ ተተክላ ትታይ ነበር። ካ፲፱፻፳፰ ዓ.ም እስከ ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ኢትዮጵያ በጣርነት ላይ ቆየች እንጅ በፍጹም ድል ሆና ለኢጣልያ ተገዠ ሆና እንዳልቆየች ዓለም ይመሰክራል። ስለዚህ የንግግሬ መደምደሚያ የኢትዮጵያ መንግሥት ከመሠረቱ ወጥቶ ነፃነቱ ጠፍቶ አያውቅም። ለዚሁም ድጋፍ መረጃ የሚፈልግ ቢሆን ከዚህ የሚከተለውን ይመልከት። በመላው ዓለም ላይ እንዳለው ሕግ በዓለም ላይ ጸንቶ የሚገኘው ሕግ ዓለም እንደሚያውቀው ፩ድ ሀገር ዓላማና ፊደል አለው። ይህንም ዓላማና ፊደል ከውጭ ኃይለኛ ጠላት መጥቶ መንግሥቱን አፍርሶ ወሰኑን ጥሶ በገባ ጊዜ የድል አድራጊ ማስታወቂያው አስቀድሞ ዓላማንና ፊደልን ማለት የሀገሩን ቋንቋ ማጥፋት ነው። ይህን ሥራ የማያውቅ ሀገር የለም ኢትዮጵያ ግን ነጻነቷ ተጠብቆ መኖሩን የሚአስረዳው ግዕዝ ቋንቋዋ ሲያያዝ ከአዳም እስከ ኖኅ መነጋገሪያ የነበረው ፩ኛው ቋንቋ ታላቁ ነቢይ ሙሴ በኦሪት ዘፍጥረት ፲፩ ፩ ወ፩ዱ ነገሩ ለኩሉ ዓለም ወ፩ዱ ቃሉ ብሎ የጻፈው ፩ኛው ቋንቋ ግዕዝ ነው። የግዕዝን የምስጢር ስጽፍ የግዕዝን ምስጢር ተከታትለው የቁጥር ትርጓሜ ፊደል ለመመርመር ለበቁ ብዙዎቹን ጥንታውያን መጽሐፍት ለመረመሩ ነው እንጅ ላዲስ ጽሑፍ አንባቢዎች አልጻፍኩትምና እነሱ የዚህን ሐተታ ቢጠይቁኝ እነሱን የሚሰማ ድምጽ የለኝም እያልኩ አስጠነቅቃለሁ። ይህን ግዕዝ ካም ወደ አፍሪካ ይዞት የመጣ ኖኅ በሕይወቱ ዓለምን ለ፫ ልጆቹ ለሴም ለካም ለያፌት ባካፈለ ጊዜ ስለ ዓለም መከፋፈል ነው መረጃው የሚገኝ ሙሴ ካጻፈውኩፋሌ ስለሆነ ምዕራፍ ፱ ወኮነ በቅድሜሁ በ፭ወ፫ ኢዮቤልው ከፈልዋ ለምድር ፫ተ መክፈልተ ለሴም ወካም ወያፌት ይላል መጽሐፉ እንደሚለው ፫ቱ ልጆች በተካፈሉ ጊዜ ኦሪቱ ፲፩ ፪ ወኮኔ እምድኅረ ተንሥኡ እምጽባሕ ረከቡ ገዳመ በምድረ ሰናዖር ወኃደሩ ህየ አንባቢ ሆይ አስተውል

የባቢሎንን ግምብ የሠሩ ወደ ሌላ ቦታ ከተከፋፈሉ መሆኑን ለመረዳት ወኮነ እምድኅረ ተንሥኡ እምጽባሕ ረከቡ ገዳመ ያለውን አስተውል ይህ የመሬት መካፈል የተደረገውን ኖኅ ሳይሞትና ገና በሕይወቱ ሳለ ነው። ኖኅ ያረፈ ዓለም በውሃ በተደመሰሰ በ፫፻፵ ዘመን በላይ ነው። ዓለም በውኃ የተደመሰሰ በ፪ሺ ፪፻፵፪ ዓለም ላይ ነው። ሲደመር ፪ሺ፪፻፪ ዘመን ይሆናል ካም ወደ አፍሪካ የመጣ በዚያ ጊዜ ስለሆነ የቋንቋ መረገም መለያየት ሳይመጣ አስቀድሞ ይዞት የመጣ ነው። ፩ድ ፩ድ ሰዎች ባለማስተዋል የኖኅ ልጆች እስከ ባቢሎን ግንብ መፍረስ ድረስ ሳይበታተኑ ፩ድ ላይ ቆይተው የባቢሎንን ግምብ ሠርተው የባቢሎን ግምብ ከፈረሰ በኋላ በየሥፍራቸው ተበታተኑ እያሉ ይጽፋሉ ይህ ጽሑፍ ከንቱ ፍሬ የሌለው

# ተ እጉድ

ነገር ነው። እንጅ እውነት አይደለም። ከማየ አይኅ እስከ ባቢሎን ግምብ መፍረስ ዘመኑ ፩፻፴፩ ነው ከዚሁ የኖኅ እድሜ ፫፻፶ ሲነሳ ፪፻፷፩ ዘመን ይገኛል። ርስታቸውን ከተቀበሉ በኋላ ይህን ያህል ፪፻፷፩ ዘመን ትተውት ቆዩ ማለት ስሕተት ነው። ፪ኛም የባቢሎን ግምብ እስቲፈርስ ካም እሥያ ነበር ማለት ከንቱ ነው። እንዲያውም አስተዋይ አንባቢ ለሆነ ናምሩድ እንኳ የባቢሎን ግምብ በፈረሰ ጊዜ በሥራውም ውሥጥ ነበር ብሎ ደፍሮ የሚነግረኝ እፈልጋለሁ ማለት አስተዋይ የሆነ እንደሆነ አይደፍርም በማለት ነው። የባቢሎን ግምብ የፈረሰ በትውልድ በፋሌቅ ነው ከኖኅ ዠምሮ እስከ ፋሌቅ ፯ ትውልድ ከሴም ፮ኛ ነው። ደግሞ አሪት ዘፍጥረት ፲ ፴፪ ወዛቲ ይዕቲ ነገደ ደቂቁ ለኖኅ በበዘመዶሙ ወእምነ እሉ ትውልደ ዘተዘርዓ እምድኅረ አይኅ ከባቢሎን ግምብ መፍረስ በኋላ ተበታትነው ቢሆን ዘተዘርወ እምድኅረ አይኅ ባላለም ነበር። ስለዚህ አሪቱን አስተውሎ መመልከት ያስፈልጋል። ይህን ሁሉ ለመዘርዘር ያደረሰኝ ስለግዕዝ አመጣጥ ነው የባቢሎን ግምብ በተሠራ ጊዜ ከ፸፪ቱ አለቆች ከሴም ዘሮች ፴፪ አለቆች ከካም ዘሮችም ፳፫ አለቆች ከያፊትም ፲፯ አለቆች ሆነው ያሡሩ ስለነበር ዘፍጥረት ፲፩ ፯ ንዑ ንረድ ወንክዓዎ ለነገሮሙ ከመኢይሳምዑ ፩ዱ ምስለ ካልዑ ሥላሴ ይህን የ፸፪ቱን አለቆች ሥራ በጠሉ ጊዜ እነዚህ ፸፪ቱ አለቆች ፩ዱ ፩ዱን እንዳይሰማው እናድርግ ዘንድ ኑ እንውረድ ብለው የ፫ነታቸውን በሚአስረዳ አንቀጽ ንዑ  ንክዓዎ ለነገሮሙ ብለው ተናገሩ። እነዚህ ፸፪ቱ ውስጥ የተቆጠሩ የካም ዘሮች በእሥያ መንግሥትን በመዠመሪያ ያቆሙ የካም ዘሮች ለመሆናቸው ማንም የሚያውቀው ነው። ዛሬ ሥለጠንን ከሚሉት አገሮች ህሉ ያነን ፩ኛ ይባል የነበረውን ቋንቋ ለማፋለም ይቆይና ከነዚህ ከ፸፪ቱ ቋንቋዎች ውስጥ እንኳ ከነዚያ ፩ዱን ይዞ ይህ የኔ ነው ብሎ ከዚያ ዠምሮ ሲያያዝ እንደመጣ አድርጎ የሚአመጣ ቢገኝ በጣም የተሻለ ነበር። ግን ይህን መርምሮ ለማግኘት የሚቻልበት ሁሉ ተገኝቶ ስለሚገኝ ማንም ሰው ይህን ከመከተል ቸል ሲል ይገኛል። የኢትዮጵያ ነፃነት ያስገኘው ፍሬ ካም በ፪ሽ፮፻፺ ዓ ዓለም በላይ የቋንቋ መረገም ሳይመጣ ወደ አፍሪካ ይዞት መጥቶ በካም ቤት የቆመው መንግሥት እየተደገፈ ከዚያ ዠምሮ እስከ ዛሬ ፬ሽ፳፻፵ ዘመነ መታሰቢያ ሆኖ የሚገኘው ጽሑፎች ሁሉ የኢትዮጵያ ግዛት በነበረው ቦታ በየድንጋይ ላይ ተጽፎ ይገኛል። የኢትዮጵያ ነፃነት ዘመኑ የሚቆጠር ነው። የግዕዝ መሠረት ከላይ እንደተጻፈው ነው በግዛትም አስቀድሞ የኩሳ ርስት ከሊቢያና ከምሥር እየተዋሰነ ብዙሪያዋ ከሚገኙ ደሴቶች ጋራ ፩ድ አድርጋ ደግሞ ከሰም አብረን አገር ከጥንት ዠምራ እስከ ፮፻ ዓ.ም ድረስ ግዛቷ እንደነበረ ጥንታውያኑ ሐውልቶች በጽሑፋቸው ያስረዳሉ ግብጹንም እየጨመረች የገዛችባቸው ዘመኖች ይገኛሉ። ኢትዮጵያ የንጉሠ ነገሥት ግዛቶችዋ ከተቀነሱም ጥንታዊ ፊደልዋንና ዓላማዋን ሳትተው እንደ ያዘች ትገኛለች ይህንም ዕድል ማንም ሊያገኘው አይችልም በዲያቢሎስ መንግሥት ባህል የተመሠረተውን ሥራ የሰው መግደያ የሚሆን ፋብሪካ አላቆመችም ተብላ ዛሬ በንቀት ዓይን የሚመለከትዋትን ስለሚያቸው

የነሱን ነገር የሚቀበሉም ይገኛሉ። ሰሎሞን እንደ ተናገረው የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ብሎ አሁንም ከኢትዮጵያ

# ቱ ሰኑይ

የበለጠ አዋቂ እንደሌለ ከዚህ ቀደም ባለፈው ዘመን ሁሉ ከከፉዎች ከኀይለኞች እግዚአብሔር ጠብቋት ፊደሏንና ዓላማዋን ይዛ የምትገኘው በዚህ ፈሪሃ እግዚአብሔር ጥበብ ነው። ኢትዮጵያ አስቀድሞ በነቢያት ከፍ ከፍ ያለ ተስፋ ትንቢት ያላት አገር ናት ይህንም ምሥጢረ ተስፋ ስለ ኢትዮጵያ የተነገረውን አሁን በዚህ ዓምድ ለመጻፍ ለጊዜው ወደ ጐን ይቆይና ወደ ኢትዮጵ ለመጻፍ ለጊዜው ወደ ጐን ይቆይና ወደ ኢትዮጵያ ፊደል መሠረት ወደ ግዕዝ እንኼዳለን የግዕዝ መሠረት የሚታወቀው ባ፬ሽ ፲፫ ዓ. ዓለም ከልደተ ክርስቶስ በፊት ፩ሽ ካ፭ ዘመን በላይ ንግሥተ ሳባ ሳለች

መጽሐፍተ ኦሪት ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተገልብጠው መጥተዋል ከዚያም በኋላ መጻሕፍቱ ሁሉ በየጊዜው ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ እየተገለበጡ መጥተዋል ከዝሁም ጋራ ጽላተ ሙሴ ስትመጣ ካህናተ ኦሪትም አብረው መጥተዋል የግዕዝን መሠረት ጽናት ለማስረዳት የሚቻለው ካህናት ኦሪት ጽላተ ሙሴን ይዘው በመጡ ጊዜ እነሱ በኢትዮጵያ ቋንቋ እንሥራ አላሉም። ይህንም ነገር ላስተዋለው ሰሎሞን በኢትዮጵያ ላይ ልጁን እብነመክን አነገሡ እያሉ የሚአወሩትን ወሬ ገለባ አድርጎ ያሳያል። እርግጥ እሱ በመንግሥቱ የሚዝ ሆኖ ቢሆን አብረው የመጡ እስራኤላውያን የራሳቸውን ቋንቋ ትተው በሌላ ቋንቋ ባልተነጋገሩ ነበር። የኢትዮጵያን መሠረት ጥልቅነት ለመረዳት መንግሥተ ሳባ ወደ ሰሎሞን በሄደች ጊዜ ያደረገቻቸው ነገሮች ናቸው ፩ኛ ስለ እግዚአብሔር የስሙ ቤት ሠራ ማለትን ሰምታ ወደ ኢየሩሳሌም መውረድዋ ፪ኛ ሰሎሞንን የሚአህል አዋቂ ንጉሥ የፍጥረት ሁሉ ቋንቋ ተገልጾለት ለነበረው ከርሱ ጋር በጠብብ ንግግር ለመፈታተን ማሰብዋ ፫ኛ በግመሎች የተጫነው ፻፳ መክሊት ወርቅ መያዝዋ የወርቁ በ፻፳ ላይ በማረፉ አስደናቂ ምሥጢር አለበት ማለት ነው። የ፫ቱን አርእስቶች ነገር በሐተታ መግለጽ የተገባ ስለሆነ ፩ኛ ለእግዚአብሔር የስሙ ቤት ሠራ ቢሏት ከሩቅ ሀገር ተነሥታ ሄጀ ልረዳው ብላ ኢየሩሳሌም ድረስ ስለምን ወረደች ይሆን ይህች ሴት የተማረችና እግዚአብሔርን አዋቂ ካልሆነች በምን ምክንያት ኢየሩሳሌም ድረስ ወረደች። ይህን አስተያየት የአንባቤዎች ልቡና ምን ግምት ሊሰጠው ይችላል። ስለ ፪ኛውም በጥበብ ለመፈታተን (ተፍትኖ ምስለ ጥበብ) ያለው በጥበብ ንግግር ከሰሎሞን ጋራ በመነጋገርዋ ነው ይህ ሰሎሞንና ንግሥት ሳባ የተነጋገሩትን መኃልዬ ምሥጢሩን መርምሮ የተረዳው ሊቅ ይኖር ይሆንን ይህን ሥራ የምትሠራ ንግሥት ያልተማረች ነበረች ማለት የተመቸ ይሆንን ስለ ፫ኛው ሐተታ የመክሊቱን ቁጥር ፻፳ መሆኑ ምሥጢር አለው ማለቴ የጌታ ቤተ ሰቦች ቁጥር ፻፳ ነው። ይህም እንደዚህ ነው። ፷፯ቱ ቅዱሳት ፪ኛ ፸፪ቱ አርድዕት ፫ኛ ፲፪ቱ ሐዋርያት ድምር ፻፳ እንደዚሁ ነው። ይህ ሥራ ያልተማረ ሰው ሥራ ይመስላልን ይህንም ለመረዳት የፈለገ ቢኖር ነገሥት ፲ ካ፩ እስከ ፲፩ ይመልከት መጽሐፍተ ብሉያት ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ አልተገለበጡም ማለት ዋና ስሕተት ነው። ኢትዮጵያ መስዋዕተ ኦሪትን እየሠዋች ሰንበትን እያከበረች ሱባዔ እየቆጠረች ሕገ ግዝረትን እየጠበቀች የኖረች ሃይማኖታዊ ሀገር ናት እንደዚህ ሕገ ግዝረትን እየጠበቀች የኖረች ሃይማኖታዊ ሀገር ናት እንደዚህ ሆና ሕገ እግዚአብሔርን እየጠበቀች የቆየችቱን ሀገር የሮማ ልዑካን ነን ብለው የመጡ መንግሥት የጦር ግሮፓድ ባልደረቦች የሆኑ ከሀገራቸው ላይ የገንዘብ ማጠራቀሚያ ማኅበር አቋመው

## ቲ ሠሉስ

ከዚያ ለሰው ማሰናከያና ማታለያ እያመጡ ኢትዮጵያን ሕዝብ ክርስቲያን እያታለሉ ከኢትዮጵያ ሃይማኖትና ጥምቀት ይበልጣል እያሉ እየሰበኩ ሕዝቡንና ሕዝቡን ሲለያዩት ይታያሉ ወደ ኢትዮጵያ ሃይማኖትና ቤተ ክርስቲያን እንዳትመለሱ እያሉ በጥብቅ መሐላ እያስማሉ እንደዚህ ያለ ሥራ ሲሠሩ ይታያሉ ስለ ጥምቀት የኢትዮጵያ ጥምቀት ቤተ ክርስቲያን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ለማጥመቅ የማይቻላት ሆና ይሆንን። በማቴዎስ ወንጌል ፳፰ ፲፱ ሑሩ እንከ መሐሩ ኵሎ አሕዛበ እንዘ ታጠምቅዎሙ በስመ አብ ወወልድ መንፈስ ቅዱስ ያለውን የማታውቅ መስሏቸው ይሆንን ወይስ ፩ ሐዋርያ ያጠመቀውን ፪ኛው ሐዋርያ እንደገና የጠበቀውን ለማጥመቅ ሕግ ይኖር ይሆንን እነሱ ዋና መኳሯና መመኪያ የሚያደርጉት በቅዱስ ጴጥሮስ ስም ሥልጣን ነው። ቅዱስ ጴጥሮስን እነሱ ስለገደሉ ደሙ ሮማ ላይ ስለፈሰሰ ቅዱስ ጳውሎስንም እዚያው ስለደገሙ የነሱ ደም የፈሰሰበትን ቦታ ዓለም ስለምታከብረው ይህንን ነገር እያሰቡ ከክፉ ነገር እንደመራቅና እንደማዘን ሁሉ ለነሱ ዋና መልካም መስሎ ስለሚታያቸው በዚህ ምክንያት ከንቱ ትዕቢት አድሮባቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ ክርስቲያን ሁሉ እንደገና እናጠምቃለን እያሉ ሲደክሙ ይታያሉ። የነሱ መከበር የኛ መናቅ ሰፋ ብሎ የሚታይበት ኢትዮጵያ ያ፩ድ ሐዋርያ ደም በመሬቷ ሳታፈስ በማስቀረቷ ይመስለኛል እንጅ ሃይማኖትን በመቀበል ስንኳንስ በኦሪት በዘመን በሐዲስም ቢሆን ኢትዮጵያ ከሮማ ወደ ኋላ የቀረች አይደለችም

ኢትዮጵያውያን ጽሑፍ ብቻ ሳይሆን ዓለም በተቀበለው መጽሐፍ ግብረ ሐዋርያት ያስረዳል ፰ ፳፮ ኢትዮጵያ ከላይ እንደተጻፈው ሕገ ግዝረትን እየጠበቀች ሰንበትን እያከበረች መሥዋዕተ ኦሪትን እየሠዋች የምትኖር ሀገር ናት ብዬ ከላይ እንዳመለከትሁት ፩ድ የኢትዮጵያዊ የንግሥት ቅንዳኪ የገንዘብ ሹም የሰንበትን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ደርሶ ሲመለስ ወነበቦ መልአከ እግዚአብሔር ለፊሊጶስ ወይቤሎ ተንሥእ ወሑር ጊዜ ቀትር ፍኖተ በድወ ዘያወርድ እምኢየሩሳሌም ለጋዛ ፳፯ ተንሥአ ወሖረ ወረከበ ብዕሴ እምሰብዓ ኢትዮጵያ ኅጽዋ ለቅንዳኪ ንግሥተ ኢትዮጵያ ወመጋቢሃ ውእቱ ላዕለ ኵሉ መዛግብቲሃ ወሖረ ኢየሩሳሌም ይሰግድ። (መመልከት ነው ወደ ኢየሩሳሌም ሊሰግድ ሄዶ ማለቱ ኢትዮጵያ አስቀድማ ሰንበትን የምታከብር እንደነበረች ሰዎቿም ፳ኤል ወደ ባቢሎን ሳይወርዱ የኢትዮጵያን ቦታ በኢየሩሳሌም ላይ ይጠብቅ የነበረው አቤሜሌክ የሚባል ስለ ነቢዩ ኤርምያስና ስለ ኢየሩሳሌም እንደ ወረደ ይናገራል) ፳፰ ወእንዘ ይገብእ ነበረ ዲበ ሠረገላሁ ወያነብብ መጽሐፈ ኢሳይስ ነቢይ። (ይኸውና ከላይ እንደተጻፈው ኢትዮጵያ የሊቃውንት ሀገር መሆንዋን ሲአስረዳ መጽሐፈ ኢሳይስ ሲያነብ ተገኘ በኢትዮጵያ መጽሐፍተ ብሉያት ከሌሉ ይህ ኅጽዋ ለቅንዳኪ ይህን መጽሐፈ ኢሳይያስ ከምን አመጣው እንበል ይሆን።) ፳፱ ወይቤሎ በመንፈስ ቅዱስ ለፊልጶስ ሑር ትልዎ ለዝ ሠረገላ ፴ ወሮጸ ፊልጶስ ወበጽሐ ወስምዓ የነብብ መጽሐፈ ኢሳያስ ነቢይ ወይቤሎ ታአምርኑ እንከ

# ታ ረቡዕ

ዘታነብብ ፴፩ ወይቤሎ ኅጽው በዓይቴ አእምር ለእመ አልቦ ዘመሐረኒ። ወአስተብቊዖ ፊልጶስ ከመ ይዕርግ ይንበር ኅቡረ ምስሌሁ ፴፪ ወነገረ መጽሐፍሰ ኅበ ያነብብ ከመዝ ይብል ከመ በግዕ አምጽእዎ ይጠባሕ ወከመ በግዕ ዘኢነብብ በቅድመ ዘይቀርጾ ከማሁ ኢከሠተ አፉሁ በሕማሙ ፴፫ ተንሥአ እምኵነኔ ወእምነ ምቅሕ ወመኑ ይነግር ልደቶ እስመ ተአተተ እምድር ሕይወቱ ፴፬ ወተመይጦ ኅበ ፊልጶስ ውእቱ ኅጽው ወይቤሎ ብቁዓኒ በእንተ መኑ ይብል ነቢይ ከመዝ በእንተ ርእሰኑ ወመሚ በእንተ ካልዕኑ። ይህ የኢትዮጵያ ንጉሥ ሹም ወደ ፊልጶስ ዘወር ብሎ ነቢዩ እንደዚህ ብሎ የተናገረው ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለ ሌላው ብሎ እባክህ አስረዳኝ አለውና ፴፭ ወከሠተ አፉሁ ፊልጶስ ወእኅዘ ይምሀሮ ወይፈክር ሎቱ

በእንተ ኢየሱስ ውእቱ መጽሐፍ በዚህ መጽሐፍ የተጻፈው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ይተረጉምለት ዘንድ በዠመረ ጊዜ ፊልጶስ አፉን ከፈተ ፴፮ ወአንዘ የሐውሩ በጽሑ ኅበ ማይ ወይቤሎ ውእቱ ኅጽው ነዋ ማይ ወመኑ ይከልአኒ ተጠምቆ። እንደዚህ እያስረዳው ሲሄድ ወደዚያው ውኃ ካለበት ደረሱና ውኃውን ባየ ጊዜ ይኸውና ውኃ አሁን ብጠመቅ ምን ይከለክለኛል አለ። ፴፯ ወአዘዘ ይቅሙ ሠረገላሁ ወዓቀሙ ወወረዱ ኅቡረ ኅበ ማይ ፊልጶስ ወውእቱ ኅጽው ወአጥመቆ ወደዚያው ፊልጶስም ሠረገላውን አቁሙ ብሎ አዘዘና ፊልጶስና የኢትዮጵያ ንግሥት ሹም ወረዱና በውኃው አጥመቀው ከዚያ በኋላ ወደ ሀገሩ መጥቶ ሕገ ጥምቀትን አስተምሯል። በዚያ ጊዜ ስንኳንስ እንደዚህ የተማረ ሊቅ ይቅርና ያልተማረ እንኳ ቢሆን በመዠመሪያ ጥምቀትን ያገኘ ሁሉ እንደ ሌዊ ዘር ቄስ ሆኖ ብቻውን እያስተማረ ያጠምቅ እንደነበረ የታወቀ ነው። ይህም የኢትዮጵያ ንግሥት ሹም በሀገሩ ላይ አላጠመቀም ማለት ከንቱ ስብከት ወሬ ነው። በማነኛውም ቦታ ቢሆን የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት ቀስ እያለ ተስፋፋ እንጅ በቶሎ እየተስፋፋ እንዳልሄደ መጻሕፍቱ ያስረዱናል። ይኸውና በሌላው ቦታ ያለው ይቆይና በኢየሩሳሌም ላይ እንኳ የጌታችን መወለድና ትንሣኤ ሳይታወቅ ብዙ ጊዜ መቆየቱን የዚህ የኢትዮጵያ ንግሥት ሹም ጌታችን ካረገ በኋላ ኢየሩሳሌም ሊሰግድ ሀዶ ሳይሰማ ሲመለስ ሲዠምር በእግዚአብሔር ፈቃድ ፊልጶስ ታዘዘለትና ለመጠበቅ ቻለ። በኢትዮጵያ ጥምቀት የተሰበከ በከሣቴ ብርሃን ሰላሜ ነው። እያሉ የሚጽፉ ሰዎች በርክተዋል የዚህ ጽሑፍ ምንጭ የተገኘው ከሮማ ልዑካን መሆኑ የታወቀ ነው። ሌላው ይቅርና ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ እንዳስተማረ ቅዱስ ማርቆስም ያባቱን ሀገር አስቀድሞም

ያውቀው ስለነበረ መጥቶ እንዳስተማረ ጊዮርጊስ ወልደ ዓሚድ ይጽፋል። ፩ድ ፩ድ ሰዎች ሐዋርያት ኢትዮጵያን ሐዋርያት አልረገጧትም ይላሉ። እንደዚህ ማለታቸው ሐዋርያት የደረሱበት የሚታወቀው በተገደሉበትና ሥቃይ በተቀበሉበት ስለሆነ ኢትዮጵያ ከሐዋርያት ደም ንጹሕ ስለሆነች ሐዋርያትንና ፸ አርዕድትን በሰላም እየተቀበለች ስለምትሸኝ ሐዋርያ የኢትዮጵያን አልረገጣትም እያሉ ያወራሉ። ኢትዮጵያን ያዋረድን መሥሏቸው ነው። ሐዋርያት ዓለምን ሁሉ እንዲያስተምሩ እንደታዘዙ ለመረዳት ማቴዎስ ፳፰ ፲፱ ሑሩ እንከ ወመሐሩ ኵሎ አሕዛብ ያለውን ይመልከት። እንግዲህ እነዚህ ከልባቸው እየፈጠሩ የሚጽፉ ሰዎች ሐዋርያት የታዘዙትን ይፈጽሙም ለማለት ይሆንን። ወይም ደግሞ ኢትዮጵያ የማታውቅ ሀገር ሀገር ሆና

# ቴ ኃሙስ

ይሆንን ወይስ ደግሞ ለሐዋርያት ምንገዱ እሩቅ ሆኖባቸው ይሆንን። ወይም ደግሞ ሐዋርያት የኢትዮጵያ ሰዎች ይገድሉኛል ብለው ፈርተው ይሆንን። ወደ ኢትዮጵያ ሳይመጡ የቀሩበትን ምክንያት ከሮማ ልዑካን የሚሠወር የለምና ምክንያቱን ቢገልጡት ምኞቴ ነበር። በፍሬ ምናጠስ ክርስትና መጣ እያሉ የሚጽፉ በስሕተት ነው እንጅ እውነት አይደለም እውነተኛውን ለመረዳት የሚፈልግ የቤተ ክርስቲያን ስነ ሥርዓት በሰፊው የተቋቋመው በቆስጠንጢኖስ መንግሥት ስለሆነ ቆስጠንጢኖስም የክርስቲያንን ሃይማኖት የወደደና ክርስቲያኖች እንደልባቸው የፈቀዱትን ሃይማኖት እንዲይዙ ያዘዘ ገና ሳይጠመቅ ነበረ ይላል የተጠመቀ በመንግሥቱ ከተቀመጠ ካ፲፯ ዘመኖች በላይ እንደሆነ ታሪክ ይጽፋል። ፫፻ በኒቅያ ጉባዔ ከተሰበሰቡ ደሙኡን አቀባበል ሕግና የቀሳውስቱን የዲያቆናቱን ሹመት ማስተናበር ከዚያ በፊት ደምበኛ ሥራ አልተስፋፋም ነበርና ስለዚህ ሁሉ ነገር አብርሃምና አጽብሐ ስለ ሰሙ ይህን የቤተ መቅደስ ሕግና ሥርዓት ለማስመጣት ባሳቡ ጊዜ ፍሬ ምናጦስን ስንቅና ሰው ጨምረው ወደ እስክንድርያ ልከውት ይህን ሊቀ ጳጳስና ተቀብሎ መጥቷል። የፍሬ መናጦስ ታሪክ በፊተኛው ዘመን ኢትዮጵያ በዙሪያዋ በሚገኙ ወደቦች ሁሉ ከማነኛውም መንግሥት በንግድ ትገናኝ ስለነበር። በንግድ ምክንያት የፍሬ ምናጦስ አባት ፪ት ልጆች

ይዞ በወደብ ሲቀመጥ ታሞ ስለሞተ ፪ቱ ልጆቹ ወደ መንግሥት ቤት ገብተው ሲማሩ አደጉና በመንግሥት ቤት ሥራ ገብተው ከቆዩ በኋላ ፩ኛው ወደ ሀገሩ ተመለሰ ፪ኛው ፍሬ ምናጦስ እዚያው ሲኖር በነገሥታቱ ዘንድ ይህ የቤተ ክህነት ወሬ ዜና በተሰማ ጊዜ ወደ እስክንድርያ ወይም ወደ ቁስጥንጥንያ የሚላክ ስለተገኘ ሰውና የተማረና ምግባሩም የቀና መንፈሳዊ ሰው መሆኑን ከተረዳ በኋላ እሱን ጵጵስና ሾሞና የቤተ ክህነትን ሥራ ሥርዓት የሥጋና የደሙን አቀባበል ተቀብሎ ወንጌልም በጽርዓዊ የተጻፈውን አምጥቷል አምጥቷል። በጽርዕ የተጻፈውን ማምጣቱ አስቀድሞ የተማረው በጽርዕ ስለሆነ ነው። ከዚያ ከመጣ በኋላ የቤተ ክርስቲያንን ሹመት ስለአደላደለ በመዠመሪያ ግዕዝ ያስተማረውን እንበረምን ጵጵስና ሾሟል ከዚያ በኋላ ቅስናና ዲቁና እየሰጠ ወንጌሉንም ከጽርዕ ወደ ግዕዝ እየተረጐመ ስለ ነገራቸው ብርሃን የተሠራው ይህ ነው። እንጅ አባ ሰላም ሊቀ ካህናቱን እንበረምንና ነገሥትቱን አብርሃንና አጽብሐን አጠመቀ ማለት ከሮማውያን የፈለቀ ነው እንጅ እውነት አይደለም እንደዚሁ ሆኖ ሲቆይ በ፬፻፸፫ ዓ.ም ላይ ባጼ ዓልአማዳ ዘመነ መንግሥት ፱ቱ ቅዱሳን ወደ አክሡም መጥተው ግዕዝ እየተማሩ ብዙ ጊዜ ከቆዩ በኋላ በየራሳቸው ከሰው ተለይተው ጾምና ጸሎት እያደረጉ ከዲያቢሎስ ለመዋጋት ልዩ ልዩ ቦታ አበጅተው እዚያ እየገቡ ዘግተው ጾምና ጸሎት ይዘው እስከ ጊዜ ዕረፍታቸው ስለቆዩ ብዙ ታምራት ተደርጎላቸዋል። በግብፅ ገዳማት ሳሉ የምንኵስናን ሥራ ከአቡነ እንጦንዕና መቃርስ ተምረው ያውቁ ስለነበር ፱ቱ ቅዱሳንም ከነሱ ጋር አብረዋቸው ስለነበሩ ሰዎች ምንኵስናን አሳይተዋል።

# ት ዓርብ

የነሱም የቀብ ልጆች በኢትዮጵያ በርክርተውና በዝተው እስከ ዛሬ ይገኛሉ ቅዱሳንና ፍሬ ምናጦስ የነበሩበት ዘመን የተለየ ነው አባ ሰላማ ከእስክንድርያ ጵጵስናን ያመጣ በ፫፻፳፩ ዓ.ም ላይ ነው ፱ቱ ቅዱሳን የመጡ በ፬፻፸፫ ዓ.ም ላይ ነው። የሮማ ልዑካን ከሽ፷፻፵፩ ፶፪ ዓ.ም ወዲህ ያመጡት ረቂቅ ፖለቲክ ኢትዮጵያን ለመያዝ በኃይልና በጦር በግልጽ ለመዋጋት የማይችሉ ስለሆነ በኢትዮጵያ ፍቅር ልባቸው ስለ ተነደፈ በጦርነት እንዳይመጡ ፈሩ። እንዳይቀሩ በምቀንነት ጦር ስለ ተወጉ ተቸገሩና የሚያደርጉትን ቢአጡ መንፈሳውያን መስለው መስቀልና መጽሐፍ እየያዙ ለመስበክ መጥተው የኢትዮጵያን መሠረት በረቂቅ ፖለቲክ ለማፍረስ ስለሚሠሩት አሳብ አገላለጥ የሮማ ልዑካን የኛ ሃይማኖትና ጥምቀት መሠረት ከላይ ጽፌዋለሁ። ደግሞ ታሪክ ስለሚነግረን ከሮማ መሠረት በመዠመሪያ ያመነና የተጠመቀው ዎርኔሎዎስ ነው። ከሱ እንዠምራለን ግብረ ሐዋርያትን ፲፩ ወሀሎ ፩ ብዕሲ በሀገረ ቂሣርያ ዘስሙ ቆርኔሌዎስ ሐቤ ምዕት ለሕዝብ ሰጺራ እንተ ይብልዋ ኢጣልቂ ፪ መልካም የሚሠራ እግዚአብሔርንም የሚፈራ ከቤቱ ሰዎች ሁሉ ጋራ እጅግም ምጽዋት ለሕዝብ ያደረገ ወደ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ለምነ። ፫ እርሱ ገባና ቆርኔሌዎስ አለው። እርሱም በተመለከተው ጊዜ ፈራ አለውም ምንድር ነገር ነው። ጌታ ሆይ መልአኩም አለው ጸሎትህ ምጽዋትህም በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰብ ወጣ ፭ አሁንም ሰዎች ላክ ወደ ኢዮጴ ስምዖንንም ጴጥሮስ የተባለውን አስመጣ ፮ እርሱም እንግድነት መጥቷል ወዳንድ ሰው ሲሞን ቆርበት ፋቂ ወደሚሉት ቤትም በባሕር አጠገብ እርሱ ይነግርሃል ታደርገው ዘንድ የሚገባህን ፯ መላኩም ቆርኔሌዎስን የነገረው በሄደ ጊዜ ነው። ሁለቱን ሎላልቱን ጸራ ዘወትር ከማይለዩት ከጭፍሮቹ ፩ዱን እግዚአብሔርን የሚፈራ ወታደር ፰ ነገሩንም ሁሉ አጫወታቸው ወደ ኢዮጴም ሰደዳቸው ፱ በነገውም እርሳቸው በምንገድ ሲሄዱ ወዳገርም በቀረቡ ጊዜ ጴጥሮስ ወደ ሰገነት ወጣ ይጸልይ ዘንድ በ፮ ሰዓት ፲ ራበውም ሊበላም ወደደ እነሱም ሲአዘጋጁ ድንጋጼ መጣበት ፲፩ ወርዕየ ሰማዮችም ተከፍተው አየ መጋረጃም መጐናጸፊያ ሲወርድ እንደ ታላቅ ልብስ ባ፬ ማዕዘን የተያዘ ታላቅ መጋረጃ ፲፪ በውስጡም

የምድር እንስሳ ሁሉ ነበረበት የሚንቀሳቀስም የሰማይ ወፎች ፲፫ ድምጽም ወደ ርሱ መጣ እንዲህ ሲል ጴጥሮስ ሆይ ተነሣ አርደህ ብላ ፲፬ ጴጥሮስም አለ አቤቱ ከቶ አልበላም የሚአጸይፍም በልቸ አላውቅምና ወኢቦአ ርኩስ ውስተ አፉየ ባሬ ርኩስ ነገር ገብቶ አያውቅምና ብሎ ጴጥሮስ ደነገጠ። ይህ በርኩስ ተመስሎ የታየው ሰው ኢጣልያዊ ነው ፲፭ ድምጽ ደግሞ ፪ኛ ወደርሱ መጣ እግዚአብሔር ያነፃውን አንተ አታርክሰው ፲፮ እንደዚህም ፫ ጊዜ ተናገረውና ከዚያ በኋላ ወደ ሰማይ ተመለሰ ፲፯ ጴጥሮስም በልቡ ሲቸገር ያየው ራዕይ ምንድር ነው ብሎ እነዚያ ሰዎች ቆርኔሌዎስ የላካቸው የሲሞንን ቤት እየጠየቁ በደጅም ቁመው ነበሩ። ፲፰ ይጠይቁ ዘንድ ተጣሩ ሲሞን ጴጥሮስ የሚባለው ከዚያ በእንግድነት መጥቶ እንደሆነ ብለው ፲፱ ጴጥሮስም ባለው ራዕይ ሲአስብ መንፈስ ቅዱስ አለው እነሆ ፫ ሰዎች ይፈልጉሃል። ፳ ተነሥ ውረድና ከርሳቸው ጋራ ሂድ ሁለት ልብም

# ቶ ቀዳም

አትሁን እኔ ልኬአቸዋለሁና ፳፩ ጴጥሮስም ከቆርኔሌዎስ ወደ ተላኩበት ምክንያት ምድር ነው። ፳፪ የ፻ አለቃ ቆርኔሎዎስ ጻድቅ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈራ በአይሁድ ዘንድ የተመሰከረለትም መልአክም ታየው ወደ ቤቱም ያመጣህ ካንተ ዘንድ ነገር ይሰማ ዘንድ ፳፫ እሱም ጸራቸውም ተቀበላቸውም። በነጋም ጊዜ ጴጥሮስ ከነርሱ ጋራ ሄዶ በኢዮጴ ከነበሩ ሰዎችም አብረውት ሄዱ ፳፬ በነጋውም ወደቂሳርያ ገቡ ቆርኔሌዎስም ዘመዶቹን የቀረቡትንም ወዳጆቹን ጸርቶ ይጠብቀው ነበር። ፳፭ ጴጥሮስም በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተቀበለው በተነሣ እኔም ሰው ነኝና ፳፮ ጴጥሮስ ግን አነሣው እንዲህ ሲል ተነሣ እኔም ሰው ነኝና ፳፯ ከርሱ ጋራም እየተናገረም ገባ እጅግም ሰዎች አገኘ ከርሱ ዘንድ ተከማችተው ነበሩና ፳፰ አላቸውም ወደ ሌላ ወገን ግን እግዚአብሔር አሳየኝ ከሰው ማንንም እንዳልል ርኩስ ወይም የሚአጸይፍ ነው። ፳፱ ስለዚህ ሳልጠራጠር መጣሁ። ብትጠሩኝ አሁንም እጠይቃችኋለሁ በምን ምክንያት

አመጣችሁኝ ፴ ቆርኔሌዎስም አለ ካ፬ቀን ዝምሮ እስከዚች ሰዓት ድረስ ጾመኛ ነበርሁ ስጸልይም በቤቴ በ፱ሰዓታ እነሆ ፩ሰው በፊቴ ቆሞ ነጭ ልብስ የለበሰ ፴፩ አለም ቆርኔሌዎስ ሆይ ጸሎትህ ተሰማችልህ ምጽዋትህም ታሰበችልህ በእግዚአብሔር ፊት ፴፪ አሁንም ስምዖን ጴጥሮስ የሚባለውን ላከና ከኢዮጴ አስመጣ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው ቁርበት ፋቂው ቤት በእንግድነት አድርዋልና እርሱ መጥቶ ይነግርሃል። ፴፫ በዚያ ጊዜ ላክሁብህ አንተም መልካም ሠራህ በመምጣትህ። አሁንም እነሆ እኛ አለን ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት እንሰማ ዘንድ አንተ የታዘዝህበትን ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ ፴፫ ፴፬ ጴጥሮስም አፉን ከፈተ አለም በእውነትም አስተዋልሁ እግዚአብሔር ለሰው ፊት እንዳይደላ። ፴፭ ነገር ግን በሕዝብ ሁሉ የሚፈራው ቅን ነገርም የሚያደርግ እርሱ በርሱ ዘንድ የተመረጠ ነው። ፴፮ ወደ ፲ኤል ልጆች የተላከውን ነገር የምሥራች ሲነግራቸው በድንገት በኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ የሁሉ ጌታ ነው። ፴፯ ይህን ነገር እናንተም ታውቃላችሁ በይሁዳ ሁሉ የሆነውን ከገሊላ ዝምሮ ዮሐንስ ካስተማበት ጥምቀት በኋላ ፴፰ ስለ ኢየሱስ ስለ ናዝሬቱ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀብቶታልና የመጣ መልካም ያደረገ ሰይጣን ያሸነፋቸውንም ሁሉ የፈወሰ እግዚአብሔር ከርሱ ጋራ ነበርና ፴፱ እኛም ምስክርዎቹ ነን ባደረገው ነገር ሁሉ በይሁዳ አገር በኢየሩሳሌም ይህን የገደሉት በእንጨትም ላይ የሰቀሉት ፵ ይህነን እግዚአብሔር አስነሣው በ፫ኛ ቀን ሠጠውም ይገለጥ ዘንድ ፵፩ ለሕዝብ ሁሉ አይደለም ለምስክሮች እንጅ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለመረጣቸው እኛም ነን ከርሱ የበላነ የጠጣንም ከሙታን ከተነሣ በኋላ ፵፪ ለሕዝብም እናስተምር እንመሰክርም ዘንድ አዘዘነ ይህ እንደሆነ እግዚአብሔር የመረጠው በሕያዋንና በሙታን ይፈርድ ዘንድ ፫ ለርሱም ይመሰክራሉ። ነቢያት ሁሉ በርሱ የሚአምን ሁሉ የኃጢአቱን

ሥርዬት እንዲወስድ በስሙ ፵፬ ጴጥሮስም ይህነን ነገር ሲናገር መንፈስ ቅዱስ ነገሩን በሰሙት ሁሉ ላይ ወረደ ፵፭ ከግዝረት ወገንም የሚሆኑ ከጴጥሮስ ጋራ የመጡ ምዕመናን ሁሉ ደነገጡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በአሕዛብ ላይ ደግሞ ስለፈሰሰ ፵፮ በሌላ ቋንቋ

# ኀ እኍድ

ሲናገሩ ሰምቷቸዋልና እግዚአብሔርንም ኢያመሰገኑ ፵፯ በዚያ ጊዜ ጴጥሮስ መለሰ ዓለም በውኑ ማንም ውኃ ይከለክላልን አሊህ እንዳይጠመቁ መንፈስ ቅዱስን ይውሰዱ እኛ ደግሞ እንደወሰድን ፵፰ በጌታ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው የዚያን ጊዜ ለመኑት ከርሳቸው ዘንድ አያሌ ቀን ይቀመጥ ዘንድ ሁሉ ድካም ሮማውያን ሕግ ግዝረትን የማያውቁ አሕዛቦች እንደነበሩ ለማስረዳት ስለሆነ ላንባቢ እንዲመቸው ለይቶ እገልጽለታለሁ። ፩ኛ ፲ ፲፬ ወኢቦአ ርኩስ ውስተ አፉየ ወኢበላዕኩ ዘኢኮነ ንጹሐ ፪ኛ ፲ ፳፰ ወይቤሎሙ ጴጥሮስ ታአምሩ ለሊክሙ ከመ ኢይከውኖ ለብዕሲ አይሁዳዊ ከመ ይሑር ወይባእ ኀበ ካልዕ ሕዝብ።

፫ኛ ፲ ፴፬ ወከሠተ አፉሁ ጴጥሮስ ወይቤ በአማን ርኢኩ ከመ እግዚአብሔር ኢያደሉ ለግ ጽ ፬ኛ ፲፩ ወአመ ዓርገ ጴጥሮስ ኢየሩሳሌም ተዋቀስዎ ቢጹ እለ እምአይሁድ።

፫ ወይቤልዎ ቦእከ ኀበ እደው እለ ኢኮኑ ግዙራነ ወበላዕከ ምስሌሆሙ ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉ ማስረጃዎች የሚነገሩትን መዝኖ ማወቅና መረዳት የግድ ነው። ይህ ጽሑፍ በዓለም ቅዱስ መጽሐፍ የሚገኝ ነው። ግን ሮማውያን ይህን ሳይመለከቱ ወደ ኩራትና ወደ ትዕቢቱ ምንገድ ሲገሠግሱ ይገኛሉ የህጽዋ ለቅንዳኪንና የ፻ አለቃ ቆርኔሌዎስን ነገርና ታሪክ ከዚህ በላይ የጻፉሑት በዓለም የሚገኙት አንባቢዎች ልኩን እንዲያውቁት ነው የሮማ ቤተ ክርቲያን ተደላድላ የቆመችበትን ጊዜ ታሪክ ይመሰክራል ለጊዜው የሮማ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አሁን እዚህ ላይ ደርሷል ለወደፊቱ በሰፊው ይቀጥላል። ከሽ፫የ፹፩ ዓ ፶፪ ዓ.ም ወዲህ የሮማ መንግሥት የጦር ፕሮፓጋንድ ባልደረቦች መንፈሳውያን መስለው በኢትዮጵያ ላይ እየተዘዋወሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ እያፋጁ ደግሞ በዚሁ ረቂቅ

ፖለቲክ የኢትዮጵያን መሠረት ለማጥፋት የዘረጉት ፖለቲክ በጣም ተስፋፍቶላቸው ስለሚታይ በኢትዮጵያ ላይ የወምበር ተካፋይነት ይዘው ሲገኙ የሚገርም ነው። በነሱ አሳብ ኢትዮጵያ ከነሱ የበለጠ መሠረት ይዛ የምትገኝ መሆንዋን ለመደምሰስ ይደክማሉ። ይህንም ድካም በረቂቅ ቀስ እያሉ ውሥጡን ነው የሚሄዱ የፖለቲኩ አካሄድ ፍሬ ምናጦስ ከውጭ የመጣ ከሆነ ፱ቱ ቅዱሳንም ከግብጽ ስለመጡና በኢትዮጵያ ክብር ያላቸው በመሆናቸው ፱ቱ ቅዱሳንንም የሮማ ናቸው ካቶሊካውያን ነበሩ ይላሉ። ስለዚህ ፱ቱ ቅዱሳን የመጡበት ፩ድ እንዲሆንላቸው አብርሃምንና አጽብሃን ሠርዘው ፍሬ ምናጦስ በአልዓሜዳ ልጅ በዔዘና ዘመን ክርስትና አመጣ እያሉ ይጽፋሉ። በተ፱ቱ ቅዱሳን እግር ገብቶ የመምህርነት ደረጃ ይዞ ለመገኘት በማለት። ለማስፋፋት ጥንት መሠረት የሌላት ለማድረግ ፍሬ ምናጦስ የኢትዮጵያ መጻሕፍት በሙሉ ከጽርዕ) ወደ ግዕዝ ገልብጦታል እያሉ ባሳተልም በጽሑፍም ይሰብካሉ ይሕም ሐሰት እንዳይባል በግዕዝ ባሳተሙት መጽሐፈ ኦሪት መቅድም ላይ ተጽፎ የሚገኘውን ከዚህ አስከትዬ ለአንባቢዎች እገልጻለሁ። ቀዳሚ አፍልሶተ መጻሕፍት ቅዱሳት ኮነ ኀበ ልሳነ ግዕዝ እመጽሐፎሙ ለ፸ ሊቃውንት ይላል ኢትዮጵያ ቅዱሳት መጻሕፍትን መቀበል የዠመረች ከልደተ ክርስቶስ በፊት ከሽ ዘመን አስቀድሞ መሆኑን ከላይ አስረድቻለሁ። እነሱ እንደዚህ ፖለቲክ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልብ አፍዝዘው የሀገሪቱን ክብር

# ኀ ሰኑይ

ዝቅ ዝቅ እያደረጉ የሕዝቡን መንፈስ ከለወጡ በኋላ የኢትዮጵያን ነፃነት ለመደምሰስ መንፈሳውያን መስለ ከሚሰብኩት የሚገኘው እንደዚህ የውሸት ፖለቲክ ሲገኝ ምን ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። ፸ ሊቃውንትን ወደ ኢትዮጵያ ምን አመጣው ወበእንተ ሐዲሳትሰ እመጽሐፈ ጽርዕ ዘሐዲስ ኪዳን። ወዓዕልዎትንሂ ኅቡረ ይሁብዎ ለቅዱስ ፍሬ መናጦስ ወለ፱ቱ ቅዱሳን እለ መጽኡ እምሶርያ ይላል። ከላይ አስተያየታቸውን እንደ ገለጹሑት ይኸውና ጽሑፋቸው እንደዚህ ያለው ሐሰት እየተጻፈ ለሚገኝ አንባቢ ሁሉ ይህን በረቂቅ ፖለቲክ መንፈሳውያን መስለው ከመንፈሳዊው መጽሐፍን አስጠግተው ጽፈውት ሲገኝ ምን ይመስላል ከመዠመሪያው ላይ ቀዳሚ አፍልሶተ መጻሕፍት ቅዱሳን ኮነ ኀበ ልሳነ ግዕዝ እመጽሐፎሙ ለ፸ ሊቃውንት ያሉት ከጽርዕ ተተረጐመ ማለታቸው ነው። ፪ኛ መለሱና ወበእንተ ሐዲሳትሰ እመጽሐፈ ጽርዕ ዘሐዲስ ኪዳን ወዓዕልዎቶንሂ ኅቡኒ ይሁብ ለቅዱስ ፍሬ ምናጦስ ወለ፱ ቅዱሳን እለመጽኡ እምሦርያ ያሉት ያው ነው መጻሕፍተ ብሉያት ከኢትዮጵያ አልነበሩም ብለው የክህደት አሳባቸውን በኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ለመዝራት አስበው የሠሩት ነው። እነሱ በረቂቅ ፖለቲካቸው ግዕዝ እንድትጠፋ ያማርኛን ትምርት እነሱ ያስፋፉ መሆናቸውንም በዚሁ ገልጸውት ይገኛል። ይህም ከዚህ እንደሚከተለው ነው። በ፲ወ፩ ዘመን ሶበ ልሳነ አምኃራ ህየንተ ልሳን ቀዳማዊ ዘኢትዮጵያ ሰፈነ ውስተ ቤተ መንግሥት ወውስተ ምግብና ፩ዱ ሰብዓ ብሔር። ጥቀ መምህራን ወጠኑ ያዕልው ቅዱሳተ መጻሕፍተ እምልሳነ ግዕዝ ለኀበ ልሳነ አምኃራ ወለዘኒ ግብር አኀዙ ይፈጽምዎ ኢየሱሳውያን እለ መሐሩ ወንጌለ ለሰብዓ ኢትዮጵያ እም፲ወ፰፻ ፱ወ፲ ዓ እስከ ፲ወ ፮፻ወ፴ ዓ.ም እለ እምነገረ ግብሮሙ ለአባ አቡፈረንጅ ወለአባ ባልዳይራ ይላል። ግዕዝ እንዲጠፋ ማሰባቸው በጥንታውያን የሚገኘው የኢትዮጵያ አባቶች ክብርና የጥበብም መዝገብ ሁሉ እንዲጠፋ ለማድረግ አስበው ነው። ይህንም የሠሩበት ዘመን በሽ፰፻፶፯ ያለው በፈረንጅ ቁጥር ነው። በኛ ከሽ፰፻፵፱ ዓ.ም እከ ሽ፮፻ወ፴፱ ዓ.ም ነው። ያማርኛን ትምህርቲየሱሳውያን ለኢትዮጵያ ሽዎች ወንጌልን ያስተማሩ እያለ ፖለቲኩን ይዘራዋል። ባለርሥቱን እየገደሉ ቤተ ክርስቲያኑን እያቃጠሉ ቤተ ክርስቲያን ሠርተን ጸሎት እናደርጋለን ይላሉ ይህን ጸሎት የሚቀበል እግዚአብሔር ነውን እግዚአብሔርማ እንደሚቀበለው ከታሰበ አስቀድሞ የማያውቅ የማይፈጽም እንደዚህ ያለውን ሥራ እግዚአብሔር አይቀበለውም እንደዚህ ያለውንማ የሚቀበል ከሆነ የቃየልንም መሥዋዕት ሳይቀበል መቅረቱ የሚሠረዝ ነው (ለማለት የተቃረበ ነው። እለ መሐሩ ወንጌለ ለሰብዓ ኢትዮጵያ ይላል ወንጌል ያሉት የክርስቶስን ወንጌል አስመስለው የሚጽፉት በረቂቅ ፖለቲክ የሚሠሩትን የቅሚያና የሥርቆት ሥራ ነው። ሥርቆትም ያልኩት ያለ ንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ ከነ ኢብራሂም ሡልጣን ማለት ገዝቶናል

እያሉ ጽፈው ስለሚገኙ ነው። ቅሚያም ያልኩት ወሰን በማያገናኘው አገር ሄዶ በሰው ርስት ላይ ቤተ ክርስቲያን ተከልኩ እያለ ሕዝቡን ማታለል። በዓለም መንግሥታት ሕግ ስንኳንስ በሌላ አገር ሂድ ያለ ንጉሡ ነገሥቱ ፈቃድ መሬት መግዛት ለእግሩ እንኳ ገብቶ ለማደር ፈቃድ ጠይቆ መሆኑን ማንም አይዘነጋውም እንደዚህ በወንጀለኛነት ገብቶ በተገደሉበት ሀገር ላይ ቤተ

# ኂ ሥሉስ

ክርስቲያን ሠራሁ እያሉ የሐሰት ጽሑፍ ከቅዱስ መጽሐፍ ጋራ እያስታከኩ መጻፍ የተገባ ይሆንን በዚሁ በኦሪት መቅድም በ፸ኛው ገጽ ዝንቱ መጽሐፍ አኮ ዘሰብዕ አላ መጽሐፈ እግዚአብሔር ውእቱ እስመ ውእቱ ለሊሁ ዘጻሐፎ ወዘአቀቦ ይላል። እንግዲህ ይህን ጽሑፍ ማስተዋል ነው። አሁን በዚህ ጽሑፍ ስንት ስሕተት አለባት ፩ኛ በ፪ኛው ገጽ ቀዳሚ አፍልሰተ መጻሕፍት ኮነ ኀበ ልሳነ ግዕዝ እመ ጽሐፎሙ ለ፸ ሊቃውንት ይላል።

፪ኛ ወዓዕልዎቶንዚ ኀቡረ ይሁብዎ ለቅ ፍሬ ምናጠስ ወለ፱ ቅዱሳን ይላል። ፫ኛው በ፫ኛው ገጽ

መቅድመ ኵሉ አስምዕ ከመ ሐለይኩ እኅትም ቃለ እግዚአብሔር በልሳነ ግዕዝ በከመ ሀሎ ይትረከብ ውስተ መጻሕፍት ሠናያት ወዘትካት ዘሀለዋ በዘመነ መዋዕሊሁ ለቅዱስ ፍሬ መናጦስ ወለ፱ቱ ቅዱሳን ይላል።

፬ኛው ቀዳሚ ዐቢይ ጻሕቅየ ኮነ አስተጋብኦ መጻሕፍት ወአስተናጽሮቶን ምዕለ መጽሐፈ ፸ ሊቃውንት ወምስለ ካልዓት መጽሐፍተ ሶርያ ወዓረብ ይላል።

፫ኛ ዳዕሙ ኢትዮጵዊት ቤተ ክርስቲያን እምጥንቱ አ ክህለት ረኪበ ፪ መጻሕፍት መቃብያን በይነ ዘኢሀለዋ በመጽሐፎሙ ለሰብዓ ሊቃውንት ይላል ፮ኛው ባ፬ኛው ገጽ ወባሕቱ ቦ በውስተ መዝገበ መጻሕፍት ዘሎንደን መጽሐፈ መቃብያን በልሳነ ግዕዝ ዘፍጹመ ይዔረ ምስለ ሮማይስጥ ይላል።

፯ኛ ወዝንቱ ኮነ በከመ እትሐዘብ አነ በመዋዕሊሆሙ ለኢየሱሳውያን ውስተ ኢትዮጵያ ዳዕሙ አንሰ ኢክህልኩ ረኪቦቶ በዝ ብሔር ይላል።

፰ኛው በእንተዝኬ ከመ ቤተ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊት ኢትኅጣዕ አሎንተ ፪ተ መጻሕፍተ ጥቀ በቋእያተ ሐለይኩ አዕልዎን እምልሳነ ዮናኒ ኀበ ግዕዝ ይላል ፱ነኛው ወአነኒ መጠነ ክሂሎትየ ኢያንተጉ ኢትካዘ ኢትጋሃ ወኢጻእረ ከመ ሰብዓ ኢትዮጵያ ይርከቡ በዝንቱ ግብርየ ቃለ እግዚአብሔር አማናዊ በከመ ተምርህዎ አበዊሆሙ እምአፉሁ ለቅዱስ ፍሬ ምናጦስ።

፲ኛው መቅድመ ኩሉ አአኵቶ ለጥቀ ክቡር አባ ገሪዞን ሰባኪያን ዘኢትዮጵያ ከላይ የተጻፈው እነዚህ ባ፲ቱ ቃላተ ኦሪት ልክ ፲ሩ ፖለቲኮች እንደተጻፉ ገጹን እያመለከትኩ መጻፌ ላንባቢ የተመቸ ምንገድ መግለጤ ስለሆነ አንባቢ ሆይ እንግዲህ ያ፲ሩን ፕለቲኮች ሐተታ ከዚህ አስከትየ በየተራቸው እሞላለሁ። ስለ ፩ኛው ቀዳሚ አፍልሶተ መጻሕፍት ኮነ ልሳነ ግዕዝ እመጽሐፎሙ ለ፸ ሊቃውንት እንግዲህ አስበው ያመጡትን ረቂቅ ተንኮል ማስተዋል ነው። ፸ዓ ሊቃውንት በበጥሊሞስ ዘመን ፸ አይሁድ አስጠርቶ ለ፸ ሊቃውንት ጽራውያን መጻሕፍተ ብሉያት እንዲገለበጡ ማድረጉን ታሪክ ይነግረናል። ግን ይህ ዛሬ የዓለም ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችው ቅዱስ መጽሐፍ ያ ፸ ሊቃውንት ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ የገለበጡት እንዳልሆነ የሚአጠራርጥ ነገር ይገኝበታል። የሚአጠራጥር ያልኩትም እንደዚህ ነው ይህ አሁን የዓለም ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችው ቅዱስ መጽሐፍ። አይሁድ ስለ ጌታችን መወለድ ጊዜው ገና አልደረሰም

## ኃ ረቡዕ

ለማለት የአበውን ዕድሜና ትውልድ ፍቀው ኃይለ ቃል ያለበትንም ከውሥጡ አጥፍተው መጽሐፈ ሄኖክና ኩፋሌን ከዚያም የተረፉ ፲፱ መጻሕፍት ጨምረው በጭራሽ አጥፍተው ያነን እንደገና አቃለውና ቆንጽለው ጽፈው የሰጧቸውን ነው። በ፸ ሊቃውንት ጊዜ የዘመኑ ቁጥርና የአበው ዕድሜ በዚያ ጊዜ ተቀነሰ ለማለት ገና ጌታችን ሳይወለድ ይህን የዘመንና የትውልድ ማሳነስ ከወዴት መጣ ለማለት ችግር ስለሆነ ነው። እርግጥ ነው የኢትዮጵያ መጽሐፈ ብሉያትና የዓለም ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችውን ቅዱስ መጽሐፍ መርምሮ ላልተመለከተ ሰው ይህ በዓለም ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚገኘው ቅዱስ መጽሐፍ ፸ ሊቃውንት የጻፉት ነው ቢል ፍርዱ ቀሊል ነው። እነዚህ የሮማ ልዑካን ግን የኢትዮጵውያን መጽሐፈ ኦሪትና የነሱን መጽሐፍ ኦሪት አመዛዝነው የአበውን ትውልድና የዘመኑን ቁጥር በኦሪት ዘፍጥረት ፫ ምዕ እንደ

ኢትዮጵያው መጽሐፈ ኦሪት አስተካክለው ጽፈውት ይገኛል። ብለው ከላይ ዘርዝሬ እየገለጽኩ እንዳመጣሁቱ አባ ሰላማና ፱ቱ ቅዱሳን ከጽርዕ ወደ ግዕዝ ገለበጡት ይላል። እሽ እንደነሱም ይሁን ያልኩ ጊዜ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ብሉያትና የጽርዓውያን ተባብረው መገኘታቸውን አውቀውታል ይሆንን። አሁን የጽርዓውያን ቅዱስ መጽሐፍ እነሱ በግዕዝ ለኛ ካሳተሙት ጋራ ትክክል ሆኖ ይገኛል ይሆንን። በምን ምክንያት ፩ ዓይነት ተጻፈ እዚህ ከመቅድሙ በ፩ኛ ገጽ ላይ ከጽርዕ የተገለበጠ ነው ተባለ። በኦሪቱ ፫ም ላይ ስለ አበው ትውልድ በተጻፈው በጽራዊው ኦሪት የሌለውን ጽፈውት ይገኛል። አንባቢ ይድከምበት።

፩ኛ ወዓዕልዎቶንሂ ይሁብዎ ለፍሬ ምናጦስ ወለ፱ቱ ቅዱሳን ከላይ እንደተጻፈው መቸም በሽ፫፻፶፬ ዓ.ም ተነሥተው የኢትዮጵያን ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት አጥፍተው ለመውረስ መክንያት ሲፍልጉ የኢትዮጵያን ነፃነት ለመደምሰስ ምንገድ ሲጠርጉ በኢትዮጵያ አስቀድሞ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ከሽ ዘመኖች በፊት በጻሕፍተ ብሉያትን ተቀብላ የኖረች ነቢያት የመሰከሩላት ገናናይቱን ሀገር ለዚሁም ማስረጃ ከላይ ስለ ንግሥት ቅንዳኪና ስለ ኢጣልያዊ ቆርኔሌዎስ በሰፊው የሁለቱን አገሮች አስተያየት በማይታበለው ማስረጃ አሳይቻለሁ። የነሱ ታሪክ ያለፈው አያጣላንም የምንጠላው የኛን መሠረት ለማፍረስ በትምርት ቀዳሚ መስለው እኛ እናስተምራችሁ እያልን አገራቸውን እንቀማቸው በማለት ስለሚሠሩብን ፖለቲክ ነው። በ፩ኛውም ላይ የተጻፈው በፊት ለፍሬ ምናጦስ። በኋላ ደግሞ ለ፱ቱ ቅዱሳን መጻሕፍት ገለበጡ ይላሉ። እንደዚህ ማለታቸው ከላይ እንደተጻፈው ፱ቱ ቅዱሳን ከግብጽ ገዳም ስለ እመቤታችን ፍቅር እመቤታችን ኢትዮጵያን ዓሥራት አድርጋ ተቀብላታለች የሚል ጽሑፍ ስላገኙ በዚህ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጽላተ ሙሴን ተማጽነው ግዕዝ እየተማሩ ብዙ ዘመን ደጅ ሲጠኑ ከቆዩ በኋላ በየበዓታቸው እንደ ሄዱ ከላይ አስረድቻለሁ። እሁን እነዚህ ሰባኪዎች የሚመኙት እነሱ ከውጭ የመጡ ስለነበሩ እኛም እነሱን ካቶሊውያን ነበሩ እንበልና በነሱ እግር ገብተን አስተማሪ እንሁንና ሕዝቡን እየሰበክን ይህን ያህል በ፬ሽ፰፻፵ ዘመን ሙሉ ነፃነቷ ታውቆ የንጉሠ ነገሥነት ክብሯ ሳይጎድል የምትኖሪቱን ሀገር በፖለቲክ እንወስዳለን

## ኄ ኀሙስ

ለማለት የኢትዮጵያ መጻሕፍት ከጽርዕ ወደ ግዕዝ የተገለበጡ ናቸው እያሉ የሐሰት ጽሑፋቸውን ከዋናው መጽሐፍ አስጠግተው ጽፈውት ይገኛል እንባቢ ሆይ ሐሰት ይዠ አገሬን ለመርዳት የተነሣሁ አይደለሁም እኔ የምረዳው እውነቱን ይዠ ነው እንጅ ለንባቢ የማቀርበው አጭር ማስረጃ በኢትዮጵያ አስቀድሞ መጻሕፍተ ብሉያት ከሌሉ የኢትዮጵያ ንግሥት ሹም ስለምን ለመስገድ ሄደ። ስለምን መጽሐፈ ኢሳይያስ ሲደግሞ ተገኘ ሐዋርያት ፰ ፲፱።

ስለ ፫ኛው ሐተታ የሚለው እንደዚሁ የተ፱ቱ ቅዱሳን ተከታይ ለመሆን ምንገዱን ለማረጋገጥና እኔ አሳቤ መጻሕፍቱን አሳተምኩ ከፍሬ ምናጦስ የተገኙትን በ፱ቱ ቅዱሳንም ይላል ያው ነው። የተለመደ ለማድረግ ይመላልሱታል።

ስለ ፬ኛው መዠመሪያ ትልቁ አሳቤ ከ፸ ሊቃውንት መጽሐፍና ከሌሎችም ከሶርያና ከዓረብ መጻሕፍቶች ለማነጣጠር ነበር ይላል። እውነት ከሆነ የ፸ ሊቃውንት መጽሐፍ ምን ይላል የሶርያስ መጽሐፍ ምን ይላል። የኢትዮጵያ መጽሐፍ ኦሪት ምን ይላል። እነሱ በጻፉት መጽሐፍ ኦሪት በገጽ ፯ ኦሪት ዘፍጥረት ፭ ፩ ዝ መጽሐፍ ዘፍጥረተ እጓለ እምሕያው ወበ ዕለተ አመ ገብሮ እግዚአብሔር ለአዳም እግዚአብሔር ገብሮሙ ፪ወፈጠሮሙ ተባዕተ ወአንስተ ወእምዘ ባረከ እግዚአብሔር ላእሌሆሙ ወስመዮ ስሞ

አዳም በዕለተ እንተ ባቲ ፈጠሮሙ ፫ ወሐይወ አዳም እምድኅረ ወለዶ ለሴት ፪ተ ፻ተ ወ፴ ዓመተ ወወለደ ሎቱ ዘከመ ራዕዩ ወአምሳሉ ወሰመዮ ስሞ ሴት ፬ ወሐይወ አዳም እምድኅረ ወለደ ለሴት ፯፻ተ ዓመተ ወወለዶ ደቂቀ ወአዋልደ ፭ ወኮነ ሁሉ መዋዕሊሁ ለአዳም ፱፻ተ ወ፴ ዓመተ ወሞተ ፮ ወሐይወ ሴት ፪፻ ፭ዓመተ ወለዶ ለሄኖስ ፯ ወሐይወ ሴት እምድኅረ ወልዶ ለሄኖስ ፯፻ተ ወ፯ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፰ ወኮነ ኩሉ መዋዕለ ሕይወቱ ለሴት ፱፻ተ ፲፪ተ ዓመተ ወሞተ ፱ ወሐይወ ሄኖስ ፻ተ ወ፺ ዓመተ ወወለዶ ለቃይናን ፲ ወሐይወ ሄኖስ እምድኅረ ወለደ ለቃይናን ፯፻ተ ፲፭ተ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ አዋልደ ፲፩ ወኮነ ኩሉ መዋዕሊሁ ለሄኖስ ፱፻ተ ወ፭ተ ዓመት ወሞተ ፲፪ ወሐይወ ቃይናን ፻ ወ፸ ዓመተ ወወለደ ለመላኤል ፲፫ ወሐይወ ታይናን እምድኅረ ወለዶ ለመላኤል ፯፻ተ ወ፵ ዓመት ወወለደ ደቂቅ ወአዋልደ ፲፬ ወኮነ ኩሉ መዋዕሊሁ ለቃይናን ፱፻ተ ወ፲ተ ዓመተ ወሞተ ፲፭ ወሐይወ መላልኤል ፻፷ ወ፭ ዓመት ወወለደ ለያሬድ ፲፮ ወሐይወ መላልኤል እምድኅረ ወልዶ ለያሬድ ፯፻ተ ወ፴ ዓመተ ወወለደ ደቀ ወአዋልደ ፲፯ ወኮነ ኩሉ መዋዕሊሁ ለመላልኤል ፱፻ ወ፭ተ ዓመተ ወሞተ ፲፰ ወሐይወ ያሬድ ፻ወ፷ ወ፪ተ ዓመተ ወወለደ ለሄኖክ ፲፱ ወሐይወ ያሬድ እምድኅረ ወለዶ ለሄኖክ ፰፻ተ ዓመተ ወወለደ ደቀ ወአዋልደ ፳ ኮነ ኩሉ መዋዕሊሁ ለያሬድ ፱፻ተ ፷ ወ፪ተ ዓመተ ወሞተ ፳፩ ወሐይወ ሄኖክ ፻፷ወ፭ ዓመተ ወወለዶ ለማቱሳላ ፳ ወአሥመሮ ሄኖክ ለእግዚአብሔር ወእምድኅረ ውለዶ ለማቱሳላ ፪፻ተ ዓመተ ወወለደ ደቂቀ ወአዋልደ ፳፫ ወኮነ ኮሉ መዋዕለ ሁሉ ለሄኖክ ፫፻፷ወ፭ተ ዓመተ። ከዚህ በላይ እንደተጻፈው የኢትዮጵያው መጽሐፈ ኦሪት እንደሚለው አድርገው በሸ፱፻፲፭ ዓ.ም አሥመራ በማኅተመ ፍራንኪስካና ከመጻሕፍተ ሶርያ ወጽርዕ ወዓረብ በብራና ከተጻፉበትም ቀደምት መጻሕፍቶች አስማምተን አሳትመነው በሚሉት መጽሐፍ ኦሪት ከላይ እንደተጻፈው

# ኀ ዓርብ

ከጻፉ በላይ መልሰው በመቅድሙ ላይ ባ፬ኛ ቁጥር እንደ ገለጽኩት አሳቤ ከ፸ ሊቃውንት መጽሐፍትና ከሶርያና ካረብ መጻሕፍቶች ለማነጣጠር ነበር ይላል የ፸ ሊቃውንት መጽሐፍና የሶርያ መጽሐፍ የተለያዩበትና የተገናኙበት የትኛው ነበር የትኛው ነው። ደግሞ አይሁድ ቆንጽለው እንደጻፉት ዓለም በተቀበለው መጽሐፍ በኋላ ከዚህ ተከትሎ ይጻፋል።

ስለ ፭ኛው ጽሑፍ ሐተታ ዳዕሙ ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያን እምጥንቱ ኢክህለት ረኪበ ፪ መጻሕፍተ መቃብያን በይነዘኢ ሀለዋ በመጽሐፎሙ ለ፸ዓ ሊቃውንት ይላል። ከላይ እንደገለጽኩ የዓለም ቤተ ክርስቲያን በተቀበለችው ቅዱስ መጽሐፍ የሌለውን ከኢትዮጵያ መጽሐፈ ኦሪት የሚገኘውን የአበውን ዕድሜ ዘመን ከጻፉ በኋላ እንደ ገና ተመልሰው የኢትዮጵያ መጻሕፍተ ኦሪት ፸ ሊቃውንት የጻፉትን ከጽርዕ ቋንቋ አባ ሰላማ ገለበጠው ብለው ለጻፉት እንዲመቻቸው ፸ ሊቃውንት መጻሕፍተ ብሉያትን ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ በገለበጡ ጊዜ መቃብያን አልተጻፉም

ነበርና ብለው በማስመሰል የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ፪ቱን መቃብያን ማግኘት አልቻለችም። ብለው ጽፈዋል። ይህን ከባድ ሐሰት ነገር በጽሑፍ ሲአሳርፉት ትንሽም ፍርሀት የለባቸውም።

ስለ ፺ኛው ሐተታ ባ፸ኛው ገጽ በጻፉት አሪት መቅድም ወባሕቱ ቦ በውስተ መዝገበ መጻሕፍት ዘሎዶን መጽሐፈ መቃብያን በልሳነ ግዕዝ ዘፍጹም ይዔሪ ምስለ ሮማይስጥ ይላል። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፪ቱ መቃብያን አይገኙም ብለው ከላይ ከጻፉት በኋላ እንደገና መልሰው በውጭ አገር የሚገኙትን መጻሐፍት የሚመሰክሩባቸው ስለሆነ በሎንዶን ቤተ መጻሕፍት ቤት በግዕዝ ለተጻፈ መቃብያን

አለ ካሉ በኋላ ደሞ መልሰው ልክ ከሮማይስጥ የተመሳሰለ ነው ብለዋል ይህ ሐሰት ዋና ተግባራቸው ስለሆነ ያለ ሥጋት ሐሰቱን በጽሑፍ ላይ አስፍረውት ሲገኝ በግዕዝ የተጻፈውን መቃብያንና እነሱ ከሮማይስጥ አገኘነው ብለው የጻፉትን መቃብያን መርምረው ባላነበቡ ሰዎች ዘንድ እውነት መስሎ ስለሚታይና ስለሚያታልል እውነት ይመስላል እንጅ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘውና እነሱ የጻፉት በፍጹም የተለያየ ነው። ፪ቱ መጻሕፍቶች ቀርበው በተነበቡ ጊዜ እንደምን ያለ ኃፍረት በተገለጸ ነበር። ግን እንዳይመረመር ብዙ ጊዜ ይህን የመሰለውን ሐሰት እየጻፉ ብዙው ሲጸናላቸው ስላዩ በቀጥታ ሐሰቱን ማዘጋጀት ዋና ተግባራቸው ሆነና ብዙውን በነሱ ምንገድ እንደነዱት ወደፊት እየገለጽሁ እጽፋለሁ። ስለ ፺ኛው ሐተታ ወዝንቱኒ ኮነ በከመ እትሔዘብ አነ በመዋዕሌሆሙ ለኢየሱሳውያን ውስተ ኢትዮጵያ አንሰ ኢክህልኩ ረኪቦቶ በዝ ብሔር ይላል። ይህም ያው ሐሰታቸውን ከላይ እንደ ገለጽነው መቸም ያው ሐሰቱ የሚታወቅባቸውና የማይማማቸው ስለሆነ እየቸገራቸው የማይመስለውን ነገር ሁሉ መረጃ እየመሰላቸው ያለሆነውን ነገር ሁሉ ይጽፋሉ። እዚህ ላይም እኔ እንደማመዛዝነው ኢየሱሳውያን ወደ ኢትዮጵያ ያመጡት ነው እንጅ በኢትዮጵያ ውስጥ መጽሐፈ መቃብያን አላገኘሁም ብለው ጽፈዋል። እንግዲህ ይህም ከእውነት ገብቶ በጽሑፍ እላይ አረፈ ለመሆኑ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሽ የሚቆጠሩ የተገኙ እንደሆነ ምን ይመስላል። ፳ኛ ሐተታ በእንተዝኬ ከመ ቤተ ክርስ ኢትዮጵዊት

## ኖ ቀዳም

ኢትኅጣእ እሎንተ ፪ተ መጻሕፍተ በቋዕያተ ሓለይኩ አዕልዎን አምልሳነ ዮናኒ ኀበ ግዕዝ ያለው ይህም ያው ነው። ፴ ውሸት ሲሰበሰብ ፩ድ እውነት ይሆን ይመስል ሐሰቱን ሁሉ እያደጋገፉ ይለቁታል የመጻሕፍቱን ጠባይ መርምሮ ያላወቀ ሁሉ ይህን እየተቀበለ እውነት ነገር ያገኘሁ እየመሰለው ይህን ተቀብሎ ወደ ሥራ በማግባት ይገኛል። ስለዚህ የኢትዮጵያን ከትክክለኛው መጽሐፍ ታሪክ መሠረት ለማውጣት እውነት የጻፉ እያስመሰሉ ሲጽፉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስበው የጻፉ መስለው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንዳታጣ አስቤ ከዮናኒ ወደ ግዕዝ ላስገለብጥላት አሰብኩ ብሎ እነሱ ባሳተሙት መጽሐፈ ነቢያት ፪ት መቃብያን ፩ኛው ፲፪ ምዕራፍ ፪ኛውም ፲፫ ምዕራፍ የሆነ ተጽፎ ይገኛል። ይህም ለዚሁ ለሐሰቱ ስብከታቸው ማስፋፊያ ብለው የሠሩት ነው እንጅ የነሱን ዝርክርክ ከ፸ ሊቃውንት የተጻፈ አስመስሎ የጻፉት ያንኑ የኢትዮጵያ መታሰቢያ ጥንታዊውን አስሊውን መጽሐፍ ለማስተው አስበው የሠሩት ነው ከኢትዮጵያ በቅንነት ለክርስቶስ የሚሠሩ ከሆነ በኢትዮጵያ የሚገኘውን ከኢትዮጵያ የተገኘ መጽሐፍ የተገለበጠ ብለው ቢጽፉት ምን ይከለክላቸው ነበር። እነሱ በረቂቅ ፖለቲክ የሚሠሩት መንፈሳዊ መስለው ከመንፈሳዊው መጽሐፍ ጋራ ሐሰቱን ሁሉ እያስጠጉ የጻፉት የውሸት ፖለቲክ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍት ቅድምና ታሪክ ለመንጠቅ የኢትዮጵያ መጻሕፍት በሙሉ ከጽርዕ የተገለበጡ ናቸው እያሉ የጻፉት ይህ ሥራ የማነው የመንፈሳውያን ሥራ ሊባል ይቻል ይሆንን። እኔ ዋናው አሳቤ የሮማ ልዑካን ስብከት በመንፈሳዊ መልክ የሚሠራው ሥጋዊ ነው እንጅ መንፈሳዊ ያይደለ መሆኑን ለወገኖች ለመግለጽ ነው የሮማ ልዑካን ስብከት ፍጹም መንፈሳዊ እየመሰለ ብዙዎችን ሰዎች ስቦ ስለማየው ነው። ስለ ፱ኛው ሐተታ ወአነኒ መጠነ ክሂሎትየ ኢያንተጉ ኢትካዝ ኢትጋሃ ወኢጻዕረ ከመ ሰብዓ ኢትዮጵያ ይረክቡ

ለዝንቱ ግብርየ ቃለ እግዚአብሔር አማናዊ በከመ ተመሐርዎ አበዊሆሙ እምአፉሁ ለቅዱስ ፍሬ ምናጦስ ይኸውና ፖለቲኩ እኔ እንደ ተቻለኝ መጨነቅን ጻዕርን አላጐደልሁም በዚህ ሥራዬ የኢትዮጵያ ሰዎች እንዲጠቀሙ ከቅዱስ ፍሬ ምናጦስ አፍ በውነት እንደተማራችሁት ይላል። ይህ ሁሉ ሥራ ከፍሬ ምናጦስ በፊት ትምርት አልነበራችሁም ለማለት ነው። ያው ከላይ እንደተጻፈው ነው። ስለ ፲ኛው ሐተታ መቅድመ

ኵሉ አእኩቶ ለጥቀ ክቡር አባ ገሪዞን ሊቀ ሰባክያን ዘኢትዮጵያ ይላል። ይህን የፖለቲክ ማካሄጅያ ጽሑፍ ያሳሰበውን አባ ገሪዞንን የኢትዮጵያ ሰባኪዎች አለቃ ይለዋል። እነዚህ ሰዎች የሮማ የጦር ፕሮፓጋንድ ለመሆናቸው ከአባ ያዕቆብ ገድለ ከተባለው መጽሐፍ መረጃአው ወደፊት ይገለጻል።

# ነ እጎድ

ቀርብ ለዓቢይ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፒዮስ ፲፩ በስም ዘፈቀደ ከመ ዝንቱ ግብር ይኩን ታሕተ ሥልጣኑ ይላል ይህውና ከላይ እንዳመለከትሁት የነሱ አሳብ መንፈሳውያን መስለው ውስጥ ለውስጥ በስብከት ሕዝቡን ከለያዩ በኋላ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን አጥፍተው የነሱን ቤተ ክርስቲያን ለማስፋፋት ዋና የሥራ ዓላማቸው መሆኑን ከሥር ዝምሬ ሳመለክት ከነሱ አሳብ ጽሑፍ ላይ የተገኘውን መረጃ እየገለጽኩ በማሳየት ነው እንጅ እንዲሁ ደርሸ የምናገር አይደለሁም የነሱ አሳብ እንደዚህ በጽሑፍ እየተገለጸ ይገኛል በኤርትራ ላይ ቆማ የምትገኝ ማኅበር ለሮማው ፖፖ የተወደደ ምሥጋና ታቀርባለች አሉ። ከሥልጣኑ በታች የፈቀደውን ያደርግ ዘንድ በኢትዮጵያ ላይ ሊሾም ሊሽር ማለቱ ነው። ከዚህም ዝቅ ብሎ ዝንቱ መጽሐፍ አኮ ዘሰብዕ አላ መጽሐፈ እግዚአብሔር ውእቱ ይላል። መቸም የሰው ማታለያ ለማሰናዳት ሰው ያውቅብናል ያለማለት ሲጽፉ ይህ መጽሐፍ የሰው አይደለም የእግዚአብሔር ነው እንጅ እያለ ማታለያውን ያሳያል ውሥጠ ነገሩ መንፈሳውያን ነን እንጅ ሥጋውያን አይደለንም ለማለት ነው። ለመሆኑ እነዚህ የሮማ ልዑካን የሚሠሩትን ሁሉ ሰው ያውቅብናል ማለት የለባቸውም ይሆንን የሰውን መጽሐፍ የክርስቶስ መጽሐፍ ማድረጋቸው ራሳቸው ሲመሰክሩ ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ነው እንጅ የሰው አይደለም ይላል። እንደዚህም ማለታቸው ሕሊናቸው ፩ድ ፩ድ ጊዜ ስለሚወቅሳቸው ነው ማለት ይህ ቤተ ክርስቲያን ሠራንበት ማኅበርም አቆምንበት የሚሉት በአሥመራ የሚገኘው መሬት በምን ምክንያት እንደተገኘ ያውቁታልና። ይህን ይህን መሬት በነሱ መሪነት የሮማ ወታደር ባላባቶችን እየገደለ የሰጣቸው መሆኑን ይህ ቤተ ክርስቲያንና ማኅበር የሚባለው የባላባቶች ደም በፈሰሰበት ላይ መሆኑን የሮማ ሰዎችስ መቸም የጥቁር ሰው ደም ከግግ ደም ያነሰ መስሎ እንደሚታያቸው የታወቀ ነው። የኢትዮጵያ ተወላጆች ይህን ነገር አለመገንዘባቸው የሚአስገርም ነው። በነዚህ ሰዎች መሪነት የፈሰሰውን የወንድሞቻቸውን ደም በሚሊዮን የሚቆጠረውን አለማሰባቸው እንደምን ይሆን።

ደግሞ ባሳተሙት ሐዲስ ኪዳን መቅድም በ፫ኛ ገጽ ባሕቱ ያኃዝነነ ለነ አፎ ነሥአ ዘንተ ጽዕለተ አምዙኃን ናዝሬውያን። እንዳኢ ለእመ በፈቂድ ወሚመ ዘእንበለ ፈቃድ መጻሕፍተ ኢትዮጵያ ዘካልዓን ይሁብ አዕልዎቶን ለሐዋርያ ዘብሔረ አግዓዚ ቅ ፍሬ ምናጦስ የኢትዮጵያ መጻሕፍት በሙሉ የመለሰ አባ ፍሬ ምናጦስ ነው ይላል በአሪቱ እንደጻፈው በዚህም በሐዲሱ ይህኑ ለማስጠናት በመቅድሙ ላይ ማነኛውንም ነገር ጽፈውት ይገኛል እንደዚህ እያደረጉ በማነኛውም ጽሑፍ ላይ ስብከታቸውን ይዘረዝራሉ እኛ ግን የነሱን ስብከት ፍሬ እየለቀምን ያነን እየቀመስን ምቀኝነት በሚባለው ጐዳና ስንጓዝ እንታያለን ይህም ጐዳና ወዴት እንደሚያደርሰን ማሰብ የለብንም ከዚህ ቀደም በ፫ት ስብከቶች ምክንያት ኢትዮጵያን ከፍ ያለ ጉዳት እንዳገኛት ታሪክ ይነግረናል። ፩ኛው ከላይ እንደ ተጻፈው ጉዲት በምትባል አይሁዳዊት። ፪ኛው ሙሐመድ ግራኝ በሚባል እስላም ፫ኛ ኢጣልያ እነዚህን ሁሉ ውስጥ ለውስጥ የሚስማሙበት አለ። የጠላቱን ነገር መመዘን ማስተዋል የተገባ መሆኑን ማስተዋል

# ኑ ሰኑይ

የተገባ ነው። ይህ ማስተዋልና ጥንቃቄ እኛ ችላ ብለነው ሳለ ማን ይሥራው። በመዠመሪያ እስላሞች በኢትዮጵያ ምንጊዜ ገቡ በኢትዮጵያ ወደቦች የንግድ ዕቃዎችን የሚቀበሉና የሚወስዱ ዓረቦች በወደቦች

የሚገኙትን ኢትዮጵያውያን ስለሰበኳቸው ቀስ አያሉ የሀብት ምንጮች የሆኑትን ወጣቶች ሁሉ ጣማቸውና ፍሬ ነገራቸው ከውጭ ሰዎች ጋራ የዕለት ጥቅም በመለዋወጥ የሰዎቹ ልብ ወደ ውጭ ስና ጠላትና ጠላት እየተስማማ ኢትዮጵያን ሲያመነምናት ጥንት ሲያያዝ የመጣውን ጐዳና መንግሥት ለመቃወም ሲአቅዱ ይታያሉ። የባሕር ግዛቷ ሀብት ከምድር ግዛቷ ሀብት ያነሰ አልነበረም ይህም የባሕር ግዛት ሀብት የሚገኘው በዙሪያዋ የሚገኙትን ወደቦቿን በመያዝ ነበር። በባሕር ውስጥ የሚገኙ የኢትዮጵያ ደሴቶቿ ብዙዎች ነበሩ ከነሱ ላይ የሚገኘው ጥቅም ከፍ ያለ ነበር። ሌላው ይቆይና የዕንቁ አዝመራ የሚለቀምባት ጨው እንዳፈር የሚዛቅበት ደግሞም ብዙ ልዩ ልዩ ጥቅሞች ይገኛሉ። እነዚሁ ሁሉ ጥቅማቸው በባዕድ እጅ ሆነው ኖሩ። የዚህ ሁሉ ጉዳት ቀላል ነውን አሁንም ቢሆን እኔው ራሴ ምጽዋ ወርጄ ማንኛውንም ነገር ስንመለከት ይህን የዕንቁ ነገር ጥቅሙን የሚወስዱት የውጭ ሰዎች ናቸው ማለት ይህን ዕንቁ እየፈለጉ የሚያገኙ ሰዎች ሁሉ አስቀድሞ ገንዘብ ከውጭ አገር ሰዎች እየተቀበሉ ስለሆነ ያነን አስቀድሞ በብድር ስም ያገኙትን ገንዘብ ውለታ በማድረግ በቀላል ገንዘብ ይሸጡላቸዋል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ጥቅም ለባዕድ ከማለፍ አያቋርጥም ኢትዮጵያ እነዚህ የባሕር ጥቅሞች ለውጭ ሰው ማዳበሪያ ለመሆን የደረሰው በእስላሞች ስብከት ነው ኢጣልያኖችም ማግቢያ ያገኙ የኢትዮጵያ መንግሥት የሮማ ልውካንን ባባረሯቸው ጊዜ እስላሞች ጥግ እየሆኑ ብዙም እርዳታ እንዳደረጉላቸው ታሪክ ይነግረናል። ይህ ሁሉ የደረሰው ከላይ ከመሠረቱ ሲያያዝ የመጣውን ያባቶቻችንን ቋንቋና ፊደል ትተን የባዕድ ፊደልና ቋንቋ ተምረን የሌላን ሰንደቅ ዓላማ የማክበርን ትምርት እየተቀበልን የጥንት መንግሥታችንን ለማጥፋት ስንጣጣር እንታያለን የሀገራችንን መሠረት የሚናገረው ጽሑፍ በድንጋይ ላይ የተጻፈው ይገኛል ምስክሮች መሬት በውስጧ ይዛ የሚመጣውን ትጠብቃለች።

የጠላት አእምሮ በረቂቅ ተንኮሉ ተመልክቶ የሀገር ዓይን ቋንቋ ስለ ሆነ መሠረቷ ቋንቋችን እንዲጠፋ በማድረግ የሞከሩትን ከላይ እንደ ተመልከተው የኢጣልያ ፖለቲክ ዋና መሳሪያ ፩ኛ የኢትዮጵያን ቋንቋ መሠረት ግዕዝን ለማጥፋት ነው። ግዕዝን እንዲጠፋ የሚአስቡበት የኢትዮጵያ ታሪክ ተጽፎ የሚገኝበት ስለሆነ ነው። ፪ኛ የኢትዮጵያ ሃይማኖት እየተቀነሰ እንዲሄድ ዋና ሥራቸው መሆኑ የኢትዮጵያ ኃይል እየተከፋፈለ እንዲቀነስ በማለት ፖለቲኩን ሃይማኖት አደረጉት። የኢትዮጵያ መሠረት የሚጠፋበት ስብከት እየተጻፈ በየቦታው ዘሩትና ይህን ጽሑፍ ያነበቡ ሰዎች ፈረንጆችም ሆነ ሀበሾች ሀበሻ ስል የዓረቦችን ቋንቋ በመውረስ አይደለም ሀበሻ ማለት የመጣ ሀበሲ የሚባል የኩሳ ልጅ ስለነበረ በሱ መሠረት ስም የሚጠሩ ሰዎች ዘሮች የወረደውን ነው። የካም ዘሮች ልዩዎች ጀግኖች እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል። ብዙውን የዕሥያን አገር አጥቅተው ይዘው ኖረዋል የካም ዘሮች ስንኳንስ አገራቸውን ለማስወገድ ይቅርና አልፈው በውጭ

# ኒ ሠሉስ

ለሌላ የሚረዱ ሰዎች ናቸው ይህንም ታሪክ ይነገረናል። በጣም ከፍ አድርጌ የምናገረው አሁን ይህ ዛሬ ያለው መንግሥት ይህ ነው መንግሥት መሠረቱ ሲመረመር ከአዳም የወረደ ነው። ይህም ከአዳም ዠምሮ እስከ ኖኅ ፲ኛ ትውልድ ሳይከፋፈል ባ፩ድ ኃረግ ወረደና በኖኅ ልጆች በሴም በካም በያፌት ለ፫ ተከፈለች። ደግሞ ከካም ላይ ለ፫ት ተከፈለች ፩ኛ ለኩሳ ፪ኛ ለሚሥራይ ፫ኛ ለሌብያ ፊደሏን ቋንቋዋን እንደያዘች እስከዛሬ የኖረች ይህች የኢትዮጵያ መንግሥት አመሠራረትዋና አመጣጥዋ እንደዚህ በቀጥታ ስለሆነ በቅዱሳት መጻሕፍትም ታውቃ በሰፊው ታርከዋ

ተጽፎ ይገኛል። አሁን ይህን በቀጥታ መጥታ እዚህ የደረሰችበትን መንግሥት አውቆ ማክበር የሚቻልበት ዘዴ ከውጭ የመጣውን ስብከት ማስተዋል በምን

ምክንያት እንደመጣ አስቦ ነገሩን መረዳት ነው። በተረፈ የጠላትን ስብከት እየተቀበሉ ከጠላት ጋራ እየተዋዋሉ አገሬን እወዳለሁ ማለት ከንቱ ነገር ነው። የዚህ ምሳሌ ምን እንስጠው በውቅያኖስ ባሕር ላይ እህል ዘርቼ አበቅላለሁ ማለት ይሻላል። በውጭ ጠላት የስብከት ጦር የተመረዙ ሰዎች ከበመርከቱ የሚታገዱበት ዘዴ ከማሰብ በቀር እውነት ያጠኑትን ነገር ትተው ባላጠኑት ነገር ያገለግላሉ ማለት የውቅያኖስ ባሕር ጨው መሆኑን ተወ ማለት ነው። ስለዚህ አስፈላጊው መሠረት ትምህርትን ሳይለቁ ግዕዝን አጥብቆ መያዝና ወደ መሠረቱ እየገቡ በጥንት አገሮች ሁሉ በየድንጋዩ ላይ ተጽፈው የሚገኙትን ሐውልቶችና ማነኛውንም ጽሑፎች የተመረመሩ እንደሆነ በቀድሞ ዘመን የነበሩትን ጽሑፎች ቅርጾት ለማንበብ ይችላል። ማንበቡን ሲችል የማዕድን ጉድጋዶችንና የጅ ሥራ ሳይንስ ጥበብ ሁሉ ያገኛል በዚህም ጥበብ የሀገር ሕዝብ ይጠቀምበታል የሮማ ሰባኪዎች የኢትዮጵያ ታሪክ የማይጠናበትን ዘዴ እየፈጠሩ ለሚጽፉለት ፖለቲክ እውነተኛነት ያለው መስሎ እንዲከበርና ሰው እንዲቀበለው በማለት የፖለቲክን ማከናወኛ ቤት አዲስ እውነተኛ አዲስ ቤተ ክርስቲያን ከፈቱ ስለዚህ ከኢትዮጵያ ላይ ሁለት ቤተ ክርስቲያኖች ቆሙ። በዚህ ጊዜ አስተዋይ ተመልካች ስማቸውን ለመጥራት በፈለገ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሮጌ ልትባል ግድ ነው። የሮማ ልዑካን ያቆምዋት አዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን መባል የግድ ሆኖ ይታያል በዚይ አያያዝ እንግዲህ ያሮጊይቱ ቤተ ክርስቲያን የመጻሕፍቶቼዋ መሠረት እየኮሰሰ ሲሄድ ያሮጊይቱ ቤተ ክርስቲያን መንግሥት ከመኮሰስ እንደምን ለመዳን ይቻላል መነኛውም ሰው ሁሉ አዲስ ነገር ይወዳል ስለዚህ ያዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በማነኛውም ረገድ ለፖለቲክ ማስፋፍያ በቆመው ማኅበር ረዳትነት ለጊዜው የተጠቀሙ መስለው ስለታዩ ያሮጊዩቱ ቤተ ክር ሰዎች እየደኸዩ እያነሱ ያዲሲቱ ቤተ ክር ሰዎች እየበለጸጉና እየበረቱ አሮጌውንም መንግሥት ማጥፋት እንደሚያሰጋው አይጠረጠርም ስለ ፩ቱ ቤተ ክርስቲያን ያሮጌው መንግሥት አማካሪዎች ሊመክሩበት አስፈላጊ መሆኑን ላስታውስ በትሕትና ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክር መሠረት ጥልቀትና የከፍታው ቁመት ከላይ በጽሑፌ አስረድቻለሁ የሮማንና የኢትዮጵያን አስተያየት በኢትዮጵያ ንግሥት ሹምና በኢጣልያ በቆርኔሌዎስ

# ና ረቡዕ

ተፈጽሞ ይገኛል። ከወደላይ የፖለቲኩን ማከናወኛ ቤተ ክር ብለው ሠይመው የቤተ ክርስቲያን ሥራ ዓይነት ሢሰሩበት እንደሚታይ ስለ ጻፍኩ የሮማ ልዑካን የሮማው መንግሥት የጦር ፖሮፓጋንድ ባልደረቦች መሆናቸውን ወደፊት በሰፊው ይገለጻል ምናልባት እስከ መጨረሻው ድረስ ለማያነቡ ሰዎች ማስረጃ የሌለው እንዳይመስላቸው አሳስባለሁ።

ስለ ሁለቱ ቤተ ክርስቲያን ያ፩ድ ክርስቶስ ሲሆኑ መለያየታቸው ስለምን ይሆን ምሳሌ ባ፩ዲት እርሻ ላይ ሁለት ጊዜ ሁለት ዓይነት ዘር የተዘራባት እንደሆነ እንደምን ይሆናል ሁለቱ ቡቃያዎች እኩል ያደጉ እንደሆነ እንደምን ይሆናል። መከርም በደረሰ ጊዜ ገበሬው እንደምን ይሆናል ጥቅም ሳይሰጥ መቅረቱ የሚጠረጥር አይደለም ይህንም ምሳሌ በማቴዎስ ፲፫ ፳፬ ካልዕተ ምሳሌ አምጽአ ሎሙ እንዘ ይብል ትመስል መንግሥተ ሰማያት ብእሴ ዘዘርዓ ሠናየ ዘርዓ ውስተ ገራኅቱ ፳፭ ወእንዘ ይነውም ሰብዑ መጽአ ጸላኢሁ ወዘርኒ ክርዳደ ማዕከለ ሥርናይ ወኃለፈ። ይላል እዚህ ላይ እንደሚአመለክተው መንግሥተ ሰማያት ያላት ትርጋሜዋ ሀገር ስትሆን መልካም ዘር በርሻው ላይ የዘራን ይመስላል መልካም ዘር ማለት ሲያያዝ የመጣውን ሀገሩን ካባቶች የመጣውን ሃይማኖት የያዘውን ነው። ክርዳድ የተባለው በሰው አገር ሄዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ቤተ ክርስቲያን ሐሰት እሰራለሁ ብሎ ጠብና ክርክር የሚያደርግ ሰው ምናልባት እንዲህ

ያለ ሰው በ፴ቁ የተጻፈው እንዲደርስበት ይረዳ በቅዱስ ወንጌል ውስጥ ብዙዎች ምሳሌ ተጽፈውልን ነበር አልተመለከትናቸውም ዮሐንስ ፲ ፩ አማን አማን እብለክሙ ዘኢቦአ እንተ አንቀጽ ውስጥ

ዓፀደ አባግዕ ወዓርገ እንተ ካልእ ገጽ ሠራቂ ውእቱ ወጉልሀያ ወደበጎች ፊት ለፊት ባለው በር ያልገባ በሌላ ከወደ ኋላ የወጣ ሌባና ሽፍታ ነው እያልኩ እውነት እላችኋለሁ ወዘሰ እንተ አንቀጸ ይበውእ ኖላዊ ውእቱ በዋናው በር የሚገባ ግን የበጎቹ እረኛ ነው። ፫ ወሎቱኒ ዓፃዊኒ ያርኅዎ ወአባግዕኒ ይስምዓሁ ቃሎ ወይጼውኦን ለአግባዒሁ በበሰአማቲሆን ወያወፍሮን ለሱስ በረኛውም ይከፍትለታል። በጎቹም ቃሉን ድምፁን ያውቁታል እሱም በጎቹን በስም በስማቸው እየጠራ ያሰማራቸዋል ፬ ወሶበ አውፈሮን ለኩሎን የሐውር ቅድሜሆን ወይተልዋሁ አባግዒሁ እስመ የአምራ ቃሎ እነሱንም ካሰማራ በኋላ እሱ በፊት በፊታቸው ይሄዳል በጎቹም ይከተሉታል ቃሉንም ያውቃሉና ፭ ወለነኪርሰ ኢይተልዋሁ እስመ ይጐይያ እምኔሁ እስመ ኢየአምራ ቃሎ ለነኪር ባዕዱንስ አይከተሉትም ይሸሹታል እንጅ የባዕዱን ቃል ቋንቋ አያውቅምና እንደዚህ እያደረገ ሲመሰክረን እኛ ግን እንመለከተውም ልብ ያለው ይመልከት ያዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ካሮጌይቱ ቤተ ክር ለመወዳደር በጣም ስለሚፈልጉ እላይ ወጥተው የ፱ቱ ቅዱሳን ልጆች ነን ለማለት ባሰቡ ጊዜ እንሱ ወደ ኢትዮጵያ የቅናት ወጥመዳቸውን መሰናዳት የዠመሩ በሽ፳፻፶፩ ዓ.ም ዠምሮ ስለሆነ ፱ቱ ቅዱሳን የነበሩበት ዘመንና ንጉሥ ካ፬፻፸፫ ዘመን በላይ ባጼ ከ፹፩ ይሆናል። እነዚህ ራቅ ብለውባቸው ስለተቸገሩ እነዚህን ፩ሽ ከ፹፩ ይሆናሉ። እነዚህ ራቅ ብለውባቸው ስለተቸገሩ እነዚህን ፩ሽ ከ፹፩ ዘመኖች ለማሳጠርና ለማቀራረብ ሲሉ በረቂቅ ጥበባቸው ማለት የግእዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት የሚሰብኩ መስለው በመታየታቸው

# ኔ ኃሙስ

ነው ወደ ላይም ከከሣቴ ብርሃን ሰላማ ለማወዳደር አብርሃምና አጽብሃን ሠርዘው ፍሬ ምናጦስን የነበረ በዔዛና ዘመነ መንግሥት ነው እያሉ የጻፉት የውሸት ጽሑፍ ዓለምን አዳርሶታል። ዔዘና ያሉት የዓልአሜዳ ልጅ ነው። አባ ፍሬ ምናጦስ የነበረው በአብርሃና በአጽብሐ ዘመን ምን ባ፫፻፴፬ ዓ.ም ላይ ነው። ፱ቱ ቅዱሳን የመጡ በአልሜዳ ዘመነ መንግሥት ባ፬፻፸ ዓ.ም ላይ ነው። ዔዘና ያጼ ካሌብ አባት በ፬፻፹፫ ዓ.ም በላይ ነው። ይህን ሁሉ አመሳቅለው የኢትዮጵያን ታሪክ ጻፍን እያሉ የሀገሩን ስለዘሩት ይህን ጽሑፍ እውነት እየመሰላቸው ስንኳንስ የውጭ አገር ሰዎችና የኢትዮጵያ ልጆችም ከፈረጅ ቋንቋ እየገለበጡ በኢትዮጵያ ላይ እያሳተሙ አበርክተውት ይገኛል ያዲሲቱ ቤተ ክር ሰዎች ማኅተሙና ወርቀቱ ከቀረበ ብለው ብዙ ነገር ለማፋለስ የሚመች ጽሑፍ በኢትዮጵያ ላይ ዘርተዋል ከላይ ፱ቱ ቅዱሳን ልጆች ነን ይላሉ ፪ኛ የአባ ሊባኖስ ልጆች ነን ይላሉ ፫ኛ አባ ያዕቆብ የሚባለው የኛ ነው እያሉ የጻፉት ይገኛል ይህ ሁሉ ሐሰት ይገለጥብናል ብለው ትንሽም አሳብ የላቸውም ፩ድ ጥያቄ ቢደረግ ምን ይመስላል ይሆን ከመጡበት ዘመን አልፈው ወደ ስር ገብተው ይህን ያህል ሲዘባርቁ ድንገት ነገሩ የተመረመረ እንደሆነ ሥራችን ሁሉ ይራከስብናል አይሉም ይሆንን። አሁን እኔ የማስታውሰው እነሱ ከሀገራቸው ድረስ ተቀጥረው የመጡበትን ሥራ ጠንክረውና በርትተው ይህን ያህል አገር ቆርጠው መጥተው ለሀገራቸውና ለመንግሥታቸው በጥብቅ ሲሠሩ የምናይ ሰዎች ለኛም ሀገር መንግሥት የሚስፋፋበትን ዘዴ በየቀኑ ከነዚያ ላይ ስንማር እየዋልን እኛም አገራችን የወረረ ጊዜ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ስንት ናቸው ይሆን የተቃጠሉ ደግሞ አዲስ የተሠሩ የሮማውያን ቤተ ክርስቲያን ስንት ነበሩ በነዚህስ ውስጥ መሥዋዕተ እግዚአብሔር ታውቆባቸዋል ይባል ይሆንን ነገሩ እውነት ነው ብለን ልንቀበለው ይገባናል ይሆንን እንደዚህ ያለውንማ መሥዋዕት ልዑል እግዚአብሔር የሚቀበለው ከሆነ ነቢዩ ኢሳይያስ ፩ ፲፩ ለምንት ሊተ ብዝኃ መሥዋዕቲክሙ ይቤ እግዚአብሔር ጽጉብ አነ እመሥዋዕተ ሐራጊት ወስብሐቲሙ ይቤ ኢይፈቅድ ድመ ላህም ወጠሊ። ፲፪ ወእመኒ አምጻእክሙ ኢታስተርእዩኒ መኑ ኃሰሰ ለዝንቱ እምእዴክሙ ወትድግሙ እንከ ከይዶዓፀድየ። ፲፫ እመኒ አምጻእክሙ ስንዳሌ ከንቱ ወዕጣንክሙኒ ርኩስ አሥእርክሙኒ ወሰንበታቲክሙኒ ወዕለተክሙኒ ዓባየ

ኢይፈቅድ ጸመክሙኒ ወጽርዓተክሙኒ ፲፬ ወሠርቀ ወርኅክሙኒ ወበዓላቲክሙኒ ነፍስየ ስቆራረ ኮነክሙኒ ወጠለቅሙ ወኢይሠሪ ለክሙ ኃጢአተሙ ፲፭ ወሶበሂ ታነሥኡ እደዊክሙ ኅቤየ እይመጥ ዓዕይንትየ እምኔክሙ ወእመኒ አብዝህክሙ ምህልላክሙ ኢይሰምዓክሙ እስመ ደመ ምሉዕ እደዊክሙ። እግዚአብሔር በከፈላቸው አገር የሚኖሩትን ክርስቲያኖች በግፍ እየፈጁ ለእግዚአብሔር ምሥዋዕት እናቀርባለን ማለት ሰውን ማታለያ ነው እንጅ እውነተኛ ሥራ አይደለም የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስቲያን ደግነታቸውንና ፈጣሪአቸውን ወዳድ መሆናቸውን በዓለም የሚገኙ ባለታሪኮች ጽፈውት ይገኛል ቅዱስ መጽሐፍም ውስጥ ሞልቷል። ይልቁንም አስደናቂው ቃል አሞጽ ፱ ፯ አኮኑ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኅቤየ ደቂቀ ፳ኤል ብሎ የተናገራቸው ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ በነብዩ አድሮ የተናገረውን

## ን ዓርብ

ማስተዋል የተገባ ነው። የኢየሩሳሌምን ሰዎች በኔ ዘንድ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች ናችሁ ማለቱ ምን ይሆን። እንደዚህ በመንፈስ እግዚአብሔር ትንቢት ተናገረላቸውን ሕዝቦች እየፈጁ ቤተ ክርስቲያያን አሠራና መሥዋዕተ እግዚአብሔር አቀርባለሁ ማለት ከንቱ መሆኑን ለወገኖች አስጠነቅቃለሁ። መጻሕፍቱ መጻፋቸው ለከንቱ አልነበረም ልንመክርባቸው እንጅ ሚክያስ ፮ ፱ ቃለ እግዚአብሔር ትሥሚ በሀገርከ

ከመ ያድኅኖሙ ለእለ ስሞ ስማዕ ሕዝብየ መኑ ያስተሬሲ ሀገረ ቃለ እግዚአብሔር ትስሚ በሀገርከ ያለው ቤተ ክርስ በሀገርህ ላይ የመስራትህ ያድናቸው ዘንድ ስሙን ሲፈሩና ሲያከብሩ ነው ያለው ሰውን አክብሩ ሲል ነው። እሳትኑ ወቤተ ዓማጽያን እለ ይዘግቡ መዛግብተ ዓመጻ ወይገፍኡ ወየኃሥሩ። የቅሚያ ገንዘብ የሚሰበስቡ የሚጋፉ ይጐሰቁላሉ ፯ ፪ ወያነሥዑ እደዊሆሙ ለእለ በእኩይ ወአጠፍኦ ለበረከቶሙ እጃቸውን ለክፋት ሰውን ለመግደል በሚነሱ ሰዎች ሀገር ንጉሥ ይለምናል መስፍኑም እንደ የዋህ ይቆጠራል ለሕይወቱ የሚያስፈልገውንም አያገኝም ከሀገሩ ላይም በረከት ርቆታልና ይህም በኢጣልያው ንጉሥና በሞሶሎኒ እንደተፈጸመ መረዳት ያስፈልጋል።

አሞጽ ፰ ፬ ስምዑ ዘንተ እለ ታግዕሩ ነዳየ በጽባሕ ወትትዔገሉ ምስኪን በዲበ ምድር ፮ ወንቅንዮ ለነዳይ በዕዳነ ወይኩነነ ምስኪነ ዘንከይድ ህየንተ አሣእን ወንትራባህ በተግባራተ እክልነ። ይህን የመሰለውን የግፍ ጓዝ በረቂቅ ፖለቲክ ሠውረው የኢትዮጵያን ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት ለመደምሰስ የመጡትን ሰዎች ሥራ ስለምን አንመለከተውም። እነሱ እንኳ የሰው ነገር እያታለሉ እንዲሰብኩ ለቅሚያ የላኳቸው ሰዎች የሚታለል ሐሳዊ ሥራቸው በተገለጠባቸው ጊዜ የኢትዮጵያ ነገሥት ካገር ውጡ ብለዋቸው በበረኃ ሲሄዱ የሞቱትን ሰዎች ልክ ባረመኔ ሕዝብ እጅ እንደ ተሰየፈው እንደ ጳውሎስ አድርገው እንደሚአከብሯቸው ማንም ያውቃል። የዓድዋና የማይጨው የውጋዴን ጦርነት ለመነሣት የበቃበት ሥሩና መሠረቱ ወዴት ነው ብሎ ለሚጠይቅ እኔ ተከታትየ በመረመርኩት አኳኋን የሮማ ልዑካን የተባሉ የሮማ መንግሥት የጦር ፖሮፓጋንድ ባልደረቦች የሆኑ የቤተ ክርስቲያን ስም ሰጥተው በውሥጡ የጦር ፖለቲክ ሥራ የሚአስሄዱበት ቤት ነው እልዋለሁ። ይህንም ቃሌን የሚቃወም ሰው የተገኘ እንደሆነ ከላይ ስለ ሮማ ልዑካን የተጻፈውን ደብዳቤ ሁሉ ይመልከት የነአንቶኖሊ ደብዳቤዎች አሉ። የሮማው መ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የጻፉቸውን ደብዳቤዎች ይመልከት በተረፈ ክፉን መልካም መልካሙን ክፉ የሚያስመስሉ አታላዮች የተጻፈውን ለማየት ኢሳይያስ ፭ ፳ አሌ ሎሙ ይብልዎ ለእኩይ ሠናየ ወለሠናይ እኩየ እለ ይብልዎ ለብርሃን ጽልመተ ወለጽልመት ብርሃነ። እለ ይብልዎ ለጥዑም መሪረ ወለመሪር ጥዑመ ፳፩ አሌ ሎሙ እለ ይጠበቡ ለእከይ ወይብሉ ንሕነ ከመ ጠቢያን ይላል እንደዚህ አድርጎ በነቢዩ አድሮ የተነገረው ትንቢት በኢየሩሳሌም ሰዎች ብቻ የሚወሰን አለመሆኑን አስረዳለሁ ያዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የጾምን ነገር ሠርዘውታል ስለዚህ እውነት እየመሰላቸው በነሱ እየተጠመቁ ወደነሱ እየዞሩ የሚሄዱ ሰዎች በጣም አይሳዝኑኛል ፪ ባሕርይ ማለትን ብቻ ስለሚሰብኩላቸው ነው የኢትዮጵያ ሃይማኖት ቀናዒቱ የታወቀችቱ የኢትዮጵያ ቅዱሳን ጌታችን ለሐዋርያት የሰጠውን ሥልጣን

# ኖ ቀዳም

ማርቆስ ፲፮ ፲፫ ፲፯ በስመ ዚአየ አጋንንተ ያውጽኡ ፲፰ ወአራዊተ ይእኅዙ ወዘሂ ይቀትል ለእመ ሰትዩ አልቦ ዘይነክዮሙ ወዲበ ድውያን እደዊሆሙ የነብሩ ወይሜጥኑ እንደዚህ በተቀበሉት ሥልጣን አጋንንትን እያራቁ ድውያንን እየፈወሱ በጾምና በጸሎት እስከ ዛሬ ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ላይ ብዙ ልዩ ልዩ ሥራዎች ታምራቶች በየገዳማቱ ይገኛሉ እነሱ የጸለዩበት ቦታ እስከ ዛሬ አጋንንትን እንዳራቀ አለ ዛሬ ይታያል የኢትዮጵያ ቅዱሳን እንደዚህ ያለ መንፈሳዊ ኃይል የሚአገኙበት ምክንያት ልብሳቸው የለፋ ቁርበት አጽፍ የሚባል ነው ሥጋቸውን ማደላደል የለባቸውም ጥፍርቸውን አይቆርጡም ጸጉራቸውንም አይላጩም ባንገታቸውና በወገባቸው ሰንሠለት ያደርጋሉ ቅዝቃዜው ሰውነታቸውን እንዲጐዳው በማለት ይህን ሁሉ ሥቃይ ለፈጣሪአቸው ፍቅር አሰናካይ ከሚሆን ሰይጣን እንዲያድናቸው ነው የዚህንም ሁሉ ሥራ መሠረት ይዘው ነው እንጅ በከንቱ አይደለም ፩ኛ ስለ ለፋ ቁርበት አጽፍ ልብስ አዳምም አባታችን ከገነት በወጣ

ጊዜ ፈጣሪውን ሲለምን ልብሱ አጽፍ እንደነበረ ኦሪት ዘፍጥረት ፫ ፳፩ ወገብረ እግዚአብሔር ለአዳም ወብዕሲቱ አዕዳለ ማዕስ ወአልበሙ ያለውን ተመልከትው ነው። ጥፍራቸውንና ጠሩራቸውን አለመቁረጣቸው መልከ ጼዴቅን መሠረት በማድረግ ነው የመልከ ጼደቅን ታሪክ ለመረዳት መጽሐፈ ቀሌሞንጦስ ይመልከት መልከ ጼዴቅን የካም ዘር የአዳምን አጽም እንዲጠብቅ ሲታዘዝ መላኩ ጥፍሩን ጠጉሩን እንዳይቆረጥ ዓጽፍ እንዲለብስ ከስንዴና ከወይን መሥዋዕት እንዳያቀርብ ሕግ ሰጥቶ ስለነበር ይህን መሠረት በማድረግ ነው ሠንሠለትም ባንገት ማድረግ መሠረት ኤርምያስ ባንገቱ ሰንሰለት እንደነበረ ኤርምያስ ፳፰ ፲ ወነሥአ ሐናንያ ነቢይ (ነቢየ ሐሰት ነው) ጋጋ በቅድመ ኵሉ ሕዝብ እምክሣዱ ለኤርምያስ ወቀጥቀጦ ሐናንያ የሚባለው ነቢየ ሐሰት ናቡከ ደነ ፆርን ድል እናደርጋለን እያለ ሲሰብክ ኤርምያስ ደግሞ ናቡከደነ ፆር ድል ያደርገናልና ልዑል እግዚአብሔርን እንማጸን ብሎ ቢአመልከታቸው ሐናንያ የሚባለው ነቢየ ሐሰት ኤርምያስን ባንገቱ ባለው ሰንሰለት እንደሚጠቀመው ስለሚያውቁ ነው። ሳሙኤልም ልብሱ ዓጽፍ እንደነበረ ነገሥት ፳፰ ወይቤላ ምንተ ርኢኪ ወትቤሎ ብእሴ ዘርቱዓ የዓረግ እምነ ምድር ወይለብስ ዓጽፈ ወአእመረ ከመ ሳሙኤል ውእቱ ወደነነ ወሰገደ ሎቱ በገጹ ዲበ ምድር ሳኦል እንዳራዊት ሳሙኤልን እንድትጠይቅለት ባደረገ ጊዜ ሳኦል እንዳራዊትን ማንን የአሺ እያለ ቢጠየቃት ዓጽፍ የለበሰ ሰው ወደላይ ሲወጣ አየሁ ባለችው ጊዜ ሳኦል የሰገደ አጽፍ የለበሰ ብትለው በልብሱ ስለአወቀው ነው። የኢትዮጵያ ቅዱሳንም ዓጽፍ የሚለብሱ ይህ ይህን መሠረት በመያዝ ነው። በውነት ልዑል እግዚአብሔርን የሚወዱ ሰዎች አጋንንትን ድል የሚአደርጉት የሚአርቁበት ዋናው መሣሪያ ሥጋቸውን በመከራ መቅጣት እንደሆነ ሮማውያን በሰይፍ የገደሉት ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈውን እንመልከት ቆሮንቶስ ፲፪ ፯ ወበእንተዝ ከመሰ ኢይትዓበይ በብዙኅ ራዕይ ተውህበኒ መልአከ ሰይጣን ዘይደጉጸኒ ሥጋየ ወይኰርዓኒ ሰይጣን በሕልሙ እየመጣ እንደተፈታተነው ፰ ወአስተብቋዕክዎ ለእግዚአብሔር ሥልስ በእንቲአሁ ከመ እያትት እምኔየ። ስለዚህ ጌታየን ፈጣሪየን ፫ ጊዜ ማለድኩት እሱን እንዲያስወግድልን ፱ ወይቤለኒ የአክለከ ጸጋየ ወኃይልስ በደዌ

# አ እኁድ

የኃልቅ ወሠመርኩ እትመካህ በሕማምየ ከመ ይኀድር ኃይለ ክርስቶስ ላዕሌየ ስጦታየ ይበቃኻል አለኝ ኃይልም በደዌ ያልቃል በላዬ ላይ የክርስቶስ ኃይል መንፈስ ቅዱስ ያድርብኝ ዘንድ በመከራዬ እመካ ዘንድ ወደድኩ። ፲ ወበእንተ ዝንቱ ሠመርኩ በሕማምየ በተጽእሎሂ ወበምንዳቤሂ ወበተሰዶሂ ወበተጽናስሂ በእንተ ክርስቶስ እስመ ሶበ አሐምም ሶቤሃ እጸንዕ። ስለዚህ መጨነቅን ወደድኩ የጭንቅ ረዳቶች መሰደብ መናቅ ማጣት ስደት ችግር እነዚህን ስችል በዚያ

ጊዜ እበረታለሁ ማለቱ ጠላቱን የሚአሸንፍለት መንፈስ ቅዱስ እንዳደረበት ሲናገር ነው። የኢትዮጵያ ቅዱሳን ይህን ሁሉ መሠረት በማወቅ ጌታችንም በወንጌል ማቴዎስ ፭ ፫ ብጹዓንን ነዳያን በመንፈስ እስመ ሎሙ ይዕቲ መንግሥተ ሰማያት ፮ ብጹዓን እለ ይርኅቡ በእንተ ጽድቅ ፱ ብጹዓን ገባርያነ ሰላም እስመ እሙንቱ ውሉደ እግዚአብሔር ይሰመዩ የኢትዮጵያ ቅዱሳን ይህን ሁሉ እየፈጸሙ ይገኛል የኢትዮጵያ ቀኙን ብርሃኑን ምንገድ ይዘው ሲጓዙ ያዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ለግራው የቀኝን ስም ለጨለማው የብርሃን ስም ሰጥተው በሰላም የሚኖሩትን የኢትዮጵያ ሕዝቦች እያፋጁ የሚኖሩበትን ቤተ ክርስቲያን እያሉ ያቋቋሚቸው ቤቶች በርክተዋል ይሄም ነገር አስቀድሞ ያው ሮማውያን ከአምልኮ ጣዖት ስለምን ውጡ ትለናለህ ብለው በሰይፍ የገደሉት ጳውሎስ ትንቢቱን እንደተናገረው ቆሮንቶስ ፲፩ ፲፫ እስመ ሀለው ኃሳውያን ገበርተ ዓመፃ እለ ይትሜየኑ ወይትሜሰሉ ሐዋርያተ ክርስቶስ ይኸውና አሳምሮ እንደተናገረው የክርስቶስን ሐዋርያት መስለው መስቀልና መጽሐፍ

ይዘው የቅሚያ ሥራ የሚሠሩ ሐሰተኞች ይመጣሉ ብሎ የጻፈው ትንቢት መፈጸም ከዠመረ ፳፻፲ ዘመን ነው። ይህን ያህል ዘመን ስለቆየ ነገሩ እየታወቀ ካገር እንዲወጡ እየታወጀባቸው ከወጡ በኋላ እንደገና እየተመለሱ እየገቡ ነው። ፲፬ ወዝኒ አኮ ለአንክሮ እስመ ለሊሁ ሰይጣን ይትሜሰል ከመ መልአከ ብርሃን ይህም እንደዚያው ውሥጠ ሥራቸው ሰውን ማጋደል ፩ዱንና ፩ዱን ማጋደል ማጣላት ማፋጀት ነው። ይህ ሥራ የማን ሥራ ነው። ለማለት ይቻላል ይሆን። በልብስና በመልክ ለማሳሳት የሚመጡትን እንድናውቅ አስቀድሞ ጌታችን እንዳስጠነቀቀን ማቴዎስ ፯ ፲፭ ተዓቀቡ አምኃሣውያነ ነቢያት እለ ይመጽኡ ኀቤክሙ በአልባሰ አባግዐ ለምድ ለብሰው ነጣቂ ተኲላዎች ይመጡባችኋልና ተጠበቁ ተጠንቀቁ አለ። መልካም መስለው ስለሚመጡ በምን እናውቃቸዋለን ያልን እንደሆነ የሚታወቁበት ምልክታቸው ሥራቸው ነው። እንዳለን ለመረዳት ፲፮ ወእምፍሬሆሙ ተአምርዎሙ። ይቀስሙሁ እምኣስዋክ አስካለ ወእምሜከላ በለሰ። እንደዚያ አድርጎ ለይቶ ተናገረ እንግዲህ ይህ ሮማ ላይ ያገር ግዛት ማስፋፋት ያ የቆመው ማኅበር በሺ፰፻፺ ዓ.ም በላይ ነው ይህንም የሚአካህደው የሮማው መ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እንደሆነ በተጻጻፉበት ደብዳቤ ተገልጧል። የተሠወረ አይደለም እርግጥ ነው በፊት ሥውር ነበር። አሁን ግን የፖለቲኩ ጽሑፍ ሁሉ ከቦታው ወጥቶ እንደተዘረዘረከ ድል አድራጊው ከፈጣሪው የተስማማው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከደረሰባቸው ማነኛውም የፖለቲክ ጽሑፍ በየሥፍራው እየተጐለተ ተገኘ ያዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ሥራችን ያልታወቀብን

# ኡ ሰኑይ

እየመሰላቸው መንፈሳውያን ነን በማለት በብዙ ሲደክሙ ይታያሉ ከንቱ ድካም ነው እነሱ ሥራ አይታወቅም ከማለት የዝቋላን ተራራ ሜዳ ነው ማለት ይሻላል። ወደ ወንጌሉ እንመለስ ማቴዎስ ፯ ፲፯ ከማሁኬ ኵሉ ዕፅ ሠናይ ሠናየ ይፈሪ ወእኩይሰ ዕፅ ፍሬ እኩየ ይፈሪ ከላይ ከሜከላ በለስ ይለቅማልን ብሎ ነበርና ከማሁኔ ዕፅ እንጨትም ሁሉ መልካምም እንጨት መልካም ፍሬ ያፈራል። ክፉውም እንጨት ክፉ ፍሬ ያፈራል አለ። ፲፰ ኢይክል ዕፅ ሠናይ እኩየ ፈርየ። ወኢዕፅ እኩየ ፈርየ ሠናየ። ያንኑ ማጥበቁ ነው ፲፱ ኵሉ ዕፅ ዘኢይፈሪ ፍሬ ሠናየ ይገዝምዎ ወውስተ እሳት ይወድይዎ አለ መልካም የማይስጥን እንጨት ሁሉ ግንዱን ከነሥሩ እየነቃቀሉ ዘሩን ለማጥፋት ማለት መሬት በከንቱ እንዳይዝ በእሳት ማቃጠል ነው ብሎ እንዲቃጠል መቃጠሉም ለሌላው ተክል የሚመቸው መሆኑን ያመለክታል ፳፩ አኮ ኵሉ ዘይብለኒ እግዚኦ እግዚኦ ዘይበውእ ውስተ መንግሥተ ሰማያት ዘእንበለ ዳዕሙ ዘይገብር ፈቃዶ ለአቡየ ዘበሰማያት የሰማያዊ አባቴን ፈቃድ የፈጸመ እንጅ እንዲሁ በአፍ እግዚኦ አቤቱ አቤቱ የሚለኝ ሁሉ ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም አለ እንደዚሁ ለእግዚአብሔር መንግሥት እንሰብካለን እያሉ ለሮማ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚአፋጁ ፳፪ ወብዙሐን እለ ይብሉኒ በይዕቲ ዕለት እግዚኦ እግዚኦ አኮኑ በስምከ ኢጋንንት አውጻእነ ወበስምከ

ኃይላተ ገበርነ ፳፫ ወይዕተ ጊዜ አአምኖሙ ግሙራ ኢየአምረክሙ ረኃቁ እምኔየ እለ ትገብሩ ዓመፃ ማለት ቅሚያ ማለቱ ነው። ወንጌላውያን ነን እያሉ ወንጌሉን ተሸክመው የሚአዘውን ሳይፈጽሙ የሚኖሩትንና የማይፈጽሙትን ለማስረዳት ፳፬ ኵሉኬ ዘይሰምዕ ዘንተ ቃልየ ወይገብሮ ይመስል ብዕሴ ጠቢበ ዘሐነጸ ቤቶ ዲበ ኰኩሕ ፳፭ ፳፮ ወኵሉ ዘይስምዕ ዘንተ ቃለ ወኢይገብሮ ብዕሴ አብደ ሐዘነጸ ቤቶ ዲበ ኆፃ ፳፯ ወወረደ ዝናም ወመጽኡ ወኃዝት ወነፍሑ ነፋሳት ወገፍዕዎ ለውእቱ ቤት ወወድቀ ወኮነ ዓቢየ ድቀቱ ምንም ቢሆን ያለፈሪሃ እግዚአብሔር የተሠራ ሁሉ ፈራሽ ነው እንጅ የሚጸና አይደለም አሁን ያዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን ሰዎች በኢትዮጵያ

መንግሥት ምድር ላይ የሠሩት ቤት ሁሉ ለዘለዓለም ርስት እንዲሆንላቸው አሳባቸው ሙሉ ነው ይልቁንም ደግሞ ባ፲፰የ፹፰ ዓ.ም ካደረጉት ጦርነት ባ፲፱የ፳፰ ዓ.ም ያደረጉት ያሰናዱት ጦር እንደበለጠ አሁንም ደግሞ እንደልማዳቸው በመካከላችን ተቀምጦ ካለፈው የበለጠ ነገር እንዲያመጡብን አሳባቸውን የድሮው ፕላን ጽሑፋቸው ያስረዳል የነሱ ፕላን በረቂቅ ፖለቲክ የኢትዮጵያን መሠረት መገልበጥ አሳባቸውን ተከታትየ የመረመርኩትን ሁሉ ከላይም አስረድቻለሁ።

እነሱ በስብከታቸው ሲያያዝ የመጣውን ጐንደ መንግሥት የተቆረጠ እያስመሰሉ የጻፉት በሰፊው ይገኛል። ስለ ቤተ ክህነቱም በ፲፻፵ ዓ.ም የተዠመረ ከነዚያውም ያነኑ ከነፊደልም ያደራጀልን ከውጭ የመጣው አባ ሰላማ ነው ይላል። ከዚያ በፊት ለፊደል እንኳ ሳንበቃ ቀርተን የፊደሎችን ደረጃ ያሰናዳ አባ ሰላማ ነው እያሉ የጻፉት ይገኛል። የኢትዮጵያን ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት እያኳሰሱ ታሪኳን ለወጣቶቹ በጣም አስጠንቅቀዋል። የኢትዮጵያ መንግሥት ከመሠረቱ ወጥቶ የማያውቀውን ወጥቶ የነበረ እያስመሰሉ ሲጽፉ ይገኛሉ። ዋናው ትልቁ ነገር ባረብ አገር የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበረ

# ኢ. ሠሉስ

የሚያስረዳ ማስረጃ እያለ በኢትዮጵያ የመሠረተ ፊደል በካም ቤት ሲያያዝ የመጣው የፊደል ቅርጽና መጽሕፍቱ ጥንታዊነታቸው የሚያስረዳ ታሪክ ያለባቸው ከዓለም ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍቶች ብልጫ ያላቸው መጻሕፍቶች እያሉ ያለ ፍርኃት የኢትጵያ መጻሕፍት ከጽርዕ ወደ ግዕዝ የተገለበጠ ማለታቸው የሚገርም ነው። የጽሑፋቸው መለያየት ባ፩ኛው አፋቸው የፊደል ደረጃ ያደራጀ አባ ሰላማ ሲሆን መጻሕፍቱን ከጽርዕ ወደ ግዕዝ ገለበጠው ይላሉ። እንግዲህ ከሁለቱ ቃሎች የትኛው ነው የሚጨበጠው ከጽርዕ ወገን አባ ሰላማ ሲሆን ከዕግዝ ወገን ማንን እናድርግ። አባ ሰላማ ግዕዝን ከማን አመጣው። የፊድሎችን ደረጃ ፯ አድርጎ አደራጀ የተባለው የጽርዓውያን ፊደል ደረጃ ፯ ናቸው ለማለት ያስደፍራል ይሆንን የፊደልን ደረጃ ፯ መሆን ከምን መሠረት አመጣው ያዲሲቱ ቤተ ክርቲያን ሰዎች ያለነሱ መጻሕፍትን የሚመለከት የለም ማለት ነው። ምንም ሐሰቱን እውነት እውነቱን ሐሰት እናድርግ ብለው ቢደክሙ ቢያስጠኑ ትልቁን ያልተኰሰ ሸክላ ትንሽ ከፊያ እንደሚያፈርሰው የነሱንም ሥራ ፬፻ ዘመን የተሠራውን ፖለቲክ በትንሽ ቀለም ፍርስርስ አደርገዋለሁ።

የኢትዮጵያን ፊደል እኛ እናውቀዋለን ሲሉ አለማስፈራቸው በጣም ያስገርማል። በነሱ ቤት የኢትዮጵያ ፊደል አስደናቂ ምሥጢር የለበትም ተብሏል። የፊደልን ምሥጢር መርምረው አውቀው ቢሆን ይህን የመሰለ መሠረት የሌለው ነገር ባልጻፉ ነበር። የፊደል መሠረት እንዲሁ በዘፈቀደ የሚነገር አይደለም። ስለ ፊደል ምሥጢር ግዕዝና የዕብራውያን ፊደል ለየብቻ ናቸው። የግዕዝ ደረጃዎቹ ፯ት ናቸው እነዚህም ፯ቱ ዕለታት ሀ ግዕዝ እኁድ ሁ ካብዕ ሰኑይ ሂ ሣልስ ሠሉስ ሃ ራብዕ ሄ ኃምስ አሙስ ህ ሳድስ ሆ ሳብዕ ቀደም እንደዚህ እያሉ ሲሄዱ ዘወትር በግዕዝ ፊደሎችና ዕለተ እኁድ አይለያዩም በሄኖክ በመጽሐፍ በሚጠተ ብርሃናት እንደ ሚሰፈረው ሚያዝያ እኁድ ሀ ሰኑይ ሁሉ ሠሉስ ሂ ረቡዕ ሃ ሐሙስ ሄ ዓርብ ህ ቀደም ሆ በዚህ ሂሳብ ፳፮ቱ ፊደሎች በ፯ ሲበዙ ፻፹፪ት ይሆናሉ ይህም

በሄኖክ ሚዛን ሲመዘን ፩ኛ ሚያዝያ እሑድ ይብታል ፴ ፪ኛ ግንቦት ማክሰኞ ይብታል ፴ ፫ኛ ሰኔ ሐሙስ ይብታል ፳፱ ፬ኛ ሰኔ ሐምሌ እሑድ ይብታል ፴ ፭ኛ ነሐሴ ጥቅምት እሑድ ይብታል። ፴ ፮ኛ መስከረም ይብታል ፳፱ ፯ኛ ጥቅምት እሑድ ይብታል ፴ ፰ኛ ኅዳር ይብታል ፴ ፲፩ የካቲት ማክሰኞ ይብታል ፴ ፲፪ኛ መጋቢት ሐሙስ ይብታል ፳፱ ጥቅል ድምር ልክ ፫፻፷፬ እንደ ዚህም የሆነ በመንፈቁ ፳፪ቱ ፈደሎች በ፯ት ሲበዙ ፻፶፬ ይሆናል ከቀኖቹ ጋር ሲመዘኑ ግዕዝ እሑድ ሳብዕ ቀዳም እየተባለ ሲመዘን ፻፶፬

ቀኖች ከ፻፶፬ቱ ፈደሎች ጋር ልክ ይሆናሉ። ይህም ፩ድ ንዑስ ሰንበት ይባላል በዚህ ሂሳብ እስከ ፸፮ ዘመን ሲቆጠር ካ፸፮ኙ ዓመቶች ፯ት ንዑስ ሰንበት ይገኛል። ከዚህም ከሰባቱ ዓመቶች ውስጥ ፯ት ፶፪ት ይገኛል። ይህም ሲደመር ልክ ፫፻፷፬ ይሆናልይህ

# ኣ ረቡዕ

፫፻፷፬ ፩ድ ዓመት ማለት ነው ይህችም በዕለተ እሑድ ትባላለች ዓመተ ኅድገት የምትባል ይህች ናት መረጃውን ለፈለገ ኦሪት ዘሌዋውያን ፳፭ ፰ ወትኄልቍ ለከ ፯ተ አረፍተ ዘ፯ ዓመት ዘምሥብዒት ወእምዝ ትሬሲ ለከ ፯ተ ሰናብተ በበ፯ ወ፱ ዓመት ያለውን ለመመርመር አስተውሎ መመዘን ያስፈልጋል ከላይ ካ፩ዱ ዓመት ፶፪ ሰንበት ይዞ እስከ ፯ ዓመት ጊዜ ፶፪ ፫፻፷፬ ይሆናል። ይህም ፩ድ ንዑስ ሰንበት ይባላል ግበር ለከ ፯ተ አረፍተ ያለው እንደዚሁ እስከ ፯ት ደረጃ ዘ፯ት ዓመት ዘምሥብዒት ያለው ከ፯ ዓመቶች ፯ት ጊዜ ፶፪ ፫፻፷፬ቱ ያ፩ ዓመት ቀኖች ስለሆኑ ቁ ፲ ወቀድስዋ ለይዕቲ ዓመት ዘ፶ ኵላ ዓመታት ወስብኩ ዓመተ ተኃድጎ ውስተ ኵሉ ምድርክሙ። ይህችን ፶ኛዋን ዓመት አክብርዋት የምትከበርም ዓመቱን በሙሉ ነው። ይህችም ዓመተ ኅድተግ ሚያዝያ ፩ድ በዕለተ እሑድ ነው። የሚብተው ፩ድ ፩ድ ሰዎች በዘመነ ኦሪት ዕለት እሑድ አትከበርም ነበር ይላሉ ካለ ማስተዋል የተነሳ ነው እንጅ ኦሪት ዘሌዋውያን ፳፫ ፲፮ እስከ ሳኒታ ለደኃኒት ሰንበት ትኆልቁ ፶ ዕለት ወታበውኡ መሥዋዕተ ሐዲስ ለእግዚአብሔር እስከ ሣኒታ ለደኃሪት ሰንበት ትኆልቁ ፶ ዕለት ያለው እንደዚህ ለይቶ ያመጣዋል ደኃሪት ሰንበት ያላት እሑድን ነው። ሣኒታ ማለት ከእሑድ ወደፊት እስካለችቱ እስከ ሰኑይ ፶ ቀን ትቆጥራለህ አለ ይህም ከትንሣኤ እስከ ጰራቅሊጦስ ያሉትን ቀኖች ማለቱ ነው ካ፸፮ኙ ዓመቶች ፯ ሰንበቶች ከሰባቱ ሰንበቶችም ፯ት ጊዜ ፶፪ አውጥቶ ፯ቱን ፶፪ት ፫፻፷፬ቱ ፩ዱቱን ዓመተ ኅድገት እንዳላት በቀንም ከትንሣኤ እስከ ጰራቅሊጦስ ካ፸፮ኙ ቀኖች ፯ት ሰንበቶች ይገኛሉ። ከ፯ቱ ሰንበቶችም ፶፪ ፶፪ አውጥቶ ፯ ፶፪ ፫፻፷፬ ይሆናል ይህች ቀን ጰራቅሊጦስ የሚውልባት ፶ኛዪቱ ቀን ናት ስለዚህ ቅዱስ ዳዊትም በ፶ኛው መዝሙር ወመንፈስከ ቅዱስ ኢታውጽእ እምላእሌየ አለ። ይህች በዓለ ጰንጠቆስጤ በኦሪትም ትከበር የነበረች ለመሆንዋ መረጃ ለፈለገ ፩ኛ ጦቢት ፩ ዕለተ በዓለ ጰንጠቆስጤ ይላል ፪ኛ መቃብያን ፲፪ ወእምድኅረ ዕለት ዘይብልዋ ጰንጠቆስጤ ይላል። ፫ኛ ኦሪት ዘሌዋውያን ፳፫ ፯ ወቀደሚት ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ኵሎ ገብረ ቅኔ ኢትገብሩ ይላል። ይህም ቀዳሚት ዕለት ያላት ዕለተ እሑድን ነው የተቀደሰች ቀን ትሁንላችሁ ሥራም አትሥሩበት ዕረፉበት ማለቱ ነው ፬ኛ ፲በ፰ ወዕለት ቀዳሚት ትሰማይ ቅድስተ ኵሎ ግብረ ቅኔ ዘትትቀነዩ ኢቅበሩ።

፭ኛ ፳፰ ሰቡዓ ዕለተ ታበኡው መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ወሳምንትኒ ዕለት ቅድስተ ትሰመይ ለክሙ ወአብኡ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር እስመ ዘጸዓት ውእቱ ኵሎ ግብረ ዘትትቀነዩ ኢትገብሩ። ፮ኛ ፳፱ ወአመ ዕለተ ፲ወ፭ሱ ለውእቱ ሳብእ ወርኅ አመ ፈጸምክሙ አስተጋብኡ እክለ ምድርክሙ ትገብሩ በዓለ ለእግዚአብሔር ሰብዓ ዕለተ ወዕለት ቀዳሚት ዕረፍት ይዕቲ ወዕለትኒ ሳምንት ዕረፍት ይዕቲ። ለጊዜው እነዚህ ማስረጃዎች ይበቃሉ ይህች ዕለት እሑድ በኦሪትም ትከበር እንደነበረች ይኸው ማስረጃዎችን አቀረብሁ። እንግዲህ ከላይ ሀ ግዕዝ እሑድ ብየ እንዳመለከትሁት ይህች ዕለተ እሑድ ግዕዝ ናት ስል በማውራት ብቻ ሳይሆን መረጃውን ጨምሬ ከ፸፮ኙ ዓመቶች ፯ ሰንበቶች ይገኛሉ። ከ፯ቱም ሰንበቶች ፶፪ ይገኛሉ። ሲደመሩ

# ኤ ኃሙስ

፫፻፷፬ ይሆናሉ። ይህችም ዓመተ ኅድገት ናት ሚያዝያ ፩ በዕለተ እሑድ ትገባለች በዕለተ ቀዳም ትጨርሳለች። በዓለ ዓመተ ኅድገት ፶ ስለሆነ በ፶ት ስታበዛው ፫፻፶ ይሆናል። ይህም ግዕዝ ማለት መሆኑን ለመረዳት በኢትዮጵያ ፊደል ገ፪፻ ዐ ፸ ዘ ፹ ድምር ፫፻፶ ይሆናል የግዕዝ ትርጓሜ መሆኑን ያልተገነዘቡ ሰዎች የግዕዝ ቋንቋ ከባቢሎን ግምብ መፍረስ ወዲህ እንደ ተፈጠረው እየመሰላቸው በማያውቁት ነገር ገብተው ሲፈተፍቱ ለነሱ ቢጤ እውነት ይመስለዋል። የግዕዝን ምሥጢር ቀሊል እየመሰላቸው ይደክማሉ። የግዕዝ ፊደል። የግዕዝን ምሥጢር ቀሊል እየመሰላቸው ይደክማሉ። የግዕዝ ፊደሎች በቁጥር ማገር የተያዙ ናቸው። ትርጓሜው የሚገኝ በፊደሎች ቁጥር ነው ፩ድ ፩ድ ሰዎች የፊደልን ቁጥር ያልተገነዘቡ በማቃለል ይመለከቱታል ፩ኛ አዳም ሲል በግዕዝ ፊደል አ ፵ ደ ፻ መ ፬ ድምር ፻፵፬ ይሆናል የዚህም ምሥጢር አዳምን የፈጠረው በየቀኑና በሳምንቱ ሊያመሰግነው ስለሆነ። ባ፲፪ቱ ሰዓቶች ዛሬም ልጆቹ ትእዛዙን አውቀን እንድንሠራ የዘለዓለም ማስታወሻ እንዲሆነን ባባታችን በአዳም ስም ቁጥር ፻፵፬ት አቡነ ዘበሰማያት በቀን በቀኑ እንጸልያለን ለዚሁም መረጃ በጃችን በሚገኙ ሰዓቶች ስንመለከት ዋናዋ ቆጣሪ ፩ ደቂቃ ስትሄድ ፪ኛይቱ ቆጣሪ ፷ውን ደቂቃ ታደርሳለች ፷ ደቂቃ ላ፭ት ስትመደበው ፲፪ ይሆናል። ይህም ፲፪ ቁጥር ፩ቀን ወይም ፩ ዓመት ሊባል የሚቻል ስለሆነ። በነዚህ ፲፪ቱ ፲፪ት አቡነ ዘበሰማያት እንድንጸልይ ባ፲፪ቱ ሰዓቶች ፲፪ ጊዜ ፲፪ ፻፵፬ ይሆናል። አዳምን በኤዶም ላይ ፈጠረው ሲል ኤዶምና በግዕዝ ፊደል ቁጥር ፻፵፬ ነው። እብራውያን ይህን የፊደል ቁጥር ስለማይገነዘቡ ኤደን ገነት ይላሉ ጌታችን ዳግማዊ አዳም ስለመባሉ ቅ. ገብርኤል የተናገረው የጌታችን ስም ኢየሱስ ነው። ኢየሱስ ሲል በግዕዝ ፊደል አ ፵ የ ፺ ሰ ፯ ድምር ፻፵፬ት ዳግማይ አዳም ማለት እንደዚህ ነው ትርጓሜው።

የፊደሉን ቁጥር ባለመመልከት ሌሎቹ ክርስቲያኖች ሁሉ ፩ዲቱን ቀለም አጉድለው የሱስ እያሉ ይጽፋሉ። የኢትዮጵያ ታሪክ ሰፊ ነው። ፩ድ ፩ድ ሰዎች የፊደልን ቁጥር ነገር እንደማቃለል ሲያደርጉት ይታያል። ኦሪት ዘፍጥረት ፯ ፲፯ ወኮነ አይጎ ዲበ ምድር ሲል አይጎ በግዕዝ ፊደል አ ፵ የ ፺ ጎ ፳ ድምር ፻፶ ይሆናል። የተባበረ ነገር ከብዙ ቦታ ይገኛል። አብርሃምም አስቀድሞ ስሙ አብራም ስለ ነበረ። በኋላ ግን ስምህ አብርሃም ይሁን ስላለው በጥንት ስሙ ላይ በኢትዮጵያ ፊደል ፩ድ ተብሎ የሚቆጠረውን ሀን/ጨመረበት አብርሃም ሲል በግዕዝ ፊደል አ ፵ በ ፱ ረ ፮ ሀ ፩ መ ፬ ድምር ፷ ይሆናል ይህ ፷ ቁጥር ዋና መሠረት ነው። ላ፭ ሲመደብ ፲፪ ይሆናል። ስለዚህ ፲፪ቱ ነገደ ፷ ኤል ከሱ እንደሚወለዱ ሲያመለክተው ስምህ አብርሃም ይሁን ብሎ ቁጥሩን ፷ሣ እንዲሞላ ያደረገው ስለዚህ ነው ኦ. ዘ. ፍ. ፲፯ ፭። ፪ኛው ሣራንም እንደዚሁ ቀድሞ ትጠራበት የነበረው ስምዋ በንጉሡ ሠ. ሣራ ፲፩ ቁጥር ስለ ነበረ። የፊተኛው ሠ ተለውጦ ፯ኛው ቁጥር ሰ ይሁን ሳራ ተባለች ቁጥር ፲፫ ሆነ። ይህም ፲፫ ቁጥር ከ፩ኛ ክፍለ አውራኅ ከ፯፩ዱ ቀኖች የሚገኘው የሰንበት ቁጥር ነው። ወደ ሰንበት ቁጥር ለመግባት ሲፈለግ ሰ የሚባለውን ቁጥር ፯ት የሆነውን ፊደል ሰጣት። ኦቲት ዘፀዓት ፴፬ ፳፰ ወጸሐፈ ውስተ ጽላተ ዘንተ ፲ተ ቃለ አሠርተ ብሎ ቃለ ያለው ያነኑ ፲ርን እንደሆነ

# እ ዓርብ

ለመረዳት በግዕዝ ፊደል ቀ ፰ ለ ፪ ድምር ፲ር ይሆናል በኢትዮጵያ ፊደል ሰንበት ሰ ፯ ቁጥር በሆነው ነው እንጅ ፭ ቁጥር በሆነው ሠ አይጻፍም ሰብዕ ሲልም ፭ ቁጥር የሆነው ሠ ሠብዕ ብሎ አይጻፍም የኢትዮጵያ ፊደል የምሥጢረ እግዚአብሔር መነጋገሪያ ነው። ከዓለም ፊደሎች ልዩነት ያለው ነው ፩ኛ የፊደሎች ተራ ቁጥር ፳፮ ነው። ፪ኛ በፊደል ቁጥር ፳፪ ፫ኛ ግዕዝ ሲጻፍና ሲነበብ ከግራ ወደ ቀኝ ነው። ፬ኛ ግዕዝ ግሥ ሲሠራ የመጨረሻውን ፊደልና የመዠመሪያ ፊደል ጠብቆ ነው። ፭ኛ ፊደሉ የሚዠምር

በሀ ነው የሚጨርስ በፐ ነው። ፮ኛ የፊደል ደረጃዎች ፯ ናቸው። የእብራውያን ፊደል ቁጥር ፳፪ ነው። ፯ኛ በፊደል ደረጃዎች ፯ ናቸው። የእብራውያን ፊደል ቁጥር ፳፪ ነው። ፰ኛ በፊደል ቁጥር ፬፻ ነው። ሲጻፍ ከቀኝ ወደ ግራ ነው። ግሥ ሲሠራ በመዠመሪያው ቀለም ነው። ደረጃዎችም ፭ ናቸው ይህም ፭ ቁጥር ዋና መሠረት አለው ይህም ሙሴ ፭ቱን ብሔረ ኦሪት ፩ድ አድርጎ ነው። ፱ኛም የጨረቃ ቁጥር የተዠመረ ጽልመት ፩ድ ሲል ባ፭ኛው ቀን ነው። የሰዓታችንም ዙሪያ ቁጥር ፭ ፭ የተከፈለ ነው። የእብራውያን ፊደል ደረጃዎች ፭ መሆኑ ስለዚህ ነው። ይህን ሁሉ የመለያ ምልክት አልፈው የእብራይስጡን እንኳ የፊደል ቁጥር ሳይጠብቁ በዘፈቀደ የእብራይስጡንም የግዕዙንም ቁጥር እያዘባረቁ የኢትዮጵያን ፊደል ግዕዝ መሠረት እናጠፋለን ሲሉ የእብራይስጥንም ፊደል ተራ ቁጥር ሲአፋልሱት ይገኛሉ። እነዚህም እንደዚህ ያለውን ሥራ የሚሠሩ የነዚያው የሮማውያን ደቀ መዛሙርቶች ናቸው። ከላይ ተጽፈው እንደሚታዩ ካ፩ድ እስከ ፮ ተጽፈው የሚገኙ ምልክቶች እያሉ። ይህን ሁሉ መረጃ ደምስሰው በኢትዮጵያ ላይ አባ ሰላማ እስቲመጣ ድረስ ፊደልም አልነበረም መጻሕፍትም በሙሉ ከጽርዕ ወደ ግዕዝ ተገለበጡ እያሉ ሲጽፉ ከኢትዮጵያ ተወላጆች ከፈረንጆች የታሪክ መጽሐፍ አገኘን እያሉ በግዕዝ ተጽፈው በየገዳማቱ ያሉትን መጻሕፍቶች ያለነበቡ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ዋናውን ታሪክ የሚደመስሰውን የጠላት የፖለቲክ ስብከት እየገለበጡ በወጣቶች ልብ ላይ ሲዘሩት ይታያል። እነሱ አስቀድመን ግዕዝ እንዲጠፋ ሲሉ የግዕዝ ትምህርት እንዳይቋቋም ዋና ሥራቸው አድርገውታል። በየተማሪ ቤቱ ውስጥ የግዕዝ መጽሐፍ በየረከተ አይገኝም እነሱ እንዳይቀዱት የግዕዝን መጻሕፍቶች የሚመለከት ጠፋ። ምክንያቱን በግዕዝ መጻሕፍትቶች ውሥጥ የሚገኘው ጥቅም ባለመታወቁ ነው እንጅ ታውቆ ቢሆን በቀላሉ በብዙ ምንገድ ኢትዮጵያን ራስ የሚአስችል ነገር እንዲገኝ እርግጠኛ ነኝ። እግርጥ ነው አያሌ መጽሐፍ ወደ አውሮፓ ተሠርቀው ተሻግረዋል። ይሁን እንጅ እዚህ ያሉት የኢትዮጵያ መጻሕፍት በኢትዮጵያ ገዳማት የሚገኙትን ብዛታቸው ልክ መጠን የሌለውን እንዲሰበሰቡ ተደርጎ ቢጠኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ሥራ ማከናወኛ የሚሆኑ ነገሮች ሁሉ የተቀበሩበትን ሀብቶች የሚነግሩ ለመሆናቸው ማስረጃ ይሆን ነበር። የሮማ ልዑካን ስብከት በኢትዮጵያ በጣም ስለተስፋፉ ከጥንት ሲያያዝ የመጣውን የፊደል መልክ ይዞ በጥርብ ድንጋይ ላይ ተጽፎ የሚገኘውን ጽሑፍ የሣባ ፊደል የሚሉ ስም ወጣለት። ጸሐፊዎችም የደቡብ ዓረብ ሰዎች ናቸው ተባለ። ያዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን ከእውነት የራቀ ጽሑፋቸው ለጊዜው የተቃናላቸው ይመስላል። ሥራቸው በሐማሴን ምድር እነሱ በያዙት ቦታ ሁሉ እዛዦች ሆነዋል፡ ኢጣልያኖች በወረራ ገብተው ሠራን ያሉት ሁሉ እነሱ

Serie Sez.

MINISTERO DELL'AFRICA ITALIANA - GOVERNO GENERALE DELL'A.O.I.

Servizio Centrale di segnalamento e identificazione

N.

Cognome Chebbede Acaliot

Paternità Acaliot Chbarlè — Madre Ighebbarnian

Soprannome — Falsi nomi

Nato il 1918 — Distretto Ades (Chioa) — Cabila o Tribù — Lahama

Domicilio: Distretto Bedelle — Cabila o Tribù — Lahama — Cittadinanza S. Ital.

Istruzione — Professione Interprete — Ricercato per dati —

Motivo dell' — sospetto di spionaggio militare e propaganda anti italiana avendo formato società antitaliane e sacrificio della patria

Identificato per

CONNOTATI CROMATICI

Aureola chiari — Pigmento br. — Capelli cast. — Baffi cast.

Periferia — Sangue — Sopracciglia — Barba

Riduzione fotografica di 1/6




Data e luogo dei rilievi segnaletici

Città Gimma Giorno 12/10/1941 Anno


Annotazioni relative alla fotografia e alle impronte

IMPRONTE DELLA MANO SINISTRA

| Pollice | Indice | Medio | Anulare | Mignolo |
| --- | --- | --- | --- | --- |



በ፩ ፡ ኣባ ፡ ማሳያ ፡ መሪነት ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ የደረሰው ፡ ግፍ ፡




በነ፡ አባ ፡ ማሲያ ፡ መሪነት ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ የደረሰው ፡ ግፍ ፡



በኑ ፡ አባ ፡ ማሳያ ፡ መሪነት ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ የደረሰው ፡ ግፍ ፡



በነ ፡ አባ ፡ ጣሳ ፡ መሪነት ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ የደረሰው ፡ ግፍ ፡



የአለቃ መርሻ ወልደ ማርያም ታሪክ የሚደንቅ ነው። አለቃ መርሻ በ፲፰፻፹፪ ዓ.ም ጐጃም ደብረ ወርቅ ላይ ተወልደዋል። በተማሪ ቤት ከኖሩ በኋላ በቤተ ክህነት ሹመት እየተዘዋወሩ ሲኖሩ በተወለዱ በ፷ ዘመናቸው የኢጣልያ ድላቸውን ተቀባይነት በማጣት ቆይተው የሰውነታቸውን መሸምገል የሚአይ ሁሉ ወርደው ካርበኞች ለመጨመር ቆርጠው ለጠላት መገዛትን በፍጹም ወደ በርኃይህ ነገር ለጠላት ተነገሮባቸው ኑሮ ፲፱፻፳፰ ዓ.ም ሐምሌ ፲፪ ቀን የጠላት ሹማምንቶች አታለው ይዘው አስቀይተው ለመግደል አስበው አስበው መጥተው ቤታቸውን ከበው ትጠራለህ ብሎ ቢነግራቸው አብሮአቸው በሚኖር ሽጉጥ ፩ድ ፩ድ አድለዋቸው በኋላ ግማሹ ሲሸሽ ግማሹ አድፍጦ ቆይቶ በብዙ ጥይት ለጀግኖቹ የሚገባውን የሞት ጽዋ ተቀብለዋል። ስል የታሪክ ዓምዶችን ያሌቃ መርሻ ታሪክ ጌጥ ሆኖ ያደምቃቸዋል። ይህን አሳባቸውን ከነምልክቱ ፩ድ ሰው ሲነግረኝ

ተምሮ ተምሮ ካልሰበሰቡት

እንዴት ያሳዝናል ሲባክን ሲባክን ዕውቀት።

ሂጅ ተመለሽ ግቢ አገርሽ ቅኔ

ወንዶች ከዋሉበት መዋሌ ነው እኔ።

ከወንዶቹ ቦታ መሄዴ ነው እኔ ሲሉ በሰማኋቸው በ፫ ቀን አረፉ ብሎ ነገረኝ ያለቃ መርሻን ልብ ማሰብ የተገባ ነው ይህ ጀግና በ፷ ዘመኑ ይህን የሠራ በ፺ ዘመኑ ላይ እንደምን አድርጎ በሠራ ነበር።

አለቃ መርሻ አይፈራም እጁ


ጠላት ሲጋበዝ እንዳወዳጁ

ገሥግሠው ሄደው እንደ ጐመጁ

በሽጉጥ ጠርሙስ ፩ድ ፩ዱን ፈጁ።

መርሻ ቢያጠጣው የሽጉጥ ጠላን

ወዲያው ወደቀ ግብዙ ጣሊያን።



የኢትዮጵያው ፡ ጀግና ፡ ዘርዓይ ፡ ድረስ ።

# አ ቀዳም

እንዳደረጉት የጥንቱ ባለርስት እንደተነቀለ ነው። አሁንም እነሱ እንደልባቸው ከመስበክ አልቦዘኑም። የትምህርት ቤታቸውን እንደልብ ያስፋፉሉ። ምንም ቢሆን የጠላት አስተማሪ መልካም መስሎ እንዳይታይ ጌታችን በቅዱስ ወንጌል አስጠንቅቆናል። ዮሐንስ ፲ ፲፪ ወአሳብ ሰ ዘኢኮነ ዘዚአሁ አባግዕ። ይህ ቃል ለኛ ማስጠንቀቂያ ነበር ማን ለማን ያስባል የሮማ ልዑካን አስቀድሞ ዝምሮ አሳባቸው ሁሉ በረቂቅ ስብከት የሕዝቡን ልብ ለመሳብ ስለሆነ የወጣቶችን ልብ ባይመርዙብን በጣም የተሻለ ነገር ነበር። የነሱ ስብከት በዛሬው ሰዓት በጣም አስጊ ነው። ነገርን ማየት ባለፈው ዘመን ሁሉ የሡሩትን እኛም አንረሳውም ቀኑ የራቀውን ብንረሳ በቅርብ ቀን የተደረገውን አንዘነጋም ማለት ጥንታቄን ማስታወስ ነው። በኛ በኩል በማነኛውም ምክንያት የሞቱን ወገኖቻችንን በመዝገበብ እያሰፈርን ጉዳታችንን እያስታወስን ለፈጣሪአችን እያዘን እያመለከትን ያለነውም እየተስማማን ብንቀመጥ እንደምን አገራችን በቀናች ኔብር። እነሱ እንደኛ አይደሉም የሀገራቸውና የወገናቸው ነገር በጣም ስለሚጠናባቸው ወደ ኢትዮጵያ መጥተው የሞቱን ወገኖቻቸውን ልክ በአሕዛብ እጅ ስለ ሃይማኖት የሞቱ እያስመሰሉ ስሙንም እየመዘገቡ እያስቀመጡ የነዚያን ሰዎች ሞት እንደ ሰማዕት ስሙንም እየመዘገቡ እያስቀመጡ የነዚያን ሰዎች ሞት እንደ ሰማዕት ሞት እያደረጉ በቀላቸውን ለመመለስ የማይዘነጉ ሰዎች ናቸው። እነሱ ከአፍሪካ ካልወጡ ኢትዮጵያ ጤና ታገኛለች ማለት ከንቱ ነው። በነሱ ምክንያት የሞቱትን ሰዎች ድምር ከላይ በመጠኑ ጽፌው ነበር ግን ወደ ሊቢያ ኢጣልያኖች ለጦርነት እየቀጠሩ እየወሰዱ እዚያ እያዋጉ ያስፈጅዋቸው ሰዎች ቁጥር በግምት ከ፺ና ከ፰ሽ አያንሱም ፪ኛ በውጋዴንም በኩል የጊዜው በሚነሳው ጦርነት ሁሉ ያለውቀው ኢጣልያኖች ምጽዋን ከረገጡ አንስቶ የዓድዋ ጦርነት መጨረሻ ፪የ፵፫ሽ ፪፻ ይሆናል። እንደዚህ ስለተባለ ለጠላትም ተቀጥረው የሞቱን ተጨምሮ ታስቦ ነው።

፪ኛ ካ፲፱፻፳፯ ዓ.ም እስከ ፴፬ ዓ.ም ከላይ እንደተጻፈው በዋናዎች ጦርነት ቦታና ደግሞ በየጊዜው በማናቸውም ምክንያት እርስ በርሱ የተቀላቀለው በግምት ፻፶ሽ ይሆናል። ይህ ሲደመር ፬፻፫ሽ

፪፻ ነው። ይህን ያህል ወገን አልቆብን ቤተ ክርስቲያኖች ተቃጥለውብን ያባቶቻችን መሳሪያዎ ሁሉ ተዘርፈውብን ይህን ያህል የመከራ ጕርፍ በላያችን ላይ አልፎብን ይህን ሁሉ ታሪክ ረስተን ያመጣብንን መርምረን ሳንረዳ መቀመጣችን በጣም ያስደንቃል። የሞቱትን ወገኖቻችንን ቁትር ባ፲፫ ዓመት በቀላል ግምት ፬ ሚሊዮን አይሆንም ነበርን። ሞት የማይቀንሰው የለም እነሱ ከገቡ ወዲህ ኢትዮጵያ እያደረገች ከማነስ በተቀር ፩ድ ትርፍ አላገኘችም ነገሥታቷ መሳሪያ እናስመጣለን እያሉ ይዋዋሉና ሃይማኖታቸውን አስከደው ፩ድ መሳሪያ ለነ አጼ ሚናስ ለነ አጼ ያዕቆብ ለነ አጼ ዘድንግል ላጼ ሱስንዮስ ለነዚህ ሁሉ ያመጡት መሣሪያ የለም እንዲሁ በቀጠሮ ነገ ይመጣል ከነገ ወዲያ ይመጣል እየተባለ ነው ለወደፊቱ እንዲመከርበት ያስፈል ከጦርነቱ በፊት የነበረ የስብከት አይነት አሁን ደግሞ ሲታይ እንቅልፍ ያስወስዳልን ምነው እንቅልፍ በዛ። የወንድሞቻችንስ ደም አይወቅሰንም ፫ ፰ ወዘሰ ኢይሄሊ ለቤቱ ወይድፍ አዝማዲሁ ውእቱ ክህደ ሃይማኖቶ ወየአኪ ዘምዘኢየአምን ለራሴ ብቻ ተመቸኝ ብሎ ከወገኖቹ ጉዳይ ጋራ አብሮ እየበላ እየጠጣ

# ከ እጉድ

# ፩ኛ ክፍል ሐምሌ

የሚኖረውን ከላይ የተጻፈውን ሳይደርሰው እንዳይቀር ለወገኖቸ አስታውሳለሁ መብልና መጠጥ ተመቸን ብሎ የቀናችቱን ሃይማኖት መለወጥ የተገባ ሥራ አለመሆኑን አስታውሳለሁ።

ይህም በከንቱ አይደለም ወገኖችን ስለወደድኩ ነው እንጅ ቅ. ጳውሎስም ሮሜ ፲፬ ፩ ወለዘኒ ድኩም ሃይማኖቱ ጹርዎ ድኩም ሃይማኖቱ ጽርዎ ወኢትገብሩ ለአድልዎ ብሎ ስለጻፈልን ነው እንጅ ወንድሞቼ ሆይ እኛ ሀገራችን ደማችን መልካችን ፩ድ ይሆንን ሰዎች የኢትዮጵያ ልጆች ሆነን ኢትዮጵያን ለመውረስ የመጣውን ጠላት ምክር በመቀበል እየተታለልን የቀንችቱን ሃይማኖት ኦርቶዶክስ ትታችሁ ወደ ሌላ ቤተ ክርስቲያን ስትሰግዱ የምትኖሩ ኢትዮጵያውን ከላይ እንደተጻፈው ሁሉ በሚሊዮን የሚቆጠረውን ሕዝብ ደም ተካፋይ እንዳትሆን ያበቃው አምላክ አሁንም ለወደፊቱ ልዑል እግዚአብሔር የሚሠራው አይታወቅምና በነገሩ እንድታስብበት አስታውሳለውሁ። ከጳውሎስ ምክር እጨምራለሁ ሮሜ ፲፬ ፳፩ ይሄይስ ዘወትር ሥጋ የሚበላበት ጾም የሌለበት ሃይማኖት እንቅፋት ከመሆን ሥጋን አለመብላት ወይንን አለመጠጣት ይሻላል አለ። ፳፪ ወእምኒ ብከ ሃይማኖተ አጽንዕ ርእስከ በተአምኖ እንዳለ ራስህ በእምነትህ አጥና በፈጣሪህ ሕግ የተሰጠው አእምሮ ራሱን የሚያስነቅፍ ብጹዕ ነው አለ። እንግዲህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችው ሃይማኖት ምን ጉድለት ተገኘበትና ነው ስለጥምቀቱም በዕለተ ዓርብ ከጌታችን ጐን በፈሰሰው ማየ ግቦ መጠመቃችንን አናውቅም ይሆንን። ወይም ደግሞ በዕለተ ሐሙስ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ዘበእንቲአከሙ ይትፈተት ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ዘበእንቲአከሙ ይትከዓው ያለውን ቃል አናውቅምን። ወይም ጾም ስለ አበዛች ዘወትር ሥጋና እንቁላል መብላት አለሌለ ነው ወንድሞቼ ሆይ ይህ መብል አታላይ መሆኑን አውቆ ቅ. ጳውሎስ ማስጠንቀቂያ ጽፎልን ነበርና ሮሜ ፲፬ ፲፯ እስመ ኢኮነ መንግሥተ እግዚአብሔር በመብልዕ ወበመስቴ ዘእንበለ ጽድቅ ወሰላም ወፍሥሐ ዘመንፈስ ቅዱስ እንደዚህ አድርጎ በመብልና በመጠጥ እንዳንሳሳት ነገረን። በመብል እንዳንሳብ ሮሜ ፲፮ ፲፯ አስተበቁዓከሙ አኀዊነ ተዓቅብዎሙ ለእለ ይገብሩ ሀከከ ወያመጽዕ ክህዶ ላዕለ ትምህርትክሙ ዘተማህርክሙ ትገብሩ ወተገሐሥዎሙ አለ። ይህም በተማራችሁት ትምህት ላይ ሸፍጥና ክርክር ለሚአመጡባችሁ እንድትጠበቁ እማልዳችኋለሁ። የተማራችሁትን ትሠሩ ዘንድ ወደነሱ አትቅረቡ ነገር ሽሹ ፲፰ እስመ ለከርሦሙ ይትቀነዩ ወአኮ ለክርስቶስ ወበሂጣነ ነገር ወበተየውሆ ያስሕትዎሙ ለብዙኃን የዋኃን ይህም የሚገዙ ለሆዳቸው እንጅ ለክርስቶስ አይዶለምና። በፖለቲክና በማታለል የዋኃኑን ያታልሏቸዋል

ያሽሚጥጧቸዋል። አለ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚጐድልባት ምኑ ነው ይሆን ሮሜ ፲ ፲፫ እስመ ኵሉ ዘጸውዐ ስመ እግዚአብሔር የሐዩ። (የእግዚአብሔርን ስም የጠራ ሁሉ ይድናል)። ፲፬ ገባእቱ እፎ ይጸውዎ እንዘ ኢየአምኑ ቦቱ

# ኩ ሰኑይ

ወእፎ የአምኑ በዘኢይሰምዑ። ወእፎኑ ዘኢሰብኩ ሎሙ። የእግዚአብሔርን ስም የጠራ ይድናል ብሎ ነበርና ሳይምኑበት እንዴት ይጠሩታል። ስሙን ሲጠሩ ሳይሰሙ እንደምን ያምናሉ ያልሰበኩላቸውንስ እንደምን ይሰማሉ። ፲፭ ወእፎ ይሰብኩ ሎሙ ዘኢትፈነወ ሐዋርያ ኀቤሆሙ። አስተማሪ ወደሰኑ ያልተላከ እንደምን ይሰብኩላቸዋል። ያለውን አስተውሎ መመልከት ነው። ኢትዮጵያ የእግዚአብሔርን ስም መጻሕፍት ሐዲሳትን አታውቅም ለማለት ይሆንን ወይስ አስቀድማ በዘመነ ኦሪት ሕገ ግዝረትንና ሕገ ኦሪትን አክብሮ ሰነበትን አውቃ ከቆየችቱ ሀገር ማነኛውንም

ሕግ ሳታውቅ የኖረችቱ ትሻላለች ይሆንን የጳውሎስን ምክር ቆሮስንቶስ ፯ ፲፬ ወኢትኩኑ ዓፋቃነ ወኢትሑሩ ውስተ አርዑተ እለ ኢየምኑ መኑ ዘአስተርአያ ለጽድቅ ምስለ ኃጢአት ወመኑ ዘይዴምሮ ለብርሃን ምስለ ጽልመት ማስተዋል ነው የተለያያችሁ አትሁኑ ወደማይታመኑ ለመግዛት አትሂዱ ጽድቅን ከኃጢአት የሚአስተካክላት ማነው ጨለማንስ ከብርሃን የሚጨምረው ማነው ፲፫ ወመኑ ዘይኃብሮ ለክርስቶስ ምስለ ቤልሆር ወመኑ ዘይከፍሎሙ ለመሐይምናን ምስለ ንፋቃን። ክርስቶስን ከመንፈሰ ሰይጣን ጋር የሚአስተካክል ማነው። ቀናዎችንና ተጠራጣሪዎችን የሚለያቸው መነው አትለያዩ አትከፋፈሉ እያለ መከረን። መልእክተ ዮሐንስ ቀዳሚተ ፩ ፱ ኵሉ ዘይናፍቅ ወኢይነብር በትእምርቱ ለክርስቶስ ኢሀሎ ፍቅረ እግዚአብሔር ምስሌሁ ወዘሰ ይነብር በትምእቱ ለክርስቶስ በአብ ወበወልድ ሀሎ። የክርስቶስ ዋናው ገንዘቡ ፍቅር ነው። ሰውን እያጣሉና እያጋደሉ የእግዚአብሔር ሰዎች ነን ማለት ከንቱ ነው። ፩ኛ ክርስቶስ ፩ድ ነው። ሃይማኖትም ፩ድ ናት ቤተ ክርስቲያንም ፩ድ ናት ባ፩ድ ሀገር መምህሩ ፩ድ ነው። በሰው ሀገር ሄዶ ላስተምር ማለት ጠብ መፍጠር ማለት ነው። ጠብን የሚፈጥር ሰውን ያሚያጋድል የማን ሊባል ይችላል ይሆን። ይህን የማታለል ሥራ ልዑል እግዚአብሔር የምንቀርብበትን ጾምና ጸሎት ለማተው አትጹሙ እያሉ ጾመኞቹን ያስገድፋሉ። አሁን እናንተስ ወንድሞቼና ወገኖቼ እናንተም ሆዳችሁን ብትወዱ ነው እንጅ በመጻሕፍቱ ውስጥ የጾም ነገር እንደተጻፈ አጥታችሁት አይደለም። አልተገንዘባችሁት እንደሆነ ስለጾም ነገር ከተጻፈው በቀላሉ ከዚህ አስከትየ እጽፋለሁ። ማቴዎስ ፮ ፲፯ ወሶበ ትጸውሙ ኢትኩኑ ከመ መደልዋን ኢትጸመሐየዩ እስመ ያማስኑ ትጸውሙ ገጾሙ ከመ ያስተርእዩ ለዓይነ ሰብዕ። ፫ኛ ሉቃስ ፮ ፳፩ እለይርኅቡ ይእዜ።

፬ኛ ማቴዎስ ፬ ፪ ወጸዊሞ መዋዕለ ፵አ ወ፵አ ለያልየ ወእምድኅረ ዝ ርኅብ ይላል። ልብ ላለው እነዚህ ፬ቱ ይበቃሉ። ለሆድ በማድላት ነው እንጅ አስቀድሞ የአዳምን ሥጋ የለበሰ እኛን መስሎ የምጠበቅባቸውን ሕጎች ለማስተማር ነው። ሲያስተምርም ሠርቶ እያሳየ ነው እንጅ በአፍ በመናገር አይደለም። ለዚሁም ማስረጃ ፩ኛ እንደኛ በ፰ ቀን ሕገ ግዝረትን ፈጸመ። ሉቃስ ፪ ፳፩ ፪ኛ ዘውገ ማዕነቅ ፳፬ ፫ ፳፩ ጌታችን እንደተጠመቀ አይ ፬ኛ ፵ መዓልትና ፵ ሌሊት

# ኪ. ሠሉስ

እንደጾመ ም ፬ ፪ ፫ኛ ርኅራሄንና ቸርነትን ለኛ ሲአስተምር ሕሙማኑን ሁሉ በነፃ እንደፈወሳቸው ሉቃስ ፫ ፲፪ ፲፰። ፮ኛ እኛ ያለዋጋ እንድናስተምር ያለ ዋጋ በሽተኞችን እንድናድን ስንቅ ሳንይዝ በትርም ገንዘብም ሳንይዝ እንድናስተምር እንዳዘዘን ሉቃስ ፱ ፪ ወፈነዎሙ ይሰብኩ መንግሥተ እግዚአብሔር ወይፈውሱ ድውያነ ወኵሎ ሕሙማነ። የእዚአብሔር መንግሥት በተባለው የሮማ

መንግሥት በሽተኞችን ፈውሱ ባለው ደህነኞችን ሕዝቦች የጦር ሠራዊት እያስመጡ ማስፈጀት በትር አትያዙ ባለው ጠመንጃ ገንዘብ አትያዙ ባለው ማነኛውንም ገንዘብ ሁሉ እየያዙ ወደሩቅ አገር ሄዶ መጋደል ሆነ። ያለዋጋ አስተምሩ የተባለው የሰው አገር ገዥ እንሆናለን ማለት ሆነ። ጥምቀት ብቻ ለማታለያ ይቆይ ተባለና ጾም ተሠረዘ መረሠረዙም ስብከቱ እርግጥ ሥጋዊ መሆኑን ለማስረዳት ነው። ፯ኛ ለዚህ ዓለም መንግሥት መገበር የሚገባ መሆኑን ሲያስተምረን ማቴዎስ ፲፯ ፳፬ ፳፫ ፳፮ ፳፯ እይ ፰ኛ ስለቀን ሠራተኞች የሠሩበትን ዋጋ ከቀኑ ሳናሳልፍ እንድንሰጥ እንዳስተማረ ማቴ ፳ ካ፩ እስከ ፲፫ እይ ፱ነኛ ጥንቃቄን ሲአስተምር ማቴ ፳፬ ካ፬ እስከ ፴፬ ፲ኛ ትሕትና ሲአስተምር ንጉሠ ሰማይ ወምድር በመንግሥቱ መሻርና መሾም የሌለበት አምላክ የሐዋርያትን እግር እንዳጠበ ዮሐንስ ፲ ፫ ፬ እስከ ፲ እይ። ፲፩ ፲፫ቱን ሕማማተ መስቀል በትዕግሥት ፈጽሞ አሳየን ጴጥሮስ እንኳ ያ፩ዱን ወታደር ዦሮ ቢቆርጥ ተቆጥቶ ሰይፍህን መልሰህ ከተት እንዳለው ማቴዎስ ፳፮ ፶፩ ፶፪ ፶፫ እይ ፲፪ኛ የሁሉን መጠቅለያ ፍቅርን ፩ድነት ሲነግረን በጣም በተቸገርን ጊዜ አምላካችንን ስንለምን ለየራሳችን ሳይሆን ለሁላችን በመተባበር እንድለምነው ያዘዘን አቡነ ዘበሰማያትን በማቴ ፮ ፱ ፲ ፲፩ ፲፪ ፲፫ እይ ይህ ሁሉ ትእዛዝ እያለ ይህን ሁሉ እረስተን በራሳችን ፈቃድ ሌላ ሕግ አውጥተን

ወንድሞቻችንን ትተን ከባዕድ ጋራ ስንከተል ስንገኝ በሚሊዮን የሚቆጠረው የወንድሞቻችን ደም እንደ ሚፋረደን አይጠረጠርም በገንዘብ እየተታለሉ በረቂቅ ፖለቲክ ለጠላት ምሽግ ሆነው አገራቸውን ለጥፋት ወገናቸውን ለባርነት የሚሙኙ ሰዎች ዋ ዋ ዋ ለስሒት መኑ ይሌብዋ። በነፍስና በሥጋ እንደምን ያለ ዋጋ ያገኙ ይሆን የሮማ ልዑካን በኢትዮጵያውያን የሆኑ ወገኖቼ ሁሉ በመሳት እውነተኛ መስሎ ስለታያቸው ወደ ካቶሊክነት ተመልሰው የሀገራቸውን ቤተ ክርስቲያን ክደው አዲስ ለቆሙችቱ ቤተ ክርስቲያን ሲሰግዱና የኢትዮጵያን የውሥጥ ሚሥጢር ሲያስተላልፉ ይገኛሉ ቤተ ክርስቲያን የምትሠራ በንጹሕ እጅ ነው። ደም ባፈሰሰ ሰው የማይገባ መሆኑን ለመረዳት ቅዱስ ዳዊት እንኳ ለጽላተ ሙሴ ቤተ መቅደስን ለመሥራት ብዙ ነገሮች አዘጋጅቶ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ዜና መዋዕል ፳፰ ፫ ወይቤለኒ እግዚአብሔር አምላክነ ኢትሕንጽ ቤተ ሊተ ከመ ይሰመይ ስመ ዚአየ ላዕሌሁ እስመ ብዕሲ መስተቃትል አንተ ወብዙኃ ድመ ከዓውከ። ብሎ የነገረውን መረዳት ነው። የሰው ደም አፍስሰሃልና አንተ በሠራህው ውስጥ ስሜ ሊአድርበት አይቻልም ብሎ የነገረውን ማሰብ አለብን። የሰው ደም ዋዛ ነገር አይደለም በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ፈጅቶ በሕዝብ ደም በታነጸ ሕንፃ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ አድሮበት በነፍስ በኵል ጥቅም አገኛለሁ ማለት ከንቱ መሆኑን ስለ ቅዱስ ዳዊት የተነገረውን ቃል ማሰብ ነው።

# ካ ረቡዕ

ካህናት ነን የሚሉት የፖለቲክ መሪዎች መሆናቸውን አስቀድሞም ማስረጃዎችን አመልክቻለሁ ለወደፊቱም ይቀጥላል። ፖለቲኩም የኢትዮጵያን መሠረቶች ሁሉ በረቂቅ ጥበብ ለማፍረስ ነው የመሠረቶች ቁጥ። ፩ኛ የኢትዮጵያን የነፃነት ዘመን ቁመት ለማሳጠር። ፪ኛ ፊደሏና ቋንቋዋ ግዛቶቿ በነበሩ አገሮች ላይ በድንጋይ ላይ ብራና ተጽፈው ስለሚገኙ የቀድሞ ክብርዋ ምስክርነት እንዳታስታውቅ ፊደሎቹን ለማጥፋት መጣጣር። ፫ኛ ኢትዮጵያ መንግሥቷ ከተወላጅዋ ወጥቶ የማያውቀውን ባዕድ የገዛት እያስመሰሉ ሽፍታውን ከንጉሥ መቁጠር። ፬ኛ ግዛቶቿ የነበሩትን አገር ገዥ ነበሩ ብሎ መጻፍ። ፭ኛ በጣም ከፍ ያለ ታሪክ ያላቸውን ነገሥታት አብርሃንና አጽብሐን ታሪካቸው በዓለም የታወቀውን ታምራት እስከ ዛሬ የሚሠራላቸውን ጻድቃን ነገሥታት ስማቸው እንደተሰረዘ ሆኖ እነሱ ታልፈው በነሱ ስም ከነሱ ፳፱ነኛው ንጉሥ ዔዛና በመተካቱ። በግዕዝ ቋንቋ ተጽጎ እየታየ በጥንታዊ ሐውልትና በድንጋይ ብራና ተጽፎ የሚገኘውን የሴም

ዘሮች የሳባ ፊደል የሚሉ ስም ስለአወጡለት። በነዚህ በ፮ቱ አርእስቶች መሠረት እያስፋፉ እየጻፉ በዓለም ስለዘሩት ከኢትዮጵያ ወጣቶች የውጭ አገር ቋንቋ የተማሩ ያነን በውጭ አገር ቋንቋ የተጻፈውን ሲአገኙ የተጻፈ እየመሰላቸው ከውጭ አገር ቋንቋ ወደ አማርኛ እየገለበጡ ለወጣቶች ያቀርባሉ። እንደዚህ እየሆነ በሮማ ልዑካን ረቂቅ ተንኮል የኢትዮጵያ ዋናው ታሪክዋ በግዕዝ መጻሕፍት በየገዳማቱ እያለ የሚመለከተው ጠፍቶ በጠላት ፖለቲክ መሪነት ሁሉም ተያይዞ ሲሄድ ስላየው ይህን ነገር ለመቃወም ብሞክር ከሰዎቹ ብዛት የተነሳ የእንጦጦም ጋራ ገፍቸ እጥላለሁ ብሎ እንደመሞከር ያህል የሚቆጠር ሆኖ ታዬኝ ቢታየኝም የኢትዮጵያ ታሪክ በተቻለኝ መጠን በየገዳማቱ እየተዘዋወርኩ በጥብቅ ስለተመለከትኩ ይህን የፖለቲክ ክምር ለመናድ ስጠጋው ትንሽ ሥጋት ሳይኖርብኝ ነው። ስለ መላው ዓለም ታሪክ እነ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ። እነ አውሻኸር። እነ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮ እነ ዮስፉስ። እነ ዜና እስክንድር። ሌሎችም ልዩ ልዩ መጻሕፍቶች በግዕዝ የተጻፉትን መላልሸ ስለ አነበብኩ የኢትዮጵያን መሠረት ከመጻፍቱ መርምሬ የክብርዋንና የቅድምዋን ነገር በተቻለኝ መጠን የዛሬውን ሳይሆን የመላውን የዓለም ታሪክ ተመልክቸ ሳመዛዝነው የኢትዮጵያን ታሪክ በሰፊው የሚገኘው በግዕዝ በተጻፉ መጻሕፍቶች ስለ ሆነ። ካማርኛው ትምርት ከሚሲዮናውያኑ ውስጥ የሚገኘው ታሪክ የወጣቶችን ልብ ሲከፍለው ሲለያየው በታየ ጊዜ ሮማውያኑ ፴፱ ዘመን ያደላደሉት ለፍሬ መድረሱን በተመለከቱ ጊዜ በጣም ስለ ተደሰቱ ከደስታቸውም ብዛት የተነሳ የኢትዮጵያን ታሪክ ጻፍን ብለው ውስጥ ለውስጥ

በፖለቲክ ሲጻፍ የኖረውን የታሪክ ማበላሸት እንደተጠናላቸው ስላወቁ በዚያው በተለመደው ሲያያዝ ፩፻ ዘመን በኖረው በተጠረገው ምንገድ የኢትዮጵያን መሠረት እያፋለሱ ጽፈው አባ ጋስፓሪን የተባሉ የኢጣልያ ተወላጅ የፖለቲክ መምህር ያሳተሙት ይህ ጽሑፍ ማይጨው ላይ ከወረደው ከመርዝ ጢስ የከፋ ስለ ሆነ ማይጨው የወደቀው የመርዝ ጢስ ለጊዜው ያገኛቸውን ሰዎች ጐድቶ ዛሬ በጭራሽ የለም። ይህ ጽሑፍ ግን ለትውልድ እየተላለፈ የሰውን ልቡና እያፈዘዘ ከነፃነት ወደባርነት የሚስብ የወጣቶች ልብ የወድነት አባለ ዘር የሚሰልብ

# ኬ ሐሙስ

ስለሆነ። ከላይ እንደተጻፈው ኢትዮጵያ ከቀድሞ ዠምራ ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች ሀገር ለመሆንዋ የዓለም የታሪክ ጥንታውይኑን መጻሕፍቶች ይመሰክራሉ ይመስክሩ ሲል ኢትዮጵያን የውጭ ሰው እገሌ ገዝቷት ስትቆይ በእገሌ ተመለሰች የሚል ጽሑፍ ካ፩፻ ዘመን በላይ የተጻፈ አለመገኘቱ ነው። እንደ እውነተኛውማ የኢትዮጵያ ነገሥታት ወደ ውጭ ለእርዳታ ይሄዱ እንደነበረ ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል። ይህንም ዓለም ያውቀዋል። ያውቀዋል። ስለ ዋና ዋና መሠረቶች ከላይ በ፮ አርእስቶች ተጽፈው ይገኛሉ።

፩ኛ የኢትዮጵያ የነፃነት ዘመን ቁመት መርዘም።

፪ኛ ፊደሏና ቋንቋዋ ግዛቶችዋ በነበሩ አገሮች በድንጋይ ብራና ተጽፈው እንደሚገኙ

፫ኛ ኢትዮጵያ መንግሥቷ ከተወላጆችዋ ወጥቶ እንደማያውቅ።

፬ኛ በጣም ከፍ ያለ ታሪክ ያላቸው አብርሃንና አጽብሐን።

፮ኛ በግዕዝ ቋንቋ ስለ ተጻፈው ጥንታዊ ፊደል ከላይ እንደተጻፈው በነዚህ በ፮ቱ አርእስቶች ሁሉ ያቃወሰውን መሠረት ያባ ጋስፖሪንን መጽሐፍ ጥያቄና መልስ እየተደረገ ይጻፋልና አንባቢዎች ባለመሰልቸት እንድትመለከቱት ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ በቀይ ቀለም ነው። የኔ ጽሑፍ በጥቁር ቀለም ነው።

ከሥር ዠምሮ በገጽ በገጹ ቁጥር እየተመለከተ ይጻፋል። ያባ ጋስፖሪን ጽሑፍ አጻጻፉ ልዩነት ያለው ስለ ሆነ በቅድሙን ከመጨረሻ ጽፈውት ስለሚገኝ እኔ መሠረቱን መቆቋሚያ ስፈልግ ከመጨረሻው ከሚገኘው ከቅድሙ እዠምረዋለሁ። የገጹ ቁጥር በግዕዝ ፊደል ፲ኛው ተ ነው። ከዚያ መዠመሩን ለአንባቢዎች አስገነዝባለሁ ፩ኛ ጥያቄ ክቡራን አንባቢዎች ይሆ። “እኔ አባ ጋስፓሪን ገብረ ማርያም ከዚህ ቀጥሎ የተጻፈውን ሃሳቤንና ምኞቴን እገልጻለሁ። የአዳም ልጅ ሲባል ከተወለደበት አገሩ ከሚወዳቸው አባቱና እናቱ ተለይቶ በስደት የሚኖርባቸው ግዴታዎች ሁለት ነገሮች ናቸው። ከ፪ቱም ፩ኛው የመለየት ነገር ፩ድ ሰው መንግሥት አዞት ወይም በደለኛ ሆኖ የመለየት በሰው አገርና በስደት የሚኖር ታዛዥ አሽከርና በደለኛ የሆነ ግዞተኛ ሰው ነው። ፪ኛውም መለየት ነገርንም መጽሐፍ ልብ ይኤዝዝ ከመ ንጉሥ እንደሚለው መንፈሳዊ ልቦናው አዞት እንደ አባቶቹ እንደ ሐዋርያት እየዞረ የሚያስተምር ሐዋርያና መናኝ መነኩሴ ወይም ኑሮውንና ሕይወቱን አሻሽሎ ለመኖር ካ፩ድ አገር ወደ አንድ አገር እየዞረ የሚኖር የሰው አገር የሆነ ሰው ነው። ከነዚህም ከቆጠርናቸው የመለየት ግዴታዎች ፩ኛው ግዴታ የኔ መሆን አለበት። እኔ መናኝ መነኵሴ ከመሆኔ የተነሳ የተወለድኩባትን አገሬን የምወዳቸውን አባቴንና እናቴን ትቸ። የአባቶችን የሐዋርያትን ሐዋርያነት ተከትዬ አገር ላገር እየዞርሁ ሳስተምር መንግሥቷ ፍትሐዊ ሕዝቧ ሰላማዊ ከሆነች ኢትዮጵያ ከተባለች ለምለም አገር ደረስሁ” ብለው የጻፉትን ጽሑፍ ውስጠ ሥራውን ያላወቀ ሰው እውነት ይመስላል። ይህም የማታለያ ስብከት ከላይ በየአርእስቶች እንደ ገለጽኩት ካጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ዠምሮ ሮማ ላይ በቆመው ማኀበር እየተራዱ እየመጡ ኢትዮጵያ በኃይል እንደማትቻል ስላወቁ ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ፈሪ ሕጉን አክባሪ እንግዳ ተቀባይ

# ከ ዓርብ

በመሆንዋ ስላወቁ መንፈሳውያን መስለው መስቀልና መጽሐፍ እየያዙ መጥተው ወደ ነገሥታቱ እየቀረቡ ለጠላት ማጥፊያ የጦር መሳሪያ እናስመጣላችኋለንና ሃይማኖታችሁን ለውጡ እያሉ የኢትዮጵያን ነገሥታት ከብዙ ጥፋት እንዳደረሷቸውና ፖለቲኩም እየተገለጸባቸው ከሀገርም የወጡ። ሳይወጡም ቀርተው ሕዝብና ሕዝብ ሲያፋጁ የተገኙ ባደባባይ ፍርድ የተፈጸመባቸው የተደበደቡ አሉ። ደግሞም ያለመንግሥት ፈቃድ ካገር ወደ አገር ሲዘዋወሩ የተገደሉ አሉ የነሱ ሥራ በሰፊው ካ፩ እስከ ፫፻ ገጽ በላይ ተጽፎ ይገኛል እነዚህ የሐዋርያት ተከታዮች እንዳልሆኑ የሚገልጽ ማስረጃ እየተጨመረ ነው በዚያው በተለመደው ምንገድ ያረጀው ሲሞት አዲሱ ከሮማ እየመጣ እየተተካ የስብከት ሥራውን እየቀጠለ ስለሚሄድ ይህን ሥራ እኛ የማናውቀው ስለ መሰላቸው ከመዝናናታቸውም የተነሳ ከላይ የተጻፈውን ሁሉ የማታለያ ስብከት በየረድፉ ሆኖ ተጽፎ ሊነበብ ከቀረበው ከቆጠርናቸው ከ፪ቱ የመለየት ግዴታዎች ፩ኛው የኔ ነው። "እኔም መናኝ መነኵሴ ከመሆኔ የተነሳ የተወለድሁበትን አገሬን ትቼ ያባቶቼን የሐዋርያትን ሐዋርያነት ተከትየ አገር ላገር እየዞርሁ ላስተምር" ብለዋል የመነኵሴ ልብስ በመልበስዎ መጽሐፍና መስቀል በመያዝዎ እርግጥ እንደሮማ ልውካን አባቶችም መሆኑን አልክድዎም እንደ አባቶች ሐዋርያት ያሉ በዚህ መጽሐፍ ከላይ ስማቸውና ታሪካቸው ተዘርዝሮ የሚገኙትን እንደሆነ ጽሑፍዎን አልቃወምም። ግን ያባቶችን የሐዋርያት ተከትየ ስላሉ እርግጥ የክርስቶስን ሐዋርያት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የሚሰብኩትንና ስለ ሮማ መንግሥት የሚሰብኩትን ሐዋርያት ላንባቢ ለይቶ ማስረዳት አለብዎ። ማለት የክርስቶስ የሐዋርያትና የሮማ መንግሥት ሐዋርያት በስምና በልብስ ቢመሳሰሉም በግብር ለየብቻ መሆናቸውን ከላይም በጽሑፍ አስረድቻለሁ አሁንም በመጠኑ አስረዳለሁ የሮማ መንግሥት ሐዋርያት ጾም አትጹሙ ጾም አይጠቅምም ይላሉ። ሐዋርያት ጾም ይጠቅማል ይላሉ ስለ ጾም ማቴዎስ ፮ ፲፯ ወሶበ ትጸውሙ ኢትኩኑ ከመ

ከመልዋን ኢትጸመሐየዩ። ያለውን ማለት ነው። ይህማ ለኦሪታዊው ነው የሚል የተገኘ እንደሆነ ክርስቶስ ካረገ በኋላ መጾምን ሲያሳይ ማ ፱ ፲፫ ወባእቱ ይመጽእ መዋእል አመ ይትነሣእ መርዓዊ እምኔሆሙ ወአሜሃ ይጸውሙ ያለውን ይመልከት። ፪ኛ የክርስቶስ ሐዋርያት የሚሰብኩ ሕዝቦች በሰላም የሚኖሩበትን ከዲያቢሎስ ወጥመድ የሚድኑበትን ነው። ይህም ትእዛዝ ቅዱስ ጴጥሮስ አጥብቆ እንደታዘዘ ዮሐንስ ፳፩ ፲፫ ወይቤሎ ኢየሱስ ረዓይኬ አባግዕየ። እስከ ፫ ጊዜ መላልሶ እንደ ነገረው ማስተዋል ነው። የሮማ ሐዋርያት ግን ጾምንም ሠርዘውታል። የሕዝቡንም በሰላም ከመኖር በጦርነት ወደ ክርስቶስ ከመሄድም ወደ ሰይጣን እንዲሄድ በሕይወት ከሚቆይ ቢሞት ከነምሉ አካሉ ከሚቆይ እጅ እግሩ እንዲጐድል ወገንና ወገኑ ከሚስማማ እንዳይስማማ ወገንና ወገኑ ከሚተማመን እንዳይተማመን ማድረግ ስለሆነ ይህን ለይቶ ማስረዳት አለብዎ። ደግሞ አገር ላገር እየዞርሁ ላስተምር ላሉትም አገር ላገር እየዞሩ ስለሮማ መስበክዎ አይካድም እርግጥ ነው ለእግዚአብሔር መንግሥት ነው የምሰብከው የሚሉ እንደሆነ በእውነት ለክርስቶስ የሚሰብኩ ከሆነስ ፩ኛ ከአውሮፓ ተነሥተው እሥያን አልፈው ኢትዮጵያ ደርሰው መንግሥቷ ፍትሐዊ ሕዝብዋ ሰላማዊ ከሆነች አገር ኢትዮጵያ ደርሼ ብለው እንደጻፉት ፍትሐዊውን

# ኰ ቀዳም

ንጉሥ ከማወክ ሰላማዊውን ሕዝብ ከመበጥበጥ የእሥያን ሕዝብ ከጥምቀት ውጭ ያለውን አልፈው መሠረተ ክርስትያኑን ለመለያየት ከእናንተ ሃይማኖት የኔ ሃይማኖት ከእናንተ ጥምቀት የኔ ጥምቀት ይበልጣል እያሉ ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን ሳይቀር እየሰበኩ የሰላሙን አገር የጠብ የመተማመኑን አገር የመጠራጠር የፍቅሩን አገር የክርክር ማድረግ

ሙያ ሆነና ያቦን ግብር የበላ ይለፈልፋል እንደተባለው ሁሉ ዝም ብሎ ሥራን በመሥራት ፋንታ የኢትዮጵያን ታሪክ እጽፋለሁ ብሎ መፈትፈት የኢትዮጵያን ታሪክ እጽፋለሁ ብሎ ምናኒ ነኝ እየተባለ የሀገር ታሪክ እጽፋለሁ ሲሉ መገኘት አስገራሚ ነው" የሐዋርያትን ሥራ ተከትየ ተቦ ተጻፈና ወደዚያው የኢትዮጵያ መሠረት ለማቃዎስ ያልሆነው ሆነ። የሆነውን አልሆነም በማለት በተለመደው ረቂቅ ፖለቲክ ገብተው ኢትዮጵያ ነፃነቷ ጠፍቶ የማያውቀውን ግዛቶችዋ የነበሩትን አገሮች ገዥ እያደረጉ የኢትዮጵያን መሠረት እያካሰሱ ክብርዋን እየቀነሱ እየተለመደው ሁሉ ለወጣቶች ለማስጠናት በጦርነቱ ጊዜ የተጻፈውን መናኒ መስለው የኢትዮጵያን የታሪክ ሐውልት ሲሰረስሩ መገኘት አይታወቅብኝም ማለትን የተደገፈ ነው። ለመሆኑ ሐዋርያት በዓለም እየዞሩ ሲአስተምሩ የሀገሮችን ነገሥታት ታሪክ ይጽፉ ነበረ ይሆንን ጴጥሮስና ጳውሎስ ስለሮማ መንግሥት የነገሥታቱን ትውልድ ስለምን ሳይጽፉት ቀሩ ጽፈውት ቢሆን በግብረ ሐዋርያት ተጽፎ እናገኘው ነበር። ኢትዮጵያ ያልመጣ የሐዋርያት መጽሐፍ ይኖር ይሆንን ከላይ አባ ጋስፓሪን የክርስቶስን ሐዋርያት ተከታይ ነኝ ለማለት የሚቻላቸው አለመሆኑን አስገነዝባለሁ። ፪ኛ ጥያቄ ወደ ለምለሚቱ ኢትዮጵያ ከደረስሁ ዠምሮ እስካሁን በደገኛው መንግሥት ኢትዮጵያ ይኸውና ይህ የፖለቲክ ጽሑፍ ሮማ ሄዶ በሚነበብበት ጊዜ ነቀፋ እንዳያገኘው የንጉሡ ነገሥቱን ስም እንዳይጠራ ሮማ ላይ ያሉትን አለቆች በመፍራት በደገኛው ንጉሠ ነገሥት ግ. ቀ. ኃ. ሥላሴ በማለት ፋንታ በደገኛው መንግሥተ ኢትዮጵያ ፕሮግራም ተብሎ የተጻፈው ደገኛው ንጉሠ ነገሥት ለማለት የታጸፈው የሞሶሎኒንና የግርማዊ ቀ. ኃ. ሥላሴን የሕይወት ታሪክ ምስክርነቱ ዓለምን ያስደነቀ መሆኑን እንደመዘንጋት ያለ ነው ደግሞ በመንግሥተ ኢትዮጵያ እየተመራሁ ብዙዎቹን ኢትዮጵያ ወጣቶች አስተምሬ ለብዙ ቁምነገር አበቃሁ የተባለው ጽሑፍ በወጣቶች ልብ የመለያያ ፖለቲክ ዘራሁ ብሎ መፎከር ነው መናኒው "እኔም የወጣቶች አባት ሆኘ ተዛምጄ መንግሥተ ኢትዮጵያን አባት ሀገረ ኢትዮጵያን ሀብት ለብሼና ጐርሸ እኖራለሁ። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከትልቁና ከትንሹ ተዛምጄ" የተባለው

እርግጥ የመንፈሳዊ ልብስ ለብሰው በለስላሳ ቃል ከሮማ ሚሲዮን ማኅበር ከሚመጣው ገንዘብ ለመስበኪያ በሥውር ብቅ እየተደረገ ውሥጣዊው ስብከት እየተሠራ ወጣቶችንም አስተምራለሁ እየተባለ ተማሪዎች ሲሰበስቡ በሻይና በዳቦ ሃይማኖታቸውን እየተታለሉ እየተነጠቁ እናያለን ተማሪ ቤት እናቆማለን የሚሉት ይህ እነሱ በማስተማር ላይ የሚገኘው ትምርት ቤት የሃይማኖት መቀሚያ ጫካ ጨለማ ስፍራ ማለት ነው። አልታወቀም በማለት ወጣቶችን እያስተማርኩ ማለት ሃይማኖታቸውን እየቀሙ የተቀሙትን ሰዎች ቁጥር ሮማ በሚገኘው የፖለቲክ ጽሕፈት ቤት የሚአስመዘግቡትን ነው የሮማ ልዑካን ሥራ እየተከታተልኩ ማጥናት ከዠመርኩ

# ወ እሁድ

ልክ ፲፯ ዘመን ነው። የነሱን ሥራ ሙሉውን ብጽፈው ወሰን የለውም አንባቢም ይታክታል። ለጊዜው ይህን በመጠኑ ከገለጽሁ በኋላ ምናልባት ተቃዋሚ ነኝ የሚል ቢገኝ ሥራቸውን እየቀጠልኩ አመጣዋለሁ "መንግሥተ ኢትዮጵያ አባት ሀገረ ኢትዮጵያን እናት አድርጌ ተብሎ የተጻፈው ይህ ቃል እውነት ሆኖ እታመናለሁ ለማለት ታስቦ ይሆንን። የኢትዮጵያን ሀብት ለብሼና ጐርሼ ማለት ይህ እርግጥ ነው ኢትዮጵያ ባትኖር የመነኵሴ ልብስ ለብሰው ስለ ፖለቲክ ሥራ ከሮማ ተቀጥረው ባልመጡ ነበር።

"እኔም ይህን ውለታና እርዳታ መሠረት አድርጌ የዚህን ፍትሐዊውን መንግሥስትና የሰላማዊውን ሕዝብ ውለታ መላሽ ለመሆን በሰፊው መንግሥትና ሐሰትና ቀልድ አልነበረም የኢትዮጵያ መንግሥት ተመኙ"። ተመልካች ከማመስገን በተቀር የነቀፌታ ቃል ተጽፎበት አያውቅም። በሰላማዊው ሕዝብ የታሰበለትን ውለታ ለማግኘት ለጊዜውም ለዚህ ለደጉና ለፍትሐዊው ንጉሥ ጤና ሰጥተህ እድሜውን አርዝምልኝ ሰላማዊ ሕዝቡንም ከለምለሚቱ ኢትዮጵያ ጋር በነፃነት አኑርልኝ እያልሁ በሱባዔ ጸሎቴ ፈጣሪዬን ዘወትር እለምናለሁ ተብሏል። አህን ይህን ያምኑኛል

ብሎ ከመጻፍ ላስታመን በከንቱ አልደከምም ብሎ መተው የተሻለ ነበር። በሀገራችን ተረት አለ ያልወለድኩት ልጅ አባባ ሲለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ ይባላል አሁን አባ ጋስፓሪን የግርማዊ ቀ. ኃ. ሥ. እድሜ መርዘም እግዚአብሔርን እለምናለሁ ማለትን እውነት ነው። ብለን እንቀበለው ይሆንን። ፩ድ ፩ድ ጊዜም ሰውን አታልላለሁ ሲባል ራስን ማስገመት መኖሩን መገንዘብ የተገባ ነበር። ውለታ መላሽ ለመሆኔ ምስክር የሚሆን ነዋሪ ጽሑፍ ለመጻፍ አሰብሁ። ከማሴቤም የተነሳ የዓለም ታሪክ መርማሪዎች የሆኑ አውርፓውያን በታሪክ መጽሐፋቸው ላይ አሳትመው በሥውር አኑረውት ተቀምጦ የነበረ የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥቷን ጥንታዊ ክብርንና ነፃነቷን የሚገልጽ መናኒው መነኰሴ የኢትዮጵያን ውለታ ለመመለስ ያውሮፓ ሊቃውንት ጽፈው ሠውረው አኑረውት የሚገኘውን ለመጻፍ አሰብሁ ተብሎ ምክንያቱ ተሰናድቷል። አስቀድሞ ይህ ሥራ የመነኰሴ አለመሆኑን ማለት ይህ ሥራ ምንኩስናውን የሚቃወም ስለሆነ ነው። የሀገር ታሪክ የፖለቲክ ነገር አለበት ለመነኰሴ ፖለቲክ ምኑ ነበር። አባ ጋስፓሪን ካባቶቻቸው ሲያያዝ በመጣው ፖለቲክ ሥራ ለመቀጠል አባቶቻቸው የኢትዮጵያን መሠረት ለማፍረስ አስበው በረቂቅ ፖለቲክ የኢትዮጵያን ታሪክ ጻፍንላት እያሉ እያበላሹ የጻፉባትን ጽሑፍ። እነሱ ለዓለም ባለታሪኮች በፈረንጅ እየጻፉ ያስተላለፉትን ከሌላ ምንጭ የተገኘ በማስመሰል የዓለም ታሪክ መርማሪዎች የሆኑ አውሮፓውያን በታሪክ መጻፋቸው ሠውረው አኑረውት የነበረ የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥቷን ጥንታዊ ክብርና ነፃነቷ የሚገልጽ ተብሎ የተጻፈው እውነት የመነኰሴ ቃል ትክክለኛ መሆኑንና አለመሆኑን ያባ ጋስፓሪንን ጽሑፍ ከመዠመሪያው ገብቸ በገጹ ቁጥር ሐተታውን ላንባቢዎች እገልጻለሁ ፩ኛ በገጽ ፩ኛ ጥያቄ የገዛ አገሩን ታሪክ ማወቅ ለግድ አስፈላጊ ነው እንበለዚያ ከብዙዎች ሴቶች መኻል እናቱን ለይቶ እንደማያውቅ ልጅ መሆን ነው።

እንደዚህም ማለት ያገሩን ታሪክ የማያውቅ ሰው እናቱን በማያውቅ ይመስላል" ብለዋል ይህ ጽሑፍ እውነትም ታሪክ ነው። እንግዲህ ባባጋስፓሪን አሳብ የኢትዮጵያ

## ዉ. ሰኑይ

ሊቃውንቶች የሀገራቸውን ታሪክ ጽፈው ለመጭው ትውልድ አላስተላለፉም ማለት ነው። ያገሩን ታሪክ ያማያውቅ የናቱን መልክ እንደማያውቅ ሕፃን የተባለ ማነው። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ስንኳንስ በብራና በጥርብ ድንጋይማ እየጻፉ የተውልን ይገኛል። ግን በግራኝ ጦርነት ምክንያት ሮማውያን ለምለም የሆነችቱን አገር ካዩ በኋላ ካረቦችና ከእስላሞች እየተስማሙ የኢትዮጵያን መሠረት ለማጥፋት መድከም ከዠመሩ ፬፻ ዘመን በላይ ስለሆነ። በዚህ ሁሉ ዘመን የሮማ ልዑካን የተባሉ ያባ ጋስፓሪን አባቶች ውስጥ ለውስጥ እየሄዱ በረቂቅ ፖለቲክ እየከፋፈሉ በሚሠሩት ሥራ በጣም ስለ ተዠናኑ እንጅ" ከላይ በ፷፪ ገጽ ባ፩ኛው ጥያቄ ላይ እንደተጻፈው የሐዋርያትን ምንገድ ተከትዬ እየዞርኩ ላስተምር" ብለው ጽፈዋል አስተማርኩ የሚሉት እርግጥ ነው ለሮማው መንግሥት ፕሮፓጋንድ ሠራተኛ ሆነው ለሰው መጉጃ ከቆመው ማኀበር ገንዘብ እያስመጡ በዚያ ገንዘብ ዳቦና ሻይ እያሰናዱ ተማሪ ቤት ከፈትኩ ይሉና ትንሽ ጊዜ ያማርኛን ትምርት ካስቆጠሩ በኋላ የተሰበሰቡትን ወጣቶች ሃይማኖት በዳቦና በሻይ ማስለወጥዎ ይህን ተማሪ ቤት ለሃይማኖት መቀሚያ ጫካ ማበጀትዎ አይካድም። ይህንም ማድረግዎ የኢትዮጵያን ሰዎች ልብ ለማከፋፈልና ወሬ ለመልቀም የሀገሪቱን መውጫና መግቢያ እየሰለሉ ወረቀት ለመጻፍ ከኢትዮጵያውያን ፩ድ ጥፋት ሠርቶ መንግሥቱ ትንሽ ቅጣት ሲቀጣው ያዩ እንደሆነ በቶሎ ጠጋ ልቡን ለማሸፈት ነው። በሕዝቡ ዘንድ የንጉሠ ነገሥቱን ሥራ እያቃለሉ መስበክ በንጉሡ ዘንድ በቀረቡ ጊዜ የሕዝቡን ክፋት እየነገሩ ሕዝቡን እንዲጨንቄን መምከር ይህ ወረቀት ፖለቲክ ለመሥራት ምቹ ሆኖ የሚገኘው በዚሁ መናኒ መስሎ አገር ላገር እየዞሩ አስተማሪ በመምሰል ስለሆነ። የዚህ ፖለቲክ ሥራ በተገለበጠ በብዙ ቀኑ አልታወቀም መስሏቸው አባ ጋስፓሪን መናኒ ሆኘ አስተምራለሁ እያሉ የስብከት ጽሑፋቸውን በከንቱ ይዘራሉ። አስተማሪ የመሰለውን ስብከት ዓለም አውቆታል ማለቴ ባ፩ድ የእስፓኛ ባለ መርከብ ሹምና የጃፓን

ሹም መካከል ስለ ደረሰው ነገር ጃፓን እንደምን ሠለጠነች በሚባለው ባቶ ከበደ ሚካኤል መጽሐፍ ባ፲፰ና ባ፲፱ኛ ገጽ ተጽፎ እንደሚለው ፩ድ የእስፖኝ መርከብ ተበላሽቶ በችግር ሳለ ጃፓኖች አግኝተውት መርከብ በተበላሸ ጊዜ የሚሠራበት ቦታ አለና ብለው ወደ ጠረፋቸው ወሰዱትና ወደ ወደባቸው ካደረሱት በኋላ ባገራቸው የተለመደ ሆኖ የሚኖር እንደ ሕግ መኖሩንና በሱ መሠረት ተበላሽቶ የተገኘ መርከብ ሁሉ ላገኙት ሰዎች እንዲሰጥ የተፈቀደ መሆኑን ነግረውት በውስጡ የሚገኘውን ሁሉ ዘርፈው ተካፈሉት የእስፖኙም የመርከብ ሹም ያገሩ ዋና ባለሥልጣን ለነበረው ለጃፓን ሹም አቤቱታውን ቢአሰማ መስፍኑ የዘረፉት ሰዎች የሚገባ ሥራ ነው ብሎ ስለመለሰለት በዚሁ ጊዜ የመርከቡ ሹም በጣም ተናደደና ጃፓኖች ለጊዜው አገራቸው ሆኖ ይህን የግፍ ሥራ ቢሠሩ የእስፓኛ መንግሥት ደግሞ በኃይለኛነቱና በብልጽግና ከፍ ያለ ገናና መሆኑን ሊገልጥላቸው ፈልጎ የዓለም ካርታ አወጣና በእስፓኝ መንግሥት ግዛት ውስጥ የሚገኙትን አገሮች በካርታው ላይ አሳያቸው። ጃፓኖችም በጣም ተደንቀው እስፓኛ እነዚህን ሁሉ አገሮች እንዴት አድርጋ ለመያዝ ቻለች ሲሉ ቢጠይቁት እሱ ሲመሰስ መዠመሪያ ቄሶች ትልካለች በኋላም ካገሩ ተወላጆች ብዙዎች ሲጠምቁ ሰዎች ባገራቸው መንግሥት ላይ እንዲነሱ

# ዊ ሠሉስ

አድርጋ እነሱን የሚረዱ ወታደሮች ትልክና በዚህ ምክንያት አኳኋን አገራቸውን ትይዛለች ብሎ መለሰችላቸው የእስፓኛ መርከብ ሹም ይህን ሲነጋገር የሰሙ የጃፓን ተወላጆች ደብዳቤ ጽፈው በዚያ ጊዜ ባለሥልጣን ለነበረው ሂዬዮሺ ለሚባለው መስፍን እንዲያውቀው ስላደረጉ መስፍኑ ወዲያውኑ ብገሩ ውስጥ ያሉትን ነጮችና ክርስቲያኖች እንዲጠፉ ዓዋጅ አስነገረ ናጋሳኪ በምትባለው ከተማ ዙሪያ ብቻ ፳፯ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ። ከዚህ በኋላ የክርስቲያን ሃይማኖት ከጃፓን አገር ጨርሶ ተነቀለ። ነጮችም ወደ ጃፓን አገር እንዳይገቡ በሞት ቅጣት ተከለከሉ ይላል። ይህ ነገር በኢትዮጵያም ላይ ነገሥታቶችዋ ይህን የመሰለ ዓዋጅ በየጊዜው እንደታወጀ ታሪክ ይነግረናል አሁን ይህን ያስታወስኩበት ይህን መንፈሳዊ እየመሰሉ ስብከትን አስቀድሞ በሠሩት ሰዎች ላይ የተገለጸ መሆኑን አባ ጋስፓሪን ገና አልሰሙትም ስለመሰሉኝ እንድገልጽላቸው በማለት ነው። ባጼ ምኒልክ ጊዜ በጦርነት ውስጥ ገብተው ያዋጉ ማንና ማንን ነው ነጮች ብቻቸውን ኢትዮጵያውያንን በኃይል እንችላለን ብለው ፲ሩን ኢትዮጵያውያን ፩ ነጮች ብቻቸውን እንችላለን ብለው ይሞክሩት ይሆንን ፪ኛስ በግርማዊ ቀ. አጼ ኃ. ሥ. በሽ፱፻፳፰ ዓ. በተደረገው የአጥቂና የግፍ ጦርነት ውስጥ እየተዋጋ ማንና ማነው። ለዚህስ ሁሉ መሪ ወረቀትችን አስተላላፊና ውስጥ ለውስጥ በብር ጦር የሰዎችን ልብ እየወጋ የሚጥል ማነው የዚህ ሁሉ መዲና ጫካ የነሱ ተማሪ ቤት መሆኑን እናውቅም መስሏቸው አባ ጋስፓሪን በጽሑፍ ያስታውሱናል። ይህ ጽሑፍ ከመዠመሪያው እንደመቅድም መሳይ ሆኖ ቀላል ሐተታ በ፪ተኛው ገጽ ከተጻፈ በኋላ ፍሬ ነገሩን በ፫ኛው ገጽ በመጽሐፉ ውስጥ ተዘርዝረው የሚገኙትን ፲፪ቱን ክፍሎች ይዘረዝራል የ፩ኛ ክፍል" ኢትዮጵያ በግብጻውያን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንዴት እንደሆነች የሚናገር ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ስረ መሠረት ከወዴት እንደመጣች የሚአስረዳ። አጭር ታሪክ።

"፪ኛ ክፍል አግዓዝያን ከነርሱ የሚወርዱባቸው የሳብውያን ፫ኛ ክፍል ከታሪክ ክፍል የነበረ የድንጊያና ከነሐስ ወይም የመዳብ ጊዜ ከቀድሞዎቹ ግብጻውያን ጋር የነበረው የኢትዮጵያውያን ግንኙነት ፬ኛ ክፍል የሴም ዘሮች ሳባውያን ከጥንት አገራቸው ከደቡባዊ ዓረብ ወደ ኢትዮጵያ ቀስ ቀስ እያሉ እንደ ተሻገሩ የሚናገር። ፭ኛ ክፍል የንግሥተ ሳባ አጭር ታሪክ ብዙ እስራኤላውያን ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ፮ኛ ክፍል የአክሡም መንግሥት ጥንታዊ ታሪክ ስለመጽናናቱና መስፋፋቱ የሚናገር

፯ኛ ክፍል በኢትዮጵያ ሃይማኖት እንደገባ።

፰ኛ ክፍል የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ዘመን።

፱ነኛ ክፍል የዘኄ መንግሥት ዘርና ተርታ።

፲ኛ ክፍል የሰሎሞን ዘር መታደሱና ተከታዮቹ ነገሥታት።

፲፩ኛ ክፍል ያሁን ጊዜ ታሪክ ከዳግማዊ ምኒልክ ይዠምራል።

፲፪ኛ ክፍል የኢትዮጵያ ነገሥታት የትውልዳቸው ተርታ ከጥፋት ውኃ አንሥቶ እስከ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ. ሥ. ን. ዘኢትዮጵያ ድረስ።ልብ ማድረግ የኢትዮጵያ ነገሥታት የትውልዳቸውን ረዥም ተርታ በማንበብ እንደሚታወቅ ሁሉ። በዓለም ላይ ካለው የነገሥታት ትውልድ ሁሉ የሚበልጥ ረዥም ተራ በኢትዮጵያ አለ።

## ፬ ረቡዕ

እንደዚህም ማለት ከጊዜአችን አንሥቶ እስከ ጥፋት ውኃ የሚደርስ የነገሥታት ተርታ አለኝ ብሎ ሊመካ የሚችል ፩ድም ዘር የለም ማለት ነው። በታሪክ ላይ የቀድሞዎቹ ግብጻውያንና ባቢሎናውያን የነገሥታት ዘር እናውቀዋለን። ይሁን እንጅ ዛሬ ፋናቸው እንኳን የለም። ከሴምም ከመዠመሪያ ዘሩ የሚአወርደው ክብር ያለው የኢትዮጵያ ዘረ መንግሥት ግን ሳያቋርጥ እስከኛ ደርሷል። እንዲሁም ለወደፊቱ በነገሥታቱ ጥበብና ሁሉን በሚችለው በእግዚአብሔር እርዳታ በአገሩ የታሪክ ትልቅ መጽሐፍ ላይ የተከበሩ ስብሐታውያን ገጾች ለመጻፍ ያብቃው እያልን ምኞታችንን እንገልጻለን ብለዋል"። ይህ ሁሉ ባልቸገራቸው ገብተው ነው። ከሴም የሚወርደው ትውልድ ማድረግ በካም ቤት ጠፍ ሆኖ ማለት ነው። የካም ዘር ስንኳንስ በክፍለ ሀገሩ በአፍሪካ ይቅርና በተሰጠው ክፍል አልፎ በሴም አገር በእሥያ መንግሥትን የመሠረተ የካም ዘር መሆኑን ዘንግተውታል መሰለኝ ከሴም ዘሮች ታላቁ ባለቃል ኪዳን ሃብታም አብርሃም ነው። በአብርሃም ዘመን የኢየሩሳሌም ዙሪያ አውራጃዎች በማን እጅ እንደነበሩ ሚስቱን የሚቀርብበት ቦታ አጥቶ ከካም ዘሮች መቃብር መሬት ገዝቶ ሚስቱን እንደቀበረ መጻሕቱ ይነግሩናል። ይህንም ለመረዳት የፈለገ ቢኖር ኦሪት ዘፍጥረት ፳፫ ፬ ነገድ ወፈላሲ አነ ምስሌሆሙ ሀቡኑ ሊተ ከመ እኀየጥ መቃብረ ክማክሙ ወእቅብር በድንየ። ያለውን ይመልከት አብርሃምን ከካራን ከተወለደበትና ካደገበት ያወጣው በተወለደ በ፸፭ ዘመኑ ነው። አብርሃም ከካራን ከወጣ ዠምሮ ፳ኤል ከግብጽ እስቲወጡ ድረስ የቆየው ፬፻፴ ነው። ኦሪት ዘፀዓት ፲፪ ወኀድረቶሙ ለደቂቀ ፳ ኤል ዘነበሩ በምድረ ግብጽ ወምድረ ከነዓን እሙንቱ ወአበዊሆሙ ፬፻ ወ፴ ዓመተ ይላል። ፪ኛ ጳውሎስም ወደገላትያ በጻፈው መ. ፫ ፲፯ እብል እንከ ዝንቱ ኪዳን ጽኑዕ ዘእምኀበ እግዚአብሔር ወእምድኅሬሁ በ፬፻ ወ፴ ክረምት መጽአት ኦሪት ይላል። ዝንቱ ኪዳን ጽኑዕ ያለው አብርሃምን ከካራን ና ውጣ ርስትህን እሰጥሀለሁ ካለው በኋላ እስከ ፬፻፴ ዘመን በላይ አቆይቶ የከንዓንን ዘሮች ነቅሎ ከርሥታቸው አገባቸው። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ዝንቱ ኪዳን ጽኑዕ ያለው ይህን ተመልክቶ ነው ጌታችንም አብርሃምን ከካራን አምጥቶ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ ያስቀመጠው አስቀድሞ ኖኅ ለ፫ቱ ልጆች ዓለምን ሲያካፍል ዕሥያን ለሴም ዕጣ ደርሶት የካም ልጅ ከነዓን ያባቱን ዕጣ አፍሪካ አልሄድም ብሎ የሴምን ዕጣ ክፍል ይዞ ስለኖረ ከሕግ ውጭ በመሆኑ እግዚአብሔር በቀላሉ የማይረሳ ስለሆነ አብርሃምን ፳፩ኛውን ትውልድና ና አገርህ ግባ ብሎ ከካራን አመጣው። ከኖኅ እስከ አብርሃም በትውልድ ፲፩ ነው። በዘመንም ከፍጥረተ ዓለም እስከ ኖኅ ዕረፍት ፪ሺ ፯፻፯ ላይ ነው። ኖኅ ዓለምን ለ፫ት ልጆቱ ያካፈለ ገና በሕይወቱ ሳለ ነው። ፯ቱን ዘመኖች ስንቀንስ ፪ሺ ፯፻ ዘመን ሆነ። እንግዲህ ከነዓን ያለ ፈቃድ በግድ በቅሚያ የኢየሩሳሌምን ዙሪያ የሚቆጠርበት ዘመን ከ፪ሺ ፯፻ ዘመን ዠምሮ ስለሆነ ከኖኅ ዕረፍት እስከ ባቢሊን ግምብ መፍረስ ፪፻፹፯ ዘመኑ ነው ከባቢሊን ግምብ መፍረስ እስከ ልደተ አብርሃም ፫፻፩ ዘመን ነው ሲደመር ፲፻፩ ይሆናል። ከልደተ አብርሃም እስከ ሙሴ ፬፻፹፩ ዘመን ነው። ድምር ፭ሺ፩፻፹፪ ይሆናል። የሙሴ ዘመን ፻፳ ድምር ፭ሺ፪፻፹፪ ዘመን ነው። የከነዓን ዘሮች በኢየሩሳሌም አውራጃዎች የቆዩበት ዘመን ይኸው ፭ሺ፪፻፹፪ ዘመን ማለት ነው። ይህን

# ዌ ሐሙስ

ያህል ዘመን በኢየሩሳሌም አውራጃዎች እክለ ፴፫ት መንግሥት አቋቁመውበት ሳለ ምንም ቢሆን ከሕግ ውጭ የተሠራ ነገር ጸንቶ ለመኖር የማይቻል ስለሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ እንደጻፈው እብል እንከ ዝንቱ ኪዳን ጽኑዕ ባለው መሠረት ይህን ያህል ዘመን የኖሩቱን የከነዓን ዘሮች አስለቅቀው ባባታቸው ርስት እንዲገቡ አደረገ ይህን ታሪክ የሮማ ልዑካን ለመረዳት ችለው ቢሆን ይህን ያህል ድካም የሮማ ልዑካን ለመረዳት ችለው ቢሆን ይህን ያህል ድካም ባላገኛቸው ነበር በታሪክ  ውስጥ ከእስያ ስመ ጥር ሆኖ

የሚገኘው ባቢሎን ነው። ባቢሎንን ያቀናና የመሠረተ የካም የልጅ ልጅ የኩሳ ልጅ ናምሩድ መሆኑን ገና አላወቁትም በዕሥያ የሚገኘው አብዛኛው ሕዝብ የካም ዘር መሆኑን በመዘንጋት ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንደሚባለው ተረት የሴም ዘሮች የካም ዘሮች ወግተው አገራቸውን ወሰዱ እያሉ በጽሑፍ ፖለቲክ መግዛት ምናልባት ተቃዋሚ የመጣ እንደሆነ መልስ መስጠት አለበትና ይህ የውሸት ጐርፍ እውነት ጥያቄ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ፩ዱት ጠርሙስ ውኃ ይገኛል አይመስለኝም። የዓለም ታሪክ በመጻሕፍቱ ውስጥ አለ። ከልደተ ክርስቶስ በፊት በጻፉ ሊቃውንቶችም ተጽፈው ሁሉም በግዕዝ ተገልብጠው ይገኛሉ። የፋርስና የሜዶን ነገሥታት ታሪክ ከነዘመናቸው ተለይቶ ተጽፎ ባይገኝ ባባ ጋስፓሪን የሐሰት ስብከት የኢትዮጵያ ታሪክ ተደምስሶ መቅረቱ ነበር። አሁንም ያባ ጋስፓሪንን ሐተታ ምርመራ እንቀጥል "በገጽ ፬ ፩ኛ ክፍል ፩ኛ ጥያቄ አባ ጋስፓሪን ገብረ ማርያም። ኢትዮጵያ በግብጻውያንና በጽርያች በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንዴት እንደ ሆነች የሚናገር። ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ሥረ መሠረት ከወዴት እንደመጣ የሚአስረዳ ይላል።"

ለአንባቢዎች ከወዴት እንደመጣ ፩ድ ነገር አለ አሁን አባ ጋስፓሪን በዚህ ጽሑፍ ይህን ያህል የደከሙበት ምክንያቱ የኢትዮጵያ ነዋሪ ባላባት ሆኖ ለመቈጠር ይሆንን ወይስ ዋጋቸውን ከክርስቶስ ለመቀበል ባዦማመራታቸው አኳኋን ነዋሪ ባለርስት ሆኖ በመቆጠር ኢትዮጵያን ተጠቀሚ ሲላት አባ  ጋስፓሪንን ከሮማ አመጣለት ይነገርማል። አሁን እኔ ላባ ጋስፓሪን የማቀርባቸው ጥያቄዎች ፩ኛ በቅዱሳት እንደመጣ የሚአስረዳ ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል ሥረ መሠረት ከወዴት እንደመጣ የሚአስረዳ ብለው ውና አርስት አድርገው ጽፈዋል ይህንም አሳብ ስመለከተው ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ከጽርአውያን የመጣ ነው። ማለት ይመስለኛል ምክንያቱም እርስዎ እንደሚአውቁት ወሬ መጻሕፍተ ብሉያትን በጥሊሞስ ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ አስገልብጧቸው ስለነበረ። የጽርዕ ሊቃውንቶች ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ ሲገለብጡ ጽርዓውያን ኢትዮጵያ ብለው ጻፉ ማለትዎ ይመስለኛል ለዚሁም ድጋፍ የሚሆንዎ ከዚያ በምን ትጠራ ነበር የሚል ጥያቄ ቢመጣ መልስ የሚሆንዎ ያገኙሉን ጐረቤቶችዋ ግብጽ ፑንፐ ቶኔቶር ኩሽ ይሏት ነበር ብለው ከ፸ ሊቃውንት በፊት ኢትዮጵያ የሚባል ስም እንደሌለ አስታውቀው ጨርሰው ዘግተው ጽፈዋል። ጠቅላላ አሳብዎ ይህ መሆኑን ላንባቢዎች እየገለጽሁና እያስረዳሁ ነው። ማለት ማስረጃ ያለው አፍራሽ እስካመጣ ድረስ ከማምጣቴ በፊት አሳብዎን ማጥናቴን መግለጽ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በግሪኮች ዘንድ ኢትዮጵያ የሚል ቃል ብቻ እናገኛለን ከእርሱም ኢትዮጵያዊ ይመጣል ግሪኮች የሚአመለከቱት

# ው ዓርብ

ከግብጽ ደቡብ የሚገኘውን አገር ሁሉ ነው። ይላል" ይህ ደግሞ ፩ድ ነገር ይጨምራል። ከግሪኮች ኢትዮጵያ የሚል ቃል እናገኛለን ከዚያው ኢትዮጵያዊ የሚል በዚህ ስም የሚአመለከቱበት ከግብጽ ደቡብ የሚገኘውን አገር ነው። እንደዚህ ኢትዮጵያ የሚለውን ቃል በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የጻፉ ጽርዓውያን ናቸው። በቅዱስ መጽሐፍም ተመልክቶ የሚገኘው ኢትዮጵያ የሚባለው ከግብጽ ደቡብ የሚገኘው አገር ነው እንጅ ይህ አሁን ያለንበትና አክሡም ዋናይቱ ከተማ ኢትዮጵያ አይደለችም ማለትዎ ነው። ለዚሁም አሳብዎ ድጋፍ ሆኖ የሚገልጽ ለወደፊት እናገኛለን። አሁን

ለዚሁ ተቃዋሚ የሆነ መልሴን አቀርባለሁ። ፩ኛ ወዳጄ አባ ጋስፓሪን ሆይ እንደርስዎ ያለ መናኒ እንደዚህ ባለ ነገር ውስጥ መግባት አይገባውም ነበር። ልብሰ ምንኵስና የለበሱበትን ነገር ስለማላጣው በጣም አልፈርድብዎትም ሆኖም ከጥልቅ ታሪክ ውስጥ ከገቡ ባመጡት ነገር መጠየቅ የሚቀርልዎ አይደለምና ፸ ሊቃውንት ኢትዮጵያ እያሉ ተረጐሙ ያሉበት ዘመን ከክርስቶስ በፊት እስክንድር በ፫፻፱ ዓ. ዓለም ላይ ነገሡ። እስክንድር ከሞተ በኋላ የእስክንድርን

አገር ላ፬ት እንደተከፋፈሉት ፩ደኛውን ሰልፎሮስ የተባለው ባቢሎንን ፪ኛ አቅጥምያሮስ የተባለው እንጾኪያን ፫ኛው አሳጥያኮስ በአፊሶን ጽርዕ ፬ኛው ምያሮስ የተባለው አንጾኪያን ፫ኛው አሳጥያኮስ በአፊሶን ጽርዕ ፬ኛው በጥሊሞስ ግብፅን የበጥሊሞስ ዘሮች ጽርዓውያን እስከ ፪፻፫ ዘመን ነው ግብፅን የገዙ። በዚህ አስተያየት ፸ ሊቃውንት መጻፍትን የተረጐመበትን ዘመን በግምት ከክርስቶስ በፊት ከ፪፻፹ ዓ.ም በላይ እናድርገው እንደዚህ ሲሆን ዓለም በተፈጠረ ፭ሺ ፪፻፳ ዓመተ ዓለም ላይ መሆኑ ማለት ነው። እንግዴህ በዚህ በተቆጠረው ዘመን ሁሉ መሆኑ ማለት ነው። እንግዴህ በዚህ በተቆጠረው ዘመን ሁሉ ጽሑፍ ኢትዮጵያ የሚል አይገኝም በእብራይስጡም መጻሕፍተ ብሉያት ውስጥ ኢትዮጵያ የሚል ጽሑፍ አይገኝም ማለትዎ ነው። ይህን አሳብዎን ገልጬና አፍታትቸ ሳቀርብልዎ መልሱን በቀጥታ ማቅረብ አለብዎ። ማለት መልሱንማ ከጽሑፍዎ ላይ ወስጀዋለሁ እንዲገነዘቡት ላንባቢዎች እንዲገባቸው ማለት ነው። ለጽሑፍዎ ተቃዋሚዎች የሚሆኑ ሁለት አርእስቶች አሉ። ፩ኛው በአፍሪካ ላይ በየመሬቱና በየወንዞቹ የጥንታውያን አባቶች ስም በየመቃብራቸውም ላይ ስማቸው በጽሑፍም በቃልም ይገኛል። ስለዚህ በሀገራችን ላይ ብዙ ጽሑፎችና ማስረጃዎች ኢትዮጲስ ሲሉ ይገኛሉ። ይህም የሆነበት ምልክት የዘመን ርቀት አለው ጽርዓውያን ከፍ ከፍ ማለት የዠመሩበት እንደሚታወቀው ከእስክንድር ዘመን በኋላ ነው። ከፍ ቢልም በፋርሶች ዘመን ዠምሮ ከክርስቶስ በፊት ቢበዛ ፬፻፺ ዘመን በኋላ ነው ታላቁ የግሪክ ፈላስፋ ሄሮዶቱስ ግብጽ ደርሶ ማነኛውንም ታሪክ እየመረመረና እየጻፈው እስከ መርዌ ከደረሰ በኋላ አስደናቂውን የዐባይን ምንጭ ሳያይ እንደተመለሰ የጻፈውን መጽሐፉን መመልከት ነው። ኢትዮጲስ የሚባለው ስም በካም ቤት የተዠመረ ከ፫ኛና ካ፬ኛ ትውልድ ዠምሮ እንደሆነ ታሪክ ይነግረናል። አገራችን ባ፬ት ስሞች ትጠራለች ፩ኛ አፍሪካ ጠቅላላዋ ካም ፪ኛ ኩሳ ፫ኛ ሳባ ፬ኛ ኢትዮጲስ። በነዚህም ስም መጠራትዋ ነግሡውበት ስለ ነበሩ ነው እንጅ በከንቱ አይደለም። ኢትዮጲስ ነግሦበት የነበረው ዘመን ከክርስቶስ በፊት ከ፪ሺ፷፪ ዘመን ላይ ይሆናል በመካከሉ ይህን ያህል የዘመን ምልክት ይዞ ሲያያዝ የመጣውን ታላቁ ነቢይ ሙሴ በመንፈስ ቅዱስ ፫ቱን ብሔረ ኦሪት ሲጽፍ ኢትዮጲስ በሚባለው ንጉሥ ኢትዮጵያ እያለ

# ዎ ቀዳም

የጻፈውን በመሠረዝ ከዚያም ወዲህ የተነሡ ነቢያት ሁሉ ኢትዮጵያ እያሉ እንደጻፉ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ፸ ሊቃውንት መጻሕፍቱን ቃል በቃል ገለበጡ እንጅ በራሳቸው ፈቃድ ጨመሩ ወይም አጐደሉ ማለት ከንቱ ምክንያት ነው። አባ ጋስፓሪን ይህን ሁሉ በከንቱ ደከሙ እንጅ መጻሕፍቱን በጣም አስተውለዋቸዋው ቢሆን ከእብራይስጡ አብረው የመጡትን ጽሑፎች ለማግኘት በቻሉ ነበር። ግን ብዙ ሥራ ያለባቸው ስለ ሆነ ወደ ሥር ገብተው ምሥጢሩን ለማየት ሳይችሉ ቀሩና ከሮማ ተልከው የመጡበትን ገለባ ነገር ይዘረዝራሉ። ተመልክተውት ቢሆንማ ኢትዮጲስ ወይም ኢትዮጵ በሚባለው ስምዋ ላይ ያ የሚባለው ፊደል ተጨምሮ ኢትዮጵያ የተባለች። የ እብራይስጡ ፊደል ቁጥር ፲ረኛ ስለሆነ ያ የአምላክ ስም እሱም የ፲ ቃላት መጠቅለያ ስለሆነ በነቢያትም ቃል እንደሚያስረዳው የእግዚአብሔር አገር ናት ሲሉ የ፸ኤል ሊቃውንት የአምላክን ስም ያ; ን ጨመረው ኢትዮጵያ አሏት። ይህም ጸንቶ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ በዓለም ቅዱስ መጽሐፍ ላይ ይገኛል። በኢትዮጵያ መጻሕፍት በግዕዝ ውሥጥ ከእብራይስጥ የመጡ ቃላት እነ ኤሎሄ እነ አዶናይ እነጸባዖት። ሚካእል። ገብርኤል ሩፋኤል። ሱራፌል ኪሩቤል። እነዚህ ይበቃሉ። እንግዴህ እኒህ በእብራይስጡ የሌሉ ናቸው ይሆንን። ከላይም የን የአምላክ ስም ነው ያልኩትን

ለማቃለል የፈለጉ እንደሆነ የፊደሉንም ቁጥር ለማመን እንዲችሉ ማቴዎስ ፳ ፲፰ አማን እብለክሙ እስከ የኃልፍ ሰማይ ወምድር የውጣ እንተ አሐቲ ቅርጸታ። ያለውን አመጣለሁ። ሐተታውም

እንዲህ ነው። አሐቲ ቅርጸታ ያለው በግዕዝ ፊደል እዝል ቅጥል የሌላት በቀጥታ የቆመች መሆንዋን የውጣ ያለው የ; በእብራይስጥ ፲ር ቁጥር ስለሆነ ይህን ሲአስረዳ ነው ፲ቱ ቃላትን አይደለም የሚሉ እንደሆነ ፲፱ ዝኬ ፈትሐ እምእላ ትእዛዛት አሐተ ያለውን ይመልከቱ። ከላይም እስከ የኃልፍ ሰማይ ወምድር ያለው ካ፲ቱ ቃላት ፩ዲቱ ቃል ከምትጐድል ሰማይና ምድር ቢያልፉ ይሻላል ማለቱ ነው። ይህንም ለመረዳት ሉቃስ ፲፮ ፲፯ ወባሕቱ ይቀልል ሰማይ ወምድር ይኅልፍ እምትደቅ አሐቲ ቃል እምኦሪት። ያለውን ስንመለከት እንደዚያው ማለት ፲ቱ ቃላትን ካ፲ቱ ቃላትም ፩ዲቱ ከምትጐድል ሰማይና ምድር ቢያልፉ ይሻላል ያለው ፲ቱ ቃላት ከታወቁ ፩ኛ እንደ ሮማ ነገሥታት ለጣዖት እየሰገዱ ለልዑል እግዚአብሔር አንሰግድም በማለት ጴጥሮስንና ጳውሎስን ለመግደል ባልደረሰም ነበር። ፲ቱ ቃላት ከታወቁ ባጼ ሱስንዮስ አባ አልፎንሱ ከጥንት ዝምረው ሕገ ግዝረትንና አክብሮ ሰንበትን ይዘው ቆይተው በዘመነ ሐዲስም ሕገ ጥምቀትንም ተቀብለው በሰላም የሚኖሩትን ሕዝቦች ሰንበትን አታክብሩ እያለ ባላስፈጃቸውም ነበር ፲ቱ ቃላት ከታወቁ በኦሪት ዘፀአት ፳ ፲፫ ኢትቅትል ያለውን ፲፬ ኢትዘሙ ያለውን ፲፭ ኢትሥርቅ ያለውን ፲፮ ኢትኩን ሰምዓ በሐሰት ያለውን ፲፯ ኢትፍቱ። ብዕሲተ ካልዕከ ያለውን ወኢትፍቱ ቤቶ ለካልዕከ ወኢገራኅቶ ወኢገብሮ ወኢዓመቶ ወኢላህም ወኢብራዕይሁ ወኢእክሎ በውስተ እንስሳሁ ዘአጥረየ አጥርዮ ቢጽከ። ያለው ሁሉ ይፈጸም ነበር። ይህን ሁሉ የጌታችንን ቃል ጥሰው የመነኵሴ ልብስ ለብሰው በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ደም አፍሰው የኢትዮጵያን መሬት በግፍና በኃይል ወርሰው የኢትዮጵያ ዋና ሰባኪዎች ሆኑና የኢትዮጵያን ስም ያወጡላት ጽርዓውያን ናቸው ብለው የሐሰት ስብከት ስለ ኢትዮጵያ

## ዐ እጐድ

ትርጓሜ በፊደሉ ቁጥር ትርጓሜን ስንከተል ወደ ፲ቱ ቃላት ወስደንና አሁን ወደ ኢትዮጵያ እንመለስ። አባ ጋስፓሪን እንዳባቶቻቸው ሥራ ከኢትዮጵያ ወደ ሮማ ከሮማ ወደ ኢትዮጵያ የሚመላለሰው ደብዳቤ ስለበዛባቸው መጻሕፍት ብሉያት ባይመለከቷቸው ነው እንጅ የኢትዮጵያ መጻሕፍተ ብሉያት የመጡ አስቀድሞ ገና የሮማ መንግሥት ሣይመሠረት ነው። መጻሕፍቱን በሰፊው ተመልክተዋቸው ቢሆን ከእብራይስጡ የተመለሱ መሆናቸን ይገነዘቡ ነበር። ከላይ እንዳመለከትሁት ኢትዮጵያን አዜብ ሲላት ይገኛል ሳባ ሲላት ይገኛል። ኩሳ ሲላት ይገኛል። በኢትዮጲስ ኢትዮጵያ ያ ስመ እግዚአብሔር ነው ያልኩት እንግዳ አይደለም የኢትዮጵያ ሊቃውንት የሙሴን ጽላት መሠረት በማድረግ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው መሥዋዕት በሚሰውበት ቦታ ለአምላካቸው ስግደትና ምስጋና ለመስጠት በጽላቱ ላይ የውጣ የሚለው ስም ይጽፉበታል ይህም ከላይ እንደተጻፈው የ በእብራይስጡ ፊደል ፲ር ስለሆነ የ ፲ቱ ቃላት ያሉበት ጽላት ያሉበት ጽላት የአምላክ ስም ባለበት የሚሰግዱ መሆናቸውን ማስተዋል ነው። አባ ጋስፓሪን በእብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ የሚል የለም ብሎ ጨርሶ ለመካድ አይችሉም። ግን ውስጥ ለውስጥ የሚሄደው አሳባቸው በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ኢትዮጵያ የሚላት ከግብጽ ደቡብ ያለችቱን አገር ነው እንጅ ዛሬ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት የሆነችቱን አሳባቸውን ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት የሆነችቱ አሳባቸው ኢትዮጵያ አይደለችም ለማለት ነው። ይህም አሳባቸው እንዲሁ በከንቱ ነው እንጅ በኦሪት ዘፍጥረት ፪ ፲፫ ወስሙ ለካልዕ ፈለግ ግዮን ውእቱ ዘየአውድ ኵሎ ምድረ ኢትዮጵያ የሚለውን ተመልከተው ቢሆን በተረዱ ነበር ፪ኛ ኦሪት ዘኁልቁ ፲፪ ፩ ወሐመይዎ ለሙሴ ማርያም ወአሮን በበይነ ብዕሲት ኢትዮጵያዊት እንተ ነሥአ ሙሴ። እስመ ብእሲተ ኢትዮጵያዊተ ነሥአ ይህም ማርያምና አሮን ኢትዮጵያውያዊዪትን ማለት ጥቁረቷን ለመንቀፍ ወደ ምድረ ርስት ይዟት ሊገባ ነውን ብለው ተነጋገሩ ማለቱ ነው። ይህንም ነገር እግዚአብሔር ስለጠላባቸው በማርያም ላይ የነጭነት ደዌ ሰጥቶ ቅጣት።

እስመ ብእሲተ ኢትዮጵያዊተ ነሥአ ያለውን ሐተታ ለማወቅ ሙሴ በፈርኦን ቤት በነበረ ጊዜ ኢትዮጵያውያን የዓባይን ውኃ ገድበው ሕዝቡ በውኃ ጥም ስለተቸገረ ሙሴን አለቃ አድርገው እስከ ፴ሺ ፈረሰኛ ሕዝብ ሰጥተው ወደ ኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት ልከውት ነበር። ዐባይንም የገደቡትም ምክንያት ግብፃውያን ስለ ዐባይ ውኃ የሚገብሩትን ወርቅ ስለከለከሉ ነው ስለዚህ ሙሴ ኢትዮጵያ ሄዶ ቢቻል በእርቅ በምልጃ ማለት ከብዙ ዓመት ግብር እኩሌታውን ከፍሎ መገላገል። ሙሴ የእግዚአብሔር ረድኤት ያልተለየው ጀግና ስለሆነ ነገሩን በሰላም አሰናድቶ የንጉሥ ነገሥቱንም ልጅ አግብቶ ወደ ግብፅ እንደተመለሰ ጊዮርጊስ ወልደ ዓሚድ ይጽፋል። ሴቷ የሔደችበት ምክንያት ይህ መሆኑን አስገነዝባለሁ። ላባ ጋስፓሪን አሳብ ላ፩ኛው ግዮን ዘየአውዳ ለኵላ ምድረ ኢትዮጵያ ባለው መሠረት ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ሌሎችም ነቢያት በሚገባ እንዳነሷት ይህችም ኢትዮጵያ ከካም በኩሳ ከኩሳ በሰብታሕ ሰብታሕ በኢትዮጵያ ናምሩድ በባቢሎን የኩሳ ልጆች እንደነገሡ ታሪክ ይነግረናል። ስለ አፍሪካ መከፈል አፍሪካን ኖኅ ለካም ከሰጠው በኋላ ከካም ልጆቹን ለማካፈል ከዕሥያ ወደ አፍሪካ እንሂድ ቢላቸው የካም ፫ቱ

## ዐ ሰኑይ

ልጆች ኩሳ ሚሥራይ ፋጥ አባታቸውን ተከትለው ተነሥተዋል። ከነዓን ግን ፬ኛው የካም ልጅ ያባቱን አገር ይሻለኛል አልሄድም ብሎ ያለሁበት አገር ይሻለኛል አልሄድም ብሎ እዚያው ስለቀረ አባቱም ይህ የኔ ክፍል አይደለምና ወደኔ ክፍል ሄደህ እንደወንድሞችህ ዕጣ ርስትን ተቀበል ቢለው አይሆንም ብሎ ስለቀረ ካምም ፬ኛውን ልጁን ከነዓንን ረግሞ ፫ቱን ልጆቹን ይዞ መጥቶ ለሁለቱ ለሚሥራይና ለፋጥ

ለሚሥረይ ምሥርን ለፋጥ ሊቢያን ከዚያ የተፈረመው ለኩሳ ሰጥቶታል። ኩሳም የወለደው ብዙ ነው ፮ቱ በአሪቱ ተጽፈው ይገኛሉ የቀሩት ግን በየታርክ ለታሚዎች መዝገብ ይገኛሉ። ካም ለ፫ቱ ልጆቹ አፍሪካን እንደከፈለ መረጃ የፈለገ ሙሴ የጻፈውን መጽሐፈ ኵፋሌ ፱ ፲፩ ወከፈለ ካም ለውሉዱ ወወጽአ መከፈልት ቀዳሚ ለኩሳ መንገለ ጽባሒሃ ወዓረቢሃ ለመጽሬም ወዓረቢሁ ለፋድ። የኖኅ ልጆች ሴምም ያፌትንም ዕፃቸውን ለልጆቻቸው አካፍለዋል እነተካፈሉ መጽሐፉ ያስረዳል። እንግዲህ ያዳም መንግሥት ለ፲ረኛው ልጅ ለኖኅ ከደረሰ በኋላ የኖኅ መንግሥት ለ፫ት ልጅጆች ተከፈለ ፫ቱም ልጆች የተማሩ የተመረጡ ጌቶች ናቸው ሁሉም በየከፍላቸው እንደመጠናቸው መንግሥት አቁመዋል ከነዚሁ ሁሉም በየክፍላቸው እንደመጠናቸው መንግሥት አቁመዋል ከነዚሁ ከካም ቤት ዋናው ኩሳ ነው። በኩሳ ቤትም ሰብታህ ነው መንግሥቱና ጽሑፉ ሲያያዝ እንደመጣ ከላይ አመልክቻለሁ። በዚሁ መሠረት ታሪክ የሚነግረን በኩሳ ቤት የመጀመሪያ ከተማ የነበረችቱ መርዌ ናት። በኋላ ግን ደግሞ ከመርዌ የዋናው ንጉሥ ነገሥት መቀመጫ አክሡም መሆኑን። አክሡም የንጉሥ ነገሥት መቀመጫ በሆነ ጊዜ መርዌ የንጉሥ መቀመጫ መሆንዋን ታሪክ ይነግረናል። መርዌና አክሡም እልፍኝና አዳራሽ ናቸው። እንጅ ልዩነት ያለባቸው አይደሉም። አሁን አባ ጋስፓሪን የደከሙበት የመጡበት ዋና ሥራቸው ወገንና ወገንን ለመለያየት ስለሆነ መርዌንና አክሡምን ለመለዬት ነው። ይህ የመለያየት የማጣላት የመነጣጠል ሥራ የማነው ከማንስ የተገኘ ነው ተብሎ ቢጠየቅ ይህች ሥራ ጌታ የሌላት አይደለችም የጌታዋ ስም ማን ይሆን የኢትዮጵያ ልጆች ይህን ሥራ መመርመር አቅቷቸው ቆብና መቁጠሪያ አየን ብለው ውስጡን ባልመረመሩት ሥራ ገብተው በበረከት ፋንታ ከእግዚአብሔር የደም መርገም ተካፋይ ሲሆኑ ይታያል። ወደ መርዌ እንመለስ የመርዌንና የአክሡምን ፩ድነት የሚመሰክሩ በአክሡምና በመርዌ በድንጋይ ተቀርጸው የሚገኙ ጽሑፎ ናቸው ጽሑፎችን ልዩ ለማድረግ ከቶ የሚቻልበት ምንገድ የለም ኢትዮጵያ ምንም ካ፩፻ ዓመት ወዲህ ታላቅ ደዌ ሥጋ ወድቆባት በገላዋ ላይ ሸክላ እየመሰለ እየወጣ አካላቷን እየለዋወጠ እጅና እግሯን እየቆረጠ በጭንቅ ላይ ስለሆነች ዘልማዱ ሂሩት እግዚአብሔር አስተዋይና ታጋሽ በሆነው ረቂቅ ልጅዋ ስነ ጥበብ ኢዮብን የፈወሰ አምላክዋ ከደዌዋ ትፈወስና ይህ አዲህ ሸክላ የሚመስል ደዌ ሥጋዋ ይለቃትና እጆቿና እግሮቿዋም ተመልሰው ለማየት

እንበቃ ይሆናል። በመርዌ ሲደነቅ የኢትዮጵያ ነገሥታት የጽሑፍ ምልክቶች በአፍሪካ ደሴቶችና ባረብም ሁሉ ገና እየተመረመሩ ይገኛሉ። በታሪክ ወገን ኢትዮጵያን የሚአሰጋት ነገር የለም። አሁን በጥብቅ ሥራ ምክር ቤቱ ሌትና ቀን ሊደከምበት የሚገባው ስለ ኢትዮጵያ ሕማም ስለ ደዌ ሥጋዋ ብቻ ነው። ባ፬ኛው ገጽ ላይ በግብጻውያንና በኢትዮጵያውያን መካከል ብዙ ሐተታ ውስጠ ነገሩን ላላወቀ ሰው የጽሑፉን ድምጽ ይዞ ሲያይ ፍሬ ነገር ያለበት መስሎ መታየቱ ስለማይቀር ላንባቢዎች ለማስረዳት የምፈልገው ባ፬ኛው

# ፯. ሠሉስ

ገጽ በመጨረሻው ምሥመር "ሰው ሁሉ ደህና አድርጎ እንደሚአውቀው ግብጻውያን ታሪካቸውን ሁሉ በትልልቅ መታሰቢያቸው ላይ ይጽፉት ነበር። በዚህ ምክንያት ግብጻውያን በኢትዮጵያ ላይ ያደረጉትን ትልቅ ዘመቻ በዚህ ቤተ ጣዖት ግብጽም ላይ ተጽፎ ይገኛል ይህም ውጊያ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በፊት ሸ፻፺ ወይም ሸ፸፺ ዓ. ነው ይላል" በጣዖቱ ግምብ ላይ ተገኘ በተባለው ሥዕል ላይ ስንኳንስ በዘመን ለይቶ ጦርነት የተደረገበትን ለማስረዳትና ይህንም ጽሑፍ አባ ጋስፓሪን ለመተርጐም ይቅርና ፩ዱን ቀለም ምን እንደሆነች ለማወቅ ችለው አይደለም። እንዲሁ አፋቸው እንዳመጣ እኛንና ግብጽን በታሪክ ፖለቲክ ሲዘሩት ምናልባት ለ፩ድ ፩ድ አንባቢዎች እውነት ሳይመስል አይቀርምና በማለት ነው።

ፍጹም ሐሰትነቱን ላንባቢዎች አስጠነቅቃለሁ "ለዚሁም በጣዖቱ ቤት ተገኘ ለተባለው ጽሑፍ ባ፭ኛው ገጽ ከግርጌው "በ፲፱፻፹፫ በፈረ ቁጥር ዶሬስ የተባለው ፈረንሳዊ በግብጻውያን ጠበብት የተሠራ ነው የሚአሰኝ ፩ድ ከሸክላ የተሠራ ራስ አግኝቷል። ይህ ራስ ምናልባት ጥንት ወደ ኢትዮጵያ ከመጡት ግብጻውያን ሥራ የቀረ ይሆናል የሚል ጽሑፍ አለ" ያባ ጋስፓሪንን ጽሑፍ ዓምድ አበራክቶ የሚገኘው ይኸውና እንደዚህ ያለው ገለባው ሁሉ ተጠራቅሞ ነው ይህ ሸክላ የተባለ ጥንታዊ ዕቃ የቀረበ ጊዜ እኔም አብሬ ነበርኩ የተገኙም ዕቃዎች ብዙዎች ናቸው ዕቃዎችም የተገኙ ከመሬት ነው። ተብለው ፩ድ ቀጠን ጐበጥ ያለ ብረት ጥንታዊ ግዕዝ የተጻፈበት ፪ኛም እንደ ተቀመጠ ሰው ሆኖ የተቀረጸ ልብሱም ባላበባ ጌጥ ያለበት በዙሪያውም ጥንታዊ ግዕዝ ያለበት ዋነኞቹ እነዚህ ሳይጸፉ የግብጽን ምስጋና ማንሻ በመፈለግ የምልክት ምክንያት የሌለበትን ሸክላ ግብፃውያን መጥተው ሳለ የቀረ ይሆናል ተብሎ ተጻፈ ለመሆኑ ግብፃውያን ትግሬ ድረስ መጥተው ነበር የሚል ጽሑፍ ከምን ተገኘ ጽሑፍስ እንዳይገኝ የታወቀ ነውና ነገሩን አንባቢ ይገምተው። የግብጽ ነገሥታት ታሪክ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በግዕዝ እየተጻፈ ይገኛል። ግብጽ በረታች በተባለ ጊዜ ከሱዳን መሬት እኩሌታ የሚሆን ትንሽ ቀን ይዛ ነበር የሚል ጽሑፍ መገኘቱ አይካድም። በተረፈ ግብጽ የዐባይን ግብር ወርቅ አይከፍልም ባለች ጊዜ የኢትዮጵያ ነገሥታት እየደረቡ ሲገዟት እንደሚኖሩ በኛ የሚገኘው ጽሑፍ ምስክረቱ ይቆይና ያደላል ተብሎ የማይጠረጠረው ሄሮደቱስ በግብጽ በሚገኘው የነገሥታት አጽም ማረፊያ ሕንፃ ውስጥ ገብቶ ሲመረምር ከ፫፻፶ው የነገሥታት አጽም ፲፰ቱ የኢትዮጵያውያን ነገሥታት አጽም ነው ብለው አሳዩኝ ብሎ የጻፈውን ማየት ነው። ፲፰ እዚያው የተቀበሩት ናቸው እንጅ ሲገዙ እየቆዩ የተመለሱም አሉ። የነሱን ዝርዝር በዚህ ለመጻፍ አያስፈልገንም አባ ጋስፓሪን የነቃቀፍኩ መስሏቸው የሆነውና ያልሆነውን ስለጻፉ ላንባቢ እውነት እንዳይመስል ይህን ጻፍሑ እንጅ ግብፅ ለኛ ሩቃችን አይደለችም። የጥበብ ሀገር ብትሆንም እንደሰታለን እንጅ አይከፉንም ያባ ጋስፓሪንን ነገር ካገኘን በኋላ አገራችንን ስለ ግብጽ ጥበብ እንደሰታለን በማለት እንወስናለን የኢትዮጵያንና የግብጽን ታሪክ ዓለም ያውቀዋል። ግን እንደ አባ ጋስፓሪን አሳብ ኢትዮጵያን በሰነፍ ዓኡም ለማየት ግብጽን በብርቱ ለመገመት ይመስላል። አባ ጋስፓሪን ማስተዋል ቢአንሳቸው ነው እንጅ ታላቁ እስክንድር ግብጽን በያዘ ጊዜ ኢትዮጵያን

## ዓ ረቡዕ

በምን ምክንያት ሳይወጋት ቀረ ፪ኛስ የሮማ ቄሳር አክላውባጥራ ትባል የነበረችቱን የሴት ንግሥት ገድሎ ግብጽን በያዘ ጊዜ ኢትዮጵያን በምን ምክንያት ሳይወጋት ቀረ ብለው ምክንያቱን መጠየቅ ነበረባቸው ጠይቀው ቢሆን ማነኛውንም ነገር ለማወቅ በቻሉ ነበር። ያውቁብኛል ብሎ ትንሽም የይሉኝታ ምልክት ስንኳን የመነኩሴ ልብስ የለበሰው ሰው ማንም ተራ ሰው እንኳ በመጻሕፍቱ ላይ ቁጭ ብሎ የሚገኘውን ነገር ኢትዮጵያ ማለት ከጽርዓውያን የመጣ ነው ብሎ በዋና ታሪክ ጽሑፍ ላይ ዓምድ የሚያሲዝ ነው እውነት በተገለጠ ጊዜ ቅሌት ውርደት ያገኘኛል ብሎ የማይፈራ ልብ ከተ ከምን አገኙት ይሆን ፳ ሊቃናት መጻሕፍት ብሉያትን ከእብራይስጥ ሲገለብጡ የአበውን ስም በጽርዕ ቋንቋ የማንን ስም ለውጠው ጻፉ ብለን ብንጠይቅዎ የማን ስም እንደተለወጠ ለማስረዳት ይችላሉ። ፩ኛ የአዳም ፪ኛ የሔዋን ፫ኛ የሴት ፬ኛ የሄኖስ ፭ኛ የቃይናን ፮ኛ የመላልኤልን ፯ኛ የያሬድን ፰ኛ የሄኖክን ፱ነኛ የማቱሳላን ፲ኛ የላሜህን ፲፩ኛ የኖኅን በጠቅላላው ከአዳም ዠምሮ እስከነበሩበት ዘመን የአበውን ስም በመሠረቱ እንዳለ አድርገው ገለበጡት እንጅ ለዋወጡት እንጅ ለዋወጡት የሚል ተጽፎ አያውቅም። በኢትዮጵያ የሚገኙ ቅዱሳት መጻሕፍት ጥልቅ መሠረት ያላቸው መሆኑን በጥንታዊው ቁጥር የሚተረጐም ምሥጢር ያለበት

መሆኑን ባለመገንዘብ የግዕዝ ትርጓሜ ምሥጢር ባማርኛ እንደሚፈተተው መስሏቸው በማያውቁት ሥራ ገብተው ከሕግ ውጭ የሆነ ሥራ የኢትዮጵያን የታሪክ መሠረት የመነኰስ ልብስ ተከናንበ ሲሰረስሩ መገኘት ቅጣት የሚአመጣ መሆኑን ያስታውሳል።

አባ ጋስፓሪን ሆይ ኢትዮጵያ የሚል ጽሑፍ በእብራይስጥ ቅዱስ መጽሐፍ ላይ አይገኝም ስላሉት የሐሰት ክምር ሳይበዛ በቀላሉ ለማስረጃ ያህል አቀርባለሁ ፩ኛ ኦሪት ዘ ፪ ፲፫ ወስሙ ለካልዕ ፈለግ ግዮን ውእቱ ዘየዓውድ ኵሎ ምድረ ኢትዮጵያ።

፪ኛ ኦሪት ዘኍልቁ ፲፪ ፩ ሐመይዎ ለሙሴ ማርያም ወአሮን በበይነ ብእሲት ኢትዮጵዊት ነሥአ ሙሴ ብዕሲተ ኢትዮጵያዊተ ነሥአ።

፫ኛ ኢዮብ ፳፰ ፲፱ ወኢትዔሪያ ተንከራ ዘኢትዮጵያ።

፬ኛ መ ዳዊት ፷፯ ፴ ኢትዮጵያ ታበጽሕ እዳዊሃ ኀበ እግዚአብሔር

፭ኛ መ ዳዊት ፸፩ ፱ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ወጸላዕቱሂ ሐመደ ይቀምሑ።

፮ኛ መ ዳዊት ፸፫ ፲፬ ወወሀብኮሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ

፯ኛ መ ዳዊት ፹፮ ፲፬ ወናሁ ኢሉፍሊ ወጢሮስ ወሕዝበ ኢትዮጵያ እለ ተወልዱ በሀየ

፰ኛ ዜና መዋዕል ፳፩ ፲፮ ወአንሥአ እግዚአብሔር ላዕለ ኢዮራም ሕዝበ ነኪር ወሰብዓ ዓረቢያ በአጽናፈ ኢትዮጵያ።

፱ነኛ ዜና መዋዕል ፲፪ ፫-- ለዘመጽአ ምስሌሁ እምብሔረ ግብፅ ወእምበሐውርተ ልብያስ ወሞጦግልያ ወሰብዓ ኢትዮጵያ።

፲ኛ ነገሥት ፲፱ ፱ ወሰበ ስምዐ ትርሃቅ ንጉሠ ኢትዮጵያ

## ዔ ሐሙስ

፲፩ኛ ኢሳይያስ ፴፯ ፱ ወወጽአ ትርሐቅ ንጉሠ ኢትዮጵያ ከመ ይ

ትቃትል ሕዝቅያስን ለመርዳት ሰናክሬምን ሊወጋ

፲፪ኛ ኤርምያስ ፴፰ ወአዘዞ ንጉሥ ለአቤሜሌክ ኢትዮጵያዊ ወይቤ

፪፲ ወይቤሎ አቤሜሌክ ኢትዮጵያዊ ለኤርምያስ ደይ አጽርቅተ ወአሕባለ ታሕተ እዴከ።

፲፫ኛ ዳንኤል ፲፩ ፵፫ ወይሴለጥ ላእለ መዛግብት ዘወርቅ ወብሩር

ወላዕለ ኵሉ ፍትወተ ግብጽ ወኖባ ወኢትዮጵያ

፲፬ኛ አሞጽ ፱ ፯ አኮኑ ከመ ደቂቀ ኢትዮጵያ አንትሙ በኅቤየ

ደቂቀ ፳ኤል

፲፭ኛ ናሐም ፫ ፱ ወኢትዮጵያ ኃይላ ለግብጽ

ከላይ ከተጻፉትም ሌላ ሞልቷል ግን ዓምድ ማባዛትና አንባቢም ማሰልቸት ፍሬ በሌለው ሐሰት ሥራ እነዚህም ፲፫ቱ ምስክሮች ፩ዱ ፫ት እየሆነ በስምንት ፪ቱ ወ፫ት ይቁም ኵሉ ነገር ባለው መሠረት ኦሪ ዘዳ. ፲፱ ፲፫። አባ ጋስፓሪን ሆይ ከላይ በተጻፉት ሁሉ ምስክሮች የተረቱ እንደሆነ ስለዚህ ስለሐሰቱ ጽሑፍዎ እኔ ተቃዋሚ ሆኘ ምን ብለው ይመስላሉ መዎቀስዎን አስቀድሞም አላጡትም።

ስለሆነ። እኔ የማቀርብልዎ ጥያቄ ይህን ሐሰት የተከናነበ ጽሑፍዎን ከየሸጡበት እየፈለጉ ተቀብለው። በዚህ ምክንያት የተቀበሉትን ገንዘብ ሁሉ መልሰው ወደ ሀገርዎ በሰላም እንዲሄዱ ነው። የሐሰት ታሪክ ጸሐፊነትዎንም ገና በሰፊው እየገለጽኩ አደራጅልዎታለሁ። እንግዲህ ወደ ሁለተኛው ክፍል እንራመድ የ፩ኛውን ክፍል ሐተታ ጨርሰን። ጥያቄ ፪ኛ በ፷ኛ ገጽ ኢትዮጵያ የሚለው ስም በግሪኮች ዘንድ። ጽርያች ማለት ነው። ኢትዮጵያ የሚል ቃል ብቻ እናገኛለን ከርሱም ኢትዮጵያዊ ይመጣል) ። እንግዲህ ከላይ የተጻፈውን ምን በቂ ትርጓሜ እንሰጠው። እንደተጻፈው ስንመለከተው ኢትዮጵያን የሚለው ስም በግሪኮች ዘንድ ጽርያች ማለት ነው። ይህ ነገር ያለ ቦታው የገባ የስሕተት ጽሑፍ ነው እንጅ እርግጠኛ አይደለም ምክንያቱም እንደዚህ ጽሑፍ ተጽፎ ባለመታቁ ነው የግሪክ ሰዎች በቋንቋቸው ጽርዓውያን እስራኤልም በቋንቋቸው ጥግ እብራውያን ይባላሉ ኢትዮጵያውያንም በቋንቋቸው ጥግ አግዓዝያን ይባላሉ። በመጻሕፍቱ የምናገኘው የታሪኩ ምንገድ ይህ ነው። ኢትዮጵያ ብሎ ጽርያች ማለት ትርጓሜው ከምን እንደሚመጣ እንደምን እንደሚተረጐም እኔን አልገባኝም ደግሞ ዝቅ፦ ብሎ አርስት ይሰጥና። ይህ ቃል ብሎ በውጭ አገር ፊደል ኢትዮጵያ ከሚለው ከግሪክ ቃል ጋር ይስማማል ይላል። የግሪኩ ቋንቋ ከፈረንሳይ ፊደል የሚስማማነው ለማለት ይሞክራሉ ይህም የማይቻል ኢትዮጵያ የሚለው ስም በፈረንሳዊ ፊደል ሲጻፍ ከግሪክ ቃል ጋር ይስማማል ይላል አሁን ይህ ነገር ከቁም ነገር ተቆጥሮ ዓምድ ይዞ መገኘቱ ከማስገረም በተቀር ሌላ የለም። ፩ድ ነገር አለኝ ላባ ጋስፓሪን የማመለከተው ይህ አሁን በፈረንሳዊ ፊደል ኢትዮጵያ ብለው የጻፉት አስቀድሞ ኢትዮጲስ በነበረች ዘመን መኖሩን ያረጋግጣሉ ይሆንን። ላቲንንም እንዳይረሱት ፊደሎች እንደምን እየተሻሻሉ እንደመጡ ያስታውሱ። ከ፸፪ቱ አለቆች ስናዖር ላይ ከተገኙት የርስዎ ቋንቋ ከየትኛው ውስጥ መሆኑን ከሴም ዘሮች ክፍል። ወይም ከያፌት ወይም በእስያ ከሚኖሩት ከካም ዘሮች ክፍል ውስጥ ከማነኛው ክፍል ያለውን ቋንቋ እንደያዙ ለማወቅ

## ዕ ዓርብ

ቢከታተሉ የተሻለ ነበር። ኢትዮጲስ የነበረበትን ዘመንና መጻሕፍተ ብሉያት የተጻፉበትን ዘመን ርቀት ከላይ ጽፌዎታለሁ። ባልቸገረዎ ገብተው ኢትዮጵያ ማለት ፍችው ነዋሪዎቹ ፀሐይ ፊታቸውን ያቃጠለው ጠያይም መልክ ያላቸው ሰዎች አገር ሰው ለማለት ነው። እንግዲህ በአባ ጋስፓሪን አሳብ እንደተጻፈው መልኩ ጠይም የሆነ ሰው ያለበት አገር ሁሉ ስመ ኢትዮጵያ መሆኑ ማለት ነው። በዓለም ላይ ስንት መልኩ ጠይም የሆነ ይገኛል። እኔ የምለው ግሪኮችና ኢትዮጵያውያን የተዋወቁበትንና የተገናኙበትን ዘመን ለይቶ ማወቅ ነው። ነገሩን አሁን ገልጨው ይመጣል። ይህም "በ፱ነኛው ገጽ ኢትዮጵያ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስለ ኢትዮጵያ የተናገሩትን ዋና ዋናወቹን ቃላት እዚህ ላይ መቀመጥ በብዙ የሚጠቅም ነው። እንደምናውቀው በእግዚአብሔር ማሳሰብ (መንፈስ) የተጻፈው ቅዱስ መጽሐፍ ውጣኔው ታሪክንና ጽሕፈተ ምድርን (ዥኦግራፊን) ለማስታወቅ አይደለም ብለዋል"። አሁን ይህ ቃል የመናኒ ቃል ይመስላል ይሆንን

በመንፈስ ቅዱስ ማሳሰብ የተጻፈው ቅዱስ መጽሐፍ እንደምን አድርጎ ጽሕፈተ ምድር ለማስታወቅ አይደለም። ተብሎ ይጻፋል። ይህ አጻጻፍ መቸም የሮማ ልዑካን በስምና በልብስ ካህናተ እግዚአብሔርን መስለው ስለመጡ ሕገ እግዚአብሔር ከተጻፈውበት ቃል መውጣታቸውን ስላወቁ ጽሕፈተ ምድርን ካርታን) ኢሳይያስም አሉ። ካርታ ማለት የወሰን ምልክት ነው። ቅዱስ መጽሐፍ የወሰን ምልክት እንደ ሚስፍ

፩ኛ አሪት ዘፍ ፲ ፩ ወከመዝ ውእቱ ልደቶሙ ለደቂቀ ኖኅ ሴም ወካም ወያፌት ወተወልዱ ሎሙ ደቂቅ እምድኅረ አይኅ ፪ ወደቂቀ ያፌት ወያኅግ ወማዴ ወያህያን ወኤልሳ ወቶቤል። ወሞሳሕ። ወቲራ። ፰ ናቸው። ወደቂቀ ጋሜር አስካንሶ ወኢራፌት ወቲራጋም። ፫። ናቸው። ፬ ወደቂቀ ይህያን ኤልሳ ወቅራሳሶ ውቂጥኢ ወሮድኢ ፬ ናቸው የልጅ ልጆች ፰ ናቸው። ፭ ወእምነ እሉ ተፈልጠ ያስደስቲሆሙ ለሕዝብ በበምድሮሙ ወበበነገዶሙ ወአሕዛቢሆሙ የያፌትን ዘሮች መሠረት ለይቶ እንደተለዩ ተፈልጠ ደስያቲሆሙ ብሎ አስረዳ። ፪ኛ ስለ ካም ዘሮች በቁጥር ፮ ወደቂቀ ካም ኩሳ ምሥጣሪም ወፋጥ። ወከነዓን ፬ ናቸው። ፯ ወደቂቀ ኩሳ ሳባ ወኤዌልጥ ወሳባታ ወራጌም። ወሰባቃታ ፭ ናቸው ወደቂቀ ራጌም ሳባ ወዮደደን ፰ ወኩላ ወለዶ ለናምሩድ ወውእቱ ኮነ ያርብሐ በምድር ፱ ወኮነ ነዓዌ ቅድመ እግዚአብሔር የኩሳ ልጆች ከናምሩድ ጋር ፮ የልጅ ልጆች ፪ት ናቸው። ፲ ወኮነ መንግሥቱ ባቢሎን ወኦሬክ ወአርክድ። ወካሌን በምድረ ስናዖር ፲፩ ወእምይእቲ ምድር ወጽአ አሶር ወነደቃ ለነነዌ ወለሮቤት ሀገር ወለካላከ ፲፪ ወዳስ ዘሀሎ በማዕከለ ነነዌ ወቃላት ዛ አገር ዓባይ እነዚህ ሁሉ ከተሞችና አገሮች ከእሥያ ውስጥ የኩሳ ልጅ ናምርድ ያቀናቸው መሆኑን ማስተዋል ነው። ፲፫ ወምሥጣሬም ወለዶሙ ለሉድኬም ወለኤኔማጠአም ወለንፍታሌም ፲፬ ወለጴጥርሶናኦን ወለከሳሮኦን እምኀበ ወጽአ ፊሌሴጤአም። ወለቃፍ ቶርአም ፰ ናቸው። ፲፭ ወከነዓን ወለዶ ለሲዶን በኩሩ። ወለኬጢኤን ፲፮ ወለኢያቡሴዎን ወለጌርጌሴዎን ፲፯ ወለኤዌዎን ወለኤሬቄዎን ወለአሰኔዎን ፲፰ ወለክራዱአን ወለሰማንኢር ወለዓመቲ ወእምድኅረ ዝንቱ ተዘርዑ ደቂቀ ከነዓን። ፲፩ ናቸው ፲፱ ወኮነ አድባሪሆሙ ለከነዓን አምነ። ሲዶን እስከ ጊራራ ወጋዛን ወይበጽሕ ሰዶም ወገሞራ ወአዳማ ወሰበዮ እስከ ሌላ። ይህ ሁሉ የካም ልጅ የከነዓን ነው። ፳ ወእሉ እሙንቱ

# ፶ ቀዳም

ደቂቁ ለካም በበዘመዶሙ ወበበነገሮሙ ወበበብሔሮሙ አሕዛቢሆሙ። የካምን ዘሮች ከ፮ ቁጥር ዠምሮ እስከ ፳፩ ቁጥር ይገኛል። ፳፩ ወለሴም ተወልዱ ሎቱ ኤላም ወአሶር ወአርፋክስድ ወሉድ ወአራም ፭ ናቸው ወደቂቀ ኤላም ኤላህ ዮምኤል ያቲር ሞሶህ ፬ ናቸው ወአርፋክስድ ወለዶ ለቃይናን ወለዶ ለሰላ። ወሳላ ወለዶ ለዔቦር ወዔቦር ወለዶሙ ለፋሌቅ ወለዮቅጣን። ከአዳም ዠምሮ እስከ ፋሌቅ በትውልድ ፲፯ ትውልድ ነው። በዘመን ከ፪ ሺ ፮፻ አይበልጥም።

፳፮ ወዮቃጤን ወለዶ ለኤልሞዳድ ወለሰሌፋን ወለሴሌራሞት ወለኢራኅ። ፳፯ ወለሐይራ ወለኤዜላ ወለዴቄላ ፳፰ ወለዑባላ ወላአቢማኤል ወለሰባ ፳፱ ወለሑፋር ወለሔዊላ ወለኢዮቦር። ወለኵሎሙ ደቂቁ ለዮቃጤን ፴ ወኮነ ምንባራቲሆሙ እምነ ማሴ እስከ ሳፌራ ይበጽሕ ደብረ ሰረቃዊ ፴፩ እሉ እሙንቱ ለሴም በበነገዶ ደቂቁ ለኖኅ በበዘመዶሙ ወእምነ እሉ ተወልደ ዘተዘርወ እምድኅረ አይኅ። እስከዚህ ድረስ ከባቢሎን ግምብ መፍረስ አስቀድሞ ያሉትን ነው ከተካፈሉም በኋላ ያለውን ግን ም ፲፩ ፪ ወኮነ እምድኅረ ተንሥኡ እምጽባሕ። ከምሥራቅ ከተነሡ በኋላ ዱር አገኙና በዚያ አድረው የጡብ ረዥም ቤት እንሥራ ብለው ምክር ዠመሩ ብሎ ያመጣዋል። በዓለም የተዘሩ አባቶች መሠረት ይህ ነው ግን ይህ በኦሪት እንደተጻፈው ስለሆነ ስለሆነ ፫ቱ አባቶች ሴም ካም ያፌታ ዓለምን በዕጣ እንደተካፈሉ

የሚአስረዳ ወሰኑንም ሁሉ እየለየ የሚአሳይ ኵዳሌው ነው። የዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰዎች መጽሐፈ ሄኖክንና መጽሐፈ ኵፋሌን ደግሞ ፲፬ት መጻሕፍቶችም አሉ እነዚህን ሁሉ አልቀበልም ስለሚሉ የዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ፪ት አርእስቶች አምልጠዋቸው ይኖራሉ። ፩ኛው መላእክት መኖራቸውን የሚአምኑ ቢሆኑ መላእክት ተፈጠሩ የሚለውን ጽሑፍ ያለበትን ሳያውቁት ይኖራሉ። ፪ኛው ይህን ዓለም ኖኅ ለ፫ት ልጆቹ በዕጣ እንደ ተካፈሉ በቃል አውሮፕላን ለያፌት እሥያን ለሴም። አፍሪካን ለካም ነው። ማለትን በድምፅ ከመስማት በተቀር ፫ቱ አባቶች እንደተካፈሉ ከተወሰኑ ተለይቶ የተጻፈውን መሠረት አምጡ ብሎ ቢጠይቋአቸው ኵፋሌውን ስለነቀፉ ለማስረዳት አይችሉም። የአውሮፓ ሊቃውንት አይሁድን ምክር እናክብር ብለው በኢትዮጵያ የሚገኙትን መጻሕፍት አንቀበልም ብለው ባይተዋቸው ኑሮ ለትርጓሜው ሁሉ እንደምን ያለ ብርሃን ምንገድ በሰጣቸው ነበር እያልኩ ዘወትር ከማዘን አላቋርጥም። ስለዚህ አሁንም ከላይ እንደ ተጻፈው የኦሪቱን ብቻ ብጽፈው በሰፊው የዙሪያውን ወሰን ሁሉ ለይቶ ስለማይስረዳ ለወገኖቼ መርጃ እንዲሆን በኵፋሌው የተጻፈውንም ከዚህ አስከትየ አጽፋለሁ ኵፋሌ ፱ ፩ በቅድሜሁ በቀዳሚ ዘ፩ ዓመት ዓመተ ሱባዔ እንዘ ይነብር ፩ዱ እምኔነ ተፈኖነ ኀቤሆሙ ወጸወዐ ደቂቀ ወቀርቡ ኀቤሁ እሙንቱ ወውሉዶሙ ወከፈለ ምድረ በዕፃዊ ዘይእኀዙ ፫ቱ ውሉዱ ፪ ወስፍሑ እደዊሆሙ ወነሥኡ መጽሐፈ እምሕፅነ ኖኅ አቡሆሙ ወወጽአ በመጽሐፍ ዕፃሁ ለሴም ማዕከለ ምድር ዘይእኅዝ በርስቱ ወበውሉዱ ወበትውልድ ዘለዓለም። እማዕከለ ደብረ ራፉ እሙፃእ ማይ እምፈለገ ጤና። ፫ ወየሐውር መክፈልቱ መንገለ ዓረብ ማዕከሉ ለዝ ፈለግ ወየሐውር እስከ ሶበ ይቀርብ ኀበ ማየ ቀላያት ወእምኀበ

## ዘ እጉድ

ይወጽእ ዝንቱ ፈለግ እምኔሃ ይከዑ ማያቲሁ ውስተ ባሕረ ሚአት ወየሐውር ዝንቱ ፈልግ እስከ ባሕር ዐባይ። ወኵሉ ዘመንገለ ደቡብ ለያፌት። ወኵሉ ዘመንገለ ገጸ ሰሜን ለሴም። (ሴምና ያፌት እንደይሚዋሰኑ ያፌት ወደ ደቡብ ሴም ወደ ሰሜን እንደሆነ ለዓለም ካርታ መሠረት ይህ ጽሑፍ እርግጠኛውን ያስረዳል።) ፬ ወየሐውር እስከ ሶበ ይቀርብ ኮራስ ዘውእቱ ውስተ ሕጽን ልሳን እንተ ትኔጽር መንገለ ሰሜን ወየሐውር መክፈልቱ እንተ መንገለ ባሕር ዐባይ ወየሐውር ርቱዓ እስከ ይቀርብ መንገለ አረቢሃ ለፈለግ እስመ ዛቲ ባሕር ልሳነ ብሔረ ግብጽ። ፭ ወትገብእ መንገለ ሰሜን መንገለ አፉሃ። ለባሕር ዐባይ ውስተ ከናፍረ ማያት ወተሐውር መንገለ ዓረብ አፈራ። ወተሐውር እስከ ትቀርብ። ኀበ ማየ ግዮን ወመንገለ ሰሜን ለማየ ግዮን መንገለ ድንጋጉ ለዝ ፈለግ ፮ ወተሐውር መንገለ ጽባሒሁ ለደብር ዘስሙ ራፋ ወይወርድ መንገለ ጽንፋ ለሙፃእ ጤና ፈለግ። (የሴምን ርስት ዙሪያ ወሰን።)

በሰሜን ግብጽ በደቡብ የያፈት እንደሆነ ለሴም የተሰጠውን አገር ዙሪያ ከላይ በተጻፈው ካመለከተ በኋላ ፯ ዛቲ ለመክፈልት ወጽአት በዕፃሁ ለሴም ወለውሉዱ እስከ ለዓለም። ዕጣ ከመጣሉ በፊት ወሰኑ አስቀድሞ ዙሪያው እንደተወሰነ ዕጣውም የዘላዓለም ጸንቶ የሚኖር እንደሆነ ማስተዋል ነው፡ ፰ ወተዘከረ ኵሎ ዘነበበ በአፉሁ በትንቢቱ

እስመ ይቤ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኩ ለሴም ወይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ማኅደረ ሴም። ወአእመረ ከመ ገነት ኤዶም ቅድስት ቅዱሳን ወማኅደሩ ለእግዚአብሔር ውእቱ ወደብረ ሲና ማዕከለ ገዳም። ወደብረ ጽዮን ማዕከለ ኅንብርታ ለምድር ፫ቱሆሙ ዝንቱ መንጸረ ዝንቱ ለቅዱሳት ተፈጥሩ። ፱ ወባረኮ ለአምላክ አማልክት ዘወደየ ውስተ አፉሁ ንባበ እግዚአብሔር እስከ ለዓለም ወአእመረ መክፈልተ ቡራኬ በጽሐ ለሴም ወለውሉዱ ለትውልድ ዘለዓለም። የሴምን ዕጣ እንደዚህ ያሳያል። ደግሞ ፪ኛውን የካምን ክፍል ይዠምራል። ቁ፲፩ ወለካም ወጽአ መክፈልት ዘዳግም መንገለ ማዕዶተ ግዮን መንገለ ሰሜን በየማነ ገነት ወየሐውር መንገለ ሰሜን ወየዓውድ ኵሎ አድባረ እሳት ወየሐውር

መንገለ ዓረብ እስከ ይቀርብ ኀበ ባሕረ ማዕከክ እንተ ይእቲ ዘኵሉ ይወርድ ውስቴታ ዘይትኃጐል ወይመጽእ ውስተ ደቡብ ውስተ ጽንፈ ጋዴት ወይወጽእ ውስተ ከንፈረ ማየ ባሕር ዐቢይ እስከ ሶበ ይቀርብ ፈለገ ግዮን ፲፪ ወየሐውር ግዮን ፈለግ እስከ ሶበ ይቀርብ በይምነ ገነተ ኤደም ወዛቲ ምድር እንተ ወጽኣት ለካም በመክፈልት ዘይእኅዝ ለዓለም ሎቱ ወለውሉዱ ለትዝምዶሙ እስከ ለዓለም። የካምና የሴም ወሰን ተለያየ። ለዘላለም እንዳይተላለፉ። ከዚህስ ቀጥሎ የ፫ኛው ልጅ የያፌትና የሴም ወሰን እጣው በደቡብ በኩል ያለውን እንደሰጠው ያሳያል። ቁ፲፫ ወለያፈት ወጽአ መክፈልት ሣልስት ማዕዶተ ጤና ፈለግ መንገለ ደቡባቲሁ ለሙፃእ ማያቲሆሙ ወየሐውር መንገለ ጽባሕ ጽባሕ ደቡብ ኵሉ ወለደ ጎግ ወኵሉ ዘጽባቲሆሙ ወየሐውር መንገለ ደቡብ ለደቡብ በየሐውር መንገለ አድባረ ቁልጥ መንገለ ደቡብ ወመገለ ባሕረ ሚኣት። ወይወጽእ መንገለ ጽባሑ ለጋዴር እስከ መንገለ ውእደቱ ማየ ሙፃእ ባሕር ወየሐውር እስከ ሶበ ይቀርብ መንገለ ባሕረ ዓረበ ፉራ ወይገብዕ መንገለ አፈራግ ወየሐውር መንገለ ጽባሕ መንገለ ባሕረ ሚኣት ወየሐውር መንገለ ውዕደ ጤና ፈለግ መንገለ ጽባሐ

## ዙ ሰኑይ

ደቡብ ፲፴ ወዛቲ ምድር እንተ ወጽአት ለያፌት ወለውሉድ ዘይእኅዝ ለዓለም የያፌትም ዕጣ ከሴም የሚዋሰንበትን ከላይ በተጻፈው መረዳት ነው። ለ፫ቱ ልጆች ወስኖ እንዳይተላለፉ አድርጎ የተሰጣቸውን ይዘው እንዲኖሩ እንዳይተላለፉ ትእዛዙን በኦሪት ዘዳግም ፲፱ ፲፴ ወኢትትኃለፍ ደወለ ቢጽከ ዘሠርዑ አበዊከ በውስተ ርስትከ ዘተዋረስከ ምድረ እንተ ወሀበከ እግዚአብሔር አምላክከ መክፈልተከ ብሎ ያዘዘ ስለዚህ ነበር። የሮማ ልዑካን ግን ይህን ሁሉ ትእዛዝ በመጣስ በሰላም ከምንኖርበት አገር መጥተው የኢትዮጵያን ታሪክ ለመደምሰስ በመሞከራቸው ላይ ደግሞ ወደ መጻሕፍቱ ገብተው በ፱ነኛው ገጽ በ፫ኛው መሥመር በእግዚአብሔር ማሳሰብ መንፈስ የተጻፈው ቅዱስ መጽሐፍ ውጣኔው ታሪክና ጽሕፈተ ምድርን (ዥዖግራፊን ለማስታወቅ አይደለም ብለው ያጻፉት ተሠውሮ የሚኖረውን ውስጣዊ ሥራ ሲገልጽባቸው ይታያል። እንዴት በቅዱስ መጽሐፍ ታሪክና ጽሕፈተ ምድር የለም። ወሰን ከሌለ ከላይ የተጻፈውን ታላቁ ነቢይ ሙሴ አባቶችህ ያቆዩልህን የርስትህን ወሰን አልፈህ የወንድምህን ርስት አትንካ ብሎ ስለምን አዘዘ ፪ኛም ኦ ዘዳግም ፫ ፪ ኢትወስኩ ላዕለዝ ቃል ዘእኤዝዘከሙ አነ ዮም ወኢታንትጉ እምኔሁ ከመ ትእቀቡ ኵሉ ትእዛዞ ለእግዚአብሔር አምላክክሙ። ያለውን ክርስቲያን ነኝ ለሚል ሰው መጽሐፉ በጁ ጨብጦ የመጽሐፉን ቃል ትቶ የሌላ የሚያወጋ ምን ይባል ይሆን። እንዴት በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የታሪክና ጽሕፈተ ምድር የለም የጽሕፈተ ምድር ከሌለ መጽሐፈ ኢያሱ ፲፫ ከ፩ እስከ ፲፫ ቁጥር የተጻፈውን ከ፲፫ ምዕራፍ እስከ ፳ ምዕራፍ የተጻፈውን ሁሉ ስለምን የተጻፈ ነው ለማለት ዘዳግም ፲፪ ፩ የጻፈልንን ማስታወስ እፈልጋለሁ ወዝንቱ ውእቱ ትእዛዝ ወፍትህ አምተዓቅር ከመ ትገብሩ በምድር እንተ ይሁበክሙ እግዚአብሔር አምላክክሙ መክፈልተክሙ በኵሉ መዋዕል ዘተሐይዉ አንተሙ ላዕለ ምድር ይላል። እንግዲህ መክፈልተክሙ ያለው በኵሉ መዋዕል በዘመናችሁ ሁሉ ያለው የምትጠብቁት ትእዛዝ ያለው ምን ይሆን። ቃሉም ከመረሳቱ የተነሣ ቅዱሳት መጻሕፍት ትእዛዝ ያለው ምን ይሆን። ቃሉም ከመረሳቱ የተነሣ ቅዱሣት መጻሕፍት ታሪክንና ጽሕፈተ ምድርን ለማስታወቅ አይደለም እስከ ማለት አደረሰ።

ታሪክንስ ካላስረዱ ስለ ጌታችን ሰው መሆን ማቴዎስና ሉቃስ የጻፉትን የትውልድ ታሪክ መመልከት አስፈላጊ ብሎ ይዠምርና በትውልድ እየቆረጠ ታሪክ እየጨመረ ማለት ፲፪ ወእምድኅረ ፍልሰተ ባቢሎን እያለ በትውልድ እየቆጠረ እስከ እመቤታችን ፵፪ ትውልድ ቁጥር ሲቆጥርም ከላይ ወደታች ነው። ይህ ታሪክ አይባልም ይሆንን። ፪ኛ ሉቃስ ፫ ፳፫ ወየአክል ፴ ክረምቱ ለኢየሱስ ወይመስሎሙ ወልደ ዮሴፍ ውእቱ ወልደ

ኤሊ ወልደ ማቲ ብሎ ወልደ አዳም እስከሚለው ፸፯ ቆጥሮ አዳምን ወልደ እግዚአብሔር አለው አዳም ከኅቱም ምድር እንደተገኘ ጌታችንም በድንግልና ከታተመች ድንግል ማርያም ዳግማይ አዳም ኢየሱስ መወለዱን ሲአስረዳ ከታች ወደላይ ቆጥሮ ጻፈ። እንግዲህ ታሪክ ማለት ይህ አይደለም ይሆንን በመንፈስ ቅዱስ የተገኘ አይደለም ይሆንን ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ ሲመለከቱት ብዙ አስደናቂ ነገር ይገኝበታል። ታሪክና ጽሕፈተ ምድርን ለማስታወቅ አይደለም ስለተባለው ኃይለ ቃል ከላይ የተጻፈው ይበቃል ደግሞ ከዚህ ከ፱ነኛው

## ዚ ሠሉስ

ገጽ ባ፲ኛው መሥመር በብሉይ ኪዳን ውስጥ በእብራዊና በፈረንሳዊ የተጻፈ ኩስ የሚለው ጽፈው ኩሳ የተባለውን ቃል ፸ ሊቃናት ቅዱስ መጽሐፍ ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ የተረጐሙት አሁንም እንደላይኛው ኩሽ እየተባለ እንደተጻፈው በውጭ አገር ፊደል ኢትዮጵያ እየተባለ ተጽፎ። (ኢትዮጵያ ብለው ተርጉመውታል ይልና ቅዱስ መጽሐፍን ከግሪክ ወደ ግእዝ የተረጐሙት ሰዎች ኢትዮጵያ አገሯን ኢትዮጵያዊ ባለአገሩን እንደዚያው ተርጉመውታል። እንደዚ እያደረጉ የኢትዮጵያን ታሪክ እንደዚህ ያሰናዱታል ነገራቸውን ስመለከተው ሲወድቅ ሲነሣ የመጣው ስብከታቸው አሁን ቀጥ ብሎ ለመቆም ራሱን በቻለላቸው ጊዜ በዚያው በተለመደው መሣሪያቸው የኢትዮጵያን መሠረት ገብተው የድናሚት ክር ማግቢያ የሚሆናቸው ይሰረስራሉ። ማለት ኢትዮጵያን መሠረት አስቀድመው ካላፈረሱት የኢትዮጵያ ልጆች ታሪካቸውን እየተመለከቱ ልባቸው ለሞት ቁራጥ እንዳይሆን አስቀድመው ልባቸውን ለማደንዘዝ ስለአሰቡ አስቀድመው የኢትዮጵያውያንን ልብ በጭራሽ ከቦታው መጥፋቱን ካላወቁ እንደ ከዚህ ቀደሙ በኃይል ሥራቸው ጥቅም እንዳላገኙበት አሁንም አስቀድሞ ያላበጁት በኋላ እንደሚአስቸግር ማቴዎስ ፲፪ ፳፱ ወእፎይክል መኑሂ በዊአ ቤተ ኃያል ወንዋዮ ሀይደ ዘእንበለ እመ ኢቀደመ አሢሮቶ ለኃያል ወእምዝ ቤቶ ይበረብር። አሁንም ያባ ጋስፓሪን ስብከት የኢትዮጵያንን ጀግኖች ልብ የፈጥኝ ለማሠር የታሰበው ሥራ ነው። ይህም ስብከት አስቀድሞ ከባቶቻቸው ሲያያዝ የመጣ መሆኑን ባሳተሙልን መጻሕፍቶች በመጽሐፈ አሪትና በሐዲሱ መቅድም ይህን ስብከታቸውን እንድናጠና ጽፈውልናል ሐተታውንም እንደተቻለኝ ከላይ ጽፌው ይገኛል። አባ ጋስፓሪን ደግሞ ይኸውና በሰፊው ከጻፉልን የታሪክ ስብከት ከላይ እንደተገለጽኩት በእብራይስጡ ብሉይ ኪዳን ኩሽ የሚለውን ኢትዮጵያ እያሉ የተረጐሙት ፸ዓ ሊቃውንት ናቸው ፸ዓ ሊቃውንት በጽርዕ የተረጐሙትን ደግሞ ወደ ግዕዝ የተረጐሙ ሰዎች ኢትዮጵያ አገሯን ኢትዮጵያዊ ባለ አገሩን አድርገው (ተርጉመውታል ብለው የጻፉትን ጽሑፍ ስመለከተው አሁን በዓለም ላይ ያለውን ብሉይ ኪዳን ሁሉ በአባ ጋስፓሪን አሳብ ፸ዓ ሊቃውንት የጻፉት ነው ተብለው ታስቦ ማለት ነው። ይልቁንስ ይህ መስታየት ውስጠ ልቦናቸውን ለማስገመት ግብዝነታቸውንም እንደ መስታዩት አድርጎ ከማሳየት በቀር በምንም ፍሬ የሚሰጣቸው ነገር የለም። ሐሰት ጸሐፊ መነኰሴ ከመባል ሳይጽፉት ቢቀር ያው አባቶቻቸው ከመንፈሳዊ መጽሐፍ እያስጠጉ የጻፉት ሐሰት ይበቃ ነበር። ሐሰትና ጉም ሲበዛ ቢውል ምንም ሊከለክል እጎል ሊያበቅል እንደማይችል ማንም አይጠረጥርም። በከንቱ ደክመው ስማቸውን ማስጠፋት አተረፉ እንጅ ነገሩ ከዚያው ከእውነቱ ፈቀቅ ለማለት አይችልም አሁንም በኢትዮጵያ ስለሚገኙ መጻሕፍተ ብሉያት ከላይም የተቻለኝን ያህል ማስረጃዎችን ጽፌአለሁ። አሁንም ደግሞ ማስረጃዎችን አመጣለሁ። ፩ኛ ከላይም ጽፌዋለሁ። በኢትዮጵያ የሚገኙ መጻሕፍተ ብሉያትና በግሪክ አገር በጽርዕ ቋንቋ ተጽፈው የሚገኙ መ ብሉያት ተባብረው ያልተገኙ እንደሆነ

በሮማ ልዑካን እንደምን ያለ ኃፍረት ነጭ ዓመድ ለብሰው ይታዩ ይሆን። በዓለም ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው መጽሐፍ ለየብቻ መሆኑን ማስረጃዎችን ከላይ ጽፌአለሁ ፩ኛ ማስረጃ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፈ ሄኖክ ይገኛል በሌሎቹ የዓለም ቤተ

# ዛ ረቡዕ

ክርስቲያናት መጽሐፈ ሄኖክ የለም። መጽሐፈ ሄኖክ መኖሩን ሐዋርያው ይሁዳ በጻፈው መልእክት ፩ ፲፬ በከመ ተነበየ ሄኖክ በእንቲአሆሙ ዘውእቱ ሳብዕ እምአዳም ወይቤ ናሁ ይመጽእ በአእላፊሁ ቅዱሳን ብሎ የጻፈውን መመልከት የተገባ ነው። እንግዴህ መጽሐፈ ሄኖክ የለም እንዳይሉ ሐዋርያው በመንፈስ ቅዱስ በከመ ተነበየ ሄኖክ ብሎ ፲፫ት ወከመ ሞገዳት ባሕር እሙንቱ ዕቡዳት እለ ያፈልሕዋ ለኃሣሮሙ ወከመ ከዋክብት ጽልሙታን ይጸንሖሙ ለዓለመ ዓለም ብሎ ስለሰይጣናት ተገዢ በሆኑት ሰዎች ላይ የተናገረውን ትንቢት ጽፎ ሲገኝ አልተጻፈውም እንዳይባል ዓለም በተፈጠረ ባ፩ሺ ፬፻፹፯ ዓመተ ዓለም የተጻፈው መጽሐፈ ሄኖክ በኢትዮጵያ ሲገኝ ተገኝ ስል ጽሑፉ ሲያያዝ የመጣውን ቃሉን ማለቴ ነው። ፪

፫ኛ ዓለም በተፈጠረ በ፫ሺ ፰፻ ፵፫ ዓ ዓለም እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ መጻሕፍተ ኦሪትንና ኩፋሌን ሙሴ የጻፈቸውን በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ከእብራይጥ ወደ ግዕዝ ተገልብጠው መጥተው ይገኛሉ። ፬ኛ ቅዱስ ዳዊት የጻፋቸው ፻፶፩ መዝሙራት በጥንቃቄ ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተገልብጠው በኢትዮጵያ ይገኛሉ። ፭ኛ ሰሎሞንም የተናገራቸው መጻሕፍቶች ፭ ናቸው ካ፭ቱ ፫ መጽሐፈ ምሳሌ መጽ መክብብ መ መኃልዩ እነዚህ አሉ ፪ቱ መጻሕፍቶች መክብብና ተግሣጽ ዓለም በተቀበላቸው መጻሕፍት ውስጥ የሉም። ፮ኛ መጽሐፈ ጦቢት መጽሐፈ ዮዲት መ ሲራክ የዓለም ቤተ ክርስቲያን በተቀበለችው ጽሑፍ የሉም በኢትዮጵያ ግን አሉ የሮማ ልዑካን ለንግድና ለስብከት ባሳተሙት መጻሕፍት ውስጥ በዓለም ቤተ ክርስቲያን የሌሉትን መጻሕፍቶች ሁሉ። አሥመራ በታተመው ብሉይ ኪዳን ውስጥ ዘተሰነዓወ ምስለ መጻሕፍት ቀደምት ዘብራና ወምስለ መጻሕፍተ ሶርያ ወጽርዕ ወዓረብ ብለው ባሳተሙት ላይ በውጭ አገር ባሉ አብያተ ክርስቲያናት የማይገኙትን። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙትን ሁሉ መጻሕፍቶች በሽ፱፻፲፭ ዓ.ም አሥመራ ላይ በማኅተመ አፍራንችስካና ባሳተማችሁት ብሉይ ኪዳን ተጽፈው ስለሚገኙ እነዚህን በዓለም ቤተ ክርስቲያን የሌሉትን መጻሕፍቶች ከምን አመጣችኋቸው። ከጽርዕ ቋንቋ ገለበጣችኋቸውን ከምን አመጣናቸው ለማለት ትችላላችሁ ይሆን በናንተ ሃሳብ አባ ሰላማ እስቲመጣ ድረስ በኢትዮጵያ ስንኳን መጻሕፍት ተጽፈው ሊገኙ ፊደልንም ያሰናዳ ደረጃ የሰጠ አባ ሰላማ ነው እያላችሁ ትጽፋላችሁ። ወረቀትና ቀለም ካልቸገረ በማለት አፋችሁ እንዳመጣ መናገር አስወቃሽ መሆኑን መገንዘብ ነበረባችሁ። ሌላው ይቅርና በግብረ ሐዋርያት የተጻፈውን ባለማስተዋላችሁ በጣም ያስደንቃል። ኢትዮጵያዊ አስቀድሞ ሕገ ግዝረትንና አክብሮ ሰንበትን አዋቂ ሰው የነበረው ሕጽዋ ለቅንዳኪ ንግሥተ ኢትዮጵያ ኢየሩሳሌምን ለመሳለም ሄዶ ሲመለስ መጽሐፈ ኢሳይያስ ሲደግም መገኘቱን በግብረ ሐዋርያት ፰ ፳፯ ፳፰ ፴ ፴፪ ፴፫ የተጻፈውን አታምኑም ይሆንን ወይስ ከነጭራሹም አላያችሁትም ይሆንን። መሆኑንማ እነሱ የጻፉትን ማን ይቃወመናል ብለው አስበውት ነው። በኢትዮጵያ መጻሕተ ብሉያት ካልነበሩ ይህ ኀጽዋ ለቅንድኪ የኢትዮጵያ ንግሥት ሹም መጽሐፈ ኢሳይያስን ማን አስተማረው ብሎ ሰው ቢጠይቃችሁ እንደምን ያለ መልስ ትሰጣላችሁ። ይህ ሁሉ ድካማችሁ እውነቱን ሐሰት ሐሰቱን እውነት እና

# ዜ ሐሙስ

እናደርጋለን በማለት መሆኑን አስቀድሞ ካ፬፻ ዓ ዝምሮ የሠራችሁትን ፖለቲክ ሁሉ በመከታተል የተሰበሰበውን ሁሉ ታሪክ ለመጻፍ ዓምድ አይችለውም። በኢትዮጵያ የሚገኙት መጻሕፍተ ብሉያትና በዓለም ቤተ ክርስቲያን

የሚገኘው ብሉይ ኪዳን የተለያዩ መሆናቸው የታወቀ የተረጋገጠ መሆኑ ያልታወቀ ሆኖ ቢሆን ስብከቱ ምንም ሐሰት ቢሆን ያው ሐሰቱ በእውነት ቦታ ለመቀመጥ ጥርጥር አለነበረም።

በኢትዮጵያ የሚገኙ መጻሕፍተ ብሉያት ልዩነታቸውን እናንተ የሮማ ልዑካን በጣም ታውቃላችሁ። እንደምታውቁት ማስረጃው ስለ አበው ዕድሜና ትውልድ ቁጥር የዓለም ቤተ ክርስቲያን ከተቀበለችው መጽሐፍ የጐደለውን ዘመንና ትውልድ በኢትዮጵያ በሚገኘው ብሉይ ኪዳን አሻሽላችሁ የጻፋችሁት ለንግድና ለስብከት በግዕዝ በሳተማችሁት ብሉይ ኪዳን ኦሪት ዘፍጥረት ፭ ከ፩ እስከ ፴፪ ቢታይ ሁለቱ የተለያዩበት ይገኛል። ፩ኛ አዳም በ፪፻፴ ዘመኑ ሴትን ወለደ ይላል። እንደ ኢትዮጵያዊው መጽሐፍ መሆኑ ነው ይህን ከምን አመጣችሁት። ስለ አበው ትውልድም ፲፩ ፲፪ ወሐይወ አርፋክስድ ፻ ወ፴፭ ዓ ወወለዶ ለቃይናን ይላል። በውጭ አገር ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው ብሉይ ኪዳን በጭራሽ ቃይናንን ከዘመኑ አይጽፈውም የሮማ ልዑካን ከወዴት አመጣችሁት። ያመጣችሁትንማ ከብራና መጻሕፍት ብላችሁ ገልጻችሁት ነበር። የናንተ ነገር ባ፩ድ መቆሙ ችግር ነው እንጅ ለንግዱና ለፖለቲክ መስበኪያ ሲሆን አውቃችሁ የኢትዮጵያ መጻሕፍተ ብሉያት እንደሚሉት በጣም ተስተካክሎ ባይገኝ እንኳ ያነኑ ዘረክራካውን መጽሐፋችሁን ስትጽፉ ነገር ሳይገኝባችሁ አልቀረም ነበር። መግባቱንማ መቸም መንፈሳዊውን ነገር የማትፈልጉ ስለሆነ ሊገባችሁ አለመቻሉን ይህ የተለያየ ሥራችሁ ይገልጸዋል። ከላይ ከኢትዮጵያ መጻሕፍት ከብራናው የተገለበጠ ነው ብላችሁ ብሉይ ኪዳንን ስትጽፉ በኢትዮጵያ እንደሚገኘው ጽሑፋችሁን ስትነግዱበትና ስትሰብኩበት ማለት አሥመራ በታተመው ብሉይ ኪዳን መቅድም በ፪ኛ ገጽ ፫ኛው መሥመር በዝንቱ ግብር ዘዐቢይ ጥብዓት ወዘብዙኅ ፃማ እንዘ ብዙኃ ጊዜ እሬእዮ ወአስተናጽሮ ወአረትኦ። (ይኸውና በብዙ ጥንካሬና ድካም ብዙ ጊዜ እያየሁ እያነጻጸርሁ እያቃናሁ እየተባለ እንደተጻፈ። (ኢያንተጉ ተሥእሎ ምክሮሙ ለዕደው ማዕምራን ዘኢትዮጵያ ወዘኢጣልያን። ይኸውና ኢትዮጵያንና ኢጣልያን የማስተባበር ንግግራቸውን ለመዝራት ከኢትዮጵያና ከኢጣልያ አዋቂዎች ምክር መጠየቄን አላጐደልኩም እያሉ በማስታከክ። ሲሰብኩ ይገኛሉ ኢትዮጵያ በግርማዊ ቀ. ኃ. ሥ. ብርታት የግብጽን እንኳ በኢትዮጵያ ላይ የነበራትን መብት አስወግደው ራስዋን እንድትችል በጥንተ መሠረቷ መሥመር ለመሔድ አብቅተዋት ሲገኙ ዛሬ ደግሞ እንደገና የሮማ ቤተ ክርስቲያን ፓፓ ደግሞ በሌላው በር ለመግባት ምንገዱን ሲያደራጅ በ፳፱ነኛው መሥመር ተጽፎ እንደሚገኘው ክብር አኅትሞቶንኬ ለቅዱሳት መጻሕፍት በምልአን በልሣን ግዕዝ ጽኑሕ ለማኅበረ ሰባክያን ካቶሊካውያን እለ በኤርትራ። በኤርትራ ለሚገኙ ካቶሊኮች መምህራን የቆየ በግዕዝ ቋንቋ የታተሙ ቅዱሳት መጻሕፍት የመታተማቸው ክብር በድልወት ሊሉይ ለክቡር አቡነ ካሚሎ ካራራ ያባ ካሚሎ ካራራ ስለ ማሳተማቸው የክብራቸው ሚዛን ሊሉይ ልዩ ነው ይላሉ ከዚህም አስከትለው በ፫ኛው ገጽ ባ፩ኛው መስመር ዳዕሙ ዝንቱ ግብር ዘጥቀ ኩርህ ለክርስቲያን ዘኢትዮጵያ ዘሠራኀኩ ቦቱ ፺ተ ዓመታት።

# ዝ ዓርብ

በሙብዕስ ወጻዕር እምኢበጽሐሂ ፺ ወኢሂ ኅበ ፍጻሜሁ ሶበ አኮ ጥቀ ክቡር ወልዑል ፒዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘሮሜ ፲፩ በስም ካቶሊካውያን የሚሰብኩበትን የግዕዝ መጽሐፍ እንዲታተም በመፍቀዱ በዚህ ምክንያት አስታኮ ለኢትዮጵያ ኩራት የሚሆናት ስደክም ፺ ዓመት ቆየሁ በጭንቅ በመከራ እያሉ ፖለቲካቸውን ያወራሉ። አሁን እኔ የምመረምረው የሮማው ፓፓ ወደ ፖለቲካቸውን ያወራሉ። አሁን እኔ የምመረምረው የሮማው ፓፓ ወደ ኢትዮጵያ እግሩን ለማስገባት የሚፈልግበትን ምክንያት ለማወቅ ነው በዚህ በመቅድሙ መጨረሻ ተጽፎ እንደሚገኘው አባ ፍራንችስኮስ ዘባሳኖ ዘብሔረ ሮሜ ዘማኅበረ ካፑችኒ። ይላል። ይህ ማኅበር የቆመበትን ሐተታ ባጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ከሽ ፭፻ ፴፪ና ፴፯ ዓ በላይ በአባ ቤርሙዴዝ ካጼ ገላውዴዎስ ተጣልቶ ወደ ሀገሩ ከተመለሰ በኋላ መሆኑን ከላይ በሰፊው ተጽፎ

ይገኛል። እነዚህ የሮማ ሚሲዮኖች ማኅበራቸውን ካቋቋሙ በኋላ በሽ ፳፻፵፰ አጼ ገላውዴዎስ ሊሞት ፪ ዓ ሲቀረው ማለት ነው። ከዚያ በኋላ አጼ ገላውዴዎስ ሲሞት ኢትዮጵያ በእቴጌ ሰብለ ወንጌል ብቻ ፩ ዓ ከቆየች በኋላ አጼ ሚናስ ነግሠዋል። አጼ ሚናስን ቀርበው እየሰበኩ። አጼ ሚናስ እቴጌ ሰብለ ወንጌል እቴጌነታቸውን ሽረው እቴጌነቱን ለሚስታቸው እንዲያደርጉ መከሯቸውና። አጼ ሚናስም እንደሚሲዮኖች ምክር እናታቸውን ሽረው እቴጌነቱን ለሚስታቸው ስለ ሰጡ ይህ ሥራ በኢትዮጵያ መንግሥት ቤተ ሰብዕ ውስጥ አስደንጋጭ እንገር ሆኖ ስለታየ በዚህ ነገር ሕዝቡ በማግመትመት ሲነጋገር ስላ እነዚህ የሮማ ሚሲዮኖች ለ፪ት የተከበሩ ካህናቶች ስለምን ንጉሣችሁን አትገሥጹም አትመክሩም ያለመኳንንቱና ያለ ሊቃውንቱ ፈቃድ ሳይመክር በራሱ ፈቃድ ንግሥቷን ሽሮ ሚስቱን ለመሾም ይችላልን። በኛ ሀገር እንደዚህ ያለ ሥራ አይሠሩም ነበር እያሉ ቢአማከሯችሁ እነዚያም ሊቃውንቶች በሀገራቸው የተለመደውን ሥርዓት ገልጠው ኣኝ በሀገራችን ንጉሥ አስጠቶ ምክር ባቀረበልን ጊዜ እየመጠናችን የተገለጸልንን ምክር እናቀርብና ከዚያው የመረጠውን ይቀበልና ይሠራል እኛ እንደለመድነው ብለው መልስ ቢሰጧቸው። ይህማ ምኑን የመንግሥት ጠብቂዎችና አሳቢዎች ትባላላችሁ ብለው ነገሩን ቀላል አስመስለው። አሁንም እናንተ ሽማግሌዎቹ ጉዳይ አለን ብላችሁ ቀርባችሁ ታላቂቱ ክብርት እናትዎን ሽረው ሚስትዎን ሾሙ አሁንም በዚህ ነገር ሕዝብዎ ተቀይሞብዎታልና አሁንም ሚስትዎን ሽረው እንደ ጥንቱ እናትዎን እንዲሾሙና ሕዝቡን ደስ እንዲያሰኙት ብላችሁ በትነግሩ ምን ይከለክላችኋል ብለው መከሯቸውና እነዚያ ሊቃውንቱም የሚቀርቡበትን ቀን ወደ ንጉሡ መለላክ ሲዠምሩ። ደግሞ እነዚህ ሚሲዮናውያኑ ወደ ንጉሡ ገብተው ፪ቱ ሊቃውንቶች ሕዝቡን አሳድመውበታል። ምክንያቱም እናትዎን ሽረው እቴጌነቱን ለሚስትዎ በመስጠትዎ ነው አሁን ይህን ነገር ለርስዎ ለማስታወስ ያደረሰን እኛ እንደ ሀገራችን ሥልጣኔ እንዲገባ በማለት እቴጌነቱ ለሚስትዎ ቢሆን መልካም ነው ብለን ያመለከትን እኝ ስለነበርን አሁን በዚህ በኛ አሳብ ምክንያት የሕዝቡን ማንጒራጒር ስለሰማን ይህን ጉዳይ ልናመለክትዎ መጣን አሁንም ጳውሊና ዝከሬ የዚህን ነገር ሊገልጹልዎ ሚስትዎን ካልሻሩ ሕዝቡ ተቀይሞብዎታል ብለው ይመጣሉና እነዚህ ዓድመኞች ላይ ትልቅ ቅጣት ካላሳዩ ሕዝቡ

## ፱ ቀዳም

ጒርምርምታውን የሚተው አይደለም ብለው ለንጉሡ ስለመከሩ በምስጋና ተመርቀው ተጋብዘው ለወደፊቱም እንደዚሁ በንጉሡ የሚሠሙትን ነገር ሁሉ እንዲነግሩ ተፈቅዶላቸው ሚሲዮኖች ወደ ማደሪያ ቦታቸው ሄዱ። ከዚህ በኋላ እነዚያ የተመከሩ ሊቃውንቶች ቀርበው ወደ ንጉሱ ንገሩልን ባሉ ጊዜ ንጉሡ አስጠርቶ ቢጠይቃቸው እነዚያ ሚሲዮናውያኑ እንደነገሩት የእቴጌ ሰብለው ወንጌልን መሻር ሲዠምሩ ገና ነገሩን ከመዠመራቸው እስኪጨርሱ ለመቆየት በንጉሡ ላይ ቁጣ ስለተመላበት ፩ዱ እንዲገረፍ ፩ዱ ዓይኑ እንዲጠፋ ትእዛዝ አስተላለፈባቸውና ባ፩ኛው የግርፋት በ፪ኛው ያይኖቹ ጥፋት የፈጸመና ደግሞ እንደገና በነዚህ ሊቃውንቶች እንደዚህ መሆን በሕዝቡ ላይ በኃዘን ላይ ኃዘን ተጨመረበት በዚህ ጊዜ ይህን ስሕተት በማድረጉ ንጉሡ ሳያዝን አልቀረም

እነዚህንም ሚሲዮኖች ችላ እንደማለት ስላላቸው ነገራቸውንም አልቀበላቸው ስላለ እየተዘዋወሩ ነገር እየፈጠሩ ብዙዎችን እየሸፈቱበት የሸፈቱም ሰዎች በሰሜን ተራራ የሚገኙ ፈላሾች ናቸው ከነሱም ሌሊት ከድንኳን ገብተው ሊገድሉ ሲሉ ተይዘው የነበሩ ሰዎች ከመሞታቸው በፊት ሲመረምሩ የሚሲዮኖችን ነገር ምሥጢር ከገለጹ በኋላ ገድለዋቸው ፪ኛም በሐር ነጋሽ ይስሐቅንም እንደዚሁ እየሰበኩ ልቡን ለውጠውበት አገር ላገርም እየሄዱ ያጼ ሚናስን ክፋት ለሕዝቡ እያስጠኑ ስለ አስቸገሩ አጼ ሚናስም ባጼ ገላውዴዎስ ተከልክለው እንደነበር አጼ ሚናስም ባጼ ገላውዴዎስ ተከልክለው እንደነበር

አጼ ሚናስም እንዳይሰብኩ ስለከለከላቸው ወደ ሐማሴን ሔደው ከበሐር ነጋሽ ይስሐቅ ጋር የስብከት ስራቸውን ስለቀጠሉ በዚህ ምክንያት ንጉሡ እንድርያስ አቤዶ የሚባለውን ሚሲዮናዊ አስጠርቶ ፪ኛ ለሕዝቡ እንዳይሰብክ ቢከለክለው እሱም ስለ ሃይማኖቴ እሞታለሁ እንጅ ሥራዬን ስብከቴን አልተውም ብሎ መልስ ስለሰጠ አጼ ሚናስም ተቆጥቶ ጢሙን ይዛችሁ ጐትቱና አምጡት ብሎ አዘዙና በግዞት አስቀመጡት ከትንሽ ቀን በኋላ ከግዞት ቤት አምልጦ ወደ ባሕር ነጋሽ ሄዶ ተደባለቀና በሐር ነጋሽ ይስሐቅን ከቱርክ ኮንስል። ጋራ አስማማው በመጨረሻው አጼ ሚናስ ከበሐር ነጋሽ ይስሐቅ ጋር ተዋግቶ ድል አደረገ። ሚሲዮናዊያኑም ሸሹ።

እንደዚህ እየሆነ ባጼ ሚናስና በሚሲዮኖቹ በኩል ቂሙ እየበርከተ ስለሄደ አጼ ሚናስ ባለፈው በሚሲዮናውያኑ ሥራቸው ስለ ተጸጸቱ ያንን ዓይኑን ያስጠፉትን ካህን ከዘወትር ማዕዱ ከግብር እንዳይለይ አድርጎለት ዘወትር ሳይለይ ዓይነ ሥውሩ እየመረቀ ራትና ምሳውን በክብር ሲመገቡ እነዚህ ሚሲዮናውይኑ ባዩት ጊዜ መቸም ሰውን ለማጋጨት ከትምህርታቸውም በላይ ዋና ሥራ አድርገው የያዙት ስለሆኑ የተመቸ መግቢያ አገኙና ዓይነ ሥውሩን ቀርበው ወዳጅ አደረጉና በማነኛውም ስለ ዓይኑ ጉዳይ ያዘኑ እየመሰሉ ልብስና ገንዘብ እየሰጡ አስለምደው በጣም የልብ ወዳጅ አደረጉትና ምሥጢርም ለመገላለጥ ከቻሉ በኋላ የኢትዮጵያን መነኰሳት የሚአጠፉበት ዘዴ ፈጥረው ለዓይነ ሥውሩ ያስጠኑት ጀመር። ባሕታውያኑን መነኰሳት በጣም ይጠሉ ስለነበር ነው። ምክንያቱም ባሕታውያኑ ወደ አጼ ሚናስ እየመጡ በጥብቅ ምክር ከካቶሊካዊ ወደ ኦርቶዶክስ እዲጸና ስላደረጉባቸው ነው። ምክንያቱም ባሕታውያኑን ወደ አጼ ሚናስ እየመጡ በጥብቅ ምክር ከካቶሊካዊ ወደ ኦርቶዶክሳዊ እንዲጸና ስላደረጉላቸው ነው። ካቶሊካዊን ስብከት በጭራሽ ስለከለከለ ስለተናደዱ ይህን ዓይነ ሥውር ሰብከው ረቂቅ ፖለቲክ ፈጠሩ ይህንም ረቂቅ ፖለቲክ ሲሠሩ ለዓይነ ሥውሩ የተቆረቁሩ መስለው ነው።

# የ እጎድ

ነገሩም እንደዚህ ነው ወደ ንጉሡ ቀርቦ የሚናገረውን ሲአስተምሩት ወደ ንጉሡ በቆይታ ቅረብና እንደዚህ በለው ንጉሥ ሆይ በየቀኑ የምታደርግልኝ ውለታ በጣም ከበደኝ ፩ድ ቀን በገዛ ጥፋቴ ስንኳን ዓይኖቼንና የሠራ አካላቶቸን ሁሉ እየቆረጥክ በትጥል ከእግዚአብሔር ተሰጥቶሃል ማን ይከለክልህ ነበር ስለዓይኖቼ መጥፋት ዘወትር በጠጅና በጮማ ታቀማጥለኛለህ ሁለት ዓይን ያላቸው ሰዎች ሁሉ የማያገኙትን እየተመገብሁና እየጠጣሁ እየለበስሁ በጌትነት እኖራለሁ አሁን በሌትና በቀን ባስብ ለጌታዬ ውለታ ስመረምር ለጌታዬ አጣሁ ዓይን ስለሌለኝ እዚሁ ሆኘ በሐሳቤ ብቻ ስመረምር ለጌታዬ ያልታወቀ ፩ድ ነገር አገኘሁ ነገሩም እንደዚህ ነው በጌታዬ ዘመነ መንግሥት ማነኛውም ሰው ሁሉ ተገዝቶ ይገብራል። ከሁሉ ተለይቶ ፩ድ ነገር አለ ይህም የሀገራችን መነኰሳት ነገር ነው በሀገራችን ላይ ብዙዎች መነኰሣት ይገኛሉ። ዝም ብለው ጨርቁን እያሰፉ ቆብ ነው እያሉ እራሳቸውን እየሸፈኑ ለመንግሥት ግብር አይገብሩ እንዲሁ እየዞሩ የማንንም እየበሉ የማንንም ሚስት እያማገጡ ይኖራሉ። ለእግዚአብሔርና ለንጉሥ የማይገዙ እነዚህ ናቸውና ፩ድ ብልሃት አድርግላቸው ምናልባት ከነዚሁ ውስጥ እውነተኞች መነኰሳት ይኖሩ ሥውሩም አስቀድሞ ነገሩን ያጠናው ስለሆነ በፍጥነት ነገሩን ተቀብሎ ንጉሥ ሆይ ብዙ ሕዝብ ለሚስቱ ጠባቂ የለውም እኒሁ መነኰሳት ነን የሚሉቱ ከሴቶች ጋራ ነው የሚውሉ ለዚሁም ምልክት አለው የእውነተኛዎቹ መነኰሳት ብልታቸው ጠጉሩ ያልተላጨ ሆኖ ይገኛል የሀሰተኞቹ መነኰሳት ግን ብልታቸው የተላጨ ሆኖ ይገኛልና መነኰሴ ነኝ የሚለውን ሰብስበህ ወታደር በድንገት ይፈትሸውና ደህነኛው ወደ ገዳሙ ይሄዳል ወስላታው ግን ሌላ ሥራ ተፈልጐለት በየሥራው እንዲገባ ብታደርግ መንግሥትህ በጣም ይስፋፋልሃል ብየ ይህን አሳብ ላመለክትህ ካሰብኩ ብዙ ቀኖች አልፈውብኛልና አሁንም ይህን ነገር በቶሎ እንዲፈጸም እንድታደርግ አሳስባለሁ ብሎ አመለከተና በማሰቡ ተመሰገነና ወደ ቤቱ እየተመራ ሄደ። ንጉሡም ይህ ረቂቅ ፖለቲክ የመጣበትን ባለማወቅ ሳይጠራጠር ነገሩ እውነተኛ መስለውና በኢትዮጵያ የሚገኙ

መነኰሳት እንዲሰበሰቡ በዓዋጅ አዘዘ። መነኰሳቱም ወደዚያው በከተማው ባለመግለጹ ደስ አያሰኝም። ይህ የሆነበት ቦታ ታውቆ ቢሆን መልካም ነበር። የንጉሡም የወታደር አለቆች አስጠራና ይህን የተሰበሰበ መነኰሴ ሁሉ በወታደር አሰብስባችሁ የመነኰሴውን ሁሉ ብልት እየገለጣችሁ እያያችሁ በብልቱ ጠጉር ያለበትን ለብቻ የሌለበትን ለብቻ አድርጋችሁ ንገሩኝ ብሎ ትእዛዙን በሰጠ ጊዜ በፍጥነት ወታደሩ መነኰሳቱን በከበበ ጊዜ መነኰሳቱ ሁሉ በቅጽበት በድንጋጤ አእምሮአቸው ተለወጠ የደነገጡበትም ምክንያት አጼ ሚናስ በካቶሊክ ጳጳስ ተሰበከ እየተባለ ሲወራ ይሰሙ ስለነበረ ባዋጅ በተሰበሰበት ወታደር ሲከባቸው ባዩ ጊዜ መነኰሳቱ ፈጽመው ሕይወታቸውን ለሞት አሳልፈው እንደሰጡ ቆጠሩትና ወታደሩ በታዘዘው መሠረት ዕርቃናችሁን ገልጠን እንይ እያለ በቀረባቸው ጊዜ መነኰሳቱ በመንፈስ ቅዱስ በነደደ ጭካኔ ስለተመሉ እኛ የምንሰየፍ እንገታችንን ነው እንጅ ብልታችንን እይደለም እያሉ የወታደሮችን ትእዛዝ

# ፱ ሰኑይ

የማይፈጽሙ ስለሆነ ወታደሮቹ በመነኰሳቱ ላይ በኃይል ተነሥተው በግድ እየገለጥን እናያለን ሲሉ መነኰሳቱም አናሳይም ሲሉ ከፍ ያለ ጩኸትና ድብልቅልቅ ሆነ ከመነኰሳቱም ውሥጥ ግማሹ በወገቡ የብረት ሠቅ የታጠቀ ግማሹም በወገቡ በገመድ የተጠመጠመበት። በግማሹ በወገቡ በደረቅ ቆዳ የታሰረ ስለሆነ ያ ሁሉ ይህን መገለጥ የማይወድ ስለሆነ ይልቁንም በብረት ሠቅ የታጠቁትን ወዲያና እዲህ ሲጎትታቸው በወገባቸው ያለው ብረት ያን ሲቆስል የኖረውን አካላታቸውን እየቆረጠ ስለጣላቸው መነኰሳቱ የነበሩበት ቦታ በደም ስለተጨማለቀ ወታደሮቹ የደሙን ብዛት ባዩ ጊዜ በደሙ ብዛትና ደሙንም

በመጥላት ከመነኮሳቱ መካከል ለመውጣት ቻሉ በዚያች ቀን ብዙዎች መነኰሳት እዚያው አርፈዋል ደገግሞ ግማሾቹ ወደ ሀገራቸው ሲሄዱ በመንገድ አርፈዋል። በዚያች ቀን ከፍ ያለ ልቅሶ ባጼ ሚናስ ላይ ተለቀሰ ይህንም ፖለቲክ ስለ ዓይኑ በቀል ዕውሩ ባጼ ሚናስ ላይ እንደዚህ ያለ ሥራ ሠራባቸውና በመነኰሳቱ ልቅሶ ምክንያት ያጼ ሚናስ ዕድሜ አጠረ እየተባለ የሚተረከውን ለውጦ ውስጥ ዓዋቂ ነኝ የሚል ጸሐፊ ሚሲዮናውያንን የታሪክ ሙያ ሲጽፍ ለዓይነ ዕውሩ ይህን ፓለቲክ ያስተማሩት ሚሲዮኖች ናቸው ብሎ ሚሲዮኖች እንደሆኑ አስረድቶ የጻፈው ይገኛል። አሁን እስከዚህ ያደረሰን የሮማው ፓፓ እግሩን ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ሲሞክር ስላዩሁት ነገሩን ካባ ቤርሙዴዝ ዠምሬ ለማምጣት ስፈልግ የልዑካን ባጼ ሚናስ ብቻ የሠሩትን ለሰሚ ይድነቀው በማለት ላንባቢዎች ገልጬላቸዋለሁ። አሁን ወደ ተነሣንበት ወደ መጻሕት ብሉያት እንመለስ የሮማ ልዑካን አሳብ አስቀድመው ባደራጁት መሠረት መንፈሳውያን መስለው መጥተው ውስጥ ለውስጥ ኢትዮጵያን በሚለያይ የሐሰት ስብከታቸው የኢትዮጵያን ሕዝብ በደግነቱ ስለተቀበላቸው የመንግሥት ሰማያት ቁልፍ ጌታችን ለቅዱስ ጴጥሮስ ነው የሰጠው እኛም የቅዱስ ጴጥሮስን መክፈቻ ይዘናልና እኛ መንግሥተ ሰማያት እናስገባችኋለን እያሉ ይሰብካሉ የሮማ ልዑካን መምጣት ከዠመሩ ወዲህ በኢትዮጵያ ላይ የሰንት ሕዝብ ደም ፈሰሰ ምናልባት ከዚያ ዠምሮ እስከ ሽ፱፻፴፮ ዓ.ም በግምት ከሚሊዮን በላይ መሆኑን ማንም አይስተውም የሮማው ፓፓ የመንፈሳዊ ልብስ ለብሶ ወደ ኢትዮጵያ እግሩን ለማስገባት ሲሞክር የሚታየው በዚህ የሚሊዮን ሰው ደም በፈሰሰበት ምድር ላይ ቤተ ክርስቲያን ሠርቻለሁ በማለት ነው። ይህ ነገር እውነት ለመባል የሚያስችለው የትኛው መንፈሳዊ ሥራ ይህን በኦሪቱ መቅድም በ፪ኛው ገጽ በ፳ኛው መሥመር ሶበ ልሳነ አምኃራ ህየንተ ቀዳማዊ ሰፈነ ውስተ ቤተ መንግሥት ወውስተ ምግብና ፩ዱ ፩ዱ ሰብዓ ብሔር ጥቀ ማዕምራን ወጠኑ ያዕልው ቅዱሳተ መጻሕፍተ እምልሳነ ግዕዝ ኀበ ልሳነ አምኃራ። ወለዝኒ ግብር አኀዙ ይፈጽምዎ ኢየሱሳውያን እለ መሐሩ ወንጌለ ለሰብዓ ኢትዮጵያ እመ ፲ወ፫፻ት ፺ወ፮ ዓ.ም እስከ ፩ሽ፮፻ ዓ.ም በሽ፫፻፵፯ ያለው በፈረንጅ ማለቱ ነው

በኢትዮጵያ ቁጥር ሽ፫፻፵፫ ዓ.ም ማኅበሩ የቆመበትን ማለቱ ነው እስከ ሽ፬፻፴፪ እስከ አጼ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ማለቱ ነው። ወጠኑ ያዕልው መጻሕፍተ እምልሳነ ግዕዝ ያለው

## ዩ ሠሉስ

# ፫ኛ ክፍል ነሐሴ

ከግዕዝ ወደ አማርኛ መተርጐም ተዠመረ ማለት ነው። ይህንም ያማርኛ ማስተማር ኢየሱሳውይና የሮማ ልዑካን አስፋፉት አያለ የሐሰት ወሬውን በኢትዮጵያ ወንጌልን የሚሰብኩ እያለ ያወራል። የወንጌል ስብከት ሆነ ምክንያቱን ወንጌል እንሰብካለን እየተባለ መጻሕፍቱ በግዕዝ እየታተሙ ለንግድና ለስብከት ሲደራጁ መጻሕፍተ ብሉያትን እንደ ኢትዮጵያዊው ብሉይ ኪዳን ጽፈው ሲነግዱበት ከቆዩ በኋላ ደግሞ ባንድ ወገን በኢትዮጵያ አስቀድሞ መጻሕፍተ ብሉያት ከጽርዕ ቋንቋ በአባ ሰላማ ተገልብጦ መጣ ይላሉ። የሮማውያን አሳብ የኢትዮጵያን ጥንታዊ መሠረቷን እያጠፉን ስንጽፍ ማነኛውንም ዓለም የሚገኘውን ታሪክ እየተከተሉ ይለምዱትና በኛ ሀሳብ ለመሄድ ይችላሉ በማለት አሳባቸውን በዚህ ወስነው ስለተነሡ የኢትዮጵያን ታሪክ ክብራና መጽሐፍ አገኘነው እያሉ በፈረንሳዊ ጽሑፍ እያሳተሙ ለዓለም ባለታሪኮች ሁሉ ስለ አስተላለፉት ያነን መሠረት የሌለውን ጽሑፍ የሌላው አገር ሰው ይቅርና የኢትዮጵያ ልጆች እንኳ እውነት እየመሰላቸው ያነን እየገለበጡ ለወጣቶች ሲያቀርቡ ይገኛሉ። በፍጹም የነሱን ስብከት ተቀብለው የጥንታዊውን ታሪክ ነገር ለመንገር በተዠመረላቸው ጊዜ እጅና እግር የሌለው ክርክር አቅርበው ዦሮአቸውን ይዘጋሉ። እንደዚህ እየሆነ ስብከታቸው ሲስፋፋላቸው ስላዩ የኢትዮጵያ መሠረት እስከ ሳብዕ ያሰናዳ አባ ሰላማ ነው እያሉ ያለ ኀፍረት በድፍረት ጽፈው ይገኛል። ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ

ወጣቶች በዚህ ካባ ጋስፓሪን በተገኘው ማታለያ የፖለቲክ ጽሑፍ በጣም ጠቃሚ ነገር ያገኙ ስለመሰላቸው ያነን ጽሑፍ በፍጥነት ሲካፈሉት ባየሁ ጊዜ በሸ፱፻፵፫ በኅዳር ፫ ቀን ካዲስ አበባ ወደ አሥመራ ሄጄ ምናልባት ለተጻፈው ታሪክ መደገፊያ የሚሆን በታላላቆቹ ገዳማት አግኝተው እንደሆነ በማለት በታላላቆቹ ገዳማት እንደተቻለኝ እየተዘዋወርኩ ከመረመርኩ በኋላ የነሱን ታሪክ የሚደግፍ ጥንታዊ ጽሑፍ ሳላገኝ ስለቀረሁ ወደ ግርማዊነታቸው እንደራሴ ጽሕፈት ቤት ስለዚህ ታርክ ጽሑፍ ጥያቄ አቀረብኩ ለጊዜው በፊት የታተመው አልቆ ፪ኛው ሊታተም ይሰናዳ ነበርና ያ መታተሙ እንዲቆይ የተደረገ መሠለኝ እንጅ ለጊዜው አባ ጋስፓሪንን ከኔ ጋራ ለማከራከር ሳይሆን የጽሑፉን ጉድለት በጋዜጣ እንድገልጽ የሚአሳይ አሳብ ከጽሕፈት ቤቱ ስላገኘሁ እኔም ከአዲስ አበባ በሄድሁ ባ፮ ወሬ በመጋቢት ወር መጨረሻ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ ከሰኔ የዚህን ጽሑፍ ምርመራ ይዠ ስደክም ከሕማሜ ጋራ እየታገልኩ ከሰኔ ዠምሬ እስከ ኅዳር ፴ ቀን ፻፶፮ኛው ገጽ ላይ ነኝ። እኔ ብሞትም ይህን ጽሑፍ በታመነ ሰው እጅ ሆኖ ለኢትዮጵያ ማገልገያ እንዲሆን ስል ነው። የፈጣሪዬ ፈቃዱ ቢሆን ለመፈጸም ያበቃኛል በተረፈም ለሀገሬ ይህን ፻፶፮ ገጽ በተቻለኝ ጽፌላታለሁ። አሁን ወደ ስረ ነገሩ እንመለስ በኢትዮጵያ መጻሕፍተ ብሉያት አልነበሩም እያሉ የማታለያ ጽሑፋቸውን እየዞሩ ስለሚአስቸግሩ ከላይም ስለመጻሕፍተ ብሉያትና ስለ ፊደል መሠረት ጽፌአለሁ አሁንም ደግሞ ስለ መጻሕፍተ ብሉያት ማስረጃዎች አቀርባለሁ የዓለም ቤት ክርስቲያን የተቀበለችው ብሉይ ኪዳንና በኢትዮጵያ የሚገኙ መጻሕፍቶች የተለያዩ ባይሆኑ እውነትም እንደ ሮማውያን አሳብ ለማድር በተመቸ ነበር።

## ያ ረቡዕ

| በኢትዮጵያ የሚገኙ መጻሕፍተ ብሉያት | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ | አዳም | በ፪፻፴ ዘመኑ | ሴትን ወለደ |
| ፪ኛ | ሴት | በ፪፻፭ ዘመኑ | ሄኖስን ወ |
| ፫ኛ | ሄኖስ | በ፻፺ ዘመኑ | ቃይናን ወ |
| ፬ኛ | ቃይናን | በ፻፸ ዘመኑ | መላልኤልን ወ |
| ፭ኛ | መላልኤል | በ፻፷፭ ዘመኑ | ያሬድን ወ |
| ፮ኛ | ያሬድ | በ፻፷፪ ዘመኑ | ሄኖክን ወ |
| ፯ኛ | ሄኖክ | በ፻፷፭ ዘመኑ | ማቱሳላን ወ |
| ፰ኛ | ማቱሳላ | በ፻፷፯ ዘመኑ | ላሜኅን ወ |
| ፱ኛ | ላሜህ | በ፻፹፪ ዘመኑ | ኖኅን ወ |
| ፲ኛ | ኖኅ | በ፭፻ ዘመኑ | ሴምን ወ |
| ፲፩ኛ | ሴም | በ፻፪ ዘመኑ | እርፋክስድን ወ |
| ፲፪ኛ | አርፋክስድ | በ፻፴፭ ዘመኑ | ቃይናንን ወ |
| ፲፫ኛ | ቃይናን | በ፻፴ ዘመኑ | ሳላን ወ |
| ፲፬ኛ | ሳላ | በ፻፴ ዘመኑ | ዔቦርን ወ |
| ፲፭ኛ | ዔቦር | በ፻፴፬ ዘመኑ | ፋሌቅን ወ |
| ፲፮ኛ | ፋሌቅ | በ፻፴ ዘመኑ | ራግውንና ዮታግን ወ |
| ፲፯ኛ | ራግው | በ፻፴፪ ዘመኑ | ሴሩህን ወ |
| ፲፰ኛ | ሴሩህ | በ፻፴ ዘመኑ | ናኮርን ወ |
| ፲፱ኛ | ናኮር | በ፸፱ ዘመኑ | ታራን ወ |
| ፳ኛ | ታራ | በ፸ ዘመኑ | አብርሃምን ወ |
| ፳፩ኛ | አብርሃም | በ፻ ዘመኑ | ይስሐቅን ወ |
| ፳፪ኛ | ይስሐቅ | በ፷ ዘመኑ | ያዕቆብን ወ |
| ፳፫ኛ | ያዕቆብ | | |

**የዘመን ድምር ፫ሺ፹፬**

## በዓለም ቤተ ክ የሚገኙ መጻሕፍተ ብሉያት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ | አዳም | በ፻፴ ዘመኑ | ሴትን ወለደ |
| ፪ኛ | ሴት | በ፻፭ ዘመኑ | ሄኖክን ወ |
| ፫ኛ | ሄኖክ | በ፺ ዘመኑ | ቃይናንን ወ |
| ፬ኛ | ቃይናን | በ፸ ዘመኑ | መላኤልን ወ |
| ፭ኛ | መላዕልኤል | በ፷፭ ዘመኑ | ያሬድን ወ |
| ፮ኛ | ያሬድ | በ፷፪ ዘመኑ | ሄኖክን ወ |
| ፯ኛ | ሄኖክ | በ፷፭ ዘመኑ | ማቱሳላን ወ |
| ፰ኛ | ማቱሳላ | በ፹፭ ዘመኑ | ላሜህን ወ |
| ፱ኛ | ላሜህ | በ፹፪ ዘመኑ | ኖኅን ወ |
| ፲ኛ | ኖኅ | በ፹፪ ዘመኑ | ሴምን ወ |
| ፲፩ኛ | ሴም | በ፭፻ ዘመኑ | አርፋክድስን ወ |
| ፲፪ኛ | አርፋክስድ | በ፻ ዘመኑ | ሳላን ወ |
| ፲፫ኛ | ሳላ | በ፴፭ ዘመኑ | ዔቦርን ወ |
| ፲፬ኛ | ዔቦር | በ፴፬ ዘመኑ | ፋሌቅን ዮታግንን ወ |
| ፲፭ኛ | ፋሌቅ | በ፴ ዘመኑ | ራግውን ወ |
| ፲፮ኛ | ራግው | በ፴፪ ዘመኑ | ሴሩህን ወ |
| ፲፯ኛ | ሴሩህ | በ፴ ዘመኑ | ናኮርን ወ |
| ፲፰ኛ | ናኮር | በ፳፱ ዘመኑ | ታራን ወ |
| ፲፱ኛ | ታራ | ፸ ዘመኑ | አብርሃምን ወ |
| ፳ኛ | አብርሃም | በ፻ ዘመኑ | ይስሐቅን ወ |
| ፳፩ኛ | ይስሐቅ | በ፷ ዘመኑ | ያዕቆብን ወ |
| ፳፪ኛ | ያዕቆብ | | |

**የዘመን ድምር ፩ሺ፯፻፹፩**

## ዬ ኃሙስ

ይህን ያህል የዘመንና የትውልድ መለያያ የለበትን መጽሐፍ ተሸክመው ይህን እንኳ አስተውሎና መዝኖ ማየት አቅቷቸው ፸፪ ሊቃውንት የጻፉትን ነው የዓለም ቤተ ክርስቲያን የተቀበለችው እያሉ ያለ ትንሽ ኅፍረት ሲአወሩና ሲጽፉ ይገኛሉ። ለመሆኑ ፸፪ ሊቃውንት ጻፉት የተባለው መጽሐፍ ወዴት አለ። ወይም ፸፪ ሊቃውንት ጽፈውት የነበረው አሁን ከላይ ተጽፎ የማይታየው በዘመንና በትውልድ ጐድሎ የሚገኘውን ጻፉት ለማለት ይሆንን። የሮማ ልዑካን ያለው የጦር ፕሮፓጋንድ ባልደረባ ወታደርነቱ እየጠቀሳችሁ ነው እንጅ ይህ ዛሬ በዓለም ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ከልደተ ክርስቶስ ከ፮፻ና ከ፯፻ ዘመን በላይ የዓለም ቤተ ክርስቲያን መስፋፋት ከዠመረች በኋላ ስለ መጻሕፍተ ብሉያት ጠይቀው አይሁድም የጌታ መወለጃ ገና ዘመኑ አልደረሰም ስለሚሉ ከላይ ባንድ ጐን እንደተጻፈው መጻሕፍተ ኦሪትን እንደገና የአበውን ዘመንና ትውልድ ቁጥሩን ቈንጽለው ብዙዎችንም መጻሕፍቶች አውጥተው ጥለው ደግሞ ከውስጡ ኃይለ ቃል ያለበትን ሁሉ ቈንጽለው እንደገና ሌላ መጽሐፍ የቀድሞውን አስመስለው ቢሰጧቸው ተቀብለው ይዘው ይኖራሉ። እንጅ። ዋናው ቁርጠኛው ነገር የዓለም ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ከኢትዮጵያ በተቀር ከልደተ ክርስቶስ በኋላ ከአይሁዶች እጅ ተቀበለች እንጅ ከግሪኮች እጅ አልተቀበለችም ከግሪኮች እጅ በፅርዕ ልሳን ከተጻፈ ብሉይ ኪዳንን ተቀበልን ለማለት ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ይቆዩና የሮማ ቤተ ክርስቲያንም ብሉይ ኪዳንን ከጽርዕ ተቀበልኩ አትልም። አሁንም ብትጠይቁ እርግጡን ለማግኘት ትችላላችሁ። የቤተ ክህነት ሰዎች አለመሆናችሁን ይህ ሥራችሁማ ይመሰክርባችኋል። ይህም ፩ድ ተብሎ ይቆጠራል። ፪ኛ ከልደተ ክርስቶስ በኋላ ከአይሁድ እጅ በተቀበልነው ብሉይ ኪዳን የጐደለ ቃል የለበትም ለማለት የምታስቡ እንደሆነ ጉድለቱን የሚአስረዳ ፩ኛ ስለ ትውልድ ቃይናንን በዓለም ቤተ ክርስቲያን በተቀበለችው ከላይ ግራና ቀኝ ተጽፎ እንደሚታየው በኢትዮጵያዊው ብሉይ ኪዳን ቃይናን ይገኛል። በዓለም ቤተ ክርስቲያንና በዓለም ቤተ ክርስቲያን ብሉይ ኪዳን ክርክር ባደረጉ ጊዜ ቅዱስ ሉቃስ ለኢትዮጵያዊው ብሉይ ኪዳን መስክሮ ተገኘ። ሉቃስ ፫ ፴፮ ቃይናን አርፋክስድ ሲል ይገኛል። ለምስክርነት ይህም ብቻ በበቃ ነበር። ግድ የለም እጨምራለሁ። በኢትዮጵያው ብሉይ ኪዳን ቅዱስ ዳዊት በጻፈው መዝሙር ፪። የኢትዮጵያው ብሉይ ኪዳን ትንቢት በእንተ ክርስቶስ ይላል። ያዓለም ቤተ ክርስቲያን ብሉይ ኪዳን በእንተ ክርስቶስ ማለቱን ትቶ መዝሙር ብቻ ይላል። ስለዚህ ሁለቱ መጻሕቶች ክርክር ባደረጉ ጊዜ ለኢትዮጵያው ብሉይ ኪዳን ሐዋርያት መስክረው ይገኛል። ግብረ ሐዋርያት ፬ ፳፭ ዘለሊከነበብከ በመንፈስ ቅዱስ በአፈ ዳዊት ግብርከ አቡነ ወትቤ ለምንት አንገለጉ አሕዛብ ወሕዝብኒ ነበቡ ከንቶ ፳፮ ወተንሥኡ ነገሥተ ምድር ወመላእክትኒ ተጋብኡ ምስሌሆሙ ኅቡረ ላዕለ እግዚአብሔር ወላዕለ

መሢሁ ፳፯ አማን አንገለጉ በዛቲ ሀገረ ላዕለ ቅዱስ ወልድከ ኢየሱስ ዘቀባዕካሁ። እንደዚህ አስተካክለው መስክረዋል። ፫ኛ በኢትዮጵያው መዝሙረ ዳዊት ፺፮ኛው በሌሎቹ መዝሙረ ዳዊት ፺፯ በ፯ኛው ቁጥር ስለ ክርስቶስ መላእክት እንዲሰግዱ የተነገረውን ትንቢት ለውጠው አማልክት ሁሉ ሰገዱለት ብለዋል። ይህንም ቅዱስ ጳውሎስ መልከተ ዕብራውያን ፩ ፮ ወአመፈነዎ ለበኵሩ ውስተ ዓለም ይቤ

## ይ ዓርብ

ይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ መላእክተ እግዚአብሔር ብሎባዋል። ይህም እንደ ኢትዮጵያው መጽሐፍ ወይሰግዱ ሎቱ ኵሎሙ መላእክቲሁ እንዳለው ቅዱስ ጳውሎስ ማረጋገጡን መገንዘብ ነው ፬ኛ ከላይም ተጽፎ እንደ ሚገኘው በኢትዮጵያው መዝሙር ፲፫ በነሱ ፲፬ኛውን መዝሙር ይብል አብድ ከሚለው ካ፬ተኛው ቁጥር እስከ ፳ ያለውን ፳ቱን መሥመር ከመ መቃብር ክሡት ጐራዒቶሙ ወጸልሐው በልሳናቲሆሙ ኅምዝ ዓርዌ ምድር ታሕተ ከናፍሪሆሙ መሪር

አፉሆሙ ወምሉዕ መርገመ ፯ ለሊህ እገሪሆሙ ለክዒወ ደም ኃሣር ወትጥቃጤ ውስተ ፍኖቶሙ ወኢየአምርዋ ለፍኖተ ሰላም ፰ ወአልቦ ፍርሃተ እግዚአብሔር ቅድመ አዕይንቲሆሙ እነዚህን መሥመሮች ኃይለ ቃል ያለባቸው ስለሆኑ አይሁድ ፍቀዋቸው የዓለም ቤተ ክርስቲያን በተቀበለችው ብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለማይገኙ ይህን የአይሁድን ተንኮል በመንፈስ ቅዱስ ስላወቀ። በሮሜ መልእክቱ ፫ ፲ በከመ ይብል መጽሐፈ አልቦ ጽድቅ ፲፩ ወአልቦ ዘየሐሥሦ ለእግዚአብሔር ፲፪ ኵሉ ዓረየ ወኀቡረ ዓለወ ወአልቦ ዘይገብራ ለሠናይት ወኢ ፩ዱ ፲፫ ከመ መቃብር ክሡት ጕራዒቶሙ። ወፀልሐው በልሳናቲሆሙ ኅምዘ ዓርዌ ምድር ታኅተ ከናፍሪሆሙ።

፲፬ መሪር አፉሆሙ ወምሉዕ መርገሙ ፲፫ በሊህ እገሪሆሙ ለክዒወ ደም ፲፮ ኃሣር ወቅጥቃጤ ውስተ ፍኖቶሙ ፲፯ ወኢየአምርዋ ለፍኖተ ሰላም። ፲፰ ወአልቦ ፍርሃተ እግዚአብሔር ቅድመ አዕይንቲሆሙ። ከላይ እንደተጻፈው ቅዱስ ጳውሎስ የሁለቱን መጻሕፍቶች ክርክር እንደዚህ አድርጎ ሲለይ ይህም ላስተዋውለውና ለመረምረው ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ታሪክ መጻሕተ ብሉያትንና ጽላተ ሙሴን አክብራ ማለት አምልኮ ባዕድን አርቃ ሕገ እግዚአብሔርን አጥብቃ ፬ሺ፭የ፵ ዘመን በነጻነቷ ፀንታ ቋንቋዋ ሳይለወጥ መንግሥቷ ሳይገለበጥ ከወሰኖቿ እንኳ መቀነስ ዛሬ አነሰ ብላ ብትታይ እንደዚህ ከላይ እንደተገለጸው ሐዋርያትና ቅ. ጳውሎስ የሚመሰክሩላቸውን መጻሕፍቶች ይዛ በመገኘቷ ይህ ታሪኳ በዓለም ራስ ላይ የሚደረግ የታሪክ ዘውድ ዓላት ለማለት የሚአስደፍር ነበር። የኢትዮጵያን ታሪክ በመሰርሰር ዘለዓለም በገንዘብ እያታለሉ ውስጥ ለውስጥ ሰባኪዎች የኢትዮጵያን መሠረት ለማናወጽ ይፈልጋሉ ከንቱ ድካም ነው። ኢትዮጵያ እንደሆነች የአልማዝ ድንጋይ ናት። ስለዚህ ማቴዎስ ፳፩ ፵፬ ወዘሰ ወድቀ ዲበ ይዕቲ እብን ይትቀጠቀጥ ወለዘሂ ወድቀ ዲቤሁ ይደምቆ። ይደምቆ ማለት ይጨፈልቃል ነው። ስንኳንስ አስባ ተነሥታና አስቦ ተነሥቶ መጥቶ በላይዋ የወደቀውንም እየሰበረች እንደምትመልሰው ልብ ማድረግ የሮማ ልዑካን ነን እያላችሁ የምትሠሩት ሥራ የሮማን መሠረት የሚአፈርስ መሆኑን ማስተዋል አለባችሁ። ይህም የምትሠሩት ሥራ ቢዘገይም የሚቀር እንዳይመላችሁ። ማቴዎስ ፯ ፩ ኢትኰነኑ ከመ ኢትትኰነኑ ፪ እስመ በኵነኔ ዘኰነንክሙ ትትኰነኑ አንትሙ ወበመስፈርት ዘሰፈርክሙ ይሰፍሩ ለክሙ ያለውን ማስተዋል አለባችሁ የኢትዮጵያ መጻሕፍት የሚነቀፉና የሚናቁ አይደሉም ይልቁንስ መጻፍቶቿ ጥንታውያኑን ጽሑፎች ይዛ በመገኘቷ ከፍ ያለ ምሥጋና ይገባት ነበር። ያ ቢቀርባትም ምንም ያማርኛ ትምህርት ቤቶች ቢስፋፉም ገና ግዕዝ አዋቂዎች ተጨርሰው ሳይጠፉ የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል እንደሚባለው ተረት ገና ሊቃውንቱ ሳያልቁ የኢትዮጵያን መጻሕፍት የሚደመስስ መጽሐፈ ሐሰት በመጻፉ የሚአስደንቅ ስለሆነ

## ዮ ቀዳም

እንግዲህ ወደ ሥሩ እንመለስና ያነኑ የሐሰት ሐተታ እንመልስ። ከላይ እንደተጻፈው በ፱ነኛው ገጽ ዝምሮ እስከ ፲፬ መሥመር በተጻፈው ኩሳ እየተባለ በእብራይስጥ የተጻፈውን ጽርዓውያን ሲተረጉሙ ኢትዮጵያ እያሉ የጻፉት ፸ ሊቃውንት ናቸው ብለው። ደግሞ ከግሪክ ወደ ግዕዝ የተረጐሙ ሰዎች ኢትዮጵያ አገሯን ኢትዮጵያዊ ባለ አገሩን አድርገው እንደዚያው ተርጉመውታል ካሉ በኋላ ባ፲፫ኛው መሥመር ኩሽ ከሚለው ቃል የሚሰሙት በግብጽ ደቡብ የሚገኙትን ሰዎቹን አውራጃዎች ነው ፩ድ ፩ድ ጊዜም በልዩ የግብጽ አዋሳኝ የሜርዊን መንግሥት ያመለክቱበት ነበር ይላሉ። አሁን ለተጻፉ ነገሮች እንደዚህ ያለ ማስረጃ ጽሑፍ አለ የሚል የለበትም። እንዲሁ እንደትእዛዝ ወይም እንዲሁ ወሬ እንደሚናገር ያለ ነው። እስቲ አንባቢዎችም አስተውሉት ጽሑፋቸው የሚሠወር አይደለም ፩ድ ጊዜ ኩሽ በሚባለው ቃል የሚሰሙት ከግብጽ ደቡብ የሚገኙትን ሰፊዎቹን አውራጃዎች ነው ይህን ሲጽፉ ማስረጃው ወዴት አለ። ለዚህ ማስረጃ ሳያቀርቡ ደግሞ ፪ኛ ፩ድ ፩ድ ጊዜም በልዩ የግብጽ አዋሳኝ የሜሮዌን መንግሥት ይጠሩበት ነበር ብለዋል። እንደዚህ ብለው የጻፉበት ማስረጃ ወዴት አለ የታሪክ አጻጻፍ ምንገዱ ቃሉን ከጻፈ በኋላ ማስረጃውን እያስከተለ ነበር እንጅ እንዲሁ እንደዛር ፈራጅ እንደዚህ ይሆናል እንደዚህ ተደርጓል እያሉ የብያኔ ንግግር እያስመሰሉ

የጽሑፍ ፈረስ መልቀቅ የተገባ አይደለም። እንደዚህ የተለለቀቀው ፈረስ ሜዳውን ጨርሶ ወደ ገደሉ በደረሰ ጊዜ ፈረሱ እንደሚሰባበርና ከፈረስዎ ወርደው ኮርቻውን ተሸክመው ወደቤትዎ መሄድ መኖሩን አላሰቡም። የጻፉትን ጽሑፍ ስመለከተው ያስደንቀኛል ምክንያቱም ቃልዎ ሁለት እየሆነ ስለማገኘው ይህም ከላይ እንደተጻፈው ማስረጃም ባይኖረው የእብራዊው መጽሐፍ ቅዱስ ኩሽ እያለ የሚጽፈውን ጽርዓውያን ኢትዮጵያ እያሉ ተርጒመውታል ብለው ይህንም ስፍራውን ለይተው አሪት ዘጥ ፪ ፲፪ና ፲ ፯ ፯ ኩሽን እያነሱ ጽፈዋል ይህ ፩ዱ ቃልዎ ነው። ፪ኛው ቃልዎ ደግሞ በአሪት ዘኁልቁ ፲፪ ፩ ፪ በዳዊት መዝ ፷፯ ፴፪ ኢትዮጵያን ያነሣል ብለው ጽፈዋል እንዳይካድም በ፱ነኛው ገጽ በ፳፩ኛውና በ፳፫ኛው መሥመር ተጽፎ ይገኛል። አስተያየትዎን ስገምተው አሪት ዘፍጥረትን የጻፉ እብራውያን ናቸው። አሪት ዘኁልቅ'ንና መዝሙረ ዳዊትን ኢትዮጵያን የሚአነሳውን ሁሉ የጻፉ ጽርዓውያን ናቸው ማለትዎ ይመስለኛል። በርስዎ ዘንድ እኮ አሪት ዘኁልቁና መዝሙረ ዳዊት የተጻፈው ከ፫ ሊ.ቃውንት ነው ሳይሉ አይቀሩም ይመስለኛል። አካሄድዎን ስመለከተው መንገዱ ይህ ነው። እርስዎን መስሎ ከታዬዎ መቸም የዘመን ሚዛን አለ ብለው ማመዛዘን እንደሌለብዎ ጉዳዩ ወደ ፊት እንደተሰናዳ ይመጣል። አሁን ቃልዎ ሁለት ሆነብኝ ላልኩዎ ሌላው ቀርቶ ፳ቱን ብሔረ አሪትና መዝሙረ ዳዊትን እብራውያን በእብራይስጥ አስቀድሞ እንደጻፉት እምነት እንዳለዎ በነዚህ መጽሐፎች ውስጥ በእብራዊ ልሳን በተጻፈው ውስጥ ኩሽ እያለ ይጽፋል እንጅ ኢትዮጵያ የሚል ጽሑፍ የለበትም ብለው ለይተውና ደፍረው የጻፉ ግን እንደዚህ ያለውን እርግጠኛውን ምንገድ አይገቡበትም ምክንያቱም እንደዚህ ሆኖ የሚሠራ ሌላ ነው እንጅ ፖለቲክ እንደዚህ ስለሆነ ካባትዎ ካባ ቤርሙዴዝ ሲያያዝ በመጣው በፖለቲኩ ምንገድ ስለሆነ ፩ድ ጊዜ ወደ ቀኝ ፩ድ ጊዜ ወደ ግራ እየሄዱ ከቀኙም አለሁ ከግራውም አለሁ በማለት በማጭበርበር የጽሑፍ ዓምድ አብዝተው ውስጡን ላላወቀው

# ደ እኁድ

ሰው ትልቅ መጽሐፍ አገኘሁ እያለ እየተደሰተ ገንዘቡን እያፈሰሰ እስከ መውሰድ ሲደርስ አይቸ እኔም እንደዚሁ ደርሼ ገዝቸ ነው። ይህን ሁሉ የፖለቲክ ድናሚት ተቀብሮ ያገኘሁት። ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ እርግጠኛ ቢሆንማ እውነቱን ከደፈሩት በእብራውያን ብሉይ ኪዳን ውስጥ ኢትዮጵያ የሚል የለም ብለው ደፍረው አይጽፉም ነበር ያባ ጋስፓሪን አሳብ ኢትዮጵያ ትባል የነበረች ኩሽም ትባል የነበርች መርዌ ናት እንጅ የአክሡም መንግሥት ያለበት ስም የለውም ማለታቸው መሆኑን እየዘረዘኩ አቀርባለሁ። "፩ኛ በ፱ነኛው ገጽ በ፲፫ኛው መስመር ኩሽ በሚለው ቃል የሚሰሙት ከግብጽ ደቡብ የሚገኙትን ሰፊዎቹን አውራጃዎች ነው። ፩ድ አንድ ጊዜም በልዩ የግብጽ አዋሳንኝ የሜርዌን መንግሥት ያመለከቱበት ነበር ይላል"። "፪ኛው በ፺፯ ገጽ በ፪ኛው መሥመር ይህ ሜሮዔ የተባለው ነገር ከጥንት ዠምሮ በኢትዮጵያ መንግሥት ሲገዛ የዚህም ማስረጃ በግብረ ሐዋርያት ፰ ፳፯ ፴ ተጽፎ እንደምናየው በህንደኬ ዘመነ ፣ መንግሥት ጊዜ የኅደኬ ባለሚል የሆነ ሰው የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ እጅ ለመንሳት የሄደው ከሜሮዌ ከኢትዮጵያ ግዛት ተነሥቶ ነው ብለው ታሪክ መርማሪዎች አረጋግጠው ጽፈዋል ይላል" እንግዲህ ያባ ጋስፓሪንን ፖለቲክ ማስተዋል ነው። አስቀድሞ ከሮማ የመጡበት ዋና ሥራቸው በፖለቲክ ስለሆነ ኢትዮጵያን ቀስ አያሉ የመናኔ ልብስ ለብሰው እንደሚያታልሉ ሰው አያውቅብኝም በማለት በረቂቅ ፖለቲክ የኢትዮጵያን መሠረት ለመለያየት ስለሆነ መርዌን ሌላ ነገር አስመስለው ኩሽ በሚለው ቃል የሚሰሙት ከግብጽ ደቡብ የሚገኙትን ሰፊዎችን አውራጃዎች ነበር አሉና ደግሞ በልዩ የግብጽ አዋሳኝ የሜርኖ መንግሥት ያመለክትበት ነበር ይላሉ። ፪ኛም ኅጽዋ ለቅንዳኬ የአክሡም ንግሥት አይደለችም ማለታቸው ነው ይህች የሳባውያን አገር ማለት ናት ማለታቸው ነው። ደግሞ ኅጽዋ ለኅደኬ ከመርዌ የሄደ ለመሆኑና ኅጽዋ ለኅንደኬ በልዩ የመርዌ የኢትዮጵያ ንግሥተ ነገሥታት እንደነበረች እንደማለት ታስቦ ለዚሁም የዓለም ባለታሪኮች ከመርዌ መሄዱን አረጋግጠዋል ተብሎ ተጽፍዋል። ለመሆኑ ከሊዋውንቱ የተጻፈው ማስረጃ ወዴት አለ ማስረጃውን ሳይዙ ይህን ጽሑፍና አሳብ ከምን አመጡት እንግዲህ ያባ ጋስፓሪን አሳብ ኢትዮጵያ መርዌ ናት እንጅ

እንደ ወሰን የሚከልልን የኢጣልያ ተወላጅ አለመሆኑን መገንዘብ የተሻለ ጉዳያቸው ነበር። የሀገራችንን ታሪክ ይቅርና አባቶቻችን አልፈው የባቢሎንና የፋርስን ነገሥታት የሮማንና የቁስጥንጥያ ነገሥታት የግብጽማ ገንዘባቸው ነው የነዚህን ሁሉ ታሪክ ከየቋንቋው ለቅመው በግዕዝ ጽፈው አስቀምጠውልና። የመጻሕቱንም ቁጥር ሳናበዛ እንኳ በቀላሉ ፩ኛ ዮሐንስ መደብር ፪ኛ ዩስፉስ ፫ኛ ዜና እስክንድር ፬ኛ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ፭ኛ አውሻክር ፮ኛ አቡፈረጅ ፯ኛ መቃቢስ ፰ኛ መጽሐፈ በረላም ደግሞ ልዩ ልዩ ጽሑፎች ይገኛሉ። እነዚህ ሁሉ የዓለምን ታሪክ የነገሥታቱን ታሪክና ተራ ከነዘመናቸው የሚጽፉ ናቸው እነዚህ ሁሉ መጻሕፍቶች ኢትዮጵያን እንደዚህ ያለ አሳብ አቅርበውላት አያውቁም በሮማ ልዑካን የፖለቲክ ማከናወኛ ማኅበር አቋቋመው ሥራቸውን ከዠመሩ ወዲህ በሮማ ልዑካን መሪነት የተጻፈውን

## ዱ ሰኑይ

ለመቀበል አንችልም። ምክንያቱም የሮማ ልዑካን የሚሠሩትን ፖለቲክ ሁሉ መጻሕፍቶች ድል አድርገናል ተብሎ ከየምሥዋር ቦታቸው ወጥተው እንደ ተዝረከረኩ ትዕግሥተኛው ንጉሠ ነገሥት በድንገት በደረሰ ጊዜ የፖለቲክ መጻሕፍቶች ከየቦታው ወጥተው ተዝረክርከው ስለተገኙ ብዙ ምሥጢር ገልጸውልናል የሮማ ልዑካን ሲአመላልሱት የኖረው ሁሉ ደብዳቤ ፎቶግራፍ እንዳለ ተገኝቷል። የነሱ ሥራ ሌላው ነገር ይቅርና በሀገራችን የሚገኘውን ሁሉ ጥፋተኛ ሰው ይታሠርበት የነበረውን እግር ብረት ሙቅ ሰንሰለት ሰው የሚገረፍበትን ጅራፍ ሰው የሚሰቀልበትን ገመድ ይህን ህሉ ሳይቀር ውስጥ ለውስጥ በገንዘብ እየተመሳጠሩ

ወደሀገራቸው ሲወስዱ እንደኖሩ የሚአስረዳ ይገኛል። ደግሞ ልዩ ልዩ ነገሮች በዚህ ጽሑፍ ሊገለጽ የማይችሉ ጉዳዮች ይገኛሉ። በኢትዮጵያ ላይ ልዩ የፖለቲክ ጽሑፍዎን ዘርተው የምዕመናኑን ልብ ለያይተውት ይገኛል። እነዚህ የሮማ ልዑካን የተባሉ ባሥመራ። በኩል ወስደዋቸው የበሩ መጻሕፍቶች በግዕዝ እየታተሙ የመጡ በአርኪዎሎዥ ጽሕፈት ቤት ይገኛሉ። በምን ምክንያት ወስደዋቸው ነበር ይሆን ጥቅም ለመፈለግ መሆኑን አናውቀውም ይሆንን ያላወቀ ሰው ከነዚያ ከታተሙ መጻሕፍቶች ባገኘ ጊዜ ሳያናብብ እንደዚሁ ፩ድ ነገር ለመያዝ የሚገባ አለመሆኑን መጠንቀቅ አስፈላጊነቱን ለወገኖቼ አስታውሳለሁ። ይህም ብቻ ሳይሆን እንደዚሁ የሮማውያንን ጽሑፍ ተቀብሎ ሳያስመረምሩ ማስቀመጥ ለመጭው ትውልድ ጉዳት የሚያመጣ መሆኑን ማሰብ አለብን። ያባ ጋስፓሪንን ታሪክ መጽሐፍ እስከ መጨረሻው ሳታነስቡ ብታስቀምጡት መልካም አለመሆኑን አስገነዝባለሁ "ባ፲ኛው ገጽ ኢትዮጵያ በቅዱስ መጽሐፍ እንደሚጠራት በሰፊው ተጽፎ ይገኛል"። እንደዚህ የተጻፈው እኛን ለመደለል ነው እንጅ በአባ ጋስፓሪን አሳብ ኢትዮጵያ የምትባል ሌላዪቱ እንደሆነች ጽሑፋቸውን በተገለጸው ጽሑፍ መረዳት ነው። ከአዳም ዠምሮ ሲያያዝ የመጣውን መንግሥት ከኖኅ ላይ ሲደርስ ለ፫ት ልጆች እንደተከፈለና ከ፫ት ልጆቹ ደግሞ በካም ቤት አፍሪካ ለ፫ት ቢከፈልም ከአፍሪካ ፲ር እጥፍ የሚሆነው ለኩሳ መሆኑ ስለሚታወቅ የኩሳ የመዠመሪያ ከተማው ሜርዌ ስለነበረች በሜርዌ የነበረው ከካምና ከኩሳ ወደ ስብታሕ የተላለፈው ሕገ መንግሥቱና ጽሑፉ እስከ ብዙ ቀኖች ከቆየ በኋላ አክሡም ከተማ ከተመሠረተች በኋላ አክሡም የንጉሠ ነገሥት መቀመጫ ስለሆነች ሜርዌ የተራ ንጉሥ መቀመጫ ሆና ስትኖር እንደ እርግጠኛው ግብጽን ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያውያን ሲገዟት እንደሚኖሩ ግብጽም ፩ ፩ ጊዜ ጦርነት ያደረገችበት አይጠፋም። ግን ግብጽ ስለ ዓባይ ውኃ ብዙ ጊዜ ለኢትዮጵያ ስትገብር መቆየቷን ታሪክ ይነግረናል ማስረጃውን በዋናው ክብረ ነገሥት እንገልጸዋለን አሁን ያባ ጋስፓሪንን ፖለቲክ እንገልጻለን ባ፲ረኛው ኢትዮጵያ ነቢያት በመንፈስ ትንቢት የነሳሿትን ሁሉ የጻፉ ይመስላል ይህ ጽሑፍ ዛሬ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ያለበትን ማለታቸው ከሆነ ከላይ "በ፱ነኛው ገጽ ባ፲፫ኛው መሥመር ኩሽ በሚባለው ቃል የሚሰሙት ከግብጽ ደቡብ የሚገኙትን ሰፊዎቹን አውራጃዎች ነው ፩ድ ጊዜም በልዩ የግብጽ አዋሳኝ የሜሮዌን መንግሥት ይመለከቱበት ነበር"

የሚሉ ጽሑፍ በምን ምክንያት ተጻፈ የሜሮዌ መንግሥት እሽ ይሁን ኩሽ ተብሎ ተጠራ የአክሡም መንግሥትስ ማን ተብሎ ይጠራ ነበር ይላሉ ይሆን። በሀገራችን ፩ድ ተረት አለ እንደዚህ ያለ ያለቦታው የገባ ነገር

## ዲ ሠሉስ

ሲገኝ የቀበሮ ጻድቅ እበግ ማኽል ገብቶ ይሰግዳል እንደተባለው አባ ጋስፓሪን የኢትዮጵያን ታሪክ አደላዳይ የላይን እታች የታቹን እላይ እያመሳቀሉ ጽፎ ሳይጠየቁ መሄድ የለም። ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ ተበጥሮ ምርቱና ገለባው መታወቅ አለበት። በ፲፩ኛው ገጽ በመዠመሪያ መሥመር "ከዚህም በላይ እንዳየነው ግብጻውያን በቀድሞ ዘመን በኢትዮጵያ ላይ የተገዥነት ሥልጣን እንዳሳዩ አይተናል። ቴብሱክሶር ላይ ባለው በአሞን ቤተ ጣዖት ላይ በተቀረጸው እንደሚታየው ግብጻውያን ወርቅ ዕጣን ጥርስና ሌላም የንግድ ዕቃ ሁሉ ያገኙ ነበር ይህ የግብጻውያን ዘመቻ የሆነው ከክርስቶስ ልደት በፊት ፪ሽና ፭ሽ፫፻ ዘመን ቀደም ነው" ብለው ጽፈዋል። እንግዲህ ይህ ጽሑፍ ሰውንና ሰውን ማጣላትና ማጋጨት ካባቶቻቸው ከነአባ ቤርሙዴዝ ከነአባ አልፎንሱ ከነአባ አንቶኔሊ ከነአባ ማስያስ ከነአባ ያዕቆብ የወረደ ልማድ ስለሆነ ነው እንጂ ምስክር የተደረገው "በ፲ኛው ገጽ የባሕር ዓሣና የሰዎችም የአትክልት ጥንታዊ ሥልጣን ጥንታዊ ግብጻውያን ፊደል ያለበት ነው። ደግሞ ፲ኛው ገጽ አስደናቂ ጽሑፍ ይገኛል። ከሥዕሉ ፊት ለፊት ነው። እንዲህ ይላል። ይህ ሥዕል ግብጻውያን በኢትዮጵያ እንደዘመቱ ያስያል ካለ በኋላ ደግሞ

ሲተረጉሙት ከላይ ወገን ኢትዮጵያውያን ፍሬውን ሲለቅሙ ይታያሉ ብለዋል (ከላይ ወገን ያሉት ኢትዮጵያውያን መሆናቸው በምን ታወቀ)። ደግሞ ከማኽሉ የግብጽ ጦር አዝማች ከኢትዮጵያ የጦር አለቃ ጋር ፊት ለፊት ይታያል ብለዋል። (ይህንስ የግብጽ የጦር አለቃ ያሉት ምን ምልክት ይዘው ነው ወይስ የትኛውን ጽሑፍ አንብበው ነው አባ ጋስፓሪን ጾምና ጸሎት ስለሚያበዙ እንደ ሐዋርያት የዓለም ቋንቋ ተገልጾላቸው እንደሆነ እንጂ ይህን ጽሑፍ አንብቦ ለመተርጐም ስንኳንስ አባ ጋስፓሪን የግብጻውያን የዛሬዎቹ ሊቃውንቶች ይህን ለማበብ ይችላሉ ብየ አላምንም። ምክንያቱም ታልቁ እስክንድር ግብጽን ከያዘ ዠምሮ የኰብት ቋንቋ ስለቀረ ነው። ይህም ፩ መንግሥት ነጻነቱን በተቀማ ጊዜ ያገሩ ቋንቋና ዓላማ እንዳይታይ በዓለም የታወቀ ሕግ ስለሆነ የግብጽ ቋንቋ ኰብት የሚባለው ከግብጽ ዓላማ ጋራ ወድቆ የቆየበት ዘመን እስክንድር ሲሞት በጥሊሞስ ተተካ ከበጥሊሞስ ዠምሮ እስከ አክላውባጥራ ሞት ዘመኑ የታሪኩ መጽሐፍ እንደሚለው ፪፻፹፬ ነው። ከዚያ በኋላም አክላውባጥራን አውግሥጦስ ቄሣር ገደለና ግብጽን ያዘ። ከዚያም በኋላም ሀርቃል እስቲሞት በሮማውያን ቆየች። ግን ፩ድ ፩ድ ታሪክ ላይ ኔሮን በሞተ ጊዜ ተቋርጦ ነበር የሚል አለ። ሀርቃል ከሞተ በኋላ ግን የሙሐመድ ሃይማኖት ገባ የግብጽ ንግግር ዓረቢኛ ሆነ። ከዚያም በኋላ ቱርክ ግብጽን ለቆ ሲሄድ በሽ፰፻፸፫ ዓ.ም እንግሊዞች ሲገቡበት የመንግሥቱ ቋንቋ እንግሊዝኛ ስለሆነ ለመሥሯ እንግሊዝኛውን ሲቀበሉ ዓረቢኛውን የናት ቋንቋ አድርገው ይዘው ኖሩ። ከዚያ በኋላ በሽ፱፻ ዓ.ም በላይ ከእንግሊዝ ወጥተው ነጻነታቸውን ሲያቆሙ የጥንት መሠረት ቋንቋቸውን በቀረ ፪ሽ፩፻ ዘመን ካለፈ በኋላ ከየመሬቱ እየቆፈሩ እያወጡ የጥንቱን ቋንቋ ገና በማጥናት ላይ ስለሆኑ ይህን ጽሑፍ አቅርቦ ተርጉሙ ቢሏቸው እንዲህ እንደ አባ ጋስፓሪን አሳብና ጽሑፍ ይገጥማል ብየ አላስብም። እንደዚህም ማለቴ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ገና የሚገለጡ ብዙዎች የሐሰት ጽሑፎች መኖራቸውን ስለተረዳሁ ነው።

በገጽ "፲፪ ባ፩ኛ መሥመር ከጌታችን ከክርስቶስ ልደት በፊት

# ዳ ረቡዕ

፫፻፴ ዓ ቀድሞ ትንቢት የተናገረው ዳንኤል እርሱም የንጉሥ አንጥያኮስን በግብጽና በልብያ በኢትዮጵያ ላይ መዝመቱን ተናግሯል። አሉ። ይህም ዘመቻ ከክርስቶስ በፊት በ፻፷፱ና በ፻፷፯ ዓ ላይ ሆንዋል እንግዲህ ያባ ጋስፓሪንን የውሳጤ ፖለቲክ ማስተዋል ነው አንድ ነገር ይጽፉና ደግሞ ያነን ተወት አድርገው ሌላ ዓይነት ተካ ይደረጋል ባ፲፩ና ባ፲፫ኛው ገጽ ከብሉይ ኪዳን እየጠቀሰ ኢትዮጵያ እየተባለ ሲጻፍ ቆይቶ ነበር አሁን ደግሞ አንጥያኮስ ሊብያንና ግብጽን ኢትዮጵያን ወግቶ ነበር አሉ። ይህ አሳባቸው ይህ ንጉሥ ምናልባት ወደ ሊብያ ላይ ወደ ግብጽም ወሰን ተዋግቶ ነበር ሲባል ሰምተው ይሆናል። ጦርነቱን ያመጡ ኢትዮጵያውያንን ወግቶ ድል አድርጎ ያዘ ለማለት አይደለም። ይህን ያነሱበት ዋና ፖለቲካቸው የሊብያንና የግብጽን ወሰን ኢትዮጵያ ለማለት የፈጠሩት ዘዴ ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ በዚህ ገጽ ፷፩ መሥመር ተራምደው በ፷፪ኛው መሥመር የኢትዮጵያን ዜና በግብረ ሐዋርያት እንደምናገኘው ፰ ከ፷፯ እስከ ፵ ኅጽዋ ለኅንደኬ ከመርዌ ሄደ ማለታቸው በዲያቆኑ በፊልጶስ እጅ እንደተጠመቀ ካመለከቱ በኋላ ባ፲፯ኛው ገጽ ላይ ባ፩ኛው መስመር በቅዱስ መጽሐፍ ላይ ኢትዮጵያን ለማመልከት የሚነገረው ቃል በእብራይስጡ ሁል ጊዜ ኩሽ የሚለው ነው። ይህ ኩሽ የሚለው ወደ ግሪክ ሲተረጐም ተርጓሚዎቹ አክሡሞች ቃል በቃል ኢትዮጵያን ተከትለው እንዳለ ተርጉመውታል። በገጽ ፱ ተ ይላል። እንግዲህ ያባ ጋስፓሪን ረቂቅ ፖለቲክ ማስተዋል ነው እስቲ ይህን ያህል ምን አደከማቸው ነበር። በማያውቁት ነገር ገብተው ይህን ያህል ከማልፋት ፩ድ ቁርጥ ያለ ቃል በበቃ ነበር። አጭሩ ነገር አሁንም

የእብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ ሳይል ኵስ እያለ መጻሕፍተ ብሉያት ሲጨርስ የተገኘ እንደሆነ ባሕረ ውቅያኖስ በቀላድ ተለክቶ እርሻ የሆነና እህል የተዘራበት አትክልት የተተከለበት እንደሆነ ያባፈራ ጊዜ የርስዎም መጽሐፍ እርግጠኛነቱ በዚያ ጊዜ ይታወቅና እንቀበልዎታለን። የርስዎ ታሪክ ነው። ደግሞ በ፲፮ኛው ገጽ በ፲፫ኛው መስመር "በመጽሐፈ አስቴር በእብራይስጥና በፅርዕ ፩ ፩ በሌላም ስፍራ ላይ ፫ት ጊዜ ትልቁ የፋርስ ንጉሥ ከህንድ እስከ። ኢትዮጵያ ድረስ ይገዛ ነበር ይላል። አሐሽዊሮስ የተባለው የፋርስ ንጉሥ ከክርስቶስ በፊት ከ፬፻፹፭ እስከ ፬፻፷፭ ዓ ቀድሞ ከገዛው ከሴርሴስ ስም ፩ድነት እንዳለው እናውቃለን"። ካለ በኋላ በመጽሐፈ አስቴር ፲፫ ፲፯ ምዕ በጽርዕ የተነገረው የርሱ ልጅ አርታክሴርሴስ ካ፬፻፷፭ -፬፻፳፬ ዓመት ቀድሞ ነግሧል"። በዚሁ መጽሐፍ ላይ እነዚ ሁለቱ የፋርስ ነገሥታት ከኅንድ እስከ ኢትዮጵያ ገዝተዋል ተብሏል። እርግጥ ነው በመጽሐፈ አስቴር ባአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ አሐዊሽሮስ ይለዋል በግዕዙ መጽሐፍ አርጤክስስ ይለዋል እዚህ በ፪ት ስም ተጠርቶ የሚገኘው ፩ድ ሰው እንደሆነ መስክረው በ፲፯ኛው ገጽ በ፰ኛው መስመር ከ፬፻፹፭ እስከ ፬፻፷፭ ቀድሞ ከገዛው ከሰርሴስ ስም ፩ድነት እንዳለው እናውቃለን ካሉ በኋላ በመጽሐፈ አስቴር ፲፫ና ፲፯ ም በጽርዕ የተነገረው የተነገረው የርሱ ልጅ አረታክታክሴስ (አርጤክስስ) ከ፬፻፷፭-፬፻፳፬ ዓ ም ቀድሞ ነግሥዋል። በዚሁ መጽሐፍ ላይ እነዚህ ሁለቱ የፋርስ ነገሥታት ከኅንድ እስከ ኢትዮጵያ ገዝተዋል ይላል። እንግዲህ መቸም ያነን የሐሰት ስብከተዎን ለማምጣት ሲፈልጉ በረቂቅ ፖለቲክ ለሐሰቱ መውጫ ደረጃ ያሰናዳሉ

# ዴ ኃሙስ

ስለዚህ አሁን ለሚአመጡት ስብከት ፪ት ነገሮች አደራጅተዋል ፩ኛው ፪ት አርጤክስስ። ፩ኛው ከ፬፻፹፭-፬፻፷፭ የነገሠ ፪ኛው አርጤክስስ ካ፬፻፷፭-፬፻፳ የሚሉት ፩ዱን ሰው ፪ አስመስለው የገዙበትንም ዘመን የለዩ መስለው የጻፉት ከምን መሠረት አምጥተው ነው የባቢሊን የፋርስ የሜዶን የጽርዓውያን ታሪክ በቅዱስ መጽሐፍ ይገኛል በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህን በዚህ እንደጻፉት ለማስረዳት ይቻለዎታል ይሆንን። ግን እርስዎ ለዚህ እንደ ፈቃድዎ

ለመጻፍ እንዲመችዎ አስበው በ፱ነኛው ገጽ በ፫ኛው መስመር በእግዚአብሔር አሳሰብ (በመንፈስ) የተጻፈው ቅዱስ መጽሐፍ ውጣኔው ታሪክንና ጽሕፈተ ምድርን ዥኦግራፊን ለማስታወቅ አይደለም ብለው አስቀድመው በርዎን ዘግተዋል። ሆኖም መጽሐፈ አስቴርን ጠቅሰው ሲገኙ የዘጉትን ስር መልሰው መክፈትዎ አልቀረምና ካልቀረ መጠይቅዎ የግድ ነውና አሁንም በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ማስረጃውን እንዲያቀርቡልኝ እጠይቅዎታለሁ የፋርስና የሜዶን ነገሥታት ታሪክ በመጽሐፈ አስቴር ብቻ ሳይሆን ፩ኛ ነገሥት ራብዕ ፪ኛ ዜና መዋዕል ስለ አርሔክስስ አስቴር ፩ ፩ ከኅንድ እስከ ኢትዮጵያ የሚለው ፩ኛ አስቴር ፪ ልጁ ዳርዮስ ዕዝራ ፫ ፪ ወለኵሉ መሳፍንት ወመገብት ሥዩማን እሉ ኵሉ ኅንደኬ እስከ ኢትዮጵያ ዘ፻፳ወ፯ቱ ምስፍና ይላል። በነዚህ እንደዚህ የሚለው ኢትዮጵያ ወሰን ማድረጉን ነው እንጅ ኢትዮጵያን ጨምሮ ገዛ የሚል የለም። ኅንድንም አልገዙም እንደ አባ ጋስፓሪን ሁለት አርጤክስስ በፋርስ ነገሥታት ውስጥ የለም ከላይ ሁለት ነገሮች አደራጅተዋል ያልኩት ፩ዱ ይኸው ሁለት አርጤክስስ የሌለውን አስመስለው። መጻፋቸው ፪ኛው በመጽሐፈ አስቴር ፲፫ና ፲፮ ምዕራፍ በጽርዕ ብለዋል። በጽርዕ የተጻፈ ከዓለም ቅዱስ መጽሐፍ የተለየ አላቸው ይመስለኛል። ይህ ሁሉ ዋዜማ ያነኑ ሐሰቱን ለመደገፍ ነው እንጅ እውነት ከሆነ ሳይለዩ መጽሐፍ ቅዱስን መጥቀስ ነበር ያባ ጋስፓሪን ታሪክ ኢትዮጵያን ለማኮሰስ ያሰቡትን ላላወቀ ሰው ለማስጠናት ስለሚደክሙ ነው እንጅ እርግጠኛውን ለመፈለግ አስበው ቢሆን የዓለምን ነገሥታት ታሪክ ለማወቅ ቢፈልጉ በዓለም ላይ ሲያያዝ የመጣውን የነገሥታቱን ታሪክ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በነገሥታቱና በዜና መዋዕል አስተውለው ይመለከቱት ነበር። በነገሥትና በዜና

መዋዕል በመቃብያን አስተውለው ተመልክተው ቢሆን የባቢሎንና የፋርስ ነገሥታተ ጦርነት ያደረጉበትንና የነገሡበትን እየለየ የጻፈውን ለማግኘት በቻሉና በተጠነቀቁበት ነበር። ነገሩ ሐሰት መሆኑን የሚያስረዱ ምንገዶች አባ ጋስፓሪንም አመልክተው ነበር። ግን አባ ጋስፓሪን ዋና ዓላማቸው ሐሰቱን ወደ መውደድ ስለሆነ ተወት አድርገው ወደ ሐሰቱ ተመልሰው በሐሰት ባሕር ገብተው ሲዋኙ ይገኛሉ። ዝምረውት የነበረውም እውነት ያልኩት በገጽ "፲፮ በ፲፱ኛው መስመር እኛ ግን ይህ ብራኅማ የተባለው ሰው የዓመት ግብር ለመቀበል ከፋሮስ ንጉሥ የተላከ ንጉሥ እንዳልነበረ እርግጥ እንናገራለን"። ይህ ቃል እንኳ ምንም እውነት ባይሆን ንጉሥ አልነበረም በማለታቸው ነበር ይህን ያልተነካከለውን ሽራፋውን ነገር ለማጽናት አልቻሉም ይህንም ቃላቸውን ለውጠው በገጽ "፴፭ በ፳፫ኛው መስመር በዓረብ ደቡብ በኩል ይኖሩ የነበሩ ሳባ ዑባል ኦፊር የተባሉት ፫ቱ የዮቅጣን ልጆች ተከታትለው ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ገብተውም በኩሽ ልጅ በጺኦሪ እየተገዙ ፲ ዓመት ያህል ከሐበሽ ዘሮች ተቀላቅለው በኢትዮጵያ ላይ ተቀምጠው ነበር

## ድ ዓርብ

በዚህ መካከል ብራህማ የተባለ የኅንድ ንጉሥ መጥቶ ኢትዮጵያን ስለወረራት ጺኦሪ የተባለውም የኩሽ ነገድ ድል አድርጎ ኢትዮጵያን ያዘ ብለው" ከላይ ፲፮ኛውን ገጽ ጠቅሰውታል ወዲያና ወዲህ ቢሉት ሐሰቱ እውነት እውነቱ ሐሰት አይሆንም ከንቱ ድካም ነው። ፲፮ኛው ገጽ ላይ ያለውንም ስለመለከት ያለሆነውና ያልተደረገውን ነገር እውነት ለማስመሰል እንዲያው ከመጻሕፍቱ ማስረጃ ያለው ለማስመሰል ከመጽሐፈ አስቴር አርጤክስስን አሐሽዊሮስን ጠቅሰው ፻፳፯ አኅጉር ከኅንድ እስከ ኢትዮጵያ የሚለውን ጽሑፍ ጫፍ ነገር ይዘው በውቅያኖስ ባሕር ላይ በሬ ተጠምዶ ሲታረስ እኅል ሲዘራ አየሁ እንደማለት ያለ ከንቱ የሆነ አሳብዎን ይህ አሳብ የርስዎ ብቻ ሳይሆን ካባቶችዎ የወረደ ነው። በዚህ ጽሑፍዎ አባቶችዎ እነ አለቃ ታዬን እነብላቴን ጌታ ኅሩይን አታልለውበት እነደነበረ ጽሑፋቸው ያስረዳል። ይህም ጽሑፍ የዮቅጣን ልጆች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር የሚል ጽሑፍ ምንጭ ከሮማ ልዑካን የገተኘውን ጽሑፍ ስላዩ ሐሰት አይጽፍም መስሏቸው በመታለል የነሱን ተከትለው በታሪክ መጽሐፋቸው ስለጻፉት ነው በሀገራችን የሚገኙ ደራስያን ሁሉ ይህን ጽሑፍ እየተከተሉ ጽፈው የሚገኙ ብዙዎች ናቸው እኔም ራሴ እንደዚሁ

ተከትዬ በታሪክ መጽሐፌ ጽፌው ነበር። ግን የኔ ሳይታተም በመቆየቱ የተሻለ መንገድ ለመስጠት ያባ ጋስፓሪን መጽሐፍ አገለገለኝ። ይህ ያባ ጋስፓሪን አሳብ አለቅጥ ጎላ ብሎ መምጣቱ ይህ የሐሰት ስብከት ፩ድ ተቃዋሚ ሳይኖረው በኢትዮጵያ ላይ ልክ ሆኖ ሲሄድ ባየሁ ጊዜ እንግዴህ የኢትዮጵያን ነጻነት ለመቃወም መርጃ ለመሆን የሚያገለግላቸውን ሥራ ለማደራጀት ለኢትዮጵያ ተቃዋሚ ለመፍጠር ሲመሠርቱ ከመጻሕቱ ማስረጃ ያለው እርግጠኛ ታሪክ ለማድረግ አባ ጋስፓሪን ባ፻፮ኛ ገጽ ባ፰ኛው መሥመር በመጽሐፈ አስቴር በእብራይስጥና በጽርዕ ፩ም ፩ቁ በሌላም ፫ላይ ትልቁ የፋርስ ንጉሥ ከኅንድ እስከ ኢትዮጵያ ይገዛ ነበር ይላል አሐሽዊሮስ የተባለው የፋርስ ንጉሥ ከክርስቶስ በፊት ካ፬፻፹፭-፬፻፷፭ት ዓ.ም ቀድሞ ከገዛው ከጠርጤስ ስም አንድነት እንዳለው እናውቃለን በመጽሐፈ አስቴር ፲፫ና ፲፮ ምዕ የተነገረው የርሱ ልጅ አርታክስስ (አርጤክስስ) ካ፬፻፷፭-፬፻፳፬ ዓ.ም ቀድሞ ነግሥዋል በዚሁ መጽሐፍ ላይ እነዚህ ሁለቱ የፋርስ ነገሥታት ከኅንድ እስከ ኢትዮጵያ ገዝተዋል ተብሏል። ይህ ተብሏል ማለት አነጋገሩ እንደ ማቃለል ያለ ሥለሆነ ያቃለሉም በማስመሰል በዚሁ ገጽ ባ፲፪ኛው መስመር ላይ ሄሮዶቱስም በታሪክ መጽሐፉ እንደዚሁ ይላል ብለዋል። ይህ እንደዚህ ይላል ማለት ያልተለየ የፍራቻ ነበር ያለበት ነው እንጅ እርግጠኛ ነገር ከሆነ በድፍረት ከዚህ መጽሐፍ ከዚህ ምዕራፍ ብሎ ሞልቶና ገፍቶ መጻፍ የተገባ ነበር። እንደዚሁም ይላል ብሎ መተው መረጃ የሌለው ወሬ ማለት ነው "ደግሞ ዳሩ ግን እርሱ ኢትዮጵያ

የዓመት ግብር ትሰጥ እንጅ የፋርስ መንግሥት ተገዥ አልነበረችም ብሎ በልዩ ያስታውቃል"። ሄሮዶቱስ በ፫ኛ በ፴፯ኛም ከላይ እንዳመለከትሁት ተብሏል ብለው ያታለሉ መስለው ሄሮዶቱስንም በትክክል የጻፈም ሳይስመስሉ ሄሮዶቱስም እንደዚሁ ይላል አሉና ደግሞ መልሰው ግን እርሱ ኢትዮጵያ ያመት ግብር ትስጥ እንጅ የፋርስ መንግሥት ተገዥ አልነበረችም ብሎ በልዩ ያስታውቃል አሉ ውሸቱን ሲቀጣጥሉት ይገኛል ደግሞ መልሰው በዚሁ ገጽ "ባ፲፯ኛው መስመር የኢትዮጵያውያን

## ዶ ቀዳም

ትውፊት ቃል በቃል የተላለፈ ማለት ስለ ሆነ ነው። ጥቂት ጊዜ ብራህማ የሚባል ፩ድ የኅንድ ንጉሥ በኢትዮጵያ ላይ እንደነገሠ ያወጋልና። እኛ ግን ይህ ብራህማ የተባለው ሰው የዓመት ግብር ለመቀበል ከፋርስ ንጉሥ የተላከ እንጅ ንጉሥ እንዳለነበረ በእርግጥ መቀበል ከፋርስ ንጉሥ የተላከ እንዳልነበረ በእርግጥ እንናገራለን ብለዋል" ስንኳንስ ለዓለም ሊቃውንቶች የሚቀርብ በደምብ ተመርምሮ የተጻፈና በቃል እንኳ የተነገረ ነገር ለመጨበጥ የሚቻልበት ሞልቷል። በዚህ ጽሑፍ ላይ ስንት ነገሮች ፩ኛ የአስቴር መጽሐፍ ተጠቀሰ ተባለ ፪ኛ የሄሮዶቱስ መጽሐፍ ተጠቀሰ ፫ኛ ሁሉም ቀረና የኢትዮጵያ ትውፊት ቃል በቃል የተላለፈ ማለት ስለሆነ ተባለና ብራህማ የተባለ ፩ የኅንድ ንጉሥ በኢትዮጵያ ላይ እንደነገሠ ያወጋናል። የመጻሕፍቱ ማስረጃ ለይምስለ ከተደረገ በኋላ እንደገና ወደ ወሬው ተመለሱና ያወጋናል ብለውት አረፉ። ደግሞ ይህን ወግ በመደገፍ እኛ ግን ይህ ብራህማ የተባለው (ንጉሥ መባሉ ቀረና የዓመት ግብር ለመቀበል ከፋርስ ንጉሥ ተልኮ የመጣ እንጅ ንጉሥ እንዳልነበረ በእርግጥ እንናገረለን ብለው ጻፉ ይህ ጽሑፍ በየትኛው የተወሰነ የሚል ጥያቄ ቢመጣ መልስ የየትኛው መሠረት መሆኑን ለማስረዳት ለመገመት የመጽሐፉም የወሬውም የተነገረና በመካከሉ እንደ ዛር ፈራጅ ያለ ንግግር እኛ ግን ይህ ብራህማ የተባለው ሰው የዓመት ግብር ለመቀበል ከፋርስ ንጉሥ የተላከ እንጅ ንጉሥ እንዳልነበረ በእግርጥ እንናገራለን ብለው ከደመደሙ በኋላ ደግሞ ይህን በጽሑፍ ላይ ያሳረፉትን ቃላቸውን አፍርሰው "፴፰ኛ ገጽ በ፳፱ነኛው መስመር ከዚህ ከላይ ሳባ ኡባል አፊር የተባሉት የዮቅጣን ልጆች ያሉበት ተሰብስበው የሐበስን ዘሮች ይዘው ብራህማ የተባለውን የኅንድ ንጉሥ ድል አድርገው ከኢትዮጵያ አሰወጥተው የኢትዮጵያን ሕዝብ ነጻ አወጡ ከዚህም የተነሳ ከግዓዚያን ነጻ አውጭዎች ተባሉ አገሪቱም ብሔረ አግዓዝያን ተብላ ትጠራ ዠመር እያሉ ታሪኩን ደርድረውታል። እንግዲህ ይህ ሁሉ ውሸት ሲቀጣጥል ቢውል

፩ ፍሬ የሌለው መሆኑን ስለተገነዘቡ አንባቢ ውስጠ ነገሩን እንዳያውቅባቸ አገም ጠቀም እያደረጉ አለባብሰው ጽፈው በዚሁ በሐሰቱ ጽሑፍ በሁለት ወገን ጥቅም አግኝተውበታል። በከንቱ ደከሙና ውሥጠ ሥራቸውንም ገለጹት እንጅ ኢትዮጵያ በሮማ ልዑካን ረቂቅ ተንኮል ትድከም እንጅ ለመሞት አልደረሰችም። እኔን የሚገርመኝ የጽሑፍ ማስረጃ ቈጠርኩ ተብሎ የተጻፈው ነው። የሮማ ልዑካን ረቂቅ ተንኮል የሚገልጽበት ጊዜው ሲደርስ አባ ጋስፓሪንን ይህን ጽሑፍ አነሳስቶ ለመጻፍ አደረሰ። የሮማ ልዑካን በኢትዮጵያ ውበትና ሀብት ልባቸው ስለተነደፈ የዓይናቸውም ልብ በመደፈኑ ብዛት ትንሽም ሳይጠራጠሩ በሙሉ ድፍረት እንደዚህ አድርገው ጽፈው ወደ ንጉሠ ነገሥቱ ፊት ለማቅረብ መቻላቸው እንደምን የሚገርም ነው። አሁንም የዚህን ያባ ጋስፓሪንን ታሪክ ለአንባቢዎቹ እገልጻለሁ አባ ጋስፓሪን በመጽሐፈ አስቴር ፩ ፩ አሐሽዊሮስ ከህንድ እስከ ኢትዮጵያ ፻፳፯ አህጉር ይገዛ ነበር የሚለውን ጫፍ ነጥቀው ኢትዮጵያን ጨምሮ ገዛ ብለው ሮማውያን ይህን ፖለቲክ ሲፈጥሩ በዚሁ በቅርቡ ዘመን ነው ያለን እንደሆነ ሰው አይቀበለንምና ዘመኑን ወደ ላይ ልናርቀው ብለው ሲመክሩ የዘመኑ ቁጥር አፍ አውጥቶ እንዲመሰክርባቸው አላወቁትምና ስለዚህ "በገጽ፲፱ ባ፩ኛው መስመር በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ባ፩ዱ ስፍራ ዘፍጥረት ፲ ም ፮ ፯ ስለ ሳባ ሲናገር ያካም ዘር የኩሽ

# ገ እኍድ

ተወላጅ ይለዋል። ወደቂቀ ካም ኩሳ ወምሥጣሬ ወፉጥ ወከነዓን የኩሽ ልጆችም ሳባ ኤዊልጥ ወሳባታ ረዕማም ሰብተቃም ወደቂቀ ራጌም ሳባ ወዮዳን በሌላው ስፍራ ደግሞ ዘፍ. ፲ ፳፰ ፳፱ ሳባን የሴም የዮቅጣን ተወላጅ ይለዋል። ወዮቃጤን ወለዶ ለኤልሞደድ ወለአቢሜል ወለሳባ ይላል ብለዋል"። እንግዲህ ሳባ ያሉት የአባልና የኦፊር ወንድም ነው። ዮቅጣን የኖኅ ፭ኛ ትውልድ ልጁ ነው። ይህም ዮቅጣን ከባቢሎን ግምብ መፍረስ አስቀድሞ ልጆቹን ወልዶ የቆየ ሰው ነው። የዘመኑን ቁጥር ስንመስን እንደ ኢትዮጵያ መጻሕፍት አቆጣጠር ከፍጥረተ ዓለም እስከ ማየ አይኅ ፪ሺ ፪፻፶፮ ዓ.ም ነው ደግሞ ከማየ አይኅ እስከ ባቢሎን ግምብ መፍረስ ፭፻፸፩ ዘመን ነው። ድምር ፪ሺ፰፻፳፯ ዓ.ም ነው። እነ አርጤክስስ አሐሽዊሮስ የነበሩበት ዘመን አባ ጋስፓሪን ባሰቡትም ቢሆን ፭ሺ፲፫ ዓ. ዓለም ላይ ማለት ነው። ከዚሁ ካ፭ሺ፲፫ ዘመን ፪ሺ፰፻፳፯ ሲነሣ ፪ሺ፩፻፹፮ ዘመን ይሆናል። የዮቅጣን ልጆች ፪ሺ፩፻፹፮ ዘመን ቆይተው ከኀንድ የመጣውን ብራህማ የተባለውን ህንድ አስወጥተው ነጻ አውጭዎች ተባሉ ብሎ መጻፍ እንደምን ያለ ታሪክ ነው። የሮማ ልዑካን ይህን የሚአክል የሐሰት ጋራ እዚህ ተጕልቶ ይህን የሐሰት ጋራ የተደላደለ መሬት ለማድረግ የደከሙት ድካም ምሳሌው እንደ ስናዖር ግምብ ማለት ነው። የስናዖር ግምብ ፩ድ ነፋስ በነካው ጊዜ ከላይ ዠምሮ እስከታች ድረስ ባ፩ድ ጊዜ ፍርስርሱ እንደወጣ ይህም ያባ ጋስፓሪን የውሼት ግምብ ሲፈርስ ሲናድ ወደ ፊት በሚገኘው አምዶች ሁሉ እየተዘረዘረ ሲታይ ይህ የውሼት ዓምድ ደግፎ የያዛቸው ነገሮች ህሉ ከላይ ወድቀው እንደተንከታከቱ ወደ ፊት ይቀርባሉ ባባ ጋስፓሪን መጽሐፍ ተሰናድተው የሚገኙ ነገሮች ኢትዮጵያን ለመቃወም የተሰናዳ ብቻ ነው። ፩ኛ ኢትዮጵያ የሚባለውን ስም ያወጡለት ጽርዓውያን ባ፭ሺ ፪፻ ዘመን በላይ ነው ይላሉ። ኢትዮጲስ የሚባለው ንጉሥ ባለፈ ከሺ፮፻ በሚበልጥ ዘመኑ ለሞተው ሰው ጽርዓውያን ስም አወጡ ሲባል የቀድሞ ስሙ ማን እንደነበረ ታውቆ እገሌ ይባል የነበረውን ንጉሥ እገሌ ብለው ጠሩት ስሙን ለውጠው እገሌ አሉት ማለት እከኗ ትንሽ የተሻለ ነበር። ሰውየው ካረፈ በኋላ ከሽ የበለጠ ዘመን ካሳለፈ በኋላ ሌላ ስም አወጡለት ማለት በስንፍና ቦታ ላይ ቆሞ ፸ ሊቃናት ብሉይ ኪዳንን ከእብራይስጥ ወደ ጽርዕ ሲገለብጡ ጽሑፉን ቃል በቃል አልገለበጡም ማለት ነው። ይህም ፸ዓ ሊቃናትን በትክክል አልገለበጡም ማለት ስሕተቱ ለ፸ ሊቃውንት ሆኖ ሊቆጠር የሚቻል አይደለም ጥፋቱ የሚቆጠረው በሮማ ልዑካን በኩል ነው። ፪ኛ ኢትዮጵያን ግብጽ ትገዛት ነበር ብለው ጽፈውት የሚገኘው ነው። ፫ኛ የጽሑፍ ጫፍ ነጥቀው ከህንድ እስከ ኢትዮጵያ በሚለው ምክንያት ያለውን ነገር ህሉ አጠራቅመው ያልተደረገ ነገር ፈጥረው ይህን ያህል ደፋርነት ሲሠሩ ይታውቅብኛል አለማለታቸው አስቀድሞ ካጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት

ዠምሮ ይህ ውስጣዊ ሥራቸው በተገለጸባቸው ቁጥር ካገር ውጡ እየተባሉ ዓዋጅ እየተነገረባቸው በተገለጸባቸው ቁጥር ካገር ውጡ እየተባሉ ዓዋጅ እየተነገረባቸው የሚኖሩ ስለሆነ ቀድሞ በነሱ ላይ ይደረግ የነበረው ሁሉ እንደገድል ጽፈው ስለሚመለከቱት በሮማ መንግሥት በኩል ዋጋ የሚአገኙበት ስለሆነ ውርደትም ቢመጣ ከክብር የሚቆጠሩት ስለሆነ ትንሽም ፍራት ሳያገኛቸው ይህን ጽፈው በማቅረባቸው ያስገርማል። በቀድሞ

## ጉ ሰኑይ

ጊዜ እንደዚሁ ጥፋት እየተገለጸባቸው ከሀገር ውጡ እየተባለ የታወጀበት ከጥንታዊ መጽሐፍ የተገኘ።

አጼ ገላውዴዎስ (አጽናፍ ሰገድ) ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ። ቲሁ። ከመ ኢይባእ ፖርቱጊዝ ሀገረ ኢትዮጵያ። ወፈድፋደስ ለእመ ኮነ ኤጲስ ቆጶስ ወካህን። ወነገረ ዓዋዲ በላዕሌሆሙ ለኵሉ ሰብአ ሀገር

ለእመ ተረከበ ፩ዱ እምኔሆሙ ከመ ይትኰነን በዓውድ ወይሙት በስቅለት። ወለእመኒ ይትቀበሎሙ ከመ ይሙት ምስሌሆሙ። ይህ ዓዋጅ እስከ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት በየጊዜው እየታደሰ እንደቆየ በሽ፰፻፸፫ ዓ.ም አጼ ምኒልክ ከኮንት አንቶኖሊ ጋር ካ፩-፲፰ ክፍል በተዋዋሉት ውል ባ፫ኛው ክፍል በሸዋ አገር ሃይማኖት ሌላ እንዳያስተምር ክልክል ነበረና አሁን በ፪ቱ አገሮች ያለመፍራት በነጻነት እውነተኛ ትምርት እንዲማሩ በትልቁ መንግሥት ሥልጣን በግልጥ ተፈቅዷል ይላል። ይህ ፫ኛው ውል ስለ ሃይማኖት ማስተማር ክልክል አዋጅ መኖሩን ያስረዳል። ይህ ውል አጼ ዮሐንስ ሳሉ ስለ ሆነ በሸዋ ብቻ ነው እንጅ ሌላ ቦታ አላለፈም ነበርና ደግሞ አጼ ዮሐንስ ካረፉ በኋላ አጼ ምኒልክና የኢጣልያ መልእክተኛ ኮንት ፔትሮ አንቶሎኒ ውጫሌ በተዋዋሉት ውል በ፱ነኛው ክፍል (በነዚህ በ፪ቱ አገሮች መካከል ያሉትን ሕዝብ እውነተኛ ሃይማኖት በግልጥ ለማስተማር በሙሉ ሥልጣን ተፈቅዷል ይላል)። ከዚያ ወዲህ ከላይ የተጻፈው አዋጅ ተሠርዞላቸው እንደልባቸው ሲሠሩ የሥራቸው ፍሬ በሽ፰፻፹፰ ዓ.ም ያነን ያህል ደም መፍሰስን አሳየ። ደግሞ ከዚያ በኋላ በሽ፱፻፳፯ ዓ.ም ዠምሮ እስከ ፴፩ት ዓ.ም ድረስ ያነን ያህል ደም ለማፍሰስ ቻለ። ከዚያ ወዲህም የነኑ የቀድሞ ሥራቸውን በመቀጠል ይህን ረቂቅ ፖለቲክ ብለው ፈጥረው ለሀገሪቱ መሠረት የኢትዮጵያ ዜጋ ሆኖ የኖረውን የደቡብ ዓረብ አገረ ገዥና አቅኒ አስመስለው እንዲሁ ከልባቸው ፈጥረው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚከፋፍል አርአያ ለውስጥ የሚሰብኩት አንሶ ያለ ትንሽ ፍርሃት በረቂቅ ፖለቲክ እያስመሰሉ ጽፈው በ፪ት ፊት ነገዱበት የኢትዮጵያ ዜጋ የነበሩትን አገሮች ብየ ስለጻፍኩ የኢትዮጵያ ዜጎች ስለ ነበሩ አገሮች ማስረጃ ከሌላ ልፈልግ ሳልል ከዚሁ አባ ጋስፓሪን ከጻፉት አመጣለሁ በገጽ ፸፪ "በ፳፬ኛው መስመር ይህም የኢትዮጵያ ንጉሥ በጀግንነትና በቆራጥነት ባሕርን ተሻግሮ ከሠራዊቱ ጋራ ተሰልፎ ከዓረብ ነገሥታት ጋራ ጦርነት ያደረገ ገደረት የተባለ ንጉሥ ነው። ይሁን እንጅ ይህ ገደረት የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ ታሪክ እንደሚነግረን በርሱ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ኢትዮጵያ እንጅ የበረታችና የሠለጠነች አገር እንደነበረች የታሪክዋ ሁኔታ ያስረዳናል። ይልቁንም ከሁሉ የበለጠ የሚገርመውና የሚአስደንቀው እንደ ታምራትም ሆኖ የሚታየው በዚያ ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሥ ለብዙ ሠራዊት የሚበቁ መርከቦችና ጀልባዎች አሠርቶ ሠራዊቱንም አስከትቶ ከኢትዮጵያ አገሩ ተነሥቶ ባሕርን ተሻግሮ በዚያ ጊዜ በጣም የሠለጠኑና የበረቱ ናቸው ተብለው የሚጠሩቱ ከዓረብ ነገሥታት ጋራ ተዋግቶ ድልን በማግኘቱ ነው)። መቸም አባ ጋስፓሪን ፩ እውነት ያሳዩና ፯ት ሐሰት ያመጣሉ ይህ ዋና ሥራቸው ነው። ያረብ አገር ሰዎች ባመጹ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ገደረት (ዘግዱርም ይላል) ወደ ዓረብ አገር ከብዙ ሠራዊት ጋር በመርከብና በጀልባ መሻገሩን ከጻፉ በኋላ ይህ

## ጊ ሠሉስ

የኢትዮጵያን ን ነ ገደረት የነበረበትን ዘመን ወደታች ጐትተው አውርደውታል። ይህንም ያደረጉበት ዓረቦች ወደዚህ መጡ ለማለት አሳብ ያላቸው ስለሆነ ስፍራውን ወደ ኋላ ጐተቱት። ይህም ይታወቅ ዘንድ "በ፸፪ት ገጽ በ፱ነኛው መሥመር ከጌታችን ከክርስቶስ ልደት በፊት ባ፩፻ ዓመት የኢትዮጵያ ነገሥታት ከዓረብ ሳባውያን አገዛዝ ነጻ ወጥተው ራሳቸውን እንደቻሉ ከዚህ በላይ እንደጻፍነው በሰፊው ተርከን አስረድተናል"። ይላል ይኸውና ታሪኩ ሲንጋጋ ከላይ እንደ ጻፍነው የተባለው ካ፲፫ኛ ገጽ ዠምሮ እስከ ፸፪ኛው ገጽ የተጻፈውን ዝባዝንኬ ገለባ ብቻ የሆነ ነገር ህሉ የጻፉበትን ነው። ይህም ከቁም ነገር ገባና ከላይ በጻፍነው በሰፊው ተርከን አስረድተናል ተባለ። አሁን ከላይ በጠቀስነው ባባ ጋስፓሪን ጽሑፍ ከክርስቶስ በፊት ፩፻ ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታት ከዓረብ ሳባውያን አገዛዝ ነጻ ወጥተው ራሳቸው እንደቻሉ ብለው የጻፉት ብህራማ ወደ ኢትዮጵያ መጣ የተባለ ከክርስቶስ በፊት ካ፩፻፹፫ ዓ.ም በታች

ነው ምናልባት ደግሞ ፩፻፸ ላይ ይሆናል ይባልም እንደሆነ አይታወቅም። ግን እሸ እንደ አባ ጋስፓሪን አሳብ ፩፻፹ ላይ ይሆን እንግዲህ እንደዚህ ሲሆን በዚህ በ፹ ዘመን ብቻ ሳባውያን ገዙ ማለት ነው። በዚህም ፹ንያ ዘመን ኢትዮጵያ ከዳር እስከ ዳር አቀኑ ማለት ነው። ከላይም እንደተመለከትነው ካ፲፫ኛው ገጽ ዠምሮ እስከ ፸፪ኛው ገጽ የተጻፈው ዝባዝንኬ የገለባ ክምር ገለባስ ሥራ ይገባል ይህስ ከገለባም ያነሰ ምን ብየ ምሳሌ ልስጠው ጓደኛ የሌለው ትእምርተ ሐሰት ሰይጣናዊ። ጉድ በዝርዝር በደረጃው እየተከታተለ ይመጣል። አሁን የዘግዱርን ዘመነ መንግሥት መጻሕፍቶች እንደሚሉት ከክርስቶስ በፊት በ፩ሺ፫፻፹ ዓ የነበረ ነው። ይህም ይታወቅ ዘንድ "በ፻፵፩ኛ ገጽ በ፳፩ኛ መሥመር ከዚህ ለተረከነው ታሪክ በእውነተኛነት የሚመሰክር ጽሑፍ ያለበት ድንጋይ በደቡብ ዓረብ ውስጥ ተገኝቷል። እርሱም የንጉሡንና የሠራዊቱን ዘመቻ ሐበሻት የተባሉ ይላቸዋል። ይህንኑም ጽሕፈት በዚህ መጽሐፋችን ውስጥ ከሳባዊ ቋንቋ ወደ አማርኛ ትርጒሙን ጽፈነዋል። ይህንም ጽሕፈት በድንጊያ ሠሌዳ ላይ የጽፋት የማያዋትን ከተማ ቅጥሮች በዙሪያዋ ያለውን ሁሉ ከውኃ ማጠራቀሚያው ጋር መውጫ መግቢያዋን ሲአድሱና ከሐበሻት አገር ተመልሰው ምሽጓን ባጠነከሩ ጊዜ ነው። ሐበሻት የህምያርን ሀገር ከበውና አስጨንቀው የሕምያርን ንጉሥና መሳፍንት ሕምያሮንና አርሐቢቶችን ገደልዋቸው" ብሎ ጊዜውን ከልደተ ክርስቶስ በኋላ የተደረገ አስመስለው ከነአጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ጋራ አያይዘው ጽፈውታል። የዚህ ታሪክ ማስረጃው ጥንታዊው ሐውልት በ፻፵፯ኛው ገጽ የሚገኘው ነው። ይህን የሐውልት ጽሑፍ እነሱ የሚሉት ባጼ ካሌብ ጊዜ አብርሃ ይባል የነበረው እንደራሴ ያስቀረጸው ነው በማለት ይህን ለመረዳት በገጽ ፻፵፫ በ፳ኛው መስመር "አክሡም ነገሥታት እንደራሴዎች ውሥጥ ስሙ በሚበቃ ያህል የታወቀ ታሪኩን ባጭሩ ቢተርኩለት ትልቅ ጥቅም ነው የሚሰጥ ፩ድ እንደራሴ ነበር። እርሱም አብርሃ የተባለ ነው ይኸው አብርሃ የተባለው በሕይወቱ ላይ የተደረጉትን ዋና ነገሮች የተጻፉት በ፩ድ ረጅም የሆነ ጽሑፍ ተገኝቷል። የዚህን መጽሐፍ መዠመሪያውን ክፍል ወደ ግዕዝና ወደ አማርኛ ገልብጠን በዚህ በታሪክ መጽሐፋችን ላይ አሳትመነዋል ይላል" ይህ ጽሑፍ

## ጋ ረቡዕ

የሚገኘው በ፻፵፯ኛው ገጽ ስለሆነ ማንም ሰው ይህን ረቂቅ ፖለቲክ ይመልከተው ይህ ጽሑፍ ያለ ጥርጥር በገደረት ጊዜ የተጻፈ ለመሆኑ የጥንታውያኑ የግዕዝ ፊደሎች ቅርጽ ያስረዳሉ። ባጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት የነበረው ጽሑፍ ይቆይና ባጼ ኤዛና የነበረው እንኳ ጥንታዊው ጽሑፍ ያስረዳል። የጥንት ፊደሎችን በመመርመር ምንም በጥናት ላይ ብሆን የጥንታውያኑን ፊደሎች ቅርጽ ሳላስተውል አልቀረሁም ማለት እንደምን እይተሻሻሉ እንደመጡ ስለዚህ አሁን በ፻፵፯ኛ የሚገኘው የፊደል ቅርጽ ካ፩ሺ ዘመን በላይ ከክርስቶስ በፊት የነበረ ቅርጽ ለመሆኑ ማስረጃዎችን በቀስታ አቀርባለሁ። ባጼ ዔዛና የተጻፈውን በ፻፲፩ኛ ገጽ ላይ የተጻፈውን አስተውሎ ማየት ነው ከታየ በኋላ ባባትዮው ጊዜ

ይህ ጽሑፍ ሲታይ በልጁ ጊዜ እንደገና ጥንታውያኑን የመሰለ ተጽፎ ሲገኝ እንደዚ የሆነበትን ምክንያት በጥብቅ መመርመር አለ። በውስጡ ብርቱ የሆነ ረቂቅ ሥራ አለበት። ይህም ሥራ ፩ድ ቦታ ብቻ አይደለም ከሌላ ቦታ ላይም ይገኛል ምሥጢሩ አብሮ ይገለጻል ግን የዘግዱርን ዘመነ መንግሥት ከክርስቶስ በፊት ባ፴፪ ዓ መሆን የሐውልቱ ደግሞ ባጼ ካሌብ ዘመን እንዲመስል የተደረገበትን ጥብብ ማመዛዘን አለ። እሺ ይህን ስናመዛዝን አጼ ዘግዱር ወይም (ገደረት) የነበረበትን ዘመን ተመልከተን መጨበጥ አለብን እንጅ የኢትዮጵያን አባቶቻችንን ጽሑፍ ትተን አባቶቻችን ውስጠ ተንኮላቸውን አውቀው ጥብቅ በሆነ ዓዋጅ ከውስጥ ያሉትም እንዲወጡ ከውጭ ያሉትም እንዳይገቡ ተከልክለው ይኖሩ የነበሩት ዛሬም ጽሑፋቸውን

ስንመለከተው ሐሰት የተሞላበት ሆኖ ሐሰቱ የተረገጠ እየሆነ እያገኘነው ስለዚህ የነአባ ጋስፓሪንን ሥራ መመርመር ግዴታ ስለሆነ በ፻፲፩ኛ ገጽ ያለውን ጽሑፍ ስንመረምረው መስመሩ ፲ር ነው ቀለሞችንም አስተውሎ ላያቸው ካዕብና ሣልስ የፊደሎች ደረጃዎች ይገኙባቸዋል። ከጥንታዊው ጽሑፍ ግርጌ የሚገኘው ጽሑፍ "ይህ ሥዕል የንጉሥ ዔዛናን ጽሕፈት መዠመሪያውን ያሳያል " ይህ ጽሑፍ ድምጽ በሚሰጠው በኢትዮጵያው ቋንቋ ተጽፎአል በጽሑፉ ላይ ድምጽ የሚሰጥ ማለት ነው ፊደል የተገኘበት መዠመሪያ ጊዜ ይህ ነው የንጉሥ ዔዛናን ጽሕፈት ትርጒሙን በዚህ መጽሐፋችን ላይ እንሰጣለን ይላል" እንግዲህ የነአባ ጋስፓሪን አስተያየት መመልከት መልካም ነው። ይኸውና የነሱ ሐሳብ ኢትዮጵያ እንዳልነበረች ነው የሚአደርጋት በኢትዮጵያ ስለሚገኙ መጻሕፍተ ብሉያት ማነኛውንም መልስ ከላይ አስረድቻለሁ በኔ ማመልከት ሳይህን አስቀድሞ ዝምሮ ሊቃውንቱንና መጻሕፍቱን ሮማ ድረስ እየወሰዱ ከተማሩ በኋላ ነው ወደ ኢትዮጵያ የሚመቱ እንደዚህ አድርገው የኢትዮጵያን ታሪክ ፩ድ ባንድ ሲቃወሙ የሚታዩ የወጣቶችን ልብ መከፋፈል ስለ ለመዱ በዚሁም ሥራቸው መጀመሪያ ሆኖ በኑሮአቸው የሚጠቀሙበት ስለሆነ የመንፈሳዊ ልብስ ለብሰው የሥጋውያኑን ሥራ ሐሰተኛ የሆነውን በማታለያ ምንገድ ሲጓዙ ይገኛሉ። አሁን ከላይ ተጽፎ እንዳገኘነው ስለ ዔዛና ጽሑፍ ከግርጌው ፊደል የተገኘበት መዠመሪያ ጊዜ ይህ ነው ተብሎ የተጻፈው ይህ ንግግር ማለት ይሆን። አሁን ያባ ጋስፓሪን አሳብ ከኢትዮጵያ ውስጥ ይህን የሚያውቅ የለም ተብሎ ታስቦ ይሆንን። ደግሞ ጥንታዊውን ጽሑፍ ወደ ግዕዝ ከተረጐምን በኋላ ደግሞ እንደገና ወደ አማርኛ ተርጒመነዋል ተብሏል። ይህንም ተርጒመን ያሉትን ፩ድ ባ፩ድ ልብ ብሎ ሲመለከቱት ብዙ ነገሮች ለማታለያ የገቡ ይገኝበታል

# ጌ ኃሙስ

፩ኛ ጥንታዊ ጽሑፍ ፲ መሥመር ነው። በግዕዝ ተገለበጠ የተባለው። አዲስ ጽሑፍ ፵፬ መስመር ተኩል ነው። ፴፬ቱ መስመር ከምንመጣ ይህም ይሁን በ፻፰ኛው ገጽ የሚገኘው ከቀኝ ወደ ግራ የተጻፈው በጥንታዊው ፊደል ፲፮ መስመር ነው። ግዕዙም በዚያው ልክ ነው። እዚህ ላይ በልኩ ፲፮ መስመር አድርገውታል ፫ኛ በ፻፫ ገጽ ላይ በጥንታዊ ፊደል ቀኝ ወደ ግራ ተጽፎ እንደ ዓረቦች እንዲመስል ተብሎ የተጻፈው መስመሩ ፳ ነው። በግዕዝ የተጻፈውም መስመሩ ፳ ነው እዚህ ላይ አስተውሎ ሲመለከቱት የጥንታውያኑ ፊደሎች ትርጒምና የግዕዙን ትርጓሜ አስተውሎ ሲመለከቱት የተለያየ ነገር ይገኛል። እሱም እንደዚህ ነው። በግዕዙ ላይ የከብት የላምና የበግ ቊጥር አለበት ይህ ቊጥር በጥንታውያኑ ፊደሎች ጽሑፍ ላይ የለም ከጥንታውያኑ ፊደሎች የሌለ ከግዕዙ ጽሑፍና ካማርኛው ላይ መገኘቱ ምክንያት ምን ይሆን በማለት በማስተዋል ዓይን ሲመለከቱት በግዕዙ ላይ ቁጥር አኃዝ ጽሑፍ በገባበት ላይ በጥንታዊው ፊደል ጽሑፍ ላይ ባዶ ሆኖ ይገኛል። በጥንታዊው ጽሑፍ ላይ ባዶ ሆነው የሚገኙ በግዕዙ ጽሑፍ ላይ አኀዝ ቁጥር የሚገኝባቸው መሆኑን አጥብቆ መመልከት ነው። ይህን አስተውለን ከተመለከትን በኋላ ወደ ምርመራ መግባት አለብን ማለት ከዚህ ከባዶው ቦታ ላይ ይህ አኀዝ ቁጥር ከምን ተገኘ እያልን ልባችንን ወዲያና ወዲህ ስናስብ ፩ድ ነገር ትዝ ይለናል። እሱም እንደዚህ ነው። በነዚህ በጥንታውያኑ ፊደሎች ዘመን የአኀዞቹ ቅርጽ የሌለ በመሆኑ ምክንያት መሆኑን

ለመረዳት እንችላለን። በማስተዋልም እንዲገባን በጣም እናስተውለው። በጥንታዊው ፊደል ቅርጽ በተጻፈው ላይ አኀዙ ቁጥሩ የሌለ መሆኑን በግዕዙ ጽሑፍ ላይ ያለው በጥንታዊው ፊደል ጽሑፍ ባዶ መሆኑን አስተውሉ ነው የምለው። ይህን ልብ አድርጋችሁ ካስተዋላችሁት በኋላ። በግዕዙ ላይ ተጽፈው የሚገኙ አኀዞች ጥንታውያኑ ፊደሎች በነበሩበት ዘመን እነዚህ የአኀዝ ቅርጾች ያልነበሩ መሆናቸውን ለመረዳት ትችላላችሁ። ይህንን በማስተዋል ከተገነዘባችሁ በኋላ

እነዚህ አኀዞች የያዙትን ቃል መቸ የተፈጠረ መሆኑን በጥብቅ ማስተዋል አለ። በጥብቅ ሲመረመር ይህ በግዕዝና ባማርኛ ተጽፎ የሚገኘው ቃል እርግጥ ከጥንታዊው ፊደል በኋላ ከተገኘው አኃዝ ጋራ የተፈጠረ ነው ለማለት አያሳፍርም። እንግዲህ ይህ በኋላ የተፈጠረው ንግግር (ቃል) በጥንታዊው ፊደል በር መግባቱን እንዳቃተው በአኀዞቹ ችግር ተገለጸ። እንደዚህም ማለት አዲሱን ነገር ባሮጌው ፊደል መልክ ለመገልበጥ ቢዥምሩት ለአኀዞቹ የሚሆኑትን ፊደሎች በማጣታቸው የአኀዞቹ ቦታ ክፍት ሆኖ በመገኘቱ የሮማ ልዑካን ፖለቲክ ተጐልቶ ተገኘ። እነሱ ይህን ረቂቅ ሥራ የሚአውቅብን የለም በማለት አዲስ ቃል ፈጥረው ይህ ጥንታዊው ፊደል በዔዛና ጊዜ የነበረ አስመስለው የሥሩት ነው። ይህም ነገር የሠሩት ስለ ሁለት ነገሮች ነው። ፩ኛ የግዕዝ ፊደሎች ከሳብውያን ደቡብ የመጡ ናቸው ብሎ ለመጪው ትውልድ ጽሑፉን ከቀኝ ወደ ግራ እጅ አድርጎ ለማሳየት። ፪ኛው ዔዛናን በአብርሃና በአጽብሐ ቦታ ለመተካት ስለሚፈልጉ ለሚል በዔዛና አባት በዓልዓሜዳ ባ፬፻፹ ዓ.ም ፱ቱ ቅዱሳን መጥተው ስለነበር ፱ቱ ቅዱሳን የውጭ አገር ሰዎች ስለሆኑ ፱ቱ ቅዱሳንን የኛ ናቸው የሚሉ ሐሳብ ፈጥረው በነሱ እግር እንተካለን ለማለት አሳብ ስላደረባቸው በ፱ቱ ቅዱሳን ከአባ ሰላማ

## ግ ዓርብ

ጋር አብረው አስተምረዋል ለማለት እንዲመቻቸው መቸም እውነትን ሐሰት ሐሰቱን እውነት ማስመሰል የተሰጠ ሃብታቸው ስለሆነ በትውልድ እስከ ፵። በዘመነ ፮፻፹፯ የሚሆን በመካከል እያለ ያነን ሁሉ ማን አለብን በማለት ተራምደው ዔዛናን በአብርሃና በአጽብሐ ቦታ ለማቆም በብዙ ስለሚደክሙ ይህን ሁሉ ረቂቅ ሥራ ጥንታዊ ለማስመሰል አዲስ ነገር የሌላውን ጽሑፍ እየለቀሙ ልክ ሥራ አስመስሎ ለማታለያ ምስክር ለማድረግ ጥንታዊውን ጽሑፍ ከዋናው ላይ በፎቶግራፍ አንሥተው የተሠራ እርግጠኛ አስመስለው በጥንታዊው ፊደል መልክ ያዲሱን ዘመን ቃል ሲስፉ አኀዙ ላይ ሲደርሱ የአኀዙ ፊደል ስላስቸገራቸው የአኀዙን ቦታ ባዶውን እየተውት በመገኘቱ ሐተታውን ከላይ እንደ ገለጽኩት ይህ ሥራ ጥንታዊ አለመህኑን እነሱ በረቂቅ ፖለቲክ የሠሩት መሆኑን ለመረዳት ፩ኛ የእጅ ሥራ መሆኑን በ፵፫ኛና በ፻፲፪ኛ ገጽ የተጻፉትን መመልከት ነው። ደግሞ በጣም አስደናቂው በ፻፲፪ኛ ገጽ ተጽፎ የሚገኘው በእጅ ያልተነካው እርግጠኛው እያለ የዚህን ምስክርነት በማቃለል ወይም ማን አለብን በማለት ፪ቱንም ዓይነት ጽፈውት ይገኛል። በ፵፫ኛውና በ፻፲፪ኛው በ፻፲፪ኛው ተጽፈው የሚገኙ እርግጠኞች እንደገና ያልተከለሱ ናቸው። የቀሩት ግን በ፻፫ና በ፻፯ ገጽ የሚገኙት በእጅ የተሠሩ ለመሆናቸው እኔ በመሰለኝ አስተያየቴን አቅርቤአለሁ። ግን ይህን አስተያየቴን እቃወማለሁ የሚል ቢገኝ ማስረጃነቱን የምቀበለው ከነሐውልቱ የተነሳውን ፎቶግራፍ ነው እንጅ እነሱ ያዘመቱትን የነሱን ግልባጭ በጅ አዞር ቢሰጠኝ አልቀበለውም።

ስለ ሮማ ልዑካን ሐሰት ስብከት ፩ኛ ኢትዮጵያ የሚለው ቃል ከግሪክ የመጣ ነው ብለው ስለጻፉት ኢትዮጲስ ባለፈ በሽ፫፻ ዘመኑ ጽርዓውያ ስም አወጡለት ማለት ፍጹም ያልታረመ ሜዳዊ ንግግር መሆኑን አስረድቸ ጽፌዋለሁ።

፪ኛ ስለ ዮቅጣን ልጆች የዮቅጣን ልጆች በፋርሶች ዘመነ መንግሥት በአርጤክስና በአሐዊሽሮስ በ፫ሽ ፫ ዓ. ዓለም ኢትዮጵያ መጥተው ከህንድ የመጣውን ብራህማ የተባለውን ንጉሥ ገድለው ኢትዮጵያን ነጻ አወጡ ብለው ስለጻፉት የዮቅጣን ልጆች በሞቱ በ፪ሺ ፪፻ ዘመናቸው ነበሩ ማለት ከንቱ መሆኑን አስረድቻለሁ።

፫ኛ ከላይ እንደ ተጻፈው በ፻፫ና በ፻፰ ገጽ ተጽፎ የሚገኘው የማታለል መሆኑን እንደ ሚገልጽ ሐተታው ከላይ ተጽፎ ይገኛል።

፬ኛ የኢትዮጵያውያን ንጉሠ ነገሥት ገደረትን ወደ ዐረብ አገር ከክርስቶስ በፊት ፰፻ ዓ.ዓ ላይ ዘመተ ብለው የጻፉትን ሐሰት በመግለጥ። ብሱ ጊዜ የቆሙትን ሐውልት ባጼ ካሌብ ጊዜ የቆመ አስመስለው በማታለል የጻፉትን ገልጨ የዘመኑን ቊጥርም ጠቅሼ የነበረበትን ዘመን ፱፻፺ ዘመን ወደ ኋላ ትተው። ከክርስቶስ በፊት ፬፻ ዘመን ላይ በ፳፻፩፻ ዓ.ዓለም ላይ ማለት ነው። ዘግዱር (ገደረት) የነበረበት ከክርስቶስ በፊት ፩፻፫፻፺ ዓ. ዓለም ላይ ነበር። ከዚያ ጀምሮ እስከ ፬፻ ድረስ ፱፻፺ ዘመን ማለት ይህ ነው። ይህን ገልጨ አባጋስፓሪንም በ፵፰ኛው ገጽ በ፱ነኛው “መስመር እኛ ግን የኢትዮጵያ ሊቃውንት የጻፉአቸውን ተከትለን የቀዳማዊ ምኒልክ እናት መሆንዋን አረጋግጠን የኢትዮጵያ ንግሥት ሆና ከኢትዮጵያ ግዛትዋ ተንሥታ ወደ ኢየሩሳሌም በሄደችበት ዘመን የዓረብ አገር ግዛትዋ ነበረና በግዛትዋ በዓረብ አገር ብኩል ግመሎችዋን ወርቅና ሰንደል ዕጣንና ሽቱ አስጭና የሰሎሞንን

# ኀ ቀዳም

ጥበብ ለማየትና ለመስማት ወደ ኢየሩሳሌም ብለን የታሪክዋን ፍጻሜ አድርገናል ብለው የጻፉትን በመጋዘን የአረብ አገር ኢትዮጵያ ግዛት ሆኖ እስከ እስላሞች መበርታት ድረስ በኢትዮጵያ ነገሥታት እንደራሴዎች ሲገዛ መቆየቱን ብዙ ማስረጃዎች ይገኛሉ። አብርሃን ሽሞ የተመለሰ አጼ ካሌብ ነበር። አብርሃ ከሞተ በኋላ ክርስቲያኖችን ዙዋንስ የሚባል አይሁዳዊ ቢአስጨንቅም እንደገና የኢትዮጵያ ንጉሥ መጥቶ ዙዋንስን ገደለና ሌላ እደራሴ ሾሞ ተመለሰ። ይላል” በእግዚአብሔር መንግሥት ታሪክም በ፪፻፳ ገጽ ፪ኛ የዘመተ አጼ ገብረ መስቀል እነሆነ ታሪክ ይነግረናል። ያጼ ገብረ መስቀል ሹም እስከ ስንት ዘመን እንደ ቆየ ወደ ፊት ይመረምራል። ኢትዮጵያ ያረብ አገርን ይዛ ለመቆየትዋ በጥንታውያኑ ፊደሎች ቅርጽ መደብ ይዞ ይገኛል። ያባ ጋስፓሪን ታሪክ መሳቂያ ከመሆኑ በተቀር ሌላ ጉዳይ እንደማይጠይቅ ከላይ በተጻፉ ባ፬ቱ አርዕስቶች የተደረገውን መመልከት ላስተዋይ ገንዘቡ ነው። ካባ ጋስፓሪን አሳብ ዋና የኢትዮጵያ መሠረት ማፍረሻ ከተሰናዱ ከላይ ተጽፈው እንደ ሚገኙ ፬ቱ ወጥመዶች መፍረሳቸውን መረዳት ነው። የሮማ ልዑካን ዋና አድርገው ለማንም አስጠንተውት የነበረው የዮቅጣን ልጆች ሳባ ዑባል ኦፊር የህንዱን ንጉሥ ብራህማን ድል አድርገው ከኢትዮጵያ አስወጥተው አግዓዝያን ተባሉ እየተባለ የሚዘራው ጉም የብራህማ ዘመን በተገለጠ ጊዜ የሮማውያን የውሸት ታሪክ ከተዘራበት ማለት ከአማርኛ ተማሮች ልብ እልም አለ። ዓምድም መሰለ። ስለ አባ ጋስፓሪን ታሪክ ከቅዱስ ወንጌል ውስጥ ሉቃስ ፳ ፵፺ ኵሉ ዘይመጽእ ኀቤየ ወይሰምአኒ ቃልየ ወይገብሮ አርእየክሙ ዘይመስል። ፵፰ ይመስል ብዕሴ ዘሐነጸ ቤቶ ወከረየ ወአእመቀ ወሣረረ መሠረቶ ዲበ ኰኵሕ ወብዙኃን አፍላግ መጺኦሙ ገፍእዎ ወሐይዝት ለውእቱ ቤት ወስእንዎ አንቀልቅሎቶ እስመ ዲበ ኰኵሕ ተሣረረ እንደዚህ ሆኖ የተሠራውን የኢትዮጵያን መሠረት እገፋለሁ ብሎ መድከም የመሠረትን ሥራ ካለመመርመር የመጣ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ የመሠረተ መሐንዲስ ትክክለኛ መሆኑን ወይስ ምዓኒ ቃልየ ወይገብሮ ያለውን የተመለከተ መሆኑን ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር የተባለውን ንባብ በዳዊት መዝሙር በ፷፰ኛው ያለውን መመልከት ነው። አሁን ይህን የጌታን ቃል ለማስታወስ ያመጣሁት የሮማ ልዑካን የኢትዮጵያን መሠረት በማቃለል አስጠንተው እርግጠኛውን ምንገድ የኢትዮጵያን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን አጥፍተው የሮማን ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ ለማስፋፋት አስበው በመሠረቱ ከካም ከኩሳ ከሰብታህ ከኢትዮጵያ ከሳባ ዠምሮ በነጻነት ጸንቶ የኖረውን መንግሥት ነጻነቱ ተሰብሮበት የነበር በማስመሰል ዜጋ የነበረውን የዓረብ አገር ገዥና አቅኚ አስመስለው ልብ ወለድ ታሪክ ነገር እየፈጠሩ የጻፉትን ጽሑፍ በምርመራ ሐሰቱን የሚገልጽ ሚዛን የዘመኑ ቁጥር የጽሑፋቸውን መሠረት በቅጽበት ሊያፈራርሰው ስለቻለ። ፵፱ ወዘሰ ይሰምዓኒ ቃልየ

ወኢይገብሮ ይመስል ብዕሴ ዘሐነጸ ቤቶ መልዕልተ ምድር ዘእንበለ መሠረት ወገፍዕዎ ወሐይዝት ወድቀ ሶቤሃ ወኮነ ድቁቀ ይህ ሥራ የሮማ ልዑካን ያስታውሳል ወዘሰ ይሰምዓኒ ቃልየ ወኢይገብሮ ያለው ከላይም እንዳመለከትኩት የሮማ ልዑካን የመናኒ ልብስ ለብሰው መስቀልና መጽሐፍ ይዘው ከእናንተ ሃይማኖት የኛ ከናንተ ጥምቀት ከናንተ ቤተ ክርስቲያን የኛ ይበልጣል እያሉ ክርስቲያኖችን ሁሉ በገንዘብ እያታለሉ እየሰበኩ የውስጠ

# ጠ እጉድ

ምስጢር መቀባበያ አድርገው ከኋላቸው የመንግሥታቸውን ጦር ስበው በሰላም በሚኖረው ሕዝብ መካከል ማለያየት ማጋደል አምጠው እስከ ሚሊዮን ሕዝብ አስፈጅተው ይህን ያህል ደም በፈሰሰበት ምድር ላይ ቤተ ክርስቲያን ሠራን እያሉ ሕዝቡን በመለያየት ምንገድ ሲመሩ ይታያሉ። ይህ ሁሉ ሥራ የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ውጭ የሆነ ማለት ለማለት አስደፈረኝ የእግዚአብሔርን ቃል የሚአውቁ ቢሆን ለክርስቲያን የተጻፈውን ፲ቱ ቃላትን በተመለከቱ ነበር። ተመልክተው ቢሆን ኦሪት ዘፀዓት ፳ ከ፫-፲፰ የተጻፈውን ያገኙት ነበር። ሁለተኛ በኦሪት ዘዳግም ሕግ ፯ ከ፯-፳፪ ከመጨረሻው በ፳ ፩ ቁጥር የወንድምህን ሚስት አትውደድ የወንድምህን ቤቱን እርሻውን አገልጋዩን ላሙን አህያውን እንስሳውን ማነኛውንም አትመኝ ብሎ ያዘዘውን ለማየት በቻሉ ነበር። ፫ኛ ኦሪት ዘዳግም ፲፱ ፲፬ ወኢትትኃለፍ ደወለ ቢጽከ ዘሠርዑ አበዊከ ውስተ ርስትከ ዘተዋረስከ ምድር እንተ ወሀበከ እግዚአብሔር መክፈልተከ ያለውን ይመልከቱ ነበር። ዘይሰምዕ ቃልየ እንዳለው መስበኪያቸውን መጽሐፍ ተሸክመዋል ወኢይገብሮ ባለው የመጽሐፉን እነ ኢትቅትልን ተራምደው ለሥጋዊ ማደሯቸው ማስፋፊያ እንዲሆናቸው የኢትዮጵያን ታሪክ እያፈለሱ ጽፈው ለመጭው ትውልድ ልብ ማደንዘዣ ፬፻ ዘመን ሲክቡት ሲቆልሉት የኖረው የውሸት ሕንፃ ከላይ ወገፍዕዎ ወኃይዝት ወወድቀ ሶቤሃ ያንጊዜ ወደቀ። ወኮነ ድቁቀ ወድቆም ደቀቀ ዓመድ ሆነ ቅዱስ ዳዊት ወጻላዕቱሂ ሐመደ ይቀምሑ። ያለው ተፈጸመ ዓመድ ሆነ። እንግዲህ የመሠረቱን ነገር ካሳየን ይህ የነሱ የውሸት ሕንፃ ምን ያህል እንደነበር ከሥሩ ካ፲፰ኛው ገጽ ዠምሮ ዝርዝሩን የታሪኩን ታሪክ ከ፳ሽ፲፫ ዘመን እስከ ፬፻ ዘመን በመካከሉ በሚገኘው በ፹ው ዘመን ብቻ ከዚያ ወደ ላይ እንዳይጨመር ንጉሥ ገደረት በ፬፻ ከክርስቶስ በፊት ወደ ዓረብ አገር ዘመተ ያሉት ስንኳን ከወደፊቱ ዘመን ለማስጨመር ወደ ዓረብ አገር ሲዘምት እንደተጻፈለት ገናናነቱ ወደኋላው ከ፹ያውም ዘመን ለመቀነስ ያሳስባል። ይሁን እንጂ እንደነሱ አሳብ ባ፳ሽ፲፫ ዓመተ ዓለም ላይ እነ አሐሽዊሮስና እነ አርጤክስስ በፋርስ ንጉሥ ጊዜ ከኅንድ እስከ ኢትዮጵያ ፻፳፯ አህጉር ይገዙ በነበር ጊዜ ኢትዮጵያም ከዚያው ውስጥ ነበረች ብለው የሮማ ልዑካን ፈጠሩላት ኢትዮጵያ መጥቶ የተዋጋውንም ሰው ስም ብራህማ ይባል ነበር ብለው ፈጠሩላት። ደግሞ ለዚሁ ድጋፍ ለሐሰቱ እንዲስማው በማለት የዮቅጣንን ልጆች ከባቢሎን ግብም መፍረስ አስቀድሞ የነበሩትን ሳባ ዑባል ኦፊር የተባሉትን ከዚህ ዓለም በተለዩ ፪ሽ፩፻ ዘመን በመቃብር ያሳለፉትን ሰዎች አስነሥተው ብራህማን ከኢትዮጵያ አስወጡና አግዓዝያን ነጻ አውጭዎች ተባሉ ብለው ታሪክ የጽሑፉ አርስት አድርገውታል። በዚህም አያፍሩበትም ምክንያቱም ሐሰት በነሱ ጌጥ ስለሆነ ነው ማለት እስከዚህ የደረሱበት የዮቅጣንን ልጆች ስም ለመፈለግ መቸም ኢትዮጵያ ለመከፋፈል ስለሚፈልጉ የንግሥተ ሳባን ስም ለመውሰጃ። ፩ኛ ሳባን ይህን ስም የፈለጉበት ከማከዳ በፊት። ሳባ የምትባል ነግሣበት የነበረውን ሳባ በሚባለው በዮቅጣን ልጅ ስም አስታከው ለመውሰድ ነው። ፪ ኦፊርን የኮፊር የሱማሌን አገር መለያ ለመፍጠር። በጠረፍ የሚገኙ ሰዎች ዛሬ በሃይማኖት እንደ ዓረቦች ሰልመው ስላዩ በዘርም እናዛምድና እንለያያለን በለው በማሰብ የሠሩት ነው። ደግሞ ይህን ሲሠሩ ማንም ሰው ከኛ በላይ

# ጡ ሰኑይ

ይህን የሚመረምር አለብን ባለማለት ነው። ይህም ረቂቅ ተንኮላቸው ይህ ብቻ ሳይሆን የሠሩት ፖለቲክ ሁሉ ብዙ ነው። ስለ ሳባውያን እያሉ የኢትዮጵያን ወገን ለመለያየት የፈጠሩት። ፪ኛ ክፍል።

አግዓዝያን ከነርሱ የሚወርዱባቸው የሳባውያን አጭር ታሪክ ፩ኛ የሳባ ወይም በዓረብ ደቡብ የነበሩት የሳባውያን ጥንተ መሠረታቸው የመንግሥታቸው አጭር ማስረጃ። ኢትዮጵያ የሚባለውን አገር የያዙት ነገደ ሴም ከሰፊው አውራጃ ደቡባዊ ዓረብ የመጡ መሆናቸው ባጭሩ ታሪካችን ላይ ይታያል"። እንደዚህም ማለት ከሳባ መንግሥት የመጡ ናቸው ማለት ነው ይላሉ። ያላወቀ ሰው ሁሉ ይህን እየተቀበለ አዲስ ታሪክ አገኘን እያለ ገንዘቡን ከማውጣቱም በላይ የሀገሩን ክብር የነጻነቷን ዘመን እየቀነሰባት ሲሄድ አዲስ ነገር ሳይሆንበት እንዳልቀረ የማንም ሰው ልብ ይታዘባል። ኢትዮጵያዊ ይቅርና የውጭ አገር ሰው ቢሆን እንኳ ሳይቸገርበት የቀረ አይመስለኝም። ከሳባ መንግሥት የመጡ ናቸው ብለው ጽፈዋል እንደለመዱት እነሱ ከልባቸው አውጥተው የጻፉት ነው እንጅ የሴም ዘሮች በደቡብ ዓረብ ላይ መንግሥት አቋቁመው እንደነበረ በምን ጽሑፍ ይገኛል። የካም ዘሮች በሴም አገር መንግሥት አቁመውበት የነበረው ሁሉ በቅዱስ መጽሐፍ ይገኛል። ጽሑፉም በመጽሐፍ መገኘቱ ለዛሬ ምስክር እንዲሆን በማለት ነው። የደቡብ ዓረብ የተባለው አገር የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበረ እንዳይካድ በሐውልቱ ተጽፎ የተገኘው በጥንታዊው ፊደል ቅርጽ የተጻፈው ይመስክራል። ፊደሎች በየዘመኑ እየተሻሻሉ እንደመጡ በየቦታው ይገኛሉ። ኢትዮጵያ ያረብ አገርን ከኢትዮጵያ ደርባ ትገዛ እንደነበረ አባ ጋስፓሪንም ጨርሰው አልካዱም። ቢክዱም እንደዚያው ከ፹ያው ዘመን አያልፉም። (በ፲፱ነኛው ገጽ ፪ኛ የሳባ መንግሥት በደቡባዊ ዓረብ ውስጥ የዓረብ መጻሕፍት ጥንት በደቡባዊ ዓረብ የሚኖሩት የቃጣን ዘሮች ነበሩ ይሉናል) እንግዴህ ይኸውና ማስረጃው ሲሰናዳ የዓረብ መጻሕፍት ነበሩ እያሉ ይሉናል ተባለ። መቸም እውነተኛ ምስክር ሊገኝ አለመቻሉን ያውቃሉና ቢቸግራቸው ያረብ መጻሕፍቶች ብለው አወሩ። እንግዲህ ይህ ታሪክ እርግጠኛ ለመሆን የሚችለው በቂ ማስረጃ ሳያገኝ ከቁም ነገር ሊገባ ስለማይችል ቁጥሩ ከገለባ ነው። ይኸውም ፩ድ ተብሎ መቆጠር ይዠምራል ባ፲፱ነኛው ገጽ (ካ፲፱ መስመር ግርጌ ፫ኛ የሳባውያን አጭር ታሪክ በባቢሎናውያን ላይ የጥንት ጽሕፈት በሳባ ላይ ይነገራል። ምናልባት በሳባ መንግሥትና በጥንቱ በባቢሎን መንግሥት የወዳጅነት ግንኙነት ይኖር ይሆናል ብለዋል)። አስቀድሞ የሴም ዘሮች በዓረብ መንግሥት ማቆማቸው ሳይረገጥ በኢትዮጵያ መሠረት ሲያያዝ የወረደውን የቋንቋ ጽሑፍ ኢትዮጵያ ስለገዥነቷ ወደ ዓረብ አገር ወስዳው የነበረውን የፊደልና የጽሑፍ ምልክት ላረቦች ለመስጠት በጣም ስለሚደክሙ በባቢሎን ከተማ ላይ በዓረብ አገር የሚገኘውን ጽሑፍ የመስለ ቢገኝ ናምሩድ የኩሳ ልጅ በመሠረተው መንግሥት ከተማ ውስጥ የተገኘው ጽሑፍ ከኢትዮጵያ ቋንቋ የተመሳሰለ ነው በማለት ፋንታ ተገዥ በነበሩት ሰዎች ስም ለመጥራት መድከም በቅርቡ ከመሄድ በሩቅ ይሻለኛል እንደሚል ያለ ነው እንጅ ባቢሎንን ያቀና የኩሳ ልጅ ናምሩድ ስለ ሆነ ካረቦች ግንኙነት ከማለት ከወንድሞቹ ከነሰብታህ ማለት የተሻለ ነበር። ናምሩድን መጻሕፍቱ እንደሚአስታሱ ኦ. ዘፍጥረት ፲፰ ወኩሳ ወለዶ ለናምሩድ ወውእቱ ኮነ ያርብሐ በምድር። ፲ ወኮነ ቅድመ

# ጢ ሠሉስ

መንግሥቱ ባቢሎን ወአረክ ወአርከድ ወካሌን በምድረ ሰናዖር እነዚህን ሁሉ አገሮች ንጉሥ ሆኖ ይዟቸው እስከ ዘሩ ኖሮበታል እስከ ብዙ ጊዜም የናምሩድ አገር እየተባለ ሲጠራበት እንደኖረ ከመጽሐፈ ነቢያት ሚክያስ ፭ ፮ ወርዕይዎ ለአሶር በኵናት ወበምድረ ናምሩድ በውስተ ኅዝእቱ የሚለውን ማየት ነው። ስለ ከነዓን የታወቀ ነው እርግጠኛው ነገር ሁሉ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ መረጃው ይገኛል። እንዲሁ በጽሑፍ

መረጃ ሳያገኙ ያለሕግ በተንኮል ታሪክ እንጽፋለን እያሉ አገርንና አገርን የሚአቀያይም ሥራ ሲሠሩ ይገኛሉ ይህም ፪ኛ ሐሰት ተብሎ ይቆጠራል። ከዚህም ዝቅ ብሎ (እነዚህ ጽሑፎች ከክርስቶስ በፊት ፫ሺ ዓመት በፊት መቅድማቸውን ማስታወስም በጣም ይጠቅማል" ስለዚህ ለሳባ ጥንታዊ ታሪክነት የሚመሰክር የዓመት ቁጥር አለን በ፳ ገጽ ባ፭ኛ መስመር በደቡባዊ ዓረብ ውስጥ የተገኙ ብዙዎች ጽሑፎች አሉ። ከክርስቶስ በፊት ፰፻ ዘመን ይቀድማሉ እነዚህ እጅግ ብዙ የሆኑ ጽሑፎች ስለ ሳባውያን ሲናገሩ እጅግ ከፍ ወዳለ ሥልጣኔ የደረሱ እንደነበሩ ይናገራሉ"። እንግዲህ ይህን ስራቸውን መመልከት ነው እነዚህ ጽሑፎች ከክርስቶስ በፊት ፫ሺ ዘመን ነው ብለዋል። ይህም ሕጋዊና እውነተኛ ነገር አይደለም። ይህ የዘመን ቁጥር በፈረንጆች እንደ አይሁድ መሆኑ የሚካድ አይደለም። እንግዲህ የዓለም ቤተ ክርስቲያን ከአይሁድ በተቀበለችው መጽሐፍ ቅዱስ አቆጣጠር ከፍጥረት እስከ ክርስቶስ ፬ሺ እንኳ አይሞላም። ሐሰት ነው ለሚል ዘመን እያሰፈሩ የጻፉ ሊቃውንቶች ሁሉ የጻፉት ይመሰክራል እንግዲህ በዚህ ሃሳብ ፫ሺ፱፻፰፫ት ዘመን ይሆናል ከዚሁ ፫ት ዘመን ሲነሳለት ፱፻ ዘመን ይቀራል እንግዲህ በዚህ ሂሳብ ሲታሰብ ነገሩ እንደምን ያስደንቃል ከፍጥረት እስከ ክርስቶስ ያለው ዘመን ልክ ፫ሺ ፱፻፹፫ ሲሆን ከዚሁ ፫ቱ ሺ የነዚህ የዮቅጣን ልጆች ጽሑፎች ዕድሜ ሲወስደው ከዮቅጣን ልጆች ዠምሮ እስከ ፍጥረተ ዓለም ያለው ዘመን ፱፻ ማለት ነው። እንግዲህ የዓለም ቤተ ክርስቲያን በተቀበለችው እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ቁጥር ሂሳብ ከፍጥረት እስከ ማየ አይኅ ፩ሺ፮፻፶፮ ዘመን ነበር። ይህም የሚካድ አይደለም። እንግዴህ በዚህ ሂሳብ ፯፻፶፮ ዘመን ከመካከል መጥፋቱ ነው። እንግዲህ ያባ ጋስፓሪን ታሪክ እንደዚህ ያለ እውነተኛ ታሪክ ነው። እንደዚህ ያለ መርማሪ ሳይገጥመው ያባ ጋስፓሪን ታሪክ ዓምድ ይዞ ሲታይ የብዙዎችን ልብ ሳይማርክ አልቀረም በ፳ኛው ገጽ የተጻፈው ዝባዝንኬ በረቂቅ ሮማዊ ፖለቲክ ተሸፍኖ የነበረው ረቂቅ ተንኮል ባመጣው ሥራ በዘመን ቁጥር ቢመዘን ከገለባ የቀለለ ሆኖ ተገኘ። ይህም ፫ኛው ሐሰት ይገባል። ፬ኛ ባ፳ኛው ገጽ (በ፱ነኛው መስመር የሳባ ነገሥታት የተባሉ ከተማቸውን ማዕሪብ ላይ አድርገው የነገሡት ነገሥታት ጊዜ ይገኛል። በኢትዮጵያ ላይ የሚገኘውን መረብ የሚባለውን የኸርማ ስም የምናገኘው ከዚህ ሳይሆን አይቀርም። እነዚህ ነገሥታት ፲፫ ናቸው የዚህ ጊዜ መዠመሪያ ከክርስቶስ በፊት ፯፻ ዓመት ይቀድማል ይላል" ያባ ጋስፓሪን ታሪክ መቸም አስደናቂ ነው። ከዘመን ቁጥር አፈስ ይደረግና እንደፈቀደ ጣል ይደረጋል ምክንያቱም ፩ድ ፩ድ ሰዎች ታሪክ አጣርተን እንጽፋለን የሚሉ የዘመኑን ቁጥር እያስተማመኑ እየመዘኑ ቁትር እየዘገኑ ይጨምሩበታል። ማዕሪብ ማለት መረብ በሚባለው የነገሡ ነገሥታት ፲፫ት ናቸው ብለዋል። ይህም የሆነው ከክርስቶስ በፊት ፯፻ ዘመን ይቀድማል ይላል።

# ጣ ረቡዕ

እንደዚህ በለው በጻፉ ጊዜ በ፴፫ኛው ገጽ በ፳፫ኛው መስመር (ከነዚህም ከሐበሳት በኋላ በዓረብ ደቡብ በኩል ይኖሩ ነበር። አባ ሳባ ኡባል አፊር የተባሉት ፫ቱ የዮቅጣን ልጆች ተከታትለው ወደ ኢትዮጵያ ገቡና በኩሽ ልጅ በጺኦሪ እየተገዙ ፭ ዓ ያህል ከሐበስ ዘሮች ተቀላቅለው በኢትዮጵያ ላይ ተቀምጠው ነበር። በዚህ መካከል በራሁማ የተባለው የህንድ ንጉሥ መጥቶ ኢትዮጵያን በግፍ ወረራት ጺኦሪ የተባለውም የኩሽ ነገድ ድል አድርጎ ኢትዮጵያን ያዘ። ከዚህ በኋላ ሳባ ኡባል አፊር የተባሉት የዮቅጣን ልጆች ከያሉበት ተሰብስበው የሐበስን ዘሮች ይዘው ብራኅማ (ገጽ ፲፮) የተባለውን የህንድ ንጉሥ ድል አድርገው ከኢትዮጵያ አስወጥተው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻ አወጡ። ከዚህ የተነሳ አግዓዝያን ነጻ አውጭዎች ተባሉ አገሪቱም ኢትዮጵያ ብሔረ አግዓዝያን ተብላ ትጠራ ዠመረች ብለዋል" አባ ጋስፓሪን የፖለቲኩን ነገር ሲአውጠነጥኑ የሚጽፉትን ነገር ማስተዋል አልቻሉም ማለት ምክንያቱም የጻፉት ጽሑፍ መሠረት

የሌለው ልብ ወለድ ስለሆነ ነው። ከላይ የዮቅጣን ልጆች ማዕሪብ መረብ ላይ የነገሡት ነገሥታት ቁጥር ፲፫ ይሆናሉ። ዘመኑም ከክርስቶስ ልደት በፊት ፯፻ ዘመን አስቀድሞ ነው ብለው ጻፉ። እንደዚህ ብለው ከጻፉ በላይ የተጻፈውን የዮቅጣን ልጆች ብራህማን ድል ያደረጉበትን ዘመን ፪ኛ ብራህማ የተባለው ንጉሥ መጣ የተባለበትን ዘመን ይህንንም

ጽሑፍ ሲጽፉ ማነኛውንም አልተገነዘቡትም ነበር ይመስለኛል። የዮቅጣን ልጆች ስንት ናቸው። ፩ድ ጊዜ በነአርጤስስ ዘመን ከክርስቶስ በፊት ባ፬፻፹፫ በታች መጡ ይሏቸዋል። ደግሞ ሁለተኛ ከክርስቶስ ልደት ፮፻ ዓመት ነበሩ ይላል። የነገሥታቱን የቁጥር ድምር ፲፰ት ብለው ጽፈዋል። ብዙ ችግር አግኝተዋል። ደግሞ ከዚሁ ግርጌ መዠመሪያው ንጉሥ ቃሪባኤል ዋጣር ይባላል ብለዋል። እንግዲህ ይህ ቃሪባኤል ዋጣር ፪ኛ ያሉት መዠመሪያ የነገሠ እሱ ነው ተባለ መንግሥቱን በምን አገኘው አባቱስ ልጁስ ማን ይባላሉ። ንጉሥ ነው ሲባል ከላይ አባቱ ከታች ልጁ እንደምን ይታጣል። ይህም እንደዚያው ፍሬ የሌለው ገለባ ነገር መሆኑ ነው። ይህም ሁለቱ ሐሰት ይቆጠራል ፯ ሐሰት ይባላል። ደግሞ በዚሁ ባ፲፰ኛው (መስመር በዚህ ጊዜ የተስፋፋ ከዚያ አንሥቶ ስባውያን ቀይ ባሕርን ተሻግረው መዠመሪያ በኢትዮጵያ ምሥራቅ ዳር ዳሩን ሰፈሩ። በኋላ ግን ቀስ በቀስ እያሉ ወጥተው በኢትዮጵያ መካከል ከሚገኙት አውራጃዎች ገቡ። በፊት የሚኖሩበትን የኩሽን ዘሮች ድል አድርገው ኢትዮጵያን ያሰለጡኑ ሳባአውያን ናቸው። ከክርስቶስ በፊት ፰፻ ዓመት ነው ብለዋል"። ከላይ ማዕብሪ ላይ ከተማቸው ነበር። የነገሥታቱም ቁጥር እስከ ፲፰ ተብሎ ነበር። ደግሞ እንደገና ማዕብሪ የሚባለው ከተማ ቀረና እንደገና መዲናውም ተለውጦ በምሥራቅ በኩል በቀስ መጥቶ በኢትዮጵያ መካከል ከሚገኙ አውራጃዎች ገቡና በፊት የነበሩትን የኩሽ ዘሮች ድል አድርገው- ኢትዮጵያን ያሠለጡኑ ሳባውያን ናቸው። ብለው ጻፉ ሁለቱም የተለያየ ነው። ድል አደረጉ የተባለውስ ከማን ጋር ተዋግተው ነው። በዚያ ጊዜስ ከነሱ ዋና እንደ ንጉሥ የነበረው የጦር አለቃው ዘመኑም ተብልዋል። ያው ልማዱ ገለባው ነገር ነው እንጅ ፍሬ ያለበት አይደለም። እንደዚያው ከ፹ንያው ቤት ሊወጣ አልቻለም ፺ኛው ሐሰት ይባላል። ፪ኛ በ፷፯ኛው (መስመር ከዚህ በኋላ በሳባ

## ጤ ኃሙስ

መንግሥት መናገሻ ውስጥ የሳባ የረይዳንና የሒምያር ነገሥታ ጊዜ የተባለ አለ። የነሱ መናገሻ ከተማ ዛፋር ነበር። ሮማውያን የኸንን የሳባን መንግሥት ያውቁት ስለነበር እጅግ ሀብታምና ኃያል መንግሥት እንደ ነበረ ይሉናል። በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ስንናገር ገደረት የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ የሳባን ንጉሥ ለመርዳት ቀይ ባሕርን ተሻግሮ አረብ አገር እንደዘመተ እናያለን ብለዋል"። ይኸ ሁሉ የተደረደረው ሐሰት ለማደናገር ታስቦ የተፈጠረ ነው ብለው ዛፋር የሚባለው አረብ የነበረውን ከተማ ነው። ትንሽም ኃፍረት ሳይታሰብ ገደረት የሳባን ንጉሥ ለመርዳት ቀይ ባሕርን ተሻግሮ አረብ አገር እንደዘመተ እናያለን ይላሉ። እንደዚህም ማለታቸው በ፸፪ኛው ገጽ" በ፹፩ኛ መስመር ይህም የኢትዮጵያ ንጉሥ በጀግንነትና በቆራጥነት መዠመሪያ ጊዜ ባሕርን ተሻግሮ ከሠራዊቱ ጋር ተሰልፎ ከዓረብ ነገሥታት ጋር ጦርነት ያደረገ ገደረት የተባለ ንጉሥ ነው። ይሁን እንጅ ይህ ገደረት የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ ታሪክ እንደሚነግረን በርዙ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ኢትዮጵያ እጅግ የበረታችና የሠለጠነች ሰፊ አገር እንደነበረች የታሪክዋ ሁኔታ ያስረዳልናል። ይልቁንም ከሁሉ የበለጠና የሚአስደንቀው እንደ ታምራትም በሚታየው በዚያ ዘመን የኢትዮጵያ ንጉሥ ለብዙ ሠራዊት የሚበቁ መርከቦችና ጀልባዎች አሠርቶ ሠራዊቱንም አስከክቶ ከኢትዮጵያ ተነስቶ ባሕርን ተሻግሮ በዚያ ዘመን በጣም የሠለጠኑና የበረቱ ናቸው ተብለው ከሚጠሩት ከአረብ ነገሥታት ጋር ተዋግቶ ድል በማግኘቱ ነው።) ብለው የጻፉትንና በ፷፩ኛው ገጽ በ፩ኛው "መስመር የኢትዮጵያ ንጉሥ የሳባን ንጉሥ ለመርዳት ቀይ ባሕርን ተሻግሮ አረብ አገር እንደዘመተ እናያለን።

ብለው ሁለቱንም ጽፈውት ይገኛል" የትኛው ነው የሚጨበጠው ቃላቸው ባንዱ መርጋትን አለመቻሉ ፖለቲኩን ሲከተሉ ነው። የዚህም የቃላቸውን መለያየት ረቂቅ ተንኰልን የፖለቲኩን አስተያየት ሳባ የሚባለውን ኢትዮጵያ የምትጠራበትን ስም ለአረቦች ለመስጠትና በሐውልቱ ላይም የተቀረጸውን ሁሉ ለመለዋወጥ ያሰቡትን ተንኰል በመገላለጥ የነገሩን ሐሰትነት በገዛ ጽሑፋቸው እያስተማመንሁና እያጋጨሁ በረቂቁ የተሠወረውን እያጐላሁ

ላንባቢዎች ህሉ የጉዱን ታሪክ አሳያለሁ። ይህም ፷ኛ ይባላል። ፺ኛ በዚህ ገጽ በ፫ኛው መስመር (የሳባ የራይዳን የሐድራሙት የያማናት ነገሥታት ጊዜ ከሚባለው የመንግሥቱ ዋና ከተማ ዛፋር ነው። ሌላም ትልቁ ከተማ ናግራን ነበር። ከዚህ በኋላ ደግሞ መንግሥቱ የሒምያር ነገሥታት የተባለበትን ጊዜ አለ። እዚህ ላይ ስለ ሳባውያን መንግሥት ጥቂት ረዥም አድርገን መናገር የያዟትና ያሠለንዋት የሴም ዘሮች የመጡት ከዚህ መንግሥት መሆኑ ነው ይላሉ)። ውሸት ካልቸገረ በማለት ዓምዱን በከንቱ ፈጅተውታል። የሴም ዘሮች ከየትኛው መንግሥት ነው መጡ የሚባለው ሁለተኛው ደግሞ የአክሱም ነገሥታት መንግሥታቸውን ካስፋፉ በኋላ እንደገና ቀይ ባሕርን ተሻግረው በሳባ መንግሥት ላይ ብዙ ጊዜ ዘምተው አገሩን መያዛቸውን ነው ይላል)። እንግዲህ ያባ ጋስፓሪን ድካም ሁሉ ከላይም እንዳስታወስኩት ልፋታቸው ሁሉ ኢትዮጵያ የምትጠራበትን ሳባ የሚባለውን ስም ለደቡብ ለመስጠትና ለማስጠናት ሳባ የሚባለውን-ስም ላረብ ካስጠኑ በኋላ በኢትዮጵያ ይደረግ የነበረውን ታሪክ ለዓረብ አገር ለመስጠት ነው። ደግሞ በዚሁ ምክንያት

# ፐ ዓርብ

በኢትዮጵያ ላይ የዓረብን ዓላማና ሃይማኖት የሚወዱ ሰዎች ለቁጥር በርከት ማለታቸውን ስላዩ ከምድር ተነስተው እውነቱና ሐሰቱን እያደባለቁ ላንባቢም ጽሑፉ አስቸግሮ ፩ድ ጊዜ ፩ድ ፩ድ ጊዜ ፩ድ እየተናገረ ውስጠ ምስጢሩን ሳይገለጥ ፫ ዓመት ለመቀመጥ ቻለ። አሁን ግን ይህን የ፩ መቶ ዓመት የፖለቲክ ድልብ ውስጡን ገብቸ በየመንገዱ እንዲሆን ሳደራጀው የሮማውያን ሕንፃ እንደ ባቢሎን ግምብ ሲናድ ሠሪዎቹን ሳይጫናቸው አይቀርም ይመስለኛል። ባ፲፪ኛው መስመር የአክሱም ነገሥታት በተውልን ጽሑፍ ላይ የከሡም ነገሥታት የሒምያር የራይዳን የሳባውያን የስልሔና የቲአማ ነገሥታት ብለው በኢትዮጵያ ታሪክ እንደጠሩ እናያለን። ይኸውና በሐውልት ላይ ተጽፈው የሒምያር የራይዳን ብሎ ከመካከሉ በላይ የሳባውያንን እዚሁ ጨምረው በሐውልቱ እንደ ተጻፈ ገልጠው ጽፈውታል። ከላይ እንዳመለከትኩት ሳባ የሚባለውን ስም ለአረብ አገር ለመስጠትና ለማስጠናት ሲሉ ረቂቅ ተንኮላቸውን ሰው ስላላወቀው ነገሩን አሁን ይኸው መግለጥ ዠምረው ይገኛል። በ፲፯ኛው መስመር (የአክሡም ነገሥታት ሁለት ጊዜ በደቡባዊ ዓረብ ላይ እንደነገሡ የሚያስረዳ ዋና ምስክር አለን። እንደዚህም ማለት መዠመሪያ ከጌታችን በኋላ ከ፫፻ ዓመት አንስቶ እስከ ፫፻፸ ዘመን ገዝተውታል።

፪ኛም ካሌብ እነ አጽብሐ ዓረብ አገር ከዘመቱበት አገሩንም አስገብረው የአክሡም ግዛት አድርገው እንደራሴ ሸመውበት ካ፭፻፳፭ ዓ.ም እስከ ፭፻፸ ዓ.ም ገዝተውታል ይላል)። እንግዲህ ከላይ እነ ንጉሥ ገደረት ዘምተው እንደ ነበረ ጊዜውም ወደ ላይ እንዳይወጣ ዘመኑን አሳጥረው ፩ድ ጊዜ አረብን አገር ንጉሥ ሊረዳ ደግሞ በሌላ ቦታ ላይ ከአረብ ጋር ሊዋጋ ሄደ ከዓረብ ነገሥታት ጋር ተዋግቶ ድልን አግኝቶ የሚለው ቀረና የሄደበትንም ዘመን ከክርስቶስ በፊት ፬፻ ዘመን ብለው ወደ ታች አውርደው ነበር። ይኸውም ቀረና እንዲያውም ከክርስቶስ ልደት በኋላ ሆነ። የንጉሥ ገደረትን ታሪክ በ፸፪ኛው ገጽ እስከ ፸፫ኛ ገጽ መመልከት ነው። አጼ ገደረት የነበረበቱ ዘመን ከላይ ተጽፎ ይገኛል። እውነት ሐሰት ሐሰቱን እውነት ለመሆኑ ይቻል እየመሰላቸው አባ ጋስፓሪን ብዙ ደከመዋል (ዓረብ ላይ ከተሾሙት የአክሡሙ

እንደራሴዎች በጣም ስሙ የገነነውና ኃይለኛይቱ የታወቀው አብርሃ ነበር። ስለርሱም በዚህ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ እንተርክለታለን። በርሱ ጊዜ በደቡባዊ ዓረብ ያሉት ክርስቲያኖች እጅግ ብዙ ስለነበሩ የንጉሡ እንደራሴ አብርሃ በማዕብሪ ከተማና በሳናዓም አሁን የየመን መናገሻ ከተማ በሆነው ማለት ነው። ብዙ ትልልቅ ቤተ ክርስቲያኖች አሠርቷል ብለዋል" ይህ ታሪክ መጻፉ ለማታለያ መቃረቢያ ማለት ነው እንጅ ይህ ታሪክ አዲስ ነገር አይደለም የታወቀ ነው። ከላይ ንጉሥ ገደረት ዘመተ ተብሎ ድል ማድረጉም ታውቆ በምን ምክንያት ግዛቱ ተቋረጠ እንበል። በሐውልቱስ

ላይ የህምያር የረዳይን የያማናት ንጉሥ እየተባለ ከኢትዮጵያ ከተሞች ጋር በምን ምክንያት ተጻፈ። ጽሑፉም ከልደተ ክርስቶስ በፊት ባለው- ፊደል ቅርጽ ምስክር የሚሆነው አስረጅ በ፻፲፩ ገጽ የሚገኘውን ማስተዋል ነው። በ፳፪ኛው ገጽ ባ፭ኛው" መሥመር ለኢትዮጵያውያን ተማሮች የሳባውያንን ታሪክ እንዲያውቁ የሚአስገድድ

## ጠ ቀዳም

ሌላ ምክንያት አለ" ይኸውም ምክንያት የቋንቋ ነገር ነው። ተማሮች መልካም አድርገው እንደሚያውቁት የኢትዮጵያ ደንበኛው ቋንቋ ግዕዝ በቀጥታው ከሳባውያን ቋንቋ የመጣ ነው ይላሉ"። ይኸውና የሮማ ልዑካን አሳብ የኢትዮጵያን መሠረት ነጥቆ ለደቡብ ዓረብ ለመሥጠት ለለሆነ ውሥጠ ሥራቸውን መመልከት ነው። በረቂቅ ተንኮላቸው የሠሩትን ታሪክ በ፻፫ኛው ገጽ ላይ ያገኘሁትን የተንኮል ሥራቸውን ከላይ ገልጬ ጽፌዋለሁ። የሮማ ልዑካን አሳብ የወጠኑት እቅድ ብዙ ነው። ፩ኛ ስለ ኢትዮጵያ ትርጓሜ ኢትዮጵስ የሚለውን ስም ያወጡ ግሪኮች ናቸው ይላሉ። ፪ኛ ግብጽ ኢትዮጵያን ትገዛ ነበር ይላሉ። ፫ኛ መጻሕፍተ ብሉያትን ከጽርዕ ወደ ግዕዝ የገለበጠ አባ ሰላማ ነው ይላሉ ፬ኛ ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ የገባ በአባ ሰላማ ነው ይላሉ። ፭ኛ ኢትዮጵያ የደቡብ ዓረቦች ይገዟት ነበር ይላሉ። ፮ኛ ኢትዮጵያ ሳባ ተብላ የምትጠራበትን ለደቡብ ይሰጣሉ። ፯ኛ ኢትዮጵያ የዓረብ አገርን ትገዛ እንደ ነበረ በዘመነ አዲስ ያለውን አምነው የኦሪቱን ከደዋል። ፰ኛ አብርሃንና አጽብሐን ሠርዘው በነሱ ቦታ ዔዛናን አግብተዋል። ፱ነኛ የፊደልን ደረጃ በኢትዮጵያ ያደራጀ አባ ሰላማ ነው ይላሉ። ፲ኛ ዛሬ የሚገኘው ፊደል መሠረት ከደቡብ ዓረብ የመጣ ነው ይላሉ። እነዚህ ፲ሩን መሠረቶች ሁሉ በረቂቅ ጥበብ አፍልሶ ኢትዮጵያን ወደ አዲስ ቅናቴ ቦታ ለማድረስ ነው የሚጣጣሩ። ኢትዮጵያ ዓረብ አገርን ትገዛ በነበረችበት ጊዜ ሮማ ለመመሥረት ገና አልታሰበችም ነበር። የኢትዮጵያ ዓላምና ነጻነት የሚታወቀው በቋንቋዋና በፊደሏ ስለሆነ። ከዓለም የተለየች ሆና የምትታወቅበት በቅዱሳት መጻሕፍትም ውስጥ ዋናው ምሥጢረ እግዚአብሔር የሚታወቅበትን የግዕዝ የሳባውያን የደቡብ አረብ ፊደል ነው እያሉ ረቂቅ ተንኮላቸውን በግብዞች ልብ ላይ ሲዘሩ ይገኛሉ። ይህንም የፊደል ቅሚያ ያመጡበት ኢትዮጵያ አዲስ ቅኝት እንድትመስልላቸው የሕዝቡን መንፈስ ለማድከም የፈጠሩት ነው እንጅ በያዙት ነገር ሁሉ እውነት ያለበት ሆኖ አይደለም። በዚህ መጽሐፍ ላይ በየገጹ ቁጥር የሐሰት ፖለቲክ የሞላበት መሆኑን ከላይ እየተገለጸ እንደመጣው አሁንም እንደዚያው እየተመረመረ ማስረጃ እየተሰጠ ገለባነቱ እየነጠረ እየታወቀ። የመሠረዝጥላ በላዩ እንደደመና ይዞርበታል። አሁንም በ፳፪ኛው ገጽ የኢትዮጵያ ደምበኛው ቋንቋ ግዕዝ በቀጥታ ከሳባውያን ቋንቋ የመጣ ነው" እያሉ በማጭበርበር ጽሑፍ ተጽፎ የሚገኘው እንደ እውነቱ የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎ በሕግ መረጃ እየተደገፈ የተጻፈ አይደለም። አስቀድሞ ኢትዮጵያ ያረብን አገር ትገዛ እንደነበረ ስለ ንጉሥ ገደረት ዘመቻና እዚያው በዓረብ አገር ስለሚገኙ ሐውልቶች ጥንታዊ ጽሑፍ ዓረብ አገር በኢትዮጵያ ይገዛ እንደነበረ አባ ጋስፓሪን አምነው የጻፉት በ፺ኛው ገጽ ከኢትዮጵያ ተነሥታ ወደ ኢየሩሳሌምም በሄደችበት ዘመን የዓረብ አገር ግዛቷ ነበርና በዓረብ አገር በኩል ግመሎቿን ወርቅና ሰንደል ዕጣንና ሽቱ የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት ወደ ኢየሩሳሌም ሄደች ብለን ታሪኳን እንደመድማለን ብሎ የጻፈ ማን ነበር አባ ጋስፓሪን።

ደግሞ ፳፩ኛው ገጽ በ፲፯ኛው መሥመር "የከሡም ነገሥታት ፪ት ጊዜ በደቡባዊ ዓረብ ላይ እንደ ነገሡበት የሚአስረዳ ዋና ምሥክር አለን

## ጸ እኁድ

እንደዚህም ማለት መጀመሪያ ከጌታችን ልደት በኋላ በ፫፻ ዓ. አንሥቶ እስከ ፫፻፸ ዓ. ድረስ ፪ኛው ካሌብ እለ ኣጽብሐ ዓረብ አገር ከዘመተበት አገሩንም አስገብሮ የአከሡም ግዛት አድርጌ እንደራሴ ሾሞበት ካ፭፻፳፭ ዓ.ም- ፭፻፸

ዓ.ም ገዝተውታል ብሎ ከልደተ ክርስቶስ በፊት የነበረውን ክዶ የጻፈ ማነው” አባ ጋስፓሪን። ምነው ያባ ጋስፓሪን ምላስ ስንት ነው። ባ፩ድ ራስ ፪ት ምላስ እንኳ የተጻፈ ያስቸግራል እንዴት መነኲስ መስሎ ባ፩ድ ራስ ፪ት ምላስ ይገኝበታል። ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ የማይታመን ሁለት ልሳን እንደሆነ ማስረጃዎችን ለይቸ ለማስረዳት አመጣለሁ። ከላይ ሁለት ቃል መሆኑ አስረድቻለሁ ያባ ጋስፓሪን መጽሐፍ ሲመለከቱት አስደናቂ ነገሮች ይገኙበታል ውና መነሻው ለኢትዮጵያ ታሪክ ሊጻፍላት ተቦ ከመጨረሻ ላይ ተጽፎ ይገኛል አባ ጋስፓሪን የሮማ ልጅ ኢትዮጵያን በፖለቲክ ስብከት ዋና አስተናባሪ በመሆናቸው የመነኲስ ልብሳቸውን ለብሰው የሚሠሩትን ሥራ ላንባቢዎች እየገለጽኩ ለማቅረብ እየመላለስኩ ባለመሰልቸት እዘረዝረዋለሁ። ያባ ጋስፓሪንን ቃል ፪ ዓይነት ነው ስላልኩ ለመነኲስ ሰው የሚገባውን ፩ድ ቃል መሆን ስለሆነ ይህንም ኢትዮጵያን ለማስተማር የማመጣው ባሕታዊ ወንጌላዊ ማቲዎስ ፭ ፴፯ ወይኩን ባሕቱ ነገርክሙ እመሂ እወ እወ ወእመሂ አልቦ አልቦ ፈድፋደስ እምእሉ እኩይ ውእቱ ብሎ የተናገረውን በመራመድ ቃላቸውን እየለወጡ ስለሚገኙ። ቃላቸው ተለዋውጦ የሚገኙበትን ለይቸ አቀርባለሁ ፩ኛ በ፫፫ኛ ገጽ ባ፲፪ኛው (መስመር ከዚህ ቀጥሎ እንደምናገኘው ታሪክም ከኢትዮጵያ ንጉሥ ገደረት በኋላ የርሱ ተከታዮች የሆኑት ብዙዎች የኢትዮጵያ ነገሥታት ባሕረ ኤርትራን እየተሻገሩ ከዓረብ ነገሥታት ጋራ ጦርነት ገጥመው ዓረቦችን ድል አድርገዋል። የዓረቦችን አገር ጽጥ አድርገው እንደ ቅኝ አገር ይዘው ብዙ ዘመን እየገዙ በመቆየታቸው ስማቸውን አስጠርተዋል። የኢትዮጵያን መንግሥት ደረጃ ከፍ አድርገው አገራቸውን አስፋፍተው ይዘዋል። በመጨረሻውም በዓረብ ደቡብ አገር የነበረውን የዓረብ ሳባውያንን መንግሥት ዘሩን አጥፍተው ይላል) ይኸውና የሚወላውለው ቃላቸው እዚህ ላይ ከላይ በተጻፈው ከዓረብ ነገሥታት እያሉ ሲጽፉ ከቆዩ በኋላ መልሰው የዓረብ ሳባውያንን መንግሥት ዘሩን አጥፍተው (እነዚህ ኢትዮጵያውያኖች በዓረቦች ላይ ነግሠው ሠልጥነውባቸው ተቀምጠዋል ይላሉ)። እዚህም ላይ ልብ ወለድ እየፈጠሩ ያገቡት አለ የዓረቦችን ነገሥታት ወግተው የሚሉ ከዓረቦች ነገሥታ እስቲ ያ፩ድ ሰው ስም እገሌ የሚባል ማስረጃ ያለው ይገኝ እንዲሁ እንደ ጥንቱ ልማድ ኢትዮጵያ ባ፩ ቤተ መንግሥት ብቻ አይቀመጡም ግዛታቸውን እየዞሩ ይጐበኙ እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል። ፩ድ ፩ድ ጊዜም አገሩ ሸፍቶ ቢወጉትም ከንጉሥ ተዋጉ አይባልም ከንጉሥ ተዋጋ የሚባለው በመጽሐፈ ነገሥት ተጽፎ ይገኛል። እኔ የምለው የዓረብ አገር ሕዝቦች የኩሳ ዘሮች ናቸው። መንግሥቱም ያገሩ ቅኝም በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የሳባ የኢትዮጵያ አገር እየተባባለ ከቀድሞ ዝምሮ እስላሞች እበረቱና ክርስቲያኑን አጠፉበት ዘመን ድረስ በኢትዮጵያውያን እጅ ለመቆየቱ በዓለም የሚገኝ ታሪክ ይመሰክራል። አባ ጋስፓሪን በረቂቅ ፖለቲክ አገርንና አገርን የማለያየት ልምድ ስላላቸው ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ እስላሞች በርክተው ስላዩ እስላሞችን ደስ ያሰኙሁና ልባቸውን ያነሳሳሁ መስሏቸው ይህን ታሪክ ነገር ከልባቸው ፈጥረው የዓረብ ሳባውያን የሚሉ ስም ሰጥተው የኢትዮጵያን ግዛት በነበረበት

## ጹ ሰኑይ

ጊዜ የነበረውን ጽሑፍ ሁሉ ዛሬ ላሉት ዓረቦች ነው በማለት ኢትዮጵያ በእስላሞች መነሳት ከኢትዮጵያውያኖች ግዛት መቅረት ወዲህ ለቆመው መንግሥት መሠረት አስመስለው በዓረብ አገር በሚገኙ ጽሑፎች ምክንያት በማድረግ ኢትዮጵያን ያቀና የድቡብ ዓረብ ነው እያሉ ነገሩ አልያያዝላቸው ብሎ ፩ድ ጊዜ ወደ ቀኝ ፩ድ ጊዜ ወደ ግራ ሲወላውሉ የሚገኙበት ምክንያት ይህ ነው። ወደዚያው እንመለስ በ፫፫ ገጽ በ፳፩ኛው መስመር (እነዚህ ሳባውያን ነገሥታት የአገራቸውን ሰዎ እየጠቀሱ የሳባ የረይዳን የሐድራሙት የያማናት የሒምያር ነገሥታት ተብለው ይጠሩባቸው ነበር። ድል ወደ ኢትዮጵያ ነገሥታ ከሆነ በኋላ የዓረብ አገር አውራጃዎች ስም ጭምር ተዛውሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት የአክሡም የሳባ የራይዳን የሐድራሙት የያማናት የሒምያር ነገሥታት እየተባሉ እንደ ፩ዲት ኢትዮጵያ አገራቸው አድርገው ከኢትዮጵያ አገራቸው ከአክሡም ጋር ዝርዝር አግብተው በኢትዮጵያና በዓረብ አገሮች ስም ሲጠሩባቸው ኑረዋል። እንዲህ ያለ ድል በዓረባውያን ላይ ከተደረገ በኋላ ግን ዓረባውያን ፈጽሞ ልባቸው ስለሞተ ተበቅለውም

ብድራቸውን ለመመለስ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት አልቻሉም ከዚያ ዘመን ዠምሮ እስካሁን ድረስ የተጻፈን ታሪክ ስንመለከት ዓረባውያን ወደ ኢትዮጵያ ዘምተው ስንኳን ድል ጦርነት ሞከሩ የሚል ታሪክ አልገኘንም ብለው ጽፈዋል) ያባ ጋስፓሪን ቃል ፩ኛው ይህ ነው። አረቦችን ኢትዮጵያ ግዛቷ አድርጋ ለመታሰቢያ በቆሙ ሐውልቶችም ላይ ያረብ አገሮችን አውራጃዎችንም ስም በጽሑፍ አስቀርጻውት የነበረውን ከሐውልቱ የነበረውን ቃልና ዓረቦች እስከ መጨረሻው አለመንቀሳቀሳቸውን አረጋገጡልን ይህ ፩ኛው ቃላቸው ነው። ደግሞ ፪ኛውን ላምጣው። በ፳ኛው ገጽ በ፺ኛው መስመር በቀድሞው በሳባ መንግሥት ጊዜ ንጉሦቹ ሙቃሪብ ይባሉ ነበር። እነዚህ ማለት ካህን ንጉሥ ማለት ነው ውና ከተማቸው ሲርዋን ይባል ነበር አሁንም ፍራሹ ይገኛል በዚያ ጊዜ ፲፬ ነገሥታት በሲርዋን ነግሠዋል ከዚህ በኋላ የሳባ ነገሥታት የተባሉ ከተማቸውን ማዕሪብ ላይ አድርገው የነገሡት ንገሥታት ጊዜ ይገኛል በኢትዮጵያ ላይ የሚገኘው መረብ የሚባለውን ስም ያገኘው በዚህ ሳይሆን አይቀርም እነዚህ ፲፫ ነገሥታት ናቸው። የዚህ ጊዜ መዠመሪያ ከክርስቶስ በፊት ፯፻ ዓ. ይቀድማል። መዠመሪያ ንጉሥ ሙቃሪብ ይባላል።) ስለ ዘመኑ ከላይ ተጽፎ እንደሚገኘው ነው ማለት የፋርስ ነገሥታ ገና ሳይወለዱ ማለት ነው። ያባ ጋስፓሪንን ታሪክ ውሸት መሆኑን ሳናውቅ አይደለም የምንጽፈው። ሐሰቱን ለማስታወቅ ስንል እንጅ። (በዚህ ጊዜ የሳባ መንግሥት በጣም ተስፋፋ ከዚያ ጊዜ አንሥቶ ሳባውያን ቀይ ባሕርን ተሻግረው መዠመሪያ በኢትዮጵያ ምሥራቅ ዳርዳሩን በኋላ ግን ቀስ በቀስ እያሉ ወደ ደጋው ወጥተው በኢትዮጵያ ማኸል በሚገኙት አውራጃዎች ገቡ። በፊት የሚኖሩትን የኩሽ ዘሮች ድል አድርገው ኢትዮጵያን ያሠለጠኑ ሰባውያን ናቸው። ፪ኛው ያባ ጋስፓሪን ቃል ያልኩት ይህ ነው ከኢትዮጵያ ማህል ገብተው የኩሽን ዘሮች ድል አድርገው ኢትዮጵያን አሠለጠኑ ይላል። እንግዲህ ከላይ ያመለከትሁት ያባ ጋስፓሪን ቃል ሁለት ነው ላልኩት ማስረጃው አቅርቤ አሳየሁ ይህንም እስቲ ፩ድ ተብሎ ይቆጠር። ደግሞ ፫ኛ የተለወጠ ቃል ይገኛል "በ፷፩ ገጽ ባ፲፯ኛው መስመር የአክሡም ነገሥታት ሁለት ጊዜ በደቡባዊ ዓረብ እንደነገሡበት የሚአስረዳ ውና ምስክር

# ጺ. ሠሉስ

አለን እንደዚህም ማለት መዠመሪያ ከጌታችን ልደት በኋላ ከ፫፻ ዓመት አንሥሮ እስከ ፫፻፸ ዓ ገዝተውታል። ሁለተኛው አጼ ካሌብ ዓረብ አገር ከዘመቱበት አገሩን አስገብሮ የአክሡም ግዛት አድርጎ እንደራሴ ከሾመበት ከ፭፻፳፭ እስከ ፭፻፸፭ ዓ. ምሕረት ድረስ ገዝተዋል ብለው ጽፈዋል።) ከላይ የተጻፈው ሁሉ ቀረና በሐውልቱ ላይ የተቀረጸው መታሰቢያ ተረሳና የአክሡም ነገሥታት በደቡባዊ ዓረብ

እንደ ነገሡበት መዠመሪያ ሁለተኛ ብለው ከልደተ ክርስቶስ በኋላ ፫፻ ያልኩት ይኸው። ደግሞ ፬ኛ አመጣለሁ "በ፳፯ኛው ገጽ። የቀድሞ ግብጻውያን ወደ ኢትዮጵያ መግባት በሚል አርእስት ግብጻውያን በ፪ሺ፭፻ ከክርስቶስ በፊት ዠምረው ወርቅና ሌላም ክቡር ዕቃ ለመፈለግ በኒል ዓባይ በአትባራ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ ይገቡ ነበር። እነሱ የመጡበት ዘመን ኦሪት ከመጻፉ በፊት ስለሆነ ያገሪቱን ስም ኩሽ ብለው ጠርተዋት ሄዱ ብለው ጽፈዋል ይህም አባ ጋስፓሪን የፈጠሩት ፖለቲክ ፍጹም ሐሰት ነው። ትንሽም ምልክት የሌለው ማስረጃውም እንደዚህ ከላይ ባ፳ኛው ገጽ ለፈጠሩት መልሱን ከላይ ጽፌው ይገኛል። አሁንም ሐሰትነቱን የሚገልጸው ማጠንከሪያ ተብሎ ተፈጥሮ የተጻፈው የዘመኑ ቁጥር ነው። የዘመኑ ቅጥሩ በመጽሐፋቸው ላይ የኢትዮጵያን ነገሥታት ዘመን ቁጥር ሲጽፉ እንኳ በፈረንጆች ቁጥር መሆኑን መረዳት አለ። ስለዚህ በፈረንጆች መጻሕፍት አቆጣጠር ከፍጥረት እስከ ከክርስቶስ ፫ሺ፱፻፹፫ ነው።

ከ፫ሺ፱፻፹፫ው ፪ሺ፭፻ ሲነሳ ፩ሺ፬፻ ይቀራል። ብዚህ ሂሳብ ከፍትረት እስከ ማየ አይኅ ከወደታች ስሆን ከላይ የሚተርፈው ፩ሺ፬፻፹፫ ስለሆነ የግብጽ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ወርቅም የፈለጉ ኩሽ የሚባል ስምም አውጥተው የመለሰ ከማይ አይኅ በፊት ፱፻ ዘመን ቀድመው ማለት ስለሆነ የታሪክ ታሪክ የውሸት ውሸት ማለት ነው። ይህም ይቆጠራል ሲቆጠርም ስለ ፯ ነው የ፳ኛውን "በ፳፱ነኛ ገጽ ፩ኛ መስመር እኒህ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የሴም ዘሮች

ለዓረብ ሳባውያን መንግሥት ተገዦች ነበሩ። የዓረብ ሳባውያን መንግሥት በቀድሞ ዘመን በጣም የታወቀና የሠለጠነ መሆኑን ከዚህ በላይ እንደጻፍነው ታውቋል ይላል። ይህ ጽሑፍ ሲመረመር ሳባውያን የሚባሉ ዓረቦች እነማን ይሆኑ። በደቡብ ዓረብ ላይ ነግሠውበት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያኖች እንደሆኑ በዚህ ጽሑዎ ተጽፎ ይገኛል። ሳባ የሚባልም የመንግሥት ስም ተጽፎ የሚገኘው በኢትዮጵያ በካም ቤት ነው። ገና በግራው ዘመን በፋሌቅ ልጅ በኢትዮጵያ ላይ ሳባ የምትባል ሴት ንግሥት ነግሣ እንደ ነበረ መጽሐፈ ቀሌምንጦስ ይናገራል። ፪ኛም በመጽሐፈ ነገሥት ፲ ፩ ወንግሥተ ሳባ ሰምዓት ስሞ ለሰሎሞን ወስሞ ለእግዚአብሔር ወመጽአት ትፍትኖ ምስለ ጥቡብ። የተባለችቱ ንግሥት እንደ ተጠራችበት ያስረዳል። እስቲ ባረቦች አገር ሳባ የሚባል ንጉሥ የነበረ ፩ ሰው እንዳለ በቅዱስ መጽሐፍ እንፈልግ። ምናልባት አባ ጋስፓሪን እንዲሁ ከልባቸው እየፈጠሩ እያስመሰሉ መጻፍ ነው እንጅ አስረጅ መፈለግ አያሻቸውም። የሳባውያን መንግሥት በጣም የሰለጠነ ይባል የነበረው በዚያ ዘመን ላይ የኢትዮጵያውያን መንግሥት መሆኑን በ፫፻ኛው ገጽ ባ፲፪ኛው መስመር በተጻፈው ተረድተናል። አሁን ደግሞ በዚሁ በ፳፱ነኛው ገጽ ባ፩ኛው መሥመር (የነዚህ የሳባውያን አገር

# ጳ ረቡዕ

በግመል ማርባትና ወርቅ ማዕድን ማውጣትና መሥራት በዕጣን መሰብሰብና መነገድ በሰንደልና በዝባድ የሌላም ይህን ይህን በመሰለ ሽቶ እጅግ የከበረ ነበር። አዋሳኞታቸው ከሆኑት ከጎንድና ከባቢሎን ከሶርያና ጢሮስ ከጳለስጢና ጋር ይነግዱ ነበር)። ይህ ሁሉ ከላይ የተጻፈው ግመሉስ የማነው ወርቁስ ሰንደሉስ ዝባዱስ ሽቶውስ ሁሉ የማነው አዋሳኞችስ ጎንድና ጳለስቲና ሶርያስ የማን ዘር ነው። ንግዱስ ከማን ጋር ነበር። ታሪኩ ለማን ያመለክታል። ለኢትዮጵያ መሆኑ የታወቀ ነው። ግን አባ ጋስፓሪን ለኢትዮጵያ የተጻፈውን ላረቦች እንዲሆን አስበው መድከማቸውን ከዚህ በሚከተለው ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስ በየስፍራው ስለ መሢህ ከርስቶስ ሲናገር ንግሥተ ሳባ ወዓረብ ጋዳ ያመጽኡ መዝሙር። ፸፩ ኢሳይያስም እንደዚሁ ወያመጽኡ መራእየ አግማል ወይከድኑኪ አግማስለ ድምያም ወኤፋ ወይምጽኡ እምሳባ ወያመጽኡ ወርቀ ወስኂነ ወይዜንዉ መድኀኒተ እምኀበ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ፷ ፮ አሁንም ከላይ እንደተመለከትሁት ሁሉ ለኢትዮጵያ የተነገረውን ትንቢት ሁሉ አስቀድሞ በኢትዮጵያውያን በተቀር ሌላ ከነሱ ውስጥ ሳይኖራቸው ለኢትዮጵያ የተነገረውን ትንቢት ላልተነገረበት ወስደው ልስጥ ቢሉም ተቀባዩ

የማያውቀውን ያልገንዘቡ አይቀበልም ለትንቢቱ ባለቤት አለው። ያባ ጋስፓሪንን ነገር አዟሪነት ሐውልት ታሪክ ሰርሳሪነት ገልጾ ያሳየን ይህ የታሪክ ጽሑፍ ነው። ይህ ጽሑፍ ባይታተም ያባ ጋስፓሪንን ውለታ አናውቅም ነበር። አሁን ግን ያባ ጋስፓሪንን ውለታ በማይረሳ ቅርጽ ጽፈን ማስቀመጥ ውና ሥራችን ነው። ደግሞ በ፴ኛው ገጽ በ፳፫ኛው መሥመር በሚመጣው ታሪካችን ገልጸን እንደምናስረዳው የነሲህን የዓረብ ሳባውያን ታሪክ ያወቅነው እነርሱ አስቀድመው የፊደል ቅርጽና ጽሑፍ ፈልስፈው ሳልወጡ ነው። ኋላም ፈልስፈው ባወጡት ፊደልና ቅርጽ ታሪካቸውን በድንጊያ ሐውልት ላይ ጽፈውና ቀርጸው ስላቆዩን ነው እኛም የነሱን ጽሑፍና ቅርጽ ተከትለን ቅርጹን ጽሑፉን እየተረጐምን ታሪካቸውን ለመጻፍ በቃን ይላል።" እንግዲህ እንደ ሕጉ በታሪክ ተጽፎ የቆመውን በመከታተል ጽሑፉ በሚአመለከተው አመራር በ፳፱ነኛውና በ፫፻ኛው ደግሞ በ፴ኛው ገጽ የተጻፉት ታርኮች ሁሉ ለኢትዮጵያ መሆናቸውን እኔ አስረዳለሁ። ላስረዳም በጻፉት ጽሑፍ ነው። እሱንም ደግሜ ባስረዳ የሚቻል ነው። አባ ጋስፓሪን የሚሉት ዋናው አሳባቸው የኢትዮጵያ ነገሥታት የሴም ዕጣ ከሆነው ከዓረብ አገር አስቀድመው በቅኝ የያዙትን ከኢትዮጵያ ጋራ ደርበው ይዘውት ሲኖሩ በቆዩበት ጊዜ ምልክት ሆኖ የሚኖር ከዓለም ልዩነት ባለው ቋንቋና ፊደላቸው በቅርጽ እየጻፉ ያስቀመጡትን ሐውልትና ጽሑፍ ታሪክ በእስላሞች መንግሥት ወዲህ ለተቋቋመው መንግሥት መርጃ ደረጃ እያስመሰሉ ፊደሎቹን ያረቦች ነው በማለታቸው ላይ ደግሞ ፩ደኛውን ያለ ኀፍረት እንዲሁ በድርቅና በደቡብ ዓረብ

ሰዎች ኢትዮጵያን ይገዙ ነበር ያሰለጠኑአትም እነሱ ናቸው የሚል ጽሑፍ ተደርድሮ መምጣቱ ነው ምንም ቢደረደር ውሸት ከውሸትነቱ ስለማይዘል በብዙ ድካም ፖለቲኩ ተገልጾ ሐሰትነቱ ታወቀ። ሲታወቅም እንደዚህ ሆኖ ነው። የመነሻ ምክንያት ያደረጉት በዓረብ አገር የሚገኘውን ጥንታዊ ጽሑፍ በመያዝ ስለሆነ መዠመሪያ ከዓረብ አገር እገሌ መጣ ለማለት በቅርብ ለሆነ አገር ማስረጃ የሚጠየቁ ስለሆነ ከሩቅ የነበሩትን የዮቅጣንን ልጆች መጡ ብለው ይህን ፈጠሩ። ደግሞ እነሱ ወደ ኢትዮጵያ የገቡትን

# ጴ ኃሙስ

# ፮ኛ ክፍል መስከረም

# ምዕራፍ ፪

ሲፈልጉ በፋርስ ነገሥታት በነአሐሽዊሮስ አርጤክስስ ዘመን ከኅንድ እስከ ኢትዮጵያ ፻፳፯ አህጉር ይገዙ ነበር የሚለው ጽሑፍ ምክንያት አድርገው። በፋርስ ነገሥታት ዘመን ብራህማ የተባለ የኅንድ ንጉሥ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ የኢትዮጵያውን ንጉሥ ድል አድርጎ ኢትዮጵያን በያዘ ጊዜ የዮቅጣን ልጆች ሳባ ዑባል ኦፊር ፫ቱ የሐበሰን ሰዎች ጨምረው ብራህማን ድል አድርገው ኢትዮጵያን ነጻ ስላወጡ ዓግዓዝያን ተባሉ ይላሉ። የፋርስ ነገሥታት የነበሩት ዘመን ፭ሺ ካ፭ ዓመት ላይ ስለሆነ። በኢትዮጵያ መጻሕፍት አቆጣጠር ከፍጥረት እስከ ማየ አይኅ ፪ሺ ፪፻ ፶፮ ዓ. ዓለም ነው ከማየ አይኅ እስከ ፋሌቅና ዮቅጣን ፫፻፳፱ ይሆናል ድምር ፪ሺ፲፻፹፭ ይሆናል የዮቅጣን ልጆች የነበሩበት ጊዜ ፪ሺ፲፻፹፱ ዓ.ም ከዚያ ዠምሮ እስከ አሐዊሽሮስ መንግሥት ፪ሺ፪፻፸፩ ይሆናል። እንግዲህ የዮቅጣን ልጆች እስከ ፪፻፹፱ ዘመን ድረስ ቆዩ ማለት ሊታሰብ ይቻላል ይሆንን ደግሞ በፈረንጆቹም መጻሕፍት አቆጣጠርም ቢሆን ፩ሺ፶፯ ዘመን ይሆናል የዮቅጣን ልጆች ይህን ያህል ዘመን ቆዩ ሲባል በጣም አስፋሪ ነገር ነው። በጣምም በቀላል የሚአስገምት ነው። ደግሞ የሚያስደንቅ ይህ ተይዞ ከንጉሠ ነገሥቱ ፊት በመቅረቡ ነው። እንግዲህ የተደረደረው ታሪክ ሁሉ መሠረቱ ይህ ሲሆን ከኅንድ መጣ የተባለው (ብራህማ አለመምጣቱ የተረገጠ ሊሆን ነው። የብህራማ አለመምጣት የተረገጠ ሲሆን የዮቅጣን ልጆች መምጣት ሐሰት ሊሆን ነው የዮቅጣን ልጆች መምጣት ሐሰት ሲሆን በኢትዮጵያ የሳባውያን የሚባለው ጽሑፍ የዓረቦች አለመሆኑ ሊታወቅ ነው። በኢትዮጵያ የሚገኘው ጥንታዊቅ ጽሑፍ የሳባውያን ፊደል የሚባለው ስሙ ሐሰት ሲሆን

በኢትዮጵያ የሚገኘው ጥንታዊው ጽሑፍና ፊደል የኢትዮጵያ ሳባ መሆኑ በግድ መታመኑ ነው። በኢትዮጵያ የሚገኘው ጥንታዊ ጽሑፍና ፊደል የኢትዮጵያ መሆኑ የታመነ ሲሆን የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበረ በተመሰከረበት አገር ላይ የሚገኘው የግዕዝ ፊደል ቅርጽ የይዘ ጽሑፍ ሁሉ የኢትዮጵያ መሆኑ በሕጋዊ አጻጻፍ የምንገዱ ሥነ ሥርዓት ይህ መሆኑን ለኢትዮጵያ ወጣቶች አስገነዝባለሁ አስጨብጣለሁ።

እንግዲህ ያባ ጋስፓሪን መጽሐፍ ያለ ፍሬ እንዲሁ በቡቃያው የቀረ ገለባ መሆኑን ብንረዳውም ያባ ጋስፓሪን ረቂቅ ተንኮል በየሥፍራው ለሰው ልብ ማሰናከያ በየአምዶቹ ላይ ተጠምዶ የሚገኘውን ሁሉ ለማስረዳት የተንኮላቸውንም ብዛት ለመግለጽ ስል ወደ አባ ጋስፓሪን ጽሑፍ ገብቶ ስመለከት በ፴፪ኛ ገጽ ባ፲፱ነኛው (መሥመር ፊኒቃውያን ከዓለም ነገሥታትና ሕዝቦች እጅግ የሰለጠኑና የበረቱ መሆናቸውን ከዚህ በላይ ጽፈን እንዳስረዳነው እንዲሁ ከዓረብ ደቡብ አገር ተነሥተው ወደ ኢትዮጵያ ሳባውያን ተብለው ለመጠራት በቁ። ካርታጅ የተባለችው የፊኒቅያን መዲና የበለጠች ሆና ሮማን ለመውጋት እንደበቃች እንዲሁም ሳባውያን ሳባውያን የመሠረቷት የአክሡም የተባለችው መዲናቸው

ይላል።) ይህን ታሪክ ልብ ብላችሁ ተመልከቱ ሳባውያን የመሠረቷት አክሡም የተባለች መዲናቸው ይላል። ይህን ጉድ ተመልከቱ በዓረብ ደቡብ አገር ከሚገኙት መሪብ ናግራን ዛፋር ሳንዓ ከተባሉት ከተማዎች እጅግ የበለጠችና የሰለጠነች ስለሆነች ከዓረብ ከግብጽ አገር መንግሥቶች እየተዋጋች ድል ለማግኘት በቃች ይላል ከዓረብና ከግብጽ እየተዋጋች ድልን ማግኘት በቃች የተባለች ኢትዮጵያ

# ጵ ዓርብ

መሆንዋን አይካድም። ድልን ያገኘች ስትሆን ከሆነችም ይህ ጽሑፍም እውነት ከሆነ የደቡብ ዓረቦች ኢትዮጵያ በኃይል ገብተው ገዥና አሠልጣኝ ሆኑ የሚል ስለምን በዚህ መጽሐፍ "በ፴፫ኛው ገጽ በ፳፩ኛው መስመር እኒህ ከዓረብ ተነሥተው የመጡ የሴም ዘሮች ሳባውያን የሠለጠኑና የበረቱ ከመሆናቸው የተነሳ ከነርሱ አስቀድመው መጥተው ኢትዮጵያን ይዘው የቆዩትን ከስብታሕ ዠምረው እስከ ጺኦሪ ፩ኛ ድረስ የነበሩትን የኩሽን ዘሮች ድል አድርገው ኢትዮጵያን መላዋን ያዙ ይላል። ተሳሳተ እንዳይባል እዚያው ገጹ ፴፪ና ፴፫ ገጽ ላይ ነው እንግዴህ ካባ ጋስፓሪን ቃላት ከሁለቱ የሚያዘው የትኛው መሆኑን አወቀው ይሆን። "በ፴፬ኛ ገጽ ባ፩ኛው መስመር ከላይ እንደአመለከትነው እኒህ በኋላ የመጡ የሴም ወገኖች ቀድሞ ከመጡ ከካም ነገዶች እጅግ የሠለጠኑና የበረቱ ሆነው ነበርና አለችግር በፍጥነት እርሱን ለመግዛት ቻሉ ይላል"። መሆኑ ላይቀር የውሸት ታናሽ ምን ያደርጋል እንደዚህ እያሳመሩ ሲሆን በጣም መልካም ነው ዡሮ የማይሰማው የለም ኢትዮጵያ ተገዥዎች የደቡብ ሰዎች ገዥዎች ሆነው ተብሎ ተጽፎ መገኘቱ በጣም አስገራሚ ነው። "ባ፲፪ኛው በዚህ መሥመር የካም ነገዶች የሆኑ የኩሽ ዘሮች ቁጥራቸው እያነሰ ኃይላቸው እየደከመ ስለሄደ ሥልጣናቸውንና እውቀታቸውን የሴም ወገን ለሆኑት ሕዝቦች መልቀቅ ግድ ሆኖባቸው ይኖሩ ነበር። ግን ፈጽመው አልጠፉም እስካሁን ድረስ አልፈው አልፈው ኢትዮጵያ በየአውራጃዋ ይገኙባታል እነርሱም በከረን አውራጃ የሚገኙት ቢለን በጎንደር አጠገብ የሚገኙ ቅማንቶች በቋራና በላስታ የሚገኙ አገዎች። እነዚህም የኩሽ ነገዶች የሆኑ ሕዝቦች ምንም እንኳ የኢትዮጵያ መንግሥት ቢቋረጥባቸው የአገራቸውን ግዛትና ባላባትነት ሳያጡ ይኖራሉ ከሴም ነገዶች ወገንም በመጋባትም ተዛምደው ፩ድ ሆነው በክብርና በማዕረግ ሳይለያዩ ይኖራሉ መዠመሪያ ኢትዮጵያን አቅንተው መንግሥትነትና ግዛትን የዠመሩበት እነዚህ የኩሽ ዘሮች ናቸው። ቋንቋቸውም ፩ድ መሆኑን ለማስረዳት በቢለንና በቋራ አገውኛ ቋንቋ የተጻፈ የወንጌል ቃል በቅዱስ ማርቆስ ወንጌል በ፮ ም. የተጻፈውን ቃል ግራና ቀኝ ከዚህ ቀጥለን ጽፈን እንገልጻለን። ለጊዜው በዚህ ጽሑፍ ላይ ይስፈርና ታሪኩን የኢትዮጵያ

ልጆች ይመልከቱት በማለት ጻፍኩት ይላል ባ፩ድ ባንዲቱ ቃል መልስ ብጽፍ ምን ወረቀትና ቀለም ይበቃል በጭራሽ እንዳይቀርም በማለት አስደናቂ አስደናቂ የሆኑትን ነገሮች እንደተቻለኝ እደክማለሁ በ፴፮ኛ ገጽ ባ፲፬ኛው (መሥመር በዓረብ ደቡብ አገር በተገኘው ሐውልት ላይ ጽሑፍና ቅርጽ ስንመለከት ሐበሳትና አግዕዝያን ስለተባሉት ነገዶች ብዙ የሚአስረዳ ታሪክ እናገኛለን ታሪኩ አግአዝያን ስለ ተባሉት ፫ቱ ነገዶች የተቀመጡባቸውን አገሮች እየለየ ያስረዳናል ከአግዓዝያን ወገን ትልቁ ሳባ ከወገኖቹ ጋር ከአከለ ጉዛይና ከሽመዛና ዠምሮ እስከ መዲናው አክሡም ሞላውን የትግሬን አውራጃ ይዞ ጅቡቲን እያዋሰነ ክፍለ አገሩን አድርጎ ተቀመጠ ከአጋዝያን ወገን የሚሆን አፊር የተባለው ነገድ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ሚነግርለት ወርቅ እስከሚወጣበት እስከ አዱላ ድረስ ሐረርንና ውጋዴን ጨምሮ ክፍል አገሩን አድርጎ ተቀመጠ)። አሁን ከላይ ተጽፎ የምናየውን ሁሉ ውስጡን ላላወቁ ሰዎች እውነት መስሏቸው ሳይታለሉ አልቀሩምና አሁን ይህን ጽሑፍ ለመቃወም ስነሳ አስቀድሜ ከግራኝ

# ጶ ቀዳም

ወረራ በፊት የተጻፉትንና ከዚያ ወዲህ የተጻፉትንና ጽሑፎች ከታላላቆቹ ገዳማት ይልቁን የጥንት ኢትዮጵያን መሠረት ልማድ አድርጋ ዕለተ ሰንበትን የመጠንቀቅን ሕግ ያለቻት ደብረ ቢዘን ገዳም የሚገኙትን መጻሕፍቶችንና ደግሞ ታላቂቱን ገዳም ደብረ መርቆሬዎስ ደግሞ ከታላቂቱ ገዳም ደብረ ሲና የሚገኙትን ጥንታውያን መጻሕፍቶች ለመመርመር መድከሜ ምናልባት ከነዚያ ገዳማቱ ውስጥ ከጥንታውያኑ መጻሕፍቶች አባ ጋስፓሪን ያገኙት ነገር እንዳለ በማለት ፈንታ ፈርቸ ለመመርመር ነበር። ይልቁንስ መጻሕፍቱ ስለ ኢትዮጵያ ከፍ ከፍ ያለ የታሪክ ጉዳይ ያመጣሉ እንጅ ስለ ሀገረ ናግራንም መጻሕፍቱ በሰፊው ይናገራሉ። ስለ ሀገረ ናግራን በገድለ ሰማዕታት ውስጥ አጼ ካሌብን ከሰማዕታት ውስጥ ስለቆጠሯቸው ገድላቸውን ከገድለ ሰማዕታት ጋር አብረው ጽፈውት በደብረ ዘመዶ በሚገኘው በሰፊው ይጽፋል። በትግሬና በሐማሴን ገዳማት ውስጥ የሮማ ልዑካን ያልቀሰሙት ሥፍራ እንደሌለ እኔ ተረድቸዋለሁ እግዚአብሔርን የሰጠን እረዳቶች የሚሠሩልንን ሥራ ይኸው እንደምታዩት ስለሆነ። አባቶቻችን ከዓለም ሊቃውንቶች ሁሉ ታሪክ ለታሪክ እንደተለዋወጡ ያስረዱናል። የውጭ አገር ሊቃውንት የጻፉአቸውን ሁሉ የዓለም ባለ ታሪኮች ከየቋንቋቸው እየገለበጡ ያስቀመጡልን መጻሕፍቶች ወሰን አላቸው ብየ ለመናገር አልደፍርም። አንባቢ ታዛቢ ተመልካች ከማጣታቸው በተቀር ለኢትዮጵያ ጥቅም የሚሆኑ ነገሮች ከየቅዱሳኑ ገድል ውስጥ ይገኛሉ ገድል ማለት ታሪክ ነው በኢትዮጵያ መጻሕፍት ውስጥ እርግጠኛው የዓለም ታሪክ ተቀምጦ የኢትዮጵያ ልጆች የኢትዮጵያ ተቃራኒዎች ለተንኮል አስበው የጻፉትን ተቀብለው የተሞሉ መኖራቸውን አውቃለሁና እርግጠኞቹ የኢትዮጵያ ልጆች የኔንም ያባ ጋስፓሪንንም መጽሐፍ በሰፊው መላልሳችሁ ሳታነቡ ለማመስገንም ለመንቀፍም እንዳትጣደፉ። ደግሞ ራሳችሁን ሳይገባችሁ ማነኛችንንም መንቀፍም ማመስገንም የአፍ ሥራ ፍሬ እንደሌለው እወቁ። አባ ጋስፓሪን ስንኳንስ በሰው አገር ሄዶ ይቅርና በሀገሩ ተቀምጦ እንደዚህ ያለ ሥራ የሚሠራ በሥውር መሆኑ እንጅ ሐዋርያቱን በዚህ በኩል በጣም ጀግና ስለሆነ ጀግንነቱን እኔ በዚህ ጽሑፌ እመሰክርለታለሁ። ከላይ ስለ መጻሕፍት ብዛት ነካ አድርጌ ትቸው ነበር ልመለስበት ሕሊናዬ አስገደደኝ። አባት ካባትም መልካም አባት ለልጅ ሥጋውን በድሎ ሥጋ ከምትወደው ጠባይ ተከላክሎ ከፍትወተ ሥጋ ተጋድሎ ለልጁ መልካም ጥሪት። መልካም ጥሪት ማነው የማይንቀሳቀስ ሃብት በማይንቀሳቀስ ሃብት ውስጥ ደግሞ ልጁ በተቸገረ ጊዜ ለችግሩ እንዲሆነው አስቦ በዚያ በማይንቀሳቀስ ሃብት ውስጥ ይቀብርና የምሥጢር የጽሑፍ ምልክቶች አስቀምጦ ያነን የተቀበረ እንዳይነግረው ላታላይ አሳይቶ ቢአስወስደውሳ እያለ ዛሬ ከነገ ሲል

የሞተ ፊታውራሪ ሕማም ደርሶ ከተፍ ባለ ጊዜ ዘመድና ቄስ ቀርበው ተናዘዝ ይሉትና ቀርበው በጠየቁት ጊዜ ያነን ዕቃ የተቀበረበትን ለሚወደው ልጁ ይሰጥና ምልክት ይሰጠዋል ምልክቱም እንዳትሸጠው ነው። ያባቱን ዕቃ ያገኘው እንደሆነ ያባቱ ነፍስ ይማር እያለ እስከ ጊዜው ከተረዳበት በኋላ እሱ ደግሞ ለልጁ እንደዚህ ያደርግና ይሞታል እንደዚህ እየሆነ በዚህ ምክንያት ባባቴ ቦታ ጦሜን አድርበታለሁ እንጅ ምንም ቢሆን አልሸጥም እያለ ያባታቸውን

# ጸ እኁድ

እርስት አንቀው የሚኖሩ አይታጡምና ሀገራችሁን ምን እንዳለባት ለማወቅ ብትፈልጉ የግዕዝን መጻሕፍት ውደዱ የግዕዝ መጻሕፍቶች ምን እንዳለባቸው መርምሩ እወቁ። ምናልባት የሳይንስ ጥበብስ ከጥንታውያኑ ሰዎች እየመረመሩ አይደለምን በኋላ ለማሻሻል የሚደርሱ ምናልባት ባፎድ ድንጋይ ተጽፎ ስለ ምን ምክንያት እንደሆነ ብናውቅ መልካም ስለሆነ እንድናውቀው ለዚሁ ጥናት የሚሆኑ ሰዎች ሳያልቁ ከነዚሁ ለጊዜው ከየግዛቶቹ ስንኳንስ ዛሬ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ የሚገኙትንና ከውጭ እንኳ ከጥንት ግዛቶቿ የጥንት ጽሑፎችን እየመረመረ የሚአመጣ ሰው ኖሮ ቢሆን የጥንታዊ ነጻነታችን መታወቂያ ያልነውን ፊደላችንን አባ ጋስፓሪን ለመንጠቅ ባልከጀለንም ነበር። የኢትዮጵያ ወጣቶች ሆይ ይህን ሁሉ መዘዝ ያመጡብን ከውስጣችን የሚገኙ በለት እንጀራ በዳቦና በሻይ እየተገዙ መሥጢራችንን እያወጡ

ከዚህም ቀደም ሰዎቻችንን ያስጨረሱ አሁንም ለወደፊቱ አሳባቸው አለማቋረጡን ይህ ታሪክ የተባለው መጽሐፍ የፖለቲኩ መሪ መሆኑን የኦፊርን አገር እስከ ሐረርና አዶላ ድረስ በመወሰኑ አውቀነዋል። የነአባ ጋስፓሪን አባቶች ካባ ቤርሙዴዝ ዠምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያሉትን ኢትዮጵያ ያልወለደቻቸውን ልጆች አዝላ ትኖራለች። ታዝለው ከመኖራቸውም የተነሳ መታዘላቸውንም ምክንያት በማድረግ የሠሩላትን ሥራ የሚአስቡላትን አሳብ ደግ መሆኑን ለመግለጽ ይኸው መመርመር ተይዟል ከሁሉም ነገር የሚያስደንቅ ግዕዝ የሌላ ቋንቋ ሆነና በካም ቤት የወረደው መንግሥት መነጋገሪያውና ቋንቋው ለመረጃ "በ፷፩ኛው ገጽ በ፳፩ መሥመር መዠመሪያ ኢትዮጵያን አቅንተው መንግሥትና ግዛት የዠመሩ እነዚህ የኩሽ ዘሮች ናቸው ቋንቋቸውም ፩ድ መሆኑን ለማስረዳት በቢለንና በቋራ አገውኛ ቋንቋ የተጻፈ የወንጌል ቃል በቅዱስ ማርቆስ ወንጌል ፯ ም. የተጻፈውን ቃል ግራና ቀኝ ከዚህ ቀጥልን ጽፈን እናነጣጥራለን። የቋንቋ ማነጣጠሪያ ምልክት በየቋንቋቸው አርስት ይጻፋል ይላል"። ይኸውም ተጽፎ የሚገኝ በ፷፮ኛው ገጽ ከግርጌው ይዠምራል ከካም በመጣው በቢለንና በቋራ አገው ቋንቋ ተጻፈ የተባለውን የታሪክ ሥራ አስተውሎ መመልከት ነው። በኢትዮጵያ ከምንገኝ ሰዎች እየያዙ ነው እንጅ ይህን እነሱ ብቻ የሠሩት አይመስለኝም ሲሆን ቢውል ይህን ሥራ የመረመሩበት ምክንያቱ እነሱ እንደሚሉት በካም ለነበረው መንግሥት ፊደል ይህ በቢለንና በቋራ አገው የተባለው መሆኑ ማለት ነው ይህ ዛሬ የያዝነው ግዕዝ የተባለው ቋንቋ የመጣበት መሠረቱ ከደቡብ ዓረብ አገር መሆኑን ማረጋገጥ ማለት ነው። ሐሰትን እውነት እውነትን ሐሰት ለማድረግ የሮማ ልዑካን የሚሠሩት ረቂቅ ፖለቲክ በየገጹ ይገኛል። በነሱ ስብከት ኢትዮጵያ የምትመራ እየመሰላቸው ነው እንጅ በኢትዮጵያ የሚገኙ ቋንቋዎች ብዙዎች ናቸው ከ፳ያም ይበልጣሉ የነዚህ ሁሉ ጠቅላይ ካም ከኖኅ ካባቱ ይዞት የመጣው የወረሰው ከቋንቋው መለያየት አስቀድሞ ወደ አፍሪካ አገሩ ይዞት መጥቶ መንግሥቱና ቋንቋው ፊደሉ ሲያያዝ የመጣውን ባ፩ሺ፰፻፵፪ ዘመኑ ከኢትዮጵያ ሊነቃነቅ መታሰቡም ታሪክ ነው። ለመሆኑ ፩ድ ነገር አለ ይህን ያህል የሮማ ልዑካን የሚደክሙበት ፊደሉን ከሌላ የመጣ ነው እያሉ የሚቸገሩበት ምክንያቱን ቢጠየቁ ምን ይመልሳሉ ትንሽም ሰው ያውቅብናል አለማለታቸው እንደምን ያስገርማል እነሱ እየዞሩ አገር ለመሰለ ሲጓዝ መኖር ዋና ተግባራቸው ስለሆነ በዓረብ አገር ላይ ሲዞሩ ከዓረብ አገር ላይ

## ጹ ሰኑይ

ጥንታዊ ቦታ ሲቆፈር ከውስጥ የጥንታዊ ግዕዝ ፊደል ቅርጽ ያለበት ጽሑፍ ሲገኝ አይተዋል ይመስለኛል። ይህን ጥንታዊ ፊደል ከዚያ ስላገኙ በቅንነት የተገኘውን ጽሑፍ አስሊውን እንዳለ አምጥተው በታሪኩ ውስጥ እንዳይገልጹ ከነሱ አሳብ ጋራ የማይስማማላቸው ስለ ሆነ አስሊውን ደብቀው እንደገና ገዥ የነበረችቱን አገር ተገዥ አስመስለው እዚያ የተገኘውን ጥንታዊ ጽሑፍ ለዓረብ አገር መሠረት አስመስለው ፈጥረው ግዕዝን ከዓረብ አገር የተፈጠረ ነው ብሎ አስበው የሠሩት ፖለቲክ ጽሑፍ ሳይገጣጠም ቀርቶ እንደ ስናፖር ግብም ወድቆ መሰባበሩን እነሱ እውስጥ ሆነው ገና አላወቁትም። የግዕዝ መሠረቱ በዓረብ አገር ከሆነ ዛሬ በዓረብ አገር ስለምን አይገኝም ግዕዝ ስንገልግ ወደ ሥር መግባት አለብን ደግሞ ወደ ላይ ወደ ጫፍ መውጣት አለብን። ወደ ሥር ወርደን ወደ ላይ ወጥተን ስንመረምረው ልኩን እርግጠኛውን ለማወቅ እንችላለን። የሮማ ልዑካን እዚህ ላይ ስለ ፊደል ጥንታዊ ቋንቋ ለማደራጀት ስትደርሱ ስለ ግዕዝ መሠረት መለያ የሆኑትን አስረጅዎች አውቃችኋቸዋል ይሆንን ወይስ እንዲሁ ዓይናችሁን ጨፍናችሁ እነዚያን በዳቦና በሻይ እያባበላችሁ የወሰዳችኋቸው የነገራችሁን ሰምታችሁን ሰምታችሁ ይሆን ወይንስ እውነተኛውን አዋቂ በዳቦና በሻይ የገዛነዉ መስሏችሁ ይሆንን ወይስ ደግሞ በዳቦና በሻይ አልተባበልም የሚል ሰው አላጋጠማችሁም ይሆንን የማይታለልስ አግኝተን ነበር ያላችሁኝ እንደሆነ እውነተኛው እሱ ነበር።

እሱ አልተባባልም ብሎ በቀረ ጊዜ እውነተኛው ነገር መቅረቱን እንድትረዱት ለወደፊቱም ገንዘባችሁን በከንቱ እንዳታባክኑ እመክራኋለሁ። ስለዚህ ከመሠረቱ ውስጥ ለመግባት ገና ትምህርት አልገባችሁም ትምህርቱ እንዳልገባችሁ አረጋግጥላችኋለሁ። ለመሆኑ እስከዚህስ ድረስ የግዕዝን ምሥጢር ያስተማራችሁ ማነው ለመሆኑ ግዕዝን ታውቃላችሁ ይሆንን አታውቁትም እናንተስ ባይሆን አማርኛን ይሆናል አማርኛም ስላልኩ የጨዋዎቹን ማለቴ ነው እንጅ የመምህራኑን አማርኛ ማለቴ አይደለም። የግዕዝን ትርጓሜ ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁን አታውቁትም እንዲሁ በሰው አገር ገብታችሁ እንደምትዘባርቁ እጃችሁን እግዕዝ ላይ አወጣችሁ የሚገርም ነው። ግዕዝን መሠረቱ በደቡብ ዓረብ ነው ብላችሁ ጽፋችኋል አሁን ግዕዝ ከዓረብ ደቡብ ወዴት ሄደ ብሎ የሚጠይቃችሁ ቢመጣ ምን መልስ ትሰጣላችሁ። የግዕዝ ቋንቋ ትርጓሜው በቁጥር መሠረት ሲሆን ይህን መሠረቱን በዓረብ አገር አለ ለማለት ትደፍራላችሁን። ወይስ ከነመሠረቱ ተነቅሎ ከዓረብ አገር ወደ ኢትዮጵያ ሄደ ትላላችሁ። ከግዕዝ መሠረቶች በዓረብ አገር የሚገኝ ፩ድ ነገር ታገኛላችሁ ይሆንን መልስ የለም። እንዲሁ አላዋቂዎች ወጣቶችን ለማጭበርበር ነው እንጅ የነገር ጫፍ እየነጠቁ የኢትዮጵያን መሠረት ለመስበት መቸኮል ስንኳንስ በችኮላ በቀስታም ቢሆን የኢትዮጵያን መሠረት መሐንዲሱ ሉቃስ ፮ ፵፰ የተጻፈውን የተመለከተ ነው። የሮማውያን አሳብ ዘወትር የኢትዮጵያን ክብር ለመደምሰስ ታሪኳን ለማርከስ ሲፈልጉ ስለሚታዩ በመጽሐፈ መክብብ የተጻፈው ፲ ፰ ዘይከሪ ግበ ሊቢጹ ይወድቅ ውስቴቱ ለባልንጀራው ጉድጓድ የሚቆፍር ሰው በቆፈረው ጉድጓድ ይወድቃል የዘይነሥት ጸቁነ ይነሥኮ አርዌ ምድር ቅጽርን የሚአፈርስ እባብ ይነክሰዋል። ፱ ወዘያስተፋልስ ዕብነ የሐምም ቦቱ ከታች ሆኖ ወደ ላይ ድንጋይ የሚወረውር መከራ ይቀበላል ይላል። የኛ መምራኖች

## ጺ. ሡሉስ

መጽሐፍቱን መመልከት የለም ዛሬ ኢትዮጵያ ሥጋዊ ጥበብ ስትሥራ ባለመገኘቷ ብቻ ነውር ሆኖባት በዚህ ምክንያት የመጡ መሳሪያ የሚሠራ ሠራተኛ እናስመጣላችኋለን እያሉ እየሰበኩ የኢትዮጵያን ነገሥታት ሲአታልሉ እንደኖሩ የሚአስረዳ ይኸውና አጼ ሠርጸ ድንግል የጻፉት ደብዳቤ መጽሐፈ መልእክት እምኀበ ንጉሥ መላክ ሰገድ ትብጻሕ ኀበ ንጉሥ ፊልጶስ። እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘነሥተ ዓረፍተ ማዕከል ዘጽኑዕ በመስቀሉ ወሰሐበ መንገለ መንግሥቱ ኵሎ ዓማንያነ እስከ ኮነ ውሉዶ መንግሥት በአሚን ዘክቡት ውስተ አልባብ እለ የአምርዎ ለማእረ ኵሉ ዘመልዕልት ወዘመትሕት ዘኮነ ወዘይከውን አስተጋብእ ሰላመ  ኀበ መካን ወማኅደር ዘንጉሥ ፊልጶስ ወይወስክ ፍቅረ በዲበ ፍቅር በግብር ዘልኩዕ ላዕለ ጠባይዕ አእምሮታዊ ዘውእቱ ልቡና እስትጉቡዕ እምዝርወት ወእምተከፍሎ ኀበ መካነ ህላዌ ዘህልው ወርኵብ አንጻረ መስቀሉ ለእግዚእነ ኢየሱስ መሠረተ ጽድቅነ ወአረቦነ ተስፋነ ሎቱ ሰጊድ ወግናይ እምነ ፈጣሪ ክቡር ወልዑል እምሕሊና እኁለ እመሕያው። ዝንቱ ሰላም ይብዛኅ ወይፈድፍድ ወይትወሰክ በላዕለ ፍቅር ወምዕመን ዘዝኩር በርዕሰ ዛቲ ጦማር ክታብ ንሕነ ናገብእ ለከ ስጣዌ መልዕክት እመ ሠምረ እግዚአብሔር ለአብጽሖቱ እስመ እምኀቤሁ ከሂል ወእምኀቤሁ ፍጻሜ ምግባራት ዘኵሉ ማዕራነ አልባብ እስመ መጽአ ኀቤነ መልእክትከ ዘቦቱ ትእምርተ ነገር ዘፍቅር ክርስቶሳዊ በእዴሁ (ለልዊስ ድሜንዶስ) ወአብጽሐ ኀቤነ ወተቀበልናሃ በትፍሥሕተ ገጽ ወበብሩህ ሕሊና ወዝንቱ ዘአምጽአ ክታበ ዘሰሙ ዮሐንስ ኢበጽሐ ኀቤነ ወሰማዕነ ዜናሁ ከመ ሞተ በፍኖት ወኃዘነነ በእንቲአሁ። ወአዲ ኮነ ምስሌነ ፍቅር (ቢይዘራዶን ያአርቴ ድምኔዝስ) እስመ ውእቱ ኮነ መሥመሬ ለፈቃድካ ወኀብረ በግብረ አሰምሮትነ ውእቱ ወእመንገለ ዝሰ ጸዋትወ ነገራት ድኅረ በጽሐ ኀቤነ መልእክትከ ዘእስትጉቡዕ ውስቴቱ ሰላም ወፍቅር ወመልእክት ዚአሁ ዘየኃድር ታሕተ ሥልጣን አግባዕነ ሎቱ ሥጣዌ መልዕክት ዘይብል ንኀሥሥ ወንጽሕት ፈድፋደ ትፈኑ ለነ ጠቢባነ እለ የአምሩ ገቢረ ራስ ቁር ወሠሪሐ ነፍጥ ወዘይመስሎ ለንዋየ ፀብዕ እመሰ በጽሐ ዝንቱ መልዕክት ኀቤከ በፈቃደ እግዚአብሔር ክ. ወል አንተኒ ሥመር ቦቱ ለመልእክት ኀቤከ ይትገበር ትእዛዝነ ዘንሕነ ንፈቅድ ወፈድፋደ አግበናሁ በፍቅር አምላካዊ ወበተሰናዕዎ በመንፈስ ቅዱስ ፈጻሜ መፍቅዳት ከመሰ ይትግህ

አፍቅሮትከ ወአፍቆሮተ ዚአነ ረከብነ እምከታበ ዚአሁ ለቢዞ ሬይደን አኣርቴ ድምኔዝስ ዘበጽሐ ኅቤነ ምስለ ክታብከ ወመልእክትከ ዘእሙት እንተ በጽሐ ኅቤነ ወጐንደዮተ ዛቲ መልእክት እስከ ይእዜ በእንተ ምኅላፈ ፍኖት ወኑኃተ ዘመን ዘርኅቀት ሀገር ዘባሕር እመስ በጽሐት ዛቲ መልእክትነ ነአምር ከመ ይትፈጸም ፈቃድነ ወጻሕቅነ በእንተ ዘኅሥሥነ ወዘፈቀድነ ጠቢባነ ወማእምራነ ዘግብረ ዕድ እንተ ንዋየ ጸብዕ ዘወእቱ ነፍጥ ወሠሪዓ ራስ ቁርዕ ወቀቢዓ ወርቅ ላዕለ ኅፂን ወእምይእዜሰ ሐተምነ ለከ ነከራተ በኅጹር ወእግዚእ አምላከ ኵሉ ይፈጽም ፈቃድነ ወፈቃዳቲከ ወለልዊስ ድሜንድሳኒ አከብር በእንቲአነ እስመ ውእቱ ይፈቱ ፍቅረኒ ወፍቅረ ዚአከ ጥቡዓ ተጽሕፈ በወርኃ የካቲት ፱ በ፲፫፻ ፳ወ፱ቱ ዓ.ም እምልደተ ክርስቶስ በኃሳበ ሮም ይህን ጽሑፍ ለአጼ ሠርፀ ድንግል በሥውር ደብዳቤ እያመጣ ደግሞ መልሱን ሲወስድ ደብዳቤውን እሱ በጻፍው ላይ የንጉሡን ማኅተም እያሳተመ

## ጸ ረቡዕ

የወሰደ ይመስላል ምክንያቱ ዓመተ ምሕረቱን በኃሳበ ሮም በማለቱ ያስታውቃል። በኢትዮጵያ ዓ.ም አለመጻፉ ጸሐፍያኑ ባይሰሙት መሆኑን ያስረዳል። ኢትዮጵያ የጦር መሣሪያ የሰው መግደያ መሥራት ባለ ማወቅም አልተጐዳችበትም ይኸውና በሰባክያኑ መሪነት ሞሶሎኒ የጦር መሳሪያውን ፵ ዘመን ሙሉ ሲያደራጅ ኖሮ የጦር ሠራዊቱንና የጦር መሣሪያውን ወደ ኢትዮጵያ የክርቲያኖችን ደም አፍስሳችሁ ቤተ ክርስቲያናቸውን አቃጥላችሁ ቤተ መንግሥቱ ለቤተ መንግሥታችን ቤተ ክህነቱ ለቤተ ክህነታችን ይሆናል ብሎ ሞሶሎኒ ሕዝቡን ባዋጅ ሰብስቦ ዘማቾችን ያሰናበተ ለት ሊቀ ጳጳሱም በጉባዔው ተገኝተው የተባረከ ዘመቻ ይሁን ብለው አሳርገዋል በዚያ ቀንም የተሰበሰበ ሕዝብ በዓድዋ ጦርነት ላይ ለሞቱ

ሰማዕታት ደም መቀበያ የሚሆን እርዳታ አድርጉ ተብሎ በጣታቸውና ባንገታቸው ያለው ጌጥ ሳይቀር ሴቶቹ እያወለቁ እንደሰጡ ታሪካቸው በጊዜው ተነቧል። በሮማ ላይ የሚገኙ ዲታዎችም ያለ ንብረታቸውን ይዘው ከጦር ሠራዊቱ እየተከተሉ ኢትዮጵያ ገብተው ግማሾቹ ድልድዩን ግማሾቹ በውኃ ገቡ መት ላይ ልዩ ልዩ የሆኑ አታክልቶችን ግማሾቹ የውኃ መተላለፊያ ቦምባዎችን ኤሌክትሪክን ስልኩን በተቻለ ፍጥነት በቤተ ክህነቱም በኩል የሮማ ቤተ ክርስቲያንም በተቻላት መጠን ሥራዋን ስታስፋፋ ሰናክሬም በሕዝቅያስ ላይ የትዕቢት ቃሉን ሲአሰማ ኢሳይያስ ፴፮ ፲፰ ኢያስሕትክሙ ሕዝቅያስ በነገር ወኢይበልክሙ እግዚአብሔር ያድኅነንክሙ ቦኑ ዘአድኅኑ አምልክቲሆሙ ለአሕዛብ ኵሎ በሐውርቲሆሙ እምእዴሁ ለንጉሠ ፋርስ እያለ እንደ ፎከረው ሞሶለኒም ኢትዮጵያ የጐዳሁ መስሎት ይህን ሁሉ ሠራዊት ልኮ ያለ ምሥጋና ብዙ ሥራዎች ካከናወነ በኋላ በእግዚአብሔር ስም የታመነው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በሠናክሬም ላይ እንደተፈጸመው ሠናክሬምን የገዛ ዘመዶቹ ደብድበው እንደ ገደሉት ሞሶሎኒንም የሀገሩ ሰዎች እንደ አበደ ውሻ ወገኖቹ ደብድበው ከቁሻሻ መጣያ ላይ ጥለውት ቁሻሻ አጥልቆት ከቆየ በኋላ የሱ ሬሳ ነው ተብሎ ወደ መቃብር ገባ ብሎ ተጽፎ ሲነበብ ነበር። በክፉ መርዝ መሣሪያው ተመክቶ የነበረው ሞሶሎኒ ያገኘውንና እደ ኅሊናውን ወደ ልዑል እግዚአብሔር አምላኩ እየተማጸነው አስተዋዩንና ትዕግሥተኛውን ንጉሠ ነገሥት ቀ. ኃይለ ሥላሴን መክብብ ፱ ትሄድስ ጥበብ እምንዋየ ሐቅል በተባለው መሠረት ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔርን በመያዝ በእግዚአብሔር አጋዥነት ኢትዮጵያ ከባርነት ቀንበር ስላወጣ በዓለም ባለታሪኮች መክብብ ፲ ፲፯ ብፅዕት አንቲ ምድር እንተ ንጉሥኪ ወልደ አግዓዚ ብለው ሊያመሠግኑ ቻሉ። አሁን ወደ ካም ፊደል እንመለስ የሮማ ልዑካን ልብ ኑሯቸው ቢሆን ተመልሰው በዚህ ፖለቲክ ገብተው የኢትዮጵያን ታሪክ ሲሠረስሩ ባልተገኙም ነበር። ግዕዝን ከደቡብ የመጣ ነው ብለው እየመላለሱ ሲጽፉ ጊዜው ብዙ ነው እነሱን በመከተል ብዙዎች የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች የኢትዮጵያን ታሪክ ሲያቃውሱት ይገኛል። ስንኳንስ የውጭ አገር ሰዎችና ከኢትዮጵያውያንም አያሌ ሰዎች የተሳሳቱ ሞልተዋል። ምክንያቱም በቀድሞ ዘመን እንደቆየው ልማደ ሕግ ያልሆነውን አይስፉትም ስለማለት ነው እንጅ አውቀው መርምረው

ከጥንተ መሠረቱ አግኝተው አለመሆኑን ያው ጽሑፍ አላፊውን ይናገራል። የሮማ ልዑካን ረቂቅ ተንኮል ምንም ባይሳት በታሪክ በኩል ይሠራሉ ብሎ የጠረጠረ የለም ነበር።

## ጼ ሐሙስ

አሁን ግን የመታመኛ ጊዜው ሲደርስ እባ ጋስፓሪን ይህን የታሪክ መጽሐፍ አስበው ለመጻፍ ቻሉና አቀረቡት። እኔም አስቀድሞ ከጠላት ዘመን ዠምሬ ወደ መሠረቴ ገብቸ ስመረምር ይህ ነገር የተዠመረ ባጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት አባ ቤርሙዴዝ እንደ ዠመረው ታሪክ ነገረኝ ከዚያ ዠምሮ እስከ ዛሬ ያለውን ጽሑፋቸውን ስመረምረው እነሱ መንፈሳውያን ነን እያሉ ውስጥ ለውስጥ ንጉሡን ከመሳፍንቱ መሳፍንቱን ከንጉሡ ነገሥቱ እያለያዩ ደም እያፋሰሱ የኢትዮጵያን ክብር በታሪክ እየቀነሱና እያኮሰሱ ጽፈው ስለማገኘው በጣም የሚጨበጥ አጥጋቢ የሆነ ነገር አጥቸ ያነኑ ከየመጻሕፍቱ የለቀምኩትን ይዠ ስከታተል። ለኔ ዋና ጠበቃና ረዳት እንደመሆን ዓይነት ውስጥ ለውስጥ በ፩ድ ፩ድ መጽሐፍ ዳርቻ ጽፈውት የነበረውን ሁሉ ሞልተውና ገፍተው አሰናድተው አቀረቡልኝ። ይህን መጽሐፍ ባዩ ጊዜ በጠላት ከጠላት እጅ ከመሞት ያተረፍከኝ ይህን ልታሳየኝ ነውን ብየ ከዚያ በኋላ ሌትና ቀን ዓይኖቸ ከሱ መለየትን ጠሉ። እኔም እሱን ሳነብ ዘወትር ነገሩ እንግዳ ሆነብኝ ገለጥ አድርጌ ስመለከት የኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳን አስቀድሞ ከእብራይስጥ እየተገለበጠ መጥቶ ነበር የተባለው ውሸት ሆነብኝ። የኢትዮጵያም በነጻነት መኖር

ውሸት ሆነብኝ አብርሃና አጽብሐ የተባሉ ሁለቱ መንትያዎች ነገሥታት በኢትዮጵያ እየዞሩ አብያተ ክርስቲያናት የሠሩ እነሱም ውሸት ሆነው ተገኙብኝ። የካም ቋንቋ ሌላ ሆነ ግዕዝ የኢትዮጵያ መሆኑ ውሸት ሆነብኝ። በዚህ መሠረት ፲፰ ዓ ያነበብኋቸው የኢትዮጵያ መጻሕፍቶች ውሸት የተመላባቸው ጸሐፊዎችም ሁሉ ሐሰተኞች ሆኑብኝ በዚህ ጊዜ ከባድ ጭንቀት ወደቀብኝ ለሰውም ባማከረው የፈረንጆች ሊቃውንቶች አመዛዝነው ከጻፉት እየመረመሩ ሊቃውንቱ ከስንት ቋንቋ የጻፉትን አንተ ፩ድ ቋንቋ እንኳ የማታውቅ ይህን የመሰለ መጽሐፍ መንቀፍሕ ለመዋረድ ነው እንጅ ለሌላስ አይደለም እያሉ ያስፈራሩኛል ስለሆነም የሚአጽናኑ ፩ድ ፩ድ አላጣም ሐሰት ሆኑ ከተባሉት ጽሑፎች ፩ዱን እንኳ እዚህ ልጻፈውና አንባቢዎች እንድትመለከቱት አሳስባለሁ። የጽሑፉም አስተያየት መጻሕፍተ ብሉያትን አሉ ነበር ለማለት እንዲያውም ፳ኤል ከባቢሎን በተመለሱ ጊዜ ዘሩባቤልን የኢትዮጵያ ንጉሡ ነገሥት ልኮ ቢአስጠይቀው መጻሕፍተ ብሉያትን አስጽፎ ላከለት ብሎ ይጽፋል። አብርሃና አጽብሐም በሽዋ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ነበር እያለ ይቀባጥራል እንግዲህማ ካባ ጋስፓሪን መጽሐፍ ወዲያ ወዲህ ምን ይሠራልኛል ግን ትንሽ ልጻፍለትና እናንብብለት መጽሐፉም ገድለ ቀውስጦስ ይባላል ወእምድኅረዝ ነበሩ አበዊነ በሕገ ሙሴ እንዘ ያከብሩ ሰንበታቲሁ ለእግዚአብሔር በትእዛዘ ኦሪተ ሕግ ወደቂቀ እሥራኤል ዘሀለው በኢየሩሳሌም ሰዓርዋ ለዕለተ ሰንበት ወተንሥኡ ደቂቀ ነቢያት ኢሳይያስ ወኤርምያስ ወገሠጽዎሙ በትእዛዘ ኦሪት ዘሙሴ ወአበዩ። ወበእንተዝ መጽአ ዓቢይ መቅሠፍት እምኀበ እግዚአብሔር። ወተጼወዉ ውሉደ ፳ኤል በዕደ ነኪራን በኢኮኑ እምኀበ አምላክነ በገቢረ ጽድቅ። ወተመዝበረት ሀገረ ኢየሩሳሌም። ወኮነት ማኅደረ ለአራዊት ወበውዕቱ መዋእል ጊዜ ጠፍአት ኢየሩሳሌም ፈነዉ አበዊነ ኀበ ዘተጼወው ባቲ ምድር ደቂቀ ፳ኤል እንዘ ይብሉ መልእክት እፎኑ ሀለወክሙ

## ጽ ዓርብ

ወእፎኑ ኮኑ መጻሕተ አብያተ ዘአበዊነ ወዘአበቂክሙ ውዕያኑ አመ ጼዋዌ በእሳት አው ድኅናን ሀለዋ ወእፎ ሀለውክሙ አንትሙ ደቂቀ ፳ኤል ወደቂቀ ነቢያት። ሰገድክሙኑ ለጣዖታተ አረማውያን ወለመላእክተ ባእዳን ወእፎ ኮንካሙ ወንርክሙኑ ሰንበታቲሁ ለእግዚአብሔር። ወእምድኅረዝ ሶበ ሰምዑ ዘንተ መልእክተ ዘበአዊነ አንናንያ ወይቤሉ ንህነስ ሀለውነ በዳኅና በጸሎተ ዳንኤል ወአዛርያ ወአናንያ ወሚሳኤል እንዘ የዓቅበነ አምልክነ አምላክ

አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ አንትሙኒ አገሪክሙ ኅሥሥዎን ለመጻሕፍተ ሕገ ሙሴ ወዘ ዘነቢያት ንሕነስ ሐለውነ-ሀገረ ጴዋዌ ወአንትሙስ ውስተ ሀገረ ሣህል ወዛህን ባሕቱ ንሥኡ መጽሐፈ ዘኮነ እምኅበ አብ አንኤል ነቢይ። ወዘይቤ ዘንተ ነገረ። መጽአ ኅቤሆሙ ለአበዊነ እመጽሐፈ ትንቢቱ ለዳንኤል በዕደ ፩ዱ ተንባላታዊ ዘተፈነወ እምንጉሠ ኢትዮጵያ አይሱር ኅበ ዳርዮስ ንጉሠ ፋርስ ወሜዶን ዘይቤ ዳንኤል ነቢይ እንዘ እገብር ጸሎተ ወእትነኅይ ኃጣውእየ ቅድመ እግዚአብሔር መጽአ ኅቤየ ገብርኤል ወለመጽሐፈ ዝኒ ነገር ደመርዋ ምስለ መጽሐፈ ኦሪተ ሙሴ ዘመጽአ እምኢየሩሳሌም በዘመነ ሰሎሞን ምስለ አበዊነ ቀደምት ወምስለ ኦሪተ ሙሴ ዘይቤ ሰዱሰ ዕለተ ተገብር ግብረከ ወበሳብዕ ዕለት አዕርፍ ወእምድኅረዝ መጽአ ቃለ ዳንኤል ነቢይ ለአበዊነ ተሐንጸት ኢየሩሳሌም በዘመነ ዘሩባቤል ወተመይጡ ጴዋ ፳ኤል ውስተ ሀገሮሙ። ወበውእተ መዋእል ሐሩ አበዊነ ኅበ ኢየሩሳሌም እስመ ለአከ ዘሩባቤል እንዘ ይብል ኅበ ንጉሠ ኢትዮጵያ ሰላመ እግዚአብሔር የሃሉ ምስሌከ ስምዓኒ በይነ ፳ኤላውያን አማኅፀንኩከ እስመ መጽሐፈ ኦሪተ ሙሴ በጽሐ ውስተ ሀገርከ እምቅድመ ጥፍኣታ ለኢየሩሳሌም በእደ እምሔውከ ወልደ ሰሎሞን። አነኒ እፌኑ ለከ ዘኮነ እምኅበ እግዚአብሔር መጻሕተ ነቢያት ሀገረ ባቢሎን ወቀርስ ዘጻሐፍዎ ትሩፋኒሆሙ ለነቢያት ቀደምት አንተሂ ፈኑ ሊተ እመጻሕተ ነቢያት እለ ይቀድሙኒ

ወእምቅድመ ጥፍአታ ለኢየሩሳሌም ዘነበሩ እመናብርተ አበዊከ ከመ ይኩኑነ ተስፋ በኅበ እግዚአብሔር ስምላከ አበቂነ ሊተሂ ወለከ። ወዘንተ ሰሚኦ ንጉሠ ኢትዮጵያ ጸውዖሙ ለአበዊነ ወይቤሎሙ ንሥኡ መጽሐፈ ኦሪት ዘሙሴ ወዘኢያሱ ወሳሙኤል ወዘመሳፍንት ወዝሙረ ዳዊት ምስለ መጽሐፈ ነገሥት ወመጽሐፈ ሰሎሞን ሐሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም ኅበ ዘሩባቤል። ወአንትሙሂ ጽሒፈክሙ አምጽኡ ሊተ እመጻሕፍተ ነቢያት ቅዱሳን ዘኢመጽኡ ኅቤነ ቀዲሙ በዘመነ አበዊነ ወንሥኡ ፳ወ፪፻ተ ዲናር ወርቅ ለስንቅክሙ። ወ፪፻ት ዲናረ ወርቅ ይኩንክሙ አምኃ ዘሩባቤል ከመ ትርከቡ ሞገስ ቅድሜሁ ፳ወ፪ቱ፪ ለፍኖትክሙ ወእምዝ ነሢኦሙ ሖሩ አበዊነ ሀገረ ኢየሩሳሌም ወበጽሑ ኅበ ዘሩባቤል ንጉሥ ወተራከቡ በሰላም ምስለ ደቂቀ ነቢያት ትሩፋን ወአርአይዎሙ መጻሕተ ነቢያት ዘመጽኡ ውስተ ሀገርነ እምቅድመ ዘሩባቤል ወውእቶሙ አርዓይዎሙ መጻሕፍተ ትሩፋት ዘኢመጽኡ እምቅድመ ዝ። አምጽኡ ትንቢተ ሕዝቅኤል ወመጽሐፈ ኢሳይያስ ወኤርምያስ። ነቢይ። ወዘንተ መጽሐፈ እሂዞሙ አበዊነ ተመይጡ እምሀገረ ኢየሩሳሌም በዘመነ መንግሥቱ ለዘሩባቤል። እንግዲህ ይህን ጽፈው ያቆዩልን አባቶቻችን ምስክር እንዲሆነን ነበር። እንግዴህ በአባ ጋስፓሪን ቃል እንጣለው እንጅ ሐሰት ከሆነ ሐሰት ለምን ከቤተ ክርስቲያናችን

# ጾ ቀዳም

እናስቀምጣለን። ፪ኛም ደግሞ አብርሃና አጽብሐ ታሪክ ይናገራል እሱም እንደዚህ ነው። ወእንዘ ሀሎ ውስተ ሀገረ ቢለት ነገርዎ እንዘ ይብሉ ካህናተ ሀገሩ አ አባ ክቡር ሀለወት ውስተ ሥርማት አሐቲ ብዕሲት ውስተ ሀገርከ ንብጌ ወምድረ ዝም ወሰብዓ ጐሮፎኒ ወቅድስጌ ይሰግዱ ላቲ በኅቡዕ ወይወስዱ ላቲ መባዓ ውስተ ጽንፈ ፈለገ ሰሪት ዘሀለወት ደብር መስማ ሰገሊ። ወለይዕቲ ብዕሲት መሠረተ ስማሱራቲ ወቀደሳ ለማየ ቀጠማ በውእቱ ሜሮን ወአጥመቆሙ በሀየ ለሰብዓ የይ ወመሐግል ወገላን ወለሰብዓ ጋሞ ወላወሶ ወሰመዮ ስሞ ለመኰንነ ይዕቲ ሀገር መርኃ ክርስቶስ ወለብዕሲቱ ክርስቶስ ኃረያ ወለእሁሁኒ እስመ ቀዳሚ ኮነ ክርስቲያናዊ አጥመቆ ማየ ቈዳር ወሰመዮ ስሞ ዓምደ ሚካኤል ወለሰብዓ ሀገርኒ ወእምድኅረዝ ሐነጸ ቤተ ክርስቲያን ውስተ ቢለት መልዕልተ ጐማ በስመ ጊዮርጊስ ወሠመ በውስቴታ ፸ወ፯ተ ካህናተ ወእንዘ ሀሎ ውስተ ቢለት ነገርዎ እንዘ ይብሉ ካህናተ ሀገሩ አ አባ ሀለወት ውስተ ሥርማት ወእምዝ ነዓርግ መንገለ መንዲዳ ወበላዕሌሃ ሐነጸ ቤተ ክ. ዘቅዱስ ቴዎድሮስ ወአጥመቆሙ ለሕዝቡ ውስተ ሳኮሩ ወሤመ ላዕሌሃ ፵ወ፬ተ ካህናተ ወትሰመይ ይዕቲ መካን ደብረ እለ ዡንበር በደኃሪ መዋዕለ እመ ይነግሥ ወልደ እምከ ዘወለደቶ እምተሰፋ ኢየሱስ ፳ኤላዊ ወበደወለ ሀገርሰ ሀለወት አሐቲ ሀገር ዘያፈቅራ። ሕንጽ ሊተ ቤተ ክርስቲያን በስምየ እስመ

አቃቢከ ወሚም ስማ በስምየ ብሂለከ ገብርኤል ውስተ ጽንፈ ፈለገ ሠሪቲ ዘሀለወት ደብር ወበል ስማ ሰገሊ እስመ አኅደጋ ሰጋሌሃ ወሖረ ውስተ ቤታ ለአረጊት ዘኮነ መዋዕለ ሕይወታ ፻ወ፷ተ ዓመታተ ወጠየቃ አቡነ ቀውስጦስ መካነ ቤተ ክርስቲያን ዘነበረ በቀዳሚ ዘመን ወአውሥአቶ ወአርዓየቶ ይዕቲ አረጊት መካነ ቤተ ክርስቲያን ዐባይ። ዘነሥታ ለሀገረ ሠርማት መተሎሜ ንጉሠ ዳሞት ወረከበ አቡነ ውስተ ይዕቲ ቤተ ክርስቲያን ዘተነሥተት ውስተ ሕንጻሃ ውዑይ በእሳት ታሕተ ሐመድ በውስጣ አዕማዲሃ ዓቢያን ወዘተርፈ ወዲቆ ዲበ አዕባነ ሕንጻሃ ዓቢያን ወመሳክዊሃ ስፉሓን ዘኢውእዩ ወኢወድቁ ዲበ መርኅባ ተጸዊኖሙ በዕብን እስመ አዘዞሙ ለሰብዓ ይዕቲ ሀገር ይክርዩ ሐመደ ወያውጽኡ ውዑየ ሕንጻሃ ወያስተሳንዩ ንሕለታ ከመ ይርከቡ መሠረታ ወዘረከቡ በውስቴታ ዓቢይ መስቀለ ወርቅ ወጽዋዓ ወርቅ ወጻሕል ዘብሩር ዘቅብዕት በወርቅ ዘነኪር ግብሩ በወርቅ ጽሩይ መጽሐፈ ወንጌል ረከበ ከዊኖ ድሑነ ፍጻሜ ጽሕፈቱ ለውእቱ ዘረከበ በውስቴቱ ጽሕፈቱ ይብል ዝ ወንጌል ዘአብርሃ

ወአጽብሐ ነገሥት ኢትዮጵያ ዘወሀብዋ ለቤተ ክርስቲያን ዘጴጥሮስ ወጳውሎስ በሀገረ ሴዋ ወተፈሥሐ ጥቀ ወሰመያ ለይዕቲ ቤተ ክርስቲያን ደብረ እለ ዝንበር ትርጓሜሁ ዛቲ ደብር እስመ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ተሰምዩ ብርሃናተ በቃለ መጻሕፍት ወፍካሬ እሉ ነገሥት አብርሃ ወአጽብሃ ኮኑ ብርሃናተ ኢትዮጵያ ሀገሪትነ ወሠርዓ እምነ ደቂቁ ፪ ካህናት። እንግዲህ ሊቃውንቱ አባቶቻችን እንደዚህ ከነትርጓሜው እያሳመሩ ሀገሪቱ ደብረ እለ ዝንበር ስለመባሏ ከሥር ጴጥሮስና ጳውሎስ የዓለም ብርሃን እንደ መሆናቸው። ፪ኛም አብርሃና አጽብሃ ለኢትዮጵያ ብርሃን መሆናቸውን አስፋፍተውና ሳምረው ጻፉልን አሁን ከዚያች በጥብቅ የፈለገ ሰው ለዚህ ጽሑፍ ድጋፍ የሚሆን እንደማይታጣ የታወቀ ሲሆን የጠላት ምክር እየተከተልን ወደ ባርነት ሀገር ስንጓዝ በማየቴ ኃዘኔ ወሰን የለውም። ከኢትዮጵያ

## ፀ እጐድ

የሚገኘው ግዕዝ ከዓረብ አገር የመጣ ነው ተብሎ የተጻፈውን ስመለከት ፊደልና ዓላማ አንድ ነው ልዩነት የለውም። ፊደል ከሌለ ዓላማ በምን ሊታወቅ ይችላል። ሰው ፊደሉን ሲቀማ ዓላማውን መቀማቱ አይደለም ይሆንን የሮማ ልዑካን በረቂቅ መንፈስ ገብተው ፴፪ ዘመን ሙሉ ደዌ ሥጋ ሆነው ወድቀውብታል። ሮማ ያለው የማኅበሩ ሥራ አይቆይም ከኢትዮጵያ ውስጥ የነሱን ገንዘብ ፈላጊ አይጠፋ ፩ድ ዓይነት ፖለቲክ ሲረክስ ሌላ ፖለቲክ ይተካል። ለዚህ ሁሉ ዋና መሪ ሆኖ ኢትዮጵያን በሚበጠብጣት ይህ ገንዘብ የሚባል ጦር ነው ይህንም እርግጠኛ መሆኑን የሚአስረዳ የቀድሞ ፈላስፎች ከጻፉት ብንመለከት የተሻለ ስለ ሆነ ከዚህ አስከትሎ ተጽፎ የሚገኘው ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኃጢን ጽኑዕ | ውእቱ | እሳት | ይመውእ። |
| እሳት ጽኑዕ | ውእቱ | ማይ | ይመጽእ |
| ማይ ጽኑዕ | ውእቱ | ፀሐይ | ይመውእ |
| ደመና ጽኑዕ | ውእቱ | ደመና | ይመውእ |
| ነፋስ ጽኑዕ | ውእቱ | ነፋስ | ይመውእ |
| ምድር ጽኑዕ | ውእቱ | አዳም | ይመውእ |
| አዳም ጽኑዕ | ውእቱ | ኃዘን | ይመውእ |
| ኃዘን ጽኑዕ | ውእቱ | ወይን | ይመውእ |
| ወይን ጽኑዕ | ውእቱ | ንዋም | ይመውእ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ንዋም ጽኑዕ | ውእቱ | ንዕሲት | ትመውእ |
| ብዕሲት ጽኑዕ | ይእቲ | ንዋይ | ይመውዓ |

ሊቁ በምሳሌ እንደዚህ አድርጎ እንደተናገረው ይህ ገንዘብ ዋና ጦር መሆኑን ስላወቁ ሮማውያን በወር በወሩ ይህን የብር ጦር ወደ ኢትዮጵያ እየላኩ የብር ጦር ሊጥል እንጅ ሲዋጋ ስለማይታይ በኢትዮጵያ

ላይ ወንድምና ወንድም መመቃቀንና መጠላላት ብቻ ሆነ። ያለ ፍቅር ፩ድነት የለም ያለ ፩ድነት ኃይል የለም ያለ ኃይል መንግሥት አይቆምም ያለመንግሥት መቆም ነጻነት የለም ያለ ነጻነት ኲራት የለም ነጻነት ማለት ኲራት ነው። እንግዲህ ነጻነት ማለት ግዕዝ ነው ግዕዝ ማለት ነጻ ሆነ ግዕዙ ነጻ ሆኑ ማለት ነው። ይህም መሠረት ይታወቅ ዘንድ ኦሪት ዘፀዓት ፲፪ ፴፯ ወግዕዙ ደቂቀ ፳ኤል እምራምሴ ውስተ ሰኮታ ፳፱ አጋር ዕደው ያለውን ጠንቅቆ መመርመር ያስፈልጋል። የእስራኤል ልጆች በግብጽ በባርነት ሲገዙ ነበሩና ከግብጽ ሲወጡ ግዕዝ ነጻ ወጡ አለ እንደባርያ ለመገዛታቸው መረጃ በኦሪት ዘዳግም ፳፬ ፲፰ ወተዘከር ከመ ገብር አንተ በምድር ግብጽ ያለውን አይቶ ይበቃል። ግዕዙ ማለት ጥልቅ ምሥጢር ያለበት ነገር ነው እንጅ እንዲሁ በጫፍ የሚወሰን ነገር አይደለም። የጽሑፍ ሁሉ ትርጓሜ በቁጥር ነው። ፊደልም ራሱ ነው። ፩ኛ ማለት ዕለተ እሁድ ናት። ይህም ይታወቅ ዘንድ ፳ኤል ባ፩ኛዪቱ ወር ባ፩ኛዪቱ ቀን በዕለተ እሁድ ከግብጽ ነጻ ወጡ ግዕዙ አለ ማስተዋል ነው። ባ፩ኛዪቱ ወር ባ፩ኛዪቱ ቀን ሲል ግዕዝ ማለት ከሀ እስከ ፐ እንደኛው ሁሉ ግዕዝ ነው። ዕለተ እሁድ ዘወትር ግዕዝ ፩ ቁጥር ናት። አሁን ለነዚህ ማስረጃ የሚሆን ፩ኛ ዕለተ እሁድን ፲፪ ፲፮ ወዕለት ቀዳሚት ትሰማይ ቅድስተ ወዕለተ ሳብዕት ትኩንክሙ ቅድስተ ፲፯ ወእቀብዋ ለዛቲ ትእዛዝ እስመ በዛቲ ዕለት አውጽኦ ለኃይልክሙ እምድረ ግብጽ ያለውን

## ፁ ሰኑይ

መመልከት ነው። ይህ በዕለተ እሁድ መውጣታቸውን ያስረዳል ፪ኛ ወሩም ፩ኛው ወር ሚያዝያ ዘፀዓት ፲፪ ፪ ዝ ወርኅ ቀዳሚየ አውራኅ ይኩንክሙ ወአቅድምዎ እምአውራኃ ዓመት ያለውን መመልከት ነው። እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ፊደል ሀ ብሎ ስለሚዠምር ሚያዝያን ፩ኛ ወር ፩ድ ብሎ በፊደል ለመጥራት ሲአመለከት ሚያዝያን ፩ድ ሲለው አ ዘፀዓት ፲፫ ፬ እስመ በዛቲ ዕለት ትወጽኡ አንትሙ በወርኃ ሃሌ ሉያ። ሲል በግዕዙ ሀ ፩ኛ ስለሆነ ባ፩ኛው ፊደል ፩ኛ ወር መጥራቱ መሆኑን ማስተዋል ነው። ይህን የመሰለውም የፊደል ትርጓሜ ይህ ብቻ ሳይሆን ከሌላ ቦታም በመጠኑ አሳያለሁ ፩ኛ ኦሪት ዘፍጥረትን ፩ ፩። በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ። ሰ ያለው በግዕዝ ፯ት ቁጥር ስለሆነ ፯ቱን ሰማዮች ማለቱ መሆኑን ማወቅ ነው። ፪ኛ ወምድር ሲል። መ በግዕዝ ፊደል ፬ት ስለሆነ መ ብል ፬ቱን ባሕርያት በመሬት ውስጥ ስለሆኑ መ ብሎ ፬ቱን ባሕርያት መናገሩ መሆኑን ማስተዋል ነው። ፫ኛ በግዕዝ ፊደል ሰ ፯ ቁጥር ስለሆነ ሰንበት ሲጻፍ ሰ ፯ኛው የፊደል ቁጥር መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። ፬ኛ ኀ በኢትዮጵያ ፊደል ፳ ስለሆነ ፳ ቁጥር የመንፈስ ቅዱስ ስም ስለሆነ ሉቃስ ፳፬ ፵፱ ወናሁ እፌኑ ተስፋሁ ለአሁየ ላዕሌክሙ ወአንትሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም እስከ ትለብሱ ኃይለ እምዓርያም ያለው ኃ ሲል በግዕዝ ፊደል ፳ ቁጥር ስለሆነ መሆኑን መረዳት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ስም ፳ ቁጥር መሆኑ በምን ይታወቃል የሚል ቢገኝ ሀብትኬ ሠናይ መንፈስ ቅዱስ ያለውን ይመልከት ሀብት ሲል ፳ ነው መንፈስ አጋንንት እንኳ ለመወዳደር ቢልሆር ፳ቁ ይዞ ይገኛል። ፳ኛ በኖኅ ጊዜ የወረደውን ማየ አይኅ ኦሪት ዘፍጥረት ፯ ፲ ወአኀዘ ይሕልቅ ማይ ወይሐሩር እምነ ምድር ወእምድኅረ ፵ወ፵ ዕለት ሐፀ ማይ ይላል። ይህን ፵ ዕለት አይኅ ብሎ በግዕዝ ፊደል እንደተናገረው አይኅ ሲል በግዕዝ ፊደሉን የጋለውን ብረት ያለ ጉጠት እጨብጣለሁ እንደማለት ያለ ነው። ደግሞ ዋናው ማስረጃ እግዚአብሔር ወልድ ስም ፲ ቁጥር ስለሆነ ኦሪት ዘፀዓት ፴፬ ፳፰ ወጸሐፈ ውስተ ጽላት ዘንተ ነገረ ፲ተ ቃለ ብሎ የተናገረው ፲ተ ብሎ ቃለ ያለ በግዕዝ ፊደል መሆኑን መረዳት ነው። ግዕዝን ፊደል ለመረዳት ኤዶምንና አዳምን በፊደል ሲመረምር ልክ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል። የፊደልን ቁትር

ምሥጢር ያላወቁ ሰዎች የፊደሎችን ዘር መለዋወጥ ጥፋት መሆኑን አይረዱትም። ስለዚህ በጥንታዊው ግዕዝ መጽሐፍ ኤዶም የሚለው የውጭ አገር ሰዎች ኤደን ይላሉ። በኢትዮጵያ መጻሕፍት ኢየሱስ የሚለውን የውጭ አገር ሰዎች የሱስ ይሉታል። ይህ ሁሉ የፊደሉን ቁጥር

ምሥጢር ጣዕም ባለመልመድ ነው። የኢትዮጵያው መጻሕፍ ኤዶም ማለቱ ኤዶምንና አዳምን በፊደል ቁጥር ተባብሮ ፻፵፬ ማድረጉ ነው። ኢየሱስ ሲልም ዳግማይ አዳም ለማለት ትርጓሜው በቁጥር ፻፵፬ እንዲሆን በማለት ነው። ጌታችን ሁሉን ሲሠራ በረቂቅ ጥበቡ እዚህ ጐደለ እንደማይባል መዝኖና አስተካክሎ ስለ ሆነ ሥራው ሁሉ በቁጥር ማገር የተያዘ ነው። ስለዚህ አዳምን ለምሥጋና ስለፈጠረው ምሥጋናውም በየሰዓቱ ስለሆነ የስሙን ቁጥር ፻፵፬ አደረገው። በየሰዓቱም እንድናመሰግን ለመፈጠራችን ታላቁ ነቢይ ንጉሥ ዳዊት በመዝሙሩ ፩ ቊ ፪ ዘዳዕሙ ሕገ እግዚአብሔር ሥምረቱ ወዘሕጎ ያነብብ መልአተ ወሌሊተ ወሌሊተ። ፫ ወይከውን እክመ ዕፅ እንተ ትክልት

## ፪ ሠሉስ

ኀበ ሙኃዘ ማይ እንተ ትሁብ ፍሬሃ በበጊዜሃ ከመ ዕፅ እንተ ትክልት ያለው እኛን ደቂቀ አዳምን ነው። በውኃ ላይ የተተከለች ያለው አምላካዊ ትምርት ያለው ማለቱ ነው። በወንዝ ዳር የተተከለች ያለው ቃለ እግዚአብሔር ባለበት እንተ ትሁብ ፍሬሃ በበጊዜሃ ያች ዛፍ ባ፲፪ቱ ወሮች እንድታፈራ። ያችም በቃለ እግዚአብሔር አጠገብ ያለች ነፍስ ወደ ፈጣሪዋ ባ፲፪ቱ ሰዓቶች ፲፪ት ፲፪ አቡነ ዘበሰማያት ታቀርባለች ማለት ነው። ባ፲፪ቱ ጊዜ ፲፪ት ጊዜ ፲፪ ፻፵፬ ነው። ይህንም በሰፊው ሐዋርያው ዮሐንስ በራዕዩ ፳፪ ፪ ወይውኅዝ ውስተ ማዕከለ መርኅባ እምለፌኒ ውእቱ ፈለግ ወእምከሐከኒ ዕፀ ሕይወት ወይገብር ፍሬ ፲ወ፪ተ ወይሁብ ፍሬሁ ለለ፩ዱ ወርኅ። በዕፀ ሕይወት አጠገብ ውኃው በሜዳዋ መካከል ይፈርሳል አለና ዕፀ ሕይወትም ፲፪ ፲፪ ፍሬ ታፈራለች ያለው ባ፲፪ ሰዓቶች የሚጸልዩትን ማለት ነው። ፲፪ት ፲፪ቱም ፍሬ ባ፲፪ቱ ወሮች ሰዓቶች ሳያቋርጡ ያፈራሉ አለና ገልጾ አስረዳ። እንግዲህ ፲፪ት ጊዜ ፲፪ት ፻፵፬ መሆኑን አለመዘንጋት ነው። ደግሞ ዛሬ የዓለም ሊቃውንቶች ወጣቶችን ለማስተማር ያደራጁት ክብ ሜትር ወይም ኮምፓስ የሚባል አለ። በነዚህ ላይ ፫፻፷ ነጥቦች በዙሪያው ይገኛሉ። እነዚህን ፫፻፷ውን ላ፭ት ሲመድቧቸው ፸፪ ይሆናሉ ፭ቱ ፸፪ት ሲደመሩ ፫፻፷ ይሆናሉ። ይህም ፻፵፬ ቁጥር በሰው ክንድ ፻፵፬ቱ በመልአኩ ክንድ ፩ ይሆናል። ይህንም ለመረዳት ራዕየ ዮሐንስ ፳፩ ፲፯ ወእምዝ መጠነ አረፋቲሃ ፻፵ ወ፬ቱ በእመተ ሰብዕ ዘውእቱ ፩ በእመተ መላክ ያለውን ማየት ነው። በሰው ክንድ ፫፻፷ው በመልአኩ ፩ት ክንድ ተኩል ነው። ፩ት ክንድ ተኩልም ማለት ዋና መሠረት መሆኑን ለመረዳት ኦሪት ዘፀዓት ፳፭ ፲ ወትገብር ታቦተ ዘመርጡል ዘዕፅ ዘኢትነቅዝ ዘካዕበ እመት ፩ት ክንድ ወመንፈቀ እመት መንፈቅ የክንድ እኩሌታ ፩ቱ ክንድ ፪፻፹፰ መሆኑ ነው የክንዱ እኩሌታ ፸፪ት ሲደመር ፫፻፷ ከላይ በጠቀስናቸው በክብ ሜትርና በቡሶል ወይም በኮምባስ ዙሪያ የሚገኙ ፫፻፷ ነጥቦች በመልአኩ ክንድ ፩ት ክንድ ተኩል መሆናቸውን ማስተዋል ነው። ዛሬ በሚታየውም ሰው ሁሉ በያዘው ሰዓት ላይ እንደሚታየው በሰዓቱ ዙሪያ ፷ሣ ደቂቃዎች ነጥቦች አሉ ዋና ቆጣሪዋ ፭ቱን ደቂቃ ስትቆጥር ደቂቃ ቆጣሪዋ ፷ውን ታደርሳለች ፷ውን ላ፭ ስትመድበው ፲፪ት ይሆናል። ደግሞ እንደዚሁ ባ፩ ሰዓት ፲፪ት እየያዙ ሲቆጥሩ ባ፲፪ቱ ሰዓቶች ፲፪ት ፻፵፬ት ይሆናል ይህ ሁሉ የአዳም ስም ምሥጢር የሚገኘው በኢትዮጵያ ግዕዝ ፊደል ቁጥር ስለሆነ ይህ ታሪክ ላስተዋለውና ለመረመረው ለልዑል እግዚአብሔር ከፍ ያለ ምሥጋና በማቅረብ ፋንታ ዘወትር የሰይጣን መላክተኛ የመሰለ ነገር እየተባተቡ በሐሰት ምንገድ እያታለሉ በነጻነት የኖረችቱን መንግሥት ለማጥፋት በማሰብ ታላቁን ክብሯን መንካት በሙሴ የተነገረውን መርገም ለመቀበል ይመስላል። ይህም ከዚህ የሚከተለው ነው ኦሪት ዘዳግም ፳፯ ፲፫ ወእሉ እሙንቱ እለ ይቀውም ለረጊም በደብረ ጌባል ሮቤል ጋድ ወአሴር ወዛብሎን ወዳን ወንፍታሌም ወያወሥኡ ለሊሆሙ ሌዋውያን ወይብልዎሙ ለኵሉ ፳ኤል በቃል ዓቢይ ፲፭ ርጉም ለይኩን ብዕሲ ዘይገብር ግልፎ ወስብኮ ዘርኩስ ሕዝብ ወይብል አሜን ወአሜን። ፲፮ ርጉመ ለይኩን ዘያስተአኪ

አባሁ ወእሞ ወይብል ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን። ፲፯ ርጉመ ለይኩን ዘይሠርቅ ደወለ ቢጹ ወይብል ኵሉ አሜን አሜን። ፲፰ ርጉመ

# ፱ ረቡዕ

ለይኩን ዘያስሕቶ ፍኖተ ለእውር ወይብል ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን። ፲፱ ርጉመ ዘይገምጽ ፍትሐ ግዩር ወዘጓለ ማውታ ወዘእቤር ወይብል ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን። ፳ ርጉመ ለይኩን ዘይሰክብ ምስለ ብዕሲተ አቡሁ እስመ ከሠተ ኃፍረተ አቡሁ ወይብል ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን። ፳፩ ርጉም። ለይኩን ዘይሰክብ ምስለ ኵሉ እንስሳ ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን።

፳፬ ዘይነሥእ ሕልያነ ከመ ይቅትል ነፍሰ ደመ ንጹሐ። ንጹሕ ደም ማፍሰስ ማለት ወሰ ከማያገኘው ባሕር ከወሰነው አገር አልፎ መጥቶ እግዚአብሔር በሰጣቸው ርስታቸው ላይ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ በሚኖሩት ሕዝበ ክርስቲያኖች ላይ የተንኮል ሥራ እየሠራ ገንዘብ በሥውር የሚቀበለውን ማለቱ ስለሆነ ከኢትዮጵያ ተወላጆች ይህን የሚሠሩ ስለማይጠፉ። ይህ መርገም እንዳይደርስባቸው መጠንቀቂያ እንዲሆናቸው በማለት ነው። ፳፭ ርጉመ ለይኩን ዘይዘብጥ ካልአ በጕሕሉት ወይብል ሕዝብ አሜን። ፳፮ ርጉመ ለይኩን ብዕሲ ዘኢይቀውም ይገብር ዘውስተ ዝንቱ በዚህ ሕግ ውስጥ ያለውን በመፈጸም የማይቆም ሰው ሁሉ ርጉም ነው አለ። ወይብል ኵሉ ሕዝብ አሜን ወአሜን። ሕዝቡም ሁሉ አዎን ይበሉ አለ። በዳግም ሕግ የተጻፈልንን ሳንመለከት እግዚአብሔር ያቆመልንን ሕግ ጥሰን የመነኰስ ልብስ ለብሰን መንፈስ ይዋሄ የተመላባቸውን ሰዎች እያታለልን ደም ወደ ተመላበት መርገም እየሳብን ስንወስድ እንታያለን ያ የማይቀረው የልዑል እግዚአብሔር መልእክተኛ የመጣለት እንደምን ያለ የዘለዓለም ልቅሶ መኖሩ የሚዘነጋ አለመሆኑን አባታችን ሙሴ የጻፈልንን ዳግም ሕግ እያስተዋልን ቅዱስ ዳዊት ወዘሕነ ያነብብ መዓልተ ወሌሊተ ወይከውን ከመ ዕፀ እንተ ትክልት ኀበ መኃዝ ማይ እንተ ትሁብ ፍሬ በበጊዜሃ ያለውን። እየጸለይን ባ፲፪ቱ ሰዓቶች ፍሬዋን እንደምትሰጥ ባለው መሠረት ይችህንም ፍሬ ሐዋርያው ዮሐንስ ፩ዷቱ ፲፪ት ፲፪ት ፍሬ እንድታፈራ እንደጻፈው ይህችም ፍሬ ቁጥርዋ እስከ ፻፵፬ ስለደረሰ። ይህም ፻፵፬ት ቁጥር የአዳም የስሙ ቁጥር ስለሆነ ይህም ፻፵፬ት ቁጥር የሚገኘው በኢትዮጵያ ፊደል ቁጥር ስለሆነ የኢትዮጵያን መሠረት በግድ ማክበር አለበት። በመጻሕፍቱ ሁሉ መሠረት ሆኖ የሚገኘው የአዳም የስሙ ቁጥር መሆኑን ለመረዳት ፻፵፬ትን ለ፬ኝ ስትመድበው ፴፮ት ይሆናል። ይህም ፴፮ት ቁጥር የጌታችን ጸርወተ መንበር ፬ቱ እንስሳ ገጻቸው ፴፮ት ነው ማለት ባ፬ቱ ባ፬ቱ ማዕዝን ገጽ ሰብዕ ገጸ አንበሳ ገጸ ላህም ገጸ ንሥር እነዚህ ፬ቱ ባ፬ቱ ማዕዝን እንደሆኑ ለመረዳት ሕዝቅኤል ፩ ወለለ፩ ፬ቱ ገጹ የሚለውን ማየት ነው። ፴፮ቱ ሁሉ ፩ድ ጊዜ ቅዱስ ሲሉ ማስተዋል ነው ፫ ናቸው ፫ ጊዜ ቅዱስ ሲሉ ፱ ይሆናል በዚህ ሒሳብ ፴፮ቱ ገጽ ፱ ፱ ቅዱስ ሲሆን ፴፮ት ጊዜ ፱ኝ ፻፵፬ ይሆናል። ፲፪ቱ ሰዓቶች የማይነቃነቁ ሐውልቶች መሆናቸውን የማይውቅ እንደሌለ የታወቀ ነው። ግን ፲፪ት ጊዜ ፲፪ት የአዳም ስም መሆኑን የውጭ አገር ሊቃውንቶች የሚአውቁት አይመስለኝም። ምክንያቱም የግዕዝን ፊደል ቁጥር ብዙዎች ስለማያቁት ነው። ሆኖም ከውጭ አገር ሊቃውንቶች የግዕዝ ፊደል ቁጥር የጻፉ አይታጡም የአዳምን ስምና ዋና መሠረት አድርጎ ቅዱስ ዳዊት ያመልከታል። እሱም እንደዚህ ያሰናዳው ጽርሐ ዓርዓያምን በመንፈስ ቅዱስ እያየ ደብተራ ኦሪትን በሌትና በቀን ሰዓቶችን ለይቶ በመላእክትና በከዋክብት አምሳል በ፲፪ቱ ሰዓት መልአት ፻፵፬ት

# ፲ ሐሙስ

ደግሞ ባ፲፪ቱ ሰዓት ሌሊት ፻፵፬ት ድምር ፩፻፹፰ት ስለሆነ በ፲፪ቱ ነገደ ፳ኤል ልክ አድርጎ ዕጣ አጣጥሎ ሰዓቶችን እንዳካፈለ ዜና መዋል ፳፭ ፯ ወኮነ ኍልቈሙ ምስለ አኃዊሆሙ ምሁራን ወልብዋን ከመ ይሰብሑ ወይዘምሩ

ለእግዚአብሔር ኵሉ ዘየአምር ፪የ፹፰ ፰ ወውእቶሙ ካዕበ ተዓፀው ዕፃ ዘሰዓት በበዕብሬቶሙ ንዑሳን ወዐቢያንሂ ወእሉ ፍጹማን ወምሑራን። ዕጣ ተጣጣሉ በየክፍላቸው በሚጠብቁትና በሚአመሰግኑበት ማለት ማመስገን መጠየቅ ፩ድ አንጻር ነው እንደ ሰማይ ሠራዊት የደብተራ ኦሪትንም ሠራዊት ዛሬም በዓለም የሚገኙ ነገሥታት ሠራዊት በየሰዓቶች እየተፈራረቁ ሲጠብቁ እንዳሚታዩ ለምድራዊም ጦር ሠራዊቶች ልዩ ልዩ የክብር ደረጃ እንዳላቸው ለሠራዊተ ከዋክብትም የክብራቸው ደረጃ እንዳለው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ፲፭ ፵፩ ኮከብ እምኮከብ ይሄይስ ክብሩ ይላል። በዚሁ መሠረት በደብተራ ኦሪት ዙሪያ ለሚጠብቁ በዕጣ ሲአከፋፍል ፪የ፹፰ ቆጥሮ እነዚህ በጣም የተማሩና የተመረጡ ናቸው ብሎ አክብሮ ጠራቸው ፱ ወጽአ ቀዳማይ ዐፃ ለአሣፍ ወለደቂቁ ወለሰኃዊሁ ፲፪

ለዮሴፍ ወለጎዳልያስ። ካዕብ ኤንያ ወአኃዊሆሙ ወደቂቆሙ ፲፪

፲ ወሣልስ ዘዝኩር ወደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፲፩ ራብዕ ኢያዝሪ ወደቂቁ ወአኃዊ ፲፪

፲፪ ኃምሳ መተንያስ ወደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፲፫ ሣድስ ቡቅያስ ወደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፲፬ ሳብዕ እስራኤል ወደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፲፭ ሳምን ኢያስያስ ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፲፮ ታስዕ ማንተያንስ ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፲፯ ዓሥር ሴማን ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፲፰ ፲፩ኛ አዝራኤል ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፲፱ ፲፪ኛ አሳብያ ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፳ ዓሥር ወሠላሣ ሱባሔል ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፳፩ ፲ኛ መንታንያስ ደቂቁ ወአኃዊሁ። ፲፪

፳፪ ፲፭ኛ ኢያሬሞት ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፳፫ ፲፮ኛ አናንያስ ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፳፬ ፲፯ኛ ኢያሳበቃጥን ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፳፭ ፲፰ኛ አናኒ ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፫

፳፮ ፲፱ኛ ሜሌቲ ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፳፯ ፳ ኤልያት ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፳፰ ፳፩ኛ ኢያቴሪ ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፳፱ ፳፪ኛ ገደልቱ ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፴ ፳፫ኛ መንዝዮት ደቂቁ ወአኃዊሁ ፲፪

፴፩ ፳፬ኛ ሮሜቴዜር ደቂቂ ወአኃዊሁ ፲፪

ከላይ የተጻፉትን ሁሉ ያ፲፪ቱን ሰዓት ሌሊትና ሰዓት መዓልት መሠረት ከአዳም ስም የተገኙ መሆናቸውን ያስረዳናል ይህም የአዳም የስሙ ቁጥር በመጻሕፍቱ ውስጥ ፳ንና ሮ፪ትን እየተመረኮዘ ዋና ሚሥጥሩን እየገለጸ ሲሄድ የሚገኘ በኢትዮጵያ ፊደል ነው። የኢትዮጵያ ፊደል ሲመረመር ታሪኩ ብዙ ነው። ለማነኛውም ሥራ መዠመሪያ የሚሠራውን ሥራ ሁሉ ስለ ቁመቱና ወርዱ መለካት መከንዳት አለ በስፍር ካልተወሰነ ማነኛውም ሥራ እንዳይካሄድ የታመነ ነው። ስለዚህ አስቀድሞ የመለኪያ መዠመሪያ ክንድ ነው። በግዕዝ ፊደል

# ፅ ዓርብ

እመት ነው። ይህም አመተ ከነዳ ካለው የወጣ ነው። በፊደል ቁጥር እመት አ ፴ መ፬ ተ ፲ ድምር ፵፬ ይሆናል ፵፬ትን ለ፮ት ሲመድቡት ፱ኝ ይሆናል በግዕዝ ፊደል በ ፱ኝ ቁጥር ስለሆነ ሙሴ ነገረ እግዚአብሔርን ሊጽፍ ሲዠምር በቀዳሚ ብሎ ዠመረ በ ብሎ የዠመረው በ ፱ ቁጥር ስለሆነ ነው። ፱ኝን ባ፲ ስታበዛው ፺ ይሆናል። ይህም ፱ኝን ባ፲ር ማብዛት ማለት ረቂቅ ምሥጢር አለበት ይህም እንደዚህ ነው በአሪት ላይ እመት ወመንፈቀ እመት የሚለው እመት ክንድ በጋት ሲሰፈር ፮ ጋት ነው። መንፈቀ እመት ያለው ስንዝር ፫ ጋት ማለት ነው ፫ቱ ጋትና ፮ት ሲደመር ፱ኝ ይሆናል። ይህም ፱ ቁጥር የመቤታችን ስም ስለሆነ በምሳሌ ፱ ጋት አለና በወልድ ስም ቁጥር በእግዚአብሔር ቃል ፲ቱ ቃላት በጽላቱ ላይ ይጻፍ ያለው ቃል ከእመቤታችን ተወልዶ እንደሚያድነን ትንቢቱን ሲአመለክት ነው። ፱ ጋት በሆነው ጽላት ፲ሩ ቃላትን እንዲጽፍ አዘዘው። ስለዚህ በ፱ኝ ቁጥር ፲ር ቁጥር ሲበዛ ፺ ይሆናል። ፺ ባ፬ት ሲበዛ ፫፻፷ ይሆናል። ይህም ፫፻፷ የጌታችን ስም ነው ስለዚህ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሲሠራ በእግዚአብሔር ስም ልክ ስለሆነ ነግሥት ፮ ፪ ወውእቱ ቤት ዘሐነጸ ሰሎሞን ንጉሥ ለእግዚአብሔር ፷ በእመት። ፷ው ክንድ በጋት ፫፻፷ ስለሆነው ንግሥተ ሳባም ሰሎሞን የእግዚአብሔር የስሙ ቤት ሥራ ባልዋት ጊዜ ከኢትዮጵያ ተነሥታ ወደ ኢየሩሳሌም የወረደች በግዕዝ ቋንቋዋ የተማረች ስለሆነች የእግዚአብሔርን ስም በማወቋ ለመረዳት ስለሆነ በጥበብ ለመፈታተን እየሄደች ነገሥቱ ያስረዳናል። ሰሎሞንም የቤተ መቅደስን ቁመት ፷ ክንድ አድርጎ የሠራው በአብርሃም ስም ቁጥር አድርጎ ለሰሎሞን ጥበብ የተገለጠለት በመሆኑ ነው። የአብርሃምም ስም ፷ ቁጥር የሚሆነው በኢትዮጵያ ፊደል በግዕዝ ቁጥር መሆኑን አስረዳለሁ አስቀድሞ የአብርሃም ስም አብራም ነበር። በኋላ ግን በኢትዮጵያ ፩ድ የሚቆጠረውን ሀ የሚባለውን ፊደል ጨመረለትና አብርሃም ተባለ። ይህም አብርሃም ማለት በግዕዝ ፊደል አ፴ በ፱ ረ፮ ሀ፩ መ፬ ድምር ፷ ይሆናል ይህም ፷ ቁጥር ዋና መሠረት ስለሆነ ዛሬ በዓለም ላይ ለሚገኙ ሰዓቶች ሁሉ ዋና መሪ መሠረት መሆኑን መረዳታ አስፈላጊ ነው። ይህ ፷ ቁጥር በክንድ ፫፻፷ ጋት ሲሆን ይገኛል ይኸውም ፫፻፷ ቁጥር የእግዚአብሔር ስሙ መሆኑን ለመረዳት ኦሪት ዘፀዓት ፮ ፯

ዘአስተረይክዎ ለአብርሃም ወለይስሐቅ ወለያዕቆብ እስመ አምላኮሙ አነ ወስምየ እግዚእ ሲል በኢትዮጵያ ፊደል አ፴ ገ ፪፻ ዘ፻ አ፴ ድምር ፫፻፷ ይሆናል። ንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም የወረደች ይህን ምሥጢር ስለ አወቀች ነው። ይህንም በእውቀቷ ተመራምራ አውቃ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዷ ጌታችን ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ የኢየሩሳሌም ሰዎች ሲወቅስ ካ፩ድሽ ፲፫ ዘመን በላይ ዕድሜ ያለውን ነገር አንሥቶ የኢትዮጵያ ንግሥት ሰሎሞን የእግዚአብሔር ስም ቤት ሠራ ቢሏት መጥታ አይታ አመነች እኔ ሰሎሞንን የሠራሁ ብመጣ አልቀበልም አላችሁ በዚያ ጊዜ የዓዜብ ንግሥት ትፋረዳችኋለች ብሎ ንግሥተ ዓዜብን እንደ ጠበቃና እንደ እንደራሴ አድርጎ ትፋረዳችኋለች ብሎ ቢናገር እንግዲህ እንደ ነገሥቱ ንግሥተ ሳባ ብሎ ጌታችንም ተናግሮ ቢሆን ይህችን ንግሥተ ዓዜብን የሮማ ልዑካን በጣም በተመቻቸው ነበር ማቴዎስ ፲፪ ፴፪ ጌታችን የዓዜብ መንግሥት ብሎ የጠራበትን ምሥጢሩን ሮማውያን ገና አላወቁትም

## ዖ ቀዳም

ንግሥተ ሳባ ለተባለውስ በትር ቅጥቁጥ ተብሎ እንደ ተነገረው የደቡብ ዓረብ የተባለውን የውሸት ምርኩዝ የተደገፈ ይንቀጠቀጣሉ ደግሞ ንግሥተ ዓዜብ ብሎ ለጠራት ምን ምክንያት ለመፍጠር ይችሉ ይሆን። የኢትዮጵያ ታሪክ መሠረቷ ግዕዝ ነው። ይህ ግዕዝ ዋና መዲናው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ናት። የሮማ ልዑካን አሳብ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ደምሰው የነሱን የጸሎት ቤት አስፋፍተው የሮማ ቤተ ክርስቲያን ጥገኛ ለማድረግ ስለሆነ ለዚሁም ይህን ገለባ የሆነ ሐሳዊ ስብከታቸውን በግብዞች ላይ ሲዘሩ ይታያሉ። የግዕዝ ፊደል መሠረቱ ጥልቅ ነው። ከላይ ግዕዙ ፷ኤል ያለውን በአሪት ዘፀዓት ፲፪ት ፴፯ ወግዕዙ ደቂቀ ፷ኤል እምራምሴ ውስተ ሰኮታ ብሎ ፷፻፻ አጋር ዕደው ፮፻ ሽህ ማለቱ ነው ይህን ፮፻ሽህ ቁጥር በከንቱ የጻፈውን አይደለም ያዕቆብም ወደ ግብጽ አገር ሲሄድ የያዕቆብን ዘሮች ቁጥሮ ከመጨረሻ ድምር ላይ ፸፫ ነፍስ ሆኖ ወደ ግብጽ ወደ ባርነት ሲገባ ማለት ነው። ከባርነት ሲወጡ ደግሞ ግዕዙ አለና ፮፻ሽ ቆጠረ እንግዲህ የግዕዝ ፊደል ቁጥር ከቁጥሩም ባ፩ኛው ቁጥር ፷፻ ነው። ፮፻ውን ሽ ለ፸፫ት ስትመድበው ልክ ፷ሽ ይሆናል። ፸፫ቱ ሰዎች ፩ድ ፩ዳቸው ፷ሽ ፷ሽ ሆኑ ከማለቱ በላይ የግዕዝ ፊደል ቁጥር ፷፻ ስለሆነ በረቂቅ ጥበብ የእስራኤል ልጆች ግዕዙ ነጻ ሆኑ ብሎ ጽፎአልን ይገኛል። ይህን የትርጓሜ ምሥጢር በማነኛውም ፊደል ቁጥር ትርጓሜ እንደማይቻል። የግዕዝ ምሥጢር አስቀድመው ሳይመረመሩ እንዲሁ የላኩትን ለማድረስ አባ ጋስፓሪን ግዕዝ ከደቡብ የመጣ ነው እያሉ በማያቋርጥ ነፋስ በሰሜን በኵል ሆነው እኪት ትትረኃው እምሰሜን። ባለው መሠረት ይህን የመርዝ ነፋስ በለቀቁት ጊዜ ከማይጨው ዘመቻ ወዲህ የተወለዱ ልጅጆች በጭራሽ የማይችሉት ስለሆነ ትንሽ የሰው ዘር ባተርፍ ለማለት ይህን ጽሑፍ በብዙ ድካም ለማደራጀት ተነሣሁ።

አስቀድሞ ሰው የሆነ ሰው ፊደልን ሲአነሳ ፊደሎች የተገኙበትንና የመጡበትን በዚያ ላይ ውሥጠ ምሥጢራቸውን መርምሮ ካጠና በኋላ ቢጽፍም ቢናገርም አይከፋም። የሮማ ልዑካን በከፊል ውስጥ ገብተው ላረብ አገርና ለኢትዮጵያ ፊደል አካፋይ ሆነው የተገኙ በምን ምክንያት ነው። ሌላው ይቆይና የቋንቋ መለያየት በተደረገ ጊዜ የነበሩ ቋንቋዎች ፸፪ መሆናቸውን ታሪክ ይነግረናል። የሮማ ቋንቋ ከዚህ ከ፸፪ቱ ቋንቋዎች ውስጥ ቁጥር ያለው ለመሆኑ ከፋሌቅ ዝምሮ ሲያያዝ የመጣበትን ለማስረዳት ይቻላቸዋል ይሆንን። ለመሆኑ የሮማ መንግሥት ከክርስቶስ በፊት ፯፻ ዘመን ቀድሞ የነበረው ዘመን ነው ታሪኩም ሮሞሎና ሬሞ ከሚባሉት ቴቤሪ ከሚባል ወንዝ ወድቀው ሲአለቅሱ ተኩላዋ ሰምታ ስታጠባቸው የተገኙ ልጆች አድገው በነሱ ስም የተጠራች መሆንዋን ታሪክ ይነግረናል። ይህ ዛሬ በሮማ የሚገኘው

ላቲን እንደምን ሆኖ ሲያያዝ እንደመጣ በጣም አሰናድቶ አጠናቆ መያዝ የተገባ ነበር። ቋንቋማ በኢትዮጵያም ብዙ ቋንቋዎች አሉ። ወደ ፊትም እንደገና እየተስፋፉ የሚሄዱ ይገኛሉ እነዚያ ሁሉ ሌላ ስለ ማያውቁ ከአዳም ዝምሮ ያለው ቋንቋ የኛ ነው ይላሉ ምክንያቱም የምሥጢር ነገር ባለማወቃቸው ነው። አሁንም የሮማ ልዑካን አማርኛን አስፋፍተው ግዕዝን ወደ ጐን እንዲቆይ አስደረጉ በኋላ በጣም ሞቅ አላቸውና በሥውር ቀስ እያለ

## ፈ እኁድ

የሚሄደውን የፖለቲክ ስብከት በጣም ዓየር አውጥተው ለቀቁት። ምክንያቱም በዓድዋ የመጣው የጦር ሠራዊት ጥቅም ሳያገኝ ተመለሰ። በሽ፱፻፹፰ ዓ.ም የመጣው ጦር ሳይሆንለት ቀርቶ ባ፵ ዓመቱ ተመልሶ ሄደ የጦር ሠራዊት ኃይል ፩ድ ቀዋሚ ነገር ሳይሠራ እነሱ ውስጥ ለውስጥ የሠሩት ፍሬ ለማግኘት በቅቶ በኢትዮጵያ ላይ የግዕዝ ትምርት ቀርቶ ያማርኛ ትምርት ቤት በመቋቋሙ የሮማ ልዑካን ደስታቸው ከልክ ያለፈ ስለሆነ ከደስታቸው ብዛት የተነሳ ይህን የፖለቲክ ሥራቸውን መግለጫ የሆነ ጽሑፍ ያለፍርሃት ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ለማቅረብ ቻሉ።

ይህንም ለመጻፍ ሲአስቡ ያደፋፈሯቸው የሀገራችን ሰዎች እንደሆኑ ታውቋል። ስለዚህ ነገር ወገን ከጠላት ገጥሞ ሲገኝ በምን ያላቅቋል። አሁን የኢትዮጵያን ግዕዝ መሠረት በመመርመር ላይ ነው ያለነው ስለዚህ የፊደል ባለቤቶች ሁለት ሲሆኑ ፩ኛው ግዕዝ ነው። አካሄዱም ከላይ አመልክቻለሁ ፪ኛው እብራይስጥ ነው። ግን ብዙዎች ሊቃውንት በመዠመሪያ መጻሕፍት ኦሪት በእብራዊ ቋንቋ ተጽፎ በመገኘቱ። ከእብራይስጥ ቋንቋ መጻሕፍተ ብሉያትን ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተገልብጠው ስለመጡ እብራይስጥን ፩ኛ ያደርጉታል። እብራይስጥን ፩ኛ የሚሉበት ምክንያት መጻሕፍተ ብሉያትን ሙሴ በእብራይስጥ በመጻፉ ነው እንጅ በምሥጢራዊ አስተያየት አይደለም። እኔ ግዕዝን ፩ኛ ነው ለማለት የደፈርኩበት የፊደሉን ቁጥር የምሥጢራዊውን ትርጓሜ የአበውንም ስም ትርጓሜ በግዕዝ የተስማማ ምንገድ ይዞ ሲገኝ ስላገኘሁት ነው እንጅ እብራይስጥ ወደ ግዕዝ መመለሱን የእስራኤል ቋንቋ እብራይስጥ አልነበረም አላልኩም። ግን የጥንቱ የእብራይስጥ ፊደሎች ፳፪ት ደረጃቸው ፭ት ናቸው። ምክንያቱም ያ፭ት ቁጥር መሠረት ከፍ ያለ መሆኑን የሚአስረዳ ዛሬ በሚታየው ዋና ጥበብ ሥራ ሌሊትንና መዓልትን የሚሰፍር ሰዓት በዙሪያው ፭ ፭ ነጥቦች ይገኛሉ ሙሴም መጻሕፍተ ኦሪትን ሲጽፍ ፭ት ክፍል አድርጎ ነው። ቅዱስ ዳዊትም ፻፶ መዝሙር ሲጽፍ ባ፭ት ክፍል አድርጎ ነው። ስለዚህ የእብራይስጥ ፊደል ደረጃዎች ፭ት ስለሆኑ ፳፪ቱ ፈደላት ባ፭ት ሲበዙ ፻፲ ይሆናሉ። ስለዚህ በዚህ በ፻፲ር የፊደል ቁጥር የተጻፈ የእብራይስጥ መጽሐፍ የሚገኝ አይመስለኝም። ምክንያቱም እንደዛሬው በግዕዙ ፊደሎች ላይ አዲስ ሕገ ወጥ ልብ ወለድ የተፈጠሩ ፊደሎች ላማርኛ መጻፊያ ሆነው ጣልቃ ገብተው ስለሚገኙ በእብራይስጡም ከጥንቱ በቁጥር የማይገቡ አዲስ የተፈጠሩ ፊደሎች በየጊዜው የገቡባቸው መሆናቸውንና አለመሆናቸውን ለመለየት ፊደሎቹን በቁጥር የሚጠብቅ ምሥጢራቸውን የሚአውቅ ቢገኝ ቅዱስ ዳዊት በሰጠን ጽሑፍ አስተያየት። በ፻፲፰ኛው መዝሙር በኢትዮጵያው ዳዊት መጽሐፍ የዳዊትን መዝሙር አወቀው አፋልሰውታል። ቅዱስ ዳዊት በ፻፲፰ኛው መዝሙር ላይ ፳፪ቱን አሌፋት አግብቶ የጻፈበት ዋና ምሥጢር አሁን ልገልጸው ስለማያስፈልግ ፩ድ ተ ን ፬፻ ብሎ ስለሚጨርስ ተ ትእምርተ መስቀል ስለሆነ ተ ፬፻ ቁጥር ነው። ይህ ፬፻ ላ፬ት ሲካፈል ፻ ስለሚደርስ ይህም ስሙ በጐ ለሠሩ ሰዎች ምልክት ስለሆነ ሕዝቅኤል ፬ ፬ ወይቤሎ እግዚአብሔር ባእ ማዕከለ ሀገር ወማዕከለ ኢየሩሳሌም ወጸሐፍ ሐትዮተ ውስተ ፍጽሞሙ ለእደው እለ ንሕኩ ወተከዙ በእንተ ዝንቱ ኵሉ ኃጢአት ዘኮነ በማዕከሎሙ። ባዘኑና በተከዙ ሰዎች በግምባራቸው

# ፉ ሰኑይ

ላይ ጻፈባቸው እለ የሚጻፈውም ታው ነው። አሁን የሚአመለክትበት ፊደል ተ ነው። ፪ኛ ይህን መሠረት አስፋፍቶ ለመግለጽ ሐዋርያው ዮሐንስ ፯ ፪ ወነጸርኩ ወመጽአ ካልዕ እምነ ጽባሕ ወይጸውር ማኅተመ እግዚአብሔር ዘሕያው ለዓለም ወይቤሎሙ በዐቢይ ቃል ለእልክቱ ፬ቱ መላእክት እለ ተውህበ ሎሙ ይቅሥፍዋ ለምድር ወለባሕር። ፫ ወይቤሎሙ ኢታሕምሙ ምዕረስ ኢምድረ ወኢባሕረ ወኢዕፀታተ እስከ ይትሐተሙ አግብርተ እግዚአብሔር ውስተ ፍጽሞሙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ፊታቸውን እስኪ ታተሙ ብሎ ተ የሚባለውን ፊደል ማመልከቻ አድርጎታል። ፬ ወሰማዕኩ። ኍልቈሙ እለ ተኃትሙ ፲፬ቱ፼ ወ፵፻ እለ ተኃትሙ እምውስተ ደቂቀ ፳ኤል አለ። እንግዴህ እዚህ ላይ የግዕዙ ፊደል ቁጥር መጣ የአዳምን ስም ቁጥር በሽ አብዝቶ አመጣው። ፻፵፬ትን በሽ ሲያበዛው ፻፵፬ሽ ሆነ። ይህንም ላ፲፪ት ሲአካፍሉ ፲፪ሽ ፲፪ሽ ይደርሳል። ፲፪ቱንሽ ለ፴ ስትመድበው ፬፻ ይሆናል። እንግዲህ የታው እብራይስጡ ፬፻ ቁጥር የሆነው ይህ ነው። የአዳምን ስም ቁጥር ፻፵፬ቱን ስለምን በሽ አበዛው ብሎ ለሚጠይቅ ኦሪት ዘፀዓት ፳ ፮ ወእገብር ምሕረተ ለ፲፻ት ለእለ ያፈቅሩኒ ወትእዛዝየ ለእለ የዓቅቡ። ኦሪት ዘዳግም ፯ ፱ ወእገብር ምሕረት እስከ ፼ ትውልድ እስከ ፲ሽ ማለቱ ነው እንደዚህ እያበዛ ይናገራል የፊደል ቁጥር የለም የሚል ከንቱ የግብዝ ሥራ ነው። በእውነትስ የመጻሕፍትን ነገር ለመርመርና ላስተዋለ የፊደልን ቁጥር ማቃለል አይቻልም። አሁን እኔ የማስታውሰው የሮማውያንን ስብከት ሐሰትነቱን ለመግለጽ ስለሆነ አሁን የኢትዮጵያ ወጣቶች በጥብቅ እንድትመለከቱት ነው። በአባ

ጋስፓሪን መጽሐፍ “በ፴፬ኛ በ፳፫ኛው መስመር በቢለን ቋንቋ እንደወሰነን አይተናል። ደግሞ (በ፴፱ነኛው ገጽ በ፳ኛው መስመር የአገርና የሰው ስሞች ማነጣጠር በኢትዮጵያ አውራጃዎች አልፈው አልፈው የሚገኙት የአገርና የሰው ስሞች ከዓረብ ቋንቋና አገር የተወረሱ መሆናቸውን የሚገልጽ ታሪክ ከዚ ቀጥሎ በሚገኘው ጽሑፋችን እናስረዳለን። ሀ. እኒህ የዮቅጣን ልጆች የሆኑ የሴም ነገዶች ከዓረብ ደቡብ አገር ሲቀመጡባት የነበረችው መዲናቸው ስሟ መእሪብ ትባል ነበር። በዚያችውም መእሪብ መረብ በተባለችው መዲናቸው ላይ በብዙ ብልሃት ተመድቦ የቆመ ትልቅ ባሕር የሆነ ኩሬ ነበር። በዚህም ሁኔታ ከዚያች መዲናቸው ተጉዘው ወደ ኢትዮጵያ እንደገቡ ድባርዋ ላይ ሰፈሩ። ከሰፈራቸው አጠገብ የሚገኘውንም የመረብ ምንጭ ካአገራቸው በነበረው ግድብ ኩሬ ስም መረብ ብለው ሠይሙት) ጥያቄ ከዚያ በፊት ስሙ ማን ነበር መልስ የለም። (ለ. እንዲሁም ሳባውያን ሲነጋገሩበት የነበረውን የዓረብ ቋንቋ ወርሳ እስካሁን ድረስ በትግርኛ ባጽዕ ተብላ የምትጠራ ትልቅ ከተማ አለች። ይህችም ከተማ የሳባውያን ግብር አስገቢዎች ሲቀመጡባት የነበረች አገር መሆኗ ይገልጻል። ሳባውያን በሚነጋገሩበት በዓረብ ቋንቋ ግብር አስገቢ ማለት ባጽዕ ይባላል) ይህ የሐሰት ስብከት በፊደል ቁጥር ተጽፎ ይገኛል። ይህ የፊደል ቁጥር የተነሳ ሀን ፩ድ ለን ፪ት ሐን ፫ እያለ በፊደሎች እየቆጠረ እስከ ጰ ድረስ ይህኑ የሐሰት ወሬ ይዘረዝራል ለመሆኑ አባ ጋስፓሪን አሁን ቢጠየቁ ማለት ይህን የፊደል ቁጥር ሀ ፩ድ ብሎ መዠመር መሠረቱን ከምን አመጡት ተብለው ቢጠየቁ ከየትኛው አገር አገኙቱት ለማለት ይቻላል ይሆን። ለመሆኑ አረቦቹስ በሀ እንዠምር ነበር ብለው ይመሰክሩላቸ

# ፊ ሠሉስ

ይሆንን። ይህን ሁሉ ሐሰት በዓረብ አገር ያሉ ሽማግሌዎች ሁሉ ይህን ጽሑፍ በሰሙ ጊዜ ይቀበሉት ይሆንን። በ፵፬ኛው ገጽ ላይ ስለ ሚገኘው ባለ አንበሳ ሐውልት ጥንታዊ ጽሑፍ “በ፵፫ኛው ገጽ። ይህ ሥዕል በኢትዮጵያ የተገኙትን ሁለት ቅርጾች ያሳያል ከላይ ወገን የሰው ራስ ያለው አንበሳ በግዕዝ ሶበድዓት የሚባል አስፊንክስ ይታያል ይህ ቅርጽ ግብጽ ላይ ከፒራሚድ አጠገብ ከሚገኘው ከእስክንፊስ የተወሰደ ግልባጭ ይመስላል ያለ ጥርጥር ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሳባውያን ጣዖት ነው)። መቸም በሮማ ልዑካን አስተዋሽነት ኢትዮጵያ ሁሉን ከመበደር በተቀር ሌላ ሥራ የላትም ፊደሉን ሥልጣኔውን ከዓረብ አገር ማሰሮ የተገኘ እንደሆነ ከግብጽ የመጣ ነው ይባላል። ደግሞ በሐውልት ላይ አንበሳ ተቀርጾ ቢታይ ይህ ቅርጽ ከግብጽ ከፒራሚድ አጠገብ እስክንፊስ የተወሰደ ግልባጭ ይመስላል ተባለና ደግሞ እንደገና ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሳባውያን ጣዖት ነው ተባለና አረፈ። በኢትዮጵያ የተገኘው ሁሉ የሀገሩ የወንዙ ስም ከሩቅ የመጣ ነው ኢትዮጲስ የሚባለው ስም ከግሪክ ኩሽ የሚባለው ስም ከግብጽ ሁሉ ነገር ከውጭ ነው። ከግርጌውም ፩ የአረመኔዎች መሠዊያ ይታያል። መሥዋዕቱ በዚህ መሠዊያ ላይ ይሠዋ ኑርዋል ደሙ

በገንዳው ውስጥ ተጠራቅሞ በሚታየው ቀዳዳ ይፈስ ነበር። በስተፊትም የሳባውያን ጽሕፈት ይታያል። ከላይ የተጻፉ ነገሮች ሁሉ ያስደንቃሉ። የጣዖት ነገር በሀገራቸው ላይ ጴጥሮስና ጳውሎስ ከሞቱበት በኋላ እስከ ብዙ መቶ ዓመት ለጣዖት ሲሰግዱ እንደ ቆዩ ታሪክ ይነግረናል ስለዚህ የጣዖታቱን ታሪክ ስለሚወዱ ጥንታዊ ሐውልት ቢገኝ ጣዖት እያሉ ተረጐሙት። በሐውልቱ የሚገኘውን ጥንታዊውን በካም መንግሥት የመጣውን የግዕዝ ጽሑፍ ሳባውያን የጻፉት ብለው ሠየሙት። ይህ ጥንታዊ ጽሑፍ መሠረቱን እንደያዙ ተቀምጧል ገና ሊመረመር ይችላል የሚገርመው ነገር በሐውልቱ ላይ የተጻፈው ግዕዝ ተተረጐመና ሲነገር የአምላክ አዳኝ ልጅ የሆነው አምላክ አጠና የተባለው ንጉሥ ይህንን ቤተ መቅደስ አሠርቶ ዘተሐም ለተባለው ጣዖት አበረከተው ተብሎ ተጽፎ ይገኛል።

(በ፵፮ኛ ገጽ ፳ኛ አግአዝያን የተባሉ ወደ ኢትዮጵያ ስላመጡት የግዕዝ ቋንቋና ጽሕፈት። አግአዝያን የተባሉ ሳባውያን ከፊኒቃውያንና ከእብራይስጥ ከዓረቦች የሚዛመደውን ቋንቋ ይዘው መጡ። ይኸውም ቋንቋ በዓረብ ሳሉ ሳባዊ ቋንቋ ይባል ነበር። ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ ግን ከጥንታዊ ሳባዊ መሠረቱ ጥቂት የተለወጠ ሆኖ ግዕዝ ተባለ)

እዚህ ላይ ፩ድ ጥያቄ ያስፈልጋል። ከጥንታዊ ሳባዊ ቋንቋ መሠረቱ ጥቂት የተለወጠ ሆኖ ግዕዝ ተባለ ብለው የጻፉት እምኑ ላይ ነው የተለወጠውስ የቀድሞውስ የትኛው ነው የተጨመረውስ የትኛው ነው። ያልሆነውን የማይዛመዱትን አዛምዳለሁ ማለት ከንቱ ነገር ስለሆነ የማይስማማውን ይስማማል ማለት ከንቱት ነው። በወንጌል ሉቃስ ፭ ፴፮ በምሳሌ ይላቸው ነበር ማንም ያዲስ ልብስ ቁራጭ ባሮጌ ልብስ አይጥፍም ያለዚያ አዲሱን ይቀደዋል። አዲሱም ቁራጭ ላሮጌው አይስማማውም የሚለውን መመልከት ነው። ያረብ አገር ፊደልና የኢትዮጵያ ፊደል ምን አገናኛቸው ትንሽ ለወጥ አለ ተብሎ የተጻፈው ትንሽ አለ የተባለው በምን አኳኋን ነው። ይህን ነገር ከማውራት ሳይነገር በቀረ የተሻለ ነበር። የኢትዮጵያና የዓረብ ፊደል በማነኛውም ዓየንት ሊጐራበት

# ፋ ረቡዕ

ሊመሳሰል ሊወራረስ አይችልም ከንቱ ነው። የዓረብ ፊደል የሚዠምር በአ ነው ሲጻፍም ከቀኝ እጅ ወደ ግራ እጅ ነው። የኢትዮጵያ ፊደል የሚዠምረው በሀ ሲጻፍም ከግራ ወደ ቀኝ እጅ ነው። አናጋሪም የለውም በ፯ት ትቅጥሎች ብቻ ራሱን ችሎ የሚሄድ ነው። ሁለቱን ፊደሎች ምን አገናኛቸውና ዓረብኛው ፊደል ትንሽ ለወጥ ብሎ ግዕዝ ሆነ ብሎ መጻፍ ከፍ ያለ ሐሳዊነት ነው። ይህ ሥራ በወንጌላዊ ቦታ ለቆመ ሰው በጣም አሳፋሪ ነገር ነው። ግን ኀፍረትን ማን ቢአውቀው ነው። ባባ ጋስፓሪን አሳብ በ፻፫ና በ፻፳ ገጽ የተሠራውን አታላይነት ሰው አላወቀብኝም በማለት ነው። እኛ ግን አላጣነውም አውቀነዋል። ይህን ያህል የጥንታዊውን ፊደሎች መልክ በያይነታቸው እየተሻሻሉ እንደመጡ የመጡበትን አኳኋን የሚነግር ጽሑፍ እኛም እናገኛለን በ፻፫ኛና በ፻፳ኛ የተጻፉ የኢትዮጵያ ጥንታውያን ፊደሎች ወደ ግራ እያዞራችሁ የጻፋችሁትን ሥራ ጉዳዩን አግኝተነዋል። እንደዚህ ያለውን የጽሑፍ ማታለያ ሥራ መሥራታችሁ በዚህም ሙያችሁ የሠራችሁት ይህ ብቻ አለመሆኑን ልባችሁ ያውቀዋል የኢትዮጵያ ቋንቋ ግሥ ሲሠራ የመዠመሪያውንና የመጨረሻውን ፊደል ጠብቆ ነው። የሌላው አገር ሁሉ ፊደል የመዠመሪያውን ፊደል ብቻ እየጠበቀ ነው። የሮማውያን ስብከት በኢትዮጵያ ስለተስፋፋ የኢትዮጵያን ፊደል በአ ይዠምራል እያሉ በአ እየዠመሩ በፐ እየጨረሱ ሰዎች ይገኛሉ። ሰዎቹም አቶ ኪዳነ ወልድ ክፍሌና አባ ገብረ ኢየሱስ ኃይሉ ናቸው። ይህ በአ ዠምሮ መጻፍ ከሮማ ልዑካን ምንጭ የተገኘ ነው እንጅ ከሌላ እንደዚህ ሜዳዊ ሥራ እብራይስጡንም የግዕዙንም የፊደል ቁጥር ያፋለሰ የለም። ግዕዝንና እብራይስጥ የፊደል ቁጥር የዓለም ባለታርኮች ጽፈውት የሚገኘውን እነዚህ ሰዎች ሠርዘውት ይገኛል። ይህንም በአ የሚዠመረውን ፊደልና የግሥ አካሄድ እንደ ኢትዮጵያው ግሥ በመዠመሪያና በመጨረሻው ፊደል

መጠበቁ ቀርቶ እንደ ውጭ አገር ሰዎች በመዠመሪያው ፊደል እያደረጉ የሚጽፉ መሠረቱን የሚለቁ ሰዎች በርክተዋል። ይህንም ሥራ ለሌላ ይቆይና የዜና ቤተ መንግሥት ማሰናጃ ሹም የነበሩት ብላታ መርስዔ ኃዘን ወ. ቂ እንኳ ይህን አበገደ በሚባል ፊደል ተስማምተውበት እንደነበረ ያማርኛ ሰዋሰው ብለው በሰየሙት መጽሐፍ (በ፳ኛው ገጽ ፴ኛው መስመር የፊደላት ተራ በሚል አርእስት

ይህ ሰዋሰው የተጻፈው ተለምዶ በቈየ ሀ ለ ሐ መ በሚለው ተራ ነው ነገር ግን አ በ ገ ደ በሚል ተራ እንዲነገር አሳባቸውን ያቀረቡ ሊቃውንቶች አሉ። ይኸውም አ በ ገ ደ የፊደል ጥንታዊ መደቡ ስለሆነ። የተወደደና የተመሰገነ አሳብ ነው። ስለ ፊደላት ሥርዓት ከደራሲው የተጀመረ ጽሕፈት ነበረ። ይሁን እንጅ ባሁኑ መጽሐፍ ለመጨረስ ስላደረሰ ቆይቷል። ስለ ፊደላት ሥርዓት ሊቁ አልቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የጻፉትን መጽሐፍ መመልከት አስፈላጊ መሆኑን ለአስተማሪዎቹ እናስገነዝባለን ይላል) ብላታ መርስዔ ካስተማሪዎቹ የተስማሙባቸው ጉዳዮች እነዚህ ናቸው ፩ኛ ቋንቋ አስተማሪዎቹ የግዕዝ ስለማይወዱ ብላታም የግዕዝ ማሳሳቻ ያማርኛ ሰዋሰውን ስለአሳተሙላቸው። ፪ኛ አበገደ የሚባለውን ፊደል ስለወደዱላቸው። ፫ኛ አ በ ገ ደ የሚባለውን ፊደል ሥነ ሥርዓት መመልከት አስፈላጊ

መሆኑን ለአስተማሪዎች እናስገነዝባለን ብለው ስለጻፉላቸው ነው። በዚህ ሥራ የኢትዮጵያ ወጣቶች ጥቅም ሳይጐድልባቸው አልቀረም። በጥብቅ

## ፊ ኃሙስ

የሀገራቸውን ሰዋሰው በጣም ተምረው ቢሆን የውጭ አገር ቋንቋም ከ፫ና ካ፬ ዓመት አያሳልፉትም ነበር። በዚያ ላይ የሀገራቸውን ጥንታውያኑ መጻሕፍቶች ባገኙ ጊዜ ለማንበብና ያገራቸውን ታሪክ ለማወቅ በቻሉ ነበር። ስለዚህም ግርማዊ ጃንሆይ በብሩህ ልቦናቸው አስበው የወጣቶቹ አእምሮ እይሰፋ የሚሄድበትን ምንገድ በተፈሪ መኰንን ቀለቡንም አደራጅተው እንዳስቀመጡ ይገኛል። ግን ተማሪዎቹ ግዕዙን ስለማይፈቅዱ በትምርት መፈተኛው ሊስት ላይ ግዕዝን ሳይገቡት ስለቀረ ወጣቶቹ ለጊዜው ፈተና የሚጠየቁበትን በማጥናት ነው። አስተማሪዎችም ግዕዝን ያላገቡበት ምክንያት በማጥናት ነው። አስተማሪዎችም ግዕዝን ያላገቡበት ምክንያት አላቸው። እሱም በግዕዙ የብላታ መርሥዔን ያምርኛ ሰዋሰው ስላገቡ ነው። ይህ ቀስ በቀስ እየሰረሰሩ የኢትዮጵያን ታሪክ ለማጥፋት የሚሠሩት ዘዴ ነው። ብላታ መሥርዔ ላስተማሪዎች ተስፋ የሰጡት መጽሐፍ ዛሬ በመታተም ላይ ይገኛል እንደዚህ እየሆነ የኢትዮጵያ መሠረት እየተሸረፈ ሲሄድ ይታያል። ስለዚህ ግዕዝን መሠረት ግሥ በቀላሉ አሳያለሁ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ለሀሀ | ቀዳ | እርባ ግሥ | |
| ለኀልሀ | ነከረ | ቀተለ | ገደለ የሩቅ ወንድ |
| ለምሐ | ለማ | ይቀትል | ይገድላል |
| ለስሐ | አልጫ ሆነ | ይቅትል | ይገድል ዘንድ |
| | ይቀትል | ይገድላል | |
| ለቅሐ | አበደረ | ቀቲል ቀቲሎት | መግደለ |
| ለብሐ | ሠራ | ቀታሊ | የገደለ |
| ለትሐ | ተጐነጨ | ቀታልያን | የገደሉ ብዙዎች |
| ለጥሐ | ገበረ | ቀታሊት | የገደለች ሴት |

የኢትዮጵያ ቋንቋ ከዓለም የተለየ ነው። መዠመሪያ መጽሐፈ ሰዋሰው ክፍሉ በጠቅላላ ፬ ነው ከነዚሁ ፩ኛው እርባ ቅምር ነው ብላታ መርሥዔ ጻፍሑ የሚሉ ቢጠቅምም ባይጠቅምም በዚህ ከእርባ ቅምር ማለት ነበር።

፪ኛው እርባ ግሥ ነው። ያማርኛው መሠረት የሚገኝ በዚህ በእርባ ግሥ ነበር ማለት ከወርና ከብር በፊት የጥበብ ነገር ሲሆን አስቀድሞ ሰሙ ይሠራና ከተቀረጸ በኋላ በቦካ ጫካ ይሸፈናል። ባ፩ድ ጐን ሥረቁት ይቀርለታል። ያነን ፀሐይ ይሞቀውና ሲደርቅ ወደ እሳት ሲገባ ያ ሰም ቀልጦ ሲወጣ በሰሙ ቦታ ወርቁ ወይም ብሩ ገብቶ ልክ ሆኖ ይገኛል። እንደዚሁም ግዕዙና አማርኛው ግዕዙ እንደሰም መሠረት ካልሆነለት አማርኛው ብቻውን ያለ ግዕዙ ጥቅም ሊሰጥ ባለ መቻሉ ወጣቶቹ ከመሠረተ ቋንቋቸው ሳይናገሩ ቀሩ። ከእርስት እንደመነቀል ነው። ፫ኛው ታላቅ ክፍል ነጠላ ግሥ ዘርና ነባር። ከላይ እንደተጻፈው የመዠመሪያውንና የመጨረሻውን ፊደል ጠብቆ የሚገኘው ነው። ፬ኛ ታላቅ ዐቢይ አገባብ ነው። ፭ኛ የኢትዮጵያ ግሥ በ፴ ሠራዊት እየተዘረዘረ የሚሄድ የሩቁን ወንድና የቅርቡን ወንድ እየለየ። ፪ኛ የሩቆቹን ወንዶችና የቅርቦቹን ወንዶች እየለየ ፫ኛ የሩቂቱንና የቅርቢቱን ሴት እየለየ

# ፍ ዓርብ

፬ኛ የሩቆቹን ሴቶችና የቅርቦቹን ሴቶች እየለየ።

፭ኛ አነ ያለውንና ንሕነ የሚሉትን እየለየ። ፲ሩም ለየራሴቸው ፬ ፬ አንቀጽ አላቸው ፬ ጊዜ ፲ ፻ የተባለው ይህ ነው። ከነዚሁ ባ፩ዱ ዘርዝሮ ማሳየት

፩ኛ አእመረ አወቀ ፪ኛ የአምር ያውቃል

፫ኛ ያእምር ያውቅ ዘንድ

፬ኛ ያእምር። ይወቅ ሲል እነ ዚህ ፲ሩ ሠራዊት ፻ ሠራዊት እየሆነ ይፈጽማል ምናልባት ፲ር ሠራዊት የተባሉትን በጥብቅ ማስተዋል አለ። እነዚህም ከላይም እንደ ተጻፈውም ፩ኛ በሩቅ ያለው ወንድ

፪ኛ በሩቅ ያለችቱ ሴት ፫ኛ በቅርብ ያለው ወንድ።

፬ኛ የቅርቢቱ ሴት ፭ኛ በሩቅ ያሉ ወንዶች።

፮ኛ በሩቅ ያሉ ሴቶች ፯ኛ በቅርብ ያሉ ወንዶች።

፰ኛ በቅርብ ያሉ ሴቶች ፱ኛ ራሱ አነ የሚለው።

፲ኛ ሁለት ሆነው ንሕነ የሚሉ እነዚህ ናቸው ፲ሩን ባ፬ት አብዝቶ ፻ ይሆናል እንደዚህ በየሠራዊቱ ሲዘረዘር ፲ሩ ፻ ፳ያው ፼ንያ። እየሆነ ይሄዳል። እንደዚህ ሲሆን አገባቡም ሁሉ ለ፲ ፲ አገባብ አላቸው ይህም ከዚህ የሚከተለው ነው።

፩ኛ የሩቁን ወንድ አእመርናሁ ፪ኛ የሩቂቱን ሴት አእመርናሃ

፫ኛ የቅርቡን ወንድ አእመርናሁ ፬ኛ የቅርቢቱን ሴት አእመርናሃ

፭ኛ የሩቆችን ወንዶች አእምርናሆሙ ፮ኛ የሩቆቹን ሴቶች አእመርናሆን

፯ የቅርቦችን ወንዶች አእመርናክሙ።

፰ኛ የቅርቦችን ሴ አእመርናክን ፱ኛ አነ ያለወ አእሚር ፲ ንሕነ ያለው አእሚረነ። አሥር ናቸው እንደዚህ እየሆነ በትክክለኛ መሠረት እየታነጸ የመጣውን ባባቶቻችን ብርታት የቆየንን ሁሉም የየህገሩን ያባቱን ታሪክ ሲአከብር ስናይ እኛ በጠላት ምክር እየተታለልን ያባቶቻችንን መሠረት ለማጥፋት ስንጣጣር እንታያለን። ስለዚህ ማስረጃውም ከብላታ መርሥዔ ወ. ቂ. ስለ ፊደላት ማሻሻል በሚል አርስት አማርኛ ሰዋሰው በ፱ነኛው ገጽ ባ፲፮ኛው መሥመር ላይ ፊደል የቋንቋ መሣሪያ ነው። መሣሪያ በየጊዜው እንዲስል እንዲሰነገ ፊደልም ለማሻሻል ከብዙ ሊቃውንት ልዩ ልዩ አሳቦች ቀርበዋል የሁሉም አሳብ በአናጋሪ ፊደል። (በዋየል)። ይነገር በማለት የተባበረ ሆኗል። ሀ መደቡ ግዕዝ ወይም ሳድስ ሆኖ በ አ ፊደል አናጋሪነት እንዲነበብ አሳብ ያቀረቡ አሉ። ደግሞ በአ ፊደልና በተመደቡ በሌሎች ፊደላት አናጋሪነት እንዲነበቡ የወሰኑ አሉ። የሁሉም አሳብ የተመሰገነ ነው። ይኸውም ሲሆን የፊደላቱ ቅርጽ ሀ ለ ሐ መ ወይም አ በ ገ ደ በሚለው ቅርጽ እንዲጸና ወስነዋል። ለ በአናጋሪ ፊደል እንዲነበብ አስፈላጊ ከሆነ ፊደሉም ባዲስ ሥርዓት መጻፉ ታልቀረ ለሥራ እንዲቀና የላቲኑን ፊደል እንቀበለው ብለው የሚመኙ አሉ)። ብለው ይህን መልካም ምኞት ለወጣቶቹ በቶሎ ለማስተላለፍ አስበው በዚህ መጽሐፈ ሰዋሰው በተባለው ጽሑፋቸው አስፋፍተው ዘርተውታል። ይህን

# ፎ ቀዳም

ጽሑፍ ለወጣቶቹ መዝራታቸው የኢትዮጵያ ጥንታዊ ፊደል እንዲጠፋ አስተዋሽ ሆነው ሲገኙ ይህ አሳብ ከማን የመነጨ መሆኑን ማወቅ ያስፈልጋል እንደዚሁ ሁሉም ፩ድ ፩ድ ጥቅም ባገኘበት ለጠላት ሲረዳና ሲአስተካክል የሚገኘውን ብላታ መርሥዔ ኃዘን ወ. ቂ. የላቲኑን ፊደል እንቀበለው ብለው የሚመኙ አሉ ብለው ያለ ኀፍረት የጻፉትን ያስረዳል። እሳቸው የተመለከቱ የለቱን ጥቅም ነው እንጅ በጥንታውያን መጻሕፍት ውስጥ የሚገኘው የኛ ድጋፍ የሚሆን ይዞ መገኘቱን አልተገነዘቡም። ስለዚህ በሀገራችን ፩ድ ተረት አለ ብለህ ያሙቱን ሞኝ የለቱን የሚሉ ብላታም ብልህ ስለሆኑ የለቱን ተመልክተው በወጣቶቹ ልብ እንደዚህ ያለ ያልሆነ ዘር በተንኑበት። በዚህ አስተያየት ባባ ጋስፓሪን ላይ ፍርዱ ቀሊል ነው። የኢትዮጵያ ፊደል ለተክኒክ ጽሑፍ የሚመች አይደለም በማለት ምክንያት ነው። ይህ የኢትዮጵያ ፊደል ይቆረጥ ይቀጠል ለመባል የደረሰው እርግጥ ለዚህም ከሆነ የኢትዮጵያን ጥንታውያኑን ጽሑፎች በሚአቀላጥፍ የቁጥር ትርጓሜ የሚሰጡ ፊደሎች ይገኙ አልነበረምን ስለቁጥርስ ዜሮ የሚባለው አስቀድሞ መሠረቱ በኢትዮጵያ መሆኑን የሚአስረዳ ጥንታዊ ጽሑፍ ዜሮ ያለበት የሥራውም አኳኋን እንደዚህ እየሆነ በጥንታውያኑ መጻሕፍት ይገኛል። ይህን ማን ይከተላል ማን ያስፋፋል። ለተክኒክም እንደሚመቹ የሆኑ የፊደላት ቅርጽ ከየገዳማቱ ስመረምር አግኝተ ነበር እነዚህ ፊደሎች እንደዚህ ሆነው ስላገኋቸው ክቡር አቶ አበበ ረታም በሽ፱፻፵ ዓ.ም ስለ ፊደል መሻሻል ጉባዔ ተዠምሮ በነበረ ጊዜ ያቀረቡት ሃሳብ ከነዚህ የሚገጥም መሆኑን የፊደል ማሻሻል በተባለው መጽሐፍ (በ፲፫ኛው ገጽ ስለ ፫ኛው አካሄድ የፊደል ማሻሻያ የሚል አርስት ውስጥ ካቶ አበበ ረታ የቀረበ አሳብ አስተያየት ነው። ይህ አካሄድ በ፳፩ በዘይብሎች የሚሆኑ ፊደላት ግዕዝ ግዕዞች ናቸው በነርሱም ላይ ምልክት ሳይታከልባቸው የግዕዝ ድምፃቸውን እንደያዙ ይገኛሉ ሀ አ ካሁን በፊት እንደተነገረው ገጽ ፲፬ እይ ኸ አ በሚአሰኝ ድምፅ ይነገራሉ። የሚጠብቁም ቃላት በደጊም ይጻፋሉ ፳፩ ዘይብሎች ሀ ለ እመ ረ ሰ ቀ በ ተ ነ አ ከ ወ ዘ የ

ደ ገ ጠ ጰ ጸ ፈ ፐ ፳፩ የተባሉ ሐ ሠ ኀ ዐ ፀ እነዚህ ስለወጡ ነው ፯ቱ የድምጽ መስጫ ምልክቶች ካዕብ ሣልስ ራብዕ ኃምስ ሳብዕ ናቸው)።

ምሳሌውን የፊደሎች መልክ አባ ሰላማ በተማረበት ፊደል እይ እንደዚህ እየሆነ በዲቃላዎችም ፊደሎች ከራሳቸው የሚደፉ ቀጸላ እየተደረገ በማለት ያቀረቡት ሃሳብ አሁንም ቢሆን ካ፳ቱ ፊደሎች መጉደል በተቀር ካ፳፯ቱ ፊደላት ላይ ፯ ምልክቶች ሲጨመሩ ለዲቃላ ፊደሎች ፪ት ፩ድ ከላይ ፩ድ ከግርጌ የሚሆን ፳፯ና ፰ ፴፬ ይሆናል በነዚህ ይልቁንስ ከዓለም የበለጠ ቅልጥፍና ያገኜ እንዲሆን ኢትዮጵያ መሠረቷንም ሳትለቅ ከሥራውም ወደኋላ እንዳትቀር እንደዚህ ያለ መልካም አሳብ ሳገኝ እስማማለሁ። እንደ ብላታ መርሥዔ አሳብ ግን የኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ፊደል ፩ዲቱ ስትጐድል ሳይ ልክ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላም እንደጠፋችብኝ ነው የምቆጥረው ማለት የዓላማ ምልክት ዋናው ፊደል ነው። የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሳይለወጥ የኖረ መሆኑን የሚመሰክርልን ዛሬ የሚታየው ፫ት ዓየንት ጨርቅ ብቻ አይደለም። ዋናው የሰንደቅ ዓላማችንና የነጻነታችን ምስክር ዋና ማስረጃችን ፊደላችንና ቋንቋችን ከካንም ዠምሮ ከ፪ሽ፯፻፯ ዓ. ዓለም እስከ ዛሬ ፬ሽ፳፻ ፵ ዘመን በላይ

# ፐ እጐድ

የቆየች መንግሥት መሆንዋን የሚአስረዳ ይህ ፊደላችንና ቋንቋችን ነው ፪ኛ የኢትዮጵያ ግዛትና ቅኝ አገሯ የነበረውን ሁሉ ለማስረዳት ለማስታወቅ የሚችለው ይህ ፊደላችንና ቋንቋችን ነው። ፫ኛ የኢትዮጵያ ነገሥታት ከተማና ዕቃ ማስቀመጫ የነበረውን የሚአመለክተን። ይህ ፊደላችንና ቋንቋችን ነው። ፬ኛ የሀገራችንን ወሰንና የዘራችንን ሐረግ የሚነግረን ይህ ፊደል ቋንቋችን ነው። ይህን ሁሉ ጥቅም በውስጡ እንዳለ ተመልክተው የኛን አላዋቂነት ገምተው

ፊደላችንን ቋንቋችን ለመቀማት ተደራጅተው። ይኸውና ፬፻ ዘመን ሙሉ የሚዘረዘሩት የፖለቲክ ዘር ፍሬ ለመያዝ አበባ ሆኖ በብላታ መርሥዔ ላይ የሚታየውን ከጽሑፋቸው ላይ የተገለጸው አሳባቸው ከወዴት የመጣ ባቶ ከበደ ሚካኤል አማካይነት በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ሲታተም ይገኛል። ማነኛውንም እሱ ያስረዳል እስከዚህ ድረስ ያለውን ሐተታ ያመጣብን (በ፵፮ ገጽ ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ ነው። ባ፳ኛው (መስመር እነዚህም አስቀድመው ከዕሥያ የመጡ የካም ወገን የሆኑ የኩሽ ዘሮች ከግብጽና ከሜሮዔ ጋር የተስማማ ቢለንን በመሰለ ልዩ ቋንቋ ይነጋገሩ ነበር። ይኸውም ቋንቋ እስካሁን ድረስ ቢለንና ቅማንት አገውም የተባሉ ሕዝቦች ሲነጋገሩበት ይታያሉ ገጽ ፴፮ ፴ ፴፰ ተመልከቱ ይላሉ)። እንግዲህ የኢትዮጵያውያን ቋንቋ ቢለንና ቅማንት አገው የሚነጋገርበት ማለት ነው። ግዕዝማ የዓረቦች እንደነበረ ዘወትር ማስረጃው እንደተንጐደጐደ ነው። (አግዓዝያን የተባሉ የዮቅጣን ልጆች ግዕዙን ይዘው ከመጡ በኋላ ግን ኢትዮጵያን ጠቅለው ስለያዙ ይህን ቢለን የተባለውን ቋንቋ እያደከሙ ግዕዝ የተባለውን ያማረ ቋንቋ አስፋፍተው ያዙ። ለዚህም ግዕዝ በተባለው ትልቅ ቋንቋ ሐሳባቸውንና ጉዳያቸውን እየገለጡና እየፈጸሙ ሕጋቸውንና ዓዋጃቸውን በዚሁ ግዕዝ እየጻፉ ይመዘግቡ ነበር። ይኸውም የግዕዝ ቋንቋ ሰፊ ቋንቋ ሆኖ በመገኘቱ ለኢትዮጵያ ከፍ ያለ የሥልጣኔ ደረጃ ሆኖ ለመላው ዓለም ሕዝብ ሁሉ አመለከተላት። ይህ ግዕዝ የተባለው የሳባውያን ቋንቋ ከዚህ በላይ አስቀድመን እንዳመለከትነው ጥንተ ነገሩ ከባቢሎናውያንና ከፊንቃውያን ከእብራይስጥና ከዓረቢኛ በጣም የተስማማና የተቀራረበ ቋንቋ ነበረ አግዓዝያንና ሐበሳት የተባሉ ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ይዘውት ከገቡ በኋላ የጥንቱ ተለውጦ ግዕዝ ተብሎ ተሠየመ) ይላሉ። እዚህ ከፍ ያለ ምርምር ይደረጋል ሐበሳት የተባሉ ሳብውያን ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ በኋላ የሚለው ቃል የሚመረመር ነው (በ፴፫ኛው ገጽ ባ፲፯ኛው መስመር እኒህ ከዓረብ አገር ተነሥተው ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ሕዝቦች ሁሉ የሴም ነገዶች ሲሆኑ በየጊዜው የመጡ ናቸው እንጅ

ሁሉም የሴም ነገዶች ሲሆኑ በየጊዜው የመጡ ናቸው እንጅ ሁሉም ፩ድ ላይ ተያይዘው አልመጡም። ከነዚህም መዠመሪያ የመጡት ሐበሳት የተባሉ የሐበስ ልጆች ናቸው። እነሱም በየጊዜአቸው መጥተው ጥቂት ጊዜ ላይኛውን ኢትዮጵያ ገዝተዋል ከነዚህም ከሐበሳት በኋላ በዓረብ በኩል ይኖሩ የነበሩ ሳባ ውባል ኦፊር የተባሉት ፫ት የዩቅጣን ልጆች ወደ ኢትዮጵያ ገቡ ይላል)። እንግዲህ በዚህ ጽሑፍ እንደሚለው ከዮቅጣን ልጆች በፊት ሐበስ የሚባል የሴም ዘር ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ነግሦ ነበር ይላል እንግዲህ ከዮቅጣን ልጆች በፊት የሴም ዘር ሐበስ የሚባል ከምን ጽሑፍ ይገኛል። እውነተኛውንስ ትውልድ ባመለክትዎ ይሻላል ሐበሲ ዓረብ ሐማሲ ጐዚ ሴዊ የሚባሉት ሁሉ የኩሳ ልጆች ናቸው። ሐበሲ

## ፑ ሰኑይ

የሚባለው የኩሳ ዘር ስለሆነ ስሙ የሚጠራበት ምክንያት ስለዚህ ሳባውያን የሚባሉም የካም ዘሮች ናቸው። ሳባ የምትባል ንግሥት በራግው ዘመን እንደነበረች መጽሐፍ ቀሌምንጦስ ይናገራል ብየ ከላይ አመልክቻለሁ። ደግሞ የሚሉት ቢአጡ ከዮቅጣን በፊት ሐበስ የሚባል የሴም ዘር መጥቶ ነበር ማለት በውቅያኖስ ባሕር ላይ እርሻ ታርሶ እህል ተዘራ በቀለ ታጨደ ተወቃ ማለት ነው። ወደ "፵፮ኛው ገጽ በ፳፫ኛው መስመር በዚያን ጊዜ እነርሱ በነበሩበት ዘመን ወረቀትና ብራና አውጥቶ መጻፍ ያልተለመደ ስለሆነ ለዘላለም ነዋሪ ሆኖ በማይጠፋ በተጠረበ ሐውልትና በትክል ድንጊያ ላይ እየተቀረጹ ሕጋቸውንና በተጠረበ ይመዘግቡ ነበር ይላል" የዓምድ ማባዣ የተደረደረው ሁሉ እውነት ይመስላል ዛሬም በተጠረበ ድንጋይ ላይ ታሪክ እየተጻፈ የሚቀመጠው ብራና ጠፍቶ ነው መሰለኝ የኛ እውነተኛ። ደግሞ ወደ ፵፺ኛው ገጽ ላይ ባ፩ኛው መስመር ዠምረን ያባ ጋስፓሪን ውሸት እንደረድራለን። "ወጣቶት ወጣት ለሆኑ ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ያገራቸውን ታሪክና ልማድ የሚያስረዳና የሚአስጠና እንዲሆን ቀደምት የሆኑ የአክሡም ነገሥታት በሳባዊና በግዕዝ በጽርዕ ቋንቋ በድንጋይ ላይ ቀርጸው ያቆዩአቸውን ቅርጾችና ጽሑፎች

ወደፊት በሚገኘው ታሪካችን ሥዕላቸውን አሳይተን ትርጉማቸውን እንገልጻለን" ይህ ሥዕላቸውን አሳይተን ትርጉማቸውን እንገልጻለን የተባለው እውነት ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የውቅያኖስ ባሕር ጨው መሆኑን ተወ ማለት የተሻለ ነው። ባለታሪኮች እንደሚአውቁት በሳባዊ ቋንቋ የተቀረጹ የትክል ድንጊያና ሐውልቶቹ ግን በአክሡም ሐውልቶች ላይ ተቀርጸው እስካሁን ይገኛሉ።" እውነቱን ደፍረው እንዳይናገሩ ከእውነት ጋራ ጥለኞች ስለሆኑ እየቸገራቸው በግዕዝ ፊደል የተጻፉ ሐውልቶች በዓረብ አገሮች ላይ መኖራቸው ከተናገሩ በኋላ ደግሞ መልሰው ግዕዝ የሚባለው ፊደል መሠረቱ ዓረብ ነው እያሉ የማይመስል ሲጽፉ ይገኛሉ። አባ ጋስፓሪን ሆነ ብለው የተነሡበት ዋናው ዓላማቸው ሐሰቱን እውነት ለማስመሰል ስለሆነ እኔ የማዝነው ሳይመረመሩ ይዘውት ለሚኖሩ ሰዎች ነው።

"ባ፵፺ኛው ገጽ ፺ኛ ወደ ኢትዮጵያ ገብተው የተቀመጡት ሳባውያን በዓረብ ደቡብ አገር ከሚኖሩ ሳባውያን ነገሥታት ነጻ ወጥተው ለነሱ መገበራቸው እንዴት እንደ ቀረ የሚናገር።" እንግዴህ ይኸ ሁሉ አምድ ይዞ ሲደረደር ሲታይ ላላወቀ ሰው የታሪክ ዓምድ የያዙ ይመስለዋል አሁን ከላይ አርስት ሆኖ የተጻፈው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሳባውያን በዓረብ ደቡብ ከሚኖሩ ሳባውያን ነገሥታት ነጻ እንደወጡ ተብሎ ሲሳፍ እንደ አዠማመሩ ፩ድ ማስረጃ የሚቀርብ ያለው ይመስላል (ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ከተቀመጡ በኋላ ሳባውያን የተባሉ የዓረብ ደቡብ ነገሥታት በነርሱ ስም ሆነው ግብር እያወጡ አዲሲቱን ኢትዮጵያ አገራቸውን የሚአስተዳድሩ እንደራሴዎች ከነዚያም ከነዚህም መርጠው ሾሙ። እነዚህንም ሹማምንቶች ግብር አስወጭዎች እንደማለት በሳባውያን ደንብ በጥንታዊ ቋንቋ ትርጉም ግብር አስወጭ ማለት ነው። እነዚህም በኢትዮጵያ ላይ ነጋሢ ነጋሢ ተብለው የተሾሙት ግብር አስወጭዎች በመላዋ ኢትዮጵያ ስለተሾሙ እጅግ ብዙዎች ነበሩ። ለዓረብ ሳባውያን መገበራቸውን ትተው ራሳቸውን

## ፒ ሡሉስ

ችለው ኢትዮጵያን ለማስተዳደር በቁ ከዓረብ ሳባውያንም መገዛት ነጻ ወጡ (እስቲ ፩ድ መረጃ) (ይህም ከሆነ በኋላ እነዚህ ነጋሢ ተብለው ኢትዮጵያን ያስተዳድሯት የነበሩ ሹማምንቶች ኃይልና ብርታት ሥልጣንና ጉልበት እያገኙ ስለሄዱ በየጊዜው ከሚገጥማቸው የውጭ አገር ጠላት እየተዋጉ ድልን ያገኙ ነበር። ይልቁንም ቀይ ባሕርን ተሻግረው ጥንት ሲገዟቸው ከነበሩት ከዓረብ ሳባውያን ጋራ ተዋግተው ጠላቶቻቸውን ድል ነሥተው የዓረብ ደቡብን አገር ለመግዛት ቻሉ። ወዲያውም ኢትዮጵያውያን የሆኑትን ሹማምንቶች መርጠው በዓረብ ሳባውያን ላይ ሹመው ግብር ማስወጣትና አገሩንም መግዛት ዠመሩ) አሁን ከላይ ያለውን ሁሉ የጻፍሑት ያባ ጋስፓሪንን ፖለቲክ ሲነበብ ሰው ሁሉ እንዲለምደው በማለት ነው እንጅ ነገሩ ፍሬ ያለበት ሆኖ አይደለም። መቸም ፍሬና ገለባ ላይ እኩል ሆነው አይገኙም ማለት ገለባ ትልቅ ፍሬ ግን ላይን ከገለባ ጋር ለማመዛዘን በምንም በምን እያባዙ የጽሑፍ ዓምድ የሚአበዙ አሉ። አባ ጋስፓሪንም ነገሩን ለማደናገር ፩ድ ነገር ያመጡና ኢትዮጵያ ነጻ ወጣች ይሉና ደግሞ መልሰው ኢትዮጵያ ዓረቦችን ትገዛ ነበር እያሉ ይጽፋሉ። እንግዲህ ለሁለቱም መሰከሩ ማለት ነው። ይህ ሁሉ ድካም የደረሰባቸው ለወደፊቱ አሳባቸው ደጋፊ የሚሆኑ ነገሮች አደራጅተው ለመጭው ትውልድ ደረጃ አሲዘው ለማቆየት ነው። ፩ኛ ኢትዮጵያ በነጻነቷ የኖረች ሀገር ናት እያለ በውጭ ሰው ሳይቀር ስለሚመሰከር የኢትዮጵያ ወጣቶችም ይህን ተከትለው እስከ ዛሬ በነጻነቷ የኖረችቱን አገራችንን በኛ ጊዜ ሞት ፈርተን ንጉሠ ነገሥታችንንና ሰንደቅ ዓላማችን አናስደፍርም ብለው ቆራጥ በሆነ ልቡና የሚገኙትን ልብ ለመከፈል ለመቀነስ በሐሰትና በቅጥፈት ነጻነቷ ተሰብሮ ነበር እያሉ ያለፍርሃት ያለኀፍረት ይጽፋሉ። ፪ኛው በማነኛውም ጉዳይ የልዑል እግዚአብሔርም የረቂቅ ምሥጢር መግለጫ እንዲሆን መጻሕፍተ ብሉያትንና ጽላተ ሙሴን ከኢየሩሳሌም አምጥተው በረቂቅ ረድኤቱ አካብቶ ጽላተ ሙሴ ከመጣች እንኳ ፪ሽ፱፻፷፪ ዘመን ማለት ነው። ግዕዝ እንዳለ ሳይለወጥ ስለኖረ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ዋና ማስረጃ የሚሆኑ ነገሮች በምሥጢር እየተገለጹ ፊደሎቹ የምሥጢር ትርጓሜ መግለጫ ሆነው በመላው የዓለም ሊቃውንት ዘንድ ተመስግነው

የሚገኙ ስለሆኑ ይህን  ግዕዝ ሌላ መሠረት እናብጅለት በማለት የደቡብ ዓረብ የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበረ እያመኑ ኢትዮጵያ በግዛቷ ላይ ያቆመችውን መታሰቢያ ከነጽሑፉ ቢገኝ ከላይ ተጽፎ እንደሚታየው ገዥ ሲአደርጉ የሚታዩት ግዕዝን በካም ዘመን መጥቶ ፬ሽ፫፻፵ ዘመን ያለውን ታላቁን ምሥጢር ትርጓሜ የሚገኝበትን ፊደል ግዕዝን ለመቀማት ያሰቡበት ነገሩ ረቂቅ ነው።

መጻሕፍቱ የተጻፉልን በግልጽ ብቻ ነው እንጅ በሥውርና በምሳሌ አይደሉም የሚል ሰው ቢገኝ ትንሽ ማስረጃዎች አቀርባለሁ። ፩ኛ ነቢዩ ኢሳይያስ ፳፱ ፲፩ ወይከውነክሙ ኵሉ ዝንቱ ነገር ከመ ነገረ መጽሐፈ ኅቱም። ወይሁብዎ መጽሐፈ ለብእሲ ዘየአምር መጽሐፈ ወይብልዎ አንብብ ዝንተ ወይብል ኢይክል አንብቦቶ እስመ ኅቱም ውእቱ ፲፪ ወይሁብዎ መጽሐፈ ለብእሲ ዘኢየአምር መጽሐፈ ወይብልዎ አንብብ

## ፓ ረቡዕ

ዘንተ ወይብል ኢየአምር መጽሐፈ ያለውን ማስተዋል ነው። ፪ኛ ዕዝራ ፫ኛው ፲፪ ፴፯ ወለከ ለባሕቲትከ ረሰየ ልዑል ከመ ታእምሮ ለዝንቱ ምሥጢር ፴፯ ወባሕቱ ጸሐፎ ውስተ መጽሐፍ ኵሎ ዘንተ ዘርኢከ ወሢም ውስተ መካን ኅቡዕ ፴፰ ወመሐሮሙ ለጠቢባን ሕዝብ ለእለ ተአምር ከመ ይክሀልዎ ዓቂቦቶ ውስተ ልቦሙ ለዝንቱ ምሥጢር ይላል ፫ኛ ማቴዎስ ፲፫ ፴፬ ወዘንተ ኵሎ ተናገረ ኢየሱስ በምሳሌ ለአሕዛብ

ወዘእንበለ ምሳሌሰ ኢተናገሮሙ ፴፱ ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ በነቢይ። እንዘ ይብል እከሥት በምሳሌ አፉየ ወእነግር ዘኅቡእ ዘእምትካት ያለውን ማስተዋል ነው። ከላይ እንደተጻፈው በምሥጢር ትርጓሜ እያደረጀ ለመስጠት የሚችለው በኢትዮጵያ የሚገኘው ግዕዝ መሆኑን ለመረዳት ፈላጊ ቢኖር ነገሥት ዜና መዋዕል ፱ ፩ ወንግሥተ ሳባ ሶበ ሰምዓት ዜናሁ ለሰሎሞን ወመጽአት ከመ ታምክሮ ለሰሎሞን በአስተማስሎ በኢየሩሳሌም በኃይል ጽኑዕ ያለውን ስንመለከተው እንደምን ያለ ትርጓሜ ሊሰጠን ይችላል። ፪ኛው ነገሥት ፲ ፩ ወመጽአት ትፍትኖ ምስለ ጥበብ ብሎ ነበር በ፪ኛው ከመ ታመክሮ ለሰሎሞን በአስተማስሎ ብሎ ጻፈላት። እንግዲህ ይህችን የአክሡም ንግሥት ዓረቦች የኛ ናት የሚሉበት ምክንያት የመጣው ትውልድ ስለማይዘነጋው ነው እንጅ ንግሥተ ሳባ ሳባስ በመልኳ ዓርብ አለ መሆኗን። ከሰሎሞን ጋር በተነጋገሩበት በኃልዩ ፩ ፭ ፮ የተጻፈው ያስረዳል። ዓረቦች በተገዥነታቸውና በዓረቦች አገር በሚገኘው መታሰቢያ ሁሉ ስሟን አጥንተው በዚህ ሰበብ የኛ ናት ቢሉም መኃልየ ሰሎሞን ሲተረጉምላቸው ልኩን ለማወቅ ይችላሉ አሁን ከላይ ያመጣነው ስለ ኢትዮጵያ ጥንታዊ ፊደል ምልክቱም የምሥጢር መነጋገሪያ መሆኑን ለመግለጽ ስለ ምሥጢራዊ ጽሑፍ ማስረጃ ከላይ የተጻፉትን ካሳየሁ በኋላ ለግዕዙ ፊደል ባለቤት ንግሥተ ሳባ የተጻፈውንም ማስታወስ ግድ ስለሆነብኝ እነዚህን ጥበቦች ምን ትርጓሜ ለመስጠት እንደሚቻል አባ ጋስፓሪንን ለመጠየቅ አስቤ ነበር። በኋላ ነገሩን አመዛዝኘ ብመለከተው ሮማ የተመሠረተችበትን ጊዜ አሰብሁና አለመቻላቸውን ተገንዝቤ መልሽ ተውሁት ለንግሥተ ሳባ የተጻፈውን የታሪክ ዘውድ ማንም እንደርሱ ያለ የታሪክ ዘውድ ለማሠራት የሚችል ባለፈው ዘመን አለመታየቱን ሳስታውስ ያለ ሥጋት ነው። የኢትዮጵያን ፊደል የሚአውቅ ያውቀዋል ያባ ጋስፓሪን አሳብ የጥንታውያኑን ፊደሎች ቅርጽ እየተመለከታችሁ የፈጠራችሁት ጽሑፍ ከቀኝ ወደ ግራ እያዞራችሁ እየጻፋችሁ የሠራችሁትን ረቂቅ ተንኮል በማይታወቅ የሠራን እየመሰላችሁ የሠራችሁት እንደ ባቢሎን ግምብ ፍርስርስ ብሎላችኋል። ከአባ ቤርሙዴዝ ዠምሮ እየተከታተሉ መጥተው የነበሩ ስንት ናቸው። የስማቸውን መዝገብ ታውቁት የለምን። ደግሞ ይህ ፖለቲካቸው እየተገለጠባቸው ከሀገር ውጡ ተብሎ ከታወጀባቸው በኋላ እየተደበቁ ሲገኙ በመንግሥት አደባባይ እየተፈረደባቸው የሞቱትን ሰዎች ቁጥር ታውቁት የለምን። ፬ኛ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ዋናው በርና ምንገድ ስለተጠበቀባቸው ዋና መንገድ ባልሆነው ዞረን እንገባለን ሲሉ ባረመኔዎች እጅ እየተገዘሩ

የሞቱትን ሰዎች ቁጥር አውቃችሁታል ይሆንን። የኢትዮጵያን ታሪክ እንጽፋለን ብሎ በከንቱ ከምንኩስና በላይ በዓለማዊ ታሪክ ገብቶ ከመዘብራረቅና የላዩን እታች የታቹን እላይ እያደረጉ ከማማሰል ከላይ እንደ

## ፔ ኃሙስ

ዘረዘርኩት ዓለምን እየተው መጥተው ይህ አደጋ ለደረሰባቸው አባቶቻቸሁ ወንድሞቻችሁ የጻፋችሁት ገድል እዚያው ውሥጥ ለውሥጥ ይሰማል እንጅ ወደ ሕዝቡ ሁሉ ለመግለጽ ስለማይወጣ የመንፈሳዊ ገድል ባይሆን እንኳ በሕይወታቸው ሳሉ ክብራቸው እንዳይገልጽ ይሠወራል እንጅ ካረፉ በኋላ ክብራቸውን ገድላቸውን መሠወር መልካም አልነበረም።

አሁንም የኢትዮጵያን ታሪክ አልጻፋችሁም ብሎ የሚአማችሁ የለምና የሚሆንላችሁ ከሆነስ የመንፈሳዊውን ሥራ ያባቶቻችሁን እያሳተማችሁ ብታቀርቡልን በውድ ዋጋ እየገዛን እያነበብን ያአባቶቻችሁ በረከት ተካፋይ ለመሆን በተቻለ ነበር። ስለ ታሪኩ የደከማችሁት ከንቱ ነው። (በ፺፱ነኛ ገጽ ባ፭ኛ መስመር ከዚህ በላይ እንደ ገለጽነው ኢትዮጵያ ከዓረብ ሳባውያን መገዛት ምንም ነጻ ብትወጣ ከዓረብ ሳባውያን ያመጣችውን ቋንቋ ሳትተው እስካሁን ድረስ ትኖራለች ይህም ግዕዝ የተባለው ቋንቋ

ምንም ጥቂት ከጥንታዊ ሳባውያን ቋንቋ የተለያየና የተለዋወጠ ቢሆን ይላል)። ይኸውና እዚህ ላይ እውነቱን ለመናገር ምንም ያህል አልቀራቸውም ነበር። ማለት የተለያዩና የተለዋወጠ ቢሆን ብለው ዝመር ካደረጉ በኋላ መልሰው ያው ጥንታዊው ያሳባውያን ቋንቋ መሆኑ የታወቀ ነው ብለዋል)። የተለያየና የተለዋወጠ መሆኑ ፩ድ ጊዜ ከታመነ ያው ጥንታዊው ቋንቋ የተባለው በምን ይታወቃል። የፊተኛውንና የኋለኛዪቱን ለይቶ ማሳየት ማስረዳት ላባ ጋስፓሪን ዋና ተግባር ነበር። ግን አባ ጋስፓሪን መንነው ሲመጡ የቅዱሳት መጻሕፍትን ነገር በጣም ያልመረመሩ ስለሆኑ እንዲያው ተላይ ተላይ ያለውን አጠራቅመው ባለው አቅማቸው ኢትዮጵያን ለመደገፍ አስበው ውለታዋን ሁሉ ለመመለስ ስለሆነ መቸም መሠረቱን በጣም ያላወቁት ሆነ በደቡብ ይገኝ የነበረውን ዛሬም በሐውልትና በገንዘብ ላይ የሚገኘውን የንግድ መሣሪያ ጽሑፍ ፊደል ቅርጽ ሁሉ የአረቦች እየመሰላቸው። ጥንታዊው ዓረብ ፊደል ጥንታዊው ግዕዝ ፊደል ለየብቻ መሆናቸውን ገና አልተመለከቱም። ግን ለወደፊቱም የሁለቱን ፊደሎች መሠረት ወደ ሥር ጠልቀው ቢመለከቱ ይልቁንስ በዚህ ምክንያት የብዙ ፊደሎች መልክ እንደምን እየሆነ መልኩ እየተሻሻለ እንደመጣ ያው የህገሩ ለምስክርነት የተቀመጠው ምስክር ሆኖ ለማስረዳት የሚቻልበትን ዘዴ ለማወቅ እንዲችሉ ነገሩ እሩቅ አልነበረም። ግን አባ ጋስፓሪን ዓለምን መነንኩ ብለው የመነኰስ ልብስ ለብሰው ቢታዩም ደግሞ ለሮማ መንግሥት ፕሮፓጋንዳ ባልደረብነት ሳይኖራቸው አይቀርምና ነገራቸው ሁለት እየሆነ ማስቸገሩ ስለዚህ ይመስለኛል። አሁንም ዋናው ያባ ጋስፓሪን አስተያየት የግዕዝን መሠረት ለደቡብ አገር ለመስጠት ነው። እኔ ደግሞ የምቃወምበት ዋናው ዓላማዬ ግዕዝ ከቋንቋ ለመለያየት በፊት ካም ይዞት እንድመጣ ከመንግሥቱ ጋር በኵሳ ቤት ሲያያዝ እስከ ዛሬ የደረሰ ስለሆነ። በማነኛውም ረገድ ግዕዝ ከዓለም ፊደል አኳኋን የተለየ መሆኑን በየጊዜው እየተሻሻለ እንደመጣ በየቦታው በሚገኙ ጽሑፎች መልክ ለማስረዳት ስለምችል ነው። በዚህ መካከል የኢትዮጵያ ፊደልም ወደ ውጭ የሚገኝባቸው ምክንያቶች ይገኛሉ። ፩ኛ ትገዛቸው በነበሩ አገሮች ላይ። ፪ኛ በንግድ ግንኙነት በነበራቸው አገሮች ላይ ቋንቋና ቋንቋ ጽሑፍና ጽሑፍ መለዋወጥ ከጥንት የቆየ ስለሆነ

## ፐ ዓርብ

ባንድ ጐን የውጭ ጽሑፍ እያደረጉ አስጽፈው ማስቀመጣቸው የራሳቸውም ሥራና ታሪክ በውጭ እንዲታወቅላቸ በማሰብ ነው። የኢትዮጵያ ፊደል ቅርጽ በጣም የተለየ የተጠበቀ አምላካዊ ምሥጢር የሚገኝበት ነው። ይህም በመጽሐፈ ሄኖክ በፀሐይና በጨረቃ ምንገድ ሲሰፈረበት ልክ ሆኖ በሚአስደንቅ አካሄድ በሰባቱ ፊደሎች ደረጃና በ፺ቱ ዕለታት እየተሰፈረ የሚሄድበትን የማይነቃነቅ ሐውልት የሆነ ማስረጃ መኖሩን አባ ጋስፓሪን ባያውቁት ነው እንጅ አውቀውት ቢሆን እንደዚህ ያለውን አሳብ ባልዠመሩትም ነበር። መዠመሩንማ የዠመሩት አባቶታቸው ወደ ኢትዮጵያ እየመነኑ የሚመጡ ሁሉ ከአባ ቤርሙዴዝ ዠምሮ ሥራቸውን ይኸው ዛሬ አባ ጋስፓሪን አጠናቀው ባ፩ድ ጥራዝ ለይተው ጽፈው ያወጡት አሰቀድሞ ከአባ ቤርሙዴዝ ዠምሮ ሲያያዝ የወረደ መሆኑን ብዙዎች ማስረጃዎች ይገኛሉ ከእነዚህም ከሮማ ልዑካን ጽሑፎች የተገለበጡ ወደ ኢትዮጵያ ወጣቶች የቀረቡ የብዙ ድርሰቶች ይገኛሉ። ፩ኛ ያቶ ተክለ ጻድቅ መኵሪያ መጽሐፍ ካጼ ልብነ ድንግል እስከ አጼ ቴዎድሮስ የሚለው ከኢጣልያኖች መጽሐፍ የተገለበጠ ነው። ያቶ ተክለ ጻድቅ መኵሪያ አሳብና ትጋት በጣ ለኢትዮጵያ በመቈርቆርና የወጣቶችን ዓይን ለመክፈት የበረታ በመሆኑ ብዙ ነገሮች እየገላለጠ ለማስረዳት ተነሥቶ በጥንካሬ የደከመው ለኢትዮጵያ በመቈርቈር ቢሆንም ታሪኩ የተገለበጠው ከኢጣልያኖች ሊቃውንቶች ስለሆነ ፩ድ ከባድ ነገሮች ባለማወቅ ከነሱ ላይ መቀበሉ አልቀረም ከነዚህም ፩ኛው "በ፲፩ኛ ገጽ በ፪ኛው ዓምድ በ፴ኛው

መስመር የመዠመሪያው የኢትዮጵያ ዘር የኩሽ ዘር የተለዩ ይመስላል። በማለት ፩ድ ፩ድ ጸሐፊዎች ሲጠራጠሩ የመጡበትን እነዚህን አዲስ የመጡ የሴም ዘሮች ባገሩ ከነበሩት ከኩሽ ዘሮች የበለጠው ኃይለኞችና ሥልጡኖች ነበሩና ገዥነታቸውን ተቀብዬ አልኖርም ያለውን በጦርነት አጠፉት ከቀሪው ሕዝብ ጋራ ግን በልማድ በጋብቻ ተደባልቀው የበላይነታቸውን አጽድቀው ተቀመጡ። ይላል" "የሖሜር መጽሐፍም በትሮያ ጦርነት የተነሳ ያነሳታል የታሪክ አባት የተባለው ግሪኩ ሄሮዶቱስ እንደ ጐበኛት ይጠቅሳል። በፊት የምጣው እንደ አገር ተወላጅ የሚቆጠረው የካም የኩሽ ዘር በኋላ ከመጡት ነገድ ዮቅጣን ከሚባሉት የሴም ዘሮች እንደዚሁ ከሌላ ነገድ ጋራ ከነገድ ፺ኤል በመደባለቁ ድብልቅነቱን ለመግለጽ ባረቦች ሐበሽ ድብልቅ ብለውታል ይላል።"

ግሪኮችም በምሥራቅ የመጣ ሕዝብ መሆኑን ለመግለጽ ኢትዮጲስ (ፊታቸው በፀሐይ የተመታ ብለውታል)። ክብረ ነገሥት ግን ኵሽ ወለዶ ለኢትዮጵያ ዘውእቱ አቡሆሙ ለኢትዮጵያውያን) ክብረ ንገሥት እስከሚለው የኢጣልያ ሊቃውንቶች የጻፉት መሆኑን መረዳት ነው። ዋናው የሥራቸው ማስታወቂያ ኢትዮጵያን ከሁለት ለመክፈል ወይም ይህችን ዛሬ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ያለችቱን ሌላ ናት ለማለት አሳብ ስለ አላቸው በረቂቅ ቀስ እያደረጉ ስለሚሰብኩ በዚሁ (ባ፲፫ኛው ገጽ በ፫ኛው መሥመር ይህን በመሳሰለው ምክንያት የኢትዮጵያ ታሪክ ግብጻዊው ሲደርስ ኩሽ ዓረብ ሲደርሰው ሐበሽ ግሪክና ሮማዊ ሲደርሰው ኢትዮጵያ እያለ ይጠራናል። በዚህም ስም ቀድሞ ከግብጽና ከሊብያ በስተደቡብ የሚገኘው ያሁኒቱ ኢትዮጵያ ሱዳንና

# ፖ ቀዳም

ስናር ጎዶፉርን ከዚያም ዛንዚባር መቃደሾ ጭምር እስከ ህንድ ውቅያኖስ ያለው አገር ይጠራ ነበር ይባላል)። (ይህንም ማስተዋል ነው ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለይቶ እንደወሰነ ጽሑፉን ልብ ብሎ ማየት ነው። ይህ ሁሉ የነሱ ፖለቲክ ነው። (፪ኛ ባ፲፭ኛው ገጽ በመዠመሪያው ዓምድ በ፳፫ኛው መሥመር የዚሁ የአክሡም የኢትዮጵያ መንግሥት የገናንነቱ ጊዜ ከክርስቶስ በፊት ከ፰ኛው ፻ ዓመት ላይ ይዠምራል ይላል)። ይህም ኢጣልያኖች የመጣ ነው። ፫ኛ (በ፲፰ኛ ገጽ በመዠመሪያው ዓምድ ባ፩ኛው መሥመር እንዲሁም በአጼ አልዓሜዳ ዘመነ መንግሥት እነዚያ በመምህርነት በጻድቃንነት ስማቸው የታወቀውና ነገዳቸው የተለያየው ፱ ቅዱሳን የተባሉ አቡነ ሰላማ የመሠረተው የክርስትና ትምህርት ለማፋፋት ከሮም ግዛት ወደ አክሡም መጡ ከዚያም በያውራጃው ተከፋፍለው ክርስትናን በኒቅያ

ጉባዔ የተወሰነውን ቀኖነ ፷ቱን ዓዕማደ ምሥጢር ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌላ የተገኘ አይደለም እርግጠኛው ታሪካቸውስ በየገድላቸው ተጽፎ ይገኛል። ፱ቱ ቅዱሳን የመጡበት ሲዝመር ለማስተማር አይደለም። የመጡበት ምክንያት ሮማውያን ለግብጽ ሊቀ ጵጵስና እየሾሙ ባስቸገራቸው ጊዜ ወደ ገዳመ አስቄጥስ በረኃ እየገቡ ሲጸልዩ እነዚህ ቅዱሳን የመቤታችን ፍቅር በጣም ያደረባቸው ስለነገሩ ከነሱ ፩ዱ አባ አረጋዊ የተባለው ሐዋርያው ዮሐንስ የጻፈውን ነገረ ማርያም ሲመለከት ኢትዮጵያን እመቤታችን አሥራት አድርጋ እንደተቀበለቻት በኢትዮጵያን እመቤታችን አሥራት አድርጋ እንደተቀበለቻት በጽሑፍ ስላገኘው። በዚህ የተነሳ የእመቤታችንን ፍቅር ለመጥገብ ካሉበት ተነስተው አክሡም ገብተው ግዕዝ እየተማሩ ብዙ ጊዜ ሳይለያዩ በማኅበር ጸሎት እያደረጉ ከቆዩ በኋላ ወደ መድከም ሲደርሱ ለየራሳቸው ብርታት ብሎ ታምራት እንደተሠራላቸው የሁሉም ሥራ በየገድላቸው ተጽፎ ይገኛል። የሮማ ልዑካን አሳባቸው እነሱን ከውጭ መጡ የሚሉ ወሬ ስለ ሰሙ ሮማውያን ናቸውና እኛም የነሱ ልጆች ነን የነሱ ተከታዮች ሆነን የኢትዮጵያ ቤተ ክህነት ተከታይ እንሆናለን በማለት ሲደክሙ ይታያሉ። ስለዚህ በያውራጃው ተከፋፍለው

አስተማሩ እያሉ በመንፈሳዊው ሥራ ሐሰት እየጨመሩ ሲጽፉ ይገኛሉ ፬ኛ (በ፪፻፴፫ኛ ገጽ በ፹፬ኛ ምዕራፍ ፩ በዓለምና በኢትዮጵያ ሥርወ መንግሥት መለወጥ በዘመነ መሳፍንት እንጅ እውነተኛነት የሌለው መንግሥት መለዋወጥ በዘመነ መሳፍንት እንጅ እውነተኛነት የሌለው የጦርነት ምክንያት። በሮማውያን ዘመን ከዮልዮስ ቄሳር ዝምሮ በርሱ መሥራችነት የዮልዮስ ክሎዲ ቤት እንደ ዲዮቅልጥያኖስ እንደ ኤሌዎጋባሉስ ያሉት የምሥራቅ የዓረብ ዘሮች በትልቁ ሮማ የንጉሠ

አንባቢ ሆይ ከሀ ዝምሮ እስከ ሆ። ከሆ ዝምሮ እስከ ፖ የፊደሎች ቁጥር በየገጹ ተመልክተው የሚገኙ ከሚያዝያ ፩ እኁድ እስከ መስከረም ፴፩ ዕለተ ቀዳም የሚገኙት ዕለታት ከግዕዙ ፊደሎች ጋር የተባበሩ መሆናቸውን አስተውሉ ይህም በሄኖክ ቀመር በምሥራቅና በምዕራብ ፮ ፮ መስኮቶች ባለው ከምሥራቁ ወገን ከላይ የተጻፉት ፻፹፪ቱ ፮ቱ ወሮች መሆናቸውን አስተውል። ፩ኛው ዕሪና ሌሊትና መዓልት የሚገኘው በዚች ዕለተ ቀዳም ነው።

## ሀ እኁድ

# ፺ኛ ክፍል ጥቅምት

## ምዕራፍ ፫

ነገሥትነት ዙፋን መቀመጥና መግዛት ችለው እንደነበረ ከዚያም በፊት በግብጽ ቤተ መንግሥት የግሪኩ የፕቶሎሚውስ በፈረንሳዊ ቤተ መንግሥት የእስፖኙ በኤስፓኙም በርቦን የሚባለው የፈረንሳዊ አብስቡርግ የሚባለው ሥርወ መንግሥት ደግሞ ከስዊስ ፊልቆ በኋላ በኦትሪሽ የቄሳር ግዛት በደንብ ተመሥርቶ ከዚያ በእስፓኝ በሐንጋሪ በሆላንድ የነጋሢነት ዘሩን በገዥነት አጽድቆ እንደነበረ እንደዚሁም ከተራ ሰዎች ውስጥ በየጊዜው እየተነሱ ዘሩ ተያይዞ የመጣውን ገዥ እየተጣሉ ለጭርም ለረዥምም ጊዜ ለራሳቸውና ዘራቸውን የመተካታቸው ታሪክ በዓለም በየመንግሥታቱ ታሪክ ውሥጥ ብዙ ጊዜ ደርሷል።) ይህን ሁሉ ሐተታ ለኢትዮጵያ ልጆች ለማስጠናት የተደራጀ መሆኑን ማሰብ ነው። (በኢትዮጵያም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ሰሎሞናዊ ነጋሢ ከትግሬ ከጋላ ካማራ ከሱማሌ ፩ድ ፩ድ ኃይለኛ እየተነሳ ዙፋን ለመቀማት የታገለው ብዙ ነው። የተከናወነለት ግን ጥቂት ነው። አስበው ያልተከናወነላቸውን ብዙዎቹን ትተን ጥቂቶች የተከናወነላቸው እነማን እንደሆኑ እናስብ ፩ኛ ፈላሻዋ ዮዲት ፪ኛ ላስታዎቹ ዛጔዎች። ፫ኛ እስላሙ ግራኝ ሙሐመድ ፬ኛ አሁን በመሳፍንትነት የገዙት የሴሩ ዳንጉል ዘሮች። እንደ ንጉሠ ነገሥት የበላይ ገዥ ለመሆን እየተነሡ ተዋግተው ሳይሆንላቸው እየቀረ በዚህ ፋንታ ስደት እሥራት እጅ መቈረጥ ስቅለት የደረሰባቸውን በዚህ ምዕራፍ ዘርዝሮ ለማሳየት ብዙ ዓምድ የሚፈጅ ነው። በክሡም በላስታ በሸዋ ቤተ መንግሥት ጊዜ ይኸውም ማለት ሽህ ከክርስቶስ በፊት ዠምሮ ይህ ያሁኑ መጽሐፍ መጻፍ እስከ ዠመረበት እስከ ሽ፰፻ ምሕረት እስከ አጼ ልብነ ድንግል በመካከሉ መንግሥትን ለመምራት ወይም ከመንግሥት ለመነጠል ገብር አልገብርም ግባ አልገባም በመባባል ያን ጊዜ የፈሰሰውን ደም ለመገመት ያህል ካጼ ልብነ ድንግል አንሥቶ እስካሁን እስከ መሳፍንት ዘመን ድረስ በዚህ በተጻፈው መጽሐፍ ውስጥ ያስረዳናል።)

ይህን ጠብና ክርክር እየዘረ ውስጥ ለውሥጥ እያጣላ የሰላሙን አገር የጦርነት የፍቅሩንና ያ፩ድነቱን አገር ለመለያየት ያደረሰ ማን ይሆን። (ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ ያለውን የበረታ የገዥነት መንፈስና የነጻነት ፍቅር ሊአሳየንና ሲአስደስተን ሲሞክር በዚህ ኩራትና ነጻነት ምኞትና

እምቢታ ምክንያት እርስ በርሱ ያለቀውን በዚህም የመንግሥቱና የሕዝቡ ኃይልና ቁጥር ወደ ድካምና ወደ መጉደል መዘቅዘቁን ስንመለከት መልሶ ያሳዝነናል።)

እዚህ ላይ እውነቱን ሊናገሩ ምንም አልቀራቸውም እርስበርሳቸው እየተፋጁ የነበሩቱ ቁጥራቸው እያነሰ ሲሄድ ስንመለከት መልሶ ያሳዝናል ማለት ነገሩ ሲገለጽ ምንም ያህል አልቀረሁም። ግን ውስጡ የፉከራ ቃል ነው። በዚህ ዘመን (ሽ፺፻ ፹ እስከ ሽ፰፻፵፫ ዓ.ም ያለው ጦርነት ዋናው ምክንያት ደግሞ ከዓረብ አገር በግራኝ ጊዜ ከመጡት ሼህ ዑመር ከየጁ ጋላ በመውሰዳቸው የርሳቸውም ዘር በትልቁ ከተማ በጎንደር ተቀምጦ በእንደራሴነት ወይም በመስፍንነት እንደምን ይግዛ የሚባለው ምክንያት ነው። እንደ መስቀል ጦርነት ዓይነት በዚህና በሌላውም በግል ምኞታቸው እየተንቀሳቀሱ እነዚህን የሴሩ ዳንጉልን ዘሮች ከጎንደር ቤተ መንግሥት ለማስለቀቅ ከግትሬ እነ ራስ ወልደ ሥላሴ እነደጃች ስባጋዲስ ከጐጃም እነራስ

## ሁ ሰኑይ ጥቅምት

መርድ እነዳጅች ዘውዴ እነደጃች ጎሹ ከሰሜን እነራስ ገብሬ እነደጃች ኃይለ ማርያም። አሁን ደግሞ ደጃች ውቤ እየተነሱ ሲመቻቸው እየተዋጉ ሳይመቻቸው እየታረቁ በታላቅ የጦርነት ግድያና የነገር ክርክር ኖሩ የሴሩ ጓንጉል ዘሮች እነራሴ አሊ እነራስ ጉግሳ እነራስ ማርዬም ያገሩን ልማድና ሥርዓት ሳይሽሩ ክርስቲያንነታቸውንም እንደያዙ ውጊያን በውጊያ ሰላማዊውንም በሰላም እየመለሱ በጎንደር ቤተ መንግሥት ያላቸውን የገዥነት ሥልጣን አደላድለው ያዙ እውነቱን መርምረን ለመረዳት የፈለግን እንደሆነ የጦርነቱ እውነተኛ ምክንያት የነራስ አሊ የነራስ ጉግሣ ከየጁ ጋላ ወይም ካረብ የመወለዳቸው ምክንያት ሳይሆን እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ የማለት ምኞት እንደሆነ ለመረዳት ምንገዱ ቀላል ነው። እነራስ አሊን ለማስለቀቅ የሚታገሉት ለሰሜኖቹ የነራስ ገብሬ የትግሬዎቹ እነራስ ወልደ ሥላሴ የጐጃም የነራስ መርድ ዘራቸው ጥንት የመጣበት አገር ከወዴት ነው። ከዓረብ አገር በኤርትራ ባሕር ተሻግረው የመጡት የነገደ ዮቅጣን ወገኖች ያው ዓረቦች አይደሉምን። የዙፋኑስ ደምበኛ ወራሽ ሰሎሞናዊው ነጋሢ ፏኤል ወገን ከህንድ በጠቅላላው ከምሥራቅ የመጣ ሲሆን ሁሉንም ያስመካውና የኮራው ክርስቲያንነቱ አይደለምን። የሼህ ዑመር ዘሮችስ ክርስትናን ገና በፊት ከሴሩ ጓንጉል ዠምረው ተቀብለው የሉምን። ይሁን እንጅ ነገሩን በጉልህ እማሳጣት ያደረሰው ትግሬዎቹና አማሮቹም ለመነሻ ምክንያት ያጋጠማቸው የሸህ ዑመር ካረብ አገር አመጣጡ ቀረብ ባለ በግራኝ ሙሐሙድ ጊዜ በሸ፲፪ ዓ.ም ሲሆን የነገደ ዮቅጣን አመጣጥ ራቅ ካለ ጊዜ ከክርስቶስ በፊት ከሸ ዓ ወዲህ። እንድናስተውል ከቀዳማዊ ምኒልክ ወዲህ ማለት መሆኑን። አስቀድሞ የገባው እንደባላገር። በኋላ የመጣው እንደ እንግዳ በመቆጠሩ ይሆናል። እንግዲህ ለማናቸውም ነገር ሰበብ እንደሚአስፈልገው እነዚህም ያማራና የትግሬ ታላላቅ መኳንንቶች መሳፍንቱን ለማስለቀቅ በተዋጉበት ጊዜ ሁሉ የነዚህ የጋላና የዓረብ ዘርነታቸውን የሚጠቅሱት ተከታይና አባሪ ለማግኘት እንዲረዳቸው መሆኑን እንገነዘባለን እነራስ ወልደ ሥላሴ እነራስ መርድ የተነሡት እኔ ልግዛ እኔ ልግዛ በሚባል ምኞት ሳይሆን በነዚህ የዘር ልዩነት ምክንያት ብቻ ቢሆን ኑሮ ከትልቁ ራስ አሊ ምስፍንና በፊት የነገሥታቱ ከላስቶች ከጋሎች ይበልጥ ጊዜ ፩ድ ፩ድ ጊዜም ወሬኛ እየተባለ ከየአውራጃውና ከየከተማው ከሚነሳው ጋራ ያን ያህል አይወጡም ነበር። ስለዚህ የጦርነቱን ሁሉ ሥረ ነገር እኔ ልግዛ የሚባለው የራስን መውደድና ራስን አኩርቶ መገኘት የመመኘት መንፈስ መሆኑን ለዘለቄታ እንገንዘብ። ምናልባት እገሌ ከሚገዛኝ እገሌ ቢገዛኝ ይሻላል እንደማለት የሸህ ዑመር ዘር ከሚዛኝ የሰሎሞን ዘር ቢገዛኝ ይሻላል በሚል መንፈስ ተመርተው አማሮቹና ትግሬዎቹ ቀድሞ በነጋሢዎቹ ጊዜ አቀዝቅዘው የያዙትን ምኞታቸውን

አሁን በሴሩ ጓንጉል ጊዜ በጋለ መንፈስ ተነሥተውበት እንደሆነ የምርጫ ጉዳይ ነው። ይሁን እንጅ ተመርጠው የነገሡትም በሚአስተዳድሩበት በነሥርፀ ድንግል በነኢያሱ አድያም ሰገድ በነበካፋም ጊዜ ሙሉ ጸጥታና ሰላም እንዳልነበረ ባለፈው ታሪክ ሁሉ ተረድተነዋል። አሁን ግን ጉዳዩን ትተን ደጃች ውቤ ደግሞ ከዋናው እንደራሴ ከራስ አሊ ጋራ ወደ ፊት የሚአደርጉትን ጦርነት ከማመልከታችን በፊት ከደጃች ስባጋዲስ ዘሮች ጋራ ያደረጉት ውጊያ) እንመልከት። ይኸውና ይህ ከላይ የተጻፈውን ሁሉ የሮማ

## ሂ ሠሉስ ጥቅምት

ልዑካን የጻፉት ፖለቲክ መሆኑን ባለመገንዘብ ለወጣቶቹ የፖለቲክ ጽሑፍ መሆኑ ሳይገለጥ በሽፍኑ መቅረቡ መልካም አይደለም አሁን ከላይ የተጻፈው መስመር ሁሉ ብዙ የፖለቲክ ነገሮች አሉበት ማለት ጉዲትንም የንገሡች አስመስሏታል። ላስቶችንም በመሶብ ወርቅ በድልነዓድ ልጅ በኩል የሄደውን መንግሥት ባዕድ አስመስለው ጽፈውታል። ፫ኛ ግራኝ ሙሐመድንም በሽፍትነት ተነሥቶ ሲዋጉ የቆዩበትን ዘመን የንጉሥ ዘመን አድርገው

ቆጥረውታል። የነአባሴሩ ጓንጕልንም ዘር አባታቸውን ሼህ ዑመርን ከዓረብ አገር የመጡ አይደለም ወይ ሌላውስ ቢሆን በቀድሞ ጊዜ ከዓረብ ደቡብ ይዘራል። መቸም እነሱ ዓዋጅም ቢደረግ እየሾለኩ እየገቡ ከየመሳፍንቱ ቤት እየተደበቁ መሣሪያ እናመጣላችኋለን እያሉ እየሰበኩ መሳፍንቱን እርስ በርሱ የሚአፋጁ እነርሱ እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል። እነዚህም የመጡበት ፕላኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርስ አፋጅተን ሕዝቡ ሲአልቅ የሀገሪቱ ኃይል ሲቀነስ ከሮም የጦር ሠራዊቱ አስመጥተን በዘንግ እንገባበታለን የሚል ስለነበር በሀገሪቱ ላይ የሚደረገውን ጦርነት ሁሉ በየቀኑ ወደ ሮማ የሚአስታውቁበትን ይመስላል። ራስ አሊንም ሼህ ዑመር ከአረብ አገር የመጡ ናቸው ያሉ ያውም በግራኝ ጊዜ ይህ ጽሑፍ በፍጹም የጠላት ፖለቲክ ነው እንጅ እርግጠኛ ታሪክ አለመሆኑን በወሎ የቀድሞ ስሟ ላኮመልዛ የእስላም ሃይማኖት የገባበትን ጊዜ ከታሪክ ጽሑፍ ያገኘሁትን ከዚህ አስከትየ እጽፋለሁ። ታሪክ በየፊቱ ነው ስለ የወሎ እስላሞች አመጣጥ እንዲህ ይላል ኑር ዓህመድ የተባለ የግራኝ ወንድም አጼ ገላውዴዎስን ገድሎ ራሱን ቆርጦ ለድል ወምበራ የግራኝ ሙሐመድ ሚስት ሰጣት ወደ ሐረር ወስዶት ሳለ የዓጼ ልብነ ድንግል እኅት የወይዘሮ ሮማነ ወርቅ ልጆች ራስ ዮሐንስና ራስ ሐመልማል የተባሉ ጀግኖች ያጼ ገላውዴዎስን ራስ በመከታተል ሐረር ድረስ ሄደው የሀገሪቱን ሰው መስለው ከቆዩ በኋላ ኑር አሕመድን አደጋ ጥለው ገድለው አገሪቱንም በጃቸው በያዙ ጊዜ ከዚያው አገር ተወላጆች ከሆኑ ሴቶች ከምርኮኞቹ መርጠው ፋጢማ ሐረሪና ፋጢማ ብሩር የተባሉትን ወሰዱና ክርስቲያን አድርገው ወለዱላቸውና በዚአው አገር ከቆዩ በኋላ ደግሞ በጦርነቱ ጊዜ ያጼ ናዖድን ልጅ ጽጌ ሮማንን የግራኝ ሙሐመድ ወንድም ኑር መሐመድ ማርኮ ወስዶ እስላም አድርጎ ፬ት ልጆች ወልዶላት ሳለ የልጆቹ ስም አሊሃ ዘሊሃ አሊላ ውስማን ይባላሉ ዘሊሃና ውስማን ከነራስ ሐመልማልና ከራስ ዮሐንስ ጋራ አብረው መጥተው ክርስትና ተነሥተዋል። አሊሃና አሊላ እዚያው ሐረርጌ እስላም ሆነው ቀርተዋል። እነሱ በዚያ ጊዜ ተመልሰው የተቀመጡት ወሎ ላይ ነበር። በኋላ ዘሊሃ ክርስትና ተነሥታ ስሟ ዓመተ ዮሐንስ ተባለችና ጐጃም አዛዥ ፍቶን አገባች ውስማን መርቆሪዎስ ተብሏል። ራስ ዮሐንስና ራስ ሐመልማል ለጊዜው ላኰመልዛ ላይ ባረፉ ጊዜ እስላሞች ከሐረርጌ እየመጡ እዚያ ሲቀመጡ ፩ድ ሰው ባ፩ድ ዓመት ወደ እስልምና ሲሄድ ሲወልዱና ሲዋለዱ ይህን ያህል ወለዱ እስከዚህ የደረሱበት ምክንያቱ ሳይበዛ ይህ ነው። ሼህ ዑመር የተባለውም የወሎ አስተማሪ የነበረ ነው። እሱም የሐረር ሰው ነው እንጅ ከዓረብ አገር የመጣ አይደለም የመጣበትም ምክንያት ወሎ ፫ቱ ወንድሞቹ ፫ቱን እኅቶታቸውን አግብተው ሲቀመጡ እሱ ወደ ሐረር ወርዶ ነበር እዚያ ይህ ሼህ ዑመር የሥልምና

# ሃ ረቡዕ ጥቅምት

ሃይማኖት ስላስተማረው ወደ ላኮመልዛ አመጣውና እርሱ የጁ ላይ ተቀመጠ ወሎ ከ፯ ሴቶች ፯ ልጆች ወለደና ፯ ቤት ወሎ የተባለው ስለዚህ ነው። የሮማ። ልዑካን ታሪክ ቀስ እያሉ ወገንና ወገንን ለማለያየትና ለማራራቅ ነው እንጅ ለኛ አስበው ሊሠሩልን እየመሰላቸው ብዙ ሰዎች የነሱን ጽሑፍ የሚቀበሉ ሞልተዋል። አሁን በቅርብ ጊዜ ባቶ ከበደ ሚካኤል አማካይነት የተቋቋመ አርኬዎሎዥ ሥራ በሚሠራው ሲመረመር በጥንታዊ ፊደል ተጽፎ የተገኘውን ጽሑፍ ሁሉ በደቡብ ዓረብ ፊደል የተጻፈ ነው እያሉ ጽፈው ይገኛል።

ሐውልቱንም የቀረጹት ሳባውያን ናቸው የሚል ጽሑፍ ታትሞ በአማርኛና በፈረንሳይ ለዓለም ተዳረሰ ማነኛውም ዛሬ በሚጻፈው አስተያየት ደራሲያኑ ሁሉ የሚከተሉት ከሮማ ልዑካን በተገኘው ፖለቲክ ጽሑፍ ነው። እንግዲህ ወደ አባ ጋስፓሪን ታሪክ እንመለስ (ባ፵፱ነኛ ገጽ ባ፲፪ኛ መስመር በቀይ ባሕርና በህንድ ውቅያኖስ ወዲህ የምትገነው አሁን ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራው አባጋስፓሪን አሁን ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራው ብለው ከዣመሩ እንደ ሕጉ አጻጻፍ ቀድሞ እገሌ ትባል የነበረችቱ ብሎ መጻፍ ታሪክ በእውነት ለሚጽፍ ሰው የተገባ ሥራው ነበር። ግን ያባ ጋስፓሪን ፖለቲክ ልብ ወለድ ሥራ ነው እንጅ ሕጋዊ የታሪክ ጽሑፍ አለመሆኑን ይህ አሁን ኢትዮጵያ ተብላ የምትጠራው

የተባለችቱ ሀገር እስከ ዛሬ ፩ድ እንኳ ስም አልነበራትም ይሆንን። በየጊዜውና በየዘመኑ የስም መለዋወጥ እንደደረሰባት ታሪክ ይነግረናል። "ይህችውም አገር የካም ነገዶች ስም በግብጻውያን በፋርስ በፑንፐ በኩሳ ኩሽ በቋንቋቸውም የአምላክ አገር እንደማለት ቶኔቶር ብለው ፫ ስም አውጥተው ይጠሯት ነበር ይላል" ይህ ሁሉ የመቀላመድ ንግግር ለመነኮሴ የተገባ አልነበረም የሙኑሴ ልብስ ለብሶ የፖለቲክ ማማሰያ ይዞ የወዲሁን ወዲያ የወዲያውን ወዲህ እያደረጉ ማማሰል የተገባ ጉዳይ አይደለም። በገጽ ፩ "፲፬ኛው መሥመር ኩሽ ደግሞ ግብጻውያን ኢትዮጵያን ለመጥራት የመሠረቱበት ፩ድ ሌላ ስም ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ኩሽ የሚለው ስም በልዩ ኢትዮጵያን ብቻ ለማመልከት" በልዩ ማለት ምን ማለት ነው። ኩሳ ኢትዮጵያ ናት ሳባ ኢትዮጵያ ናት ዓረብ ኢትዮጵያ ናት ወሰኗንም የምናውቀው እኛ ተቀምጠን የሮማ ልውካን ለወሰን መጣስ ታሪክ ለማፍረስ ንጹሕ ደም ለማፍሰስ በዚህ ነገር ስማችሁ ሲሞገስ ሰማሁ እንጅ ኢትዮጵያ እንዲህ ትባል ነበር። እያሉ የቆጥ የማገሩን መለፍለፍ ማንን ለማታለል ይሆን። እናንተ ባትመጡ የኢትዮጵያን ታሪክ ማን ይጽፍላታል ነበር ይሆን። እኛም የምንደነቅ በናንተ ቅን አሳቢነት ነው (በ፷፱ነኛ ገጽ በ፲፩ኛው መሥመር በዓረብ ሳባውያን አገዛዝ ዘመን የሆነውን ታሪክ ነጋሢ ተብለው የዓረብ ሳባውያን እንደራሴዎች ሆነው መኖራቸውን ጽፈን አስረድተናል ትንሽ የቀረው ታሪክ አለ ብለን የተናገርነው ቃል ግን እንደዚህ ነው እኒህ ነጋሢ ነጋሢ ተብለው በኢትዮጵያ ላይ ተሾመው የኖሩት እንደራሴዎች።) ላይ ትንሽ የቀረ ነገር ከላይ ዠምሮ እስከዚህ ድረስ የዓረብ ሳባውያን እንደራሴዎች ነጋሢ ነጋሢ ተብለው ተሾመው ተብሏል ነጋሢ ማለት የሹመት ስም ነው። ለመሆኑ እንደ ሕጉ አጻጻፍ ስለማረጋገጥ ሲባል የተሾሙትን ሰዎች ስም መጻፍ አለ። ፪ተኛም የነበሩበትን ዘመን ፫ኛም ስንት ዘመን ፩ዱ ሰው ተሾሞ እንደ ቆየ ፬ኛ በደቡብ

# ሄ ኃሙስ ጥቅምት

የነበቱት ነገሥታ በዓረብ አገር ላይ ኢትዮጵያን የምታህል የገዙ ነገሥታ ከብዙዎቹ ያ፩ዱ ስም እንኳ ለምን አይጠራም እንደራሴዎቹስ ምን ስለምን አይጠራም። ከሕጉ አጻጻፍ ፬ት ነገሮች የጐሉ ሲሆኑ በታሪክ አምድ ላይ ምን ይዞ ሠፈረ። ከዚህ ውስጥ ሲፈልግ ፩ድ ማስረጃ አልፊ የሌለው ስለሆነ ይህ ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ የጠላት ፖለቲክ መሆኑ ማስረጃ የሌለው ቃል እየተጻፈ በመገኘቱ ዋጋ የሌለው ሆኖ ከመሠረዝ በተቀር ሌላ ሥራ የለውም። ከዚህ ቀደም በጻፍነው ታሪካችን አስረድተናል። ቆይተው ግን ከነርሱ ወገን የሆነውን በእውቀትና በሥልጣን ከፍ ያለውን ፩ዱን ነጋሢ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አሰኝተው በመላዋ ኢትዮጵያ ላይ አንግሠውት ነበር። ይህን ከነርሱ ወገን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ብለው ያነገሡት ነጋሢ ግን ሰውነቱ የትኛው እንደሆነና ስሙ ማን እንደሆነ የነገሠበት ጊዜም በስንተኛው ዘመን እንደሆነ ታሪካችን ለይቶ ለማስረዳት አልቻለም ይላል)። ከላይ እኔ እንደዘረዘርኩት አባ ጋስፓሪንም እንደኔ አድርገው የአጻጻፉ ሕግ መጉደሉን መስክረው ታሪካችን የነጋሢውን ስሙንና ዘመኑን ለይቶ ለማስረዳት አልቻለም ብለው መጻፍዎ እንዲሁ ያለ ሕግ የጻፍሑትን ቃል ተቀብለው ብሎ እንደ ትእዛዝ ያለ ነገር ይመስላል። ከሥሩ ላይ ሲወጠን በጽሑፍ ላይ ከመስፈሩ በፊት ማስረጃውን መፈለግ አለ። ማስረጃው ከተሰናዳ በኋላ ቃሉ ይጽፋል። ማስረጃ የታጠለትን ቃል ራሱ ባለቤት ሕጉን ተመልክቶ ይሠርዘዋል። አባ ጋስፓሪን ግን ዋናው ራሳቸው የሐሰት ፖለቲክ መሪነት ስለሆነ ሕጉን አዋቂ ለመምሰል የነገሡትን ሰውነቱ የትኛው እንደሆነ ፪ኛ ስሙ ማን እንደሆነ ፫ኛ የነገሠበት ጊዜ በስንተኛው ዘመን እንደሆእን ታሪካችን ለማስረዳት አልቻለም የሚል ድምጽ ሰጡና የጻፉትን በመሠረዝ ፋንታ ወደዚያው ቀጥለው (ይህ ስሙ ያልታወቀ በኢትዮጵያ ላይ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ የንገሠ ነጋሢ ምንም ስሙንና የንገሠበትን ዘመን ለይተን ባናውቀው በኢትዮጵያ ከፍ ያለ ክብርና ነጻነት የሰጣት ንጉሥ እርሱ መሆኑን ሥራውና የሥራውን ምልክት ያስረዳል ይላል)። በመላው እየቀጠሉበት ይሄዳሉ ማለት ምንም ስሙንና የነገሠበትን ዘመን ለይተን ባናውቀው ይህ ንጉሥ የሠራው የሥራ ምልክት ያስረዳናል አሉ። እንግዲህ በታሪክ አጻጻፍ ሕግ አለ ሕጉንም ያልዘነጉ በመምሰል ራሳቸው ቃላቸውን ሰጥተዋል ከዚህ በኋላ ሥራው ያስረዳናል ማለት ከሕግ የወጣ ያታላይነት መሆኑን ይህ

ጽሑፍ መመስከሩ አይደለም ይሆንን። ሲሆንማ ለእደዚህ ያለው ከባድ ነገር ማስረጃው ከፍ ያለ የበረታ መሆን ነበረበት ስንኳንስ የራሱ ስምና ያባቱንም ስም ከነወገኑ ለይቶ መጻፍ ሕግ መሆኑን ካባቶቻችን የመጣው ቅዱስ መጽሐፍ በነገሥታት ታሪክ የተጻፈው ያስረዳናል። ነገሥት ፩ኛ ፱ ፩ ወሀሎ ፩ዱ ብዕሲ እምደቂቀ ብንያም ወስሙ ቂስ ወልደ አቤሄል ወልደ አዴል ወልደ የአኪ ወልደ ያፌቅ ወልደ ብዕሲ ኢያሜንየ ብዕሲ ጽኑዕ ፪ ወውእቱ ወልድ ወስሙ ሳኦል ይኸውና ስለ ሳኦል ወገኑንም ለይቶ እስከ ፺ት ትውልድ እንደጻፈለት ማስተዋል ነው። ፪ኛ ስለ ዳዊት ዜና መዋዕል ፪ ካ፲፪-፲፯ ፺ኛ ልጅ ነው ዘሩም የታወቀ ለመሆኑ ካ፲፪ቱ ነገደ ፳ኤል ለመሆኑ የታወቀ ነው። ማንም ሰው ቢሆን ሲሆን የናቱን ስምና የነገዱን ባይሆን ደግሞ ያባቱን ስምና የነገሠበትን ዘመን ሳይጽፍ የሚገኝ የለም ስለዚህ ከመማርም አልፈው በማስተማር

# ሀ ዓርብ ጥቅምት

ላይ የሚገኙ ሰው እንደዚህ ያለ ጐደሎ ሥራ ራሳቸው እየመሰከሩ ከመሰከሩም በኋላ እንደገና በሥራው ያስታውቃል። የሥራ ምልክት ይቅርና ሰውም በስም እንኳ ይሳታል ስለተባለ ያባቱ ስም የናቱ ስም ወገኑ እየተለየ ይጻፍ መባሉ በትክክል እውነት ጽድቅ እንድትጠበቅ በማለት ነው። በሥራ ማለትም ያው እናንተ ያመጣችሁት ማታለያ ባ፫ኛው ገጽ (፳፬ኛው መሥመር ዶሬስ የተባለው የፈረንሳይ ሊቅ በግብጻውያን ጠበብት የተሠራ ነው የሚአሰኝ አንድ ከሸክላ የተሠራ ራስ አግኝቷል። ይህ ራስ ምናልባት ጥንት ኢትዮጵያ ከመጡት ግብጻውያን ሥራ የቀረ ይሆናል ተብሎ እንደተጻፈው) ይሆናል እየተባለ በናንተ ግምት እንደሚወራው ታስቦ ማለት ነው። ግብጻውያን ኢትዮጵያን መጥተው እንደነበር የሚአስረዳው ጽሑፍ ወደት አለ ይሆን ፪ኛ በ፮ኛው ገጽ የሚገኘውን ሥዕል ግብጻውያን በኢትዮጵያ እንደዘሙቱ ያሳያል ብላችሁ እንደፈጠራችሁት ያው ማለት ነው የናንተ ፖለቲክ በጥብቅ የሚመረምር ነው። በዚያው መንገድ ሲቀጥሉ በመጨረሻው መስመር ከግርጌ (፳፬ኛው ገጽ ከርሱ ቀጥለው በኢትዮጵያ ላይ የነገሡ ነጋሢዎችም ምንም እንደ ርሱ ስማቸውን ለይተን ባናውቀው ታሪካቸውንና ሥራቸውን ተመልክተን የርሱ ወገኖች ሆነው

ኢትዮጵያን ከፍ ወዳለው ሥልጣኔ ደረጃ እንዳራመዷት ያን ጊዜ የመሠረቷቸውን ኋላም ፈርሰው የተገኙ ከተማዎች በውሥጣቸውም የገተኘ ታሪክ ምልክት ያስረዳል ይላል።) አሁንም የተጻፈው የማሳሳትና ለማደናገሪያ የተባለ ነው እንጅ ፩ድ እንደ ሕጉ የተጻፈ ነገር የለም በዚያው በተለመደው ምንገድ ከሱ ቀጥለው የነገሡትንም ስማቸውን ባናውቀውም ታሪካቸውንና ሥራቸውን ተመልክተን የነሱ ወገኖች ሆነው ኢትዮጵያን ከፍ ወዳለው ሥልጣኔ ያደረሷት እያሉ የነኑ የሐሰት ፖለቲካቸውን ይዘራሉ። ከዚህም አስከትለው "በ፳፫ኛው ገጽ በ፫ኛው መስመር ስሙ ያልታወቀ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ ኢትዮጵያን የገዛ አጭር ታሪኩን የጻፍንለት አገሩንና ሕዝቡን የሚአስተዳድርበት ሕግና ሥርዓት አውጥቶ ሕጉንና ሥርዓቱን በኤርትራ አውራጃ ሠራዬ በተባለው አገር ላይ መሠረት ብለው የሚናገሩ ጥንታውያን የኤርትራ ሽማግሌዎች አሉ። ይኸውም እንደምናየው ምልክቱንም በያይነቱ እንደምናገኘው እውነት ሳይሆን አይቀርም ይላል"። ይህም ያው ሐሰታቸው ስለማያልቅ የማታለያ ፖለቲካቸውን በመቀጠል እንደዚያው ስሙ ላልታወቀ ታሪክ ጻፍን እያሉ ሲጽፍ ኀፍረትን አለማሰባቸው እንደምን ያለው መንፈስ በልቡናቸው ቢኖር ይሆን ስሙ ሳይታወቅ ምን ተይዞ ታሪክ ለመጻፍ ይቻላል ስሙ አይታወቅ ይቅር የነበረበት ዘመን ሳይታወቅ እንደምን ታሪክ ጻፍን ለማለት ይቻላል። ድግሞስ ጥንታውያን የሆኑ ሽማግሌዎች አውርተውናል የሚናገሩ አሉ እየተባለ ወሬው ከቁም ነገር ገብቶ ስንኳንስ ይናገራሉ ያወራሉ በማለትና በፊርማቸው እንኳ ቢያመልክቱ ቃላቸውን የማንቀበላቸው ሰዎች ይገኛሉ። እነሱም የሮማ ልውካንን ስብከት ሰምተው በዳቦና በሻይ ተገዝተው አገራቸውንና ሃይማኖታቸውን የካዱ ሰዎች ስለሚገኙ ነው። ይህ ስለ ሳባውያን የተጻፈው ነገር እኮ ተርታ ነገር አይደለም የኢትዮጵያ ግዛት የነበረውን አገረ ገዥ

ነበረ ተብሎ ሲጻፍ ፩ድ በቂ ማስረጃ ሳይኖር እንዲሁ በይመስላል እስከዚህ ስለደረሰ ነገሩ ከፍ ያለ ስለሆነ ከፍ ያለ ማስረጃ ማምጣት አስፈላጊ ነው በተረፈ ነጻነቷን ጠብቃ የምትኖሪቱን ሀገር ነጻነቷን ሰብሮ ታሪኳን

## ሆ ቀዳም ጥቅምት

አቃልሎ መጻፍ የሚአስከትለው ከፍ ያለ ዕዳ ስለሆነ አጥብቆ መመርመር ያስፈልጋል። ከዚህም አስከትሎ (በ፷፫ኛው ገጽ ባ፲ኛው መሥመር በኤርትራ አውራጃ በአሥመራ በስተደቡብ በኩል አግዓዝያንና ሐበሳት የተባሉ ሳባውያን ሕጋቸውንና ደምባቸውን አቋቍመው የፍርድ ሥራቸውን ሲፈጽሙበት የነበረው በመሪብ መረብ አለው የጠሩት ሠራዬ የተባለ አገር አለ። ይህም አገር ሠራዬ ተብሎ የተጠራበትን ምክንያት ካሁን በፊት ገጽ ፵ ጽፈን አስረድተናል" ይላል። ይህም ያው የተለመደው የፖለቲክ ምንገድ ነው እንጅ እንደ ታሪክ ጽሑፍ ሕግ በቂ ማስረጃ የለበትም አሁን ከማስረጃ ተቆጥሮ የሚገኘው ባረብ አገር መሪብ የሚባል ቦታ አለና በአሥመራ ሠራዬ ላይም መረብ የሚባል የወንዝ ስም ካለ ይህ በኤርትራ ሠራዬ ውስጥ የሚገኘውን መረብ የሚባለውን የወንዝ ስም ያወጡለት ዓረቦች ናቸው ስለማለት አይበቃም ለማለት የሚደረድረው አስቀድሞ የደቡብ ዓረብ ሰዎች በገዥነት ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸው በእርግጥ የታመነ ሆኖ ሲገኝ ነው እንጅ ባልተደላደለ ነገር በይመስላል ነጻነት መስበር የቋንቋ መቀማት ነገር የሚሆን አይደለምና በቂ ምስክር አስፈላጊ መሆኑን አባ ጋስፓሪን እያስገነዘብኩ ምርመራዬን እቀጥላለሁ። "ባ፲፰ኛው መስመር ይህ ሥራዬ የተባለው የአገር ስም ከሳባዊ ቋንቋ ተለይቶ የወጣ ግዕዝ የተባለው ቋንቋ በሠለጠነበት ዘመን የወጣለት ስም ነው የስሙም አወጣጥ እንዲህ ነው ሠርዓ ባለው ሥርዓት ተገኘ በሥርዓት ሠራዕያን ተባሉ። ያም ሀገር እነዚህ ሠራዕያን የተባሉ የፍርድ ዳኞች የተቀመጡበት አገር ስለሆነ በሠራዕያን ሠራዬ የሚሉት ስም ወጥቶለት እስካሁን ድረስ አገሩ ሲጠራበት ይኖራል ይላል" አሁን ከላይ የተጻፈውን ሁሉ ስምም ለማውጣት ሕግም ለማደራጀት ቻሉ ወይም አልቻሉም ሁሉ ስምም

ለማውጣት ሕግም ለማደራጀት ቻሉ ወይም አልቻሉም ለማለት የሚቻልበት የመግቢያው በር እንደ ታሪክ ጽሑፍ ሕግ አስቀድሞ እነዚህ ሰዎች ካዓረብ አገር ተነሥተው በጦር ኃይል የገቡበት ማስረጃዎች ሲገኝ ነበር እንጅ እንዲሁ በግምት በይመስላል የኢትዮጵ አባቶች ሲጠሩበት የኖሩትን አገር ስምና ቋንቋ ለሌላ አገር እየሰጡ በይመስላል ተጠግቶ በቂ ማስረጃ ሳያመጡ ማምለጥ የሚቻል አይደለምና እኔ የምቃወምበት ዋናው ዓላማዬ ልብ ብለው ያዳምጡ ግዕዝም አስቀድሞ በካም ዘመን ከቋንቋ መረገም በፊት ብለው ያዳምጡ ግዕዝም አስቀድሞ በካም ዘመን ከቋንቋ መረገም በፊት እንደመጣ ከዚያ ዠምሮ እስከ ዛሬ እንደጻና አለ። ይልቁንም የዚሁ እዚህ ዋና ግንዱ ሆኖ ኢትዮጵያ ትገዛቸው በነበሩ አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያ ጥንታዊ ፊደል የተጻፈ በሐውልቶችና በድንጋዮች ላይ መኖሩን ራስዎ አባ ጋስፓሪን የጻፉት መረጃ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተገኝቶ የተጻፈበትን ጊዜበመከራከር ላይ እንገኛለን። ይህም ሐሰት እንዳይመስል (፸፫ ገጽ በ፩ኛው መስመር ይህንም ለማተት ያስብንበት ምክንያት ስሙ ብቻ እንጅ ከፍ ያለው ሥልጣኑና ታሪኩ ሳይታወቅ የነበረው ገደረት ወይም (ዘግዱር) የተባለው የኢትዮጵያ ንጉሥ በዓረብ ደቡብ አገር ተጽፎ በተገኘው ሐውልት ላይ ስሙንና ከፍ ያለውን ሥልጣንነ መንግሥቱን ኃይሉንና ጉልበቱን የሚገልጽ ታሪክ አግኝተን ለመጻፍ ስለ

## ለ እኁድ ጥቅምት

በቃን ነው ይላል)። ይኸውና ከላይ እንዳመለከትሁት የኢትዮጵያ ግዛት በነበሩ አገሮች ላይ በጥንታዊው ግዕዝ ላይ ይገኛል ብየ እንደጻፍኩት ይህን ማስረጃውን ከሩቅም ሳይሆን በዚሁ መጽሐፍ አባ ጋስፓሪን እንደጻፉት ማስረጃውን አቅርቤአለሁ። ሆኖም የተጻፈበትን ዘመን በማሳነስ ክርክር ገና እንቀጥላለን። ስለዘመን አምሳጠራቸው የምንከራከርበት እንደዚህ ነው። እርሳቸው መቸውንም ከውነት የራቁ በመሆናቸው በሐውልቱ ላይ የተገኘውን ጽሑፍ ካመኑ በኋላ

የተጻፈበትን ዘመን አሳጠሩት፡ ይህንም ለመረዳት (በ፸፪ ገጽ ባ፲ኛ መስመር ከጌታችን ከክርስቶስ በፊት ፬፻ ዓ የኢትዮጵያ ነገሥታት ከዓረብ ሳብውያን አገዛዝ ነጻ ወጥተው ብሎ በ፳፪ኛው መስመር ላይ የኢትዮጵያ ንጉሥ በጀግንነትና በቆራጥነት ባሕርን ተሻግሮ ከሠራዊቱ ጋር ተሰልፎ ከዓረብ ነገሥታት ጋራ ጦርነት ያደረገ ገደረት የተባለ ንጉሥ ነው ይላል)። ከላይ እንደተጻፈው እኔ እንዳመለከትሁት ሁሉ አባ ጋስፓሪንም አምነው ጽፈውት እንደሚገኝ ከላይ በ፸፫ኛ ተጽፎ ይገኛል። ፪ኛም ዘመኑን አሳጠሩት ያልኩትን በ፸፪ኛ ገጽ እንደተጻፈው ከክርስቶስ በፊት ባ፬፻ ዘመን ገደረት ሳላሉ። እኔ የምለው ገደረት የነበረው ዘመን የኢትዮጵያው ክብረ ነገሥት በሚለው ከክርስቶስ በፊት ፩ሺ፫፻፶፫ ዘመን ላይ ነው ምን ያህል ዘመን አጕደሉ ፱፻፶፫ ዘመን ማጉደላቸው ነው ስለዚህ ከጽሑፋቸው ላይ አሁንም እንደዚህ ያለ እምነት በመፈለግ ላይ ስለሆንኩ ነው እንጅ መረታቱንማ በገዛ ጽሑፋቸው ዠምረዋል። አሁን እኔ የምለው ከላይ እንዳመጣሁት በቂ ማስረጃ ሳያመጡ እንዲሁ በይመስላል ግዕዝን የደቡብ ዓረብ ቋንቋ ነው ማለት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ገደረት ወደ ዓረብ አገር መዝመቱና አገሩን መያዙ ታምኖ ባ፬፻ ዘመን ላይ ነው መባሉ ከክርራችን እንግዲህ ስለ ግዕዝ አስቀድሞ ወደ ኢትዮጵያ ግዛት ወደ ዓረብ አገር መሄዱ ከታመነልኝ የግዕዝ መሠረት ኢትዮጵያ መሆኗን ማመንና መረታት አለብዎ ፪ኛም ንጉሠ ነገሥት ገደረት ወደ ዓረብ አገር የዘመተ ባ፬፻ ዓ ከክርስቶስ በፊት ብለው ወደ ዓረብ አገር መዝመቱን ካመኑ በ፪ቱም አርስቶች የተረቱ መሆን አለብዎ ቀድሞውን ይህ ነገር በጽሑፍ ላይ የሰፈረ እንዲሁ በከንቱ ነው እንጅ በሕግ አይደለም። ግዕዝን ኢትዮጵያ በእጅዋ ይዛለች ያንች አይደለም የሚል ሲመጣ መርቻውን ይዞ መምጣት አለበት የሚረታበት ሲያመጣ መረታቱ ግን መሆኑን ማወቅ ላባ ጋስፓሪን ዋን ተግባራቸው መሆኑን መገንዘብ አለባቸው። የደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው መንግሥት ይዘው ነበር ለተባለውም። ይልቁንም የኢትዮጵያ ነገሥታት አስቀድመው ከክርስቶስ በፊት ፩ሺ፫፻፶፫ ዓ ቀድሞ በንጉሠ ነገሥት ገደረት ዘመነ መንግሥት ተዋግቶ ድል አድርጎ ስለ ድሉ ምልክት ያቆመው ሐውልት ከተገኘ። ከዚያ ወዲህም ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ተዋግተው ገቡ እንዳይባል ያባ ጋስፓሪንን ቃል ጽሑፍ ያባ ጋስፓሪን ቃል አይጥሰውም ማለት የጠበቀ ሕግ አለ ሰው ሁሉ በጻፈው ቃል እንዲቆም። የጻፍኩት የለም የሚሉ እንደ ሆነ። የኢትዮጵያው ንጉሥ ገደረት ከወጋቸው በኋላ ስንኳን ተዋግቶ ድልን ማግኘት ይቅርና ጦርነት የሚሉትን እስከ መጨረሻው አልዠመሩትም ብለው አባ ጋስፓሪን የጻፉት (በ፸፫ኛ ገጽ በ፴ኛው መስመር እንዲህ ያለ ድል በዓረባውያን ላይ ከተደረገ በኋላ ዓረባውያን ልባቸው ፈጽሞ ስለሞተ ተበቅለውም ብድራቸውን ለመመለስ ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት

## ሎ ሰኑይ ጥቅምት

አልቻሉም ከዚያ ዠምሮ እስካሁን ድረስ የተጻፈውን ታሪክ ስንመለከት ዓረባውያን ወደ ኢትዮጵያ ዘምተው ስንኳን ድል ጦርነት ሞከሩ የሚል ታሪክ አላገኘንም ይላል) እንግዲህ አባ አስፓሪን ከላይ

በሰፈረው ጽሑፋቸው መሠረት የደቡብ ዓረቦች ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ከአዱሊስ እስከ አክሡም እስከ መርዌም ደርሰዋል ኢትዮጵያን ኮፊር ወሰን ድረስ አስፋፍተው ብለው የጻፉትን በዚሁ በራሳቸው ጽሑፍ መሠረዝ ይገባቸዋል። አሁንም በዚሁ ጽሑፍ የተሠረዘ መሆኑን ይህ ፪፻፵፮ኛ ገጽ ምስክር ነው። ዓረባውያን ከዘግዱር (ገደረት) ዠምረው እስከ እስላሞች መበርታት ድረስ በኢትዮጵያ መንግሥት ሲገዙ መኖራቸው ከላይ ተጽፎ ይገኛል። አሁን ክርክራችን ያለበት ሳባ የሚባለውን ስም ለደቡብ ዓረብ በመስጠታቸው ብቻ ነው እንጅ የኢትዮጵያ ቋንቋ ግዕዝ በደቡብ ዓረብ ላይ በቆመው ሐውልት ስለመገኘቱ በኔ ጽሑፍ ላይ እንደተፈጸመ ያስረዳል። ፪ኛ የደቡብ ዓረቦች ፪ኛ ጦርነት እስከ መጨረሻው አለማንሳታቸውን በዚሁ ጽሑፍ መመልከት ነው። ፫ኛ (በ፳፫ኛው ገጽ ባ፲፫ኛው መስመር ይህ ሠራዬ የተባለው አገር ስም ከሳባዊና ከዓረብ ቋንቋ ተለይቶ የወጣ ግዕዝ የተባለው አገር ስም ከሳባዊና ከዓረብ ቋንቋ ተለይቶ የወጣ ግዕዝ የተባለ ይላል)። ሠራዬ የተባለውም ስም ከሳባዊና ከዓረብ ቋንቋ ተለይቶ የወጣ ግዕዝ የተባለ ሲል ተገኘ።

እንግዲህ እኔ ወደ ሩቅ ሳልሄድ ያባ ጋስፓሪንን ጽሑፍ አጥብቆ መመርመር ስለተሻለኝ አሁን ከላይ ከሳባው ከዓረብ ቋንቋ የወጣ ግዕዝ ያሉት ሳባዊና ከዓረብ ማለት ሳባ ኢትዮጵያን ዓረብ የነኑ ዓረብ እንደሆነ ቢታመን ነገሩ ወሰን አገኘ ማለት ነበር። ፩ኛ (በ፷፩ኛ ገጽ በ፳፬ኛው መስመር ሳባውያን የተባሉ ኢትዮጵያውያን መዠመሪያ ያቀኑአቸው ይላል)። እዚህ ላይ ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ይላል ይህስ ደግሞ ምን ማለት ነው። ከላይ ከሳባዊና ከዓረብ ቋንቋ ብሎ ነበር አሁን ደግሞ ሳባውያን የተባሉ ኢትዮጵያውያን ሲል ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ ተገኘ እንግዴህ እንዴት ይሆናል መቸም ከላይ እንደ ተጻፈው ያባ ጋስፓሪንን ቃል ያአባ ጋስፓሪን ቃል አይሽረውምና እንደ ጽሑፉ ቃል ሳባውያን የሚባለው ስም ወደ ኢትዮጵያ ሊመለስ የተገባው መሆኑን እያረጋገጥኩ። ወደ ፊት ምርመራዬን እቀጥላለሁ። ያባ ጋስፓሪንን ጽሑፍ መመርመር ያስደንቃል (በ፷፩ኛ ገጽ በ፳፪ መስመር ከዓረብ ደቡብ አገር ፈልሰው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሳባውያን በዚያ ዘመን ቀይ ባሕርን ተሻግረው አዱሊስ ላይ አረፉ አዱሊስን በከተማነት መሥርተው ጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ወደ ደጋይቱ ኢትዮጵያ ወጥተው በኤርትራ አውራጃ ውስጥ ሽመዛና የተባሉትን አገሮች አቀኑ በዚያውም አገር መላውን ኢትዮጵያን ለመያዝና ለማስፋፋት ሲጓዙ የመሠረቷቸው ከተማዎች ብዙ ናቸው እነርሱም ቆሐይቶ (ቆሎየ) ቶሆንዳዕ ከስከስ መጠራ የሐ የተባሉት ናቸው እነዚህም ከተማዎች ስማቸውንና መላውን ታሪካቸውን ከነሥዕላቸው ከዚህ ቀጥለን በምንጽፈው መጽሐፋችን ላይ እናሳያለን ቀደምት የሆኑ ኢትዮጵያውያን መሥርተዋቸው የነበሩ ከተማዎችና አገሮችንም እስካሁን ድረስ ስማቸው ሳይጠፋ የኖሩ አለመሆናቸው የአዱሊስን ሁኔታ እንዳስረዳነው የነዚህንም ከተማዎች ሁኔታቸውንና ታሪካቸውን ባጭር እናስረዳለን። ከላይ ከደቡብ አገር ፈልሰው ማለት ተሰደው በቀይ ባሕር

# ሊ ሡሉስ ጥቅምት

ተሻግረው አዱሊስ ላይ አረፉና አዱሊስን ከትማ ቆረቆሩ አለና ደግሞ መልሶ (በ፷፮ኛው መስመር ቀደምት የሆኑ ኢትዮጵያውያን መሥርተዋቸው የነበሩት ከተማዎችና አገሮችም እስካሁን ድረስ ስማቸው ሳይጠፋ የኖሩት ለመሆናቸው የአዱሊስን ታሪክና ሁኔታ እንዳስረዳነው የዚህንም ከተማዎች ሁኔታዎችንና ታሪካቸውን ባጭር እናስረዳለን ማለት እንደ ጽሑፉ አዱሊስን የቀድሞዎቹ ኢትዮጵያውያን ያቀኑዋት አስመሰሉና መልሰው ስማቸው ሳይጠፋ የኖሩት ለመሆናቸው ሲል እንደዚህ አድርገው የነገር ማሳረፊያ ምልክት ሰጡና ደግሞ አልፈው የአዱሊስን ታሪክና ሁኔታ እንዳስረዳነው ሲል ደግሞ የነገር ማረፊያ አድርገው የእነዚህንም ከተማዎች ሁኔታዎችንና ታሪካቸውን ባጭር እናስረዳለን ይላል። እሺ ይሁን እነዚህ

ሰዎች ካረብ አገር ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ የገቡ መቼ ነው። ፪ኛ ከእነዚህ ሰዎች ጋር አለቃ የነበረ አንድ ሰው ስሙ የሚታወቅቅ የለም ወይ? ፫ኛ ፭ቱን ከተማዎች የመሠረቱበት ዘመኑ መቸ ነው።

፬ኛ እነዚህ ከተማዎች ሲመሠረቱ እንደ ንጉሥ የነበረው ማን ይባላል።

፭ኛ ቀደምት የሆኑ ኢትዮጵያውያን መሥርቶባቸው የነበሩት ከተማዎችና አገሮች ያልዋቸው የትኛዎችን ነው። ፮ኛ ሳይጠፉ የኖሩ ለመሆናቸው ብለው ነቁጣ አደረጉ። ፯ኛ የአዱሊስን ታሪክና ሁኔታ እንድናስረዳ ነው ሲሉ ስለምን ጻፉ። አይታወቁም ብሎ የመጨነቅ ፖለቲክ ከመጻፍ አስቀድሞ በቀላሉስ ቢበቃ ምን ነበር ሕጋዊ ጽሑፍ አይደለም። ሰው በብርቱ ድካም ታሪክ መጻፉ ምስጋና ለማትረፍ ነበር አባ ጋስፓሪን በሐሰተኝነት ለመጠራት በመዠመሪያ የሮማ ልውካን ለእግዚአብሔር መንግሥት መስበኪያ የነበረችቱን ወንጌል ለሮማ መንግሥት ማስፊያ መስበኪያ አድርገው የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በእርሱ እያፋጁ እስከዚህ አደረሱት። አሁን ደግሞ ፖለቲኩን ከታሪክ ጋር ቀላቅለው እውነተኛ ታሪክ አስመስለው ጽፈው የለቀቁትን እንፍሎዛዊ ታሪክ ዓምድ ይዞ የሚገኘውን ሲመረምሩ ከሐሰት በተቀር ፩ድ እውነት የሌለው ዜሮ የሆነ ይገኛል። (፷፫ኛ ገጽ በ፳፱ነኛ መስመር የዓረብ ሳባውያን እንደራሴዎች ሆነው

ኢትዮጵያን ሲአስተዳድሩ ሲገዙ የነበሩት ሹማምንት ነጋሢ ነጋሢ ይባሉ ነበር። ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ገጽ ፷፬ ኋላ የዓረብ ሳባውያን ከድተው ራሳቸውን ችለው ኢትዮጵያን ነጻ አውጥተው ሲገዙአት ከነበሩት ከነጋሢዎች ወገን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ተብሎ የነገሠው ንጉሥ ስሙ ማን እንደሆነ አልታወቀም ብለን ጽፈን ነበር ይኸውም ከአዱሊስ ዠምረው እስከ ከስከስ ድረስ ያለውን ነገር ያቀኑና ከተማዎቹን የመሠረቱ ነጋሢዎች እውነት ነው እንደጻፍነው ስማቸው ተለይቶ አልታወቀም። ከስከስ በተባለችው ከተማ በተገኘው ሐውልት ላይ ተቀርጾና ተጽፎ እንደ ተገኘው ታሪክ ግን ስሙ የሳሊም የልጅ ልጅ ንጉሥ ወዓራን ሕይወት የተባለ ከፍ ያለውን ታሪክ የሠራ ስሙ የታወቀ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆኖ የገዛ ንጉሥ መገኘቱን እንገልጻለን። ይህም ወዓራን ሕይወት የተባለው ንጉሥ ምንም ስሙ ቢታወቅ የንገሠበት ዘመን ተለይቶ አልታወቀም)። እንግዲህ ያባ ጋስፓሪን ታሪክ ታሪክ ለመሆን የታሪኩን ደምብ አልዘነጋም። ማለት ይኸውና ከሳባውያን ሹማምንቶች ተመርጦ በኢትዮጵያ

# ላ ረቡዕ ጥቅምት

የነገሠው ስሙና የነገሠበት ዘመን ተደብቆ ነበርና አሁን በጭንቅ ስሙ ተገኝቶ ዘመኑ ደግሞ በመፈለግ ላይ ነው። የዘመኑ መገኛ በጣም ሳይቸገር አይቀርም። ከአዱሊስ እስከ ከስከስ ያሉትን ሁሉ ያቀኑና የመሠረቱ ነጋሢዎች ናቸው ተብለው ተጽፎ ይገኛል ደግሞ (በ፷፫ኛ ገጽ ባ፲፫ኛ መሥመር ቶኾንዳዕ በዓዲ ቀይህ አውራጃ ውስጥ ቶኾዳዕ የተባለ ሌላ አገር አለ በዚህም አገር ላይ ጥንታውያኑ ኢትዮጵያውያን ሕዝቦች የመሠረቱት ጥንታዊ ከተማ ነበረበት በዚያም ከተማ ላይ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ያነጹአቸው ትልልቆች ቤቶች ነበሩ። ከዘመን ብዛት የተነሳ በኋላ ግን የቤቶቹ የድንጊያ መሰሶዎች ብቻ ቀርተው እስከአሁን ድረስ ይታያሉ ለዚሁም ማስረጃ የቤቶቹን ምሰሶዎች ሥዕል ከነቅርጹ ይኸውና በዚህ መጽሐፋችን ላይ ይታያል ይላል" እንግዲህ ይህችን ከተማ የሠሩ ፩ድ ያን ጊዜ ነጋሢዎች ናቸው ተብሎ ተጻፈ ደግሞ ሁለተኛ ጥንታውያን የሆኑ ኢትዮጵያውያን የመሠረቱትን ከተማ የነበረውን የድንጊያ ምሰሶዎች ቆመው ይታያሉ ይላል። ይህችን ቶኾዳዕን የተባለች ከተማ ያባ ጋስፓሪን ቃል ለሁለቱ ስለ ሰጠ ነገሥ የተባለው ወዓራን የነገሠበት ዘመን የሚታወቅ ካልሆነ እንዲሁ በይመስላል በማለት ዋና ታሪክ ነው ለማለት የሚታወቅ ካልሆነ ከስከስ በተባለችው ከተማ ተቀርጾና ተጽፎ እንደ ተገኘው ታሪክ ግን ስሙ

የሳሊም የልጅ ልጅ ንጉሥ ወዓራን የሚል ጽሑፍ በሐውልቱ ጽሕፈት ሥዕል በዚህ መጽሔፍ ስለምን የለም።

አሁን ከላይ ሲደበቅ የቆየው የንጉሥ ስም አሁን በሐውልቱ ላይ ተገኘ ማለት እውነት ስልምን በሥዕሉ ሳይገለጥ ቀረ። ያባ ጋስፓሪን አሳብ የኢትዮጵያን ክብር ለመቀነስ ለማዋረድ ነበር ከንቱ ድካም አተረፉ እንጅ እውነት እሺ ብሎ የሚለቅ አይደለም። አሁንም ይህ በሐውልት ተጽፎ አገኘሁት ያሉት የሐሰትዎ አስደናቂነት የዓረብ ነገሥታት እንደራሴዎች ውስጥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የተመረጠው ንጉሥ ባሠራው ሐውልት ላይ ስሙ የሳሊም የልጅ ልጅ ወዓራን ሕይወት የሚባል ተገኝቷል ብለው የጻፉት እውነተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የውቅያኖስ ባሕር ጨው መሆኑን ትቶ ወተት ሆነ ብሎ እንደመናገር ያለ ነው። ማለት ያባ ጋስፓሪን ፖለቲከሰው ያውቀዋል ሳይባል የተሠራ ነው። እንዳይመረመር የሚል ማስረጃ ካልተገኘ በተቀር ያባ ጋስፓሪንን ታሪክ ምርመራየን አልተውም ይህን ከአዱሊስ እስከ ከስከስ ያለውን ከተማ አቅንተው ከነበሩ ነጋሢ ነጋሢ ከሚባሉት መካከል ተመርጦ ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሆነ ስሙም የሣሊም የልጅ ልጅ ወዓራን ሕይወት የሚል ጽሑፍ ተገኘ ሲሉ ጽሑፉ ከቀኝ ወደ ግራ መሆኑን ለማረጋገጥ አልሞከሩትም ይህ የምጽፈው ያባ ጋስፓሪንን የሐሰት መዝገብ በርክቶ እንዲታይ በማለት ነው እንጅ ነገሩ እውነት አለመሆኑንና ገና ከ፹፫ኛ ገጽ ላይ ተረድቸዋለሁ። አሁንም በምርመራው እንጨምርበት። በዚሁ በ(፷፱ነኛው ገጽ ባ፲፪ኛው መስመር ይህ ወዓራን የተባለው ንጉሥ ምንም ስሙ ቢታወቅ የነገሠበት ዘመን ተለይቶ አልታወቀም። ነገር ግን ታሪክና ቅርጽ መርማሪዎች ይህን በከስከስ ከተማ ላይ የተገኘውን ቅርጽ መርምረው ከሌላ ዓይነት ቅርጽ ጋራ

አመዛዝነው የተቀረጸበትን ዘመን ገምተው እንዳስረዱን ከክርስቶስ በፊት ፬፻ ወይም ፫፻ ዓመት ቀደም ብሎ ይሆናል ብለው ነው ይላል) ። እንግዲህ ያባ ጋስፓሪን ሐሰት የታሪክ መዝገብ እንዲበረክት ስል ለአንባቢዎች ደስ አለ

# ሌ ሐሙስ ጥቅምት

ማሰኘቱን አልዘነጋሁም። ይህ ንግግር በግድ ስለመጣብኝ ነው። ነገሩ ሐሰት ያውም ወሰን የሌለው። የታሪክ ሕግ የሌለው አስቸጋሪ ነገር ስለ ገጠመኝ ነው። ይኸውና ከላይ በሐውልቱ ላይ የተጻፈ ስም ተገኘ ብለው አስመስለው ጽፈው ደግሞ ያነኑ ውሸትኑን የውሸት ማስረጃ ጽፈው ካ፬፻ እስከ ፫፻ ባለው ላይ ነው ብለው ጽፈው ተገኘ ይህ ሁሉ ነገር በፍጹም ሐሰትነቱን የሚአስረዳ ራሳቸው የጻፉት ይገኛል እሱም "፸፪ ገጽ በ፱ነኛው መስመር ከጌታችን ከክርስቶስ በፊት ፬፻ ዓመት የኢትዮጵያ ነገሥታ ከዓረብ ሳባውያን አገዛዝ ነጻ ወጥተው ራሳቸውን እንደቻሉ ከዚህ በላይ እንደጻፍነው በሰፊው አስረድተናል። ከዚህ በኋላ እስከ አያሌ ዓመታት በሰላምና በፍቅር እየተሳሰቡ ቀይ ባሕርን እየተሻገሩ ለመነገድ ወደ ጥንታዊ አገራቸው ይመላለሱ ነበር ከዚያም ከጥንት አገራቸው ከሚኖሩት ሕዝቦች ጋር እየተዋዋሉ በወርቅና በብር በዕጣንና በከርቤ በዝኆን ጥርስና በዝባድ ሲነግዱ ቆይተዋል። ጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ግን በንግድና በሌላም አሳብና እየተለያዩ ስምምነት። ስላጡ ዓረባውያን ጠብ አንስተው ኢትዮጵያውያንን እጅግ በደሏቸው። በዚህ የተነሣ የኢትዮጵያ ንጉሥ አዝኖ ሠራዊቱን አስከትቶ ተነሳና ዓረብ አገር ዘመተ ይላል)። እንግዲህ ነገሩ የተመሰቃቀለበትን እንለይ ከላይ ከክርስቶስ በፊት ባ፬፻ ዘመን ላይ የሳሊም የልጅ ልጅ ወዓራን ሕይወት የተባለው ነግሦ ነበር ሐውልትም አቆመ ተባለ። ፪ኛ አሁን ከላይ እንደተጻፈው ከክርስቶስ በፊት በ፬፻ ዘመን የኢትዮጵያ ነገሥታት ከዓረብ አገር ነጻ ወጡ አለ። ከ፪ቱ ዓይነት ጽሑፎች እውነት ሆኖ የሚጨበጠው የትኛው። ወዓራን የተባለው ኢትዮጵያዊ ነው ለማለት እንዳይመለሱ በ፷፬ኛ ገጽ በ፲፪ኛው መስመር በዓረብ ሳባውያን እንደራሴዎች ሁነው መኖራቸውን ጽፈው አስረድተናል ትንሽ የቀረው

ታሪክ እኒህ ነጋሢ ነጋሢ ተብለው በኢትዮጵያ ላይ ተሹመው የነበሩ እንደራሴዎች ጥቂት መሆናቸው ቀርቶ በመላዋ የኢትዮጵያ አውራጃ ላይ ሠልጥነው ቆይተው ግን ከነርሡ ወገን የሆነውን ፩ዱን ነጋሢ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት አሰኝተው በመላው አንግሠውት ነበር ተብሎ የተጻፈለት ይህ የሳሊም የልጅ ልጅ ወዓራን ሕይወት የተባለው መሆኑን መረዳት ነው። እንግዲህ ከላይ የተጻፈው ሁሉ ያባ ጋስፓሪንን ታሪክ የውሸት ውሸት ፖለቲክ መሆኑን ለአንባቢዎች እገልጻለሁ። ከላይ የተጻፈው ሁሉ ፍጹም ሐሰት መሆኑን ደግሞ ወደፊት በሚመጡ ዓምዶች ይገለጻል። ያባ ጋስፓሪን ታሪክ አስደናቂ መሆኑን ወደፊት እያጣራሁ በርቀት የተሠወረውን ተንኮል እየገለጥኩ አወጣለሁ (በ፷፱ነኛ ገጽ ባ፲፯ኛው መስመር መጠራ የሳባውያን ዘር የሆኑት ኢትዮጵያውያን ያቀኑት በኤርትራ አውራጃ በሰነዓፌ አጠገብ የሚገኝ መጠራ የተባለ አገር አለ። አገሩም ጥንት የነርሱ ከተማ መሆኑን የሚገልጽ ታሪክ አግኝተናል። ታሪኩም በዚሁ መጠራ በተባለው አገር ላይ ጥንት ከተማ በነበረ ጊዜ ቀርጸው ያቆሙት በጣም ከፍ ያለ ረዥም የድንጊያ ሐውልት ይገኛል። ሐውልት የመንግሥት ምልክትም የሠለጠነ ንጉሥ ካልሆነ በቀር ማንም እንደማያቆመው የታወቀ ነው በዚህም ሁኔታ ቀደምት ከሆኑት ኢትዮጵያውያን እጅግ የሠለጠኑ ነገሥታት እንደነበሯቸው ይገልጻል። እነዚህ ቀደምት የሆኑ የኢትዮጵያውያን

# ል ዓርብ ጥቅምት

በዚያ ዘመን የኦሪትን ሕግና ሃይማኖት የተቀበሉ እኩሌቶች በጨረቃና በኮከብ በሌላም ልዩ ልዩ ጣዖት የሚሰግዱ ነበሩ። እነዚህ በመጠራ ከተማ ይኖሩ የነበሩ ሳባውያን የተባሉት ኢትዮጵያውያን ያነን ከዓረብ ደቡብ አገር ያመጡትን መንግሥታቸውን የሃይማኖታቸው ምልክት የሆነውን ጨረቃና ኮከብ እንደያዙ በዚያው ተቀምጠው ነበር ይህም

የሚያመለክቡት ጨረቃና ኮከብ ከዓረብ ደቡብ አገር ይዘውት የመጡት ለመሆናቸው ማስረጃ በዚያው እነሱ ባቆሙት ሐውልት ላይ አንሥተን ሥዕሉን በመጽሐፋችን ላይ እናሳያለን) አሁን ከላይ የተጻፈውን ስንመለከተው ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ መሠረት የሌለው መሆኑን ያስረዳል። መጠራ በቆመው ሐውልት ላይ የሚታየውን የፀሐይና የጨረቃ ምልክት ስላዩ ዛሬ በዓረብ አገር ዓላማ ላይ የጨረቃና የኮከብ ምልክት ስለሆነ። ይህ በዓረብ መንግሥት ዛሬ የሚታየው የጨረቃና የኮከብ ምልክት በደቡብ ዓረቦች አገር ላይ የነበረ ስለ መሰላቸው ባለማስተዋል የጨረቃና የኮከብን ነገር ይዘውት የመጡ ለመሆናቸው ምልክቱ በሐውልቱ ላይ የሚገኘው የጨረቃና የኮከብ ምልክት ነው ብለው ጽፈዋል። ያባ ጋስፓሪን ታሪክ እንዲሁ በይመስላል የተጻፈ ግብጽ ሥራ መሆኑን ይህ ጽሑፋቸው ያስረዳል። የታሪክ ሰው የሆነ ቢሆን የዓረቦች ዛሬ የሚታየው ዓላማ በደቡብ ዓረብ አገር ላይ የቆመ ከመቶ ዝምሮ መሆኑን መመርመርን አስበው ይህን ከመጻፍ በዳኑ ነበር። በደቡብ ዓረብ አገሮች ላይ ይህ ጨረቃና ኮከብ ያለበት ዓላማ የተተከለው የሙሐመድ ሃይማኖትና መንግሥት መሥፋፋት ከጀመረ በኋላ የኢትዮጵያ ግዛትነቱ ቀርቶ በእስላሞች ግዛት ሲሆን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተነቅላ ያረቦች ዛሬ የእስላሞች ዓላማ ከተተከለች በኋላ መሆኑን ሳይገነዝቡ ባለማስተዋል ዓይናቸውን ጨፍነው እንደዚህ አድርገው ልብ ወለድ ፖለቲክ ሲጽፉ ይገኛሉ።

የደቡብ ዓረቦች አገር እርሳቸው እንደጻፉት እንኳ ከክርስቶስ በፊት ፬፻ ዓ ዝምሮ ሲል ይገኛል በዓረብ አገሮች ላይ የኢትዮጵያ ነገሥታት ብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት አሠርተውባቸው እንደነበር ታሪክ ይነግረናል። ይህንም መላው ዓለም ያውቀዋል። በዚያ ጊዜም ከአይሁድ በተቀር እንደ ዛሬው እስላምና ክርስቲያን እንዳልነበረ ታሪክ ይነግረናል። የጨረቃና የኮከብ ምልክት ያለበት ዓላማ ዛሬ በደቡብ ዓረብ አገሮች ላይ ስላዩ በኢትዮጵያ ላይ ፀሐይና ጨረቃ ያሉበት ሐውልት ቢአዩ መሠረቱን ሳይመለከቱ ፀሐይና

የጨረቃ ሥዕል ከላይ ያለበትን አይተው ይህን ሐውልት የሠሩ የደቡብ ዓረብ ሰዎች ናቸው ብለው ጽፈው ለዓለም አንባቢዎች በታሪክ ገበታ ላይ አስቀመጡት። የታሪክ አንባቢዎችንም ለማጥገብ አለመቻሉን ይኸውና እኔ ጉድለቱን እየገለጽኩ አሳያለሁ። ስለዚህ "ከ፷፫ ገጽ-፸፪ ገጽ ስለ የሳሊም የልጅ ልጅ ወዓራን የተባለው ታሪክ በፍጹም ሐሰቱን ጽፈውታል እውነት አይደለም። (፸፩ኛ ገጽ በልዩ ልዩ ከሆነው ላይ የሚገኘው ጽሑፍ ይህ መበጠራ አገር ላይ የሚገኘው ሐውልት በዚህም ሐውልት ከፍ ብሎ ከጫፍ የተቀረጸው ቅርጽ የሳባውያንን ምልክት ያሳያል። ዝቅ ብሎ በጥንታዊ ግዕዝ የተቀረጸው ቅርጽ ግን የቀደምት ኢትዮጵያውያን ጽሕፈት መሆኑን ያስረዳል ይላል።" የጥንታውያን ቅርጽ ነው ብለው ጽሑፉንም ጥንታዊው ግዕዝ መሆኑን ተረድተው ከጻፉ በኋላ እንደ ገና

# ሎ ቀዳም ጥቅምት

ተመልሰው "በዚህ ሐውልት ላይ የተገኘው የሁለቱ ወገኖች ቅርጽ የሳባውያን የ፪ቱን ሕዝቦች ታሪክ አጣምሮ እያከታተለ በጽሑፍ ያስረዳል ይላል።" እንግዲህ የሁለቱን የተባለበት ምክንያት ፩ኛው የጥንታውያን ኢትዮጵያውያን ጽሑፍ ያለበት መሆኑን በመገንዘብ ነው። ፪ኛው የሳባውያንን ምልክት የተባለው ከላይ እጫፍ የፀሐይና የጨረቃ ሥዕል በመታየቱ ብቻ ነው እንጅ እንዲያውም አለመኖሩ አውቀውት አይደለም። እንግዲህ ባላወቁትና ባልተረዱት ነገር ምክንያት ፈልገው ባይናቸው ያዩትን ነገር ባላዩት ለውጠው በማስመሰል የማይገጣጠመውን ነገር የገጠምኩት መሰላቸውና በሐውልቱ ላይ ተጽፎ ያዩትን ጥንታዊ ፊደል እያኮሰሱ ከላይ ያዩትን የፀሐይና የጨረቃን ሥዕል ትርጓሜውን ሳይመርምሩ እንዲሁ በመላ ዛሬ በዓረብ መንግሥታ ግዛት ውስጥ የጨረቃና የኮከብ ዓላማ ስላዩ በቀድሞ ዘመን ይህ የጨረቃና የኮከብ ዓላማ የነበረ በማስመሰልና በማጭበርበር ምክንያት ገብተው የኢትዮጵያን መጻሕፍት መኖርና እንዲያውም ኢትዮጵያ ፊደል አልነበራትም ይህ አሁን ያለው ግዕዝ ብቻ ፊደሎችም ከደቡብ አረቦች የመጡ ናቸው ይህ አሁን ያለው ግዕዝ ብቻ ፊደሎችም ከደቡብ አረቦች የመጡ ናቸው እስከ ማለት ደርሰው ይገኛሉ። ለዚህም

መረጃ (ባ፲፪ኛ ገጽ ፩ኛ መሥመር ለኢትዮጵያውያን ተማሪዎች የሳባውያንን ታሪክ እንደሚአውቁት የሚአስገድድ ሌላ ምክንያት ደግሞ አለ። ይኸውም ምክንያት የቋንቋ ነገር ነው ተማሮች መልካም አድርገው ከሳባውያን ቋንቋ የመጣ ነው ይላል"። እንግዲህ ያባ ጋስፓሪን ቃል ፪ት መሆኑ መመልከት ነው መጠራ ላይ የሚገኘው የሐውልት ጽሑፍ የማን አገር ፊደል ነው ለማለት ይቻል ይሆን። አባ ጋስፓሪንም የጥንታውያን ኢትዮጵያውያን ጽሑፍ መሆኑን አረጋግጠው በዚህ ሐውልት ላይ የሁለቱ ወገኖች ቅርጽ የሁለቱን ሕዝቦች ታሪክ አጣምሮ ይዟል ብለው መስከረዋል።

በሐውልቱ ላይ የሚገኘው ጽሑፍም እንደ ዛሬው ግዕዝ ከግራ ወደ ቀኝ የሚሄድ መሆኑን አስረጅነቱን ይዞ ይገኛል። ይህ በመጠራ ላይ የሚገኘው ሐውልት በ፫ኛው ገጽ ተሥሎ የሚገኘው ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ያለ ነው እንዳይባል (በ፰፱ነኛ ገጽ በ፳፯ኛው መስመር እነዚህ ቀደምት የሆኑ ኢትዮጵያውያን በዚህ ዘመን እኩሌቶቹ የኦሪት ሕግና ሃይማኖት የተቀበሉት እኩሌቶቹ በጨረቃና በኮከብ በሌላም ልዩ ልዩ ጣዖት የሚሰግዱ ነበሩ። እነዚህ በመጠራ ከተማ ላይ ይኖሩ የነበሩ ሳባውያን የተባሉ ኢትዮጵያውያን ግን ያነን ከዓረብ ደቡብ አገር ያመጡትን የመንግሥታቸውንና የሃይማኖታቸውን ምልክት የሆነውን ጨረቃና ኮከብ እንደያዙ እንደዚሁ እያመለኩበት ጨረቃና ኮከብ እንደያዙ እንደዚሁ እያመለኩበት ጨረቃና ኮከብ ከዓረብ ደቡብ አገር ይዘውት የመጡ ለመሆናቸው ማስረጃ በዚያው እነርሱ ባቆሙት ሐውልት ላይ አንስተን ሥዕሉን በመጽሐፋችን ላይ እናሳያለን ይላል)። እንግዲህ ይህ በመጠራ ላይ የሚገኘው ሐውልት በኦሪት ጊዜ የነበረ መሆኑን ለመረዳት ከላይ ስለ ኢትዮጵያዊን ሲጽፍ እኩሌታዎቹ የኦሪትን ሕግና ሃይማኖት ያመኑ በማለቱ ያስረዳል። እንግዲህ አስቀድሞ ከልደተ ክርስቶስ በፊት የግዕዝ

ጽሑፍ መኖሩ መረጋገጡ ትክክል ሊሆን ነው። ለዚሁም ድጋፍ የሚሆነው ጽሑፍ ከግራ እጅ ወደ ቀኝ እጅ ሆኖ መገኘቱ ነው።

# ሐ እጉድ ጥቅምት

ይህንም ለመረዳት በ፻፲፯ኛ ገጽ ላይ ተሥሎ ባጠገቡም መጠራ ላይ በሚገኘው ሐውልት በጥንታዊው የኢትዮጵያ ፊደል የተቀረጸ ጽሑፍ ይላል። እንግዴህ ከላይ በተጻፈው መሠረት የኢትዮጵያ ፊደል ግዕዝ መኖሩ የተረጋገጠ መሆኑ ማለት ነው። አሁን ከላይ "ከ፰፱ነኛው ገጽ በ፳፯ኛው ከጠቀስናቸው ቃላት ላይ ሁለት ነገሮች ማስረጃዎች መያዛችንን ማስተዋል አለ። ፩ኛው ስለ ግዕዝ ፊደሎች ካባ ሰላማ መምጣት አስቀድሞ የጥንታውያን ኢትዮጵያውያን ጽሑፍ መረጃ። ፪ኛው በኢትዮጵያ ሕገ ኦሪት እንደ ተሰበከ የሚአስረዳ። እነዚህ ሁለቱ ነገሮች ከአባ ጋስፓሪን አምልጠው የቀሩ ናቸው እንጅ ባ ጋስፓሪን ፪ቱን አርስቶች አጥብቀው ካገር ያጠፋኋቸው መስሏቸዋል። ኢትዮጵያ በዘመነ ኦሪት መጻሕፍተ ኦሪትን ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ አስገልብጣ አስመጥታ ሕገ ኦሪትን ሌዋውያንም ጽላተ ኪዳንን ይዘው መጥተው ኢትዮጵያ የኦሪትን ሕግ ፩ኛ ሕገ ግዝረትን ፪ኛ አክብሮ ሰንበትን ይዛ መቆየቷን አባ ጋስፓሪን ክደዋል ስል የመጻሕፍተ ብሉያትን መምጣት እንደ ጽላተ ሙሴ ሙሉ ለሙሉ ደፍረው ሌዋውያን ብሉይ ኪዳንን ይዘው መጡ አላሉም። ያሉት እንዴት ነው ለሚል በ፶፫ኛ ገስ በ፫ኛው መሥመር ሌዋውያንና ሌሎቹ ከኢየሩሳሌም የመጡ ነገዶች ሁሉ በመንግሥቴ ግዛት ላይ ሃይማኖትን ብሉይና የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት የ፳ኤልን ትእዛዝ ማለት ነው ይላል)። በጣም ተገልጾ አልተጻፈውም ማለቴ ነው እንጅ እምነቱም ከደቱም በጣም ሳየልይ እዚህ ላይ አኀበር ሆኖ ቀርቷል። ከሌላ ቦታ ላይ ግን ስንኳንስ ብሉይ ኪዳን ሊጻፍ ይቅርና የፊደሎች ደረጃዎች እንኳ የተደራጁ በከሣቴ ብርሃን ነው ተብሎ ይገኛል። መረጃውን ለፈለገ "በ፻፳፩ኛ ገጽ በ፳፪ኛው መሥመር በቅዱስ ፍሬ ምናጦስ ጊዜ ወንጌልን መተርጐም ዠምረው በኋላም ቅዱሳት መጻሕፍትን በሙሉ ከጽርዕ ወደ ግዕዝ መልሰውታል" ያለውን ይመልከት ስለ ፊደሎች መደራጀት ደግሞ "በ፻፲፫ኛ ገጽ ባ፲፰ኛው መሥመር መሠረታዊው ግዕዝ ከተወለደ ዠምሮ እስከ ትልቁ ኤዛና ድረስ አቅም አዳም እንዳልደረሰ ሕፃን አድርገን እንቆጥረዋልን ይህም ምሳሌ እነዚህ ፳፯ቱ የግዕዝ ፊደሎች ባ፩ኛ ደረቅ

ግዕዛቸው ሲጻፍባቸው ይኖር ነበር እንጅ እንዳሁኑ አጻጻፍ ካዕብ ሣልስ ራብዕ ኃምስ ሣድስ ሳብዕ አልነበረም። ከዚህ በኋላ ትልቁ ዔዛና የጽርዓውያንን ፊደል አጻጻፍ ተከትሎ ከካዕብ ዠምሮ እስከ ሳብዕ ያሉትን ፯ቱን ፊደሎች በዝርዝር እየጻፈ ሕዝቡ እንዲለምዳቸው አደረገ ይላል" ይኸውና ስለ ፊደል ደረጃዎችም ከላይ የተጻፈውን መመልከት ነው። ያባ ጋስፓሪንን ረቂቅ ተንኰል ለመረዳት ከላይ በተጻፈው "በ፶፫ኛ ገጽ በ፫ኛው መሥመር ሌዋውያን ወደ ኢትዮጵያ በመንግሥቱ ግዛት ላይ ሃይማኖትንና የብሉይ ኪዳንና ሥራት አቆሙ ኡ ኡ አባ ጋስፓሪንን ለመጠየቅ ያሉ አሳቦች

፩ኛ የኢትዮጵያን መጻሕፍተ ብሉያት አስቀድሞ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመን ዓረቦች ግዕዝን አመጡ የሚሉበት

፪ኛ የደቡብ ዓረቦች ግዕዝን አመጡ የሚሉበት

፫ኛ የኢትዮጵያን የደቡብ ዓረቦች ይገዟት ነበር የሚሉበት

፬ኛ ሳባ የሚባለውን የኢትዮጵን ስም ለደቡብ ዓረብ የሰጡበት

፭ኛ ኢትዮጵያን ግብፅ ትገዛት ነበር የሚሉበት

፮ኛ ግዕዝን እስከ ዔዛና ዘመነ መንግሥት አቅመ አዳም እንዳልደረሰ ሕጻን ሆኖ ነበር ያሉበት።

# ሑ ሰኑይ ጥቅምት

፯ኛ በ፻፫ና በ፻፰። በ፻፹፯ ገጾች በጥንታዊ ፊደል ከቀኝ ወደ ግራ እያዞሩ የጻፉበት። በነዚህ ሁሉ ሥራዎች ይህን ያህል የደከሙበት ምክንያቱ ምን ይሆን። በነዚህ በ፯ቱ አርስቶች የተዘረዘሩ ነገሮች ሁሉ ሲያያዝ እንደምጣው በኢትዮጵያና በኢጣልያ መካከል ፖለቲክ መሪዎች እነዚህ የቤተ ክህነት ልብስ ለብሰው ውስጥ ለውስጥ እየሰበኩ የኢትዮጵያን ሰላም የሚአጠፉ እነዚህ የሮማ ልዑካን መሆናቸውን የማይረዳ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለኝምና አሁንም እነዚህን ከላይ የተጻፉት ፯ቱን አርስቶች በምን ምክንያት ተጻፉ ስንኳንስ እንደዚህ ያለ ታላቅ ነገር በመካከሉ ያለበት የሰው አገር ተወላጅና የሀገር ተወላጅ እንኳ ቢሆን ከፍ ያለ የሀገር መሠረት መንካት ሕግ የሚፈቅድ አለመሆኑን ማስታወስ አለ። ይህም በኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት ሕገ መንግሥት በ፴፱ነኛው አንቀጽ የሕዝቡን መልካም ጠባይ ወይም ፀጥታና ወይም በፖለቲካ ረገድ የሚያውክ ካልሆነ በቀር በንጉሥ ነገሥቱ መንግሥት ግዛት የሚኖሩ ሰዎች የሃይማኖታቸውን ሥርዓት አክብረው በነጻ ከመፈጸም አይከለከሉም የሚለውን መመልከት አስፈላጊ ነበር። ይህ ጽሑፍ ጸጥታን የሚቃወም ፖለቲክ ነው። አባ ጋስፓሪን ይህን ሕገ መንግሥት አልጠበቁም ፪ኛም በሕገ መንግሥቱ ፻፳፫ኛው አንቀጽ ማንም ሰው የሃይማኖትን ሥራና የሃይማኖትን ድርጅት በሕግ እንደተፈቀደው ካልሆነ በተቀር ለንግድ ማስፋፊያ አድርጎ አይሠራባቸውም የሚለውን አልተመለከቱም ሕገ መንግሥቱ ያስታወሳቸውንና ያስጠነቀቃቸውን ያልተገነዘቡ ስዎች ሕጉ እንደሚጠብቃቸው ይጠብቃቸዋል እነሱ ግን አላወቁትም።

እንግዴህ ወደ አባ ጋስፓሪን እንመለስ አባ ጋስፓሪን መጻሕፍተ ብሉያትን አስቀድሞ ኢትዮጵያ አልመቱም ማለታቸውን የሚገልጸው (በ፻፳፬ኛ ገጽ በ፳፩ኛው መሥመር በቅዱስ ፍሬ ምናጦስ ወንጌልን መተርጐም ዠምረው በኋላም ቅዱሳት መጻሕፍትን በሙሉ ከጽርዕ ወደ ግዕዝ መልሰውታል በሚለው ጽሑፍ ነው። ይህም አጻጻፍ የእምቢታና የሰው መናቅ ነው እንጅ የሮማ ልዑካን በኢትዮጵያ የሚገኙበትን መጻሕፍተ ብሉያትን አሳምረው ከዓለም መጻሕፍተ ብሉያት የተለዩ መሆናቸውን እንደሚአውቁ አሥመራ በታተመ ብሉይ ኪዳን ማወቃቸውን አውቃለሁ። ግን ሆነ ብለው አውቀው የሠሩት ነገር ነው። ከአባ ጋስፓሪን ታሪ "፸፫ኛ ገጽ ፲፬ኛ መሥመር በኢትዮጵያ አካባቢ ወደሚገኙት ሌሎች አገሮች መመላለስ የነዚህንም ነጋዴዎች ቋንቋ ጽርዓዊ ስለ ነበረ በሚሄዱበትና በሚነግዱበት አገር ሁሉ ጽርዓውያን ሲመላለሱባቸው የነበሩበትም አኅጉሮች በምሥራቅ በኩል ያሉት እስከ ህንድ አገር በምዕራብ በኩል

ያሉት እስከ ሮም ድረስ የነበሩ አጎጉሮች ናቸው። እነዚህም ነጋዴዎች ጥበብ መርማሪዎች የሆኑ ጽርዓውያን በቀይ ባሕር ዳር ለዳር ሲመላለሱ የመርከብ ማረፊያዎች የሚሆኑ ብዙ ወደቦች አልፈው አቋቁመው ነበር ትልቋ ወደብ ከሳባውያን በጽርዓውያን ተቋቁማ የፈረሰችው አዱሊስ የተባለች መዲና ናት ብለዋል)። አሁን ሆነ ተብሎ ተጽፎ የሚገኘው የጽርዕ ነጋዴዎችና ጥበብ መርማሪዎች ብዙ ወደቦች አልፈው አቋቁመው ነበር ወደቢቱም አዶሊስ እንደ ሆነች ተጽፎ የሚገኘውን እንግዲህ ማንም አንባቢ በጥብቅ በመረመረው ጊዜ ነጋዴ ሰው

# ሐ. ሠሉስ ጥቅምት

በሌለበት በረሃ የሚቀመጠው የያዘውንስ ለማን ሊሸጥ የሚፈልገውንስ ከማን ሊገዛ ነው ተብሎ ይገመታል አሁን ይህን ነገር እውነት ለማስመሰል በዓምድ ላይ ማስፈር በታሪክ የተገባ ነውን። በዚያ ጊዜ በመርከብና በጀልባ የሚሄዱ ነጋዴዎች ፈረንጆች ብቻ አልነበሩም ኢትዮጵያም የባሕር ግዛት ስለነበራት ብዙ

መርከቦችና ጀልባዎች እንደነበሯት የሚካድ አይደለም። ከውጭ የሚመጡትም ከየወደቦቹ ላይ የሚገኙትን ልዩ ልዩ ሃብቶችን የሀገር ተወላጆች እየሰበሰቡ እነ ዕንቁን እነ የከበረ ድንጋይን አልማዝን ይህን የመሳሰሉ ልዩ ልዩ ሃብቶች ይገኙ ስለነበረ የውጭ አገር ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ ወደቦችና ታላላቆች ከተማዎች ድረስ እየመጡ ይነጋገሩና ይነግዱ እንደነበር የሚካድ አይደለም። እስቲ በማያውቀው አገር ሄዶ ዕንቁና አልማዝ የከበረ ድንጋይ ፈልጎ የሚአገኝ እንደ ምን ያለ ሰው ነው። ይህን የማያጠግብ ጽሑፍ እዚህ ላይ አስፍረውት የሚገኘው በኢትዮጵያ ወደቦች ላይ ሰው አልነበረባቸውም ለማለት ነው። ይህን ማለትም አሁን ኢጣልያኖች ሰፍረውባቸው የሚገኙትን ወደቦች አዲስ ቅኝ አድርጎ ባለርስት ለመሆን ታስቦ ነው። ይህን ፖለቲክ በታሪክ አስታኮ ለዛሬውም ትውልድ ለማስጠናት ለመጭውም ትውልድ ዓምድ አሲዞ ለመቆየት ታስቦ የተሠራ መሆኑን እኛ ፖለቲክ በታሪክ አስታኮ ለዛሬውም ትውልድ ለማስጠናት ለመጭውም ትውልድ ዓምድ አሲዞ ለመቆየት ታስቦ የተሠራ መሆኑን እኛ መገመት አንችልም ማለት ነው። እነዚህ ቦታዎች በኢጣልያ ተወላጅ እጅ የሚገኑ የማይንቀሳቀሱ ሃብቶች የኢጣልያኖች ተወላጆች ተላላፊ ሆኖ ሲገኝ የኢትዮጵያ ወደብ ባላባቶች ደም ውኃ ሆኖ በከንቱ ፈሶ መቅረቱ ማለት ነው። (በ፳፱ነኛው ገጽ በ፲ኛው መሥመር የጽርዓውያን ቋንቋቸውና እውቀታቸው ባገሩ ሕዝብ ላይ የሠለጠነ እንደ መሆኑ መጠን የንግድ መለዋወጫ የሆኑ ገንዘቦች ሁሉ የታተሙት በጽርዓውያን ቋንቋና ስም ነው የአክሡም ነገሥታት መሥሪያ ቤቶችም መዝገባቸውን የሚመዘግባቸው የቃል መለላከ የሚጻጻፉባቸው ደብዳቤዎችም እዲሁም በትምህርት ቤቶች ውስጥ ለወጣቶች የሚሆን እውቀት የሚገልጹባቸው በጽርዕ ቋንቋ ነበረ። የፅርዕ ቋንቋ በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ ላይ የተስፋፋ በመሆኑ መጠን ከእብራይስጥና ከሌላ ከልዩ ልዩ ቋንቋ ወደ ጽርዕ ይገለበጥ ነበር። እንደዚህ ሆኖ ከቆየ በኋላ የግዕዝ ቋንቋ እየሠለጠነ የጽርዕ ቋንቋ እየተገለበጡ ወደበረታው ወደ ዘመናዊ ግዕዝ ተተረጐሙ ግዕዝ ቋንቋም በኢትዮጵያ ላይ ሠልጥኖ የሃይማኖትና የማኅሌት መጻሕፍት ተጻፉበት ይላል" እንግዲህ ከላይ ለተጻፍው በንግድ ገንዘቦች ላይ ባ፩ድ ጐን በጽርዓዊ ቋንቋ ተጽፎ መገኘቱ ስለንግድ ግንኙነት ሁለት አገሮች ላይ እንደነበረ ያስረዳል ይኸውም ትልቅነቷን ያመልክታል። ፩ኛ የአክሡም ነገሥታት መዝገባቸውን የሚመዘገቡባቸው የተባለው ለ፩ድ መንግሥት በራሱ ቋንቋ ቢጻፍለት ያስመግናልል እንጅ አስነዋሪ አይደለም ፪ኛ ለወጣቶችም ትምህርት ቤት አቁሞ ነበር የተባለው ራሳቸውን የመቻል አሳብና ሥራ እንደነበራቸው የክብር ማስታወቂያ ነው ፫ኛ የጽርዕ ቋንቋ በኢትዮጵያ ላይ የተስፋፋ እንደመሆኑ መጠን ከዕብራይስጥና ከሌላ ልዩ ቋንቋዎች እየተረጐሙ ማለት (ከግዕዝም እንደ ማለት ነው።) ወደ ጽርዕ ተተረጐመ ይህቺ በፍጹም ልብ ወለዲቱ ሥራ ናት። ፬ኛ ከዚህ በኋላ ደግሞ የግዕዝ ቋንቋ እየሠለጠነ የጽርዕ ቋንቋ እየደከመ ሄደ ከመድከሙ የተነሳም የኢትዮጵያ መጻሕፍት ሁሉ

# ሓ ረቡዕ ጥቅምት

ከጽርዕ ቋንቋ የተገለበጡ የሚለው ጽሑፍ በፍጹም ሐሰት ልብ ወለድ የተፈጠረ ነው። ግዕዝ በኢትዮጵያ ላይ ፪ሺ፯ ዘመን በላይ ነው ከጽርዓውያን ግንኙነት እስከነበረት ዘመን ማለቴ ነው። በኢትዮጵያ የሚገኙ መጻሕፍተ ብሉያት ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ እንደተገለበጡ ናቸው እንጅ ወደ ጽርዕ ቋንቋ አልተገለበጡም። ይህም አጻጻፍ ጽርዓውያን ከኢትዮጵያውያን ግንኙነት የነበራቸውን ጊዜ ሲገምት ሮማውያን ግብጽን አክላውባጥራን ገድለው እስቲወርሱ ድረስ በነበሩ ዘመኖች መሆኑን መገመት አለ ከዚያ በፊት ጽርዓውያን ግብጽን ይገዙ በነበረበት ዘመን መሆኑ መታመን አለ ጽርዓውያን የነበሩበት ዘመን ሲታመን "በ፻፳፬ ገጽ በ፳፩ኛው መሥመር በቅዱስ ፍሬ ምናጦስ ጊዜ ወንጌሉን መተርጐም ዠምረው በኋላም ቅዱሳት

መጻሕፍትን በሙሉ ከጽርዕ ወደ ግዕዝ መልሰውታል ያሉት ጽሑፍ ያፈርሰዋል። ማለት ከጽርዕ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተገለበጡ ብለው የጻፉትን "በ፸፱ኛ ገጽ ባ፲፯ኛው መሥመር የጽርዕ ቋንቋ ከመድከሙ የተነሳ የኢትዮጵያ መጻሕፍት በሙሉ ከጽርዕ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተገለበጠ ያሉትን መመልከት ነው።" ከመዠመሪያውም የመጻሕፍተ ብሉያትን መምጣት በግልጽ ለመጻፍ አፍረውበት ቆየ እንጅ በአነጋገርዎ ላይ የመጻሕፍቱን ሥራ መግለጽዎ አልቀረም ይህም የሚገኝበት ፩ኛ "በ፶፫ኛ ገጽ በ፫ኛው መሥመር ሌዋውያንና ሌሎቹም ከኢየሩሳሌም የመጡ ብሉይንና የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት አቆሙ ብለው ጽፈዋል" የሌዋውያንን መምጣት የብሉይ ኪዳንን ማቆም ከጻፉ መጻሕፍተ ብሉያትን በኢትዮጵያ እስከ አባ ሰላማ መምጣት አልነበሩም ማለት ራስዎን በቀላል ራስዎ ከማስገመትዎ በተቀር እውነቱን ለመረዳት ጽሑፍዎ መብቱን አስረከቦ ይገኛል። ፪ኛው "በ፸፱ነኛ ገጽ በ፳፩ኛው መሥመር ፫ኛው "በ፳፱ነኛ ገጽ በ፳፯ኛው መሥመር እነዚህ ቀደምት የሆኑ ኢትዮጵያውያን በዚያ ዘመን እኩሌቶቹ የኦሪትን ሕግና ሃይማኖት ተቀብሉ የሚለው ነው። ፬ኛ በነዚህ በ፫ቱ ማስረጃዎች ላይ "በ፸፱ነኛ ገጽ ባ፲፫ኛው መሥመር የግዕዝ ቋንቋ እየሠለጠነ እየበረታ የጽርዕ ቋንቋ እየደከመ ሄደ ከመድከሙ የተነሣ የኢትዮጵያ መጻሕፍት በሙሉ ከጽርዕ ቋንቋ እየተገለበጡ ወደ በረታው ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተተረጐመ ይላል"። እንግዴህ ይህን መመልከት ነው። አባ ጋስፓሪን አሳብ በኢትዮጵያ መጻሕፍተ ብሉያት አልመጡም በማለት ነበር።

ሐሰተኛ መባልን አተረፉ እንጅ አስቀድሞ ገና በንግሥተ ሳባ መንግሥት ቀዳማዊ ምኒልክ ወደ ኢየሩሳሌም በወረደ ጊዜ ብሉይ ኪዳንን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ መልሰው ካህናት አዛርያስ ሆኖ መጥተው እንደነበር ጌታችን በተወለደ ጊዜ የነበረው ሊቀ ካህናት አኪን ይባል ነበር። በአብርሃ በአጽብሐ ደግሞ የነበረው እንበረም ነበር። እስከዚህ ያሉ የሌዋውያን ዘሮች ብሉይ ኪዳንንና ጽላተ ሙሴን አክብረው ይዘው የቆዩ ለመሆናቸው ክብረ ጽዮን የሚባለው ጥንታዊውና ታላቁ መጽሐፍ ይመስክራል የጽላተ ሙሴን መምጣት አምኖ ብሉይ ኪዳንን አልመጣም ማለት። ከዓይነ ሥውር የተባሰ ልበ ሥውር ማለት ነው እንጅ። ልቡ ያልታወረ ዓይኑ ብቻ የታወረ ሰውስ በግብረ ሐዋርያት ፰ ፳፰ ወእንዘ ይገብእ ነበረ ዲበ ሠረገላሁ ወያነብብ መጽሐፈ ኢሳይያስ ነቢይ የተባለውን ንባብ

# ሔ ኃሙስ ጥቅምት

ባይኑ ባያይ እንኳ በዦሮው ሰምቶ ለመረዳት ይችል ነበር። የሮማ ልዑካን ጉዳይ እስከዚህ ድረስ ነው። ጽላተ ሙሴ በኢትዮጵያ ላይ ከክርስቶስ በፊት ፱፻፹፪ ዓ.ም ስትቀመጥ ሰንበት እየተከበረ ሱባዔ እየተቆጠረ ሕገ ኦሪት የተጠበቀ ሕገ ግዝረት እየታወቀ ሲኖር ብሉይ ኪዳንን በኢትዮጵያ አልነበረም ማለት እንደ ምን ያለ ነገር ይሆን። ይህንንም ጽሑፍ ሰው ይወቅልኝ ብሎ ለዓለም ጽፎ የሚአድል እንዴት ያለ አእምሮ ይሆን። "፹ኛው ገጽ በ፳፫ኛው መሥመር ከዚህ ቀደም በ፴፱ኛና ፵፫ኛ ገጽ የሳባውያንን ሕዝብ ታሪክ ስንጽፍ የኢትዮጵያንና የሳባውያንን የሰውና የሀገር ስም

እያነጣጠርን ጽፈን ነበር። ሌላም እንደዚሁ በኢትዮጵያ የተገኙትን ያገር ስሞች ከአውሮፓ ከእሥያ ስሞች ጋር እያነጣጠርን እንጽፋለን።" በአባ ጋስፓሪን አስተያየት የዓለም ሕዝብ ሁሉ ወደ ኢትዮጵያ እየመጣ ባለ ርሥት ይሆናል ለማለት። የዕሥያን ሕዝብ በገዥነትም በእንደራሴነትም በወታደርነትም በነጋዴነትም እየመጣ ባላባት መሆኑን አረጋገጡና አሁን ደግሞ ወደ አውሮፓ ተሻገሩ መቻም ማስረጃው የሀገሩ ስም ማለት ነው። በዕሥያና በኤሮፕ ያለ አገር ስሙ ኢትዮጵያ ከሚገኙ አገሮች የገጠመ እንደሆነ ልክ ያ አገር ለዕሥያ ወይም ለአውሮፕ መሆኑ የተረገጠ ነው። አሁን ከዚህ አስከትሎ የሚጻፈው የዚሁ ዓዋጅ ነው። ሀ/ እንጽፋለን ያልነው ያገርና የሕዝብ ስም በትግሬ አውራጃ ዓጋሜ በተባለችች አገር በስተምሥራቅ በኩል ከኤሮፓ የመጡ ሕዝቦች አሌጤና በተባለች አገር ተተክለው ይኖሩ ነበር እነዚያም ሕዝቦች እስካሁን ድረስ ስማቸው ሳይለወጥ

ኤሮፓዎች በተባሉበት ስማቸው ኤሮፐ ተብለው ሲጠሩ ይኖራሉ ለ/በዚያም መቀሌና ገረዓልታ በተባለው አገር አጠገብ ጽርዓውያን ተቀምጠው ይኖሩ ነበር መቀመጣቸውንም የሚአስረዳ ሰፍረውበት የነበረው አገር በጽርዕ ጽራዕ ተብሎ እስከ ዛሬ ይጠራል። ባገሩ የሚገኙም ባላባቶች ሹም ጽራዕ ተብለው ይጠሩበታል። ሐ/ ከዕሥያ እየፈለሱ መጥተው በኢትዮጵያ ላይ የተተከሉና የተመሠረቱ ሌሎች ልዩ ልይ ሕዝቦች አሉ። እነርሱም ሶርያውያን ናቸው። ሶርያውያን የተባሉ ሕዝቦች እስከንድር በተባለው በትልቁ ንጉሥ ዘመን ከሶርያ አገራቸው መጥተው ለአክሡም በስተምዕራብ ደቡብ በምትገኘው አፋፍ ላይ ሰፍረው ይኖሩ ነበር። ያችም የሰፈሩባት አገር በሶርያ ሽሬ ሕዝቦች በሶርያውያን ሽሬዎች ይባላሉ። መ/ ሶርያውያን በሌሎችም በኢትዮያ አውራጃዎች አልፈው አልፈው ተተክለውና ተመሥርተው ኑረዋል። የተመሠረቱባቸውን አገሮች በአሩሲ አውራጃ በየጦስ በስተጐን ወደ ሱዲና ወደ ሮቤ መውጫ ሆና በምትገኘው አፋፍ ላይ ሰፍረው ይኖሩ ነበር ያችውም የሰፈሩባት አገር በሶርያ ሲሬ ተብላ ትጠራለች። እንዲሁም በአሩሲ አውራጃ ነጌሊና ጐምቦ ከተባሉት አገሮች ከፍ ብሎ በደጋው በኩል በሚገኘው አፋፍ ላይ ሶርያውያን ሰፍረውበት ነበር። ያም ሰፍረውበት የነበረው አገር ዛሬ ከተማ ሆኖ ሽሬ ተብሎ ይጠራል። ሠ/ ለአዲስ አበባ በስተምዕራብ በኩል ጌዶንና ትቤን አልፎ ዋቢ የተባለውን ትልቁን ወንዝ ተሻግሮ በወለጋ ግዛት ውስጥ በምትገኘው አፋፍ ላይ እኒህ ሶርያውያን ሰፍረው ይኖሩ ነበር። ያችም ስፍራ ሰፍረውባት የነበረች ስፍራ ከተማ ሆና በሶርያ ሺሬ ተብላ ትጠራለች። እንግዲህ ይህን የሮማ ልዑካን ዓዋጅ ለሰው ሁሉ እንዲገባ ሐተታውን ትንሽ ለመዘርዘር ከዚህ የምዝምረው ነው። ፩ኛ ያውሮፕ ሰዎች ጋሜ ጸለጤና በተባለችው አገር የአውሮፓ ተተክለው ይኖሩ

# ሕ ዓርብ ጥቅምት

ነበር ተብሎ የተጻፈበት ከአውሮፕ ፋይሎች ኢሮብ በተባለው አገር በነዚህ በ፪ቱ ፊደሎች ኢ. ሮ እነዚህ ሁለቱ ፊደሎች በመገኘታቸው ብቻ ነው እንጅ ሌላ ማስረጃ የለም ፫ኛ ሲሬ ሶርያውያን ሰፍረው ነበር የተባለበት ምክንያት በ፪ቱ ፊደሎች ሺሬ ባለው ብቻ ነው እንጅ ሌላ ማስረጃ የለም በሩሲ ብቻ ፫ አገሮች አሉ ምክንያቱ ያው ፩ድ ነው ፭ኛ ዋያን ተሻግሮ በወለጋ ግዛት ላይ ሶርያውያን ሰፍረው ነበር የተባለው በፊደሎች ምስያ ነው እንጂ ሌላ ማስረጃ የለም። እንግዴህ ይህን ነገር ሌላ ትርጓሜ እንዳለው አንባቢዎች ይመዝኑት የሮማ ልዑካን ኢትዮጵያን እየዞረ በሐገሩ ስምና መልክ እየፈጠሩ የሚመኙትን አሳብ በዚህ አስተያየት መመልከት ነው። ይህን ጽሑፍ እንዲጠና በመጽሐፍ ላይ ዓምድ አሲዘው ማስቀመጣቸው ኢትዮጵያ ባላባት ባለርሥት የሌለባት ባዶ ማንም መጥቶ የሚሰፍርባት ናት እንደማለት ዓይነት የፖለቲክ ስብከት ነው እንጅ ይህ ጽሑፍ ታሪነት ያለው አይደለም። ፳፰ኛ ገጽ ታልድት ከተባለው ንጉሠ ነገሥቱና እቴጌይቱ በክብረ መንግሥት ዙፋናቸው ላይ ግራና ቀኝ ተቀምጠው እያለ የጻፈው የማሾፍ ይመስላል ከመጨረሻው። ላይ ይህ ንጉሥ የኢትዮጵያ መንግሥት ዓረብን ይገዛ በነበረ ጊዜ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እንደራሴ የነበረ ሰው ነው ብሎ ኢትዮጵያዊ ኩሽ መሆኑን አረጋግጦ ጻፈ ይላል። እንደራሴውን ንጉሠ ነገሥት ማለት የተገባ

ሳይሆን የማሾፍ ይመስላል ያልሁት ስለዚህ ነው በ፺፫ኛ ገጽ በ፱ነኛው መሥመር ይህ አልዓሜዳ የተባለው ትልቅ ንጉሥ በእርጅና ምክንያት ዕለተ ሞቱ በደረሰ ወራት ሕዝቡንና ሠራዊቱን ሰብስቦ መንግሥቱን ለዔዛና ለልጁ አወረሰ መንግሥቱን ለልጁ ካወረሰ በኋላ ታሪክ የተሰናዳው መጣ በአብርሃና በአጽብሃ ቦታ ዔዛናን አግብተው የጻፉበት ምክንያት በኋላ ይገለጻል አሁን ከንግሥት ሶፍያ እስከ ዔዛና በትውልድ ፴፪ኛ ነገሥታት ይገኛሉ በዘመን ደግሞ ከንግሥት ሶፍያ እስከ ዔዛና ወልደ አልሜዳ ፩፻፹፭ ዘመን ነው ይህን ሁሉ ተራምደው። እንግዲህ የትውልዱን በመንግሥትነት

፴፪ት። በዘመን ፩፻፹፭ ብያለሁ ይህን ሁሉ መረጃ ተራምደው የአልዓሜዳ በ፫፻፷፭ ዓ.ም ዔዛና ነገሠ ብለው ጻፉ። ይህ የነገሥታቱ ታሪክ በኢትዮጵያ ክብረ ነገሥት በየገዳማቱና በየአድባራቱ በሽ በሚቆጠር ጽሑፍ ይገኛል። ስንኳን በኢትዮጵያ የሚገኘው ይቅርና በውጭ አገር የሚገኙ ጽሑፎች እንኳ ወሰን የላቸውም የአብርሃና የአጽብሃ ታሪክ በዓለም የታወቀ ሲሆን የሮማ ልዑካን ሐሰትን ልክ እንደ እውነታስመስለው ስለያዟት እነዚህን የኢትዮጵያ ዋና የታሪክ ዓምዶች የሆኑትን ነገሥታት ከታሪክ ቦታቸው ላይ ሠርዘዋቸው ተገኙ። አብርሃና አጽብሃ አባታቸው ሰይፈ አርድ። እናታቸው ሶፍያ ይባላሉ። የተወለዱትም ፩ድ ቀን ነው ያደጉም አብረው እየተማሩ ነው። እናታቸው በሞተች ጊዜ ሕዝብ የትኛውን ለማንገሥ ስለተቸገሩ ነገሩን ከእግዚአብሔር ረድኤት ለማግኘት ሱባዔ ገብተው ቢያመለክቱ ፪ቱም ልጆች እግዚአብሔር ያደረባቸው ቅዱስ ምግባር ያላቸው ብፁዕን መሆናቸውን ገልጾ አስረድቶ ፪ቱንም ፩ድ ቀን ለ፪ቱም ፪ት ዘውድና የመንግሥት ሥርዓት

# ሐ ቀዳም ጥቅምት

ነግሥ ፈጸሙላቸው የሚል ፈቃድ አግኝተው እንደተለመደው ሥርዓተ ንግሥ ተፈጽሞላቸው ፪ቱ ወንድማማቾች ፩ቀን ነግሠው እንደ ዓለማዊ ሳይቀናኑ በትሕትና በፍቅር ሲቀመጡ በዘመናቸው በቈስጠንጢናስ መንግሥት ቁስጥንጥንያ በሆነ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ስለተቋቋመ ይህ የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት በማነኛውም አገር ቤተ ክርስቲያን ከቈስጠንጢኖስ መንግሥት በፊት ነጻነት ስለአልነበሩት የቤተ ክርስቲያን ነገር የሥጋውን የደሙ አቀባበል የካህናቱ ሹመት ደረጃ ይህ ሁሉ ገና አልተወሰነም ነበረና ከዚያ በፊት በማነኛውም አገር በመዠመሪያ የታወቀው ጥምቀት ስለሆነ ጥምቀትን በመዠመሪያ ያገኘ ሰው እሱ እንደ ሐዋርያ እየሆነ ማጥመቅና ክርስቲያን የሆኑ ሰዎች የሚሰበሰቡበትን ቤት ቤተ ክርስቲያን የሚባል እሱ ስለነበር አሁን አሕዛብ ወይም አይሁድ እየቀኑ ያቃጠሉት ሰዎችን በልዩ ልዩ ሥቃይ ያሰቃይዋቸው በነበረ ጊዜ አምላክ ክርስቲያን ቈስጠንጢኖስን አስነስቶ ቤተ ክርስቲያን ነጻነት ባገኘች ጊዜ አብርሃና አጽብሃ ይህን ወሬ ስለሰሙ ጥምቀትን አስቀድሞ በሕጽዋ ለኅንደኬ ተቀብለው የሥጋውና የደሙን አቀባበል ሥነ ሥርዓትና የቤተ ክርስቲያን ሹማምንት አኳኋን እንደምን እንደሆነ ከቁስጥንጥንያ ለማስመጣት ምንገድና ቋንቋ አዋቂ ሰው ሲፈልግ ፍሬ ምናጦስ ስለተገኘ ሰውና ስንቅ ጨምረው ልከውት እስከንድርያ ደርሶ ከእስከንድርያ በቅዳሴ የሚደረገውን ጸሎትና የሥጋና የደሙን አቀባበል የቤተ ክርስቲያንን ሹማምንቶች ነገር አደራጅቶ እሱም ራሱ በኢትዮጵያ ሲቆይ ግዕዝ እየተማረ አድጎ ስለነበር ሐዲስ ኪዳንንም ከጽርዕ ወደ ግዕዝ እንዲመልስና ለኢትዮጵያ ሊቃውንት እንዲሰጣቸው ለኢትዮጵያ ጳጳስ አድርጎ አባ አትናቴዎስ ስሙን ሰላማ ብሎ ሹሞ ሰደደውና አብርሃና አጽብሃም በታላቅ ደስታ ተቀብለው ደስታ አደረጉ። ስሙንም ከሣቴ ብርሃን ብለው ቀጸሉበት ወሶበ ስምዑ አዝማደ እሞሙ ዘሀገረ ግማድ ወስምዑ ሰብዓ አይባ ወሰብዓ ትግሬ ወጽራዕ ወሰብዓ ገርዓልታ ወሰብዓ ሐረማት ወድንግላት መቅድመ ኲሉ ሴሞሙ ለ፫ቱ ደቂቅ ዘነበሩ ውስተ ደብተራ ከመ ይኩኑ ልዑካነ ወይትራድዕዎ በጊዜ ቅዳሴ ወቍርባን ወወሰዶሙ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ወሰመዮ ለፊንሐስ ተንሥአ ክርስቶስ ወለዐሮን ስምዖን ወለአዛርያስ ማቴዎስ ወለአቤሜሌክ ስብሐት ለአብ ወለኄኖክ አማኑኤል ወለመልከ ጼዴቅ ፩ዱ አምላክ ወለሳዶቅ ማዕቀበ እግዚአ ወረሰዮሙ

ዲያቆናተ ወኃረየ እምላዕካነ ጽዮን ፪ዔ ፩ዱ ተክለ ሃይማኖት ወካል ገብረ መስቀል ወሤሞሙ ጸሐፍተ ወእምድኅረዝ ሤሞ ቀሲሰ ለተንሥአ ክርስቶስ ወለኵሎሙ ቀሳውስት ከመ ይሡዑ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ወተከሉ አብርሃ ወአጽብሐ ፫ተ ሐይመታት። ወአንበርዋ ለታቦታ ማርያም ወበካልዕ ወሐይመት አንበሩ ታቦተ ሚካኤል። ወበሣልስ ሐይመት አንበሩ ታቦተ ገብሬል።

ወማእቀበ እግዚእ ይንበር ማዕከሌሆሙ። ይህ ከጥንታዊ ጽሑፍ የተገኘ ነው። እንበረምን አልጻፈውም ግን የደብረ ሲናን የሚናገር ሌላ አለ አሁን የምንፈልገው ስለ አብርሃና አጽብሐ ስለሆነ ሌላውን ጽሑፍ አቆይተነዋል። ወዳግመ ሤምዎ ንቡረ ዕድ ለዓምደ ሃይማኖት ወልደ እኅቶሙ ዘውእቱ ዳንኮሞር የአብርሃና የአጽብሐ እኅት ትእማር ትባላለች ይህ ዳንኮሞር ማለት ወልደ እኅቶሙ ትእማር መሆንዋን ማስተዋል ነው። ፩ድ ፩ድ ሰዎች ትእማር የሚል ሲገኝ የዳዊት ልጅ ከምኒልክ ጋር የመጣች እየመሰላቸው እየተሳሳቱ ስላገኘሁ ነው። የአብርሃና አጽብሐ ታሪኮች በብዙ

# መ እጐድ ጥቅምት

መጻሕፍቶች ይገኛሉ አብርሃና አጽብሐ የተሠረዙ እንደሆነ የኢትዮጵያ መሠረት ተለለባበጠ ማለት ስለሆነ አብርሃና አጽብሐ በኢትዮጵያ የሠሩዋቸውን ሥራዎች ከብዙ በጥቂት በዚህ አስከትየ የምጽፈው ነው ወሐሩ አብርሃ ወአጽብሐ ምድረ ገረዓልታ። ሐነጹ መቅደስ ዘትሰመይ ደብረ ማርያም። ወካዕበ ሐነጹ ካልዓ መቅደስ በየማና ለይዕቲ ደብር ወቅሩቡ ይዕቲ ኀበ ፈለገ ኦር ወሥልሰ ነሐጹ መቅደስ በምድር ምንዳዕ ወይዕቲ ምስካበ በድኖሙ ለቅዱሳን። አብርሃ ወአጽብሐ የተቀበሩበት ቦታ እስከ ዛሬ ታአምራት እየተሠራበት ድውይ ሲፈወስ እየታየ የዕረፍት ቀናቸው እስከ ብዙ ሕዝብ እየተሰበሰበ በታላቅ ክብር የሚውልበትን ታላቅ ሐውልት ሆኖ የሚቆጠር ብዙ የጽሑፍ ማስረጃ የሚገኝበትን ይህ ሁሉ ታሪክ እያለ በጠላት ፖለቲክ የአብርሃና የአጽብሐ ታሪክ ከቦታው ዓምድ ላይ ተሠርዞ መገኘቱ አስገራሚ ነው ወገብሩ ትእይንተ በምድር አይባ ወሐነጹ መቅደሰ በህየ ታሕተ እግረ ደብር ዘትሰመይ ጉልሳ። ወኃለፉ እምህየ ወበጽሑ ምድረ ሐረማት ወሐነጹ በህየ አሐተ መቅደሰ ዘትሰመይ ሐውዜን ወእንዘ ሀለው በህየ ሰብዓ ትግሬ ወይቤልዎሙ አብርሃ ወአጽብሐ ለካህናተ አክሡም መጽአ ጸላዊ እምአመ ሖርነ ወይቤሉ ካህናት እወ ይመጽእ ወየሐውከነ በከዊነ ኵሉ። ወእምድኅረዝ ሖሩ መካነ አክሡም ወዓቀሙ በህየ ሐውልተ በአምሳለ ት እምርተ መስቀል ከመ ኢያቀርቡ ሰይጣናት ወኃለፉ እምህየ ወገብሩ ትዕይንተ በምድረ ጽራዕ ወሐነጹ መቅደሰ ኀበ ጽንፈ ባሕር ዘይሰመይ ውቀሮ ወአሐተ መቅደሰ ሐነጹ በመደቄ ዘሠናይ አርዓያሃ ወአልቦ ዘይትማሰላ እምኵሉ መቅደሰ ዘተኃንጸ ቀዳሚ ወተሠወረት። በምድረ አጽሊ ፩ድ ቤተ ሐነጹ በሸዋም ደብረ እለ ጀንበር የምትባል ቤተ ክርስቲያን ሠርተው እንደነበር ከገድለ ቀውስጦስ በተጠቀሰው ከላይ ይገኛል። በጐጃምም መርጦለ ማርያም አብርሃና አጽብሐ የሠሯት በሚአስደንቅ እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል። በመርጡለ ማርያም ቤተ ክርቲያን እስከ ዛሬ ዕለት ዕረፍታቸው ባመት ባመቱና በየወሩም ከፍ ያለ በዓል ሲደረግ ይገኛል። በዚያም ስለ አብርሃና አጽብሐ የተጻፉ መታሰቢያዎች በብዙ ይገኛሉ እንግዲህ አብርሃና አጽብሐ የአክሡም ጽዮንን በወርቅ ያጌጸች ቤተ ክርስቲያን ሠርተው እንደነበረ የዓለም ባለታሪኮች ሁሉ ያውቃሉ። ደግሞ ታሪክ እንደሚናገረው ለአክሡም ጽዮን የሰጧት ሥርት ጉልት ከዚህ የሚከተለው ነው

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ | ደረቃ | ፲፩ኛ | ዓድ ገይ |
| ፪ኛ | ዓዲቀርኒ | ፲፪ኛ | ዓድ ምክር |
| ፫ኛ | ዓዲዳዳ | ፲፫ኛ | ክቱር |
| ፬ኛ | ቤተሰማዕት | ፲፬ | ዓድሳሁ |
| ፭ኛ | ዓዲዘሰቶ | ፲፭ኛ | ዓድ ረፋይ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፮ኛ | ቀነፍ | ፲፱ኛ | መደልባ |
| ፯ኛ | ዓዲሖጻ | ፳ኛ | ፊረማ |
| ፰ኛ | ብላ እንድ | ፳፩ኛ | አናቁሊ |
| ፱ኛ | ዓድ ቤታ | ፳፪ኛ | ጦማሎ |
| ፲ኛ | ዓድቀርቀራ | ፳፫ኛ | ዓድዘክረም |
| ፲፩ኛ | ዓዲ ዓደጉ | ፳፬ኛ | ዓድኳራ |
| ፲፪ኛ | ሐመድ አልባ | ፳፭ኛ | ድምበዛ |
| ፲፫ኛ | አዘዊ | ፳፮ | ማዕከይቶ |



አክሱም ፅዮን



በታላቂቱ የኢትዮጵያ ከተማ የሚገኙ ሐውልቶች ይእቲ አክሡም ጽዮን

# ሙ ሰኑይ ጥቅምት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፳፯ | ዳባልቅ | ፷፫ | ዓድ ጸሐፊ |
| ፳፰ | ስህ ታቡክ | ፷፬ | ፍልፋሊ |
| ፳፱ | ባሕኑና | ፷፭ | ማይ ጸዓዳ |
| ፴ | ዓዲ ገዛይ | ፷፮ | ማይ ዘግራ |
| ፴፩ | ዓዲ አምባ | ፷፯ | ዓድ መሠረት |
| ፴፪ | ቤተ ኤልያስ | ፷፰ | ዓድ ሥዩም |
| ፴፫ | ሰጐት | ፷፱ | ዓድ ሐንከራ |
| ፴፬ | ምሬና | ፸ | ዓድ ራዛ |
| ፴፭ | ደምበበያ | ፸፩ | ጋቅማ |
| ፴፮ | ሰገሞ | ፸፪ | ጸሊም ቤት |
| ፴፯ | ላስሶ | ፸፫ | ዓቃቢ መርኖ |
| ፴፰ | ስንኮቤት | ፸፬ | ዓዲ ዋጦት |
| ፴፱ | ሰግላሜን | ፸፭ | ቤተ ዮሐንስ |
| ፵ | ሐምቦራ | ፸፮ | አውልዖ |
| ፵፩ | ቈጸሎ | ፸፯ | ኮዳ |
| ፵፪ | ሐውዜና | ፸፰ | ጽላዕሎ |
| ፵፫ | ዓድ መርን | ፸፱ | ሂላ |
| ፵፬ | ዐድ ቅኔ | ፹ | ወልታ ወርቂ |
| ፵፭ | ሐዲስዓድ | ፹፩ | ግሙዕ |
| ፵፮ | በርዝላ | ፹፪ | ብዕዛ |
| ፵፯ | አፅሚሐርማዝ | ፹፫ | ቤተ ገበዝ |
| ፵፰ | እንኩዔላ | ፹፬ | ዓድ አርጉዲ |
| ፵፱ | ዓድሐንዝ | ፹፭ | ፃኢ |
| ፶ | ዕንባቱንቂ | ፹፮ | ብዞት |
| ፶፩ | ኰኰሒ | ፹፯ | መደጌ ብዘፈራ |
| ፶፩ | ዓዲ ገርጣጥ | ፹፰ | ዓዲ አበዘ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፶፫ | አዲ ቀዲ ዳዊ | ፺፱ | ዓዲ እታይ |
| ፶፬ | አክልትና | ፻ | አዲጐሊ |
| ፶፭ | ዓድ ምልዖ | ፻፩ | ግዝግዝያ |
| ፶፮ | ቀጠጥ እክሊ | ፻፪ | ማይ ወይን |
| ፶፯ | ሐንከሰቲ | ፻፫ | አባሳጌ |
| ፶፰ | ማይ ብዋከ | ፻፬ | ዓጻ |
| ፶፱ | ዓድ ሰዮ | ፻፭ | ታዕካ ማርያም |
| ፷ | ድራ | ፻፮ | ሳውኒ |
| ፷፩ | አምኮ | ፻፯ | ዓዲ ደጊቡ |
| ፷፪ | ድቡራ | ፻፰ | ዓዲ አድኅኖ |
| ፷፫ | ካባኑት | ፻፱ | ማይ ምውት |
| ፷፬ | ማይሰዬ | ፻፲ | ማይ ኃኢ |
| ፷፭ | ዓድ ጽሕሎ | ፻፲፩ | ዓዶ ግንድ |
| ፷፮ | ምላዞ | ፻፲፪ | ስመማ |
| ፷፯ | ወርናዕሌ | ፻፲፫ | ማይ ጣፋት |
| ፷፰ | ዕድጠፈረት | ፻፲፬ | ዓዲ ንቡረ ዕድ |
| ፷፱ | ይቡሳ | ፻፲፭ | ኵሉ ፈርሃ በዘፈራ |
| ፸ | ምናድቅ | ፻፲፮ | ቡር ማዕዖ |
| ፸፩ | ዝባንዕገ | ፻፲፯ | ሙዘተ |
| ፸፪ | ገብገብ | ፻፲፰ | ስንፍቲ |
| ፻፲፱ | ስሔታ | ፻፴፫ | ጐንዳ |
| ፻፳ | ሶዶዎ | ፻፴፬ | ቄራር |
| ፲፳፩ | ደብረ ሰላም | ፻፴፭ | ደብረ ዘካርያስ |
| ፻፳፪ | ጉብሳ | ፻፴፮ | ቤተ ዮሐንስ |
| ፻፳፫ | ዓድ ብፅዓት | ፻፴፯ | ዔራሥርው |
| ፻፳፬ | ሰላዕ | ፻፵ | አድ አስሐትያ |

# ሚ ሠሉስ ጥቅምት

ምንም በስም አጠራር ጥንታዊውና በኋላ የገባውን ለማጣራት ሁለተኛ ባናጣጥረ ጊዜው ስለ ነገሥት ጻድቃን መታሰቢያ ከሰጡት በአክሡም በመናገሻ ከተማቸው የሙሴ ጽላተ ሕግ ባለችበት አብርሃና አጽብሃ ያሠሯት ቤተ ክርስቲያን የሥነ ሥርዓቷ የተለየ መሆኑን ስለ መሠረቱ አኳኋን የጀርመኑ ሊቅ ሙሴ ዲልማን እንኳ በታሪክ መጽሐፉ ገልጾላታል። ይህ ግን በጥንታዊ መጽሐፍ ከተገኘው ከዚህ አስከትየ የምጽፈው ነው የሥነ ሥርዓቷም ነገር አስደናቂ ነው። ከመዝ ሥርዓታ ጽዮን ገበዘ አክሡም እስከ ፲ወ፭ቱ በእመት ኢረከቡ መሠረታ ወጳፍጸፈ ከዲህ ፯ቱ በእመት እምድኅር እስከ አፈ ጽዮን ወከርሠ ንድቁ ፯ቱ በእመት ወኑሁ እምሥራቅ እስከ ምዕራብ ፻ወ፳ወ፭ቱ በእመት ወእምደቡብ እስከ ሰሜን ፺፪ በእመት (የአክሡም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን መሠረት ቅርጽ እንደ ኢትዮጵያ ፊደል መጨረሻ እንደ ፐ ነው። ይህን ታሪክ ለመረዳት አክሡም በቅርብ በተገኘው በዘነ የሚል ጽሑፍ በድንጋይ ተጽፎ በውስጥ ተገኝቶ እንደሚናገረው የባዜን መቃብር ከበላዩ ቀለል ያለ ሐውልት ያለበትን መቃብር ቅርጹን አስተውሎ ሲመለከቱት ልክ እንደ ፐ ሆኖ ተቀርጾ ይገኛል ይህም ለኢትዮጵያ ፊደል ዋና ምስክር ማለት ነው። የፐን የፊደል ቁጥር ምሥጢሩን ከላይ ስለገለጽኩት አያስፈልግም ግን የቅርጹን ሁኔታ ለማወቅ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ፻፳፭ ክንድ አለው። ከሰሜን እስከ ደቡብ ፺፪ ክንድ ያለውን በማስተዋል ሲመለከቱት ልክ ሆኖ ይገኛል። ወስፍሑ ፶፫ በእመት ወኑሁ እምድር እስከ ርዕሰ ቀመር ፴ወ፪ቱ በእመት። ዓዕማድ ዘንድቅ ፴፪ ዘንድቅ ያላቸው በወፍራሙ እንደምሰሶ ሆነው በረዥም የተሠሩ ግንቦች ናቸው። ወዓዕማድ ዘዕብን ፴ወ፪ በጥርብ ድንጋይ ምሰሶዎች በኵሉ ድሙር ፷፬ ማዕጾ ዓቢያን ዘአናቅጽ እመንገለ ዓረብ በአፍአ ፬ቱ ወበውሥጥ ፬ቱ። (እነዚህ ላይ በምዕራቡ በር ላይ ፬ መዝጊያዎች ከውሥጥ ፬ መዝጊያዎች ከውጭ ያልው

ግምቡ ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ መዝጊያዎችም እጥፍ መሆናቸውን ያስረዳል) ወጽርሕ ፩ዱ ሰሜናዊ ፩ዱ ደቡባዊ። ይህም ቤተ መቅደስ ባ፩ኛው ቤተ ዮሐንስ በ፪ኛው ቤተ ማርያም መግደላዊት ቤተ ዮሐንስ የሚለው የሐዋርያውን አይደለም የመጥምቁ ዮሐንስን ነው። ማርያም መግደላዊት የሚለው የቅዱስ ማርቆስን እናት ነው። (ምክንያቱም የመጥምቁ ዮሐንስ ዓጽም የተቀበረው ከቅዱስ ማርቆስ እናት ቤት ነበረ ቅዱስ ማርቆስ ሀገረ ትውልዱ ኢትዮጵያ ስለሆነ እሱ መጥቶ ሲአስተምር ስለሚአውቁት የማርቆስን እናትና የመጥምቁ ዮሐንስን መታሰቢያ አቆሙ። ስለዚህም ዋናው ማስረጃ የነገሥታቱ ገንዘብ ካንገቱ ስለሆነ ርዕሰ ዮሐንስ እያሉ ስሙን እስከ ዛሬ ይጠሩታል። መጥምቁ ዮሐንስ በአክሡም ላይ በጣም የታወቀ መሆኑ ምክንያቱ በማርቆስ እናት ነው። ስለዚህ ፩ድ ፩ድ ሰዎች ጥምቀት ወደ ኢትዮጵያ የመጣ በፍሬ ምናጦስ ነው እያሉ ባለማወቅ

# ማ ረቡዕ ጥቅምት

ይጽፋሉ። እሽ ቅዱስ ማርቆስ ባረፈ ከ፪፻፺ ዘመን በላይ የሆነውን በምን ምክንያት እናቱን ከ፴፮ቱ ቅዱሳት እንስት መሆንዋን አውቀው መታሰቢያ አቆሙላት። ቅዱስ ማርቆስ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አላስተማረም ማለት ከፍ ያለ ስንፍና ነው። ሳይረዱ ከመናገር አስቀድሞ መመርመር ከስሕተት የሚአድን ዋና ጋሻ መሆኑን መገንዘብ ጠቃሚ ነው። ወደሥሩ እንመልከት ቤተ ማኅበር ፪ ፪ ቤተ መዛግብት በምሥራቅ በኩል ከሰሜን እስከ ደቡብ በቤተ መቅደሱ አኳያ ክፍሎች ፲፫ት ናቸው የመዝጊያዎችን ብቻት ፩፻፷፩ ናቸው ይላል። መስኮቶቹ ፻፷፰ ወመንኮራኵራቲሃ ፺፻ወ፹ ወቀስት ፲። ወርዕሰ ኅበይ ፴ወ፷፻ ርዕሰ ኅበይ ማለት ከላይ በዙሪያው ቁጥ ቁጥ ብለው የሚገኙ አሉ እነሱን ነው ወመስረበ ማይሂ ፻፺። በ፵ወ፱ቱ ዓ.ም ኮነ ሠራፌሃ ወተፍጻሜታሂ ኮነ በ፺፩ ዓ.ም ስትሠራ ፵፪ ዘመን ጨርሳለች ማለት ነው ዓለምስ ሕልም ወጽላሎት ወአልቦ ዘይዌስክ ዘእንበለ ዘይነትግ ያችን የመሠለች በወርቅ የተጌጠች ቤተ ክርስቲያን በሴት

ወምበዴ እጅ ተቃጥላ ምልክቶቹ ሁሉ ከመሬት ውስጥ ሆኑና ያችን የሠሩ ጻድቃን ነገሥታት ከታሪክ ደረጃቸው ስማቸው ለመሠረዝ ደረሰ የሀገር ታሪክ ለመደምሰስ የሚቻለው መንግሥቱ በጦር ኃይል የወደቀና ዓላማው የጣጠፈ እንደሆነ ነው እንጅ በዘውድ የተጨቀ ንጉሠ ነገሥት በመንበረ መንግሥቱ ተቀምጦ እንደዚህ ያለ የታሪክ ፖለቲክ በማንም ጊዜ ተጽፎና ተወርቶ አያውቅም የአብርሃና የአጽብሃን ታሪክ በመጠርኑ ከመወሰን በተቀር በኢትዮጵያ ላይ የሠሩትን ለመጻፍ ይህ ዓምድ ስለማይበቃው ከዚህ ወደ ዔዛና እንራመዳለን። ያባ ጋስፓሪን ጽሑፍ ከንግሥት ሶፍያ (ወይም አሒየዋ ዘመነ መንግሥት ዝምሮ በመካከል ያለው ሁሉ ተሠርዞ ይገኛል። እንዲያውም የሶፍያንም ዘመነ መንግሥት ሠርዘውታል። ማለት የአብርሃና የአጽብሐን አባት ታዜርን (ወይም ሰይፈ አርድን) አላዓሜዳ ብለው ሠይመው ከሰይፈ ዓርድ አባት ከሰልዓደባ ዝምረው አልዓሜዳን በ፫፻፳ ዓ. ምሕረት የነገሠ አድርገው የጻፉበትን ምክንያት ስንመረምረው ያገኘነው ፩ድ ምክንያት አለ እሱም ከዚህ የሚከተለው ነው። ፱ቱ ቅዱሳን በዓልዓሜዳ ዘመነ መንግሥት ባ፬፻፹፫ ዓመተ ምሕረት ላይ ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸውን ብዙ ጽሑፎች ለማስረዳት ይገኛሉ። ይህን የሚአስረዱ ጽሑፎች ምንም በብዙ የሚሆኑ ቢሆኑ ለሮማ ልውካን የዘመኑ መርዘም የሚያስፈልግበት ቦታ ሆኖ ስለተገኘ። ስንኳንስ ፱ቱ ቅዱሳን በ፫፻፳ ዓ.ም ያባቶቻቸው አባቶች እንኳ ተፈጥረው ነበር ሊባል ከማይቻለው ፻፹፫ ዘመን አራምደው የሰልዓደባን ልጅ የንግሥት ሶፍያን ባል ታዜር (ሰይፈ አርዕድን) አልዓሜዳ ብለው የዘመኑን ቍጥርና የነገሥታቱን ተራ ቁጥር ዘለው በ፫፻፳ ዓ.ም አልዓሜዳ ነገሠ ብለው የ፱ቱ ቅዱሳን ዘመን ከፍሬ ምናጦስ ጋር እንዲሆን በማለት መሆኑን በግልጽ ተረዳነው። ፱ቱ ቅዱሳንን የኢትዮጵያ ተወላጆች አለመሆናቸውን ስላወቁ ስለ ፱ቱ

ቅዱሳን “በ፻፴ ገጽ በ፳፩ኛው መስመር ፱ ቅዱሳን ከቅዱስ ፍሬ ምናጦስ በኋላም የክርስቶስ ሃይማኖት ተሰብኮ በሌሎቹ ልውካን ሰባክያን ተስፋፍቷል በብዙዎቹ አውራጃዎች ጻድቃኖች የክርስቲያንን ሃይማኖት አስፋፍተዋል። በመጠራ በባረክናሃ ቤተ ክርስቲያኖች የጻድቃንን ተረፍ ነው የሚሉት ሰብዓዊ ቅሬታ ይታያል በዚሁ በባረክናሃ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ፩ድ ሥዕለ ስቅለት አለበት በኢትዮጵያ ላይ የተሳለ መዠመሪያ የክርስቲያን ሥዕል ይህ እንደሆነ

# ሜ ኃሙስ ጥቅምት

ይታመናል። ሌላው ትልቁ የክርስቲያን ሃይማኖት የመጣው ከሮም ሲሆን የንጉሥ ልጅ ነበር በልዩ ወንጌልን የሰበከው በኢትዮጵያ ሆኖ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን ተክሏል። አሁንም እንኳ መታሰቢያነቱ በሠራዬ ላይ በጣም ይገኛል ከሁሉም ይበልጥ ደግሞ ስማቸው እጅግ የገነነው ፱ቱ ቅዱሳን ናቸው እነርሱም ዘሚካኤል አረጋዊ ጋሪማ የሚባለው ይስሐቅ ሪማዊው ጰንጠሌዎስ ሊቃኖስ ዘቁስጥንጥንያ ይምዓታ ጽሕማ ዘአንጾኪያ ጉባ አፍጼ አሌፍ ናቸው። የነዚህ ቅዱሳን ታሪክና ስብከት በግብረ አረጋዊና በግብረ ገሪማ ላይ ይገኛል። ግብር ተብሎ የተሠየመ ገድሉ ነው”። እንግዲህ ከላይ እንደተጻፈው ፱ቱ ቅዱሳን ከፍሬ ምናጦስ ተከታዮች ሰባክያን የሆኑበት አባ ጴጠንሌዎን ሮማዊ ተብሎ ስለ ተሰየመ ነው። አባ ሊባኖስም እንዲያውም የሮማው ንጉሥ ልጅ ስለ ተባሉ እነዚህ ሰዎች ሮማውያን ከሆኑ እኛም ከሺ፫፻፵፩ ዓ.ም ወዲህ ዝምረን በኢትዮጵያ ላይ መስቀልና መጽሐፍ ይዘን ኢትዮጵያን ወደ ልማት የምንመራ እውነተኞች ሰባክያን የቅዱስ ጴጥሮስን መርኖ ይዘን ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚአስገባውን በር የምንከፍት እኛነን እያሉ ክርስቲያኖችን ሁሉ ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት እያወጡ እነዚህንም ሰዎች እየመዘገቡ ወደ ሮማ መንግሥት እየላኩ ሮማ ለዚሁ ሥራ ማከናወኛ ከቆመው ማኅበር ቤት ሂሳባቸውን ስለሚአገኙ ይህ ሮማ ላይ የቆመው ማኅበር የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እያደከመ በኢትዮጵያ ላይ የሮማ ቤተ ክርስቲያን እንድትቋቋም ባለሙሉ ተስማ ስለሆነ በኢትዮጵያ ለሚገኙ የሮማ ልውካን በቂ ገንዘብ ስለ እሚሰጣቸው እነዚህም የሮማ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ላይ በቶሎ የምትስፋፋበትን ለሕዝቡ ለማስጠናት ሮማውያንም በኢትዮጵያ ላይ ስብከትን ዝማሪ ናቸው ለማለት የስብከቱን ዘመን እያስረዘሙ ቅድመ አባቶቻቸው ሳይወለዱ ከነበረው ዘመን ላይ እናወጣለን ሲሉ በኢትዮጵያ ሲያያዝ

የመጣውን የመንግሥት ኃረግና ትውልድ አጨደማ እንደዚህ ባለ ድፍረት ይህን የሐሰት ፖለቲክ ታሪክ አስመስለው ጽፈው አቀረቡት ለመሆኑ አባ ጋስፓሪን ወዳጀ ሆይ በ፫፻፷ ዓ.ም ከሮማ ኢትዮጵያ ድረስ ለምናኔ የሚችል መነኵሴ ከምን ተገኘ ይህ ምንኩስና የተዠመረው ግብጽ ላይ በነአባ እንጦንስና እነ አባ መቃርስ ነበር እነዚህ እንጦንስና መቃርስ በ፫፻፷ ዓ.ም ነበሩ ለማለት አይፈሩም ይሆንን። ወይም ምንኵስናን የዠመሩ እንጦንስና መቃርስ አይደሉም የሚሉ ይሆንን እነዚህ ፱ቱ ቅዱሳን በ፫፻፷ ዓ.ም ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ጊዜ መንኵሰው ነበር እንዳይሉ በ፫፻፷ ዓ.ም ዘመን ላይ እንጦስንና መቃርስ አባቶቻቸውም ገና አልተወለዱም ነበር። እንጦስና መቃርስ ሳይወለዱ ገና በሕሊና አምልካ ሳሉ ፱ቱ ቅዱሳንን አመንኵሰው ወደ ኢትዮጵያ ከላኩ በኋላ አባቶቻቸው ተወለዱና ደግሞ እነሱ ተወልደው ይመነኵሱ ዠመር ብለው መጻፍዎ ማለት መሆኑን ስገነዘበው በጣም አድነቅወታለሁ በዚህ አስተያየት የተሸለሙትም ሽልማት በጣም ስላነሰዎ እንደኔ አሳብ የሚሆን አሁንም ሊጨመርልዎ የሚገባ መሆኑን እመሰርክርልዎታለሁ። ታሪክ መጻፍ ማለት እንደዚህ ያለ የታሪክ ታሪክ ነው። የሮማ ልዑካን ስብከት ሁሉ ጣዕሙ ልክ ሦከር ሦከር የሚል ስለሆነ የሮማ ልዑካንም ከጣፈጠልን ብለው ለትንሹም ለትልቁም ሲአቀርቡት በለጋስነት ስለሆነ ከብዛቱ የተነሳ ልኩን አያውቀውም ስለ ሮማውያን ታሪክ አሁና ጥንት ከተባለ መጽሐፍ ከኤሮክሶን ቄሳር ኔሮን በ፷፬ት ዓ.ም ክርስቲያኖችን በሮሜ

# ም ዓርብ ጥቅምት

ሥቃይ ሲአስጨንቋቸው ያ ብርቱ ስደት እስከ ፫፻፲፩ ዓ.ም ዘገየ። ፩ድ ጊዜ ዝግ እያሉ ፩ድ ጊዜ ደግሞ በጣም እየበረታ ኋለኛው ከ፫፻፫ እስከ ፫፻፲፩ የበረታ ነው። በዚያ ጊዜ አሳዳጆች ሁሉ አብያተ ክርስቲያናትን ውድማ አደረጉ መጻሕፍትን ሁሉ አነደዱ ክርስቲያኖችን ሁሉ ይልቁንም ካህናቱን ለብርቱ ሥራ ፈረዱባቸው ወይም በክፉ ሥቃይ ገደሏቸው ግን ይህ ሁሉ የአረሚነት ኃይል ከንቱ ሆነ። ክርስቲያንን ሃይማኖት ለማጥፋት ችሎት አጡ በ፫፻፲፫ ዓ.ም ቈስጠንጢኖስ እስቲ ነግሥ ክርስቲያኖቹ ነጻነት አላገኙም በክርስቲያኖችና በሮማ ነገሥታት መካከል የነበረው ጠብ ለነገሥታቱ ጣዖታት ክርስቲያኖች አንሰግድም በማለትነው። ቈስጠንጢኖስም የተጠመቀው ዕረፍቱ በደረሰ ጊዜ ነው። ከሱ በኋላም ቄሳር ዩልያኖስ ለጣዖት ካልሰገዳችሁ እያለ ብዙ ክርስቲያኖችን እንደ ፈጀ ታሪክ ይነግረናል”። የሮማ ልዑካን እስከ ፫፻፸ ዘመን በሀገራቸው ላይ የነበረውን ታሪክ ሳይገነዘቡ የኢትዮጵያ መምህር ለመሆን ይጣጣራሉ አምላካዊ ሥራ ሐሰት አይጨመርበትም ነበር የሮማ ልዑካን ስብከት ሐሰት የበዛበት በመሆኑ ያሳዝናል “፺፮ ገጽ በ፳፩ኛው መሥመር የንጉሥ ዋዜብ ስም የተጻፈበት ገንዘብ ተገኝቷል ከርሱ በፊት በኢትዮጵያ የነገሡት ነገሥታት ገንዘቦች ሁሉ በላያቸው የተጻፈው ቃል በጽርዕ ፊደል ሆኖ ሳለ የንጉሥ ዋዜብ ገንዘቦች ግን በቀድሞው በኢትዮጵያውያን ፊደል ተጽፈዋል። ስማቸውን የጠራነው የኢትዮጵያ ነገሥታት ሁሉ በየገንዘባቸው ላይ ያተሙት ምልክት የአረመኔ የአሕዛብ መለዩ ነው ይላሉ”። የኢትዮጵያ ነገሥታት በፊትም በሕገ ኦሪት የመኑ ሕገ ግዝረትንም ያጸኑ ሰንበትን አክባሪዎች እግዚአብሔርን ፈሪዎች ለመሆናቸው ብዙ ማስረጃ እያለ ፩ድ ፩ድ ምክንያት እየፈለጉ ከነሱ ለማመሳሰል ያረመኔነት ስም እየሰጡ ሲጽፉ ይገኛሉ። ግዕዝ የማያውቁትን ጥንታውያኑን ግዕዝ እንተረጕመዋለን ይላሉ። ይህ ሁሉ ሐሰትን ካለመጥገባቸው የተነሳ ነው ያረመኔ ያለበትን አምጡ ቢሏቸው ባይን ማሳየት የለም እንዲሁ ይመስላል በማለት ያለ ስማችን ስም ሲሰጡን ይገኛል “በ፺፰ ገጽ ባ፲፫ኛ መሥመር ይህ ሥዕል ከሜርዌ ባ፩ድ ትክል ድንጊያ ላይ በግሪክ ቋንቋ የተጻፈውን ይሳያል። ከጌታችን ከክርስቶስ በፊት በ፰ኛው ፻ ዓ. ውሥጥ ተመሥርቶ የጸናው አትባራ ዕባይ ኒል ከሚገናኙበት በስተደቡብ የሚገኘው ሜርዌ የትልቅ መንግሥት መናገሻ ከተማ ነበር በግብጽ ላይ የነገሡውን ፳፭ኛውን ዘረ መንግሥት የመሠረቱት የኢትዮጵያ ነገሥታ መኖሪያቸው የኖብያ ዋና ከተማ ናፓታና ሜርዌ ነበር የ፳፭ኛው የግብጽ ዘረ መንግሥት የሚናገረውን እዚህ በላይ ገጽ ፲፩ ተመልከት። በዚህ ጊዜ ከሱማል ጠረፍ ዠምሮ እስከ ግብጽ ያለው ሰፊ ሰፊው አገር ኢትዮጵያ ይባል ነበር በቅዱስ መጽሐፍ ላይ ስለ ኢትዮጵያ ነገር ስንናገር ይህነን አመልክትነዋል። ነቢይ ኢሳይያስ ስለ ኢትዮጵያ የተናገረውን መመልከት ያስፈልጋል ኖብያ የሜርዌ መንግሥት ለብቻ ኢትዮጵያ

የምትባለው አገርና። የሱማል አውራጃ ቅዱስ መጽሐፍና ግሪኮች ኢትዮጵያ ከሚሉት እጅግ ትልቅ ከሆነው አገር ልዩ ልዩ የሆኑ አውራጃዎች አገሮች ነበሩ።” እንግዲህ እዚህ ላይ ሰፊ ሐተታ ይገኛል መቸም የሮማ ልዑካን አሳብና ሞኞች ዛሬ የኢትዮጵያ መንግሥት በጁ የያዛትን አገር ስም የሌላት ትርፍ የቅኝ ቦታ አባት የሌላት ለማስመሰል ነው የሚደከሙት በዚህ መጽሐፍ ላይ ዋናው አስተያየታቸውና ዓላማቸው። ፩ኛ ሳባ የሚለውን

## ሞ ቀዳም ጥቅምት

ኢትዮጵያ   ስም ለደቡብ ዓረብ ለመስጠት። ፪ኛ ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ሜርዌና ኖባን ይዞ ወደ አፊር ላለው አገር ስጥቶ ይህችን ዛሬ በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ሌላ ለማድረግ ነው የሚደከመውና ይኸውም ዋና ተግባራቸው አገርና ወገን ለመለያየት ስለሆነ ይህኑ ዘወትር ሲደክሙበት ይታያል ይህኑ እየመላለሱ

ይተበትቡታል እስቲ ታሪክ አዋቂዎች ከሆኑ ከላይ እንደገለጽኩት ያለውን መሳቂያ ነገር የዮቅጣን ልጆች ከዓለም በሞት በተለዩ በ፪ሺ፪፻ ዘመን በላይ በፋርስ ነገሥታት ዘመን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ጦርነት አደረጉ መጻፍ ባልተገባቸውም ነበር ፩ዱን ከ፩ዱ እየቀጣጠሉ ከሻይና ከዳቦ ጋራ ሲአቀርቡት ለጊዜው አመስጋኙ ሲበዛ ስላዩ ከመጻሕፍቱ ውስጥም እየተገባ ሲዘባረቅ ይገኛል። ወደ መጻሕፍቱ መቅረብ ፩ኛ ሕዝቅኤል ፩ ፩ ወኮነ አመ ፴ ክረምት ፪ኛ ዕዝራ ፩ ፩ አመ ፴ ዓመት እንዘ ውድቅት ሀገርነ ያለውን ፴ ዓመትና ፴ ክረምት ብለው የተናገሩትን ይህ ፴ ዓመት ወይም ክረምት የተባለው። ፳ኤል የተማርኩበት ዘመና ማንም ፩ድ ጊዜ ባይሆን እነዚህ ሁለቱ ነቢያት እንደዚህ ብለው የተናገሩበትን ምሥጢር ማወቅ አስፈላጊ ሆኖ ለማወቅ ሲቻል ፳ኤል ወደ ኢየሩሳሌም የገቡበትን ለማወቅ ምቹ ይሆን ነበር ከሰው አገር ውስጥ ገብቶ ደርሶ ወሰንና ፊደል ያገር ስም በገጽ “፲፪ በ፳ኛው መስመር አሐሽዊሮስ የተባለው የፋርስ ንጉሥ ወይም አርጤክስስ ሁለቱም ፩ድ ናቸው በስም ስለተለያዩ እንጅ ለ፩ዱ ስም አሐዋሽሮስ ሲል ከክርስቶስ በፊት ከ፬፻፹፭ እስከ ፬፻፷፭ ፳ ዘመን ሰጥተውታል። ፪ኛደግሞ አርጤክስስ በሚባለው ስሙ ካ፬፻፷፭ እክሰ ፬፻፳፬ ዓመት ፵፩ ዘመን ሰጥተውታል። በዚህ ሂሳብ ፳ኤል ከናቡከደነ ፆር ዠምሮ እስከ አርጤክስስ ዘመኑ ሲቆጠር ፳ኤል የተመለሱበት ፸ዓው ዝመን ማለፉን መመልከት የለም የባቢሎን ነገሥታት ምን ያህል እንደገዙ ከዚያ ደግሞ በፋርስ ነገሥታት ምን ያህል እንደተገዙ የነገሥታቱስ ቁጥር ስንት እንደሆነ ማወቅ የተገባ ነበር ይሁን ደግሞ ታሪክ አውቂ ነኝ የሚል ሰው የዘመኑን ቁጥር ከታች ወደ ላይ ከቆጠሩ በኋላ ደግሞም ከላይ ወደታች መቁጠር የተገባ ሥራ ነበር ማለት ከላይ ከክርስቶስ በፊት ካ፬፻፹፭ ዓ በላይ ካሉ ደግሞ ከላይ ያለውን የዘመን ቁጥር ለሰው ለማትረፍ መቁጠር የተገባ ነበር ከፍጥረት እስከ ክርስቶስ ፭ሺ፭፻ን ምሥጢር ከፍጥረት እስከ ክርስቶስ መጸነሥ ድረስ ልክ ፭ሺ፭፻ ነው ፩ድ ፩ድ ሰዎች ባ፭ሺ፭፻ ዘመን እመጣለሁ ያለበትን ንባብ እንፈልጋለን እያሉ በግልጽ ተጽፎ ካላገኘን እያሉ የሚደክሙ አይታጡም። የሱ ሐተታ ይቆይና ጌታችን ስለ አዳም በደል ዲያቢሎስ በተንኮል ዘመን ተጠብቆ ጽዋ ሲሞላ በ፯ት ባ፩ንድ ጽዋ አዳምን ዕፀ በለስ አስበልቶ ከገነት ስለ አስወጣው ፯ትን ጽዋ የሚል ከምን ይገኛል የሚል ቢገኝ ኦሪት ዘፍጥረት ፬ ፳፬ እስመ ቃልየ ተፈጽየ ህየንተ ፩ዱ ፯ተ በቀለ። ላሜህሰ ይትፈደይ ፸ወ፯ተ ያለውን ይመልከት ይህም ፸ወ፯ተ ያለውን ፯ት ስትመድበው ፲፬ ይሆናል ስለዚህ የጽዋ መሠረት አመጣጡ እንደዚህ መሆኑን ከተገነዘብን በኋላ በጽዋ ቤት ዘመኑን ወደ መመደብ እንሄዳለን ፻፲ ፲ ጊዜ ፲፬ ስለሆነ ፲ ጽዋ ይባላል ፻፵ው። ፳ ጽዋ በዚህ ሂሳብ ፩ሺ፬፻ው ፻ ጽዋ ፭ሺ፭፻ ጸዋ ይሆናል። በዚሁ ጠብቆ ዲያቢሎስ በዚያው

## ሠ እኁድ ጥቅምት

ያዳምን አስቶ ከገነት ባወጣበት ዓርብ ቀን ዕፀ በለስን አብልቶ ቢያስወጣው በዕፅ ተሰቅሎ አዳም ከሲኦል አወጣው ስለዚህ ጌታችን ከተጸነሠባት ከሚያዝያ ፩ እሑድ ዠምሮ ዓመተ ምሕረት ተብሎ የሚቆጠር ስለዚህ ነው ከፍጥረት

እስከ ክርስቶስ ፳ሸ፫፻ ዘመን አልሞላም ማለት ያይሁድን የፖለቲክ ጽሑፍ ተከትሎ በስሕተት ምንገድ መጓዝ ማለት ነው። ይህም የዘመን ቁጥርና የሱባእው ምንገድ ተስማምቶ የሚገኘው በኢትዮጵያ መጻሕፍትና ፊደል ቁጥር መሆኑን ባለመገንዘብ የሮማ ልዑካን የማይቻለውን ነገር የኢትዮጵያን ስም እንለውጣለን ወይም እናጠፋለን ወይም ከዚህ ቦታ ሌላ ስሟን ገፍተን እንሰዳለን የማለት አሳብ አለባቸው ስለዚህ ግፊያው ከመሬቱ ጋር ሆነባቸው ማለት ስሟ ከመሬቱ የተሳማማ ስለሆነባቸው ለፍተው ሊያልቁ ነው። ይህ አሳባቸው እንደሚያደርሳቸው እኔ ገምቸ ልኩን ልናገረው የሚቻለኝ አይደለም። "በ፸ኛው ገጽ በ፩ኛው መሥመር የኢትዮጵያ ንጉሥ ነገሥት ትልቁ ዔዛና ከ፫፻፳፭ እስከ ፫፻፷ ዓ. ግድም የነገሡ ንጉሥ የአልዓሜዳ በሞተ ጊዜ ልጁ ዔዛና ትንሽ ነበር በዚህ ምክንያት

መንግሥቱን ይዞ መግዛት አልቻለም። ባለመቻሉ የመንግሥት እንደራሴ ሆኖ የሚገዛ የሞግዚት መሪ መምረጥ አስፈልጎ ነበር። የኢትዮጵያ መጻሕፍት ግን ከናቱ ከሶፍያ ጋር ገዛ ይሉና"። እንግዲህ ይህ ከላይ የተጻፈው ሁሉ ፩ድ እውነት የለበትም በፍጹም ሐሰት ነው። አልዓሜዳ የሰላዓዶባ ልጅ የዔዛና አባት በ፫፻፳፭ ዓ.ም ገና አልተወለደም ደግሞም በድፍረት ከናቱ ከሶፍያ ጋር ገዛ ይሉናል ተብሎ የመጻሕቱም ስም ለይምሰል ተጠርቷል። ምን ይገርም ታሪክ ከሆነም አይቅር ታሪክ እንደዚህ ነው ለመሆኑ እንደዚህ የሚነገረውን የኢትዮጵያን ታሪክ መጽሐፍ አምጥታችሁ አሳዩን ተብለው ቢጠየቁ ምን ይመልሱ ይሆን። ግን ከላይ በእኔ ጽሑፍ ካ፩ደኛ ዠምሬ እስከዚህ ገጽ እስከደርስ እነሱ በኢትዮጵያ ላይ የሚጽፉትን ፖለቲክ ለዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ዘርተውት እነዚያም እንደ ሕጉ የታሪክ ጽሕፈት እውነት እየመሰላቸው ስንኳን የውጭ አገር ሊቃውንቶችና በኢትዮጵያም የሚገኙ ብዙዎቹ ደራስያን እነሱ ያስተላለፉንት ኮፒ እየጻፉ ለወጣቶች እንደቀረበላቸውና ወጣቶችም እንደ ተቸገሩ እያየሁ ስለዚህ ጉዳይ የሮማውያን የፖለቲክ ስብከት የብዙዎቹን ወጣቶች ልብ አበላሽብን በማለት የዚህ ጽሑፌ ዓላማ መሆኑን ከላይ ያለው ጽሑፌ ያስረዳል። እኔ የኢትዮጵያ ታሪክ ነው ብየ ልቀበለው የምችለው የሮማ ልዑካን ወደ ኢትዮጵያ መምጣት ሳይዠምሩ የተጻፈ ልክ ፬፻ ዘመን ዕድሜ ያለው ካልሆነ በተቀር ከዚህ ወዲህ የተጻፈ ጽሑፍ በግዝም ቢሆን አልቀበለውም። ስለዚህ በየገዳማቱና አድባራቱ በሸ የሚቆጠሩ ጥንታውያን መጻሕፍቶች ንግሥት አሕየዋ (ሶፍያ) የአልዓሜዳ ሚስት ነበረች የሚል ጽሑፍ ተጽፎ ቢገኝ እንደዚህ ያለው መቃወም ከፍ ያለ ፖለቲክ የሚነካ ስለሆነ ለመቃወም ባሰብሁበት ቅጣት ይገባል ስል በራሴ መፋረዴን አረጋግጣለሁ "በ፸፪ኛ ገጽ ባ፳ኛው መሥመር ከነዚህ ፲፩ዱ ሐውልቶች ከ፫ቱ ሐውልቶች ላይ ያገኘነው ታሪክ ቅርጽና ጽሕፈቱን ተርጒመን አሳትመናል የቀሩትን ሐውልቶች ታሪክ አይቶና መርምሮ ለመረዳት የሚፈልግ ሰው ቢገኝ ግን የጀርመርንና የኢጣልያ ሊቃውንቶች በጻፏቸው መጻሕፍቶች ላይ ሊአገኝ ይችላል ብለዋል"። እኔም ከላይ ያመለከትኩት ይህንኑ ነበር እንደዚያው እኔ እንዳልኩት የኢጣልያና የጀርመን ሊቃውንቶች የጻፉትን ማየት ይላል

# ሥ ሰኑይ ጥቅምት

ሲል ይገኛል የ፫ቱን ሐውልቶች ጽሑፍ ተርጒመን አሳትመናል ይላል ለዚህም ምስክሮች የተቆጠሩ የኢጣልያና የጀርመን ሊቃውንቶች ሆነው ተገኙ እንግዴህ እኔ የምቀበለው ይህ ነው ይሆንን። "፪ኛ ከዚሁ ገጽ ትልቁ ንጉሥ ዔዛና በሐውልቶቹ ላይ ቀርጾ ያሰፈራቸው ታሪኮችም የጽሕፈታቸው ቃል በ፫ ዓይነት ቋንቋ የተጻፈ ነው። እነሱም ቋንቋዎች በአክሡም ዘመነ መንግሥት ጊዜ በታወቁትና በተለመዱት በ፫ቱ ቋንቋዎችና ፊደሎች የተጻፉ ናቸው። እነዚህም ቋንቋዎች ፩ኛ ሳባውን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሲመሠረቱ ሲነጋገሩበት የነበረው ፪ኛ ጥንታዊ የሆነ ግዕዝ የተባለ የኢትዮጵያ ቋንቋ ነው። ፫ኛ የአክሡም መንግሥት የሥልጣኔ መምሪያ ሆኖ ከግዕዝ ጋራ እንደ ሠላጤ ሆኖ የነበረ ቋንቋ"። ከላይ የተጻፉትን ፫ቱን አርስቶች ልብ አድርጎ ማስተዋል ያስፈልጋል። ፩ኛ የተባለው የሳባ ፊደል ነው። ይህ የሳባ ፊድል የተባለውና የጥንታዊ ግዕዝ የተባሉት የፊደል መልክ ተለይተው አይገኙም ማንም አንባቢ ፈልጎ ሳባውያን ፊደል መልክና የጥንታዊ ግዕዝ መልክ ተለይቶ ስለማይገኝ እዚህ ላይ ብርቱ ችግር አለ። ማለት የፊደሎች መልክ ዓይነት

፩ድ ሲሆን ስሞች ፪ት እንደምን ሆኑ። እዚህ ላይ ሰፊ ሐተታ ያስፈልጋል። ይህ እንደኛ ሆኖ የተቈጠረው ሳባዊ የሚለው ንግግር ያለቦታው የገባ መሆኑን ላንባቢዎች እገልጻለሁ ሳባ የሚባለው ስምም የኢትዮጵያ ገንዘቧ ነው ፊደሉም ዓለም ያወቀው ገንዘቧ ነው። ፪ቱም የኢትዮጵያ የታወቁ ገንዘቦቿ መሆናቸውን ከላይ ማስረጃውን ሰጥቻለሁ። ግን የሮማ ልውካን ከሀገራቸው የፖለቲክ ማሳኬጃ

ማኅበራቸውን አቋቁመው በመጡ ጊዜ በልባቸው የኢትዮጵያን ስምና ፊደል አጥፍተን እኛ ባዲስ መሥርተን አቅንተን እንቀመጥባታለን የሚል ቁርጠኛ ሐሳብ ስለነበራቸው ይህኑ አሳብ እንደ ጸሎት ሌትና ቀን ሲወተውቱ አእምሮአቸው እንደ መለወጥ ፩ድ ፩ድ ሰው አለ በቀን ሲያየው የዋለውን ሌሊት የሚለፈልፍ አሁንም እንደዚሁ ይመስለኛል። በሕልማቸው የጻፉት። በሕልማቸው ካልሆነ እውነት በደህናቸው ይህን ጽሑፍ ጻፉ ለማለት እኔ ለራሴ ሳስበው ይህ ነገር ይቸግረኛል እንግዲህ ለሳባውያን ፊደል መልክ መቸም ልዩነት አለው የሚል ማስረጃ ሊገኝለት አልተቻለም። ቢሆንም ባይሆንም ከዓረቦች ወገን የመጣው ፩ድ ነገር አለ። እሱም ከቀን ወደ ግራ እጅ መጻፍና ማንበብ ነው። የዚህ ሐተታ ወደ ፊት ይገኛል። ፫ኛ የተባለው ፊደል ከጽርዕ ኢትዮጵያ በዘመኗ ከሀገሯ ላይ የሚገኙ ብዙዎች ሀብቶች በነበርዋት ጊዜ የጽርዕ ነጋዴዎች በኢትዮጵያ ከተሞች እየገቡ ዕቃ ስለሚገዙ። የኢትዮጵያ ነጋዴዎች ወደ ግሪክ አገር እየሄዱ የፈቀዱትን ስለሚገበያዩ ፪ቱ መንግሥታት በንግድ ስለተስማሙ ግሪኮች የግዕዝን ፊደል ኢትዮጵያውያን የግሪክን ፊደል ለንግድ መገናኛ በቋንቋም መለዋወጣቸውና መገናኘታቸው እርግጥ ነው። በሐውልቱም ላይ የተጻፈውን የውጭ አገርም ሰው እንዲያውቀው በማለት ባ፩ድ ገጽ ባ፩ድ ገጽ የጽርዕ ቋንቋ መታየቱ ስለዚህ ነው እንጅ ኢትዮጵያን ግሪክ ገዥዋ ወይም አሠልጣኝዋ ነበረች የሚል ተጽፎ አላገኘንም በዓለምም አልተስማም እነ አባ ጋስፓሪን ግን ባ፩ድ ጐን የተጻፈውን የግዕዙን ጽሑፍ እየተው የክሪኩን ጽሑፍ እያደናነቁ ሲጽፉ ይታያሉ ምክያቱም ኢትዮጵያን የግሪክ ጥገኛ እንደማስመሰል ያለ ነው። ይህንም ያሰቡበት ኢትዮጵያን አስቀድሞም ነጻነቷ ተከብሮ የኖረ አልነበረም ለማለት ምክንያት

## ሢ ሠሉስ <u>ኅዳር</u>

ያገኘን እየመሰላቸው ነው። የሮማ ልውካን አሳብ እስከዚህ መሆኑን ማሰብ ነው። ደግሞ ወደ "፺ ፪ኛው ገጽ በ፳፪ኛው መሥመር ትልቁ ንጉሥ ዔዛና ፊደሉን ሳባዊ ምሥጢሩንና ቋንቋውን ግዕዝ አድርጎ የዘመቻውን ታሪክ በሐውልት ላይ ቀርጾና ጽፎ አስገኝቶ ነበር በሳባዊ ፊደል ተጽፎ የነበረውን የግዕዝ ቋንቋ በርሱ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ቋንቋ በኢትዮጵያ ላይ ታውቆና ተለምዶ ነበርና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከግዕዝ ጋር አስተባብሮ እንዲአነበው ሲል ወደ ጽርዕ ቋንቋ አስተረጐመው ይላል"። አሁንም ያነኑ እየመለሱ ይጨምቁታል ነገር ሲመላለሱት ቢውሉ ሐሰቱ እውነት ለመሆን አይችልም እነሱ ግን ሐሰቱን በመመላለስ እውነት የሚሆን እየመሰላቸው። ያነኑ ሲመላልሱ ዓምዱን ያበረከቱታል እንግዲህ ረቂቁን ታሪክ ልብ ብሎ ማስተዋል ነው። ፊደሉን ሳባዊ ምሥጢሩንና ቋንቋውን ግዕዝ ላስተዋለውና ለመረመረው ይህ ንግግር ብቻ ይበቃል እስቲ አንባቢዎች ይህን ጽሑፍ አስተውሉት ነገሩ ሐሰት ስለሆነባቸው በጣም ይቸገራሉ ነገሩም አልገጥም በማለቱ ይታወቃል ፊደሉን በሳባዊ ምሥጢሩንና ቋንቋውን ግዕዝ አድርጎ የዘመቻውን ታሪክ በሐውልት ላይ ቀርጾና ጽፎ አስገኝቶ ነበር የተባለው በ፻፫ኛ ገጽ የሚገኘው ጥንታዊውን ጽሑፍ ነው። የግዕዙን በሱ ዘመነ መንግሥት ጊዜ ወደ ጽርዕ ቋንቋ አስገለበጠው የተባለው ባ፲፪ኛ ክፍለ ባ፭ኛው ገጽ ላይ በግሪክ ተጽፎ የሚገኘው ነው። እነዚህም በግሪክ ተጽፈው የሚገኙ ሐውልቶች ሁለት ናቸው ማስተዋል ነው። እነዚህም በማስተዋል ለተመለከተ ሁለቱ ሐውልቶች ለየብቻ ናቸው ፩ኛው ጥንታዊው እርግጠኛውን ታሪክ ይዞ የሚገኘው ነው። ፪ኛው ቁመቱ ረዘም ያለው እነሱ ቃሉን አዲስ ፈጥረው የጻፉት ነው እንጅ ከዚያው ከጥንታዊው የተገለበጠ ነው ብየ አላምንም። ማለት እነሱ የሐሰት ጽሑፍ የሚጽፉበትን የማውቅበት ነገር አለኝ ባ፲፪ኛው ክፍል

ባ፩ኛው ገጽ የተጻፈውን የግሪክ ቋንቋ ገለበጥነው ያሉትን ፴፩ መስመር ጽሑፍ ግልባጭ በ፻፫ኛው ገጽ በጥንታዊ ፊደል እንደዓረቦች እንዲመስል ከቀኝ ወደ ግራ እጅ በ፴ መስመር ጽፈውት የሚገኘው ነው።

ደግሞ ጥንታዊው የኢትዮጵያ ፊደል መልክ። የሳባውያን ባረቦች ፊደል ተብሎ ከቀኝ ወደ ግራ የተገለበጠውን ከ፻፫ ገጽና ባ፻፭ኛ ገጽ ፳፪ መስመር ሆኖ ፩ኛ በግዕዝ ተገልብጦ ይገኛል።

ግዕዙ ደግሞ ከ፻፭ኛው ገጽ ከ፳፩ኛው መሥመር ዠምሮ ባማርኛ በ፻፫ኛው ገጽ እስከ ፴፩ኛው መስመር ተጽፎ ይገኛል።

ይህ ሁሉ ድካምና ልፋት የኢትዮጵያን መሠረት ለመሰርሰር ጥንታዊ ታሪኳን ለመለዋወጥ ነው የኢትዮጵያ ነገሥታት ጽላተ ሙሴ ከመጣች ወዲህ በፍጹም ለጣዖት መስገድ ጣዖትም ማቆም የሌለውን ስንኳንስ ጽላተ ሙሴ ከመጣች ወዲህ እሷ ሳትመጣም በኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ እገሌ ጣዖት አቁሞ ይሰግድና ያሰግድ ነበር የሚል ጽሑፍ በኢትዮጵያ የተጻፈ የማይገኝባትን። በፊትም ከነቢያት ከሌዋውያን ዘሮች በኋላም ከሐዋርያት ከሰብዓ አርድዕት ከሰማዕታት ደም ንጽሕት ሆና የምትገኘቱን ትርጓሜ ሀገር የሮማ ልውካን በሀገራቸው ያጠኑትን የጣዖት ታሪክ ትርጓሜ እያመጡ አስጠግተውብን ይገኛል። አንባቢ ሆይ እንግዴህ እነዚህን ከላይ በ፫ት ፊደሎች የተጻፉትን ከፅርዕ ቋንቋ አስገልብጠን ተብሎ "በ፬፻ ገጽ በ፳፫ኛው

# ሣ ረቡዕ ኀዳር

መስመር ከዚህ ቀጥለን የኢትዮጵያ ወጣት የሆኑት ተማሮችና ጥበብ ፈላጊዎች ትልልቆች ሊቃውንቶች ከግዕዝ በፊት የነበረውን የጥንታዊ ቋንቋቸውን ጽሕፈት አነባበቡን አጻጻፉን አይተው ይረዱ ዘንድ ጽሑፉን እናያለን ሳባዊ ጽፈትና ንባቡ የሚጻፈውና የሚነበብው ከቀኝ ወደ ግራ ነው። የጽፈቱ ቃል የሚለይበት ዓረፍተ ነገሩም በሥዕሉ እንደሚታየው በ፪ት ነጥብ ሳይሆን ዘንግ በመሰለው መለያና መ በመሰለው ጽሑፍ ነው ከላይ የተጻፈውን የሳባዊ ጽሕፈት ልዩነት እንዲረዱት ስንል ነው። የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ትልቁ ዔዛና ብጋ በተባሉት ፺ት ነገሥታትና ሕዝቦች ላይ ያገኘው ድል ከግሪክ ቋንቋ ወደ ጥንታዊው ሳባውያን ፊደል የተገበጠው"። ፩ኛ ከግዕዝ በፊት የነበረውን የጥንታዊ ቋንቋቸውን ጽሕፈት አነባበቡንና አጻጻፉን አይተው ይረዱ ዘንድ ጽሑፉን እናሳያለን ያሉት ከግዕዝ በፊት የነበረ ጽሑፍ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አለ ለማለት አይቻልም በዚህ የነበረ ጽሑፍ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አለ ለማለት አይቻልም በዚህ መጽሐፍ ላይ ከቀኝ ወደ ግራ ዞሮ የሚነበብ ሆኖ ተጽፎ የሚገኘውም ፊደል ራሱ ግዕዝ ነው። አጃ ወቅጠው ቢዘሩ ተመልሶ ከዘሩ እንዲሉ ከቀኝ ወደ ግራ ሆኖ ተጽፎ ቢገኝም የፊደሉ መልክ ቅርጹን ለውጦ እብራይስጥና ዓረብ ለመሆን አይቻሉም። እብራይስጥንና ዓረብንም ፊደል ከግራ ወደ ቀኝ እያዛወሩ ቢጽፉት መልኩ ተለውጦ ግዕዝ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ ከግዕዝ በፊት የነበረ ፊደል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አለ ብሎ ልከራከር ቢለኝ እኔ የምመለከተው የሰውየውን አንጐል ልክ መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ ብቻ ነው።

፪ኛ ሳባዊ ጽሕፈትና ንባብ የሚጻፈውና የሚነበበው ከቀኝ ወደ ግራ ነው ለሚለው እኔ የፊደሉን ቅርጽ ብቻ ግዕዝ መሆኑን እጅግ አጻጻፉ ከቀኝ ወደ ግራ ተጽፎ በመገኘቱ አሁን አልቃወምም። እኔ አሁን አጥብቄ የምቃወመው በ፻፫ኛ ገጽ ከቀኝ ወደ ግራ ተጽፎ የሚገኘውን የፊደል ቅርጽ ግዕዝ ነው እያልኩ ነው የምቃወመው። ይህን የፊደል ቅርጽ ማን ይባላል ብየ ስጠይቀው እብራይስጥ ወይም ዓረቢ ወይም ሱርስት የፊደሉ ቅርጽ ይህ ነው ቢለኝ በመልካም ፍቅር በብርቱ ትጋት መረጃውን አሳየኝ ብየ መረጃውን ካየሁ በኋላ የነዚህን ፊደሎች ቅርጽ ባገኘሁ ጊዜ ለመረታት እችላለሁ። በተረፈ እነ አባ ጋስፓሪን የጽሑፍ አገላባበጥ ሥራቸው መሆኑን ስለማልዘነጋው የግዕዝ ፊደሎችን ከቀኝ ወደ ግራ

አዙረዋቸው ባገኝ ቢሆንልኝ ወደ ጥንተ ቦታቸው ለመመለስ እደክማለሁ የግዕዝ ፊደሎችን መልክ እያየሁ ሌላ ናቸው ብሎ

ቢነግረኝ ካይኔ የበለጠ ዋጋ ለዠሮዬ ልሰጠው የሚቻለኝ አይደለሁም። በዠሮው ሰምቶ የሚከተልም ይኖራል እሱም ካይነ ዕውራን ውስጥ ይሆናል። እኔ ግን ዓይኔ በወሬ የምነዳ አይደለሁምና የግዕዝን ፊደሎች መልክ እያየሁ አለቅም እሞትባቸዋለሁ እንጅ በማጭበርበር ሊነጠቅ የታሰበው አይቻልም ሕልም ነው። ፫ኛ የጽሕፈት ቃል የሚለይበት ዓረፍተ ነገሩም በሥዕሉ እንደሚታየው በ፪ት ነጥብ ሳይሆን ዘንግ በመሰለው መለያና መን በመሳሰለው ጽሑፍ ነው እነዚህ ሁሉ ፩ደኛ ፪ኛ መ ምልክቶች ቅርንጫፍነታቸው ለግዕዝ መሆናቸውን ለመመስከር አስቦ ምስክሮቹን እንደማቅረብ ከርዳታ የሚቆጠር ያህል ነው ስለዚህ እነዚህ ምልክቶች የግዕዝ ዳዞች ለመሆናቸው መረጃ ይመጣል። ፬ኛ ከላይ የተጻፈውን የሳባዊ ጽሕፈት ወደ ግዕዝ ጽሕፈትና ቋንቋ ገልብጠን። ወደ አማርኛ

# ሜ ኃሙስ ኅዳር

የመተርጐማችን አንባቢዎቻችን አነጣጥረውና አመዛዝነው ፪ቱ ጽሕፈት ልዩነት እንዲረዱት ስንል ነው የሚለው ንባብ ሳየው በጣም አባ ጋስፓሪንን አመሰግናለሁ በሳባዊ ጽፈት የተባለውን ፊደሉ ግዕዝ ከቀኝ ወደ ግራ ሆኖ ከተጻፈው ማለት ነው። ወደ ግዕዝ ገልብጠን የተባለውን ከታች የተጻፈው እየተሻሻለ በመጣው ባዲሱ ፊደል ቅርጽ የተጻፈውን ነው። የኛ መምር የሮማ መናኒ የኢትዮጵያ አሳቢ ግዕዝ የሚሉት ባዲሱ ፊደል የተቀረጸውን ማለታቸው ነው። የኛ መምር አሁን ካለው ካዲሱ ፊደል ቅርጽ በፊት የነበረውን ለመመርመር አልቻሉም ይመስለኛል። ደግሞ ወደ አዲሱ ፊደል ግዕዝ መገልበጣችን ከግዕዝም ወደ አማርኛ መተርጐማችን አንባቢዎቻችን አነጣጥረውና አመዛዝነው የሁለቱን ጽሕፈት ልዩነት እንዲረዱት ስንል ነው ብለው የምርመራ ፈቃድ በመስጠታቸው እያመሰገንሁ የሁለቱን ጽሑፎች ልዩነት ምርመራ ስቀጥል ደስ እያለኝ ነው። እነዚህም ፪ቱ ጽሑፎች ከግሪኩ ጽሑፍ ላይ ከ፴፩ መስመር የተጻፈው ማለት ነው። ፫ኛው ባዲሱ ግዕዝ ፊደል መልክ ከግራ ወደ ቀኝ ሆኖ የተጻፈው ማለት ነው። ፬ኛ ደግሞ ባማርኛ የተተረጐመውም አለ እንግዴህ አባ ጋስፓሪንም ፈቃድ አድርገዋል እንደፈቃዳቸው የጽሑፎችን ትክክልነት ወይም ልዩነት መመርመር የተገባ ስለሆነ እዚህ ላይ ፩ድ ከባድ ጥያቄ ይገኛል። ይህም ጥያቄ ከግሪኩ ፊደል እንደተገለበጠ ነውን ወይስ ባዲሱ ግዕዝ ፊደል መልክ የተጻፈው ነው አስቀድሞ የገልበጣችሁት በየትኛው እንደሆነ ለማወቅ ነው። ሆኖም የጽሑፉን አመጣጥ ስንመለከት በግሪክ ቋንቋ ከተጻፈው ሐውልት ላይ የተገለበጠ መሆኑን በ፻፪ኛው ገጽ በ፳፩ኛው መስመር እስከ ፻፫ት መ የሚገኙ ፲፬ት መሥመሮች ውስጥ ይሉ ጽሑፎችን በ፲፪ኛ ክፍል ባ፬ኛ ገጽ ከግርጌ በተጻፈው የሚገኘው ያስረዳል። እንግዴህ ይህን መሠረት በማድረግ በሳባዊ ፊደል ከቀኝ ወደ ግራ የተጻፈውንና ባዲሱ ቅርጽ ግዕዝ የተጻፈው ቃሉን ስናመዛዝነው ትክክል ሆኖ አይገኝም የ፪ቱም ጽሑፎች መስመር ፳ ነው። ቃሉ ግን የተለየ ነው ከቀኝ ወደ ግራ በተጻፈው ፩ኛ በ፺ኛው መስመር /፺ቱ ነገሥት ብሎ ፵፻ወ፬፻ የሚለው የለም ፤ ፪ኛ በ፳ኛ ፴፪ ፻፲፪ቱ-፳፩ ፪፻ ፳፬ የሚለው የለም ፤ ፫ኛ ባ፲ኛው ፪፻፻ ፳፻ የለም ፤ ፬ኛ ፲፰ኛ ፪፻፻ ፶፻ ፻፵ የለም ይህ ፲፺ት ፤ ፭ኛ ፲፰ኛ ፵፻ ፻፯ የለም ይህ ፲፰ ተዛውሮ ነው

ከቀኝ ወደ ግራ በተጻፈው በጥንታዊው ግዕዝ መልክ ከላይ የተጻፉ አኃዞች ሳይጻፉ ባዶ ባዶ ስፍራ ቀርቶ ይገኛል። በምን ምክንያት ባዶ ስፍራ ተገኘ በምንስ ምክንያት ባዲሱ ግዕዝ ፊደል ቅርጽ ላይ እነዚህ

አኃዞች ከምን መጥተው ተተረጐሙ። ይህ አዲሱ ግዕዝ ፊደል ቅርጽ ቀደመ እንዳልን "በ፻፪ ገጽ በ፳፪ኛው መሥመር ትልቁ ንጉሥ ዔዛና ፊደሉን ሳባዊ ምሥጢሩንና ቋንቋውን ግዕዝ አድርጎ የዘመቻውን ታሪክ በሐውልት ላይ ቀርጾና ጽፎ አስገኝቶ ነበር ሳባዊ ቋንቋ ጽፎት የነበረውን የግዕዙን ቋንቋ በርሱ ዘመነ መንግሥት ሕዝቡ እንዲላመደው ወደ ጽርዕ ቋንቋ አስተርጐመው"። እነዚህ ሁሉ ንግግሮች ሕግ ያልያዙ የማይጨበጡ ናቸው ፩ኛ ንጉሥ ዔዛና

# ሥ ዓርብ ኀዳር

ፊደሉን ሳባዊ እዚህ ላይ ሳባ ማለት ኢትዮጵያን ሆኖ ቢሆን የተመቸ ነበር ግን ለዓረብ እየሰጡ የግዕዝ ፊደል ለማይመስለው እሰጣለሁ። ማለት የነዚያን የደንቆሮዎችን ነገር ያሳስባል። በሀገራችን የሚተረት አለ። ፩ድ ደንቆሮ ሴት ልጅ አዝላ እህል ስታርም ደግሞ ፩ድ ደንቆሮ ሰው በጎችና ፍየሎች ጠፍተውበት ወደ ደንቆሮዪቱ ሴት ለመጠየቅ ሄደና በጎችና ፍየሎች አየሽልኝ ወይ ብሎ ቢጠይቃት ስታርመው የዋለችውን ለማሳየት በእጅዋ ጠቅሳ ስታሳየው ወደዚያ ዓይኑን አሳልፎ ቢመለከት ፍየልና በጎች ስለተኙለት ከነዚያ ውስጥ ፩ እግረ ሰባራ በግ አምጥቶ ቢሰጣት እኔ በግህን አልሰበርኩም በማለት ተጣላችውና ወደ ዳኛ ሄዱ ዳኛውም ደንቆሮ ነበርና የሚሉትን ሳይሰማ ልጅ አዝላ ስላያት በልጅ የተጣሉ መስሎት ልጅዋን ከጀርባዋ ነጥቆ ለሰውየው ሰጠውና ልክ አንተን ይመስላል ይዘህ ሂድ አለው ይባላል። መቸም እኔ የምደክመው ይህ ያባ ጋስፓሪን ታሪክ ሁሉ ሐሰቱን ተገልሶ የሚታይበትን ምንገድ ለማስፋት ስለሆነ። የኢትዮጵያ ነገሥታት ቤተ ክርስቲያንን በሰፊው አደራጅተው በነበሩበት ዘመን ባ፬፻፺፫ ዘመን ላይ የነበረውን ንጉሠ ነገሥት ዔዛና ከስድስት ነገሥታ ጋር ተዋግቶ ድል ባገኘ ጊዜ ሐውልቱ ላይ አስጽፎት የነበረ ነው ተብሎ ከሐውት ላይ ተገልብጦ ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተገለበጠ የተባለውን ለአንባቢዎች ለመግለጽ ባ፹፬ኛው መሥመር እኛ ዔዛና የአክሡም የሕምያር የረይዳን የሐበሳት የሳባ የሠልሄ የድያሞ የካሱ የብጋ ንጉሠ ነገሥት የሆን በጠላት ድል የማይሆን የመኃረም ልጅ እኛ ዔዛና የብጋ ሕዝቦች በግፍ ስለተነሡብን እነርሱን ለመውጋት ሥዓዛናና ሐዴፋ የተባሉትን ፪ቱን ወንድሞቻችንን ላክንባቸው ከነርሱም አገር ከደረሱ በኋላ ፮ ነገሥታት ከነነገዳቸው በሰላም ተገዙላቸው በሰላም ከተገዙላቸው በኋላ ግን እነዚህ ፪ቱ ወንድሞቻችን ፮ቱን ነገሥታት ከነልጆቻቸውና ከነሚስቶቻቸው ሕዝቦቻቸውን ከነከብቶቻቸው ወደ ሌላ አገር በጉዞ እንዲሄዱ አዘዙዋቸው የነዚህም የ፮ቱ ነገሥታት ሕዝቦች ቁጥራቸው ፵፻፬ አራት ሽ፻፬ የበጎቻቸውም ቁጥር ፫፻ ፪፻፹፬ ፯ሽ ፪፻ ፹፬ የጭነት አጋሰሶቻቸው ቁጥር ግን ሐውልቱ ስለ ተሰበረ ልካቸውን አይናገርም። እነዚህ ፮ቱ ነገሥታት ከነሕዝቦቻቸው አገራቸውን ለቀው ፬ ወር ያህል ሲጓዙ የሚበሉትንና የሚጠጡትን ምግብ በየቀኑ ይሰጡአቸው ነበር የምግቡም ዓይነት እንጀራም በቀን ፹፪ ነበር የሚጠጡትም እንደሚበቃቸው ያህል ጠላና ነቢት ይሰጧቸው ነበር እነዚህ ምርኮኞች የሆኑት ፮ቱ ነገሥታ ከሕዝቦቻቸው ጋር ወደኛ ወደ አክሡም መዲናችን ከደረሱ ኋላ ግን ፮ቱን ነገሥታት ከነሕዝቦቻቸው ልብሳቸውን ለውጠን ሌላ ልብስ አለበስናቸው። ፪ኛም ለነገሥታቱ ልዩ ልዩ ልብስ አለብስናቸው አልብሰንም ደለወ ገይራን በተባለው አገር ከደረሱ በኋላ እንዲቀመጡ በክብር ላክናቸው ወዳዘዝንላቸው ክፍለ አገር ከደረሱ በኋላም የሚመግቧቸውን የሥጋ ከብቶች ለያንዳንዱ ንጉሥ ድርሻው ፬ሺ፻፫ የሚሆን ከብት አዘን በድምሩ ለ፮ቱ ነገሥታት ፹፫ሺ፻፺ ያህል ፍሪዳ እንዲደርሳቸው አድርገን እኛ ዔዛና ንጉሥ ለወለደን ላባታችን ለመሐረም የክብር መታሰቢያ እንዲሆን ይህን ሐውልት አሠርተን

# ሦ ቀዳም ኀዳር

የወርቅ የብር የነሐስ ፫ቱን ምስል አቆምንለት ከዚህ በኋላ ይህን የሠራነውን ታሪክ በዝርዝር ጽፈን ከሐውልቱ ሥራ ውስጥ አግብተን ለአሥተር ለምድር ለወለደንም ለመሓርም እጅ መንሻ አቀረብንላቸው ይህን ያቆምነውን ሐውልትና ሥዕል የሚአበላሽ በብረትና በድንጋይ የሚወቅረው ከተቀመጠበትም ስፍራ ገልብጦ የሚጥለው እርሱ ራሱ ይሙት ዘሩና ልጆቹም ካገር ተነቅለው ይጥፉ ይህን ሐውልታችንን የሚአከብር ሰው ግን ይባረክ እኛ ያቆምነው ሐውልት ለኛ መታሰቢያ ሆኖ በመዲናችን ላይ ለዘላለም ይኑር ለመሐረም አባታችን የተከለለውን ቦታም ሰፊ የሆነውን አደባባዩን አስቀድሰን ሰጠነው ይላል” አሁን እኔ ላንባቢዎች የማመለከተው እነዚህን በ፫ት ደረጃዎች ሆነው የተጻፉትን ማመንና መቀበል የተገባ አለመሆኑን እንደምትመረምሩና እንደምትረዱ ለማመልከት ነው ፩ኛ በ፻፫ኛ ገጽ የሚገኘው ከቀኝ ወደ ግራ እየዞረ ተጽፎ የሚገኘው።

፪ኛ በ፻፷ ገጽ እንደዚሁ ከቀኝ  ወደ ግራ ተጽፎ የሚገኘው

፫ኛ በ፻፴፯ኛ ገጽ እንዲሁ ጥንታዊው የፊደል ግዕዝ ቅርጽ ከቀኝ ወደ ግራ እየዞረ ተጽፎ የሚገኘው የቀሳጢነት ያታላይነት ሥራ የሚገኝበት ሕገ ወጥ ጽሑፍ ነው እንጅ የታሪክ ሕግ ይዞ የተጻፈ አለመሆኑ የምትገነዘቡበት። ፬ኛ ዔዛናን ጣዖት አቁሞ ነበር እያሉ የጻፉትን ለማግኘት በ፻፬ ገጽና በ፻፫ኛ ገጽ ለወለደኝ መኃረም ፫ ሐውልት ፩ድ የወርቅ ፩ድ የብር ፩ድ የነሐስ ይላል ለዐሥተርም ይላል። ይህ ሁሉ በፍጹም የጠላትነት ሥራ ነው እንጅ በእውነት የታሪክ ሕግ ይዞ የሚሄድ አለመሆኑን እንድትገነዘቡ ነው። እውነተኛውን ታሪክ መርምሬ ልረዳ የሚል በ፻፫ኛ ገጽ የተሳለውንና የሱን ትርጒም ከ፩ድ እስከ ፳፪ መሥመር የተጻፈውን ባስተዋላችሁት ጊዜ ባዲሱ ግዕዝ ፊደል መልክ ተጽፎ የሚገኘው አጎዝ ባዶ ሆኖ ታገኙታላችሁ እዚህ ዋናው ተንኮ በጥንታዊ ፊደል መልክ የተጻፈው ሁሉ የዔዛና አይደለም እርግጠኛ የዔዛና የታሪክ ሐውልት ጽሑፍ በ፻፲፩ ገጽ የሚገኘው በጅ ያልተከለሰው እሱ ነው።

ዔዛናን አሕዛብ ነበር ጣዖትም አቁሞ ነበር እያሉ የጻፉት የሐሰት ስብከት ሞልቷል። እስቲ በዚህ እነሱ ባልከለሱት ላይ የአሕዛብ ምልክት የሚገኝ እንደሆነ ማንም ይመልከተው። የሮማ ልዑካን አይታወቅብንም እየመሰላቸው የጻፉት ፖለቲክ "በ፻፫ኛ ገጽ በ፳፱ነኛው መስመር ማስታወቂያ ፩ኛ ይህ ትልቁ ዔዛና በተባለው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የወለደው አባቱ አልዓሜዳ መሆኑን በሚመጣው እናስረዳለን ትልቁ ንጉሥ ዔዛና መሐረም የተባለውን ሐሰተኛ አምላክ የወለደኝ አባቴ ብሎ መጥራቱ በአረማዊነት ሳለ ጦርነት ሄዶ ድል እያደረገ ስለሚመለስ እንደጽርዓውያንና እንደሮማውያን ልማድ ከጥቃትና ከውርደት ያዳነኝ አምላኬ ነው ሲል ወለደኝ አለው እንጅ የወለደውስ አባቱ አልዓሜዳ ነው ይላል"። እንግዴህ ማስተዋል ነው እንዲሁ ከመሬት ተነሥቶ ፩ድ እውነት ሳይዝ እንዲሁ በድፍረት የኢትዮጵያ ነገሥታት ከኢትዮጵያም አልፈው የደቡብ አገርን ቤተ ክርስቲያን አሳንጸው ሕዝቡን በክርስቲያን ሃይማኖት እየጠበቁ ሲያኖሩ የነበሩት ክርስቲያኖችን ነገሥታት ሐሰተኛ አምላክ ወለደኝ አለ እያሉ ከሆድ እየፈጠሩ መጻፍ ይህ ነገር እውነትና ሐሰቱ ይመርመር በተባለ ጊዜ እንደምን ያለ ጭንቅ ይወለድ ይሆን ነው የምለው። ደግሞ

# ረ እጉድ ጎዳር

እንደጽርዓውያን እንደሮማውያን ነገሥታት ልማድ ተብሎ የተጻፈው የጣዖት ማምለክ ከክርስቶስ ልደት በኋላ እንኳ እስከ ፬፻ ዓ.ም ከቤተ መንግሥቱ ጣዖታት ሳይርቁ እንደነበሩ ታሪክ ይነገረናል። እስቲ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት እገሌ የሚባል ጣዖት ያመልካል ተብሎ የተጻፈበት ፩ ሰው ቢገኝ ስለ ብዙ ይቆጠር ነበር ኢትዮጵያ በነቢያት መንፈስ ትንቢት ቅድስት ሀገርነቷ የተመሠከረና የታወቀላት ሀገር መሆኗ ቀረና እንዲያውም ከነሱ ጋራ እኩል ስተደረደር ለመስማት በቃን። የመጨረሻው ቃሌ ዔዛና እንደዚህ ያለ ጽሑፍ ያለበት ጽሑፍ አስጽፎ የተገኘ እንደሆነ በራሴ እኔው ቅጣት እንደፈረድኩባት ምስክሬ ይህ ጽሑፌ ይሁን። ግን የሮማ ልዑካን በረቂቅ ተንኮል የሰው አባት እንዲሁ ደርሰው እየሰደቡ እውነት እያስመሰሉ የማታለያ ጽሑፍ በ፻፫ኛ ገጽ ተጽፎ የሚገኘው ሲመረመር በጭራሽ ከባድ መቀጫ እንደሚአመጣ እንዲአውም ይህ የአባ ጋስፓሪን ያታላይነት ጽሑፍ በኢትዮጵያ ን ነ መንግሥት ምክር ቤት ገብቶ የሚታይ ነው።

፩ኛ የኢትዮጵያን ፊደል ጥንታዊውን ግዕዝ የሌላ አገር ያውም የኢትዮጵያ ግዛት ለነበረው ለማዛወር ጥንታዊውን የኢትዮጵያ ፊደል ከቀኝ ወደ ግራ እያዛወሩ ጽፎ ከሐውልት የተገኘ አስመስሎ በጅ ጽፎ ማቅረብ በጭራሽ ይህ ብቻ ነገሩ ሩቅ ከፍ ያለ ነው።

፪ኛ ክርስቲያኑን ንጉሥ አረመኔ እያሉ መስደብ ጣዖቱን ወለደኝ አለ እያሉ መጻፍ ጽሑፉንም እውነት ለማስመሰል ከኮፒ ኮፒ አስተላለፍን የማለት ዘንድ ምልክት መስጠት ኮፒ የትክለኛነት ምልክት ነበር በነሱ ዘንድ ግን የለም የዓለም

አንባቢዎች የሚመለከቱት አስቀድሞ በታሪክ ጸሐፊ ላይ የነበረውን ሕግ ግን የሮማ ልዑካን ሥራ ልዩ የመምህር የመነኮስ ልብስ ለብሰው የሚሠሩት የወታደር መግቢያ ነው። ወንጌልን ጨብጠው መንፈሳውያን ነን እያሉ ኢትዮጵያን እንደሚያታልሉ ደግሞ የዓለምን ሊቃውንት የኢትዮጵያን ታሪክ ጻፍን እያሉ ሐሰቱን በዓለም ዘርተውት ይገኛል። ይኸውና ይታያል ያለ ትንሽ ፍርሃት ክርስቲያኑን ንጉሥ አረመኔ እያሉ የጻፉት የስድብ ታሪክ። "በ፻፷ኛ ገጽ ባ፭ኛው መሥመር ትልቁ ንጉሥ ዔዛና በአረመኔነቱ ሳለ ሲአመልክባቸው የነበሩት እነዚህ የሐሰት አማልክቶችን ዐስተር የሰማይ አምላክ ምድር የምድር አምላክ መሐረም የጦርነት አምላክ ብሎ ይጠራቸው። የዔዛና ጽሑፍ በሌላ መሥመር እንደምናገኘው ብሔር የተባለ ሌላ ሐሰተኛ አምላክ ነበረው ይህም ሐሰተኛ አምላክ የባሕር አምላክ ብሎ ይጠራው ነበር በዚሁም መሠረት በባሕር ብሔር የተባለው የሀገር ስም በግዕዝ ይጠራበት ዝምር ፭ኛ ዔዛና ሲአመልክባቸው የነበሩት ዐስተር ማንቴስ የተባለው ሁሉ ማስረጃው ከምን ይገኛል"። ይህ ፻፪ና በ፻፷ኛ ገጽ በግዕዝ ጥንታዊ ፊደል ከቀኝ ወደ ግራ እየሆነ ተጽፎ ከሐውልት የተገኘ እንዲመስል በፎቶፍራፍ ተነሥቶ የፎቶግራፉ ሥዕል በክልሼ ተሠርቶ በመጽሐፉ ውስጥ እንደ ጥንታዊ ሆኖ ከክልሼ የተገለበጠ ትክክለኛ መስሎ የሚገኘው እነሱ ፈጥረው የጻፉት ነው። ግን ይህ እነሱ ባታላይነት የጻፉትን ግን ምክር ቤቱ ገና ይመረምረዋል። ፪ኛ መሐርምን የጦርነት ብሎ የጠራው ተብሎ የተጻፈው በጭራሽ በኢትዮጵያ መንግሥት መዝገብ እንደዚህ ያለ የጽሑፍ ዘር የለም። ይህ እንደዚህ ያለው በነገሥታቱ ቁጥር አዲስ ጣዖት

# ሩ ሰኑይ ኀዳር

እየተፈጠረ ሲሰገድበት ሲኖር በዚህ ምክንያት ጴጥሮስና ጳውሎስ እስከ መሞት የደረሱበትን እነሱም ከሞቱ በኋላ ይህ የጣዖት መስገድና መገበር እስከ ብዙ ዘመኖች የቆዩበትን ቦታ ፈልጎ ከዚያ ማግኘት ይቻላል እንጅ በኢትዮጵያስ ከነዚህ አታላዮች ቀጣፊዎች ከጻፉት በስተቀር እንደዚህ ያል ሥራ የለም።

፫ኛ የዔዛና ጽሑፍ በሌላ መስመር እንዳገኘነው ብሔር የተባለው ሌላ ሐሰተኛ አምላክ ነበረው ተብሎ የተጻፈው በሕግ የተጻፈ ነው ለማለት የሚቻልበት ሥነ ሥርዓት አለው ይሆንን ሰው ሆኖ ፩ድ ነገር ሲጽፍ በዚያው መረጃውን አደራጅቶ ላንባቢውም እንዲመቸው ማድረግ የሚገባ አልነበረም ጽሑፉን ከመዠመር በፊት ማስረጃውን አደራጅቶ ነበር ሕጉ ፬ኛ ዐስተር ስለተባለው የሰማይ ጣዖት ይህ ዐስተር የተባለው ጣዖት ጥንታውያን አረማውያን የጣዖታቸውን ስም ዐስተር በለው ይጠሩት ነበር የሚል ጽሑፍ ይገኛል በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ይህን ጽሑፍ ምን አገባው ይባላል። ኢትዮጵያ የአሕዛብ አገር አትባልም የአረመኔም አገር አትባልም አረመኔ ተብሎ መጠራት የሚገባው ሕገ እግዚአብሔርን የማያውቅ በጣዖት አምልኮ የሚኖር ለጣዖት ሲሰግድና ሲአጨበጭብ የኖረ ከልደተ ክርስቶስ በኋላም ጣዖቴን አለቅም ብሎ ሐዋርያትን ሥቃይ ያስቀበለና የገደለ ነው እንጅ ሕገ እግዚአብሔርን የተጻፈባቸውን መጻሕፍተ ብሉያት ተቀብሎ በሕግ ጠብቆ ጠንቅቆ የሚአቆይ ዘመነ ብሉይ ተሸሮ ዘመነ ሐዲስ ሲገባ እንደ አይሁድ እንኳ ኦሪትን አንለቅም በማለት ትንሽ ክርክር ሳይሆን ከሐዋርያትና ከ፸ዓ አርድዕት ያ፩ድ ሰው ደም ያልፈሰሰባት አገር ያረማውያን ታሪክ ሊተረከባት አይቻልም። የሮማ ልዑካን አፋቸውንና እጃቸውን አላረሙም። የሮማ ልዑካን ፩ኛ በ፻፫ኛ ገጽ ፪ኛ በ፻፲ኛ ገጽ ፫ኛ በ፻፹፯ኛ ገጽ በጥንታዊው ፊደል ቅርጽ ከቀኝ ወደ ግራ እየዞረ በጅ ተጽፎ ፎቶ ግራፍ ከተነሳ በኋላ እንደገና ከልሼ ተነሥቶ የታተመውን ከሐውልቱ ላይ ፎቶግራፍ አሥለው ፎቶግራፉን በክልሼ አንስተው ያተሙት አስመስለው የሠሩትን የማታለያ ጽሑፍ ገለበጥነው እያሉ በአዲሱ ፊደል ቅርጽ በግዕዝና ባማርኛ ተጽፎ የሚገኘው እውነተኛ ጽሑፍ አለመሆኑን ለኢትዮጵያ ወጣቶች አስጠነቅቃለሁ። የሮማ ልዑካን ከላይ በተጻፉ ገጾች የተጻፉትን ከቀኝ ወደ ግራ እያዞሩ ጽፈው የሚአሳዩ ፩ኛ ግዕዝ ከዓረብ የመጣ እንዲመስል። ፪ኛ የግዕዝ ከዓረብ አገር መምጣት የተረገጠ ሲሆን ዓረብ አገር ኢትዮጵያን ለመግዛቱ ማረጋገጫ እንዲሆን ዓረብ ኢትዮጵያን መግዛቱ የተረገጠ ሲሆን ኢትዮጵያ የአረብ ቅኝ

መሆኗ የተረገጠ እንዲሆን የተፈጠረ ሆነ ተብሎ የተሰናዳ ፖለቲክ መሆኑን መገንዘብ ነው። ፫ኛ እነሱ በፈቃዳቸው እየፈጠሩት በጃቸው ስፈው ፎቶግራፍ አንስተው ፎቶ ግራፍ አሥለው ባሳተሙት ውስጥ ያረመኔዎችን አማልክቶች እያገቡ መጻፋቸውን የአረቦችን ምልክት በር መግቢያ ማሰናዳታቸው ነው እንጅ እውነት ከኢትዮጵያ ነገሥታት የታሪክ ምንጭ የተገኘ አለመሆኑን ለኢትዮጵያ ልጆች አስጠነቅቃለሁ። ፬ኛ ይህን አሁን ካባ ጋስፓሪን ተጽፎ የወጣውን ረቂቅ ፖለቲክ መጽሐፍ ፍጻሜው ዛሬ ቢሆን የተወጠነበትን ጊዜ ከሥር ዠምራችሁ ስታነቡ ታገኙታላችሁ።

## ሪ ሠሉስ ኅዳር

የኢትዮጵያን ጥንታዊ ፊደሎች እየተሻሻሉ የመጡበትን ለመረዳት የፈለጋችሁ እንደሆነ ፩ኛ ባ፹፬ኛ ገጽ ፪ኛ በ፻፲፩ኛ ገጽ ፫ኛ በ፻፲፯ኛ ገጽ የተጻፉትን ልብ አድርጋችሁ ስትመለከቱ ከቀኝ ወደ ግራ ያሉትንም ያነኑ የስብከታቸውን ልክ ለማግኘት ትችላላችሁ። በ፹፯ኛው ገጽ ላይ የሚገኘው አስፈላጊ ስለሆነው አጥብቃችሁ መርምሩ አሁን በዝርዝር የምንመለከተው ፹፬ኛ ገጽ ስለሚገኘው ሐውልት “በ፹፫ኛ ገጽ ላይ የሚገኘውን ሐተታ ምርመራ ፩ኛ ይህ ሥዕል በኢትዮጵያ የሚገኙትን ሁለት ቅርጾች ያሳያል።

ከላይ ወገን የሰው ራስ ያለው አንበሳ በግዕዝ ሶበድዓት የሚባል ይታያል ይላል”። በሐውልቱ ላይ አንበሳ ማድረግን ከነውር ለመቁጠር አሳብ ያሳያሉ ዛሬ በሰንደቅ ዓላማችን ላይ የሚታየው አንበሳ ሲያያዝ የመጣ ታሪክ ረዥም ጊዜ ያለው መሆኑን የሚገልጽ ዋና የታሪክ ዘውድ ስለሆነ በረቂቅ ፖለቲክ ለማዋረድ ለሥዕሉ አመል ያበጁለታል። ምንም ቢባል አንበሳ መሆኑ አልተካደም። ይህም የአንበሳ ቅርጽ በድንጋይ የኢትዮጵያ ነገሥታት ሲአደርጉት የቆየ ለመሆኑ በአክሡም ምዕራብ በሚገኘው ጋራ ጥግ አንበሳ ውድም ያስቀረጸው የአንበሳ ሥዕል ይገኛል። ይህ በ፹፬ኛው ገጽ የሚገኘው ሐውልት በቆመ ጊዜ ሮማ ገና አልተመሠረተችም በዚህ ምክንያት የቅናት ወሬ ይወራል።

“፪ኛ ይህ ቅርጽ ግብጽ ላይ በፒራሚድ አጠገብ ከሚገኘው ከእስፊንክስ የተወሰደ ግልባጭ ይመስላል ይላል” ምቾም የሮማ ልዑካን በኢትዮጵያ የሚገኘውን የክብር ምልክት ነገር ሁሉ ሌላ ጌታ እንደፈለጉት መገኘታቸውን በዚህ ዓምድ ብቻ ለመረዳት እንችላለን ስለዚህ ይህን ሐውልት ግብጽ በፒራሚድ አጠገብ ከሚገኘው የተወሰደ ይመስላል አሉት ይህ ፩። “፫ኛ ያለጥርጥር ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሳባውያን ጣዖት ነው።” ይኸውና እንዲያውም ጥርጥር የሌለበት የታመነ ነገር ሲያመጡ ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ሳባውያን ጣዖት ነው ተብሎ አረፈ። ሳባውያን መምጣታቸው ሐሰት መሆኑን በሰፊው ከላይ ተጽፎ ይገኛል ይህም ፪ኛ “፬ኛ ከግርጌውም ፩ድ የአረመኔዎች መሠዊያ ይታያል ይላል። ከላይ እንዳመለከትኩት በማነኛውም ዓይነት አስተያየት ኢትዮጵያን ለማዋረድ ብቻ መሆኑን ለመግለጽ ከሐውልቱ ግርጌ ያረመኔዎች መሠዊያ ይታያል ይላል ይህም ፫ኛ “፭ኛ መሥዋዕቱ በዚህ መሠዊያ ላይ ይሠዋ ኑርዋል። አስቀድሞ በኢትዮጵያ ላይ ለጣዖት የሠዋ አለ ተብሎ ፩ድ ጽሑፍ የማይገኝባትን በቅዱስ መጽሐፍ ላይ በመልካም እንጅ በክፉ ተጠርታ የማታውቂቱን ቅድስቲቱን ሀገር የሮማ ልዑካን መልካም ስሟን ሲአረክሱ ይገኛሉ ይህም ፬ኛ።

፯ኛ ደሙ በገንዳው ውስጥ ተጠራቅሞ በሚታየው ቀዳዳ ይፈስ ነበር። ደሙ መጠራቀሙን ማስታወስ አይከፋም። አጠራቃሚውም ገንዳ መልካም ግን ደሙን የሚአፈሰው ቀዳዳው ዋሾው የደሙ ምንገድ መሆኑ ነው ፭ኛ። ፯ኛ በስተፊትም የሳባውያን ጽፈት ይታያል ይላል።”

የሳባውያን ጽፈት የተባለው ያረቦችን ጽሑፍ ማለት ነው ከላይ እንዳመለከትኩት ማነኛውም የተገኘ ነገር ሁሉ የሌላ ነው የሚሆነው ፯ኛ “፰ኛ በዚህ በጣዖቱ መሠዊያ ላይ የተቀረጸው ጽሑፍ በሳባዊ ቋንቋ ስለሆነ ፊደሉ ምንም ግዕዝ ቢመስል ትርጉሙና ቋንቋው ዓረብን የሚከተል ሳባዊ ቋንቋ ነው” በጣዖቱ መሠዊያ ላይ የተቀረጸው

## ፊ ረቡዕ ኅዳር

ጽሑፍ በሳባዊ ቋንቋ ስለሆነ አለና ችግር ሲለው ጊዜ መልሶ ፊደሉ ምንም ግዕዝ ቢመስል ትርጉሙና ቋንቋው ዓረብን የሚከተል ሳባዊ ቋንቋ ነው አለ። ግዕዝን እናያምንም ቸገረ ዓረብ ነው እንዳይባልም ግዕዙ ፊደል አስቸገረ ሆኖም ነገሩ ባረቡ ፀና ይህም ፯ "፱ነኛ የዚህንም በሥዕል ላይ ያለውን የሳባዊ ቋንቋ ቅርጽ መዠመሪያ እንዳለ ገልብጠን ካሳየን በኋላ ቀጥለን ለሕዝቡ እንደሚታወቅ አድርገን ቅርጹን ቃል በቃል እንተረጉመዋለን"።

የዚህንም በሥዕል ላይ የሚገኘውን የሳባዊ ቋንቋ ቅርጽ መዠመሪያ እንዳለ ገልብጠን ካሳየን በኋላ ቀጥለን ለሕዝቡ እንደሚታወቀው አድርገን ቀርፀን ቃል በቃል እንተረጉመዋለን። በሮማ ልዑካን ዘንድ

በሐውልቱ ላይ ተቀርጾ የሚገኘውን የፊደል መልክ ከነሱ በቀር የሚአውቀው ሌላ የለም ማለት ነው። ሕዝቡም የሚመራ በነሱ ጽሑፍ መሆኑን ተማምነውበታል በሐሰቱ ምንገድ ፰ኛ "፲ኛ ይኸውም በሥዕሉ ላይ የሚገኘው የሳባዊ ቋንቋ ቅርጽ አንባቢዎች ትርጉሙን አይተው ንባቡን እንዲያነጣጥሩ የቅርጹ ዓይነት አጻጻፉ። በሥዕሉ የሚታየውን በጥንታዊ ግዕዝ ተጽፎ የሚገኘውን ያለ ትንሽ ኃፍረት በሳብዊ ቋንቋ ቅርጽ አንባቢዎችም ተረጐምን ተባለ አስቀድሞ ፊደሉ የማን እንደሆነ መታወቅ በተገባው ነበር መቸም እነሱ በመሩት እንድንከተል በማወቅ ወደ ገደል ሲመሩን ይታያሉ የሚጠራጠርም የለም ይህም ፱ነኛ "፲፩ኛ የመዠመሪያውን መሥመር እንዳሁኑ የዓረቦች አጻጻፍ ከቀኝ ወደ ግራ የተጻፈ ነው ይላል። ፪ኛው መስመር ግን እንዳሁኑ የኢትዮጵያ አጻጻፍ ከቀኝ ወደ ግራ የተጻፈ ነው ይላል።"

አሁን እንግዴህ አስተውሎ መመልከት ነው። በሐውልቱ ላይ ያለውን ጽሑፍ የመዠመሪያው መሥመር እንዳረቦች ከቀኝ ወደ ግራ ነው ተብሎ የተጻፈው መቸም የነሱ ነገር ግብዝ መሆኑን የሚአስረዳ እንደዚህ የነገር ጫፍ ይነጥቁና ያችን ይዘው እስከ ብዙ ስሕተት ምንገድ ለሚሔዱ ነው። ይህም እንደዚህ ነው። በላይኛው መሥመር ላይ መ ስ ትጻፍ ፊቷ ከቀኝ ወደ ግራ ሆና አግኝተው በዚች ባ፩ዲቱ ፊደል መልክ መዞር ብቻ ፩ዱ መስመር ከቀኝ ወደ ግራ የተጻፈ ነው ብለው ለመጻፍ ቻሉ። ይህን ጽሑፍም የሚአነብ ሁሉ ተቀበለ። እንግዴህ የነሱ ነገር እንደዚህ ያለ ፍሬ ቢስ መሆኑን ያላየና ያላወቀ ሰው እርግጠኛ ቀዋሚ ነገር የያዙ ሳይመስለው አይቀርም። አሁን ፩ደኛዪቱን ፊደል መን ብቻ አዩ እንጅ የቀሩትን ፊደሎች መልክ አስተውለው አስተውለው ቢሆን በመ አጠገብ የሚገኙትን ፊደሎች በላይኛው መስመር የሚገኙ ፊደሎች ፲፫ት ናቸው ከ፲፫ቱ ፊደሎች ፪ ለ ፪ አ ፩ ነ ፭ት ፊደሎች አሉ እነዚህ ፭ቱ ፊደሎች እንደ ግዕዙ መሠረት ከግራ ወደ ቀኝ የሚነበቡ ሆነው የተጻፉ መሆናቸውን ያስረዳሉ ብቻ ፩ድ ፊደል መ ፊቷ እንደዚህ ዞሮ አየን በማለት ነው። የነሱ ሥራ መሠረት ያለው ከሆነ ያ፩ድ ፊደል መልክ ብቻ ነጥቆ ከሙብረር በጣም አስተውሎ ፊደሎችን ሁሉ ማስተዋል ይገባቸው ነበር። እንግዴህ ከ፩ድ መስመር ላይ እሽ እንደነሱም ቢሆን ካ፭ትና ካ፩ድ የየትኛው ምስክርነት ሊጨበጥ ይቻላል። ያውም መ የተባለው ፊደል በሌላም ቦታ ላይ ባይመለከቱት ነው እንጅ ፊቱን ወደ ቀኝም ወደ ግራም ወደ ላይም በ፫ቱ ወገኖች እንደዚህ እየሆነ ይገኛል ግን በነሱ ቤት ይህን ጥንታዊ ፊደል እየተከታተሉ

## ሬ ኃሙስ ኅዳር

የሚመረምር መኖሩን አያቁም እንጅ እውነት አውቀው ቢሆን ይህን ያህን ይሳሳታሉ አይመስለኝም። ስለ ሁለተኛውም መስመር እንደ ግዕዝ ነው ቢሉም ከመዠመሪያው በተገኘችቱ ባ፩ዲቱ ፊደል ብቻ ሁሉንም ጠቅልለው የደቡብ ዓረብ ፊደል አድርገው ተርጉመውታል ይህም ከባድ ስሕተት ስለ መቶ የሚቆጠር ነው ይህም ፲ኛ ፲፪ኛ ይኸውም የጣዖት መሠዊያ ተብሎ የተሠራው ቤተ መቅደስ አሠርቶ ለጣዖት ያበረከተው ንጉሥ ወይም ባላባት ማን እንደሆነ አይታወቅም ይላል።"

በብዙ ኪነ ጥበብ ተሠርቶ ለመጭው ትውልድ መታሰቢያ የቆመውን ሐውልት ውስጠ ምሥጢሩን ምን እንደሆነ ሳያውቁ እንዲሁ ልብ ወለድ ንግግራቸውን በሀገራቸው ላይ እንደተለመደው የጣዖት መሠዊያ እያሉ ተርጉመውታል ምሥጢሩ እንደልባቸው የሚአስረዳው ሐውልቱን ለጣዖቱ ያበረከተው ማን እንደሆነ አይታወቅም ሳላሉ አይታወቅም በማለታቸው ነው ይህም ፲፩ድ ፲፫ኛ ቤተ ጣዖቱ ተሠርቶ ለጣዖቱ የተሰጠ መሆኑን ቅርጹ ይነግረናል" የጣዖቱ ቤት ተሠርቶ ለጣዖቱ የተሰጠ መሆኑን ቅርጹ ይነግረናል የተባለው አንበሳውስ ጣዖት መሆኑ በናንተ ሀገር እንደሆነ እንጅ በኢትዮጵያ የሚገኘው የአንበሳ ሥዕል

የኢትዮጵያ አስቀድሞ በዘመነ ብሉይ በነበሩ ሊቃውንቶች በንግሥት ሳባ ወይም በቀዳማዊ ምኒልክ ብሉይ ኪዳን ከተቀበሉ በኋላ ከ፲፪ ነገደ ፳ኤል ፬ት አለቆች እንዳሏቸው እነዚህም ፬ቱ በውስጣቸው ፪ት ፪ት ነገዶች እንደገደሏቸው ይነግረናል ፩ኛ ይሁዳ ተከታዮቹ ፩ኛ ይሳኮር ፪ኛ ዛብሎን ፪ኛ ሮቤል ተከታዮቹ ፩ኛ ስምዖን ፪ኛ ጋድ ፫ኛ ኤፍሬም ተከታዮቹ ፩ኛ ምናሴ ፪ኛ ብንያም ፬ኛ ዳን ተከታዮቹ ፩ኛ አሤር ፪ኛ ንፍታሌም አራት ዘኍልቍ ፪ ፩ ወነበቦሙ እግዚአብሔር ለሙሴ ወለአሮን ወይቤሎሙ ፪ ብዕሲ በበሥርዓቱ ወበበትእምርቱ ወበበቤተ አበዊሆሙ ይትዓየኑ ደቂቀ ፳ኤል ያለውን እስከ ፴፫ ቁ የተዘረዘረን መርምረው የግዕዝ ልጆች የኢትዮጵያ ሊቃውንት ሲያየዝ በመጣው በግዕዝ እውቀታቸው መንፈሳዊ አእምሮ ፬ቱ አለቆች ምሳሌ ካ፬ቱ ፀወርተ መንበር ፩ኛ ገጸ ሰብዕን ለሮበል ፪ኛ ገጸ አንበሳ ለይሁዳ ፫ኛ ገጸ ላህም ለኤፍሬም ፬ኛ ገጸ ንሥር ለዳን መሆኑን ተመልክተው ካ፬ቱ አለቆች ትእምርቶች በ፪ኛው ቁጥር የሚገኘውን ገጸ አንበሳን መርጠው ካ፬ቱ አለቆች ከ፪ኛው ከይሁዳ በተገኘው ሀብት መንፈሳዊው ሥነ ሥርዓት አምላካዊ ትምህርት ዓላማቸውን ያንበሳ ምሳሌ አደረጉበት ይህን ምሳሌ ለመግለጽ በማነኛውም ደስ በሚአሰኝ ነገር ሁሉ የአንበሳ ሥዕል ማድረግ የኢትዮያ ልማድ ስለሆነ ፩ድ ንጉሥ በሐውልቱ ላይ የአንበሳ ሥዕል ያለበት ሐውልት በግዕዝ ጽሑፍ ታሪኩን ጨምሮ ያስቀመጠውን የሮማ ልዑካን ምን ብለው ተረጐሙት የጣዖት መሥዋዕት ማቅረቢያ አሉት

# ር ዓርብ ኅዳር

ግን እነሱ እንደዚህ ያለ ጥልቅ ምሥጢር ያለበት ፊደልና ጽሑፍ ስለማያውቁ ለማመስገን የማይቻላቸው ስለ ሆነ ዝም በማለት ፋንታ መንቀፍ በማይገባው ነቀፋ ስለ ጻፉ ማቴዎስ ፯ ፭ መዳልው ቅድመ አውጽእ ሠርዌ እምውስተ ዓይንከ ወእምዝ ትሬኢ ለአውጽአ ኃሠረ ዘውስተ ዓይነ እኁከ ፮ ኢተሀቡ ቅድሳትየ ለከበባት ወኢትደዩ ባሕረየክሙ ቀደመ አኅርው ከመ ኢይኪድዎሙ በእገሪሆሙ ወተመይጦሙ ይንጹሑክሙ እንዳለው ዕንቍ በእሪያ አፍንጫ ቢንጠለጠል በጭቃ ይለወሳልና በእግርም ይረገጣል እንደተባለው ብልሆችና ጠንቃቃዎች የሆኑ የኢትዮጵያ አባቶች ለመጭው ትውልድ ማሳሰቢያ የሚሆን አስደናቂ ሐውልት ከነጽሑፉ መታሰቢያ አስቀምጠውት ከ፫ሺ ዘመነ በላይ ዕድሜ ያለውን መታሰቢያ ሁሉም ቀረና የሰይጣናዊ የጣዖት መሥዋዕት ማቅረቢያ ብለው ተርጉመውት አረፉ ወተመይጦሙ ይነጽሑክሙ እነዚያ ባፍንጫቸው ዕንቍ የተንጠለጠለባቸው ተመልሰው አሰናክለው ይጥሏችኋል ያለውን ቃል ማስታወስ የተገባ ነው ለመደነቅ ለመከበር የተቀመጠውን መሠረታዊ ሐውልት እንደዚህ ያለ ሥያሜ ጥፋቱ ከፍ ያለ ነው (፻፲፩ ፲ኛ ዘተሐመየመ ሳባውያን ይሰግዱለት የነበረው የጣዖት ስም ነው) ። አሁን ይህን ጽሑፍ ዓምድ አሲዘውት ያየ አንባቢ እውነተኛ ጽሑፍ አገኘሁ ብሎ ይህን ሐሰት በማስተዋል ጊዜ ሲፈጅበት ውስጡን ላወቀ ሰው በጣም ያሳዝናል። ሰው የሆነ ሰው ምንም ቢሆን ይህን በሰው አገር የሰው ካልወሰድኩ ብሎ ይህን ያህል ስሙን በሐሰት ቀለም መመዝገብ የሚአስደንቅ ነው። አሁን ከላይ ዘተሐመየመ ብለው የጻፉት ከታችኛው ከግራ ወደ ቀኝ የተጻፈ ነው ብለውት የነበረውን አሁን እንደገና ከቀኝ ወደ ግራ ፊደሎችን ገልብጠው ነው ሳባውያን ይሰግዱለት የነበረው የጣዖት ስም ነው ብለው የጻፉት አፋቸው እንዳመጣው እንዲሁ የፈጠሩት ነው እንጅ እውነት ያለበት

አይደለም ፍጹም ሐሰት ነው። (፻፪ ፲፫ኛ ደግሞ ዘተሐመየመ የተባለው ሲተረጐም የአምላክ አዳነ ልጅ የሆነው አምላክ አጠና የተባለው ንጉሥ ይህን ቤተ መቅደስ አሠርቶ ዘተሐመየመ ለተባለው ጣዖት አበረከተው ይላል። ዘተሐመየመ የተባለው ጽሑፍ የአምላክ አዳነ ልጅ ተብሎ የተተረጐመ በምን ቋንቋ ነው አሁን እዚህ የተጻፉ ነገሮች አምላክ አጠና የተባለውም ዘተሐመየመ ሆነ ሐውልት ተቀባዩም እሱ ሆነ እንደዚህ እያደረጉ ፖለቲኩን እውነተኛ ታሪክ እያስመሰሉ አምድ አሲዘውት

ሲገኝ አንባቢዎቹ በዚህ በሐሰት ምንገድ ሲሄዱ የሚደርሱበትን ማስተዋል ነው። ፻፫ኛ ይህ ፻፫ኛ የተባለው ከ፵፫ኛና ከ፵፬ኛ ገጽ ላይ የተመረመረ ነው ማለት ስለ ጥንታዊው ፊደል ቅርጽ እርግጠኛውን ግዕዝ ለውጠው ይህን ያህል ስሙን ያቆሸሹት በሚገባ የቆመውን መታሰቢያ ነው። ደግሞ ፪ኛ "በ፻፩ኛ ገጽ ስለተጻፈው ሐውልት ይህ በሥዕል የሚታየው ቅርጽ እርግጠኛው በጅ ያልተከለሰ መሆኑ የታመነ ነው። ልክ በዔዛና በአልዓሜዳ ልጅ ባጼ ካሌብ አባት የተቀረጸ መሆኑ እርግጥ ነው። ግን የሮማ ልዑካን ልዩ ነገር እየፈጠሩ ጽፈውት የሚገኝ ከቅርጹ (ግርጌ ይህ ሥዕል የንጉሥ ዔዛናን ትልቅ ጽሕፈት መዠመሪያውን ያሳያል) ፩ኛ የሮማ ልዑካን መዠመሪያ ሲነሱ የኢትዮጵያ መሠረት ለዋውጠው አዲስ ምንም ታሪክ ያለነበረባት

# ሮ ቀዳም ኅዳር

ለማስመለስ ስለሆነ ምንም እውነተኛ ነገር በማይሰሳት በድንጋይ ብራና ተጽፎ በኢገኙ እንደምን ብለው ነገር ሳይፈጥሩለት ይቀራል ማለት ከንቱ ነው። አሁን የሚተኩበት ቢአጡ የጽሕፈት መዠመሪያውን ያሳያል ብለውት አረፉ። እንግዴህ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ተጽፎ አያውቅም ማለታቸውን መገንዘብ ነው። (፪ኛ ይህ ጽሑፍ ድምጽ በሚሰጠው በኢትዮጵያ ቋንቋ ተጽፏል ፪ኛ ደግሞ መልሰው በኢትዮጵያ ቋንቋ ድምጽ በሚሰተው ተጽፎአል ይህ ቃል ደግሞ ይለወጣል። ቃል መለዋወጥም ደህና ነገር ሆኖ ተይዟል "፫ኛ ፊደል የተገኘበት መዠመሪያ ጊዜ ይህ ነው" ይኸውና ይለውጣል ያልኩት ቃል ሳንርቅ በኢትዮጵያዊው ቋንቋ ተጽፍዋል ተባለና ደግሞ ወደዚያው ፊደል የተገኘበት መዠመሪያ ይህ ጊዜ ነው ተብሎ ተጻፈ እንግዴህ ይህንን ነገር አንባቢ ምን ብሎ ሊተረጉመው ይችላል ጥንታዊው በጅ ያልተገበጠው ጽሑፍ ላይ የጣዖት ነገር ለመጻፍ አልቻለም። በኢትዮጵያ ላይ አምልኮ ጣዖት አለመኖሩን የሚአስረዱ በሐውልቱ ላይ የሚገኙ ጽሑፎች ናቸው ደግሞ "በ፻፬ ገጽ ባ፳ኛው መስመር ትልቁ ንጉሥ ዔዛና ወደ ኢትዮጵያ ምዕራብ አገር ያሉትን አገሮች አቅንቶ ከተመለሰ በኋላ ለኢትዮጵያ ሥልጣኔና የእምነት መሠረት የሚሆኑትን ፪ት ነገሮች መሥርቷል። ከነዚህም ከ፪ት ትልልቆች ነገሮች ፩ኛ ደክም የነበረውን ግዕዝ የተባለውን ቋንቋ እንደ ገና አድሶ በሐውልቱ ላይ ጽፎ አግኝተነዋል"። ከላይ ፊደል የተዠመረበት ይህ ነው ተብሎ ተጽፎ ነበር አሁን ደግሞ ደክሞ የነበረውን ግዕዝ እንደገና አድሶ በሐውልቱ ላይ አግኝተነዋል። አሉ። (በኢትዮጵያ ታውቀው ተለምደው የነበሩትም ሳባዊና ጽርዓዊ የተባሉ ፪ቱ ቋንቋዎች እንዲደከሙና እንዲቀሩ አደረገ። የታደሰው ጥንታዊ ግዕዝ ግን በምናሳየው ሥዕል ላይ ተጽፎ እንደሚገኘው ከግዕዝ እስከ ሳብዕ ያሉ ሰባታ ፊደሎች ሙሉ ሆነው እንዲነገሩ በየደንባቸውና በየአስካካቸው እንዲነበቡ አድርጎ ጨምሮ አድሷቸዋል ይላል።) አሁን ይህ ሁሉ ሐተታ የመጣበት ዔዛና በአብርሃና በአጽብሐ ቦታ የሆነበት ፊደልም እንደገና ተዠምረ የተባለበት ፱ቱ ቅዱሳን በአልዓሜዳ ዘመን መጡ ስለ ተባለ ፱ቱ ቅዱሳን የኢትዮጵያን ፊደል እነሱ አደራጅተው መጻሕፍት መጻፍ ተጀመረ ለማለት ነው አስቀድሞም በኢትዮጵያ ስለ ቤተ ክህነት ትምህርት መሥርተው ያቋቋሙ እነሱ ናቸው።

አሁንም እኛ የኢትዮጵያ አስተማሪዎች ሰባኪዎች ሆነን እያስተማርን ቤተ ክርስቲያን አቋቁመን በኢትዮጵያ ላይ የሮማን ቤተ ክህነት ሥልጣን ወደ ኢትዮጵያ እናገባለን ማለት ዋና ምኞታቸው ስለሆነ። የጣዖት ምድር ከነበረችቱ ከሮማ መጥተው ኢትዮጵያን የጣዖት አገር ነበረች እያሉ ያለ ኀፍረት ሲጹ ይገኛሉ። እነሱ ያስባሉ ኸረ የዚች መሬት

ባላባቶች በዚች መሬት የተነሳ ስንቱ አልቀዋል ስንት ደም ፈሷል። እንግዴህ በነሱ ልብ እነሱ ይህን ስብከት ከዠመሩ ወዲህ በነሱ ነገር አመላላሽነት በኢትዮጵያ ያለቀው ሕዝብ ከ፪ት ሚሊዮን የሚአንስ አይደለም። አሁን እነሱ የሕዝቡን ደም እንደ መሬት መቅለዣ

ወይም እንደ ውኃ ገብ መሬት እንዲያጠጣ ማለት ነው። ባይገነዘቡት ነው እንጅ ቢገነዘቡትስ እንባቆም የጻፈውን ትንቢት ፪ ፲፪ አሌ ሎ ለዘየሐንጽ አኅጉረ በደም ወያጸንዕ አኅጉረ በዓመጻ ፲፫ ኢኮነኬ ዝንቱ እምኀበ እግዚአብሔር ዘኵሎ ይመልክ ወኃልቁ ብዙኃን አሕዛብ በእሳት ወተመንደቡ ብዙኃን ሕዝብ ይህን መመልከት ወንጌላዊ ነኝ ለሚል ዋና ተግባሩ ነበር። በዚች ምድር ስለ ፈሰሰ ደም

## ሰ እጐድ ኅዳር

በሽ፲፻፹፯ ዓ.ም በፈረ ቁ ፳፫ የራስ አሉላ ወታደሮች ተዳዓሊ ላይ ከመንገድ ስለፈጅዋቸው ኢጣልያኖች በሮማ የነበረው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ሮባላቴ ግን የተደዓሊ ዕዳቸውን ለመክፈል የሚሆን የጦር መሳሪያ ሲያሰናዱ አስቀድመው ወደ ኮንት አንቶኖሊ እንዲህ ብሎ ጻፈ የኢጣልያ ልጆች ክቡር ደማቸው በኢትዮጵያ ምድር ከፈሰሰች አሳባችን ሁል ጊዜ የኢትዮጵያን በጃችን ለመያዝ ነውና የበለጠው ነገር ማኅበራችን በኢትዮጵያ ገብታ የፖለቲክ ሥራ መሥራት ነው ይህች መልእክት የምታመጣልን ፍሬ መጀመሪያው ንጉሥ ምኒልክ ከነመሳሪያዎቹ ሁሉ እኛን ተከትሎ ካጼ ዮሐንስ መጣላቱ ነው። ፪ኛ የበለጠ ነገር እርስዎ በዚያው ሥፍራ ሆነው በኢትዮጵያ የተደረገና የሚደረገውን ነገር ሁሉ ለመንግሥታችን ማስታወቅ ነው። አሁን በክቡርነትዎ በጊዜው የተሠሩትን ነገሮች ሁሉ ገልጠው በቶሎ እንዲጽፉልኝ እለምንዎታለሁ። ይህን ለመጻፍ ያሳሰበን ከላይ ስለተጻፈው ስለ ሮባላንቱ ንግግር ስለ ኢጣልያ ልጆች ደም መፍሰስ። የኢጣልያ ልጆች ደም ከፈሰሰ ኢትዮጵያ ለኢጣልያ ሆነች ማለቱና የኛ የበለጠው ነገራችን ማኅበራችን በኢትዮጵያ ገብታ የፖለቲካ ሥራ መሥራት ነው ብሎ የጻፈውን በማስታወስ ነው እንጅ ደብዳቤ በሙሉ ከላይ ተጽፎ ይገኛል። አሁንም የማን ደም የማንን አገር ይወርሳል ማንስ የወንድሙን ደም ይረሳል። "በ፻፲፫ኛ ገጽ ባ፻፲፬ኛው የግዕዝ ቋንቋ ስለ መሠልጠንና መድከም ከደከመም በኋላ ስለመታደስ ግዕዝ የተባለው የኢትዮጵያ መሠረታዊ ቋንቋ አግዓዚያን የተባሉት ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሲመሠረቱ አብሮ ተመሠረተ በመላው ዓለም ላይም ታውቆና ተለምዶ ሲኖር የነገሥታት ሕግና ደንብ ማስታወቂያ ሆኖ ያገር ነበር። ይኸውና የሮማ ልዑካን ስብከት እንደ ሸማኔ መወርወሪያ መስል ፩ድ ጊዜ ወደ ቀኝ ፩ድ ጊዜ ወደ ግራ እየተዘዋወረ። ከላይ አርእስቱን የግዕዝ ቋንቋ ስለ መሰልጠንና መድከም ተባለና ተዠመረ ደግሞ ግዕዝ የተባለው መሠረታዊ ቋንቋ አግዓዝያን የተባሉት ሳባውያን ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ሲመሠረቱ አብሮ የተመሠረተ ነው ተባለ። እንግዴህ ጥንታዊ ግዕዝ የተባለው ከሳባውያን የመጣው መሆኑ ነው ከሳባውያን ጋር የመጣው ግዕዝ መሠረት ሲሆን ከሳባውያን መምጣት ከተባለው በፊት በኢትዮጵያ ቋንቋ አልነበረም ማለት ነው። ግን ከላይ የቢለንና ያገው ቋንቋ የኩሳ ቋንቋ እሱ ነው ተብሏል እዚህ ላይ ግን መለየት የለም እንዲሁ ማደባለቅ ማመሳቀል ነው" "፪ኛ በመካከሉ ግን ሳባዊና ጽርዓዊ የተባሉ ፪ት ቋንቋዎች እንደሰላጤ ሆነው ገብተው የቤተ መንግሥት መነጋገሪያና የሥልጣኔ መምሪያ ሆነው ስለተገኙ ይህ ግዕዝ ጥቂት ደከመ ብሎ ነበር ያሉት።" እንግዲህ አሁን ከላይ የተጻፉ ቋንቋዎች ፫ት መሆናቸውን ማስተዋል ይገባል። እነዚህ ፫ቱ ፩ኛ ግዕዝ ፪ኛ የሳባውያን ቋንቋ ፫ኛ የጽርዓውያን እነዚህ ቋንቋዎች ከብዙ ቦታዎች ላይ ሲጠሩ ይገኛሉ በጽሑፍ ሆነው በፊደል ቅርጽ መደብ ይዘው የሚገኙ ፪ት ዓይነት ፊደሎች ናቸው እነዚህም ፩ኛው ግዕዝ ፪ኛው በጽርዕ ፊደል የተጻፈው ነው ፫ኛ የሳባውያን ፊደል የሚባለውን ተለይቶ ይህ ነው ተብሎ አይገኝም። ጥንታዊውን ግዕዝ የሳባ ፊደል እንዳንለው የግዕዝን ቀዳሚነት የሳባውያንን ቋንቋ በኋላ መግባት እያረጋገጡ ጽፈውት ይገኛል። ፩ኛ ሳባዊና ጽርዓዊ የተባሉት ፪ት ቋንቋዎች ማለት።

# ሱ ሰኑይ ኅዳር

፪ኛ ይህ ግዕዝ ጥቂት ደከም ብሎ ነበር። ማለት እንግዴህ ሳባዊ ጽራዊ ግዕዝ ፫ኛ አይባሉም ይሆንን። ደግሞ ለዚሁ ማጠናከሪያ "በ፻፫ኛ ገጽ ፲፰ኛው መሥመር መሠረታዊ። ግዕዝ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቋንቋ መሆኑ የታወቀ ነው ይላል። " ሁሉም የሮማ ልዑካን ጽሑፍ ነው። ይህን መከረኛ ግዕዝ ካረብ አገር መጣ ይሉታል። ደግሞ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ቋንቋ ይሉታል እንግዴህ የሚጨበጠው የትኛው ነው እያልኩ የምክር ጥያቄዬን ለአንባቢዎቹ አቀርባለሁ። ይህ ግዕዝ ከተወለደ ዝምሮ እስከ ትልቁ ዔዛና ድረስ አቅመ አዳም እንዳልደረሰ ሕጻን አድርገን እንቆጥረዋለን ይላል"። ዓላማና ፊደል ፩ድ ነበር ስለ ኢትዮጵያ ዓላማ ትዕምርት ሆኖ የቆመውን በሐውልት ላይ ተጽፎ ቢገኝ ወቦ ሽማኔ ጣዖት ተባለ ፪ኛ ግዕዝ የተባለውን ፊደል ግዕዝ ማለት ምን እንደሆነ የማያውቁትን እንዲሁ ዓይናቸውን ጨፍነው። ግዕዝ ከተወለደ ዝምሮ እስከ ንጉሥ ዔዛና ድረስ አቅመ አዳም እንዳልደረሰ ሕጻን አድርገን እንቆጥረዋልን ብለው ጻፉ። ይህ ሁሉ የተገባ ሥራ ነው ለማለት ይቻላል ይሆንን። ይኸውም ምሳሌ እነዚህ ፳፮ቱ የግዕዝ ፊደሎች ባ፩ኛ ደረቅ ግዕዛቸው ሲጻፍባቸው ይኖር ነበር ይላሉ"። በሰው አገር የሄደ ሰው ማነኛውንም ነገር ለማወቅ ልክ አገሬውን መምሰል የተገባ ነበር። እነዚህ ፳፮ቱ ፊደላት ስንት ጠባይና ትርጓሜ እንዳለባቸው ምኑን አወቃችሁትና እንደዚህ ያለን ሕገ ወጥ ጽሑፍ ለመጻፍ ደፈራችሁ። ለመሆኑ የኢትዮጵያን ፊደሎች የምሥጢር ሥነ ሥርዓት ለማወቅ የሚቻላችሁ ይሆንን። በናንተ ልብ በግዕዝ ፊደል ተጽፈው የሚገኙት የፊደል ደረጃዎች ሳይታወቁ ቀርተው ማለት ነው። እሽ እንደ እናንተ ሃሳብ ልከተል የግዕዙ ፊደሎችስ በዔዛና ጊዜ በፍሬ ምናጦስ በ፱ቱ ቅዱሳን መሪነት የ፳፮ቱ ፊደላት ከካዕብ እስከ ሳብዕ ፮ ደረጃዎች ፯ት አደረጉና የ፻፹፪ት ለማድረግ ቻሉና ኢትዮጵያን አዲሶቹ መምህራን አዲስ ፊደል አምጥተው ኢትዮጵያን አሠለጠኑ ብላችሁ የምትሰብኩት ትክክለኛ ስብከታችሁ ገብቶናል። በጽርዓውያንም ቢሆን ወይም በሱርስት ወይም በላቲን ወይም በእብራዊ የፊደል ደረጃዎች ከ፫ት የበለጠ አይደሉም። ስለዚህ ይህን የፊደል ፯ት ደረጃ ከምን እንደመጣ ለመረዳት ሕሊናዬ ስለ አስገደደኝ ይህን የ፯ቱን ደረጃዎች መሠረት ለመጠየቅ የበረታሁበት ማንኛውም ጸሐፊ ፩ድ ነገር ሲጽፍ ወይም ሲናገር ምሳሌና ሞክሼ እየሰጠ ስለሆነ ጌታችን እንኳ የነቢያትን ቃል መሠረት እያደረገ በወንጌል ፩ኛ ማቴዎስ ፲፫ ፲፬ ወይትፈጸም ላዕሌሆሙ ትንቢተ ኢሳይያስ ነቢይ ዘይቤ ሰሚዓ ትሰምዑ ወኢትሌብዉ ወነጽሮ ትኔጽሩ ወኢትሬዕዩ። ፲፭ እስመ ገዝፈ ልቡ ለዝንቱ ሕዝብ ፪ኛ ፴፭ ከመ ይትፈጸም ዘተብህለ በነቢይ እንዘ ይብል እከሥት በምሳሌ አፉየ ወእነግር ዘኅቡዕ ዘእምትካት።

፫ኛ ፳፬ ወአመ ርኢክሙ ኃሣሮ ለሙስና ዘተብህለ በዳንኤል ነቢይ እንዘ ይቀውም ውስተ መካን ቅዱስ ዘያነብብ ብለቡ። ውስተ መካን ቅዱስ እንደዚህ እየለየ መካን ብሎ ቅዱስን አመጣ የተቀደሰ ማለት ንጹሕ ደም ያልፈሰሰበት ማለት ስለ ሆነ እዚህ ላይ የሮማ ልዑካን ውስተ መካን ቅዱስ ባለው ለመስማማት አይቻላቸውም ይኸውና ሁሉ ነገር መሠረት ሳይለቅ የሚሄድ ስለሌለ ማስረጃዎችን አቀረብኩ ይሁን ፩ድ ተብሎ ይቆይ ደግሞ ሲጻፍና ሲነበብ ከላይ በቈጠርናቸው ፊደሎች ሁሉ ከቀኝ ወደ ግራ እጅ ናቸው በምን

# ሲ ሠሉስ ኅዳር

ምክንያት አዞሩት ይህንስ ከምን አገኙት ፫ኛ ከላይ የቆጠርናቸው ፊደሎች ሁሉ በአ ይዝምራሉ የኢትዮጵያን ከምን መሠረት አግኝተው በሀ ዝምረው በፐ ጨረሱት። ፬ኛ የተጻፉ ፊደሎች ቍጥራቸው ፳፪ ነው። በግዕዙ ፊደሎች የጨመሩ ከምን አምጥተው ነው። ለዚህ ሁሉ ዋና ማስረጃ ማቅረብ እንዳለ መጠየቅን አውቃችሁት ቢሆን ይህን ሁሉ የሐሰት ክምር ሰብስባችሁ ያልታረመ ንግግራችሁን በጽሑፍ ላይ ለማስፈር ባላሰባችሁም ነበር።

“በ፻፫ኛ ገጽ ከታች መጨረሻ ካለው መስመር ይህ ግዕዝ እንዲህ ሳይጎለምስና አቅም አዳም ሳያደርስ ግን የሳባዊን ልብስ ፊደሎች ተጎናጽፎ በሳባዊ ቋንቋ ሞግዚትነት ተሸፍኖ ይኖር ነበር። ይላል) አሳባቸውን ሁሉ ስንመለከተው የልብ ወለድ ፖለቲክ ሥራ ነው። እንጅ እንደ ታሪክ ጸሐፊዎች ሥነ ሥርዓት የሆነ አይደለም። ይህ ሁሉ ትብትብ በኢትዮጵያ እስከ አባ ሰላማና ፱ቱ ቅዱሳን ስንኳን መጽሐፍ ፊደሎች አልነበሩም ማለት ነው። ይህን ጽሑፍ አስተውሎ የተመለከተ ሁሉ ካልሳቀ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ከመሆኗ አትለወጥም። አሁን በቀስታ ለሮማ ልዑካን ፩ድ ጥያቄ አቀርባለሁ። ይህም እንደዚህ ነው የጽርዓውያንን መጻሕፍቶች ታውቋቸዋላቸውን መጻሕፍተ ብሉያት ፹፫ት ብቻ መሆናቸውን የዓለም ቤተ ክርስቲያንም ጽሑፍ ይመሰክራል። ይህም ቃል። እናንተም አትክዱም። ይህንን የምትገነዘቡ ስትሆኑ ደግሞ በኢትዮጵያ የሚገኙትን መጻሕፍተ ብሉያት ታውቋቸዋላችሁ ፺፪ት እንደሆኑ ከነዚህ የተረፉትን መጻሕፍቶች ፩ኛ መጽሐፈ ሄኖክ ከማየ አይኅ በፊት በሽ፬፻፹፯ ዓ.ም በኢትዮጵያ መጻሕፍት ከማየ አይኅ በፊት ፩ሽ፫፻ ፺፬ ዓ.ም ማለት ነው በዚያ ጊዜ ነው መጽሐፈ ሄኖክ የተጻፈ በኢትዮጵያ በመገኘቱ ብዙዎች ሊቃውንቶች ተጠቅመውበታል ፪ኛ በ፫ሽ ፫፻፺፫ ዓ.ዓለም ላይ ፳ኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ካ፳ቱ ብሔረ ኦሪት ጋራ ስለ ዘመንና ስለ ትውልድ በሰፊው ሙሴ የጻፈው ኩፋሌ የተባለው መጽሐፍ በኢትዮጵያ ይገኛል። ፫ኛ ፫ኛው መ. ዕዝራ ፬ኛ ፬ኛው መ ዕዝራ ፭ኛ መ ጦቢት ፮ኛ መ ዮዲት ፯ መ ጥበበ ሰሎሞን ፰ መ ሲራክ ፱ መ ባሮክ ፲ ዝማሬ ፫ቱ ደቂቅ ፲፩ኛ ተረፈ ኤርምያስ ፲፪ኛ ታሪክ ዘሶስና ፲፫ኛ ስለ ቤል ወከይሲ። ፲፬ኛ ጸሎተ ምናሴ። ፲፭ኛ ፩ኛ መቃባውያን። ፲፮ኛ ፪ኛ መቃባውያን እነዚህ ሁሉ መጻሕፍቶች በየጊዜው እየተጻፉ መጥተው በአይሁድ እጅ ሳይቆነጸሉ ቀርተው በትክክል የዘመኑን አቆጣጠር እንደያዙ የሚገኙ የኢትዮጵያ መጻሕፍቶች ናቸው ፳ኤል ተማርከው ባቢሎን በነበሩበት ዘመን የተጻፉ መጻሕፍቶች በኢየሩሳሌም የተጻፉ መጻሕፍቶች መቃብያኖች ሁሉ ተጽፈው መጥተዋል። እነዚህ ሁሉ መጻሕፍቶች በግዕዝ ተጽፈው በቤተ መንግሥቱና በቤተ ክህነቱ ሲገኙ እነዚህም መጻሕፍቶች እርግጠኛነታቸውን ይዘው በምስክርነት ቦታ ቆመው ለዓለም እየታዩ የሮማ ልዑካን መኖራቸውን አናውቅም ብለው ቢክዱ ምን እንችላለን ከላይ በኢሳይያስ አፍ ዓይን ቦሙ ወኢይሬእዩ ተብሎ እንደተነገረው የነሱ ዓይነ ልቡና የተሠወረ ቢሆን የኢትዮጵያ መጻሕፍት ታሪካቸውን ይዘው ከመቀመጥ አይሠወሩም ማለት በግልጽ ቁጭ ብለው ዓይን ያለው ልቡም ያልጠፋበት እየመጣ ጥበቡን እየጠጣ እየረካ በማመስገን ይሄዳል

ለምሳሌ በዓለም በሽ የሚቆጠሩ ዕውራኖች አይታጡም የፀሐይ ብርሃን ለማየት ባይቻላቸውም በሙቀቷ ስለምታስረዳቸው። በዚህ ዓለም ላይ የሚገኙ ዕውራን ፀሐይን አይክዱም። ስለዚህ እነሱን ቅዱስ

# ሳ ረቡዕ ኅዳር

ዳዊት እግዚአብሔር ያጠብቦሙ ለዕውራን ብሎ። ተናገረ ዓይን ያላቸውን ዓይን ቦሙ ወኢይሬእዩ ያላቸው እንደሮማ ልዑካን ያሉትን እያዩ እንደማያዩ የሆኑትን ነው። የኢትዮጵያ ፊደሎች እንዲህ በጭፍን ዓይን የሚታዩ አይደሉም ከመናገር ከመጻፍ በፊት አስተውሎ መመልከት የተገባ ነው።

ስለ ማንኛውም ነገር ሁሉ ቅን ልቡናን ከያዝ ለሰው ማነኛውም አገር ገንዘቡ ሆኖ ለመኖር ይችላል ቅንነት ከሌላ ግን ከዲያቢሎስ በተሰወረው ምቀኝነትና ተንኮል እንደመናኒ ከሀገር ወጥቶ ወደሰው አገር ገብቶ በፖለቲክ ሕዝብና ሕዝብን እያፋጀ መኖር ለማንም ጠቃሚ አለ መሆኑን ባለፉት ነገሥታት የምንመለከተው ታሪክ ይነገረናል። ዓለም የደም ማፍሰስን ተግባር ከማን እንደወረሰችው። ደም ማፍሰስ ገንዘብነቱ የማን እንደሆነ ሳይገነዘቡ የሰው ደም ማፍሰስን መልካም ሙያና የክብር የጀግንነት መጠሪያ አድርገው። ዓለም ይህን የሰው ደም አፍሳሽን ስም ማክበርዋን ትታ የሚአዋርድ ስም ሰጥታው ቢሆንበዚህ

አሁን በምናየው ምድር ላይ ምን ያህል ሕዝብ ምድርን ሸፍኗት በታየ ነበር ግን ዓለም የምትለማበትን ትታ የምትጠፋበትን የዘችና የደም አፍሳሹን ስም በክብር በክብር ቦታ ትመዘግብ ዠመር ከዓለምም ውስጥ ይህን ውዳሴ ከንቱ የሕልም ሥራ እኔ እይዝ እኔ እጽፍ በመባባል በዓለም ሜዳ ላይ ብርቱ ትግል ገጠሙ። ከነዚህም ሰዎች ለምልክት ብናወሳላቸው አይከፋም ከነዚህም በባቢሎናውያን እንዠምር በኢትዮጵያ መጻሕፍት ቁጥር በ፭ሺ፱፻፵ ዓመተ ዓለም በባቢሎን ላይ ናቡ ከደነ ፆር የሚባል ከዓዌ ደም ተነሳና የዓለምን ከንቱ ውዳሴ በወርቅ ጽዋ ይጠጣ ዠመረ። ወደዚያው መጠጡ ሞቅ አደረገውና በነገሠ ፲፰ኛው ዓመት ሆሎፎርኒስ የተባለውን የሮ ጠቅላይ ከብዙ ሠራዊት ጋራ ወደ ኢየሩሳሌም ላከውና ኢየሩሳሌም ከቦ ካስጨነቃት በኋላ ፩ዲት መልከ መልካም የ፳ኤል ዮዲት የምትባል ሴት በፍቅር አታላ ገደለችው በዚህ ተናዶ ናቡከደነፆር ራሱ ወደ ኢየሩሳሌም ዘምቶ ኤልያቀምን ማርኮ ሴዴቅያስን ሾሞ ተመለሰ ሴዴቅያስ ፲፩ ዓ. ከነገሠ በኋላ ሸፈተና እንደገና ተመልሶ ሴዴቅያስን ማርኮ ኢየሩሳሌምን በጭራሽ አጥፍቶ ከተመለሰ በኋላ እንግዴህ ታሪኩ ይቆይና ባቢሎናውያን የነገሡበትን ዘመን እይና። ናቡከድነ ፆር የገዛ ብዙዎቹን አትጉሮች ነበር ራሱ ፳፯ ዓ. ነገሠ ፪ኛ ልጁ ኤልማሮዴቅ ፳፫ ዓ. ነገሠ ፫ኛ ልጁ ብልጣሶር ፳፩ ዓ. ነገሠ ድምር ዘመናቸው ፸፩ ነው ከዚህ በኋላ የሜዶን ንጉሥ ዳርዮስ ብልጣሶርን ገደለና መንግሥቱን ሲወርስ ደቂቀ ፳ኤልን ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ፈቃድ ሰጠ ግን ቂሮስም አለ በፋርስና በባቢሎን በሜዶን አብረው በፍቅር እንዲቆዩ ዳርዮስ ሲሞት ቂሮስ ሁሉንም ጠቅልሎ ሲይዝ ኢየሩሳሌም እንድትሠራ ፈቀደና ትእዛዝ ሰጠ በዚህ ጊዜ ከ፳ኤል ተማርኮ ወርዶ የነበረውን ዕቃ ሁሉ ይዘው ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ ንጉሡም ዘሩባቤል ሆነላቸው ዘሩባቤልንም አንግሦ የሰደደ የቂሮስ እኅት ልጅ ፪ኛው ዳርዮስ ነው ስለ ፳ኤል። ሕዝቅኤል ወአመ ፴ አመት እንዘ ውድቀት ሀገርነ ያለውን ለማግኘት በኢትዮጵያ መጻሕፍት ቁጥር ፳ቱን ሺ ዘመን በታላቁ ሱባዔ ባ፩፻፺ ሲመድቡት ፩ሺ ፪ ህኖ ፳ ይተርፋል በዚህ ሂሳብ ካ፳ቱ ሺ ፩፻ ይነሳል ፩፻ው ሲነሳ ፲መደብ ይሆናል እንግዲህ ፳ኤል ወባቢሎን የወረዱ ባ፭ሺ፱፻፵ ዓ. ዓለም ላይ ማለት ናቡከደነፆርም በ፭ሺ፱፻፲፪ ዓ. ዓለም

## ሴ ኃሙስ ኅዳር

ቢነግሥ ነው። እንግዴህ ፳ኤል ወደ ባቢሎን የወረደበት በዚሁ ካ፳ሺ ዘመን ሱባዔ በወጣው በ፺ቶው ዘመን ሥልምናሶር ፱ኙን ነገድ የወሰዳቸው ይህ ፺ኛው ዘመን ሲገባ ይመስላል ግን ትክክለኛው ፳ኤል ባቢሎን የቆዩበት ዘመን ከ፴ ዠምረው ነው።

ዕዝራም ያረገው ልክ ባ፳ሺ ዓ. ዓለም ላይ ለመሆኑ ፫ኛው መጽሐፈ ዕዝራ ፲፬ ፵፰ ወገበርኩ ከማሁ አመ ራብዕ ዓመት እምነ ስንበታተ ዓመታት እምድኅረ ዓመተ ኵነኔ በ፶፻ አመ ፲፩ ጽልመት በሣልስ ወርኅ ወመዋዕሊሁ ፺ወ፪ ሎቱ ውእተ አሚረ ነሥእወ ለዕዝራ ወወሰድዎ ብሔረ እለ ከማሁ ጽሒፎ ኵሎ ዝንተ። ወውእቱ ተሰምየ ጸሐፌ ጥበቢሁ ልዑል። የደም ማፍሰስ ውዳሴ ከባቢሎን ወደ ፋርስ ከፋርስ ወደ ጽርዓውያን ከጽርዓውያን ወደ ሮማውያን እንደዚህ እየሆነች እየተላለፈች ስለምትኖር ይህን ሁሉ ሕዝብ ስታስፈጅ አስተውሎ የሚመለከታት ሳይኖር እስከ ዛሬ ደረሰች ዛሬ ግን አስተካክሎ የሚአይ ጊዜ የሚባል መነጽር ስለተገኘ ሁሉም ማስተዋል ዠምሮ ይገኛል። ኢየሩሳሌም በሮማውያን እጅ በነበረበት ጊዜ ጌታችንን አይሁድ ሰቀሉት በኋላም ሮማ ላይ ጴጥሮስና ጳውሎስ ተሰቀሉ ተሰየፉ። የደም ነገር በሮማውያን ጌጥ ነው። የሮማ ልዑካን የካም ዘር ዕሥያን ወርሶ ያቀና መሆኑን ባለማወቅ ያልሆነ ነገር ሲጽፉ ይገኛሉ የካም ዘሮች ዕሥያን አቅንተው መንግሥትም መሥርተው የኖሩባት የካም ዘሮች መሆናቸውን ቅዱስ መጽሐፍ ከሚአስታውቀውም በላይ የኢትዮጵያ ጥንታውያን መጻሕፍቶች ከሚነግሩት ከዚህ ቀጥሎ የሚገኘው የኩሳ ልጆች ፳፰ ናቸው ከነዚህ ፺ቱ በቅዱስ መጽሐፍ ይገኛሉ ፳፪ቱ ግን በአዋልድ

መጻሕፍቶች ነው የሚገኙ ከነዚህም ስሙ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ሳባ የኩሳ ልጅ ፪ኛ ስሙ ቱይፌር ኩሳ ታውኔ ከምትባል ከሴም ዘር ከሆነች ሴት የወለደው ነው።

እሱም ኢትዮጵያዊና የፋርስ ባሕር አጠገብ ያሉት የየማን ዓረቦች አባት ነው ሀዋለ ወይም ሀዊላ ከለዳውያን ወይም የምዕራብ አፍሪካ ህንድ እኩሌታና የየማን ሕዝብ አባት ነው ይህ በሴም ወገን ማለት ነው። ደግሞ በኩሳ ረዕማ ራማ ወይም ራየም የተባለው በፋርስ ባሕር ዳር ለዳር የሚኖሩ የ፩ድ ፩ድ ዓረቦች አባት ነው ሰብታቃ ወይም ሰብታሕ ከጐረቤቶቻቸው ፩ድነት የመስሉት ደግሞ ይወስዳሉ። ናምሩድ የባቢሊንና የነነዌን ከተማ የቆረቆረ ነው እናቱ አርባ ትባላለች ናምሩድ ሴባስን ሀዊላህን ራግማላን ፫ቱን ይወልዳል። ሀዋላህ ፪ት ህንድ ፩ዱ ቀደህ ፩ዱ ጸሊም ወደቂቀ ሴባዕ ሰዌን ኖባ ብብያ ዓረብ ናቸው። ወደቂቀ ራግማን ከከታዕ ተራግማዕ ህንድ ፋርስ ሸኬዕ ዴን ሰባዕ ይላል። እነዚህ ሁሉ የናምሩድ ዘሮች መሆናቸውን መረዳት ነው የከነዓንንም ዘሮች ሲዶን አቡሁ ለጢኖስ ሔቱ ያቡሳዊ አምራዊ ጌርጌሲሐዊ ሲኒ አርዋዲ ዲየማዲ ሔማት ወደቂቀ ሴም አርፋክስድ አቡሆሙ ለከለደውያን አራም አቡሆሙ ለሶርያ ኤላም አቡሆሙ ለቀይህ ህንድ ወለባርቶስ ለአኮራድ ወለንጂም ወደ ኩሳ ዘር እንመለስ ሐበሲ በአልብየን የተወለደው በሐበስ ነገሠ የቀድሞ ሐበሲዎች አባት ሆነ ዓረብ በዓረብ አገር ነገሠ ያረቦች አባት ተባለ ጥንታውያኑ መጻሕፍቶች ከሚናገሩት ከብዙ በጥቂቱ ለአባቢዎች መሠረት መቋቋሚያ እንዲሆናቸው በማለት ይህን መጨበጫና መረጋገጫ አስማተ አኅጉር በከመ ወለጠ ጥንተ አስማቲሆን ንጉሡ ትርኩ ቅድመሰ ነበረ ስናዖር ከመ ተአተተ ማኅፈድ ተሰምየት

# ስ ዓርብ ኅዳር

ባቢሎን እስመ ባቢሎን ብሂል ዝሩት ወእምድሬሁ ተሰምየት ከላዴዎን እስመ ከላዲዎን ብሂል ተሰምየት በስመ እለ ይሰመዩ ከለዳውያን እስመ ከለዳውያን ብሂል ማዕማራን ወጠንቋልያን ወእምድኅሬሁ ተሰምየት መውዕል ወትርኩሂ ባቅዶቅ ወለፋርስ ሰመያ ሰፊ ወለሜዶን ቅዝል ባሻ ቅዝል ባሻ በልሳኖሙ ቀይሕ ወባሻሂ ርእሰ ሶበ ጠምጠሙ በርእሶሙ ቀይሐ ወበእንተዝ ተሰምየት ቅዝል ባሻአ ወለአርመንሂ ሰማያ መረዲ ወለቁስጥንጥንያኒ ቅድመ በራንጥያ ወቈስጠንጢኖስ ሰመያ በስሙ ቁስጥንጥያ ወትርኩሂ ሰመያ እስጥንቡል እስመ አስጥንቡል ብሂል ታዕካ ንጉሥ የሀገሮች ስም እንደዚህ እየሆነ በየጊዜው ልዑካን የኢትዮጵያን ዘርፍ ለመቀነስ አስበው ከሀገራቸው የመጡበት ጊዜው ብዙ ስለሆነ የብዙዎችን ሰዎች ልብ ለውጠው ይገኛል። የሮማ ልዑካን በደቡብ ዓረብ ላይ በኢትዮጵያ ፊደል በግዕዝ ፊደል የተጻፈ ሐውልት ሳልገኙ የደቡብ ዓረብ የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበረ በኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ በጥንታዊው ፊደል ተጽፎ የሚገኘው ሐውልት እየለፈለፈ የሮማ ልዑካን ጋራ የሚአክለው በግፍ ለዓለም ተገልጾ የሚታየውን ዙር ምልስ ገዥ የነበረችቱን ኢትዮጵያን ተገዥ አስመስለው ሳባ የሚለውን የንግሥት ስም ወስደው ፪ኛም የግዕዝን ፊደል የሴም ዘሮች ፊደል ነው እያሉ በወንጌል ምክንያት እየሰበኩ የብዙዎች ሰዎች ደራስያን እስከመሆን የደረሱትን ሁሉ በዚህ ስብከት ወስደዋል። ከደቡብ ዓረቦች አንዲቱ የመን ናት የጥንት ስሟ የማን ነው ይህም በግዕዙ የኢትዮጵያ ቀኝ ማለት መሆኑን ማየት ነው። የሮማ ልዑካን በነአርጤክስስና በዳርዮስ በፋርስ ነገሥታት ከባሕር ማዶ የነበረውን የኢትዮጵያን ግዛት መውሰዳቸውን እንኳ የሚአስረዳ የለም። ማለት ያንጊዜ እነሱ ወስደውት ቢሆን ዳርዮስን ገድሎ እስክንድር የዳርዮስን ግዛት ሁሉ በወሰደ ጊዜ እስክንድር አብሮ እንዲገዛው ጥርጥር የለበትም ነበር እስክንድርም ይዞት የነበረውን ላ፬ቱ ሹማምንቶች አካፍሎ ባለፈ ጊዜ ተከታዮቹ እስከ ፪፻ ዘመን ከእስክንድር በኋላ እንደ ነገሡ ሮማውያን ተነሥተው ግብጽ ድረስ ሲመጡ በማነኛውም ጊዜ የደቡብ ዓረብ አገሮች በኢትዮጵያ እጅ እንደነበረ

የሚታወቀው ባ፫፻፳፫ ዓ.ም አጼ ካሌብ ስለ ክርስቲያኖች ባደረገው ዘመቻ ነው። ከወደፊት በዘግዱር ወይም ገደረት ዘምቶ ያቆመው ሐውልት ቅርጽ ፊደል ነው የፋርስ ነገሥታት ስንኳን ባሕር ተሻግረው ኢትዮጵያ ገብተው ሊገዙ ከባሕር ማዶ ለነበረውም ለኢትዮጵያ ግዛት ከልደተ ክርስቶስ በፊት ከሽ፫፻ ዘመን አስቀድሞ የእስላሞች ሃይማኖት

እስቲበረታ ድረስ የደቡብ ዓረብ በኢትዮጵያ እጅ መቆየቱን የታሪክ መጻሕፍቶች ስለሚአረጋግጡ የፋርስ ነገሥታት ኢትዮጵያ መጥተው ነበር ማለት አሣ እና ጉማሬ ከባሕር ወጥተው ደጋ ተቀመጡ ደግሞ በደጋ የሚገኙ ዓራዊቶች ከታላቁ ባሕር ገብተው ተቀመጡ ማለት የተሻለ ነው። ለዚያውም የእርግጠኛነቱ ምልክት የዮቅጣን ልጆች በሞቱ ፩ሺ፪፻ ዘመን በላይ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር ተብሎ የተጻፈው ለዓለም መደነቂያነት በጣም የተሰናዳ ነው። የፋርስ ነገሥታት የሠሩት ሥራ ከመጻሕፍቱ የተሠወረ አይደለምና ማንም ባለታሪ ቢመረምርና ቢገምተው የማለት አሳቤን ለዓለም ባለታሪኮች ለማካፈል ምኞቴን እገልሳለሁ። እንደዚህ ያለ አስደናቂና አስጨናቂ ነገር በመካከሉ እያለ የሮማ ልዑካን ወንጌል እናስተምራልን እያሉ ወንጌልና መስቀል

## ሶ ቀዳም ኀዳር

እየያዙ በኢትዮጵያ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ የትምህርት ቤቶ አቆምን እያሉ ወጣቶችንና በትምህርት ያልበሰሉትን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ከሮማ ላይ ካፑችኒ ከሚባለው ማኅበር በሚመጣው ገንዘብ በዳቦና ሱካር እያባበሉ ሃይማኖታቸውን እያስጣሉ የኢትዮጵያን ታሪክ መሠረት እየሠረሠሩ ይህንም ለቀረባቸው ሁሉ ስለአጠኑና በመጽሐፉም እየጻፉ ለዓለም ስለ ዘሩት በወጣቶች ሁሉ ልብ ሊገባ ሲደረጃጅ ይገኛል በግዕዝ ላይ የሮማ ልዑካን እስቲነሱበት በኢትዮጵያ ላይ ፬ሺ፩፻፵ ዘመን ያገኘ ነበር እነሱ ከተነሱበት ፩፻ ዘመኑ መሆኑ ነው ይህን ያህል ዘመን እነሱ እንደሰረሰሩ አሉ ሆኖም አሳባቸው በጣም ተያይዞላቸው ስለሚገኝ አሁን ደፍረው የኢትዮጵያ ታሪክ ብለው ፖለቲኩ ለቀቁት የተያዘላቸው ማለቴ የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ይመርመር ተብሎ አርኪአሎዥ ሠራተኞች መጥተው በምርመራ ላይ የተገኙትን ጽሑፎች በድንጋይ ሐውልት ላይ የተገኙትን ጥንታውያን የግዕዝ ፊደሎች ስም እየሰጡ የግርማዊን ን ነ ቀዳማዊ ኃ. ሥላሴን ፳፭ኛ የንግሥ በዓል ምክንያት በማድረግ ተከፍቶ በነበረው ኢግዚብሽን ውስጥ የቀረቡት ጥሩ መሠረትን ለመስጠት ችለዋል ከተማቹትም ዕቃዎች መካከል ከአዲግራት ሰሜን ምሥራቅ ፳፫ ሰሜን ከሚገኘው ከአዝቢ ዴራ የተገኙት ጥንታዊ ዕቃዎች ይገኙበታል። ከአዝቢ ዴራ የመጡት ዕቃዎች ከትግሬ ጠቅላይ ግዛት መሥሪያ ቤት ውሥጥ ከመቀሌ የተገኙ ናቸው የአዝቢ ዴራ ከተማ የምትገኘው ከደንከሌ ዓዛቅት ሥፍራን ከትልቁ አቀበት ሲሆን ይህች ጠባብ ምንገድ ከአክሡም ወደ ቀይ ባሕር የምትወስድ ሳትሆን አትቀርም ከዚች ከተማ የተገኙት የዕቃ ድርጅቶች ግራጭ አረንጓዴና ነጭ የሆነ ከኖራ የተሠራ ሐውልት ፩ድ ሰው ቀሚስ እንደለበሰ ሆኖ ባ፩ድ በኩል ደግሞ ከመሠረቱ ላይ ሰውዬው በዙፋን ላይ እንደተቅመጠ የሚአሳይ ነው በዚህም ላይ የደቡባዊ ዓረቦች ቃል ተጽፎበት የነበባል ይላል" እንግዲህ በዚህም ላይ የደቡባዊ ዓረቦች ቃል ይነበባል የተባለው ጽሑፍ ከሮማ ልዑካን ትምህርት ምንጭ የተቀዳ ነው። በፊተኛው በዘውዱ በዓል ምክንያት ባማርኛና በፈረንሳይ ከቤተ መጻሕፍት ወመዘክር አላፊነት ታትሞ የወጣው በደቡብ ዓረቦች ፊደል ይላል። ከዚይ በኋላ ደግሞ በጋዜጣና ማስታወቂያ ክፍል ፪ኛ ላልሰማው ለማባዛት ሲጻፍ የደቡባዊ ዓረቦች ቃል አለበት ተብሏል። ይህ መሻሻሉ ማለት ነው እንግዴህ ጽሑፍ ያነበበ ሁሉ ይህን ይዞ ሲሄድ ዓለምም ሲቀበለው የሮማ ልዑካን ይህን ባዩ ጊዜ ተቃዋሚ ቢመጣም እዚያው የኢትዮጵያን ሰዎች አላፊ አድርገን እናቀርብና እርስ በርሳቸው እናጣላቸዋለን መቸም የኛ ጠቃሚው ሥራችን የኢትዮጵያውያን መጠላላት ነው ብለው ይህን ፩፻ ዘመን የተቀመመ የፖለቲካ ጽሑፍ

አፈሰሱብን "፪ኛ ከአክሡም ደቡብ ፲፪ ኪሎ ሜትር ራቅ ብሎ ከሚገኘው ሐውልት ሚላዞ ከተባለው ከተማ እ.ኤ.አ ባ፲፱፻፶፫ ዓ. በጥቅምት ወር በተደረገው ምርመራ ከዚህ በታች የሚከተሉ ዕቃዎች ተገኝተዋል ባ፩ ማዕዘን የተሠራ ቤት ከዚህም ውስጥ የአማልክ ደቡባዊ ዓረቦች ታላቁ እግዚአብሔር ብለው የሚአመልኩበት የጨረቃ ምልክት ብዙ ክብር ያሏቸው ታቦቶች ብዙ የሸክላ ሥራዎች በአረንጓዴ ጠቃጠቆ መልክ ያለው ትንሽ ወይፈን የቅርጽና በደቡባዊ ዓረብ ፊደል የተጻፉ ጽሑፎፍ ተገኝተዋል ይኸውና እዚህ

## ቀ እሁድ ኅዳር

ላይ በደቡባዊ ዓረቦች ፊደል የተጻፉ ጽሑፎች ተገኝተዋል ብሎ ጻፈለት።" ይህን ያነበበ ሁሉ የኢትዮጵያን መሠረት ታሪክ ለማፍረስ ካላይ ከጉልሉ ዝምረው የታሪክ ጉልላት ማለት ፊደል ነው። የማፍረስም መሠረት አለው ማለት በፊት ሥራ የሚዝመርበት ነው ይህም ይታወቅ ዘንድ ኢጣልያኖች ኢትዮጵያን በወረሩ ጊዜ ያጸ ምኒልክን መታሰቢያ ለማፍረስ ከጉልሉ ዝምረውት በኋላ በከተማ ያለው ሕዝብ ሁሉ ይህን ባየ ጊዜ ወደ አርበኞቹ ሄዶ የተጨመረ እንደሆነ እኛ አንችለውም በማለት አመዛዝነው መልሰው ጠገን አድርገው እንደተውት መመልከት ነው። ስለዚህ የታሪክ ጉልላት ፊደል ስለሆነ የሮማ ልዑካን የኢትዮጵያን ታሪክ ለማፍረስ በፈለጉ ጊዜ አስቀድሞ ጉልላቱን ፊደሉን ዝመሩት የኢትዮጵያን ታሪክ ለማፍረስ በፈለጉ ጊዜ ገድለው ከፍነው ሊቀብሩ መቃብር ሊያወርዱ ሲሉ ደራሲው በድንገት ደረሰባቸውና ምክንያቱን ለመረዳት ይመረምራቸው ዝመር። የሮማ ልዑካን ጥበብ ፩ድ ፩ድ ጊዜም ሳይሳተው አይቀርም የኋላ የኋላ ጊዜ ሮማ ላይ ስለሚወጣው ገንዘብ ፍሬ ሳያገኝ በቀረ ጊዜ በኢትዮጵያ ሲዘሩት የኖረው ጠብና ክርክር በሰፊው አፍርቶ ለለቃሚ ሳያስቸግር የሚቀር አይመስለኝም። ስለ ፫ቱ ሐውልቶች ጥንታዊ ቅርጽ የሆነውን ያህል ማስረጃዎችን አሳይቻለሁ አሁን ደግሞ ፩ድ ጥያቄ አለኝ አባ ጋስፓሪን ሆይ ዔዛናን የመንግሥት ዕፍያ ልጅ ነው ብለው በ፫፻፳፭ ዓ.ም ምሕረት ነገሥ በዘመኑም ፱ቱ ቅዱሳን ባባቱ በአልዓሜዳ መጥተው ስለነበረ ከፍሬ ምናጦስ ጋራ አብረው ኢትዮጵያን በማስተማር አሠለጠኑ ብለው በአብርሃና በአጽብሐ አይደለም በማለት። አብርሃና አጽብሐ የሚለውን የኢትዮጵያን ክብረ ነገሥት ነቅፈው በዔዛና ነው ዔዛናም የአልዓሜዳ ልጅ ነው ብለው በሰፊው ጽፈው ዓምድ አሲዘውት ይገኛል። አሁን የምጠይቆ ይሕ ዔዛና ማንን ወልደ በመንግሥቱስ ማንን ተካ ለነዚህ ሁለቱ ጥያቄዎቼ መልስ እፈልጋለሁ። አባ ጋስፓሪን የሮማ ልዑካን ነገረ ፈጅ መሆንዎ የሚካድ አይደለም ማለት ይህ አሁን በጥራዝ ፩ድ አድርገው ጽፈው ያቀረቡት ከሽ፬፻፱ ዓ.ም ዝምሮ እስከ የሮማ ልዑካን ከሚስፉት ከምሉ በክፍሉ ስለሆነ ነው። አሁን የምጠይቅ እርስዎን ብቻ ሳይሆን የሮማ ልዑካንን ከደቀመዛሙርቶቻቸው ነውና በጥንቃቄ መልሱን እፈልጋለሁ የኢትዮጵያን ክብረ ነገሥት አልነቀፍኩም እንዳይሉ "በ፻፹ ገጽ ባ፲፩ኛው መሥመር ንጉሥ አብርሃንና ንጉሥ አጽብሐን በሚያየው ወይም በሚነካው ነገር ላይ ያለ ወግ ይህ አነጋገር ስለማኮሰስና ስለመናቅ ማለት ነው እርስዎ ግን አይገነዘቡትም "የነሱ አባት ሰይፈ አርድ ይባል ነበር ከነዚህ ልጆች ፩ዱ እኩለ ሌሊት ፩ዱ ማለዳ ጽባሕ ተወለደ ብለው ያወጋሉ አብርሃ በተወልደ ጊዜ ፩ድ ብርሃን በራሱ ላይ አበራ አብርሃ ሌላውም በተወለደ ጊዜ ፀሐይ በራሱ ላይ አበራ እነርሱም አኃው ፍቁራን የሚፋቀሩ ወንድማሞች ባ፩ነት ፳፯ ዓመት ከ፯ወር ባ፩ድ መንበረ ጽሑፍ የተጻፈ ስለ ማቃለል መሆኑን መረዳት በዚሁ ገጽ በ፯ኛው መሥመር እጅግ ትልልቅ የሆኑትን ነገሮች ተከትለው ብዙ ወሬና መንፈሳዊ ታሪክ ፩ድ ፩ድ ጊዜም ልብ ወልደ ታሪኮች እንደ ተጻፈ አሁን በጣም የሚናቅ ነው የተባለው

## ቁ ሰኑይ ኅዳር

ጽሑፍዎ ምን ማለት ይመስልዎታል ልክ አድርገው ነቅፈው ጽፈዋል ለሰው ቃሉ ፩ድ መሆን እንደሚገባው የታዘዘበትን ከላይ ጽፈልዎታለሁ ስለዚህ ፩ድ ሰው ሁለት መላስ ሲሆን ምን ለመባል ይቻላል አሁንም የኢትዮጵያን ታሪክ ጽሑፍ ነቅፈው አብርሃና አጽብሐን ሠርዘው እርስዎ እንደፈቀዱት በትውልድ ከሰይፈ አርድ እስከ ዔዛና ፹፩ኛ በዘመነን ፱፻፱ ነው እንደዚህ የሚሆነው የሰይፈ አርድና የሶፍያ ዘመነ መንግሥት ሲጨመር ነው። እንግዲህ ከላይ ላቀረብኩት ጥያቄ የኢትዮጵያን ታሪክ ነቅፈው በትውልድ ፹፩ኛ በዘመን ፬፻፶፫ኛ ዓ.ም የሆነውን ዔዛናን እላይ አውጥቶ ያን ሁሉ ሐተታ ሰጥተው አሰናዱለት እነም ይህን ካነበብሁ በኋላ ልጠይቅዎ የፈቀድኩት በመካከሉ ስለቀረው ዘመንና ትውልድ ነው። ስለዚህ ዔዛና በ፫፻፳፭ ዓ.ም ነግሦ እስከ ፫፻፴ ዓ.ም እንደ ገዛ በገጽ ፯ኛ በ፪ኛው መስመር የተጻፈው ያስረዳል እንግዴህ የዔዛና ዘመነ መንግሥት በ፫፻፴ ስለ ሆነ ከ፫፻፴ ዓ.ም ዝምሮ የነገሠው ማነው ግን እርስዎ የጻፉበትን

ስመለከተው እንደ ኢትዮጵያው ክብረ ነገሥት አጼ ካሌ ያጼ ዔዛና ተከታይ እንደሆነ የሚአስረዳ በገጽ "፻፴፪ በ፳፪ኛው መሥመር በደቡባዊ ዓረብ ውስጥ የነበሩ አይሁን ብዙዎች ስለነበሩ በክርስቲያን ሃይማኖት መስፋፋት ቀንተው እነርሱን ለማጥፋት ተነሡባቸው በሌላውም ወገን በደቡብ ያለው የዓረብ ግዛት አረማዊ ስለነበረ ክርስቲያኖች በሁለት ጠላቶች ውስጥ ስለሆኑ በክርስቲያኖች ላይ ብርቱ ስደት ደረሰና ክርስቲያኖች ስለ አለቁ በዚያ የነበሩትም የቁስጥንጥንያና የግሪክ ነጋዴዎችም ተቸግረው ነበር። በዚያ ጊዜ የኢትዮጵያ ነገሥታትና ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ቅንዓት ተቃጥለው ወንድሞቻቸውን ለማዳን ፈለጉ። በዚህ ምክንያት የአክሡም ንጉሥና የቁስጥንጥንያ ንጉሥ ስምምነት አደረጉ። የአክሡም ንጉሥ መርከቦቹን አዘጋጅቶ የዓረብን አገር ክርስቲያኖች ለመርዳት ባሕር ተሻግሮ የክርስቲያኖችን ጠላት አሸንፎ ዋናውን ከተማ ዛፋርን ከያዘ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ "በ፻፴፫ኛ ገጽ ባ፲፭ኛው መሥመር በቁስጥንጥንያ ንጉሥና ባጼ ካሌብ መካከል ስለ ተደረገ ቃል በዚህ ጊዜ አክሡም ላይ ነግሦ የነበረው አጼ ካሌብ ነው ይላል"። ከዔዛና አስከትሎ ኢትዮጵያን መንግሥት የወረሰ አጼ ካሌብ መሆኑ የተረገጠ ሲሆን የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ ተነቅፎ የነበረው መሠየሙ ቃልዎ መለወጡ የተረገጠ መሆን አለበት። አሁንም ቢሆን መጠየቅ አይቀርም ማለት የሚጠየቁበትን መገንዘብ ነው። ይህም አልዓሜዳ ከንግሥት ሶፍያ ዔዛናን ወለደው ብለው እርስዎ ይህን ጽሑፍ ከልብዎ ወልደው ስለጻፉት የንግሥት ሶፍያ ባል ሰይፈ አርድ መሆኑ ቀርቶ አልዓሜዳ ከሆነ ከሰይፈ አርድ እስከ አጼ ካሌብ ሰይፈ አርድ የነበረበት ዘመን በ፪፻፶፪ ዓመተ ምሕረት ስለነበረ ዔዛና በ፫፻፳፫ ዓ.ም ነገሠ ካሉ በኋላ አጼ ካሌብን ከዔዛና ተከታይ ሆነ ብለው ስለጻፉ አጼ ካሌብ የነገሡበትን ስንመለከት በ፻፴፭ኛው ገጽ ላይ አጼ ካሌብ የነገሡው ባ፭፻፳፭ ዓ.ም መሆኑን ገልጸውት ይገኛል። እንግዴህ ይሁን እርስዎ እንዳሉት ከ፫፻፳፫ት እስከ ፭፻፳፭ ልክ ፪ት፪ ዘመን ዔዛና ገዛ ማለትዎ መሆኑን አልተገነዘቡትም ተሰምቶ ነው እንዳልል የሮማ ሊቅ የኢትዮጵያ መምህር ነዎ በብዙ ደቀመዛሙርቶች እንዳሉዎ አውቃለሁ። ሆኖም ነገሩ ያልተለመደ በመሆኑ ፪፻ ዘመን በሙሉ ፩ድ ሰው ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ ያውም ከ፫፻፳፫ ዓ.ም በኋላ ፩ድ

## ቂ ሡሉስ ኀዳር

፪፻ ዘመን ነገሠ ብለው በመጻፍዎ ስለተቸገርኩ ይህን ረቂቅ ጥበብዎን እንዲገልጹልኝ እፈቅዳለሁ። እኔ የተሳሳትኩ እንዳይመስልዎ ልክ ራስዎ የጻፉትን እየጠቀስኩ መሆኑን ይመልከቱ ፩ኛ ዔዛና ከ፫፻፳፫ እስከ ፫፻፷ ዓ.ም ነገሠ ብለው በ፯ኛው ገጽ የጻፉት ነው። ፪ኛ "በ፻፴፭ኛ ገጽ ባ፩ኛው መሥመር አጼ ካሌብ ወደ ዓረብ አገር የዘመተበትን ፭፻፳፭ ዓ.ም ብለው የጻፉት እገሌ ይገንዘቡት። ፫ኛ ዓረብ አገር የዘመተበትን ፻፴፭ኛው ገጽ በጻፉት እገሌ የሚል የለም። ስለዚህ ካሌብ አለቦታው ባልነበረበት ዘመን ነገሠ ብለው

ጽፈው ብትውልድ ፴፮ ሰው። በዘመን ፪፻ ይህን ሁሉ ማስረጃ በማጭበርበር ተራምደው አጼ ካሌብ ላይ እንደ ኢትዮጵያ ክብረ ነገሥት ያጼ ካሌብ ታሪክ በዓለም የታወቀ በመሆኑ አስገድዶዎ አጼ ካሌብን የዔዛና መንግሥት ተከታይ አድርገው እርስዎ ይህን ሲጽፉ ደግሞ ባንድ ወገን ስለመዘኑና ስለትውልዱ የተጻፈው አልጋጠም አለና እሳትና ሰም መሰለ ሰም እሳት ሲቀርበው ውኃ ይሆናል እሳት ሲርቀው ተመልሶ ይረጋና ሰም ይሆናል። ይህም ጽሑፍም ሚዛን ሳይመጣበት ልክ ሆኖ ተስተካክሎ ይገኛል ሚዛኑ ሲቀርብ ግን የመራራቁ ነገር የትና የት እንበል ከአሜሪክ የራቀ ነው። የሮማ ልዑካን ፖለቲክ ካባ ጋስፓሪን የተገለጸውን ስመለከተውና ስንመረምረው ስመዝነው ምንም በታሪክ ገጽ የሚገኝ ጽሑፍ አይደለም የጽሑፉ አስተያየት የሚሰጠው ግምት አገርና አገር ሕዝብና ሕዝብ ለማነቃቀፍ የተሠራ ልብ ወልደ ፖለቲክ ከመሆኑ በተቀር ሌላ የሚሰጠው ፍሬ እንደሌለ ላንባቢዎች እገልጻለሁ

የሮማ ልዑካን የሐሰታቸውንና የድፍረታቸውን ብዛት ላንባቢዎች ለመግለጽ በ፻፳፭ኛ ገጽ ከታች በመሥመር ተከቦ በረቂቅ ፊደል የተጻፈ ከላይ ሁለት ጥንታዊ ገንዘቦች የተሳሉበት (በዚህ ሥዕል ላይ የሚታየው የንጉሥ ዔዝና አንዱ

የወርቅ ገንዘብ ነው ገጹና ጽሑፉ በ፪ቱም ወገን በጣም ይታያል። ይህ ገንዘብ የተሠራው ንጉሥ ዔዛና ክርስቲያን ሳይሆን ነው ማስረጃው በገንዘቡ ምሥል ላይ ፩ድም የክርስቲያን ምልክት አለመታየቱን ነው። ገንዘቡ ብዙ ጊዜ በምድር ውስጥ ተቀብሮ በመኖሩ ምክንያት ቅርጹ ተበላሽቷል።) ከላይ ጽሑፉ በሁለቱም ወገን በጣም ይታያል ተብሎ ነበር ደግሞ ትንሽ ዝቅ ብሎ ቅርጹ ተበላሽቷል ወይም ቅጡ ጠፍቷል ተብሎ ተጽፏል። (ልክ የሆነ ነገር አይገኝም ይሁን እንጅ ምንም ቢበላሽ የሳባውያን መለዮ የሆነው ግማሽ ጨረቃና ኮከብ ይታዩበታል።) ይልቁንም ጥሩ የሆነ የክርስቲያን ምልክት የለበትም ተብሎ ተጽፎበታል ፪ኛ በገንዘቡ ሥዕል ላይ የግማሽ ጨረቃና ፩ ኮከብ ምልክት የሳባውያን አለበት ይላል "በ፻፷፯ኛ ገጽ የደቡብ ዓረብ መልዮ ይገኝባቸዋል እንደዚህም ማለት ከበላዩዋ ፩ድ ኮከብ ያለባት ግማሽ ጨረቃ አለችባቸው ማለት ነው። ይህ መለዮ በደቡብ ዓረብ የነብሩ ሳባውያን ምልክት እንደሆነ በጣም የታወቀ ነው በኋላም የእስላሞች መለዮ ሆኖአል በኢትዮጵያም ይህ መለዮ በብዙ ሐውልቶች ላይ ይገኛል" ይህ ዛሬ ያረቦች ዓላማ ላይ የሚደረገው ግማሽ ጨረቃና ፩ድ ኮከብ አስቀድሞ በደቡብ ዓረቦች ዘንድ ያልነበረ መሆኑን ባለመገንዘብ እንዲሁ ዛሬ ያለውን ዓላማ ስላዩ ቀድሞ በደቡብ አረብ ያልነበረውን በደቡብ አገር መኖሩን አስቀድመው ሳይረጋግጡ ኢትዮጵያ ገብቶ ነበር እያሉ ዘወትር የለመዱትን ያልታረመ

## ቃ ረቡዕ ኅዳር

ቁሻሻ ንግግር ይጽፋሉ። እኔ በጥብቅ የምናገረው ይህ ግማሽ ጨረቃና ፩ድ ኮከብ አስቀድሞ በደቡብ ዓረቦች ዘንድ የገባው የእስላሞች ኃይል ጠንክሮ የዓረብን አገሮች ከኢትዮጵያ መንግሥት እጅ ከወሰዷቸው በኋላ ነው እንጅ ከዚያ በፊት በዓረብ ደቡብ አገር የነበረ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ነው እንጅ ሌላ ዓላማ አልነበረም ሌላ ዓላማ ሳይኖር ዛሬ የሚታየውን ዓላማ አስቀድሞ ትንቢት አድርጎ አምጥቶ ነበር ማለት ያው የተለመደው የሮማውያን ስብከት ማለት ነው። ደግሞ አስገራሚው ቅጥፈት ስለ አብርሃና አጽብሐ ቀ'የስጥንጥንያ ንጉሠ ነገሥት ቁንስጣ ለአክሡም ነገሥታት አብርሃና አጽብሐ የተጻፈውን ለዔዛና ለውጠው ለዔዛና የተጻፈ ካላስመሰሉት በኋላ ከመጨረሻው ላይ የተከበራችሁ ወንድሞች እግዚአብሔርን ይባርካችሁ ይላል ማለቱን አልካዱም እዚህ ላይ እምነት አስጨብጠዋል ይህን ከጻፉ በኋላ ለዚህ ማፍረሻ የሚሆን ፩ድ ነገር ፈጥረዋል ይህም እንደዚህ ነው "በ፻፷፫ኛው ገጽ በ፳፫ኛው መሥመር በዚህ መጽሐፋችን ላይ በ፫፱ እንዳገባነው በጥንታዊው ኢትዮጵያ ቋንቋ በተጻፈው ጽሑፍ ላይ ንጉሥ ዔዛና በብጋ ሕዝብ ላይ ብዙ የጦር ሠራዊት ሰደዱበት የዚህ ጦር አዝማቶች ሥዔዛናና ሐዴፋን ወንድሞች

ናቸው ይላል" አሁን ይህን ተከትለን ብንመረምረውም እንዲሁ የመጨነቅ አማርኛ ነው እንጅ ደምበኛ መስል አናገኝም የቁስጥንጥንያው ንጉሥ ወዳ አብርሃና አጽብሐ ጽፎ የሚገኘው ፩ድ አርዮሳዊ በቀይ ባሕር ተሻግሮ ወደ ኢትዮጵያ ገባ የሚባል ወሬ ስለሰማ ያርዮሳዊውን ለገር ለማስጠንቀቅ ነው- እንጅ ስለጦርነት አልጻፈም ቢጽፍም ለንጉሥ ይጽፋል እንጅ ለንጉሡ የጦር አዝማቾች ማለት ሐሰት ነው። እንጅ እውነት አይደለም የንጉሡ የጦር ሹማምንቶች ሥዔዛናና ሐዴፋን "በ፻፫ ገጽ እንደተጠቀሰው ከሥዕሉ ግርጌ ከመጨረሻው መስመር ፈኖነ አኅዊነ ሥዔዛና ዌሐዴፋሃ ይላል በግዕዝ እንግዲህ እነዚህ ሰዎች ንጉሥ ናቸው ለማለት የሚቻልም እንደሆነ አንባቢ ይገምተው ንጉሥ ላልሆኑት ለጦር አዝማቶች የቁስጥንጥንያ ንጉሥ ጻፈ ማለት የሚመች ምክንያት መሆን የሚችል እንደሆነ አንባቢ ይገምተው "በ፻፷፱ነኛ ገጽ ዔዛና ከሶፍያና ከአልዓሜዳ የተወለዱ ሥዓዛናና ሐዴፋ የተባሉ ፪ት ወንድሞች ወይም ፩ ብቻ ይኖረው ይሆናል" አሁን ይህ ነገር በታሪክ ገጽ ሲቀርብ ምን ለመባል ይቻላል ባዕድም ሆኑ ወንድሞቼ የቁስጥንጥንያው ንጉሥ የተከበራችሁ ወንድሞቼ። እግዚአብሔር ይባካችሁ ብሎ አልጻፈላቸውም የጻፈላቸው ለአብርሃና ለአጽብሐ ነው ይህም ጽሑፍ ባትገነዘቡት ባታዩት ነው እንጅ አሳምሮ መስክሮባችኋል አብርሃና አጽብሐ ንጉሥ ቁንስጣንስ የነበሩት ዘመን ፩ድ በመሆኑ ዋና ማስረጃ ነው። ፩ድ ፩ድ ጊዜም ለመስበኪያ የሚስፉ ነገሮች ለውሸት

ማያያዣ ከሆኑት "በ፻፴፰ኛ ገጽ ኢትዮጵያ በዓረብ አገር የነበራትን ግዛት መጨረሻ እስከ ዓርብ አገር ድረስ ገፉት ማለት አስገበሩት ማለት ነው አብርሃ በፋርስ ጦረኞች የተሸነፈው በ፭፻፸፪ ዓ.ም እንደሆነ ይታመናል ማንኛውንም የኢትዮጵያን ታሪክ መቀነስ ዋና ተግባራቸው ስለሆነ ነው እንጅ ዓረብ አገር ከ፻፪ ዘመን በላይ ከኢትዮጵያ እጅ መውጣት የለበትም ብዙዎች የዓረብ መጻሕፍት በመጨረሻው ጊዜ ኢትዮጵያ የዓረብን አገር በመግዛቷ ላይ

# ቈ ሐሙስ ኅዳር

ሲናገሩ አብርሃ ኃይለኛ የሆነ ብዙ የጦር ሠራዊትና ዝኆኖችም እንደ ነበሩት ይናገራሉ የዓረብ አገር ባለዝማሬዎች ግጥም ገጣሚዎችም ማለት ነው ኢትዮጵያውያን በዓረብ አገር ያሳዩትን የጀግንነት ሥራ በቀረርታቸውና በሽለላቸው በፉከራቸው ያመሰግናሉ ፩ዱ የዓረብ መጽሐፍ በአክሡም ንጉሥና በደቡባዊ ዓረብ እንደራሴው ማኸል የሆነ ነው ተብሎ ፩ድ አስደናቂ ታሪክ ይተርካል ታሪኩም የሚከተለው ነው አብርሃ ከአክሡም ንጉሥ ነጻ መሆኑን መሸፈቱን ባሳየ ጊዜ ንጉሡ በጣም ተናዶ ቀይ ባሕርን ተሻግሬ የዓረብን አገር በእግሬ ረግጨ በገዛ ጠጉሩ ሳላንጠለጥል አልቀርም ብሎ ባደባባይ ማለ። አብርሃ ይህን በሰማ ጊዜ ለንጉሡ ታማኝነቱን በፍጥነት አስታውቀ። ለዚሁም ማስረጃ ከቆንዳላ ጠጉሩ ቆርጦ ፩ድ ከረጢት የዓረብ አገር አፈር ላከለት። ከዚህ በኋላ ንጉሡም ማረው ይላል። የዓረብ ደቡብ አገር በኢትዮጵያ ነገሥታ ስትገዛ ለመኖርዋ ብዙ ማስረጃ ሞልቶ የሮማ ልዑካን እንደዚሁ በጠላትነት ተነሥተው በጦር ኃይል የማይሆንላቸው ቢሆን በታሪክ ፖለቲክ ፈጥረው በልባቸው የሚመኙትን ምኞታቸውም የሮማን ሃይማኖት በኢትዮጵያ ዘርግተው ቤተ ክርስቲያን አስፋፍተው እነሱ የኢትዮጵያ ሐዋርያነት ይዘው በኢትዮጵያ ውስጥ የሮማ ቤተ ክርስቲያን ሥልጣንን ለማስገባት ከዚያ ደግሞ ቀስ እያሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ የሚአፋጅ ነገር እየፈጠሩ እንደልማዳቸው የኢትዮጵያ ሕዝቦች መቸም እያነሱ እንጅ እየበረከቱ ስለማይሄዱ እንደዚሁ ለኢትዮጵያ ደዌ ሥጋ ሆነው ሕዋሳቶቿን እየቆራረጡ እጅዋ የማይጨበጥ እግርዋ የማይረግጥ ሲሆን ጠብቀው የኢትዮጵያን ዘርዓ መንግሥት ያለውን ፈጽመው ካጠፉ በኋላ ዘሩንና ነገዱን የማያውቀውን በነሱ የሚመራውን የቀን ሠራተኛ አድርገው ለመግዛትና በኢትዮጵያ ምድር ውስጥ የሚገኘውን ሃብት ወርሶ ለመጠቀም አስበው ነው። የነሱ ሐሳብ ይህ ስለሆነ ካገራቸው በሚመጣው ገንዘብ

ሕዝቡን እያባበሉ እየሰበኩ ልቡን ለያይተውት ይገኛል የሕዝብ መለያየት ለመንግሥት ጉዳት የሚአመጣ ነው። ስለዚህም እስክንድር ሊቃውንቶቹን እንደ ጠየቀ ከሊቃውንቱ ንግግር ወተሠአሎሙ እስክድር ለጠቢባነ ባቢሎን ወይቤሎ አርስጣጣሊስ አመ አዘዘ እስከንድ ወይቤሎ ዓለምሰ ገነት ወሐጹራኒ ንግሥ ንጉሥኒ ኖላዊ ዘየዓውድዎ ሠራዊት ወሠራዊትኒ ሐራ ዘያስተጋብዖሙ ንዋየ። ንዋይኒ ጸጋ ዘአስተጋድ ይዕቲ ጥዒናሃ ለዓለም ፍትሕሰ ጽንዑ ለዓለም ርዕሰ ሠናያት ወቦቱ ይበዝኃ ንዋያት ፍትሕሰ ያስተፋቀር ወውእቱ ጽንዑ ለዓለም ትብህለ ንጉሥ ወሃይማኖት ዕሩያን እሙንቱ ፪ሆሙ ዓቃብያን እሙንቱ ኢይከብር ፩ እምነ ካልዑ ሃይማኖት አሚን ውእቱ ንጉሥሰ ዓቃቢ ውእቱ ይህ ጽሑፍ የሚአሳየው ለሰው ዋና ጠቃሚው ንጉሡና ሃይማኖቱ እንደሆነ ያመልክታል የሕዝብ ብዛት ያለሃይማኖት ጥቅም የለውም ሕዝቡም ያለንጉሥ የወንድም ንጉሥ ወንድምነቱም በሥጋና በሃይማኖት ልዩነት የሌለው ማለት ነው። ንጉሥ ማለት ሲያያዝ ከመጣው ጉንደ መንግሥት ሥር ያለውን የታወቀውን ነው እንጅ ማንንም ለጊዜው ሥራ ማስተናበር አውቃለሁ ቢልም ያነኑ ወገናችንን እንድንመርጥ የታዘዝንበትን ሙሴ የጻፈው ዳግም ሕግ ፲፯ ፲፫ ወትሠይም ለከ መልአከ ዘኃርየ እግዚአብሔር አምላክከ እምውስተ አኃዊከ ወኢትክል ሠይመ ለከ ብዕሲ ነኪረ እስመ ኢኮነ እሁከ

# ቅ ዓርብ ኅዳር

ከወንድሞችህ እግዚአብሔር የመረጠውን ትሾማለህ አለ። እግዚአብሔር የመረጠው ማለት በሕግ የሚአድር ሕግ የሚጠብቅ ነው። ይህንም ከወንድሞችህ ነው ባዕድ ሰው ግን አትሹም ማለቱ ወንድምህ ሥጋህ ተቆርቋሪህ አይደለምና አለ። እንደዚህ ብሎም ያዘዘን ለኛ ለራሳችን መጠቀሚያ ነው እንጅ ስለመጉጃችን አይደለም ነበር። ግን ፩ድ ፩ድ ሰዎች ከቅንዓት የተነሳ ከወንድም ባዕድ የሚጠቅም እየመሰላቸው ሲታለሉና በዕለት ሆድ ተገዝተው የዘለዓለም ባርነት ወደሚመጣበት ጉድጓድ ዓይናቸውን ጨፍነው ይዘው ለመግባት ወገናቸውን ሲስቡ ይታያሉ ፩ድነት ከሌለ ኃይል አይገኝም ኃይል ከሌለ የወሰን መታፈር አይገኝም ወሰን ካልታፈረ ካልተከበረ ነጻነት አይገኝም። ያለ ነጻነት በባዕድ ቀንበር መግባት ከተፈረደበት ከተፈጸመበት በኋላ ያለ ዋጋ ክብር በሌለው በወራዳ ሥራ አገልጋይ መሆን ማለት ነው የለት ጥቅም ፈላጊው እየበዛ ሲሄዱ ነጻነትን ሳያስጋት አይቀርም። መገመት ቀላል ጉዳይ ጉዳይ አይደለም ሁሉም በየጊዜው እየተነሣ የለት ጥቅሙን ፈላጊ ሲሆን የለት ጥቅሞች ከሩቅ አገር ድረስ በመምጣት ቁጥራቸው እየበዛ ሲሄድ የለት ጥቅም ፈላጊዎችም እንደዚሁ ሲሆኑ ማለት ነው። የሮማ ልዑካን የጻፉ ሁሉ ምንም እውነት ቢሆን ዳግም የበለጠ ሆኖ የሚገኘው (በ፵፫ኛ ገጽ በ፲፺ኛው መሥመር አክሡም የተባለውን አውቆ በታሪክ ጽሑፍ ላይ የጻፈ ሰው አላገኘንም ነገር ግን ምርምርን አውቆ በታሪካችን ሥዕሉንና ቅርጹን ጽፈን እንደምናስረዳው የአክሡም ነገሥታት እንደራሴ ሆኖ የዓረብ ደቡብ አገር አውራጃውን ሁሉ ጠቅልሎ ይገዛ የነበረው ሹም አብርሃ ይባል ነበር ይህ አብርሃ የተባለው እንደራሴ የወለደው ልጁ ግን ስሙ ምንም ትርጉም ባናውቀው ከዓረብ ሳባውያን ስም የተወረሰ ሳይሆን አይቀርም ብለናል ይላል) እንግዴህ የሮማ ል ዑካንን አሳብ በጥብቅ መመርመር ያስፈልጋል አሁን ከላይ የተጻፈውን ታሪክ ቀናውና ወደ ግራ ጠምዘው አዙረው እንዳመጡት ሲዠምሩት የአክሡምን ትርጓሜ እንደሚአውቁ አስመስለው ነው ቀስ እያሉ ግን በደቡብ አገር የነበረው አብርሃ የተባለው የወለደውን ልጅ ስሙን አክሡም ይለው ነበር የሚል ጽሑፍ ስላገኙ ይህን አዙረው አክሡም በአብርሃ ልጅ ስም ትጠራ ዠመር አክሡም የሚባል ስም ከዓረብ ሳባውያን የተወረሰ ሳይሆን አይቀርም ብለው ጻፉ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ የሰጣት አሳቢ እንደዚህ ሆኖ ይገኛል የሮማ ልዑካን እንደሚሉት አብርሃ የተባለው እንደራሴ በዔዛናና በካሌብ ዘመነ መንግሥት ነው

ባጼ ዔዛናና ባጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ስምዋ ማን ነበረ ተብለው ቢጠየቁ ምን ብለው ይመልሳሉ የኢትዮጲስ መናገሻ ስምዋ አክሡም የሆነበትን ምሥጢር ማስረዳት ይቀይና ስምዋ አክሡም ተብላ መጠራት የተጀመረበት ጊዜው መቼ እንደሆነ ማሰብ የለም።

እንግዴህ በሮማ ልዑካን አሳብ ለአክሡም ስም የተቀበለችው ከልደት ክርስቶስ በኋላ መሆኑ ማለት ነው። ስለ አክሡም የሮማ ልዑካንን ጽሑፍ አኮስሼ እኔ መሠረቱን ሳልገልጽ ባልፈው እንደዚያው ፈትፋች መሆኔ ማለት ስለሆነ ከታሪክ መጻሕፍቶች እንዳገኘሁት ይህ አሁን አክሡም ጽዮን ያለችበት ቦታ ከጽላተ ሙሴ መምጣት በፊት ስምዋ ዓፀቦ ነበር ይላሉ። በዚያም ላይ ታላቅ ባሕር ነበር ከዚያም

## ቆ ቀዳም ኅዳር

በኋላ ጽላተ ሙሴ መጥታ ኢትዮጵያ በደረሰች ጊዜ በመላኬ አክሡም ዛሬ ምዝብር ከምትባል ቦታ መቃብረ ኢትዮጲስ ከሚባለው ወደ ቀኑ ዛሬም የምኵራቡ መሠረት ከወደ ምዕራቡ የነበረው የመሠረቱ ግምብ ይገኛል። ስለ ኢትዮጲስ ዘር ኢትዮጲስ ተሮጎለዳጤን አንገየን ጋጌንዩን ሰቤኑን ይክትዮፍኔን እሌኔቁን ፯ ልጆች ይወዳል ማንም አንባቢ ይህን መሠረት መጨበጥ ይገባዋል የአክሡም ጽዮን በየጊዜው ስማቸው ቢለዋወጥም ፳ኤል ከባቢሎን በተመለሱ ጊዜ ከ፲፪ቱ ነገደ እሥራኤል ፲፪ ሰዎች ተመርጠው እንደቆሙ በአክሡምም በየጊዜው በነዚህ በ፺ቱ አባቶች ፺ ፺ አባቶች እየቆሙ ሲመዘገቡ እንደቆዩ ታሪክ ይነግረናል ኢትዮጲስ መሠረት ከምሉ በክፍሉ ይበቃል የሮማ

ልዑካንማ ኢትዮጲስ የሚባለውን ስም ያወጡ ጽርዓውያን በበጥሊሞስ ጊዜ ነው። ተሮጎሎዲጤንም በኋላ የወጣ ስም ነው እያሉ ሲጽፉ ይታያሉ አሁን ወደ ሥሩ ወደ ጽላተ ሙሴ እንመለስ ጽላተ ሙሴ ወደ ኢትዮጵያ የመጣችበት ዘመን ከ፱፻፹፫ ዓ.ም ከክርስቶስ ልደት በፊት ነው በዚያ ጊዜ ዛሬ ምዝብር በሚባለው ቦታ ባረፈች ጊዜ ከላይ ዛሬ ቤተ ክርስቲያኒቱ ያለችበት ታላቅ ባሕር ነበረበት ብየ አመልክቻለሁ በዚያ ባሕር ውስጥ ታላቅ ጋኔል ሌሊት ነበር ይላሉ። በመላእክት ብርሃን ለመመሰል ከዚያ ከባሕሩ ውስጥ ሌሊት እንደ ዕንቍ ያለ ያበራ ነበር ያም ሙብራት ዕንቈሶም እንደ ማለት አክሦም ተባለና እየቈየ አሁን አክሡም ሲባል ደርሰን እኛም አክሦም ብለን ብንጽፍ ሰው ስለማያውቀው በዚሁ በተለመደው አክሡም እያልን እንጽፋለን ያ ጋኔል ግን ጽላተ ሙሴ እዚያ ከገባች በኋላ ያ መብራት ቢፈለግም ስለጠፋ ቅ. ጳውሎስ በቆሮንቶስ ፲፩ ወዝኒ አኮ ለአንክሮ እስመ ለሊሁ ሰይጣን ይትሜሰል ከመ መላእክተ ብርሃን እንደተባለው ሰይጣናዊ መሆኑን ሲመሰክር ያመልኰበት የነበሩ ሰዎች ቢፈልጉትም ሳይገኝ እንደቀረ ታሪክ ይነግረናል። ስለ አክሦም ስም ትርጓሜና ስለ ኢትዮጲስ ልጆች ፮ቱ የአክሡም ባላባቶች መሠረት ከጥንታዊ መጽሐፍ ያገኘሁትን እንዳገኘሁት ገልጬ ላንባቢዎች አቀርባለሁ በ፮ቱ አባቶች የተተኩ ፩ኛ ባግዖ ፪ኛ ነፋሶ ፫ኛ አኮሮ ፬ኛ ኩድኩይ ፭ኛ ፈርህባ ፮ኛ መልኬ አክሡም የአክሡም አባቶች መሬት ዕጣ ፮ት ብቻ ነው መሠረቱም በኢትዮጲስ ልጆጆች ልክ መሆኑንም ማስተዋል የተገባ መሆኑን አሳስባለሁ። እንደዚህ ያለ ሰፊ ታሪክ እያለበት የሮማ ልዑካን አክሡም የሚባለው ስም ከደቡብ የመጣ ነው ብለው መብረቅ የመሰለ ንግግራቸውን በለቀቁት ጊዜ ጀሮውን ያልያዘ የለም። ቀድሞውንስ የጨነቀው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል እንደተባለው ተረት ሆኖ ነው እንጅ እነሱ ብሎ የኢትዮጵያን ታሪክ ጸሐፊ መቸ አገባቡ ነበር። እኔ ፖለቲክ ነው አንባቢ እውቀት ታሪክ ያገኘን መስሎት በታሪክ አስመስሎት ፖለቲካ ያልተለመደ መሆኑን ባለመገንዘብ ስለሆነ አሁን ይህን የፖለቲክ ጽሑፍ ገልጬ ላንባቢዎች ሳቀርበው እነሱ የጻፉትን እየተከተልኩ ነው እንጅ እኔ ከልቤ አስቤ የጨመርኩት ፩ድ ነገር አይገኝም ይኸውም ብዙውን ነገር ይቅር እያልኩ በማለፍ ነው የሮማ ልዑካን ግን በማነኛውም በኩል የማኮስስና የማሰናከል አሳባቸው

ስለማያቋርጥ ማነኛውንም ነገር ካረብ አገር የመጣ ለማድረግ ስለሚጣጣሩ በ፻፶፱ኛ ገጽ የጻፉትን ለንባቢዎች እገልጻለሁ። (፩ኛ የኢትዮጵያ ነገሥታት ስመ ግርማ አድርገው

## በ እሁድ ኅዳር

የሚጠሩበት ዣን ጃንሆይ የተባለ ስም በዓረብ ቋንቋ የተገኘ መላእክት የነበሩት አጋንንት የሚጠሩበት ስም ነው ብለዋል)። አሁን ከዚህ ሁሉ ሐተታ ከማያውቁት ገድል የገቡበት ምክንያት ፩ድ ጫፍ ነገር ነጥቀው ነው እንጅ እውነት ትንሽም ምሳሌነት እንኳ በቂ ነገር አገኙቸው አይደለም ከላይ እንደተጻፈው የሚጠሩበት ስመ ግርማ ዣን ጃንሆይ የተባለ ብለዋል ይህ ንግግር ለሐሰቱ መውሰጃ ታስቦ የተቦተለከው ነው ማለት አሁን የነገሩን ጫፍ የተነጠቀው ዣን የተባለው ንግግር ነው ዣን ሆይ ይባላል ነገሩ በቶሎ ሊገልጽላቸው ሆነ ጃንሆይ እንዳይሉ ያረቦችን ታሪክ ለማምጣት የሚደግፋቸው ዣን የሚባለው ንግግር ሆነና ስለተቸገሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት ዣን ጃንሆይ ተብለው ይጠራሉ ብለው ይጻፉ እንግዴህ ይህ በጽሑፍ ላይ አስፍረውት የሚታየው ፪ት ነው ፩ኛው ዛን ፪ኛው ጃን ነው ከነዚህ ከሁለቱ አማርኛ በጣም የማያውቅ ሰው ዣንሆይ ሲል ይገኝ ይሆናል በጣም በሰለጠነውና በታወቀው አማርኛ ግን ጃንሆይ ይባላል። የሚጠሩት ከሁለቱ ባ፩ዱ ነው እንጅ በ፪ቱ አይጠሩም። ይህም ጃን የተባለ ቋንቋ መሠረቱ ግዕዝ ነው ይህም ጃን ማለት በቀድሞ አባቶች ጊዜ አን ነበረ ዳን ማለት በግዕዝ ፈራጅ ነው ግን ከቀን ብዛት የተነሣ ዳን ይባል የነበረው ዛሬ ባማርኛ ጃን ተባለና ሆይ ሲጨመር ጃን ሆይ የተባለበት ምክንያቱ ይህ ነው። ይህንም የመሰሉ የስም መለወጥ የሚገኝባቸው ብዙ ነገሮች አሉን ፩ኛ በጥንታዊ ጽሑፍ ሴዋ ሲል ይገኛል ዛሬ ሸዋ ይባላል ፪ኛ በጥንታዊ ጽሑፍ ጐዛም ሲል ይገኛል ዛሬ ጐዣም ጐጃም ይባላል። ፫ኛ በጥንታዊ ጽሑፍ ሲረ ሲል ይገኛል። ዛሬ ሺሬ ይባላል ፬ኛ በጥንታዊው ጽሑፍ

መቅደሶ ሲል የሚገኘው ዛሬ መቅድሾ ይባላል ይህም እንደዚሁ ባማርኛ ፊደል ቤቱን ሳይለቅ የተለወጠ ማለት የተሻሻለ ነው እንጅ ሌላ ነገር አይደለም። የሮማ ልዑካን ግን ጥልቅ መሠረት ያለው መሆኑን ሳይገነዘቡ ያልታረመ ሜዳዊ ንግግራቸውን ለጥፈውት ይገኛል "ዓረቦች ጋኔን ሲሉ ዠን ይላሉ" ብለዋል እነሱ ዓረቦች ከአጋንንት ጋር በሚተዋወቁበት ቢነጋገሩ በዚህ መካከል እኛን ምን አገባን ደግሞስ በቃል መለዋወጥ የሚተረጐም ብዙ ነገር አለ። ይህን የነገር ጫፍ ቄንጠረው ነው። "ሰማያዊ ንጉሥ ሰውንና መላእክትን አጋንንትን ጨምሮ እንደሚገዛ ምድራዊ ንጉሥም ሰውንና አጋንንትን በግርማ መንግሥቱ ቀጥቆ ይገዛል እንደማለት ጥንትውያን የሆኑ የኢትዮጵያ ነገሥታት አጋንንትን ጨምረን እንገዛለን ሲሉ ዣን ጃንሆይ በሉት በሚባል ስመ ግርማ መጠራት ዠመሩ) ይላል። እንግዴህ ይህን የማሾፍ ንግግር መመልከት ነው የኢትዮጵያ ነገሥታት የሰማያዊ ነገሥታት ተወዳዳሪ ሆነው አጋንንትን ለመግዛት የሚችሉ ሆነው ቢሆንማ ብዙዎች አጋንንት በሀገራቸው ላይ ገብተው በብዙ በሚቆጠሩ ዘመኖች ሕዝቦቻቸውን እርስ በርሳቸው እያፋጁ የሕዝባቸውን ቁጥር የሚቀንሱባቸውን በረቂቅ ሥራ ውስጥ ለውስጥ የሚጐዱ ሥራዎች የሚአመጡባቸውን ሕዝባቸውን ጾም እንዲገድፉ በዓል እንንዲሺሩ ወንድሞቻቸውን እንዲገድሉ እያደረጉ አገራቸውን ባዶ የሚአደርጉት አጋንንትን ሁሉ ልቅም አድርገው ከጠለቀ ጉርጓድ በከተቱና ኢትዮጵያ እንደ ጥንቷ በሰላም ተስማምታ እግዚአብሔር የከፈላትን ርስት ሀብቷን እየተመገበች ፈጣሪዋን እያመሰገነች ለመኖር በቻለች ነበር። የኢትዮጵያ ነገሥታት አጋንንት የሚገዙና የሚአዙ ሆኖ ቢሆን ፩ድ ጋኔን እንኳ

# ቡ ሰኑይ ኅዳር

ከባሕር ወጥቶ ፩ድ ጫማ መሬት ሊረግጥ ፈቃዳቸው አልነበረም። የሮማ ልዑካን የምፀት ንግግር መመልከት ነው በማነኛውም ረቂቅ ተንኮል ይለፋሉ የደከማሉ እንግዴህ መጨረሻው ምን ይሆን ልዑል

እግዚአብሔርስ በከፈላቸው አገራቸው ላይ ይህን የመሰለ እርስ በርስ የሚአፋጅ ረቂቅ ቀምበር ለኢትዮጵያ ሕዝቦች አሸከሚቸው የሚኖረው እስከ መቼ ይሆን ልዑል እግዚአብሔር በእውነት በገዛ አገራቸው ላይ በግፍ ያላቁትን ሕዝቦች ደም ከውኃ ቁጥረሽዋል ይሆንን ልዑል እግዚአብሔር ከግራኝ ሙሐመድ መነሳት ዠምሮ የተቃጠሉትን አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለው እንዲቀሩ ፈቃድህ ነው በማለት እናስብ ይሆንን በኢትዮጵያ ሕዝብ የደረሰውን ነገር ስመለከተው ባለፉት ዘመኖች የነበረውን የታሪክ መጻሕፍቶችን ስመለከት ያለቁትን ሕዝቦች ብዛት ስገምተው ልዑል እግዚአብሔር እንደዚህ አድርጎ የጨከነበት ምን ይሆን የሮማ ልዑካን ይህን መጽሐፍ ያሳተሙት ፩ኛው አሳባቸው የኢትዮጵያን መሠረት ለማጥፊያ ፪ኛው የሮማ ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ላይ ተስፋፍታ ክብርዋ የሚታወቅበትን ለመግለጽ ፫ኛ ኢጣልያኖች በሚሲዮኖች መሪነት ገብተው በጠረፍ ገሚገኙ ባላባቶችን በገንዘብ ገዛን የሚሉትን ሕገ ወጥና የሥርቆት ሥራ ሕጋዊ ሥራ ለማስመሰል ስብከታቸውን ለመጭው ትውልድ የታሪክ ሥራ ለማስመሰል ስብከታቸውን ለመጭው ትውልድ የታሪክ ዓምድ አሲዞ ለማቆየት ስለማደራጀት ነው። "በ፻፸፩ኛ ገጽ ባ፲ኛ መሥመር በኤርትራ አውራጃ ሐም የተባለው አገር ላይ በ፰፻ ዓ.ም ግድም አባ መጣዕ ሊባኖስ የተከሉት ገዳም አለ ይላል"። ባ፰፻ ዓ. ምሕረት አባ ሊባኖስ መጣዕ በኢትዮጵያ ውስጥ የለም ሐሰት ነው። ፩ኛ የደብረ ዳሞን አባ ዘሚካኤል አረጋዊ የተከለው። ተብሏል። በብዙ ድካምና ችግር ቤተ ክርስቲያን ከገደሉ ግርጌ እንጨቱን አሰብቦ ለመውጫው የሚሆን መሠላል በዚያ አያስወጣ አሰርቶ ቦታውንም እንዲከበር እርስትና ጉልት ሰጥቶ የገደመው ንጉሠ ነገሥት አጼ ገብረ መስቀል በምን ምክንያት የንጉሠ ነገሥቱ ስም ስለገዳሙ ስሙ አይወራም ግን እናንተ የኢትዮጵያን ነገሥታት ስም ለማጥፋት የመጣችሁ መሆናችሁን ዘንግቸ ስለምን የንጉሠ ነገሥቱ ስም አይጠራም በማለቴ ይቅርታ ከላይ ከተጻፉት በ፫ኛው ቁጥር ክፍል ኢጣልያኖች በሚሲዮኖቻቸው መሪነት ያገኙትን ከጠረፍ ባላባቶች ላይ ሚሲዮኖች በሥርቆት ተዋውለው በአሰብና በምጽዋ ወደቦች ላይ የኢጣልያን የጦር ሠራዊት አምጥተው አሥፍረው የኢትዮጵያ ጀግኖች

ንጹሕ ደም ያስፈሰሱበትን የቅሚያውንና የሥርቆቱን ሥራ ሕጋዊ አስመስሎ ለመጭው ትውልድ የታሪክ ዓምድ አሲዞ ለማስተላለፍ በ፻፹፫ኛ ገጽ "በ፲፮ኛው መሥመር ኢጣልያ ወደ ኢትዮጵያ መግባት የኢጣልያ መርከበኞች በ፲፰፻፷፱ ዓ.ም የመርከብ ማረፊያ የሚሆን ወደብ ስጠን ብለው የአሰብና የራዔታ ባላባቶች ከሆኑት ሡልጣን ኢብራሂምና ሡልጣን ሐሰን ከተባሉት ጋራ ተስማምተው ትንሽ መሬት በገንዘብ ገዙ ይላል"። ይኸውና የሮማ ልዑካን ሥራ ይህ ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ ሲአፋጁ ኑረው የሕዝቡን ማነስና የጀግኖችን መጨረስ ባወቁ ጊዜ የሮማ ጦር መጥቶ የሚሰፍርበትን ቦታ ለማደራጀት ሮማ ላይ ለዚሁ ሥራ ማከናወኛ ከቆመው ማኅበር ቤት ያታልሉበትን ሥራ እንደኑዛዜ ያለ ታሪክ በትንሽ ገንዘብ መሬት ግዙ ብለው ጻፉ። እኔስ ይህ ጽሑፍ እንደኑዛዜ ይመለኛል ኑዛዜም እንዳልለው ከሥራቸው አልተመለሱም



ሡልጣን ኢብራሂም አሰብን ለሮማ ልውካን ሸጥኩላችሁ አለ የሚባለው ።



የአዳል ፡ ባላባት ፡ ከሮማ ፡ ሚሲዮኖች ፡ ጋር ፡ የመከረ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ወደቦች ፡
እንሸጣለን ፡ ሲል ፡ የነበረ ፡ የራሄታ ፡ ሡልጣን ፡ ሐሰን ፡ መሐመድ ።

## ቢ ሠሉስ ኅዳር

አሁን እሺ እንደነሱም ይሁን መሬቱን ሲገዙ ዳኛ ማነው እዚያ የነበር ያለዳኛ ሚሲዮኖች ብቻ ናቸው ሲባል ያው ሥርቆቱ ማለት ነው የሮማ ልዑካን ጉዳይ እስከዚህ ነው "፪ኛ በሽ፰፻፹፪ በፈረንጅ ቁጥር ነው። የኢጣልያ መንግሥት የአሰብን መሬት ከመርከብ ኩባንያዎች ገዛ። በፊት ገንዘብ ሰጥተው የቆዩ ሚሲዮኖቹ ነበሩ በኋላ ግን መሬቱን የጦር ሠራዊት መሪ የሆነው ሲረከብ ከፍ ያለ ገንዘብና ምስጋና የሮማ መንግሥት ከፈላቸው መንፈሳዊያኑ ዋጋቸውን አገኙ። አሁን በነሱ ልብ የዚህ ሁሉ የፖለቲክ ጽሑፍ አይታወቅም "፫ኛ ቀጥለውም በየካቲት ፳ት ቀን በሽ፰፻፹፭ ዓ.ም በፈረ ቁጥር ኢጣልያኖች ምጽዋንና

በይሉልን ሐርጊጎንና ዙላን ጥቂት በጥቂት ሲሉ ግን እየቆየ ከአረፋይሌ እስከ ሠሐጢ ድረስ ያእልውን መሬት ያዙ" ይኸውና በሮማ ልዑካን መሪነት ኢጣልያ የጦር ሠራዊቱን ላከና ከላይ የተቆጠሩትን አገሮች ሁሉ መያዝ ዠመረ። ከዚያ ዘመን በኢትዮጵያ አቆጣጠር አጼ ዮሐንስ በሽ፰፻፷፫ ዓ.ም ነግሠው ነበር በዘመናቸው ፩ድ ሚሲዮናዊ እንዳይገባ ክልክል ነበር ስለዚህ የሮማ ልዑካን በሐሰብ በኩል እየሾለኩ ወደ አጼ ምኒልክ እየመጡ በአንኮበር እየተቀመጡ ብዙ ሰዎች ይሰብኩ ነበር ሌላው ሐተታ ከላይ ተጽፎ ይገኛል። ግን በዚያ ጊዜ ጊዜ ሲአስተምሩ ብዙ ሊቃውንቶች ስብከው ሃይማኖታቸውን አስለውጠዋቸው ሲቆዩ አጼ ዮሐንስ በሽ፰፻፸ ዓ.ም ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ በሸዋ የነበሩ ኦርቶዶክሳውያን ሊቃውንቶችን ከሰው አጼ ዮሐንስ ላይ አቀረቧቸውና በመምህር አካለ ወልድ አማካይነት ተከራክረው ሌሎቹ ሲቀጡ አለቃ ክፍሌ የተባሉት አምልጠው ሄደው በሮማ ልዑካን ዘንድ ሲረዱ ኖረው አለቃ ኪዳነ ወልድን አስተምረዋል። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የኢትዮጵያ ፊደል በሀ የሚዠምረው ብለው የሮማ ልዑካንን መሠረት በማድረግ በአ እየዠመሩ እንደውጭ አገር ፊደል አድርገው የኢትዮጵያን መሠረት የሚአፈርስና የሚአረክስ የዘለፋ ቃል እየተጨመረ የተጻፈ ይልቁንም ከመቅደሙ ላይ ኢትዮጵያን የሚያቃልል ሐተታ ያለበት ጽሑፍ ባቶ ከበደ ሚካኤል አማካይነት ባቶ ደስታ እጅ በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ሲታተም ይገኛል የኢትዮጵያን መሠረት የሚአናውጽ ስለሆነ ነው እኔ የምለው ዛሬ ያለው የቃል መገኛ የተባለው ሰዋሰው መጽሐፍ ሰፊ ነው። ሌላ የቃል ማውጫ አይጨመር ማለቴ አይደለም። የፊደሎች አገባብ እንደ ጥንቱ ይሁን እንጅ ስለምን ጥንታዊው ይለወጣል ነው የምለው። በሮማውያን ሚሲዮን የተማሩ ሰዎች ሁሉ የግዕዙ ፊደል ሥነ ሥርዓት ለማፍረስ ይፈልጋሉ። የግዕዝ ፊደል ሥነ ሥርዓት ካልተጠበቀ የኢትዮጵያ ነጻነት ምልክት ጠፋ ማለት ነው። የኢትዮጵያን ነጻነት ለመቃወም የሮማ ልዑካን ብዙ ጊዜ የደከሙበት ነው። አሁን በአባ ጋስፓሪን የተገለጸው እነሱ ዋና አሳባቸው ግዕዝን ለማጥፋት ብቻ ነው። የነሱን ውስጠ ተንኮል ባለመረዳት የኛ ሰዎችም መልካም ነገር ያገኙን እየመሰላቸው በጭራሽ የነሱን እየተከተሉ ጽፈዋል (አባ ገብረ ኢየሱስ ኃይሉም እንዲሁ ስለ ግዕዝ መሠረት ብለው ባሳተሙት መጽሐፍ በጥንታውያንኑ ፊደሎች አርዕስት ይላል)። እንደዚህ ብለው የጻፉት ባ፩ድ ጐን ጥንታዊውን ግዕዝ ፊደል ደግሞ ባንድ ጐን አዲሱን ግዕዝ ማለት እየተሻሻለ የመጣውን ነው ሲጽፉም በአ ዠምረው በፐ

## ባ ረቡዕ ኅዳር

ጨርሰውታል። ይህም በአ መዠመራቸው እንደ እብራውያን በፐ መጨረሳቸው እንደ ግዕዙ ማለት ነው። ስለዚህ የግዕዙንም የእብራይስጡንም የፊደል ቁጥር አጥፍተውታል። ስለዚህ መሠረት መጠበቅ የተገባ ሥራችን ስለሆነ የዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ሁሉ የእብራውያንን ፊደልና የግዕዝ ፊደል ቁጥር ለይተው ጽፈው ይገኛል። ደግሞ ስለ ግዕዝ በጻፉት "በ፳፱ነኛ ገጽ ባ፳ተኛው መስመር በታተመው መጽሐፍ እንደምናየው የግዕዝ ፊደሎች ከሳባዊ ፊደል መሆናቸው ግልጥ ነው በግዕዝ ቁጥራቸው ፳፯ ሲሆን በሳባ ፳፱ ነው የሳባ አጻጻፍ ከቀኝ ወደ ግራው አካሄዱ ስለምን ጥንታዊ መሆኑን

ሁሉም ግዕዝ ነው አ ወ የ በቀር ሌሎቹ አስደማጮች ምልክቶች የሉበትም ሳባዊ አ በ ገ ደ ብሎ የሚዠመር አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ግዕዝም አማርኛም እንዲህ ብሎ ይዠምር ብለውታል ከጥንትም ግዕዝ እንዲህ ኑሮ እንደነበረ ጥርጥር የለበትም ምክንያቱም የምሥራቅና የምዕራብ እንደዚህ ስለሆነ አ የአፍ መክፈቻ ተብሎ ሲዠመር እንደህ እያደረጉ ጽፈው ይገኝል።) ይህ እንደዚያ ያለው አስተያየት የሳባ ፊደል የሚሉ ስም ለጥንታዊው ግዕዝ ፊደል መስጠት በሁሉ ዘንድ የተጠና ሆኖ ይገኛል የዚህ ነገር ምንጩ የሮማ ልዑካን ናቸው ምክንያቱም ጥንታዊውን ፊደል የኢትዮጵያ ወጣቶች እየተከተሉ ያጠኑት እንደሆነ የኢትዮጵያን መሠረት

ጽሑፍ ግዛቷ ከነበሩት አገሮች ላይ የሚገኙትን ጽሑፎች እንዳያውቁ እንዳይራራቁ በማለት አስበው የፈጠሩት ፖለቲክ ነው እንጅ ያረቦችና የኢትዮጵያ ፊደል ጥንታውያንና ጥንታዊውን ብናስተያየው የተለየ ነው። እነሱ እንደዚህ እየፈጠሩ የሚሰብኩት ጥንታዊውን ፊደል መርምሮ የሚለየው የለም በማለት ነው እንጅ እርግጠኛ ነገር አግኝተው አይደለም “በ፻፵፬ኛ ገጽ ኢትዮጵያውያና እና ዓረቦች ወዳጅነትና ግንኙነት እንደነበራቸው የሚገልጽ ብዙ የአገርና የሰው ስም ማስረጃ አግኝተናል። ይኸውም ዓረቦች የኢትዮጵያ ተገዥዎችና ዜጎች ከመሆናቸው የተነሳ ብዙ ወዳጅነት ከያዙ ዘንድ ግን የዓረቦች ስም በልጅዋ በምኒልክና በራስዋ በመንግሥተ ዓዜብ ስም ይታወቃል)። አሁን ከላይ ዓረቦች የኢትዮጵያ ተገዥዎችና ዜጎች እንደነበሩ መስክረው የጻፉ ንግሥተ ሳባን ኢትዮጵያዊ አይደለችም እንደማለት በስም ትርጓሜ ጠልፈን ወደ ዓረቦች እናዞራለን ብለው የማሳሰባቸውን መመልከት ያስፈልጋል። የዓረብ አገር ከጥንት ዠምሮ እስከ እስላሞች መንግሥት መቋቋም ድረስ በኢትዮጵያ መንግሥት እጅ ለመሆኑ ብዙ ማስረጃ አለ። አሁን የሮማ ልኡካን የሚመኙት ደግሞ ያረቦች ገዥነት ቀረና በተገዥነታቸው በኩል መሆኑን መገንዘብ ነው። የግዛቱም ዘመን ከንግሥተ ሳባ ዘመን አስቀድሞ መሆኑን እንዳመኑ መገንዘብ ለአንባቢ ተግባሩ ነው ገና ከንግሥተ ሳባ በፊት ካልሆኑ ንግሥተ ሳባ ወደ ሰሎሞን ስትሄድ በዓረብ አገር በኩል አድርጋ ወደ ኢየሩሳሌም ባልወረደችም ነበር። “የምኒልክ ስም ከዓረቦች የተገኘ መሆኑን ከዚህ ቀደም ጽፈን አስረድተናል ገጽ ፵፫ ባ፲፬ኛው መሥመር ማስታወቂያ ንግሥተ ሳባና የንጉሥ ሰሎሞን ልጅ በክብረ ነገሥት ላይ ስሙ በይነ ለሐኪም ተብሏል ይላል”። እዚህ ላይ የተጻፈው ዣን ተብሎ እንደተጻፈው ማለት ያለ ነው እንጅ መደበኛው ስሙ ብዙዎች መጻሕፍቶች እንደሚስማሙበት ዋና ስሙ እብነ መልክ ነው። ወደ ትርጓሜ ከመሄድ። አስቀድሞ ስሙን ጠንቅቆ መያዝ ይገባል። በዚያ ጊዜ የሚተረጐምበትን ምሥጢር የተርጓሜ ለመሆን ችሎታችሁ አይደለም።

## ቤ ኃሙስ

## ፱ኛ ክፍል ታኅሣሥ

## ምዕራፍ ፬

(ከዚህ ምርመራ ውጭ እንጅ ከውስጥ ለመግባት የናንተ እውቀት ሊደርስበት አይችልም ለንግሥተ ሳባና ለልጅዋ ለእብነ መለከ ስም ራዋ የምትነገር መሆንዋን ስለንግሥተ ሳባ የተጻፈውን ነገሥት ፱ ፩ ወንግሥተ ሳብዓ ስምዓት ዜናሁ ለሰሎሞን ወመጽአት ከመ ታመሮ ለሰሎሞን በአስተማስሎ የተባለውን መመልከት ነው ሰሎሞንን የሚአኽል ጥበባት ሁሉ የተገለጠበትን ንጉሥ በምሥጢር ትርጓሜ ለመፈታተን ሄደች የሚለው ምክንያቱ ስለምን ይሆን “ማከዳ ማለትም ትርጉሙ ዓረቢኛ ይህችን የመሰለች ማን አለ ማለት ነው ይላል)። (በ፵፫ኛ ገጽ ባ፲፮ኛው መሥመር ምኒልክ የተባለው ስም የመጣለትን መመርመር የተገባ ነው። ሁሉ በኅብረት ምኒልክ መኑ ይልቅህ ብለው ፪ት ላይ ይከፍሉታል።

እንደዚህም ማለት እንደርሱ ያለ ትልቅ ማን አለ ማለት ነው። ይሁን እንጅ ይህ ሥረ መሠረት እውነት ሊሆን አይችልም። ስለምን እንደዚህ ሩቅ በነበሩበት ጊዜዎች አማርኛ አይነገርም ነበር"። እንግዴህ በማስተዋል መመልከት ላንባቢ ዋና ሥራ ነው ከላይ ማከዳ ማለት ባረቢኛ ይህች የመሰለ ማን አለ ተብሎ ባማርኛ ተተረጐመ። በኛ በኩል ከላይ የተጻፈው እንደርሱ ያለ ማን አለ ማለት ነው ተብሎ ቢተረጐም ይህ አማርኛ በዚያን ጊዜ አልነበረምና እውነት ሊሆን አይችልም ተብሎ ተነቀፈ ይህ ሁሉ የመጨነቅ ጠባ የነ እንጅ ሁለቱም አማርኛ ስለሆኑ ፩ዱን አማርኛ መቀበል ፩ዱን አማርኛ የለም ማለት ከችግር የተነሳ ነው እንዲሁስ በግምት ቢታሰብ የማን ዜጋ ለማን ንጉሥ ልጅና ለንጉሡ ስም አወጣ ሠየመ ተብሎ የተጻፈ ነገር ከዓለም መዝገብ ገጽ የሚገኝ ይሆንን ይህን ሁሉ ሐሰት ከማቀናወጥ አፍን ማሳረፍ የተሻለ አለነበረም ይሆንን በ፻፵፫ኛ ገጽ በ፳፩ኛው መሥመር በአሥመራ አቅራቢያ ባለው ምድረ ጽዮን በሚባለው ሥፍራ ብዙ ዋሻ

ያለው ፩ድ ትልቅ የማዕድን ጉድጓድ ተገኝቷል ይህ ጉድጓድ ያለ ጥርጥር በቀድሞቹ ግብጻውያን ይልቁንም በበጅያዎች የተቆፈረ ነው እንደዚህ ያለ የወርቅ ጉርጓድ ከኢትዮጵያ ሁሉ ተገኝቷል ይላል) መቸም የሚቀጥሉት ነገር አያጡም አሁን ደግሞ ከላይ እንደተጻፈው ብዙ የማዕድን ጉርጓዶች አሉ የቆፈርዋቸው ግብጻውያን እስከ ደጋይቱ ኢትዮጵያ ምን ሲሠሩ መጡ ታሪክ ጸሐፊዎች ሁሉ ያውም ከግብጽ ሊቃውንቶች ብዙዎች የዓለምን ታሪክ ሁሉ ጽፈውት ይገኛል ፩ድ የግብጽ ንጉሥ ኢትዮጵያን እላይ ድረስ ወጥቶ ገዛ የሚባል ጽሑፍ አላነበብኩም ባይሆን ትንንሽ ቀኖች ኖብያን የሚል ይገኝ ይሆናል እንጅ የኢትዮጵያን ነገሥታት ስንኳን ሀገራቸውን ሲያስወስዱና እነሱ አልፈው ለሌላ ረዳት እየሆኑ ይረዱ እንደነበረ ታሪክ ይነግረናል። የሮማ ልውካን የሚፈጥሩት ነገር ስለሚያጡ እንዲሁ አፋቸው ያሰበውን ሁሉ ሲዘረዝሩ ይገኛሉ። ደግሞ በጅያዎች የሚሉ ቀጥለውበታል መቸም (በ፻፳፯ኛ ገጽ ባ፲ኛው መሥመር ካጼ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት በፊት ካቶሊካውያን የሆኑ ል ዑካን በኢትዮጵያ ገብተው ነበር። በኢትዮጵያና በሮማ ሊቃነ ጳጳሳት በአውሮፓ ካቶሊካውያን ነገሥታትም ማኻል ብዙ ጊዜ በመቀራረባቸው ምክንያት ግልጥ የሆነ ጥቅም ተገኝቶበታል። ይላል" የተገኘው ጥቅም ምን ይሆን የሮማ ልዑካን ያመጡት ጥቅም የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ ማፋጀትና ማቂራረጥ ነገር እየለቀሙ መርዋሯጥ ነው እንጅ ፩ ፍሬ ነገር ለሕዝብና ለመንግሥት ጥቅምና ልማት የሚሆን ነገር ወረቀት ከማመላለስ በቀር ፩ድ የተደረገ ጥቅም የለም። ላጼ ሚናስም ወረቀት ከመስበክ በቀር ምን ተደረገላቸው

## ብ ዓርብ ታኅሣሥ

ለተከታዩም። ላጼ ያዕቆብ በነሱ ምክንያት መኳንንቱና ሊቃውንቱ መከረው እናርያ ወስደው አጼ ዘድንግል በሮማ ልዑካን ስብከት እስከ መግደል ደረሰ ግድያውም በጦርነት ነው አጼ ሱስንዮስም እንደዚሁ እየሰበኩ ከካቶሊክ ሃይማኖት የተቀበልክ እንደሆነ ስንኳን መሳሪያ እንዲያአውም ነፍጥ የሚሠሩ ብልሃተኞች እናመጣለን እያሉ ምለውና ተገዝተው የሄዱቱ እዚያው እየቀለዱ ሲቀሩ እዚህ ሃይማኖቱ አስለውጠው። ደግሞ ምክንያት እየፈጠሩ በገዳማቱ ሁሉ እኛ ካልሾምንበት እያሉ ሊቃውንቱን እነርሱ እራሳቸው ባለሙበት ሆነው እያሠሩና እየደበደቡ እየገደሉ እነሱ የጨረሷቸው ሊቃውንትና መነኮሳት ቀሳውስት ከ፷ሽ ይበልጣሉ። በዚህ ምክንያት በሙሉ ኢትዮጵያ ላይ ከፍ ያለ ሁከትና ጦርነት ተነሥቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በርሱ ከመተላለቁ የማይመለስ ቢሆንና የሮማ ልዑካን ስብከትም ለማታለል እርግጥ ለራሱ ለመንግሥቱ መስፋፊያ የሚሆን ፩ድ ፍሬ ያለው ነገር በማጣቱ እንደገና የጠላት መሆኑ ስለገባው አዝኖና ተጸጽቶ ያጼ ሠርፀ ድንግል ልጅ ወይዘሮ ኢጋያ ከዙዋይ ውስጥ ያጼ ልብነ ድንግል ራዕይን መጽሐፍ ቀስዳ አንብባለት ነገሩ በጣም ከገባው በኋላ በሠራው ሥራ በጣም ተጸጽቶ ይልቁንም በጦርነቱ የልጁ ባል ራስ ዮልዮስና ወንድሙ ራስ ብዕለ ክርስቶስ ሃይማኖታችንን አንክድም ብለው ብዙዎች ዘመዶቹ ስለአወቁበት ከፍ ያለ ንስሐ እንዳደረገ። ወደዚያው መላሱን ታመመ መናገር ከለከለው ልጁ ፋሲለደስ ከየገዳማቱ መነኰሳቱን እየፈለገ አባቴ ወደ

ጥንት ሃይማኖቱ ተመልሷልና እያለ መነኲሳቱን ሰብስቦ ጸሎት አድርሰውለት ከደዌው ከተፈወሰ በኋላ። ለልጁ የሮማውያንን ረቂቅ ተንኮል ያደረጉበትን ሁሉ ምሥጢር አስጠንቶ ኢትዮጵያ ላይ እነሱን አስገብቶ ከነሱ ሲወዳጅ የተገኘ ሁሉ አብሮ እንዲሞት ብሎ መንግሥቱንና የሮማ ልዑካንን በቀል ስላወረሰው። ልጁ ፋሲለደስ በኢትዮጵያ ላይ በነገሠ ጊዜ ፋሲል ነገሠ ሃይማኖት ተመለሰ ብሎ ዓዋጁን አስነግሮ ባባቱ ጊዜ ከየገዳማቱና ከየአድባራቱ በየበረሃው ተሰደው የነበሩትን ሁሉ በዚህ ዓዋጅ አሰብስቦ አክሡም ጽዮንም ከአክሡም ተሰዳ ቡር ወደሚባለው አገር ድግሳ በምትባል ቦታ ፲፪ ዓመት ቆይታለች ከአክሡም የወጣችበት በ፯ሺ፮፻፲፬ ከፍጥረተ ዓለም ኅዳር ፯ ቀን

ተቀብለው በጽኑዕ ቦታ አስቀምጠው አቈይተው ፋሲል ነገሠ በመዠመሪያው ዓመት ሐምሌ ፳፯ በዕለተ እሑድ አክሡም ተመልሳ ገብታለች በአክሡም ቤተ መቅደስ ባለ ሕግ ቄስ ገብቶ መቀደስ የተዠመረ ከዚያ ወዲህ መሆኑ ይተረካል። ምክንያቱም ባጼ ሱስንዮስ ጊዜ ፓድሮች ካቶሊካውያን አስቀድመው መነኲሳቱን እየፈለጉ ሥቃይ እያሳዩ በፈጇቸው ጊዜ ግማሾቹ በሞት ግማሾቹ ስደት ስለተበታተኑ ወደ ስደቱ ይዘዋት የሸሹ ሕጋውያን ስለሆኑ ከዚያ ወዲህ መነኰሴም ባለሕግም እንደተገኘ ሆኖ ይገኛል የአክሡም ጽዮን ዕቃ በየባላባቱ እንደተመራ የቀረው በዚያ ጊዜ ነው ባ፩ድ ባላባት እጅ የተሰጠ ጽሑፍ እንደሚለው "፻፶፬ ወርቅ ጻሕል የጽዋው የእርፈ መስቀሉ የኩስኩስቱ የመስቀሉ የጽንሐው የወንጌሉ የዚህ ሁሉ ወርቅ ብቻ ቁጥር ቀርቶ የጻሕሉ ቁጥር ከሽ ይበልጣል። የኢትዮጵያ ሀብት ከፍታው እስከዚህ እንደነበረ ያስረዳል። በዚያ ጊዜ እንደወጣ የቀረው የአክሡም ጽዮን ሀብት ይህን ያህላል ተብሎ ሊገመት አይቻልም ያ ሁሉ እንደተመራ በየባላቱ እዚያው ቀረ ይላሉ ምክንያቱም በሃይማኖት ምክንያት የተነሳው ጦርነት

# ቦ ቀዳም ታኅሣሥ

በቶሎ ያልቆመ በመሆኑ ማነኛውም ነገር ስለተደባለቀ ነው ከግራኝ ጊዜ የበለጠ ጉዳት ነው በአክሡምና በላሊበላ በየገዳማቱ የደረሰው መከራ ለመጻፍ ይህ ዓምድ አይችለውም በዚህ ምክንያት እርስ በርሱ የተላለቀውን ሕዝብ ቁጥር በጽሑፍ የሚገኘው ከ፪ሺ በላይ ነው እሱም ቀርቶ ቁጥሩን ፶ሺ ብለው የ፶ሺ ሕዝብ ደም ቀላል ነገር ይሆንን። ይህን ያህል ሐተታ ያለበትን ነገር ታሪክ እንደ ቀላል ነገር ወደ ጐን አሉትና ባውሮፓ ካቶሊካውያን ነገሥታት ማኸል ብዙ መልክቶች መለላክና ደብዳቤዎች መጻጻፍ በመቀራረባቸው ምክንያት ግልጥ የሆነ ጥቅም ተገኝተውበታል ተብሎ የተጻፈው ንግግር በጣም አስደናቂ ነው "በ፻፷፮ኛው ገጽ ካ፲፫ኛው መሥመር። ኢትዮጵያ የገቡት ልዑካኖችም ኢትዮጵያ ከውጭ አገሮች ባላት ግንኙነትና ታሪክ ላይ ብዙ መጻሕፍት ጽፈዋል። ይላል) እነሱ ጽፈዋል የሚሉት ንግግር ተንኮላቸው። የኢትዮጵያን ክብር እያጎደሉና እየቀነሱ ለዓለም ታሪክ ጸሐፊዎች ይስተላለፉትን የሐሰት ጽሑፋቸውን ነው። የኢትዮጵያን ፊደል ግዕዝን የሳባውያን ያረቦች ፊደል ነው እያሉ እንዲያውም ዓረቦች ኢትዮጵያን አቀኑ እያሉ ጥንታዊውን የግዕዝ ፊደል በረቂቅ ተንኮል ከቀኝ ወደ ግራ እጅ እያዞሩ እየጻፉ የሚሠሩትን ረቂቅ ተንኮል ከሙያ ቆጥረውት ታሪክ ጽፈውታል እየተባለ ይፎክራል መልካም ፋከራ ነው ስብከቱም ደምቋል ጽሑፉም ታውቋል። (፪ኛ ኢትዮጵያ በዚያ ጊዜ በውጭ አገር በጣም ታውቃለች ከዚያ ዘመን በፊት የሮሜ ሊቃነ ጳጳሳት ለኢትዮጵያውያን ብለው ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የቅዱስ እስጢፋኖስን ቤተ ክርስቲያን አሠርተው ነበር። ይላል" ለኢትዮጵያ መታወቂያ ይሆናል ተብሎ በሮሜ ሊቀ ጳጳሳት ፈቃድና አሳብ በቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የእስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን የተሠራውን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አውቀዋለሁ የኢትዮጵያን ቋንቋ ለመማርና ሀገረ ልማዱን ለመመመር ችሎታ የሚገኝበትን ትምርት ለማጥዒያ የፖለቲክ ማካሄጃ የሠራችሁት ቤት ነው። ከኢትዮጵያ ፩ድ ፩ድ ሆድ ወዳድ የሆኑት ሰዎች እያባበላችሁ እየወሰዳችሁ እነዚያ ሲአስተምሩአችሁ ወደ ኢትዮጵያ እየመጣችሁ መሳሪያ አመጣልሃለሁ ደብዳቤ ብትሰጠኝ ከሮማ ንጉሥ መልስ አመጣልሃለሁ እያላችሁ ለመቅጠፍና ለመቦልተክ እንዲመቻችሁ ብላችሁ ያቆማችሁት ነው እንጅ ለኢትዮጵያ ጥቅም አሳባችሁ ይሆንን እነሱ እዚያ ሆነው

ባያስተምርዋችሁ ወደ ኢትዮጵያ መጥታችሁ ወደ ንጉሥ ገብታችሁ ለመቦልተክ በፈለጋችሁ ጊዜ ደብዳቤ ጽፋችሁ ብትሰጡ ማን ያንብላችሁ ማንስ ያነጋግራችሁ ነበር ይሆን እነሱ ባስተማርዋችሁ ጽሑፍ ጽፋችሁ ባታቀርቡ አማርኛስ ባትነጋገሩ እንደምን ትሆኑ ነበር ደግሞስ የኢትዮጵያው ንጉሥ ወደ ሮማው ንጉሥ ሲል በሥውር ማን ይጽፈው ነበር። ደግሞስ እነሱ ባያስተምሩአቸው በጽሑፍ የሚገኘውን ምሥጢር ለማወቅ

በየሀገሩ ከሕዝቡ ላይ የሚገኘውን ወሬ በምን ታውቁት ነበር። ደግሞስ ከሕዝቡ ጋር እንደ ልብ እየተነጋገሩ አሳቡን ለመውሰድ እንደምን ይሆንላችሁ ነበር ቤተ ክርስቲያን ብላችሁ ያቆማችሁት ልክ የፖለቲክ ማጣሪያ መሆኑ የታወቀ ነው። ስለዚህ የሠራችሁት ለራሳችሁ ጥቅም መሆኑ እወቁት "፫ኛ ከዚያም በኋላ በየቦታው ለኢትዮጵያውያን ተብሎ ሌላ ኮሌጅ ትምህርት ቤት ተሠርቷል)። ይህም እውነት ነው ሆዳቸውን የወደዱ ሀገራቸውን የካዱ በመልካቸው በኩል በሳሪያ እንዲሆናቸውና የናንተን ስብከትና ትምህርታችሁን የምታስጠኑበት ዋና የዋና ጥቅም

# ተ እሁድ ታኅሣሥ

ማግኛችሁ የምታሰናብዱበት ቤት ነው እኛም አውቀነዋል። ዕድሜ ለእናንተ እንጅ ኢትዮጵያ ምናለባት በናንተ እርዳታ እዚህ ደርሳለች። በ "፻፷፩ኛ ያጼ ፋሲልን ግንብ ይህ ሥዕል በፖርቱጋል መሐንዲሶች ፕላን የተሠራ ያፄ ፋሲል ትልቁን ቤተ መንግሥት ይላል" በኢትዮጵያ ከሚገኙ ነገሮች ሁሉ ጌታ የማይበጅላቸው አይገኙም ጉርጓድ ተቆፍሮ ቢገኝ ግብጻውያን የቆፈሩት ነው ይባላል ማሰሮ መሳይ ሲገኝ የግብጻውያን ሥራ ነው ይባላል ሐውልት ተሠርቶ ፀሐይና ጨረቃ ከላይ ስለታዩ ዓረቦች የሠሩት ነው ይባላል በድንጋይ ብራና ተጽፎ ሲገኝ የደቡብ ዓረቦች ፊደል ነው ይባላል። ፖርቱጊዞች ሳይመጡ በኢትዮጵያ አስደናቂ ሕንጻ የለም የማለት አሳብ ለማሳያት ነው። እዚህ ላይ ስለ ዘመኑ አቈጣጠር በኢትዮጵያ መጻሕፍት አቈጣጠር ከፍጥረት እስከ ማየ አይኅ ፪ሺ ፪፻፶፯ ዘመን ነው ከማየ አይኅ እስከ ኖኅ ዕረፍት ፫፻፶ ነው ሲደመር ፪ሺ፮፻፯ ይሆናል ኖኅ ለልጆቹ ዓለምን ያካፈለ በሕይወቱ ሳለ ነው ስለዚህ ወደ ክፍለ ሀገሩ የመጣበትን መመርመር ስንዠምር ካም አባቱ ሳያርፍ ወደ አገሩ አልመጣም ብንል አባቱ ካረፈ በኋላ ዠምረን ካም ወደ ሀገሩ አፍሪካ የመጣበትን ዘመን በ፪ሺ ፮፻፯ ዘመን በላይ መሆኑን ይዘን ለመቁጠር አስፈላጊ ነው ፩ድ ፩ድ ሰዎች እስከ ባቢሎን ግምብ መፍረስ ድረስ ካም ወደ አፍሪካ አልመጣም አፍሪካም ባዶ ነበረች እያሉ ይጽፋሉ ይህ ጽሑፍ ምንጩ ከሮማውያን ነው። ከኖኅ ዕረፍት እስከ ባቢሎን ግምብ መፍረስ ፪፻፳፩ ዘመን ነው። ከማየ አይኅ ፭፻፷፩ ዘመን ማለት ነው ይህን ያህል ዘመን በአፍሪካ ሰው አልነበረበትም ለማለት የሚአስቡ አይሁድ የቀነጸሉትን መጽሐፍት የተቀበሉ ሰዎች የዘመኑን መቈረጥ ያላወቁ እንደዚህ ቡሉ በነሱ ላይ ፍርድ የለባቸውም ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ግን ይህ ሳይመለከቱ ቢቀሩ ከስንፍና መቈጠሩ አይቀርም የዚህን ሐተታ በሰፊው ከላይ ጽፌው ይገኛል አሁንም ስለዘመኑ ጉዳይ እዚህም ካጋጠመኝ አልዘለውም ስለዝህ የአፍሪካ መንግሥት የተመሠረተው በካም ነው ዘመኑም በ፪ሺ ፮፻፯ ዓ. ዓለም ነው ላይ ከዚያ በኋላ የካም መንግሥት ለ፬ ተከፈለ ፩ኛው ለኩሳ ፪ኛው ለሚሥራይ ፫ኛው ለፉጥ ሊብያ ለነዚህ ተከፈለ እነዚህ ፫ቱ ክፍለ ሀገራቸውን ይዘው እንደሚኖሩ ታሪክ ይነግረናል ፫ቱ ልጆች አገራቸውን ይዘው ስላልኩ ሚሥራይና ሊብያ ክፍለ ሀገራቸውን በሙሉ ይዘው ይገኛሉ። የኩሳ ክፍል ግን ታላቅ ልጅ ስለነበረ ወይም ለከነዓን የተባለውን ዕጣ ደርቦ ይያዝ ምክንያቱ አይታወቅም። የኩሳ ክፍል ከመጠን ያለፈ ስለነበር ዛሬ ተከፋፍሎ መሬቱ የውጭ አገር ነገሥታት ቅኝ አገር እያደረጉ ደግሞ በተንኮላቸው ፩ድ የሆነ እንደሆነ ኃይል እንዳያገኝ በማለት ወዳጅ እየመሰሉ ለየብቻው መንግሥት እንዲአቆም እየሰብኩ እንደለያዩት ያችን ኩሳ ያቆማትን መንግሥት ንጉሠ ነገሥት የመባልን ስም ነው እንጅ አገሮችማ ተከፋፍለው በሰው እጅ ይገኛሉ። አሁን ማነኛውም እየተነሳ ፲ር ምክንያት ሲፈጥር ይህች በልዑል እግዚአብሔር ታምራት የእግዚአብሔርን ስም ተደግፋ የቆመች የኢትዮጵያ መንግሥት ንጉሠ ነገሥት የሚባለውን ስምና ግዕዝ ቋንቋዋን ሳትለቅ በመቆየቷ ቅናት ስለሚያቃጥላቸው ወዳጅ እየመሰሉ ለግዕዝ አመልና ሌላ

አባት ለማበጀት ሲደክሙ የሚገኙ ውስጠ ምክንያቱ ከኩሳ ዝምሮ የመጣውን የንጉሠ ነገሥትነት ክብር ማዕረግ ለማጥፋት ወይም

## ቱ ሰኑይ ታኀሣሥ

ለመቀነስ በማሰብ ነው። ለኩሳ መንግሥት በቆመበት ሁሉ የግዕዝ ጽሑፍ ምልክት እየተገኘ ምስክር ሆኖ ቢአስቸግር ግዕዝን ሌላ ጌታ እናበጅለት ተብሎ ሲደክምበት የኖረውን የሠሩትን ተንኮል ከላይ ገልጨ አስረድቻለሁ። አሁን ያለ ነው ስለ ኩሳ መንግሥት ነው የኩሳ መንግሥት የተመሠረተው በ፪ሺ፷፪ ዓ. ዓለም በላይ ከክርስቶስ በፊት ፪ሺ፱፪ ዓመት ነው (ባ፭ኛው መሥመር የኢትዮጵያ ነገሥታ ታሪክ ካውሮፓ ታሪክ ታር የገጠመውና እውነተኛ ታሪክ የሆነውን እየመረመርን ጽፈናል።” የኢትዮጵያ ነገሥታት ታርክ ካውሮፕ ታሪክ ጋር የገጠመውንና እውነተኛ የሆነውን እየመረመርን ማለት ነገሩ አይገባኝም። ካውሮፕ ነገሥታት ታሪክ የገጠመውን የተባለው ያውሮፕን ታሪክ የታሪክ ምስክር መመሳከሪያ ነው ያለ ማነው ምስክር ለመሆን የሚቻለው ልጅ ነውን ወይስ ሽማግሌ።

የስናፖር ግምብ በፈረሰ ጊዜ ከነበሩት ከ፸፪ቱ ቋንቋዎች ፩ኛው ሳይለወጥ እንደ ኢትዮጵያ ፊደል ከነቁጥሩ ሳይሳሳት ይዞ የሚገኝ ይሆንን ምክንያት ካውሮፕ የገጠመውን ታሪክ ተባለ ያውሮፕን ታሪክ ከኢትዮጵያ ታሪክ ምን ግንኙነት አለው ይህም ያው ውሥጣዊ ፖለቲክ ነው “፪ኛ ልዩ ታሪክ ፫ኛ እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ ተቆፍረውና ተመርምረው በተገኙ ገንዘቦች ላይ በሳባዊና በፅርዓዊ በግዕዝ ቋንቋ ተጽፈውና ተቀርፀው የተገኙትን የነገሥታት ስሞች ተርጉመን ስላወቅነው ምንም ቢአነሱ ስም ተመልክ አድርገን ተራ ቁጥራቸውን ጭምር ከዚህ ቀጥለን እንጽፋለን)። ከመሬት ውስጥ በተገኙ ገንዘቦች ላይ በሳባዊና በጽርዓዊ በግዕዝ ፊደሎች የተጻፉትን የነገሥታት ስሞች ተርጉመን ስላወቅነው ተብሎ ተጽፏል በጽርዓዊ ፊደል የተባለው ኢትዮጵያውያንና ግሪኮች በንግድ ገንዘብ ይለዋወጡ በነበረ ጊዜ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት እንደተቀመጠ የቆየ ይሆናል እንጅ የኢትዮጵያ መንግሥት ስሙን በግሪክ ፊደል ብቻ ጽፎ ይገኛል የሚለውን ታሪክ እውነት ነው ብለን አንቀበለውም ደግሞም ካ፩ድ ገጽ ግዕዝ ካ፩ድ ገጽ በጽርዕ ሆኖ ቢገኝ ግን ተቀብለን ታሪኩ የሚገኝበትን ቦታ ፈልገን በታሪኩ ሥፍራ እናገባዋለን እሽ ይሁን ይህ ነገር እውነት ከሆነ በግዕዝ ፊደል የተጻፈው ወዴት ላይ አለ። ይህ ለኢትዮጵያ አሳቢነቱ ካለ እነዚያን ገንዘቦች ከመጽሐፉ ጋር አብሮ ለመስጠት የተገባ የዕውነተኛ ሥራ ይህ ነበር ማለት እነዚያ ገንዘቦች በቤተ መጻሕፍት ተቀምጠው ከነሱ የሚገጥም ስም የንጉሥ ታሪክ የተገኘ እንደሆነ ታሪኩ በቦታው እንዲገባ የተመቸ ይሆን ነበር። አሁን የተጻፈው ፖለቲክ በፍጹም የማታለል ሥራ ነው እንጅ እንደ ታሪክ ጸሐፊዎች የሕግ ገጽ ይዞ የሚገኝ አለመሆኑን እየዘረዘርኩ አስረዳለሁ። በጽርዓዊ ፊደል ለተባለው ከላይ መልሱን ሰጥቻለሁ። ፪ኛ በሳባውያን ፊደል የሚሉት የማጭበርበር ሥራ ነው እንጅ የሳባውያን የሚሉት የጥንቱን ግዕዝ ፊደል ነው። አሁን ቅረቡና የሳባውያን ፊደል ያላችሁት የትኛው ነው ብሎ ቢጠይቃቸው የሚመልሱት አይታወቅም በሕጋዊ ምንገድ እንደ እውነት ሥራ በኢትዮጵያ በሐውልት ላይ ባ፩ድ ገጽ የግዕዝ ባ፩ድ ገጽ በግሪክ ፊደል ተጽፎ ይገኛል። እነአባ ጋስፓሪን ግን በግሪክ የተጻፈውን በፎቶግራፍ እያነሱ በመሐፉ ያስገቧቸው ፩ኛ በ፺ ገጽ ፪ኛ በ፺፱ ገጽ ፫ኛ በ፲፫ኛ ምዕራፍ ባ፩ኛ ገጽ ከነዚህ ከ፫ቱስ

## ቲ ሠሉስ ታኀሣሥ

ሁሉ በግዕዝ የተጻፈውን ገጽ ለማየት አልፈለጉም ምክንያቱም ግዕዝን ያልነበረ። ወይም የኢትዮጵያ መንግሥት ተቋርጦ የነበረ ለምስመስል ነው። ይህስ ባይሆን ፩ዱን ገጽ መግቢያ ይዘው ይህን ካገኘን ብለው ኧረ ዋናውን ግዕዝ የሳባውያን ግዕዝ የሳባውያን ፊደል መባል ገንዘቡ ስለሆነ በዚህ ምክንያት ገቡና ሳባ የሚባለውን ስም ለደቡብ ሲሰጡ ግዕዝንም ወደ ዓረብ አገር ሲወስዱ ምን ረዳት ፈለጉ በዓረብ አገር የሚገኘውን ጥንታዊ ግዕዝ ባገኙ ጊዜ ዓረብ አገሮች

ለኢትዮጵያ ግዛት ሆነው መኖራቸው ቀረና እንዲያውም ዕድሜ ለሮማ ልዑካን የኢትዮጵያ አቅኒና አጥኚ ሆነው ተገኙ በኢትዮጵያ ለሚገኙ ጥንታውያኑ ጽሑፎችና ቅርጾች ሁሉ የዓረቦች ተብለው ተሰይመው ይኸውና የግዕዝ ፊደሎች ያረብ ፊደል የሚባል ስም ከሮማ ልዑካን ተቀብለው ይገኛሉ። ዋናው ሐሰት በኢትዮጵያ ልብ ሊቀረጽ የተሰናዳው እኔ የምሞርደው በዚህ መካከል ከፍ ያለ ትግል አለ ምንም ብንታገል የኢትዮጵያን አባቶች በጣምም ያባ ጊዮርጊስን አምላክ በመደገፍ ልክ ሞቴን በዚህ ትል ምክንያት እንዳገኝ የቆረጥኩ ስለሆንኩ ይህን የሮማ ልዑካን ስብከት ጽሑፍ ለመሞረድ ተሰናድቸ የቆምኩ ነኝ። ወደ ኋላዬም አልመለስም። ዋናው የትግሉ ቦታ ይህ ከላይ ተጽፎ የሚገኘው የሳባውያን ፊደል በሚለው ጽሑፍ ላይ ነው ይህ ጽሑፍ የኢትዮጵያን ወጣቶች ልብ ሁሉ ወስዶታል። ይህ የፊደላችን መቀማት ለመጭው ትውልድ የሚአስከትለውን ውርደትና ስሕተት ስመለከተው በጣም ነገሩ ስለሚገርመኝ በዚህ ባባ ጋስፓሪን ጽሑፍ ላይ ነፍሴ አብራ እንድትወጣ ስል ወድቄበታለሁ። እኔ የምለው ይሕ የሐሰት ፖለቲክ ጽሑፍ ነው እንጅ ታሪክ አይደለም። መጨረሻው ላይ "በ፫ኛው ገጽ በፊደል ሐ በኢትዮጵያ ሊቃውንት ዘንድ ታሪካቸው በፍጹም ያልተገኘ እኛ የዓለም ታሪክ መርማሪዎች ከጻፉአቸው እውነተኝኖች ታሪኮችና በኢትዮጵያ ላይ ከተገኙትም ሐውልቶች ቅርጻቸውንና ጽሑፋቸውን ተርጉመን ያገኘነውን የነገሥታት ስምና ተራ ቁጥር እንጽፋለን ይላል"። አሁን ከላይ እንደተጻፈው እኔም በተቻለኝ መጠን የነገሥታቱን ታሪክ ስመረምር ከተራ ቁጥር ያልገቡ ስሞች አገኛለሁ። ወደ ምርመራም ገብቼ ስከታተል ፩ኛ የንጉሥ ስም ሁለት ስለሆነ። ሁለተኛው ስም ስመ መንግሥት ነው። ስለዚህ ብዙ ችግር አለበት። ማለት በቀድሞ ጊዜ በአክሡም እገሌ ይባሉ የነበሩ ሁሉ ከቀን ብዛት የስማቸው ቁጥር በጣም የበዛ ነው ግን ንጉሠ ነገሥቱን በንጉሠ ነገሥትነት ተራውን ንጉሥ በተራነቱ እያደረጉ ለመጻፍ ለዚሁ ሥራ በርከት ያሉ የግዕዝ ሊቃውንትና መጽሕፍት ካልተሰበሰቡ የዚህን ሥራ ፩ድ ሰው መርምሮ ስለማይዘልቀው እኔም የተመልከትኩት ብዙ ይገኛል። ሆኖም ይህን ያህል የሮማ ልዑካን የኛን ነገሥታት ታሪክ ለማጥፋት እንጅ ለማልማት ስለማይፈልጉ የነሱን አሳብ እወንት ነው ብለን መቀበል ጉዳት የሚአመጣብን መሆኑን መዘንጋት አይገባንም። አሁን በኢትዮጵያ ሊቃውንት ታሪካቸው ያልተገኘ አሉ አርስት ሰጡና ካ፩ድ እስከ ፴ ቁጥር ተራ ሰጡ በነዚህ መካከል አልዓሜዳንና ዔዛናን አጼ ካሌብን በመካከል አግብተው ጻፉ። ይህ ተራ ቁጥር ዔዛናን አጼ ካሌብን በመካከል አግብተው ጻፉ። ይህ ተራ ቁጥር የተሰጠ ጥንት በመዝገቡ ሳይገቡ ሳይታወቁ ለቀሩ ነው እነዚህ ፫ቱ ነገሥታት የማይታወቁ ይመስል በምን ምክንያት ከነዚህ ካልታወቁት እንግዶቹ ጋራ ተራ

## ታ ረቡዕ ታኅሣሥ

ቁጥር ገቡ በዚህ ጊዜ የሮማ ልዑካንን ጥበብ እኛ አናውቅም ማለት ነው አልዓሜዳን ባ፬፻፹፯ ዓ.ም የነገሠውን አውጥተው በ፱፻፲፱ ዓ.ም በነገሠው ባጼ ሰይፈ አርድ ቦታ አግብተው ጽፈው የአልአሜዳን ልጅ ዔዛናን በአብርሃና በአጽብሃ እናት በሶፍያ ወይም በአሕየዋ ቦታ ላይ በ፫፻፺፯ ዓ.ም አውጥተው ጽፈው ከ፫፻፺፯ እስከ ፬፻፲፫ ዓ.ም ያለው የዘመንና የትውልድ ቁጥር በመካከል ቁጭ ብሎ ላስቸገራቸው ለማደናገር ሲሉ እነዚህን ስሞች ለቃቅመው አመጡና ያልታወቁ ሰዎች ብለው ተራ ቁጥር ሰጡና በነሱ መካከል አጼ አልዓሜዳን አጼ ዔዛናን አጼ ካሌብን ከነዚህ ጋር መግባባታቸው ከ፫፻፺፯ እስከ ፬፻፲፫ ዓ.ም ድረስ በመካከል ያለውን የዘመንና የትውልድ ቁጥር ለማደናገር ነው። አጼ አልዓሜዳን እስከ ፱፻፲፱ ዓ.ም አውጥተው የሰቀሉት ፱ቱ ቅዱሳን በዓልሜዳ ዘመነ መንግሥት መጡ ሲባል ስለ ሰሙ ገና የ፱ቱ ቅዱሳን አያቶች ለመወለድ ሳይታሰቡ ተወልደው ኢትዮጵያ መጥተው ያስተምሩ ነበር የተባለው አብርሃና ከአጽብሃ

ከፍሬምናጦስ አብረው ነበሩ ለማለት ነው። የሮማ ልዑካን ነገር ሁሉ በዓምድ ተደርድሮ ቦታ ይዞ ሲታይ ለጊዜው እውነት መምሰሉ አይቀርምና አንባቢዎች ይህን ረቂቅ የተንኮል ሥራ በጥብቅ እንድትመለከቱት አሳስባችኋለሁ።

ከነዚህም ስማቸው አልታወቁም ነበር ከተባሉት በ፺ኛው ተራ ቁጥር ተጽፎ የሚገኘው “በ፷፱ነኛው ገጽ ከስከስን ያቀና የሳሊም የልጅ ልጅ ወዓራን ሕይወት የተባለው የደቡብ ዓረብ ሰው ነጋሢ ነጋሢ ነጋሢ የሚባሉት የደቡብ ዓረብ ሰዎች ከመካከላቸው አነገሡት ተብሎ የተጻፈው እሱም ከቁም ነገር ተቈጥሮ እንደዚህ ተጽፎ ሲገኝ እንግዴህ ምን ማለት ይቻላል። ከ፺ኛው ቁጥር ዠምሮ እስከ ፸፪ኛው ቁጥር ፳ቱ ሰዎች የነዚህ ሰዎች መረጃ በ፻፷፯ኛው ገጽ ላይ በተሣለው የገንዘብ ጽሑፍ ላስተዋለውና አንባቢዎች መገንዘብ አለባቸው። ያባ ጋስፓሪንን ጽሑፍ ላስተዋለውና ለመረመረው መረጃዎችን ሁሉ ለማግኘት ይችላል። ኢትዮጵያ ከብዙ ኃይለኞች የጦር ኃይል ሳትደፍር የቆየች የታሪክ አምባና ምሽግ የነበረችቱን ኃፍረትን የማያውቁ ሰዎች ታሪክዋን ለመመዝበር ሲደከሙ ይታያሉ። ኢትዮጵያ እግዚአብሔርን ፈሪ ሕግ አክባሪ ሆና በመገኘቷ ምክንያት መስለው እንደዚሁ በልባቸው ውስጥ ዋና ሥራቻእውን ደብቀው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠብና ክርክር የመሩባት ሰላም ያጠፉባት የሕዝቡን ቁጥር ያጐደሉባት የንጹሕ ሰው ደም ያስፈሰሱባት እነዚህ የሮማ ልዑካን መሆናቸውን በዚህ መጽሐፍ ከ፩፻ ዘመን በኋላ ያለውን ሁሉ የተቻለኝን ያህል ገልጨለታለሁ። ይህንም ድካም ያሰብኩበት ምክንያቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ አባቱ የሞተበትን ጦር ሲስም እንደሚታይ ገርነት የሚአበዛ ሕዝብ በብዙ እየበረከተ ሲሄድ ስለማይ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ፩ድ አካል መሆን ስለሚገባቸው ነው በ፳ቱ ዘመን ወረራ ጊዜ ከበድ ያለው ኃዘን የኢትዮጵያ ልጆች እርስ በርሳችን እየተላለቅን መሬቱን ባዶ ሆነ እያለ ምንም እስቲመለከተው በመድረሱ ነው። የሮማ ሕዝብ መሬት ጠበበን ይላል የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እያደረ በማነሱ ምክንያት የሚታሰብለትን ማሰብ ይገባልና ነው። መቸውንም ጊዜ ቢሆን የሮማ ልዑካን ከገቡበት ወዲህ በኢትዮጵያ ላይ ፍቅር እየመነመነ ስለሄደ እግዚአብሔርም ከመካከላችን

# ቴ ኃሙስ ታኅሣሥ

ስለራቀ ጸሎታችንንም ወደ ልዑል እግዚአብሔር በቶሎ ሊደርስልን አለመቻሉ። በማቴዎስ ወንጌል ፲፯ ፳፩ ዝንቱ ዘመድ ኢይወጽእ ዘእንበለ በጾም ወበጸሎት የተባለውን ተመልክተን ስለዚሁ ጉዳይ ቀን ቁጥረን ሱባዔ ሰፍረን በጣም የጠበቀ ጾምና ጸሎት አድርገን ቢሆን ልዑል እግዚአብሔርን ቃሉ የማይታበል ሚዛኑ የማይጐድል ስለሆነ በመካከላችን ገብቶ ውስጥ ለውስጥ የሚአበጣብጠንን ሰይጣን አውጥቶ ኢትዮጵያ እንደቀድሞዋ የፍቅር ሸማዋን ተጐናጽፋ በውስጥዋ የሚገኙትን ሀብቶች ሁሉ ለመፍቅዶቿ እያዋለች ወደቦቿን በጅዋ ካደረገች ፍቅርን ስትይዝ እግዚአብሔርን ያዘች ማለት ነበር እግዚአብሔርን ያገኘ ሌላ ምን ይፈልጋል የጠላቶቻችንን ፕላን አስተውሎ ለተመለከተው ጦርነት ከማድረግ በፊት የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ እያፋጀ የደም ምድር አድርጎ ከልዑል እግዚአብሔር አጣልቶ በመካከሉ መቅጫ ሆኖ ለመግባት ነው። ከጐረቤት መቀላወጥ የለመደ ልጅ እናትና አባቱን ሳያስቀይም እንዳይቀር እኛም ከጠላት ወገን ልዩ ጥቅም ሳናስቀይም አንቀርምና ይህም ጉዳት ለሁሉ ስለሆነ ፩ድ ኢትዮጵያ የወለደችው በገንዘብ እየተታለለ ማነኛውንም ነገር እያቀበለ ኢትዮጵያ የምትታወክበትን ነገር የሚፈጥር ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ እንደም ያለ ዋጋ ያጋጥመው ይሆን። ጠላቱን የማያውቅ እንደ ምን ያለ ሰው ነው ደግሞስ ታሪክ መጻፉ በከንቱ አይደለም ያለፈውን ታሪክ መጭው ትውልድ እየተመለከተ መልካም ሠርቶ በጎ ዋጋ ያገኘውን አይቶና ተመልክቶ እንደ እገሌ እሆናለሁ ብሎ እንዲጠነቀቅበት ማለት እንደ ሞሶሎኒና እንደ

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ። ይህ የሁለቱ ታሪክ የልዑል እግዚአብሔርን ታምራት እያሳሰበ ዘለዓለም ለመጭው ዓዋጅ ጋራ ሆኖ የሚኖር ማለት የዘለዓለም አብነት ነው። ይህንን ለመጭው ትውልድ የሚተላለፈውን። ታሪክ እኛ በጊዜው የምንገኝ ሰዎች በሰፊው አንመለከተውም ምክንያቱም ዓይናችንን የሚከልለን ነገር በመኖሩ ነው ይህም በኦሪት ዘዳግም ፲፮ ፲፱ ወኢያድልው ለገጽ ወኢይንሥዑ ሕልያነ ይህ ንባብ ሲመከር በፍርድ የተሾሙትን ብቻ አይደለም

ማነኛውንም ሰው ገንዘብ ተቀብሎ እውነትን ለሐሰት እንዳይለውጥ በማለት መሆኑን ማሰብ ነው። በኢትዮጵያ ላይ ሐሰት የተጠላ ገንዘብ የተናቀ በነበረበት ሀገር የሐሰት ባሕር ለቀቁበት ለኢትዮጵያ ማጥፊያ ብለው የሠሩት ሥራ ተመልሶ ራሳቸውን ሳይመቻቸው እንደማይቀር በሽ፱፻፴፫ ዓ.ም ዓይተውታል። ለኢጣልያኖች ልብ ቢኖራቸው ከሽ፱፻፴፫ ዓ.ም በኋላ በኢትዮጵያ መታየት አይገባቸውም ነበር (ስለ አባ አረጋዊ አመጣጥ አውሮፕ ታትሞ ከመጣ ገድለ አረጋዊ የተገኘ ያባቱ ስም ይስሐቅ የናቱ ስም እድና እናቱ አብደልመሢሕ ትለው ነበር ትርጓሜው ገብረ ክርስቶስ ማለት ነው አባ ጳኵሚስ ልብስ ምንኵስና ባለበሰው ጊዜ ዘሚካኤል ተባለ የመነኰሰበት ያውኖስ በሚባል በጽርዕ አገር ነው ይላል።)

የመነኑበትንም ስንመረምር በቍስጥንጥንያና በእስክንድርያ የነግሡ የነበሩት። ቄሣሮች ንስጥሮሳውያን ስለነበሩ ንስጥሮሳውያኑን እየሾሙባቸው በዚህ ምክንያት ከሰው እየተለዩ ወደ በረኃ ገቡና እየመነኰሱ ኖሩ። ዛሬ ስለበዛ አባራሪዎቹ እነማን እንደ ነበሩ ተረሳ መሠለና ካባራሪዎቹ ወገን የነበሩትን አንታወቅም በማለት ፱ቱ

# ት ዓርብ ታኅሣሥ

ቅዱሳንን የኔ አባቶች ናቸው በማለት የነሱን ዘመን ለማስረዘም ሲባል አብርሃና አጽብሓ ተሠርዘው በነሱ ስፍራ የአልዓሜዳ ልጅ ያፄ ካሌብ ዔዛና ለመተካት ቻለ። የትውልዱና የዘመኑ ቍጥር ርዝመት ባያፈርስባቸው ፖለቲኩ የተቃናላችሁ መስሎ ነበር። ግን የናንተ ሥራ መሠረት የሌለው ስለሆነ ሥራቸው ሁሉ ከንቱ ሆኖ ቀረ። እንጅ ፱ቱ ቅዱሳንን መንኰስ ማን የማን ወገን እንደሆነ መመርመር ያስፈልጋል። የመነኰሱበት ቦታ ወዴት ነው። በአባ ጳኵሚስ እጅ መሆኑን እንግዴህ ያባ ዘሚካኤል ትምርት ኦርቶዶክሳዊ መሆኑን ማሰብ ነው። ፱ቱ ቅዱሳንን የኛ አባቶች ናቸው በማለት እነሱ መንነው መጥተው በኢትዮጵያ በብዙ ጸሎትና ጾም ስግደት ወደልዑል እግዚአብሔር የቀረቡ ቅዱሳትን ስለ ነበሩ እኛ እናከብራቸዋለን እናንተ ግን የነሱ ልጆች መሆናችሁንም አናውቅም እናንተም አንወድም ምክንያቱም ስለምትሠሩት ፖለቲክ ነው ፖለቲኩም የኢትዮጵያን መሠረተ ታሪክ ለመደምሰስ የታሰበውን ያ፬፻ ዘመን የፖለቲክ ጥንስስ አባ ጋስፓሪን ገብረ ማርያም በጥብጠው በጥንስሱ ቀለም ጽፈው ወደ ግርማዊ ጃንሆይ ንዑስ አምኃ ተብሎ በቀረበው መጽሐፍ የሮማ ልዑካን በረቂቅ የተሠራው ሁሉ በልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ የሚገልጽበት በደረሰ ጊዜ ሉቃስ ፰ ፲፯ ወአልቦ ኅቡዕ ዘኢይትከሠት አልቦ ክዱን ዘኢያስተርኢ ወገሃደ ይከውን ምንም ተሠውሮ ቢኖር ላይገለጥ በግልጽ ወጥቶ በአፍአ ሳይታይ እንደማይቀር የተጻፈው በሮማ ልዑካን ላይ መላ ተፈጸመ እንግዴህ በሰፊው የተጠበቡብን ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ መሠረት ስለሆነ ለታሪክ ምን ምሳሌ ልንሰጠው ይገባናል ይሆን እኔ ግን ታሪክን የተጠረገ ጐዳና ብዬ ምሳሌ ሰጥቸዋለሁ ምክንያቱም ሁሉ ነገር በምንገድ ሲሄድ ይታያል ማነኛውም ፍጡር እንስሳት እንኳ ምንገድ ያበጃሉ በዚያ በዚያ ምንገድ ከኋላ የሚመጡ ሁሉ ይሄዱበታል በምንገድም የሚሄድ ሁሉ በጥንቃቄ ወዳሰበው ይደርሳል ታሪክ ያለውም ሕዝብ ያባቱን ምንገድ አባቱ ይሠራው የነበረውን እየተመለከተ በዚያው ላይ እየጠለቀና እያስፋፋ ሲሄድ በፍጥነት ወደ አሰበው ለመድረስ ይችላል ምንገድ የተበላሸበት ሰውና ታሪኩ

የጠፋበት ሀገር ፩ድ ነው ያ ምንገድ የጠፋበት ሰው እንቅፋቱና እሾሁ አላስሄደው ብሎ በቶሎ ካሰበው እንደ ማይደርስ ታሪኩ የጠፋበትም ሕዝብና ሀገር አዲስ ታሪክ እስቲያደላድል ድረስ ብዙ ድካም አለበት ስለዚህ የሮማ ልዑካን በረቂቅ ፖለቲክ መንፈሳውያን መስለው ቀርበው የኢትዮጵያን የታሪክ መሠረት ሲሠረስሩ ተገኙ ሐሰት ነው መሰርሰር የለብንም ለማለት ቢሞክሩ ይኸውና ለማስረዳት ዝግጁ ነኝ አሁን እኔ የማስታውሰው ታሪክ ማለት መሠረት ነው። ያለ መሠረት የተሠራውን ሥራ ማሰብ ነው። ጥልቅ መሠረት ያለውን ቤት ትርፎች አይንዱትም ቢበዙም ላዩን ገለፋፍጠው ይሄዳሉ እንጅ ከሥሩ ነቅለው ለመውሰድ እንደማይችሉ የተጻፈውን መመልከት ነው። ታሪክ ያለውም ሀገር ለጊዜው ባኃይል ቢጫነውም ሲያያዝ የመጣውን በመሬቱ ውስጥ ያለውን ሀብት ጥሎ ለመሄድ ከጦር ሜዳ ላይ

ፊቱን አይመልስም። ብዙዎች ጀግኖች ቢሞቱም ጥቂቶቹም ቢሆኑ በቆራጥነት ሲከላከሉ ይመልሱታል። እንደዚህም ለማድረግ የሚችል የሀገሩን ታሪክ ጠብቆ የሰከረ ወጣት ነው። ስለዚህ የሮማ ልዑካን የወጣቶች ልብ እንዲፈዝና እንዲቀዘቅዝ ለማድረግ የኢትዮጵያን ታሪክ

# ቶ ቀዳም ታኅሣሥ

በረቂቅ ፖለቲክ ነጻነቷ ተጠብቆ የምትኖሪቱን ሀገር ነጻነቷ ተሰብሮ ነበር እያሉ ጽፈዋል ይህም ፩ ይባላል።

፪ኛ ግብጽም ኢትዮጵያን ትገዛ ነበር ብለው ጽፈዋል።

፫ኛ የደቡብ ዓረብ ኢትዮጵያን ይገዙ ነበር ብለው ጽፈዋል።

፬ኛ በኢትዮጵያ የሚገኘውን ግዕዝ ያረቦች ፊደል ነው ብለው ጽፈዋል ፊደላችንን ከውጭ የመጣ ነው ማለታቸው አስቀድሞ የኢትዮጵያ ግዛት የነበሩ አገሮች ዛሬ ከኢትዮጵያ ውጭ ሆነው ሌላ መንግሥትና ፊደል አቁመው ስለሚገኙ በመሬቱ ውስጥ የኢትዮጵያ ጥንታውያን ፊደሎች ምስክርነታቸውን እያዘዙ ብቅ እያሉ አስቸገሩ እነዚህ በውጭ የተቀረቱ አገሮች ቋንቋ ለቋንቋ ከመገናኘት የተነሳ ወደ መሠረተ ዓላማችን ተመልሰን ፩ድ እንሆናለን እያሉ የተመለሱ እንደሆነ ኢትዮጵያ ኃይል ታገኝና ያሰብነውም ሳይፈጸም ይቀርብና ያወጣነውም ገንዘባችን በከንቱ ይቀራል ብለው የሚመጣውን አሳልፈው ተመልክተው ነው ኢትዮጵያ በቀደምትነት ማዕርጓ እንደተከበረ የንጉሠ ነገሥቷን ስም በዓለም ነገሥታት ዘንድ እየታወቀ በሥልጣኔም ኢትዮጵያ በንጉሠ ነገሥቷ መሪነት ከፍ ከፍ ወደማለት ደረጃ ስትይዝ ስላዩ በጣም ከባድ ፍርሃት አደረባቸውና ስለዚህ የወጣቶችን ልብ ለማፍዘዝ ይሕን ሁሉ ሐተታ ባልቸገራቸው ገብተው አሳፋሪ የሆነ ሥራ ጽፈው አቀረቡ ማፈርንማ እነሱ ወዴት አውቀውት ለወደፊቱ ግን ማፈራቸው ስለማይቀር ነው። የኢትዮጵያ ወጣት ሆይ ኢትዮጵያ ሀገራችን የታሪኳን ዝና ከውጭ ሰዎች እንደምትሰሙት ከውጭ ሰዎች ስል ባ፴፻፶ ዘመን በላይ የተጻፈ ያገኛችሁትን ነው እንጅ ከ፴፻፶ ዘመን ወዲህ የተጻፈውን የተመለካታችሁ እንደሆነ ምንም ጥቅም እንደማታገኙ አስጠነቅቃችኋለሁ። የሮማውያን አሳብና ጽሑፍ ሁሉ ከንቱ ብቻ ነው ዓምድ ይፈጃል። በማለት ብዙውን በማለፍ ነው እንጅ እነሱ የለፈለፉትን ሁሉ ሐተታ ብንከታተል ዓምዱ አይበቃውም። በሮማውያን ከቀዳማዊ ምኒልክ በፊት በኢትዮጵያ መንግሥት እንዳልነበረ ለማድረግ መሆኑን ለመረዳት "በ፶፬ኛ ገጽ በ፷፪ኛው መስመር ከዚህ በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን ልጁን ከሸዋ ደቡብ እስከ ጎንድ ምሥራቅ በተዘረጋው ምድር ላይ የኢትዮጵያ ንጉሥ አድርጎ በካህኑ በሳዶቅ አስቀባው ይላል።" ከሸዋ ደቡብ እስከ ጎንድ ምሥራቅ በተዘረጋው ምድር የኢትዮጵያ ንጉሥ አድርጎ ቀባው ማለት ያው የተለመደው የሮማ ልዑካን ሐሰት ነው በካህኑ በሳዶቅ ቅብዓ መንግሥት አስቀባው ማለት እርግጥ ነው አገር ሳይሰጥ ቅብዓ መንግሥት እንደምን ይሰጣል ብሎ የሚጠይቅ ቢኖር ነገሥት ፲፯ ወነሥአ ሳሙኤል

ቀርነ ቅብዕ ወቀብዖ በማዕከለ አኃዊሁ። ወመጽአ መንፈሰ እግዚአብሔር ላዕለ ዳዊት እምይዕቲ አሚር ወለዝላፉ ወተንሥአ ሳሙኤል ወአተወ ውስተ አርማቴም ያለውን ይመልከት። ዳዊት ከተቀባ በኋላ ወዲያው ንጉሥ ሆነ የሚል እንዳለ ከዚያ በኋላ በጎች ጠባቂ እንደነበረም ፲፯ ፲፭ ወዳዊት ሖረ ወተመይጠ እምኅበ ሳኦል ይርዓይ አባግዓ አቡሁ ውስጠ ቤተልሔም ያለውን ይመልከት። ሰሎሞንም እብነ መለከን ቅብዓ መንግሥትን ያስቀባው በሕገ ሙሴ ጨምሮ በሥርዓተ ሙሴ አድርጎ አስቀብቶ መስደዱ የታመነ ነው እንጅ አንግሦ ሰደደው ማለት ሐሰት ነው ይልቁንስ ቅብዓ መንግሥት አስቀብቶ መስደዱ የታመነ ነው እንጅ አንሦ ሰደደው ማለት ሐሰት ነው ይልቁንስ ቅብዓ መንግሥት አስቀብቶ ሌዋውያን ጨምሮ በሥርዓተ ሙሴ አድርጎ አስቀብቶ መስደዱ የታመነ ነው እንጅ አንግሦ ሰደደው ማለት ሐሰት ነው ይልቁንስ ቅብዓ መንግሥት አስቀብቶ ሌዋውያንን ሰጥቶ ሲሰደው መጻሕፍተ ኦሪትን አልሰጠውም ብሎ ከመገመት ቅብዓ

# ኀ እሁድ ታኅሣሥ

መንግሥት ሲቀባው አስተማሪ የሚሆን ሌዋውያንን ሲሰጠው መጻሕፍተ ብሉያትንም ሰጥቶ ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተገልብጦ እስከ ዛሬ የሚገኘው የሱ ዘር ነው ብሎ ይህን አስተካክሎ አምኖ መጻፍ የተገባ ነበር "፪ኛ ወዲያው ከ፳ኤል ዐበይት የተወለዱትን ፳፩ የበኩር ልጆች አባቶቻቸው በኢየሩሳሌም የሚሠሩትን በኢትዮጵያ እንዲፈጽሙ ነው ይላል። ይህ ቃል ከሌላ ላይ ተክዶ የኢትዮጵያ ነገሥታት አረመኔ ሲባሉ ባይገኝ መልካም ጽሑፍ ነበር "፫ኛ እነሱም ከኢየሩሳሌም ሲነሱ ጽላተ ሙሴን ከቤተ መቅደስ ወስዷት" ይህም እርግጥ ነበር ያመጧትም ሌዋውያን ናቸው ይህም በፈቃደ እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ ንጉሥ ሰሎሞንም ራዕይ አይቶ ነበር እግዚአብሔር ነው ስለዚህ ንጉሥ ሰሎሞንም ራዕይ አይቶ ነበር። ይህንም ለመረዳት በታተመው ብሉይ ኪዳን ነገሥት ፫ ፹፫---- ወይዕተ ጊዜ ነበበ ሰሎሞን በእንተ ውእቱ ቤት ሶበ ፈጸመ ሐነፆታ ፀሐይ አርአየ እግዚአብሔር በሰማይ ወይቤ ይኅድር እምዓዜብ ወሐኒጸ ቤትየ ቤተ ዘድልው ለከ ለኃዲር በሕዳሴሁ አኮኑ ዛቲ ጽሕፍት ውስተ መጽሐፈ ማኅሌት ይላል። እንግዴህ ሐተታውን እንመልከት ፀሐይ ማለቱ ነው ኢትዮጵያን ዓዜብ አይላትም የሚል ቢገኝ ማቴዎስ ፲፪ ፵፪ ንግሥተ ዓዜብ ትትነሣእ አመ ዕለተ ደይን ምስለ ዛ ትውልድ ወትትፋታሓ እስመ መጻት እምአጽናፈ ምድር ከመ ትሰማዕ ጥበቦ ሰሎሞን ወናሁ ዘየዐቢ እምሰሎሞን ዝየ የተባለውን ይመልከት በኢትዮጵያ ላይ አምልኮ ጣዖት ኖሮ ቢሆን ጽላተ ሙሴ ጣዖት ባለበት አለመቀመጥዋ በኢሎፍላውያን ላይ የተመሰከረ ነው። ንግሥተ ዓዜብ ጽላተ ሙሴን በድላ ቢሆን ጌታችን ከላይ እንደተጻፈው የኢየሩሳሌምን ሰዎች ሲወቅስ የዓዜብ ንግሥት የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት ከምድር ዳርቻ መጣች እናንተ ግን እኔ ሰሎሞንን የፈጠርሁ መጣ አንቀበልም አላችሁ በዚያች በደይን ጊዜ ትፋረዳችኋለች ባላለም ነበር ከላይም ይኅድር እም ዓዜብ ካለ በኋላ ወሐኒጸ ቤትየ ቤተ ለድልው ለከ ለኃዲር በሕዳሴሁ ያለው አስገራሚ ምሥጢር አለው ይህ ሁሉ ታሪክ ስለ ኢትዮጵያ ነው ደግሞ "፹፫ኛው ገጽ ከዚህ በኋላ በዓዜብ በዋቂሮና በሜዛስ አልፈው ከከተማቸው ከደብረ ማከዳ ደረሱ ጽላተ ኪዳኒንም ከተራራ ላይ አኖርዋት እብነ ሐም የመንግሥትን ሥልጣን ከንግሥት እናቱ ተቀበለ"። እብነ ሐኪም ከንግሥት እናቱ ሥልጣን ተቀበለ ማለት አሁን በሚገባው ተጻፈ ንግሥት እናቱ ተቀበለ ማለት የተገባ ጽሑፍ ነው አስቀድሞ ሲሄድም እዚያ ተባብሎ እንዳይቀርባት እሷም መንግሥቷን የሚወርስ እሱን ስለአሰበች እንዳይቀር ለሱም አጥብቃ ነግራው ነበር ወደ ንጉሥ ሰሎሞንም በታምሪን እጅ ደብዳቤ ጽፋ ልካ እንደነበረ ሥርዓተ ጽዮን የተባለው መጽሐፍ ይናገራል "ሌዋውያንና ሌሎቹም ከኢየሩሳሌም የመጡ ነገዶች ሁሉ በመንግሥቱ ግዛት ላይ ሃይማኖትን ብሉይና የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት የ፳ኤልን ትእዛዝ አቆሙ ማለት ነው"። ይህም ላይ የተጻፈው በሚገባ የተጻፈ ነበር የዳዊት ዘሮች ብዙዎች መጥተው በመሳፍንትነት በየክፍል አገሮች ላይ ዘውድ እየሰጠ እንዳሾማቸው ሥርዓተ ጽዮን የሚባለው መጽሐፍ ይናገራል። ይህ ሥርዓተ የሚባል መጽሐፍ የሚናገረው አስቀድሞ ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሲሠራ ሲዠምር ከኢትዮጵያ የሚፈልጉትን ነገሮች ለማግኘት ከታምሪን ጋራ ሰሎሞን ንጉሥ እንደ ተነጋገረ

# ኍ ሰኑይ ታኅሣሥ

ይናገራል። የታምሪንም የንግድ ማመላለሻዎች ፫፻ ገመሎች ነበሩ ታምሪን በኢየሩሳሌም የታወቀ ሰው ከንጉሥ ሰሎሞን  የሚገናኝ እንደነበረ የሚናገር ታላቅ መጽሐፍ ነው። ይህም መጽሐፍ ዋናው ፀ ፻ ፀ ፮ ፬ ፮ ፰ ፮ ፰ ፯ ይገኛል ከላይ እንደተጻፈው የብሉይ ኪዳንን ሥርዓት ሰንበት ማክበርን በአምልኮተ

እግዚአብሔር መኖርን ሊዋውያን እርግጥ አስተምረዋል። ይህም ትምህርት ሲያያዝ እንደመጣ ወንጌልንም ከተቀበሉ በኋላ ሰንበትን ማክበር ሰይተው ስለሚኖሩ የግብጽ ጳጳሳት ቀዳም ሰንበት ስለምን አይሁድን ይመስል ታከብራላችሁ

በማለት ከኢትዮጵያ ሊቃውንት ጋራ ብዙ ጠብና ክርክር ባደባባይ እስከ መገረፍ ደርሰውባታል አቡነ ፊልጶስ የደብረ ቢዘኑ ብዙ ክብር ለመቀበል የደረሱ በዚሁ በሰንበት ምክንያት ብዙ ሥቃይ በመቀበል ነው። ዛሬም ቢሆን በደብረ ቢዘን ገዳም ይህ መሠረት እንደ ጸና ይገኛል በደብረ ቢዘን ሥነ ሥርዓት በ፪ቱ ሰንበታት ከውጭ ወደ ግቢ መግባት ከውስጥም መውጣት ክልክል ነው። አሁን እኔ በተቻለኝ መጠን የምደክመው ስለ ኢትዮጵያ መሠረት መናወጽ ነው። በሰው ባህርይ ላይ ብዙ ደካምነት መኖሩ የማይካድ ስለሆነ አዳምንና ሔዋንን ያሳተ ዲያቢሎስ ዛሬም ሥራውን ያልፈታ መሆኑን ማሰብ የሚከፋ አይደለምና የጠላትን ስብከትና ትምህርት ተቀብሎ ልሂድ ብሎ ከማሰብ ካም ወደ አፍሪካ ከመጣበት ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ያለውን መዝኖ ማወቅ የተገባ መሆኑን መረዳት አስፈላጊ ነው። አስቀድሞ መንቀፍ ከሚባለው ቦታ ላይ መቆም የሚቻለው ግዕዝንና በግዕዝ የተጻፉትን መጻሕፍት አስተውሎ መርምሮ ካወቀ በኋላ ነው። የግዕዝን መጻሕፍት መርምሮ ሳያውቅ እንዲሁ በጭፍኑ መንቀፍ ከባድ የሆነ ነገር የሚአስከትል መሆኑ የማይጠረጠር ነው። ፩ድ ሰው ለጊዜው ተመቸኝ ብሎ ፩ድ አጉል ቢጽፍ ወይም በቅርጽ ቢያሳይ ትንሽ ከቆየ በኋላ ታሪኩ ተጠያቂ መሆኑ አይጠረጠርም። ስለዚህ ፩ድ ፩ድ ሰዎች የውጭ አገር ቋንቋን እንደ ፩ድ ኪነ ጥበብ ቆጥረውታል። ጥበብን ሰዎቹ በብዙ ትጋት መርምረው ደረሱበትና ሠሩበት እንጅ ቋንቋው ብቻ ጥበቡን ለሰዎቹ ያመጣላቸው አይደለም። ቋንቋን ብቻ ጥበብን ፈልጐ የሚአመጣ ከሆነ ይህች ጥበብን እየፈለገች የምታመጣ ቋንቋ በዓለም ላይ እንደምን ያለ ዋጋ ባገኘች ነበር። ጥበብን ፈልገው አምጥተው እንደዚህ አድርጋችሁ ሥሩ የሚሉ ቋንቋዎች ስንት እናገኛለን። ምናልባት ስንመለከት በመንግሥታቱ ሀገር ሁሉ ሆነው እናገኛቸዋለን። እንደዚህ ከሆነማ እኛም በእኛ ቋንቋ እየተነጋገርን ጥበብን ስለምን እንፈልጋትም ይሆን። በሀገራችን ላይስ ይገኙ የነበሩትን በያይነቱ የእጅ ጥበብ ሥራ ሲሠሩ የመጡትን በጠላት ስብከት እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ማቅረብ አያስፈልግም ሰውን የሚበሉ ናቸው። የሚባለውን ምክር ወይም ስብከት ተቀብሎ ከማራቅ እነሱን ከጥንት ጀምረው ጊዜው በሚገጥመው አኳኋን ጦሩን ጐራዴውን አፋውን ቀስቱን እነዚህን ሁሉ መሣሪያዎች ኢትዮጵያ ከማን እየገዛች ነበር ጠላትዋን አትከላከል የቆየችው ከማን እየገዛች ነበር የጐራዴው ሰገባና ጋሻ በዚያ ጊዜ ከማን ይገዛ ነበር። እነዚህን ሰዎች የሚያስቀይም ስም ከመቀበላቸው በፊት እንደዚሁ በያዙት ሥራቸው ላይ በየጊዜው እየቀጠሉ በሄዱ ጥቅሙ ወዴት ነበር። ይህንስ ሠራተኞች የሚያስቀይም ነገር ማን አመጣው ከማንስ የተገኘ ይሆን ዛሬውንስ የኛን መሠረተ ቋንቋ ግዕዝ ወደኋላ እንድትቀር እነብላታ መርሥዔ ኀዘን ወ ቂ

## ኂ ሡሉስ ታኅሣሥ

እንዲሁም በጭራሽም እንድትለወጥ የሚፈልጉ ሰዎች በርክተዋል ይህም አስተያየት ከጠላት ምንጭ የተቀዳ መሆኦኑ የታመነ ነው። ሲሆን ቢውል ራስ ያለው ሰው ግዕዝን እንዴት ይጠላል ግዕዝን የሚጠሉ ሰዎች ምንን ሊተኩ ይሆን። ለቴክኒክ ሥራ እያሉ ያመሀኛሉ። ይልቁንስ ወደ ትንተ መሠረቱ ገብተው ቢመለከቱ ቀልጣፋ በሆነ መንገድ የሚአስሄደውን መንገድ ባገኙበት ነበር። ግዕዝ ከታወቀ ጥበብን አላሳውቅም ብሎ ይከለክል ይሆንን።

ኢትዮጵያ ከካም መንግሥት ዠምራ እስከ ዛሬ ፬ሺ፫፻፵ ዘመን የቆየችበት በዚህ ግዕዝ ነው ጽላተ ሙሴ ከመጣች ዠምሮ እስከ ዛሬ ስትመሰገን የቆየችበት ይህ ግዕዝ ነው የግዕዝ ቋንቋ ፊደል ራሱን የቻለ እውነትም ነጻነት ያለው መሆኑን ራሱ ምስክር ሆኖ እያስረዳ አናይህም በማለት ግዕዝ

የነጻነት ሐውልት ነው ይህንም ለማወቅ ኦሪት ዘፀዓት ፲፪ ፴፯ እይ ግዕዝ መልክ ነው ኢትዮጵያዊ በግዕዝ ግዕዝ በኢትዮጵያ ይታወቃል ግዕዝ ዓላማ ነው ዓላማ ማለት የነጻነት ክብር ምልክት ነው። ግዕዝ ያባት ቅርስ ነው አባቶች ያስቀመጡት ሀብት ሁሉ መገናኛ ግዕዝ ነው ግዕዝ የሀገር ወሰን ምልክት ነው ማለት ወሰኑ በጽፈት ድንጋይ ተተክሎ የግዕዝ የጥበብ መምህር ነው የግዕዝን መጻሕፍት በጥብቅ ያነበበ ጥንታዊ ጥበብን ያገኛል መምህር ሀብት ነው ግዕዝን አጥብቆ የመረመረ እውነተኛይቱን ዓለም ይገኛል ግዕዝ ማይ ነው ማይ ከሥላሴ ልጅነት ይገኝበታል ግዕዝም ምስጢሩ

ግዕዝን ማይ ለማለት ግዮንን ያመለክታል ግዮን ግዕዝ ፊደሉን ግን መመልከት ነው ግዕዝ መልክ ነው ያልኩት ኢትዮጵያዊ ፊደሉን ለውጦ ቢገኝ መመልከት ነው ፩ድ ነገር ቀብቶ እንደመታየት ያለ ነው እንግዲህ አሁን ፩ድ ኢትዮጵያዊ መልኩን ነጭ ወይም ቀይ ቀለም ቀብቶ በዓለም አደባባይ ቢታይ የሚመሰገን ይሆንን። ደግሞ ዋንው ጠቅላላው ነገር ግዕዝ የእግዚአብሔር ምሥጢር መነጋገሪያ የልዑል እግዚአብሔር ስም ነው እግዚእ አግዓዚ አጋዕዝት አግዓዘ ግዕዝ ከነዚህ ሁሉ ቃሎች የትኛው ሊቀነስ ይገባል። ይኸውም ፊደል ማለት መያዣ መጨበጫ ማወቂያ ነው ማነኛውን የፊደልን ቁጥር የለም ብሎ የሚክድን ሰው ሲገኝ ሰው እንዳላገኙ ሆኖ መልስ አለመስጠት ከእንስሳት እንደመቆጠር ማለት ነው። ሮሜ ፱ ፳፰ እስመ ኍሉቀ ወምቱረ ነገረ ይነግር እግዚአብሔር ውስተ ዓለም ዘሀለዎ ይግበር የሚሠራው ሁሉ የተቆጠረና የተቆረጠ ማለቱ ያለ ቁጥር የሚሠራ አለመኖሩን ነው። ሙሴ ሲዠመር በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ያለውን ፊደሎች ምን ምን እንደሆኑ አማርኛ ሳይመጣ ለማስረጃ እንደምን ነውን ይተረጐሙ እንደነበር የማያስብ ሊቅ እንደምን ያለ እድላም ማለት ነው። የሊቅነቱን ስም ከተሸከመ በኋላ ወደ ጥልቅ ምርመራው ውስጥ ገብቶ መልፋትን በምን ምክንያት ሊፈልገው ይችላል። ስለካም ዘሮች ከዮሐንስ መደብር የተጻፈ ይህንም መጽሐፍ ከዓረብ ወደ ግዕዝ የገለበጠው ቅብርያል የሚባል ግብጻዊ ዲያቆን ነው ያስገለበጠችውም እቴጌ ማርያም ስና ናት። በዕሥያ የሚገኙ የካም ዘሮች የኩሳ ልጆች ፩ኛ ማንሩድ ፪ኛ አሮክሰስ በፋርስ መንግሥት የዠመረ አዳኝ ነበር ይላል። ወአውስበ ብዕሲተ እምሶርያ ዘስማ አውራን ወወለደት ሎቱ ፪ ደቂቀ ፩ኛ በክዮስ መሰመይዎ ራአን። ፪ኛ ኒንዮስ ዘሐነጸ ሀገረ በሶርያ እንተ ይዕቲ ነነዌ። ወአሮክሰስ ኃደገ ወልደ በመንግሥቱ ወሖረ ኀበ ምዕራብ ወነግሠ ላዕሌሆሙ እስመ

## ኃ ረቡዕ ታኅሣሥ

ሀለው እንበለ ንጉሥ ወበክዮን ወልዱ ዘተሰመየ ቤሩስ ተንሥአ ላዕለ አክሮስስ አቡሁ ወቀተሎ ወአጽነሳ ለወለተ ኒኪስ እንተ ትሰመይ አውራን በኪስስ ዓደ ዘውእቱ ኔሩስ ውእቱ ቀደመ ነሢአ እንተ ይመስሎ ለአሮክስስ አበ አቡሁ ወአክሮስስ እምሔው እምድኅረ ሞተ ዝንቱ ዓዲ አምላክዎ ፋርስ ምስለ አመልክት እምድኅረ ሞተ ወልዱ ልዮስ ነግሠ በሶርያ እኅወ አቡሁ ወአውሳባ ለሳሚ ወአንበረ ሕገ ርኵስ ወአስተደኃረ ሎሙ ለእለ ይተልውዎ ወተሰምዩ በዝንቱ ስም እስከ ይዕዜ ወኮነ ዕቅፍተ ዘሮች በዕሥያ የቀሩት ያባቶቻቸውን ፈቃድ እየጣሉ እርግማን እየተቀበሉ ስለሆነ መምለኬ ጣዖትና ማኅደር አጋንንት በመሆናቸው ያሳዝናል እንጅ በጉልበትና በኃይል ደካማ ናቸው በሀገራቸው ላይ ሌላ የውጭ ሰው ነገሠባቸው የሚባል ታሪክ የተጻፈ አይገኝም። ካለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ የተጻፈ ስለ ፊደል መሠረት "ከ፫ኛ ክፍል ፴፫ ገጽ በጅ ከተጻፈው ነው ስለ ፊደል ተረክቦና ጥንት ስለ ትምህርቷም ሰማያዊነት ፊደልና ጥፈት ለአዳም ልጆች የተገለጠውና የተሰጡ በአዳም ዕድሜ ነው ከዚያውም በሳብዓይ ፪ ወሳልሳይ ትውልድ ይህም ከአዳም እስከ ሄኖክ ያለው ዘመን ፯ኛ ፻ቶ የሚሆነው በኢትዮጵያው ብሉይ ኪዳን ነው እንጅ በሌላው የዓለም ቤተ ክርስቲያን በተቀበለችው መጽሐፍ ፩፻፳ ብቻ ነው ፊደል በሄኖስ ነው ይላል ለአዳም ያልተገለጸ ስለምን በሄኖስ ተገለጠ ለዚህ ያመጡት ሐተታ እንዲህ ይላል "ሰው በግዜር ምሳሌ መፈጠሩ እንደመላእክት ሕያው

ሆን በሕገ ልቡና ሲኖር እንጅ በተፈጥሮ የተሰጠውን ሕግ ረስቶ እንደገና መጽሐፋዊ ሕግ ሊጥፍና ሊያስጥፍ ልቡናውን በመጽሐፍ ሊደግፍ ሕይወቱንም አጥቶ ሊቀበር እንደ ቅጠል ሊረግፍ አልነበረም። ብለዋል ይህም ከንቱ አስተያየት ነው እንጅ እውነት ሥራ አይደለም በግዜር ምሳሌ መፈጠሩ እንደ መላእክት ሕያው ሆኖ ሊኖር ብለዋል መላእክት መነሳታቸው ከሆነማ ይልቁንስ ባ፩ድ ሰዓት የሳተ ማነው። አዳምስ ቢስትም በ፯ት ዘመኑ ነው። በተፈጥሮ የተሰጠውን ሕግ ረስቶ እንደገና መጽሐፋዊ ሕግ ሊጥፍና ሊአስጥፍ ይላል። ሐተታ በተፈጥሮ የተሰጠውን ሕግ ማለት እንደምነው ፊደልና ጽሑፍን ሳያውቅ ማለት ነውን ወይስ ጽሕፈትና ፊደልስ አልፎ ሌላም ያውቅ ነበር ማለት ነው ግን

አሳብዎን ስለመከተው በፊት እውቀቱ በመጠን ነበር ካጠፋ በኋላ ግን እውቀቱ በዛለት ፊደልና ጽሕፈት ተገለበጠለት ማለትዎ ይመስላል። ውስጠ ምሥጢሩን በኩፋሌው ላይ ባይመለከቱት ነው እንጅ ተመልከተውት ቢሆን ምዕ ፫ ፪ ወበይዕቲ ዕለት አፈ ኵሉ አራዊት ወእንስሳ ዘያንስሱ ወዘይትኃውስ እምነቢብ እስመ ኵሎሙ ይትናገሩ ዝንቱ ምስለ ዝንቱ ከንፈረ ፩ደ ወልሳነ ፩ደ። ከጥፋት በፊት የአራዊትን የእንስሳትን ቋንቋ አዋቂ ነበር በኋላ ግን የእንስሳትንና የአራዊትን ቋንቋ ማወቅ ቀረቡት እንግዴህ በዚህ ሂሳብ አዳም ከበደለ በኋላ ጥበብ ከቀድሞው በለጠ ከማለት ጐደለ ተቀነሰበት ማለት አዋረዳቸው እንጅ እንደገና ካጠፉ በኋላ እውቀት ገለጠላቸው ማለት ማለት መንገዱ የተመቸ አይመስለኝም። ከክብራቸውም መዋረድ ማለት ሳይበድሉ አስቀድሞ በምድር የበቀለው ሁሉ የሚጣፍጥ ምግብ ስለነበረ ጣፋጮችን አትክልቶች ይዛ የነበረች ምድር ስሟ ገነት ነበር ገነት ማለት የተክል ቦታ መሆኑን ማስተዋል ነው።

# ኄ ኃሙስ ታኅሣሥ


ጣፋጮች አትክልት ሳሮች በተረገሙ ጊዜ ማለት ምድር በተረገመች ጊዜ የሳሮችና ያትክልቶች ጣዕም ተለወጠ ምድርም ነገት መባሏ ቀረ። ምድር ስለ መረገምዋ ማስረጃ ኦሪት ዘፍጥረት ፲፯ ርግምተ ትኩን ምድር ተግባርከ ወበኃስዘን ብላዕ ኵሎ መዋዕለ ሕይወትከ ያለውን ይመልከት እንደዚህ ካለ ውርደት ልፋት ያዘዘበት ስለ እውቀት መግለጽ ማለት ይሆንን ስለ ኩራታቸውም ኦሪት ዘፍጥረት ፩ ፳፱ ወይቤ እግዚአብ ወሀብኩክሙ ኩሎ ሣዕረ ዘይዘራዕ ወይበቍል ዘርው ተዘሪአ ዲበ ኵሉ ምድር ወኩሎ ዕፀወ ዘሀሎ ውስቴቱ ዘርዕ ዘይዘራዕ በፍሬሁ ለክሙ ውእቱ ሙብልዕ ፴ ስለ እንስሳቱም ማነኛውንም አደራጅቶ ሲሰጠው ጽሕፈትና ፊደል አልገለጸለትም ማለት ከንቱ ምርምር ነው እንጅ እርግጠኛ ከመጻሕፍቱ ምንጭ ይዞ የሚገኝ አይደለም። አዳምን ንጉሥ አልነበረም የሚል ይገኛል አይመስለኝም ለአዳም ፺ቱ ሀብታት አልነበሩትም የሚል ይገኛል አይመስለኝም። ስለዚህ አዳም ፊደልና ጽፈት አያውቅም ማለት ፊደልና ጽፈትን ሰዎች በመመራመር በኋላ አገኙት ለማለት ይመላል አጋዕዝተ ዓለምን ሲፈጥሩ በነቢብ ጭምር ነው። በነቢብ የተነገሩ ቃላት ኦሪት ዘፍጥረት ከ፫-፳፱ ያሉት ሲቆጠሩ ፱ኝ ናቸው የ፱ኝ ቍጥር መሠረት ጥልቅ መሆኑን ይህ ያስረዳል ይህን መሠረት በመመርኮዝ ሙሴ ኦሪቱን ሲዠምር በ፱ ቁጥር ስለሆነ በቃዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ ብሎ ዠመረ የፊደልን ቁጥር አጭበርብሮ ለማጥፋት ሲፈልጉ ይታያሉ እሽ ይሁን ዓለም በተፈጠረ ጊዜ ፊደል ከሌለ ለዕታቱ ካ፩ድ እስከ ፺ት በምን ተቈጠሩ። እነዚህ አሁን የሚገኙ አኀዞች ፊደሎች በዚያ ጊዜ አልነበሩም ለማለት ይታሰብ ይሆንን ስለ  ፊደላት ቁጥር የዓለም ባለታርኮች ሁሉ ጽፈውት ይገኛል የፊደልን ቁጥር ምሥጢር ያልመረመረው ሰው ጽሑፍ ከማንበብ ከመሽታ ቤት ገብቶ ወሬ ከማዳመጥ በጣም የተሻለ ነው ስለዚህ ዓለም ሲፈጠር ፊደል አልነበረም። ማለት ከንቱ ነው ሰማየ ሲል ሰ ፺ ፺ቱ ሰማዮች ወምድረ መ ፱ቱ ባሕርያትይህ ፊደል ማለት አይደለም ይሆንን። አዳምንና ኤዶምን በፊደል ቁጥር ማስተባበሩ ማለት አይደለም ይሆንን በሰማይ ፲፪ቱ ከዋክብት በምድርም ፲፪ቱ ነገደ ነገደ ፳ኤል ባ፲፪ሩ ፳ኤል ፲፪ቱ ሐዋርያት እነዚህ ሁሉ በቁጥር የተባበሩ ፩ድ ሆነው የሚገኙ

ማለት አይደሉም ይሆንን (ሄኖስን በራዕይ እንደ ሙሴ ስቦ ረቂቁን ሕግና ትእዛዝ አጉልተውና አግዝፈው የሚአሳዩ ዓይነ ልቡና መነጽሮች ፊደላትን ሰጠው ፳፪ቱን አሌፋን በ፳፪ሩ ሥነ ፍጥረት አምሳል በጸፍጸፈ ሰማይ ጽፎ አሳይቶ ወዲያው በልቡ እየሳለ ሥነ ፍጥረትን ፲ቱ ቃላትን በቃል ያ ፊደል ሥሎና መስሎ ስሙንም አሌፍ ብሎ ታው ለማሳየትና ለመስበክ ነው ይላል"። ፳፪ቱን ፊደላት በጸፍጸፈ ሰማይ ጽፎ አሳይቶ ወዲያው በልቡ እየሣለ ሥነ ፍጥረት ያስተምራቸው ዘንድ የተባለው ጽሑፍ ልብ ወለድ እንደሆነ መልካም ነው ማንም ከልቡ እያወጣ ሲጽፍ ሰነፍ ይከተላል መልካም ነው ማንም ከልቡ እያወጣ ሲጽፍ ሰነፍ ይከተላል ልብ ያለው ግን አሳልፎ አይቶ ይተወዋል መሠረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል አይደለም ለአዳም ሳይገለጽ የቀረ ለሄኖስ በምን ምክንያት የተገለጠ ፊደሎች እንደሆኑ በጸፍጸፈ ሰማይ የተቀረጹ ናቸው ይህም የሚታወቅበት ጥበብ አለ። ያመት ቀኖች በዕለት ሚያዝያ ፩ድ እሁድን ፩ እስከ መጋቢት

መጨረሻ ቀዳም ድረስ ያሉ ቀኖች ልክ ፫፻፷፬ ናቸው በጨረቃ ጽልመት ፩ድ ያለበትን ሚያዝያ ፳ ኃሙስን ፩ድ እስከ መጋቢት መጨረሻ ዕለት ቀዳም ድረስ

## ኀ ዓርብ ታኅሣሥ

ያሉትን ቀኖች ሲቆጥሩ ልክ ፫፻፷ ብቻ ይገኛል ስለዚህ የዓለም ሊቃውንቶች በክብ ሜትርና በዙሪያም ፫፻፷ ነጥብ ይገኛል። ፪ኛም ዛሬ የሰለጠኑት ጠቢባን ሰዓት ሠሪዎች በሚሠሩት ሰዓት እንደሚታየው ዋናዪቱ ቈጣሪ ፩ቱን ደቂቅ ስትቆጥር ደቂቃ ቆጣሪዋ ብዙሪያዋ ያሉትን ፷ውን ደቂቃ ታደርሳለች እንደዚህ እያለች እስከ ፮ት ሰዓት ፮ት ፷ ፫፻፷ ደግሞ እንደዚሁ እስከ ፲፪ቱ ሰዓት ፫፻፷ ሲደመር ፯፻፳ ይሆናል። ከላይም ፯፻፳ ያልነውን በዳዊት አምባ ስንመዝነው ፅዮን በኢትዮጵያ ፊደል ፀ ፮፻ የ ፺ ነ ፴ ድምር ፯፻፳ ይሆናል ከዚሁ ለሁለት ስትከፍለው ፫፻፷ ይደርሳል ይህን ፫፻፷ በመሬቱ ላይ ትእምርተ መስቀል ዘርግተውህ ባ፬ቱ ማዕዘን ስትመድበው ፺ ፺ ይደርሳል ፬ት ጊዜ ፺ ፫፻፷ ይሆናል ደግሞ ፫፻፷ውን በዙሪያው ፺ ፺ ስትመድበው ልክ ፬ት ጊዜ ፺ ፫፻፷ ይሆናል።




የኢትዮጵያ ፊደሎች የአዳምና የመላእክት መነጋገሪያ ነበሩ ብየ ስናገር ባ፩ድ ፩ድ ሰዎች ዘንድ ቃል ስጋ አልሆነም ብየ እንደተናገርኩ አድርገው ስለሚቆጥሩት የግዕዝ ፊደሎችና ፺ቱ ዕለታት ተባብረው በወር እየተሠፈሩ ያመቱ ከመንፈቅ ፻፹፪ቱ በምሥራቅ ተመዝነው የተጻፉትን አስተዋይ ሲመለከት ፳፮ እሁድ ይገኛል። እሁድ ስለተባለ መለያው ለየራሳቸው ቊጥር ለ፺ቱም ፊደሎች እንዳላቸው በሰንጠረዥ የተጻፈውን አስተውሎ መመልከት ነው።

# ኆ ቀዳም ታኅሣሥ

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | ሀ | ግዕዝ | እኍድ | ፩ | ሁ | ካዕብ | ሰኑይ | ፪ | ሂ | ሣልስ | ሠሉስ | ፫ | ሃ | ራብዕ |
| ፪ | ለ | ግዕዝ | እኍድ | ፪ | ሉ | ካዕብ | ሰኑይ | ፬ | ሊ | ሣልስ | ሠሉስ | ፮ | ላ | ራብዕ |
| ፫ | ሐ | ግዕዝ | እኍድ | ፫ | ሑ | ካዕብ | ሰኑይ | ፮ | ሒ | ሣልስ | ሠሉስ | ፱ | ሓ | ራብዕ |
| ፬ | መ | ግዕዝ | እኍድ | ፬ | ሙ | ካዕብ | ሰኑይ | ፰ | ሚ | ሣልስ | ሠሉስ | ፲፪ | ማ | ራብዕ |
| ፭ | ሠ | ግዕዝ | እኍድ | ፭ | ሡ | ካዕብ | ሰኑይ | ፲ | ሢ | ሣልስ | ሠሉስ | ፲፭ | ሣ | ራብዕ |
| ፮ | ረ | ግዕዝ | እኍድ | ፮ | ሩ | ካዕብ | ሰኑይ | ፲፪ | ሪ | ሣልስ | ሠሉስ | ፲፰ | ራ | ራብዕ |
| ፯ | ሰ | ግዕዝ | እኍድ | ፯ | ሱ | ካዕብ | ሰኑይ | ፲፬ | ሲ | ሣልስ | ሠሉስ | ፳፩ | ሳ | ራብዕ |
| ፰ | ቀ | ግዕዝ | እኍድ | ፰ | ቁ | ካዕብ | ሰኑይ | ፲፮ | ቂ | ሣልስ | ሠሉስ | ፳፬ | ቃ | ራብዕ |
| ፱ | በ | ግዕዝ | እኍድ | ፱ | ቡ | ካዕብ | ሰኑይ | ፲፰ | ቢ | ሣልስ | ሠሉስ | ፳፯ | ባ | ራብዕ |
| ፲ | ተ | ግዕዝ | እኍድ | ፲ | ቱ | ካዕብ | ሰኑይ | ፳ | ቲ | ሣልስ | ሠሉስ | ፴ | ታ | ራብዕ |
| ፲፩ | ኀ | ግዕዝ | እኍድ | ፳ | ኁ | ካዕብ | ሰኑይ | ፵ | ኂ | ሣልስ | ሠሉስ | ፷ | ኃ | ራብዕ |
| ፲፪ | ነ | ግዕዝ | እኍድ | ፴ | ኑ | ካዕብ | ሰኑይ | ፷ | ኒ | ሣልስ | ሠሉስ | ፺ | ና | ራብዕ |
| ፲፫ | አ | ግዕዝ | እኍድ | ፵ | ኡ | ካዕብ | ሰኑይ | ፹ | ኢ | ሣልስ | ሠሉስ | ፻፳ | ኣ | ራብዕ |
| ፲፬ | ከ | ግዕዝ | እኍድ | ፶ | ኩ | ካዕብ | ሰኑይ | ፻ | ኪ | ሣልስ | ሠሉስ | ፻፶ | ካ | ራብዕ |
| ፲፭ | ወ | ግዕዝ | እኍድ | ፷ | ዉ | ካዕብ | ሰኑይ | ፻፳ | ዊ | ሣልስ | ሠሉስ | ፻፹ | ዋ | ራብዕ |
| ፲፮ | ዐ | ግዕዝ | እኍድ | ፸ | ዑ | ካዕብ | ሰኑይ | ፻፵ | ዒ | ሣልስ | ሠሉስ | ፪፻፲ | ዓ | ራብዕ |
| ፲፯ | ዘ | ግዕዝ | እኍድ | ፹ | ዙ | ካዕብ | ሰኑይ | ፻፷ | ዚ | ሣልስ | ሠሉስ | ፪፻፵ | ዛ | ራብዕ |
| ፲፰ | የ | ግዕዝ | እኍድ | ፺ | ዩ | ካዕብ | ሰኑይ | ፻፹ | ዪ | ሣልስ | ሠሉስ | ፪፻፸ | ያ | ራብዕ |
| ፲፱ | ደ | ግዕዝ | እኍድ | ፻ | ዱ | ካዕብ | ሰኑይ | ፪፻ | ዲ | ሣልስ | ሠሉስ | ፫፻ | ዳ | ራብዕ |
| ፳ | ገ | ግዕዝ | እኍድ | ፪፻ | ጉ | ካዕብ | ሰኑይ | ፬፻ | ጊ | ሣልስ | ሠሉስ | ፮፻ | ጋ | ራብዕ |
| ፳፩ | ጠ | ግዕዝ | እኍድ | ፫፻ | ጡ | ካዕብ | ሰኑይ | ፮፻ | ጢ | ሣልስ | ሠሉስ | ፱፻ | ጣ | ራብዕ |
| ፳፪ | ጰ | ግዕዝ | እኍድ | ፬፻ | ጱ | ካዕብ | ሰኑይ | ፰፻ | ጲ | ሣልስ | ሠሉስ | ፩ሺ፪፻ | ጳ | ራብዕ |
| ፳፫ | ጸ | ግዕዝ | እኍድ | ፭፻ | ጹ | ካዕብ | ሰኑይ | ፩ሺ | ጺ | ሣልስ | ሠሉስ | ፩ሺ፭፻ | ጻ | ራብዕ |
| ፳፬ | ፀ | ግዕዝ | እኍድ | ፮፻ | ፁ | ካዕብ | ሰኑይ | ፩ሺ፪፻ | ፂ | ሣልስ | ሠሉስ | ፩ሺ፰፻ | ፃ | ራብዕ |
| ፳፭ | ፈ | ግዕዝ | እኍድ | ፯፻ | ፉ | ካዕብ | ሰኑይ | ፩ሺ፬፻ | ፊ | ሣልስ | ሠሉስ | ፪ሺ፩፻ | ፋ | ራብዕ |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፳፮ | ፐ | ግዕዝ | እኁድ | ፰፻ | ፑ | ካዕብ | ሰኑይ | ፩ሺ፮፻ | ፒ | ሣልስ | ሠሉስ | ፪ሺ፬፻ | ፓ | ራብዕ |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ፬ | ሄ | ኃምስ | ሐሙስ | ፭ | ህ | ሣድስ | ዓርብ | ፮ | ሆ | ሳብዕ | ቀዳም | ፯ | ፩ |
| ፰ | ሌ | ኃምስ | ሐሙስ | ፲ | ል | ሣድስ | ዓርብ | ፲፪ | ሎ | ሳብዕ | ቀዳም | ፲፬ | ፪ |
| ፲፪ | ሔ | ኃምስ | ሐሙስ | ፲፭ | ሕ | ሣድስ | ዓርብ | ፲፰ | ሖ | ሳብዕ | ቀዳም | ፳፩ | ፫ |
| ፲፮ | ሜ | ኃምስ | ሐሙስ | ፳ | ም | ሣድስ | ዓርብ | ፳፬ | ሞ | ሳብዕ | ቀዳም | ፳፬ | ፬ |
| ፳ | ሤ | ኃምስ | ሐሙስ | ፳፭ | ሥ | ሣድስ | ዓርብ | ፴ | ሦ | ሳብዕ | ቀዳም | ፴ | ፭ |
| ፳፬ | ሬ | ኃምስ | ሐሙስ | ፲፫ | ር | ሣድስ | ዓርብ | ፴፪ | ሮ | ሳብዕ | ቀዳም | ፴፪ | ፮ |
| ፳፰ | ሴ | ኃምስ | ሐሙስ | ፴፭ | ስ | ሣድስ | ዓርብ | ፵፪ | ሶ | ሳብዕ | ቀዳም | ፵፱ | ፯ |
| ፴፪ | ቄ | ኃምስ | ሐሙስ | ፵ | ቅ | ሣድስ | ዓርብ | ፵፰ | ቆ | ሳብዕ | ቀዳም | ፶፮ | ፰ |
| ፴፮ | ቤ | ኃምስ | ሐሙስ | ፵፭ | ብ | ሣድስ | ዓርብ | ፶፬ | ቦ | ሳብዕ | ቀዳም | ፷፫ | ፱ |
| ፵ | ቴ | ኃምስ | ሐሙስ | ፶ | ት | ሣድስ | ዓርብ | ፷ | ቶ | ሳብዕ | ቀዳም | ፸ | ፲ |
| ፹ | ኄ | ኃምስ | ሐሙስ | ፩፻ | ኅ | ሣድስ | ዓርብ | ፻፳ | ኆ | ሳብዕ | ቀዳም | ፻፵ | ፳ |
| ፩፻፳ | ኔ | ኃምስ | ሐሙስ | ፻፶ | ን | ሣድስ | ዓርብ | ፻፹ | ኖ | ሳብዕ | ቀዳም | ፪፻፲ | ፴ |
| ፻፷ | ኤ | ኃምስ | ሐሙስ | ፪፻ | እ | ሣድስ | ዓርብ | ፪፻፵ | ኦ | ሳብዕ | ቀዳም | ፪፻፹ | ፵ |
| ፪፻ | ኬ | ኃምስ | ሐሙስ | ፪፻፶ | ክ | ሣድስ | ዓርብ | ፫፻ | ኮ | ሳብዕ | ቀዳም | ፫፻፶ | ፶ |
| ፪፻፵ | ዌ | ኃምስ | ሐሙስ | ፫፻ | ው | ሣድስ | ዓርብ | ፬፻፳ | ዎ | ሳብዕ | ቀዳም | ፬፻፳ | ፷ |
| ፪፻፹ | ዔ | ኃምስ | ሐሙስ | ፫፻፶ | ዕ | ሣድስ | ዓርብ | ፭፻፵ | ዖ | ሳብዕ | ቀዳም | ፬፻፺ | ፸ |
| ፫፻፳ | ዜ | ኃምስ | ሐሙስ | ፬፻ | ዝ | ሣድስ | ዓርብ | ፮፻ | ዞ | ሳብዕ | ቀዳም | ፭፻፷ | ፹ |
| ፫፻፷ | ዬ | ኃምስ | ሐሙስ | ፬፻፶ | ይ | ሣድስ | ዓርብ | ፩ሺ ፪፻ | ዮ | ሳብዕ | ቀዳም | ፮፻፴ | ፺ |
| ፬፻ | ዴ | ኃምስ | ሐሙስ | ፭፻ | ድ | ሣድስ | ዓርብ | ፮፻ | ዶ | ሳብዕ | ቀዳም | ፯፻ | ፻ |
| ፰፻ | ጌ | ኃምስ | ሐሙስ | ፩ሺ | ግ | ሣድስ | ዓርብ | ፩ሺ፪፻ | ጎ | ሳብዕ | ቀዳም | ፩ሺ፬፻ | ፪፻ |
| ፩ሺ፪፻ | ጤ | ኃምስ | ሐሙስ | ፩ሺ፭፻ | ጥ | ሣድስ | ዓርብ | ፩ሺ፰፻ | ጦ | ሳብዕ | ቀዳም | ፪ሺ፩፻ | ፫፻ |
| ፩ሺ፮፻ | ጴ | ኃምስ | ሐሙስ | ፪ሺ | ጵ | ሣድስ | ዓርብ | ፪ሺ፬፻ | ጶ | ሳብዕ | ቀዳም | ፪ሺ፰፻ | ፬፻ |
| ፪ሺ | ጼ | ኃምስ | ሐሙስ | ፪ሺ፭፻ | ጽ | ሣድስ | ዓርብ | ፫ሺ | ጾ | ሳብዕ | ቀዳም | ፫ሺ፭፻ | ፭፻ |
| ፩ሺ፬፻ | ፄ | ኃምስ | ሐሙስ | ፫ሺ | ፅ | ሣድስ | ዓርብ | ፫ሺ፮፻ | ፆ | ሳብዕ | ቀዳም | ፬ሺ፪፻ | ፮፻ |
| ፪ሺ፰፻ | ፌ | ኃምስ | ሐሙስ | ፫ሺ፭፻ | ፍ | ሣድስ | ዓርብ | ፬ሺ፪፻ | ፎ | ሳብዕ | ቀዳም | ፬ሺ፱፻ | ፯፻ |

፫ሺ፱፻ ፔ ኃምስ ሐሙስ ፬ሺ ፕ ሣድስ ዓርብ ፬ሺ፫፻ ፖ ሳብዕ ቀዳም ፭ሺ፮፻ ፫፻

# ተሰውሮ የኖረ

የኢትዮጵያ ልጆች ሆይ የኢትዮጵያ ፊደል መሠረት ሲመረመር የመሠረቱ መገኛ ትልቅ ነው። የቀድሞዎቹ አባቶቻችን ማነኛውንም ምሥጢር ለመጻፍ ወይም በሥውር ለማስቀመጥ እንደዚህ ስለው እየጻፉ ያስቀምጡት የነበረውን እንድትለምዱትና እንድትከታተሉት ጽፌላችኋለሁ።

ከላይ ከሀ መጨረሻ ዝምራችሁ ፯ቱን ፩ድ እያላችሁ እስከ መጨረሻ ለ፯ት እያካፈላችሁ ስትወርዱ ከመጨረሻው ያለውን ቁጥር በማስተዋል ስትከመለከቱት በ፳፮ቱ ፊደላት መጨረሻ ከ፯ት እስከ ፭ሺ፮፻ ያለውን ቁጥር ለ፯ት እየመደባችሁ ስትሄዱ ፫፻ ታገኛላችሁ። የጥበቡ ምንጭና በር መሆኑን እንዳትዘነጉ። የተጻፉ የፊደሎች ዘርዕ ፳፮ በ፯ት ደረጃ ሲበዙ ፻፹፪ ናቸው። በነዚህ የተጻፉ መጻሕፍተ ቃላት ለጊዜው የተለቀሙ አንቀጽነት ያላቸው ፬ሺ፩፻፵፫ ጥሬ ዘር የሆኑ የሌላቸው ፺ሺ፩፻፴፩ ቃላት ናቸው። ለጊዜው እነዚህን ተደግፎ ደግሞ ይለቀማል።

ከላይ የግዕዝን ፊደሎች የወጡበትን ሱባዔ ማስተዋል አለ የግዕዝ ትርጓሜ ነፃነት መሆኑን ለመረዳት ኦሪት ዘፀዓት ፲፪ ፴፯ "ግዕዙ ደቂቀ ፳ኤል እምራማሴ ውስተ ሰኮታ ፫፻፶" ያለው ሲተረጐም ያዕቆብ ወደ ግብጽ ሲሄድ ፸፭ ነፍስ ስለነበር ፫፻፶ ትስመድበው ፫ሽ ይሆናል። ፸፭ት የነበሩት የያዕቆብ ልጆች በቁጥር ፫ሽ ሆኑ ብሎ በምሥጢር ከግብጽ ባርነት ነፃ ወደሚወጡበት ምድር ርስት ጉዞ መዝመራቸውን ግዕዙ ፳ኤል ብሎ አመለከተ።

ከላይ በተዘረዘረው ሠንጠረዥ ከሀ አንድ ቁጥር እሁድ ዝምሮ እስከ ፖ ቀዳም ፭ሽ፮፻ ቁጥር የተዘረዘሩት ዕለታቱና ፊደሎቹ ጥልቅ መሠረት አላቸው። ፩ኛ እሁድ ያለው ሚያዝያ ፩ የተባለውን እሁድ ነው። ፪ኛ ፖ ቀዳም ፭ሽ፮፻ ቁጥር ያለው ያመቱ መንፈቅ የመስከረም ወር መጨረሻ ቀዳምን ነው። ስለዚህ ከላይ በሰንጠረዡ የተዘረዘሩትን ዕለታቱና ፊደሎቹን ለሚያዝያ ፴ ለግንቦት ፴ ለሰኔ ፴፩ ለሐምሌ ፴ ለነሐሴ ፴ ለመስከረም ፴፩። ሲመደቡ መትረፍና መጉደል ሳይኖር ልክ ፻፹፪ ሆነው ይገኛሉ። እንደዚህ የሆነው ፯ ወሮች ኄኖክ እንደጻፈው ፯ቱ መስኮቶች በምሥራቅ ፯ቱ መስኮትች በምዕራብ ባለው መሠረት የግዕዝ ፊደሎች ያመቱ ቀኖች የሚገኙባቸው መሆኑን መረዳት ለኢትዮጵያ ልጅ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ አለ።

በጣም ለመረዳት ፫፻ን በ፸፭ት ሲአበዙት ፫፻፶ ይመጣል ፫፻፶ን ለ፸፭ ሲመድቡት ፫ሽ ቁጥር ይመጣል ፫ሽን ለ፲ ሲመድቡት ፫፻ ይመጣል ፫፻ን ለ፲ር ሲመድቡት ፴ ቁጥር ይመጣል ፴ያ ቁጥር ክርስቶስ ሲል ነው። ክርስቶስ ማለት የነፃነት ጌታ ማለት መሆኑን ለሚያምኑ ክርስቶሳውያን ክርስቲያኖች ሁሉ መሠረት ትርጓሜ የሚገኝበትን ግዕዝን መርምረው እንዲረዱ ለዓለም ሕዝበ ክርስቲያኖች ሳስታውስ በትህትና ነው።

ይህን መርምሮ ለመጻፍ የተነሣሁበት የኢትዮጵያ ተቃራኒ የሆኑ ሰዎች በረቂቅ ፖለቲክ መጪውን ትውልድ ከመሠረቱ ለማስለቅ ፬ሽ፫፻ ፵ ዘመን ዕድሜ ከካም ወደ ኩሳ ዘር ተላልፎ።

# ኖ ቀዳም ታኅሣሥ

ሲያያዝ የመጣውን ፩ኛውን ቋንቋ ለማጥፋት ስፍራ ሲፈልጉለት ስላየሁ ነው።

በጸፍጸፈ ሰማይ ዙሪያ ምልክት ሆነው ተጽፈው የሚገኙ በግዕዝ ፊደል ነው። ይህም የሚታወቀው በሄኖክ ሚዛን ሲመዘን ነው። እሱም በሚጠተ ብርሃናት ይገኛል። ግዕዝን በኋላ ነው የመጣ የሚሉ ሰዎች ሁሉ ዋና መረጃቸው ይህ

በጸፍጸፈ ሰማይ የተጻፈው ፊደል ባመቱ ቀኖች ልክ ግዕዝ ግዕዙ እሁድ ካዕብ የሚለው በሰኞ ሣልስ የሚለው በማክሰኞ ራብዕ በረቡዕ ኃምስ የሚለው በኃሙስ ሣድስ የሚለው በዓርብ ሳብዕ የሚለው በቀዳም እንደዚህ እየሆነ ነው ሚያዝያ ፩ድ ብሎ እስከ መስከረም መጨረሻ ፫፻፷፭ ቀኖች ናቸው። ከነዚሁ ወሮች ሚያዝያ ግንቦት ፴ ፴ ቀኖች ናቸው ሰኔ ፴፩ ቀን ነው። ሐምሌ ነሐሴ ፴ ፴ ቀኖች ናቸው መስከረም ፴፩ ፫፻፷፭ ቀኖች የተባሉ እነዚህ ናቸው የኢትዮጵያ ፊደሎች ፶፪ ናቸው በ፯ ዕለታት ምሳሌ በሆነው ቁጥር በ፯ት ሲበዙ ፫፻፷፭ ይሆናሉ እነዚህን ሄኖክ ሲመዝን ስለ ፀሐይና ጨረቃ መውጫ ፯ቱን በምሥራቅ ፯ቱን በምዕራብ ከምሥራቅ ባሉት መስኮቶች ትይዩ በምዕራብ የሚገኙት የ፯ቱን መስኮቶች ቁጥር ተመልክቶ የሚገኘው ከምሥራቅ ባሉት ፊደሎች ነው። ይህን በጥብቅ ማስተዋል ነው በምሥራቅ ባለው ትይዩ የምዕራብ መሆኑን ማስተዋል ነው ስለዚህ በምዕራብ ፫፻፷፭ቱ ፊደሎች ከምሥራቅ መሆኑን ማስተዋል ነው ስለዚህ በምዕራብ ፫፻፷፭ቱ ፊደሎች

ከምሥራቅ ፫፻፷፭ ፊደሎች ምሥራቁንና ምዕራቡን ፩ድ የሚአደርጉ ፀሐይና ጨረቃ የሚገቡና የሚወጡበትን የሚጠብቁ ቁጥሮች ፊደሎች ናቸው መዝኖ መረዳት ላስተዋይ ገንዘቡ ስለሆነ መርምሮ መረዳት የተገባ ነው። የነዚህን ጥበብ ከመጽሐፈ ሄኖክ ያልተመለከቱ ሰዎች ግዕዝን በኋላ የተገኘ ዲቃላ ፊደል ለማድረግ ሲደክሙ ይታያሉ ከንቱ ድካም ነው። (ባ፬ኛ ክፍል በ፵፪ኛ ገጽ ፊደል ማለት የቋንቋና የቃል ያነጋገር ሁሉ ምልክት መግለጫ ማለት ነው። በግዕዝም ፊደል ብሎ ጣፈ ቀረጠ ለየ መረጠ ይላልና ፊደል ከዚህ ይወጣል። ልዩ ምርጥ ማለት ነው ዓረቦች ኃርፍ እብውቅያን ኦት ይሉታል በተገኘ ምልክት ማለት ነው። ፪ኛ የግዕዝ ሥር መሠረት የትግሬና ያማርኛም ጥንት እሊህ ናቸው አ በ ገ ደ ሀ ወ ዘ ሐ ኀ ጠ የ ከ ለ መ ነ ሠ ፈ ጸ ፀ ቀ ረ ሰ ተ ፐ።" ከላይ የተጻፉትን ፊደሎች ለማደናገርና ለማታለል እንደ እብራውያን ከአ ከዘመሩ በኋላ ደግሞ ወደ ግዕዙ ተመልሰው በእብራይስጡ ፊደል የሌሎትን ፬ት ፊደሎች ጨምረው ቁጥራቸውንም እንደ ግዕዙ ፳፮ት መጨረሻውንም ፐ አድርገው ጽፈውታል። እዚህ ላይ በእብራዊ ፊደልም በግዕዝም ያለውን የፊደል ቁጥር ሁለቱንም አደባልቀውታል የፊደል ቁጥር መኖሩን የዓለም ባለታሪኮች አውቀው የግዕዙን ፊደል ቁጥር ፳፮ የእብራይስጡንም ፊደል ፳፪ አድርገው ጽፈውት ይገኛል ይህን ባለታሪኮች የጻፉት ይገኛል ባይሆን የካዕቡንና የሣልሱን የራብዑን የኃምሱን የሣድሱን የሳብዑን ቁጥር ስንኳንስ በውጭ አገሮች በኢትዮጵያውያንም ሊቃውንቶች እንደምሥጢር በሥውር ስለሚያኖሩት ብዙዎች ይህን አያውቁትም እንጅ ግዕዙን ብቻ ፊደል ቍጥር አውቀው ፳፮ ብለው ጽፈውት ይገኛል በምን ምክንያት ይመስላል ይህ የተዘባረቀ ፊደል መሠረቱ ከወዴት የመጣ ነው ከዚህ ከሮማ ልዑካን ነው። "የፊደል ሁሉ እራስ አርስቱና መዝመሪያው መነሻ አልፋ ኦ ስለሆነ ፊደል ሁሉ በአ ዝምሮ በማናቸውም ይጨርሳል። ምንም መዝመሪያው

## ነ እሁድ ታኅሣሥ

፩ድ ቢሆን መጨረሻው ከርሱርትና እብራዊው አይተባበርም)። ከሱርስትና ከእብራዊው ካልተባበረ በምን ምክንያት እንደዚህ ተደባልቆ ተጽፈ። (ዓረብና ጽርዕ ሮማይስጥ በየ በዘ ይጨርሳሉ ሌላውም ሁሉ እንደዚህ ነው)። እንግዴህ የግዕዝ ጓደኝኖች እነዚህ ማለት መሆናቸው ከሆነ በዓለም ሊቃውንት መዝገብ የገቡትን ከሰናዖር ግምብ መፍረስ ዝምሮ የቆዩበትን ታሪካቸውን ለመረዳት እፈልጋልሁ። እነዚህ ፊደሎች በቅዱስ መጽሐፍ ላይ እንደ ግዕዝ ዋና የትርጓሜ መሠረት ይዘው አይገኙም። ግዕዝ ፊደል የሚይዘውን ሁሉ ከላይ አመልክቸ ይገኛል (ከጥንት ከአበው ከሄኖስ ከቃይናን በኋላም ከዔቦር ከነገድ የግዕዝ ፊደል ግን ኀን ከሐ ጸን ከፀ ደርቦ ዘሩ ፳፪ት ብቻ ስለሆነ ተራውና ስሙ ሳይፋለስ እንደ እብራይስጥ በእልፍ ዝምሮ ቦታው ይጨርሳል) እንግዴህ በአ ዝምሮ በታው የሚጨርስ በመሆኑ ፪ኛ ከ፫ቱ ሀ ሐ ኀ ፩ዱን ኀን ከ፪ቱ ፀጸ ፩ዱን ፀን አስቀርቶ ፳፪ት ብቻ ስለሆነ ተራውና ስሙ ሳይፋለስ። ይላል) ተራው አልተፋለሰም ከተባለ ከላይ የተጻፈው በአ ዝምሮ በፐ እየጨረሰ የተጻፍው የእብራይስጡን ተራ። ቁጥር ይዟል ለማለት ታስቦ

ይሆንን ይህ ሁሉ ውሸት ነው። (፫ኛ ፪ቱ ፊደላት ጰና ፐ ግን የተጨመሩ በኋላ ነው መጨመራቸውም መጻሕፍት ከተቀዱበት ምንጭ ከጽርዕ ከዮናን ለመስማማት እንጅ በግዕዝ ፊደላት ገጽ ኑሮ አይደለም ከ፪ቱ ደግሞ መደበኛ ፐ ነው ምንም በመልክና በቅርጽ በመጥበቅና በመላላት ፪ት መስለው ታይተው ፪ት ቢባሉ ፊደልነታቸው ፩ድ ነው። ሲላላ ፐ ሲጠብቅ ጰ ይባላል በጰ መልክና ቅርጽ ከደ የወጣ ነው እንጅ ከጽርዕ በላቲን ተ ይባላል ፈ ማለት ነው እብራውያንም ነቁጣ ጨምረው ፈን ፐ ይሉታል ቁጥሩም በጽርዕና በቅብጥ በእብራይስጥ ፈ ፹ ነው)። ይኸውና እዚህ ላይስ የእብራውያን ፊደል ቁጥር ብቅ አለ። ፈ ፹ ቁጥር መሆኑ ታመነ። ከላይ የተጻፈው የፊደል መሠረት የተባለው ቁጥሩ ስለምን ተዘባረቀ የግዕዝ የእብራዊውም የፊደል ቁጥር ተደባልቋል። አሁን ግን የእብራዊው ፊደል ብቅ አለ። ይህ

ሁሉ ድካም የኢትዮጵያን መሠረት ለማሳነስ መንግሥቷንና ቤተ ክህነቷን ለመውረስ በታሰበው ሸንጎ ከጠላት ጋራ ከተዋዋሉ በገንዘብ እየገዙ የሚአመጡት የሐሰት ፐለቲክ ስብከት ነው እንጅ እርግጠኛ አይደለም። (አኅዛችን ሁሉ የጽርዕና የቅብጥ ፊደል እንደሆነ ኋላ በቦታው እናመጣዋለን ጰ ከጋልኛ እንዲስማማ ፐ ደግሞ ከወላሞዎች ይስማማል)። ይህ ሁሉ ድካም እንዲሁ ከልብ አዲስ የተፈጠረ እንጅ መሠረት ያለው ነገር የለም "፬ኛ ጰና ፐ ለግዕዝ ቋንቋ በውድ በግድ አያስፈልግም እነሆ ዓረቦች ጴጥሮስ ጳውሎስ ጲላጦስ ፓጥሮስ ፓውሎስ ፒላጦስ በማለት ፋንታ ቡጥሩስ ቡሉስ ብለውስ ይላሉ እብራውያንም ፊጥሮስ ፎሎስ ፊላጦስ ይላሉ። በግዕዝም በጰና በፐ ፋንታ በ ወይም ፈ ይበቃ ነበር"። ይህን ሁሉ ድካም ለወጣቶች ለማስጠናት ነው የደከሙት እንደምን ይህን የመሰለ ሥራ በኢትዮጵያ ተወልዶ ሲሆን ከጠላት ጋራ ይከራከራል ባይሆንስ ደግሞ ጠላት በረቂቅ ተንኮል የኢትዮጵያን ታሪክ ለማጉደል ያመጣውን ፖለቲክ ስብከት ተቀብሎ የወጣቶችን ልብ ለማፍዘዝና ለማደንዘዝ ይህን ሁሉ የፖለቲክ ጭቃ እሰክ አንገቱ የሚአቦካ ምን ይባላል ይህን

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |



ትዮጵያ፡ሊቀ፡ካህናት፡እንበረም፡ፍሬምናጦስንና፡ኦድስዮስን፡ኦክ.ሃም
ራዱ፡ቃል፡በምትባል፡ቦታ፡ግዕዝ፡ፊደል፡ሲያስተምር።ጃቱ፡ቅዱሳንም፡ግዕዝ፡
የተማሩ፡በዚሁ፡ቦታ፡ነው።

## ኑ ሰኑይ ታኅሣሥ

የ ጠላት እንኳ እንደምን ይታዘብ ይሆን ፊደሎቹ ምን አስቸገሩ የተጠሉበት ምክንያት ታሪክን ይዘው በመገኘታቸው ነው። (ከጽርዕና ከቅብጥ ከሮማይስጥ የመጣ ጥሬና ነባር ስም ካልሆነ በቀር በግዕዝና ባማርኛ በትግርኛም ሳይቀር ጳንና ፐን የሚአስፈልግ ቃል የለንም። ከጥንት የነበረ የግዕዝ ፊደል አለመሆኑ ቅድምና ዝምድና የሌለው ባዕድና ደባል የኋላ ቅጥል መሆኑ በዚህ ይታወቃል ተብሏል) የሮማ ልዑካን ዳቦና ሻይ እንደዚህ ያናግራል። ጳና በ በኋላ የተገኙ ናቸው ተባለና ጽሑፉ ተሰናዳ ተሰውሮ የተሠራው ሁሉ በግልጽ ቦታ መውጣቱ የማይቀር ስለሆነ ይኸውና የተሠራ በሥውር ነበር አሁን ወደ መታየት ወጣ። "የግዕዝ ፊደልስ ቢሆን ስንኳን ከግዕዝ ካማርኛ ከትግሬ ከትግርኛ ባልታጣም ነበር አባታቸው ግሥ ነውና በግሥም ውስጥ ገንጸለ ሄጰ ዴፐ ጸንጰወ እያለ ቢገኝ ሁሉም በበና በፈ ፋንታ የገባ ነው)። ይኸውና ተሰናዳ እንግዴህ ጳና ፈ ከኢትዮጵያ ወጥተው እንዲጠፉ ትእዛዝ ወደ ኢትዮጵያ ወጣቶች መተላለፉ ማለት ነው እንዲጠፉ ትእዛዝ ወደ ኢትዮጵያ ወጣቶች መተላለፉ ማለት ነው ያሳዝናል። እንዴት አንድ ሰዓት አብሮ ለማይቆይ ሻይ ሰው የሆነ ሰው የዘለዓለም ታሪኩን ወደ ኋላ ለመወቀስ ጥሎ ይሄዳል። አባ ጋስፓሪን ቢጽፉ ጻፉ ተብለው ፍርዱ ቀሊል ነው የሚደንቀውና የሚገርመው የኢትዮጵያ ልጆች እያወቁ አባታቸው የተወጋበትን ጦር ሲሰሙ የሚገኙት ናቸው እንጅ ሮማውያን ፍርድ የለባቸውም። (ግዕዝ ማለት ዋህድ ማለት ነው አንድ እንደ ማለት አንድነቱንም ፳ት ዓጽቅ አለው። በተቋመ ወርቅ ይመስላል ግዕዝ የቋንቋና የፊደል ስም ሲሆን በአልፍአ እንጅ በዓይን አይጣፍም)። የመበየን ታሪክ ይጻፉል እርግጠኛ ምሥጢር አለ የሚል ትርጓሜውን ገልጦ ነው እንጅ እንዲሁ ትእዛዝ ተገቢ ሥራ አይደለም የምሥጢሩ መገኛማ ቁጥር ተሰረዘ ቁጥሩ ካልተጠበቀ በምን ሊታወቅ ይችላል። ከክርስቶስ ልደት በፊት በዘመነ ብሉይ ኋላም በዘመነ ሐዲስ እስከ አብርሃ ወአጽብሐ ዘመን ድረስ ካዕብ ሣልስ ራብዕ ኃምስ ሳድስ አልነበረም። በግዕዝ ብቻ ይጥፉበትና ያነቡበት ነበር። ግዕዝ የተባለ ስለዚህ ነው። ፳ኛ ይኸውም ሊታወቅ በጥንታዊ ፊደል ተጥፎ በአክሡም ሐውልት የተገኘ ጥንትዊ የግዕዝ ንባብ እንዲህ ይላል ዘሐወለት /ዘአገብረ/አገዘ/ለአበወኅ /ወሰበሀ/ መሐዘተ/ አወየ/ ለነ ፀበለነ ወሀለፈነ/ ወመጸ/ ነገሠ/ ወፈተወ/ ወነገሠ/ አነዘ/ሀለከ/ በአከሠመ/ ዘከመ/ ገዐዘ/ አበወሀ/ በነደየ/ ፀወወነ/ ፀወ/ መፀ/ አከሠመ/ ወሃዐየ/ ዘአደወየ/ ወወከሐ/ ዘመጻአ/ አመ/ ቀደመ የተከዐወ/ ደመ/ ተነየከ/ ነገሠ/ አከሠመ/ ወፈነወከወ/ የነጸረ/ አከሠመ/ በሀገረ/ መነገሠተየ ይህን የመሰለ ሁሉ ብዙ ዓሳብ አለ መልክዓ ፊደሉም እንደ ሰው መልክ ብዙ ጊዜ በየ ዘመኑ ተለዋውጧል ከፊተኞቹ የኋለኞቹ አሻሽለውታል አሠራሩንም ከሶርያና ከፊንቂ አመሳስለውታል ካህኑ ዕዝራ እብራይስጥን ከአሶር ፊደል ቋንቋነቱን ፊደላቱ ያረጀና ያፈጀ ግዕዝ ብቻ ሆኖ ባዲሱ ዘመን አነጋገር ንባብ የሚአከፋ ምሥጢር የሚአጠፋ አፍ የሚአስከፍት ነገር የሚአስጐትት ስለሆነ ከሣቴ ብርሃን ሰላማ በዘመነ ሐዲስ መጻሕፍትን ከጽርዕ ወደ ግዕዝ ሲመልስ በግዕዝ ብቻ ለመተርጐም አልመችህ ቢለው ያይሁዶችንና የጽርዖችን ፊደል እንደቋንቋው ሥርዓት ድምጥ እየለወጠ በሚአስኬድ በነቁጣ በዋየል ፋንታ ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያሉትን ፳ት አዕፁቅ አግብቶ በጽርዕ ቋንቋ ሸ የሚሉ ፊደል ስለሌለ ሳን ሸ ብሎ ከሸነቱ አውጥቶ በንባቡና ባገባቡ ከጽርዕ ፊደል

## ኒ ሠሉስ ታኅሣሥ

አስማምቶ እንደ እብራይስጥ አድሶታል ለብሉይና ለሐዲስ የበቃና የተቀደሰ ብርሃን የለበሰ ከዚያ ወዲህ ነው የዚህ ማስረጃ ከትርጓሜ ፊደል የተባለ ከግራኝ ወዲህ ለኢትዮጵያ ብዙ ታሪኮች መጻሕፍቶች መጻቸውን ስለተረዳሁ ከግራኝ ወዲህ የተጻፈ ታሪክ አልቀበልም። እኔ የምቀበላቸው የታሪክ ጽሑፎች ካጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት በላይ የተጻፉትን ነው ያውም በጥብቅ መርምሬ። (፲፫ኛ ፵፫ኛው ገጽ ፍናወ ፊደል ወሑረታቲሁ የጥንቱ ግዕዝ ፍጹም የሴም ቋንቋ ነው ስለኛ አካሄዱና ምንገዱ እንደ ወንደሞቹ እንደ ዓረብና እንደ ሱርት እብራይስጥ ከቀኝ ወደ ግራ ነበረ

ይህኑም በየመን ያሉ ሕምያር ነገደ ዮቅጣን እብራውያንም ሳይቀሩ በቃል ታሪክ ይመሰክራሉ ፪ኛም ፊደሉና ቋንቋው ቅን ስለሆነ እንደ እርሻ አካሄድ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራኝ ወደ ቀኝ በ፪ት ወገን ይጣፍና ይነበብ ነበር ይህነንም እኔ ከቃላቸው እንደ ሰማሁ በትግሬ መሬት ከዚያውም ባጋሜ ወረዳ ዋሻ ውስጥ በድንጊያ ተጥፎ ያዩት አሉ በሰላማ ጊዜ በአብርሃና በአጽብሐ ዘመን የያፌት ልጆች ጽርዓውያን የካምም ልጆች ግብጻውያን ከያፌት ቋንቋ ሊያስማሙ በጭራሽ ከግራ ወደ ቀኝ አዙረውት ከሴም ቋንቋ ምንገድ ወጥቷል። ከዚያ ወዲህ በጉረሮ የሚነገረው ቃልቃል የሐውት ሐና የዓይኑ ዐ ድምጥ እየደከመና እያነሰ ሄዷል።) ይህ ሁሉ ሐተታ ከዚህ መጻፉ አንባቢ እንዲመለከተው ነው የሮማ ልዑካን ታሪክ ውስጥ ለውስጥ ብዙውን ሕዝብ አዳርሶታል ይህ የኢትዮጵያን ታሪክ በመሰርሰር እንደ ሃይማኖት በጣም ለሕዝቡ እየተሰበከ ተጠንቷል ስለዚህ የሮማ ልዑካን ሥራ ዛሬ አለማቋረጡን ይህ ያባ ጋስፓሪን ፖለቲክ ጽሑፍ ያስረዳል። “ፍልሰተ ፊደላት የተፋለሰና አልፋ አ ከርስቱ ከቀዳሚነቱ ተነቅሎ በርሱ ፋንታ ሀ መዠመሪያ ፊደል የሆነ ከፍሬ ምናጦስ ወዲህ ነው አ በ ገ ደ የነበረውን ሀ ለ ሐ መ ሠ ረ ሰ ሰ ብለው ከላይ እስከታች ያፋለሱትም ከርሱ ጋራ አብረው የነበሩ ጽርዕውያን ቅብጣውያን ናቸው ይባላል። አብረው ነበሩ የሚባል ፱ቱ ቅዱሳንን ነው ለማለት ታስቦ ነው። ያፋለሱበትም ምክንያት የግዕዝን ፊደል ከዓኃዝነት አውጥቶ የርሳቸውን ፊደል አልፋ ቤታ ጋማ የነበረውን ፩ድ ፪ ፫ የነበረውን በግዕዝ ፊደል ላይ አኀዝ አድርጎ ለማግባት እንዲመቻቸው ነው።) የቀድሞው ፊደል ግዕዝ አኀዝ ቁጥር ነበር ብየ ከላይ እንዳመለከትኩት አሁን ሳያውቁት በድንገት መስክረው ጻፉ። ይህችን በስሕተት የጻፏትን የኢትዮጵያ ፊደሎች ዓለም የቁጥር መያዣ አኀዝ ማለት መጨበጫ ማለት ናቸው ብየ ከላይ ጽፌ ነበር አሁን ከላይ የተጻፈው ባይገኝ ማለት አኀዝነቱን ባይመሰክር የኔ ጽሑፍ ለአንባቢ ሀገሩን ለማስከበር የፈጠረው ነው ተብሎ በሃሳብ ግምት ሳያርፍበት አይቀርም ነበር። ዓለም ሲፈጠር አኀዝ ሆነው የተፈጠሩትን በምን ምክንያት ለመቁረጥ የተመኙበት ምክንያት ይህን የኢትዮጵያ ፊደል ጥልቅነቱ እያደረ በዓለም ሊ ቃውንት ዘንድ የታወቀ እንደሆነ ኢትዮጵያ በዓለም ዘንድ የክብር ስም ያገኘች እንደሆነ ስምዋ እየታወቀና እየገነነ የሄደ እንደሆነ አሳባችን ከንቱ ሆና ይቀራል ስለማለት የኢትዮጵያን ቤተ መንግሥትና ቤተ ክህንት ክብር ለማዋረድ የሚደክሙበት ስለዚህ ነው። የኢትዮጵያ ፊደል በጸፍጸፈ ሰማይ ተለክተው ተመዝነው የተሠሩ መሆናቸውን በሄኖክ ቀመር ከሚጠተ ብርሃናት ባላገኘውና መርምሬ ባልረዳው ይህን ያህል ተዳፍሬ ባልደከምኩም ነበር ግዕዝ ይህን ያህል

# ና ረቡዕ ታኅሣሥ

መከራው የበዛበት ከካም ዠምሮ እስከ ፩ሺ ፲፻፶፪ ዘመን የቆየ ሽማግሌ በመሆኑ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ዓላማዋ ግዕዝ ነው። “ከኢጣልያና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ስለ ጠረፍ ጥያቄ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ባልጋ ወራሽነት ሳሉ በሺ፱፻፲፮ ዓ.ም ስኔ ፲፩ ቀን ሮማ በገቡ ጊዜ ከሲኞር ሙሶሊኒ የኢጣልያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በተገናኙ ጊዜ ከሰላምታ በኋላ በአውሳ በኩል ኢጣልያኖች ከኢትዮጵያ መንግሥት የወሰዱትን ጠረፍ ለኢትዮጵያ መንግሥት እንዲመልሱ ቢአድርጉልኝ እጅግ ደስ ይለኛል። ብለው ስለጠየቁ ሲኞር ሙሶሊኒ የፖለቲካውን ዲሬክተር ኮንት ኦሬኔን ጠርተው የጠረፉን ነገር ከልዑል አልጋ ወራሽ ጋራ ተነጋር ብለው አዘዙትና ኮንት ኦሬንም ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ይህን ጠረፍ ለመስጠት ፈቃድ አድርገዋልና በልብዎ ቆርጠው የፈለጉት ጠረፍ ማናቸው እንደሆነ ያስታውቁኝ ስላለ ልዑል አልጋ ወራሽም እኔ ፈቃድ የአሰብ በር ቢሆንልኝ ነው አሉትና እሱም ሁሉንም ነገር ተማክረን ምላሹን ኮንት ኮሊ ያስታውቅዎታል አላቸው። ይህንም ሲነግራቸው አብሮ የነበረ ማርኬዜ ፓውሌች ይባላል። የዚህንም ምላሽ ይዣለሁ ብሎ ኮንት ኮሊ ወደ ልዑል አልጋ ወራሽ መጣ ስለጠረፉም የኢጣልያ መንግውሥት ያሰበውን በጽፈት አሳየ ቃሉም እንዲህ የሚል ነው። ፩ኛ የኢጣልያ መንግሥት በኢጣልያና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል የሚኖረውን ፍቅር መሣሪያ እያጠበቀ ለመሄድ ፍጹም ፈቃዱ ስለሆነ ስለ ኢትዮጵያም የገንዘብና የፖለቲክ ጥቅም ልማት እስካሁን በኢጣልያ መንግሥት እጅ ያለውን በከተማውም ውስጥ ያሉትን የኢጣልያ መንግሥት ገንዘቦች

የሆኑትን ቦታዎችና ቤቶች ሁሉ ደግሞ የአሰብን በርና ባሕር ከባሕሩም በር አንስቶ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ድረስ ለምድር ባቡር የሚመች ቦታ እስከ ፺፱ ዓመት ለኢትዮጵያ መንግሥት ሰጥቷል ይህም ሁሉ ዘመን እስቲፈጸም የኢትዮጵያ መንግሥት ከኢጣልያ መንግሥት በተቀበለው በአሰብ በር ባሕርና እስከ ወሰኑ ባለው ምንገድ ሙሉ ሥልታን አለው። ፪ኛ በባሕሩና በአሰብ ስፍራ ዙሪያ ወሰን የተሠሩትም ቤቶች ተጨምረው ደግሞ ከአሰብ የባሕር በር አንስቶ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን የምድር ባቡር ለመሥራት የሚአስፈልገውን መሬት የኢትዮጵያ መንግሥት የሚመርጣቸው አዋቂዎች እዚያው ድረስ ሄደው ለባሕሩ በርና ለአሰብ ንግድ እንደሚያስፈልግ እዚያው ይወስናሉ። ፫ኛ የኢትዮጵያ መንግሥት በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን የፍቅር ማሠሪያ እያጠበቀ ለመሄድ ፍጹም ፈቃዱ ስለሆነ በዚህ በተባለው የባሕር በርና ቦታ በውሉ የተስማሙ እንደሆነ የገንዘብና የፖለቲካ ጥቅም ከኢጣልያ ዜጋ በተቀር ለሌላ መንግሥት ዜጎች አይሰጥም በጨረታውም በኩል የሆነ እንደሆነ ደቀምትነቱ ለኢጣልያ ዜጋ ነው። ግን በኢትዮጵያ መንግሥት ራሱ ወይም ባገሩ ሕዝብ ለማሠራት ቢፈልግ የወደደውን ለማድረግ ይችላል። ፬ኛ በአሰብ የባሕር በር የኢጣልያ መንግሥት ምናልባት ዕቃ የሚአሳርፍበት ቦታ የቸገረው እንደሆነ የኢትዮጵያ መንግሥት ፩ድ የተወሰነ ቦታ ይተውለታል። ፭ኛ የኢጣልያ ነጋዴዎች የንግድ ዕቃቸውን በአሰብ ባሕር በር በሚያስተላልፉበት ጊዜ ቀረጡን የኢትዮጵያ ነጋዴዎች በሚያስቀርጡበት ልክ ይከፍላሉ ፮ኛ የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕሩን በርና የባቡሩን ምንገድ ሥራ ከአሰብ ዠምሮ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ድረስ ለኢትዮጵያና ለኢጣልያ ኩምፓንያዎች ይበልጣል። እነዚህም የኢጣልያና የኢትዮጵያ ኩባንያዎች ሲቆሙ ፪ቱን እጅ ገንዘብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያወጣል ፩ዱን እጅ

## ኔ ኃሙስ ታኅሣሥ

የኢጣልያ ሕዝብ ያወጣል ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማውጣት ያልቻለ እንደሆነ ሌላ የውጭ ሰው ሳይገቡ ሁለቱ ወገኖች ብቻ ገንዘቡን እኩል እኩል አዋጥተው ኩባንያው ሊሆን ይችላሉ። ፯ኛ የኢትዮጵያ መንግሥት ወደፊት ከሌላ መንግሥት ጋራ የባሕር በር ውል የተዋዋለ እንደሆነ ደግሞ በማናቸውም ሌላ

የባሕር በር ነጻ የሆነ የቦታ ክፍል ወይም ስፍራ ያገኘ እንደሆነ በዚያውም መልካም ጥቅም የሚገኝበት የሆነ እንደሆነ የኢጣልያ መንግሥት ያነኑ የባሕር በር ውል አድሶ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስፋፋት ተስማምቷል። የኢትዮጵያ መንግሥትም የባሕር በር ውል ከሌላ መንግሥት ጋር ተዋውሎ ከሌላው መንግሥት በውሉ ጥቅም የሚአገኝ የሆነ እንደሆነ የኢጣልያ መንግሥት ይህነኑ የባሕር በር ውል አድሶ ጥቅም ለማግኘት ይችላል። ፰ኛ ከዚህ ቀድሞ የኢትዮጵያና የኢጣልያ መንግሥት የተዋዋሉት የወሰን ነገር ውሉ እየታየ ከ፪ቱም ወገን አዋቂዎች ተመርጠው የወሰኑ ነገር እንዲጨረስ ፪ቱም ወገኖች ተስማምተዋል። ደግሞ በእርሻም በንግድም በማዕድንም ከዚህ ቀደም ውል የተቀበሉትን የኢጣልያ ኩፓንያዎች ችግር እንዳያገኛቸው የኢትዮጵያ መንግሥት በሚቻለው ይረዳቸዋል። ፱ነኛ ስለ ጁባና ስለ ዋቢ ሸበሌ ውኃ የኢትዮጵያ መንግሥት ለራሱ ጥቅም ከሚአስፈልገው በተቀር ለውጭ ሰዎች ጥቅም ሰጥቶ ወደ ሱማሌ አገር እንዳይወርድ አድርጎ ውኃውን በጭራሽ እንዳይዘጋ ውል ገብቷል። ፲ኛ የኢጣልያ መንግሥት የአሰብን የባሕር በርና በአሰብ ያሉትን ቦታዎችና ቤቶች ሁሉ ጨምሮ ለባቡሩም ምንገድ መሥሪያ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን የሚበቃ ቦታ ስለሰጠ ከኢትዮጵያ መንግሥት ገንዘብ እንዳይፈልግ ውል ገብቷል።" ካ፩ድ እስከ ፲ክፍል ሆነው የተዘረዘሩትን የፖለቲክ ወጥመዶች በተለመደው ፖለቲካቸው ባጼ ምኒልክ እንደተለመደው ባማርኛው ፩ድ ነገር በኢጣልያኛው ፩ድ ነገር እየጻፉ ማጭበርበር ተለመደና በአሰብ በር ምክንያት ፲ሩ የፖለቲክ ወጥመዶች በኢትዮጵያ ን ነ መ አልጋ ወራሽ ልዑል ራስ ተፈሪ መኰንን ፊት ተዘረጉ ለሥራ የታጠቀውና የተጠነቀቀው ጀግና ግን ወጥመዱን ትቶት ባለፈ ጊዜ አጥማጁም ወጥመዱም ፈዘው ቀሩ የወጥመዶችንም አስተያየት ከየክፍላቸው በመጠኑ ልንገጸው ከሚቻለው ባ፩ኛው ክፍል የአሰብን የባሕር በርና ከባሕሩ አንሥቶ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ለምድር ባቡር የሚመች ቦታ እስከ ፺፱ኝ ዘመን

ያለው የተጠየቀ የባሕሩን ወደብ ብቻ የባቡር ምንገድ ምን አመጣው እስከ ፺፱ የተባለውስ ኢትዮጵያ የምትወረርበት መሳዊያ እየተሰናዳና ስንቁ እየተጫነ እስከ፺፱ ዓመት እንቆያለንና የባቡር መንገድ ሥሩልን ማለት እንደማን ተመስሎ ነበር ይሆን የአሰብን በር ከጠየቁበት እስከ ኢትዮጵያ መወረር የቆየውን ፲፬ ዘመን እንበለው በኢጣልያና በኢትዮጵያ መካከል የሚኖረውን ፍቅር ማሠሪያ እያጠበቀ ለመሄድ ፍጹም ፈቃዱ ስለሆነ የተባለው ይህ ድግስ እየተሰናዳ ነበር። በ፪ኛው ክፍል ከአሰብ ባሕር በር አንሥቶ እስከ ኢትዮጵያ መንግሥት የሚመርጣቸው አይተው ይወስናሉ የሚለው ከላይ እንደተጻፈው ስለባቡሩ ምንገድ አሥተያየት ንግግሩ ምነው በረከተ። በ፫ኛው በዚህ በባሕር በር የተስማሙ እንደሆነ የገንዘብና የፖለቲክ ጥቅም ከኢጣልያ ዜጋ በተቀር ለሌላ መንግሥት ዜጎች አይሰጥም ማለትን ምን አመጣው። በ፬ኛው ክፍል በአሰብ የባሕር በር የኢጣልያ መንግሥት ምናልባት ዕቃ እይሚአሳርፍበት የተወሰነ ቦታ

## ን ዓርብ ታኅሣሥ

ይላል ለጦር መሣሪያ ማከማቻ ማለቱን አይታወቅም ማለት ነው። በ፭ኛው ክፍል የኢጣልያ ነጋዴዎች እንደ ኢትዮጵያውያኖች እንዲቀረጡ ይላል ለማስመሰል። በ፮ኛው ክፍል የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕሩን በርና የባቡሩን ምንገድ ሥራ ከአሰብ ዠምሮ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን ለኢትዮጵያና ለኢጣልያ ኩፓንያዎች ይሰጣል ከነዚህም የገንዘቡ ወጭ ፪ት እጁን የኢጣልያ ሕዝብ ያወጣል ይላል። ይህም ስለ አሰቡት ወረራ የመንገዱ አስቸጋሪነት ከባድ አሳብ ሆኖባቸው ስለ ነበር በቶሎ መግቢያ አገኘን መስሏቸው ገንዘብም እስከ እኩሌታ ቢሆንም እናወጣለን እስከማለት ያደረሳቸው ለወረራው ስለቸኮሉ ነበር። በ፯ኛው ክፍል የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕር በር ውል ከሌላ መንግሥት ጋራ የተዋዋለ እንደሆነ የኢጣልያ መንግሥት

ውሉን አድሶ ጥቅም ለማግኘት ይችላል ይላል ከሌላ መዋዋል የለም ማለት ነው በ፰ኛው ክፍል ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያና የኢጣልያ መንግሥት የተዋዋሉት የወሰን ነገር ሁሉ ውሉ እየታየ ከ፪ቱም ወገን አዋቂዎች ተመርጠው የወሰኑ ነገር እንዲጨረስ ሁለቱም ተስማምተዋል የሚለው ባጼ ዮሐንስ ዘመን ንጉሥ ምኒልክን እያታለሉ ባማርኛው ፩ድ ነገር በኢጣልያንኛው ፩ድ ነገር እያጻፉ ያስፈርሟቸው የነበረውን በማታለል ያስፈረሙትን ያጼ ምኒልክን ማኅተም በደም የተሠረዘውን ለመቀደስ ታስቦ ፪ኛም በርሻም በንድም በማዕድንም ከዚህ ቀድሞ ውል የተቀበሉትን የኢጣልያ ኩፓንያዎች የኢትዮጵያ መንግሥት ይረዳቸዋል ይላል ይህ ውል በጭራሽ ከመካከሉ ለመግዛት የታሰበበት በር ነበር ግን ማን ቢታለል የደሙን ሥርዝ የሚዘነጋ አልሆነም። ስለ ፱ነኛው ክፍል ስለጁባና ዋቢ ሸበሌ ውኃ የኢትዮጵያ መንግሥት ለራሱ ጥቅም ከሚአስፈልገው በተቀር ለውጭ አገር ሰዎች ጥቅም ሰጥቶ ወደ ሱማሌ አገር እንዳይወርድ እንዳይዘነጋ ውል ገብቷል ያለው በውጋዴን የሚአገኘው ጥቅም በነዚህ በ፪ት ወንዞች ስለሆነ እነዚህን ይዘጉብኛል እያለ በጥብቅ ስለሚአስብ ከዚህ አሳብ ለማረፍ ነበር አሁንም በነዚህ በሁለቱ ወንዞች ነገር ኀዘኑ ከራሱ አልወረደለትም የነዚህ ወንዞች የሁለቱ ነገር በኢትዮጵያ ልጆጀች ልብ የተቀረጸ ይሁን። በ፲ኛው ክፍል የኢጣልያ መንግሥት የአሰብን የባሕር በርና በአሰብ ያሉትን ቦታዎችና ቤቶች ሁሉ ጨምሮ ለባቡሩም ምንገድ መሥሪያ እስከ ኢትዮጵያ ወሰን የሚበቃ ቦታ ስለሰጠ ከኢትዮጵያ መንግሥት ገንዘብ እንዳይፈልግ ውል ገብቷል ብሎ በለሰለሰ ቃል ሸፍኖ ቢያቀርበው ለመታለል ሳይቻል ቀረና እስከ ፲፬ ዓመት ጊዜ ለማግኘት ተቻለ። የሮማውያን ፖለቲክ በርቀት ኢትዮጵያን ለማታለል መሆኑን መረዳት አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ነው። ብልሁና አስተዋዩ የኢትዮጵያ ን ነ መ አልጋ ወራሽ ወ ልዑል ራስ ተፈሪ መኰንን ከላይ ባ፲ ክፍል የተዘረጉትን ወጥመዶች አስተውለው በማየት ሳይገቡባቸው ስለቀሩ ያሰቡት አሰብ ሳይፈጸም ስለቀረ ትንሽ ጊዜ ሳይፈጅባቸው አልቀረም። በአድዋ ላይ ስለተፈጸመው ድል በቀላቸውን ለመመለስ በወዳጅንት ምንገድ እያስገቡ ያስቀጧቸውን ሰባክያንና ቆንስሎች ድጋፍ በማድረግ ማለት ሰባክያኖቹ ለቆንስሎቹ ቆንስሎቹ ላስመራው ገዥ ያሥመራው ገዥ ለኢጣልያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እያስታወቀ ሲሠራ እንደቆየ

የሚአስረዳው ኢትዮጵያ ለመወረር እይደረሰችው በጦር ኃይል ሳይሆን በልዑካን መሪነት ውስጥ ለውስጥ በሚሄድ በገንዘብ ጦር መሆኑን በየጊዜው የተሠራባቸው በፊት ምሥጢራዊ በኋላ አፋዊ

# ኖ ቀዳም ታኅሣሥ

*መሆኑን ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ መረዳት ነው። ከላይ እንደ ተጻፈው በ፫ቱ አርስቶች ላይ በሥውር በሥርቆት መሠራቱን በሠፊው ያስረዳል። ያታላይነቱን ምንገድ በመከታተል ኢትዮጵያውያኖችን ግን ግባር ጦር እያደረጉ ነው እንጅ ኢጣልያኖች በጉልበትና በኃይል ሞክረውት እንደማያውቁ ታሪክ ይነግረናል። ሙሶሊኒም ለባዶልዮ ባስታወቀው የምሥጢር ቴሌግራም በገጽ "፳፩ በ፳፪ኛው መሥመር ምንም እንኳ የደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣን ደጋፊነት ቢይዝም ማርሻል ባዶልዮ ራሱ የጠየቀውን የአዝማችነቱን ሥራ ተረክቦ ፭ ወር ያህል እንደ ቆየ ይላል።" የትግሬን መሬት ኢጣልያኖች የገቡ በደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣ ጉልበት መሆኑን ይህ ያስረዳናል። በማነኛውም ጊዜ ኢጣልያኖች የመንፈሳዊ ልብስ ለብሰው በልዩ ልዩ ዕቃዎችን በገንዘብ በማታለል እንጅ በጀግንነት በጉልበት አለመሆኑ የዓለም ሊቃውንቶች የጻፉት ያስረዳል። እኛ ኢትዮጵያውያን የሆን ጸሐፊዎች ብቻ ሳንሆን የውጭ አገር ሰዎች ገልጸው ከጻፉት ታሪክ በኢትዮጵያ ድምጽ ቁጥር ፻፳፪ ግንቦት ፪ ፲፱፻፶ ዓ.ም ከዶክተር ሪቻርድ ተጽፎ በገዳሙ አብርሃም ተተረጐመ በሚለው ጋዜጣ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ነጻነት ለማጥፋት ከተወጠኑት የቅኝ ግዛት ማስፋፊያ ተንኮሎች አሥጊ የሆነውን የመጀመሪያውን ጠንቅ የፈጠረው እ.ኤ.አ ቁ በ፲፰፻፶፪*

*ዓ.ም ሥልጣን የያዘውንና ባ፲፰፻፸ ዓ.ም በተደረገው የፈረንሳይና የፕሩስያ ጦርነት እስኪሸነፍ ድረስ የፈረንሳይን የውጭ ጉዳይ ፖለቲክ ይመራ የነበረው ሣልሳዊ ናፖሊዮን የተባለው ዴክታር በፈርንሳይ ቆንሲልና ጁሴፔ ሳፔቶን ሞንሲኞር ዲ ጃኮቢስ በተባሉ ሁለት የኢጣልያ ቄሶች አማካይነት የኢትዮጵያን ሰሜናዊ ወደብ ለመያዝ ተስፋ ነበረው በዚያ ጊዜ ሸፍቶ ከንጉሠ ነገሥት ጦር ሠርዊቶች ጋር ሲዋጋ ለነበረው ንጉሤ ለተባለው ሸፍታ ፈረንሳዮች ድጋፋቸውንና እርዳታቸውን ሰጡ ይላል። ሐተታ ከላይ እንደተመለከተው የፈረንሳይ ዲክታተር ተብሎ ከታሪክ ተቆጥረው የታሪክ ዓምድ ይዘው ይገኛሉ። ውሥጥ ለውሥጥ ስለሚጎዳው ረቂቅ ፖለቲክ ባጼ ቴዎድሮስ ደጃች ንጉሤን ባጼ ዮሐንስ ንጉሥ ምኒልክ ባጼ ምኒልክም ደጃች ባሕታን ደጃች ደበበን ደጃች ሐጎስን ራስ ስበሕትን ሳይሆን ይቅር እንጅ ራስ መንገሻንም ለመስበክ ሳይታሰብ አልቀረም። ኢጣልያኖች ወደ ላይም የወጡበት ወደ ታችም የወረዱበት በነዚህ ጀግኖች ኃይል መሆኑ አይዘነጋም ባጼ ምኒልክ የኢትዮጵያውያንን ዞሮ መገናኘት ካወቀ በኋላ የጠላት ልብ በከፊን ልብሱ ተሸፋፍኖ ቆይቶ ነበር። ግን በውስጣችን የገቡ በሽታዎች ውስጥ ለውስጥ እየሄዱ በእግራችን እየገቡ ዓይናችንንም እያወሩ ዠሮዎቻችንንም እያደነቆሩ ይህነንም ጉዳታችንንም ለውጭ እያወሩ የነሱን ስብከት ስምቶ በልቡ ተስፋ ያደረገ እንቅልፍ አጣ እንደልማዱ ደግሞ ከግርማዊ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣን ያባትህን ያጼ ዮሐንስን መንግሥት እሰጥሃለሁ በሚል የሐሰት ድምጽ ካ፩ድ ሚልዮን ብር ጋር በዚህ ምክንያት የኢጣልያ የጦር ሠራዊት በትግሬ መሬት ለመግባት ቻለና ሲኞር ሙሶሊኒ ኢትዮጵያን በኃይል የጦር ሠራዊቴ ኢትዮጵያን ወረረ እያለ ጉራውን ለዓለም ይነዛ ዠመረ። ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን እምነቷን ሳታፈርስ በትዕግሥት ሥራዋን ስታካሂድ ትገኛለች። ሮማውያን በጀግንነት ኢትዮጵያውያኖችን ለመወዳደር ከሆነ ፩ሺ የኢጣልያ ወታደር ከ፪፻ የኢትዮጵያ ወታደሮች ጋር ይጋጠሙ ቢባል ኢጣልያኖች*

# አ እሁድ ታኅሣሥ

፺፫ ብልጫ አነሰን ይጨመርልን ሳይሉ ይቀራሉ አልልም። እነሱ መንፈሳውያን መስለው ገብተው ሥጋዊውን ፖለቲክ በገንዘብ እየጐተቱ እያገቡ ወንድምና ወንድሙን እያፋጁ መሆኑን የማረዳው ያለ አይመስለኝም። እንግዴህ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣን ከኢጣልያኖች ያገናኘና ያስተማመነ ማን እንደሆነ አሁንም ቢሆን ለመመርመር የሚከለክለን የለም። ያለፈውን ዓይነት ለወደፊቱ እንድንጠነቀቅ የሞሶሎኒ ምሥጢር የተባለውን መጽሐፍ (ባ፵፱ነኛው ገጽ በ፪ኛ አንቀጽ በ፳፯ኛው መሥመር በገንዘብ በኩል አስፈላጊ መስሎ የታየዎትን ያህል ይስጡ ይህም ከሹማምቶች ጋራ የሚአደርጉት ግንኙነት ፩ኛው የትግሬ ሹም ከደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጋር ከተጀመረው መቀራረብ ፍሬ ነገር እንደሚሰጥና የተቃና ምንገድ እንደሚአስገኝ አልጠራጠርም እሱም እንደተጠቀሰው ሰው ሁሉ በቅርብ ጊዜ ወደኛ ፊቱን መልሶ ታማኞችን ለመሆኑ ቃል የገባልን ሰው ራስ ሥዩም ተቃዋሚዬ ናቸው ሲል የገለጸልን ነው። የሆነው ሆኖ አሁን ለተነሣንበት ለዚህ ለመዠመሪይው ግባችን የትግሬን ሹማምንቶች በወዳጅነት ስንገባቸው ማንኛውም ይበልጥ መድን ያለው ተግባር እንደሚፈጸምልን ያስገነዝበናል ይላል። ፪ኛ በ፶ኛው ገጽ ባ፲፩ኛው መሥመር የምሥጢር ቴሌግራም ፩ድ ሚልዮን ሊሬ እንዲላክልህ አዝዠሃለሁና በዚህ የማርያ ትሬዚያ ብር ለውጠህ ላስፈልግህ ሁሉ ዝናህን ለመናኜት ይረዳሃል ይላል። ፫ኛ በ፶፯ኛ ገጽ ባ፲፰ኛው መሥመር የመቀሌም ከተማ በጃችን ከገባ በኋላ ደጃዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣን በተያዘው አገር ላይ ዋና አስተዳዳሪ አድርጎ ሾሞ ለሥራ አዝማች ኃይለ ሥላሴ ጉግሣን በተያዘው ማስኬጃ አገር ላይ ዋና አስተዳዳሪ አድርጎ ሾሞ ለሥራ ፩ድ ሚልዮን የማርያ ትሬዝ ብር እንዲሰጠው ማድረግ መልካም ይመስለኛል ይላል።) ሹመቱ ለጊዜው ነው እንጅ የነደጃች ደበበ ታሪክ ያስረሳል ማለት ከንቱ ነው። ፫ኛ ናፖሊዮን የተባለው የኢትዮጵያን ሰሜናዊ ወደብ ለመያዝ ተስፋ ነበረው ሲል የሮማን ቄሶች ተደግፎ መሆኑን ያስረዳል። የሮማ ቄሶች የመነኰሴ ልብስ እየለበሱ ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ነገር እየለቃቀሙ ወደ አውሮፓ እየሔዱ እገሌ የሚባል ከንጉሡ ነገሥቱ ተጣልቷልና አሁን በቶሎ የጦር መሳሪያና የሚአበረታታ ደብዳቤ ሰጥታችሁን ብንወስለት የሀገሩን ንጉሠ ነገሥት ባሸነፈ ጊዜ ስለ ውለታችን በኛ ታማኝ ሊሆን ይችላል እያሉ ከክርስቶሳውያን ስብከት ውጭ የሆነ ስብከታቸውን እየዘሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ እርስ በርሱ ሲአፋጁት የሚኖሩ የሮማ ልዑካን መሆናቸውን ያስረዳል። ጁስቴ ሳፒቶርና ሞንሲኞር ዴ ጃኮቢስ በተባሉ ሁለት የኢጣልያ ቄሶች አማካይነት ያለው ጽሑፍ ይህን ሥራቸውን መግለጹ ግዴታ ነው። ለዚህም መደገፊያ የሚሆን ፈረንሳዮች ለንጉሤ እርዳታቸውን ሰጡ ማለቱ ይህ እርዳታ የተባለው የጦር መሣሪያ አይደለም ለማለት ይሆንን ወይስ የጦሩን መሳሪያ አማካይነታቸውን የተነገረላቸው ሰዎች ቀርተው ሌላ ሰው አቀበለ እንበል ይሆንን ሐተታው ይቆይና ወደ ዠመርነው እንመለስ። "ንጉሤም ሁከቱን ካስነሣ በኋላ የፈረንሳይ ወታደሮች እንዲረዱ ከተዋዋሉት ለ፫ኛ ናፖሊዮን የአዱሊስን ሰላጤና ደሴትን ለፈረንሳዮች የሚሰጥ መሆኑን በመግለጽ የውለታ ሐሳብ ቀረበ ይላል"። ሐተታ የውለታ ሐሳብ አቀረበ የተባለው ጽሑፍ አልተገልጸም ሆኖም ነገሩ የተሸፈነ ቢመስልም መታወቁ የሚቀር አይደለምና ይህን

# ኡ ሰኑይ ታኅሣሥ

የሐሳብ ድርድር ከወዲህ ወዲያ ከወዲህ ወዲህ የሚአመላልሰው ማነው ይሆን ይሆን ከራስ አሊ እስከ ራስ ዱሜይ ድረስ ያለው ቀጥተኛ ሜዳና የአቦክ ወደብ በቅኝ ግዛት ለመያዝ ተስማሚ ነው ሲሉ ፈረንሳዮች ወሰኑ በዚህም ውሳኔ መሠረት ለቀበሌው ሹም አሥር ሽህ የማሪያ ትሬዛ ብር በመስጠት የአቦክን ወደብ ገዙ ይላል። ሐተታ ስለ አቦክ ወደብ ከቀበሌው ሹም አሥር ሽህ ብር የአቦክን ወደብ ገዙ የተባለው ይህን ከሕግ ውጭ የሆነ የቀሳጢና ያታላይነት ሥራ መሪ ሆኖ ያስፈጸመ ማነው ይሆን ይህ ሥራ በሌብነት የተሠራ መሆኑን የሚአስረዳ ይህም የአቦክን ወደብ የሸጠው ሹም ገንዘቡን እንደተቀበለ ወዲያውኑ ጠፋ በማለቱ ነው። ወደዚያውም ወራሹ የአቦክ ገዥ ሕገ ወጥ ድርጅት ነው ሲል ተቃወመ ብሎ ግን ማንም አላዳመጠውም አለ"። ሐተታ ይህ ነገር ሲመርመር እውነተኛ ሥራ ነው ለማለት ያስደፍራል ይሆንን የመንፈሳዊ ልብስ ለብሶ ባታላይ ገበያ ውስጥ መገኘት የተገባ ነው ለማለት ያስደፍራል ይሆንን

ፈረንሳይም የፈረንሳይ ሱማሌ ብላ ወደ ኋላ ለጠራችው ግዛት የመዠመሪያውን ማቋቋሚያ ሰፈር በዚህ ሁኔታ መሠረተች አለ የጅቡቲ ወደብም በሮማ ቄሶች አማካይነት የተሠራውን ረቂቅ ተንኮል ገልጾ አስረዳን ፈረንሳይ በሮማ ቄሶች አማካይነት ዠምራው የነበረው ረቂቅ ፖለቲክ በ፩ኛው ናፖሊዮን ሥልጣን መውደቅና ፈረንሳይ በፕሮሲያ መሸነፍ ባ፲፰፻፸፫ ዓ.ም ቆመ ይላል። ከዚህ በኋላ ደግሞ የሮማ ጦር ሠራዊት ስበው እንደመጡ አስቀድሞ ንጉሤ ከተባለው ሽፍታ ጋራ ወደሮማም የዠመርት ስለነበራቸው ንጉሤ የተባለውን ጸጥታ ነሽ ሽፍታ የኢትዮጵያ ንጉሥ ነው በማለት እ.ኤ.አ ቁ ፲፰፻፷፱ ዓ.ም ጀምሮ በቴየም ንጉሥና በንጉሤ መካከል የንግድ ስምምነት ያዘጋጀው ሳፒቶ የተባለው የኢጣልያ ቄስ ሩባቲኖ ካምፓኒ ለተባለው የኢጣልያ ኩምባንያ በአሰብ ቦታ ገዛ ይህነንም ቦታ ሲገዛ ይህ በባሕር ጠረፍ የሚገኝ ቦታ የሚአገለግለው የመርከቦች የነዳጅ ከሰል መሙያ ጣቢያ በመሆን ብቻ ነው ሲል ነበር በአሰብ ወደብ ውስጥ ፩ድ አነስተኛ ቦታ በዚህ ሁኔታ ከተገዛ በኋላ ስዊዝ ካናል በተከፈለበት ቀን የኢጣልያ ባለመድፍ መርከቦች ከወደቡ ላይ ደረሱ ይላል"። ሐተታ የሮማ ልዑካንን ሥራ መመልከት የጦር ፊታውራሪዎች ሰላማዊውን ሕዝብ መጽሐፍና መስቀል እያሳዩ እያታለሉ ከኋላቸው የሰው መፍጃ መሳሪያ እያስከተሉ ኢትዮጵያን የደም ምድር አደረጓት። ይህም ረቂቅ ፖለቲካቸው እስከ ዛሬ ሳይታወቅና ሳይገለጽ መኖሩን የሚአስረዳው የኢትዮጵያ ተወላጆች ለፖለቲካ ካቆሙት ቤት ልዑል እግዚአብሔርን ለማግኘት እየሄዱ ጸሎት እናደርጋለን ሲሉ በማየቴ ነው። በሚሊዮን የሚቆጠረውን የኢትዮጵያውያንን ደም ልዑል እግዚአብሔር አይቆጥረውም ይሆንን የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናትስ በነሱ ምክንያት በመጣው ጦር የተቃጠሉት በሺ የሚቆጠሩ ሲሆኑ በነዚህ ቦታዎች ሁሉ የልዑል እግዚአብሔር ክቡር ስሙ የተጻፈባቸው ቅዱሳት መጻሕፍት አልተቃጠሉም ይሆንን። በዐጸደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተማጽነው የነበሩ ስንት የእግዚአብሔር ሰዎች ንጹሕ ደማቸው በግፍ ፈሰሰ ይህን ሁሉ ግፍ ልዑል እግዚአብሔር አይቆጥረውም ይሆንን በማስተዋል ዓይን የሚመለከት ቢኖር ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያን ላይ እንደምን ዘመቻ ታደርጋለች ማለት የሮማ ልዑካን በብዙዎች ላይ ቤተ ክርስቲያኖች ናቸው እያሉ አቁመዋቸው

# ኢ. ሠሉስ ታኅሣሥ

የምናያቸው በጣም በርክተዋል። ኢትዮጵያ ለኢጣልያኖች የድም ምድር መሆንዋ የሚካድ አይደለም ማለት ኢጣልያኖች ወደ ኢትዮጵያ ሲገቡ ምንም ከጀግንነት በማይቅጠር ባታላይነት የመነኰሴ ልብስ ለብሰው እንደ መናኔ ዓለም መስቀልና መጽሐፍ ተሸክመው በውስጣዊ ፖለቲካ ውሥጥ ለውስጥ ሰላማዊውን ሕዝብ እየለያዩ ብዙ ጀግኖች ስለአጋደሉ የጀግኖቹ ደም በምድራቸው ላይ እንደተጣለለ መሆኑን ታሪክ በሚባል መሥታዮት እናየዋለን ባጼ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥትም የሮማ ልዑካን ቀሳውስት ልብስ እየለበሱ የኢትዮጵያን ሊቃውንት ደም የታላቅ ዝማን ጉርፍ አስመስለው በኢትዮጵያ ላይ አፍልሰውታል። ይህም እንዳይካድ ታሪክ የሚባለው መስታዮት ይመሰክራል ይህም መሥታዮት እንዳይካድ የሮማውያን ጠበብት የሠሩት ስለመሆኑ መታመን በግድ ይገባዋል። ለመካድ የሚቻል አይደለም። ከላይ የተጻፈው ሁሉ የታመነ መሆኑ ሳይካድ መረጃው በየጊዜው እየተገለጸ ሲሄድ ዓይናቸውም እያየ ዡሮአቸውም እየሰማ ከኢትዮጵያ ተወላጆች ውስጥ ብዙ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ነው ተብሎ በወንድሞቻቸው ደም ላይ ከተሠራው በበዓላት

ቀን እግዚአብሔርን ደጅ እንጠናለን እያሉ እየሄዱ ሲምበረከኩ ይታያሉ። ልዑል እግዚአብሔር በገለጸልን አእምሮ ስንገምተው አስገራሚ ነገር ይገኛል። ልዑል እግዚአብሔር በደም ከታነጸ ቤት ላይ መሥዋዕት የሚቀበል ከሆነ አክአብም ናቡቴን ገድሎ ርስቱን ስለወረሰ እግዚአብሔር አልተቀየመበትም በዚያ በናቡቴ ቦታ ላይም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቅርቦ እግዚአብሔር መስዋዕቱን ተቀብሎት ነበር እንደማለት ያለ ነው። ም ፳፩ አክአብስ ስለናቡቴ ደም ያደረበትን ፍዳ ንግሥት ራብዕ ፱ ፳ ፱ ፲። ፪ኛውም ፲ ፪ ፲፯። ፳ ባ፩ድ ናቡቴ ደም ከአክአብና ኤልዛቤል በተቀር

ወደልጆቹ ወርዶ የ፳ዓን ልጆች ራስ አስቆርጦ ከመንታ ምንገድ ያስቀላቸውን ጽሑፍ አስተውሎ መመልከት የተገባ ነበረ። እንግዴህ ከላይ እንደተጻፈው ስንመለከት ርስታችንን አንሰጥም እያሉ በሀገራቸው ላይ ደማቸው የፈሰሰ ስንት ይሆናሉ። በቀላል ግምት ካጼ ሚናስ መንግሥት ዠምሮ እስከ ዛሬ በነሱ ተንኮል ምክንያት የሚአልቁ ኢትዮጵያውያን ከሚሊዮን ያነሰ አይሆንም። ከዚህም በላይ ፩ኛ አካላታቸው ይጐደለባቸው ፪ኛ በልዩ አባለ ዘራቸውን ተቀምተው ያለ ዘርዕ የቀሩ ፫ኛ በገንዘብ ተታለው አገራቸውንና መንግሥታቸውን ስለ በደሉ በእሥር ቤት የሚገኙ ፬ኛ በነሱ ፖለቲክ ምክንያት አገራቸውን ጥለው የተሰደዱ የዚህ ሁሉ ግፍ ባለቤቶች ይህን ያህል ደም ባፈሰሱባትና ይህን ያህል ግፍ ባደረጉባት መሬት ላይ ቤተ ክርስቲያን አቁመናልና እየመጣችሁ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት ብታቀርቡ ልመናችሁ ይፈጸምላችኋል እያሉ ሲሰብኩ ይታያሉ። አስገራሚ ነገር ይህ ነው። ልዑል እግዚአብሔርን ያህል ንጉሥ ይህን ዓለም ፈጥሮ ሕግን ሳይጥስ እንዲሁ ተወው ለማለት እንዳይቻል በቅዱስ መጽሐፍ አስገንዝቦናል። ማለት ማንም የሰው ዘር ከተለየለትና ከተወሰነለት እንዳያልፍ ያ፩ዱን ፩ዱ እንዳይመለከት የታዘዝንበትን ኦሪት ዘፀዓት ፳ ካ፩ ፲፰ ቁ እይ ፪ኛም ዘዳግም ፲፱ ፲ ፲፬ እይ እንግዴህ የልዑል እግዚአብሔርን ቃል ተላልፎ በጉልበቱ የሌላውን አባት አገር ወርሼ እኖራለሁ የሚል በሴም ዘሮችና በካም ዘሮች የተጻፈውን ይመልከት ያስተውል። ማለት የካም ዘሮች ከነዓን ያባቱን ክፍል አፍሪካን ትቶ የሴምን ዕጣ የኢየሩሳሌምን አውራጃ ተመልክቶ አባቱ ካም ወደ አፍሪካ እንሂድና

## አ ረቡዕ ታኅሣሥ

በወንድሞችህ ጋር ርሥትህን ክፍልህን ልስጥህ ቢለው እምቢ ብሎ ያባቱን ፈቃድ ጥሶ ቀርቶ የኢየሩሳሌም አውራጃዎች ባለቤት ሆኖ ትውልዱ ሲተላለፍ እስከ ፳ኤል ከግብጽ መመለስ ማለት ኖኅ ድምርን ለ፫ት ልጆች አካፍሎ በ፪ሽ ፮፻፯ ዓመተ ዓለም ላይ ካረፈበት ዠምሮ ነው። ዘመኑ ሲታሰብ ፩ሽ ፪፻ ፴፯ ይሆናል። የከነዓን ዘሮች የመሬቱ ባላባት ሆነው ይህን ያህል ዘመን ቢቆዩበት ልዑል እግዚአብሔር ለጥንት ባለክፍሉ ለሴም ዘር መመለሱን የማይረዳ ሰው ያለ አይመስለኝም። በሮማውያን ዘንድ በጣም የተሠረዘ ነው። እንግዴህ በከነዓን ልጆች የደረሰውን ውርደትና መከራ መመልከት አስፈላጊ ነበር። ይህንም ችላ ማለት የልዑል እግዚአብሔርን ቃል ማቃለል መሆኑን ማሰብ የተገባ ነበር። አሁን ይህን ለመጻፍ ያሳሰበኝ የዶክተር ሪቻርድ መጽሐፍ የኢትዮጵያን ጥንታዊ ነጻነት ለማጥፋት ከተወጠኑት የቅኝ ግዛት ማስፋፊያ የሚለውን ስመለከተው ከታሪኩ የቀረለትን ላንባቢዎች ለማስታወስ ነው። ከላይ እንዳመለከትሁት። በሮማ ልዑካን ተሰብስበው የሀገራቸውን ቤተ ክርስቲያን ትተው ወደ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የሚሰግዱ ብዙዎች ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ስለሚገኙ ይህን ጽሑፌን ለመቃወም እንደሚነሱ አውቃለሁ። እርግጥ ነው መቃወም ይገባቸዋል። እኔም አልፈርድባቸውም ማለት እነሱ የተማሩትን መያዝ ይገባቸዋል ውስጠ ነገሩን በጽሑፍ አብራርቶ የሚነገራቸው ባለማግኘታቸው ነው እንጅ ውሥጠ ምሥጢሩን የሮማ ልዑካንን ረቂቅ ፖለቲክ የኢትዮጵያን ቤተ ክህነትና ቤተ መንግሥት ለመደምሰስና ነጻነቷን ለማጥፋት መሆኑን ባለመረዳት ተለመደና በዚያው በልማዱ መቆየት ነው እንጅ ከኢጣልያ ወረራ ወዲህ የነጻነትን ስብከት ከጠላት ጭቆናና ውርደት ያልተማረ የለም። የሮማ ልዑካን ለኢትዮጵያ ነጻነት የመደምሰሻ በር ከፋች መሆናቸውን ይኸውና ከዶክተር ሪቻርድ የተጻፈውን መመልከት ነው። የሮማ ሰዎች ኢትዮጵያውያንን ለማታለል የመነኵሴ ልብስ ለብሰው መጽሐፍና መስቀል ይዘው ይመጡና የፖለቲክ ሥራቸውን ይቀጥላሉ። በሰው አገር ሄዶ ይቅርና በሀገሩ ላይ እንኳ መናኒ የሆነ ሰው ርስት መግዛት ታላላቅ ቤት መሥራት እንደምን ይቻለዋል። ይህንስ ገንዘብ ካገኘ እንደምን መናኔ ዓለም ሊባል ይቻላል። መናኔ ዓለም መሆንና የገንዘብ ጌታ መሆን በጣም የተራራቁ ናቸው ይህም እንድንገነዘብ ጌታችን አስረድቶናል በቅዱስ ወንጌሉ ማቴዎስ ፲፱ ፲፮ ፲፯ ፲፰ ፲፱ ፳። ፳፩ ፳፪ ፳፫ እይ በ፳፬ኛው ቁጥር ላይ የተናገረውን ፍጻሜ መገንዘብ አለ። ብዙ ገንዘብ ጭነው እየመጡ በገንዘብ ሃይማኖት እናስተምራለን እያሉ እየመጡ የማታለል ሥራ እየሠሩ የኢትዮጵያን መሠረት ለማፍረስ ሲሠረስሩ ይገኛሉ። ረቂቅ ሥራቸውንም የገዛ ሥራቸውን መዝገብ እነሱ የጻፉት እየተገኘ ይመሰክርባቸዋል።

ይኸውና ያባ ያዕቆብም ገድል ተብሎ ከተጻፈ የተገኘ ግልባጭ (በ፻፮ ገጽ ፪ኛው ክፍል መ ም ስላባታችን አቡነ ያዕቆብ ከቅዱስ ጴጥሮስ ወምበር ከሮም ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በስም ፲፪ኛ ጎርጎርዮስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣትዎን ይገልጻል። ከጌታ ልደት በኋላ ባ፲፰፻ ጥቅምት ፲ኛ ቀን የናፖሊዮ ግዛት በምትሆን በባዚካት በቅዱስ ሳንፈለስል ተወለደ በኢትዮጵያ ቁ ፩ሺ፯፻፶፪ በጥቅምት ፫ኛ ቀን ይሆናል ከያዕቆብ ዮሐንስ መጥምቅና ዮሴፍ ሙሴም ለተወለዱቱ ፲፬ ወንድሞችዎ ፺ኛ ነበሩ። ወላጅዎም በሕግ የጸኑ ስለሆኑ ልጆቻቸውን በቀና ሥርዓት አሳደጉ በፈረንሳዊ ቋንቋ የተጻፈ ገድልዎ ልጆች

## ኤ ኃሙስ ታኅሣሥ

፲፬ ነበሩ ይላል። ከርስዎ አፍ ሰማነ የሚሉ አባ ኪዳኑና አባ ገብረ ኢየሱስ ፲፫ ወንድማማች ነበሩ ይላሉ። ፱ኙ በሕጻንነት ሳሉ ሞቱ ከ፮ቱ እርስዎ ሌሎች ፪ት ወደ ክህነት ደረሱ። ፪ቱም ሌሎች በንጽሕና ኖሩ ፩ዲቱም በድንግልና ቃል ኪዳን አድርጋ በገዳም ገብታ ኖረች ከካህናቱም ፩ዱ ወንድምዎ ወደ ፐኑ ገዳም ቅዱስ ቡሩሮ ገባ በንጽሕናም ከሚኖሩቱ ወደዚህ ከመጡ በኋላ ሞቱን ቢሰሙ እንግዴህ የኛ ቤት ተጨረሰ አሉ ይልና ስለ አስተዳደጋቸው ስለተምህርታቸውም በሕጻንነታቸውም ታመው እንደነበር ይተርካል የመዠመሪያው ስማቸው ዮስቴኖስ ነው የጥቅምት ስምዎ የያዕቆብ ስም ነው በሽ ፳፻፲፰ ዓ. ወደ ቅ ቅናቢንቸንሲዮ ማኅበር ገቡ ከዚያ በሽ፳፻ ዓ.ም ላይ በአውሮፓ አሰተኞች ተነሡ በፊተኞቹ አሰተኞች ነቢያት የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን እንደ ጕሰቆለች ለእስላምም ባርነት እንደገባች በኋላም ለምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ክፉ የነፍስ ፌራ ገባ ያርዮስና የንስጥሮስ ያውጣኪም ኑፋቄ የሙሐመድን ትምርት እንደወለደች ባገራችንም ፀረ ማርያም ኤውሮፓን ፕሮቴስታንት የሚባሉ ሃይማኖትና ሌላውንም ነገር መቀበል ድንቁርና ነው ቅ. ጴ ከሌሎቹ ሐዋርያት ብልጫ እንዳልነበረው በወምበሩም የተቀመጠው የሮም ጳጳስ ከሌላው የሚበጥልበት ሥልጣን የለውም ዳግመኛ መጻፍን ብቻ አንብቦ መርምሮ የያዛት የሃይማኖት ያለምግባር ታጸድቀዋለች አሉ። ሌላውንም ከቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ካቶሊካዊት ጋራ የሚጣላውን ብዙ ተናገሩ ስለዚህ ለዚህ ትምህርት ተከታይ ከአሕዛቦችና ከሙሐመድ ትምርት ይልቅ የከፋች የረሲዓን ትምርት ተገለጠች ይላል። በነሱ አሳብ ኢትዮጵያ የተሠሩትን ጉባኤዎች ሁሉ የማታውቅ ናት መስሏቸዋል። ኢትዮጵያ ስለቅዱሳት መጻሕፍት አስቀድማ በሰሎሞን ጊዜ ዠምራ መጻሕፍተ ብሉያትን ከእብራይስጥ ወደ ግዕዝ አስገልብጣ አምጥታ ሱባዔውን እየቆጠረች ሰንበትን እያከበረች የቆየች አገር መሆንዋን ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል። ከሐዋርያት ከአርድዕት ከሰማዕታት ደም የነጻች ለመሆንዋ የዓለም ባለታሪኮች ይመስክራሉ። በዘመነ ሐዲስም ከላይ እንደተጻፈው በሕጽዋ ለቅድኪ ጥምቀት ስለመጣ ጥምቀትን ተቀብላ በሰላምና በደስታ እስከ ፫፻፲፰ ዘመን ቆይታለች ከዚያም በኋላ የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት የሥጋውና የደሙ አቀባበል በቈስጠንጥኖስ መስፋፋትና መደላደል ስለተዠመረ የውጭ ቋንቋና ምንገድ የሚአውቀውን

ፍሬ ምናጦስን ስንቅና ሰው ጨምራ ልካ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንንና የሥጋና የደሙን አቀባበል ቅዱስ ወንጌልንም አስመጥታ ወንጌሉን ከጽርዕ ወደ ግዕዝ አስገልብጣና መልሳ የእግዚአብሔርን ቃላት በብዙ ጥንቃቄ እንደያዘች እስከ ሮማውያን መምጣት ድረስ ቤተ ክርስቲያንም ያለ ኑፋቄ ፩ዲት ቤተ ክርስቲያን እስከ ዓረብ አገር ድረስ ተስፋፍታ እንደነበረች የኢትዮጵያ ግዛት በነበሩ አገሮችና በዙሪያዋ በሚገኙ ደሴቶች በዓረብ አገርም ላይ የነበሩ የቤተ ክርስቲያን ፍራሶች ውሥጥ በግዕዝ የተጻፉ ምልክቶች ይገኛሉ ለኢትዮጵያ መንግሥት የነጻነት ምልክቱ ግዕዝ ነው። የቋንቋዋና የመንግሥቷም ዘመን ርዝመቱ ከላይም እንደተጻፈው ከኖኅ ዕረፍት ዠምሮ እስከ ዛሬ ፬ሺ፲፱፻፺ ዘመን በላይ ነው። እስከዚህ ድረስ የታሪክ መሠረት ያላትን ታላቂቱን ሀገር ለማጭበርበር የመነኵሴ ልብስ እየለበሱ እርስ በርሱ እያፋጁ ምድሩ ባዶ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑና ቤተ መንግሥቱን ለመውረስ ከብዙ

## እ ዓርብ ታኅሣሥ

ገንዘብ ጋራ በየጊዜው መላክ ዋና ተግባራቸው ስለሆነ አባ ያዕቆብንም እንደላከ የሚናገር ጽሑፍ ግልባጭ ከዚህ የሚከተለው ነው። በ፫ኛም ምዕ ከጌታችን ልደት በኋላ "ባ፲፫የ፴፱ ዓ. ጌታ ወደ ሰጠዎ ስብከት ወደ ኢትዮጵያ ሊመጡ ከሮም መነሳትዎን ይናገራል በኋለኛው ጊዜ ከርስዎ ጋራ የመጡ አባ አቲኒ እንዲህ አሉ የናፖሊ ንጉሥ ፈርናዲኖ ያበህ የያዕቆብንም ደግነት ሰምቶ ጳጳስነትን እንዲሾምለት ለሮም ልኮ ነበረ እርስዎ ግን ቅዱስ አባቴ ሆይ ሕዝብን ለማስተማር ወደ አሜሪካ ይላኩኝ እንጅ የንጉሥን ፈቃድ አያድርጉብኝ ብለው ጽፈው ነበሩ ፓፓም እሽ እሽ እኔ ወደማስበው እሰድሀለሁ አሉዎ ዳግመኛም በዚያ ዘመን ፩ድ ካርዲናልና በዚያም በሮም የነበሩ አባ ጊዮርጊስ ዘገለበዳ ያችውም በተምቤን ወደ ኢትዮጵያ ሲላኩ የነበሩ አባ ጊዮርጊስ ዘገለበዳ ያችውም በተምቤን ወደ ኢትዮጵያ ሲላኩ የነበሩ የቀሩበትን ምክንያት አላወቅሁትም ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ፍልጥዎሙ ሊተ ለበርናባስ ወለሳውል ለግብር ዘፈቀድክዎሙ እንዳለ አባታችነን እንደመረጠ ይመስለኛል ስለዚህ ቅዱስ አባት በካርዲናል ፍራንጉኒ የፕሮፓጋንዳ አለቃ ትእዛዝ ተጠርተው ከናጉሊ ወደ ሮማ ሄዱ ኢትዮጵያ መላካቸውን በሰሙ ጊዜ እጅግ ደስ አላቸው። ነገር ግን በሌላ ወገን የሚአስጨንቅዎን አገኙ)። አንባቢ ሆይ ከላይ የፕሮፓጋንድ አለቃ ትእዛዝ ተጠርተው ያለውን አጥብቀህ ተመልከት ወደዚያው እንመለስ ፩ዱ ይህነን ስብከት ካርዲናል ለርስዎ ብቻ በመስጠታቸው ተቸገሩ ስለዚህ ከርስዎ አስፈቅደው ይመስለኛል ከሮም ወደ ፓሪስ ሄደው የመታዘዝዎን የትሕትናዎን ብዛት ለገዳም አባትዎ ገለጡ ይህችም የመልእክት ስብከት ቅ ቢንቸንሲዮን ለተላከለት ማኅበር ላዛሪስቲ ለምትባል እንደትሆን እርስዎም ከርስዋ ትእዛዝ ጋራ የካርዲናልን ትእዛዝ ሊፈጽሙ ለመኑ። አበምኔትም እሽ ስለ አለዎ ደስታ መልቶብዎ ወደ ናፖሊ አገርዎ ተመለሱ ፪ኛዱቱ ጭንቀትዎ ከርስዎና ከእግዚብሔር በቀር ሌላ የማያውቃት ነበረች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን እርሷም የርስዎን አሳብ የጌታችን ምላሽ በወረቀት ጽፋ ሰደደችላቸው ስለዚህ ወደ ኢትዮጵ ከመጡ በኋላ ስብከትዎን የሚአፈርስ ፈተና ስትመጣብዎ ባዩ ጊዜ ቃልህ የማይታበል ጌታዬ ሆይ እርዳኝ ሲሉ ነበረ። ከዚህ በኋላም አቡነ ፍሬ ምናጦስ ያገርዎ የናፖሊ ሰው በተማሪ ቤት አብረው የኖሩ ሊሰናበቱ ከናፖሊ ወደ ሮም ሄዱ በዚያ ጊዜ ሊጎሪ ያገርዎ ጳጳስ የነበረውን ሌሎችም ቅዱሳን የሚባሉ በዓል ስለሆነች ይህነን ለማክበር በዚያ ሊቆዩ ወደዱ ቅዱስ ፓፓ በስም ፲፮ኛ ጎርጎርዮስ ግን እነዚያ የሚጫኑባት መርከብ በዚያ የማትቆይ ስለሆነች ልጆቼ ሆይ ይህንን በዓል መንግሥተ ሰማይ ታያላችሁና ዛሬስ ሂዱ ብለው ባርከው አሰናበቷቸው ይላል። በመርከብ ተጉዘው በኢትዮጵያ ምድር ከደረሱ በኋላ ወደ ደጋው ሲወጡ በዚያ ዘመን ክርስቲያንን የሚጠብቅ ኮንስል አልነበረም ናይቦች ባለሥልጣን ስለሆኑ ይልቁንም

አባታቸው ሙሐመድ እንዳላቸው ክርስቲያንን መግደል የሚወዱ ስለሆኑ ይልቁንም በኤሮፓውያንና በተንባላተ በቱርኮችም መካከል ቀድሞ ደም እንደ ጒርፍ የፈሰሰባት ጦር ስላደረገች ፈረንጆችን እጅግ ይጠላሉ። ነገር ግን የክርስቲያን ኃይል ስለ በረታባቸው ከሌላው ሰው ይልቅ አውሮፓውያንን እጅግ ይፈራሉ በውሥጥ ግን አሣሁርታ የሚባሉ ሽሆች በምንገድ አሉና የመጣውን መንገደኛ ለመጒዳት ተንኮላቸውን በነዚህ ላይ ያደርጉ ነበረ ከድኖዋ እስከ ጎላይ

# ኦ ቀዳም ታጎሣሥ

ወይም እስከ ድግሳ የክርስቲያን አገር መርተው የሚአደርሱ እኒህ ሽሆች ናቸው ይህ ምንገድ ፈጥኖ ለሚሄድ ለ፫ት ወይም የ፫ ቀን ተኩል ይሆናል። በምንገዱም ከሚአስፈራራና ከሚአሳዝን ሽሆ በቀር እግዜር በጥፋት ውኃ ወይም በእሳት ከከፋፈላቸው ደረቆች ተራሮች በቀር ላይን ደስ የሚአሰኝ ነገር የለበትም እንግዴህ ናይብ አውሮፓዊ መሪን ሊቀበል በመጣበት ጊዜ በፊት ያሳሁርቶችን ራት ኋላም የመሪውን ደሞዝ አምጣ ይለዋል። ያም እንዳለው ለናይብ

ይሰጣል። ጥቂቱን ከዚህ ለመሪው ሰጥቶ የበዛውን ለራሱ ያስቀራል። ከዚህ በኋላ ከድኖዋ ተነሥቶ ወደ ምድረ በዳው ባለፈ ጊዜ ንሥር ደም ስትፈስ በሩቅ ቅጽበት ወደዚያ እንዲደርስ በዚያ መንገድ በተራሮች ያሉ በመልካቸው ሰዎች በጠባያቸው ግን ነብርና ድብ የሆኑ አሞሮች ነጭ ሰው በወንዙ በሐዳስ እንደ ደረሰ በሩቅ ሳሉ ሰምተው ወይም አይተው ወደርሱ ይመጣሉ። ሥራን የማይሠሩ ስለሆኑ ራብ ይጸናባቸዋል ስለዚህ ይህነን ለማስታገሥ ምግብን እንዲሰጣቸው በማስፈራራት ይታዩታል የትርኩ በሚመስል ቋንቋቸው ድምጽ ያስደነግጡታል። ስለዚህ እንግዳው ሰው የፈለጉትን በመፍራት ይሰጣል። ይህም ሐምሐም የሚባል የወንዙ መዠመሪያ ይዞ እስከ ክርስቲያን አገር ነው። ባይሰጥ ግን ገንዘቡን ይሠርቃሉ። እግዴህ አባታችን አ ያዕቆብ በመዠመሪያ ጊዜ በናይቦችና በነዚህ ሽሆች የተቀበሉትን መከራ የወሰዱብዎን ገንዘብም አላወቅሁም። ከዚያ በኋላ ግን በዚያ ምንገድ ሲአልፉ ከርስዎ ጋራ ነበርሁና ያገኜዎ ጭንቅ ብዙ ነው። ፪ኛም ሉዊስ ሞቶሪ ነው በመዠመሪያ መምጣቴ ለምሳ በዚህ ሥፍራ አርፈን ሳለን ብዙ ሽሆ ከነመሳሪያ ሲመጣብን ቢያዩ ወንድሜ ሙሴ ሞንቶሪ ደንግጠው ተነሡና ላንዱ በቅሎ ተቀምጦ ለነበረው ሩጠው ሄደው ብርሃን ጨቀመጤ የተረታን አቀበት እግር ነው። ከዚህ በኋላ ወጥተው ሠዓሥዕ አድረው ከዚያም ወደ ድግሳ ደርሰው ባሕር ነጋሽ ዘጌርጊስ በሚባሉ በሹሙ ቤት ገቡ ወዲያው የኢትዮጵያ ሰው ነጭ ሰውን ሲያዩ ይገድላሉ ይበሉማል የሚል ተጽፎዋል እንግዲህ እኒህ የወንጌል መልእክተኞች ባገራቸው ሳሉ ይህን ታሪክ አውቀው ሳለ ወናሁ እፌንወክሙ ከመ አባግዕ ማዕከለ ተኵላት ያለውን ለመፈጸም ሊበሉ በፈቃዳቸው መምጣት ለፍቅራቸው መጠን ዳርቻ የላትም። የኢትዮጵያ ሰው ሰውን የሚበላ አገሩ ተለይቶ አልተጻፈላቸውምና ሰውን ባዩ ቁጥር የሚበላቸው ይመስላቸው የነበሩ ይመስለኛል። ስለዚህ ሙሴ ሞንቶሪ ከዚህ በላይ እንዳየን ፍራስ ስለገባችባቸው የበይውን አፍ በብር እንዲገዙ ፈጠኑ አ አ ያዕቆብም ይህነን ስላዩ ድግሳ በደረሱ ጊዜ እኔ ብሞት እነዚህ ይቀራሉ ብለው ሁለቱን በዚያ አገር ትተው ወደ አድዋ ተነሡ ከርስዎ ጋራም በምንገድ የነበረ የተከራይዋትንበቅሎ ከሚመልስ ፩ድ ሽሆ እስላም በቀር ቋንቋውን የሚአውቅ ስንቅ የሚሸከም የሚረዳዎም አልነበረም። ጦም እየዋሉ ማታ ማታ ጥቂት ወተትን ወዳደዋ ደረሱ። ይህም ምንገድ ለፈጣን ለ፫ቀን ይሆናል። ከራቡ ይልቅ በዚያ ጊዜ ቋንቋን አለማወቅና የፍራት ጥርጥር እያስጨነቀዎ ይመስለኛል ወደዚህ ከተማ ግን ገብተው ያገርዎን ሰዎች ሳልገኙ ደስ አለዎ እኒህም በኛ-ገጽ የተጻፈው ሙሴ ዮሴፍ ሳፒቶ ዮርዮሞንቴ ኢጣልያዊና ቴዎፍሎስ ፈረንሳዊ ናቸው። ነገር ግን በንጽሕና ኃይለ ነፍስ እሳት የተቃጠለች የጻድቅ ነፍስ

## ከ እኁድ

# ፲ኛ ክፍል ጥር

እነዚህን ሰዎች አገባባቸውን ለውጠው ባገኘቻቸው ጊዜ ከርሳቸው ጋራ ለመጫወት ለመኖርም ተሰቀቀች። ስለዚህ ሌሊት ብቻ አድረው ከነዚያ ተለይተው ገንዘብ ምንም ሳይኖራቸው ያቶ ተስፋ አንጥረኛን ቤት በመታመን ተከራይተው ገቡ። ይህም ደጃች ውቤ ትግሬን ከገቡ በኋላ በ፱ነኛው ዓመት ጌታችን ልደት በኋላ ፲፰፻፴፱ ዓ.ም በምሥራቃዊ ቁ ግንቦት ፰ ቀን ከዚህ በኋላ ፈጥነው ወደ ድግሳ ተመለሱና ወንድማማችዎን ይዘው መጡ በ፲ኛው ምዕራፍ ካቶሊክ ሃይማኖት በኢትዮጵያ እንዳትስፋፋ እንቅፋት ስለሆነ ነገር ይነገራል ካባ ያዕቆብ መምጣት በፊት የፕሮቴስታንት መልእክተኞች ወደ አገራችን መጥተው ነበር። ሳሙኤል ሌላው ጉበኛ እንግሊዝ በደጃዝማች ስባ ጋዲስ ጊዜ መጡ ዝንበርግና ሌሎቹም በደጃዝማች ውቤ ዘመን የመጡ ይመስለኛል። እነዚህም የመጡበት ምክንያት ካቶሊካዊ ሮማዊት ቤተ ክርስቲያን የምታስተምረውን ለማፍረስ ነው። ይህንም ለማድረግ የሚተጋ ቻይ ማድረጊያ አላቸው። ከቅ ቤ ካቶሊካዊት ለየተለዩበት ጊዜ በምእባራዊ ቁጥር በሺ፭፻፶፫ በምሥራቃዊ ፰ የጐደለው ነው። ስለዚህ እናታአቸው

ያጠባቻቸው የመንፈሳዊ ትምህርት ወተት ኃይል እስካሁን አላቸውግን ከእግዜር የተሰጡንን አምላካዊያት መጻሕፍቶች እውነተኛንም አምልኮ ለማሳሰብና ለመከተል የተደረጉትን መስቀልና አቃጠሏቸው የግዜር ወዳጆች እንደ መሰሉ እኒህን መጻሕፍቶች በቋንቋ ሁሉ ለመለዋወጥ ይተጋሉ በዚያም በሰው ክፋት ምክንያት የተጻፈ ታሪ አለበትና ከቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ወደ ዓለማዊ ቋንቋ ገልብጠው በሰጡት ጊዜ እንስሳዊት ፍትወት ላሸነፈችው ሰው ለክቱ ማገገን ሰጡት ይልቁንም ቅዱስ ጳውሎስ ፍሩኃከ ንበር አውልዓ ገዳም ያለውን አስበህ ከመፍራት ከቅዱስ ጴጥሮስ ቤ ክ ጋር ኑር እንጅ በርሳቸው ላይ አትመካ እነሆ እነዚያ በምሥራቃውያን ስሕተት ሲመኩ ይህንን መውደቅን ያገኑ ይመስለኛል። ሉተር የነምሳ ወይም ያልማ አገር ሰው ነው። መንኖ ወደ ገዳም ገብቶ መንኵሶ ሲኖር ኋላ ግን እጅግ ብልህ ነበርና በትዕቢት ኃይል መንፈስዊት ጸጋ ብትርቅለት እንስሳዊ ፍትወት አሸነፈችው ይላሉ። ካልቢኖም እንደ ምዕራባዊያን ሥራት በንጽሕና ማዕረግ ተቀብሎ የፍራንቅያ ዲያቆን ነበረ። እንዲሁ በሌላው ጊዜ በክፎች ነገሥት ልጆች ቅ ቤ ክርስቲያን ካቶሊካዊት ከሁከት ከመከራ አላረፈችም ባ፲፮ ዘመን በተነሳች መለያየትና ኑፋቄ ሁሉ የከፋች ዓይነትዋ ልዩ ስለሆነ እጅግ ታወከች ወደ ፕሮቴስታንት በግድ ለማግኘጥ የኃለኞች ሰይፍ ተመዘዘች ዳግመኛም ከሰይፍ ይልቅ የከፋ ነፍስ የሚያሳስትና የሚገድል ድርሳን በዛ። ይህንንም ጽሕፈት የሚአበዛ ማኅተም በብዙ ገንዘብ ተደረገ። ምዕመናን ካቶሊካውያን ስለወንጌል ሰባኮች ገንዘብን እንደኢመጸውቱ ፕሮቴስታንቶችም ከኒህ ይልቅ ፫ት እጽፍ አብልጠው ፲፫ ሚሊዮን ብር ወይም ፍራንክ ይሰበስባሉ ይላሉ። በዚህ ገንዘብ እውነተኛን አምልኮ ለማፍረስ ይሠሩበታል። እንግዲህ በፊት እንዳልሁ የነዚህ ወገን መልእክተኞች ወዳገራችን በመጡ ጊዜ እንደፈቃዳቸው እንጂ እንደ እግዜር ፈቃድ ያይደለ የመጽሐፍቶችን ቃል እያጐደሉ ቃሉንም እየለወጡ እያጐደሉም ያተሙትን መጻፍ ሌላውንም የኑፋቄአቸውን መጻፍና ድርሳን ብዙ አመጡ። ይህነን ሌላውንም ገንዘብ በመስጠት የዝንበርግ ስም በዓድዋ ታወቀች። በዚያም ፪ ታላቅ ቤት በብዙ ወገን የተከፈለ አሠሩ። አሥራ ፩ዱን ጨርሶ ፪ኛውን

# ኩ ሰኑይ ጥር

ሊዝምር ሳለ ደጃዝማች ውቤ አስለቅቀው ሰደዱት። ያስለቀቁበትም ምክንያት ያድዋ መድኃኔ ዓለም አለቃ ዕንቈ ሥላሴና ሌሎችም ካህናቶች በሃይማኖት ስለ ከሰሱት ነው። ነገር ግን ሰውነቱ ለቀቀ እንጅ ለካቶሊካዊ መልእክተኛ ዕንቅፋት የምትሆን ነገሩ አለቀቀችም። ከርሱ ገንዘብ ሲቀበሉ የነበሩ እግዜርን መፍራት የሌላቸው ወደ አቡነ ያዕቆብ መጥተው ገንዘብ ያበድሩኝ አሉዎ ቁጥሩም ፺ ብር ይመስለኛል። አባታችንም እኒህ ኃይለኛ ሰው ያደረጉትን ሰምተው ነበሩና እነሆ ያልከኝን አበድርሃለሁ።

ነገር ግን ብድርህን እንዳትከፍል ፩ዱን አውሮፓዊ እንደሰደድከው ሰምቻለሁና እንደርሱ እንዳታደርግብኝ ትከፍለኛለህ አለዚያስ ይቅርብህ ስሉት። ነገር ግን ከሮም በተመለሱ ጊዜ ከፈለ። እንደ ፕሮቴስታንቶች ባሕል ጾም የለም። ቊርባንም ከበሉ በኋላ ይገባል ይላሉ። ዝንበርግ ይህንና ሌላውን ልማድን በቤቱ ሲአደርግ ያዩት ባወሩበት ጊዜ በመልክ ፩ድ ስለሆነ አውሮፓውያን ሁሉ ተነቀፉ። ዳግመኛም ልጁንና የሎሌውን ልጅ በቤቱ ውስጥ ማስቀበሩ እስላም ነው አሰኘው። ከዚያ በኋላ ያቡነ ያዕቆብ ደግነት ይልቁንም ወደ ሮማ ይዘዋቸው የወረዱ የደጃች ውቤ መልእክተኞች እነ አለቃ ሀብተ ሥላሴ ከዚያ ተመልሰው እስኪ መሰክሩ ድረስ ኤውሮፓዊ ሰው ክርስቲያን አይመስላቸውም ነበር። ባጼ ሱስዮስ ጊዜ በጥንቸል ሥጋና በውሻ ጥንቅላት ባፍርንጅ ካልቆረባችሁ እያለ ዘመዶቻችንን ያስፈጀ ወገኖች እኒህ አይደሉምን ዓይናችሁ ይፍሰስ ዳግመኛም አሁን ሊአደርጉ ወደአገራችን መጡብን እንዳውሬ አሁን ይበላሉ ምን ምን እርም ያላቸውም እስላም ያረደውን ያበላሉ ብዙ መጥላት ብዙ ነቀፋም አላቸው። እንግዴህ አባታችን አ ያዕቆብ ፩ድ አካል ፪ ባሕርይ ብለው ሲአስተምሩ ራስዎን ለመጠበቅ ስንኳ በዚህ ሕዝብ ማሃል ለመኖር ጌታችን ባይጠብቅቀ አይችሉም ነበር። እርሱም አጋዥነቱን እንዲአበዛልዎ ጨለማ ሁሉ ባ፩ድ ጊዜ የሚያርቅን የምሕረቱ

ብርሃን በኢትዮጵያ ላይ እንዲገለጥ ወጥሮ በታላቅ ጭንቅ ወደርሱ ሲለምኑ ነበር። ከመዠመሪያው አባታችን የኢትዮጵያ ሐዋርያት ፍሬ ምናጦስ ጭንቅ እኒህ አባታችን እንድትበረታ የታወቀ ነው። እንዴታ ቢሉ በታሪከ ነገሥት እንደተጻፈ በስንክሳርም እንዳለ ፍሬ ምናጦስ ከሣቴ ብርሃን ከሕጻንነትዎ ዠምሮ እስኪ አድጉ በንጉሥ ቤትና በሌሎችም በአክሡም ባላገሮች የተላመዱ የተወደዱም ነበሩ ስለዚህ ተመልሰው ወደዚህ በመጡ ጊዜ በደስታ ተቀብለዋቸው ትምህርታቸውንም ለመቀበል የ፱ ነገሥታት ወንድሞች የአብርሃና አጽብሃ ልብ በአምላካዊት ፍቅር የተቃጠለች ስለሆነች አክሡምም አገሪቱ ታላቅ ሆነች እርስዋንም አብነት አድርገው ሌሎች አሕዛብ የጌታችንን መልእክተኞች አልገደሉም። ከጉባዔ ኬልቄዶንም በኋላ ከሮም የመጡ ፱ ቅዱሳን ፩ድ ባሕርይ ማለት ገና በዚች የክርስቶስ እርሻ አልተዘራችም ነበርና ምክራቸውንና ትምህርታቸውን በፍቅር ተከሉ እንጅ አልተሰቃዩም። ከነዚህ በኋላ የመጣ አቡነ አልፎንስ የፊተኛውም ሰባኪ አ ጴጥሮስ ፓዴዝ ባሰናዳለት የንጉሥ መኳንንቱም ካቶሊካውያን ሁነው ስላገኛቸው በሩቅ የነበረ በደስታ እንዲመለስ ወደዚች አገር ገባ እንጂ በጭንቅ አልገባም በደስታውም ብዛት በራሱና በወንድሞቹ ላይ የማጥፋትን አዘን መከራንም አመጣ። ይህም ከዚያ ጊዜ ዠምሮ እስካሁን የማይጠፋ እሳት ሆነ። ፪ት ባሕርይ ከማለት ይልቅ ለኢትዮጵያ

# ኪ. ሥሉስ ጥር

ሰዎች የምታሰናዳቸው በአልፎንሱ የተደረገች ነገር ናት። ፈረንጆችን ሲያዩ መግደላቸውን ይመኛሉ። እንግዴህ ሌሎች ዘግተዋት የሄዱ የውኃ አዘቅት ያዕቆብ መጥቶ እስኪከፍትላቸው ድረስ በጎች ጽማት እንዳቅበዘበዛቸው እግዜርን የምትፈራ ነፍስም በኃይላተ ነፍስ እጅግ የበረቱ አባታችን አ ያዕ እስኪመጡ ድረስ በግብጾች አስተኛ ከዚህ በፊትም በጠራሁት ስሕተት ታላላቅ ደንጊያዮች የተዘጋችን ኢትዮጵያ ከርስዋ በፊት የመጡ መልእክተኞች መክፈት ስለአልተቻላቸው ጠባቂ እንደሌላት በግ ሁና የሕይወት ውኃን አጥታ ስትቅበዘበዝ ነበረች። አሁን ይህን በብዙዎች ኢትዮጵያውያን እጅ ስለሚገኝ ይህ ጽሑፍ ይህን ጽሑፍ እየመሰላቸው ልባቸው እንደተማረከ በወረቀት ላይ ለማስፈር የምደከመው በከንቱ አይደለም ይህ ጽሑፍ እንዳይቀር በማለት ነው። እንደ እውነተኛው ኢትዮጵያ አረማዊ ሆና ኖረች ብሎ መጻፍ የኢትዮጵያ ሕዝቦች አስተማሪ አጥተው በድንቁርና ኖሩ ማለት ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር መጋፋት አይሆንም ይሆንን ወደሥሩ እመለሳለሁ። እንግዴህ ይህንን ደንጊያ ማንሳት የግዜር ኃይል መሆንዋን እንድናውቅ የዘመኑን ርዝመት እንይ።

፩ድ ፩ድ ባለታሪኮች እንዳሉ በ፲፮ኛ፻ መጨረሻ ያውጣኪ ትምርት ፩ድ ባሕርይ ወደ ኢትዮጵያ ገባች በጊዮርጊስ ወልደ ዓሚድ ታሪከ ስለ አባ ብንያሚን በጻፈው ግን ከዑመር ተንባላታዊ የተማመለበትን ብናይ በ፲፮ኛ፻ ይመስለኛል። እንግዴህ እስከ ብዙ ዘመን ያልተቀበሉት ቢሆን ከዚያ ዠምሮ እስካሁ ፩ሺ፩፻፫ ዘመን ሆንዋልና ይህን ያልህ ጊዜ ፩ድ ባሕርይ በማለት የተዘጋችን ልብ መክፈት የእግዜር ኃይል እንደ ሙሐመድ በሰይፍ ካልሆነ ባ፩ድ ድካም መነኵሴ ይህነን ማስለቀቅ የማይችል ነበረ ይላል።) የሮማ ልዑካን ከኋላቸው ጦር ማስከተላቸው እየተስማቸው የኢትዮጵያን ሕዝበ ክርስቲያን ለመፍጀት ቤተ ክርስቲያንንም ለማቃጠል አሳብቸውን የገለጹበት ጽሑፍ እንደዚህ ሆኖ ሲገለጽ ይታያል። "በ፫ኛ ክፍል ባ፪ኛ ም በ፻፲ ገጽ አባታችን አ ያዕቆብን ደጃች ውቤ የለመኑበትን ምክንያት ይገልጣል። ካዋጅ በፊት ደጃች ውቤ ወደምስር ጳጳስ ወዳባ ጴጥሮስ ጳጳስን እንዲሰዱላቸው ልከው ነበረ የሱን የእሽታ ምላሽ ወደርሳቸው ያመጡ ከኢየሩሳሌም የተመለሱ መነኰሳት ናቸው። እኒሁም ባላባራስ ኪዳነ ማርያም አባ እንግዳ አባ ገብረ ሕይወት ናቸው። አቡነ ያዕቆብንም እንዲለምኑ ለደጃች ውቤ ያማከሩ እነዚህ ናቸው ይላሉ። እንዲህ ሲሉ ፈረንጆች በእስላም ላይ በርትተዋል ስለዚህ በዓድዋ ያሉን አባ ያዕቆብን ከመልክተኞችዎ ጋራ ባይሰዱ በእስላሞች እጅ እጅግ መከራን በምንገድ ሁሉ ልንቀበል ነን። ገንዘብዎም እሰከ ምሥር ሳይደርስ ይፈጁታል ብለው ነገሩ ገዥውም ይህነን ምክርን

ሰምተው አባታችንን አስጠርተው እንደዚህ አሉ ጳጳስ ለማስመጣት አሁን ወደ ምሥር ልልክ ነኝና ከመልክተኞች ጋራ ሂድልኝ አሉዎ ይህችም ልመና ባባታችን ልብ ገብታ እጅግ አስጨነቀች ጭንቀቱም በ፪ ወገን ነው ፩ድ ያ አይሆንልኝም ቢሏቸው ስለሚመጣው መከራ ነው። ፪ኛው እሽ ቢሉ ካገርዎ ሰዎች የምትመጣብዎ መነቀፍ ናት ስለዚህ እሺ ወይም እምቢ ሳይሉ ወደቤትዎ የተመሰሉ ይመስለኛል ከዚህ በኋላ በዚያ ጊዜ ከደጃች ውቤ የነበሩ ኋላም ወደ ሮም ሄደው ካቶሊክ የሆኑ አማሬ ክንፉ እንዲህ አሉኝ እስላምና እንግዳ የሚባሉ የተጠያየቁበትና የተከራከሩበት የሚመስል ታናሽ መጽሐፍን አምጥተው ለደጃች ውቤ

## ካ ረቡዕ ጥር

ሰጡ በርሱም የካቶሊክ ሃይማኖት ብቻ እውነተኛ እንደሆነች የሮም ጳጳስ ሃይማኖተኛ ጠባቂ የማይሳሳት ዳኛ መሆኑን የኬልቄዶን ጉባዔ የወሰኗት ሃይማኖት ከንስጥሮስ ሃይማኖት እጅግ ልዩ እንደሆነች ተጽፏል ይላል። የንስጥሮስና የልዮንን ሃይማኖት ምን ለየው ሊባል ይሆን ከንስጥሮስ የተለየ መስሎ የሚታየው ፪ አካል ማለት ቀረ እንጅ ፪ ባሕርይ ማለት አልቀረም። ዛሬም ከካቶሊካውያን መጻፍ እግዚአብሔር ወልድ በመለኮት ከአብ በታች ነው ሲል ይገኛል ይህ ምን ማለት ይሆን።

"ነገር ግን ባየነው ጊዜ ይህ ሰው እንዴት እንደ ደፈረ ወደዚህ መጥቶ የልዮንን ሃይማኖት እስኪ ድረስ አልነ አሉኝ በፈረንሳዊ ቋንቋ የተጻፈ ገድልዎ እንደዚህ ይላል። ወደ ደጃች ውቤ ተመልሰው እንዲህ አሉ እኔ ካቶሊክ ነኝ ደግሞ ከሰዎችም ጋራ ወደ ግብጽ መሔድን አልወድም የተወደደችውን ሃይማኖቴን በልቤ እየጠየቅሁ እያንን ማገዝ እውነት ነው እላለሁ ገዥውንም እንዲህ አሉ ራሳቸውንና ገንዘብዎን ለመጠበቅ ከመልእክተኞችዎ ጋር እሽ እሄዳለሁ ነገር ግን እኔም ፪ት ነገር እሽ እንዲሉኝ እለምንዎታለሁ። ፩ድያ መልእክተኞችዎ ከኔ ጋራ ሄደው በቅዱስ ጳውሎስ ወምበር ተቀምጦ ያለውን የጌታችንን ምስለኔ እንዲያዩልኝ ፪ኛም ከዚያ ወደዚህ ስመለስ የምቀርበት ታናሽ ቦታን ማለት ቤተ ክርስቲያንን የምሠራበትን እንዲሰጡኝ እለምንዎታለሁ አሉ። ገዥውም እሽ አሉ ነገር ግን ስለ ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ከምሥር ጳጳስ ጋራ ተማከሩ። እርሱ ቢወድ እኔም እፈቅዳለሁ። ስለዚህ እነሆ ወረቀቴን ወደርሱ የምትደርስ እሰጥሃለሁ ብለው አትመው ሰጡ። የሚባለውንም ቃል በሱ የተጻፈ አላውቅሁም ዳግመኛም አባታችን ከደጃች ውቤ ለሮም ርዕሰ ሊቀ ጳጳስ የምትደርስ ወረቀትን ለመኑ በርሱም የተጻፈው አባታችን ከደጃች

ውቤ እንደተለመኑ የርሳቸውም መልእክተኞች ሮምን ደርሰው ከቅዱስ ጴጥሮስ ተከታይ ለመገናኘት እንዳዘዙ ነው። ፫ኛ ምዕ በ፻፫ኛ ገጽ የመልእክተኞችን መነሳት ይናገራል ይህም በጥር ፲፪ኛ ቀን ከክርስቶስ በፊት በሽ፰፻፵፫ ዓ ነው አባታችንም ወደ ዓድዋ ከገቡ ባ፲፮ኛው ወር ያይነተኞችም መልእክተኞች ቁ ፯ ርዕሰ ደብር ወልዱ የደጃች ውቤ ንስሐ አባት ሌሎችን ፫ቱ ፯ኛውም አባቴ ገብረ ሚካኤል የካቶሊካውያን ታሪክ በተጻፈበት በሌላው መጽሐፍ በግዕዝ በተጻፈው እንደተነገረ ቁጥር ኋላ እንናገራለሁ። የገንዘቡ ቁጥር ግን ፰ሺ ነበር ይላሉ (ሐተታ ፰ሺ ሲባል በጥሬ ብር ማለት ነው። እንጅ ወርቅ አይደለም ይህም ፰ሽ የተባለው ፩ዱ ወቄት በ፰ ብር ሲታሰብ ልክ ፻፻ ወቄት ብር ይሆናል ከሌላም ከብዙ ብታ ላይ ተጽፎ የሚገኘው ፻፻ ወቄት ወርቅ ነው። አሁም ፰ሽ ብሎ መጻፉ ደህና ነው። "ለታላላቅ ሰዎችም በረከት የሚሰጡ ፱ ባሮች ነበሩባቸው ይላል መልእክተኞች ከማይ ደላዕታ ከደጃች ውቤ ሰፈር ምጽዋን ሲነሱ አባታቸው አርቃዴዎስ ፈረንሳዊ እንደታመመ ሰምተው ወደዛና ሄደው ነበር ካባታችንም ጋራ እንሄዳለን እያሉ ብዙ ጐበዞች ተነሥተው ነበሩ ከነዚህ ሁሉ ወልደ ሚካኤል የሚባል ሄዶ ነበር እሱም እዚያው ሙቆ ቀረ። የሞተም ሄዶ የፕሮፓጋንዳ ትምህርት ቤት ገብቶ ሲማር ነው። ምጽዋ ሲደርሱ ከፍራስያ ተመልሰው ጌታ ሌፌብር ወይም ቴዎፍሎስን

## ኬ ኃሙስ ጥር

አገኙ እኝህ ሰው የደጃች ውቤን መልእክተኞች እስካገራቸው ወስደው ከፍራንሲያ ንጉሥ ሊዊ ፊሊጵ ጋራ ተገናኝተው መጡ ከዕርሳቸውም ብልሐተኞችን ሰዎች ከብዙ መሣሪያቸው ጋራ አምጥተው ነበረ። መድፍን ቦምባን ምንጣፍን ሌላውንም ብልሃት አድራጎት ነበሩ ነገር ግን ደጃች ውቤ አዋቂ ብልህ ሲባሉ በዚህ ነገር አላስተዋሉም የጌታ ቴዎፍሎስን ምክር እንደሚገባ አልሰሙምና ይባላል። ፪ኛም በገጽ ፻፲፪ኛ ከምጽዋ ወደ ጂዳ መነሳታቸውን ይናገራሉ ከመነኰሳቱ ፳፯ ሰዎች ነበሩ እስላሞች ክርስቲያንን በመጥላት ከምጽዋ ከተነሡ በ፲፩ኛ ቀን ጊዳ ደረሱ አባታችን መልእክተኞችን ወደ ኮንሱል ፈረንሳዊ አገቧቸው (ከዚያም ወደ ግብጽ ገብተው ስለ ጳጳሱ መቀበል ሕጻን ስለነበሩ ብዙ ጭቅጭቅ እንደተደረገ ይጽፋል ከመልእክተኞቹም ግማሾቹ ካባ ያዕቆብ ጋራ በዚያውም ወደ ሮማ ሄደዋል ግማሾቹ አቡኑን ተቀብለው በቀጥታ ወደ ሀገራቸው መጥተዋል። ከሮማ እስከመለስ ሊጠብቁን ምለውልን ነበር። መሐላውን አፍርሰው ሄዱ ይሏቸዋል። በ፻ሠ፱ ገጽ ካባ ያዕቆብ ጋራ በደጃች ውቤ ጉዳይ ወደ ግብጽ ሄደው ከግብጽ ወደ ሮማ ሄደው በነበረ ጊዜ አብረዋቸው ሄደው ለነበሩ ሰዎች ሃይማኖታቸውን ለተቀበሉ። ፫ቱ ዓይነተኞች ከፓፓ ፫ት የወርቅ መዳልያ ተቀብለዋል። ሌሎችም እንደ መዓረጋቸው የብር መዳልያ መስቀልን ተቀበሉ። ከካርዲናሎችም የፍቅር ማሳሰቢያ የሚሆን ሥዕል መስቀልን ተቀበሉ። አባታችን ለደጃች ውቤ የምትደርስን ከፓፓ ተቀበሉ። ቅ አባታችን እኔ ስለምን ውቤን ደስ የሚአሰኝ ነገር ለማግኘት የመዝገብ ሹም ካርዲናልን ጠይቅ አለኝ በመጨረሻም ወደኔ የደረሱ የፓፓ ቃሎች እንደዚህ ሆኑ ቀጥሎም አበሻን ወደንስሐ ለመመለስና እኛን ለማሰናበት የሐዋርያዊት ሰውነት መስማቶችን ገለጸ። ለደጃች ውቤ የሚሆኑ ገጸ በረከቶች ተዘጋጁ ከነዚህም ፩ዱ በታላቅ ጥበብ የተሠራ እጅግም ባማረ በወርቅ ድሪ የተንጠለጠለ መስቀል ነበረ። በዚችም ባምላክ ልጅ ፪ት ባሕርይ እንዳሉት የሚአመለክቱ ቃሎችን ይዛ ነበረች። አብረው ሄደው ለነበሩ ከፓፓ ሽልማት አግኝተው ደግሞ ወደ ንጉሡ ቀርበው ለ፫ት ዓይነተኞች በወርቅ ዲሪ የተንጠለጠሉ ፫ት የወርቅ ሰዓቶች ዋጋው እያንዳንዱ ፪፻፹ ይሆናል ለሌሎቹም በምሥል የፈሰሰ የፊቱን መልክ ዋጋው ፳ ፳ ብር ይህን ተቀብለው ጥቅምት ፳ ቀን ባ፲፰፻፵፩ ዓመተ ሥጋዌ ከናፖሊ በፈረንሳዊ የእሳት መርከብ ወደ እስክንድርያ መጡ በ፻፶፯ኛ ገጽ ባ፲፫ኛ ም አባ ያዕቆብ ከምሥር

መነሳታቸውን ይናገራል አባታችን አቡነ ያዕቆብ በፊት የጠራኋቸውን ወንድሞችዎንና ከኢየሩሳሌም ያመጣናቸው ሰዎች ይዘው ከምሥር ተነሱ በዚያ ዘመን እንዳሁኑ የሠረገላ ምንገድ አልነበረምና ሰውም በግመል ወይም ባሕያ ይሄዱ ነበረ በዚያ ምንገድም ስለ ኢትዮጵያውያን ምንገደኝኖች በብዙ መድከማቸውን ብዙማ ገንዘብ ማውጣቸውን ይናገራል ሮማ በምን ያህል ፍተር ኢትዮጵያን እንደወደደች አሁን በምናስከትለው ነገር ይታይላ። እነሆ ወደ ሮም ገብተው እስቲወጡ ድረስ ባ፩ ወር ብቻ ስለ ሀገራችን ሰዎች የፈጁት ገንዘብ ፫ሽ ብር ነው ይላሉ። እንዲህ ከሆነ ከምጽዋ ተነሥተው እስከ ምሥር እስከ ኢየሩሳሌምና ሮማ ከዚያም ወደ አገራችን እስቲመለሱ ስለመልእክተኞችና ስለ ሌሎችም የፈጁት በጥቂቱ ብናስበው ፳ሽ ይሆናል። ይህም ብቻ አይደለም ከዚያ ዠምሮ እስካሁን ፴፰ ዓ ሆነ በያመቱ ስለ ኢትዮጵያ

# ከ ዓርብ ጥር

ደኅንነት ቅ ቤ ያን ካ መልእክተኞቿ እጅ ያፈሰሰችውን ገንዘብ ካቅሜ በላይ ነውና መቁጠሩ አይቻለኝም ከፕርፓጋንዳ ብቻ በያመቱ ባባታችን ባቡነ ያዕቆብ ፬ሽ ብር ታዞ ነበረ። መባ ወይም እንደ ስለት የተሰጠ ከኤውሮፓውያን ሰዎች ግን ቁጥሩ ባገራችን ያሉት ካቶሊካውያን ፓፓ ብቻ ያውቃል። እነሆ ካ፲፰፻፸ ዓ ዠምሮ እስከ ፸፩ኛው ዓ.ም ድረስ ለድኃ በባጎስና በሌላውም አገር አባታችን አቡነ ዮሴፍ የመጸወቱት ባይበዛ ፲፪ሽ ብር ይሆናል

አባት እናታቸው የሞቱትንም የተአሉትንም አሽከሮች አሰብስበው በታላቅ ቤት እስካሁን ይመግባሉ። አባት ነኝ የሚለው ከምሥር የመጣው ግን የሚጠቅምን ነገር ለልጆች አይሰብም። ከኢትዮጵያ ያገኘውን ገንዘብ ፩ ወገን እንደሻው ለመኖር ለሥጋው ፍትወት ፪ኛው ለመናገጃ ፫ኛው በምሥር ለቤት መሥሪያ አድርገው እንዴት በጎ ያደረገችለትን እናት ጠልቶ መዋረድን መሰደብን የሚአደርግ በሊውንና ነጣቂውን ተኰላ የሚወድ ከሆነ ጌታችን ታምራቱንና በጐነቱን በናቁ ሰዎች የተናገሩትን ወዮታ እንዲደርስባት እርግጥ ነው።) እንግዴህ ከላይ የተጻፈውን ሁሉ ልብ ብሎ ማስተዋል ነው። ኢትዮጵያ የተዋጋችበትን ጦር መመልከት ነው። ከላይ የተጻፈውን ሁሉ ማስተዋል ለማንኛውም ጠቃሚ መሆኑን ለወጣቶቹ ለመግለጽ ነው። “በ፻፳፱ ገጽ ያዕቆብ የመጣውን ዕቃ አሲዘው ካድዋ ደጃች ውቤ ወዳሉበት ሐውዜን ሔዱ። የዕቃውም ዓይነት ብዙ ነበር። አዲስ ግምጃና ምንጣፍ አዲስ ዓይነትም ነፍጥና ጐራዴ ባለመንኰራኵር አጎበር ጉልላትም ያለበት አልጋ ከነሰርፉና ከነመከዳው ክቡር ዕንቍም ያለበት ዋጋ ፫፻ ብር የሚሆንም ወርቅም በሚመስል የተቀባ የፍንጃል ወጭት ሌላም ስጦታ ደጃች ውቤም ከጧት ዠምረው እስከ እኩለ ቀን ድረስ ሲመለከቱ ዋሉና በደስታ ተቀበሉ። ስለዚህ ሁሉ ገንዘብ ዋጋው ቁጥር ካባታችን በቅር ሌላ የሚአውቀው ያለ አይመስለኝም ይህን ሁሉ መስጠትዎ ቤተ ክ የሚሠሩበት ቦታ ለማግኘት ነበር። ምንም ደስ ቢላቸው ይህነን መስጠት አልደፈሩም ግን ፳፫ት ጫን እህል ቢአዙላቸው አልቀበልም ብለው ተውት ይላል። በ፻፸ ገጽ ደጃች ውቤ ላባታችን ያደረጉትን ወሮታ ይናገራል ከሮማ ከተመለሱ በኋላ በ፫ኛው ዓመት በሐውዜንም በፊት እንዳልሁ ለገጁ ከተናገሩ በኋላ ባ፩ ዓመት ደጃች ውቤ ቦጎስን ዘርፈው ተመልሰው በፈረስ ማይ በሰፈሩ ጊዜ አባታችንን አስጠሩ። እንትጮን ጉልት መኖሪያ እንድትሆን ሰጥቸኽለሁ አልዋቸው ይህች አገር መስኖና አታክልት ያለባት መልካም አገር ናት ነገር ግን ያቶ ኮፊን ሹመት የነበረውን ብቻ ስጡዎ እንጅ እንኪጮን በሙሉ አልሰጡም ባይበዛ ባመት የሚወጣ ከዚያ አገር ፳፻ ሸማ ግብር ይሆናል። እኒህ አቶ ኮፊን በራስ ወልደ ሥላሴ ዘመን የመጡ የእንግሊዝ ወታደር ወይም ጨዋ ናቸው ከዚህ ዠምረው እስከ ደጃች ሰባጋዲስ ነበሩ። ከደጃች ሰባጋዲስ ወደ ጊዮርጊስ የእንግሊዝ ንጉሥ አሁን የሞተች የእንግሊዝ ንግሥት ቢክቶሪያ አባት ተልከው ሄደው ነበረ። ንጉሥ እስከ ሽህ የሚሆን ባለቡላድ ነፍጥ ወይም የበዛ ለደጃች ስባጋዲስ ሰደደ። እንግሊዞች

በሁሉ እርሳቸውን በኢትዮጵያ ሊአነግሡና ደጃች ሰባጋዲያስም እነዚያ የፈለጉትን ሊያደርጉ ሊሰጡ ተዋውለው ነበር ይላሉ፡ ነገር ግን አቶ ኮፊን ነፍጡን ይዘው ወደ ምጽዋ ሲደርሱ ደጃች ሰባጋዲስ ከራስ ማርዩ ጋር በማይ እስላማይ ተዋግተው ሞቱ። ይህም ውጊያ ከጌታ

# ኮ ቀዳም ጥር

ልደት ባ፲፻፹፮ ዓ ነው።” መቸም ስለ ኢትዮጵያ የሚያስብ ስለሌለ እንግሊዞችም በበኩላቸው ደጃች ሳባጋዲስን አባብለው ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ሚሲዮኖች ዠምረው እንደነበር ያስረዳናል። የአውሮፓ ሚሲዮኖች በየሀገሩ የሚወጥኑት ለምድራዊ መንግሥታቸው መሆኑን በነሱ አማካይነት ከላይ የተጻፈው መሣሪያ ያስረዳል። “በ፻፸፯ኛ ከምጽዋ ከመጡ እንግሊዞች ጋራ በዚያ ተገናኙ ስማቸውም ቤል ዮሐንስ ጵላውደን ቅርኪን ጊዮርጊስ ይባላሉ መዠመሪያ ወዳገራችን የገቡበት ጊዜ ነው እኒህ ጌቶች ሳይመጡ ዠምባርግና ክራፍ ከደጃች ውቤ ወርና እኩል ሆኖ ነበር። በ፪፻፱ነኛ ገጽ በ፲፻፴፯ኛ ዓ.ም ባጼ ሣህሉ መንግሥት በደጃች ውቤ ዘመን በጎልዓ ቦታን ገዝተው ብዙ ቤት አሠርተው እንደነበር ይናገራል። ባለአገሮችም የሚሸጡልዎ ስፍራን ካዩ በኋላ ነገሩን ለማጥናት ላይነተኞቹ ብቻ የሚሆን ፷ ብርን ሰጡ። ያዩትም ቦታ ይህ ነው ማይ መስኖ ከሚባለው ከምዕራብ ወገን ወደ ምሥራቅ ሲመጡ በግራ ኩል የምትባል እርሻ አሳዩ የሻለቃ ሐጐስን ቤት በቀኝ ትተው ላዕላይ ገዛ ወደሚባለው ዓለት ያለበትን ባድማ አሳዩ እዳ አቡነ እስጢፋኖስ የሚባለው ትናሽ ውኃ ያለበትን ዱር ወደ ቀኝ ትተው ዝባን ላባት ወደሚባለው መጡ። ከዚያም ገመገሙን ዞረው ወደ ካህናቱ ቤት ወረዱ የቄስ ወልደ ኤዎስጣቴዎስ ቤት ወደ ቀኝ ትተው ስለ አባቅልቶችዎ

እንድትሆን ብለው በዱር ያለች መስክ ወደ ግራ ትተው ኩክ ወዳልኋት ተመለሱ ከበቡት በውሃው መሄጃ ካሉ ዛፎች በቀር ረግጠን ያሳየንዎ ቦታ በቤተ ክርስቲያኑም አጠገብ ያለ ዱር ሁሉ እነሆ የርስዎ ይሆናል አሉ። ከዚያም ከዱር የሚወጣው ውኃ አለበትና መስኖ ያጠጡበታል ወደቤትም ይመራል ይላል።) የሮማ ልዑካን መናኔ ዓለም ነን እያሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት ተቆርቋሪ ሆነን ለማስተማር መጣን ይላሉ። ይኸውና ሰፊ ምድር ሲገዙ ይታያሉ። ይህ መሬት መግዛት የማን ሥራ ይሆን ዓለምማ ስንኳን የሌላ ሊገዛ የራሱንም ሼጦ ለነዳያን ይመጸውታል የነሱን ረቂቅ ሥራ በጥንቃቄ መመልከት ነው (በ፪፻፴፫ኛ ገጽ ወደ ተጠሩት ፫ ደጃች ውቤ ሹማምንት ወደ ፈረንጅ ሃይማኖት የገቡትን ካህናት አሥራችሁ ስደዱልኝ ብለው ላኩባቸው በወርኀ ታኅሣሥ ቄስ ገብረ መድኅንና ቄስ ገብረ ሕይወትን ይዘው ወሰዱ ሌሎች ግን አመለጡ የነዚህ ካህናቶች ቤት ተዘረፈ አባታችን በነገታው ወደ ሹማምንት ሄደው እንዲያስለቅቋቸው ለመኑ አልሰሟቸውም። ከዚያ ተመልሰው አባቴ እምነቱንና አባ ገብረ ኢጋዕዝትን ወደ ደጃች እሸቱ ላኩ። እርሳቸውም ያን ጊዜ መጥተው በሠሪሮ ሠፍረው ነበረ። መነኰሳቱ ብዘትን በደረሱ ጊዜ የፊታውራሪ ገብረ አምላክ ልጆች በሽፍትነት የነበሩ አሻግረው አይተዋቸው አቡን የሰጣቸውን አክሎች ወሰዱባቸው ደብድበው ልብሳቸውንም ገፈዋቸው ሄዱ በዚህ ምክንያት መከራ ደረሰባቸው። በ፪፻፴፯ ገጽ ፲፰ኛ ምዕራፍ አባ ሰላማ ደብረ ዳሞ ወጥተው የተመቸ ጥኑ ስፍራ ባገኙ ጊዜ ግዝታቸውን ከበፊቱ ይልቅ አበረቱ ጌታችንም እውነተኞቹን ከሐሰተኞች ተለይተው ለሁሉ ዓይን እንዲገለጡ ብሎ ፈቃዱን አልከለከለውም እነሆ በዚህ ዘመን ደጃች ውቤ በሰሜን ተጨንቀው ሳሉ መኳንንቶች በእርሳቸው በመፍራት ያቡን ፈቃድ አልፈጸሙም ነበር። ግን ወደ ሐውዜን ከመጡ በኋላ ይፈርዋቸው ይመስል ናቅዋቸው አቡን ፩ዱን መነኵሴ ካሉበት ወደ ሐውዜን እንዲገዝት ሰደዱት። ስለዚህ ባደባባይ ቁሞ ውቤን የተከተልህ

# ወ እጉድ ጥር

አቡን ገዝተውሃል አለ። ደጃች ውቤም ይህን ሰምተው ተናደዱ ከተማዪቱን አዙረህ ግረፈው አሉ። ዳግመኛ የግዝትን መልእክት ሁሉ በትግሬ ገዳማትና ገባያ ሰደዱ። ቃሉም እንደዚህ ነበር። ፈረንጅ ሁነዋልና ውቤን የተከተልክ እንጨት የሰበርህ ውኃም የቀዳህ ውጉዝ ነህ ዳግመኛ አብያተ ክርስቲያን ሁሉ እንዳይከፈቱ የተወለደ እንዳይጠመቅ የሞተም እንዳይፈታ አውግዣለሁ አሉ። በዚህ ምክንያት ስባጋዲስ ጓንጉል ካቶሊካዊያንን ያስጨንቁ ዠመሩ። በ፪፻፵፩ኛ ገጽ አብቡን ከደብረ ዳሞ እስቲወርዱ ድረስ አቡነ ያዕቆብን ከጐልዓ ይለቀቅ ኋላ አስመልሰዋለሁና በምሥጢር ንገሩት ብለው ላከዋቸው። ከዚህም በኋላ መልእክተኛ ከደጃች ውቤ ወደ ጉልዓ ከጎልዓ ይለቀቁ ወደ ጐንደደር ወይም ወደ ምጽዋ ቢፈልጉ እሸኘዎታለሁ አሉዎ ብሎ። ፈጥሞ ነገረ አባታችን ግን ከገዥው ካልሰማሁ አለቅም ብለው ወደ ሐውዜን ሄዱ ከደጃዝማች መኳንንቶችና ከመካሮች ጋራ በታላቁ አዳራሽ በተቀመጡ ጊዜ ሊቀ ካህናት ሃብተ ሥላሴና ብላታ ኮከቤ ላባታችን እንዲህ አሉ። የተወለዱ ሳይጠመቁ የታመሙ ሳይናዘዙ መሞት አብያተ ክርስቲያናትም መዘጋት እነሆ በርስዎ ምክንያት ሆነና ይልቀቁልን አሉዎ። አባታችንም ነገሩ ሲዠምር ቆሙ ጌታችን በጲላጦስ ፊት አልቆመምን ብለው አባቶች ሆይ እሺ እለቅላችኋለሁ ነገር ግን ልጆቼን ብትበድሉ ቤቴንም ብታፈርሱ እኔም ከነዚያ ጋር ልሞት እመጣለሁ አሉ። ሊቀ ካህናትና ብላታ ኮከቤም በልጆችዎ ላይ ክፉን አናደርግም ለቤትዎም ጠባቂ ያኑሩበት አሉ። ነገር ግን በዚህ አልቆመም ከዚህ በኋላ አባታችን ከሐውዜን ወደ ጐልዓ ተመለሱ። አቶ ወርቁም የአከለ ጉዛይ ሹም እርስዎን ሊአስለቅቁ እስከ ምጽዋ አፋፍ ሊአደርሱ ታዘው መጡ። አባታችን ከጐልዓ እስከ ምጽዋ ሲሰደዱ በመስከረም ፴ ከልደት በኋላ ፲፰፻፵፩ ዓ.ም ነ። ከሮም በተመለሱ በ፮ኛው ዓመት ወደ ጐልዓ በገቡ በ፱ነኛው ተነሱ ተነሱ ሲነሱም ከሩቅና ከቅርብ ያሉም ምዕመናን ልጆችዎ ከቤትዎ ሲወጡ ዝምሮ በንቴ ወደ ምትባል እስቲደርሱ እንደ ዕለተ ሞትዎ ሁሉ ልቅሶና ወዮታን አስደርጉ እርስዎም እየተንስቀሰቁ እየጮሁም እንባዎን እያፈሰሱ እንደዚህ ባለ ታላቅ ኃዘን ምጽዋ ወርደው በምንኵሉ ሳለ ከዚህ በኋላ በዓድዋ ገባያና በሌላም ዓዋጅ ተነገረ እንዲህ የሚል ያባ

ያዕቆብን ሃይማኖት የያዘ ከግዛቱ እስከ ፪ት ወር ባይለቅ ቅጣቱ በላዩ እንድትሆን ይወቅ ብለው ሹማምንቱን አስነገሩ መኳንንቶች ይልቁንም ብላታ ኮከቤ ያጋሜ ሹም ምስለኔ ስለሆኑ በዚያ ያሉትን ካቶሊካውያን ገንዘባቸውን ለመውረስ በስርም አስጨነቁ ከርሳቸውም ወደ ሊቴና ወደ ሐላይ ወደ ምጽዋ ሸሹ የሚበዙቱ ሃይማኖታቸውን ካዱ ፩ድ ፩ዱ ግን በያገራቸው ቀሩ። የከዱትም የጐልዓ ባላገሮች ካህናቱ ታቦታቸውን ወደ አቡን ወስደው አስባረኩ ለካህናቱ ፩ድ ፩ድ ዓመት ለጨዋው መንፈቅ መንፈቅ እንዲጾሙ ቀኖና ሰጧቸው። አቡንም የባረኩት የጐልዓ ታቦት የቡኮትና የልቃያ ካህናቶች እንዲሸከሙት አዘዙ ወደ አገር በቀረቡ ጊዜ እኒህ ተሸካሞች በፊታችን የቆሙች የያዕቆብን ምልክት ካልሰበራችሁ አንገባም አሉ ይህችም አባታችን በበዓል ለቡራኬ የተከሏት ዕፀ መስቀል ነበረች ባላገሮች ነቅለው ጣሏት ካመትም በኋላ አቡን ባባ ማስያ የቀሰሱትን እንዲሰጣቸው አስጠሩ። በካቶሊካውያን የተጠመቁ ሕፃናቶችን ዳግመኛ እንዲጠመቁ አዘዙ። አቡን ጠላቴንን ካስለቀቅሁ ደስታን እንዳገኙ መስሏቸው ነበረ። አቡን ስለሁለት ነገር ደብረ ዳሞ

## ዉ ሰኑይ ጥር

ሊቆዩ ፈልጉ ፩ኛው ባ፲፩ኛ ጥቅምት የሚለውን ያባ አረጋዊን በዓል ለመዋል ፪ኛው አባ ሰይፉ አማረ ክንፉ ሽምብር ግብረ ድንግል እኒህ ፫ቱ ካቶሊካውያን ስለሆኑ በዚህ ምክንያት ከደብረ ዳሞ አልወርድም ማለትን ደጃች ውቤ በሰሙ ጊዜ አቡን አልወርድም ካሉ ያዕቆብን አምጥቼ እቤቱ አገባዋለሁ ፫ቱንም አሽከሮቸን አልሰድም ብለው ስለተቆጡ ከደብረ ዳሞ ወርደው ወደ ሐውዜን መጡ አባ ያዕቆብ ከጉልዓ በተሰደዱ ባ፲ ወር ተመልሰው ገብተው ስለተገኙ ሊቀ ካህናት ሃብተ ሥላሴና ብላታ ኮከቤ ርዕሰ ደብር

ወልዱን አባ ቴዎፍሎስ ፈረንሳዊን ልከውባቸው ባዋጅ የወጣ ሰው ባዋጅ ይገባል እንጅ በራሱ ፈቃድ መመለስ የማይገባ ሥራ ነውና አሁንም ወደነበሩበት ይመለሱ ተብለዋል አሏቸው በ፪፻፹፫ ገጽ ባጼ ዳዊት ትእዛዝ ስለሃይማኖት በፊት አቦ በድንጊያ የተደበደቡ ካህናት የቅዱስ ፍራንቺስ ኮስ ልጆች ናቸው አባታችን ባባቴ ገብረ ሚካኤል ላይ የፈለጉትን የቅዱስ ሥራትን ካሳደደ በኋላ ሁላችን በፊትዎ አስቀምጠው ጠየቁኝ እንዲህ ሲሉ ወደ ሸዋ አሁን መሔዴ መልካም ነውን ወይስ አይደለም አሉኝ እኛም ወደ ሸዋ መሄድ በ፫ት ምክንያት መልካም እንዳልሆነ አሉኝ እኛም ሆንም ይልቁንስ ወደ ደጃች ካሣ አ ቴ ቢልኩ መልካም ነው። አልነዎ ይሁን አሉ እንዲህ የምትል መልእክት ጻፉ መልእክት እምኅበ ያዕቆብ ካቶሊካዊ ኀበ ደጃች ካሣ ርዕሰ መኳንንት ሰላማ እግዚአብሔር ወፍቅራ ለእግዝእትነ ማር የሃሉ ምስሌከ ወንድሞቸ የገዥን ፈቃድ ሳታውቅ እንዴት አሁን ወደ አማራ አገር መሄድ ይሆንልሃል ሲሉኝ ከትግሬ ተነሥቼ ወደ ግዛትዎ መጥቻለሁ። ነገር ግን ቅዱስ ጳውሎስ መኳንንትሰ ኢኮኑ ግሩማነ አላ ለዘእኩይ ምግባሩ ያለውን አይቸ በጎንደር ሆኘ ልጄን አባ ተክለሃይማኖትን ወደርስዎ ሰደድሁት እውነተኛዪቱ ነገር በፊትዎ የተገለጠች ትሆን ዘንድ ጌታችንን ክር አማላጅነት ጸጋውን ይስጥዎ አሜን። በ፪፻፺ ገጽ አባታችን አ ያ ጐንደር በግቡ ጊዜ ከ፴ ቀን በኋላ በዕጨጌ ቤት ታላቅ ጉባዔ ሆነ የንጉሥ አዛዦችና ዓይነተኛ ሰው ዕለቱም ተጽዒኖ ነበረና ይምጡ ቢሏቸው በስቅለት ቀን እመጣለሁ እንጅ ዛሬስ አለምጣም አሉ አይሁድን ትመስላላችሁ ሲሉ ነው እንግዴህ እጨጌ አጋፋሪንና የከንቲባ ኃይሉንም ብላታ ፋንታ የሚበሉ ሹማምንትን ወዳባታችን ሰደዱ ከቤታችን እስከ እጨጌ ቤት ድረስ ደቂቅ እንኳ አያስሄድም ቅርብ ነው። አባታችንን ወደዚያው አለማስጠራታቸው ምክንያቱን አላወቅሁም አቡነ ቢያንኬሪን ወደዚያው አለማስጠራታቸው ምክንያቱን አላወቅሁም አቡነ ቢያንኬሪን አቡነ ዮሐንስን ወደዚያው ሲአስጠሯቸው ነበሩ። እንግዴህ በሚመጣው እንዲታይ አዛዦች በልብ አባታችንን ይወዱ ነበርና በማክበር ይመለኛል መልእክተኞች ወደርስዎ በመጡ ጊዜ ተላብሰው ሲገቡ ነበሩ እርስዎም። የከበረውን ስፍራ ለነዚያው ሲመጡ በወራድ ስፍራም ሲቀመጡ ነበሩ እጨጌና ጉባዔው እንዲል ሲል ወደርስዎ ላከን መምጣትዎ ለኛ ከበደነ ራስዎ ማነን ያደርጋሉ ጳጳስን ወይን ንጉሥ እንዴትስ ብለው መጡ መምጣትዎን ሳናውቅ በማን ሥልጣን ይኖራሉ አሉዎ አባታችን እንዲህ ሲሉ

መለሱ። እንደኔ ያለ ምስኪን ደካማ መነኩሴ ወደ ቤቱ ሲገባ መለከቱን እንዲአስነፋ በሁሉ አገር ልማድ የለም። ይህችም ቤቴ እንደሆነች ታውቃላችሁ። እንግዴህ በቀን ወይም በሌት ብገባ ይገባኛል ስለ አመጣጤና መኖሬ ግን በሰጡ ሥልጣን አይደለም እናንተ እንዳላችሁ ጳጳስ ከሆንኩ ወኢይቤ ኢኮንኩ ብብሬ ወዴታለች ወደ

# ፱ ሠሉስ ጥር

መነኰሳት ልጆችዎ በጅዎ አመልክተው ከኒህ በቀር ሌላ ጦር የለኝም ሌላም ኃይል የመንግሥት ምልክት ከኔ ሳይኖር እንዴት ንጉሥ ነህ ትሉኛላችሁ ወንድሞቼ ሆይ እኔስ በትሕትና ለፍቅር የካቶሊክ የሃይማኖት ዓዋጅ ነጋሪ እንድሆን በሮም ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳት የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስለኔ የተላክሁ እንደሆንሁ ለላኳችሁ ንገሩልኝ አሏቸው። ተመልሰው ይህኑ ነገሩ ፩ድ ነገር በ፪ኛው ቀን ጉባዔን አድርገው በቦታችን ሲኖሩብን አንወድምና ይልቀቁልን ብለው ላኩብዎ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅነት የምታመጡብኝን መከራ እቀበላለሁ እንጅ መልቀቅ አይሆንልኝም ከኔ ጋራ ጭፍራ እንደሌለ ትላንትና ነግሬአችኋለሁ ብለው መለሱ። ዳግመኛም አለቃ ወልደ ያሬድ የሚባሉትን ሽፋጭ የደብረ ብርሃን ሌሎችንም ነገር አዋቆችን ከብላታ ፋንታ ጋራ ሰደዱብዎ። እነሆ የከንቲባን ሹም አምጥተዋልና ወደርሳቸው እንድንሚገት እንሂድ አሉዎ አባታችን ግን በሃይማኖቴ የኔ ዳኛ የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ ምስለኔ ነው ብለው መለሱ።

ከንቲባም ይህነን ሰምተው በግዛታችን ተቀምጠው ስሉ እንዴት አልዳኝም አሉ። አሁንም ይዳኙ መጥተው በኔ ፊት ይባባሉ ብለው ላኩ። አባታችን ለመልእክተኛው እንዲህ ብለህ ንገርልኝ የተናገርሁት ቃል ከንቲባን ለማዋረድ አይደለም። ስንኳንስ እርሳቸውን ያህል ታላቅ ሰው ላዋርድ አሽከር እንኳ ላዋርድ አልወድም። ይህነንስ የተናገርሁ የቅዱሳት መጻሕፍትና የአበው ቃልን ትእዛዝ እንዳላፈርስ ነው ዳግመኛም እንደወዳጅ እመክርዎ አለሁና ምክሬን ቢቀበሉኝ መልካም ነው። በበላይም ጌታ ላኩዎ በኔ ላይም የሚሎውን ሰምተው ያደርጋሉና ወደርሳቸው ቢልኩ ይሻላል ብለው ላኩት ስለዚህ ከንቲባ ኃይሉን ወደ ጌታቸው ላኩ እስከ ጕዣምና ትግሬ ድረስ ወደ አሁን ላኩ የሚል አለ ሰሙነ ሐማማት በወጣች ጊዜ አባታችን ሱባዔ አድርገው ብለው ዝምረን ጊዜው ታላቅ ሰልፍ እንደሆነ አውቀው። ልጆች ወንድሞች ሆይ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ የኃይል ወሥጋ ድኩም ያለውን አንርሳ ሌላውንም ይህን የምስለ ምክር ሲይበዙልን ነበር ሊቀ ካህናት እጨጌ ግን ፫ በሰኞ በሌላውም የቅድስት ሕማማት ሳምንት ክፋትን ለማድረግ ጉባዔን አልፈቱም ባለቤታቸው እንዲህ አሉ እርሱ ባይሰማነ እኛ ሄደን ቤቱን እናፍርስበት እነሆ እጨመራለሁ ደግሞ ሰዎቹ ከገበያ ይከልከሉ አሉ። ዋልድቤ እንግዳ ውኃንም እንዳይቀዳ እንከልክል አሉ። ከዚህ በላይ እንዳልሁ አዘዞች ሌሎችም የጐንደር ካህናት ግን አባታችንን የሚወዱ ነበሩና አለቃ ጎሩት የሚባሉ ዓይነተኛ ያዘዞ ከሌሎችም ጋራ ሆነው አባታችን ይህ ነገር በግዜርና በሰው ፊት መልካም አይደለም። እኛስ ለዚህ ነገር ከሴራው ጋራ አንተባበርም። ባይሰሙን ግን ከሎላልትዎ የዋልድባ ሰዎች ጋር ሆነው ያድርጉት አልዋቸው ዳግመኛ የካቶሊክ ወዳጅ የነበሩት አለቃ ተክለ እስጢፋኖስ አባታችን ሆህ ይህነንስ እናድርግ ይልቅስ ከከንቲባ ጋራ ተማክረን ወደ ደጃች ካሣ ብንልክ መልካም ነው አሉ። ይህም ምክር መልካም ስለሆነ ላኩ። ከዚያም ፩ድ ፩ኡ ወደ አባታችን መጥተው በርስዎ ግን ልኬ ምላሽ መጥቶልኛል ሳይሉ የመጣብኝን እቀበላለሁ እንጅ አልክም አሉ። በ፻፻፺፪ በ፫ኛ ምዕ አባ ያዕቆብ ያባ ሰላማን ወደ ጎንደር መነሳታቸውን በሰሙ ጊዜ ከተማሪዎቻቸው ጋራ የኃዘን ድርጅት እንዳደረጉ ያመለክታል። ልጆቼ ሆይ እንግዴህ እኔ ለካቶሊክ ሃይማኖት ውርደት እንዳይሆን ከጎንድር መሸሸ አይሆንልኝምና

# ፲ ረቡዕ ጥር

ከናንተ የሚያናዝዘኝ ፩ድ ቄስ ብቻ ይቅርልኝ የቀራችሁ ግን በበለሳ አድርጋችሁ ወደ ትግሬ ሽሹ አሉ። ነገር ግን ወንድሞቸ እንዴት እኮ እንሄዳለን አይሆንልንም አሉ። እርስዎ ግን በልብዎ ያለችን እንደ እሳት የምትቃጠል ፍቅርዎን ለመግለጥ ከናንተ ፩ዱ ከኔ ጋራ ቢታሠር ወይም ቢገረፍ ለኔ ዕፅፍ መከራዩ ይሆንብኛል አሉ። አባቴ ተክለ ሃይማኖት እንዲህ ከሆነ እሺ እሔዳለሁ አሉ አባ ገብረ ሚካ ግን በቁርጥማትና በሽንትማጥ የተያዝኩ ሰው ነኝ በሌላ ምንገድ በከንቱ ወድቄ ከምቀር ስለ ሃይማኖቴ በዚሁ መሞት ይሻለኛል አልሄድም አሉ። አባ ተክለ ሚካና አባ ተስፋ ጽዮንም እኛስ ከርስዎ አንለይም አሉ። በኋላም እኔን ብቻየን አድርገው እስካሁን ያልነገርኩህ ከኔ ጋራ ትቀራለህ ብየ ነው አሁን ግን ሳስብ ባ፩ድ አያስሩንምና አንተ ብትሸሽ መልካም ነው አሉኝ። እኔ ግን አባታችን ሆይ ስንኳንስ መጥተውልኝ ሳይመጡ ካባ ገብረ ሚካ ጋራ እንዳንለቅ በፊት ምክራችንን ጨርሰናል ያገራችንና ያገርዎ ሰዎች ቢበሉ ሊጠጡ ነው እንጅ መቸ ሃይማኖትን አውቀው እነሆ እስካሁን ይሰድቡናል። ዛሬስ እውነተኛዪቱን ነገር በእግዜር ኃይል ብትገልጥ መልካም ነው መሸሽ አይሆንልኝም አልሁዎ ዝም አሉ ይህም የጌታችን ፈቃድ የሆነ ይመስላል በላይ እንዳልሁ ፈቃድዎን ለመፈጸም አ ተ ሃ ይ አባ ገብረ ሚ ወደ በጌምድር ሊሄዱ ሲነሱ እነሆ ገብረ ሩፋኤል ካባ ቢአንኬሪ ተልኮ መጣ ባጋሜና ባከለ ጉዛይ የነበሩ ካቶሊካውያን

እንደተሰደዱ እንደታሠሩም ወሬን ስላመጣ ቀሩ የመከራቸው ወሬ ግን በሌላው መጻፍ በ፳፫ው ክፍል በግዕዝ ተጽፍዋል። እንግዴህ ደጃች ካሣ አቡንን በመልካም ተቀበሉ ብለው ወደ እጨጌና አድባራቱ ስለ ላኩ ለጸጋ ልጆች ጭንቅ ሆነ። ስለዚህ በእጨጌ ቤት ተሰበሰቡ ፩ዱ ርኩስ መናፍቅ ብለን ያወጣነውን እንዴት በክብር እንቀበለዋለን አሉ። የሚበዙት ግን ባንቀበል ሪማችንን ይነቅሉን የለምን አሉ። እጨጌ አይውጡ እኛ ግን እንቀበል አሉ። ስለዚህ እንዲቀበሏቸው እስከ አንገረብ በወጡ ጊዜ አቡን የመጣውንና የቀረውን እንዲያውቁ በየደብሩ ተለይቶ በፊቴ ይርገጥልኝ አሉ። በደብረ ብርሃናት ያሉት በልባቸው ያቡንን ሃይማኖት በአፍአ ግን እጨጌ ነን የሚሉ ካቶሊካውያንን እንግዴህ ያጠፍዋቸዋል ለማለት ይመስለኛል ተወልደ ለነ ሰላማ መድኅን ቤተ ያዕቆብ ዘይኳንን ብለው ወረቡላቸው። በዓቶች ግን ከደጃች ውቤ ጋር ሲታረቁ ሃይማኖት እንዲህ መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ብለው ነበረና ደጃች ውቤም ከልባቸው ነበረና በእጨጌ ቤትም መልእክትን አንብበው ነበሩና ሰላማ እንዘ ይበውእ ውስተ ጽርሐ ንጉሥ አተበ ገጸ በመንፈስ ቅዱስ አሉ። የከተማ ቅሬዎችም በዙሪያው ከበው ሲዘፍኑላቸው ሳሉ ፩ዲት ሌላይቱን እቴ ኮሶና አብሽ እንዲህ ያወፍራል አለቻት። ያቡን ምግብ ኮሶ ነው ተብሏልና በዚያ ጊዜ ሁሉ መጥቶ እጨጌ ሳይመጡ ስለቀሩ አቡን ቢጠየቁ ታመው ቀሩ ቢልዋቸው ካልመጣ አልገባም አሉ እጨጌ ሰልፈሩ ፮ ራሳቸውን ሆነው ሄደው እጅ ነሱና እኛም ይህን ባየን ጊዜ የጸጋ ልጆች በሃይማኖታቸው አይጸኑም አልነ ግንቦት ፳፬ ቀን በታላቅ ክብር ወደቤታቸው ገቡ። ባ፬ኛ ምዕ በ፩፻፺፬ ገጽ ያቡን መናደድና መዣር ባባታችን ባቡነ ያዕ ላይ ይነገራል። ሊቀ ካህናት እጨጌና የከተማይቱ ከንቲባ የየሩሳሌም ምሳሌ የሆነች ጐንደር ካህናት ባባታችን ላይ ተነስተው ነበር። ነገር ግን ያች ያለም መዳኒት ሕማም በ፪ ሊቅነ ካህናትና የቅንዓታቸው ትጋት እንዳደረገች በዚህም ጊዜ ስለ ሰው ቤዛ

## ዌ ኃሙስ ጥር

በሰውነቱ ባሕርይ ታመመ ብለው የሚአስተምሩን ሐዋርያ የሚአስጨንቁ ፪ኛ ሊቀ ካህናት በመጡ ጊዜ ታላቅ መታወክ ሆነ። ፪ የደጃዝማች ምለኔዎች በዚያ ነበሩ። ያንዱ ስም ፈንጅ እንግዳ ነው። እኒህ አቡንን ሊቀብሉ እስከ ይስሐቅ ደብር በወጡ ጊዜ አቡነ ያዕቆብን ከጐንደር አውጥታችሁ ካልሰደዳችሁልኝ አልገባም ብለው በከተማው ተሰምቶ ነበር። አቡን ከገቡም በኋላ በ፫ ቀን እጨጌንና አድባራቱን ወደቤት ሰብስበው ልጆቼ ሆይ በእኔና በእናንተ

መካከል ያለች ጠብ እንዳባትና ልጅ ጠብ ናት አሁን ግን የሁላችንም ጠላት ያዕቆብ ሮማዊ እንዴት በመካከላችሁ አግብታችሁ አኖራችሁት በለው ጠየቁ። እነዚያም እኛ አላገባነውም መምጣቱን እንኳ አልሰማነውም ኋላም አወቅን ተሰብስበን ልቀቅልን ብንለው ደጃች ካሣ በላያችሁ ሳለ እናንተ በኔ ላይ ልታደርጉ የምትችሉት አይደለም አለነ አሉ። ነገር ግን ይህ ቃል ከልብ የወጣ አልነበረም። በውስጥ በ፪ ምክንያት ተጨንቀው ነበረ። ፩ ያባታችን መምጣት በዚያ ጊዜ ሳይፈሩም ከሰዎችም ጋራ ተደላድለው በጐንደር መቀመጥዎን አይተው ምናልባት ከካሣ ፈቃድ አግኝቶ ይሆናል በማለት ነው። ፪ኛም በፊት እንዳልሁ የእጨጌንና የከንቲባን መልእክተኛ በመጠበቅ ነው። እጨጌና ጉባዔ ይህንን ስላወቁ ደማችን አያፈሱብንም ብለው ለመኑ ከርሳቸው እንኪያስ እኔ እቀራለሁ። ይህን ፈቃድ እስክናገኘው ድረስ ነገር ግን እንዳያመልጥ ይልቁንም አባ ገብረ ሚካኤልና ያድዋ ተክለ ሃይማኖት እንዳይሾልኩ ጭፍሮች ሄደው ይጠብቁ አልዋቸው አለቃ ሃብተ ሥላሴ ምነው እኛ ያደረግነውን ርዕቅን ፈልገን አይደለምን ደጃች ጓንጉልና ብላታ ኮከቤን ከትግሬ እስከ ዳሞት የሰደድን አሁን ምክራችንን ቢሰሙ መልካም ነው። ከዚህ ወደሌላ ቢሄድ ይሻለዋል አሉዎ። አባታችን እንዲህ መለሱ አዎን እናንተ መንግሥታችሁ እንዳትፈርስባችሁ እንዲህ አደረጋችሁ እኔም ሥራዬን የሮም ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት እንዳላፈርስ ሥራዬን አውቃለሁ። የሮም ሊቀ ጳጳሳት ፈቃድ ራሴን ለሞት እሰጣለሁ አሉ። ሊቀ ካህናት

ሃብተ ሥላሴ እኛ አረመኔዎች አይደለንም ማን ይገድልዎታል ጳጳስ እንኳ ይህን ማድረግ ቢፈልጉ እንከለክላቸዋለን ነገር ግን ጉይ እንተ ካልዕታ ያለውና ቢለቁላቸው መልካም ነው። እኔም ሰዎችዎንና ዕቃዎንም እንዳይነኩ አደርጋለሁ አሉ እርሳቸውም ይህን ሁሉ እንደ ወዳጅ መናገራቸው አቡንን ደስ ለማሰኘት ነበረ እንጅ አባታችን ለመጠበቅ አልነበረም። ከዚያ በፊት ወዳጅ መስለው የጠመሙት ብዙ ነው ስለዚህ አባታችን በርሳቸው ላይ እጅግ አዝነው ቆብዎን ከራስዎ አውልቀው ሽበቴን ይዩ አሽከር አይደለሁም አርጅቻለሁ የርስዎን ምክር አልፈልግም አልዋቸው አባ ወልደ ማርያም ካለቃ ኃ ሥ ወደ ሮም ሄደው የነበሩቱ ጌታቸውን ሲሸሹ በዚህ ጊዜ መጥተው ነበሩና አባታችን እርሳቸውን እኔና እናንተ በእግዜር ፊት እንገናኘለን አሏቸው መልእክተኞች ወደ አቡን ተመለሱና አይሆንም አሉ ሏቸው። አቡን ተቆጡ ባሰትም እንግዲያስ የወደድከውን አድርግበት ብሎ እንሆ ልኮብኛልና ከቶ በቤቱ አላሳድርረውም አሉ እንመክረዋለን ለዚያ ሌሊት ይታገሡልን በለው ለመኑ ገዳማቸው እንዳይሻርባቸው ብለው ነው። አቡንም አለማድረጋቸው የገጁን ፈቃድ ባያውቁ ነው። ከንቲባ ኃይሉንና ፈንጃ እንግዳን በዚያች ቀን እንዲሰቃዩላቸው ለመኑ። እነዚህ ግን ካልታዘዝን አናደርገውም አሉ። ከዚህም በኋላ አቡን ወደ እጨጌ በጣም እንድታስጠብቁ ብለው ላኩ በሄዱላቸው ይጠሉ

## ው ዓርብ ጥር

ይመስላል። ምን ጠብቁ ያሰኛል ብለው ሁለት ጠባቆች ሰዎች ሰደዱ። ፩ዱም ከዚህ በፊት የጠራሁት አጋፋሪ ማረየ ነበረ። አባታችንም እነሆ ባልጋዬ ተኙ እኔ በምድር አለኋቸው ማሪዬ እንዲህ ያለን ትሕትና አይቶ አባታችንን ለብቻዎ አግልሎ ማምለጥ የፈለጉ እንደሆነ እኔ። በሌት አውጥቸ እሰድዎታለሁ እርስዎ ግን ለመሞት እንጅ ለመሸሽ አለመጣሁም አሉዎ። እንዲህ ማለቱ ለመፈተን ነው ያሉ አሉ ፪ቱም ምንም እንዳይወጣና እንዳይገባ በደጁ አልጋውን አደረጉ ዳግመኛም እጨጌ በክልላቸው ያለውን ክርስቲያና እስላም የለኔ ሁሉ እኛን ለመጠበቅ እንዲመጣ አዘዙ። ከነዚኸውም በሌሊት መጥተው በውስጥ ያሉትን ከናንተ ጋራ ሁነን እንድንጠብቅ ታዘናልና ክፈቱልን አሉዋቸው። ነገር ግን እኛ እንዳንከፍትላቸው ከለከልናቸውና በውጭ ቀሩ። ዳግመኛም አቡን ፈረንጅ እንግዳንና ሌላውን ሹም እጨጌ ቤትን ሁሉ ከበው በዚያች ሌሊት እንዲጠብቁላቸው አዘዙ። ስለዚህ ደብተራ ኃይሉ ከኛ ጋራ ነበሩና በማይጠረጠረው ወገን በወጡ ጊዜ ፩ድ ወታደር ጐራዴውን መዞ ሮጠባቸው ነገር ግን በእግዚእትነ ማርያም አማላጅነት በነጋታው ብርን

እንዲሰጡት በርሳቸው የነበረውን ምንጻፍ አስጥሎ ሰደዳቸው። በልንጀሮቹም ምንድር አሮጠህ ቢሉት ጅብን አይቸ አላቸው። በነጋው ወደ ቤታችን መጥቶ ፩ድ ብርን ወሰደ። እርሳቸው ግን ተይዘው ቢሆን ለርሳቸውና ለኛ እጅግ መከራ ባመጡን ነበረ። ይህ ሰው የበጐነቱ ምክንያት እንዲህ ነው ቀድሞ አባታችን ባድዋ ሳሉ እጨጌ ማኅፀንቱ የፊተኛው ልከውት መልካም አድርገውለት ነበርና ነው ባለቤቱ እንዳለኝ። ይህች ሌሊት ካለፈች በኋላ እጨጌና ካህነቱ ባቡን ቤት ተሰበሰቡ ሊቀ ካህናት ሃብተ ሥ በመካከላቸው ቁመው እንዳሉና ትላንት ላባ ያዕቆብ አሰማኒ እርሳቸው ግን ለሞት ቆርጠው አላቅም አሉነ አሏቸው አቡን ይህን ሰምተው እርሱን ማን ይገድላል እንደርሱ ያለን ሰው መግደል ባገራችን ነውር ነውና ግን ቤቱን ሽጦ ገንዘቡን ይዞ ይልቀቅልኝ ወይም ለቤቱ ጠባቂ ያድርግ። የርሱን ሃይማኖት የተቀብሉትን ግን ከርሱ ጋራ አልሰድም አሉ። በዚያ የተሰበሰቡቱ ጉባዔ ይህን ቃል በሰሙ ጊዜ የደጃች ካሣ ሎሌ እንዳልመጣላቸው አውቀው እርሳቸውስ አይለቁም በቤቴ እንድቀመጥ ገጁ መብት ሰጥቶኛል ብለው አሏቸው። ዳግመኛም ሊቀ ካህን ሃብተ ሥላሴና አለቃ ተከለ እስጢፋኖስ ሌሎችም ያዘዙ ታላላቆች ካቡን ተልከው ወዳባታችን ይህን ሲአሰሙ መጡ መዝመሪያ እንዲህ አሉ ትላንት የቁጣ ቀን ነበረ ዛሬ ግን የምሕረት ቀን ናት (ብለው የመጣችልዎ የጳጳሱን ይስሙን ብለው ሲዝምሩ ያባታችን

ሰውነት ይህነን በመስማት ብቻ ታወከች መታገሥን አልቻሉምና። ወንድሞቼ ሆይ ከሮም ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳት በቀር ጳጳሳችሁ ሰውነቴን እንዳላስገዛ ከቶ እስከ ዛሬ ድረስ አታውቁምን አሉ። እኒያ ጨመሩ እንጂ ቃላቸውን አልተውም ወዳጆችዎ ነኝ ምክራችንን ይስሙን የፊተኛይቱን የገጁን ቃል ለማጥናት የሚመጣውንም ነው ምምግት ተያይዘው ቢሄድ መልካም ነው። አባታችንም በማዘን አለቃ ሃብተ ሥላሴን የወዳጅ ምክር እንዲህ ናት ከጠላቶቻችሁ ጋራ እስከ ጐዣም ዳር ድረስ ሂድ ማለት የጠላትነት ነው እንጅ የወዳጅነት አይደለም። ዳግመኛ ባገር ሁሉ ልማድ ከሳሽ ወደ ዳኛ ሄዶ ይመጣል እንጅ ተከሳሽ አይሄድም ከተጠራ ይከተላል። እኔ ገጁ ተገመጥ እንዳሉኝ አልጠራጥርም የሚጠራጠር ሄዶ ይጨህ አሉ። ከዚህ በኋላ መልእክተኞች ወደ አቡን

# ፃ ቀዳም ጥር

ተመልሰው ያባታችንን ቃል ነገሩ ከዚህ በኋላ አቡን ወደ ደጃች ካሣ መልእክተኞችን እስከ ጐጃም ሰደዱ። የዚያም ምላሽ እሲመጣ እጨጌና ከንቲባ ፫ት ጠብቆች አኖብነ። አባታችን የቅርጣግና ቆጵርያኖስ ሰማዕት አንገቱን ለሚቆርጡ ገንዘብን ሰጠ። አሁንም ልጆቼ ሆይ ለሞት ለሚጠብቁን ለኒህ መልካም ነገር አድርጉላቸው እኒያም ያባታችነን ቸርነት አይተው ወደኛ የሚመጡትን ወዳጆች አልከለከሉም አባታችን በብርቱ ኃዘንና ጸሎት ሌትና ቀን ሲደክሙ ከቆዩ በኋላ ደግሞ በዚህ ላይ ከባድ ኃዘን ባባታችን ላይ ተጨመረ በትግሬ ባሉት ልጆችም ምዕመናን በሆኑ ላይ መታሰርና ስደት ነበር። ይልቁንም ከዚህ የባሰ እርስዎን ያሳዘነ ሌላ ነገር ተገኜ የሐላይ ካህናት ከመንግሥቱ እኩሌታ አገር የሚሆን መከዳታቸውን በመስማት አቡነ ቢያንኬሪይ ከመነኰሳት ጋራ ትተውነ ወደ ምጽዋቸው ከሸሹ እኛ ይልቅ በለሚስቶች ባለልጆች እንዴት መከራን መቀበል ይቻለናል ብለው ከዱ። ዳግመኛም አቡነ ቢያንኬሪ ወደ ምንኩሉ ከወረዱ በኋላ እንግዴህ ተስፋ የለኝም ብለው መነኰሳትን ወደዚያም የሚመጡትን ባላገሮች ጠባያቸውን አልታገሡም በመሃላቸው ታላቅ ጠብ ሆነ እንግዲህ አባታችን ከሁሉ የባሰ ጭንቅ ኃዘን የቤትዎ መናወጽ ነበረ የተጣባትም ነገር እንዲህ ናት አቡነ ቢያንኬሪ ላ፩ድ ፩ዱ ቤት ላለ መነኩሴ ላመት ለልብሱ ለቀሚሱ ለሱሪው ፪ብር ይበቃዋል ብለው ወስኑ ይህም አባታችን ወደ አማራ አገር ከሐላይ በተነሱ ጥቂት ጊዜ መነኰሳትን ሰብስበው እነሆ በየራሳችሁ ፪ ፪ ብር እሰጣለሁ እንግዲህ እንደወደዳችሁ አድርጉበት አሉ መነኰሳት ግን ቢገኝ ይሰጡናል ይመግቡናል ባይገኝ የቤት ልጆች በግድ ደመወዘኛ ያምጡ አንልዎም ብለው አልተቀበሉም ኋላም ይህን የሚአደርጉበት ቦታ ስላገኙ ስደት በሆነ ጊዜ ይህነኑ ነገር መለሱ ፩ድ ፩ዱ በመፍራት ተቀበሉ ሌሎች ግን አልተቀበሉ እንግዴህ በዚህም በሌላውም ምክንያት አቡነ ቢያንኬሪና መነኮት

ከቶ አልተፋቀሩም እንግዴህ አቡነ ያዕ ገንዘብ እየሰጡ የተሰበከውን ነገር መጠበቅ እኒህ በሥራት ያልሆኑትም መነኮሳቶቹን መጠበቅ አልችልም እርሱንም ወደዚያ ይገድሉታል ወይም ወደ ስናር ይሰዱታል። እኛም ወደ አገራችን እንሄዳለን አሉ። ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ዘመን የብላታ ኮከቤን ልብ ወደ መልካም ስለ ገለበጠ መነኮሳትና ምዕመናንም ሁሉ በየሥፍራቸው እንዲኖሩ ቻሉ። ይህም ባባቴ እምነቱ ምክንያት ሆኖ በሀላይ ቢኖር የርሱን ነገር እየሰሙ መነኮት እኔን አይሰሙኝም ብለው አቡነ ቢያንኬሪ እርሳቸውን ወደ ቦጎስ ሰደዋቸው ነበር ኋላ ግን በካቶሊካውያን ላይ ስደት እንደሆነ ቢሰሙ ከቦጎስ ወደ ምንኩሉ መጥተው ካቡነ ቢያንኬሪ ፈቃድን ለምነው ወደ ብላታ ኮከቤ ወጡ ወደ አባ መጣዕ አርፈው አገኙአቸው አነጋገርን ማውቅ ብልሃት ተሰጥቷቸው ነበሩና ይልቁንም ካቶሊክ ሃይማኖት እንዳትጠፋ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሹሙ ዘንድ ሞገስን አገኙ ከዚያም ቃላጤ ተቀብለው ዌ ሐላይ መጡ ያም ካቶሊካውያን እንደ በፊት ይኑሩ ብሎ ተፈጽሞ ለሹሙ ነገረ። ስለዚህ ሸሽተው በዱ የነበሩ በምኩሉም የነበሩ ወደ ሐላይና ወደአገራቸው ተመለሱ ላሉቱ በመከራና በእሥራት እንዳሉ ሰምተው በዚያ ስለተገኙ ለብላታ ኮከቤ ተናግረው በጎድዓት እንዲኖሩ አደረጉ። ዳግመኛም ብላታ ኮከቤ ሌሎችንም እንደ በፊት

## *ዐ እኀድ ጥር*

ይኑሩ ብያለሁ አቡነ ቢያንኬሪ ግን የርስዎን ፈቃድ እስኪጠይቅ ድረስ በምጽዋ ይቆይ ብያለሁና እንዴት ይሁን ይላሉ በለው ጌታቸውን ጠየቁ ደጃች ውቤም ከዚህ ቀደም እንዲሰደድ አልተናገርሁም አሁንም እንዲመለስ አልከለክልም አሉ። አባቴ እምነቱም ይህነን ከብላታ ኮከቤ ሰምተው እጅግ ደስ አላቸው። ዳግመኛም እጃች ውቤ ሲናገሩ ባሻ ኡለው ነበሩና በቋንቋቸው ይጻፉልኝ ብለው አባቴ እምነቱ ለምነዋቸው ጽፈው ሰጧቸው። ይህነንም አድርገው በታላቅ ደስታ ወደ ሐላይ ተመልሰው ይመለሱ የሚለውን ላቡነ ቢያንኬሪ ላኩና እርስዎ አላመኑም ወይም አልወደዱም ወደ ሐላይ አልወጣም አሉ። ዳግመኛም ከርሳቸው ሳይማከሩ ክረምት ሳይገባ ብለው አባቴ እምነቱ አባታችነን ደስ ለማሰኘት መልእክትን ወደ ጐንደር በመስደዳቸው የምስክርም ወረቀት ከባሻ ብላውዴ በማጻፋቸው አዝነውባቸው ወደ ቦጎስ መልሰው ሰደዱላቸው የቀረው ግን በካቶሊካውያን ታሪክ በግዕዝ ተጽፍዋል። በ፫፻፬ኛ ገጽ ባ፳ ምዕ አባታችን ከነልጆችዎ መነኰሳት ጋራ መያዝዎንና መታሠርዎን ይናገራል። ይህም የሆነ ወደ ጐንደር ከገቡ በኋላ ባ፳ኛው ወር በሐምሌ በ፱ነኛው ቀን በ፲፰፻፵፯ ዓ.ም ነው። ደጃች ካሣ ቴዎድሮስ ደጃች ብሩን አሥረው ከጐጃም ወደ አምባ ጮራ መጡ። አቡንም ወደርሳቸው የርሳቸው ደጃች ጎሹ ብሩን ፍታልኝ ከደጃች ውቤም ታረቅልኝ እንዳይሉ ሃይማኖትን ብቻ እንዲናገሩ መከሯቸው። ስለዚህ ደጃች ካሣ አቡንን አባቴ አትግዛ ቢሉኝ እንጣላለን ሌላውን ነገር ግን የፈለጉትን ሁሉ አደርግልዎታለሁ ብለው አስቀድመው ነገሩዋቸው እርሳቸውም እንኪያስ ጠላቴን ያዕቆብን ስደድልኝ አሉ። እርሳቸውም እሽ እሰድለዎታለሁ አሉ። በዚህ ጊዜም ባባቴ ሃይማኖት ያልገባ ከፍ ብዬ አንገቱን ዘቅ ብዬ ባቱን እቆርጠዋለሁ ብለው ዓዋጅ አስነገሩ። የሃይማኖቱም ቃሉ እንዲህ የሚል ነው። በሰውነቱ አምላክ በሰውነቱ እንደ አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ ያውቃል ማለት ነው። ፫ቱም ወገን ቅብዓት የጸጋ ልጅ ወልደ ቅብዕ በዚህች ባዲስ ሃይማኖት በግድ በመፍራት ተገዙ። ፩ድ ፩ድም በሩቅ ያሉት አድባራት እንዳይቀሩ በደጃዝማች በየሹመቱ ያለውን ካህን እያስጨነቀ እንዲአመጣ መኳንንቶቻቸው ሁሉ አዘዙ። ወልድ ቅብዕ የሚሉትንም ማስገዘታቸው ግን የፈቃድ ይመስለኛል እንጂ እንደ ፪ቱ ወገን የከፉ አይመስለኝም በዚህ ጊዜ ዮሐንስ ቤል ሌላም ያገራችን ሰው ከገጁ ተልከው ወዳባታችን መጡ። ከራስ አሊ ጋራ ከቡላውድምን ጋራ ካገራቸው እንግሊዝ ከፓርስንስ ጊዮርጊስ ጋራ ቀድሞ ወዳገራችን የመጡ ናቸው። እኒህም ሰዎች አሁኑን አጋጅ አድርገው የፈለጉትን ጉዳይ ካገራችን ገዦች እንዲያገናኙ ለርሳቸው ባመት ፫፻ ብር ከእንግሊዝ መንግሥት ሊሠጧቸው ነበሩ። ዳግመኛም ያገራችን ነገሥታት ስለሃይማኖት ነገር አይነሱም ስለዚህ በዚህ ያሉትን የካቶሊካውያን ሰባኮች ብታባርሩዋቸው የሚመጣባችሁ ነገር የለም አሏቸው። እንግዲህ ዮሐንስ ቤል ኋላም ሊቀ መኳስ የተባሉበት ወደ አባታችን መምጣት ስለምስክርነት ይመስለኛል እንጂ

መልእክትተኛነት ብቻ አይደለም የመጡበትም በሐምሌ ፫ኛ ቀን ወደ ማታ ነበረ ቤል አስቀድመው ወደ አባታችን መጥተው ነገሩን ነገሩአቸው አባታችንም እኛን ሰብስበው ነገሩን። መሰደድ ይሻለናል ወይስ አይሆንም ማለት ምከሩ አሉን እኛም መሞት ይሻለናል እንጂ ባ፩ድ ፩ዱ ፩ዱ በጐርፍ በወምበደ ወደ ከተማ ስንሔድ ከመሞት እዚህ በሃይማኖታችን ብንሞት እጅግ

## ዑ ሰኑይ ጥር

ይበልጥብናል። ዳግመኛም ቢያስር እርስዎን ነው እንጂ እኛን እንዳይሰናዱ በፊት ተናግረዋል። አልነ ደብተራ አሰጋሽኝና ደብተራ ኃይሉ ግን መሸሽ ይሻላል አሉ ስለዚህ አባታችን እንግዲህ እናንተ ሽሹ ራሳችሁን አውጡ አልዋቸው። ዮሐንስ ቤል የመከራዎ መላከተኛ ሲሆኑ አልጋዎን ሥፍራውን ሰጧቸው

በክብርም ሁሉ እንደወንድም አከበሯቸው። የደጃች ካሣ ትዕዛዝ ነበርና የአድባራት ሊቃውንት አዛዦችም እጨጌና ከንቲባም የአቡንም ሹም ሁሉ በ፩ድነት ባ፬ኛ ቀን እንደተሰበሰቡ ወደ አባታችን መጡ። ቤል እኒህን ሁሉ ሹሞችን አድርገው በማህላቸው እርሳቸውና ሌላውን መልዕከተኛ ሆነው እንዲህ አሉ። የደጃች ካሣ ጌታችን አገሬን ልቀቁልኝ በመተማ አድርገው ወደ ስናር ይሒዱ ከዚያም ወደ አገርዎ ይሂዱ ቤትዎን ይሽጡልኝ ዋጋውንም ከመተማ ገዥ ከእብራሂብ ይቀበላሉ አሉዎ ብለው ተፈጥመው ተናገሩ። አባታችንም እንዲህ መለሱ ልኖርበት አስገዝቼ አሠራሁት እንጅ የሮም ሰው ድንጊያና ጭቃ ልሸጥ አለምጣሁም ሂድ ስለአሉኝ ነገርዎ። እኔ ከገዢየ ጋር ልከራከር አልችልም ነገር ግን በዚህ ጊዜ ወደ መተማ የሚሄድ በጎርፍና ባንዳንድ በወንበዴም እንድሞት ነው ጌቶች ሆይ እናንተ ከዚህ ያላችሁም ታውቃላችሁ አሉ እነዚህም እውነት ነው ይህ ሁሉ እንዲያገኝዎ ነገር ግን እኛኮ ምን ኃይል አለን ይህንኑ ቃልዎን አጽፈው ወደ ደጃች ካሣ ይሰደዱ እንጅ አሉዎ ማን ይወስድልኛል በዚህ ጊዜ በገዢው ፊት የሚቆም። እኔ ወሰነተኛው እንዴት አገኛለሁ አሉ በዚህ ጊዜ ኢጋፋሪ ገብረ ሥላሴ ቆሞ ቀድሞ ጌታዬ ከኢጋሜ አባረሩት አሁን ደግሞ በሥውር መጣ እንደ ልማዱ ደግሞ ተሸሽጎ እንዳይመለስ አቡን ፍቅር ያላችሁ እንደሆነ ጠብቁት እሡሩት ያለዚይማ የሚጠብቁትን ሰዎች እናግባ አለ አላዋቂ ነህን ታኖራቸው ዘንድ የምትወድ ጌቶችህ በቀን ወይም በሌሊት ሊለቋቸው ይወዳሉ አሉት አባታችን መናገር ሲጀምር ተነስተው አንተ የደጃች ሎሌ እይደለህምና ከቤቴ እንዳትናገር ጫንቃዎን ብለው አረዱበት በዚያ ቀን ያነጋገርዎን ማማር መጨነቅዎንም የሰውነትዎንም የፊትዎንም መልክ አይተው ጉባዔ ፩ድ ፩ዱ ቀስ ብለው እርስ በርሳቸው በአሰት ኃጢያት ባይበዛ እኒህ ሰው ያገራችን ጳጳስ መሆን በተገባቸው ነበር አሉ ሁሉ ለርስዎ እንዳዘኑ ገብረ ሥላሴ አውቆ በእኒያና ባባታችን ላይ እየተሳደቡ ወጣ

እነዚያም ከሔዱ በኋላ ዮሐንስ ቤል መልእክት ቢጽፉ እኔ አደርስልዎታለሁ አልዎ ስለዚህ መልእክት ጽፉ ቃል አባ ያዕቆብ ካቶሊካዊ ትብጻሕ ኀበ ደጃዝማች ካሣ ርዕሠ መኳንንት በስመ እግዚአብሔር ወፍቅራ ለዕግ ማርያም የሃሉ ምስሌከ እግዚኦ ሰማዕኩ ድምፀከ ወፈራኅኩ ርኢኩ ግብከ ወአንከርኩ እንባቆም ነቢይ እንዳለ ወደ ስናር ተሰደድ ብለውሃል የሚል ቃልዎን ከጌታ ዮሐንስ ሰምቼ አደነቅሁ እኔስ ፲፬ ዓመት ትግሬ ከተቀመጥኩ በኋላ ለሰው ፊት የማያደሉ መሆንዎን ሰምቼ ወደ ግዛትዎ መጣሁ አሁንም በነገሬ ላይ በውነት ይፍረዱልኝ እንጂ ቃሌ አያሳንስዎ የሕሌና ቅንነትም ትተው መከራን በበላዩ ያመጡብኝ በግዕዝ ማር አጋዕዝት ኃይል እቀበላለሁ ከዚህ ቀደም ወንድሞቼ ስለሃማይኖት በዚች ከተማ እንደሞቱ እኔም እንደርሳቸው መሆንን አልጠላም ሐምሌ ፬ ቀን ፲፰፻፵፮ ዓ.ም በጐንደር ተጽፈች በዮሐንስ ቤል እጅ ተሰጠች ጌታ ዮሐንስ ወደ

## ዒ ሠሉስ ጥር

ሰፈር ከተመለሱ በኋላ መልከተኛ ወዳባታችን ስደዱ ቀለምና ወረቀትን ይስደዱልኝ ብለው ስለላኩ ሰደዱላቸው እንዲህም የምትልን መልእክት ላባታችን ጻፉልዎ ክረምት እስኪአልፍ ድረስ በቤታቸው በሌላ ዲከርሙ እንጅ በቤቱስ አይሆንም አሉኝ ገዡ ግን ጳጳሱ ያውቃሉ በማለት ነገራቸውን ጨርሰዋል ምግብና ልብስ ቸግሮኛልና ፲፫ ብር ያበድሩኝ ብለው ላኩ። አባታችን ወዲያው ምላሽን ጽፈው ሰደዱላቸው። እንዴት እንደርስዎ ያለ ጥበበኛ የእንግሊዝ ሰው እንደዚህ ይናገራል። ለአገረ ገዥ እምቢ ካሉ መቸ እኔ የዲዮስቆሮስን ልጅ ይለምኑልኝ አልኩዎ። አሁንም ሰሜን እንኳ በዚያው ፊት እንዳያነሱብኝ እለምንዎታለሁ። ፲፭ት ብር ሰድጄልዎታለሁ የሚል ነው። ያቡነ ያዕቆብን ነገር ሳልጨርስ ወደ ጐንደር አልመለስም ብለው ነበሩና ደጃች ካሣ አባቴ በነፍስ እያዝልሃለሁ ቢሉኝ አንገት አንገቱን እቆርጠዋለሁ አሏቸው። አቡን ግን ከእግዜር ኃይል በግድ ታዘው በዛሬ ዘመን የወንጌልን ሥራት የጠበቀ እንደ ያዕቆብ ያለ አይገኝምና ሞትስ አይገባውም። እርሱን መስደድ በሱ ሃይማኖት የገቡትን አበሾች እንድትሰጠኝ አሏቸው ደጃዝማችም ይሁንልዎ አሏቸው። ነገር ግን ለርሱ በናዝን ወደ ሌላ እንዳይሔድ የሚጠብቁት እንፈራለንና አሁን መተማ መስደድ አይሆንም አልዋቸው። አብቡን አባታችንን ጻድቅ ሰው ነው ማለታቸው ሥጋዊ ፍራት ነው። ዳግመኛም እርስዎን ሌላም የኤሮፓ ሰው ከርስዎ ጋራ ቢኖር አስለቅቀው ይሰደዱ እንጂ ምንም አይንኩ አበሾችን ግን እንደ ወደዱ ያድርጉባቸው። ብለው ባሻ ቡላውንዴን ልከውላቸው ነበር ይላሉ። ባሻ ማለት በውነት አልነበረም። ኮንሱል ማለት ግን እውነት ይመስለኛል ደጃች ካሣ ግን ጌታችን የፊተኛው ጲላጶስን እስመ ተውህበ ለከ እንዳለው ጳጳሳቸው ያዕቆብ ጻድቅ ሰው ሲሉዋቸ ክፋትን ለማድረግ ጠኑ እንጅ እውነትን አልፈለጉም። ካቶሊካውያንም ካባታቸው ጋራ ይህችን ቅድስት መከራን ሊቀበሉ ከብዙ ጊዜ ወደው ነበርና ልቅቀርባቸው አልወደዱም። ስለዚህ የበዓል ልብሳቸውን ከተሸሸገበት አስመጥተው በርሱ ወደ ሰርግ እንደሚሄዱ ሰዎች መሰሉ። በ፫፻ኛው ገጽ በ፮፻ ቍ እንደ ተጻፈ የሰማዕታትን ገድል አባታችን ሲነግሩን ጃፓን በሚባል አገር እግዜር ጸጋውን ስላፈሰሰባቸው የነዚያ ክርስቲያኖች በዕልልታና በሰላም ወደ ሰማዕትነቱ ተቀዳደሙ አሽከር እንኳ ቢያልቅ እንግዲህ ሰማዕት አትሆንም ቢሉት ማልቀሱን ይተው ነበር።”

(በጃፓን የተደረገው ታሪክ ከላይ ተጽፎ ይገኛል።) “ከዚህ በኋላ ሐምሌ ፱ ቀን በ፪ኛው ሰዓት ቤታችን ተከበበች ባይበዙ ፴ ይሆናሉ። የፈረንጅ ነገር ብልሃቱ ብዙ ነው። ተብሎ ነፍጥ ለጉሞ ቋድም ተቃጥሎ ነበር። የተላኩት ያይነተኞች ስም አሸብር ወልደ ተክሌ የሰቀልት አሳላፊ ኪዳኑ ደጃች ካሣ የጳጳሱ አጋፋሪ ገብረ ሥላሴ የከንቲባውም አጋፋሪ ትርፌ ይህም ትርፌ አባታችንን በትህትና መናገር ቢዠምር አሸብር ወልደ ተክሌ ስለምን ትፈሩታላችሁ ይህንስ ማክበራችሁ ስለምን ብሎ አንተ ከቤትህ ልናወጣህ መጥተናል። ጌታችን አዘውናል እያለ እየሰደበ አባታችንም እነሆ አለሁ ያዘዝዋችሁን አድርጉ አሉ። ያገርዎ ሰው ከርስዎ ጋር ያለን አትሥሩ ብለውናል ብለው ጠየቁ። አባታችን አልመለሱም። ፩ድ ቀይ ወንድማችን በዚያ ነበርና

# ዓ ረቡዕ ጥር

እነዚይ እርሱ ፈረንጅ መስሏቸው ጠየቁ። እርሱም ይህንን አውቆ የለም አለ። በዚያን ጊዜ አሸብር ወልደ ተክሌ በጥፊ መታው በደርቡ በታች የነበሩትንም ይልቁንም ያቡን ሰዎች እንደ ነብር ከፍየል እንደ ተኩላ በበግ ላይ በወንድሞቻችን ላይ ሆኑ። አባታችን እኔን ምታ ልጆቼን ግን አክሎሎቼ ናቸውና አትንካ ብለው ቃል ተናገሩ። እርሱ ግን ቀርዩ ከርስዎ ነጥሎ ስቦ ወደታች ወሰደው አወረደውና የገንዘባችሁን ቁጥር ስጠኝ አለው። ወንድማችን ግን ሁሉን በጃችሁ ይዛችኋል ም ቁጥር ያስፈልጋል ቢለው ዳግመኛ መታው የተመታውም ጌታዬ ይህን ጥፊ ስላንተ እንድቀበል ያደረግኸኝ አመሰግንሻለሁ እያለ በታላቅ ድምጽ ጮሆ ቤቱንም በረበሩ። ከዚህ በኋላ አባታችንን ቤትዎን የሚጠብቅ ከከንቲባ ሰው ፩ዱን ይጥሩ ስሉዎ እስዎም በጥበብዎ እንግዳ ወርቅን መረጡ። ከዚህ በኋላም በበቅሎ እንዲቀመጡ ያስጭኑ አሉዎ እርስዎ ግን አልፈልግም ብለው በግርዎ ሄዱ። በወጣን ጊዜ መከራን ሲአስቀብሉን በቅርብ ያሉ ባላገሮች

ሲያዩ ነበሩ። በየልብሳችንም ይዘው በየገበያው ወዳለች ወደ አጋፋሪ ትርፌ ቤት ወሰዱን። አባታችንንና አባቴ ገብረ ሚካኤልን እኔን ወደ ደርቡ አወጡነ አባታችን ልጆቼን ወደዚህ እንዲወጡ አድርጉልኝ ብለው ለመኑ እርሱ ግን አይሆንም በታች ይኑሩ አለዎ። ከዚህም ወደ በዓታ ከንቲባ ቤት ወዳለው ዶርብ አወጠነ። በዚህ ጊዜ ፩ ደጃዝማች መልክተኞች እንግዴህ የጌታችንን ቃል ይስሙ እርስዎ እስከ ኅዳር ሚካኤል በከንቲባ እጅ ይኑሩ ኋላም በስናር አድርገው ወዳገርዎ ይሄዳሉ። ሰዎች ግን ለአቡን አሳልፏቸው ብለውናል አሉ። በዚህ ጊዜ ባባታችን የገባ ኃዘን ይህነን ይመስላል ብየ ልጽፍ አይቻለኝም ፩ዱ ኃዘንዎ ስለ ሃይማኖት መሞትን ከቀድሞ ዠምረው ይወዱ ነበሩና ይህን ስላጡ ነው። ፪ኛው እንዴት ከሞት በፊት ከልጆቼ ተለየሁ በማለት ነው ስለዚህም መልእክተኞች ከጌታችሁ ዘንድ እኔ ኃጢአተኛ ከሆንኩ ለምን እኔን ትታችሁ ልጆቼን ትወስዳላችሁ በደላቸው የእግዜርን ቃል ከኔ ስለ ስሙ አይደለም) የእግዜር ቃል ያሉት ከአርዮስ ባንስጥሮስ ከንስጥሮስ በልዮን ጥበብ እየተሸፋፈነ የመጣውን ኑፋቄ ነው።

(ወንድሞች ሆይ እኔን መሣቀይ እነዚህን መተው በተገባ ነበረ አለዚያ እኔን ከነዚህ ከልጆቼ አትለዩኝ አሉ። አሸብር ወልደ ተክሌ እኛ ያዘዙንን እናደርጋለን እንጅ ይህስ አይቻለንም አሉ። በዚህም ጊዜ ከንቲባ መልካም አደረጉ ከርሳቸው ጋራ የሚኖር ከሰዎችዎ ፩ድ ስጡኝ አሉ አሸብር ማነን ይፈልጋሉ እንድተውልዎ ብለው ጠየቁ። አባታችንም እኔን ተውልኝ ቢሉ ያባ ገብረ ሚካኤልና የሳቸው ስም በአቡን ዘንድ ተጠርቷልና አይሆንም አሉዎ ሌሎችም ቢጠየቁ ሲፎካከሩ አሸብር ተቆጡና እርስዎ ከዚህ ይቀመጡ። እናንተ ተነሱ ወደነዚያ ሂዱ ባሉን ጊዜ እኔ ወዳባታችን እግር ወድቄ እንግዴህ ይባርኩኝ አባታችን ባልሁ ጊዜ መታገሥ ተነሳዎ የወንድማችንን አንገት ይዘው ጮሁ አለቀስሁ። የግብጽ ንጉሥ ሎላልት ግን ይልቁንም አሸብር በርስዎ እንግዲህ አልፈራም ከንቲባ ግን አለቀሱ አሁን የዚህ ፍዳ በማን ላይ ይሆን አሉ። ከዚህ በፊት በአቡነ ቢያንኬሪ ጊዜ ከንቲባ ተነሥተውብኝ ነበርና እኔም በሃይማኖታችን እንሞትባታለን ብያችሁ ነበርሁና የፈራነ እንዳይመስል ብዬ እንባዬን ከለከልሁ በሌላ ጊዜ ግን ይህን እያሰብሁ እጅግ አስለቀሰኝ አባ ገብረ ሚካኤል በዚያ ቁመው ነበሩና

# ዓ ኃሙስ ጥር

አባታችን የርሳቸውንም አንገት ይዘው አለቀሱ። አሸብር እርስዎን በክንድዎ ስበው አስቀሩዎ እኛን ወደ ወንድሞቻችን ወሰዱን ባ፩ ቤት ባደረገነ ጊዜ በርስዎ አማላጅነት ጸጋውን እንዲሰጠን የእመቤታችን ሊጣንያ አደረሰን። ሽህ አሊ የሚባል ፋቅራ ታላቅ መስጊድን በፊት አቦ በታች አሥርቶ ነበረና በደጃዝማች ካሣ ትእዛዝ በዚህ ቀን ወደ ፱ ሰዓት ከከንቲባ ቤት ወደ አቡን አሻገሩነ። አባ ገብረ ሚካኤል በጅ ሰንሰለት አስረው ገብረ ማርያም ኃይለኛን ሰው ቁራኛን አደረጉ። ደብተራ አሰጋኸኝንም በሰንሰለት አስረው ለጭፍራ ሳለፉአቸው። አባቴ ተክለ ሃይማኖትና አባቴ ተስፉ ጽዮንን በግር ብረት አቆራኝተው ጉምበል ወልዱ ለሚባለው ባላገር ወስደው አስጠበቁባቸው። አባ ተክለ ሚካኤልና አባ ገብረ ማርያምንም እንደዚሁ በግር ብረት አስረው መዘዌ ገብረ ማርያም ቤት አገቡና ከዚህ በኋላ በኛ ላይ የሆነውን ነገር በግዕዝ በተጻፈው በካቶሊካውያን ታሪክ ይገኛል። በ፫፻፲፭ኛ ገጽ ባ፳ ምዕ ያባታችን ኃዘን ይናገራል።

እንግዴህ ከንቲባ አባታችነን ወደ ታናሽ ጠባብ ቤት አግብተው በጠባቂ አስቀመጧቸው ምኝታ ክፉ ምግብ ክፉ ልብስም በቅማል የተሞላ ነበረ። በ፺፪ ቁጥር እንደተጻፈ ከኔ ጋራ ፩ድ ብታሰር ዕፅፍ ይሆንብኛል እንዳሉ ወደ ግንድ መግባታችንን የልብሳችንን መገፈፍ በጨለማም ውስጥ መኖራችንን እርስዎም የሚሰዱልንን ምግብ ያቡን ሎላልት እንዲካፈሉት ሰምተው በታላቅ ኃዘን ነበሩ። የነዚያን ዘመን ያባታችን አነዋወር እንደፋርስ አነዋወር ሆነ። ዳግመኛም ከእኛ እሥራት ይልቅ የደብተራ አሰጋኸኝንና የወልደ ገብርኤልን መካድ ሰምተው ነው። እነዚህ መከራው ስለጠናባቸው ካዱ ከዚህም በኋላ ወይዘሮ ለምለም ባላቸው ሲገኙ ወዳቡን ሃይማኖት ዋስን እንደጠሩ ሰምተው እንግዲህ ወደርስዋ አትሂዱ ወደእኔም ብትመጣ አታስገቡብኝ ብለው አዘኑ። ደግሞ ይህ ድካም ወደኛ እንዳያልፍብን ፈርተው ግምባርዎን

ከምድር ጋራ አጣብቀው አምላኬ ሆይ በመፍራት አንተን እንዳይሰድቡ ልባቸውን አጽና ከንፈራቸውንም ጠብቅ እያሉ ሲጸልዩ ነበር። ይህም ጭንቀት ከተያዝነ ጀምሮ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ሆነ። ከርስዎ ጋር የነበረው አሽብር ጭንቀትዎን አይቶ የኛን ወሬ አይነግርም ነበረ። ከዚህ በኋላም

ጭንቀት ቢበዛብዎ መከራችንን ሁሉ ጽፈው ታምራትንና ገብረ ሩፋኤልንም ወደ ደጃች ካሣ ሰደዱዋቸው በዚያ ጊዜ እርሳቸው ወደ ሰሜን ገሥግሠው ነበርና መልዕክተኞቹ መንገድ አጥተው ተመለሱ። ዳግመኛም አባታችን ታምራትን ሰደዱ እርሱም ወርቁ ብሩ ገባ ለወርቁ ብሩ መከራችንን ሁሉ ነገረና ወቁ ብሩ መልክተኛን ለማቅረብ ስለፈሩ ወሬ ሰማሁ ብለው ሲዝምሩ ደጃዝማች ተቆጡና የሚአመጣልኝ ገባኝ በቆራረጥኩት ብለው ስለተናገሩ ወርቁ ብሩ ሂዱ ራሳችሁን አውጡ ብለው በሥውር ሰደዱዋቸው ደጃዝማች ወደ ጎንደር ሊመጡ ነው በተባለ ጊዜ እንዲያገናኙኝ ብለው አባታችንን ከተሸሸገበት አውጥተዎ መልካም ሥጋጃን ምንጣፍ ሰጧቸው ነገር ግን በመጡ ጊዜ ወደ ከንቲባ ቤት መምጣት ትተው በቦራ ሰፈሩ። ከንቲባም ታመው ነበሩና መሔድ ስለአልቻሉ ካሣን ያባታችን መልክተኛ ካጋፋሪ ትርፌ ኃይሉ ጋራ ወደ ደጃዝማች እንዲያቀርቡት ሰደዱ። ካሣም በፊታቸው ቁሞ እጅ ነስቶ ጌታዬ እንዲህ አሉ የኔታ ሆይ ልጆቼን እንዲፈቱልኝ ወደ ወደዱትም ስፍራ እንዲሰዱልኝ

## ዕ ዓርብ ጥር

ይህም ባይሆን ሰውነቴን ከነሱ ጋራ እንደሚጨርስዋት እለምናለሁ አሉ አለ። ደጃዝማች ግን በቁጣ ባባታችን ላይ እንዲአስተምር ማን ጠራው አቡንስ መኖርን እንዴት ይላሉ ይህንኑ ሲናገሩ አሽብር ወልደ ተክሌንና አሳላፊ ኪዳኑን በቁጣ ዓይን አዩዋቸው። ይህንንሳ ለምን ተዋችሁት ቢሏቸው እነሱም ፈርተው ባቡን ፈቃድ አሉ። ደግሞ ወደ መልክተኛው መልሰው አንተስ አገርህ ወዴት ነው ቢሉት ካሣም ፈርቶ ትግሬ ነው አለ። ደጃዝማችም ያ ያባተ ትግሬ አሉ። እንዲህም ማለታቸው ካቶሊክ የሆኑቱ ካማሮች ይልቅ ትግሬዎች እንደበዙ ስለሰሙ ይመስላል ካሣም መልሶ ያየውንና የሰማውን ሁሉ ቢነግርዎ ምሕረት እንደለለች ተስፋ ቆረጡ አባታችንም ልብሳችንን እንደተገፈፍን ሰምተው በ፷፻ ቁጥር የተጠራውን እንግዳ ወርቅ ልብስን አስገዝተህ በስውር ስደድላቸው አሉት እርሱም ሰደደ በጨለማ ውስጥ ላሉቱ ተቻለ ካባቴ ገብረ መስቀል ለይተው ወደ ብርሃን አውጥተውኝ ነበርና ለኔ ግን መልበስ አልተቻለኝም። ዳግመኛም የአባታችን ጠባቆች እንዲካፈሉት ሰምተው እንግዳ ወርቅን በዚያው ላይ እንዲጨምርልን ላኩበት እኛ የጠላትን ጭከና አስቀድመን አውቀን በራብ እንሞታለን ብለን ስናስብ ነገር ግን በመከራና በጠባብ መንገድ መስቀሉን ተሸክሜ ብከተል ማን ይመጣብኛል የሚል እንዳይን እንሆ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርቱን ለሚሰሙ ኅብስትን አብርክቶ እንደ መገባቸው ስናታሰር እንኳ እንደዚህ አልተመቸንም ያቡን ሰዎች ግን ጌታቸው ባለ ሹመትና ባለ ገንዘብ ሲሆኑ ወደኛ ሲቀላውጡ ነበሩ"። የሮማ ልዑካን ወገኖቻችን በምግብና በልብስ እያባበሉ ሃይማኖታቸውን እንዳስካዱ ምስክሩ ይህ ጽሑፍ መሆኑን ማስተዋል ነው። (ከዚህ በኋላ ደጃች ካሣ በዓለ መስቀል በቀረበ ጊዜ አቡንና በኋላ ከንቲባን ጐንደርን ወደ አምባጫራ ጠሩ። እኒህም ከሄዱ በኋላ አባታችን ናፍቆት በዝቶብዎ ፊቴን በከሰል አጥቁሬ ፩ድ ጊዜ መጥቼ ልገናኛችሁ ብለው ላኩብን እኛ ግን ሰውን ወዳድ አባታችን ሆይ እኛም ፊትዎን ብናይ እጅግ በወደድን። ነገር ግን ይህ እንዴት ይቻላል። እነሆ በፊቱ ላይ ጠባቆች ተጨምረውብናል ጠባቆች ቢይዙዎ በዚህ የባሰ መከራ በርስዎና በእኛ ያመጡብናል ብለን ላክንብዎ። በ፻፲፱ኝ ገጽ በምዕ ፯ አቡንና ደጃች ካሣ በቍርባን ምክንያት መጣላታቸውን ይናገራል ወደ አምባ ጫራ በደረሱ ጊዜ አቍርቡኝ አሏቸው አቡን ይናገራል ወደ አምባ ጫራ በደረሱ ጊዜ አቍርቡኝ አሏቸው አቡን ግን የተላኸውን ሳትታረቅ ማለህን ከድተህም ያሰርካቸውን ፋሪስ አሊንና ሌሎችንም ጐሹ ብሩንም ካልፈታህ አላቆርብህም አሏቸው ደጃች ካሣ ግን ባቡን ላይ ተቆጡ እኔኮ እንደ ደጃች ውቤ አይደለሁም

ወደ ስናር ግን ባቡን ላይ ተቆጡ እኔኮ ደጃች ውቤ አይደለሁም ወደ ስናር መስደድ አውቃለሁ አንቱ ባታቆርቡኝ የነፍስ አባቴ ያቆርቡኛል ፩ድ ግብጽ

አላውቅምን እያሉ ባቡን ፊት ደነፉ። ፫ት ቀን ያህል ሳይተያዩ ከኖሩ በኋላ ደጃዝማች ካሣ የጦር ልብሳቸውን ተጠርረው ወዳቡን መጡ። ከነዚያም ተመልሰው በምሽታቸውና ባቡን ፊት ደነፉ በቁጣ ቃል አቡኑን እንዴት ጠላቶችህን ፊትተህ ስደድ አሉኝ ይወዱኛል። ወይስ አይወዱኝም አልዋቸው አቡንም ምነው አልወድህ ካንተ በቀር ማን ዘመድ አለኝ ብለው መለሱ። እኒያስ ከኔ በቀር ሌላ እንዳይወዱ ይማሉልኝ አሉዋቸው። አቡንማ ማሉና ወደ ቤታቸው ሲሄዱ መምር አስካል የደብረ ዳሞ ተከትለዋቸው እርሳቸውም የሁለቱ ወዳጅ ነበሩና ደጃዝማችን ደፍረው እርስዎና አቡን ጉበዛዝት ናችሁ ስለዚህ እውነተኛይቱን ነገር መናገር በናንተ ፊት እንፈራለን አሉ

## ያ ቀዳም ጥር

እርሳቸውም ያሉት እውነት ነው በምን እንግዲህ ይበልጡኛል አሁንም ፈቃዴን እንዲፈጽሙ ይምከሯቸው አሏቸው ስለዚህ መምር አስካልና ከንቲባ ወዳቡን መጡ ቢአቈርቡአቸው ይሻላል። ቢሏቸው ቃላቸውን ለወጡ ምሽታቸው የራስ አሊ ልጅ ካገቡዋቸው ብዙ ዘመን ነበረ። በዚያን ጊዜ ቁባታቸውን ፈትተው ባቡን ቃል ኪዳን አሠሩ። በመጽሐፈ ተክሊል ቅባትን ያዛልና ቀብዋቸው። ቤተ ክርስቲያንም አስመጥተው አክሊላትን ደፉላቸው ነገር ግን በፍትሐ ነገሥት ይህ ደናግል ላልሆኑ እንዳይደረግ ይከለክላል። ወዲያውም ባለቤታቸው ቀድሰው አቈረቧቸው በዚህ ጊዜ አቡን ፫ ነገር ተነቀፉ ፩ዱ ፈርተው በማይገባ ማቍረባቸው ፪ኛው እርሳቸው በማይገባ አስረው ሳሉ ሌላውን ፍታ አሉ ተባሉ። ፫ኛ ከሁሉ ይልቅ የተነቀፉበት ቈራቢው በዝቶ የተቀደሰው።

ከቍርባን በኋላ (ደጃች) አጼ ቴዎድሮስ አቡንን በቀኛቸው እጨጌን በግራቸው አስቀመጧቸው። ከዚያ በፊት ግን ያገራችን ነገሥታት ካሁን ይልቅ እጨጌን ስላበለጡ በቀኝ ሲአሥቀምጡ ነበሩ። ዳግመኛ በዚህ ጊዜ ዓዋጅ ወጣ እንግዲህ ወዴት ትኼዳለህ ቢልህ ወደ ንጉሥ ከየት ትመጣለህ ቢልህ ከንጉሥ በል እንጅ ከደጃች ካሣ ያልህ ለራስህ እወቅ ተባለ። ስለዚህ ከኛ ፪ቱን ያነግሡን ይሆናል ሲሉ ያነበሩት ወይዛዝር ተስፋቸውን ቆረጡ ፪ኛም ዓዋጅ ሁሉ ሰው ባንዲት ሴት እንዲኖር እንዲቆርብም ባርያም እንዳይሸጥ ተነገረ። ባለጠግነታቸው ባርያን በመሸጥ ነበረችና ይህ አቡንን እስላሞችን አስጨነቀ ባንዲት ሴት ቍረቡ ማለት ለሁሉ አስጨነቀ ይልቁንም ለደብተሮችና ላቡን ሰዎች አስጨነቀ። ከዚህ በኋላ አቡንን እንደ ገሰጽዋቸው ተግሳጽንም የማይሰሙ ስለሆኑ እንዳገዛቸው ሊገድሏቸው ብዙ ጊዜ ጠመንጃን እንዳነሡባቸው በሁሉ ዘንድ የታወቀ ነው።

በ፲፻፹፪ኛው ገጽ በ፷ ምዕራፍ አባታችን ከጐንደር ወደ መተማ መሰደድዎን ይናገራል። ንጉሥ ካሣ ከቍስቋም በዓል በደብርዋ እንደቈረቡ ካምባ ጮራ ወደ ጐንደር ከምሽታቸው ጋራ በኅዳር ፩ ቀን መጡ እንግዲህ ንጉሥ በዚህ ጊዜ ባቡን ቤት ሳሉ ጳጳሱ በንጉሡ ስም ለመተማ ገዥ የምትደርስን መልክት ጽፈው አነበቡላቸው። በማኅተምህ አትምልኝ አልዋቸው ቃሉም እንዲህ ይላል የመተማ ገዥ አብራሂም መልክተኞቻችን የሚአመጡልህን ያዕቆብን እንዳያመልጥህ እወቅ ጠብቀው ወዳገሩ እንዳይሄድ ወደዚህም እንዳይመለስ በእስራት አኑረው በሥውርም አጥፋው አሉት የሚል አለ። ንጉሥ ቃልዎ ስለከፋ በፊት አይሆንም ብለው ኋላ ግን አተሙላቸው ያለ አለ። ዳግመኛ በዚህ ጊዜ ንጉሥ አባታችነን ሊያዩ ወደዱ ይላሉ አቡን ግን እርሱን ማየት ከፉ መሳቴ ነውና ያስትሐል አልዋቸው ንጉሥ ከጐንደር ወደ አምጫራ ሲመለሱ ከንቲባን ያዕቆብ እንግዲህ የምሔድባት ቀን ቀረበች በሉት አሉዋቸውና እጨጌ የከተማውን ሁሉ ሰው ሲያገኙአቸው ወጥተው ሳሉ አባ ገብረ ሥላሴ የሚባሉ የእጨጌ ሊቀ ካህናት የኔታ

ሆይ ያባ ያዕቆብን ሃይማኖት የያዙ አሉ ብለው ከሰሱ እንግዲህ እንዴት እስከ ዛሬ ወደኔ ሳታመጣባቸው ቢሉ ይህን ወደርስዎ እናመጣለን አሉ። ስለዚህ በገበያ ቅዳሜ ቀን የያዕቆብን ሃይማኖት የያዝህ ሰው ወደ ሃይማኖቴ ባትገባ አንገትህን በሰይፍ እቆርጣለሁ ብሎ ተናገረ ነገር ግን በታሰሩት ሆኖ በሥውርም ባሉት የካቶሊካውያን የልብ ገሮ ይህ

## ዘ እኁድ ጥር

ዓዋጅ አልገባም። ይህ አዋጅ በታላቅ ክብር እንዲነገር ያቡን ወምበርና የወርቅ መቋሚያ የእጨጌም ወምበር ጁህ ለብሶ በዚያ ነበሩ። ከዚህ በላይ እንዳልሁ ከንቲባን ከንጉሥ የታዘዙትን ቃል ላባታችን ነገሩ እንዲህ ሲሉ የሚሄዱባት ቀን እንግዲህ ቀረበች ባገራችን መኖርን ቢፈልጉ ወደ ሃይማኖታችን ይግቡ አለዚያ ቤትዎን ሽጠው ይሂዱ አሉዎ ብለው ተናገሩ። አባታችን ግን ልጆቼን ካልሰጣችሁኝ እንዴት እሄዳለሁ ከነዚያ ጋራ እሠሩኝ እንጅ ከቶ አልሄድም አሏቸው። ከንቲባም ይህን ቃል ወደ ንጉሥ ላኩ ያቡን ነገር ስላሸነፈ አባታችን ከጐንደር በጭከና በግድ የሚአወጡ ያቡንና የንጉሥ ሰዎች መጡብዎ ይህም በኅዳር ፳፫ በእሑድ ቀን ከግዞት ከቆዩበት ለበዓታ ቤተ ክርስቲያን ቅርብ ናትና በመስኮት ወጥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲማጠኑ ብሩ የሚባል የጐንደር አሽከር ከርስዎ ጋራ ነበርና እንዳገር ልማድ መጥቅን መታ። መልክተኞች ዙረው ወዳሉበት እርስዎ ገብተው ከኛ ጋራ ያለው የንጉሥ ቃል መልካም ነው ስለምን ወደዚህ ሸሹ አሁንም ወደ ደጅ ይውጡና እንድንነግርዎ አሉዎ። እርስዎ ግን መልካም ከሆነ ስለምን እዚህ አትነግረኝም ሲሉ እነዚያ በከንቲባ ፊት እንድንነግርዎ እትዛዝ አለነ ብለው ሲናገርዎ እኒያ አሽብር ወልደ ተክሌ ጨካኝ ሰው መጡ። ይህ በአቡናችን ላይ መሆንን የሚፈልግ እርሳቸውንም የሚአስነቅፍ በቃሉስ ያገራችንን ሰዎች የሚአስት አይደለምን አትጐትቱትም ስለምን ክብር ትሰጡታላችሁ ብለው ጐተቱዋቸው። ከዚህም በኋላ አባታችን ቢቆምሙ በድንጋይ ላይ ወረወሯቸው ከዚህም ላይ ረገጧቸው በድልድሉም በድንጊያ ላይ ስለ ጐተታቸው ከግሮችዎ ደም ፈሰሰ። አጥንትዎም ተቀጠቀጠ በዚህም ጊዜ ሆድዎን ታመው ሰንበተው ነበሩና ከዚያም ሰውነትዎም በሌላ ሕመም በተጋድሎም ባዘንም መንምና ነበረችና ከዚህ በኋላ ከተጨመረብዎ እንግዲህ አልተረፉም አልነ እስከ ከንቲባ ቤት ፩ት ሰዎች ተሸከመው አደረሱዋቸው በነጋታው ከከተማው በወጡ ጊዜ ወሬዎን የሰሙ ሁሉ ሊያዩዎ የመኙዎ ነበረና መጡ አባታችንም መንገድን በዠመሩ ጊዜ እኛም ልጆችዎን አስበው አለቀሱ። አጋፋሪ ገብረ ሥላሴ ያባታችን የቁጣቸውን መልክተኛ በበትር እየመቱ አባረሩዋቸው በዚህም ጊዜ ወልደ ገብርኤል ካባታችን ነጥለው አምጥተው አሠሩት። ይህም ላባታችን እጅግ አሳዘነ። እርሱም እንዳልሁ በመፍራት ሃይማኖቱን ክዶ የነበረ ነው እንግዲህ አባታችን ከጐንደር ተነስተው ወደ አደርጅሐ ደርሰው በካቶሊካውያን ቤት ገቡ ከርስዎ ጋራም ያረቡ ናቸው እንጅ ገብረ ሩፋኤልና ካሣ ኃይሉ የሚባሉ ጐበዛዝት ገብረ ሩፋኤል ፈርቶ ከጭልጋ ተመለሰ። ያባታችን ጠብቂ የከንቲባ ሎሌ ነበር በነጋታው ከድርጅሐ በተነሱ ጊዜ ታምራት እርስዎን ሊከተል በሥውር ተነሳ የከንቲባ ሎሎ አውቀው እንዳይከለክለው ተሠውሮ ባጠገብዎ እየሄደ ወደ ጭልጋ ደረሰ በዚያም የከንቲባ ሎሌ ቀኝ አዝማች ጣዩ ለሚባል ቅማንት ላገሩ ገዥ አባታችንን አሳልፎ ሰጥቶ ተመለሰ ታምራት ሰው እንዲመለስ አውቆ አባታችን ወዳሉበት ቤት መጥቶ አነቃ ፪ቱንም ከርስዎ ጋራ የነበሩትንም አነሳቸው። ነገር ግን እንቅልፍ በዝቶባቸው ተመልሰው ተኙ ታምራትና አባታችን ግን ጠባቆቹ አልሰሙምና ተኝተው ወደ ጠገዴ የምትወስድን መንገድን ይዘው ሁለት ወይም ፫ ሰዓት የሚያህል ከሄዱ በኋላ ታምራትን ልጄ ሆይ አሁን ከጠላቶችህ እጅ በእንግዲህ ያለ አወጣጥ አልፈልግም በግዜር ፈቃድ ካልሆነ እንግዲህ

## ዙ ሰኑይ ጥር

እኔን ቢአጡ በእንቅልፍ ምክንያት የቀሩትን በልጆቼም ላይ ከመራ እንዳያበዙባቸው እመላለሳለሁ። አንተ ግን አገርህ ተመለስ ምሽትህን ልጆችህን ጠብቅ አሉት ታምራት ግን አባታችን ሆይ እግዜር ካወጣነ በኋላ ወዴት

እንፍሳችንን ወደሚፈልጉት ተመልሰን እንገባለን ብሎ ለመነዎ አባታችን ግን አይሆንም ስለአሉ ተመልሰው ወዳገሩ ባጠገብ በደረሱ ጊዜ እንግዲህ ልጄ ሆይ ከኔ ተለይ በደህና ያውልህ እግዜር ይባርክህ ብለው አሰናብተውት ሲመለሱ አይተው ተኝተን ሳለን ይህ ሰው ወኅኒ አውርዶ መልክተኛው ለሹሙ ሰጠ እንደተጻፈ መልክት በንጉሥ ማኅተም የታተመችውን የያዙ ካቡን መልክተኞች ጋራ በወኅኒ ተገናኙ ከኒህም ፪ኛው ወይም ፫ኛው ባርዎችንና ፈረሶች ሊገዛ ከሱዳን አገር በዚያ ጊዜ የመጣ ነው። ነገር ግን ባሮች እንዳይሸጡ ታውጆ ነበርና ስለዚህ ሰው ጭንቅ ሆነበት ስለዚህ አቡነ ያዕቆብን ጠብቀህ ውሰድልኝ እኔ እንድትገዛ ከንጉሥ እለምንልሃለሁ ያስገዙት ነው መልኩ ክርስቲያን ይመስላል ሌሎቹም አቡን በትግሬ ሳሉ ከምጽዋ የሸሹ የቱርኮች ወታደሮች ናቸው ከነዚህም ፩ዱ ቱርክ የቀሩትን ግን ጥቋቁሮች ነብሩ እነዚህም ከኛ ጋራ ይልቁንም ካባ ተክለ ሚካኤል ተወዳጅተው ከርመው ነበሩ ሲጣሉ አስታራቂ ገንዘባቸውንም ጠባቂ ነበሩና እርሳቸውን እንድወንድማቸው አዩአቸው። ባባታችንና በኛም ግፍ ግንዱን እያዩ ሲአዝኑ ነበሩ። እንግዲህ በወህኒ በተገናኙ ጊዜ ሹሙ ያብራሂም ሎሌ በዚያ አግኝቶ የደጃች ካሣ ትዕዛዝ ነውና እኒህን ሰው ከጠባቆቸው ጋራ ወደ ጌታህ አድርስ ብሎ አዘዘው እስከ መተማ የ፪ ቀን መንገድ ነው ነገር ግን ወደዚህ ከደረሱ በኋላ አባታችንን ባገሩ ውጭ ትተው ወደ ከተማ ገቡ። ለአብራሂም እንዲናገሩ ፩ድ እንኳ የተጋ የለም ከዚህ በኋላ መልክተኞቹ ወደ ወንዙ መጥተው የምሕረትን እንገር ባባታችን ላይ አንብበው የቃልዋን ክፋት አይተው ጣሏት። ከነዚያም ፩ዱ ምስጢር እንዳያወጣ ተማማሉ። አባታችን በሜዳ ከነጋዴ ጋራ ሰፍረው ነበሩ ባጼ ፋሲል ትዕዛዝ በበሰኪን ስለሃይማኖት የተቀመጡትን የቅዱስ ፍራንችስኮንስ ልጆች እያሰቡ ሞትን ጽኑ ግዛት ሲቆዩ ሳሉ ከዚያ ፩ዱም መዠመሪያ ወደርስዎ መጥቶ አይዞዎ ደስ ይበልዎ ያችን ክፉ መልእክት ቀደን በውሃ ጣልናት አለዎ አይነተኛው መልእክት የተቀበሉ ግን አባታችን የተገፉ ሰው እንደሆኑ አውቄአለሁና አሁንም ወደ ወደዱት እንሂድ ሥልጣን አላቸው ገንዘብ ባይኖር ለስንቅ እኔ እሰጣለሁ አሉዎ። አባታችን የመፍተን መስለዎ እንጅ አላመኑም ከርሱ በኋላ ግን ሌላው ትርኩ መጥቶ ጥቂት አማርኛ ያውቃልና የምሥራች ብሎ መልክቲቱን መቅደዳቸውን ሌላውንም ነገር ማድረጋቸውን ነገርዎ። እንግዲህ እኛ ወደ ጐንደር እንመለስ እስዎም በወደዱት ይሂዱ አሉዎ አባታችን በኤርማኩለታ በግዕዝ ማርያም አማላጅነት በጌታችን በኢ ክ ቸርነት አመሰገኑ ወደ አውሮፓ ሊመለሱ አስበው ነበረ ኋላ ግን ወደ ጐንደር ሊመለሱ ቆረጡ በ፴፩ ገጽ በ፱ ምዕ አባታችን ከመተማ ወደ አደርጅሐ መመለስዎን ይናገራል የተወደድ ኢትዮጵያዊ ወንድሜ ሆይ የልብህን ዓይን እግዜር ያብራልህ። እነሆ በፊት በዚህ መጽሐፍ እንዳየህ ብዙ ጊዜ ራስዎን ስለአንተ ፍቅር ለሚሰጡ እነሆ ዳግመኛ አሁን ያገርዎ መንገድ በዚያ ሰፊ የተመቸ ሁኖልዎ ሳለ

## ፲ ሡሉስ ጥር

ሰውነትዎን መግደል ወደሚሹ ተመልሰዋልና እስኪ እይ በ፲፯ ቀን ያህል በመተማ ከውጭ ነጋዴ ጋር ከኖሩ በኋላ ከጥጥ ነጋዴዎች ጋራ ከዚያው ተነሡና ገንዱዋ እስከሚባል ወንዝ ታላቅ ፈሳሽ ከደረሱ በኋላ የሔዱባትን የወህኒን ትተው ወደ ጣቁሳ  የሚወስደውን ያዙ ለነጋዴዎችም ፍሪዳን አስገዝተው ሰጡ። ከነዚያም ፫ቱ እንደ ልጆች ስለረዱዎ ፩ብር ሰጧአቸው እነዚያም በጠገቡ ጊዜ አባታችንን አመሰገኑ ወደዱዎም እርስዎም ራስዎን ሳያስታውቁ ሲአስተምሯቸው ነው ነገር ግን በፊት የተጠራው ሎለዎ ካሣ ይሙት ሲል ሰምተው አውቀዎ አባታችን ከቀድሞ ዠምረው እስከ ዕረፍትዎ ይህንን ልማድ ከልክለው ነበረ። ከ፫ቱም ፩ዱ ገለቱ ይባላል ጣቁስ በደረሱ ጊዜ ወደ ቤት ገቡ። ከዚያም መልክተኛን ወደ

ታምራትና ወደ እንግዳ ወርቅ ላኩ በቅሎን ይዞልኝ ይምጣ ብለው እኒህም ወንድሞች ቶሎ ወደኛ ላክልን ባዘን ጨለማ ተውጠን ሳለን ይህ የምሥራች እንደ ብርሃን ሆነልን ቢሆንም ጣቁሳ ያቡን ጉልት እንዳለች ሰምተን ወደ መጨነቅ ገባነ። ታምራት ግን በቅሎን ይዞልዎ በሌላ መንገድ አለፈ። የተመለሱበትም ጊዜ ከተሰደዱ በኋላ ፳፱ ቀን

ታኅሣሥ ፲፯ ነው ከዚህ በኋላ አባቴ ዮሴፍ ካባታችን ጋራ ተገናኙ። የ፪ቱም መገናኘት በዚያ ጊዜ ደስታን ስላበዛላቸው እንደ ሕልም መሰላቸው በዚያ ሆነው በላኩብን ጊዜ እጅግ ደስ አለን። ልጆቼ ሆይ ጌታዬ በደህና ወደዚህ ካደረሰኝ የናንተን መከራ ፍጻሜውን በዚህ ሁኙ ልሰማ እወዳለሁ አሉ ከደርጅሐ እስከ ጐንደር ፫ ወይም የ፬ት ሰዓት መንገድ ነው አባታችን ሆይ ወደ ትግሬ ብቻ በቶሎ እንዲሄዱ እንለምናለን ብለን ላክንብዎ እርስዎ ግን መሄድን አልፈቀዱም ከዚህ በኋላ አቡን እኛን ገረፉን አባታችን መገረፋችንን ሰምተው ስለ ጽናታችን ደስ አለዎ ጌታዬ ተመስገን ይህንን ጽናታቸውን ያደረግልህ ያስማኸኝም አሉ። በሌላ ወገን ግን እንደ ሩሩነትዎ እንዴት መነኩሳትን ዕርቃናቸውን አውጥተው ይገርፋሉ አያሉ አለቀሱ። ባላገሮችም መገረፋችንን ሰምተው እጅግ አዘኑ። የሚአውቁትም ወደ ታምራት መጡ። እንፈራለንና እነዚህን ሰዎች አስለቅቅልን አሉት እሱም መንገሩን ስላፈረ ባለቤታቸው ነገረዎ እርስዎ ግን የመጨረሻውን እስካይ በዚህ ተሸሽጌ ልቆይ እባካችሁ ብለው ቢለምኗቸው አይሆንም ፈርተናል አሉዎ። ስለዚህ እንግዲህ ጌታዬ የልጆቼን መገረፍና መጥናትን ካሰማኝ ይህንኑ ስንቅ አድርጌ እሄዳለሁ ብለው ታኅሣሥ ፴ ቀን ከደርጅ ተነሡ። አባ ዮሴፍ ወንዴ የፊተኞችም ካሣና ኃይሉ ከርስዎ ጋራ ነበሩ ታምራትም ካ፩ድ የታመነ ወዳጅ ዘላን መሪአቸው ሆነ ነገር ግን ከዚህ የመነሳትዎን ትቸ በታምራት ላይ የሆነውን እናገራለሁ። እርሱ አባታችንን ሸኝቶ ከተመለሰ በኋላ አቡን ጦራቸውን ሰደዱበት እግዜር ግን አወጣው። ንጉሥ በዚያ ወራት ክተት ብለው አሳወጁ ስለዚህ የጣቁስ ሰዎች እኛ የርስዎ ዜጐች ነንና መዝመት አይገባንም ብለው ወዳቡን በመጡ ጊዜ አባታችን ከመተማ ተመልሰው ከዚያ አገር ገብተው ማለፍ ነገርዋቸው። ይህም መሰማት አቡንን እብድ አደረጋችሁ። በሰብዓ ሰገል ወሬ ሄሮድስ እንደ ታወከ ስለዚህ ወሬኞችን የነና የካሣ ጠላት መሆኑን እያወቃችሁ ያልያዛችሁት ብለው ተቆጡባቸው እነዚያም እኛ ደርሱብን ካገር ዳርቻ ወደ መሀከላችሁ ሲገባ ምን እንበለው አሁንም በሥውር የገባበትን ቤት እናሳያለን ጠላትዎ

አያመልጥም እንኪያስ ስዌን ይዛችሁ ሄዱና አያምልጣችሁ ብለው ሰደዱ። አባታችን ገብተውባቸው የነበሩትን አስረው ወስደዋቸው። በዚህ ምክንያት በሀገሩ ላይ ብዙ ጉዳት ተደርጐአል። አባታችን ከድርጅሐ ተነስተው በ፰ኛው ቀን በመሪ እየሄዱ ቆላ ወገራ በደረሱ ጊዜ ታምራት ከጓደኛው ጋራ ካባታችን መልዕክት ይዞ ጐንደር ወደ ታሠሩት ተመለሰ። መልክቱም መልዕክት አቡነ ዘትበጽሕ ለመቁሐን ወይእቲ ወይእቲ እምኀበ ያዕቆብ ሮማዊ ለዕለ ተሞቅሑ ወተቀሥፉ በእንተ እግዚ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላመ እግዚአ ወረድኤታ ለኢማኩላታ የሃሉ ምስሌክሙ በጸሕኩ መንገለ ምድረ ፀገዴ በምሕረቱ ለአምላክነ ወበ ጸሎት ክሙ ወባሕቱ አነ ወአኀዊክሙ እለ ምስሌየ ቦአ ውስተ ስጋነ ሕማሙ ተቀስፎትክሙ። እስመ ፩ አባል ንሕነ ወበከመ ተፈስሐት ነፍስክሙ በመቂዖተ ኃይለ ሰይጣን ንሕነሂ ተፈሣህነ ምስሌክሙ በመንፈስነ ኦ ደቂቅየ አዕፃዳተ ወይን ዘአፍለስክሙ እግዚአ በሂሩቱ እምክህደተ ምድረ ግብጽ ሰዲዶ አሕዛበ ኢትዮጵያ ተከለ ኪያክሙ ወጼሐ ወመለዓ ምድረ ወከድነ አድባረ ትዕቢቶሙ ለሰበዓ ኢትዮጵያ ጽላሎተ ትሕትናሆሙ ሰፍሐ አዕጹቂክሙ እስከ ባሕር ወእስከ አፍላግ ሠርጽዕክሙ አምጣነ ተተከልክሙ በሐምሌ ወፈረይክሙ በኃጋይ እግዚአ ይዕቀብክሙ እምኩሉ መንሱት በ፲፻፹፻፶፯ኛ ገጽ ከአደርጅሐ በ፪ ወር ካ፳ ቀን ወደ ሐላይ ደረሱ ከዚያም ተነስተው ተከዜን እስቲደርሱ የሄዱበት መንገድ አቀበትና ቁልቁለት እጅግ የሚያስፈራ ዱር ነበረ። ጊዜውም የጦር ጊዜ ስለሆነ ሁሉ እርስ በርሱ ታውኮ ፩ዱ በሌላው ላይ ተነስቶ ነበረ። አባታችን ግን ዋልድባን እስቲ ገቡ ድረስ አቡንና ንጉሥ በወገራ ነበሩ።

በዚያ ጊዜ ደጃች ውቤ ድል ከሆኑ በኋላ አቡን እንሆ ጠላታችን ያዕቆብ ከመተማ ተመለሰ አሁንም ባድወሰኔ እንደሆነ እሰማለሁ ንጉሥ ግን እኔ በዚህ ሊታሰር ወድጄ ነበርሁ እርስዎ አይሆንም ስደድልኝ ብቻ አሉኝ እንግዲህ ምን ላድርግ ፩ድ መነኩሴ ወዴት ሄደ እያልኩ በኋላው የምከተል ነኝን አሉዋቸው። ባ፲፩ ምዕ አባታችን ወደ ሐላይ እንደ ደረሱ ይነግራል።

አባታችን በሐላይ ፫ት ሳምንት ካረፉ በኋላ ደሌ የሚባል የፈራስያ ኮንሲል መልክትን ተቀበሉ በዚችም የተጻፈው ቃል የራሴ ነበር ይህም እንዲህ ነው አቡን አጼ ቴዎድሮስን አስፈቅደው በዚያ ጊዜ ከዱ በተባሉቱ ባቶ ሽምብር

መልክተኛ መልክትን ወደ ምጽዋ ሰደዱ። ወደ ኮንሱል እርሱም የቡላውድን ወዳጅ ስለሆነ ባቡን ስብከት መኖር አይገባም ብሎ ጻፈልዎ ስለዚህ ከላይ ሰው ጋራ በቃል ካልሆነ በመልክት አይሆንም ብለው ከሐላይ ወደ ምጽዋ ወረዱ ወደ ሽሐ ጋዴ ሲደርሱ በእኩል ቀን ሲሆን በወንዙ አርፈው ስላኡ አንበሳ መጣብዎና ልብስዎን ትተውለት ሸሹ። አንበሳው ግን ሰውን ያገኘ መስሎት በልብሱ ላይ ተቀመጠ አባታችን በደህና ወደ ምጽዋ ደርሰው ካቡነ ቢያንኬር ከኮንሱልም ጋራ ተገናኙ። ለኮንስ ግን የተናገሩትን አላወቁሁም እርሱም ተሽሮ ሌላ ሊመጣ መሆኑን ሰምተው እንግዲህ ከባሮኒ ጋራ ሳይገናኝ መገናኘቱና ነገሩን መናገር በግድ ነው ብለው እየጠበቁ በምንኩሉ ፲፬ ወር ያህል ተቀመጡ።

# ፵ ኃሙስ ጥር

በ፳፮ ቁ/ እንደተጻፈው አቡን ቢያንኬርና ወንድሞች አልተስማሙም። ስለዚህ አባታችን ከመከራው ወጥተው ወደ ሐላይ በደረሱ ጊዜ ወንድሞች የተበደሉትን ነገሩዎት። ይልቁንም ላባታችን ያሳዘነ ፩ዱ አባቴ ዮሴፍ ባማራ አገር ስላኡ ባለ ሕግ ካልሆነ ክህነትን አልሰጥም አሉን ቢሉዎ ልጆቼ ሆይ ተዉ ሽማግሌ ሰው ናቸውና አቡነ ቢያንኬሪ እንደዚህ ያለ ነገር ይላሉ ብለው አላመኑም ነበሩ። ኋላ ግን እርግጡን አውቀው አዘኑ።

፪ኛም አባታችን ወደ ሐላይ ሳይገቡ አቡነ ቢያንኬሪ ወደ መኰሳት በላከዋት መልእክት እነሆ የተገኘ ለቀበላቸው ጥቂት ገንዘብ እንግዲህ ግን የለምና አትላኩብኝ። አቡነ ያዕቆብም ወደ መተማ ከወረዱ በኋላ ወሬአቸው ከጠፋ እኛም ወደ ሀገራችን እንሂድ ትላለች ወንድሞችም በዚህ ነገር እጅግ አዝነው ትንፋሽንም የመቁረጥ ጨለማ ሸፍኖአቸው ስላእ እነሆእ በ፪ኛው ወይም በ፫ኛው ቀን አምላካቸው ያዕቆብ ብርሃንን አወጣላቸው። እንግዴህ አባታችን በዚህች መልእክት እጅግ አዘኑ ፫ኛም አቡን ደጃች ውቤም ወዳማራ አገር ከተሻገሩ በኋላ የሚአስፈራቸው አልነበረምና ወደ ስብከታቸው ሳይወጡ በምጽዋ በመቀመጣቸው።

፬ኛውም በግልጥ የኢትዮጵያ ሰው ሁሉ የሚአነውረውን እስላሞች ያረዱትን በመብላታቸው ለከለ ግዛይ ሰው ሁሉ እንቅፋት እንደሆንባቸው ሰምተው አዘኑ።

ስለዚህ ነገር አባታችን ወደ ሮም ጻፉ ከዚያም እንቅፋት ሆነ ሰባኮች ካህናቶች አይብሉ የሚል ምላሽ መጣልዎ።

በዳር በዳር ያሉት እስላሞች ጐረቤቶች ክርስቲያኖች በጭንቅ በራብ ጊዜ እስላም ያረደውን ቢበሉ እንግዲህ እስላም ያረደውን አለመብላታቸው መልካም ነበር።

አሁን ግን አቡነ ያዕቆብ ወደ ሮም በመላካቸው መልካም አላደረጉም ብለው አቡነ ቢያንኬሪና አባ ዘካርያስ ለአክሡም ተናገሩ።

ግን እስላም ያረደውን ካህን ሲበላ ቢያይ ይህ እስላም ነው ክርስቲያን አይደለም ይሉታል።

ስንኳንስ ትምህርቱን ሲለሙ ሳይደበድቡት አይቀሩም ይመስለኛል ምሕረትም ያላቸው ቢሆን አገራቸውን እንዲአስለቃኡት ግድ ነው።

አባታችን ከሃላይ ወደ ምጽዋ በወረዱ ጊዜ አቡነ ቢያንኬሪ በወንድሞች የተበደሉትን በቃልም በወረቀትም ሆነ ላባታችን ነገሩ አላዩም በኔ ላይ የተናገሩትን የጻፉትን እንዴት ከቤት ሳይሰጧቸው ቀሩ ብለው በላይ እንዳልሁ ፲፬ ወር አባታችን ከልጆችዎ ጋራ በምንኩሉ አቡነ ቤያንኬሪ ግን ከረድኦ ፊልጵኒ ጋራ በምጽዋ ኖሩ። በምክርም በሥራት ባለመጋጠም ይመስለኛል ከዚህም በኋላ በ፪ኛ ዓመት ከሮም ስብከትን ከ፪ት እንዲከፈል ትወዳላችሁን የሚል መልእክት ወደ ፪ቱ አባቶች መጣ አደን የቀረውም ዳር ዳር አገር ከቦጐስ ዠምሮ እስከ ላዕላይ ግብጽ እስከ ስናርና

ካርቱም ላ፩ዱ እንዲሆን ምጽዋን ትግሬን አማራን አገር የተባለውን ሁሉ ለሌላው እንዲሆን ብለው ላኩ አባታችን እሺ ብለው ተመለሱ።

## ዝ ዓርብ ጥር

አቡነ ቤያንኬሪም እሺ ነገር ግን ባለን ቦጐሱ ፬ት ወይም ፫ት ካህናት አቡነ ያዕቆብ ካላነሰው አይሆንለትም አለ። ኋላ ግን ካርዲናል በርናቦ ተውት።

ከዚህም በኋላ አቡነ ቢያንኬሪ ካባ ፊልጶስ ጋራ ወደ ቦጐስ መጡ አባታችንን አስፈቅደው በፊት ካቡነ ዮሐንስ ከዚያ የነበሩ አባቴ እምነቱ ግን በዝያ መጠበቅ አይቻለኝም ብለው አባታችን ወደ አበ ምኔታቸው ላኩ አቡነ ቢያንኬሪ ግን ላቡነ ያዕቆብ መነኰሳትን ያምናሉ እንጅ ሙሴ እስቴላ ደህና ናቸው ለእንግዲሁ በቦታ ብቻ አልተለያዩም እንጅ በምክርም በሌላው ነገር አልተጋጠሙም ካገራቸውም የሚመጣላቸውን ገንዘብ እኩሌታ ለነዚያ እኩሌታውን ላባታችን ይከፈል ነበር"። ይኸው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖት የሚያከዱበት ሰላምና ፍቅርን የሚጠፉበት በገንዘብ መሣሪያ መሆኑን ይህ ጽሑፋቸው ይመክራል።

"ደግሞ የቦጎስ ሰባኮች ከቡላድ የእንግሊዝ ኮንሱል ከምስለኔአቸው ካባ ሮኒ ጋራ ፍቅር ሆኑ ምክንያቱም ቦጎስ በእስላሞች በተዘረፈና በተማረከም ጊዜ ሙሴ አስቴላ ወደ ደሌ የምጽዋ ኮንሱል መጥተው የሰበኳቸውን ሰዎች እስላሞች ማርከዋቸዋልና ይርዱኝ ቢሉ አይሆንልኝም አሉዋቸው። ወደ ኮንሱል ቡላውዶን ሔደው ቢነግሩ ግን እሺ አሉዋቸው ከምጽዋ እስከ ጋሽ ባ፩ድ ሄዱ ፪ቱም ወደ እስክንድርያ ላሉ ፈረንሳዊ ኮንሱል ጀኔራልም ለምስር ንጉሥ ነግረው ፻፶ የሚሆኑ ሰዎች ስለ ሌላውም ገንዘብ በብር አስመለሱ ስለዚህ ኮንሱል ቡላውዶን በከበረ ተቀማጭ ሆኑ። ሰባኮችም እርሳቸውን ጠባቂ አደረጉ ዳግመኛም እኛ በዱር ነነ ያለነው።

ካቡንና ካጼ ቴዎድሮስ እንዲኖራቸው ወዳጆች ሆኑ ፫ኛም ከሮም በቀር በወዲያ አገር ያሉት ወንድሞችዎ ካቡነ ቢያንኬሪ ጋራ አሳባቸው ተጋጠመች እንጅ አባታችን ጋራ አልሆነችም ይላሉ። በ፻፶፪ ገጽ አባታችን ወደ ደጃች ንጉሤ መላከዎን ይናገራል።

ከደጃች ውቤ የት ልጅ ከወይዘሮ እታገኝ ደጃች ንጉሤን ወለዱ። ደጃች ውቤ ካጼ ቴዎድዎስ ድል በሆኑ ጊዜ ልጅ ንጉሤ ተዋግተው ወደ ደረስጌ ሸሹ። ንጉሥ በዚያ ወራት ከስሜን ወደ ጋላ ወደ ሸዋም ስለዘመቱ ወደ ደብረ ታቦር በደረሱ ጊዜ ልጅ ንጉሤ ባገራቸው በሣህላ የተሾመውን የንጉሥ ምስሌን ሻሩት ከዚያም ወደ ሰሜን መጥተው የደጃች መርሶን ልጅ አባረሩ ያለምን እኛ የሞትንም ከኛ ደጃዝማች ንጉሤ ያላልክ ለስራህ እወቅ ብለው አሳወጁ፡

መሸሻ ንጉሤ የተባሉትም የደጃች ውቤ ልጅ ከመኳንንቶቻቸው ጋራ ለደጃች ንጉሤ ታዘዙ።

ኃይሌ ምርጫ የጠለምት ባላባት ከንጉሥ እጅ ፳፪ ነፍጥ ተቀብሎ የተሾመውን ድል አደረጉት ከዚህም በኋላ እስከ ጐንደር ሄደው ባሕር ግብ የሚለውን ቦታ ገልሞ ፈንጃ እንግዳ የሚሉት የንጉሥ ምስሌኔዎች መቱ በዚያም ብርቱ ውጊ ሆነ ይላሉ። ስለዚህ በኋላ ወደ ትግሬ መጥተው ሐራጕር በሚባል በሐውዜን አጠገብ አቶ ኃይለ ማርያምን የትግሬን ሁሉ ምስለኔ መቱ ስለዚህ እርሳቸው በትግሬ ወንድማቸው ደጃች ውቤ የገዙትን ሁሉ ገዙ።

## ዞ ቀዳም ጥር

እንግዴህ አቶ ኃይለ ማርያምን ገድለው ወደ ዓድዋ አጠገብ በመጡ ጊዜ አባታችን ሰላምታን እንዲነግሩ አባቴ እምነቱን ወደርሳቸው ላኩ እርሳቸውም በፍቅር ተቀብለዋቸው ፩ድ መልክት ላባታችን ፪ኛም ለኮንሱል ቢሊያርድ

ባባቴ እምነቱ ሰደዱ። ቃሉም ባገራችን ዳግማይ ግራኝ ተነሥቷልና እርዱኝ የሚል ነው። አባታችንም የላኩብኝን ነገር ሰምቻለሁ። ነገር ግን ከኮንሱል ጋራ ቢገናኙ መልካም ነው ብለው መለሱ። ዳግመኛም በዚያ ዘመን ከንጉሥ ነገሥት ናፖሊዮን በላንተ ጌታ ላባታችን መልክት መጣች የከሪሚያ ጦር ከተጨሬሰ እንግዴህ ወደናንተ እንመለከታለን እጃችነንም ወደናንተ እንዘረጋለን የምትል ነበረች እኛም እንዲህ ብለው ጻፉ ደጃች ንጉሤም እርዱኝ ካሉ ለአገራችን የሚጠቅም ነገር ይደረጋል መስሎን ተስፋ ነበረን አባታችን እንደላኩባቸው ደጃዝማች ንጉሤ ኮንሱል እንዲገናኙ ፈልገው አባታችን እንደላኩባቸው ደጃዝማች ንጉሤ ኮንሱል እንዲገናኙ ፈልገው የተሸለመችን በቅሎ ሰደዱላቸው ነፈጥንም የሚገዛበት ብርን ሰደዱ። ኮንሱልም በዚያ ወራት ሁለት ነገር አደረጉ ፩ ቅፍለትን በሐላይ እንዲሔድ ማድረጋቸው ነው። ቀድሞ በደጃች ውቤ ኃላዮች ባባታችን ዘመን ቅፍለት ባገራችን ሄደው ነበር ብለው ጮሁ። ብላታ ኮከቤ ከድግሦች አስለቅቀው ሰጧቸው። አማሬ ክንፉ ካቶሊካዊ ግን ወዲያው ነገሩን ገልብጠው በድግሳ እንዲሆን አስደርገው ነበረ።

ባ፳፱ ቁ እንደተጻፈ። ኋላ ወደ ኃላይ ስደት በሆነ ጊዜ ግን ሐላዮች አባታችነን የሚያሳርፉ ሆኑ ስለዚህ ለኮንሱል ነገሩ። ኮንሱልም ለባሻ ወቃይመቃም ነግረው በሐላይ እንዲሄንድ አደረጉ። ይህም ለአሳውርታ ለአካለጉዛይ ለሌላም አስደነቀ። እንደዚህ ያለ ችሎትን አላቸው እያለ አከበረ የድግሳ ሰዎች ግን ባባታችን ላይ እግጅ አዘኑ። ከሐላይ ወደ ሂቦ ሲወርዱ ሊገድልዎ ደጃዝማች ስለኔ ብለውልኝ ነው እንጅ ለማን ወደረኛ ተነሣበት ብለው አሉ። ወዲያው ግብር ገባ ኮንሱል የለመዱትን እንዲመክሩ ይላሉ። ኋላ ግን የካቶሊካውያንን መብለጥ እየበዛች ስትሔድ አይተው ካባታችን ጋራ ተፋቀሩ። እኛም ወዳገራችን ይምጡልን እንጅ ልጆችዎ እንሆናለን ቤተ ክርስቲያንም እንሰጥዎ አለን አሉ በዚያ ዘመን ነፍጥ እንዳይመጣ ቱርኮች ከልክለው ነበሩ። በዚያ ጊዜ ግን ኮንሱል በዚያ ገንዘብ የተገዛውን ፳፱ ነፍጥ የደጃች ንጉሤ ማስታወቃቸውን ሁሉ አደነቀ። ዳግመኛም በዚያ ጊዜ ኢየአስ ጎሹ የሚባል የጎንደር ነጋዴ ፩ድ ታላቅ እስላም ብሎ ሰደባቸው። ካፊር አንተ ብለው በመለሱለት እንዴት ትክክል ተሳደብነ ብሎ ተቆጣ ካበሻም ወታደር አምጥቶ ተማጠናቸው እርሳቸው ግን ኮንሱል ፈረንሳዊ ነው ዳኛዬ ብለው ወደ ኮንሱል ቤት ሄደው ተቀመጡ ደጃች ንጉሤ እስካሉበት ጐልዳም ድረስ ኮንሱል በመጥን ደረሱ አባ እምነቱ ከርሳቸው ጋራ ሄደው ነበሩና ወደፊት አልፈው ደጃዝማችን መከሩ ይኸውና በመኳንንቱ ቤት እየገቡ መካር እንደነበሩ ደጃዝማችም ምክራቸውን ሰምተው ኮንሱልን በታላቅ ክብር ተቀበሉ።

ዕለቱ የመስቀል በዓል ስለነበረ ሠራዊት ሁሉ በታላቅ ግባት እንደአገራችን ነገሥታት ልማድ ተሰበሰበ ሰልፍም በግራና በቀኝ ሆኖ ቆመ ኮንሱልም ያነን የደጃች ንጉሤን ነፍጥ አሲዘውት ነበርና ተኩስን ዠመሩ የተሰለፈውም ተኮሰ ነጋሪቱም እምቢልታውም መለከቱም ሳያርፍ ኮንሱል እስካዳራሹ መጡ። ደጃዝማችም ከመኳንንቶችዎ ጋራ ከዙፋንዎ ደርሰው ወደ ምድረኩ መጥተው ለኮንሱል እጅዎን

# የ እጉድ ጥር

ሰጡ። እርስዎም ወደ ዙፋንዎ ተቀመጡ። ኮንሱልንም በሌላ አልጋ አስቀመጡ። ወደዚያውም ግብር ገባ ኮንሱል ያለመዱትን ጠጅ ስለጠጡ ራሳቸው ዞረ ሲገቡ የነበረች ክብር ወደ ውርደት ተለወጠች። እነሆ አእምሮ ጠፋ። ብብርቱ መደገፍ ወደ ሰፈራቸው ገቡ።

በሌላው ቀን መገናኘት ሆነና መልክትን ከሰደድሁልህ ፩ድ ዓመት ሆነ ደግሞ መርከብ ሊመጣ ነው ብለህ ልከህልኝ ነበረ እንዴት ሆነ ብለው ጠየቁ። የኮንሱል አስተርጓሚ ልጁ ነው። አባቴ እምነቱ ባረቢኛ የደጃዝማችን ቃል ለርሱ ነገሩ እርሱም ላባቱ አሰማ። እዚህ ላይ ቃል ለቃል ያልተስማማ አለ። ተቆጡ።

አጼ ቴዎድሮስ ስናርን ካርቱምን ልቀቅ ያባቶቼ መንግሥት ነበረ አለዚያስ ሰፊ ሜዳ ይዘህ ቆየኝ ብለው ልከው ነበረ። የምስር ንጉሥ ፈርቶ አስታራቂ የምሥርን ጳጳስ ወይም በትረክ አባ ዳውድን ንጉሥ ቴዎድሮስ ሰደደ እርሱም ወደ ካርቱም ደርሶ ነበረ። `ከዚህ በኋላ ኮንሲል ለደጃዝማች ሥራ ቤቶች እንደየሹመታቸው ማዕርግ የሚሆነንን ብር በተኑ ተመሰገኑም ነገር ግን ከርሳቸው በኋላ ለሄዱት ኤሮፓውያን ይህ ጭንቅ ሆነባቸው። ኮንሱል ከደጃችማች ሲሰነባበቱ ተናግረው ነበርና አማሬ ክንፉ ያከለ ጉዛይ ሹም የቡላውዴን እንግሊዝ ኮንሱል መልክትን ይዘው ለደጃዝማች ሰደዱት እርሳቸውም ተርጉመህ አጽፈህ ስደድልኝ ብለው ወደ ገልብጠው ሰደዱላቸው። በዚህም መልክት በትግሬ ያሉ የካቶሊካውያን ሚሲዮኔር መልክተኞች ገንዘባቸውን እየሰጡ ሽፍታን አውጥተዋል። ስለዚህ ንጉሥ ሊቀጧቸው ነው። በከረን እርስዋም የቦጎስ ክፍል በምትሆን ያሉት ወንድሞቻቸው ግን እኔ እጠብቃቸዋለሁ የሚል ቃል እንደነበረበት ሰማሁ ግን ኮንሱል ብላውዴን ስንኳን በከረን ያሉትን ሚሲዮን ሊያድኑ ራሳቸውን ስንኳ አላዳኑም። ሽፍቶ የንጉሥ የወንድም የደጃዝማች ክፉን ልጅ ጋረደ የተባለው ገደላቸው ወዳጆች ናቸው። ቢሉ እውነት መናገር ነበረ በሰባኮች ይገዛሉ ይበረታሉ ማለት እጅግ ታላቅ ውሸት ነው ኮንስሉ ቢልዓርድ ከጌታ ባሮኒ የኮንሱል ቡላውዴን ምስሌነ ጋራ ጠብ ነበሩ። በሚሄዱባት ጊዜ ግን በፍቅር አድርገው አባቴ ዘካርያስ አከሡም ነብሩ። አባታችን ወደርሳቸው ፪ት ጊዜ ቢልኩ እንዲፈቱላቸው እምቢ አሉ። ስለዚህ አባታችን ባለቤትዎ ወርደው ከሐፍስ አሰወጧቸው በኮንሱል ፈቃድ ኮንሱል ከዚህ በኋላ ወዳገራቸው ሄዱ። በዚያ ጊዜ ወደ ድሆኖ ስንደርስ ተማሪ የቄስ ወልደ ሥላሴ ልጅ ተስፋይ የሚባለውን ነፍጠኛ የሚባል ደዌ ገደለው። በዚያ ጊዜ ብዙ ሰው አለቀ።

በ፫፻፷፩ ገጽ ባ፲፪ኛ ም ባ፲፰፻፶ኛ ዘመን የሆነን ነገር ይናገራል። አፄ ቴዎድሮስ ከሸዋ ዘመቻ ተመልሰው ሱባጋዲስ ካሣንና የትግሬን ባላባት ሒዱ ንጉሤን አስታገዙ ብለው ሰደድዋቸው ነገር ግን ደጃች ካሣ ብቻ ሲቀሩ ሌሎቹ ወደ ደጃች ንጉሤ ገቡ እኒኝህ ደጃች ካሣ ደጃች ውቤን ወዘን በሚባል በሰሜን አምባ ፲፫ ዓ ያህል አስረዋቸው ነበሩ። አጼ ቴዎድሮስ እርሳቸውን አሸንፈው ትትዋቸው አባታችን በጐልዓ ሳሉ ለሚስታቸው እንደችሎታዎ ረድተው ነበር። ውለታውን ረስተው በአጋጣሜ ባሉት ካቶሊካውያን በደቦ ይኩቶም ላይ ባንዲት ሌሊት ጦርን ሰደዱ ከአጋጣሜ ብዙ ካቶሊክ

# ዩ ሰኑይ ጥር

አስጨነቁ። አስካዱ። ይህም በ፺፪ኛ በ፺፫ኛ ክፍል በሌላ መጽሐፍ በግዕዝ በሰፊው ተጽፎ ይገኛል።

የደጃዝማች ንጉሠ አሽከር በኅዳር ወደ አባታችን ተልኮ እስከ ሐላይ መጣ መልክቱም እንዲህ ነበረ። አባቴ ሆይ እንዴት ነዎ ዋግሹም ገብረ መድኅን ሊገቡልኝ ናቸውና የማለብሳቸው ቀሚስ ወርቀ ዘቦ ግምጃን አስፈልገው ይስደዱልኝ ንጉሥ ቀድሞ ወርቀ ዘቦ ቀሚስ አልብሰዋቸው ነበርና እንዳይንቁኝ ብዬ ነው የኔ መናቅ የርስዎ እንዳይሆን አባቴ ሆይ አደራዎን በቶሎ ይላኩልኝ ዋጋውንም ኋላ እሰጣለሁ ብለው ጻፉልዎ። አባታችንም ለዚህ ልመና ወይም ግድን የምትመስል ናት ብለው የለኝም ማለትን ፈርተው ከመንኰሳት ጋራ ተማክረው በቤት የነበረኛ እጅግ መልካም ግምጃን አባቴ እምነቱንና እኔን ይዛችሁ ሂዱ ብለው ከመልክተኞቹ ጋር አብረን ሄንድንና ወደ ሰፈር ገብተን አለቃ ወልደ ሚካኤል ወደ ደጃዝማች ንጉሤ አገቡንና ያባታችንን መልክትና ግምጃውንም ሰጠን በነገታው አባቴ እምነቱ ለደጃዝማ ምስክርን ሰጡ።

እንግዲህ ማኅተምን ያሠሩ ወደ ፍራንስያ ቢሊኩ በረከትም ቢሰዱ መልካም ነው አልዋቸው። ምክሩም በደጃዝማች ዘንድ ስለተመሳገነ መልካም ነው ተብሎ መጣመር ኮርቻና ሌላንም በረከት እንሰዳለን አሉ። ነገር ግን ወደ ዓድዋ ልከን እስክናስመጣው ድረስ በዚህ ቆዩ አሉ አጼ ቴዎድሮስ ለአድዋ አንጥረኞች መጣመር ኮርቻን እንዲሠሩ ብርን ቀድሞ ሰጥተዋቸው ነበሩ ያንን የገኸ ለገኸ ይገባኛል ብለው አንጥረኞችን ሠርታችሁ አምጡ ቢሉዋቸው የሚቀባውን ወርቅ

ይስጡን አሉ። ነገር ግን የኛ ምክር እንደሆነ አውቀው አንጥረኞች ቶሎ ሊሠሩ አልወደዱም”። በኢትዮጵያ ጥበብ ሠሪዎችና በልዑካኑ መካከል የተፈጠረውን ተንኮል እንደሚጠባበቁ ማስተዋል ነው የጥበብ ሠራተኞች ሁሉ ተንኮላቸውን አውቀውት እንደነበር ይህ ያስረዳል እኛም ያሰናበቱን ብንል ቆዩ እያሉን ሰንቆይ ዋግሹም ገብረ መድን በኦፍላ ተያዘ አጼ ቴዎድሮስ ሰቀጣ ደረሰ የሚል ወሬ መጣ በሰፈሩም ፍርሃትና ሽብር ሆነ ደጃዝማች ከአጉዕዲ ወደ ሐውዜን ወደ ሌላውም እየተዘዋወሩ ሲቆዩ እኛም ስለዘገየን ከአባታችን የተላከ የቁጣ መልእክት ደረሰን።

ቃልዎም እንዲህ ነው እስከ ዛሬ ድረስ በሰፈር ምን ያስቀምጣችኋል ደጃዝማችስ ካቶሊክ ሳይሆን ወዴያ መልእክተኛን መስደድ እንዴት ያስባሉ ወደ ሮም ምን ብዬ ልጽፍ ነው የሚሔዱቱ መልእክተኞችስ ስንቃቸው ከወዴት ነው ብለው ጻፉልኝ አባቴ እምነቱ አባታችን እንዲህ ካሉ ትተን እንሂድ አሉ እኔ ግን እጅግ ተስፋ ነበረኝና የሚሆን መስሎኝ በፊት ወደ አባታችን ልሂድ ሁሉንም ነግሬዎ አይሆንም ቢሉ ይምጡ ብዬ እልክብዎአለሁ ቢሰሙኝ ግን ተመልሼ እመጣለሁ ብዬ በማርያም ሸዊቶ ከሰፈሩ በኋውላ ደጃዝማችን ተሰናብቸ ወደ ሐላይ ሄድሁ ካባታችን ጋራ ተገናኘሁና ጠየቁኝ እኔም ንጉሤ እርስዎን እንዲወዱ ካቶሊክ ሃይማኖትንም እንዳመሰገኑ መኳንንቶቻቸው ግን እኛን እንደ ጠሉን በዚህም ምክንያት እንዳይከዱዋቸው ፍራት እንዳለባቸው መምር ወርቁና ሌሎችም የውስጥ አሽከሮች ነገሩን ካቶሊክ ነኝ ብለው ይግለጡ ብንላቸው አይሆንልኝም እፈረአልሁ ሲሉኝ ነው። ቢያደርጉም ሁሉም ፩ ሳይቀር

## ዩ ሠሉስ

# ፲፩ኛ ክፍል የካቲት

ሊነሣባቸው ነው። እኛንም በዚያ በመታየታችን ለመኳንንቱ ይልቁንም ለናታቸው ወገኖች ለጃናሞችና ለመነኰሳት መምራን ነነ ለሚሉትም ከብደናቸዋል። ከኛም ፩ድ ቁም ነገር አላገኘንም እነሆ ከኮንሱል ጋራ ከተገናኙ መርከብ ይመጣል እንዲሁም ይሆናል ካልዋቸው ወደ ፲ ወር ይሆናል። እስቲ ያለ ፩ድ ነገር ሃይማኖትዎን ይግለጡ ማለት አይሰሙንም እንኪያስ አይሆንም ቢሉ ግን እኔ እቀራለሁ። አባቴ እምነቱ እንዲመጡ እንላክባቸው አልሁዎ።

አስበው አባታችን ይህንን የስለት ቃልን አንብብላቸው እሺ ቢሉ እኔም እንደ ችሎቴ ለሚሄደው ለነ ሰው ስንቅን እሰጣለሁ።

ለራሳቸው ሰው ግን ባለቤታቸው እንዲአስቡበት ንገር። ዳግመኛም ወንድማቸውን ወይም ቅርብ ዘመዳቸውን እንዲሰዱ ንገር ይህን ሁሉ ግን አይሆንም ቢሉ ዝም ብላችሁ ኑ አሉኝ።

የሥዕለቱም ቃል እንደዚህ ነው ብፅዓት ዘገብረ ንጉሠ ኢትዮጵያ ንጉሤ ተፈትነው ለብሔረ ሮማ ከመ ትንበር ዲበ መቃብሪሆሙ ለቅዱስ ጴጥሮስ ወለቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያት አሜን።

ከመ ይቤሎ እግዚእነ ቀዳሚ ለቆስጠንጢኖስ እንዘ ሃሎ በሥርዓት አሕዛብ እንዘ ያርእዮ ትእምርተ መስቀል ትመውዕ ጸላዕተ በዝንቱ ትእምርተ መስቀል።

ሊተኒ ይቤሉኒ ዮም ላእካኒሁ ለርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘሮም ፒዮስ ተስአዊ በስም ዘፈነዎሙ ውስተ ብሔር እንዘ ይብሉ አንትሂ ትመውዕ አጽራረከ በስመ አምላከ ፒዮስ ወጴጥሮስ ወጳውሎስ ወበእንተ አነ ንጉሤ ገበርኩ ብጽዓተ እንዘ እመ ይሁበኒ አምላከ ፒዮስ መዊዓ በዲበ ጸላዕትየ ወያጸንዕ መንግሥትየ እትዌከፍ ፍጡነ ሃይማኖ ካቶሊክ ሐዋርያዊ ወሮማዊተ ወአአቅብ እስከ ጊዜ ሞትየ ናሁ አነ ንጉሤ ገብርኩ ዘንተ ብዓፅተ በቅድመ ቅድስት ሥላሴ ወበቅድመ ድንግል ማርያም እንተ አልባቲ ኃጢአተ አዳም። ወበቅድሜሆሙ ለቅዱሳን ሐዋርያት ጴጥሮስ ወጳውሎስ

ወአነብራ ላዛቲ ክርታስ ብፅዓትየ መልዕልተ መቃብሩ ለጴጥሮስ እንዘ ሀሎ በመንበሩ ቅዱስ ፒዮስ አቡሆሙ ለኵሎሙ ምዕመናን። ነገር ግን ባማርኛ ናት ተጽፋ የነበረች ፪ኛይቱም የሰላምታ መልዕክት ነበረች ቃልዋም ቃሌን ካባ ተክለ ሃይማኖት ይሰማሉ ትላለች።

ከሐላይ ተመልሼ በማርያም ሸዊቶ በተውኳቸው ሰፈር አገኘኋቸው። አባቴ እምነቱና እኔ ወደ ደጃዝማች ገባነ እርስዎና አለቃ ወይም ሊቀ ካህናት ገብረ ሚካኤል ሳሉ በፊት የሰላምታውን የምከሩንም ቃል ሰጠሁ አሰማሁም ከዚህ በኋላም የሥዕለቱን ወረቀት አነበብሁላቸው እሺ አሉ። አለቃ ገብረ ሚካኤል ባለመውደድ ይመስለኛል ወይም ነገሩን ለማጠንከር አስተውለውታልን አልዋቸው። እርስዎም አዎን አስተውየዋለሁ ብለው መለሱ።

ኰርቻው ተሠርቶ መጣ ነገር ግን በዚህ ጊዜ በ፩፻፫ ቁጥር እንደ ተናገርሁት ጐበዜ መንገሻ ደጃች ካሣና ባልጋዲ ማሩ ተዋግተውት ተሻረ ወይም ሞተ። ደጃች ካሣም መላሱን አስወጥተው ንጉሥ ቴዎድሮስን ደስ እንዲያሰኙ እስከ መቅደላ ሰደዱዋቸው እንግዲስ

# ያ ረቡዕ የካቲት

ይህ መርዶ ወደ ደጃች ንጉሤ ስለደረሰ በማዘን በመናደድ ሆኑ። የኛን ምክር ረሱ ከዚህም ተነስተው ወደ ገንደብታ ወጥተው ሰፈሩ። ከዚያም ወደ እንደርታና ወደ ተምቤን ተመለሱ በዚህ ጊዜ እኛ ያሰናበቱን ብለን ተናገርን እርሳቸውም ሒዱ እለፉ እኔም እመጣለሁ በጕራዕ ልሰፍር ነኝና ነገሩን በዚያ እናደርገዋለን ብለው አሰናበቱን ከሐላይ በጐንደር ወጣና በሐምሌ ወደ እርሳቸው ተመለስን ደጃዝማች እንደ አሉት ከፍቃዳ መጥተው በጐራዕ ሰፈሩ ከዚህ በፊት ወደ ከሌ የተባለ አልገባም ነበርና ከድግሶች በቀር ሁሉም ገባልዎ በሰፈር ሳለነ ካባቴ እምነቱና ከኔ ጋራ የተጫወቱ ፪ት መምህራን አሣፍ ወልደ ሥላሴና ሁለት የውስጥ አሽከሮች በፍልሰታ በዓል ወደ ሒቦ መጡ። መልካም ሥራትን አይተው ሃይማኖታችንን እንዲአመሰግኑ ቢቀቡ መልካም በሆነ ነበር ብለን ነግረንዎ ነበር። እርስዎ ግን ዑደት በሆነ ግዜ በምስለ ፍቁር ወልዳ ላይ ፀሐይ እንዳይወድቅባት እንዳንድ አሽከር ሆነው ድባብን ያዥ ሆኑ

ከዑደት በኋላ ግን ሜሮንን እንዲቀቡ የሹመትዎን ልብስ ለብሰው ሜትራ የተባለውን ደፍተው እንዲቀቡ ሲቀቡ መቋቋሚያዎንም ይዘው ሲሰብኩ ባዩ ጊዜ እጅግ አደነፍፋ ዳግመኛም ያን ያህል ሰው ቅዳሴን በመስማት በፀጥታ እስኪጨረስ ድረስ ከ፪ቱም የውስጥ አሽከሮች ፩ዱ ችኩሉ የሚበላው ሌላውን አፍለኝ የሚባለውን እንዲህ አለው እንግዲህ ከዚህ መውጣት አይገባንም በዚህ እንኑር ባልንጀራው ግን አይቻለንም አለው አሣፍ ወልደ ሥላሴ ካቶሊክ ሃይማኖት መልካም ናት እያሉ ሳይፈሩ ሳያፍሩም በመኳንንትም በካህናቱም ፊት በሰፈሩ ገልጠው ሲናገሩ ነበሩ በ፻፶-ቁጥር እንደተጻፈው መዓሥርቶች ከካህናታቸው ጋራ ሲከዱ አቃጽኖች በካቶሊክ ሃይማኖት ጸንተው ቀሩ። ቤተ ክርስቲያንም ባዑንና በደጃች ውቤ መኳንንቶች ምክንያት በመፍራት ለመዓሥርቶች ሁና ነበረች። እንዲህ በላይ እንንዳልሁ መድኔ ቃለ አጤ ተቀብሎ መጥቶ ቢያሰማቸው አንሰማም አሉ። ቀሳውስቶች ቃለ አጤውን ይዘው ወደ ቤታቸው ሄዱ ዳኘኝ እንዳሉህ አያይዘህ ውሰደኝ አለው ዳግመኛውም ተዳኙ ብሎ ቢይዛቸው ጨኸት ሆነ መዓሥርቲ መሣሪያቸውን ይዘው ወጥተው መድኃኔንና ቃለአጤን አጐሳቁለው አቃጽኖችም ይህንን ሰምተው ጨኸትና መታወክን አደረጉ መሣሪያቸውንም እየነጠቁ ወጡ መዓሥርቶች ወዳሉበት ሄዱ ሊጋደሉ ተቃርበው ሳሉ አባታችንና ወንድሞች በመካከል ገብተው ገላገሉ።

የደጃዝማች አሽከርም የተባለውን እንዳይናገር ይህም ሌስብከት ዕንቅፋት እንዳይሆን ብለው ቁጥሩን አላውቅም እንጂ ብርን ሰጡት) ይህንም ረቂቅ ተንኮል ማስተዋል ነው (ደግሞ ድግሦች አባታችንን ሲገሉ እንደወደዱ ተቸገረ አባታችን ግን ስለነዚህ ምሕረትን ሊአደርጉላቸው ወደዱ። ካጼ ቴዎድሮስ ጋራ ያሉትን ከንቲባ ዘርዓይን ተስፋ

አድርገው ሁሉ ሲገባ አንገባም ብለው አገራቸውን አስጠፉ። አባታችን ከሐላይ መጥተው ከደጃዝማች ንጉሤ ጋራ ተገናኙ። በመዠመሪያ ባለቃ ገብረ ሚካኤል ድንኳን ገቡ ደጃዝማችም ጠጅንና ፍሪዳውን ሰደዱ። በኋላም መጥተው ተገናኙ ሲገቡም ተላብሰው እጅ ነሡ። አባታችን ቁመው ቆዩአቸው በነጋታውም መጥተው ሰን አስወግደው ይምከሩኝ አሉ። አባታችን ከሁሉ የምትበልጥ ነገር መንግሥትን የምታጠነክርና እግዜርን መፍራት እውነትን መጠበቅ ናት። የስሜን ነጋሪት

## ፱ ኃሙስ የካቲት

እስከ ፲ኛ ትውልድ ወረደ ይባላል። ከደጃች ውቤ ግን እንሆ ለሌላ ተሰጠች ምነው ቢሉ ካቶሊካዊ ሃይማኖትን እንደርስዎ አድርጎ መርምሮ ያውቃት አልነበረም። ቢሆንም አውቀዋት ስላኡ እንደሚገባ አላደረጉም። ስለዚህ ተሸነፉ። አሁንም እርስዎ በውነተኛ ቢጽኑ እግዜር ከርስዎ ጋራ ይሆናል ሌላውንም መልካም ነገር መከርዋቸው ከዚህ በኋላ ይባርኩኝ አቡነ ዘበሰማያት ይስጡኝ ብለው ተባረኩ። አባታችንም ወደቤትዎ ከተመለሱ በኋላ ደጃዝማች ባሕርን አያለሁ ብለው ሊመጡ መከረው ሳሉ ደጃች መርድ አገራቸውን ሾሙዋቸው። ወደ ሐማሴን መጥተው ነበሩ። ነገር ግን ደጃች ኃይሉ ያጼ ቴዎድሮስ ነበሩና በፊት ሸሹ ኋላ ግን ደጃች ንጉሤ ሩቅ መሆናቸውን ሲሰሙ ከሸሹበት ተመለሱ። ስለዚህ ደጃች መርዕድ በዚህ ቀን ካልረዱኝ ጠፋሁ ብለው ወደ ደጃች ንጉሤ ላኩ። እርስዎ ከድግሳ ገሥግሠው ወደ ማታ በድንገት ጸዓዘጋ ደርሰው ደጃች ኃይሉን መቱ።

እርሳቸው አመለጡ ልጃቸው አቶ ተስፋ ጽዮን የደጃች ንጉሤን ወልደ ጊዮርጊስ ኃይሉ የሚባል ስለሞቱ ተይዘው ተደበደቡ። ከዚህ በኋላ መረብ ምላሽ ለደጃች ንጉሤ ተገዛች። ከድግሳ ገሥግሠው በኋላ ሪዞ የሚባለው ኢጣልያ በምጽዋ ነጋዴ ነበረ። ወዳባታችን መጥቶ ወደ ደጃች ንጉሤ ልሄድ መጥቼአለሁና አባ እምነቱን እንዲአገናኙኝ ይዘዙልኝ ብሎ ለመነ። አባታችንም እሽ አሉ።

በዚህም ጊዜ እኛ ፰ ወር የደከምንበት ነገር ባይቀር መልካም ነበር። እነሆ አባቴ እምነቱን አሁን ከሄዱ ለደጃዝማች ቢነግሩ መልካም ነው ብየ ላባታችን ነገርኩ። ስለዚህ ከሐላይ ተነሥተው ወደ ሐማሴን ደርሰው በመልካም ተገናኙዋቸው አባቴ እምነቱ ስለነገሩኝ አባታችንም ደስ ለማሰኜት ለጊዜው አስመራ ሹመት ሰጥተው አባቴ እምነቱም ስለተዠመረው ነገር መልካም ነው ብለው የሚሄደውን ሁሉ አቅርበው ጣቃዬ የሚባለው ያክስትዎን ልጅ ሂድ ብለው ሰደዱዋቸው። ነገር ግን እናባቴ እምነቱ ወደ ሐላይ በተመለሰ ጊዜ አባታችንን አላገኙዋቸውም።

ባባቴ ዘካርያስ መታሰር ምክንያት ወደ ምጽዋ ወርደው ነበሩና ከደጃዝማች የሰሙትን የተቀበሉትን ነገር ላባታችን ነገሩ ሰጡም። መልክትም እንዲህ የምትል ሰጡ በፊት እንዳልሁዎ እነሆ ሰድጃለሁ ወደዚያው የሚሄድ መልክትም እርስዎ እንደሚያምር አድርገው በኔ ስም ይጻፉልኝ ማኅተሜንም ሰድጀለዎታለሁ እንዲአትሙት ትላለች። ስለዚህ አባታችን ወደርዕሰ ሊቀ ጳጳሳትና ወድ ፍራንሲያን ንጉሠ ነገሥት ናፖሊዮን የሚያደርሱትን መልክታት አጽፈው ወደ ቋንቋቸው ገለበጡ ፩ዱትም ይህች ናት መልእክት ዘተፈንዎት እምንጉሠ ኢትዮጵያ ንጉሤ ኀበ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፒዮስ እንተ ሮማ ተጽሕፈት አመ ፲ ለጥቅምት እምልደተ እግዚእነ በ፲፻፹፻፶፮ በሐሳበ ኢትዮጵያ

ኦ አብ ክቡር ወቅዱስ ሶበ ተራከብነ ምስለ ኤጲስ ቆጶስ ያዕቆብ ወልድከ ወምስለ ቀሳውስትሂ እምስሌሁ ሰሚዕየ ነገረ ሃይማኖት ካቶሊካዊት ወዜና ዚአከ ሠናይት ወእመጽሐፈ ዚአነሂ ፍትሐ ነገሥት ዘየዓቢ እምካልዓን መጻሕፍተ ሊቃውንት ዘይቤ ወይኩን ሊቀ እምኔሆሙ ወመኰንነ በላዕለ ጴጥሮስ ዘሮም በከመ አዘዙ ሐዋሪያት ወሊቀ ጳጳሳት ከመ አብ በሥልጣኑ ላዕለ ውሉዱ ወበከመ ለሊቀ ጳጳሳት በትእዛዝ ወሥልጣን ላዕለ ዛታሕተ እዴሁ ከማሁ በአለ ለመንበረ ሮምያ ቦቱ ሥልጣን ላዕለ ሊቃነ ጳጳሳት እስመ

# ይ ዓርብ የካቲት

ውእቱ ሊቅ ከመ ጴጥሮስ ዘኮነ ሎቱ ሥልጣን ላዕለ ኵሎሙ ሊቃነ ክርስቲያን ወማኅበረ ሰብዕ እስመ ውእቱ ህየንተ ክርስቶስ እግዚእነ ላዕለ ሕዝቡ ወአብያተ ክርስቲያናቲሁ ወዘለዓለወ ዘንተ ሕገ እንተ ሠራዕናሃ ሲኖዶስ ያወግዞ አፍቀርኩ አነሂ ርእየ ምስሌሆሙ በሃይማኖት ወባሕቱ ከመ ኢይኩን ሀከከ ወጋዕዝ ውስተ ምኵናንየ በምክንያተ ሃይማኖት እጸንህ እክሰ ያጸንዕ ወያረትዕ መንግሥትየ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወዕስዕል እምኅቤከ ኦ አብ ክቡር ወልዑል ከመ ተአዝዝ ትንበር ለመልዕክተ ብፅዕት ዘፈነውክዋ ምስለ ዛቲ መልዕክት በላዕለ መቃብሪሁ ለቅዱስ ጴጥሮስ ከመ ያፈጽመኒ መሐላዬ ወበእንተ ዓቂቦቶሙ ለካቶሊካውያን ምስለ አብያቲሆሙስ ድልው አነ እምአመ ኰነንኩ ምድረ ትግሬ እስከ ይዕዜ ወእምይዕዜኒ አዓቅቦሙ በኵሉ ነገር ዘይትከሃለኒ ወባሕቱ ጸሊ በእንቲአየ ከመ እግዚአብ ይግበር ዘንተ ሕሊና ልብየ ወናሁ ፈነውክዎ ለወልደ እኅተ እም ኀበ ገጸ መበርከ ቅድስት ከመ ይሳልም ህይንቴየ እግረ ዚአከ።

ወእምድኅረዝ ኦ አቡየ ክቡር እስእለከ ትግበር ሊተ ከመ ይብጻሕ ኀበ ንጉሠ ነገሥት ናፖሊዮን ወካዕበ እስእለከ ከመ ታስተፋቅረኒ ምስለ ኵሎሙ ነገሥታት አውሮፓ ዘየኅብሩ ምስሌከ በሃይማኖት ወለከሂ ኀቤየ እመ ብከ ግብር ዘትፈቅድ እስመ እገብር በፍሥሐ ወበፍቅር ለእመኒ በዝኁ ጸላእትየ ብየ ተስፋ ከመ እከይዶሙ በኃይለ ጸሎትየ ወእመ ይከውን ዓዲ ፈቃዱ ለእግዚእነ ብየ ተስፋ ከመ እንግሥ በቅብዓ መንግሥት በከመ ሥርዓተ ካቶሊካውያን

የሀበ እግዚአብሔር ኪያከ ለነዋህ መዋዕል ለዓለመ ዓለም። ፪ኛይቱ ያች የብፅአት መልእክት ነበረች ፫ኛይቱም ይህች ናት መልዕክት ዘተፈነወት እምኀበ ንጉሠ ኢትዮጵያ ንጉሤ ኀበ ንጉሠ ነገሥት ናፖሊዮን ተጽሕፈት እምልደተ እግዚእነ አመ፲ ለጥቅምት ፲፰፻፶፩ በርስዎና በበታችዎ ላሉ መሳፍንት ሠራዊቶዎ ሁሉ ሰላም እላለሁ የርስዎ ታላቅነትና በጐነት ከአቡነ ያዕቆብ ሰዎች የልቤን አሳብ እንዲነግርዎ ከዚች መልእክት ጋር ቅርብ ዘመዴን ጣቃዬንና መምር እምነቱን ወደርስዎ ሰድጃለሁ። ቀድሞም ጠላትን በርቶብኛልና ይግዙልኝ ብዬ በምጽዋ በነበረ ኮንስልዎ እጅ መልእክትን ሰድጄልዎ ነበር። እስካሁን ምላሽን አላገኘሁም። ነገር ግን እርሱ የርስዎን መልእክት አድርጐ ወደ አገራችን በመጣ ጊዜ ከርስዎ ጋር የተገናኘሁ መስሎኝ እጅግ ደስ አለኝ አሁንም ለርስዎ እንዲህ እላለሁ ኢትዮጵያ ከብዙ ዘመን ዠምሮ በመልካም ነገር ሁሉ ወድቃለችና የርስዎ እጅ ካልተጨመረ በኔ ብቻ ላነሳት አይቻልምና ኃይለኛዪቱን እጅዎን ፈጥነው እንዲዘረጉልኝ አለምንዎታለሁ።

አገራችን በሃይማኖት በ፫ ወን ስለተከፈለች ቋረኛ ካሣ እንደ አሕዛብ ሥራት በግድ ወደ ሃይማኖታቸው አስለወጡት። ይህንንም የማይገባን ነገር አይቶ እርሱን ለማፍረስ ለመከልከልም እግዜርን አምኜ በድንግል ማርያም አማላጅነት በወዳጆቼም ጸልቶ በርሱ ላይ ተነሳሁ። ስለዚህ በጥቂት ጦር የርሳቸውን ሹማንት ፯ት ጊዜ ድልን አድርጌ ያጐቴን መንግሥት ይዣለሁ በኔም ግዛት ለመንግሥትዎ የሚጠቅም የንግድ ሥራ ወይም በሌላ እንዳለ እኔ አላውቅምና ፩ድ አዋቂ ሰው ቢሰዱልኝ የምችል ብሆን ይንገረኝ አደርጋለሁ። አቡነ ያዕቆብን ከምዕመናኖችዎ ጋራ ከመጠበቅ በተቀር አሁን ለርስዎ የማቀርበው

# ዮ ቀዳም የካቲት

ገጸ በረከት አላገኘሁም ግን ይህችን መልክት የሚሰጥዎ መምሬ እምነቱና ጣቃዬ የነ መሆናቸውን እንዲያውቁልኝ ፩ድ መጣመር ኮርቻ ፩ድ ቢተዋ ፩ድ ሾተል ፩ድ ያንበሳ ለምድ ሰድጃለሁና ለጣቃዬ ከደጃዝማች የተሰጠ ፻፺ ብር ይመስለኛል ላባቴ እምነቱና ለፈረንሳዩ አስተርጓሚ አባታችን የሰጡት ስንቅ ቁጥሩን ረስቻለሁ የነፍጥ መግዣ ብለው ፬፻ ብር ሰደው ነበር። በእስላም ጀልባ ተጭነው ወደ ጅዳ በደረሱ ጊዜ ኮናስሎችና የገደሉትን በደለኞች ለመቀበል

መርከቦች አገኙ የእስክርንድርያ ኮንሱል ጄኔራል ሳፒቶ የሚባሉት በዚያ ስለተገኙ በርሳቸው ትእዛዝና እርዳታ በፈረንሳዊ የእሳት መርከብ አግብተው ወደ ስዊስ ያስደረሷቸው ይመስለኛል።

ከዚህ በኋላ በደህና ወደ ሮም ደረሱ። አባቴና እምነቱ ወደ ኤውሮፓ ከሄዱ በኋላ የሆነ ነገር ይናገራል።

አባ ልዮን ደዘባንሽ ያቡነ ማስያስ ወገን በዚያ በምንሉ ባባታችን ቤት ነበሩ።

ካርዲናል በርናቦም ስለርሳቸው ነገር ወደ አባታችን ጽፈው ነበር። እንደዚህ ሲሉ ቢሆንልዎ እሰከ አቡነ ማስያስ ድረስ እንዲአገናኙአቸው። ባይሆን ግን እንዲጠብቃቸው ልከውባቸው ነበር። እናባቴ እምነቱ ከሄዱ በኋላ በጥር ይመስለኛል።

እርሳቸውን ከደጃች ንጉሤ ጋራ ለማገናኘት አባታችን እኔን ሰደዱኝ ወደ አሥመራ በደረሰኝ ጊዜ በ፻፫፻፪ ቁ እንዳልሁ ሪዞ ያን አገር የተሾመ ነበርና በመልካም ተቀበለን ከርሳቸውም ጋራ ዮሐንስ የሚባል ፩ድ ነጋዴ ጽርዓዊ ነበረ ወደ አሥመራ በደረሰነ ጊዜ ሪዞ ወደ ምጽዋ ሊወርድ የነበረ ካባ ልዮን የዘበንሽ ጋራ ተማክረው ወደ ደጃች ንጉሤ ሊሄዱ ባንድ ተነሣ። እርሳቸውም በዕዳ መጣዕ ሰፍረው ነበሩ። ወደዚያ በደረሰን ጊዜ ደጃዝማች ንጉሤ ስላባታችን መልክት በፍቅር ተቀበልዋቸው። የመልክቱም ቃል አይነተኛ ነገር እነዚህ መነኰሴ ከሮም ተልከው የመጡ ወዳቡነ ማሳያ ወደ ጋላ የሚሄዱ ናቸውና እስከ ጐንደር እንዲሰዱልኝ ለደጃች ውቤም ወደ ታሡሩበት አምባ እርስዎ ባወቁት ፳፫ ብርን እነሆ ይሰደዱልኝ ማለት ነበር)። “ከደጃች ውቤ ሚሲዮኖች ሥራ እንደነበራቸው ይህ ያስረዳል።

“ደጃዝማች እሽ እስከ ወንድሜ እሰዳቸዋለሁ። አሉኝ። ከዚህ በኋላ አባ ልዮን ለደጃዝማች የምናገረው ምሥጢር አለኝና ውጣልኝ አሉኝ ወጣሁላቸው። እርሳቸውም ለሪዞ እርሱም ባረብኛ ቋንቋ ሎሌውም ለደጃዝማች አስተረጐመ። በዚያ ዘመን ካውሮ የሚባል የኢጣልያ የፒዮንቴ ንጉሥ ብላንቴን ጌታ የሮም ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳትን መንግሥት ሊያፈርስ የሚፈልግ ነበረ። አባ ልዮን የርሱን መልክት አምጥተው ለደጃዝማች ሰጡ። ደጃዝማችም ባስተርጓሚ የሰጡትን ቃል አባ ልዮንን ባማርኛ አጽፉ አሏቸው።

በዚያ ጊዜ እኔን ውጣልኝ ማለታቸው ምሥጢሩን ላባታችን እንዳልነግርባቸው ነበረ። ግን ያነን መልክት ባማሬ ክንፍና ባባቴ ዮሴፍ መጻፍ መሆኑን አይተው እኔን አስጠሩኛ በዚሁም መልክት ፱ኝ ወይም ፲ የውል ነገሮች ነበሩበት። ከነዚህም ፩ዱ ኮንስልን እንዲቀበሉ

# ደ እኁድ የካቲት

እርሳቸውም ኮንስል መስደድን ቢወዱ ቢክቶር አማኑኤል እንዲቀበሉ ውሉም እስከዚህ ዘመን ድረስ እንድንል። ያ ግን ሲፈጸም ብንወድ እንጨምራለን ባንወድ ግን እንተዋለን የሚል ነበር።

ደጃዝማች እናባቴ እምነቱ የሄዱበትን የማያፈርስብኝ ከሆነ መልካም ነው አሉ። የመልክቱን ቃል አጻፉ። አባ ልዮን በቋንቋቸው ገልብጠው ለሪዞ ሰጡት። እርሱም ወደ አደን ወደ ወንድማቸው ሰደደው ነገር ግን እንግሊዞች አይተውት ባደን የነበረን ካፑችንን በዚህ ምክንያት ካደን አስለቀቁት።

ፕሮፓጋንዳም ሰምተው እንዴት ከቤተ ክርስቲያን ከጠላት ጋራ ፍቅር አድርጎ ተላላኪ ሆነ ብለው በአባ ልዮን አዘኑባቸው። ሪዞ የተሾመውን አገር ለካውር አሳልፎ ሊሰጥ ካባ ልዮን ጋራ እንደተዋዋሉ ሰምቶ ዳግመኛ አባ ልዮን ከጌታ ባሮኒ እንግሊዝ ኮንሲል ምስለኔ ጋራ ወዳጅ ነበሩ። እርሳቸው አጼ ቴዎድሮስ ወደ ጋላ ማለፍን እንዳይከለክሏቸው ስለዚህ ንጉሡ በመልካም ተቀበሉኝ ንጉሤ ንጉሥ አይደለም ብለው ሌላም ብዙ ነገር ጽፈው አባታችንን አባይ ለማድረግ

ወደ ኤሮፓ ጻፉ። በሚባል ወረቀት ታትሞ ተነበበ። ካባ ልዮን ጋራ ፳ት ወይም ፺ት ጭነት በኃላ ቤት ዕቃ ነበረ። ወደ አባ መጣዕ ሳሉ ያድዋው ነጋድራስ በዚያ ነበርና እቀርጣለሁ አለ።

አባ ልዮን ግን የጌታ ባሮኒን ምክር ለመፈጸም የተደረገላቸውን በጉነት ረስተው አባታችንን ለማሳበል ሽፍታ ነው ብለው ጻፉ። ነገር ግን ያደረጉትን ውል ወደ ቢክቶር አማኑኤል ንጉሥ ንጉሤ ብለው የጻፉትን ስለረሱ ወይም ስለዋሹ ይመስለኛል።

በ፲፻ ቁጥር እንደተጻፈው ደጃዝማች ካሣ የቋረኛ የወልደ ጊወርጊስ ኃይሉ ልጅ ከጌታቸው ከራስ አሊ ሸፍተው እርሳቸውን አሸንፈው ደጃዝማች ውቤንም ደግመው አጼ ቴዎድሮስ እንደተባሉ በነገሡ በ፫ኛው ወር ውጊያ ቆስለው የነበሩ ልጅ ንጉሤ ያጐቴን መንግሥት ለባዕድ አልሰጥም በማለት እንደተነሱ እንደ አጐታቸውም ትግሬንና እስከ ጐንደር ዳርቻ እንደገዙ ሁሉ ክርክር የሌለበት ነው እንደ ደጃች ንጉሤም የጐጃሙ ደጃች ተድላ የጋላም በሽር አመዴና ብዙ እንደተዋጉ ሁሉ ያወቀው ታሪክ ነው።

እርሳቸውም ራሳቸው አጼ ቴዎድሮስ የቀድሞውን ዘመን ታሪክ ስለአወቁ ንጉሥ መባልን ፈርተው ነበር። አቡነ ሰላማ ናቸው ንገሥ ብለው ያነገሱዋቸው አባቴ እምነቱ ወደ ሮም በደረሱ ጊዜ ከካርዲናል በርናቦ ጋራ ስፒቶ እንዲያገኙዋቸው እርሳቸው ወደ አገራችን ካቡነ ያዕቆብ በፊት መጥተው የነበሩቱ ዮሴፍን እንዳሉ ሰምተው የነበሩና ከርሳቸውም ጋራ ይተዋወቁ የነበሩና አስፈለጉዋቸ። አናባቱ እምነቱ ከርሳቸውም ጋራ ይተዋወቁ የነበሩና አስፈለጉዋቸው። እናባቱ እምነቱ ሳይነሱ አስቀድመው ልከው ነበርና ፕሮፓጋንዳ አለቃ ካርዲናል በርናቦም ስለአባታቸው መልክት በመልካም ተቀበሏቸው።

የኢየሱስ ክርስቶስ ምስለኔ ለኢትዮጵያም ማረፊያ እንዲሆን በሮምያ ያለን የቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን ገዳምን ባጼ ዘርዓ

# ዱ ሰኑይ የካቲት

ያዕቆብ ዘመን ይመስለኛል ሰጥተዋልና) የሐሰታቸው ብዛት ነው እንጂ ባፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን ካቶሊካውያን ኢትዮጵያን አስረገጡም። መልክተኞችን አገቡዋቸው።

“ከዚህም በኋላ አስተርጓሚአቸው ሳፒቶንን አደረጉላቸው የወሰዱት አስተርጓሚው ሳይሰማቸው ስለቀረ። አባቴ እምነቱም ካረቢኛ በስተቀር ኢጣልያና ያውሮፕ ቋንቋ አያውቁም ነበርና ካርዲናል በርናቦ ባለማወቃቸው አዘኑ።

ከዚህም በኋላ አባቴ እምንቱ ይህን መልእክት ወደ አባታችን ጻፉ። ተጽፈውት አመ ፳ ወ ፱ ለየካቲት ሰኑይ በ፲ ወ፰ ፻ ፺ ወ፩ ዓ.ም ኦ አቡየ ክቡር በኵሉ ወሐዋርያ ያዕቆብ ሰላም ለከ ሰላመ እግዚአብ ወፍቅራ ለእግዝእትነ የሃሉ ምስሌከ ከጅዳ እስከ ሰዊስ በደህና መድረሳችንን ጽፌ እንዲደርስዎ በፈረንሳዊ መርከብ ሰጥቼ ነበርኩ። ከስዊዝ ወደ እስክንድርያ ኮንሱል ጄኔራል ሳፒቶ በደህና አደረሱ። ወደ ላዛሪስት ቤት ገባነ።

፫ት ሌሊት በዚያው አደርነ ኮንሱል ቢነግሩአቸው ነው። የተረዱ አቡነ ፔርፒቶም በመንገድ አገኘኋቸው መልክቱንም ኮንሱል ጄኔራል ከእስክንድርያ እሰከ ሲቢታኬያ እስክንድር ለመርከቡ ዋጋን ሰጡልን። ለምግባችን ግን እኛ ከፈለን። በየካቲት በ፪ኛ ሌሊት ወደ ሮም ደረሰን በእንግዳ ቤት አደረነ። በነጋውም አቡነ ዮሴፍን ስናስፈልግ ዋለነ። አላገኘናቸውም። ለጥሩስን ይጀ ወደ ፕሮፓጋንዳ ሄዱ ወረቀቱንም ለካርዲናል በርናቦ ሰጠሁዎ በመልካም ፊት ተቀበሉነ። አቡነ ዮሴፍን አስፈልጌ እስከሰደው ድረስ በዚያ ባላችሁበት ቆዩ አሉነ ከዚያም ወጥተን ወደ ላዛሪስት የማኅበር ቤት ገባነ። የአቡነ ዮሐንስን ወረቀት ሰጠነ አቡነ ዮሴፍን አስፈልጉልነ አልነ። እነዚያም ፈልገው አመጡልነ

እጅግ ደስ አለኝ። ሁለታችን ወደ ካርዲናል ሄደነ። ምግብንም ልብስንም ስፍራንም እንደ እውቀትህ አድርግላቸው አሉ። ሁሉንም አደረጉልን የምነግርዎ ጉዳይ አለኝ ብልዎ በወረቀት ጽፈው አቡነ ሳፒቶ በኢጣልያ ቋንቋ ገልብጠው ይሰጡኛል አሉኝ። ሊታተሙ የወሰዷቸው መጻሕፍቶች ለርሳቸው ስጥ አሉኝ ሰጠሁ።

እንዳሉኝም ቃሉን ጻፍሑ እርሳቸው አሳምረው ገለበጡት። ካርዲናሎችና ጉባኤም ፓፓም ሁሉ አመሰገኑት። አቡነ ዮሴፍ ከሁሉ ታላላቆች ጋራ አገናኙኝ። ብልሃቱን ያውቁበታልና እርሳቸውን ባናገኝ ይቸገረን ነበር። የተገናኘናቸው ታላላቅ ሰዎች ነገራችንን አመሰገኑት።

ብፁዕ ፓፓም መልክተኞች ከሳፒቶ ጋራ ይምጡ እገናኛለሁ ብለዋል ልጅ ጣቃዬ እንደወታደር ለብሶ ቢተዋውን አግብቶ አንበ ለምዱን ለብሶ ሾተሉንም ታጥቆ ነበር እኔም እንዳገራችን ቄስ ጋብርም (ሎሌ) እንደ ትርኩ ለብሳን ገባነ ተምበርከንም እግርዎን ሳምነ አቡነ ዮሴፍ በፊታችን ሆነው ወረቀቱን ሰጡ በመልካም ተቀበሉነ የሃማኖት ነገር ቢሆን ነው እኔን የሰደዱኝ

ንጉሥ ንጉሤም ይህንን መልእክት ከቅዱስ ፓፓ እግር ታች ልናኖር ሰደዱነ

የሥዕለቲቱም መልእክት በማይጠፋ አስደርገው ትሰቅልልኝ ብለው አልሁ።

# ዲ ሠሉስ የካቲት

አቡነ ዮሴፍንም ላስተርጓሚነት ወደ ፓሪስ እንዲሰጡን ለመንሁ በመልካምም እንዲቀበሉን ወረቀትን እንዲሰዱልኝ ለመንሁ የጐንደሩን ቤታችንንም ፕሮቴስታን እንደገባበት ተናገርሁ አቡነ ዮሴፍም እንግዲህ ኢትዮጵያ ከ፫ቱ ወገን ወደ ፩ዱ ሳትሆን አትቀርም እነዚህም ካቶሊክና ፕሮቴስታንት እስላሞች ናቸው ብለው ተናገሩ። ቅዱስ ፓፓም ስለጐንደሩ ቤት የሚያያስደርጉትን ፈሪሳውያን ያውቃሉ ያውቃሉ እጽፋለሁ ሳፒቶም ይሁን ከናንተ ጋራ ይሂድ ለፓሪስ የሚሆን ገንዘብም እሰጣለሁ ሁሉንም አደርግላቸአለሁ አሉን። በዚህ ባለ የፍራንሲያ አምባሳደር በንጉሥ ፈንታ ወደ ናፖሊዎን እንዲሰዳችሁ

አደርጋለሁ። አሁን የምገናኛቸው ሰዎች አሉኝና መልእክቱን በሌላ ጊዜ አየዋለሁ አሉን። አቡነ ዮሴፍን እሁድ ማታ ወደ እኔ እንድትመጣ አሏቸው ባለቤትዎም መጥተው መዳሊያን ሰጡን ለሳፕሩስ ግን አልሰጡትም ጣቃዬ አግብቶት የነበረውን ሁሉ ቅዱስ አባታችን አዩ ጠላቶች የመንግሥት ነገር እያደረጉት ካልፈሩ ያገራችንን ነገር ለማቅናት እጅግ ይወዳሉ ስለኛ መልካም ነገር የሚሆንን በማሰብና በመውደድም ካርዲናል በርናቦ እንደ ቅዱስ አባታችን ነዎ።

ከዚያም ወጥተን በሠረግላ ሆነን ከታላላቆች ካርዲናሎች ጋራ ተገናኘተን። እንግዲህ የኛ ነገር በሮም እንደሆነ በፓሪስም ቢሆን እንዲ ቀና እጅግ ተስፋ አለኝ በ፫ ወይም ባ፬ኛው ወር ባገራችን እንድትሆን ተስፋ አለኝ። የሐበሻ ወሬ ቢኖር ልሰማ እወዳለሁ እምነቱ ወልድከ ዘአባ ገሪማ ወዘእሴፎ ቅድስተ ጸሎተ ዚአከ።

ዳግም በፓሪስ የተጻፈ ተጽሕፈት አመ ፰ ሚያዝያ በ፲፰፻፶፩ ዓ.ም በሐሳብነ ኦ አብ ክቡር ሰላም ለከ በእግዜር ቸርነት የእመቤታችን አማላጅነት በርስዎ ጸሎት ነገራችን ሊቀና ነው። በመኳንንቱና በንጉሡ ልብ ገብቶአል ኮንሱል በርግጥ ሊሰዱ ነው። መርከብም ሊመጣ ነው ሥፍራውም ከተማ ሊሆን ነው ኋሐቶም መውጫ ሊሆን ነው እንግዲህ አይነተኛ ምንገድ ስፍራ እሱ ነው በዓሌተና መንገዱ ክፉ ነው በአጽቢም ፈለጉ ከባሕር እሩቅ ነው

አይሆንም አሏቸው። ወይ አበሸስ ቶሎ የሚአስገባ መልካም መንገድ በዙላና በአርኪኮ ወይም በጸንአ ድግሌ ወይም ወደ ቀይሕ ኮር ነው ከሁሉም ዙላ ይበልጣል። ምነው ቢሉ መርከብ የሚቆብምበት ወደብ ባሕሩ ፵፫ ክንድ ይጠልቃል

በጋሊኔና በፍሬ በጻፉት ታሪክ እኔ እንዳልሁት ሆኖ ተገኘ። ጋሌነም እየመጡ ይጠይቁኛል ጦርን ሲሰዱ እርሳቸው የጦር አለቃ ሆነው ይቀመጣሉ አይነተኞች ሰዎች እየመጡ በሐላይ ታላቅ ቤት አለን እያሉ ይጠይቁኛል። የእግዜር ፈቃድ ቢሆን ታላላቆች ሰዎች ሳይመጡብዎ አይቀሩም።

ስለዚህ ቤት እንዳያንስ አስቀድመው እንዲገቡ ጳፍሑልዎ በሐላይ ፩ድ ሰፊ የጸሎት ቤት ቢገኝ መልካም ነው በተኸንዳሆ ቤት ቢሰራ ይህ ማለቴ ጦርን ባይሰዱ ኮንስልን።

ደጃች ንጉሜንም ደስ ያሚሰኝ በረከት እንዲሰዱ ርግጥ ስለሆነ ነው። አጼ ቴዎድሮስ በካቶሊካውያን ቤተ ክርስቲያን እንዲሦሩ እንዳይከለከሉ በሁሉም ነገር አርነት ቢሰጡ ወይም ባይሰጡ። አስቀድመው ሊጠይቁ ነው።

# ዳ ረቡዕ የካቲት

ይህም ጦር ቢመጣ ወይም ባይመጣ አይቀርም። እንግዲህ ፍራንስያ ስለ ሐበሻ በሚሆን ነገር ዝምታ የለም።

በሮምም ስለ አቡነ ቢያንኬሪ የተጻፉትን ካርዲናል በርናቦና ሞሰኘር በደኒ ነገሩኝ። እንዲህ ሲሉ ንጉሤ ጠፋ ወደ እናንተ የመጡት ታላላቆች ሲመለሱ አያገኙትም በምልክቱም ምክንያት ቋረኛ ካሣ እኔን አያኖረኝምና በዚህ መቀመጥ ታክቶኛል እንድመጣ ጥሩኝ ብለው ጻፉ።

ፕሮፓጋንዳ ግን እውነተኛ እናት ናትና ይህንን ነገራቸውን ከቁም ነገር አላገባቸውም። ይህም ሊታወቅ ከዚህ በኋላ ነው። ነገራችንን ያቀኑልን ላዛሪስትም ፩ድ ቄስ ወደርስዎ ሊሰዱ ነው። ላባ ተክለ ሃይማኖት በሰደድሁት ምልክት ጥቂት ወሬ አለበት። ነገር ግን ሌላ ሊሰማው አልወድም በሚመጣው ሐምሌ ወደ አገራችን ብንደርስ መልካም በሆነ። ቅዱስ ፓፓ ወደ ሮም ተመለሰ ብለውኛልና ወደዚያው ልንመለስ ነን። የሐበሻ ወሬ አልሰማንም። ኢትር ስለነ በጸሎትከ እምነቱ ኃጥዕ ገብርከ።

ተጽሕፈት አመ ፳ኑ ለሚያዝያ በዕለተ ዓርብ በፓሪስ ትብጸሕ ኀበ እግዚእየ ጀስቲኖ።

፪ኛይቱ ይች ናት ለኔ የጻፏት።

ወደ ፓሪስ ጉዞ።

ብሮም ላለው የፈረንሳዊ ምስሌነ ነግረውት ነበሩና እስፒታቤኪያስ ስንደርስ ወዲያው ወደ መርከብ አገቡነ። እንደ ንጉሥም በመዠመሪያ ሥፍራ አስቀመጡነ። እጅግም አከበሩነ። በዚያም ዳርቻ የምትሆንን መልካም ነገር አየሁ በ፫ኛውም ቀን ወደ ማርሲሊያ ደረሰነ። ምስሌነው ሠረገላን ሰዶ ተቀበለን። እርሱም አባታችን ያገራችን ሰዎች የደጃች ውቤ መልክተኞችን ይዘው ወደገርዎ በተመለሱ ጊዜ ከምስር ኮንስል ጋራ የነበረ ነውና ነው። ከዚያም ሌሊቱን ተነስተን ወደ ፓሪስ ገባነ። መዠመሪያውም ደጀ ሠላም ሠረገላ አቆዩን።

ወደ ከበረ ሥፍራ አገቡነ። ስለኛም በየለቱ የሚአመጡልን ምግም ያ፵፫ ብር ነው)።

የሆዱን ታሪክ ሲያወራ አያፍርም። ይህ ጽሑፍ የዘለዓለም ምስክር መሆኑን አያውቁም። (ናፖሊዮን ንጉሡ ስለኛ እንዲህ ማድረግዎ ብፁዕ ፓፓና የፕሮፓጋንዳ ካርዲናል በርናቦ ስለላላቴን ጌታው ጋራ ተገናኘን የነገርናቸውንም ጉዳይ በደስታ ሰሙነ። ነገ ግባት ሊደረግ ነውና ንጉሥና ንግሥት ወደዚያው ሊወጡ ናቸው እናንተም ልታዩ ብትመጡ መልካም ነው አሉነ። ወደዚያው በደረስን ጊዜ ሁሉን ወደሚአሳይ ረጅም ሰቅሰቅ አወጡነ ድንቅ የሆነ ሰልፍ አየነ። ጦሩን ባየን በሳምንቱ ከንጉሥ ነገሥት ናፖሊዮን ተገናኘን ወደርስዎም ሲአስጠሩነ ፪ የወርቅ ሠረገላን አሲዘው ፩ድ

መኰንን መጥቶ ወሰደን። ከእስጥንቡል ንጉሥ መልክተኞች ተገናኝተው ሲወጡ እኛ ገባን። ጣቃየና እኔም እጅን ስንነሳ በራሳቸው የነበረውን አክሊል የሚመሥል አወረዱልን።

ሰላምታውንም ነግረን መልክቱንም ሰጠን። ምን ትፈልጋላችሁ ብለው ጠየቁን እኛም በወረቀቱ ይገኛል አልን። ወረቀቱስ የሚአሳይ

## ዼ ኃሙስ የካቲት

የለውም አሉ። እኔም በኢትዮጵያ ያሉትን ካቶሊካውያን የተበደሉትን በደል ቤታቸውንና ምድራቸውን ገንዘባቸውን መቀማታቸውን የፕሮቴስታንቶችም ሁሉን ተናገርሁ። አሁንም ንጉሥ ንጉሤ ለካቶሊካውያን ወዳጅና አጋጅ በመሆናቸው ለጠላታቸው ያጐታቸውን አገር ሊአስለቅቋቸው መፈለጉን ነገርሁ። ንጉሡም ዳግመኛ አሁን ከኔ ምን ትሻለህ ብለው ጠየቁኝ እኔም እንዲህ መለስሁ።

ንጉሥ ንጉሤ ካቶሊክ ናቸውና በዚህ ምክንያት መንግሥታቸውን እንዳያጠአፉባቸው የርስዎ ስም ታላቅ ሳለች በጥቂት ነገር ሐበሻት ለሌላ እንዲያስገቡዋት በጦር መድፍ በጥበብ ይገዙኝ አሉ። ንጉሥ አልሁ። መርከብ ብሰድ ወዴት ይቆማል ጦሩስ በወዴት ወደ ሐበሻ ይወጣል ብለው ጠየቁኝ። እኔም መርከብ የሚቆምበት መልካም ቦታ አለ ስሙ እገሌ የሚባል በባሕር ዳር መንገድን የቀና አለ ብየ መሰልሁ። ጀዖግራፊያ በሚል ወረቀት አይተው ጋሌኔና ፌሬ እንዳመልከቱት እኔ ባልሁት በዚያ ወደብ የባሕሩ ጥልቀት ፵፫ ክንድ እንደሆነ ተገኘ።

እንግዲህ ተስፋ ያባታችንንም ሰላምታ ለንጉሡ ነገርሁ። እርስዎም ምስጥር እንዴት ሆነዋል አሉኝ። ያንን የመጣውንም ገጸ በረከት ሰጠን። ንግሥቲቱም መጥተው ተገናኙነ በደስታም ተቀበሉን። መጣምሩን ኮርቻ አይተው እንዳገሩ ሥራ ነው አሉ። እኛ ስንገባ ንግሥት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ቅዳሴን አስፈጽመው ተመልሰው ነው የተቀበሉን ባልና ሚስት መንፈሳውያን ይመስላሉ እኔ ያገራችነን የጅ መስቀል ይጀ ነበርና ንጉሥም ይህ ምንገድ ነው ብለው ቢጠይቁኝ እነሆ ብየ ሰጠሁዎ አይተውም መልሱልኝ ንጉሥ ቢአይልኝ እወዳለሁ። አልሁዎ እሺ አሉኝ።

ሌላ ጊዜ እንገናኛለን አሁን ሂዶ አሉን ንጉሠ ነገሥትም ስንወጣ ሾኙን ዓቃቤ ሰዓቱም እስከ ሰፈራችን መጣ በፓሪስ ሰው እኛን ለማየት ተገልብጦ መጣ። ለጃስቱኖ አባታችን እዴም ከሰጠልን የብፁዕ ፓፓ የፕሮፓጋንዳ አይን ወደኛ ነው እንደዚህ ከሆነ አገራችን እንድትቀና ተስፋ አለኝ ወደ ላዛሪስት ገዳም እየሄድሁ እቀድሳለሁ ወደ ልዮንም ማኅበር ጠርተውን ሄደን በስብከት ቀን አየነ እጅግ ብዙ ሰውም አየነ ሰባኪውም እኛን በዚያ አስቀምጠው ያገራችንን መሞትን ሲሰብኩ ነበሩ ሕዝቡም እኛን እያየ ደስ አለው። ደስታውም ሐበሾች እንኳን በሃይማኖት ከኛ ጋራ ፩ድ ሆኑ በማለት ነው። ካቶሊክ የሆኑትን ሐበሾች ያሳየኸን ተመስገን እያሉ እግዜርን አመሰገኑ ልጅ ጣቃዬም በምጽዋ ሳለ የዞመረው ሕማም ያመዋልና ሐኪም መድኃኒት እያደረገለት አሁን በጎ ነው ከንጉሡ ናፓሊዮን ዘመዶች ሁሉ ተገናኘን ኮንሱል ቢሊያርድም ባለቤታቸውም ደህና ናቸው ይጠይቁናል ስለ ሔቦ ቤተ ክርስቲያን ጻሕልና ጽዋ ሰጥተውኛል። አምኅ ሊተ ለኵሎሙ አኃውየ እምንቱ ኃጥዕ

ትብጻሕ ለእሁየ አባ ተክለ ሃይማኖት ዘዓድዋ) ይህን ታሪክ የጻፈ ሰው አባ ተክለ ሃይማኖት የተባለ የዓድዋ ሰው ነው። አባ እምንቱ የተባለውም የአባ ገሪማ ገዳም ሰው ነው። እነዚህ ሁለቱ ብቻ የዘሩት መርዝ እስከ ዛሬ ይበቅላል። (ሙሴ እነዚህ ሁለቱ ብቻ የዘሩት መርዝ እስከዛሬ ይበቅላል። (ሙሴ ሳፒቶ የነገሩዋቸውን ትተው ሌላን በመናገራቸው ወይም በማጉደላቸው በማጥመማቸውም በመላ እያዩ አባ

## ድ ዓርብ የካቲት

እምነቱ አዘኑ እርሳቸውን በማገኘት ደስ ያላቸውን ያህል ከፋቸው ይልቁንም እርሳቸውን አስተርጓሚን አድርገው ወደ ፓሪስ በሔዱ ጊዜ ተንኮላቸው ጥቂት መታወቅ ጀመረች በዚያ ዘመን የፓፓን መንግሥት ሊያፈርሱ ክፉች ሰዎች የፒየሞንቴን ንጉሥ አለቃ አድርገው ሲያስቱ ነበሩ ሙሴ ሳፒቶም በላይ መልካም መስለው የፕሮፓጋንድ አስተርጓሚ ነበሩ በውስጥ ግን የሽፍቶቹን ጉዳይ ሲያቀኑ ነበሩ። ይህንም ተንኮላቸውን አባቴ እምነቱ አውቀው ቋንቋ ባለማወቅ ዳግም የሔዱበትንም ጉዳይ እንዳያፈርሱብኝ በማለት ፈርተው እጅግ ታግሥዋቸው ኮማንዳ ሩሴልም እርሳቸውን አስተርጓሚ አድርጎ ወደ ምጽዋ በደረሱ ጊዜ አባቴ እምነቱን ከፈረንሳውያን የምትፈልጉትን እኔ ከሌላ ቶሎ ላደረግላቸው እችላለሁና ለኒያ የሚአደርጉት ላገሬ ንጉሥ ቢሆን መልካም ነበረ አላቸው አባቴ እምነቱ ግን ይህነኑ ለሚገባው ሰው ነገሩ። እርሱም ለኮማንዳ ሩሴል ነገረ ስለዚህ ኮማንዳ ሩሴል ከሙሴ ሻፒቶ መጠንቀቅን አደረጉ። አባታችን እናባቴ እምነቱን ከሸኙ ያ ደዌም ከበረደ በኋላ አባ ፊሊጺኒን ጠባቂን አድርገው አባ ዘካርያስ ታናሹንና አባ ኪዳኑን አባ ዮሐንስን ወደ ዓድዋ በጥር ሰደዱ ምክንያቱም ፩ድ ቤት ለመግዛት ነው።

፪ኛም ባቡነ ሰላማ ቁጣ በቤተ ክርስቲያ መቀበር የተከለከለውን በማይቆላ ዱር የተቀበረውን ታላቅ ተዝካር ለማድረግ አጥንቱን እዚያ አውጥቶ ወደ ቤተ ክርስቲያ ለመቅበር ዘመዶቻቸውንም ደስ ለማሰኘት የካቶሊካውያንንም ውርደት ከፍ ለማድረግ ነው። ነገር ግን ስንኳንስ ይህነን ማድረግ ቤት መግዛት ስንኳ አልተቻለም ወንድሞችና አባ ፊልጶስ በከተማው ቢታዩ ጊዜ የመድኃኔ ዓለም ካህናት እጅግ አዘኑ ታወኩም የተሰማምዋትን ቤት እንዳትሸጥ ከለከሉ። እንዴት አቡን የገዙት ፈረንጅ ወደ ከተማችን ተመልሶ ገብዞ በክልላችን ቤትን አማረው ብለው ተናደዱ እርዱን ብለው ወደ አድባራቱ ላኩ አባ ገሪሞች አባ ገሪማ ካቶሊክ የሮም ሰው ሮማዊ ነበሩና በወንድሞቻቸው ላይ አንነሳም በማለት ወይም ደጃች ንጉሤን በመፍራት አንመጣም ብለው ላኩባቸው አክሡሞች ግን አባ ዘካርያስ አስለቅቀው ሰደዱ አባ ዘካርያስ ባገራቸው በአክሡም ነበሩ ፩ ቀን ከደብተሮቹ ወደርሳቸው መጥተው በትምህርት በታሪክም ጠየቋቸው እርሳቸውም እንደሚገባ ከመለሱ በኋላ ከነዚያ ፩ዱን ቀድሞ ፵ ዓ የገዛው ዘንዶ ኋላም ፱ቱ ቅዱሳን የገደሉት አንድ ነውን ወይስ ሌላ ነው ብለው ቢጠይቁት አንድ ዘንዶ ነው። አለ በዚያ ሰው ተሳቀበት ስለዚህ ነገር አፍሮ እርሳቸውን ለማስለቀቅ በሰው ፊት ቅዱሳን ወደሚመስሉ ባሕታውያን እየዞረ እናንተ በዚህ ሳላችሁ እንዴት ርጉም መናፍቅ የልዮን ልጅ በአይነተኛይቱ ደብር በአክሡም ኑፋቄውን ሊያስተምር ዝም አላችሁ ብሎ አነሳሳቸውና እነዚያም ከየቦታቸው ወጡ ደወሉን ደወሉ ሁልም ሰምቶ ተሰበሰበ ሹም አባ ዘካርያስን አስጠርቶ ወደ ጉባኤው በደረሱ ጊዜ ይህንን እርጉም መናፈቅ እንድትደበድቡት ውጉዝ ብለው ገዘቱ። ስለዚህ ሁሉ በቁጣ በርሳቸው ላይ ተነሳ ይልቁንም ባላምባራስ ኪዳነ ማርያም የደጃች ንጉሤ ሹም እጸድቃለሁ ብሎ ሊገድላቸው ጠመንጃን አወጣ በዚህ ጊዜ ፩ድ መነኰሴ ስለ አባ ዘካርስ ቆሙላቸው። እኔን በፊት ካልገደላችሁኝ ይህንን አታገኙትም ብለው በግድ ከጉባኤው ዓይንና እጅ አስለቅቀው ወደ አድዋ አመጧቸው እኚህ ያዳንዋቸው መነኰሴ ባኩሡም የሞተን ወስነተኛ በመቅበር

# ዶ ቀዳም የካቲት

እንደ ጦቢት በመሆናቸው በዚያ አገር ስማቸው የተጠራ ነበር የርሳቸውም ደቀ መዛሙርት ከዚያ በፊት እየሩሳሌም ሊሄዱ ምንኩሉ ደርሰው በሁሉ ተጨነቁ አባታችን በዚያ ነበሩና ወደ ቤትዎ አግብተው መገብዋቸው። አንዱን አስታመው አዳኑት የተደረገላቸውም በጉነት ለመነኰሴው ነግረው ነበርና ያባቴ ዘካርያስ መዳን በዚህ ምክንያት ነው። አክሡሞች እይኛ አስለቅቀናል የናንተን እንደ እውቀታችሁ ብለው ወደ ዓድዋ ካህናት ላኩ በዚህ ጊዜ አባቴ ኪዳኑ ካድዋ ወደ ዕዳ መጣ ዕ ተሻግረው የመድኃኔ ዓለም ካህናት ያደረጉባቸውን ለደጃች ንጉሤ ነገሩ ንጉሤም ቃላጤን ሰጥተው ሰደዱባቸው መጋቢት ፳፯ ቀን በበዓሉ ቀን በቤተ ክርስቲያን ካህናትና ሕዝብ ተሰብስበው ሳሉ አባ ኪዳኑና አባ ዘካርያስ ንዑስ ቃለዓጤውን ይዘው ወደዚያ ገቡ።

የማርያምን ጠላት ቡላውዴን ቤትን ማስገዛት የግድ አቡነ ያዕቆብን መከልከል የእኔ ወዳጅ በመሆናቸው ነውን።

አሁንም አትከልክልዋቸው ይግዙ ብለዋል ንጉሤ ይሙት ብሎ ተናገረ። መልክቱም እንደተነገረ ካህናቱ ታወኩ ተቆጡ እኒህን እርጉሞች ያልመታህ ብለው ገዘቱ ስለዚህ በዚያ የነበሩ ፍሬ ሕይወት ሣህሉ ልጆቹ ዣናሞሮች ካቶሊካውያንን አይወዱምና በወንድሞቻችን ላይ ተነሡ ደበደቡዋቸው ሊገድሉዋቸው ሲሉ ስካር ወልደ ሚካኤል የሚባሉ ሰው ስለወንድሞቻችን ቆሙ መሥሪያቸውን ያዙና በዚህ ያለህ የኔታን የምትወድ ሁሉ ወደኔ ና ብለው ጮኸው ተናገሩ ስለዚህ የተነሱቱ በረዱ በርሳቸውም ምክንያት ወንድሞቻችን ዳኑ ደጃዝማች ከዳባ መጣዕ ለቀው ወደ አክለ ጉዳይ በሰፈሩ ጊዜ አባ ኪዳኑና አባ

ዘካርያስ አክሡም በተገደሉትና አድዋም ከቃለዓጤ በላይ መደብደባቸውን ለደጃች ንጉሤ ነገሩ ደጃች ንጉሤም ዳግመኛ ወደ አድዋወትና ወደ አክሡሞች ኑ የሚል መልእክትን ላኩ። ደጃዝማችም ከቆላውም ተነስተው በዝባን ቡር በሰፈሩ ጊዜ አባታችን ከሃላይ ሄደው ተገናኙ ቤትን ሊገዙ ልኬ ነበር አሁን ካህናት ከለከሉ እርስዎ ሁከት እንዳይሆንብዎ ይቅር አሉ።

ደጃዝማች ግን አይደለም ለምን ይቀራል ይገዛ እንጅ አሁን ሰው እሰዳለሁ አሉ።

ነገር ግን ካህናቱ አሸነፉ እንጂ እርሳቸው ያሉት አልሆነም። ዳግመኛም ፈረንጅ ሆኑ እያለ ሰዋቸው ያጉረመርምባቸው ነበር። ከካህናቶች ጋራ ስለኛ መጣላትን ፈሩ ወንድሞች ፺ት ወር ያህል ተቀምጠው ወደ ሐላይ ተመለሱ ደጃዝማችም ከዝባን ቡር ወደ ሽመዝና አልፈው ዘረፉት። በዚያ ጊዜ አባቴ ወልደ ገብርኤል ከሮም ተመለሱ ከርሳቸውም ጋራ ከምሥር የነበሩ ፪ት ፈረንሳዊያን መጡ ፩ዱ ቃብጣን ቢርቱ ይባላል ሰልፍን ማስተማር አውቃለሁ ያለ በዚያ በዚያ ዘመን ሙሐመድ ደንከሊ የሚባል የፅመር ባጁነት መልእክተኛ ሺህ ከ፫፻ ነፍጥ ባለድባ ሽልጦዎ ነበር። ነገር ግን የኔታ ሚካኤል ወልደ ሥላሴ በሌሎችም ነገሥታት ያልተደረገ ነገር እንሆ በርስዎ ጊዜ ተሠራ ምንኛ ሐብታም ነዎ እንደዚህ ያለ ሠራተኛ ያስመጡልዎ ሲሏቸው ጊዜ ደስ አላቸው በ፲፻ኛ ቁጥር እንደተጻፈ አባቴ እምነቱና እኔ በአጉዕዲ ነበርና ወረቀቱን አይተን ከደጃች ንጉሤ ገጠምናቸው እርስዎም ትበብ ታውቃላችሁን ቢሏቸው ፩ዱ የፈረንሳይኛ ሰልፍ

# ገ እጉድ የካቲት

፪ኛው መድፍን መሥራት ፫ኛው በአድዋ ቀርቶ ነበርና ትጦማላችሁ ቢሉት አስተርጓሚው አባቴ እምነቱ አንጦምም ያላቸውን በወዲያ አገር ወታደር አይጦምም ብለው መለሱ ስለዚህ ደጃዝማችና በዚያም የነበሩቱ እንዴት አይጦሙም ቢሉ ስለዚህ በአድዋም በጦሙ ሥጋን በመብላታቸው ይልቁንም ጥንቸልን ሌሎችንም ተሐዋስያን ሲበሉ ቢታዩ ጊዜ አምልኮን አሰደቡ ደጃዝማችም እንግዲህ መድፉን ለመሥራት ምን ይምጣላችሁ ነሐስን ወይስ ብረት ብለው ቢጠይቋቸው የብረቱ ደንጊያ ነው የምናደርገው አሏቸው። እንግዴህስ ወደ አድዋ ተመለሱ አሏቸው በዚያ ሁናችሁ ሥሩ ምግባችሁን አደርጋለሁ አሉዋቸው። እንሄዳለን ማርን ቅቤን ፍሪዳን እህልን በየወሩ ስጥ መልካም ቤትንም እነሱ የፈለጉትን አቅርቡላቸው ስለ ተባለ እነዚያ እንዳሉ ብቁል የተባለን የብርቱን ዲንጊያ ከእንተጨው እስከ አድዋ ባላገሩን አሽከሙ ከድቅሬና ከሌላውም አገር ከሰልን አስመጡ ንግድም አቋረጡ ይህንን ሁሉ እስኪያስበስቡ ድረስ ፺ት ወይም ፰ት ወር ካለፈ በኋላ ድንጋዩን ሊያቀልጡ በሰፌድ አንግቦት የማይሆን ሆነ እጅግ ትሳቀባቸው እኛን የሚጠሉ ሁሉ የሚሆን መስሏቸው አዝነው ነበሩና አለመሆኑን አይተው እጅግ ደስ አላቸው። ባ፩፻፫ ገጽ በ፲፻፵፰ ቁ እንደተጻፈ አቡነ ቢያንኬሪና ሙሴ እስቴላ ኮንሱል እንግሊዝን ጠባቂ ማድረጋቸው እነ ያዕቆብ ያሉበት አገር ባጼ ቴዎድሮስ ሲጠፉ እኛ ያለንባት ትቀራለች ብለው ነበር እኛንም በቴዎድሮስ ወደእኛ ልትሸሹ ናችሁ ሲሉነ ነበሩ። ነገር ግን ይህ ነገር ተለወጠ ደጃች ኃይሉ ከአጼ ቴዎድሮስ ተሹመው በመጡ ጊዜ ሙሴ እስቲላን ወርሰዋቸው አስጠርተውም ሃይማኖትን

ጠየቋቸው እርሳቸውም ፈርተው ይመስለኛል እውነተኛይቱን ሃይማኖት ከሐሰተኛይቱ ጋራ ፩ድ አስመስለው መለሱ ደጃዝማች ግን እንዲህስ እንደሆነች ሃይማኖት ባቡንና በንጉሥ ፊት ልትገኙ አውሱ አሏቸውና ቄስ ገብሬ የደብተራ እንቁ ልጅ አውሰው ወደ ከረን ተመለሱ ቀኑ ሲደርስ ተከረምት በኋላ ወደ ምንኩሉ ሸሹ። ባ፲፫ ምዕራፍ ፲፰፻፶፪ ዓመት አባታችንና በካቶሊካዊያን የሆነችን ኃዘንና መከራን ይናገራል በ፰፻፲፮ ቁጥር እንደተጻፈው ብጹዕ

ፒዮስ በስም ፱ነኛ አባቴ እምነቱን ወደ ሮም ተመለሱ ብለዋቸው ነበርና ወደ ሮም ተመለሱ ነገር ግን ከርሳቸው ጠይቄ የጻፍሑት ተዘርፈዋል አሁን የምናገረው ጥቂቱ ያልተረሳሁትን ነው እንጂ እየተደረገ ሁሉን ላውቅ አልቻልኩም ንጉሠ ነገሥትና ናፖሊዮን ፲፫ ሉል እንደርሱም ባይነታቸው አዕናቍ ያለበትን የወርቅና መስቀል መጠኑና ሥራው እንደዚያ እንደወደዱት የመሰለን ዋጋው ፪ሺ ብር ይሆናል የተባለን ላባቴ እምነቱ ሰጡ። ለልጅ ጣቃዬም ማኅደሩ በብር የተሠራ ወርቅን የተቀባ አዕናቍም ያለበት መልካም ጐራዴን መልካም ጠመንጃ ሸልመው አሰናብተዋቸው ነበር። ግን በመንገድ መርከብ ተበላሽቶ ዕቃውንም ማንም ወስደው ልጅ ጣቃዬም በባሕር ዳር ሞተ አባቴ እምነቱንም አሣ ፈላጊ አግኝቶ አወጣቸውና መጡ።

ብዙ ከታመሙ በኋላ ከስዊስ ወደ እስክንድርያ ተመልሰው መከራቸውን ነገሩ እንደፊተኛው በክቡር በፍቅርም አልተቀበሏቸውም በፕሮፓጋንዳ ትእዛዝ አቡነ ፔርፔቶ የተባሉትን ምዕራባዊው ጳጳስ ወይም ሊቀ ጳጳሳት በእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ፈንታ የሚኖሩ ለስንቃቸው ጥቂት ገንዘብ ሰጥተዋቸው ያ ባ፬፻ ብር የተገዛ የደጃች ንጉሤ ነፍጥ ቱርኮች አናሳልፍም ስለአሉ በቀራጩ ቤት ተይዞ ነበርና እርሱ ብቻ

## ጉ ሰኑይ የካቲ

ሊቀር በመርከብ ያገቡት ዕቃ ሁሉ ጠፋባቸው) እንግዲህ አስተዋይ የሆንክ ኢትዮጵያዊ ይህን ታሪክ ተመልከት ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ለማስተማር የመጣ ሰው ከዓለም ነገሥታት ፖለቲክ ውስጥ ገብቶ እስከ መሣርያ የሰው መግደያ ለማቀበል መድረስ ይህም ሰይጣናዊ ሥራ ከመንፈሳዊ ሥራ ተቆጥሮ ስለ ቅዱስነት የምስክር ገድል (ታሪክ) ተብሎ ሲገኝ ይህ ብቻ አያሳፍርም ይሆንን (አባቴ እምነቱ መልክትን ወደ አባታችን ሰደዱ በዚህም መልእክት የመርከቡ መሰበር የልጅ ጣቃዬን መሞት የወንድማቸውንና የፈርዲናይንም የናፖሊዮ ንጉሥ መርፎ ተጽፎበት ነበር። ከፈርዲናይ ጋራ እጅግ ፍቅር ነበረዎና የኢትዮጵያን ስብከት ለመተቀምና ለማጥናት የሚሆን ነገር ከርሱ ይገኛል ብለው ተስፋ ነበርዎ እነ አባቴ እምነቱ የሄዱበት ጉዳይ በቀና መልካም ይወጣል መቼ ይመለሱ ይሆን ሲሉ የጣቃዬ መሞት እጅግ አሳዘነዎ ዳግመኛም እነዚያ ዳኑ ወንድሜ ሞተ ብለው ደጃች ንጉሤ ላይ ክፋትን ያስቡ ይሆናል ብለው ተጠራጠሩ አባቴ እምነቱም ሄደው የጣቃዬን ሞት ሰውረው ወደኋላ ቀርተዋልና ይመጣል ብለው ለደጃች ንጉሤ ፓፓ እንደነገሩኝ ታላቅ ሰውን ወደ እርስዎ የሚሰዱ ናቸውና ምናልባት ወደ እርስዎ ሳይደርስ ግን ፩ድ ነገርን ቢፈልግ የእርስዎ ምስለኔ ሆኜ እንዳደርግለት ፈቃድዎ ቢሆን ማኅተምዎን መውሰድ ያስፈልገኛል አሉ። ደጃዝማችም እሺ አድርጉ ብለው ማኅተማቸውን ሰጥተው ሰደዱዋቸውና ወደሕላይ ተመለሱ እርሳቸውም ከተመለሱ በኋላ አባታችን ከሐላይ ወደ ምንኩሉ ወረዱ በገጽ ፬፻፰ ባ፲፪ ም

የኮንሱል ጀልበርት መምጣት ይነገራል አባቴ እምነቱ ካውሮፕ ከተመለሱ በኋላ ባ፩ድ ወር ፈረንሳዊ ኮንሱል ጀልበርት ወደ ምጽዋ ደርሰው ወዲያው ወደ ሐላይ ወደ አባታችን ላኩ እንግዲህ ሲሉ የምኒስተር (ብላቴን ጌታ) ወይም አፈ ንጉሥ መልእክት ለርስዎ የተሰደደች ከኔ ጋራ አለች።

ሌላም ጉዳይ አለኝ ከርስዎ ልገናኝ እወዳለሁ ስለዚህ ከሐላይ ወደ ምንኩሉ ወረዱ። እኒህ ኮንሱል በእስጥንቡል የነበሩ ናቸው።

የቱርኮችን ልማድ ያውቃሉ። በዚዐ ዘመንም ምጽዋም ገና የምስር ገዥ ኮንስል አልገባባትም ነበር። ደግሞ በዚያ ወራት ናይብ እድሪስ ናይብ የሐሰን ልጅ ተሹሞ ነበረ እርሱም የፈረንሳዊያን ወዳጅ

ነበረ። ናይብ ሞሐመድ ግን ያብድራሒም ልጅ የናይብ አህመድ ወገን የሚሆን የእንግሊዞች ወዳጅ ነበረ። ቱርኮች ግን እድሪስን ሽረው ሙሐመድን ሹመው ግባ አሉት ሊያስሩት ፈርቶ አልገባም አለ። አባቴ እምነቱ እኛ ለምናስበው ጉዳይ ናይብ እድሪስ በሹመቱ ቢጸና መልካም ነው ብለው ላባታችን ነገሩ እርስዎ ለኮንሱል ነገሩ ወንድመ አህመድ ኦሬ በሌሊት መጣ ኮንሱልም አይዝዋችሁ ቢሆንም ለሽፍታ መርዳት አይሆንልኝምና ወንድምህን አስመጣ አሉት ስለዚህ ናይብ እድሪስ ከሐባብ ወደ ምንኩሉ ድረስ ፈርቶ በሌሊት መጣ። ኮንሱል ግን በብርሃን እገናኛለሁ ብለው አይሆንም አሉትና በነገታው ተገናኝተው ሂደና ባሻን ኮንሲል ጀልበርት ጋራ ተገናኝቼ መጣሁ አንተንም ሰላም እልሃለሁ በዚህ ምክንያት ጐሹ የሚባል ቀዋስ ዙፋን (ቤት ስለእርሱ ወደ ብሻው ላኩለት በነገታውም ሄደው ሹመቱን አጸኑለት ዳግመኛም በዚያ ጊዜ የወረደው ቅፍለት (ጭነት)

# ጊ ሠሉስ የካቲት

ሁሉ እንዳይሄድ ተከለከሉ በምንኩሉ ሰፍሮ ብዙ ቀን ተቀምጦ ነበረ። ኮንሱልም ለባሻ ነግረው በወደዱት እንዲሄዱ አደረጓቸው ስለዚህ ነጋዴ ሁሉ አባታችንን አመሰገነ በዚህ ጊዜም ቤተ ክርስቲያን የሚሠሩበት ቦታን አባታችን በራስ ምድር ያለውን ተቀበሉ። አቡነ ቢያንኬሪ በምጽዋ ቤተ ክርስቲያን ብናገኝ መልካም ነው ብለው ወደ አለቆቻቸው ልከው ነበሩ የፈረሲስ ንጉሥ የእስጥቡልን ንጉሥ ለመኑ። እርሱም እሺ ብሎ ምላሽን ሰጠ። ነገር ግን ጥኑ ኮንስል በመታጣት ይመስለኛል። ፲ ዓ የሚሆነን ነገር ሳይጨርስ ኖረ ኮንሱል ጀልበርት ግን በመጡ ጊዜ የጅዳ ባሻ ፊርማ የተባለች የሱልጣን መልክት የያዘን አይነተኛ ሰው ወደ ምጽዋ ሰደደ። ስለዚህ ኮንሱልን አስጠቶ እርሳቸውም አባታችንን አስጠርተው ከምንኩሉ ወደ ደሴቱ ገቡ። ከዚህ በኋላ እኒህ ሁለቱና ባሻ ከመልክተኛው ጋራ ወደ ራስ ምድር ወጡ ምድሩንም ሰፍረው ሰጥተው ድንጋያዋንም በዙሪያው አኖሩት በዚያ ቀን የምጽዋ ባሻ ሁለቱንም ለምሳ ጠራቸው አባታችን ግን እሳላሞች ያረዱትን በመብላአት በዚያ ላለ ነጋዴ ክርስቲያን ሁሉ እንቅፋት እንዳይሆን ብለው ቀሩ።

በ፩፻፲ ገጽ ባ፲፯ ምዕ ባ፲፰፻፶፪ ዓ.ም የንጉሠ ነገሥት ናፖልዮን መልክተኛ ኮማንዳ ሩሴል የመን የምትባል የነጋዴ የእሳት መርከብ ወደ ምጽዋ ወጡ ያለቃ ብጣኑ ከርሳቸው ጋራ ከፍራንሳያ የመጡም ፲፪ ሰዎች ነበሩ። እንደ ደረሱም ወዲያው ወደ ምንኩሉ ወደ ኮንሱል ላኩ እርሳቸውም ማታውኑ ሄዱ። አባታችንም በነገታው ሄደው ተገናኙ ኮማንዳም እኛ ወደርስዎ ልንመጣ ነበረ። ሞንሲኜር ጌታዬ ለምን መጡ አሉዎ። በማክበር ነው። ከዚህም በኋላ ስለ ጳጳሱ ክብር መድፍን መተኮስ ልማድ አለና ፯ ጊዜ ተኮሱላቸው። አባታችን እነዚህን በማየት ከዚህም ጋራ በመጫወት ለቁም ነገር እንደመጡ ስምተው ደስ አለዎ ነገር ግን ይህች ደስታ ፩ድ ቀን እንኳ ሳትሞላ ወደ ጭንቅ ተለወጠችባቸው። ኮማንዲ እንዲህ ይላሉ ኮንሱል ላባታችን የተናገሩትም ቃል ይህ ነው። ንጉሤ እስካለበት ድረስ የምንቀመጣቸውን አባልቁቶችና ዕቃችንንም የምንጭንባአቸውን ፴ የሚሆኑ አጋሰሶች የሚቀበለንም ፩ድ ደጃዝማች እንዲሰዱልን አሉ። አባታችን ደጃች ንጉሤ ስለራቋቸው በችግር ላይ ስለሆኑ ደጃዝማችም ይህን የሚአደርጉ አይመስለኝም እኔም እንዳላደርግላቸው ገንዘብ የለኝም በዚህ ምክንያት ይህ ታላቅ ነገር ሊፈርስ ነው። ብለው ተጨነቁ። ይህ ጭንቀት ለመፈሳዊ ሰው ተግባሩ ነው። የሚል አንባቢ ይኖር ይሆንን ግን አባቴ እምነቱ የኮማንዳ መምጣት ለመውጣትም የሚፈልጉትን ነገር ሁሉን እንዲሰዱላቸው መልክተኛን ወደ ደጃዝማች ሰደዱ ኮማንዳም በዚህን ያህል ቀን እመለሳለሁ ብለው ከምጽዋ ወደ እንፊላ ወደ በርበራም በባሕር ዳር ዳር ወደዳለ አገር ሄዱ። አባቴ እምነቱም በዚያ እንዲገናኙ ከኮማንዳ ጋራ ቀጠሮ አድርገው ነበረና ወደ ዙላ እንዲሄዱ ፈልገው ስለስንቃቸውና ስለ እንግዶቹም የሚፈልገውን ነገር ላባታችን ነገሩ። እርስዎም ከላይ እንዳልሁ እጅግ ተጨነቁ። ዕመር ባጅነት ከሚባለው ነጋዴ እስላም ከጌታ ባሮኒም

ገንዘብን ትበደሩ። ከዚህም ከፍለው ላባቴ እምነቱ ሰጥተው ከምንኩሉ ወደ ሐላይ ተነሱ። ከምንኩሉም ተነሥተው ወደ ሐምሐም ሲደርሱ ወደ ደጃች ንጉሤ ተልኮ የነበረን መልክተኛን አገኙት። ያመጣውም ምላሽ ኋላ እከላለሁና

## ጋ ረቡዕ የካቲት

ተበድረው ያድርጉልኝ ተቀባይን ግን ደጃች ብሩን እሰዳለሁ የምትል ምልክት ሰጠዎ

ዳግመኛም አጼ ቴዎድሮስ በወገራ እንደደረሱ ደጃች ተሰማም ጻሕሎን ለቀው ወደ ትግሬ እንደ ተሻገሩ አወራልዎ ቀኑ የልደት በዓል ነበረና አባታችን በዚች በታላቂቱ በዓል ደስ ሊያሰኙን አልወደደም አሉ። ሱባጋዲስ ካሣ በፊት በ፲፻፰፻ ቍጥር እንዳልሁ ከንጉሥ ተሹመው መጥተው ነበሩ። የማይችሉ ስለሆኑ በደብለኽን መሽገው ተቀምጠው ነበሩ። ግን ደጃች ንጉሤን ወንድምዎ ደጃች ተሰማ ጠላታችን ደርሷልና በዚህ ሆነን እንድንዋጋ በቶሎ ይምጡ ብለው ቢልኩባቸው ከደብለኽን ወደዚያው ተነሡ። ነገሩን ተነስተው ሄዱ። ስለፈሩ ይመስለኛል ከማንዳን የሚቀበል ሳይሰዱ ተነስተው ሄዱ። ከወንድማቸውም ጋራ ባድዋ ተገናኙ። ጦራቸው እጅግ ብዙ ሲሆን ፍራት በመኳንንቶቻቸው ስለሆነች እንሽሽ ብለው መከሩና ወደ ሥራዬ ተመለሱ። ስለዚህ ከላይ እንዳልሁ አባታችን ላባቴ እምነቱ ተበድረው እንደሰጡ ዳግመኛም እነዚያ የሚቀመጧቸው ፲፬ አብቅሎች ከዝባንቡር ተከራይተው እስከ ዙላ ሰደዱ። ዕቃቸውንም የሚሸከም አጋራይ እስከ ኩምዓሊ ድረስ ሰደዱ ኮማንዳ ከምጽዋ ከተነሱ በኋላ ባ፲ኛው ቀን ወደ ዙላ መጡ። አባ እምነቱንና አብቍልቶችንም በዚያ አገኙ ከዚያ ዕቃቸውን በግመል አስጭነው ወደ ከመይሌ መጡ። በዚያም በግመል የነበረውን ባጋራይ እሸከመው በእንስሶችም አስጭነው በሰሮ አድርገው ወደ ተኾንዳ መጡ። አባታችንም አብረው እንዲሄዱ ተዋውለው ነበርና ከሐላይ ወደ ተኾንዳ አለፉ ደግሞ ከሮም ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳት የመጣን መልእክተኞችና ሥዕልን ለደጃች ንጉሤ ለመስጠት ነበረ”። ይህን ሁሉ ፖለቲክ አንባቢ ይገምተው ግን በላይ እንዳልነ ደጃች ንጉሤ ከደብለኽን ለቀው ወደ ትግሬ ሄደው ነበር።

ኮማንዳ ኋታቶን ሊያዩ ወጡ ይህ ስፍራ አዶሊስ ከተማ ሳለ እርሱም ከተማ ነበረ ይላሉ በዚያ ጊዜ በድንጋዩ ላይ በግዕዝ የተጻፈን አገኙበት ያገሩንም ፍራሽ አይተው ወደ ተኾንዳ ተመለሱ) እዚህ ላይ ባገራችን የሚተርከው ተፈጸመ ማለት ጻድቃን ባልተቃጠሩበት ይገኛሉ ኃጢዋአን ግን በተቃጠሩበት ይተጣጣሉ የሚባለው ከባሕር ማዶ ድረስ በብዙ ድካም የመጣውን ኮማንዳ በብዙ ድካም ወደ ተኽነዳ መጥቶ ደጃች ንጉሤን ይቅርና አንድ ተቀባይ እንኳ አጥቶ ከጭንቅ ላይ ወደቀ።

“አብረው መጥተው የነበሩ ፩ኛ ባለመድኃኒት ሐኪም ፪ኛ አስተርኖሚያ የከዋክብትን ትምህርት የሚያውቅ ፫ኛ የመጡባት መርከብ ቃብጣን ፬ኛ አስተርጓሚ ሙሴ ሳፒቶ ፭ኛ ከርሳቸው ጋራ ለመጡ ጥቂቶች ወታደሮች አለቃ አባታችን ለነኝህ ሁሉ ለየብቻቸው ቤትን ሰጡ።

ዳግመኛም ሙሴ ዳልሞንቴ እነኮማንዳ ወደ ሐላይ ከገቡ በኋላ አባታችን የነበሩትን ታችኛውን ቦታ ለርሳቸው ሰጥተው በመሐሉ መመላለሻ ተቀመጡ። ባ፩፻፲፬ ገጽ ፴፰ ምዕራፍ ኮማንዳ ከመጡ በኋላ በጥቂት ቀን በጦር መከበባችንን ይናገራል።

## ጌ ሐሙስ የካቲት

ከላይ እንዳልሁ ደጃች ንጉሤ ሸሽተው ወደ ሥራዬ ከወጡ በኋላ ወደአባታችን የመጡት እንግዶች ሰዎች ጦር ያላቸው እንደሆን ይምጡ ብለው ላኩ። አባቴ እምነቱም ለኮማንዳ ከዚህ ደጃች ንጉሤ እስካሉበት ቅርብ ነውና ይጀዎ

ልሂድና ይገናኙ ቢሏቸው የሚቀበለኝን ካልሰደዱልኝ አልሄድም አሉ። በዚህ ጊዜ ነው ነገር የተበላሸ ይልቁንም ሄደው ቢሆን ፪ኛ ቀን ደርሰው ዉላቸውን ጨርሰው በቶሎ ወደምጽዋ ሊመለሱ በቻሉ ነበር። ደጃች ንጉሤ ደጃች መርዕድን አስረው ወደ ሻንቅላ ሸሹ። ከዚህ በኋላ ሐላዮች ተሰብስበው ወደ አባታችን መጥተው ደጃች ንጉሤ ከሸሹ ንጉሥም መጡ ከተባለ እርስዎም እንግዶችን ይዘው በዚህ ጊዜ ቢሸሹ መልካም ነበር አሉ። አባታችን ግን ገና የንጉሥ መምጣት እርግጡ አልታወቀም እንዴት አስቀድመን እንሸሻለን አሉ ነገር ግን በዚህ ጊዜ ሸሽተው ቢሆን መልካም ነበረ። አጼ ቴዎድሮስ ጋሎችና ሸዎች ስለሸፈቱባቸው ደጃች ንጉሤን መውጋት አልፈለጉም ነበር። ኋላ ግን ሙሴ ባሮኒ ሙሴ ሻምፔር አቶ ሽምብር አሁን ካልደረሱ መንግሥትዎ ፈረሰች ብለው ወደ አጼ ቴዎድሮስ ስለላኩባቸው ከሸዋ ገስግሰው ወደ ወገራ ደረሱ ከዚህም ወደ ማይ ጻህሎ መጥተው ከንቲባ ዘረአይን ወደ አክለ ጉዛይ ሰደዱ ከንቲባ ዘርአይ ከደጃች ውቤ ሸሽተው አባ ሰላማ በወጡ ዘመን ወደ እሳቸው ገብተው ተማጠኑ። ከትግሬ ወደ አምራ አገር ተሻግረው ካቡን ጋራ ተቀምጠው የጭፍራቸው አለቃ ስለአደረጓቸው የሻለቃ ዘርአይ ተባሉ አባታቸው በሐር ነጋሽ ዘርግስ ከአክለ ጉዛይ ሁሉ ሽፍቶች ከደጃች ግልቱና ከብላታ ኮከቤ ጋራ በበለሳ ሲዋጋ ሞተ። ሻለቃ ዘርአይ አቡንን ትተው አጼ ቴዎድሮስን ተከተሉ። አጼ ቴዎድሮስ ያባትህን አገር ሰጥቸሃለሁ አሏቸውና ፈረንሳዊያን ብዙ ሆነው እስከ ሐላይ መጡ። አገዎች ግን ከሸሹ በኋላ ተገለጠ አጼ ቴዎድሮስን ሁሉ ፈርተዋልና ተቀብላቸው ወደ ሀገራቸው ወደ ድግሳ ገቡ ላም ሳይሰማራ በሐላይ መጣ። ከንቲባ ዘርአይ ደረስ ተብሎ አገር ታወከች። ሁሉም መሳርያውን እየነጠቀ ወጥቶ ተሰለፈ። አባታችንም በመዠመሪያው ጩከት ወጥተው በኔ ምክንያት ጦር ከሚሆን እኔ እራሴን አሳልፌ እሰጣለሁ በማለት ከጦሩ ፊት አለፉ። ኮማንዳም ሰዎቻቸውን አስልፈው ወደ እዚህ መጡ ዘግይተው ነበርና አልተመሰገኑም። ከዚህ በኋላ ባራተኛው ቀን ማይሠራው በሚባለው ያክለ ጉዛይ ታላላቆች ከከንቲባ ዘርአይ ጋራ ሆነው ተሰበሰቡ። የሐላይም ዓይነተኞች ወደ እዚኸው ሸንጐ ገቡ። ዘርአይና ታላላቆች እኛ ያልናችሁን እንድታደርጉ ማሉልን አሏቸው። ማላውም አባታችንና ኮማንዳን ሊይዙ ሲመጡ ዝም እንዲሉ ነው። ስለዚህ ከንቲባ ዘርዓይና ያአከለ ጉዛይ ሹማምንቶች እንዲቀጥራቸው ወደ ሐላይ መጡ ጦሩም በ፪ት ወገን መጣ። ወደከሌ የተባለ ማይሐራሳት የጉዛይና ከንቲባ ባርያኡ አክራን በዓድ ቀልቀል በሚባለው በዝቶ መጣ። እጅግም ታወከነ እጅግም ፈራነ ቤታችንም ታች እንደሆነች ኮማንዳ አይተው ከፍ ያለውን ቦታ እንያዝ አሉ አባታችን ግን ፈለጉ ይላል።

# ግ ዓርብ የካቲት

አምልጠው እንደወጡ ይነግራል። ሐተታው ስለ በዛ ለጊዜው ባ፬፻፷፫ኛው ገጽ ላይ ተወት አድርገነዋል።

ኮማንዳ ሩኤል ወደ አጼ ቴዎድሮስ ደብዳቤ ጽፈው ኑሮ በፈረንሳዊ ቋንቋ ስለነበረ ከርሳቸው ጋራ የነበሩ እንግሊዞች መክሬርና ቤል ዮሐንስ ባነበቡላቸው ጊዜ ናፖሊዮንን ያገኘሁ መስሏቸው አጼ ቴዎድሮስ ተቆጥረው ተራዳውን በጐራዴ መቱት ይላል። የአባ ያእቆብ ገድል በተባለው መጽሐፍ አጼ ቴዎድሮስን በጣም ይጠላል ምክንያቱም የካቶሊክ ሃይማኖት ከኢትዮጵያ እንድትጠፋ ስላደረጉ ነው። ማለት ካቶሊክ ሃይማኖት ከኢትዮጵያ እንድትጠፋ ስላደረጉ ነው። ማለት ካቶሊክ የሆነው ሁሉ እየተያዘ ስለተቀጣ ነው። ካቶሊክ የሆነ ሁሉ ወደ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት በተመለሰ ጊዜ በሮማና በፓሪስ ያሉ ሰዎች ገንዘባቸው ዋጋ ሳይገኝ በከንቱ ስለ ቀረ ነው። ባጼ ቴዎድሮስ ላይ ሕዝቡም እየሸፈተና እየከዳ ያስቸገረ በነዚህ በሮማን ልዑካን ስብከትና ወረቀት አመላላሽነት መሆኑን በገድሉ ላይ አልፎ አልፎ ይገኛል።

፪ኛም አጼ ዮሐንስ እንደዚሁ ኢትዮጵያን አንድ ሃይማኖት ለማድረግ አዋጅ ነግረው ለመላ ኢትዮጵያ ፩ድ ጳጳስ አይበቃም ብለው ፬ት ጳጳሳት ከግብጽ አስመጥተው እንደ ፩ድ ሐዋርያ ሆነው ቢነሱ የሮማ ልዑካን ወደ ሸዋ ገብተው ንጉሥ ምኒልክና አጼ ዮሐንስስ የሚአጣላ ስብከት ዠምረው የሡሩት የፖለቲክ ጽሑፍ።

ከላይ በተጻፈው መረዳት ነው። አጼ ዮሐንስ ሳሉ ዠምረው ካጼ ምኒልክ ጋራ የተዋዋሉት ሁሉ የሐሰት ፖለቲክ መሆኑ ታውቆ አድዋ ላይ በደም ከተሠረዘው ሁሉ የኢጣልያኖች ቤተ ክርስቲያን የተባለ ሳይነሳ በመቆየቱ

የማይጨውንና የውጋዴንን ጦርነት አስከተለ። በዚሁም በሮማ ልዑካን ቤተ ክርስቲያን በተባለ ውስጥ የኢትዮጵያውን ንጉሠ ነገሥት ገናናውን አጼ ቴዎድሮስን እንደ አረመኔ አስመስሎ ሐገሩንና ሐይማኖቱን ክዶ በልዩን ሃይማኖት ገብቶ ነገር እያስመላለሰ የኢትዮጵያውያንን ደም ያስፈሰሰው ሐሳዊ ጻድቅና ቅዱስ ሲባል ይገኛል።

ቅዱስ የተባለውም ገብረ ሚካኤል የሚባለው መነኵሴ አጼ ቴዎድሮስ አስረውት የሞተው ነው።



ብፁ አባ ገብረ ሚካኤል

## ኀ ቀዳም የካቲት

አባ ገብረ ሚካኤል በዲቦ (ጐጃም) በ፲፰፻፹ ዓ.ም ተወለዱ። ቤተ ሰባቸው መንፈሳዊነት በሞላው አስተዳደግ አሳደጉዋቸው። በሕፃንነታቸው ትምህርትን ዝመሩ ብልህ በሆነ አእምሮዋቸው በቶሎ ከሌሎች ተለዩ። በዕድሜያቸው ፳፫ ዓመት መርጡለ ማርያም ገዳም ገብተው የመንኵሴን ብፅዓት አደረጉ። ያገራቸውን ሕዝብና ሊቃውንቶች ሊያይቶ እርስበርሳቸውን ያጣላ የነበረው ስለ ሃይማኖት መከራከር አሳዘናቸውና የጥንቱን መጻሕፍት መርምረው ኡነተኛውን ትምህርት እንዲያገኙ የኢትዮጵያን ትልልቆች ገዳሞች ጠየቁና ጐበኙ።

በ፲፰፻፴፪ አዲስ የተዋሕዶን አቡን ለማምጣት ወደ ምስር ይሔዱ ከነበሩ መልእክተኞች ጋራ ተቀላቀሉ ከዚያ ቀጥለው በአቡነ ያዕቆብ ዩስጢኖስ ካቶሊካዊ ሰባኪ መሪነት ከጓደኞቻቸው ጋር ሮማንና ኢየሩሳሌምን ጐበኙ። ከዚህ የተነሳ መንበረ ማርቆስ እስክንድርያን መንበረ ጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያት ሮምያን ቅዱስ አገሪቱ ኢየሩሳሌምን አይተው ከተመለሱ ያዩትን ነገር በሁለት ዓመት ውስጥ መርምረውና አስተያይተው ያችን በመንበረ ጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያት ያገኙዋቸውን ሃይማኖት መረጡ። በዚህ ምክንያት ጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያት ያገኙዋትን ሃይማኖት መረጡ። በዚህ ምክንያት ተያዙ ታሠሩ ሥቃይንና ግርፋትን ተቀበሉ ከንጉሥ ፊት ቀረቡ ንጉሥም "የሮማ ወርቅ አንተን አሳስቶ እንዳይሆን እኔ አብልጬ ልስጥህ አሉዋቸው" እሳቸው ግን "ወከርቅና ከሀብት ሁሉ ኡነትና ጽድቅ ይበልጠኛል" ብለው መለሱላቸው። ስለዚህ ሙሉ ሕይወታቸውን በእስራትና በሰንሰለት እንዲያሳልፉት ተፈረደባቸው። ዳሩ ግን ሥቃይ በዝቶባቸው ከጥቂት ጊዜ በኋላ ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፰፻፵፯ ዓ.ም ዓረፉ። አባታችን ፒዮስ ፲፩ኛ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፲፱ ዓ.ም

## ጠ እኁድ የካቲት

በቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያን በትልቅ አጀብና ግርማ እኒያ የሃይማኖት ጅግና የሆኑት የኢትዮጵያ ልጅ አባ ገብረ ሚካኤል በመላው ዓለም "ብፁዕ" ተብለው እንዲከበሩና እንዲጠሩ አዘዙ።

## ጸሎት።


ኦ ብፁዕ ገብረ ሚካኤል ዘከአውከ ደከመ ወመጦከ ነፍሰከ በእንተ ሃይማኖትከ ወተዐገስከ ሞተ መሪረ በእንተ መንግሥተ ሰማያት ሰአል በእንቲአነ ኃበ እግዚአብሔር የሀበነ ለነኒ ዘከመዝ እምነተ ወኃይለ ከመ ንሕነኒ ናጥብዕ በእንተ  ሃይማኖትነ ወንዕቀባ ዘእንበለ ኃፍረት ወዘእንበለ ፍርሀት።

ወዓዲ ተዘርከር ወጸሊ በእንተ ኵሉ ሕዝበ ብሔርከ ከመ እግዚእ ያርኁ ወይከዐው መዝገበ በረከቱ ላዕሌሁ ወይፈኑ ዲቤሁ ብርሃን ዚአሁ ከመ ይርከብ አማናዌ ብርሃን ወይትመየጥ ኀበ መንበሩ ለሊቀ ሐዋርያት ጴጥሮስ ከመ ይኩን መርዔተ ለአሐዱ ኖላዊ። አሜን።

ለይትኀተም። ጴጥሮስ ፏን ሊይርድ ህየንተ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት በፏቲካን አመ ፳፫ ለጥር ፲፱፻፵፰።

ይህ አስደናቂ ታሪክ ኢትዮጵያ ታስተውላለች

## ጡ ሰኑይ የካቲት


ED. MEISSNER SC.

(ከስጋዌ በኋላ በ፲፰፻፵፯ኛ ዓ በወርኃ ሐምሌ በአምባ ጩራ ሰፈረው ሳሉ አፄ ቴዎድሮስ ያቡነ ሰላማን ፈቃድ ሊፈጽሙ በሰውነቱ አምላክ። በሰውነቱም እንደ ፩ አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ ያውቃል ያላልህ ከፍ ብዬ አንገትክን ዝቅ ብየ ባትህን እቆርጥሃለሁ ብለው ባምባ ጩራና በጎንደር ዓዋጅ አስነገሩ።

ያገራችን ካህናቱ መከራንና ቅጣትን ፈርተው ወደቡን እየመጡ ሲከዱና ሲገዝቱ አየነ። በኋላ አብያተ ክርስቲያናት እንደተኮሱ ታቦታትንም እንዳረከሱ ሥዕላትንም እንዳስቀደዱ መስቀልንም እንደሰበሩ በሁሉ ኢትዮጵያ የታወቀ ነው ይህን የማይገባን ነገር ሊያደርጉ ያስደፈራቸው የሱስ ክርስቶስ በሰውነቱ አምላክ ከሆነ አልታመመም ካልታመመ መስቀልና ሥዕል በከንቱ ነው ያሰኛቸው ይመለኛል።

ደጃዝማች ካሣ ሲባሉ በእብናት ወዳለች ያቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ሊሰሙ ገቡ መጋረጃውን ገልጦ የጌታችንን የሕማማቱን ሥዕል ቢያሳያቸው አንተ ቆማጣ የቆማጣ ልጅ አሁን ይህ ሁሉ ነገር በርሱ ደርሶበታልና ብለው ተቈጡት አሉ ይላሉ

# ጢ. ሠሉስ የካቲት

ደግሞ እልፍ ብሎ (ሥጋ የባሕርይ አምላክ ሆነ እንደ አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ ያውቃል ማለት። ወበንተሰ ይዕቲ ዕለት ወይዕቲ ሰዓት አልቦ ዘየአምራ ወኢመላእክተ ሰማይ ወኢወልድ ዘእንበለ አብ ባሕቲቱ። ያለውን አፍራሽ እንደሆነ አስተውለው መስቀልና ታቦት የሰበረውን ሥዕላትና አብያተ ክርስቲያናት ያቀጠለውን ያረከሰውንም መሢሕ ወገን ነው እንዳልህ በሰውነቱ አምላክ በሰውነቱ እንደ አብና እንደ መንፈስ ቅዱስ ያውቃል ንዴት ጠፋ በሰውነቱ አልታመመም የሚለውንም። በሰውነት ሰው ሆነ በውነት ከኃጢአት በቀር የሰውን ግብር ሁሉ ፈጸመ ስለኃጢአታችን ካሣም በመስቀል ተሰቅሎ ሞተ ስለዚህም መድኃኔ ዓለም ተባለ ያሉን ቅዱሳት መጻሕፍት አስተኞች ያደርጋል ሐሳዊ መሢህ እንደሆነ አስተውል።)

የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ ይህን ታሪክ አስተውለው የጀግናውና የገናናው ንጉሠ ነገሥት ቴዎድሮስ ታሪክ እንደዚህ እየሆነ ተጽፎ የሰላም ማጥፊያ የስም ማከፊያ ሆኖ መገኘቱን እይ እንግዲህ ኃይሉ ቴዎድሮስ ሐሳዊ መሢሕ ሲባል ቴዎድሮስ ቅብዓ መንግሥት የተቀባባት ቤተ ክርስቲያን ማን ማን መሆኗ ነው። አባ ገብረ ሚካኤል ቅዱስ ሲባል ከአሕዛብ ወገን መሆኑ ይመልህል። ከነሱ መጽሐፍ የተገለበጠ

# ጣ ረቡዕ የካቲት



ይህ ፡ ወሬሳው ፡ ካሳ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዮሐንስ ፡ ናቸው።

አጼ ዮሐንስ ከሠሐጢ የተመለሱበት ምክንያት የሮማ ልዑካን የነገሥታቱን ዓዋጅ እየጣሱ ሲሰብኩት በተገኙ ቁጥር በጐንደር ከተማ ላይ ቅጣታቸውን ይቀበሉ ስለ ነበር የወገኖቻቸውን በቀል ለመከፈል ጐንደርን ለማስጠፋት ብዙ ያስቡ ስለነበር አጼ ዮሐንስ ወደ ሠሐጢ ለጦርነት ሲወርዱ ጊዜ ስለገጠማቸው ደርቡሽን ጠቅሰው እያደፋፈሩ አምጥተው ከንጉሥ ተክለ ሃይማኖትም አዋተው የጐንደርንም ሕዝበ ክርስቲያን አሳርደው ከተማውንም አጠፍተው በጐንደር ላይ ከፍ ያለ መከራ ስለወደቀበት የጐንደር ሊቃውንት ወደ አጼ ዮሐንስ የጻፉት ደብዳቤ መዝ ፸፰ ፩ እግዚኦ ቦኡ አሕዛብ ውስተ ርስትከ

# ጤ ሐሙስ የካቲት



መጽሐፈ ምክር ከተባለ የካቶሊካውያን መጽሐፍ። በ፳፪ኛ ገጽ ከ፩ኛው መሥመር። በተረፈ ቄርሎስ የተጻፈውን እንስማ። ዘአውሴብዮስ ጳጳስ ዘኤራቅልያ ዘጳንጦስ ይቤ ኅዳጠ እነግር በፍቅር ለሕዝበ እግዚአብሔር እንዘ ይኄይለኒ ትእዛዞሙ ለአበው እለ አስተጋብኦሙ ኢየሱስ ክርስቶስ ብርሃናተ ኵሉ ዓለም። ወዘእምግብጽ እምኀበ ውእቱ

# ፐ ዓርብ የካቲት

ተጸውዓ። እስመ ይቤ እምግብጽ ጸዋዕክዎ ለወልድየ። ወበዓይቴ አስተጋብኦሙ ኀበ ዘይትፈቀር እምኔሁ ረድዕ ዮሐንስ። እንዘ ይርኢ ከመ ሎሙኒ ያፈቅሮሙ ዘአስተጋብኦሙ አኮ ዮም ይትመሐሩ ሰቢከ ሃይማኖት እስመ እምንእሶሙ ትምህሩ ኵሎሙ ቅዱሳን መጻሕፍተ አላ ከመ ይክሥቱ ትዕቢተ ዲያቢሎስ ዘበቈለት ከመ አሜከላ ላዕለ ጽድቅ ወሃይማኖት ቅዱሳን አበው እንተ ተውህበት በጕሚያቱ ለከይሲ። ወይሥዓሩ በጽንዕ ቀጥቂጦሙ ርእሶ ለጽሩፍ ከይሲ ወለተኵላ ዘይለብስ ሥናየ ልብሰተ ዘበግዕ ሐስዎ ይርዕይዎ እምበግዕ ወለኖላዊ ከመ ኀስው ኖላዊ። ወለዓቃቢ ሠራቂ ወለፈዋሲ ቀታሊ። አኮ ዘይፈውስ አላ ዓዲ ዘይቄስክ ቁስለ ነፍስ። አኮ ዘይቄስክ መክሊተ አላ ይሠርቅ። ወህየንተ ኅብስት እብነ ይሜጡ ለዘሰአለ። ወኅየንተ ዓሣ ዓርዌ ምድር። ዘውእቱ ህይንተ ሃይማኖት ኢአሚን።

ይህን ከላይ የተጻፈውን ስለነርሱ መሆኑን መረዳት አቅቷቸው ሌላ ትርጓሜ ሰጥተው በመጻፋቸው አግብተው ጽፈውታል። ይህ ከላይ የተጻፈው ልክ ስለ ልዮን ልጆች ስለሆነ በጣም እንዲገባቸው ምልክታቸውን በሮማ መንግሥት (ዋና አርማ በራሳቸው የሚደረገው ከይሲ ያለበት መለዮ ግርማዊ ጃንሆይ በድል አድራጊነት በተመለሱ ጊዜ ዕቃቸውን ጥለው ሲሸሹ የተገኘው መለዮ ከይሲ ያለበት። በዳዊት መዝሙር ፸፫ ፳፮ ቅዱስ ዳዊት ከይሲ ዘፈጠርከ ይሣለቅ ላዕሌሆሙ ብሎ የተነበየባቸው ሮማውያን። አባ ቁርሎስም በጽሩፍ ከይሲ ወለተ ኵላ የተባሉ የልዮን ልጆች መሆናቸውን ይህ መለዮ ዋና ምስክር ስለሆነ አንባቢዎች እንዲመለከቱ ነው።

ይህን የሚአህል ነውራቸውን ተሸክመው እሰው ቤት ገብተው ሲፈተፍቱ ይገኛሉ።

# ጦ ቀዳም የካቲት

ኢሳይያስ ፶፱ ቍ፭ ወያነቅዑ አንቆቅሆ አርዌ ምድር ወየአንሙ ፈትለ ሣሬት።

እስመ ዘበልዖ ለአንቆቅሆ ዓርዌ ምድር ይመውት ፍጡነ። ወእም አንቆቅሆ ይወጽእ ከይሲ።

፮ ወፈትለ ሣሬት ኢይበቍዕ ለተዓጽፎ ወኢይትዓፀፉ በምግባሮሙ። እስመ ግብረ ዓመፃ ግብሮሙ።

፯ ወለኃጢአት ይረውጻ እገሪሆሙ ወያፈጥና ለክዒወ ደም። ወይመክሩ ለቀቲል ኃሣር ወቅጥቃጤ ውስተ ፍኖቶሙ።

፰ ወኢየአምርዋ ለፍኖተ ሰላም። ወአልቦ ጽድቅ ውስተ አፍሆሙ እስመ ጠዋይ ፍኖቶሙ ዘይሐውሩ ወኢየአምርዋ ለሰላም፡

፱ በእንተ ዝንቱ ርኅቀ ጽድቅ እምኔሆሙ ወኢትረክቦሙ ርትዕ። ወኮኖሙ ጽልመተ ብርሃኖሙ እንዘ ይጸንሑ ብርሃነ የሐውር ውስተ ጽልመት።

፲ ወያረመስሱ ውስተ ዓረፍት ከመ ዕውር ዘአልቦ ዓይን። ወይወድቁ መዓልተ ከመ ዘመንፈቀ ሌሊት ይትመነደቡ ከመ ዘይመውቱ። ይህ ትንቢት ለማን ተነገረ በማንስ ተፈጸመ።

ዘካርያስ ፳፱ ፯ ኅሥሡ ሰላማ ለሀገረ ኀበ አፍለሰኩክሙ ህየ ወጸልዩ በእንቲአሃ ኀበ እግዚአብሔር እስመ በሰላመ ዚአሃ ይከውን ሰላምክሙ። በሰው አገር ለሚኖር ህይን ቢመለከት ይጠቅመው ነበር።

# ጰ እሁድ የካቲት





ይህች የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ የቆመችበት ምድር የኢትዮጵያ ጀግኖች ደም የፈሰሰባት አጥንታቸው የተከሰከሰበት መሆኑን የሚያስቡ ኢትዮጵውያን ከዚያ ሲሰግዱ በመታየታቸው ላስተዋይ አስደናቂ ነው።

# ጱ ሰኑይ የካቲት



የኢጣልያ የጦር ፊታውራሪ አባ ማሳያ የሚባለው ፖለቲክ አመላላሽ መነኰሴ መሳይ በኢትዮጵያ ላይ ብዙ ደም ለማስፈሰስ ያደረሰ ነው።

# ጺ. ሠሉስ የካቲት

የተላከ ከብላታ ገብረ እግዚአብሔር ይድረስ ከብላታ ጳውሎስ እንዴት አሉ እጅጉን። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። በሐረርጌ ሳለሁ ካንድ ካቶሊካዊ በከረን አገር በሽህ ፹፻፺ ዓመተ ምሕረት አባ ዮሐንስ የካቶሊክ መነኵሴ ያተሙት ትንሽ መጽሐፍ አየሁ። መጽሐፉን ባስተውለው እጅግ የሚያስደንቅ ነገር አገኘሁበት። እንደምን ቢሉ። አንድ ካቶሊካዊ እስከንድርያ ገብቶ ከአንድ ግብፃዊ ቄስ ጋራ ከቤተ ክርቲያን ተዋወቀና የሃይማኖት ነገር ሲከራከሩ ካቶሊካዊው ረታ ግብፃዊ ተረታ ይላል። ቢረታ ደግሞ ደብተራም ቢያመጣ በክርክር እየተረቱ ገቡ የሚል አገኘሁበት። መጽሐፉ እንዳልከልዎ። ባለቤቱ እሺ ብሎ አይሰጠኝምና። ይኸው ግብጻዊ ተረታ የተባለበትን ጥይቅና ምላሻ ሁሉ በደብተር አስጽፌ ሰድጀለዎታለሁና። ከብሉይ ከሐዲስ ከሊቃውንት። የተቀደሰች ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖት አውጣው ይላኩልኝ በ፲፱፻፺ ዓመተ ምሕረት በዘመነ ዮሐንስ ኅዳር ፲፪ ቀን። ሐረርጌ ከተማ ተጻፈ።

ይድረስ ከብላታ ገብረ እግዚአብሔር እንዴት አለህ እጅጉን። እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ የላከህልኝ የሃይማኖት ክርክር ያለበት ደብተር ደረሰልኝ። ካቶሊኮች እውነትን በሐሠት ለመለወጥ አይፈሩም። ስለምን ቢሉ የመንግሥተ ሰማያት መከፈቻ ይዘናልና ምናለብን ይላሉ። ጌታ በቅዱስ

ማቴዎስ የተናገረው ይፈጸምባቸው ዘንድ ፳፫ቁ ፲፫። ወዮላቸው እላንተ ጻሕፎች ፈሪሳውያንም ግብዞች መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ትዘጋላችሁና እላንተ አትገቡምና የሚገቡትንም ይገቡ ዘንድ አትተውም። ደግሞ ሉቃስ ም፲፩ ቁ ፶፪ ወዮላቸው እላንተ የኦሪት ሰዎች። የእውቀት መከፈቻ ወስዳችኋልና። እናንተም አልገባችሁ። የሚገቡትንም እከለከላችሁ። እንዲህ ሲል ነግሮባቸዋልና ሐሠት ለመናገር አይመለሱምስ

# ጳ ረቡዕ የካቲት

አሁን የላከህልኝን ክርክር ሁሉ አስተውዬ ሳበቃ በእግዚአብሔር ቸርነት ጽኑ ምላሽ አጽፌ እልካለሁ አይተህ ስታበቃ ለዘመዶቻችን ሁሉ እንድታሳየው ይሁን። ፲፰፻፺ ዓመተ ምሕረት ሚያዝያ ፲ ቀን አዲስ አበባ ከተማ ተጻፈ

## ጥያቄ

የካቶሊክ መነኵሴ አባ ዮሐንስ ቃል ከሥጋ ጋራ ከተዋሀደ በኋላ ሥጋ አምላክ ሆነ ለማለት ለጆሮ እጅግ ይከፋል ማለታቸው እውነት ነውን።

## መላሽ።

ሰማይ ከምድር እንዲርቅ። እንዲሁም ጽድቅ ከኃጢአት እንዲለይ። ይህ ሐሠት ትምህርታቸው ከእውነት እጅግ ይርቃል። ሊቃውንትንም ማሳበል ልማዳቸው ነው። ክቡር እግዚአብሔርን ግን ማሳበል አይቻላቸውም። ሥጋ በተዋህዶ አምላክ አልሆነም ማለት የከሃዲ የንስጥሮስ ሃይማኖት ነው ማርያም የወለደችው ነው እንጂ አምላክ አይደለም ሲል ይቃጅ ነበር። ከርሱም በኋላ የእስላም ነቢ መሐመድ የሚባል። ኢሳ ነቢ ማርያም የወለደችው ሰው ነው እንጂ አምላክ አይደለም ይል ነበር።

የካቶሊክ ትምርትና የእስላም ትምርት አንድ አይደለም። ምን ያህል ይራራቃል። ካቶሊኮች ተሰቀለ እስላሞች አልተሰቀለም ከማለት በቀር። መሐመድ ሲል እግዚአብሔር ቃሉንና መንፈሱን ወደ ማርያም ቢልከ። ፍጹም ሰው መስሎ ወለደችው በድንግልናም ተወለደ ይላል። ግን አምላክ አይደለም የከበረ ሰው ነው ሲል ከብላታ ጳውሎስ መጽሐፍ የተገኘ ግልባጭ

# ጴ ሐሙስ መጋቢት ፲፪ኛ ወር ፬ ምዕራፍ


# አንባቢዎች ሆይ።

የግዕዝ ፊደል መሠረት ለመግለጽ በፊደሎች ደረጃ ልክ እየሆኑ ዕለታት በ፲፪ ወሮች እየተጠቃለሉ ፩ድ ዓመት እንዲሞሉ ዠምሬው ነበር።

፲፩ዱ ወሮች ተፈጽመው ፲፪ኛው ወር መጋቢት ፩ድ ቀን ጴ ሐሙስ እስከዚህ እንደ ደረሰ ማስተዋል ነው።

መጋቢት ፴፩ ቀን በዕለተ ቀደም ይፈጸማል መጋቢት ፴፩ ቀን ሌሊትና መዓልት ዕሩያ የሚሆኑበትን ቀን ማስተዋል በጣም ይጠቅማል

በዚህ መጽሐፍ ሳይገለጡ የቀሩ ፊደሎችና ዕለታት ከጴ እስከ ፖ ፴፩ መሆናቸውን እንድትረዱ የግዕዝ መሠረት ጥልቅነት ከሄኖክ ምንጭ በተገኘው ካሙቱ ቀኖች የተተካከለ መሆኑን እንድትገነዘቡ። አሳስባለሁ።



ፊታውራሪ ዓለማየሁ ጐሹ



Inspecting an anti-aircraft Lewis gun post.

ግርማዊ ጃንሆይ በማይጨው ጦርነት።




ግርማዊ ጃንሆይ በማይጨው ከጠላት ጋር በጀግኝነት ሲዋጉ።



ግርማዊ ጃንሆይ በዠኔብ ጉባኤ የኢጣልያንን ግፍ እንዳመለከቱ



# ክቡር ራስ ደስታ ዳምጠው

ክቡር ራስ ደስታ ዳምጠው ለጠላት አልገዛም ብለው እየተዘዋወሩ ከባድ የሆነ ጦርነት እያደረጉ ስለወጉት በጦርነት የማይቻለው ቢሆን በውስጥ ለውሥጥ በሰላይ ያሉበት ተከታትሎ ጦሩ በተበተነበት ጊዜ አደጋ ጥሎ በጭካኔ እንደ ተገደሉ ይህን ታሪክ ትውልድ ያጠናል።





## ክቡር ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ

ክቡር ደጃዝማች ኃይሉ ከበደ


ለጠላት አልገዛም በማለት ጠላትን ከፍ ባለ ኃይል እየወጉ ሠራዊቱን ስለጨረሱበት በጭካኔ የሠራባቸውን ግፍ ያሳያል።


በዋግ አውራጃ ወለህ ማርያም ላይ አረፉ ፤

የደጃዝማች ኃይሉ እጁ ውድ ናት የቀመሱ ሁሉ ሲያመሰግኗት ፤



ፊታውራሪ ኃይሌ አባ መርሣ የነፃነት አስከባሪው ጀግና


ስመ ጥሩው ጀግና ኃይለማርያም ማሞ
እውነተኛው ጀግና ኃይለማርያም ስሙ እንዳይረሳ ጻፍልን በደም።
እንዲህ ያለው ጀግና እንዲህያለ ወንድ ጌጥ ይሆናቸዋል ለታሪኮች ዓምድ




ግርማዊ ጃንሆይ በሱዳን አገር ላይ ሆነው የበረኃውን ምንገድ አሻግረው ሲመለከቱ።




ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከሱዳን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲመጡ ፡ በበረሃው ፡ በፈረስ ፡ ሲጓዙ ።



ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ከሱዳን ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሲመጡ ፡ በበረሃው ፡ በፈረስ ፡ ሲጓዙ ።



ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሲገቡ ፡ በጐጃም ፡ ጠረፍ ፡ ኦሜድላ ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያን ፡
ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ እንደተከሉ ።



ግርማዊ፡ ጃንሆይ ፡ በድል፡ አድራጊነት፡ ፲፱፻፴፫ ዓ፡ም፡ ሚያዝያ፡ ፳፯፡ ቀን፡ ከመናገሻ ፡ ከተማቸው፡ እንደ ፡ ገቡ።




ሚያዝያ 27 አደባባይ ሐውልት በኃይለ ሥላሴ ተመልሲ የቆመው




በዕድለኛውና ፣ በኃይለኛው ፣ ንጉሠ ፣ ነገሥት ፣ ግርማዊ ፣ ቀዳማዊ ፣ ኃይለ ፣ ሥላሴ፣ ትጋትና ብርታት ፣ የኢትዮጵያን ፣ ከካም ፣ ዠምሮ ፣ እስከ ፣ ንግሥት ፣ ማክዳ ፣ በካም ፣ ቤት ፣ ሲያያዝ የመጣውን ፣ ቋንቋና ፣ ፊደል ፣ በንግሥት ፣ ማክዳም ፣ የተጻፉትን ፣ መጻሕፍተ ፣ ብሉያት ፣ ሕግ ፣ ኦሪት ፣ ይዛ ፣ እስከ ፣ ልደተ ፣ ክርስቶስ ፣ መቆየቷን ፣ ተመልክቶ ፣ ብፁዕ ፣ አቡነ ፣ ባስልዮስን ፣ ለሊቀ ፣ ጳጳሳትነት ፣ ስለአደረሰ ፣ ስንኳን ፣ የኢትዮጵያ ፣ የሌሎች ፣ ታሪክም ፣ ምስጋናውን ፣ እያቋርጥም ።




የካቲት ፤ ፲፪ ፤ ቀን ፤ አደባባይ ፤ ስለ ፤ ኢጣሊያኖች ፤ ግፍ ፤ ለተሠራው ፤ በደል ፤ መታሰቢያ ፤
የቆመው ፤ ሐውልት ።



ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ጠላት ፡ ብዙ ፡ ዘመኖች ፡ ሲገምደው ፡ የኖረውን ፡ የፖለቲካ ፡ ገመድ ፡ በመንፈሳዊ ፡ መቀስ ፡ ቆርጠውት ፡ አሥመራ ፡ እንደገቡ ።



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት በአዲስ አበባ የአፍሪካ ኤኮኖሚክ ኰሚሽን በተከፈተ ጊዜ ንግግር ሲያደርጉ



የኢትዮጵያ ፡ ፓትሪያርክ ፡ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ባስልዩስ



ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ሐረር ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተከፈተው ፡ የጦር ፡ አካዳሚ ፡ ከክቡር ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገሩ ።